# የልምዣት



ሀዲስአለማየሁ

NIGUSS
DIGITAL LIBRARY

# የ ል ም ዣ ት

ከሀዲስ አለማየሁ

# ማውጫ


የማደጎ ጋብቻ ........ 5

የደመቀች ማምለጥ ........ 12

ደመቀችና ሁለቱ እመበለቶች ........ 17

ህልም እንጂ እውን የማይመስል እውን ........ 28

አዲስ አበባ ........ 34

የሱሉልታዋ ኩበት ለቃሚ ........ 44

የጎጃምዋ ገልቱ ........ 59

ትዝታና ምኞት ........ 63

ደመቀችና ደጀኔ ........ 72

ደመቀችና ወይዘሮ ጽጌ ........ 84

ተከስተና ወይዘሮ ጽጌ ........ 92

የጨለማ እሳት ወርዋሪ ለጠላቱ መንገድ ይሳያል ........ 108

ደመቀች በትምህር ሚኒስቴሩ ፊት ........ 118

የምስራች! ........ 130

ያራዳ ልጅ! ........ 153

ባሻህ ማነው? ........ 180

የተከስተ ተፈሪ መኮንን ትምርት ቤት መግባት ........ 227

ዱብእዳ ........ 237

የህገወጦች ህግ ........ 256

አስተርዮ ማርያም ........ 264

ከፉ አጋጣሚ እየጠሉት ያስጠላል .................................... 272
የማይበላ ካሳ ........................................................ 288
ፍኖተ ድህነት ........................................................ 303
ወይዘሮ እሁድ ........................................................ 334
በሻህ ደማሙ ........................................................ 346
‹እስመ ነፍስ ተአምር ቀታሊሁ› .......................................... 368
ፍቅር እውር ነው አይናማ? ............................................. 383
የተፈራ ሉልሰገድ ግብዣ ............................................... 400
የጭንቅ ሳምንት ...................................................... 420
ምሾ የሚያስጠራ የምስራች ............................................. 433
በፍቅር ፊት የሚቆም ቆራጥ ጀግና አለ? .................................. 445
የተባረከ ሴራ ........................................................ 460
የልም እዣት ........................................................ 468
እድሜ ላምቦ ጠበል ................................................... 477
አምባው ተሰበረ! .................................................... 496
ያመነው ለጠላው መድህኒትም የለው ...................................... 516
የደመቀችና የታምራት ተገኘ መፋታት ..................................... 534
ከፉ ቁራኛ ለቅቆ ሲሄድ አስለቅሶ ነው! .................................. 556
የበሻህና የደመቀች ጋብቻ ............................................... 570
ስለደራሲው በጥቂቱ .................................................. 598

# ምዕራፍ አንድ

# የማደጎ ጋብቻ

ደመቀች ጸሐይ፤ ለታምራት ተገኘ ስትዳር፤ የመልከዋ ንድፍ፣ መስመሩ ብቻ ውብ ሆኖ ተሰምሮ፥ የወደፊት ውበትዋ ገና በውጥን የሚታይ የዘጠኝ አመት ለጋ ቡቃያ ነበረች። ታምራት ተገኘ አምስት አግብቶ የፈታ ያምሳ አመት ሰው ነበር።

የደመቀች አባት ባሻ ጸሀይ አበራ፥ ካባታቸው ጀምረው፣ ወደ ላይ፣ ብዙ ፊታውራሪና ደጃዝማች አያት ቅድመ አያቶች የሚቆጥሩ፥ መሰረተ ጌታ ነበሩ። ነገር ግን ጌቶች አባቶቻቸው፣ ሀብቱን ሁሉ በየጊዜው ዜያቸው እነሱ ጨርሰው፣ «የጌታ ዘር» መባሉን ስሙን ብቻ አውርሰዋቸው ስላለፉ ባባቶቻቸው ስም ብቻ የሚኖሩ ችግረኛ መኮንን ነበሩ።

መቸም የጌታ ልጅነት ከሀብት ጋር ሲገኝ ማለፊያ «የውር ስጦታ» ነው የጌታ ልጅነት ከበት ተለይቶ ብቻውን ሲመጣ ግን፥ ክፉ የድህነት ቁራኛ ነው።

ከጌታ የተወለደ ድሀ ሰው፣ አርሶ፣ ወይም ነግዶ እንዳይበላ «የመሰረተ ጌታው፣ የገሌ ልጅ ገበሬ ወይም ነጋዴ ሆነዉ ይሉኛል፤ የጌትነት ስሜ በስራ ይጐሰቁልብኛል» በማለት ኑሮዉን ለማሻሻል ነጻነት የሌለው ያባቶቹ ስምና የራሱ ከንቱነት ግዞተኛ ሆኖ ይኖራል። ባሻ ጸሀይ፣ እንዲህ ካሉት የስም ግዞተኞችና ከንቱዎች አንዱ ነበሩ። እንዲህ ያሉት ከንቱዎች፥ ሰርቶ ከመኖር፣ ያባቶቻቸውን ስም እንደ ምጽዋት መቀበያ ቁና እያስቀደሙ ሲለምኑ መኖር ክብር ስለሚመስላቸው ባሻ ጸሀይ፣ ካንድ ጠፍ ጉልበታቸው ከሚያገኙት እህልና ትንሽ ገንዘብ ጋር፣ ከየመኳንንቱም ሆነ ከየነጋዴው ለምነው በሚያገኙት፣ ምንጊዜም ቢሆን አንድ የኮርቻ በቅሎና አንድ የጃቸው ጠመንጃ አምጥተው አያውቁም። በዚያ ላይ ከቤታቸው አምስት ስድስት ወንድና ሴት ሎሌዎች አይጠፉም። ስለዚህ፥ ጌታ ባይሆኑ ጌታ መስለው፣ ያ ክፉ ጊዜ አልፎ የጭዋ ልጅ በመብራት እዬተፈለገ የሚሾምበት ጊዜ ሲመጣ፣ ቤተሰባቸውና አብረዋቸው ለሚንገላቱ አሽከሮቻቸው ለማድረግ የሚያስቡት፣ ግሩም የሆነ ነገር መኖሩን ተስፋ እየሰጡ፣ እንዲያ ያለው መልካም ጊዜ እስኪደርስ ከብርቱ ትግስት ጋር በብርቱ ተስፋ የሚጠባበቁ ነበሩ።

ልጃቸውን ደመቀችን የዳሩለት ታምራት ተገኘ ግን፣ ጨርሶ ከሌላ ምንጭ የተቀዳ ነበር። ወላጆቹ እጅግ ድሆች ስለ ነበር፣ ከትንሽነቱ ጀምሮ፣ አገሩ ኤልያስ የጥጃና የላም እረኛነት እየተቀጠረ አደገ። ሁዋላም የነጋዴ ጎረደማን ሆነ።

ታምራት ለጌታው አጋሰሶችና ለጭነት እቃው ሁሉ በመጠንቀቁና በትጋቱም ሆነ በብርታቱ እጅግ የተመሰገነ ከመሆኑ ሌላ፣ ሳይሰማ፣ በስጦታ «ተኩሶ ይስታል» የማይባል ጥሩ ተኩዋሽ ስለ ነበረ፣ በነጋዴዎች መሀከል እንደ ጉዋደኛ እንጂ፣ እንዳሽከር አይታይም ነበር። የነጋዴ አሽከር በነበረበት ጊዜ፣ እረፍት ሲያገኝ ጠምንጃ እየተዋሰ ነብር ይገድልና የቆዳውን ጌታው ወደ አዲስ ኧበባ ከሚያስጭነው የበሬ ቆዳም ሆነ የፍየል ሌጦ መሀከል ሸጉጦ ወስዶ ይሸጣል። አምስት ዓመት ያክል የነጋዴ አሽከር ሆኖ፣ በኤልያስና በአዲስ አበባ መሀከል ብዙ ጊዜ ከተመላለሰ በሁዋላ ከደመወዙ ይልቅ ከነብር ቆዳ ሽያሽ ያጠራቀመው ብር ራሱን የቻለ ነጋዴ አደረገው። የቆዳ ቱጃሮች፣ መሀከል፣ ስሙ የተጠራ ሀብታም ነጋዴ ለመሆን ብዙ ጊዜ አልወሰደበትም።

በኤልያስና ባካባቢው አመት ባል የሆነ እንደሆን ታምራት ተገኘ በሰጋሩ ተቀምጦ ፈረሱን ቀሚስ አስለብሶ በፊት እያሳበ፣ ባምስት ስድስት ባለብረትና በብዙ ጀሌ ታጅቦ ሲሄድ፣ የማይቀናበት አልነበረም። ድግስ ሲያደርግ ሰፊ ዳስ አስጥሎ፣ ለተሰበሰበው ሁሉ ስጋ እንደ ጎመን አብልጦ ጠጅና አረቄ እንደ ውሀ አጠጥቶ ድግሱ እንደ ተዝካር ያለ የሀዘን መታሰቢያ ያልሆነ እንደሆነ፣ አዝማሪውን አቅራሪውን ፈካሪውን ሸልሞ ሲሸኝ የማይገረም አልነበረም። በኤልያስና ባካባቢው፣ ሌባ ወይም ወንበዴ ተነስቶ «ከብት ተሰረቀ ቤት ተቃጠለ» የተቃለ እንደሆነ «ታምራት ካሽከሮቹ ጋር ሌባውን ወይም ወንበዴውን አጣድፎ ሳይዝ አያርፍም» ስለሚባል፣ የማይፈራው አልነበረም። ስለዚህ፣ ታምራት ተገኘ በኤልያስና ባካባቢው በሀብቱና በጉልበቱ የሚፈራና የሚከበር ነበር። ብቻ ለሱ ይህ ሁሉ አልበቃውም፤ አላጠገበውም። ሀብትና ጉልበት ያለው መሆኑ የሚፈራና የሚከበር መሆኑ ለልቡ ሙሉ ደስታ ለህሊናቸው ሙሉ እረፍትን ሊሰጠው አልቻለም። አብልቶ አጠጥቶ፣ ተቸገርሁ ለሚለው ገንዘብ ሰጥቶ የሚሸኘው ሁሉ፣ ዘወር ብሎ የማያማውና የማያሽሙዋጥጠው መሆኑን እንዴት ያውቃል? እንደሱ ችግርን ሀብታሞች የሆኑ ለጋሶች የሆኑ እንደሆነ «ይህ አይቶ አያውቅ፣ ያዲስ ጌታ ይህ ባለጌ በገንዘብ እንዳፈር ይጫወታል። አዬ ጉድ ደሀ ሲከብር የሚደኸይ፡ አይመጽለውም! » እየተባሉ ሲታሙ በድህነቱ ሲሰማ ኖሮዋል። እነሱን ከፊቱ ዘወር ሲሉ እንዲህ እንዳያሙት በምን ያውቃል? ያለ ጥርጥር ያሙታል! ለዚህ መድኃኒቱ ለዚህ ፍቱን አብነት የሚቻል ቢሆን ከቅድመ ቅድመ አያት በላይ፣ እንዲያው ካርባና ካምሳ ትውልድ በላይ እንኩዋ ቢሆን፥ ሲሆን ሲሆን በቀጥታ ያለዚያም በጎን አንድ

የማእረግ ስም የነበረው ሰው በቤቱ ቢገኝ እሱን እንደ ምንም ስቦ አምጥቶ ከራሱ ጋር ማያያዝ ነው። ዋናው ነገር እንዲህ ያለ ባለ ማዕረግ ሰው ከቤቱ መገኘቱ ነው እንጂ መራቁ ግዴለም፤ ብዙዎችን ትውልዶች ከመካከል አንስቶ ወዲያ ጥሎ ማቀራረብ ይቻላል! ከዚያ «አያቴ ፊታውራሪ ወይም ቀኛዝማች ወይም ደጃዝማች፥ እገሌ እንዲህ ይሉ ወይም ያደርጉ ነበር! » እየተባለ ማውራት ይቻላል። ከዚያ በሁዋላ «አዲስ ጌታ ባለጌ ሀብታም» ብሎ የሚያማ አይኖርም! ቢኖርም ራሱ «አላዋቂ» ነገር ግን፣ እንዲህ ያለ ባለ ማዕረግ፣ በታምራት ተገኝ ቤት ተፈልጎ ሊገኝ አልተቻለም። መቸም እንዲህ ያለው ነገር፣ ከባለቁጥር ዘመድ በቀር ከማንም ጋር የሚያወያዩት ስለሆነ ታምራት «ዘር መቁጠር እናውቃለን» የሚሉትን ዘመዶችን ሁሉ ጠይቆ ወደ ላይ ቆጥረው ሊደርሱ እስከሚችሉበት ድረስ ሄደው ቢፈልጉ ወይ አንድ! ስለዚህ በዚያ በኩል ተስፋ ተቆረጠ።

እንግዲህ መሠረተ ጌታ አባት ከጠፋ ከዚያ ቀጥሎ፣ ያለው፣ ሁለተኛ መንገድ ከመሠረተ ጌታ መጋባት ነው። ይህ እንኩዋ ለራሱ ምንም ያክል አያገለግልም፣ የሀሜተኛንና የሽሙዋጣጭን አፍ አይዘጋም። እንዲያውም እሱነቱን አስጥሎ ለተጋባቸው መሠረተ ጌታዎች ጥገኛ የሚያደርግ ነው። በመሠረተ ጌቶች ሰፈር የፈረንጅ ሴት ካገባች በሁዋላ ስምዋን ጥላ «የገሌ ሚስት» ስትባል እንደ ምትኖር እሱንም ስሙን «የገሊት ባል የገሌ፥ አምቻ» ሲባል እንዲኖር የሚያደርገው ነው። ብቻ ቢሆንም ለልጅ መልካም ነው። መቸስ መልካም አባት ማለት ራሱን መስእዋእት አድርጎም ቢሆን ለልጆቹ ለዘሩ መልካም መሠረት የሚጥል አይደለም? ስለዚህ ታምራት ተገኘ፤ ለራሱ የሚኮራበት አባት ቢያጣ፣ ልጆቹ የሚኮሩበት አባት እንዲያገኙ ‹የመሠረተ ጌታ ልጅ› ለማግባት አጥብቆ ይፈልግ ጀመር።

«ለባል መድረስዋን አላውቅም እንጂ - ባሻ ጸሀይኮ አንድ ልጅ አለቻቸው» አሉ ከታምራት ዘመዶች አንዱ ባንድ ላይ ተቀምጠው ስለ ጋብቻ ነገር ሲወያዩ።

«የቱ ባሻ ጸሀይ? » አለ ታምራት።

«ባሻ ጸሀይ አበራ» የንዶዳሙ።

«እሳቸውም ማለፊያ ጨዋ ናእው፣ አውቃቸዋለሁ። ልጅ አለቻቸው? »

«መኖርስ አለቻቸው፤ ብቻ የዘጠኝ ሲበዛ ያስር አመት ልጅ ብትሆን ነው፤ ከዚያ የምትበልጥ አይመስለኝም።»

ባሻ ጸሀይ ልጃቸውን ለታምራት እንዲሰጡ ሲለምኑ በዘር የማያክላትና የማይመስላት መሆኑ ልባቸውን በምሥጢር ቅር ከማሰኘቱ ሌላ እና ለጋብቻ ያልደረሰች በመሆንዋ መፍቀዱ በጣም አስቸግሮዋቸው ነበር።

«እስቲ ሌላውን ሁሉ እንተወውና ገና በዘጠኝ አመትዋ፣ ትዳር ምን መሆኑን እንኳዋ ሳታውቅ ብድራት ‹ልጁን ማሳደግ አቅቶት ለሀብታም ሸጣት› አልበላም? » አሉ ባሻ አማላጅ ሆነው ለመጡት ሽማግሎች።

‹እንኳዋንስ ልጅዎን ብዙ ባእድ እያሳደሩ፣ ማነው ደግሞ እስዎን ‹ልጃቸውን ማሳደግ አቃታቸው› የሚልዎ? » ከሽማግሌዎች አንዱ።

«ግዴላችሁም እኔ እንዳልሁት ትንሽ እንቆይና እንምከርበት፣ ልጅቱም ባይሆን አስራ ሁለት ዓመት ይሙላት፣ እስከዚያ ለሌላ ሰው ቃል አልሰጥም።

«ልጅ ታምራት የስዎን ዝምድና አጥብቆ ስለ ፈለገ ነው እንጂ፣ ምሽትኮ ጠፍቶ አይደለም ጌታየ! ስለ ዕድሚዋ ግን፣ እስከ አስራ ሁለትም ይሁን እስከ አስራ ሶስት አመት ላይደርስባት፣ ቃሉን በማላ ይሰጣል። ስለዚህ ላቅመ ሄዋን እስክትደርስ በማደጎ እንዲሰጡን ነው የምንለምንዎ።»

ከብዙ ምልጃ በሁዋላ ባሻ ጸሀይ ተሸነፉና ታምራት፣ ደመቀችን፣ አስራ ሶስት አመት እስኪሞላት ላይደስባት፣ ባላባትዋ ቃሉን ሰጥቶ፣ በዘጠኝ አመትዋ «ግሩም» በተባለ ሰርግ በማደጎ አገባት። ብቻ «በምሽቱ አልደርስም» ብሎ ቃል መግባቱና መማሉ መቸም ዘበት ነው። ልጅን ለባል ድሮ፣ ባል በምሽቱ እንዳይደርስ ማማል ስጋ ለጅብ አጉርሶ «እንዳታላምጥና እንዳትውጥ ማልልን» ለማለት የተለየ አይደለም።

ደመቀች ከተዳረች አመት እንኩዋ ሳይሞላ እድሜዋ አስር ዓመት ያክል ሲሆን የታምራት፣ ሚዜዎች፣ ህግ የማድረሱን የምስራች ለሙሽራዋ ወላጆች ለማብሰርና ለመዝፈን፣ የደም ሸማ ይዘው ሄዱ። መቸም ልማድ ነውና፣ የደመቀች ወላጆች «የምሥራች» ተብለው ተዘፈነላቸው! እንደ እወነቱስ ቢሆን ልጃቸው አይደርስ ስቃይ ደርሶባት ስትሰቃይ ገና የጾታ ስሜት የሌለውን፣ የህንጻ ገላዋን፣ ርህራሄ የሌለው ጨካኝ አብጠልጥሎት ስትጨነቅ የወለዱ እንዳት አባትዋ ማዘን እንጂ መደሰት ባልተገባቸው ነበር። ነገር ግን ደስ አላቸው፤ አዘፈኑ! ደመቀች ታራት ተገኝ ህግ ካደረሰ በሁዋላ ተካክሎ ሶስት አመት የሞላ ጊዜ አብራው አልቆየችም። ብቻ ያው የቆዬችው ያክል የመከራ የስቃይ ጊዜ ነበር! ሁልጊዜ ጸሀይ ዘቅዘቅ ስትል ማታ የሚገጥማት መከራ ከራሱ

ከመከረው ብዙ ጊዜ ከፍቶ ይታያትና፣ ጨካኝ አውሬ ሆኖ ይታያትና፣ ማልቀስ ትጀምራለች። አትበላ፣ አትጠጣ፣ እንቅልፍ አይወስዳት ከስታ ከስታ ገላዋ አለቀና የገላዋ ጥላ ሆነች። በሁዋላ፥ አድሮ የማይሻላት ስለሆነና ታምራት በጄ እንዳትሞትበት ስለ ፈራ፥ ሳይፈታ እንዲሁ እወላጆችዋ ዘንድ እድንትቆይ ሰደዳት። ጸንሳ ነበር። አስራ ሶስት አመት እንኩዋ ሳይሆናት፣ «ሞተች» ተብሎ ተሰፋ ከተቆረጠላት በሁዋላ በብርቱ ጣር ወንድ ልጅ ተገላገለች።

ደመቀች ከባልዋ ቤት ወደ ወላጆችዋ ከተመለሰች በሁዋላ እስዋን ብቻ ሳይሆን ወላጆችዋን ጭምር፣ በኑሮዋቸው ቀጥ አድርጎ የያዘ እሱ ነበር። ወንድ ልጅ መገላገልዋን ሲሰማ፣ እልሙ ሞለላትና እጅግ ደስ አለው። የምሥራቹን የሰማ እለት፣ አንድ የሰባ ፍሪዳ አስነድቶ ማርና ቅቤ አስጭኖ፥ ልጁን ለማየት ወደ ንዱዳሞ ሄደ። ከዚያ በሁዋላ በየግዜው አስጭኖ፥ ልጁን ለማየት ቅቤውን ዱቄቱን በርበሬውን እያስያዘ ይሄዳል። ደመቀች ግን፥ «ታምራት መጣ» ሲሉዋት «ሞት መጣ» እንዳሉዋት ሁሉ፣ የምትሸሸግበት ቦታ አልበቃት እያለ ትጨነቅ ነበር እሱም ምሽቱ እዚያ ያልተገኘበትን፥ የውሸት ምክንያት ወላጆችዋ ፈጥረው በነገሩት ቀን፣ ልጁን ብቻ አይቶ ይመለሳል። ልጁ እውነትም ደስ የሚያሰኝ በጣም፣ የሚያምር ነው። ሰሙን አያቱ ባሻ ጸሀይ ከንስሀ አባታቸው ጋር ተመካክረው «ተከስተ» አሉት። ታምራትም ምን ማለቱ መሆኑን ሲነግሩት ተስማማ።

ተከስተ በተወለደ ባመቱ፣ ታምራት ሚስቱንና ልጁን እንዲሰጡት የደመቀችን ወላጆች ስለ ጠየቀ ወደ ባልዋ እንድትሄድ ቢያባብሉዋትም ቢያስፍራሩዋትም «እሺ» የማትል ሆነች። አስገድዶ ለታምራት ለመስጠት መወሰናቸውን ያወቀች እለት እንደ ምትጠፋ ወይም ገደል ገብታ እንደምትሞት አባት እናትዋ በአንድ ላይ ባሉበት እየመላለሰች ስትነገራቸው እናትዋ ወይዘሮ ሙሉነሽ ይሰጉና፣ ከስዋ ጋር ሆነው ሲሆን እንዲያፋቱዋት የለዚያም እንድትቆይ ባላቸው ይለምናሉ። ባሻ ጸሀይ ግን ይቆጡና፣

«ለልጆች ፊት መስጠትና ‹እንዳላችሁ› ማለት ያባልጋቸዋል እንጂ ምንም አይፈጥላቸው። ይችም - አንቺ ‹አልሁሽ እያልሻት ነው እንዲህ ራስዋን ‹አንቱ› ብላ አልታዘዝም› ያለች» ይላሉ።

ደመቀች እናትዋና የቤተሰቡ የንስሀ አባት ቄስ መንግሥቱ ከሌሎች ዘመዶች ጋር ሁኔታዋን አይተው ባይቃወሙ ኖሮ አባትዋ እስከዚያ ድረስም አስረው ለዚያ ጨካኝ አውሬ ለታምራት ይሰጡዋት እንደ ነበእና ወደፊትም አንድ ቀን ይህ እንደማይቀርላት ስላመነች ከመጥፋት በቀር ሌላ ማምለጫ መገድ ጠፍታ ወዴት እንደ ምትሄድ

አታውቅም። በዚያ ላይ የልጅዋ ነገር አስቸገራት። ጥላው መሄድ መቸም የማይታሰብ ነው! ለመታዘል እንኩዋ ወገቡ ገና ያልጸና ህጻን ይዞ የሚሄዱበትን ሳያውቁ መንከራተቱም አደገኛ ነው! እስዋስ እይደረሰ ቢደርስባት ግዴለም፤ ከዚያ ታምራት ከተባለው አወሬ ጋር አንድ ሌሊት፥ ኧረ አንድ አፍታ እንኩዋ ብቻዋን ከመገኘት የባሰ ነገር ምንም ቢሆን ሊደርስባት አይችል! ግን ልጅዋ ብርድ ወይም ጸሀይ ረጭም ጊዜ ታዝሎ መንገላታት አልችል ብሎ፥ በጀርባዋ ላይ ቢሞትባትስ? «እግዜር አያድርስ! የሰይጣን ጆሮ አይስማ! ጭራሽ አይሆንም! » ደመቀች ይህን ሁሉ ባሳብዋ ታወጣ ታወርድ ታሰላስልና፣ መፍቻ ስታጣለት ብቻዋን ቁጭ ብላ ታለቅሳለች። «እናት በልጅዋ ትጠመዳለች» ይባላል፤ ይልቁንም ልጅ እናት! ሴት ልጅ እንኩዋንስ የወለደችውን ልጅዋን በልጅ መልክ ሰርተው የሰጡዋትን ምስል (አሻንጉሊት)፥ ካንጀትዋ ትወዳለች! ስለዚህ ደመቀች ሽሽታ እንዳታመልጥ የልጅዋ ነገር የሾህ አጥር ሆኖባት የምትፈራው አውሬ እስኪይዛት ዝም ብላ ተቀምጣ እያየች ታለቅስ ነበር።

ታምራት ተገኘ፣ አንዳንድ ጊዜ ራሱ እየመጣ፥ ሌላ ጊዜም አማላጅ እየላከ ሲለምን፣ ባሻ ጸሀይ በበኩላቸው አንዳንድ ጊዜ ልጃቸውን ሲያባብሉ ሌላ ጊዜ «በግድ አስሬ እሰታለሁ» እያሉ ሲጋበዙ፥ ደመቀች የያዘችው ቀን አልፎ የሚከተለው ቀን ሁሉ ታሰራ ለታምራት የምትሰጥበት እየመሰላት ስትፈራና ስትጨነቅ፥ ሌላ አመት አለፈ። ተከስተ ሁሉ አመት፥ እስዋ አስራ አምስት አመት ሆናቸው፤ እስዋም እሱም ባካልና በአእምሮ ያንድ አመት እድገት ጨመሩ።

ከዚያ በሁዋላ ታምራት ተገኘ፣ በልመና የፈለገውን ለማግኘት የማይችል ስለ መሰለውና ስለ ሰለቸው ዘዴውን ለወጠ። ወደ ባሻ ጸሀይ ቤት መሄዱንም ተወ። ገንዘብም ሆነ ሌላ ነገር በየጊዜው ይልክላቸው የነበረውንም ጨርሶ አቆመ። ይህ ባሻ ጸሀይ የማይችሉት፥ ብርቱ ቅጣት ነው! በዚያ ላይ ባሻ ጸሀይ ምሽቱና ልጁን በፍቅር የማይሰጡት ከሆነ፥ እሳቸውን አስደብድቦ ቀምቶ ለመውሰድ የቆረጠ መሆኑን ያስወራ ጀመር። ባሻ ጸሀይ ይህን ሲሰሙ ባለቤታቸውንና የንስሀ አባታቸውን ዘመዱንም ሁሉ የሚያሸንፉበት ጥሩ ምክንያት አገኙና ልጃቸውን አስገድደው ለመስጠት ወስነው መጥቶ እንዲወስዳት ወይም ሰው ልኮ እንዲያስወስዳት ቀን ቆርጠው ላኩበት። ውሳኔያቸውን ባልተቤታቸውና የንስሀ አባታቸው ባሉበት ተቀምጠው ሲናገሩ፣

«ይቺ ልጅ ከሱ ጋር ሳለች ከሰውነት ወጥታ እንደ ነበርና አሁንም ተመልሳ ብትሄድ ሰው እንደማትሆን እያወቁ፥ «መጥተህ ውሰዳት» ማለትዎ እንድትሞት

መፍቀድዎ፥ በገዛ ልጅዎ የሞት ፍርድ መፍረድዎ መሆኑን አውቀው ይሰድዱዋት» አሉ ወይዘሮ ሙሉነሽ እንባቸውን ካይኖቻቸው በኩታቸው ጫፍ እየጠራረጉ።

«ጠላትዋ ይሙትና - የምን ሞት ነው እንድትሞት የፈረድሁባት? «ወደ አብልዋ፥ ወደ ቤትዋ ትሂድ» ማለት የሞት ፍርድ ነው? ከባሎቻቸው ጋር የሚኖሩት ምሽቶች ሁሉ የሞት ፍርድ የተፈረደባቸው ናቸው? » አሉ ባሻ በመገረም።

«የሰዋውና የሱ ‹ባልና ሚስትነት› አይባልም፥ እንጃ ሌላ -» ብለው ወይዘሮ ሙሉነሽ፥ የጀመሩትን ሳይጨርሱ ደመቀች ሰምታ፥ በቁጣ እዬተቀጠቀጠች ገባች። በብርቱ ስትቆጣ ሁልጊዜ እንደ ሚሆነው ዞማ ጠጉርዋን ወደ ፊት ተመልሶ ተንጨብርሮ የደፈረሱ አይኖችዋ በሙሉ ተጎልጉለው ወጥተው ፊትዋ ሁሉ ተለዋውጦ ታስፈራራ ነበር።

«እኔ - እኔ» አለች አባትዋን ለማነቅ እንዳሰበች ሁሉ፣ አርስ የጅ ጣቶችዋን ፊት ለፊት ወደሳቸው አንጨፍርራ። «እኔ - እኔ ዱር ለዱር ስሄድ፣ እዚህ የንዶዳም ጅብ ይበላኛል፣ ያለዚያም ያለዚያም በ - በስምና ገደል ገብቼ እሞታለሁ እንጂ፣ ወደሱ ወደሱ አ - አልሄድም! » አለች ወዳባትዋ አንጨፍራቸው በነበሩ የሁለት እጅ ጣቶችዋ ፊትዋን ሸፍና መሪር ልቅሶ እያለቀሰች።

«አንቺ አዛዥ የሆንሽ አለት፤ አንቺ ያልሺው ይሆናል እስከዚያ ግን ‹ልጆች አባቶቻቸውን ይዘዙ› ተብሎ አዋጅ እስኪወጣ፥ እዚህ ቤት አዛዡ እኔ ነኝ» አሉና ባሻ ጸሀይ ተነስተው ወጡ። እውጭ እንደ ቆሙ ሁኔታዋ ሁሉ ባይነ - ህሊናቸው ፊት መጥተው ስለ ታያቸው ትንሽ እንደ መስጋት ብለው ሲተክዙ ቆይተው «ምኒቱን አውሬ ፈጠርናት እባካችሁ! ሰው አውሬ ይወልዳል? › አሉ ለብቻቸው። ወዲያው ‹ላይሰሩ ይፈክሩ የልጆች ጠባይ ነው› የሚባለው ትዝ ሲላቸው እንደ መጽናናት አሉ።

## ምዕራፍ ሁለት

# የደመቀች ማምለጥ

ደመቀች ከመጥፋትዋ በፊት፣ የተወለደችበት አገር ከንዶዳም ኪዳነ ምህረት ወጥታ የምታውቃቸው ባካቢው ያሉትን አገሮች አማሪት ዮሀንስን የደቦና ማርያምን፣ የውያን ገብርኤልንና የነሱ ሰበካዎች የሆኑትን አንዳንድ መንደሮች ብቻ ነበር። ባመት ባል በሰርግ፥ ወይም በሌላ የደስታና የጨዋታ ጊዜ፣ የቅርብ ዘመድና ወዳጅ - ልጅ አዋቂ ሳይባል - ሁሉም ባንድነት ተሰብስቦ ደስታውን መካፈል ያገር ልማድ ስለሆነ፥ ገና ከትንሽነትዋ ጀምራ እንዲህ እንዲህ ባሉ የደስታና የጨዋታ ጊዜያት ከወላጆችዋ ጋር እየሄደች እነዚህን አገሮች ደህና አድርጋ ታውቃቸዋለች። ከነዚህ አገሮች ሌላ፥ ያራት ሰአት ያክል መንገድ ርቃ ሁለት ወይም ሶስት ጊዜ ደብረ ማርቆስን አይታለች። በቃ፥ ደመቀች ከደስታዋ በፊት የምታውቀው አለም ይህ ነበር!

ከባልዋ ቤት ተመልሳ ከወለደች በሁዋላ፣ ከወላጆችዋ ጋር ስትቆይ አማሪት ዮሀንስ ያክስትዋ ቤት በርከት ያሉ የድሜ ጉዋደኞችዋ የሆኑ ልጆች ስለ ነበሩበ እዚያ አዘውትራ ትሄድ ነበር። ብዙ ጊዜ ልጅዋን አዝላ እዚያ ትሄድና፣ ምሳዋን እዚያው በልታ፣ አንዳንድ ጊዜም እዚያው ስትጫወት አምሽታ ማታ ያክስትዋ ልጆችና የልጅ ልጆች ባንድ ላይ ሆነው ወደ ቤትዋ ይመልሱዋታል።

አንድ ቀን ጥዋት፣ ተከስተን ምሳ ስታበላ፣ እስዋም አብራው ትንሽ በልታ፣ አማሪት አክስትዋ ቤት ስትጭወት ለመዋል መሄድዋን ለናትዋ ነግራ፥ እንደ ልማድዋ ልጅዋን አዝላ ወጣች። ነገር ግን እንደ ልማድዋ ልጅዋን አዝላ ወታች። ነገር ግን እንደ ልማድዋ ቀን ወይም ማታ ወይም ማታ የራት ጊዜ እስኪያልፍ፣ ወላጆችዋ ቢጠብቁ አልተመለሰችም! ከዚያ በፊት፣ ያን ያክል አምሽታ አታውቅም። ስለዚህ ሰግተው፣ መላክተኛ ወደ አምሪት አክስትዋ ዘንድ ቢልኩ መላክተኛው ተመልሶ ‹እንዲያውም ዛሬ ከነጋ ጀምሮ ወዲህ ብቅ አላለችም› አሉኝ ብሎ ሲናገር ጸሀይ ቤት መጀመሪያ ብርቱ ድንጋጤ ከዚያ ወዴት ልትሄድ ወይም ምን ሊደርስባት እንደሚችል ባለማወቅ ችንቀት ጥበት ሆነ! ከዚያ ‹ወደ ታምራት ተገኝ የምትመልሱኝ መሆናችሁን ሳውቅ፣ ገደል ገብቼ እሞታለሁ› እያለች ለናት ላባትዋ መላልሳ ትናገር የነበረውን ሲያስታውሱ፣ በያሳባቸው አፍነው ሲያብሰለስሉት የቆዩት ጭንቀት ፈነዳና ጩኸት ድብልቅልቅ ሆነ! የናትዋ ሁኔታማ አይነሳም! እዬወደቁ እየተነሱ ቀሚሳቸውን ሲቀዱና ጠጉራቸውን እየነጩ ሲጮሁ ለያዥ ለገራዥ አስቸገሩ! ባሻ ጸሀይ ለራሳቸው ተጨንቀው የሚያደርጉትን

አጥተው ሳለ ደግሞ በዚያ ላይ ምሽታቸው የሚሆኑትንና የሚያደርጉትን ሲያኡ ይብሱ ግራ ገብቶዋቸው እሳቸውን ወደ ማባበሉና ወደ ማጽናናቱ ሄዱ።

«እስቲ እባክሽ ረጋ በይ! ወዲያውም - የምታደርጊውን ክፉ ምልኪ ነው፤ በልጅነቱ ክፉ አታምልኪባት። ረጋ ብሎ ተቀምጦ ምህረቱን፥ እንዲያወርድልን ከጉድ እንዲያወጣን አምላክን መማጠን ነው እንጂ - እድኒህ ያለው ክፉ ምልኪ ደግ አደለም፥ ክፉ ያመጣል» አሉ ባሻ። ነገር ግን ወይዘሮ ሙሉነሽ በመጽናናት ፈንታ እንዲያውም በባላቸው ላይ መአት ያወርዱባቸው ጀመር።

«ዝም ይበልኝ እስዎ! » አሉ ወይዘሮ ሙሉነሽ «ዝም ይበሉ! ልጄን በገደል ጥለው የገደሉዋት ልጄን የበሉዋት እስዎ ነዎ! የልጄ ገዳይ ደመናዬ እስዎ ነዎ፣ እፋረድዎታለሁ! » ሲሉ ስሜታቸውን መግታት ተስኖዋቸው። ባሻ ጸሀይ ምሽታቸውን ለማጽናናት የጀመሩትን መቀጠል በከንቱ ጊዜ ከማጥፋት በቀር ምንም ፍሬ የሌለው መሆኑን ስለ ተረዱ እዚያው እየወደቁ እየተነሱ በሚጮሁበት ትተዋቸው ወጥተው፤ የቤቱንም፥ የጐረቤቱንም ወንዶች ሰበሰቡና ባካባቢው ወዳሉት አገሮች ሄደው፥ በየዘመዱ ቤት እንዲፈልጉ አከፋፍለው ሰደዱዋቸው። ከዚያ እሳቸውም በበኩላቸው አንድ አሽከር አስከትለው ደመቀች ‹ልትደርስባቸው ትችላለች› ብለው የገመቱዋቸውን ቦታዎች ሁሉ አንድ ሳይቀራቸው ሲፈልጉ አድረው እሳቸውም ሆኑ ሌሎች እንኩዋንስ ደመቀችን ወሬዋን አጥተው ተመለሱ። የደመች አባት እንኩዋንስ ደመቀችን ወሬዋን አጥተው ተመለሱ። ቀኖች ድካምና የእንቅልፍ እጦት ሳያሸንፉዋቸው ዘመድ ወዳጅ የተባለውን ገደል ሆነ ዱር አንድ ሳይቀር በርበሩ፤ መነጠሩ፤ ነገር ግን የደመቀችን አንዳች ምልክት አላገኙም። የደመቀች የውሀ በሽታ ሆነች፤ ደብዛዋ ጠፋ!

በሶስተኛው ቀን ባሻ ጸሀይና ምሽታቸው ወይዘሮ ሙሉነሽ ፍሊጋውም ልቅሶውም አድክሞዋቸው አዝሎዋቸው ሊያጽናኑዋቸው ከተሰብሰቡት ዘመዶቻቸውና ወዳጆቻቸው ጋር ተቀምጠው ቀጥሎ ምን ማድረግ እንደሚሻልና እንደሚቻል ሲወያዩ፥ ‹ታምራት ተገኘ መጣ› ተባለ። ታምራት ምሽቱ የምትቀመጥባትን በቅሎ በጥልፍ እቃ አስጭኖ ቀሚስ አስለብሶ ፊት ለፊት እያሳበ፥ ልጁን የምታዝለዋን ሞግዚት - ካባ ሲቀር - ልክ እንደ ወይዘሮ ማለፊያ ቀሚስና ኩታ አልብሶ በበቅሎው አስቀምጦ እሱ ብዙ ባለ ብረትና ጀሌ አሽክሮች አጅበውት በሰጋሩ ተቀምጦ እንዶዳም ሲደርስ፣ ሁኔታው ሁሉ አዲስ ምሽት ለማግባት በሰርገኛ የታጀበ ሙሽራ እንጂ ተለይተው የቆየች ምሽቱን ወደ ቤትዋ ለመመለስ የመጣ አይመስልም ነበር። እዚያ ምሽቱን ወደ ቤትዋ ለመመለስ የመጣ አይመስልም ነበር። እዚያ እንደ ደረሰ የደመቀችን እስከ ልጅዋ መጥፋት ሲሰማ

ሊያምን አልቻለም። ከዚያ በፊት ምሽቱ ወደ ወላጆችዋ ከተመለሰች ጀምሮ ከሁለት አመት በላይ እሱ ራሱ ወላጆችዋ ከተመለሰች ጀምሮ ከሁለት አመት በላይ እሱ ራሱ እየተመላለሰም ሽማግሎች እዬላከም እንዲሰጡት ሲለምን ባሻ ጸሀይ «እሺ» የሚሉት እየመሰሉ አንዳንድ ጊዜም «እሺ» ካሉበሁዋላ ልዩ ልዩ ምክንያት እየፈጠሩ ቃላታቸውን ማጠፋቸውን ያውቃል። ስለዚህ፥ አሁንም ‹ጠፉች› ያሉት እስዋንና ልጅዋን ሸሽገው ላለመስጠት የፈጠራት አዲስ መላ፥ መሆኑን አምኖ በብርቱ ቁጣ እንደሚቀበላቸው እየማለና እዬዛተ ባዶ እጁን ተመለሰ።

ደመቀች አክስትዋ ቤት የምትሄድ መሆንዋን ለናትዋ ነግራ ከወጣች በሁዋላ የደብረ ማርቆስን አቅጣጫ ይዛ እማሪት ዮሀንስንና ባቅራቢያው ያሉትን መንደሮች እስከታልፍ የሚያውቁዋት ሰዎች አግኝትወ የምትሄድበትን እንዳይጠይቁዋት መንገዱን ወደ ጎን እየተወች ትንሽ ራቅ ብላ ሜዳውንም ዳሩንም ስትሄድ ቆይታ እንደርሞ ወንዝ ደረሰችኛ ስትሻገር «እማ ዋዋ» አለ ተከስተ። በሱ አማርኛ «ዋ ዋ» «ውሀ» ማለት ነው። ከመቾኮልዋ የተነሳ ረስታ ምሳውን ስታበላው ውሀ አላጠጣችውም ነበር።

«እሺ አብዬ» ብላ ከተሻገረች በሁዋላ አውርዳ ከወንዙ ዳር አስቀምጣው፥ ዙሪያውን ስትመለከት ከመሻገሪያው ትንሽ ዝቅ ብሎ ከዘንባባዎች መሀከል አንድ ካባ ስላዬች እዬሮጠች ሄዳ፣ ከዚያ ኮባ ቅጠል ቀዳ አመጣችና አንዳንድ ጊዜ መንደር በቅርብ በሌለበት ውሀ ሲጠጡ እንደሚያደርጉት ካንድ ወገን ሾጠጥ ከሌላ ወገን ሰፋ አድርጋ ሸብልላ የኮባ ዋንጫ አበጀች። ለተከስተ ከዚያ የኮባ ዋንጫ አንድ ጊዜ ጠልቃ ያጠጣችው በቃው። እስዋ ግን ምንም እንኩዋ ራስዋን ይሁን ሆድዋን ወይም ማናቸውንም ሌላ አካልዋን የተመመችው ባይኖር፥ ከፍራትዋና ካሳብዋ መታወክ የተነሳ ትኩሳ ስለ ነበራት፥ እዬደጋአገመች፣ ከልክ አሳልፋ ጠጥታ፣ ትንሽ እንኩዋን ሳታርፍ፥ ቶሎ ልጅዋን አዝላ ጉዞዋን ቀጠለች። ነገር ግን የቸኮለችውን ያክል ብዙ ልትሄድ አልቻለችም። የግብጣይትን አቀበት እንዳጋመሰች፣ ሳንባዋ ከቦታው ወጥቶ ጉሮሮዋ እንደ ተወተፈ ሁሉ ከላይ ከላይ እየተነፈሰች፥ ሰውነትዋ ሁሉ ከጠጣችው ውሀ በበለጠ ላብ ተነክሮ፥ ጉልበቶዋ እስዋንና ልጅዋን መሸከም ተስኖዋቸው እየተብረከረኩ ብርቱ ድካም፥ ጠቅላላ ዝለት፥ ተሰማት። ወዲያው መንገዱን ትታ ወዳንድ ቁጥቋጦ ውስጥ ገባችና፣ ልጅዋን አውርዳ እፊትዋ አስቀምጣ፣ ላብዋ ጠፈፍ እስኪልላት ጠለቅ አድርጋ መተንፈስ እስክትችል፥ እግሮችዋን ሰተት አድርጋ ዘርግታ በጀርባዋ ተኝታ ትንሽ አረፈች።

እናቱ ስትተኛ ሲያይ፣ «እማ፣ ኛ ኛ» አለ ልጅዋ። «ኛ ኛ» በሱ አማርኛ «አስተኝኝ» ማለት ነው። አንድ ክንድዋን አንተርሳ በጎንዋ እንዳተኛችው ወዲያው እንቅልፍ ወሰደው። እድኒያ ትንሽ አርፉ ቆይታ ሰውነትዋን አጥልቆት የነበረው ላብ እንደ መድረቅ ሲልና እንደ ልብዋ መተንፈስ ስትጀምር ተጠንቅቃ ተነስታ ልጅዋን እንደ አንቀላፋ አዝላ ቀስ እያለች አቀበቱን ዘለቀች።

ከዚያ ገና በሩቅ ሰው ስታይ ወይም ያዬች ሲመስላት መንገዱን ትታ፥ በጎን፣ ቁጥቋጥው ለቁጥዋጦ እዬሄደች፣ ከዚያ ቆም ብላ ትመለከትና፥ እስከ ወዲያ ድረስ በመገዱ ሰው አለመኖሩን ስታረጋግጥ መንገዱን ይዛ እየሄደች፣ ካራት ሰዓት፥ ግፋ ቢል - ለደካሞች እንኩዋ - ካምስት ሰዓት የበለጠ የማያስኬደውን መንገድ ሰባት ሰዓት ተጉዛ፣ በዘጠኝ ሰዓት ደብረ ማቆስ ደረሰች።

ደብረ ማርቆስ፣ ከተማ የገባች እንደሆነ ድንገት የሚያውቃት ሰው በመንገድ እንዳያጋጥማት ፈርታ፥ በቀጥታ ወደ ቤተ ክርስቲያን ሄደች። እዚያ፥ ከቤተ ክርስቲያኑ ቅጽር ውጪ ስትደርስ፥ በመግባትና ባለመግባት መሀከል ስታመነታ ትንሽ ከቆየች በሁዋላ እንደ ሌባ ቀስ ብላ፣ በጥፍሮችዋ እያጠቀሰች ደጀ ሰላሙን ገብታ ቆመችና፣ ያን ሰፊ አደባባይ በቁሙም በወርዱም፥ ከዳር እሰከ ዳር ብትመለከት የሰው ይቅርና የሌላ ነፍስ ያለው ነገር ምልክት አይታይም። ሰው እንኩዋ፣ ምንጊዜም ቢሆን፥ ባዘቦት ቀን ከዘጠኝ ሰዓት በሁዋላ፥ ከቤተ ክርስቲያን ቅጽር ውስጥ አለመገኘቱ የተለመደ ነው። እሱዋም ከሰው ስለምትሸሽ፣ እዚያ ሰው እንዲኖር አትፈግም። ነገር ግን፣ የዚያ ሰፊ አደባባይ ፍጹም ባዶነት፣ ከሰው የባሰ አስፈራት። ከዚያ ግቢ ተለይተው የማያውቁት የዚያ ግቢ ነዋሪዎች የሆኑት፣ የርግቦች፥ የወፎች፣ የሽኮኩላዎች ምልክትም ያንለት አይታይም ነበር። ያንለት አይን የሚያየው ብቻ ሳይሆን፥ ጆሮ የሚሰማውም አንዳች ነገር አልነበረም። ያንለት ወፎች እያፉዋጩ፥ አሽኮኩላዎች አይንጫጩ ነፋሱስ አይተነፍስ፣ ዛፉ አይንቀሳቀስ፣ እንዲያው ሁሉም ዝም እንዲያው ሁሉም ጸጥ፣ ሰት ብሎ ያስፈራራ ነበር! ስለዚህ የዚያ ልብ የሚያባባ ዝምታ፥ የዚያ ርጭታ ግርማ ያስፈራራትና ቀስ ብላ በጥፍሮችዋ እየቆመች የገባችውን ደጀ ሰላም እየሮጠች ወጥታ እውጭ ቆመች። እዚያ ከቆመችበት አጠገብ አንድ የወደቀ ደረቅ ግንድ ነበር። እሱን ስታይ፥ እስከዚያ ድረስ ሰባት ሰዓት ሙሉ ስትጉዋዝ ያልተሰማት ብርቱ ድካም ብርቱ፥ ዝለት ተሰማት። ወዲያው ከሰባት ሰዓት በላይ እስዋንና ልጅዋን ባንድ ላይ ተሸከመው የዋሉት ጉልበቶችዋ፥ ያ ተጭኖዋቸው የዋለው ከባድ ሸክም አንገፍግፎዋቸው፥ በሱ ላይ ለማዶም እንደ ፈለጉ ሁሉ ያን ተጭኖዋቸው ጨቁኖዋቸው የዋለ ከባድ ሸክም «እምቢ በቃን» ብለው ለመገልበጥ እንደ ፈለጉ ሁሉ በሀይል መታወክ፥ በሀይል

መናወጥ ሲጀምሩ፥ በቶሎ ጎንበስ ብላ በሁለት እጆችዋ ግንዱን ተመርኩዛ በላዩ ተቀመጠች። ትንሽ ተቀምታ የሚንቀጠቀጠው ጉልበቶችዋን ካሳረፈችና ሰውነትዋን ሁሉ አዝሎት የነበረው ብርቱ ድካም እንደ ማለፍ ካለላት በሁዋላ ከዚያ፥ ተነስታ ለመሄድ ብታስብም ወዴት እንደምትሄድ አቅጣጫውም መድረሻውም ጠፋት።

ከወላጆችዋ ቤት ልጅዋን አዝላ ስትጠፋ መጥፋትዋን እንጂ ጠፍታ ወዴት እንደምትሄድና ምን እንደምታደርግ ባሳብዋ ያስቀመጠችው ነገር የለም። ደብረ ማርቆስ ከምታውቃቸው አገሮች ሁሉ የራቀ ስለ ሆነ በሱ በኩል አድርጋ የትም ቢሆን፥ ምንም ቢደርስባት ደግሞ ከሱ ሩቅ ወደ ሆነ አገር ሄዳ ለመጥፋት ነው እንጂ፥ ደብረ ማቆስ የሽሽትዋ መጨረሻ እንዲሆን አስባ አልመጣችም። የሽሽትዋ መጨረሻ፥ አላማዋ፥ ከታምራት ተገኝ እጅ ማምለጥ ብቻ ነው! የዚያ የምትጠላውና እንደ ጣእረሞት የምትፈራ፥ ታምራት ተገኝ ከፉ መንፈስ «ሹ» እንዳሉት ከፉ ውሻ፥ ጥርሱን አግጥጦ፥ ሊይዛት አሰፍስፎ፥ ሁዋላ ሁዋላዋን ስለሚከተላት፣ ስለሚያሳድዳት የሽሽትዋ መጨረሻ፥ አላማዋ፥ ከሱ ማምለጥ ብቻ ነው! ከሱ ካመለጠች የትም ብትደርስ፣ ምንም ቢደርስባት በሱ እጅ ከመውደቅ የማይሻል ነገር የለም! ነገር ግን ከደብረ ማርቆስ ወዲያ፥ እንኩዋንስ መልኩንና አቅጣቻውን፥ በሙሉ ጎጃም ስሙን የማታውቀው፥ ሩቅ አገር የለም። ስለዚህ ከዚያ ተነስታ የምትሄድበት ጠፍቶዋት፥ ዝም ብላ በግንዱ ላይ እንደ ተቀመጠች አሳብዋ በያቅጣቻው ሲባክን፣

«እማ፥ እንጣ» አለ ተከስተ።፡ ‹እንጣ› ‹አብይኝ› ማለት ነው።

«እሺ፥ አብዬ» አለች፥ ራስዋን የራሱ ላይ ወዳለበት ወደ ትከሻዋ አዙራ።

ተከስተ አንዳርሞ ወንዝ እንደ አንቀላፋ፥ ታዝሎ ብዙ መንገድ ከተጐዋዘ በኋላ ሲነቃ እናቱ አንድ ጊዜ በመንገዱ፥ ከዚያ በቁጥቋጦው እንደገና በመንገዱ ከዚያ፣ በዱሩ ደግሞ እንደ ገና በመንገዱ፥ በገባችና በወጣች ቁጥር የሚለዋወጠው አዳዲስ አካባቢ፣ ከዚያ በፊት ከሚያውቀው ከባሻ ጸሀይ ግቢና በዙሪያው ካለው፥ ጠባብ አለም የተለዬ ስለ ሆነበት፥ አስገርሞት ይሁን አስፈርቶት ዝም ብሎ ከመመልከት በቀር አንድ ቃል ሳይተነፍስ ነው የዋለ። እናቱ እዚያ ደረቅ ግንድ ላይ ተቀምጣ ካረፈችና አካባቢው ሁሉ በየደቂቃው መለዋወጡ ሲቀር፥ የሱም ስሜት ከሚለዋወጠው አካባቢ ጋር መለዋወጡን ትቶ አረፈ። ወዲያው ራብ ስለ ተሰማው «እንጣ» አለ።

«እንጣ - አ» አለ ሁለተኛ፥ የመጀመሪያው ‹እንጣ› ከተሰፋ በቀር የሚበላ ነገር ስላላመጣለት፥ እንደ ማልቀስ ቃጥቶት።

«እሺ አብዬ፤ ትንሽ ቆይ» አለች ደመቀች፥ ትንሽ መቆየት የሚባላ ነገር ይፈጥላት ይመስል። ልጅዋ ርቦት ማልቀስ ሲጀምር «አይዞህ የኔ ጌታ፥ ትንሽ ቆይ» እያለች አባብላ ዝም እንዲል ካደረገችው በሁዋላ፥ ከተቀመጠችበት ግንድ ተነስታ የምትሄድበትን አቅጣጫ በመምረጥ ስለ ቸገራት ትንሽ ስታመነታ ቆየች። ከዚያ በቤተ ክርስቲያኑ እድሞ ጥግ ለጥግ፥ ወደ ምስራቅ መሄድ እንደ ጀመረች፥ ብዙ ሳትርቅ፥ መቃብር ቤቱ፥ ዙሪያውን ካለው ዱር በቀር ባጠገቡ ሌሎች መቃብር ቤቶ ስለማይታዩ፣ በጫካው ውስጥ ብቻውን የተሰራ፥ የመናኝ በአት ይመስላል። እደጅ ሁለት እመበለቶች ተቀምጠው ይጫወታሉ።

## ምዕራፍ ሶስት

# ደመቀችና ሁለቱ እመበለቶች

ሁለቱ እመበለቶች፥ እናታችንና እማሆይ ወለተየሱስ ተረጂና ረጂ ናቸው። ተረጅጂቱ እናታችን፥ ጐጃም፥ ወደ ደጋው ክፍል፥ ጣሜ ጊዮርጊስ በሚባል አገር ነው የተወለዱ። ወላጆቻቸው ገና በህጻንነታቸው ስለ ሞቱባቸው፥ መነኩሲት አክስታቸው፣ በሴቶች ዘንድ ብዙ ያልተለመደውን ዜማም ቅኔም፥ እያስተማሩ ሲያሳድጉዋቸው የባል ማግቢያ ጊዜያቸው ስላለፈ፥ ካለማዊው መንፈሳዊውን ጥሪ ወደ መከተሉ አዘነበሉና ያለም፥ ስማቸውን ትተው በክርስትና ስማቸው «እማሆይ አመተ ድንግል» ተብለው መነኮሱ። ያን ጊዜ፥ ያገሩ ሰው ‹ለካ ገና ክርስትና ሲነሱ «አመተ ድንግል» የተባሉ፥ በድንግልና እንዲመነኩሱ ጥንቱን እግዚአብሔር የመደበው ስለ ሆነ ነው!› እያለ ተገረመ።

እማሆይ አመተ ድንግል ከመነኰሱ በሁዋላ፥ ጣሜ ጊዮርጊስ አልቆዩም። ላጫጭር ግዜ፥ ሞጣ፣ ደረብ ወርቅና፥ ዲማ ሲዘዋወሩ ቆይተው ደብረ ማርቆስ አንድያቸውን ተቀማጭ ለመሆን የገቡበት ጊዜ ረዥም ከመሆኑ የተነሳ እንኩዋንስ ሌላ ሰው እሳቸውም ረስተውታል። ከሊቅነታችወ ሌላ ‹ንጽህት፥ ቅድስት ናቸው› የመባልን ዝና በደብረ ማርቆስ ብቻ ሳይሆን ባካባቢው ሁሉ አግኝተው ይኖራሉ። ‹ህልማቸው በመሬት ጠብ የማይል ከመሆኑ ሌላ፥ ትርጉም የማያሻው፥ ገሀድ ነው፤ እግዚአብሄር በግልስ ያነጋግራቸዋል› ተብሎ ስለሚታመን ‹አይርሱኝ› የሚለው እንደ ታቦት

‹ያማልዱኝ› የሚለው ሁሉ የሚያገባላቸውን መብል መጠጥና ጥሬ ገንዘብ መልሰው ለተመጽዋች ባይናኙት ኖሮ፥ መብል መጠጡ ቀርቶ ገንዘቡ ብቻ፥ ከሀብታሞች «አንድ» ተብለው የሚቆጠሩ ሊያደርጋቸው በቻለ ነበር! ጊዜ እያለፈ ሲሄድ በትልቁም፥ በትንሹም፥ ዘንድ እየተወደዱና እዬተከበሩ ስለ ሄዱ፥ በትልቁም በትንሹም ዘንድ እየተወደዱና እዬተከበሩ ስለ ሄዱ፥ «እማሆይ አመተ ድንግል» መባላቸው ቀርቶ፥ «እናታች» ተባሉ።

የማሆይ ወለተየሱስ ምንኩስና ታሪኩ ሌላ ነው። ከመመንኮሳቸው በፊት፥ ያለም ስማቸው ‹ጥሩ ወርቅ አየለ› ነበር። የሚበዛውን ጊዜ ንጉስ ሴንግስ ተራ ሰው ሲመነኩስ በክርስትና ስሙ መጠራት ልማድ ስለሆነ ሲመነኩሱ በክርስትና ስማቸው ‹እማሆይ ወለተየሱስ› ተባሉ።

ወይዘሮ ጥሩ ወርቅ አየለ እዚያው ደብረ ማርቆስ ተወልደው አድገው፥ ላጫጭር ጊዜ ሁለት ባሎች እያገቡ ከፈቱ በሁዋላ የባል ማግባቱን ነገር «ወዲያ» ብለው ባለማዊነታቸው ስማቸውን አስጠርተው ይኖሩ ነበር። እድሜ ከቆየ መቸም ብልትትና አይቀር፣ አዬበለተቱ ሲሄዱ፥ ያ ያማረ የጋመረ መልካቸው እየደበዘዘ፥ ዝናቸው እየቀዘቀዘ ሄደ። ሁዋላ ሁዋላ እንዲያውም ችላ ወደ መባሉ ወደ መረሳቱ ስለ ደረሱ፥ አስበው አሰላስለው፥ ባለፈው ለኖሩት ህይወታቸው ስርዬትን ወደፊት ለሚኖሩት ህይወታችው ሙሉ እረፍትን የሚያገኙ፣ መንኩሰው መቃብር ቤት የተቀመጡ እንደ ሆነ ብቻ መሆኑን አምነው መነኮሱ። ልጆች፥ ወይ እህቶችና ወንድሞች ስላልነበሩዋቸው በገንዘብ ሆነ በሌላ ንብረት የነበራቸውን ሀብት ለቅርብና ለሩቅ ዘመዶቻቸው አከፋፍለው፥ ዘመዶቻቸውም እማሆይ እስካሉ ድረስ፣ እህል ውሀና ልብስ ሊሉዋቸው የምንት ቃላቸውን ሰጥተዋቸው እናታችንን እየረዱ መቃብር ቤት ሊቀመጡ ሄዱ።

እናታችንና እማሆይ ወለተየሱስ፣ በተዝካር በዝክር በክርስትና ቀን ከቤተ ክርስቲያን ከሚገኘው ሌላ ለናታችን ከየቤቱ ለማሆይ ወለተየሱስ ከዘመዶቻቸው ቤት ከሚመጣው መብልና መጠጥ የሚበዛው፣ በየመቃብር ቤቱ ለሚኖሩት መነኮሳትና ደጀ ሰላም እድረው ለሚሄዱት መንገደኞጭ፡ኘው የሚናኘው። እነሱ ዘንድ የሚቀረ፣ እማሆይ ወለተየሱስ በቀን አንድ ጊዜ በዘጠኝ፥ ሰዓት ግድም የሚበሉትና የሚጠጡት፥ እንዲሁም ለምንም ለምን መጠባበቂያ ብለው የሚያስቀምጡት ብቻ ነው። እናታችን መቸም ከቅዳሜና ከሁድ በቀር ባፋቸው እንጀራ አይገባ! ከኛስ እስከ አርብ፥ ባቄላ ወይም ሽምብራ ቦቀልት ተቀቅሎ ጎመን ምንም ዓይነት ቅባትና ጨው ሳይነካው

እንዲሁ በውሀ ሁሉ ፊተኛው ሁልጊዜ እሸት ሁልጊዜ በጫጉላ ተቀምጣ የምትቀለብ ሙሽራ እንጂ፣ በጥሬና በቅጠል የሚኖሩ የመናኝ መነኩሲት ፊት አይመስልም።

ደመቀች ያን ሳታየው የቆየችውን መቃብር ቤትና ሁለት እመበለቶች ድንገት ስታይ «ቁሚ» የሚል ትእዛዝ እንደ ሰማች ሁሉ እግርዋ ሊራመድ የቃጣውን ቶሎ ገታ ቆመችና ዝም ብላ ወደ ሁለቱ መነኩሲቶች ትመለከት ጀመር። ሁለቱም የለበሱት ልብስና የደፉት ቆብ ወይባ የተነከረ ይሁን እንጂ ንጹህ መሆኑ ከሩቅ ያስታውቃል። የቆመችበት ከነርሱ ትንሽ ራቅ ያለ ስለሆነና፥ ወዲያውም በሁዋላቸው በኩል ስለሆነች፥ ምን እንደሚነጋገሩ ለመስማትና ፊታቸውን ለማየት ባትችልም፥ ባጫጭር ጊዜ ውስጥ እየመላለሱ ሲስቁ ድምጻቸው እዚያ ድረስ ስለ ተሰማት፣ በጣም፥ ደስተኞች መስለው ታዩዋት። ‹ከነሱ ጋር እየተጫወቱና እየሳቁ፥ እዚህ መኖር እንዴት ጥሩ ነው!› አለች ባሳብዋ። ወዲያው፥ ትንሽ ልጅ ሳለች ጀምራ፥ የባሻ ጸሀይና የቤተሰባቸው የንስሀ አባት ቄስ መንግስቱ ከወላጆችዋ ጋር ባንድ ላይ ቁጭ ብለው ጠላ እየተጠጣ ሲጫወቱ ስለ ምናኔና ስለ ምንኩስና የሚያወሩት አሳብዋ መጣ። ቄስ መንግሥቱ እንደሚሉት «አንድ ሴት በድንግልናዋም ይሁን ወይም ካገባች በሁዋላ፥ ባልዋን ትታ ከመነነችና ገዳም ከገባች ወይም መንኩሳ መቃብር ቤት ከተቀመጠች ከዚያ ወጥታ ለባል እንድትሰጥ የሚያስገድዳት የለም። ከዚያ በሁዋላ ለራስዋ አዛዥዋ እስዋ ብቻ ናት። በብር የተገዛች አገልጋይ እንኳዋ ከመነኮሰች ነጻ ናት። ‹የመነኮሰ በራሱ ነገሰ› የሚባል ለዚህ ነው» ይላሉ አባ መንግሥቱ፥ መንኩሰው ከአለም የተለሉ፥ ማለት ገዳም ወይም መቃብር ቤት ገብተው የተቀመጡ ሁሉ፣ በሌላ ባይሆን በራሳቸው ላይ አዛዦቹ እነሱ መሆናቸውን በምሳሌ ሲያስረዱ። እናትዋ ወይዘሮ ሙሉነሽም ሲበሳጩ ብዙ ጊዜ ካፋቸው የሚወጣ መንኩሶ መቃብር ቤት መቀመጥ ነው። ባላቸው ትልቁንም፥ ትንሹንም ጉድለት እዬቆጠርኡ ሲጨቀጨቁዋቸው ወይም አሽከሮች የያዙዋቸውን እንደ ፈለጉት አድርገው ሳይፈጽሙላቸው ብስጭት ይሉና፥ ምነው እኔይቱ ሙሉነሽ! ካንድ ወገን እሳቸው - ውሀ በቀጠነ ሲጨቀጭቁኝ ደግሞ ካንድ ወገን እናንተ እዬመላለስሁ የምነግራችሁን - መስሚያችሁን ይድፈነውና - አንስማ እያላችሁ ልቤን ስታቆስሉኝ እንዲህ በሁለት እሳት መሀከል ስቃጠል ከመኖር - ሁሉንስ ጣጥዬው፥ ቆቤን ደፍቼ፣ መቃብር ቤቴ አልገባም? የባል ይሁን ያሽከር ወይም የሌላ ጣጣ እዚያ ተከትሎኝ አይመጣምኮ! ይሁን ሁሉ፥ የተሸከምሁትን ጣጣ ከራሴ  አውርጄ ጥዬ፥ መቃብር ቤቴ ግብቼ ‹ኧሁ -!› ብዬ አርፋለሁ! » ይላሉ። ስለዚህ ቄስ መንግሥቱና የደመቀች እናት ወይዘሮ ሙሉነሽ እንደሚሉት ከሆነ፥ ምናምኔ ምንኩስና ለባሉ፥ ለኑሮ

ችግሩ ለጭቅጭቁ፥ ኧረ ለስንቱ፥ አለምን ለሚያስጠላው በሽታ ሁሉ ፍቱን አብነቶች እሙን መድሀኒቶች ናቸው!

ደመቀች ያን መቃብር ቤትና ሁለቱን መነኩሲቶች እየተመለከተች እንደ ቆመች፥ ስለ ምንኩስና ስትሰማው የኖረችው ሁሉ ባንድነት ሰብስቦ፥ ተሰብስቦ ባሳብዋ መጣ። ይልቁንም ምንኩስና ተገድዶ ለባል ከመስጠት የሚያድን መሆኑን ቄስ፣ መንግሥቱ ብዙ ጊዜ ሲናገሩት የሰማችው፣ ከሁሉም ጎልቶ ለእዝነ ህሊናዋ ተሰማው። «አንድ ሴት ባልዋን ትታ ከመነኮሰችና መቃብር ቤት ገብታ ከተቀመጠች ከዚያ አውጥቶ ለባል የሚሰጣት የለም! » አለ የቄስ መንግሥቱ ድምፅ ጆሮዋን እስኪያማት ጮሆ። «በብር የተገዛች አገልጋይ እንኳዋ ከመነኮሰች፥ ነጻ ናት! » አለ ድምጹ ደገመና። ወዲያው ከሱ ጋር ተያይዞ ሌላ እስከዚያ ቀን ድረስ ተቀምጣ ባሳብዋ ተኝታ በልምዋ፥ ታይትዋት የማያውቅ አዲስ አሳብ ድንገት ብልጭ አለባት፥ «መመንኮስ! » ከመነኮሰች ለዚያ ለጨካኝ ባልዋ፥ ለታምራት ተገኝ አስገድዶ የሚሰጣት የለም!

«ከመነኮሰች ነጻ ናት፥ ከመነኮሰች ነጻ ናት! » አለ የቄሱ ድምጽ እዬደጋገመ በጆሮዋ።

«እመነኩሳለሁ በቃ፥ ነጻ ነኝ! » አለች እስዋም ያሰበች እንጂ የተናገረች ሳይመስላት፣ ድምጽዋን አሰምታ። ወዲአይው፣ ያ እንደ ከፉ ውሻ «ያሽሁሽ» እያለ የሚያሳድዳት የታምራት ተገኝ ክፉ መንፈስ የቄሱ ፍርድና የስዋ ፉከራ እንዳባረሩት ሁሉ ከሁዋላዋ ሸሽቶ የጠፋ፥ ከሱ ነጻ የሆነች መስሎ ተሰማትና ከደስታዋ ብዛት የተነሳ፥ ልብዋ ፈጥኖ እዬመታ፣ እግሮችዋም እንደ ልብዋ ፈጥነው እዬተራመዱ ከመነኩሲቶች ፊት አቁመዋት አገኘች። ሁለቱ መነኩሲቶች ያችን፥ ልትላክ የተጠራችው ይመስል ስተት ብላ ሄዳ አንድ ቃል ሳትተነፍስ ሰላምታ እንኩዋ ሳትሰጥ እፊታቸው የቆመች እንግዳ ልጅ ሲያዩ ገርሞዋቸው፥ ጨዋታቸውን አቋርጠው፥ ዝም ብለው ይመለከቱዋት ጀመር። ደመቀች የምትናገረው ጠፍቶዋት፥ ግንባርዋ ጭምድድ ፊታ እያለ ከፍነርዋና ጉንጮችዋ እየተንቀጠቀጡ ዝም ብላ ስለ ቆመች፥ መናገር እየፈለገች የማትችል፥ ድዳ መስላቸው ሊያረጋግጡ ፈለጉና፣

«ምን ትሻለሽ፥ የኔ ልጅ? » አሉ እናታችን። ደመቀች ካፍዋ ቃል ከመውጣቱ በፊት ካኖችዋ እንባ መውረድ ሲጀምር፥ ልጅዋን እንዳዘለች ከፊታቸው ወድቃ፣

«አባ እባካችሁ ከሞት አድኑኝ፤ ልሞ - ልሞት ነው። አባ - እባካችሁ አድኑኝ፤ እና - እናቶቼ። እባካችሁ አመ - አመንኩሱኝና እድሜ - እድሜ ልኬን፤ እናንተን

እያገለገልኩ እዚህ - እዚህ ልቀመጥ፣ ሌላ ም - ምንም አልፈልግ» እያለች ስታለቅስ ሲያይና ንግግርዋን ሳግ ሲያደናቅፈው ሲሰማ፥ ተከስተም እኒያ መነኩሲቶች አንድ ከፉ እንገር አድርገው ያስለቀስዋት መስሎት፥ አብሮዋት ምርር ብሎ አለቀሰ።

ከዚያ ሁለቱ እመበለቶች፣ እኒያ ሁለት ልጆች ድንገት እንደ ዱብ እዳ፥ ከፊታቸው ወደቀ ተያይዘው ሲያለቅሱ ሲያዩ፥ ተደናግጠው ቶሎ ከተቀመጡበት ተነስተው፣ ደመቀችን ከነልጅዋ አንስተው የስዋንም የልጅዋንም እንባ በልብሳቸውም በጃቸውም እያባበሱ ሲያባብሉዋቸው ቆይተው ጸጥ ሲሉላቸው -

«በይ እስቲ እዚህ ተቀመጭና የሆንሽውን ንገሪን» አሉ እናታችን ለደመቀች የምትቀመጥበት ቦታ በጎናቸው በኩል እያመለከቱ። ደመቀች ባለመከትዋት ቦታ ተቀምጣ የሆነችውን ለመናገር የምትጀርምበትን ስትፈልግ ተከስተ እኒያ እናቱን «አስለቀሱ» ብሎ ፈርቶዋቸውና ጠልቶዋቸው የነበሩ መነኩሲቶች እስዋንም እሱንም ሲያባብሉ ሲያይ፥ ወዲያው ዘመዶቹ አድርጎዋቸው ፍራቱንም ጥላቻውንም ረስቶ፥ «እማ፥ እንጣ» አለ።

«እኔ አፈር ልብላ፤ ርቦታል። እማሆይ እባክዎ እንጀራ ይስጡት፤ ለሁለቱም የሚሆን ያምጡላቸው» አሉ እናታችን። ከዚያ ወደ ደመቀች ዘወር አሉና፥ «ቀድመሽ እህል ቅመሽ፤ ሁዋላ ትነግሪናለሽ» አሉ።

«አይኔ ይፍሰስ፥ ልጄን ርቦታል። ከዚህ፥ ከከተማ አይደለም የመጣችሁት? » አሉ እማሆይ ወለተየሱስ፥ እንጀራ ሊያመጡ ሲነሱ።

«አይደለም፤ ከንዶዳም ኪዳነ ምህረት ነው። ጥዋት ተነስተ አሁን ነው - እዚህ የደረስን» አለች ደመቀች። ሁለቱ መነኩሲቶች እንዶዳም ኪዳነ ምህረት አይተውት ስለማያውቁ፥ ‹ከጥዋት እስከ ማታ የሚያስሄድ ከሆነ ሩቅ መሆን አለበት› ብለው፥ ያን ያክል መንገድ ልጅ አዝላ ስትሄድ በመዋልዋ ለደመቀች ያዘኑላት ከመሆናቸውም ሌላ ተገረሙ።

እንጀራ ሊያመጡ የተነሱት መነኩሲት ሁለት እንጀራ በዝብድያ (የሽክላ ቁና) አድርገው፥ በላዩ ወፍራም የክክ ወጥ በርከት አድርገው አፍስሰው ሲሰጡዋት፥ ደመቀች ሰግዳ ተቀብላ፥ ልጅዋን አብታል ካጠገበች በሁዋላ፥ እስዋም እስክትጠግብ በላች። ከዚያ እማሆይ ወለተየሱስ፣ በትልቅ ጥዋ ጥሩ ጠላ አምጥተው ሲሰጡዋት ተከስተ አይቶ «እማ ዋ ዋ» እያለ አስቸገረ።

«ዋ ዋ» ምን ይሆን? » አሉ እማሆይ ወለተየሱስ እንደ መሳቅ ብለው።

«ውሀ» ማለቱ ነው። «ውሀ ይኖር ይሆን እናቴ? » አለች ደመቀች አስቸገረችን ይሉኛል ብላ እየፈራች።

«አዬ - ትንሽ ነበር - ቅድም - በተሳት ምሳ በልተን እጃችንን ታጠብንበት። ውሀ የምታመጣልን ልጅ ደግሞ ትዘገይ ይሆናል። ታዲያ - እንደ ጠማው ከሚቆይ - ጠላ ቢጠጣ ምን ይለዋል? » አሉ እማሆይ ወለተየሱስ።

«ደሞ ጠላ ምን ይለዋል? እህል አደል? » አሉ እናታችንም ቀበል አድርገው። ብቻ ተከስተ ሁለቱ መነኩሲቶች ስለ ጠላ መጉዳት አለመጉዳት ምስክርነታቸውን እስኪሰጡ አልጠበቀም። በጣም ተጠምቶ ስለ ነበረ ገና እነሱ በመነጋገር ላይ እንዳሉ፥ እናቱን አሸንፎ መጠጣት ጀምሮ ነበር። ጥሙን እስኪቆርጥ ስምጥጥ አድርጎ ጠጥቶ ሲያበቃ የተረፈውን ለናቱ ሰጠና፥ እስዋ ገና ጠጥታ ሳትጨርስ የጠጣው ጠላ ወደ ትንሽ ራሱ ወጥቶ ስላሰከረው ፊቱም ጆሮዎቹም እንደ ፍም ቀልተውና ግለው፥ የኮረኮሩትን ያክል ትንፋሽ እስኪያጥረው እየሳቀ የበሉበትን እቃ «ካልሰበርሁ» ብሎ «ለያዥ ለገራዥ» አስቸገረ! እናቱ ለመያዝ ሞክራ አልሆንላት ስላለና፣ እንዲያውም የባሰ ራሱን የሚጎዳ ስለሆነ ርቆ እንዳይሄድ እየተከላከለች ብቻ ዝም ብላ፥ የሚያደርገውን ትመለከት ጀመር። እማሆይ ወለተየሱስ እቃውን ከጁ ስላገኙ ያን አንስቶ እየሳቀ እናታችነን «ካልመታሁ» ብሎ ሲጋበዝ ቆየና እሱንም ተቀማ። ከዚያ ጠበኛነቱን ትቶ ወደ ሰላማዊ ጨዋታ ዞረ። በሳቅ እየተንከተከተ መዝለል፥ አንዳንድ ጊዜም መሮጥ ከመጀመሩ ይወድና ይንከባለላል። መዝለል፥ አንዳንድ ጊዜም መሮጥ ከመጀመሩ ይወድቅና ይንከባለለል። እድኒህ ሲዘልና ሲሮጥ ወድቆ እየሳቀ ሲንከባለል ቆይቶ፥ ደግሞ ያን ተወና የህጻናትን «የሽሽጎሽ» ጨዋታ መጫወት ጀመረ። ህጻናት ሰው እንዳያያቸው ሲሸሹ፥ የገዛ አይኖቻቸውን በሁለት እጆቻቸው መሸፈን ነው። ተከስተ አይኖቹን በጆቹ ሸፍኖ፥ መሬቱን በግሮቹ እዬዳበሰ፥ ድምጹን ሳያሰማ ቀስ ብሎ ሲሄድ ይቆይና ሲወድቅ እዬሳቀ ይንከባለላል። እንዲህ ሲወድቅ ሲነሳ ደግሞ ወድቆ ሲንከባለል ዘለግ ያለ ጊዜ ቆይቶ፣ እዬደከመው ስለ ሄደ መጨረሻ ወድቆ በሚነከባለልበት እንዳለ፣ እንቅልፍ አሸነፈውና ተኛ። ከዚያ ደመቀች ከወደቀበት አንስታ ወደ ተሻለ ቦታ ወስዳ ኩታዋን ግማሹን አንጥፋ፥ ግማሹን አልብሳ፥ አስተኝታ፥ ባጠገቡ ተቀምጣ ትጠብቀው ጀመር።

ተከስተ እንዲያ ሳቁን ስያቁዋርጥ፥ መጀምሪያ «እቃ ካልሰበርሁና ካልተማታሁ» ብሎ ሲጋበዝ፥ ከዚያም እየዘለለ፥ እየሮጠና ወድቆ እየተንከባለለ ሲያደርገው የነበረው የተመልካቾቹን ለማጫወትና ለማሳቅ እንጂ፣ ሰክሮ ሳያውቅ የሚያደርገውን እንዳልነበረ ሁሉ ሁለቱ መነኩሲቶች ደስ ብሎዋቸው አንድ አፍታ እንኩዋ ጥርሳቸውን ሳይከድኑ ያን ሁሉ ጊዜ አብረውት ሲስቁ ቆዩ። ደመቀች ግን የሚያልፍለት ስላልመሰላት የምታደርገው ቅጡ ጠፍቶባት ፈዝዛ ነበር። መነኩሲቶች ጭንቀትዋን ከፊትዋ ከተመለከቱ በሁዋላ አስቀድመው የስዋን ሁኔታ ሳያዩ፥ ያን ያክል ሲስቁ በመቆየታቸው የህሊና ወቀሳ ተሰምቶዋቸው እርስ በርሳቸው ተያዩና -

«አይዞሽ፥ አሁን እንዲህ ከተኛ አለፈለት ማለት ነው። እንዴት ያለ ደማም ልጅ ነው! ምንሽ ነው? » አሉ እማሆይ ወለተየሱስ።

«ልጄ ነው» አለች ደመቀች እንደ ማፈር ብላ መሬት መሬት እያየች።

«አንቺ የወለድሽው? » አሉ ሁለቱ መነኩሲቶች እንደ ተማከሩ ባንድ ላይ።

«አዎ» አለች ደመቀች አንገትዋን እንደ ደፋች።

መነኩሲቶቹ ትንሽ ዝም ብለው የመገረም አይን ከተለዋወጡ በሁዋላ፣

«በይ እስቲ እንግዲህ - ይህን ትንሽ ልጅ አዝለሽ ወደኛ የመጣሽበትን ምክንያት ንገሪኝ» አሉ እናታችን።

ደመቀች፥ ያን እንደ መርግ ልብዋን ተጭኖ ሲያስግራት ሲያሰቃያት የኖረውን ከባድ ሸክም እንዳለ አውጥታ ዘረገፈችላቸው! በቅደም ተከተል ተራ አስይዛ አጣፍጣ አይሁን እንጂ፣ እንደ ልጆች ሁሉ፥ የፊቱን ሁዋላ የሁዋላውን ፊት አድርጋ፣ አመሰቃቅላ አንድ ሳይቀር ሁሉንም ነገረቻቸው።

«ታዲያ - በግድ ወላጆችሽ - ለባልሽ እንዳይሰጡሽ ነው - ጠፍተሽ የመጣሽ ማለት ነው፥ አይደለም? » አሉ እናታችን በረዥሙ አደበላልቃ ከተናገረችው ፍሬ የመሰላቸውን ብቻ አጠቃለው።

«አዎ! »

«ሁለት አመት ያክል ተለያይታችሁ ከቆያችሁ - ምናልባት አሁን ደህና ሰው ሆኖ ይሆናል። ታዲያ - ወላጆችሽ እንዳሉሽ ተመልሰሽ አይተሽው፥ ካልተለወጠ ደህና ሰው

ካልሆነ፥ ከዚያ በሁዋል አንድያሽን ፈትተሽው ብትወጪ አይሻልም? አሁን ፈቃዳቸውን ፈጽመሽ ከተመለስሽ በሁዋላ፣ ሳይስማማሽ ቀርቶ ትወጪ እነሱም እንደገና በግድ «ሂጂ» አይሉሽ ይሆናል።

«የለም የለም እሱ ደህና ሰው አይሆንም፥ ሁልጊዜ ክፉ ነው። አንድ ቀን ተመልሸ ከገባሁ አይለቀኝም። አባባም እሱ ያላቸውን ብቻ ስለሚሰሙ፥ ‹ያውጡኝ› ብላቸው ‹እሺ› አይሉኝም» አለች ደመቀች እናታችን የወላጆችዋን ፈቃድ እንድትፈጽም ሲመክሩዋት ልክ እንዳባትዋ «አንቀን እንሰጥሻለን» እንዳሉዋት ሁሉ ፊትዋ በቅጽበት ተለዋውጦ። ሁለቱ እመበለቶች ላጭር ጊዜ ዝም ብለው እስበሳቸው ሲተያዩ ቆዩና፣

«ታዲያ - ወደኛ የመጥሽ ምን እንድናደርግልሽ ፈልገሽ ነው? » አሉ እናታችን።

«እንድታመነኩሱኝና እናንተን እዬረዳሁ እዚህ አብሬያችሁ እንድቀመጥ ብዬ ነው። መንኩሼ መቃብር ቤት ከተቀመጥሁ አባባም እሱም አስገድደው አይወስዱኝም። አባቴ ቄስ መንግሥቱ የናባብ የንስሀ አባት ሁልጊዜ ሲናገሩ ሰምቻለሁ።»

«አይ የልጅ ነገ - ር! እኛ መነኩሲቶች ነን እንጂ ለማመንኮስ ስልጣን ያለን መሰለሽ? የሚያመነኩሱኮ ቄሶች ናቸው። ይህንም አታውቂ? » አሉ እናታችን የቅርታ ፈገግታ ባንድ አፍታ በፊታቸው አልፎ ሲሄድ እየታየ።

«እሱንስ አውቃለሁ፤ ብቻ - ለቄሶች እናንተ ከነገራችሁዋቸው ‹እንቢ› አይሉም ብዬ ነው እንጂ! »

«አንቺም እኛም ብንነግራቸው ‹እሺ› አይሉም። አንቺ ገና ልጅ ስለ ሆነሽ እኛ ወላጆችሽ ስላልሆን ያንቺንም ሆነ የኛን ቃል ተቀብለው አያመነኩሱሽም። የወላጆችሽን ፈቃድ ይጠይቃሉ።»

«ወላጆቼ? ወላጆቼማ እንኩዋንስ እንድመነኩስ ሊፈቅዱ እዚህ መሆኔን ካወቁ አባባ ይዘው ለሱ - ይሰጡኛል። እባ - እባካችሁ እዚህ መሆኔን እነሱ አይ - አይወቁ። እዚህ መሆኔን ካ - ካወቁ ይዘው ይሰ - ይሰጡኛል። ወደሱ ከመመለስ የትም ስሄድ ጅብ - ጅብ በልቶኝ ወይ ገደል ገብቼ መሞት ይሻ - ይሻለኛል? » አለች ደመቀች እንባዋ ግራና ቀኝ ጉንጮችዋን ሞልቶ እዬወረደና ሳግ ሲተናነቃት የምትናገራቸው ቃሎች ባጭር ባጭር እየተቁዋረጡ።

«እስቲ ልቅሶሽን ተይና የኛን ምክር ስሚ፤ ልጄ» አሉ እናታችን። «የኛን ምክር ስሚ። እንዲህ - አሁን ለኛ እንደ ነገርሽን ፥ ለሱ ለባልሽ መልሰው ከሚሰጡሽ ሞት የምትመርጪ መሆንሽን ከነገርሻቸው የገዛ ልጃቸውን ‹ሄደሽሙቺ› ብለው አይሰዱሽም። ስለዚህ - አባትሽን ሰው ልከን እናስመጣቸውና የደብሩን ገበዝ ጨምረን ያለ ፈቃድሽ እንዳይሰጡሽ ‹አደራ› ብለናቸው፥ ልጁን ጨምረሽ ከምታንገላችው ብትመለሺ ይሻላል።

«እባካችሁ፤ ስለ እግዝእትነ ማርያም ብላችሁ አታምጡዋቸው፤ እናቶቼ! አባባ ካገኙኝ ይዘው ነው የሚሰጡኝ። እባ - እባካችሁ ዛሬ ብቻ ስለ እመ አሳድሩኝና፥ ነገ በ - በጥዋት እሄ - እሄድላችሁዋለሁ፥ አላስቸግራችሁም። ብቻ - ብቻ ላባባ አትስጡኝ። እባ - እባካችሁ! » አለችና፥ እያለቀሰች በግራቸው ልትወድቅ ስትነሳ ሁለቱም ቶሎ ተነስተው ይዘው ያባብሉዋት ጀመር።

«ላንቺም ለልጂሽም የሚሻል የመሰለንን መከርንሽ እንጂ ካልፈለገሽ ተይው፣ አንልክባቸውም። ተመካክረን ሌላ የሚሻል መንገድ እስክንፈግ እዚህ ከኛ ጋር ትቆያለሽ፥ አታስቸግሪንም» አሉ እናታችን፤ አንገትዋን ይዘው። እማሆይ ወለተየሱስም ምጥንታዋን ሲሰሙና፣ ውስጣዊ ጭንቀትዋ ምን ያክል ጽኑ መሆኑን ከሁኔታዋ ሁሉ ሲያዩ ቆስሎ የሚሰቃይ ልብዋ ባይኖችዋ የሚያፈሰውን የደም እንባ ሲያዩ ጽኑ አዘን ተሰማቸውና አንጀታቸው በስለት እንደ ተመተረ ተንሰፈሰፈና አልቅሰው አላቆም አሉ! «አይዞሽ ልጄ፥ አሁን እናታችን እንዳሉት ተመካክረን የተሻለ መንገድ እስክናገኝ አባትም ሆኑ ሌላ ሰው አይመጣብሽም ማንም ሳያይሽ እዚህ ትቆያለሽ» አሉ እማሆይ ወለተየሱስ ደመቀችን ከናታችን እጅ ወስደው፥ ግንባርዋንም ጉንጮችዋንም እዬሳሙ።

ደመቀች ሁለት እመበለቶች ሲያባብሉዋት፥ በተለይ እማሆይ ወለተየሱስን አብረዋት ሲያለቅሱ ስታይ፥ ያዘኑላት መሆናቸው ተስማትና ለመጀመሪያ ጊዜ ከናትዋ ሌላ፥ ውስጣዊ ስቃይዋን የሚረዳላት ሰው ያገኘች መሰላትና፥ በፍራትና በጭንቀት ጨልሞ የነበረው የልጅ ፊትዋ ከባድ ደመናው ጸሀይ እንዳስገደችላት የክረምት ሰማይ በደስታ ወገግ አለ።

ደመቀች፣ እዚያ መቃብር ቤት ከናታችንና ከማሆይ ወለተየሱስ ጋር ሶስት ሳምንት ያክል ስትሰነብት የምግብ ችግር አላዬችም። እስዋና ልጅዋ፥ የፈለጉትን ያክል እንጀራ በወጥ በፈለጉ ጊዜ እዬበሉ እስዋ ጠላ እሱ ውሀ እዬጠጡ፥ እስዋ - ለብዙ ጊዜ ትታው የቆዬችውን በጥዋት ተነስታ ዳዊት፣ መልክ ኢዬሱስና መልከ ማርያም ከደገመች በሁዋላ

- በእማሆይ ወልተየሱስ እግር ተተክታ፣ ቤት ስትጠርግና እቃ ስታጣጥብ በጣም ደስ ብሎዋት ሰነበተች።

ደመቀች ከመጣች በሁዋላ ጀምረው፣ እማሆይ ወለተየሱስ ያለወትሮዋቸው ከተማ እዬሄዱ፥ ቆይተው መምጣትን አዘውትረው ሰነበቱ። አንድ ቀን እንደ መሰንበቻቸው ከተማ ቆይተው ተመልሰው፥ ከናታችን ጋር ለብቻቸው ቀስ ብለው ሲነጋገሩ ቆይተው ደመቀችን ጠሩና፥

«ሰማሽ፥ ልጄ! » አሉ እናታችን፥ ደመቀች ሊነግሩዋት ያሰቡትን ስትሰማ የምትሆነው አስቀድሞ እንዳስፈራቸው ሁሉ እያመነቱ። «ሰማሽ ልጄ፥ መቸም - እዚህ ተሸሽገሽ ሁልጊዜ ልትኖሪ አትችይም! እዚህ መኖርሽ እስካሁንም ሳይታወቅ አይቀር! ታዲያ - አባትሽና ባልሽ እዚህ መሆንሽን ሰምተው የመጡ እንደሆነ፥ እኛ ሁለት ደካሞች እነሱ ተከላክለን አንቺን የምናድንበት ጋሻና ጦር የለንም። ስለዚህ፥ ወደ ወላጆሽ እንድትመለሺ ብንመክርሽ ‹ወደነሱ ከመመለስ ሞቴን እመርጣለሁ› ስላልሽ ከመሞት ወዳዲስ አበባ ሄደሽ፥ እዚያ የሚቀጥርሽ ሰው ብታገኚ እየሰራሽ እንድትኖሪ ነው የምንመክርሽ።»

ደመቀች ችግርዋን ሁሉ ፈተናዋን ሁሉ ያለፈች መስሎዋት ደስ ብሎዋት የሰነበተችውን ያክል፥ እናታችን የተናገሩትን ስትሰማ፣ ሰማይ የተደፋባት፤ ዙሪያዋን ጨለማ የከበባት መስሎ ተሰማት የምትለውም የምታደርገው ቅጡ ጠፍቶዋት፣ ምንም ሳትተነፍስ ሳትንቀሳቀስ ዝም ብላ ቆየች። መልስ በመስጠት ፈንታ ዝም ብላ እንደ ቆመች እንባዋ ሲወርድ ስላዩ፥

«ለምን ታለቅሻለሽ? ላንቺ የሚሻል ሰለ መሰለን ነውኮ - እኛ ተቸግረን ሰው ጭምር ስናስቸግር የሰነብትን» አሉ እማሆይ ወለተየሱስ። ደመቀች አልገባትም።

«እንዴት - እንዴት አድርጌ ነው የምሄድ? » አለች፥ የተሰበረ ድምፅ።

«እዚያ ከደረስሽ በሁዋላ የምትሆኚን እግዚአብሔር ያብጅልሽ እንጂ እስከዚያ የሚያደርስሽ እማሆይ ወለተየሱስ ሲቸገሩ ዘመድም ሲያስቸግሩ ሰንብተው አግኝተውልሻል» አሉ እናታችን። እናቱ ስታለቅስ ሲያይ፥ ተከስተም ጡዋ ብሎ ያለቅስ ጀመር። የስዋ ክፍል የስዋ ቅጂ ስለሆነ ደስ ሲላት ሲያይ አብሮዋት ደስ ይለዋል። ስታለቅስ ሲያይ አብሮዋት ያለቅሳል!

በማግሥቱ እንጋት ላይ የማሆይ ወለተየሱስ ዘመዶች ፈልገው ያገኙላቸው «አቶ መላኩ ረዳ» የሚባል ባለ ካሚዮን ነጋዴ፥ የቤተ ክርስቲያኑ መንገድ መኪና ሊያስሄድ እስከሚችልበት ድረስ ካሚዮኑን ቀረብ አድርጎ አቁሞ፥ እሱ ወደ እናታችን መቃብር ቤት መጣ። ደመቀች ልጅዋን እንጀራ በወጥ አብልታ፥ ውሀ አጠጥታ፥ እስዋ ልብዋ እዬተሸበረና እዬተናነቃት መብላት ስላቃታት፥ ትንሽ ከቀማመሰች በሁዋላ እቃውን አንስታ፥ ተከስተን በኩታዋ አዝላ ትጠባበቅ ነበር።

አቶ መላኩ እናታችንን እጅ ነስቶ፥ እንደ ተቀመጡ ጉልበታቸውን ለመሳም ጎንበስ ሲል «ተው ተው፣ እግዚአብሔር ይባርክህ ልጄ ሀብት ያድልህ» ብለው፥ በሁለት እጆቻቸው ቀና ካደረጉት በሁዋላ፥ «በል እንግዲህ -» አሉ፥ አንድ ጊዜ እሱን አንድ ጊዜ ደመቀችን እያለዋወቱ እያዩ። «በል እንግዲህ ይችን ልጅ አደራ ሰጥቸሃለሁና፣ ልጅ አዝላ እንዳትንገላታ ተጠንቅቀህ አዲስ አበባ እንድታደርስልኝ። ከዚያም - ቢቻል አንተ፥ ባይቻል የሚቻለው ሰው፣ ቀጣሪ ፈልጎ እንዲያስቀጥራት እንድታደርግልኝ አደራ! በል እንካ በምድር የሰጠሁህን በሰማይ ትሰጠኛለህ! » አሉ እናታችን፤ የጥብቅ አደራ ምልክት የሆነውን ሳር አግበስብሰው።

«ኸረ ግዴለም እንኩዋንስ ይህን ትንሹን ነገር - አቅሜ ተቻለ ለናታችን ሌላ ትልቅ ጉዳይ ብላክስ - ደስታውን ችዬው ነው? » አለ ነጋዴው ሳሩን ከናታችን እጅ ሲቀበል እንደ መስገድ ብሎ። ከዚያ እናታችን ደመቀችን ለብቻ ወስደው አስራ ሁለት ብር ቆጥረው ከሰጡዋት በሁዋላ ጸሎተ ማርያም ደግመው በስዋም በልጅዋም ላይ «ትፍ ትፍ» ብለው መርቀው አሰናበቱዋቸው። ደመቀች እያለቀሰች የናታነንና የማሆይ ወለተየሱስን ጉልበት ስማ፥ ካሚዮኑ በቆመበት እስክትደርስ ወደ ሰነበተችበት መቃብር ቤት እዬዞረች እያዬች ሄደች። እካሚዮኑ ውስጥ ገብታ ስትቀመጥ፥ «እዚህ መቃብር ቤት መኖር እንዴት ውብ ነበር! » አለች ለራስዋ ብቻ በሚሰማ ዝቅተኛ ድምጽ።

# ምዕራፍ አራት

# ህልም እንጂ እውን የማይመስል እውን

አቶ መላኩ እናታችን «አደራ» እንዳሉት፥ ደመቀችና ልጅዋ እንዳይንገላቱ፥ ረዳቱን እውጭ ከጭነቱ ጋር እንዲቀመጥ አድርጎ እነሱን እካሚዮኑ ውስጥ፥ ባጠገቡ አስቀምጦ፥ ሞተሩን ሲያስነሳ ልክ፥ እንዳቆሰሉት ነበር ዙሪያ ገባው እስኪናወጥ ስላጉራራ፥ «ወዬው እናቴ! ምን አውሬ ነው እዚህ ውስጥ ያለ? » አለች ደመቀች፥ ከመደንገጥዋ የተነሳ ፊትዋ በቅጽበት ተለዋውጦ ተንስታ ለመሮጥ እየቃጣች። ተከስተም መኪናው ሲያጉራራና እናቱ «አውሬ» ስትል ሲሰማ እንዳዘለችው አንገትዋን በሁለት እጆቹ ጠምጥሞ ይዞ ይጮህ ጀመር። እንኳዋንስ ተከስተ፥ ደመቀችም እስከዚያ ቀን ድረስ ካሚዮን ውስጥ መግባት ይቅርና ካሚዮን በሩቅ አይታ አታውቅም።

«አይዞሽ አውሬ አይደለም፥ መኪና ሊሮጥ ሲነሳ መፈክርሩ ነው! » አለ ነጋዴው፥ የደመቀችን ፍራት ከፊትዋና ከሁኔታዋ ሁሉ ሲያይ እዬሳቀ። «ይልቅስ -» አለ ሲስቅ ቆይቶ። «ይልቅስ ወደ ሁዋላ መደገፍ እንድትችይ ልጁን ከጀርባሽ አውርጂና በቅፍሽ ያዢው።»

ደመቀች እንደ ተመከረችው ልጅዋን ከጀርባዋ አውርዳ በቅፍዋ ይዛ ስትቀመጥ፥ ካሚዮኑ በመሀከለኛ ፍጠንት እዬሄደ የደብረ ማርቆስን ከተማ ወጥቶ ጭሞጋን ካለፈ በኋላ፥ አንድ ረዥም ሜዳ መጥጦ በፊቱ ተዘረጋ። ከዚያ፥ ያ፥ የሚፈክር ካሚዮን እያጉራራ ፍጥነቱን በጥፍ ከዚያ በሁለት፥ ከዚያ በሶስት እጥፍ ጨመረና፥ ያን በረዥሙ የተዘረጋ ሜዳ በቅጽበት ጥቅልል፥ ሽብልል አድርጎ በጉያው አሳልፎ ወደ ሁዋላው ሲጥል፣ ወዲያው አንድ አቀበት መጥቶ በፊቱ ተደቀነ። ያንም እንዲሁ ባንድ አፍታ ጠቅልሎ፥ በጉያው አሳልፎ ወደ ሁዋላው ወረወረው። ከዚያ ቁልቁለት ከዚያ ለጥ ያለው ሜዳ፥ ከዚያ አቀበቱ፥ ደግሞ ቁልቁለቱ እንደ ገና ለጥ ያለው ሜዳ እዬተከታተሉ እዬመጡ ሲገጥሙት ሁሉንም፥ እንዳመጣጣቸው በየተራ ጥቅልል፥ ሽብልል እያደረገ፥ በጉያው አሳልፎ የሁዋሊት፥ እየወረወረ እዬጣለ ሲነጉድ፥ ደመቀችና ልጅዋን፥ በፍራት ፈንታ ደስታና ሲቃ ተተክተው ያቁነጠነጡዋቸው ጀመር!

«እውነት ይኸ - መኪና እንዲህ የሚያጉራራ ሲፈክር ነው አይደ? » አለች ደመቀች፥ የልጅ ፊትዋ በደስታ እያበራ።

«ታዲያስ! ሰማንያ ኩንታል ጤፍና እኛን እራታነን ሁላ ባንድ ላይ ተሸክሞ፥ ለገስጋሽ ሳምንት ሙሉ የሚወስደውን ጎዳና ታንድ ቀን ባነሰ ጊዜ ‹ፉት› የሚል ጎበዝ ‹ሊፈክር አይገባውም› ትያለሽ? » አለ መላኩ እንደ መሳቅ ብሎ በቀልድ መልክ።

«ኩንታል ጤፍ? ኩንታል ጤፍ ደሞ ምንድር ነው? »

«ኩንታል መስፈሪያ ነው። አንድ ኩንታል ጤፍ ማለት ሀያ ጎራድ ጤፍ ማለት ነው። እይውልሽ ታዲያ - ይኸ መኪና ተኛ፥ ታራታችን ሌላ አንድ ሽህ ስድስት መቶ ጎራድ ጤፍ ተሸክሞ ነው - እንዲህ የሚጋልበው! »

«ው - ! » አንድ ሺህ ስድስት መቶ ጎራድ ጤፍ? እሮ እውነት እንዴት ያለው ጎበዝ ቢሆን ነው? የኛ ‹ጎበዝ ነው› የሚሉት አጋሰስ፥ ሳሙኤ ከሀያ ጎራድ ጤፍ የበለጠ አይጫንም። ሁለት ወይም ሶስት ጎራድ እንኩዋ መጣያ ይጨምረበት የተባለ እንደሆነ ‹አጋሰሴን ልትገሉት ነው ወይ?› ብለው አባባ ይቆጣሉ። ግን - ይኸ እንደ አጋሰስ አይደለም። እንዲያው እንጃ፥ ሌላ ‹ይሉኝ አይል› (የቀረበለትን ሁሉ ‹በቃኝ› ሳይል እያግበሰበሰ የሚውጥ ሆዳም) ነገር ነው! » አለች ደመቀች እዬሳቀች። አቶ እምላኩም የዚያችን የባላገር ልጅ ፍጹም ገርና፣ ከይሉኝታ ሁሉ ነጻ የሆነ አነጋገር ሲሰማ ከልቡ ሳቀ።

«ደግሞ ሌላ የገረመኝ ነገር» አለች በስዋ አላዋቂነት መሳቁን ስላልተረዳች፥ አብራው ስትስቅ ቆይታ። «ሌላ እዚህ አገር ያየሁት የሚያስገርም ነገር፥ ሜዳው ተራራው ዛፉና ቁጥቋጦው ሁላ - እግር ያለው ይመስል መሮቱ ነው! እኛ አገር ሜዳና ተራራ ወይም ዛፍና ቁጥቁዋጦ አይሄድም» አለች ካሚዮኑ በፍጥነት ወደ ፊት ሲበር ሜዳው የተሰማራበትን የከብት መንጋ እንደያዘ፥ አቀበቱም ሆነ ቁልቁለቱ የበቀሉበትን ዛፎችና ቁጥቁዋጦዎች እንደያዘ፥ ሁሉም ወደ ፊት ከምትሄድበት ወዳለፈችው ወደ ሁዋላዋ የሚሮት መስሎ ስለ ታያት።

«የለምኮ! » አለ ነጋዴው፤ አሁንም ከልቡ እዬሳቀ። «የለም ሜዳውም ሆነ ዛፉና ቁጥቁዋጦው አይሮጥም፤ እንዳንቺ አገር ሜዳ ዛፍና ቁጥቁዋጦ የቆመ ነው። ብቻ - ይኸ መኪና እኛን ይዞ ወደ ፊት በፍጥነት ሲሮጥ ሌላው፣ ነገር ሁላ ወደ ሁዋላችን የሚሮጥ ይመስላል። ታዲያ - ለኛ የሚሮጥ ይመስለናል እንጂ፣ ሁሉም በያለበት የቆመ ነው። ቆይ፣ አሁን እኛ ስንቆም፥ እንኩዋንስ መሮጥ የሚንቀሳቀስ ነገር አለ መኖሩን ታያለሽ»

አለና ፍጥነቱን እዬቀነሰ እዬቀነሰ ሲሄድ ቆይቶ በመጨረሻ ሲቆም ሁሉም በያለበት ቆመ።

«አዬሽ? እኛ ስለ ቆምን፣ የሚሮጥ ይመስል የነበረው ሁላ እንኩዋንስ ሊሮጥ ንቅንቅ አይልም! »

«አሀ! እውነትም እኛ ስንቆም ሁሉም ቆመ። እንግዲያ እንዴት ነው እኛ ስንሄድ ሁሉም የሚሄድ፥ ከኛ ጋር እልክ የተጋባ ይመስል? » አለች ደመቀች ትንሽ እንደ መሳቅ ብላ።

«እኛ በፍጥነት ስንሄድ የሚሄድ ይመስላል፥ እንጂ፣ አይሄድም አልሁሽኮ! » አለና መላኩ ረዳ እንደገና መኪናውን አስነስቶ እንደገና እያስጎራ እንደገና እያስፈከረ፥ አከነፍንፎ፥ ገና ቀትር እንኩዋ ሳይሆን አውራ ርፋድ ላይ ደጀን አፋፍ ደረሰ።

«እይውልሽ፥ እዚያ ታች የምታይው፣ ያባይ ቆላና ወንዙ ነው አለ ነጋዴው ካሚዮኑን አፋፍ ላይ ሲያቆም።

«የኛ አገር አባይ? » አለች ደመቀች፤ ከመበለቶች ጋር ተመሳጥሮ በተዘዋዋሪ መንገድ ወዳገርዋ መልሶ የወሰዳት መስሎዋት በጣም ደንግጣ።

«የእናንተ አገር የት ነው? »

«አንዶዳም ኪዳነ ምህረት። እንዶዳም ኪዳነ ምህረት፥ እኩዋት አፋፍ ወይም - አማሪትና ያውያን አፋፍ ሆኖ ነው ያባይ ቆላ የሚታየው።»

«እ - የለም፤ ይኸ የንዶዳም አባይ አይደለም፤ የደጀን አባይ ነው። አባይ ከዚህ ሄዶ ነው - ሁዋላ በናንተ አገር፥ በንዶዳም በኩል የሚታይ። እንግዲህ» አለ መላኩ፥ ወዲያው ቀጠል አድርጎ። «እንግዲህ፥ እዚህ እንውረድና እኛ መኪናችነን እስክናጠባብቅ እንቺና ልጅሽ ትንሽ ወዲያ ወዲህ እያልችሁ ጉልበታችሁን ስታፍታቱ ቆይታችሁ መንገዳችነን እንቀጥላለን። ምሳችነን ጎህጽዮን ብንበላ ይሻላል። ‹እዚህ እንባል› ያልነ እንደሆነ፥ ከቀትር በሁዋላ ጸሀዩ ስለሚጠነክር ያንጊዜ ወደ አባይ ብንወርድ ሀሩሩ ልጁን ይበድለዋል» አለና ቀድሞ ወርዶ ደመቀችን ልጅዋን እንደ ያዘች ደግፎ ሲያወርድ -

«እማ፥ እንጣ» አለ ተከስተ።

«አሀ! ይህን ጎበዝ ርቦታል፥ ቆይ ዳብ ልስጠው» ብሎ መላኩ በኮረጆ ካስቀመጠ ስንቅ አንድ ዳቦ አምጥቶ ሰጠው።

መላኩ ረዳና ረዳቱ ካሚዮናቸውን ፈትሸው የሚጠባበቀውን ካጠባበቁና የሚተካከለውን ካስተካከሉ በኋላ መንገዳቸውን ቀጥለው፥ እቀተር ላይ አባይ ወንዝ ደረሱ።

«እንዲህ ያለ ድልድይ አንቺ አገር አለ? » አለ መላኩ፥ ሲቀልድ፥ ያባይን ድልድይ ከመግባቱ በፊት መኪናውን እዳር አቁሞ።

«ኧሮ! እንዲህ ያለ ወንዝ ያለ ይመስል፥ ደሞ እንዲህ ያለ ድልድይ እኛ አገር ምን ሊያረግ ይመጣል? እኛ አገር «ትልቅ» የሚባለው ወንዝ «የምንጭ» ብቻ ነው። የየምንጭ ውሀ በጋ፥ በጋ እስከግራችን አንገት እንኳዋ የማይደርስ በጣም ሞሳ ስለሆነ በግራችን ገብተን ነው የምሻገረው። ክረምት ክረምት ግን ውሀው ሲሞላ፥ የንዳዳሞና ያማሪት ጎበዝ ባንድነት ቱልቱላ ነፍቶ ወጥቶ፥ በጠባቡ በኩል ወፍራም እንጨት ይደረድርበትና፥ በዚያ ላይ ነው ሰው ሁላ የሚሻገር» አለች ደመቀች፥ ያባይ ድልድይ ስራውም ትልቅነቱም የሚሻገር» አለች ደመቀች ያባይ ድልድይ ስራውም፥ ትልቅነቱም አስገርሞዋት፥ አይኖችዋንም አፍዋንም በሰፊው ከፍታ ስታይ ቆይታ።

«ከብቱስ? ከብቱስ በንጨቱ ድልድይ ነው የሚሻገር? »

«አዋ! ደሞ ከብት በንጨት ድልድይ ይሻገራል አሉህ? » አለች ደመቀች፥ ባቶ መላኩ አላዋቂነት እዬሳቀች።

«እንግዲያ እድኔት አድርጎ ነው የሚሻር? »

«ከብቱማ ውሀ ስለማይበላው ገብቶ እዬዋኘ አደል የሚሻገር? »

«ከብት ውሀ ውስጥ ገብቶ እዬዋኘ አይተሻል? »

«ኧረ አታስዋሽኝ እኔስ አላይቸም አያ! »

«እንግዲያ ካላዬሽ ከብት ሲዋኝ ውሀ እንደማይበላው እንዴት አወቅሽ? »

«እዋ! እኔ ባላይ የሚያውቆች ሁላ ሲናገሩ አልሰማም? ‹ከብት የቁም ዋና ስለሚዋኝ ውሀ አይበላውም› እያሉ የኛ አገር ሰዎች ሲጫወቱ ብዙ ጊዜ ሰምቻለሁ።»

«ደምቀች፤ ከንዳዳሞ ኪዳነ ምህረት የንዳዳሞ ጎረቤቶች ከሆኑ አገሮች በቀር ሌላ ስለማታውቅ፥ ኤልያስ ከባልዋ ጋር በቆዬችበት ጊዜ እንኳዋ፣ ከሱ ግቢ ወጥታ ምንም የማታውቀው ስላልነበረ ያነለት በመንገድ ያዬችውን ሁሉ እንደዳሞ ከምታውቀው ጋር እያመሳሰለች ወይም እያመዛዘነች፥ በልጅ አስተሳሰብና በሚጥም፥ የልጅ አነጋገር ስታወራ መላኩ ረዳ ወሬዋ እዬጣመው እንደ ድሮው ሳይደከመው ሳይሰለቸው እንደ ሳቀ ያባይን ቆላ ምሳቸውን ጎሀጽዮን በሉና፥ ሳይመሽ አዲስ አበባ ለመግባት ገሰገሱ። ነገር ግን አዲስ አበባ ሊደርሱ ትንሽ ሲቀራቸው ስሉልታ ላይ ካሚዮኑ ስለተሰናከለ አዲስ አበባ የገቡ ከመሽ ቡሁዋላ ነው።

የመላኩ ረዳ ካሚዮን ተጠጋግኖ እንደ ምንም እያነከሰ፥ ቢመሽም ገና ላይን ሳይጨልም እንጦጦ አናት ብቅ ሲል አዲስ አበባ ታዬች። አዲስ አበባ የመሬት ስስት እንዳደረባቸው ስስታሞች ሁሉ መሬት «አይቅረኝ» ብላ ባካባቢው መሬት የተባለ ሁሉ እንዳያመልጣት ከላይ ራስዋን በንጦጦ ተራራ ደረት አስጠግታ፥ ከታች እግሮችዋን እስከ ቃሊቲ አንሰርትታ፥ ግራና ግራ እጆችዋን ከገፈርሳ እስከ ኮተቤ ዘርግታ በዚያ ሁሉ አገር ምድር ላይ፣ ከሳርና ከቆርቆሮ ከፎቅና ከጎጆ ባንድ ተደበላልቆ የተደረተ የቤት ውጥንቅጥዋን እንዳትቀማ የፈራች ይመስል፥ ሁሉንም በውስጥዋ እፍግ፥ ትንፍግ አድርጋ ሽሽጋ በዚያ ላይ ተኝታ ታዬች! አውራ ጎዳናዎችዋ አደባባዮችዋ እንደ ትምህርት ቤቶች፥ የህክምና ቤቶችና እነሱን የመሳሰሉት የህዝብ አገልግሎት መስጫ ቦታዎች ልዩ ልዩ ቀለም ባላቸው መብራቶ አጊጠዋል። ታዲያ፥ ውስጣዊ ጉስቁልናቸውንና መልከ ጥፉነታቸውን በሚያብለጨልጭ ጌጣጌጥ ሸፍነው ከሩቅ ሲያዩዋቸው እንደሚያታልሉ ጎስቁዋሎች ሁሉ አዲስ አበባም ያን ሁሉ ጎስቁዋላ እፍግዋን፥ ያን ሁሉ ትንፋገዋን፥ እንዲያ በውስጥዋ ደብቃ በልዩ ልዩ ቀለማት ባጌጡ መብራቶችዋ አሸብርቃ ከሩቅ ስትታይ እንኳዋንስ እንደ ደመቀች ከባላገር ለመጣች ልጅ፣ ለከተመኞችም እጅግ የምታምር ውብ ትመስላለች። ብቻ የማታው ጨለማ ተነስቶ፣ ቀን ካውራ ጎዳናዎችና ካደባባዮች ዘወር ብሎ ወደ ውስጥ ገባ ሲሉ የሚታየው ሌላ ነው! እሱ «ዋ እቴ፥ ውስጡን ለቄስ! » እንደሚሉት ነው!

«እይውልሽ እንግዲህ አዲስ አበባ ይሉሻል ይሄ ነው! » አለ መላኩ እንጦጦ አፋፍ ላይ ከሚዩኑን ቆም አድርጎ።

«ኧሮ፥ ኧሮ፥ ኧሮ! እና ይሄ ሁላ አንዱ አገር ብቻ ነው? » አለች ደመቀች፥ ያዲስ አበባ ትልቅነት አስገርሞዋት።

«ይሄ ሁላ አንድ ከተማ ብቻ ነው።»

»አቤ - ት! ይሄማ - እንደዳሞ፥ አማሪት፥ የውያንና የደቦና ባንድ ቢጨመሩስ ይበልጣቸው የለ? »

«በመሬት ስፋት እንኳ እንጂ - በቤትና በሰው ቁጥርማ በጣም ይበልጣቸዋል። እንኩዋንስ ከነሱ - ከሙሉ ጎዛምንና ማቻከልም -» ብሎ መላኩ የጀመረውን ሳይጨርስ፥

«እማ፥ እፉ» አለ ተከስተ ጥዋት ደጀን ላይ «እንጣ» ካለ በሁዋላ ቀኑን ሙሉ አንድ ቃል ሳይተነፍስ ውሎ።

«አዎ አብዬ፥ እፉ» አለች ደመቀች። «እፉ» በተከስተ አማርኛ «እሳት» ነው።

«እና ዛሬ ያዲስ አበባ መስቀል ሆኖ ነው? ወይስ - ሌላ ምንድር ነው ሰው ሁላ እንዲህ ደቦት (ችቦ) ያቀጣጥሎ? » አለች ደመቀች፥ ከተከስተ ወደ አቶ መላኩ መለስ ብላ።

«ደሞ አዲስ አበባ ለብቻው የተለየ መስቀል አለው አሉሽ? » አለ መላኩ እዬሳቀ።

«እዋ! እኔ አውቅለታለሁ? እንግዲያ ለምንድር ነው ሰው ሁላ እንዲህ ደቦቱን ያቀጣጥሎ? »

«ይሄ የምታዩው ሙብራት ሁላ ደቦት መስሎሽ ነው? ደቦት አደለምኮ! በመንገዶችና በትልልቅ ግቢዎች ሲበራ የሚያደርግ የንትሪክ ሙብራት ነው። ቆይ አሁን ወደ መሀከል ገባ ስንል ታይዋለሽ» አለ መላኩ።

«ለደመቀች የንትሪክ ሙብራት» እንደ ካሚዮኑና እንደ ሌላው ከዚያነለት በቀር አይታውም ሰምታውም የማታውቅ ነገር ሁሉ እንግዳ ነው። መቸም ያነለት፥ እዚያ ካሚዮን ውስጥ ከገባች ጀርማ ያዬችው ሁሉ እልም እንጂ እውን የሚመስል ነገር አልነእብረም። አባትዋ ባይኖሩና ይዘው ለባልዋ እንዳይሰጡዋት ባትፈራ ወዳገርም ተመልሳ ያነለት ያዬችውን ሁሉ ያን እልም እንጂ እውን የማይመስል እውን ሁሉ ለጉዋደኞችዋ ብታወራ እንዴት ደስ ባላት እንዴት በኮራች በተንጠራራች ነበር! ወዲያው አገርዋ ተመልሳ በጉዋደኜኖችዋ መሀከል ተቀምጣ ያን ሁሉ ያዬችውን ድንቅ ነገር ያን ሁሉ ታምር ስታወራ ሁሉም ባድንቆት አፋቸውን ከፍተው እየተቁነጠነጡ ሲሰሙዋት ታያትና ለብቻዋ የቅርታ ፈገግታ ፈገግ አለች።

# ምዕራፍ አምስት

# አዲስ አበባ

አቶ መላኩ ረዳ፣ አዲስ አበባ በሚቆይበት ጊዜ የሆቴሉን ወጪ ስለፈራ፥ ጉለሌ «ወይዘሮ አልጣሽ ጎርፉ» በሚባሉ የጠጅ ነጋዴ ቤት ነው የሚያርፍ። ወይዘሮ አልጣሽ፥ ምንም እንኩዋ በዚያ ስራ ጉለሌ ከተቀመጡ ብዙ ዘመን ቢሆናቸው፥ ስማቸውን እንደ መልካቸው እድሜ የማያቀዘቅዘው ዝነኛ እንደ ሆኑ የኖሩ ናቸው። ሰፊ ግቢያቸው በሸበተ ጥሬ ካብ ታጥሮ፥ እዚያ ውስጥ አንድ ሰፊ የጠጅ መነገጃ ሌላ፥ በርከት ያሉ ክፍሎች ያሉት ቤት ለሳቸው መኖሪያ እንዲሁም ላሻሻጮችና ለሰራተኞች የሚሆኑ ቤቶች ስላሉበት፥ ይህን ሁሉ ባንድነት ከውጪ ሲያዩት፥ የጥንት ባለ ብዙ ስራ የቤት መኩዋንንት ግቢ እንደ የጠጅ ነጋዴ ግቢ አይመስልም።

አቶ መላኩና ወይዘሮ አልጣሽ፥ ግንኙነታቸውን፣ እንደ መጀመሪያው በንግድ መልክ መመልከቱን ከተዉት ቆይተዋል። አቶ መላኩ ከጎጃም በመጣ ቁጥር፥ ማር እያመጣ በገዛበት ዋጋ አለፍ አለፍ ብሎም በነጻ ይሰጣቸዋል። ከዚያ ሌላ፥ አዲስ አበባ የቂየውን ያክል ቆይቶ ወዳገሩ ለመሄድ ሲነሳ፥ ለሱና ለረዳቱ - ያልጋ ክራይ መቸም አይታሰብም - ለመብልና ለመጠጥ፥ «ሳታወጣ አትቀርም» ብሎ ራሱ የገመተውን፥ በዚያ ላይ «ለመሀረብና ለሽቶ ይሁንሽ» ብሎ ተረፍረፍ አድርጎ ሰጥቶዋቸው ይሄዳል።

ሁለቱ በፊርማ ወይም እንደ ጥንቱ ልማድ በውሉ ሰሚኢዎች ፊት የጋብቻ ሥነ ሥራት ተፈጽሞም አይጋቡ እንጂ አዲስ አበባ በሚቆይበት ጊዜ እሱ ለሳቸው «ባል - አከል» የሚሉት አይነት ነው! ወይዘሮ አልጣሽ፤ በንትሹ እናቱ ሊሆኑ ስለሚችሉ ከተዋወቁበት ጊዜ ጀምሮ፣ በንግድ ደንበኝነት ሲኖሩ፣ አክብሮ «እስዎ» ነበር የሚላቸው። ከተደፋፈሩበት እለት ጀምሮ ግን «አንቺ» ብሎ ስማቸውን ያላንዳች ማንጠልጠያ ሲጠራ አፉን ትንሽ አልያዘውም። እሳቸውም «ክብሬ ተነካ» ብለው በመቀየም ፈንታ እንዲያው «ስለ አወደደኝ ልጅ መስዬ ታይቸው ነው» ብለው በጣም ነው ደስ ያላቸው። አዲስ አበባ ስራውን ጨርሶ ወደ ደብረ ማርቆስ ሲመለስ፥ እሱ እዚያ ካለችው ምሽቱ ጋር፥ እሳቸው አዲስ አበባ፥ የዕድሜያቸውን ገደብ ጥሰው

የሚመጡ ሲገኙ፥ ከነሱ ጋር «ምን ይለኝ?፥ ምን ትለኝ? » ሳይባባሉ፥ በደንብ የታወቀ ኑሮዋቸውን ይቀጥላሉ!

«ስሚ አንቺ፥ አልጣሽ፥ ይቺ ልጅ ከታቦት ባደራ የተቀበልሁዋት ናትና፣ ስራ ፈልገን እስክንቀጠር ለስዋም ለልጅዋም የተደረገውን ወጪ ያልጋውን ከራይ ጭምር፣ ከፋይ እኔ ስለ ሆንኩ በምንም እንዳይቸገሩ አደራ! » አለ አቶ መላኩ ደመቀችን ከነልጅዋ ይዞ አዲስ አበባ በገባ ማግስት፥ እጥዋቱ ላይ ጤፉን እህል በረንዳ ወስዶ ሊሸጥ ሲነሳ።

«የምን ታቦት አደራ ነው በል? » አሉ ወይዘሮ አልጣሽ።

«አንድ - ፥ ሰው ሁላ እንደ ታቦት የሚያከበራቸው፥ ማርቆስ ቤተስኪያን የሚኖሩ - ግሁሳን ናቸው ሳር አስጨብጠው ‹አደራ› ያሉኝ»

«ማን ይባላሉ? »

«እናታችን» ሲባሉ ነው እንጂ - በሌላ ስም ሲጠሩ ሰምቸ አላውቅም»

«ሴት ናቸው? »

«አዎ፥ ሴት ግሁሳን ናቸው»

«ወይ እዱስ ሚሀየ - ል! እናንተ የማዶ ሰዎች አትፈጥሩት ጉድ የላችሁ! ደሞ ብላችሁ ብላችሁ የሴት ግሁሳን ፈጠራችሁ? » አሉ ወይዘሮ አልጣሽ የፌዝ ሳቅ እዬሳቁ።

«በይ ዝም በይ፤ በማታውቂያቸው ግሁሳን ላይ ማፌዙ ይብቃሽ! ህ፥ ከግዚሀር ጋርኮ - እንደ ታቦት በገሀድ የሚነጋገሩ ናቸው! ለዚህ ነው - ሰው ሁላ ልክ እንደ ታቦት የሚያከብራቸው! ስለዚህ በሳቸው ላይ መቀለዱን ተይና፣ ይልቅ አሁን እንዳልሁሽ፣ ለነሱ ያወጣሽውን አስበሽ ስትነግሪኝ ስለምከፍልሽ፥ አናቲቱም፥ ልጅዋም እንዳይቸገሩ። ወዲያውም - ከኔ አንቺ ብዙ ሰው ስለምታውቂ እስቲ የሚቀጥራት ሰው ቢገኝ አጠያይቂ።

«የምን ፌዝ ነው በል? እኔ ኽማርያምና ኸናትዋ በኧር የሴት ታቦት ሰምቸ ስላማላእና፣ ዛሬ እናንተ ስለ ፈጠራችሁ በናንተ ተገረምኩ እንጂ አላፌዝኩም። «እንዳይቸገሩ» ላልከው፥ «ወጪያቸው ሁሉ እኸፍላለሁ» ታልክ፥ አይቸገሩም

አትስጋ። ያንተን ገንዘብ ይጭንአዋል እንጂ አልጣሽን አይጨንአትም! «የሚኸጥራት ሰው ፈልጊ» ስላልከው ግን - እንጃ፥ ታማአቸው ሰዎች «ገረድ እኸጥራለሁ» ሲል የሰማሁት የለም።»

እውነትም ደምቀች እስከ ልጅዋ እወይዘሮ አልጣሽ ቤት አስራ አምስት ቀን ያክል ስትቀመጥ፣ የተቸገራት ነገር የለም፣ ተመችቶዋት ነው የሰነበተች። ወይዘሮ አልጣሽ በሚኖሩበት ቤት አንድ ትንሽ ክፍል ውስጥ፥ እንኩዋንስ ልትተኛበት ባይንዋ አይታው የማታውቀው አልጋ ተሙዋልቶ እንደ ተነጠፈ ተሰጥቶዋት፥ በመብል በኩል ለስዋና ለልጅዋ ቁርስ፥ ምሳና፣ ራት ጊዜው ተጠብቆ እዬቀረበላቸው በዚያ ላይ፥ በምግብ ጊዜ ልጅዋን ወተት፥ ተጠብቆ እዬቀረበላቸው በዚያ ላይ፥ በምግብ ጊዜ ልጅዋን ወተት እስዋን ጠጅ ሳይለያቸው፣ በጥንቃቄ ተይዘው ሰነበቱ። ብቻ ተከስተ አዲስ አበባ የገባ እለት ሌሊቱን ጀምሮ አንድ ሳምንት ያክል እያሳለው በዚያ ላይ ተቅማጥና እግባት ተጨምሮበት ስለ ታመመ እናቱ ተጨንቃ ከሱ ጋር እንደ ተቆራኘች፥ ወጪውን ሳታይ ሰነበተች። በመጀመሪያዎቹ ሁለት ቀኖች እመሙ በጣም ጽኑ ስለ ነአብረ፥ ደመቀች የምትሆነው ቅጡ ጠፍቶዋት ነበር። ሁዋላ ወይዘሮ አልጣሽ ከቤታቸው የማይለይ፥ የሀኪም ረዳት የሆነ ዘመዳቸውን እንዲያየው ስለ ለመኑት፥ እሱ አይቶ፣ መድሀኒት ከሚሰራትበት ሀኪም ቤት አምጥቶ አደራረጉን ለደመቀች አሳያትና ስታደርግለት እዬተሻለው ሄዶ በሳምንቱ መጨረሻ ድኖ ተነሳ።

አቶ መላኩ ጤፉን ከሸጠ በሁዋላ ፍርድ ቤት የተቀጠረ ጉዳይ ስለ ነበረው፥ የቀጠሮው ቀን ባይደርስም፥ ወዳገሩ ከመመለሱ በፊት ከጠበቃው ጋር እዬተማከረ ጠበቃው «ያስፈልጉኛል» ያለውን ማስረጃዎች እዬፈለገ ሲሰጥና፣ አገሩ የሚወስደውን ሸቀጣሸቀጥ ሲገዛ መሰንበቻውን ምንም እረፍት አልነበረውም። ይሁን እንጂ፥ ተከስተ ታሞ በነበረበት ጊዜ፥ ምንም ቢሆን፣ ጥዋት ወደሚሄድበት ከመሄዱ በፊት፥ ደመቀችን አይቶ፥ ልጅዋ እንዴት እንዳደረ ሳይጠይቃት ሄዶ አያውቅም።

ስለ ራስዋ ጉዳይ፥ ስለዋም ሆነ ለወይዘሮ አልጣሽ ለመንገር አልመቸው ብሎ፥ ቀን ሲቀጥር ቆዬ እንጂ፥ እዚያው እወይዘሮ አልጣሽ ጠጅ ቤት «አሻሻጭ» ሆና እንድትቀጠር ነው ያሰበ። በሱ አሳብ፥ ደመቀች ልጅ ከመሆንዋም ሌላ፥ እዚያ ካሉት አሻሻጮች ሁሉ ውበትና ደም ግባት ተባብረው ያስጌጡዋት ስለ ሆነች እስዋን ሲል እስዋን ፍለጋ፥ ለሚሰበሰበው ወንድ ሁሉ፥ ወይዘሮ አልጣሽ የሚበቃ ጠጅ አሰናድቶ ማቅረቡ ያቅታቸው እንደሆነ እንጂ፥ «ገብያተኛ አጣለሁ» ብለው ስጋት

እንደማይኖርባቸው እርግጠኛ ነበር። ለስዋም ቢሆን - ካሻሻጭነት የተሻለ የረፍት ስራ የሚገኝ አልመሰለው።

ያቶ መላኩን አሳብ ወይዘሮ አልጣሽም ሳያስቡት አልቀሩ። ነገር ግን አውጥተው አውርደው፥ ካሰላሰሉት በሁዋላ፥ ልጅነት ዋና ውበትዋ ስቦዋቸው ከሚመጡት ወንዶች የሚያገኙትን ጥቅም ካንድ ወገን፥ ለስዋና ለልጅዋ የሚያወጡትን ወጪ ከሌላ ስለ ታያቸው ላለመቅጠር ወሰኑ።

አንድ ቀን ጥዋት፥ አቶ መላኩ ወደ ጉዳዩ ከሄደ በሁዋላ ወይዘሮ አልጣሽ ወደ ጠጅ መነገጃቸው ሊሄዱ ከመኖሪያቸው ሲወጡ፥ ደመቀችን ከልጅዋ ጋር እውጭ ስላዩ «እንዴት አደርሽ ልጄ? ማሞ በጣም ደህና ሆነልሽ? » አሉ፥ ተከስተን ይዛ ወደ ቆመችበት እያመሩ።

«ጤና ይስጥልኝ እመይቴ፥ አሁን ደህና ሆኖዋል» አለች ደመቀች ለጥ ብላ እጅ ነስታ።

«የሚኾጥርሽ ሰው የመፈለጉን ነገርኮ - አልረሳትሁትም። ብቻ - እናንተ ተመጣችሁ ተዚህ ግቢ ስላልወጣሁ፥ እዚህ ሲመጡ ለማአቸው ሰዎች ሁሉ «ገረድ የሚኾጥር ሰው ፈልጉልኝ አደራ» ብያቸው ነበር - ፥ ሁሉም «እናእም» አሉኝ። ያ - መለሁም ጉዳዩ ከራስ ጠጉሩ የበዛ ስለሆነ አያደርሰው። ታዲያ - ለኛ እስኪመቸን እንዲህ ቦዝነሽ ተመኾመጡ አንቺስ እየወጣሽ ብትጠይኢ አይሻልም ልጄ? »

«እኔ ማነን አውቃለሁ? » አለች ደመቀች፥ አንገትዋን ደፍታ።

«ኡ ኡ! ደሞ ይኸ እውኾት ያስፈልገዋል? አጥር ያለው፥ ትልእ ቤት ስታይ፣ ወደዚያ ሄደሽ «ገረድ ትኾጥራላችሁ ወይ» እያልሽ መጣዩእ ነውኮ። ያገኘሽ እንደሆነ ተመልሰሽ ለመላሁ ትነግሪውና ስለ ደመወዝሽም ስለ ሁሉም እሱ ይነጋገርልሻል። ታላገኘሽም - ያው መመለስ ነው»

«ስመለስ - መንገዱ ይጠፉኝ እንደሆነ ብዬ ነው እንጂ! »

«መንገዱን እስትትለምጅው ርኸሽ አለመሄድ ነው። ርኾሽ ተሄድሽም ‹የጉለሌን መንገድ አሳዩኝ› ማለት ነው፤ የሰፈራችን ስም ጉለሌ ነው። ጉለሌ ተደረስሽ ደሞ - ‹ወይዘሮ አልታሽ ቤት› ስትይ ማንም ያሳይሻል። ለማናቸውም አውራውን ጎዳና አለመልኾእ ነው።»

«እዲ እመይቴ» አለች ደመቀች፥ ነገሩ ቢከብዳትም ወይዘሮ አልጣሽ «ምክሬን አቃለለችብኝ» እንዳይሉዋት ፈርታ። ከዚያ ልጅዋን በኩታዋ አዝላ እንደ ተመከረችው ስራ ፍለጋ ወጣች። እወይዘሮ አልጣሽ ቤት ስትሰነብት፥ ሰማቸውን ያባታቸውን ስም ጭምር አጥንታለች። የሰፈሩ ስም ጉለሌ መሆኑን ግን ገና ያነለት መስማትዋ ነው። ስለዚህ እንዳይጠፋት «ጉለሌ፥ ጉለሌ፥ ጉለሌ» እያለች እዬደጋገመች አውራውን ጎዳና ይዛ ወደ አራዳ መሄድ ስትጀርም ከመንገዱ ዳር አንድ ትልቅ ባላጥር ቤት ስላዬች ወደ በሩ ተጠግታ ትጠብቅ ጀመር። ትንሽ ቆይታ አንድ ሴት ከቤት ወጣችና እዚያ ቆማ ስታያት «ምን ትፈልጊያለሽ? » አለቻት።

«ገረድ ትቀጥሩ እንደሁ ብዬ ነው» አለች ደመቀች፥ ስትፈር ስትቸር።

«አነቅጥርም» አለች ሴትዮዋ። ከዚያ፥ ወደ መንገድዋ ተመልሳ ገብታ እንደገና «ጉለሌ፥ ጉለሌ፥ ጉለሌ» እያለች ትንሽ እንደ ሄደች አንድ ሌላ ትልቅ ባለጥር ቤት አዬችና ሄዳ እንደ ቅድመ «ገረድ ትቀጥሩ እንደሁ ብዬ ነው» ብላ ብትጠይቅ እዚያም አልቀናት።

እንዲያ አውራውን ጎዳና ሳትለቅ ባጠገቡ ወዳዬችው ትልቅ የታጠረ ቤት እዬሄደች «ገረድ ትቀጥሩ እንደሁ ብዬ ነው» ስትል አንዳንዶቹ «አንቀጥርም» ሲሉዋት ሌሎቹ ልጅነትዋን አይተው የምትቀልድ እዬመሰላቸው «ሂጂ፥ ከጉዋደኞችሽ ጋር ተጫዎቺ እኛ ካንቺ ጋር የምንጫወትበት ጊዜ የለንም» እያሉ ሲያባርሩዋት «ጉለሌ ጉለሌ፥ ጉለሌ» እያለች የደጃች ይገዙን ሰፈር የራስ ደስታ ሀኪም ቤት ሰፈር፥ የዮሀንስን ሰፈር አልፋ መሀል አራዳ አደባባይ ደረሰች። እዚያ መንገዱ ሁሉ አውራ ጎዳና ሆነባት! ወደ ባቡር ጣቢያ የሚሄደው አውራ ጎዳና ወደ እሪ በከንቱ የሚሄደው አውራ ጎዳና፥ ወደ አራት ኪሎ የሚሄደው አውራ ጎዳና ወደ ጊዮርጊስ የሚሄደው አውራ ጎዳና ወደ ጉለሌ የሚሄደው አውራ ጎዳና፥ ሁሉም አውራ ጎዳና ብቻ ሆነ! ቤቱም ወይዘሮ አልጣሽ እንዳሉት አጥር የለውም እንጂ፣ ሁሉም ትልልቅ ነው! ስለዚህ፥ የትኛውን አውራ ጎዳና ይዛ ወደየትኛው ትልቅ ቤት ሄዳ እንደምትጠይቅ ቸገራትና ዝብ ብላ ቆማ ትመለከት ጀመር። የአቶሞቢሉ የጋሪውን የሰዉ ብዛት ምሳሌ የሌለው እጅግ የሚያስገርም ነው! እወይዘሮ አልጣሽ ጠጅ ቤት መሸት ሲል ብዙ ባለአቶመቢል ብዙ ባለጋሪና ብዙ እግረኛ ሲመጣ ሲሄድ ስታይ ስለ ሰነበተች፣ ባይነቱ እንግዳ አልሆነባትም። ብዛቱ ግን እንግዳ ነገር ነው! ከዚያ ሁሉ ሰው በጣም የሚበዛው እንደ እግረኛ ከመቀመጫው በላይ ጥብቆ የደረበ ነው እንደ አባትዋና አመትባል ሲሆን የከት ነጫጭ እጀ ጠባባቸውንና

ሱሪያቸውን ለብሰው፥ ነጫጭ ኩታቸውን ደርበው እንደሚወጡት፥ ያገርዋ ትልልቅ ሰዎች ያሉም አለፍ አለፍ ብለው አንዳንድ ይታያሉ። በመኩዋንንቱና በባላገሩ መሀከል እንዳሉት የንዶዳም ሰዎች፥ ያደፈ እጀጠባብና ያደፈ ባት - ምላሽ ሱሪ ለብሰው ያደፈ ጋቢ የደረቡ ግን ቢኖሩም ከዚያ ሁሉ ባለጥብቆ መሀከል፥ የተፈለገው በወረንጦ የሚለቀሙ በጣም ጥቂት ናቸው። በንዶዳምና ባካባቢው በብዛት እንደምታውቀው ባላገር ጋቢውን ተከናንቦ ግልድሙን አገልድሞ፥ ረዥም ሽመሉን ይዞ የሚሄድ እንዲያውም አንድ የለ።

እዚያ አውራ ጎዳናዎች ሁሉ ከያቅጣጫው መጥተው በሚመሳቀሉበት መሀከል ላይ ቆሞ አቶመቢሉን ጋሪውንና ሰዉን ሁሉ ወደሚሄድበት ተራውን እዬጠበቀ እንዲሄድ የማመራውን ፖሊስ ስታይ ሌላውን ሁሉ ረሳችና ዝም ብላ ቆማ እሱን ትመለከት ጀመር።

ፖሊሱ፥ ካኪ እጀጠባቡና ሱሪ ለብሶ፥ በላይ ጥብቆ ደርቦ፥ ያን ባንድነት በጥቁር ሰቅ ታጥቆ፥ ጥቁር ጫማና ገንባሌ በግሩ፥ እስከ ባቱ እኩሌታ አጥልቆ፥ ዙሪያው ካኪ፥ መሀሉ ነጭ የላይ ከፍነሩ እንደ እሪያ ከንፈር ወደ ፊት ቀድሞ የተንከረፈፈ ቆቡን ደፍቶ ሁለት እጆቹን የሚያሳፍር ነገር ያለባቸው ይመስል በነጭ በሸፈኛ የሸፈነ ነው። ታዲያ እንዲያ የተሸፈኑ ዱሽ እጆቹን፥ ግራውን ወደ ሰማይ ቀስሮ፥ ቀኙን ወደ ግራ፥ ወደ ቀኝ፥ ዙሪያ፥ በቄንጠኛ አሆሁኑዋን እያወናጨፈ፥ አፉ ምንም ሳይናገር፥ እንደ ድዳ፥ በጥቅሻና በፉጨት ብቻ የሚሰጠውን ምልክት ተከትሎ፥ በያቅጣቻው እስከ ወዲያ ድርስ መሰመሩን ይዞ፥ የተሰለፈው አቶመቢልና ጋሪ፥ ሲሄድ የነበረው ባንድ ጊዜ ቀጥ ሲል ቆሞ የነበረው የግራው ወደ ቀኝ የቀኙ ወደ ግራ፥ ዙሪያ የሚዞረው ዙሪያ የሚዞረው ዙሪያ እዬዞረ፣ ሁሉም እንደ ውሀ ሙላት መንገዱን ይዞ ሲጥመለመል በጣም ደስ ይላል። ደመቀች እዚያ ቆማ ስትመለከት ደስ ከማሰኙቱ አልፎ ያሳቃት ፖሊሱ የሚያንጎዳጉደው ቄንጠኛ እንጉድጉዶ ነው። ያ ፖሊስ ከአቶመቢልና ከጋሪ መሀከል ቆሞ፥ አታሞ የሚመታና የሚያጨበጭብ፥ ወይም የሚያቀነቅንና የሚቀበል ባጠገቡ ሳይኖር፥ ብቻውን እጆቹን ግራና ቀኝ እያወናጨፈ፥ ቄንጠኛ እንጉድጉዶ ሲያንጎዳጉድና እግሮቹን እያፈራረቀ ዳንኪራ ሲመታ አንዳንድ ጊዜም ወገቡን ዙሪያ እያሽከረከረ ሲጨፍር እንደ ደመቀች ከባላገር መጥታ መጀመሪያ ለምታየው ልጅ ይቅርና ላዋቂም የሚያስቅ ነው። ደመቀች ባገርዋ እንደምታውቀው አታሞ የሚመታ የሚቀናቅንና እያጨበጨበ የሚቀበል በሌለበት እንደዚያ ፖሊስ ብቻውን ተነስቶ እያንጎደጎደ የሚዳክር ያበደ፥ ያለዚያ የሰከረ ነው! ስለዚህ ያን ያበደም ይሁን የሰከረ ፖሊስ

እዩተመለከተች ከሰዎች መሀከል መሆስንዋን ረስታ ከትከት ብላ ስትስቅ ባጠገብዋ ያሉት ሰዎች አይተው ይቁባት ጀመር።

እንዲያ እስዋ በፖሊሱ፥ በሌሎች በስዋ ሲስቁ፥ አውቶመቢሉና ጋሪው ቆመና፣ ሰው የሚሻገርበት ተራ ስለ ደረሰ ተሰልፎ የሚጠባበቀው ሰው ባንድ ላይ ተንዶ መንገዱን ሲሻገር እስዋም አብራ ተሻገረች። አብሮዋት ከተሻገረ ብዙ ሰው፥ ወደ ቀኝ የሚሄደው ቀኙን ወደ ግራ የሚሄደው ግራውን እዩያዘ መንገዱን ሲቀጥል፥ ሌላው እዚያው አጠገብ በየሱቁ የሚታየው እዩያዘ መንገዱን ሲቀጥል፥ ሌላው እዚያው አጠገብ በየሱቅ የሚታየውን እቃ እዩሄደ ሲያይ ስላዩች ወደዚያ ሄደች። «አቤ - ት! ይኸ ደሞ ምን አይነት ነገር ነው? ይኸስ ታይቶ የማይጠገብ ነገር ነው! » አለች። ሱቅ እስ በሱ ተቀጣጥሎ ተቀጣጥሎ መጀመሪያውና መጨረሻው አይታይም! መጀመያ እዚያ እንደ ደረሰች ያዩችው ጨርቅ በያይነቱ የሚታይም! መጀመሪያ እዚያ እንደ ደረሰች ያዩችው ጨርቅ በያይነቱ የሚታይበት ሱቅ ነው። ነጩ ጥቁሩ፥ ቀዩ፥ አረንጉዋዴው ቢጫው ዝጉርጉሩ ኧረ ስንቱ ብትኑና የተሰፋው አንዳንዱም የሰው ምስል ለብሶት ከመስተዋት አጥር ውስጥ ሆኖ እያዩ ይታያል! ባገርዋ፥ እንዳዩችውም እንደ ሰማችውም ከነጩ ልብስ በእር ሌላው ዝንጉርጉሩም ሆነ ሌጣው ግምጃ ቄሶችና ዲያቆኖች ሲቀድሱ የሚለብሱት ነው። ወይም ሰዎች ሁሉ እንደ ሰማችው የስላም ሴቶች ልብስ ነው። ደመቀች ሁሉ ጨርቅ ወዲያና ወዲህ እዩተመላለሰች፥ በመገረም ስታይ ቆዩችና «ከነጩ ልብስ - ዝንጉርጉሩና ሌጣው ግምጃ የሚበዛ እንዴት ነው? የዚህ አገር ሰው ቄሱና ዲያቆኑ፥ እስላሙ ጭምር ይበዛል መሰለኝ» አለች በልብዋ። ቀጥሎ ጀበና፥ ስኒ ሰሀን ብርጭቆና፥ ሌላ የመብልና የመጠጥ መሳሪያ በያይነቱ ተሰልፎ የሚታይበት ሱቅ ነው። «አቤ - ት እናቴ የደንጋያላይቱ! ይኸ ደሞ እንዴት ያምራል! የመይቴ አልጣሽ ብርጭቆ እንደዚህ አያምርም» አለች ዝም ብላ ስትመለከት ቆይታ። ከዚያ ቀጥሎ ያለው መብል ቤት ነው። ከመግቢያው በስተቀኝ፥ ከመስኮቱ መስታወት ሁዋላ ጮማው ስጋ ሙዳ ሙዳ ሆኖ እዩተቆረጠ በሰፌ ዳታና ተቀምጦ፥ ጥብሱ ከትፎው እንፍሌው፥ ቀዩና አልጫው ወጥ፣ እንዲሁም ሌላው የስጋና ያትክልት ወጥ በያይነቱ በጎድጉዋዳ ሰሀን ሞልቶ፥ ሻሽ የመሰለው ነጭ እንጀራ ና የማታ ጸሀይ የመሰለው ዳቦ በጥልፍ መሶብ - ወርቅ ተቀምጦ፥ ይህ ሁሉ ጥሩ ነገር፥ አንዳንዱ በውን፥ ሌላው በሥዕል እዩሆነ፥ ሲያዩት እንጂ ሊበሉት እንዳልተሰራ ሁሉ የመስተዋት አጥሩን በፊቱ አጥሮ፥ ተደርድሮ ሲመለከቱት እንዴት ያስጎመዣል!

«እማ፤ አንጣ» አለ ተከስተ፥ ያን የሚያስጎመዥ ምግብ ሲያይ።

«እሺ አብዬ፥ ቆይ ሁዋላ» አለች ደመቀች፥ እንዳዘለችው ከታች በደገፈችበት እጅዋ ለማባበል ትንሽ መታ መታ እያደረገች።

ከዚያ ከሚያስጎመዠው ምግብ ሁሉ ወደ መጨረሻ፥ ከምግብ ቤቱ መግቢያ አጠገብ ፓስታ እስኪጠይም በተቁላል መረቅ ተለውሶ፥ በትልቅ ጉድጉዋዳ ሰሀን ቸርፈፍ ብሎ ሞልቶ ስታይ፥ ኮሶ ተጠጥቶ ሲያሽር የሚታየውን አስጸያፊ ነገር አሳሰባትና ድንገት ሆድዋን ግልብሽ ስላደረገው፥ «አክ! እናቴ የደንጋያላይቱ! ይኸ ደሞ እዚህ ምን ሊያረግ መጣ? የኢህ አገር ሰው እንዲህ ያለውንም ይበላል? » አለች ራስዋን እያንገፈገፈች። ዳግመኛ ምግቡ ወደ ተሰለፈበት ማየት አልፈለገችም። ከዚያ አልፋ ልትሄድ ስትል ከሙብል ቤቱ በር ላይ ሊበላ የሚገባውና በልቶ የሚወጣው ሰው እንደ ሰራተኛ ንብ በሩ ጠቦት እስበሱ ሲገፋፉ አየችና ዝም ብላ ቆማ እሱን ትመለከት ጀመር። ትንሽ ቆማ ከቆመችበት ወደ ውስጥ አስገብታ ብታይ አዳራሹን ጋብ ስላለ፥ ከቆመችበት ወደ ውስጥ አስገብታ ብታይ አዳራሹን ሞልቶ በዬጠረጴዛው ዙሪያ ተቀምጦ የሚመገበው ሰው እጅግ ብዙ ነው። «አሀ! እዚህ ቤት ድግስ አለ መሰለኝ! ያልተጠራም ይገባ ይሆን? ኧረ እንጃልኝ! » አለች፥ ምንም እንኩዋ እስዋን ራብ ባይሰማት ተከስተን ርቦት «እንጣ» ስላለ ገብታ እሱ የሚበላው ለመለመን አሰባ። ወዲያው ስትፈር ስትቸር ወደ በሩ ጠጋ አለችና፥ አሁንም ወደ ውስጥ አስገብታ ስታይ ተቀምጠው ከሚበሉት አንዳንዶቹ፣ ያን የሚያስጸይፈውን ነገር እንደ ማግ እያጠነጠኑ ከብሰው ግራ ቀኝ ጉንጫቸውን እስኪፈጥ ሲጎርሱ ስላዬች፣ «በግድ ይዘው ሊያጎርሱሽ ነው» እንደ ተባለች ሁሉ ፈርታ ሸሸች። ከዚያ በሁዋላ ወደዚያ መብል ቤትና ልዩ ልዩ ምግብ ተደርድሮ ወደሚታይበት መስኮት አልተመለሰችም። ነገር ግን የመሀል አራዳን አደባባይና የራስ መኮንን ድልድይ መመለሻዎች አድርጋ፥ በነሱ መሀከል እንደ ሸማኔ መወርወሪያ ወዲያና ወዲህ ስትመላለስ፥ እንኩዋንስ የሁለት አመት ልጅ በጀርባዋ ያዘለች፥ ሁለት ቅንጣት ገለባ በጅዋ ያንጠለጠለች ሳይመስላት ቀኑ ተገባደደ። በያንዳንዱ ሱቅ መስኮት ያለውን እቃ አይታ ካለፈች በሁዋላ፥ በተከታዩ ዙር ስትመለስ ያላዬችው እቃ ታገኛለች፤ ያዬችውም ያላዬችው ይመስላታ። ይልቁንም አንጥረኞች ሱቅ ያለው የወርቅ ጌጥ፣ ድሪው መስቀሉ፥ ጉትቻው፥ ቀለበቱ፥ አንባሩ፥ ኧረ ስንቱ! እንኩዋንስ ሲያዩት መዋል ሲያዩት ቢኖሩ አይጠገብም! «እንግዲህ የሚቀጥረኝ እስካገኝ እዚህ እዬመጣሁ ሳይ ነው የምውል» አለች በልብዋ። እንደገና ተመልሶ ጥዋት ቢሆን እንዴት በወደደች! ብቻ ቀኑ ተገባደደ። ጀንበርዋ ከወጣችበት ተነስታ ሽቅብ ወደ ሰማዩ አናት፥ ወደ ቀትር ስትጉዋዝ፥ አቀበቱ እንደሚጋፋት ሁሉ፥ ዝግ ብላ ነበር የምታዘግም። ቀትሩን አልፋ ወደ መግቢያዋ ቁልቁለቱን፥ ከጀመረች በሁዋላ ግን፥

በማዝገም ፈንታ ዘቅዝቃ እዬተንደረደረች የለት ጉዞዋን ልትጨርስ ምንም ያክል አልቀራት።

ደመቀች ከራስ መኮንን ድልድይ ተመልሳ መሀል አራዳ አደባባይ ስትደርስ ወደ ምዕራብ ብትመለከት ጀንበርዋ የወርቅ አለሎ መስላ፣ ወደ መግቢያዋ የወረወረቻቸው ጨረሮችዋ የወርቅ ከስቶች መስለው ባድማሱ ላይ ተተክለው ያካባቢው፣ ሰማይ ሳይቀር በወርቅማ፥ ቀለም አጊጦ አይችና፣ ያን ትርእይት እንዳዲስ ነገር ዝም ብላ ቆማ ስታደንቅ ቆዬች። ጀንበር ስትገባ እንዲያ አምራና የምትገባበትን አካባቢ አሳምራ ስትገባ ጉዳዬ ብላ አይታ ስለማታውቅ የዚያነለቱ ትርእይት አዲስ መስሎ ታያት። ወዲያው መምሸቱ ትውስ ሲላት ወደ ቤትዋ ለመመለስ አስባ፣ የሰፈርዋን ስም ብትፈልግ ካስቀመጠችበት ጠፋ! አሳብዋን ብታስጨንቀው ብትጠምቀው ጉለሌ ጠብ አልል አለ! ጉለሌን ስትፈልግ፥ በሱ ፈንታ ቀኑን ሙሉ ስታየው የዋለች ያ የሚያጎዳጉደው ፖሊስ በዬሱቁ መስኮት የተደረደረው ልብስ፥ የቤት እቃው ምግቡ፥ ምንጣፉ፥ ጌጡ ኧረ ስንቱ! ራስዋን ሞልቶ አንዱ ታይቶ ጥልቅ ሲል ሌላው ብቅ እያለ አንዳንድ ጊዜም ባንድ ላይ እዬተተራመሰ ይታያታል! ያ ሁሉ ብቅ ጥልቅ የሚለው ያ ሁሉ የሚተራመሰው ውጥንቅ፤ ጉለሌን እንዳይጠፋ ስንት ጊዜ እየመላለሰች አጥታ ካስቀመጠችበት ወዲያ አስወጥቶ አባር ራስዋን ስለ ሞላው ጉለሌ የትሜናውን ሄደ፤ የውሀ ሽታ ሆነ! ዘልግ ያለ ጊዜ ስታስብ ቆይታ፣ የሰፈርዋን ስም በሙሉ ባታገኘውም «ገ እና ለ» ያለበት መሆኑ ትዝ ስላላት «ላገኘው ነው ብላ በጣም ደስ ብሎዋት ነበር። ነገር ግን ምንም ያክል ብታስብ ሙሉ ስሙን ማግኘቱ አልሆነላትም። መቸም «ገ እና ለ» ብቻ ጉለሌ አይሆኑ! «ገ እና ለ» ያሉበትን ስም ስትፈልግ ባሳብዋ ውስጥ የሚመጣ አገርዋ ሳለች ስታየውና ስትሰማው የኖረችው ያገር የቃ የሰውና የሌላ ነገር ስም ነው። «ጉሊት፥ ጉልሞ፥ ጉልቻ፥ ገልባ፥ ጉልላት፥ ገላውና እንዲህ እንዲህ ያለው ሁሉ፥ «ገ እና ለ» ያሉበት ስም ከጉለሌ፥ በቀር በሀሳብዋ ያልመጣ የለም! በመጨረሻ የሰፈርዋን ስም እንደማታገኘው ተስፋ ቆረጠችና ራስዋን ማሰብ ስለደከመው፥ ዝም ብላ የመጣችበትን አውራ ጎዳና ይዛ ለመሄድ ተነሳች። ብቻ የመጣችበት መንገድ መስሎዋት የያዘችው አውራ ጎዳና ወደ ጉለሌ የሚወስደው ሳይሆን ወደ ገነተ ልኡል ቤተ መንግሥት የሚወስደው ነው።

ከደጃች ውቤ ሰፈር በታች ያለውን ወሀኒ ቤት አልፋ፥ «አፍንጮ በር» ከሚሉት በታች ባለው ድልድይ ስትደርስ ጥዋት የመጣችበት አውራ ጎዳና አለመሆኑን በርግጥ አወቀችና፣ ወደ ሰፈርዋ የማትደርስ መሆንዋን መጥፋትዋን ተረዳች። ጀንበርዋ

ገብታለች። ከዚያ በሁዋላ ምኞትዋ፥ ሁሉ ጉለሌ የሚያደርሳትን መንገድ ማግኘት መሆኑ ቀርቶ ተጠግታ የምታድርበት ቤተ ክርስቲያን ማግኘት ሆነ።

መንገዱን ከሞላው ብዙ ተላላፊ ህዝብ ሌላ፥ አንድ በልተት ያሉ ገመድ ጠቅልለው ከግራ ብብታቸው ስር የያዙ ሴት ከደጃች ውቤ ሰፈር ጀምረው እዬቀደሙዋት እዬቀደመቻቸው፥ አንዳንድ ጊዜም ጎን ለጎን እዬሄዱ አብረዋት ከድልድዩ አጠገብ እንደ ደረሱ አውራውን ጎዳና ትተው የቀጨኔን መንገድ ሲይዙ ወደሳቸው ጠጋ አለችና፣

«ጤና ይስጥልኝ እማዬ» አለች።

«እንዴት ዋልሽ ልጄ» አሉ ሴትዮዋ ቆም ብለው።

«እዚህ ግድም ቤተ ክርስቲያን ይኖር ይሆን እማዬ? »

«በዚያ በኩል ቅድስት ማርያም፥ እዚህ ላይ ቀጨኔ መድህኔ ዓለም አሉ» አሉ ባልቴቲቱ ሁለቱ ቤተክርስቲያኖች ያሉበትን በቀኝ እጃቸው አመልክተው።

«ደጀ ሰላምና መቃብር ቤት ይኖራቸዋል ብለዎይ? »

«መቸስ - መቃብር ቤቱን እንጃ እንጂ ደጀሰላም የሌለበት ቤተ ክርስቲያን ያለ አይመስለኝም። ብቻ እኛ ሰበካችን ቀጨኔ መድህኔዓለም ስለሆነ፥ እኔ ደህና አድርጌ የማውቀው እሱን ነው። ታዲያ እዚያ ትልቅ ደጀሰላምና ብዙ መቃብር ቤት አለ። ለመሆኑ ለምን ነው ደጀሰላምና መቃብር ቤት የምትጠይቂ? »

«የሰፈሬ መንገድ ጠፍቶኝ ደጀሰላም ወይም መቃብር ቤት ተጠግቼ አድራለሁ ብዬ ነው።»

«ሰፈርሽ ማን ይባላል? »

«የሱም ስሙ ጠፍቶብኝ ነው።»

«ለከተማው አዲስ ነሽ? »

«አዎ፤ አሁን ነው የመጥቼ።»

«አገርሽ ወዴት ነው? » አሉ ባልቴትዋ፥ ካነጋገርዋ የመጣችበት አገር ምን መሆኑን ጠርጥረው።

«እንዶዳም ኪዳነ ምህረት ነው።»

እንዶዳም ኪዳነ ምህረት አላውቀውም፤ ወዴት ነው? »

«ጎጃም ነው።»

«ጎጃም? አይኔ ፍስስ ይበል! የኔም አገሬ ጎጃም ነው። ቤቱ የድሀ ቤት ስለሆነ የሚበላ ራት አላገኝልሽም እንጂ፣ ለማደሪያነቱስ - ከደጀሰላምና ከመቃብር ቤት ሳይሻል አይቀርም። ነይ፤ ከኔ ጋር ታድሪያለሽ» አሉ ባልቴትዋ። ደመቀች የጋበዙዋት ሴት «አገሬ ጎጃም ነው» ሲሉዋት ጎጃም የገባች መሰላትና በጣም ደስ ብሎዋት ምንም ሳትግደረደር «እሺ እማዬ» ብላ ተከትላቸው ሄደች።

# ምዕራፍ ስድስት

# የሱሉልታዋ ኩበት ለቃሚ

ባልቴትዋ እቤታቸው እንደ ደረሱ፥ ደመቀችን እውጭ ትተው፥ ከፍተው ገቡና፣ ቶሎ እሳት አንድደው ሲይስገቡዋት -

«ስምሽ ማን ነው? እኔ ፈቃድዋ እባላለሁ፤ ፈቃድዋ ይሁን» አሉ።

«ደመቀች ጸሀይ ነው» አለች ደመቀች።

የመት ፈቃድዋ ይሁን ቤት እውነትም የድሀ ቤት ነው። መቀመጫው መብያው መተኛው እንጀራ፥ መጋገሪያው መስሪያው የቃ ማስቀመጫው፥ ሁሉንም ማድረጊያው አንድ ክፍል ነው። ከምድጃው አጠገብ፥ ባንድ በኩል እስከ ግድግዳው የሚተኙበት አንድ ሰፊ መደብ አለ። አንድ፥ እንደ መደቡ ሰፊ፥ የኬሻ ፍራሽ ካንድ ብርድ ልብስ ጋር ተጠቅልሎ ከመደቡ ራስጌ ተከምሮዋል። እዚያ አንድ ክፍል ውስጥ፥ መደቡ ከያዘው የተረፈውን ቦታ እንስራው፥ ምጣዱ ሙግዱ፥ ድስቱ፥ የቡሆ እቃው፥ ቶፋው፥ ሰፌዱና ሌላው፥ ለዬለቱ አገልግሎት የሚያስፈልገው ቁሳቁስ ሞልቶታል።

እመት ፈቃድዋ ደመቀችን እመደቡ ላይ አስቀምጠው እሳቸው በገበታ ውሀ ቀድተው እግራቸውን ከታጠቡና ለስዋም ሰጥተዋት ከታጠበች በሁዋላ -

«እንግዲህ - እሳቱ ሳይጠፋ ቶሎ ራታችንን በልተን እንተኛ። የዚህ አገር እንጨት በገንዘብ ተገዝቶ ነው እንጂ እንዳገራችን ከዱር ተለቅሞ አይመጣም። እዚህ አገር ቤቱ በገንዘብ ተከራይቶ እንጨቱና ሌላው ነገር ሁሉ በገንዘብ ገዝቶ ነው። እዚህ አገር ያለገንዘብ፥ ‹አይኔን አውጡልኝ› ብትይ ‹እሺ› የሚልሽ አታገኝም» አሉ፥ ከደመቀች ጎን፣ እመደቡ ላይ ከተቀመጡበት ራት ሊያቀርቡ ሲነሱ።

«እማ እንጣ! » አለ ተከስተ ተኝቶ የዋለው ራቡ የራትን ወሬ ሲሰማ እንደ ተቀሰቀሰ ሁሉ።

«አይኔ ፍስስ ይበል! ልጄን ርቦታል» አሉ ባልቴትዋ።

«አዎ ርቦታል። ጥዋት እስፈራችን ቁርስ ተቀመሰ በሁዋላ ምንም ስላልበላ ርቦት ሲያስቸግረኝ ነው የዋለ» አለች ደመቀች።

እንግዲያ - ከራበውስ፣ ለራቴ ያስቀመጥሁት አንድ እንጀራ ብቻ ስለሆነ አይበቃንምና እንዲህ ላድርግ» አሉ እመት ፈቃድዋ አይኖቻቸውን ወደ ጣራው አስንተው ሲመለከቱ ቆይተው። «ዛሬ ሱሉልታ ሄጄ ስለቅም የዋልሁትን ኩበትና ቅጠል ሽጬ ትንሽ ገንዘብ አለኝ። እንዲያውም ከዚያ ስመጣ ነው፣ ቅድም በመንገድ የተገናኘን። ስለዚህ ሮጬ፥ እዚህ አጎረቤታችን ካለው ሱቅ ዳቦና ሻሂ ገዝቼ ላምጣና፣ እሳቱ ሳይጠፋ ሻሂ አፍልቸለት፥ ልጁ ዳቦ በሻሂ ነክሮ ይብላ አንቺና እኔ አንዱን እንጀራ በወፍራም ተልባችን ብልት፥ ውሀችንን ጥጥት አድርገን እንተኛለን» አሉ ትንሽ እንደ መሳቅ ብለው።

«ገንዘብማ እናታችን የሰጡኝ አለኝኮ እማዬ፥ የሚገዛ ዳቦና ሻሂ ተተገኘስ በኔ ገንዘብ እንግዛ። ይዩት፥ እናታችን አስራ ሁለት ብር ሰጥተውኛል» አለች ደመቀች፥ እናታችን የሰጡዋትን አስራ ሁለት ብር ቁዋጥራ በጉንፍዋ ካስቀመጠች አውጥታ ላስተናጋጅዋ እያሳየች። እመት ፈቃድዋ አይኖቻቸውን በጥፍ አውጥተው፥ አንድ ጊዜ አስራ ሁለት ብር አንድ ጊዜ ደመቀችን እያለዋወጡ እያዩ ፍዝዝ ብለው ቀሩ።

«ስንቱ ይበቃል እማዬ? » አለች ደመቀች ባልቴትዋ፥ ገርሞዋቸው ዝም ብለው እንደ ፈዘዙ ስለቀሩ።

«እንዲያውም ስንቱ? አንዱም ይበዛል ልጄ! ባስር ሳንቲም ለልጁ ደህና አድርጎ የሚበቃ ዳቦ በሀያ ሳንቲም ሻሂና ስኩዋር ተገዝቶ ከብሩ ሰባ ስንቲም ይመለሳል።

«እንግዲያውስ ሲገዙ እንዳይ እኔም አብሬዎ ልምጣ፤ መግዛት ስለማላውቅ እንድማር» አለች ደመቀች። ወዲያው ልጅዋን እንደገና አዝላ፥ ካስተናጋጅዋ ጋር አብረው ሄዱና፥ ከሱቅ በሰላሳ ስንቲም ሳይኖ በሰባ አምስት ሳንቲም ዳቦና ሻይ፥ ስኳዋር በርከት አድርገው ገዝተው ተመለሱ። ከዚያ እመት ፈቃድዋ ከደጅም ከቤትም ጠራርገው ሊያገኙ በቻሉት የንጨትና የቅጠል እንክትካች እንደ ምንም ብለው ሻይ አፍልተው ተከስተ ብቻ ሳይሆን እሳቸውና ደመቀች ጭምር እስኪጠግቡ በልተው፥ ሻይ ጠጥተው እዚያ ሰፊ መደብ ላይ፣ ያን የኬሻ ፍራሽ ዘርግተው፥ ሶስቱም የዬራሳቸውን ልብስ እንደ ልበሱ አንድ ብርድ ልብስ የጋራ ደረበው አደሩ።

ደመቀና ልጅዋ ደከሞዋችወ እንኩዋንስ ሊነቁ መጀመሪያ ከተኙበት ጎናቸው ሳይገላበጡ ነው ያደሩ። ባልቴትዋ ግን ድካም ከብዙ ጊዜ ጀምሮ አብሮዋቸው የቆየ ስለ ሆነ፥ አዲስ ስላልሆነ እንደ ልማዳቸው ከኩለ - ሌሊት በሁዋላ ነቅተ አለሙን ሲያፈርሱ፥ እንደገና ሲሰሩ ሀብታሙን ሲያደኽዩ፥ ድሀውን ሲያከብሩ፥ ነጋላቸው። ከዚያ፥ ደመቀችንና ልጅዋን እንደ ተኙ ትተዋቸው ወጥተው ትናንቱን ኩበትና ቅጠል ከሸጡበት ባስር ሳንቲም እንቸት ባስር ሳንቲም ካለፈው ማታ ለተረፈው ዳቦ መጨመሪያ ገዝተው ሻይ፥ አፈሉና እንግዶቹ ሲነሱ እዬተጫወቱ ቁርስ አደረጉ።

ደመቀች ያስራ ሁለት ብር ጌታ መሆንዋን ካዩ በሁዋላ እመት ፈቃድዋ፣ እንደ ለማኝ ጥገኛ መመልከታቸው ቀርቶ፥ እንደ ከብር እንግዳ ቆጥረዋት፥ ባነጋገራቸውም ሆነ ባድራጎታቸው በጎ አድራጊዋ መስለው እንዳይታይዋት ከመጠንቀቃቸው አልፈው፥ እንዲያውም እንደ ጉዋደኛ ብሶታቸውን ያጫውትዋት ጀመር።

«እይውልሽ፥ ባሌ ከሞተ በሁዋላ ሀብቴን በተዝካሩም፥ ከዘመዶቹ ጋር በሙግቱም ጨርሼ በድህነት ላይ ወደቅሁ ‹መሸታ ሽጣ ለምታድር ሴት አዲስ አበባን የመሰለ እንገር የለም› ሲሉ እውነት መስሎኝ ከዘመዱ፥ ዘመድ፣ ከገንዘቡ ገንዘብ ሳይኖረኝ፥ ባዶ እጅና እግሬን ይዤ ካገሬ መጥቼ እንዲህ በባሰ ድህነት በባሰ ችግር እኖራለሁ። ‹የግዜር እንግዳ› ብላ ለመጣች ልጅ እንኩዋ፤ ራት አብልቼ በማሳደር ፈንታ በንግዳዬ ገንዘብ ራት በልቼ የማድር ሆንኩ» አሉ ባልቴትዋ በሚያሳዝን ድምጽና በሚያሳዝን ፊት። ደመቀች አስተናጋጅዋ የተናገሩትን በሙሉ ማስተዋል ባትችልም የሚያሳዝን ድምጻቸውን ስትሰማና የሚያሳዝን ፊታቸውን ስታይ፣ እንደ ማዘን ብላ አንገትዋን ደፋች።

«ብዙ እንኩዋ ባልፈልገሁ» አሉ ቀጠሉና፣ «ብዙ ባልፈለግሁ። አስምት ብር ወረት ቢኖረኝ ወይም አምስት ብር የሚያበድረኝ ዘመድ ባገኝ፥ እኔ እናትሽ ‹ሙያ

ላስተምራችሁ› እል እንደሆን እንጂ ‹አስተምሩኝ› የምል ስላይደለሁ፥ ባምስት ብር ያገሬን፥ የጎጃምን ጠላ በንስራ ባደርግ፥ በስምቱ አምስቱን ብር ቢያንስ ቢያንስ አስር አደርገዋለሁ። ከዚያ በሁዋላ ያን እያገላበጥሁ፥ እስከ ወሩ መጨረሻ በንስራ አይደለም፥ በጋን እንኩዋን አይደለም በበርሜል የምደፈድፍ እሆን ነበር። ብቻ ምን ይሆናል አምስት ብር ከሰማይ የራቀ ሆነ! በዬለቱ ሱሉልታን ያክል አገር ሄጄ አምጥቼ ከምሸጠው ኩበትና ቅጠል የማገኘውን ገንዘብ ለስንቱ ላድርገው? ማጣፊያው አጥሮ፥ ለራስ ሲሉት እግር፥ ለግር ሲሉት ራስ፥ እየተራቆተ፥ አስቸገረ። እንኩዋንስ አምስት ብር ለመቆጠብ፥ ከለት ራትና ከቤት ኪራይ አያልፍም። ለዚህ፥ ቆም ቢከርም ቆሞ ይበጃል፥ ለማይባል የዘመድ ቤት የምከፍለው ኪራይ በወር ሶስት ብር ነው። ታዲያ ከለት ቀለቤና ከቤቱ ኪራይ ማስተረፍ አልሆንልኝ ስላለ ለቤተክሲያን፥ መሳሚያ አንድ ንጹህ ልብስ የምገዛበት አጥቼ፥ እይው፥ በዚህ ኩበት በምለቅምበት ልብስ ነው - ቤተክሲያን የምስም! ይህ ሁሉ ያምስት ብር ወረት ባይኖረኝ ነው እንጂ አምስት ብር ባገኝ፥ ባንድ ወር እድሜ ይህን ሁሉ ችግር ወዲያ አራግፈው ነበር! » አሉ ባልቴትዋ ችግራቸው በግዘፈ ስጋ መጥቶ በፊታቸው እንደ ቆመ ሁሉ፥ አይኖቻቸውን ቦዘዝ አድርገው በትካዜ ፊት ለፊት እዬተመለከቱ። ብዙ የቸገራቸው ሰዎች፥ እንኩዋንስ ባጠገባቸው ተቀምጦ ጆሮውን የሚሰጣቸውን፥ ዝም ብሎ የሚያዳምጣቸው አግኝተው፥ ሰው በሌለበት ብቻቸውን ተቀምጠው፥ ወይም እዬሄዱ ችግራቸውን ለራሳቸው የሚናገሩ መሆናቸው የታወቀ ነው። የደመቀች አስተናጋጆችም ችግራችውን ከሚያወሩት ሁሉ «ገንዘብ እገኛለሁ» ብለው ሳይሆን እንዲያው ልማድ ሆኖባቸው፥ ያነለት ለስዋ የሚነገሩዋትን በቤተክስቲያን በልቅሶና፥ በሌላ ከሰው፥ ተገናኝተው በሚጫወቱበት ቦታ ሁሉ ለስንት ሰው፥ ስንት ጊዜ እንደ ተናገሩ እግዜር ብቻ ይወቀው!

ደመቀች አስተናጋጅዋ አምስት ብር በማጣታቸው የደረሰባቸውን ችግር የነገሩዋት፣ አምስት ብር እንድትሰጣቸው ስለ ፈለገ መስሎዋት! —

«እና - አምስት ብር ለቤተክስቲያን መሳሚያ ልብስና ጠላ ለማድረግ የሚያስፈልገውን - ፥ ብቅሉን፥ ደረቆቱን፥ አብሽሎውን ጌሾውን፥ ሁላ ለመግዛት ይበቃል? » አለች።

«አ - ይ፥ ይህን ሁሉ ባንድ ጊዜ ለመግዛት አምስት ብር አይበቃም። ቅድም እንዳልሁሽ መጀመሪያ ባምስት ብር አንድ እንስራ ድፍድፍ እደፈድፍና፥ እዚህ አገር የጎጃም ጠላ ብርቅ ስለሆነ፥ ቢያንስ ቢያንስ አስር ብር ይጣራል። ከዚያ ባስር ብር ድፍድፌን በጋን የደፈደፍሁ እንደሆነ፥ ያን ደግሞ አስር ቀን ሳይሞላ በሀያ ብር አጣራና፥

በወሩ መጨረሻ ላይ፣ በበርሜል ለመደፍደፍ እበቃለሁ። ከዚያ በሁዋላ ምን ልበለሽ - ለቤተክስቲያን መሳሚያ ቀሚስና ኩታ ብቻ ሳይሆን ሌላም ለማድረግ እችላለሁ።»

«እንግዲያስ እናታችን ከሰጡኝ አምስት ብር እነሆ» አለች ደመቀች፥ በጨርቅ ቋጥራ በጉንፍዋ ካስቀመጠችው ብር አምስቱን አውጥታ። ባልቴትዋ «አምስት ብር እነሆ» ስትላቸው፥ አምስት ብር እንደ ጠፋቸው በጣም ደንግጠው፣ ምንም ሳይናገሩ ዝም ብለው ቆይተው ድንጋጤው እያለፈ ሄደ ማሰብ ሲጀምሩ የሳቸው ድህነትና የዚያች ትንሽ ልጅ ደነት ባንድ ላይ ሆነው ልባቸውን መተውት ስላለቀሰ፥ ከውስጡ ገንፍሎ የወጣው ትኩስ እንባ አይኖቻቸውን ሞቶ በፊታቸው ይፈስ ጀመር።

«ምነ እማዬ ምን ሆኑ? » አለች ደመቀች ደንግጣ ተነስታ።

«ምንም አደል ልጄ፥ ምንም አደል ተቀመጪ» አሉ ባልቴትዋ በተቀደደ እጅጌያቸው አይኖቻቸውንም ፊታቸውንም እዬጠራረጉ። ደምቀች ያለቀሱበት ምክንያት ስላልገባት አምስቱን ብር እንደ ያዘች እፊታቸው ዝም ብላ ቆማ፥ በድንጋጤ አይን ትመለከታቸው ነበር።

«ተቀመጪ ልጄ» አሉ ደገሙና። «እባክሽ ተቀመጪ። ገንዘቡን ግን አልቀልም፥ እግዚአብሔር ይስጥልኝ።

«ለምን? ባይበቃ ነው? ይበቃል ሲሉ ጊዜ ነው እንጂ፣ ካልበቃ ልጨምርልዎ፥ ወይም ሁሉን ልሰጥዎ።»

«ኧረ አነሰ ብዬ አይደለም፥ አምስቱም ሲበዛ ነው። ገና እኔ ከችግር እወጣ ብዬ፣ አንቺ በችግር ላይ እንድትወድቂ ባደርግ እግዚአብሔር አይወድልኝም፥ ገንዘቡም አይባረከም ብዬ ነው። በይ አሁን ተቀመጪ፥ እግዚአብሔር ይስጥሽ ልጄ! »

«ግዴለም ሰፈሬን ታገኘሁት አልቸገርም እማዬ። እስትቀጠር አይያ መላኩ እዬከፈለልኝ እመይቴ አልጣሽ ቤት እቆያለሁ። ተቸገረም ታንድ ወር በሁዋላ መጥቼ እስዎ ገንዘብ ሲያገኙ ይሰጡኛል። ስለዚህ እባክዎ «እንቢ» አይበሉም፥ በናቴ የደንጋያላይቱ! » ብላ ወደ ጉልበታቸው ጎንበስ ስትል፥ ቶሎ ተነስተው፥ ቀና አድርገው፥ ግራ ቀኝ ጉንጮችዋንም አፍዋንም ሰመው፥ አምስቱን ብር ተቀበሉና ይመርቁዋት ጀመር።

ልጆች ከልጅነታቸው መጥተው በውቀት ይሁን በጉልበት ወይም በሀብት ከሌሎች፥ ይልቁንም ትልልቆች በልጦ መታየት፣ ከሁሉ የበለጠ ደስ ስለሚያሰኛቸው፥ ደመቀች ያስራ ሁለት ብር ጌታ ሆና፣ እኒያን የተቸገሩ ሴት ለመርዳት በመቻልዋና ያን ያክል በመመረቅዋ፥ ነፍስ ካወቀች ጀምሮ እስከዚያ ድረስ እንደዚያነለት ደስ ብሎዋት አያውቅም። ባልቴትዋ የሚያውቁትን ምረቃ ሁሉ በላይ በላዩ እዬደራረቡ ካሸከሙዋት በሁዋላ፥ -

«ስራ እስካገኝ ለመቆያየ ይከፍልልኛል ያልሽው ሰው ዘመድሽ ነው» አሉ።

«አይያ መላኩ ዘመዴ አይደለም። እናታችን - ‹ስራ ፈልገህ አስቀጥራት› ብለው አደራ ያሉት ባለ መኪና ነጋዴ ነው። አንደ ሺ ስድስት መቶ ጎራድ ጤፍ ጭኖ መጥቶ፥ አሁን - ሁሉንም ሸጠው።

«የጎጃም ሰው ነው? »

«አዎ፥ የማርቆስ ሰው ነው።»

«ታዲያ - የጎጃም ነጋዴዎችኮ ካንዳንዶቹ እሌላ ቦታ የሚሰፍሩበት ዘመድ ካላቸው በቀር፥ ሁሉም የሚሰፍሩ ጉለሌ» ብለው እመት ፈቃድዋ የሚናገሩትን ሳይጨርሱ።

«እ - ሱ ነውኮ እማዬ፤ ጉለሌ ነው! ጉለሌ ማለት ጠፍቶኝ ነው ያን ያክል የተጨነቅሁ! » አለች ደመቀች፥ ከተቀመጠችበት በደስታ ዘላ ተነስታ እዬሳቀች። «የታባቱ ተሸሽጐ ነው ያን ያክል ያስጨነቀኝ» አለች ቀጠለችና።

«በይ ተቀመጪ፥ አሁን ከተሸሸገበት አግኝተነዋል፥ ከንግዲህ ምንም ቢሆን አይጠፋም» አሉ ባልቴትዋ እንደ መሳቅ ብለው።

«ተዚህ ሩቅ ነው? »

«በጣም ሩቅ አይደለም፤ እኔ በጋሪ እወስድሻለሁ። እመይቴ - ማነው ያልሻቸውን ቤትስ ታውቂዋለሽ? »

«እመይቴ አልጣሽ ናቸው። እዚያ ተደረስን ማንም ያሳዬናል።» ብሬን ሳልነካ፥ ኩበትና ቅጠል ከሸጥሁበት ሳንቲም በተረፈው እንጨት ልግዛና፥ ከትናንት ወዲያ ያቦካሁዋትን ሊጥ ጋግሬ ትንሽ ምስር ክክ አለችኝ እስዋን ወጥ ሰርቼ፥ እንጀራ በወጥ

በልተን ስንጨዋወት ውለን ሳይመሽ እወስድሻለሁ» አሉ እመት ፈቃድዋ። ደመቀች ደስ ብሎዋት ግብዣቸውን ተቀበለች።

እመት ፈቃድዋ እንዳሉት፥ እንጨት ገዝተው አምጥተው እንጀራ ሲጋግሩ፥ ደመቀች የምትሰራውን ነገር አቀራርበውላት ወጥ ሰርታ፥ ምሳችወን በሉና አርፈው ሲጫወቱ ቆይተው ባስር፥ ሰአት ግድም ወደ ጉለሌ ለመሄድ ወጡ። ያንጊዜ ሀይለኛ ነፋስ ተነስቶ፥ ጠብቆ ያልተቸነከረውን ቆርቆሮ ሁሉ በዬቦታው ሲያንኳዋኩዋ ወረዳ ክዳን ከተከደነው ጣራ ሁሉ ሳር ሲገፍርና ባህር ዛፉን በያለበት መሬት እስኪልስ እያሰገደ በህይወት ባይሆን በንብረት ብርቱ ጥፋት እንዳይደርስ ያሰጋ ነበር።

«እንጃ፥ ዛሬስ ይኸ እግዜሩ፥ ይህን አለም ሊያሳልፈው አስቦዋል መሰለኝ» አሉ እመት ፈቃድዋ፥ ነፋስ ቀዳዳ ነጠላቸውን እንዳይቀማቸው እዬተከላከሉ።

«እንዴት? » አለች ደመቀች።

«እንዲህ ያለ ነፋስ የሚመጣ የዚህ አለም ማለፊያ ሲደርስ ነው ይባላል»

እመት ፈቃድዋና ደመቀች መደረቢያ ልብሳቸውን ንፋሱ እንዳይቀማቸውና ባይናቸው አቡዋራ እንዳይገባ እስከ ቅንድባቸው ደህና አድርገው ተከናንበው ትንሽ እንደ ሄዱ፥ አንድ፣ ሰው ያላሳፈረ ባለጋሪ ከሁዋላ ስለ ደረሰባቸው አቁመው ጉለሌ ድረስ በስንት እንደሚወስዳቸው ቢጠይቁት፥

«ሁለት ብር ነበር - እስቲ ይሁን፤ ለታዘለው ልጅ 25 ሳንቲም ቅናሽ ላድርግና ብር ከሰባ አምስት ክፈሉኝ» አለ ባለጋሪው።

«ባይሆን - ብር ካምሳ አታድርግልንም? » አሉ ባልቴትዋ።

«እሺ ይሁን፥ የማታ ገበያ አልገፋም» አለና ባለጋሪው ብር ካምሳ ስንቲሙን ከደመቀች ተቀብሎ፥ ይዞዋቸው ዮሀንስን አለፍ እንዳለ የነፋሱ ኃይል ቀነስ እያለ ሄደ። ነገር ግን ሀይሉ ይቀንስ እንጂ ነፋሱ ጨርሶ ስላልተወ፣ ደመቀች ኩታዋን ከቅንድብዋ ትንሽ ገለል ብታደርግም እንደ ተከናነበች ነበረች። ፓስተር እንስቲትዩት ሲደርሱ አንድ መኮንን ካኪ ተፈሪ ቅድ ሱሪ ታጥቆ ከጉልበት በታች የሚደርስ ነጭ እጀ ጠባብ ለብሶ ካኪ ኮት ደርቦ፥ ደግሞ በዚያ ላይ ነጭ ኩታ ደርቦ፥ ረዥም ዘንግ በግራ እጁ፥ ነጭ ጭራ በቀኙ ይዞ ሰፊ፥ ባርኔጣ አድርጎ፥ ሁለት ጠመንጃ ያነገቱ አሽከሮች ተከትለውት ከወደ ጉለሌ ይመጣል። አንዳንድ ጊዜ ነፋሱ ባርኔጣውን ከራሱ ሊነጥቀው ሲቃጣ፣ የባርኔጣውን ጫፍ፣ ጭራ በያዘበት እጁ ይጨብጣል። ደመቀች ያን መኮንን ስታይ ልክ

መብረቅ እፊትዋ እንደ ወደቀ ደንግጣ፣ ክው ብላ ቀረች። ያን ጊዜ በጦር ቢወጉዋት ደም ባልወጣት! እሜት ፈቃድዋ ካገራቸው እንደ መጡ ጉለሌ ካንዲት ሴት ጋር በደባልነት ሲኖሩ የደረሰባቸውን፥ ተረት እንጂ እውን የማይመስል፥ ረዥም ወሬ ይዘው ለስዋም ለባለጋሪውም እያወሩ ያስቁዋቸው ነበር።

«እሱ ነውኮ፥ እሱ ነው! » አለች ደመቀች አቁዋርጣ።

«ምኑ? » አሉ ባልቴትዋ። ነፋሱ የተከናነቡትን ቀዳዳ ነጠላ ከራሳቸው ላይ «ካልገፈፍሁ» ብሎ፣ ከሱ ጋር እዬተጣሉ፥ ወደስዋ መለስ ብለው አላዩዋትም። ደመቀች ለጠዬቁዋት በመመለስ ፈንታ ወደ ጎን በጋሪው መደገፊያ ትከሻዋን አስደግፋ እንደ ተቀመጠች ዝም አለች። ባልቴትዋም ወሬያቸውን ቀጠሉ። ነገር ግን ጋሪ ነጂው ይሰማቸው እንደሆነ እንጂ፣ እስዋ ሰውነትዋ ሁሉ ደንዝዞ አትሰማም አታይም ነበር። እንዲያ ሁለመናዋ እንደ ደነዘዘ ትንሽ ከሄዱ በሁዋላ፣ አእምሮዋ ከጠፋበት ትንሽ በትንሽ እየተመለሰ ሲሄድ ልብዋ ፈጥኖ እዬመታ ሰውነትዋ ሁሉ በላብ ተነክሮ አገኘች። ከዚያ እንደ ምንም ቀና ብላ መኮንኑን ወዳዬችበት፥ ወደ ጋሪው ፊትም፥ ወደ ሁዋላም ብትመለከት የለም፤ ርቆ ሄድዋል።

«የኔን የማያልቅ ጉድ ለማውራት የመጣሁ ይመስል ወሬዬን ሳደቅ ቤቱን አልፈነው እንዳንሄድ። ጉለሌን ልንጨርስ ምንም አልቀርንኮ» አሉ እሜት ፈቃድዋ፥ ወደ ደመቀች ዞወር ብለው።

«ባጠገቡ እንደዚህ ያለ፥ «የነዳጅ መቅጃ» የሚሉት አለ። እስቲ እዚህ - «የወይዘሮ አልጣሽ ጠጅ ቤት ብለን እንጠይቅ አለች ደመቀች፥ እዚያ ባጠገባቸው ወዳለ የቤንዚን ማደያ ባገጭዋ እያመለከተች። እሜት ፈቃድዋ የደመቀችን አይኖች መደፍረስ የፊትዋን መለወጥ ሲያዩ እንደ መደንገጥ ብለው፥

«ምነ ምን ሆንሽ? » አሉ።

«ምንም አደል፤ ትንሽ አሞኝ ነው» አለች ደመቀች።

«አሁን ነው ያመመኝ፤ አሁን ይተወኛል»።

«አይኔ በፈሰሰ! ወትሮም እንዲህ ድንገት ያምሻል? »

«አዎ፤ አንዳንድ ጊዜ ያመኛል» አለች፥ ውሸትዋን።

የወይዘሮ አልጣሽ ጠጅ ቤት፣ ከቤንዚን ማደያው ትንሽ ወረድ ብሎ መሆኑን እዚያ ከቆሙት አንዱ ስላመለከታቸውና፣ ወደዚያ የሚወስደው መንገድ ጠጠር የለበሰ አይሁን እንጂ መኪናም፥ ጋሪም እንደ ልብ ስለሚያስኬድ፥ ባለጋሪው ያለ ምንም ችግር፥ ሰተት አድርጎ እስከዚያው አደረሳቸው።

ደመቀች ከጋሪ ስትወርድ በውጭ የነበሩት የወይዘሮ አልጣሽ ሰዎች ሲያዩ፥ ከሞት አገር ተመልሳ እንደ መጣች፣ ሁሉም ወደስዋ እዬሮጡ ሄዱና ከበው፣ «ወዴት ጠፋሽ? ምን ሆንሽ? ደህና ነሽ? » እያሉ ይንጫጩ ጀመር። ወዲያው አንድዋ ሄዳ ላቶ መላኩ - ደክሞት አልጋው ላይ በተጋደመበት - ስትነግርው ከደስታ ብዛት የተነሳ ካልጋው እንዴት ዘሎ እንደ ወረደ ሳይታወቀው፥ እዬሮጠ ወጥቶ አንድ ቃል ሳይናገር፥ ደመቀችንም ልጅዋንም እያገላበጠ ከሳመ በሁዋላ አይኖቹን ወደ ሰማይ አቅንቶ እጆችኑ እያርገበገበ፥ «ተመስገን አምላኬ፥ ተመስገን የናታን አምላክ፥ ከተፈርዶ ያዳንሽኝ! » እያለ ሲያመሰግን ቆይቶ፥

«ለመሆኑ ምን ሆነሽ ነው? ወዴት ነው የጠፋሽ? » አለ ወደ ደመቀች መለስ ብሎ።

«የሰፈሩ ስምና መንገዱ ጠፍቶኝ ነው።»

«እናአ ወዴት አደርሽ? »

«እማዬን እመንገድ አገኘሁዋቸውና የማድርባት ቤተክስያን እንዲያሳዩኝ ብለምናቸው፣ ‹እኔ ቤት እደሪ› ብለው አሳደሩኝ» አለች፥ ወደ እመት ፈቃድዋ እያመለከተች።

«እግዚሀር ይስጥዎ እናቴ፤ ትልቅ ስራ ነው የሰሩት» አለ አቶ መላኩ፥ ወደ እመት ፈቃድዋ ዘወር ብሎ።

«አየ ማሳደር አያ! ማሳደር እንዲህ ነው? ‹ቤተክሲያን ሄዳ ከሙቶች ጋር መቃብር ቤት ከምታድር ባዶም ቢሆን ቤት ይሻልላ› ብዬ ወሰድሁዋት እንጂ ምን አደረግሁላት? የራዋን ገንዘብ አውጥታ ለራስዋ ብቻ ሳይሆን ለኔ ጭምር ራት አብልታ ስላደረች - ደግሞ እኔ ልመሰገን ነው? » አሉ እመት ፈቃድዋ።

«ኧረ ትናንት ራታችነንም፥ ዛሬ ምሳችነንም እሳቸው ናቸው ያበሉን» አለች ደመቀች፥ ባልቴትዋ እንደ ጨዋዎች ሁሉ ውለታቸውን ዝቅ አድርገው ለማሳዬት ስለ ሞከሩ፣ ለሰሚ እወንት እንዳይመስል።

«ያም ሆነ ይህ፥ ‹የግዜር እንግዳ› ተብሎ፥ በማያውቁት ቤት ገብቶ ማደር ድሮ ቀረ። ዛሬ ባዲስ አበባ የማያውቀውን ሰው ከመንገድ ወስዶ እቤቱ የሚያሳድር ብዙ ስለማይገኝ፥ እስዎ ያደረጉት በጣም የሚያስመሰግንዎ ነው፥ እናቴ» አለና አቶ መላኩ፥ እሳቸውንም፥ ባለጋሪውንም ጠጅ እንዲጋበዙለት ለምኖ፥ ወይዘሮ አልጣሽ ጠጅ ከሚነግዱበት ውጪ፥ እበረንዳው ላይ ‹በቃን› እስኪሉ አጠጣቸው። ከዚያ እመት ፈቃድዋን ወደ ጎን ወስዶ፥

«ምስጋናየን በቃል ብቻ ከምገልጽ ብዬ ነው እንጂ ‹ለስዎ የሚሆን ነው› ብዬ አይደለምና እባክዎ ‹ደፈርኸኝ› አይበሉ» ብሎ አስር ብር አጥፎ ሊሰጣቸው እጁን ሲዘረጋ፥

«ኧረ ኧረ በስማም! ምን ሊያደርግልኝ? እባክዎ ይተዉኝ» አሉ እመት ፈቃድዋ ደንግጠው፥ ያቶ፥ መላኩን አስር ብር የያዘ እጅ ወደሱ መልሰው እዬገፉ። ድንጋጤያቸው የተነሳ የተናገሩትም ያደረጉትም አልታወቃቸውም።

«እባክዎ አያሳፍሩኝ፤ ዛሬ ስላልተመቸኝ ነው እንጂ፣ በተመቸኝ ቀን ቢሆን ኖሮኮ በዚህ ባልደፈርሁዎ ነበር! » ብሎ አቶ መላኩ ገንዘቡን በግድ እጃቸው ውስጥ ሲያደርግላቸው አፍረው አንገታቸውን እንደ ደፉ እያመሰገኑ ተቀበሉ።

ደመቀች መኮንኑን በመንገድ ስታይ አእምሮዋን እክታጣ ከደንገጠች በሁዋላ እንኩዋ ድንጋጤው ቀስ እያለ ቢያልፍና ሰውነትዋን ብታውቅ ፍራት እንደ ብርቱ ብርድ ከልብዋ አልወጣ ብሎ እያንቀጠቀጣት፣ እክፍልዋ ገብታ ትጨነቅ ነበር። ያ ሰው ያ መኮንን እንደ ጣረሞት የምትፈራውና የምትጠላው፥ አገርዋን አስጥሎ ያሰደዳት ባልዋ ታምራት ተገኘ ነበር! ቀድሞዋት ይሁን ተከትሎዋት መጥቶ እዚያ አገኘችው! «ዛሬ ወይም ነገ፥ የለዚያም ሰሞኑኡን እዚህ መሆኔን ያለ ጥርጥር ስለሚሰማ እጄን አንጠልጥሎ ይወስደኛል! እንግዲህ ወዴታባቴ ልድረስ? » እያለችና በልብዋ ከዚያ ክፉ ጣረሞት ሸሽታ የምትሸሽግበት አጥታ ስትጨነቅ እመት ፈቃድዋ ካቶ መላኩ ተሰናብተው እስዋ ያለችበትን ክፍል ጠይቀው ገቡ።

«እጅ ለምለምዋ ገደ መልካምዋ ልጄ» አሉ፥ ደመቀች በጥልቅ አሳብ ተውጣ እንደ ተቀመጠች። «እጅሽ ለምለም ሆኖ ገድሽ አምሮ እይው አሁን ደግሞ፥ አንቺን ያመጡሽ ሰው ይሆን ሰጡኝ» አሉ አቶ መላኩ የሰጣቸውን አሰር ብር ለደመቀች እያሳዩ «መቸም» አሉ፥ ቀጥለው። «መቸም እግዚአብሄር ሲጣላም ይሁን ሲታረቅ ሰበብ ፈልጎ ነውና፥ ሊታረቀኝ ስለ ፈለገ፥ መከራዬን ቆጥሮ «በቃሽ» ሊለኝ ሰለ ፈለገ ነው መሰለኝ - ትናንት አንቺን መላከተኛው አድርጎ የላከልኝ! አሁን አንቺ የሰጠሽኝን ብር ልመልስልሽ ካሉ በሁዋል «የለም የለም! አልመልስልሽም» አሉ ድንገት ሀሳብ በአእምሮዋቸው ብልጭ ብሎላቸው። «የለም አልመልስልሽም። ጥሩ ገድ ሆኖ ይህን ያመጣልኝ ያንቺ ብር ስለ ሆነ፥ ምናልባትም ተዝገቶ ለኖረው መልካም እድሌ መከፈቻ እንዲሆን አምላኬ ባንቺ እጅ የላከልኝ ሊሆን ስለሚችል፥ እሱን አለመልስልሽም፤ እሱን አልነካው፤ እንደ ታቦት ሸፍኜ፣ ተጠንቅቄ ነው የምጠብቀው። ላንቺ የምሰጥሽ ጠላ ሽጬ ከማገኘው ነው። እንግዲህ ለጠላ የሚያስፈልገኝን በዚህ ሳምንት አሰናድቼ በሚመጣው ሳምንት ድፍድፌን በጋን እደፈድፍና፥ በሶስተኛው ሳምንት ቢያንስ ቢያንስ በሰላሳ ብር አጣራዋለሁ፤ የሰላሳ ብር ጌታ እሆናለሁ! እስከዚያ ስራ ካልያዝሽ፥ እንደተነጋገርነው ባንድ ወር ውስጥ መጥተሽ ጠይቂኝ። እስካንድ ወር ድረስ ቤት ሳልለውጥ እጠብቅሻለሁ። ባንድ ወር ውስጥ ካልመጣሽ ግን፣ ስራ እንደ ገባሽ አምኘ ቤት እለውጣለሁ። ከዚያ - » በላዬ ላይ ይወድቅ አይወድቅ› እያልሁ ከምፈራው ቤት እወጣለሁ! ልብ አድርጊ የጭዋ ልጅ ቃል፥ የመሀላ ያክል ነውና የሰጠሽኝን ቃል እንዳትረሺ! » ብለው እስዋንም ልጅዋንም፣ ስመቸዋቸው ሄዱ። እመት ፈቃድዋ ያን ያክል ሲለፈልፉ ድምጻቸውን እንጂ ምን እንደ ተናገሩ የሰማች አትመስልም፤ ፈዛ ነበር።

አቶ መላኩ፤ ትናንት ማታውን አመሻሽ ላይ፥ ከዋለበት እንደ ገባ፥ ደመቀች እዚያው በቅርቡ፣ ሥራተኛ መቅጠር የሚፈልጉ ሰዎች ብታገኝ፥ ተጠያይቃ እንድትመለስ ነግረዋት ትዋት እንደ ወጣች፣ አለመመለስዋን ወይዘሮ አልጣሽ ሲነግሩት ልክ የወለዳት ልጅ «ጠፋች» ያሉትን ያክል ደንግጦ የሚናገረውም የሚያደርገውም ቅጡ ጠፍቶት ዝም ብሎ ቆየና -

«እስቲ - አገሩን ይሁን ሰዉን እንደማታውቀው እያወቅሽ፣ እንዴት ‹ሂጂ ስራ ፈልጊ› ብለሽ ትሰጃታለሽ? » አለ።

«እኔ እዚህ በእርቡ ተጠያያኸሽ ተመለሺ» አልኩዋት እንጂ «ርኸሽ ሂጂ» አላልኩዋት። ወዲያውስ እንዲህ በተላኸችበት ጠፍታ የምትኸር ተሆነች ‹ማን

ይኧጥርልኛል› ብለህ ኖሮዋል ያመጣሀት? አዲስ አበባ ‹ታልጋ ወርደሽ አፈር፥ ከቤት ወጥተሽ አፄር አይንህሽ› የሚል ገረድ ኧጣሪ የሚገኝ መስሎህ ኖሮዋል? እኸ - ኸ - ኸም! » አሉ ወይዘሮ አልጣሽ፥ በገዛ ቀልዳቸው ያሽሙር ሳቅ እንደ መሳቅ ብለው።

«እባክሽ፥ ይህን የማይረባ ቀልድሽን ተይና፥ ይልቅ አሁን ምን ማድረግ እንደሚሻል ንገሪኝ» አለ አቶ መላኩ በስጨት ብሎ።

«እስዋስ ምንም አትሆን። ራዲዮ ስለማትሰማ ላንተ አዲስ ሆነብህ እንጂ በዬኧኑ ራዲዮ የሚለፈልፈው፤ ተቤታቸው ስለ ጠፉና በፖሊስ ጣቢያ ስለሚገኙ ሰዎች ስለሆነ፣ እስዋም - አሁን አንዱ ፖሊስ ጣቢያ ሳትሆን አትኧርምና በዬፖሊስ ጣቢያ እዬዞርክ መጠዬእ ነው። እንዲያው ለነገሩ ግን አንተ እንዲህ ያለችዋን - ወትታ መግባት የማታእ ደንአሮ ‹ግርድና አስኧጥራለሁ› ብለህ አደራ ተኧብለህ መምጣትህ የምታስገርም ነህ! »

«እኔማ - ስራ በዝቶብኝ ‹ከዛሬ ነገ› ስል አልነገርኩሽም እንጂ ‹አንቺ አሻሻጭ አድርገሽ ብትቀጥሪያት ትጠቅምሻለች፣ ሁኔታዋን ካዬሽ በሁዋላ የማትጠቅምሽ መስላ ከታዬችሽም፣ እስከዚያ አገሩን ስለምትለምደው እስዋ፣ ራስዋ ስራ ፈልጋ ትይዛለች› ብዬ አስቤ ነበር።

«እሱ አንተ ሳትነግረኝ አስቤው፥ የማያዋጣኝ ስለሆነ የተውኩት ነው።»

«ለመሆኑ ምኑ ነው የሚያዋጣሽ? ልጅቱ ከመልኩዋ ማማር ሌላ ልጅ ናት።»

«አይ ኢዲያ እቴ! እናንተ ወንዶችች ‹ልጅ ልጅ› ስትሉ፤ ልጅነት የማናኧው ታስመስሉታላችሁ! አልፈነው ትተነው የመጣነው አይደለም? ሌላ ነው? ለሱ እኔ ደንታ የለኝም ልጅ ብትሆን፥ ባትሆን ሁሉም ለራስዋ ነው። ይልእስ ‹ምኑ ነው የሚያዋጣሽ› ላልከው አንድ ሰው ኧጥሬ ትጠእመኝ ሳላእ ሁለት ራስዋን መኧነስ› የሚሉት፣ ለማደግ ብዙ ሙብላት የሚያስፈልገው ስለሆነ እንዲያው ‹ከስዋ የበለጠ ምግብ አምጡ› የሚል ነው። እዚህ ከመጣ ጀምሮ ለሱ ምግብ የተደረገውን የወጪ ሂሳብ ለብቻው ስናኧርብልህ ታየዋለህ።»

«እሺ ተይው ግዴለም» አለ አቶ መላኩ ማዘኑ ከፊቱ በግልጽ እዬታዬ።

ደመቀች አሻሻጭ ሆና እንድትቀጠር ታስቦ የነበረው አሳብ በስዋ ፊት አለመነሳቱ ነው እንጂ፣ እስዋ ብትሰማውና አሻሻጭነት ምን መሆኑን ብታውቅ ኖሮ የወንድና የሴት ግንኙነት እስዋ ከምታውቀው ከዚያ አገርዋን አስጥሎ ካሳደዳት የተለዬ መስሎ የማይታያት በመሆኑ ወይዘሮ አልጣሽ ለመቅጠር ፈቃደኛ ቢሆኑም እሱን ‹ራስ› ብላ አትቀበለውም ነበር። አሻሻጭ ሆኖ በመቀጠር፥ አባትዋ ወደ ታምራት ተገኘ እንድትመለስ ሲያባብሉዋት ሁልጊዜ እንደምትለው ‹ዱር ለዱር ስትሄድ ጅብ ቢበላት፥ ወይም ገደል ገብታ ብትሞት› ብትመርጥ ስለ ነበር፥ የወይዘሮ አልጣሽና ያቶ መላኩ መጨቃጨቅ ‹የሚሸጠው ሳይኖር በዋጋ ክርክር› እንደሚሉት ያለ ነበር።

አቶ መላኩ፥ ከወይዘሮ አልጣሽ ዘንድ ወጥቶ በዬፖሊስ ጣቢያው እዬዞረ ሰፈራቸው የጠፉቸው ሰዎች እንዳሉ ወሬ ሲጠይቅና ደመቀች እንድትፈለግለት ስምዋንና መልክዋን፥ ሌላ ሌላ መለያ ምልክትዋንም ሁሉ በዝርዝር ሲያስጽፍ ከሌሊቱ እስከ አምስት ሰአት አምሽቶ ከተመለሰ በሁዋላ፥ ያነለትም ትናንት ማታውን ሁኔታዋን ባስጻፈውባቸው ጣቢያዎች ወሬ ሲጠይቅ፣ ባላስጻፈባቸው ሲያስጽፍና ሞኝ ይመስል በዬበረንዳው እዬዞረ ‹ወንድ ልጅ ያዘለች መልከ ቀና ልጅ አያችሁልኝ ወይ?› እያለ ሲጠይቅ ውሎ እንደ ተመለሰ፣ አህል ቀምሶ ለማረፍ አልጋው ላይ ገደም ከማለቱ ነበር የደመቀችን መመለስ የሰማ። የመገኘትዋን የምሥራች ሲሰማ የነበረው ደስታ ትልቅነት፣ የመጥፋትዋን መርዶ የሰማ እለት ከነበረው ድንጋጤ ትልቅነት አያንስም። ከዚያ በሁዋላ ወዳገሩ ሊሄድበት የነበረውን ቀን አስተላልፎ አንድ ሳምንት ሙሉ ልክ የራሱን ስራ ሲከታተል እንደሚያደርገው ጥዋት ወጥቶ ‹ገረድ ይቀጥራል ወይም ያስቀጥርሉ› የተባሉትን ሰዎች ሲፈልግም ሲያነጋግርም እዬዋለ ሲገባ ሰነበተ። አንድ ቀን ወዳገሩ ከመሄድ የዘገዬበት ምክንያት ለደመቀች ስራ ለመፈለግ ለጠበቃው ላቶ በላይነህ ዘውዴ ሲነግረውና ሁኔታዋን ሁሉ ዘርዝሮ የሚቀጥራት ሰው እሱም በበኩሉ እንዲፈልግላት አጥብቆ ሲለምነው፣

«ይህን ያክል የምታሳስብዎ ልጅ ከሆነች ለምን ቀደም ብለው አልነገሩኝ? አንድ ደንበኛዬ የሆኑ ትልቅ ሰው ለሚስታቸው፣ የምትላላክ ልጅ እንድፈልግላቸው ‹አደራ› ብለውኝ ነበር። ብቻ ከነገሩኝ ውሎ አድሮዋልና ምናልባት ቀጥረው ይሆናል። ነገር ግን ‹ልጅ አላት› ስላሉ ልጅ ያላት ገረድ - አይፈልጉ ይሆናል። እስቲ ለማናቸውም ልጠይቃቸውና መልሳቸውን ባሉበት ቤት ዛሬ ማታ ወይም ነገ ጥዋት በስልክ ልንገርዎ» አለ አቶ በላይነህ ዘውዱ።

በዚያ ሳምንት፥ ደመቀች እያንዳንዱ ቀንና ሌሊት ባልዋ አንቆ የሚወስድበት እዬመሰላት ፈርታ፥ ብትተኛ እንቅልፍ አይወዳት፤ ሆድዋን አዬራበው እህል አይዋጥላት፤ ራቡና እንቅልፍ ማጣቱ፣ ፍራቱ ባንድ ላይ ሆነው፥ ስጋዋን በልተው ደምዋን ጠጥተው እንደ ጨረሱት ሁሉ ከስታ ደብዝዛ፥ የደመቀች ጥላ እንጂ ደመቀችን አትመስልም ነበር!

ደመቀች ከጠፋችበት በተመለሰች ሳምንት፥ አቶ መላኩ ጠበቃውን ባነጋገረበት ማግስት፥ እጥዋቱ ላይ ቁርሱን አድርጎ፣ እንደ መሰንበቻው ስራ እንዲፈልጉ ‹አደራ› ያላቸው አግኝተውላት እንደሆነ እዬዞረ ለመጠዬቅ ሊወጣ ሲል «በስልክ ትፈለጋለህ» አሉት። ፈላጊው፣ ጠበቃው አቶ በላይነህ ነበር።

«አሎ ጤና ይስጥልኝ። ለዚያ - አደራ ‹አደራ› ላልሁዎ ጉዳይ ወደ ርስዎ ልመጣ ስነሳ ነውኮ - ‹ስልክ ይፈልግሀል› ያሉኝ» አቶ መላኩ ፈላጊው አቶ በላይነህ መሆኑን ሲሰማ።

«እኔም ለሱ ነው የደወልሁልዎ። ዛሬ ፍርድ ቤት ቀጠሮ ስላለብኝ፥ ነገ በጥዋት ልጅቱን እኔ ጽህፈት ቤት ድረስ ይዘዋት ይምጡና ወስጄ አገኛታለሁ» አለ አቶ በላይነህ።

«ቀጣሪ ተገኘ? » አለ መላኩ ከደስታው ብዛት የተነሳ ስልክ ባለበት ክፍል የነበሩት ሁሉ እንደ ነውረኛ ዘወር እያሉ እስኪያፈጡበት በጣም ጮሆ።

«አዎ፤ የስዎን መቸገር አይቼ እኒያን - ‹ደንበኛዬ ናቸው ያልሁዎትን ታላቅ ሰው በጣም አጥብቄ ስለ ለመንሁዋቸው ‹ምንም እንኩዋ ልጅ ያላት ገረድ ባልፈልግ ስራዋና አመልዋ ካማረ፥ ላንተ ስል እቀጥራታለሁ› ብለውኛል።»

«ትልቅ ውለታ ነው የዋሉልኝ በውነት - በጣም ነው ደስ ያሰኙኝ አቶ፥ በላይነህ። እግዚሀር ደስ ያሰኝዎ፥ ውለታዎን ለመክፈል ያብቃኝ» ብሎ አቶ መላኩ፥ አቶ በላይነህም፥ ራሱንም መርቆ የምሥራቹን ለመንገርና የስዋንም የልጅዋንም ልብስ አጥባ፥ ሰውነትዋን አሰማምራ ለነገው እንድትሰናዳ ለማስጠንቀቅ ደመቀች ወዳለችበት ሄደ።

ደመቀች የምሥራቹን ስትሰማ፥ ደብዝዞ የነበረ ፊትዋ እንደ ንጋት ሰማይ በደስታ ወገግ አለ። ስራ ከማግኘትዋ ይልቅ ደስ ያሰኛት፥ ልብዋን ተጭኖት ከሰነበተው ከባድ

ሸክም ነጻ የሆነች መስሎ የተሰማት ከዚያ ባልዋ ካዬችበት ሰፈር ስትርቅ ካይኑም የምትርቅ ስለ መሰላት ነው።

በማግሥቱ፥ ልጅዋን የታጠበ ልብሱን አልብሳ፥ አሮጌውንና ቁንጮውን በሚዶ ነቃቅሳ አሳምራ፥ እስዋም ተንጨብሮሮ የሰነበተ ጠጉርዋን ታጥባ አባብሳና ነቃቅሳ የታጠበ ልብስዋን ለብሳ እስከዚያ ቀን ድረስ ከነበረችው - ከመክሳትዋ በቀር - አምራ አቶ መላኩ ወዳቶ በላይነህ ጽህፈት ቤት ይዞዋት ሄደ። ከዚያ ሁለቱ ወደሚቀጥሩዋት ሰው ወደ ደጃዝማች አሰፋ ተጫኔ ቤት ወስደው ደጃዝማች «ገና ሰው ወደሚቀበሉበት ክፍል አልገቡም» ስለ ተባለና አቶ በላይነህ ወደ ስራው ስለ ቸኮለ ካዛዡ ጋር አገናኝተዋት ተመለሱ። አቶ መላኩ ደመቀችን ሲሰናበታት አሰር ብር እጥፍ አድርጎ በጅዋ ውስጥ አስቀመጠና እስዋንም ልጅዋንም ስሞ፥

«አይዞሽ እንግዲህ በርቺ። ምናልባት ሳይመቸኝ ቀርቶ እንደገና ያልተገናኘን እንደሆነ እኒህን ስራ ያገኙልሽን ወዳጄን እንዲጠይቁሽ ‹አደራ› እላቸዋለሁና፤ የሚቸግርሽ ነገር ሲኖር ለሳቸው ንገሪያቸው፤ እኔም ስመጣ እጠይቅሻለሁ» ብሎዋት ሄደ። ደጃዝማች ወደ እንግዳ ቤት እንደገቡ፥ አዛዡ፣ አቶ በላይነህ የምትቀጠር ልጅ ማምጣቱን ሲነግሩዋቸው፥

«እ፥ አመጣት? እስቲ ጥራት» አሉ ደጃዝማች አሰፋ። ደመቀች ገብታ ልጅዋን እንዳዘለች፥ የራስ ጠጉርዋን መሬት እስኪጠርግ ለጥ ብላ እጅ ስትነሳ፥ በጣም ልጅ መሆንዋን አይተው፥ ‹እቀጥራታለሁ› ብለው ቃል በመስጠታቸው እንደ መጸጸት ቢሉም፥ እጅ አነሳስዋ ደስ ስላሰኛቸው ፈገግ ብለው ‹ልጅ አላት› ብሎኛል። ልጁ ስንት አመቱ ነው? » አሉ፥ እጅ ነስታ ቀና ስትል።

«ሁለት ነው» አለች ደመቀች።

«አንቺስ ስንት አመትሽ ነው? »

«የኔይ? የኔማ - አስራ አራት ወይም - አስራ አስምት ነው መሰለኝ፤ በጣም አላውቀውም»

«ታዲያ - ባስራ ሁለት፥ ወይም ባስራ ሶስት፥ አመትሽ ነው የወለድሽው ማለትኮ ነው፤ ይገርማል! » አሉ ደጃዝማች፥ እስዋንም፥ ልጅዋንም እያለዋወጡ እያዩ። ደመቀች አንገትዋን እንደ ደፋች የገዛ እግርዋን አውራ ጣቶች እዬተመለከተች ዝም አለች።

«ታዲያኮ - አንቺ ራስሽ ልጅ ነሽ፤ በዚያ ላይ ልጅ ይዘሻል። ባንቺ አቅም ልጅ መጠበቅና ስራ መስራት ባንድ ላይ ይሆንብሻል? ስራው እንኩዋ ይህ ያክል ከባድ አይደለም፤ ባለቤትዋን ልብስ ማልበስና - እስዋን መርዳት፥ እስዋን መላላክ ነው። ነገር ግን ይህ ሁሉ ጽዳት ስለሚያስፈልገው የሚያስቸግርሽ ይመስለኛል» አሉ፥ ካንድ ወገን ለስራው የማትሆን ስለ መሰላቸው ከሌላ ወገን አሳዝናቸው መግፋቱን ስለ ጠሉ እያመነቱ።

«ልጁ ባስቀመጥሁበት ይቀመጣል፤ አያስቸግረኝም» አለች ደመቀች የሚያማምሩና የሚያሳዝኑ ጣምራ አይኖችዋን እመሬት ከተተከሉበት አንስታ ወደ ደጃዝማች ወርወር አደረገችና።

«እንጃ፤ እንዲያው ልሞክረውና ሲያቅተኝ ልተወው» ትይ እንደሆነ ነው እንጂ የሚሆንልሽ እንኩዋ - አይመስለኝም።»

«አዎ፤ ልሞክረውና ያቃተኝ እንደሁማ ይቅርብኝ እንጂ! »

«እሺ ሞክሪው ስምሽ ማነው? » አሉ ባነጋገርዋ መሳቅ፥ ቢያምራችውም፥ እንዳታፍር ሳቃቸውን ገትተው።

«ደመቀች ነው፤ ደመቀች ጸሀይ።»

«በይ እስቲ - እናይሻለን። ውሰድና ከወይዘሮ ጽጌ አገናኛት» አሉ ደመቀችን በፈገግታ ካሰናበቱ በሁዋላ ወደ አዛዥቸው ዘወር ብለው።

## ምዕራፍ ሰባት

# የጎጃምዋ ገልቱ

ደመቀች እደጃዝማች አሰፋ ተጫኔ ቤት፥ የሚስታቸው የወይዘሮ ጽጌ፥ የውስጥ አሽከር ሆና ስትቀጠር ገና ለጋ ቡቃያ ነበረች። በካልም ሆነ በመንፈስ፤ ውብና ብልህ የምትሆን ለመሆንዋ ያው፣ ብቃያዋ ውጥንዋ የሚያመለክት ቢሆንም፥ ገና አድጋ

ስላላበቃች ሰው ልጆች ሰውነትና ስሜት ወይም ጠቃላላ ሁነታ፥ ካሸር ሁሉ የራቀ ፍጹም ገራገር ነበር እንጂ፥ ላቅመ ሄዋን እንደ ደረሱ ወይዛዝር ሁነታ ኅበዝዝትን «ኑ ግጠሙኝ! » እያለ ለፍልሚያ የሚጠራ፥ ኅበዛዝትን ለፍልሚያ ለመጋበዝ ያክል የፋፋና የሚደነፉ አልነበረም። ስለዚህ የምታስበውን ሆነ የሚሰማትን በፍጹም ገርነትና በጎጃም የባላገር አነጋገር ስትናገር፥ በጣም ደእስ ታሰኝና ታስቅ ስለ ነበረ፥ ባጭር ጊዜ ውስጥ የደጃዝማች አሰፋ ቤተሰብ ሁሉ - ሴቱም ወንዱም - የሚወዳት፣ የሁሉም ባለሙዋል ሆነች። ጊዜ እያለፈ በሄደ መጠን የቤቱንና ያካባቢውን ሰው አነጋገር እዬለመደች የስዋን እዬረሳች እስከትሄድ ድረስ፥ በምትናገረው ለመሳቅ ሁሉም እስዋን እዬጎተጎቱ ማናገር ይወዱ ነበር።

«ላሸከር ግንባራቸውን ፈተው ጥርሳቸውን ገልጠው አያውቁም» የሚባሉት፥ የቤቱ እመቤት፥ ወይዘሮ ጽጌ እንኩዋ፥ የደመቀች አነጋገር ደስ ስለሚያሰኛቸውና ሰለሚያጫውታቸው በወረት፥ ከስዋ ጋር እዬተጫወቱና እዬቀለዱ መሳቅ ጀምረው ነበር። ወረትዋ እስኪያልፍ ድረስ፥ ባዲስነትዋ በስምዋ ጠርተዋት አያውቁም። «የኔ ገልቱ ገልቱየ» ነበር የሚሉዋት። እስዋም በባለሙዋልነትዋ ተመክታ ይሁን ወይም ጠባያቸውን ገና ስላላወቀች ቀልድና ጭዋታ የሚወዱ መስሎዋት፥ በፊታቸው ተዝናንታ፥ እድነ ልብዋ ትቀልድና ትጫወት ነበር።

«ገልቱይተ ቁርስሽን በላሽ? » ይላሉ ወይዘሮ ጽጌ፥ መሳቅ ሲያምራቸው።

«አለበልቸም» ትላለች ደመቀች።

«ልጅሽስ፥ በላ? »

«አልበልቶም» ስትል ወይዘሮ ጽጌ የኮረኮሩዋቸው ያክል ይስቃሉ።

«እሮግ! እኔን መቀለጃ ማድረጋቸው ነው እያ፥ በምናገረው ሁላ የሚቀልዱብኝ? እንግዲህ አልናገር! » ትላለች እስዋም ወይዘሮ ጽጌ ባነጋገርዋ ሲስቁ፥ የተቆጣች ለመምሰል በውሸት ግንባርዋን ኩስትር አድርጋ።

«ወይ አህዮ! ደሞ - እኛ ስንስቅልሽ ደስ መሰኘቱ ቀርቶ ሊከፋሽ ነው? »

«እሮግ! ደሞ መቀለጃ ሲሆን ደስ የሚለው ሰው አለይ? »

«እኔኮ አሁን አነጋገርሽ ደስ ስላለኝ ሳቅሁኝ እንጂ አልቀለድሁብሽም።»

«ስናገር ሁላ ‹ገልቱ› እያሉ የሚስቁብኝ ሲቀልዱብኝ አደል! እኛ አገርኮ ገልቱ የሚባሉ ሌላዎች ናቸው» አለች እንደ መሳቅ ብላ።

ይህ ደመቀችን ለወይዘሮ ጽጌና ለቤተሰቡ ባለሙዋል ያደረጋት «ገልቱ አነጋገርዋ» ብዙ ጊዜ አብሮዋት አልቆዩም፤ ባጭር ጊዜ ከንዱዳም ኪዳነ ምህረት ወደ አዲስ አበባ ለብሳው የመጣችውን ልብስ እንኩዋ ሳትለውጥ አነጋገርዋን ባዲስ አበባ አነጋገር ለወጠች። እንኩዋ እቴቴ» በማለት ፈንታ «ጋሼ፥ እትዬ» «እሮግ! አልበልቶም» በማለት ፈንታ «ኧረ! አልበላም» «ሁላ፥ ይባላሉይ? » በማለት ፈንታ «ሁሉ ይባላሉ? » ማለት ለመደች። ወዲያው፣ አነጋገርዋ ስትለውጥ ወይዘሮ ጽጌም ሌላ ደስ የሚያሰኝ ወይም የሚያስቅ ነገር አጡባትና፣ ከስዋ በፊት ከነበሩት ገረዶቻቸው ልዩ መስላ መታየትዋ ቀረና፥ ከስዋ በፊት ለነበሩት ገረዶቻቸው ያሳዩዋቸው የነበረውን በቁጣ፥ የተቆዋጠረ ግንባርና የተሸራመመ ከንፈር ያሳዩዋት ጀመር! «የኔ ገልቱ» እያሉ የማቆላመጡ ከስዋ ጋር እንደ ጉዋደኛዋ ቀልድ «እንኪ - ለንኪ» እየተለዋወጡና እዬተሳሳቁ የመጨዋወቱ የዚህ ሁሉ እድሜ፥ እንደ ሙሽርነት እድሜ ባጭር ተቆረጠ! የዚህ ሁሉ እድሜ ቢጠሩት እንደገና እንደማይመለስ ትዝታው ብቻ ትቶ እንደሚያልፍ የሙሽርነት እድሜ አለፈ!

ደመቀች፣ የወይዘሮ ጽጌን መለወጥ ከፊታቸውም ከጠቅላላ ሁኔታቸውም ከተመለከተችና ክፉ አመለቢስ መሆናቸውን አቤቱ ሰዎች አንዳንዶቹ በምሥጢር አስረድተው እንድትጠነቀቅ ከመከሩት በሁዋላ ልክ እንደ ተመከረችው፥ ካልጠዬቁዋት የማትናገር ለጠዬቁዋት ከመመለስ በቀር አንድ ትርፍ ቃል የማትጨምር ሲያዝዋት ወይም ሲልኩዋት፥ አንገትዋን ደፍታ ስሞታ እሺታዋን፥ በቃል ሳይሆን በእጅ በመንሳት ብቻ የምታሳይ «ስልጡን ገረድ» የሚሉዋት አይነት ሆነች። በማይረባ ምክንያት ወይም ያላንዳች ምክንያት ተቆጥተው ሲሰድቡዋትና ሲረግሙዋት እንኩዋ፥ አንገትዋን ደፍታ ሰምታ አንድ ቃል ሳትተነፍስ እንደ መረቁዋት ሁሉ እጅ ነስታ መሄድ ከተሰጣት ምክር አንዱ ስለሆነ እሱንም ለመደች።

የመቤትዋ አመል አጠናቃ እስክታውቅ ድረስ ትንሽ ቢደናገራትም፥ አመላቸውን ካወቀችና ከሚወዱት ያሰራር ዘዴ ጋር ከተለማመደች በሁዋላ የጠባያቸው፥ ክፋትም ሆነ የስራቸው ብዛት ምንም ያክል አልከበዳትም። ደስ ብሎዋት እዬሰራች ደስ ልታሰኛቸው አጥብቃ ትጥር ጀመር። ይልቁንም ቤታቸው ቀን ከሌት በዘበኞች የሚጠብቅ የታፈረና፥ የተከበረ ስለ ሆነ፥ ከዚያ ግቢ እስካልወጣች ድረስ ባልዋ ታምራት ተገኝ እዚያ ገብቶ ሊወስዳት እንዳማይችል እምነት ስላደረባት፥ ደስታዋ

ፍጹም ሆነ። ይህ ነው አይነተኛው ነገር! የምትወዳቸውን እናትዋንና አገርዋን ትታ የተሰደደች ከታምራት ተገኘ ሽሽታ፥ በታምራታ ተገኘ እጅ እንዳትወድቅ ፈርታ ስለሆነ፥ በሱ እጅ ከመውደቅ የማይሻል ምንም ነገር የለ! በታምራት ተገኘ እጅ ከመውደቅ አንጻር ሲታይ፥ የወይዘሮ ጽጌ ከፉነትም ሆነ የስራቸው ብዛት የቅንጣት ገለባ ያክል የማይከብድ በጣም ቀላል መስሎ ታያት።

የወይዘሮ ጽጌ የውስጥ አሽከር መሆንዋን፤ የጉለብት ድካም ያለበት ቢሆንም ካጥር የማያወጣ መሆኑንና ካጥርም፣ ካልወጣች ባልዋ በምንም መንገድ ሊያገኛት የማይችል መሆኑን ስታስብ ደብረ ማርቆስ የናታችነን መቃብር ቤትና ሁለቱን እመበለቶች አይታኡ ለመመንኮስ የወሰነች እለት የተሰማት ደስታ፥ የተሰማት ነጻነት ተሰማት፥ ልክ እንደዚያነለቱ ሁዋልሁዋልዋላ እዬተከተለ የሚያሳድዳት የታምራት ተገኘ ክፉ መንፈስ ትቶዋት የሸሸ መስሎ ተሰማትና ደስ አላት። «የታቦቱ! እዚህ መሆኔን አያውቅ! ቢያውቅም እዚያው የገዛ ከንፈሩን እዬነከሰ የገዛ ደሙን ይመጣል እንጂ፣ እኔን እንደሁ አያገኘኝ! እዚህ ገብቶ፣ ከዚህ ሁሉ ሰው መሀከል ሊወስደኝ አይችል! » አለች ባልዋን ተናዶ ከንፈሩን እዬነከሰ አቁስሎ፥ የገዛ ደሙን ሲመጥ በልብዋ ስላ፣ ባይነ - ህሊናዋ እዬተመለከተች ብቻዋን እንደ መሳቅ አለችና።

ታምራት ተገኘ እንኩዋንስ ጉለሌ እንዳዬችው ሁለት አሽከሮች አስከትሎ ኤልያስ እንደምታውቀ በብዙ ባለብረት ጀሌ ሰራዊት ታጅቦ ቢመጣ፥ እደጃዝማች አሰፋ ተጫኔ ግቢ ገብቶ ሊወስዳት እንደማይችል እምነትዋ እዬጸና በሄደ መጠን፥ የልብ እርጋታም የመንፈስ ጸጥታም እያገኘች ሄደች። ከዚያ ሁለት አመት እንኩዋ ተካክሎ ሳይሞላት የቀን እረፍትና የሌሊት እንቅልፍ አሳጥቶ የምትበላውና የምትጠጣው እህል ውሀ ሰውነት እንዳይሆናት አድርጎ፥ ያሰቃያት ከነበረው፥ ከባልዋ ፍራት ነጻ ስትሆን በውጥን ይታዩ የነበሩ የሰውነት ክፍሎችዋ ሁሉ ከድሜዋ ቀድመው በያሉበት እዬሞሉ፥ እዬጎሉ እያማሩ፥ እዬዳበሩ፣ ሄዱ። እያበበችና እዬተዋበች ሄደች።

ቁመትዋ በመጠኑ ዘለግ ብሎ አቆቁዋም አሳማሪና «ገረድ መልካም» የሚሉዋት ናት። ፊትዋ እጅግ ሳይረዝም፥ ወይም ሳያጥር በላዩ ካሉት ክፍሎቹ ጋር በጥንቃቄ ተመጣጥኖ፥ ተስማምቶ የተሰራ፥ ውብ ነው። የጥቁር ሀር ነዶ መስሎ በራስዋ ላይ የተረፈረፈ ጠጉርዋ ከጥቁረቱ የተነሳ ያን ውብ ብሩህ ፊትዋን የበለጠ ያደምቀዋል። አስተያየትዋና ፈገግታዋ የስዋ ብቻ የሆኑ፥ ልዩ ናቸው። ያይን ሽፋሎችዋ ያጥቢያ ከዋክብት የመሳሰሉ አይኖችዋን፥ ውብ ከንፈሮችዋ ተካክለው የተሰኩ ነጫጭ ፈርጦች የመሰሉ ጥርሶችዋን በሽር ሳይሆን በማፈር ገልጥ አድርገው እንደ መሸሸ ሲሉ፥

የተመልካችዋን ልብ ሰርቀው ይሄዳሉ። ደረትዋና ዳሌዋ በመጠኑ ኮራ፥ ኮራ፥ ብለው ከያሉበት የግራ ቀኝ መስመሮቻቸውን እያጠበቡ ይሄዳሉ እወገብዋ ላይ «ሽብልል» ብለው ሲዋሀዱ ቅርጽዋ ቅጥዋ የግሩም ግሩም ነው! ጠበብት ተጠንቅቀው የቀረጽዋቸው ጣምራ ሽንኮሮች የመሳሰሉ ባቶችዋ ክብልል ብለው ይወርዱና እንደ ተደፉ ኮልባዎ «ክብልል» ባሉ ተረከዞችዋ ላይ ውብ ሆነው ተዋደው ከሁዋላ፥ ሲያዩዋቸው አይ ማማራቸው! እንዲያው ባጭሩ በቁጥር መልክ፥ ከራስ ጠጉርዋ እስከ እግር ጥፍርዋ በዝርዝርና ሁሉም አንድ ላይ በጥምር፥ ስህ የማይወጣለት፥ የውብ ውብ ናት። በዚያ ላይ ደም ግባቱን ምስህቡን ያደላት ናት።

ደመቀችን ስትቆጣ ለማየት ነው! ካልተቆጣች ምን ጊዜም ቢሆን፥ በዚያ ውብ ፊትዋ፥ የሚታየው ሁሉ ደስታ ብቻ ነው። ካልተቆጣች ምን ጊዜም ቢሆን፥ ያ ውብ ፊትዋ የንጋት ጎህ ወገን እንዳደረገው የበጋ ሰማይ ደስ ብሎት ተመልካቹን ሁሉ ደስ የሚያሰኝ ውብ ልጅ ናት። ስትቆጣ፥ ግን እግዜር አያድርስ! ስትቆጣ፥ ለዛ ጠሩርዋን ወደ ግንባርዋ ተመልሶ ይንጨፈረርና ለስላሳ፥ ውብ ፊትዋ እንዳንገረገቡት ሽንብራ ይጨማተርና፥ ሰውነትዋ ሁሉ እዬተንቀጠቀጠ ጥርሶችዋ እስ በሳቸው ሲፋጩ፥ ውይ ማስፈራትዋ! ያንጊዜ፥ ደስ ብሎዋት ደስ የምታሰኝ፥ ውብ ልጅ መሆንዋ ይቅርና፥ ግልገልዋን የሚቀማ ጠላት እንደ መጣባት አራስ ነብር የምታስፈራ ትሆናለች! ብቻ ደግነቱ ‹እንድፈርሽ› ካላሉዋት እንዲህ በቀላሉ ተናዳ አትቆጣም። እስዋን አናዶ ለማስቆጣት ብዙ መቆስቆስ፥ ብዙ ማጤጢያስ ያስፈልጋል!

## ምዕራፍ ስምንት

# ትዝታና ምኞት

አንድ ቀን፥ ሁለት የደጃዝማች አሰፋ አዛውንት መኩዋንንት ከልፍኙ አጥር ውጪ፥ ባንድ የደረቀ ግንድ ላይ ተቀምጠው ይጫወቱ ነበር። አንዱ፥ ባላምባራስ ተካ ሉሉ፥ ደጃዝማች አገረ - ገዥ በነበሩ ጊዜ በሹመት ላይ ለነበሩ አንዳንድ ሎሌዎቻቸው፥ በየቦታው ካለ ብዙ ርስታቸው ቀንሰው እንደዬማእረጋቸው አከፋፍለው ሲሰጡ፥ ለሳቸውም፥ ገና በልጅነታቸው ከሞግዚታቸው ጋር ሆነው ያሳደጉዋቸው ስለሆኑ፥ «አዳበርጋ» ከሚባል አገር፣ አንድ ሩብ ጋሻ መሬት በርስትነት ሰጥተዋቸው፥ እነዚያ

እዬኖሩ ጌታቸውን አይተው ለመመለስ የመጡ፥ ደርሶ ሂያጅ ናቸው። ሁለተኛዉ፥ ልጅ ክንፌ ይፍሩ፣ በሽምግልና ዘር ቆጥረው የመጡ፥ የደጃዝማች የሩቅ ዘመድ፥ እዚያው ቤት ግብረበላ ሆነው የሚኖሩ ናቸው። ሁለቱ መኩዋንንት እጅግ ከመዋደዳቸውና አብሮ አደግ ከመሆናቸው የተነሳ፣ ባላምባራስ ተካ አዲስ አበባ ቆይተው ሲመለሱ፣ ልጅ ክንፈን አብረዋቸው እንዲሰነብቱ ይዘዋቸው የማይሄዱበት ጊዜ ጥቂት ነበር።

ደመቀች እንደ ልማድዋ፥ ቀሚስዋን አጠር አድርጋ ታጥቃ፥ ባሚዶ ደርቆ የተተኮሰ፥ ነጭ ሽርጥዋን ከፊት ወደ ሁዋላ በጥብጣብ ሸብ አድርጋ፥ እመቤትዋ ቡና እንድታፈላ ልከዋት ከልፍኝ ወደ ማድቤት ለመሄድ ባጠገባቸው ፈገግ ብላ እጅ ነስታቸው ፈጠን ፈጠን እያለች ስታልፍ፥ ከሁዋላዋ የሚያምሩ ባቶችዋንና ተረከዞችዋን፥ ከፍ ብለው፥ የፈጣን እርምጃዋን ቅኝት ተከትለው የሚያረገርጉ ወገብዋንና ዳሌዋን አይኖቻቸውንም፥ አፋቸውንም በሰፊው ከፍተው፥ ማድቤት እስክትገባ ድረስ ሲመለከቱ ቆዩና -

«ወጀው ጉ - ድ! እንዴት እግዜር እጁን ታጥቦ የሰራት ልጅ ነች እባክህ? አሁን - እኛ ስንሽመግል እንዲህ እንዲህ ያሉት ይፈጠሩ? » አሉ ደርሶ ሂያጅ ሽማግሌ ባላምባራስ ተካ።

«ደመቀች? አ - ! በጣም ጥሩ ልጅ ናት፥ መልከዋ ብቻ አይምሰልህ፥ ጠባይዋም ጥሩ ነው። በዚያ ላይ ስልጡን ናት። እጅግ ቢበዛ ከሁለትና ከሶስት ወር የበለጠ የውስጥ አሽከር ማቆዬት ለማይችሉት ለመይቴ እንኩዋ ተስማምታ ይኸው እንግዲህ ሶስት አመት ሊሆናት ነው መሰለኝ - መቀመጥዋ ለስልጡንነትዋና ጠባየ መልካም ለመሆንዋ አይነተኛ ምስክር አደለም? » አሉ እዚያው ቤት ነዋሪው ሽማግሌ።

«አሙዋልቶ የሰጣት ናት በለኛ! » አሉና ደርሶ ሂያጅ ሽማግሌ፥ የደመቀችን የሚያረገርጉ ወገብና ዳሌ ባሳባቸው መልሰው አምጥተው ባይነ ህሊናቸው ሲመለከቱ ቆይተው «ምነው እድሜን ስቦ ወደ ሁዋላ መመለስ የሚቻል በሆነ! » አሉ፥ የቅርታ ፈገግታ በፊታቸው ሲጫወት እዬታዬ፥ ወደ ጉዋደኛቸው መለስ ብለው።

«ምን ልታደርግበት? » አሉ ጉዋደኛቸው።

«አየ -! እድሜን ወደ ሁዋላ ስቦ መልሶ፤ ላንድ ሌሊት እንኩዋ ወጣት መሆን የሚቻል ቢሆንማ እንደይች ካለች ልጅ ጋር በፍቅር ሲሰከሩ፥ ሲጨፍሩ ማደር - በቁም መንግስተ ሰማያት መግባት ነበር! በውነት ‹ጽድቅ በምድር› ማለት እሱ ነበር! »

«አሆ - ! አንተ እውነትም ገና አላረጀህ! እዚያ ባላገር - ከምታረባው ፍዬል ጥቦትህን እያማረጥህ እዬበላህና ትኩስ ወተት እዬጠጣህ የሴት ፍላጐትህ፥ ገና አላለፈም መሰለኝ። እኛ እንዲህ ያለው፥ የሴት አሳብ ከራሳችን ከጠፋ ዘመንም የለው፥ ወንድሜ።»

«አዎ - ይ! ሌላው ቢቀር ደሞ ምኞቱም ይቅር? ሽማግሌ ምኞትንና ትዝታን ካጣማ ምን ይቀረዋል? ምስኪን ህይወቱ የባሰውን ምስኪን፥ የባሰውን ባዶ ይሆን የለ? »

«እንዴት! እባክህ? »

«ሰው ከሸመገለ፥ በውበቱ ቆንጆ አያባብል፥ በጉልበቱ ታጎ አይጥል፥ ዘምቶ ጀብድ አይሰራ በልብሱና በትጥቁ ማማር አይኮራ፥ እንደነይህ ያሉት ታላላቅና መልካም ነገሮች ሁሉ በጎልማሳነት ጊዜ ብቻ የሚያደርጉ፥ ከጎልማስነት ጋር አብረው የሚያልፉ ናቸው። ከጎልማስነት ጋር አብረው የሚያልፉ ሰው ከሸመገለ በሁዋላ በህይወት እስካለ ድረስ ደስ ሲያሰኙት የሚኖሩ ጎልማሳ ሳለ ሲያደርጋቸው የኖረ፥ የመልካም ነገሮች ትዝታና ምኞት ናቸው።»

«እሱስ እውነት ነው ‹ሽማግሌ የትናንቱን፥ ጎበዝ የማግስቱን ልጅ የለቱን ስያልሙ ያድራል› እንደሚሉት ማለት አደል? »

«እ - ንደሱ ማለቴን ነው» አሉ ባላምባራስ ተካ። ከዚያ ሁለቱም ዝም ብለው፥ በዬበኩላቸው ሲያስቡ ትንሽ ከቆዩ በሁዋላ፣

«ታውቃለህ? » አሉ ባላምባራስ ፈገግ ብለው ወደ ጉዋደኛቸው መለስ አሉና። «ታውቃለህ? መቼም - ‹ምስጢር ሲያረጅ ገበያ ይወጣል› እድነሚሉት ነውር ስራ፥ ነውር ሆኖ ሰሪውን ባለጌ የሚያሰኘው ወይም የሚያስጸይፈውና የሚያስነቅፈው ባዲስነቱ ነው ውንጂ፥ ካረጀ በሁዋላ፥ ይፋ ቢሆን፥ ነውር መሆኑ ቀርቶ የሚያጫውትና የሚያስቅ ነው የሚሆን። ስለዚህ እስቲ እኔም ለሳቅና ለጨዋታ ያክል፥ አሮጌ ነውሬን አሮጌ፥ ጉዴን ልንገርህ።»

«በእሱማ የታወቅህ ነህ፥ እስከ ዛሬ ሰው የማያውቀው ምን ጉድ ሳይኖርብህ? » አሉ ጉዋደኛቸው፥ ገና ነውር ወይም ጉድ የተባለውን ሳይሰሙ ትንሽ እንደ መሳቅ ብለው።

«እንደ ዛሬው እድሜ ሳይጫነኝ፥ ድሮ ባፍላዩ ሳለሁ፥ ከመጠን ያለፈ ሴት ወዳጅ ነበርሁ። ሴት ወዳጅነቴ ስንት ከፍተኛ ሹመት ስንት ከፍተኛ ማእረግ እስቀርቶብኛል መሰለህ! ያንጊዜ አንተ አልነበርህም እንጂ፥ የጌቶች አባት፥ ደጃዝማች ተጫነ አባ ምታው እንደ ሞቱ፥ ሎሌዎቻቸውን የሸዋ ታላላቅ መኳዋንንት በማእረግ ስምና ባገር ግዛት እያባበሉ ሲከፋፈሉዋቸው፥ እኔንም ቢለምኑምኝ - ያን ጊዜ የጌቶችን ሞግዚት እወድ ነበርና፥ ከስዋ መለየቱ ሞት መስሎ ስለ ታዬኝ አገር ግዛትና የማእረግ ስም እያገኙ ከሄዱት ጉዋደኞቼ ተለይቼ እዚህ ቀረሁ። ያንጊዜ ጌቶች ገና የፊት ጥርሳቸውን ያላወለቁ ህጻን ነበሩ እየውልህ «አገር ግዛት እንካ፥ የማእረግ ስም እንካ» እያሉ ሲያባብሉም፥ ሁሉም ‹አሻፈረኝ!› ብዬ ገፍቼ ገና ሎሌ ምን መሆን እንኩዋ ለማያውቅ ህጻን ሎሌ ሆኘ እንድቀር ያደረገኝ የሴት ፍቅር ነው! » ሲሉ እዬሳቁ፣ ጉዋደኛቸውም አብረዋቸው ሲስቁ ቆዩና፥

«መቸም - ወንድ ሆኖ ተፈጥሮ ሴት መውደድ እንኩዋ የነበረ ነው፤ የተሰራ ህግ ስለሆነ - ሴት የማይወድ ወንድ የለም። ብቻ - ካገር ግዛት ከሹመትና እንደነሱ ካለው የሚያስከብር ነገር አብልጦ ሴት የሚወድ ሰው - እንጃ! ምን ይባላል ልበል? ‹ራቱን ለዳረጎት የሚለውጥ፥ ሞኝ ወይም እብድ› ሳይባል ይቀራል! » አሉ ሳቃቸው ወዳሽሙር ፈገግታ ተለውጦ፥ ጉዋደኛቸውን የጎድን እያዩ።

«ሞኝነት ወይም እብደት ወይም ሁለቱን ባንድነት በለው አያሳዝነኝም! እንዲያውም ይግረምህና አሁን ባለፈው ህይወቴ ‹ለምን እንዲያ ሆንሁ?› ብዬ በመጸጸት ፈንታ ‹እንኩዋን እንዲያ ሆንሁ!› ብዬ ደስ ይለኛል! ምክንያቱም ያንጊዜ፥ ባፍላው፥ ከምወዳትና ከምትወደኝ ልጅ ጋር በፍቅር ስንሰክርና ስንጨፍር አየው የነበረውን ልዩ አለም፥ አገኘው የነበረውን ደስታ፥ አሁን ካለፈ በሁዋላ የዚያ ሁሉ ትዝታ የሚሰጠኝን ደስታ ካገር ግዛትም ከማእረግ ስምም ከምንም፥ ላገኘው የምችል ስለማይመስለኝ ነው። ይልቅስ ሳልርሳው፥ ‹ከግዛትና ከሹመት የበለጠ ሴት የሚወድ ራቱን ለዳረጎት እንደሚለውጥ..... ነው› ያልኸው - ምሳሌ አልገባኝም ምን ማለት ነው? »

«መቸ አጣኸው? አገር ግዛትና ሹመት ካለ፥ ሀብት፥ ድሎት መከበርና መወደድ፥ አቅሙ ከተገኘም - አዳራሽ ሙሉ ሴት ጭምር ሳትጠራው ይመጣል! ሴት አገር ግዛትና ሹመት ከሚያመጡት ብዙ መልካም ነገር አንዱ ብቻ ነው። ስለዚህ - ‹አገር ግዛትና

ሹመት እንደ ራት፥ ሴት ከራቱ አንዳንድ ትንሽ ክፍል፥ እንደ ዳረጎት ነው ማለቴ ነዋ! »

«እ - ፣ እንዲያ ነው? ታዲያኮ ከራት ዳረጎት ይጥማል አሉ። ባላምባራስ ካሸሙር ፈገግታ ጋር ጉዋደኛቸውን የጎድን እያዩ።

«ስላነሰ ነዋ! ስላነሰ ይጥም ይሆናል፥ ግን እንደ ራት አያጠግብም እንደ ዳረጐቱ ነው። ከራት የበለጠ የሚያጠግብ ዳረጐትም አለ። ብቻ ያም ሆነ ይህ፥ ለኔ የሴት ፍቅር አንተ እንደምትለው ግዛትንም፥ ሹመትንም፥ ሀብትንም ተከትሎ የሚመጣ፥ ሳይሆን፥ የምንም ክፍል ያልሆነ፥ የምንም ራት ዳረጎት ያይደለ፥ ለብቻው ራሱን ችሎ የሚያጠግብ፥ ለብቻው የሚያደስት ልዩ ነገር ሆኖ ነው የሚታዬኝ።»

«ለመሆኑ፥ ወንዱ ሁሉ እስከ ዛሬ ያላገኘውና እግዚአብሔር ላንታ ብቻ ደብቆ የሰጠህ ልዩ የሴት ፍቅር እንዴት ያለ ይሆን? » አሉ ልጅ ከንፈ፥ እዬሳቁ።

«እግዜር ይሁን ሰይጣን የሴት ፍቅር እንዲጸናብኝ ያደረገ ማን መሆኑን አላውቅም። ‹ያንተ ልዩ የሴት ፍቅር እንዴት ያለ ነው? ላልኸውም መልኩ እንዴት ያለ እንደ ሆነ ልነግርህ አልችልም። ብቻ ከምወዳቸው ከምትወደኝ ልጅ ጋር ሁለታችንም በፍቅር ስንሰክር፥ በፍቅር ስንኾበረበር፥ የሚሰማኝ ደስታ ልዩ መሆኑን፥ ካገር ግዛት ሆነ ከማእረግ ስም ወይም ከማናቸውም ሌላ ነገር ሊገኝ የማይችል፥ ልዩ መሆኑን ልተርክልህና እስቲ አንተ መልክ ስጠው ወይም ስእል መሳል ታውቅ እንደሆነ ሳለው! »

«በል እስቲ» አሉ ጉዋደኛቸው አሁንም እዬሳቁ።

«አሁን እንዳልሁህ ከምወዳትና ከምትወደኝ ልጅ ጋር ሁለታችንም በፍቅር ሀይል ሙቀን፥ ግለን መሬት እንለቅና፥ ሁለታችንም በፍቅር ክንፍ መሬት ለቀን ወደ ላይ፥ ልዩ የደስታ አለም እንመጥቅና እንዲያ እዚያ እንዳለን፥ ‹እንዳንተ የምወደው ወንድ የለም! በወርቅ አስጊጬ፥ ባልጋ አሰምጬ፥ እመቤት አድርጌ አኖርሻለሁ› የሚል ራስ ደጃዝማች ቢመጣ፥ «አንተን ለሱ አልለውጥህም! ፍጹም ደስታ የምትሰጠኝ እንደ ፈጣሪ አምላኬ ሙሉ ህይወቴን የምትሰጠኝ አንተ ብቻ ነህ!› እያለች እውነት መስሎዋት ውሸት ስትናዘዝልኝ እኔም የምትናዘዘው ውሸት እውነት ይመስለኝና ደስታና ቅጥ መጠኑን ያጣ ይሆናል! እውነት ከራስ ከደጃዝማች የበለጥሁ፥ እውነት ህይወትዋን ከሰጣት ፈጣሪ አምላክዋ የተካከሁ ይመስለኝና፥ ደስታየ የደስታን ወሰን አልፎ ስካር

ይሆናል! ያንጊዜ ሁለታችንም በፍቅር ሰክረን ከመሬት ወደ ሌላ እጹብ - ድንቅ አለም በምንመጥቅባት ጊዜ ለስዋ እመቤትነት ድሎትና ጌጥ ለኔ አገር ግዛትና ሹመት፥ ራስ ደጃዝማችነት፥ ምንም አይመስለን! ያንጊዜ ይህ ሁሉ ምስኪን ነገር እዚህ ታች በመሬት ላሉት ስምኪኖች ትተን፥ እኛ እዚያ እጹብ ድንቅ አለም ውስጥ ገብተን፥ ሁሉንም ረስተን ምን ልበልህ? በደስታ እንጨፍራለን! » ሲሉ ያን ጊዜ ከሚወዱዋትና ከምትወዳቸው ልጅ ጋር በፍቅር እንደሚጨፍሩ ሁሉ እዬተወዛወዙ፥ ጉዋደኛቸው ሁኔታውን እዬተመለከቱ ገርሙዋቸው እሳቸውም ራሳቸውን እዬወዘወዙ ይስቁ ጀመር።

«ታዲያስ! » አሉ ባላምባራስ፥ ቀጠሉና። «ታዲያስ! እንዲህ ያለ ደስታ የሚሰጥ ከሴት ፍቅር በቀር ሌላ ነገር በምድር ይገኛል? አገር ግዛት ራስ ደጃዝማችነት እንዲህ ያለ ደስታ ይሰጣል? ሰው አገረ - ገዥ ሲሆን፥ ወይም ራስ ደጃዝማች ተብሎ ሲሾም የሚያገኘው በፍቅር ፈንታ ጥል ጭቅጭቅ ብስጭት ከዚያ ለብስጭቱ ምክንያት የሆነው ሰው «ያዝልኝ በልልኝ፥ እሰርልኝ፥ ግረፍልኝ» ማለት ያ ሁሉ አልፎ፥ ከሸመገለ በሁዋላ፣ እድኒህ እድነኛ መለስ ብሎ ያለፈ ህይወቱን ሲያስብ፥ እንደ ሴት ፍቅር ደስ የሚያሰኝ ትዝታ ፈንታ፥ በስልጣን በነበረ ጊዜ በስራው በደል የሚያሳዝን ጸጸት አደለም? ታዲያ ይህ ከሴት ፍቅር የሚመረጥ ነው? የለም፣ ከሴት ፍቅር የሚመረጥ ነገር እግዚአብሄር በዚች ምድር አልፈጠረም! የለም፥ የሴት ፍቅር የሚመስል አይገኝም! የሴት ፍቅር በጊዜው ደስታው፥ ሲያልፍ ትዝታው ሕይወትንና ሙቀትን እየሰጠ የሚያኖር ነው። ‹እውነቱን ንገረኝ› ካልከኝ ያለፈ እድሜየን እንደገና መመለስ የምችል ብሆን - ‹ምን እዬበላህ?› አትበለኝ እንጂ ከምወዳትና ከምትወደኝ ልጅ ጋር ቤቴን ዘግቼ በፍቅር ስጨፍር ከመኖር በቀር ሌላ ባልፈለግሁ! » አሉ፥ ያለፈ እድሜያቸውን መልሰው ለመኖር አለመቻላቸው አሳዝኖዋቸው የቅርታ ፈገግታ በሽማግሌ ፊታቸው ላይ እዬታዩ።

«ወይ ግሩ - ም! እውነትም አንተ የምታስገርም ልዩ ሰው ነህ! » አሉ ጉዋደኛቸው፥ መሳቃቸውን ትተው በመገረም ራሳቸውን እዬወዘወዙ። ከዚያ ሁለቱም ዝም ብለው ትንሽ እንደ ቆዩ፣

«ታዲያ እየውልህ» አሉ ባላምባራስ፥ ዝምታውን አቋዋርጠው፥ «እየውልህ ቅድም በዚህ እንዳለፍችዋ ያለች ውበት ብቻ የሆነች ልጅ በታዬች ቁጥር፥ ያ አሁን የተከሁልህ ውብ ህይወት ትዝ ይልና፥ በዚያ ውብ ህይወት ውስጥ ያሉ ይመስልና ወይ

ደስ ማሰኘቱ! ዋናው ነገር -» ብለው ሊቀጥሉ ሲሉ ደመቀች ያፈላችው ቡና፥ እንፋሎቱ በጀበናው ጡት እየተትጎለጎለ በግራ እጅዋ ይዛ ከማድ ቤት ብቅ ስትል፥ ስላዩ «እ! ያችውና መጣች! » አሉ ጭዋታቸውን አቋርጠው። እመቤትዋ ቡናውን ይጠባበቁ ስለ ነበረ ፈጠን ፈጠን እያለች ትራመድ ነበር። ከደረትዋ በታች ያለ ክፍለ አካልዋ፥ የሚያሰባ ምግብ መሸከም እንደ ተጸዬፈ ሁሉ ከቦታው ሸሽቶ ከጀርባዋ ተጠግቶ፥ ሁለት ጡቶችዋ ለዬሳራቸው ነፍስ እንዳላቸው ጨቅላዎች እርምጃዋን ተከትለው በደረትዋ ላይ፥ ሽቅብ ቁልቁል እያጋፈቱ እዬተሟወቱ መጥታ፥ አጠገባቸው እስክትደርስ አፋቸውን ከፍተው ሲመለከቱዋት ቆዩና፣

«እስቲ አንድ ጊዜ ወዲህ ነይ፥ ማሚቴ» አሉ ባላምባራስ ፊታቸውን ሁሉ በደስታ ወገግ እንዳለ።

«እቸኩላለሁኮ ጌታ» አለች ደመቀች፥ ሽማግሌውን ላለማሳዘን ቆም አለችና።

«አይዞሽ አናቆይሽም፥ ትሄጃለሽ።»

እመ ትዋ ‹ዘገየሽ› ብለው እንዳይቆጥዋት ስለ ፈራች፣ አሳብዋ ወደ ሁዋላ እዬጎተታት ወደሳቸው ቀረብ ስትል፥

«እጅሽን ምን ነካው? እስቲ ወዲህ በይው» አሉ ባላምባራስ የሳቸውን እጅ ወደስዋ ዘርግተው።

«እ? እጇን ምን ነካው? » አለች ደመቀችም፥ እንዲሁ ሳታስብ ደመነፍስዋን፣ እጅዋን ወደ ባላምባራስ ዘርግታ። ማድቤት ቡና ስታፈላ ራቁት ከንድዋን ከሰል ወይም የቡና ፍንጣቂ ያበላሸው መስሎዋት ትንሽ እንደ ማፈር ብላ ነበር። ባላምባራስ ያን የተዘረጋ እጅዋን ለቀም አድርገው ከንፈሮቻቸውን በላዩ ከማሳረፋቸው፥

«እንዴ! እርሶ ደግሞ -» አለችና እጅዋን በሀይል ነጥቃ የፈላ ቡያ የያዘችበትን ጀበና አናታቸው ላይ ልትሰብርባቸው ስትል ልጅ ክንፈ ቶሎ ተነስቶ ያዙዋት።

«ምን መሆንሽ ነው? አበድሽ? ሳይገባሽ ነውኮ? » አሉ ልጅ ክንፈ፥ በባላምባራስ አናት ላይ ለማንዘር ያነሳችውን ጀበና የተሸከመ እጅዋን እንደ ያዙ። ከንዴትዋ ብዛት የተነሳ፥ መናገር እንኩዋ አልቻለችም። ካጭር ጊዜ በፊት በፈገግታ ተውቦ የነበረ ፊትዋ ጭምትርትር ብሎ ጠጉርዋ ወደ ግንባርዋ ተመልሶ ቆሞ የወባ መንሾ ያለበት ይመስል ትንቀጠቀጥ ነበር! ባላምባራስ አድራጎትዋን እንዲያ በቅጽበት

መለወጥዋ አስደንግጦዋቸው፥ አይኖቻቸውንም፥ አፋቸውንም፥ በሰፊው እንደ ከፈቱ ዝም ብለው ሁኔታዋን ከመመልከት በቀር አንድ ቃል አልተነፈሱም።

«ነገሩ ባይገባሽ ነው እንዲህ ያለ - በሌሎች ላይ እንኩዋ የምትጠይውን ነውር ነገር ያደረግሽ» አሉ ልጅ ከንፈ፥ ቀጠሉና። «አዬሽ? ወንድሜ ባላምባራስ፥ ልክ አንቺን የመሰለች ልጅ አለችው። ቅድም በዚህ ስታልፊ፥ ‹ልጄን መሰለችኝ› ብሎ - ‹መች ተመልሳ ባነጋገርዋት› እያለ ሲጠብቅ ነው - የመጣሽ። እና ልጁን መስለሽው ስለ ወደደሽ፣ ያባትነት ፍቅሩን ለመግለጽ ነው እንጂ - ለሌላ ነገር አይደለም» ብለው ቁጣዋን የሚያበርድ የመሰላቸውን ውሸት ሁሉ አጠራቅመው ከነገሩዋት በሁዋላ፥ «አንተም - ሳታውቅ፥ በስህተት ያደረገችው ስለሆነ አትቀየማት! ይቅርታ አድርግላት» አሉ፥ የተናገሩት ውሸት ለደመቀች እውነት እንዲመስላት ወደ ባላምባራስ ዘወር ብለው። ደመቀች ልጅ ከንፈ የተናገሩትን ስትሰማ፥ በቁጣ ፈንታ እፍረት ተሰማትና፣ በቁጣ ተጨማትሮ የነበረ ፊትዋ ለስለስ እያለ ሄዶ በጸጸትና በቅርታ ቀለም ሲዋብ ይታይ ነበር። ብቻ አእምሮዋን ሙሉ በሙሉ ገዝታ ልታደርገው የሚገባትን ለይታ ማወቅ ገና ስላልቻለች፥ ባላምባራስን ይቅርታ ሳትለምን ዝም ብላ እየሮጠች ያቁዋራጩን አጥር በር ገባች።

ባላምባራስ አይኖቻቸውን ሳያረግቡ፣ ቦዘዝ አድርገው፥ ያቁዋራጩን አጥር እስክትገባ ሲመለከቱ ቆይተው፥ «እስዎም ደግሞ! » አሉ ራሳቸውን እዬወዘወዙ፥ ደመቀች ያለችውን ደግመው፥ «እስዎም ደግሞ ትበለኝ? ወይ አለመሙተዋወቅ! ከቶ ምን መስያት ይሆን? «እስዎም ደግሞ! » አሉ እንደገና፥ እኒያ ሁለት ቃሎች ክብራቸውን አቁስለውት፥ ድንጋጤያቸው ካለፈ በሁዋላ እመሙ እዬቆየ ተሰማቸው።

«እስዎም ደግሞ» ማለትኮ - «እንደስዎ ያለ ትልቅ ሰው እንደስዎ ያለ ሽማግሌ ሰው፥ ልጅ ይመስል፥ እንዴት እንዲህ ነገር ያደርጋሉ? ማለት ስለሆነ፥ ይሄ ማክበር ነው እንጂ መናቅ አደለም። ስለዚህ - መቀየም የለብህም» አሉ ልጅ ከንፈ።

«እኮ፥ ‹እንዳንተ ያለ ሽማግሌ፥ እንዳንተ ያለ ውዳቂ እንዴት ይደፍረኛል!› ማለት አይደለም»

«እንደሱ ማለትዋ አይደለም አልሁህኮ! ምነ ምን ሆንህብኝ? ‹እስዎም ደግሞ ሽማግሌው ሰው ልጅ ይመስል› ማለትዋ ሽማግሌ ስለሆንህ ንቃህ አደለም። የዚህ ቤት ልጆች፣ ሳቅና ጨዋታ መውደድዋን አይተው የግብረ ስጋ ጉዋደኛቸው እንድትሆን

አሳስቀውም አባብለውም ሳይሳካላቸው ጊዜ፥ በሀይል ሊደፍሩዋት ስለ ፈለጉ አንተ የማታውቀው፥ ብዙ ጉድ፥ ብዙ መሳቂያ ነገር ደርሶዋል። በሀይል ሊደፍሩዋት ከሞከሩ የዚህ ቤት ጎረምሶች፥ ፊቱን በሙጭራ ነብር የዋለበት ያስመስለችው በቢልዋ የወጋችው፥ አፍላል ሙሉ በርበሬ ወጥ በራሱ አከናንባ ‹እሪ የውሀ ያለህ፥ እሪ ድረሱልኝ› ያሰኘችው፥ ሌሎችም እንዲሁ ስላስቸገሩዋት ለጌቶች ‹አቤት› ብላ ብርቱ ቁጣና ማስጠንቀቂያ የተሰጣቸው አሉ። ከዚያ በሁዋላ ሁሉም ተስፋ ቆርጠው ተዋት። አንዱን አሁን እንዳልሁህ፥ ፊቱን በሙጭራ ነብር የዋለበት ስላስመሰለችው ነው - ‹የነብር እራት› የሚባል ስም አውጥተውላት የነበረ። እየውልህ፥ እንዲያ ሲያስቸግሩዋት የነበሩት ጎረምሶች ተሸንፈው ሲተዋትና እስዋም ‹አረፍሁ› ስትል አንተ እንደገና ያን - ከንስቱ ጋር ተጣልታ፥ ተደብድባም ደብድባም፥ ያስቀረችውን ነገር ይዘህባት ስትመጣ ጊዜ ነው - ‹እስዎም ደግሞ እንደ ልጆች› ያለች እንጂ፣ ላንተ እንደ መሰለህ አደለም» አሉ ልጅ ከንፎ።

ባላምባራስ፥ ጉዋደኛቸው በደመቀችና በጎረምሶች መሀከል «ደረሰ» ያሉትን ጉድ ሲያወሩላቸው በድሜ ላይ ቁጣ ተጨምሮ ይብስ አጨማትሮት የነበረ የሽማግሌ ፊታቸው፣ እድሜ ያጨማተረው ሲቀር የቁጣው ፊታ እያለ ሄዶ፣ እንዲያውም ፈገግ አለና፣ «ወይ ግሩ -ም! ለመሆኑ ድንግል ናት? ወይስ - ምንድነው እንዲህ ወንድ ያስፈራት? » አሉ።

«ድንግል እንኩዋ - አይደለችም። እንዲያውም ይግረምህና ልጅ አላት። ያንበሳ ቡችላ የመሰለ ድንቡሎ ልጅ! » አሉ ልጅ ከንፈ።

«ታዲያ ምን ልሁን ብላ ነው? ጥንቱን ወዳ ያስጠፋችውን ድንግልና አሁን እድነገና ማብቀል የምትችል መስሎዋት ነው? »

«ወዳ ይሁን ተገዳ - ድንግልናዋ የጠፋበትን ሁኔታ አላውቅም፤ እዚህ ከመምጣትዋ በፊት የተሰራ ታሪክ ነው። እኔ የማውቀውና ልናገር የምችለው እዚህ ከምጣች የሆነውን ነው» አሉ ልጅ ከንፎ።

በደመቀችና በደጃዝማች አሰፋ ቤት ጎረምሶች መሀከል ተነስቶ የነበረው ጦርነት ልጅ ከንፎ፥ ለጉዋደኛቸው በጭሩ እንዳወሩት፥ ደጃዝማች ባልተቤታቸው ሰምተው፥ ከፈቃድዋ በላይ ሊደፍሩዋት የሚሞክሩ ሁሉ፥ ያለ ምንም ይቅርታ ከቤት እንዲባረሩ መሆናቸውን በብርቱ ቁጣ እስኪያስታውቁ ድረስ፥ አልቆመም ነበር። «ጆሮ ለባለቤቱ

ነውር ሩቅ ነው» እንደሚሉት ደጃዝማች አሰፋና ወይዘሮ ጽጌ ያን ሁሉ፥ በደመቀችና በቤታቸው ገረምሶች መሀከል፥ በገዛ ግቢያቸው ውስጥ ሲደረግ የቆዬውን አምባጉዋሮ ካጥር ወትቶ ጎረቤት ሁሉ አውግቶት ካረጀ በኋላ ነበር የሰሙት። በመኩዋንንት ስራ የቤት መሀከል ያንዱን ወይም ያንዱዋን ነውር ለጌቶች መንገር «አሳባቂ» አሰኝቶ የሚያስንቅና የሚያስጠላ ስለሆነ፥ ይህን በመፍራት፥ የነገራቸው አልነበረም። በሁዋላ ብቻ ደመቀች ራስዋ እያለቀሰች አቤቱታ ስታቀርብላቸውና እነርሱም አንዳንድ ሽማሎችን ጠይቀው በዬጊዜው የሆነውን ዝርዝር ሲነግሩዋቸው ለስዋ በማዘን ብቻ ሳይሆን እንዲህ ያለ፥ የጎረቤት መሳቂያ የሆነ ነውር ስራ ከግቢያቸው ውስጥ መሰራቱ የነሱን ክብር የሚነካ፥ የራሳቸው ጥቃት ሆኖ ስለ ተሰማቸው በጣም ነበር የተቆጡ።

# ምዕራፍ ዘጠኝ

# ደመቀችና ደጀኔ

«ውበት አንድም ለማጥመጃ ወይም ለማጠመጃ» ስለሆነ የደመቀች ውበት እስዋ ለሌሎች ማጥመጃ ልታውለው ባትሻ፥ ሌሎች የምትኖርበት ቤት ገረምሶች እስዋን የሚያጠምዱበት ሆኖ ተገኘና ሰላም አሳጣት። የደጃዝማች አሰፋ ቤት ገረምሶች የፊት መልክዋን ማማርና ደም ግባትዋን ምስህብዋን፥ ይልቁንም ካንገት በታች ያለ ሰውነትዋን ሲያዩ እብዶች ይሆኑ ነበር። ያን በሚያድበለብል የመኩዋንንት ቤት ጋሬና ዶዮ የሚኖር የማይመስል ሰውነት ሲያዩ ያን በንብ ወተትና በማር እሸት እንደምትኖር የንቦች ንግስት የደረትና የዳሌ ኩራት ከወገብ ቅጥነት ጋር ተስማምተው የተዋሀዱበት ሰውነት ሲያዩ፥ ያን የሚያማምሩ ባቶችዋና ተረከዞችዋ ውብ ሆነው የተዋደዱበትን ሰውነት ሲያዩ፥ ያን ለውብ ሴት ቅጥና ቅርጽ አራያነት እንደ ተፈጠረ ሁሉ ስሀ የሌለው ሰውነት ሲያዩ፥ የደጃዝማች አሰፋ ቤት ገረምሶች ፍትወት አስከሮዋቸው፥ አእምሮዋቸውን መቆጣጠር ይሳንቸውና፣ ነውርን ሁሉ ንቀው ይሉኝታ ሁሉ ደቅድቀው ያችን ሴት ልጅ ሲደበድቡና በዚያች ሴት ልጅ ሲደበደቡ የሰው መሳቂያና መሳለቂያ እስኪሆኑ ድረስ ራሳቸውን ያላጋለጡ ጥቂት ነበሩ! ከኒያ፥ በውበትዋ ተጎትተው ብየዬጊዜው አምባጉዋሮ እያነሱ ሰላም ከሚነሱዋት ሌላ ደግሞ፥ ለማንም እጅዋን አለመስጠትዋን፥ ሁሉንም ማሸነፍዋን ያዩ፥ ይቺን፥ ሁሉም ያሸነፈቻቸውን አሸንፎ

መማረክ ከሁሉ በላይ የሚያደርጋቸው መስሎ ስለ ታያቸው፥ ለጉራ ሲሉ ለጀብደኝነት ሲሉ፥ በውድድሩ ውስጥ ገብተው የሚያስቸግሩዋት ነበሩ። ከጎረምሶች መሀከል አንዱ ደጀኔ አግደው የሚባለው ብቻ ያንጊዜ፥ እንደ ሌሎች በማስቸገር ፈንታ እንዲያውም ለደመቀች ረዳት ሆኖ እስዋን «አይዞሽ! » እያለ ከማበረታታት አልፎ ከሚያስቸግሩዋት ጋር እዬተጣላ እስከ መደባደብ የደረሰበት ቀን ነበረ! ታዲያ እሱም ቢሆን ወደ ግቡ ለመድረስ የተሻለ ዘዴ መስሎት የያዘው ነው እንጂ ርዳታው ከንጹህ ልብ የመነጨ፥ እስዋን ለመርዳት ብቻ ብሎ የሚያደርገው አልነበረም። ደመቀች ግን የቤቱ ጎረምሳ ሁሉ በስዋ ላይ ያሴረ ይመስል ያን ያክል መከራ ሲያሳያት፥ እሱ ብቻ እንደናትዋ ልጅ አብሮዋት ተሰልፎ ካስቸጋሪዎችዋ ጋር እስከ መደባደብ የደረሰ በደግነቱ በትልቅነቱ ካልሆነ፥ «ሌላ የተሸሸገ ምክንያት ቢኖረው ነው» የሚያሰኝ አንዳች ምልክት ስላሳዬችበት መውደድ ብቻ ሳይሆን ታምነው ነበር። ደጀኔ እንደ በግ ነድቶ፥ ወይም ጎትቶ የትም «ልውሰድሽ» ቢላት፥ እስዋ ላይ «ሌሎች የሚያስቡትን ያስብ ይሆን? » ብላ ሳትጠረጥር፥ ሳታመነታ ተከትላው ትሄድ ነበር። ሲናገር የምትሰማው ሆነ ሲያደርግ የምታየው ሁሉ እምነትዋን የሚያጠነክር እንጂ የሚያደክም አልነበረም። ጎረምሶችን ስለ አድራጎታቸው እዬነቀፈ ሲዘልፍ «እነዚህ - የሰው ባህሪ የሌላቸው፥ ኮርማዎች» ይላቸዋል። መክሮዋቸውም ስድቦዋቸውም፥ አንሰማ ብለው ከስዋ ጋር አምባጉዋሮ ሲያነሱ ያገኛቸው እንደ ሆነም በክርን ወይም በዱላ ልክ ያገባቸዋል! እንኩዋንስ ለብቻዬ ከፈለጉ ባንድነት ቢመጡ፥ እንደ ኮርማዎች መንጋ ሊነዳቸው የሚችል ዱለኛ ነው! ስለዚህ፥ ምንም እንኩዋ እኒያ ሲያስቸግሩዋት የነበሩት ጎረምሶች ሁሉ፥ የማትበገር መሆንዋን ከተረዱና ባለቤቶች ብርቱ ማስጠንቀቂያ ከሰጡዋቸው በሁዋላ እዬታገስዋት ቢሄዱ በተጨማሪ እንደ ደጀኔ ያለ የባእድ ወንድም «እናቴ የደንግያላይቱ» ስላወረደችላት፥ በመጨረሻ ሰላም ያገኘች መስሎዋት በጣም ደስ ብሎዋት ነበር።

እንዲያ ያለ ሙሉ እምነት እንደ ጣለችበት ደህና አድርጎ ከተረዳ በሁዋላ ደጀኔ ቀስ እያለ፣ በማባበል ልብዋን የሚማርክበትንና ሲጀመር ጀምሮ ወደ ፈለገው ግብ የሚመራበትን ልዩ ልዩ ዘዴ መፍጠር ጀመረ። የመጀመሪያው ዘዴ በገንዘብ መደለል ነበር። ገንዘብ ሳይኖረው አምስት ብር ካምስት ሰዎች ተበድሮ፥ ተለምኖ፥ ሊሰጣት ቢሞክር የማትቀበለው ሆነች። «እትና ወንድም መሆናችነን የሚያስታውስሽ ጌጥ እንድትገዥበት ብዬ ነው እንጂ ለሌላኮ አይደለም» እያለ፥ ተንኮሉን ለመሸፈን ውሸት በውሸት ላይ እዬደራረበ ቢለምናት የማትቃጣ ሆነች! ደመቀች እናትዋ ወይዘሮ

ሙሉነሽ «የሰው ገንዘብ አሙካ (ቅባት እድፍ) ነው» ሲሉ እዬሰማች አድጋ፥ የሰው ገንዘብ ልክ እንደ አሙካ ነበር የምትጸዬፍ። ከወላጆችዋ ጠፍታ ወደ አዲስ አበባ ስትሸሽ ብቻ፥ ከባታችን አስራ ሁለት ብር፥ ካቶ መላኩ ረዳ አስር ብር የተቀበለች ግዴታ ሆኖባት ነው። በተረፈ፥ እስከዚያ ድረስ የሰው ገንዘብ በጅዋ ገብቶ አያውቅም። ደግነቱ ገንዘቡን «አልቀበልም» ብትልም፥ ካነጋገርዋና ከጠቅላላ ሁኔታዋ ምስጢሩን ያወቀችበት አትመስልም ነበር፤ እውነትም አላወቀችም። ስለዚህ የገንዘቡ ወጥመድ እንዲያዘለት ሲያውቅ፥ ዘዴውን ለወጠ። ቀስ ብሎ በለሰለሰ ቃሎችና ልብ በሚማርኩ ግጥሞች ማወዳደሱ ከጊዜ ብዛት አለዝቦ በመጨረሻ ሊያሸንፋት የሚችል መሎ ታዬውና፥ እሱ ግጥም መግጠም ስለሚያውቅ፥ግራ ጌታ ስንቄ ለሚባለው የጊዮርጊስ ደብተራ ደመቀችን፥ ከመጠን ያለፈ እንደሚወድና እንደ ማታውቅ ችላ እያለች ያስቸገረችው መሆንዋን ከገለጸለት በሁዋላ፥ እሱን ለምኖ አስገጥሞ እኒያ የተውሶ ግጥሞች እንዳይጠፉት እዬመላለሰ ደህና አድርጎ አጥንቶ ተመለሰ። ግራ ጌታና ደጀኔ ከዝምድናቸውም ሌላ ምሥቲር የማይደባበቁ፥ የምስጢር ጉዋደኞች ናቸው።

አድን ጥዋት፣ ለልጅዋ ቁርሱን ወስዳለት ስትመለስ በመንገድ ጠብቆ፥ «ደመቁ ‹አንድ ሰው ለሚወዳት ልጅ ገጠመላት› ብሎ ሰዎች ሲቻወቱ የሰማሁትን ግጥም ልንገርሽ» አለ ደጀኔ ለስዋ የተገጠመ መሆኑን የገለጸላት እንደሆነ «ትቆጣ ይሆናል» ብሎ ፈርቶ።

«እነማን ናቸው? »

«ሰዎቹን አታውቂያቸውም። አንድ ዘመዴ ቤት ድግስ ነበረና እዚያ በተሰበሰብንበት ሲጫወቱ ሰምቼ - ላንቺ ለመንገር ብዬ አጠናሁት።»

«እስቲ» አለች ደመቀች ቆም ብላ። እሱን ደስ እንዲለው ነው እንጂ ግጥሙን መስማት ፍላጎት ኖሮዋት እንኩዋን አልነበረም።

«እ -፥ አዎ» አለ ደጀኔ፥ መጀመሪያው ጠፍቶት አንድ፥ ጊዜ ሰማይ አንድ ጊዜ መሬት ሲያይ ቆይቶ ሲያገኘው ፈገግ አለና፤

«ልቤ ከልብሽ በር፤ ቆሞ ደጅ ሲጠና፤

ደግሞ መጣ ክረምት፤ በጋው አለፈና።

«ደጅ ጥናቱን አይቶ፥ ምጥንታውን ሰምቶ፥

«አላስገባም» ካለ፣ ልብሽ በሩን ዘግቶ፥

መከረኛው ልቤ፥ ሲያለቅስ ሊከርም ነው፣ እንባውን ሲያነባ

ዘንድሮም እንዳምናው፣ ክረምቱ እስኪጠባ።

ልቤ ከልብሽ በር፣ ቆሞ እዬለመነ፤

ስለእግዚአብሔር ብሎ ቢከፍትለት ምነ?

ለሚጠላስ ቢሆን፣ እንኳዋን ለወደደ፤

መራራትን አደል እግዜር የፈቀደ? »

«ውይ - ! እንዴት ጥሩ ግጥም ነው! ለመሆኑ ይህን ሁሉ - አንተ እንዴት ሰብስበህ ያዝኸው? እኔ እንዲህ - ብዙ ግጥም መያዝ አይሆንልኝም» አለች፥ በፍጹም ቅንነት።

«እኔማ - ላንቺ መንገር ብዬ - እኒያስጠኑኝ ለመንሁዋቸውና አስጠኑኝ» አለ እስዋን ፊት ለፊት ማየቱን ፈርቶ እንደ ልማዱ አንድ ጊዜ ሰማይ አንድ ጊዜ መሬት እያዬ። ደጀኔ ከማንም ጎበዝ ጋር «አምባጐዋሮ» ሲሉት የሚደፍረውን ያክል ሴቶችን በተለይ ደመቀችን ይፈራል።

«ውይ ጋሽ ደጀኔ ለኔ ለመንገር ብለህ? ምን የሚያደርግልኝ መስሎህ ነው? እኔኮ ግምጥ ማጥናት አይሆንልኝም። በግድ ባጠናው እንኳዋ - አብሮኝ አይቆይም፤ ወዲያው ረሳዋለሁ። ትንሽ ልጅ ሳለሁ ከጐዋኞቼ ጋር እንዘፍነው የነበረውን - ብቻ ነው የማልረሳው። በል - ደህና ሁን፤ ደግሞ - «የት ቆዬሽ» ብለው እመይቴ እንዳይቆጡኝ ልሂድ» ብላው፥ እዬሮጠች ያቁዋራጩን አጥር በር እስክትገባ ዝም ብሎ ሲመለከታት ቆይቶ ካይኑ ስትጠፋ ስሜትዋ ምንም «ቅስቅስ» ባለማለቱ፥ ግጥሙን ሆነ እሱን ራሱን ከምንም ባለመቁጠርዋ በጣም ተናዶ የሚያደርገው ጠፋውና «ህእ! ‹ምን የሚያደርግልኝ መስሎህ ነው!› ኸልች ይቺ - ጨካኝ አረመኔ! » አለ በቆመበት እንዳለ። «ሌላ ሰው ለወዳጁ የገጠመላት ግጥም ነው» እያለ ራሱ እዬነገራት ለስዋ ባልተገጠመ ግጥም፥ ሌላ ሰው ለሌላ ልጅ ልብዋን እንድትከፍትለ» እዬተማጠነ በገጠመው ግጥም «የስዋ ልብ ሳይራራ በመቅረቱ» መናደድና «ጨካኝ አረመኔ» ማለት እንኳዋ መቸም እንዲያው የራስን ጉድለት ላለማመን ለራስ መደለያ የሚሰጥ ምክንያት ነው። ጨካኝ አረመኔ ባትሆንም፥ ሌላ ሰው ለሚወዳት ልጅ ባበረከታት የፍቅር መገለጫ የስዋ ልብ

ራርቶ፣ የሰዋ ልብ ተማርኮ ለሱ በሩን አይከፍትም። ታዲያ፥ ተስፋ ቆርጦ እንዳይተዋት ስለ ወደዳት የሚወዳት መሆኑን ገልጾ እንዳይነግራት ስለ ፈራት የሚያደርገው ጠፍቶት ተናደደ፥ ቀደም ብሎ ግራ ጌታ ስለ ስንቄን የመስተፋቅር አብነት እንዲሰጠው ለምኖት፣ ቁርጡን ሳይነግረው ቆይቶ ስለ ነበረ፥ እንደገና አጥብቆ ሊለምነው ወደሱ ተመልሶ ሄደ።

«እባክህ ስንቅዬ፥ የማስተፋቅር አብነት ገንዘብ ካልተከፈለበት አይሰምርም የሚባለው እውነት እንደሆነ ከ - ተደበርሁት ገንዘብ የተረፈ አራት ብር ስላለኝ - እሱን ልስጥህና አድርግልኝ። ይችን አውሬ የግጥሙ ጋጋታ እንደሆነ - እንኩዋንስ እልብዋ ውስጥ ገብቶ ሊያገርማት፣ ጆሮዋን በቅጡ የነካው አይመስልም። እንዲያውም ‹ግጥም የሚያደርግልኝ መሰለህ?› አለችኝ» አለ ደጀኔ፥ ለደመቀች መደለያ ተደምሮ ለምኖም ካጠራቀመ አምስት ብር ባንዱ ግራ ጌታ ስንቄን እመጠጥ ቤት ጋዞት ሲጠጡ። ግራ ጌታ ወደ መጠጥ ቤት ሲሄድ አጭር ጥምጣሙን እቤቱ አውልቶ ጥሎ፥ መሀይም መስሎ ነው የሚሄድ። «ገንዘብ ያልተከፈለበት አብነት አይሰምርም የሚሉት እንኩዋ እንዲያው - ለቀልድ፥ ከዚያም አልፍ ሲል ለንግድ የፈጠሩት መላ ስለሆነ በኔና ባንተ መሀከል - ቀልድ ቢኖር ‹ንግ ይኖራል› ብለህ እንደማትጠረጥር አምናለሁ። አይነተኛው ነገር እሱ አይደለም፥ ሌላ ነው። አይነተኛው ነገር የተለጸ እንደሆነ ላንተም ለኔም፥ በተለይ ለኔ ደግ አለመሆኑ አደገኛ መሆኑ ነው»

«እኔ አልናገር፤ እሰዋ አታውቅ፣ እንዴት ይገለጻል? ማን ይገልጸዋል? »

«መቸም እኔ እንኩዋ - እንዲያው ለውቀቱ ብዬ የተማርሁት ነው እንጂ - አንዳንድ ጊዜ በግድ አስፈላጊ ሆኖ ካላገኘሁት - መኖሪያ አድርጌ ብዙ ጊዜ ስለማልሰራበት፥ እግዚአብሔር ይመስገን፥ እስከ ዛሬ አጋልጦኝ አያውቅም። ነገር ግን አንድ ያቦ ደብተራ ጉዋደኛየ፥ ከችግርም ሌላ ብርቱ ውርደት ደርሶበታል።

«እንዴት? »

«አ -! ታሪኩ ረዢም ነው! ብቻ ባጭሩ፥ አንድ ድሀ ጎበዝ አንድ ልጅ ይወድና ‹አበድሁ› ይላል። ልጅነቱ ግን ከሌላ በሰውነቱም በሀብቱም ከምትወደው ሰው ጋር ተጫጭታ ስለ ነበረ ይህን፣ ‹አበድሁልሽ› ባዩን ፊት ብትነሳውም አልገባው ሲል ጊዜ አፍዋን አውጥታ ‹ዳግመኛ ፊቴን እንዳታይ› ስትለው ተናዶ ሄዶ፥ ከቦው ደብተራ የመስተፋቅር አስማት ይገዛና ወስዶ ያዞርባታል። ከዚያ በሁዋላ፥ ድንገት ያን የምትወደውን እጮኛዋን ትታ በልምዋም በውንዋም የሚታያት ያ፥ «ዳግመኛ ፊቴን

እንዳታይ» ብላ ያባረረችው ጎበዝ ይሆንና፣ እስዋንም፥ ወላጆችዋንም ግራ ሲገባቸው፥ ወደ - አዋቂ ሄደው ይጠይቃሉ። ከዚያ ወዲያማ ምን ልበልህ! ምሥጢሩ ሁሉ ይገለጽና - አስማት አድራጊውም አስደራጊውም በፖሊስ ተይዘው ፍዳቸውን ያያሉ! ደብተራው እንዲያውም ፖሊስ ያሳዬው ስቃይ ሳይበቃው ቀርቶ፣ ‹በንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ እንደሚሉት ያቦ ደብር አለቃ፣ በነውረኛነት ቶፍነቱን ነጥቀው ለሌላ ሰው ይሰጡበትና ነውሩንም ችግሩንም ባንድ አፍ ላይ ደራርቦ ተከናንቦ እዚህ ሲዞር መታየቱ ስላሳረፈው፥ አገር ለቆ ይሄዳል! እየውልህ፤ እንዲህ ያለው ነገር እንዲህ እንዲህ ያለ አደጋ የከበበው ስለሆነ ነው -› ባናደርገው ይሻላል› ያልሁህ» አለ ግራ ግራ ጌታ፥ እውነቱን ይሁን ፈጥሮ፥ ከሱ በቀር ማንም የማይውቀውን ታሪክ ተርኮ ሲጨርስ ደጀኔን ፊት ለፊት እያዬ።

«ታዲያ እንግዲህ - ምን ባደርግ ይሻለኛል? ያላደረግሁትኮ የለም! ልብዋን የማገኝ መስሎኝ፣ ያላደረግሁት የለም። በሀይል ሊደፍሩዋት ከሞከሩ ስንት - ጎረምሶች ጋር የስዋ ረዳት ሆኘ ተከላከልሁ፤ ተዋጋሁ እስዋ ‹አልቀበልም› አለችኝ እንጂ፥ እኔ የምትወደውን ጌጥ ስለማላውቅ ራስዋ መርጣ እንድትገዛ ያቅሜን ያክል ገንዘብ ‹ልስጥ› አልኩ፤ ያው እንደምታውቀው - አንተ የገጠምህልኝን ግጥም በረከት አቀረብሁ፤ ይህን ሁሉ አደረግሁ። እስቲ ሰው ከዚህ የበለጠ ምን ያደርጋል? መጨረሻ የቀረኝና - ‹እሸንፍበታለሁ› ብዬ ተስፋ አድርጌ የነበረ ይህ - የለመንሁህ ነገር ነበር፤ የሱንም ጣጣውን አበዛኸው። በኔ እንኳዋ የደረሰ ቢደርስብኝ - መቸም ይቺ አውሬ ለጥፋቴ የተፈጠረች ናት መሰለኝ - ግድ ባለነበረኝ! ነገር ግን አንተን እችግር ውስጥ የሚያገባህ ከሆነ በኔ ምክንያት ችግር እንዲያገኝህ አልፈልግም» ስለ ደጀኔ፣ ያንድ ወገን ፍቅር የሚፈጥረው ጭንቀት በፊቱ ጎልቶ እዬታዬ። ግራ ጌታ ዝም ብሎ ፊቱን ሲያጠና ቆይቶ አዘነለትና፥

«እስቲ ይህን - እኔን የጠየቅኸኝን ለጊዜው አቆይተን፥ ሰዎች ሲያወሩ የሰማሁትን - ‹መስተፋቅር› ልንገርህና ቀድመህ እሱን ሞክረው። እሱ ካልሰራ ስለ ሌላው ግዴለም፥ ሁዋላ እንነጋገራለን። ይህን ‹ሰዎች ሲያወሩ ሰምቻለሁ› ያልሁትን እኔ ራሴ እንኳዋ አልፈተሁት፤ ብቻ ብዙ ሰዎች ‹ፍቱን ነው› ይላሉ» አለ የቅርታ ፈገግታ ፈገግ ብሎ።

«ብዙ ሰዎች የሚያውቁት ከሆነ እንዴት - አብነት ይሆናል? » አለ ደጀኔ «ግራ ጌታ የተለመደውን ላለመስጠት የተፈጠረው ዘዴ ሳይሆን አይቀርም» ብሎ ጥርጥሮ እንደ መቀየም አለና።

«እህል የራብ አብነት መሆኑን ሰው ሁሉ ስላወቀ አብነትነቱ ይቀራል? » አለ ግራ ጌታ፥ የቅርታ ፈገግታው በፊቱ እንዳለ። «ይልቅ አንድ ነገር ልጠይቅህ» አለ ቀጠለና።

«ከልጅቱ ጋር - በጣም ትቀራረቡ የለም? »

«እንዴት ያለ መቀራረብ? »

«አብራችሁ ቆማችሁ፥ ወይም ተቀምጣችሁ እንደ መጫወት ያለ።»

«ለዚያስ - አብረን ቆመን፥ ወይም ተቀምጠን ከመጨዋወቱም አልፈን እንደ ጉዋደኞች ወይም እንደ ወዳጆች እጅ ለእጅ ትከሻ ለትከሻ ተያይዘን እንሄዳለን ብቻ - የሁለት ወንዶች ጉዋደኝነት የሁለት ወንዶች ወዳጅነት አይነት ሆነብኝና አልጥመኝ አለ እንጂ አለ ደጀኔ ቅር ያለው ፊቱን የገዛ ቀልዱ ትንሽ ፈገግ አድርጎት።

«እንግዲያስ - አብራችሁ ቆማችሁ ወይም ተቀምጣችሁ ስትጫወቱ ድንገት ሳታስበው ሰርቀህ አፍዋን ሳማትና ስትደነግጥ አንተም አብረህ ደንግጥ አንተም ሆነ ብለህ ያላደረግኸው ለመምሰል ደንግጠህ ሽሽ፤ ሩጥ፤ ከዚያ በሁዋላ ለሶስት ቀናት ያክል አትታያት፤ ተሸሸጋት። ያን ጊዜ፥ እኒያን ሶስት ቀናት ልብዋ አንተን ፍለጋ ሲነተርካት ሲቅበዘበዝ ይሰንብታል! እየውልህ ይህን ነው - ‹ብዙ ሰዎች ፍቱን መስተፋቅር ይሉታል› ያልሁህ» ብሎ ግራ ጌታ፥ ብርሌ ጠጁን አንስቶ ከጨለጠ በሁዋላ ወደ ደጀኔ ጠጋ አለና -

«የሴት ልብ ፍለጋ ምን ያስጨንቅሀል?

ያው ከከንፈርዋ ላይ ተቀምጦልሀል!

ከንፈርዋን ካገኘ ሌላ ልብ የላትም፤

እሱን ሳምና ሩጥ አንተን ተከትላ ትሄዳለች የትም› ይላሉ፤

የሴት ልብዋ ከንፈርዋ መሆኑን በግጥም ሲገልጹ። ስለዚህ - እስቲ ሞክረው» አለ ሲነሳ እንደ መሳቅ ብሎ። ደጀኔም ግብዣው ሆነ ልመናው ተስፋ ያደረገውን ፍሬ እንዲሰጡ ሲያይ እያዘነ ብሩን ከፍሎ ግራ ጌታን ተከትሎ ወጣ።

ነገር ግን፥ ምንም እንኩዋ ፈልጎ የሄደለትን ባለማግኘቱ ማዘኑ ባይቀር «ሞኝ ያስያዙትን አይለቅም» እንደሚባለው፥ ግራ ጌታ ስንቄ «ብዙ ሰዎች ፍቱን መስተፋቅር ይሉታል» ያለው ካሳቡ ሳይጠፋ ባሳቡ ውስጥ ሲጉላላ ሰነበተ። እንዲያውም እዬዋለ እያደረ በሄደ መጠን በመረሳት ፈንታ ስጋና ነፍስ አበጅቶ እያደገ እዬጎላ ሄደና ከሱ በቀር ሌላ ማየት፥ ወይም ማሰብ ሆነ ማድረግ ከለከለው። ስለዚህ ለመሞከር ወሰነ። ብቻ ባሳብ መወሰንና ያሰቡትን በግብር መፈጸም የተለያዩ በመሆናቸው ያፈጻጸምሙ ነገር ሊወጡት የማይቻል ገደል መስሎ ታዬውና የብዙ አሳቦች መንጋ በራሱ ውስጥ ተደባልቆ እዬተተራመሰ አስጨነቀው።

«አብረው ቆመው ወይም ተቀምጠው በሚጫወቱበት ጊዜ፥ ድንገት ሳታስበው ሰርቆ ሲሰማት ደንግጣ በቢልዋ፥ በብረት መጥበሻ ወይም በሌላ በያዘችው ነገር ያለችው እንደሆነ፥ ወይም አንዳንዶቹ እንዳደረገቻቸው በጥፍርዋ «ነብር የዋለበት ያስመሰለችው» እንደሆነስ? ብትሩ ወይም ቁስሉ እንኩዋ ይህን ያክል የሚያም አይደለም፣ እሱ ምንም አደል። ከብትሩም ሆነ ከቁስሉ ይልቅ ውርደቱ እፍረቱ ነው የሚያመው! ከዚያም የከፋ ከሁሉም የባሰ ደግሞ፥ ከዚያ በሁዋላ ተጣልተው ተለያይተው ሊቀሩ የሚችሉ - መሆናቸው ነው! ከዚያ በሁዋላ «የመስተፋቅሩ አብነት» ሳይሰምር የቀረ እንደሆነ እንኩዋንስ ሌላው፥ እንኩዋንስ ያ ደመቀችን የግሉ ለማድረግ በናፍቆት የሚጠባበቀው ተስፋ ፍጻሜ ሊያገኝ እንዲያውም ባጠገብዋ ቆሞ፥ ወይም ተቀምጦ፥ እዬሳቀች ስታጫውተው ለዛዋ የሚቀሰቅሱት ፍትወት ይህ ሁሉ ሊቀር የሚችል መሆኑ ነው! ታዲያ ለዚህ ሁሉ መድሀኒቱ ፊቱን አይታ እሱ መሆኑን ሳታውቅ ሰርቆ የሚስምበት ዘዴ ቢገኝ ነበር! እንዲያ ያለ ዘዴ ማገኘት የሚቻል ቢሆን፥ «የመስተፋቅሩ አብነት» ከሰምረ እሰዬ! ነገሩ አለቀ ማለት ነው! ካልሰመረም ማን እንደ ሳማት ስለማታውቅ ባይህን ተጣልተው መለያየታቸው ይቅርና እንደገና ተመልሶ ያኑ «የንጽህና ወዳጅዋ» መስሎ ካጠገብዋ ሳይለይ በተስፋ መኖሩን ሊቀጥል ይችል ነበር! ብቻ - ከንፈሩ በፊቱ ላይ ሆኖ እንዴት እሱ መሆኑ ሳይታወቅ ሰርቆ ሊስማት ይችላል? አይ - ምነው ለያንለት ብቻ ከንፈሩ በሁዋላው፥ ከማንጅራቱ ስር በሆነ! » እንዲህ እንዲህ ያሉት ጥያቄዎች ነበሩ ደጀኔ መልስ አጥቶላቸው ሲያስቸግሩት የሰነበቱ።

በመጨረሻ ለችግሩ መፍትሄ ያገኘ መስሎ ታዬውና እሱ መሆኑን ሳታውቅ ሰርቆ የሚስምበት መንገድ ያገኘ መስሎ ታዬውና ደስ አለው።

ደመቀች ማታ እመቤትዋን ስታገልግል ስለምታመሽ፥ እስዋና ልጅዋ በሚኖሩበት ቤት ካራት ሰአት በፊት ገብታ አታውቅም። አንዳንድ ጊዜም እስከ አምስት ሰአት እዚያው እሳቸው ዘንድ ትቆያለች። ግብር ምላሽ እመቤትዋን ጉዋሮ አዙራ መልሳ፥ ልብሳቸውን ሲያወልቁ ረድታ አስተኝታ፥ እጅዋን ታጥባ ካደረቀች በሁዋላ፥ በጠቅላላ ገላቸውን በተለይ በጀርባቸው እሽት እሽት ከዚያ ለሰስ አድርጋ ዳሰስ ዳሰስ ስታደርጋቸው ወዲያው ያን ሰውነት የሚያዘና ለሰስተኛድ አሰሳ ተከትሎ እንቅልፍ ይመጣና ቀስ እያለ እያባበለ ይዘዋቸው መሄድ ሲጀምር፥ «በቃኝ እንግዲህ፥ ሂጂ ወግጅ ኤዲያ! » ይሉዋታል ያን እስዋ ያመጣችላቸውን የሚያባብል ውብ እንቅልፍ «መልሽ ልውሰድብዎ» ያለቻቸው ይመስል እንደ መቆጣት ብለው። ያንጊዜ እጅ ነስታ የስዋንና የልጅዋን ራት - እንጀራውን በዝርግ ሰሀን ወይም በስፌት መሳይ ወጡን በጎድጉዋዳ ሰሀን ይዛ ወደ ቤትዋ ትሄድና፥ ከዚያ በሁዋላ ወጡን አሙቃ እክልጅዋ ግር ራታቸውን በልተው ነበር የሚተኙ። ደጀኔ ያን ያክል ከመቤትዋ ጋር ማምሸትዋን ስለሚያውቅ፥ ግራ ጌታ ስንቄ የነገረውን «ፍቱን የመስተፋቅር አብነት» እንዲያ አምሽታ ወደ ቤትዋ ስትመለስ በመንገድ ጠብቆ ለመሞከር አቀደ።

«ቤትዋ ከልፍኙ አቁዋራጭ አጥር ራቅ ብሎ፥ ከዋናው አጥር ጥግ፥ ከማድ ቤቱ አጠገብ ስለሆነ፥ እሱ ማድቤት ሲጫወት ያመሸና ሰው ሁሉ ወደዬመኝታው ሲሰማራ ቀስ ብሎ ዘበኞች ሳያዩት የማታውን ጨለማ ለብሶ፥ በዚያ ላይ የደመቀች ቤት ዝንቦ የሚጥለውን ጥላ ደርቦ፥ ደግሞ በዚያ ላይ ኩታውን ተከናንቦ እጉዋሮ ይቀመጣል። ከዚያ ባጫጫር ጊዜ እዬተነሳ፥ ጥግ ለጥግ ወደ በሩ ጠጋ እያለ መምጣትዋን ሲጠባበቅ ይቆይና፥ ያቁዋራጩን አጥር ከፍታ ብቅ ስትል፣ ወደ ሁዋላ አፈግፍጎ በማይታይበት ጨለማ ውስጥ ቆሞ ይቆያል። ከዚያ የቤትዋን መዝጊያ ከውስጥ ልጅዋ እስኪከፍትላት ላጭር ጊዜም ቢሆን እበር ቆማ መቆዬትዋ ስለማይቀር፥ ያንጊዜ ከተሸሸገበት ድምጽ ሳያሰማ በግር ጥፍሮቹ እያጠቀሰ፥ እንደ ጥላ «ውልብ» ብሎ ይቀርብና፥ በሁለት እጆችዋ ራት በመያዝዋ መከላከል ስለማስትችል፥ አንገትዋን ይዞ አፍዋን ስሞዋት ይሮጣል። ከዚያ በሁዋላ አብነቱ ከሰመረ ‹ልብዋ አብሮት ይሮጣል› ካልሰመረም - መቸስ ምን ይደረገ? ካልሰምረ እሱ መሆኑ ስለማይታወቅ፥ ‹የንጽህና ወዳጅዋ› እንደ መሰለ የተሻለ እድል እስኪገጥመው ሲጠብቅ ያቆያል።

ደጀኔ እቅዱን እንዲህ አድርጎ በዝርዝር ከሰራ በሁዋላም፥ በግብር ለመፈጸም ድፍረት ድፍረት ስላነሰው፥ ስለፈራ፥ «ልበል፥ ልተው» እያለ ሲያመነታ ጥቂት ቀናት አሳለፈ። እንደዚያ ጊዜ ልቡ ተሸብሮበት፥ ልቡ ተጨንቆበት አያውቅም። ብቻ እንዲያ ልቡን የሚያሽብረውና የሚያስጨንቀው ነገር ፍራት ይሁን፥ ወይም ሌላ፥ ስም ሊያገኝለት አልቻለም። «እኔ ደጀኔ ፈሪ ነኝ እንዴ! ፈሪ አይደለሁም! » ይላል፥ ለማድረግ ያቀደውን ነገር ባሰበ ቁጥር ልቡ ከደረቱ ውስጥ ሮጦ ሊወጣ ሲንደፋደፍና ሁለመናውን ላብ ሲያጠልቀው ይመለከትና። «የለም እኔ ደጀኔ ፈሪ አደለሁም። ፈሪ አለመሆኔን እኔ ብቻ ሳልሆን ሰው ሁሉ ያውቃል። ስለዚህ ይች አጥማጅ - አንድ ሌላ ነገር አንድ ገርጋሪ ቢኖራት ነው እንጂ ፍራት አደለም እንዲህ - እኔ ደጀኔ ከነገርጋሪዋ አሳያታለሁ! » አለና ልቡ ፈርቶ «እንቢ» እያለ፥ ከሱ ያቀደውን ለማድረግ ቆረጠ።

አንድ ማታ ግብር ምላሽ ሆኖ ከደጃዝማች ስራየ ቤት በርከት ያሉ ሴቶችና ጥቂት ወንዶች ማድ ቤት ተሰብስበው እያወሩም፥ እዬተዳደሩም ሲያወኩ፣ ደጀኔም ገብቶ ተቀመጠ። ነገር ግን እዚያ ቢቀመጥም እኒያ ሰዎች የሚያደርጉትንም ሆነ የሚያወሩትን አያይም፥ አይሰማም ነበር። ለሱ የሚታየው ከደመቀች ጋር ሲገናኙ የሚሆነው በልዩ ልዩ መልኩ ተስሎ፥ የሚሰማው ስላቀደው እቅድ ልዩ ልዩኢ አሳቦች በራስ ውስጥ ሲንጫጩ ነበር። አንዳንድ ጊዜ ብቻ ከሚጫወቱት መሀከል ወደሱ ዘወር ያሉ እንደሆነ፥ በራሱ ውስጥ የሚተራመሰውን ያሳብ መንጋ ያዩበት መስሎት አይደነግጥና፥ የተናገሩትን ወይም ያደረጉትን ባያውቅም እንዲያው ግብኑን አብሮዋቸው ይስቃል። ደጀኔ እዚያ ገብቶ ከተቀመጠ ጀምሮ ከመሳቅ በቀር አንድ ቃል ሳይተነፍስ ወሬውና ድሪው እዬሞቀ እዬደራ ሲቀጥል አምሽቶ፥ የቀናቸው ወንዶች እዬማረኩ ያልቀናቸው እዬተከዙ ወደዬመኝታቸው ሲሰማሩ፥ እሱም ወደሚተኛበት እንደሚሄድ ወጣ አለና ማንም ሳያየው ከደመቀች ቤት ጥግ በጉዋሮ በኩል ሄዶ ከዝንበው ስር ተቀምጦ ይጠብቅ ጀመር። ማድ ቤት ተቀምጦ ያመሸበት ጊዜ ከመጠን ያለፈ ረዥም መስሎ ታይቶት፥ ደመቀችን ወደሚጠብቅበት እንዳይሄድ እኒያ ሰዎች እዚያ ከቤትዋ አጠገብ ያሉ ያቀደውን ማድረግ እንዳያጋልጠው ሰግቶ ዝም ብሎ እንዳይቀመጥ ስራዋን ጨርሳ የምትወጣበት ጊዜ ደርሶ ወደ ቤትዋ ገብታ እንዳታመልጠው ፈርቶ ጨንቆት ነበር። ከቢትዋ እዬተመለከተም መጠበቅ ከጀመረ በሁዋላ ደግሞ፥ የጊዜው ርዝመት ማድ ቤት ተቀምጦ ካመሸበት ብዙ እጥፍ ሆነበት! የግቢው ጭልታ መርፌ ብትወድቅ የሚያሰማ፥ ነፍስ ያለው ነገር ባጠገቡ እንደሌለበት የሙታን አገር ሁሉም ጸጥ፣ ያለ ሰጥ ያለ ነበር! ያን ጸጥታ የሚያውኩት የገዛ ትንፋሹና ልቡ ፈጥኖ ሲመታ የሚሰማውን ድውድውታ ብቻ ንበሩ! ብዙ ምእራፍ እንደ ሮጠ ቶሎቶሎ ሲተነፍስና የተጨነቀ ልቡ

መዝጊያውን ሰብሮ መውጣት እንደ ፈለገ ሁሉ በሀይል ሲመታ። እንኩዋን ለሱ ባጠገቡ ሰው ቢኖር በሰማ!

ደጀኔ፥ እንዲያ ልቡ በሀይል እዬመታና ቃታ እዬተናነቀው በዬደቂቃው እጉዋሮ ከተቀመጠበት ተነስቶ ወደ በሩ ቀረብ እያለ ሲመለከት፥ ከዚያ ተመልሶ ሲቀመጥ፥ አንዳንድ ጊዜም የተቀመጠ መስሎት ሳይቀመጥ ወደ መቀመጫው ደርሶ ሲመለስ ቆዬና «ይች - ይች አጥማጅ ዛ - ዛሬ ምን ሆነች? ይህን ያክል ስም አም - አምሽታ አታውቅም! » አለ፥ ቃታ እያደናቀፈው። ታዲያ ያንጊዜ ለሱ መሰለው እንጂ ድሮ ከምትወጣበት ካራት ሰአት በላይ አላመሸችም። በመጨረሻ ደመቀች በር አጠገብ ቆሞ የመምጫዋን አቅጣጫ ሲመለከት ቆይቶ ሊመለስ ሲል ያቁዋራጩ አጥር የቆርቆሮ በር ሲከፈትና ሲዘጋ ስለ ሰማ «እስዋ ናት፤ መምጣትዋ ነው! » አለ ያን ያክል በናፍቆት ሲጠብቀው የቆዬው ነገር ሲሆንለት ልቡ በመደሰት ፈንታ ፈርቶ እየተሸበረ።

ያነለት ሰማዩ፣ የጨረቃና የከዋክብት ብርሀን የማይታዩበት ደመናማ ስለ ነበረ፥ ማታው ጨለማ ነበር። ደመቀች በዚያ ጨለማ የስዋንና የልጅዋን ራት በግራና ቀኝ እጆችዋ ይዛ፥ እንዳትደናቀፍና የያዘችው እንዳይወድቅባት ቀስ እያለች፥ እዬተጠነቀቀች ወደ ቤትዋ ስታመራ፥ በጨለማ ውስጥ የሚንቀሳቀስ፥ የሰው መልክ ሳይኖረው የሰው ቅርጽ ያለው ከማታው ጨለማ ይብስ የጠቆረ ጥቁር መንፈስ መስላ ታስፈራ ነበር! እንዲያ በሚያስፈራ ጥቁር ግርማ ቀስ እያለች ወደ ቤትዋ በር ስትቀርብ፥ ደጀኔ አመጣጥዋን ሲመለከት ከቆዬበት ወደ ሁዋላ አፈግፍቶ በማይታይበት ጨለማ ውስጥ ገብቶ ቆሞ ይጠብቅ ጀመር።

«አብዬ ተኝተሀል? ተነስ ክፈትልኝ» አለች፥ እንጀራ ያለበት ዝርግ ሰሀን በግራ እጅዋ በርበሬ ወጥ የሞላ ጎድጉዋዳ ሰሀን በቀኝዋ እንደያዘች እበር ስትደርስ። ልጅዋ ተከስተ በጊዜ ኩራዝ አብርታለት እንደ ሄደች አልጋው ላይ ሲጋደም፥ ሲነሳ አንዳንድ ጊዜም እንቅልፍ ሽልብ እያደረገ ሲመልሰው አምሽቶ፥ የናቱን ድምጽ ሲሰማ በደስታ ዘሎ ተነሳና -

«እመዬ መጣሽልኝ? » አለ፥ መዝጊያውን ሊከፍት ወደ በሩ እዬሮጠ። ያንጊዜ፥ ተከስተ በሩን መክፈቱና ደመቀች ከመግባትዋ በፊት፥ ደጀኔ ከተሸሸገበት ቀስ ብሎ በግር ጥፍሮቹ እዬቆመ መጥቶ፥ ከሁዋላዋ አንገትዋን ይዞ ወደሱ ሊያዞር ሲሞክር «ዋ - የታባትህ! » ብላ ጮሀ ዞረችና በቀኝ እጅዋ የያዘችውን ጎድጉዋዳ ሰሀን ሙሉ በርበሬ ወጥ በራሱ አከናነበችው! ልጅ ክንፌ ለባላምባራስ ተካ አጋነው እንዳወሩት «አፍላል

ሙሉ በርበሬ ወጥ» ሳይሆን፥ ጎድጉዋዳ ሰሀን ሙሉ በርበሬ ወጥ በራሱ አከናነበችው እሱም ቢሆን ብዙ ነው! እንኩዋን ጎድጉዋዳው ሰሀን ሙሉ የበርበሬ ወጥ ፍንጣቂም አይንካ እንካ ከነካ ያሳብዳል! ደጀኔ የደመቀችን መምጣት እንዳዬ፥ ሲቃ ይዞት ወዲያና ወዲህ ሲንቆራጠጥ የተከናነበው ኩታ ከራሱ መውረዱን ልብ አላደረገ ኖሮ በኩታው ፈንታ እስዋ ያከናነበችው በርበሬ ወጥ ከራሱ እዬወረደ ፊቱን ሁሉ እያጥለቀለቀው፥ ባይኖቹ፥ ባፉና ባፍንጫው ገብቶ ትንፋሹ እስኪቆረጥ እያሳለና እያስነጠሰ መድረሻ አሳጣው! ወዲያው እንዲያ ሳልና ማስነጠስ ሲያጣድፉት፥ እስዋን ትቶ፥ እንባው ከልሀጩ ጋር ተደባልቆ እዬተዝረከረከ፥ እውር ድንብሩን መሬቱንም፥ አዬሩንም እየዳበሰ፥ የሚሄድበትን ሳያውቅ ማድ ቤት ደረሰ። ማድ ቤት የተኙት ሴቶች የደመቀችን ጩኸትና የልጅዋን ልቅሶ ሰምተው «ምንድን ነው? » እያሉ ደንግጠው ሲወጡ «ው - ውሀ፥ ስለግዜር ውሀ እባ - እባካችሁ፥ ራሴንና ፊ - ፊቴን አጥ - አጥብበት ውሀ! » አለ ደጀኔ እንዳቃጠሉዋቸው ጣምራ ሻማዎች እዬነደዱ የሚፈሱ አይኖቹን በሁለት እጆቹ ይዞ ንግግሩን ሳልም ማስነጠስም እያቁዋረጡት። ከዚያ፥ ሴቶች በመጥለቂያ ያመጡለት ውሀ ራሱና ፊቱ የለበሱትን በርበሬ ወጥ ሊያስወግድ ስላልቻለ፥ በባሊ አምጥተው ያፈሱበት ጀመር። እንዲያ ሴቶቹ እዬረዱት ራሱንም፥ ፊቱንም ሲያጥብ፥ ዘበኞች ጫጫታውን ሰምተው «ምን ሆናችሁ? » እያሉ ከታች፥ ከዋናው በር መምጣታቸውን ሰምና አይኖቹን በልብሱ እዬጠራረገ፥ ቶሎ ወደ ማድቤቱ ጉዋሮ ዘወር ብሎ ቆይቶ ከዚያ - ዘበኞች ከሴቶች ጋር ጫጫታው ስለ ተነሳበት ምክንያት ሲነጋገሩ - አጥሩን ሳይለቅ፥ ጥግ - ለጥግ በጁ እየዳበሰና አንዳንድ ጊዜ አይኖቹን ብልጭ - ድርግም እያደረገ ከዋናው በር ሲደርስ ወጥቶ ሄደ። ዳግመኛ አልተመለሰም። እፍረትና የጌታውን ትእዛዝ የመተላለፉ ፍራት ባይሆን ላይ ሆነው ከዚያ ቤት አባረሩት!

ደመቀች ከድንጋጤዋ እንደ ወጣች፥ ልጅዋ በጭኖችዋ ተጠምጥሞ «እሪ» ይል ስለ ነበረ፥ እሱን ወደ ማባበሉ ገብታ፥ አደጋ ጥሎባት የሸሸውን ሰው ለመከተልና ለማየት ስላልሞከረች፥ የማድ ቤት ሴኦች እስኪነግሩዋት ድረስ ደጀኔ መሆኑን አላወቀችም ነበር። ካወቀች በሁዋላ እንኩዋ ማመኑ አስቸግሮዋት ነበር። ነገር ግን ከዚያ ሌሊት ማግስት ጀርሞ መሰንበቻቸውን የግቢ ስራ የቤት በደጀኔና በስዋ መሀከል የተደረገውን የስዋን ጀግንነትና እይሱን ጅልነት እያጋነነ እያወራ ሲያወካ ከመሰንበቱ ሌላ፥ የሱ መጥፋት የሰማችው እውነት መሆኑን ስላረጋገጠለት፥ ማዘን ብቻ ሳይሆን የብቸኝነት ስሜት፥ መንፈስ ጭንቀት ጭምር ተሰማት። እስከዚያ ጊዜ ድረስ

ሊያጠቁዋት በዬጊዜው ከሚነሱት ጎረምሶች ጋር ስትዋጋ «ከናቴ የደንግያላይቱ» ሌላ «ይረዳኛል» ብላ የምትተማመንበት፥ መመኪያዋ እሱ ብቻ ነበር። አሁን እሱም ከስዋ ተለይቶ ካጥቂዎችዋ ከጠላቶችዋ ጋር ተሰለፈ!

«ወይ ጋሽ ደጀኔ -! እሱም እንዲያ ሳምነው - እንዲህ ሊያደርግ! ለካስ - ወንድ ሲባል ሁሉም ያው ነው! ስለዚህ - ወንድ ማመን ከንቱ ነው! » አለች፥ «ልውደድሽ» ማለቱን «ልረድሽ» ያላት ይመስል እንደ ብርቱ ክህደት፥ እንደ ብርቱ ጠላትነት ቆጥራው። እስዋ የምታውቀው የወንድ መውደድ እንደ ማረድ ስለሆነ ለግብረ ስጋ ወደጅነት የሚቀርቡዋትን ወንዶች ሁሉ ሊያርዱዋት እንደ ቀረቡ ጠላቶችዋ ነበር የምታያቸው! ታዲያ እደጃዝማች አሰፋ ቤት ከገባች ጀምሮ ደጀኔ እስካነቃት ድረስ ምንም ያክል ሰላም ስላልነበራት ካንድ የጎጃም አራጅ ሸሽታ፣ ብዙ ያዲስ አበባ አራጆች መሀከል በመግባትዋ ዙሪያው ገደል ሆኖባት እንደገና ከዚያ የምትሸሽበት መንገድ ጠፍቶዋት ተጨንቃ ነበር። ደግነቱ እዚያ ቤት በቆየችበት ጊዜ ያስቸግሩዋት ከነበሩት ጎረምሶች ደጀኔ የመጨረሻው መሆኑ ነው። ከዚያ በሁዋላ፥ እንዳሽናፊዎች ሁሉ ጠላቶችዋ ሁሉ አሸንፋ ሰላም አገኘች።

## ምዕራፍ አስር

# ደመቀችና ወይዘሮ ጽጌ

ደመቀች ምንም እንኩዋ በግብረ ሥጋ ለሚከጅሉዋት፥ ስትቆጣ እንደ አራስ ነብር የማታስቀርብ መሆንዋ ስለ ታወቀላት፥ ሁሉም ተስፋ ቆርጦ ትቶዋት ሰላም ብታገኝ፥ የመቤትዋ፥ የወይዘሮ ጽጌ አመል እንኩዋንስ ሰው አህያ የማይችለው ከባድ ስለሆነ፥ ሰላምዋ ሙሉ አልነበረም። እዚያ ቤት ተቀጥራ እስክትገባ ድረስ አሽከር ሆና ባታውቅም ካሽከሮች ጋር ስላደረገችና «ጥሩ አሽከሮ» የሚባሉት የሚያደርጉት ታውቅ ስለ ነበረ እንደነሱ ጥሩ አድርጋ ሰርታ እንደነሱ «ጥሩ አሽከር» ለመባል አጥብቃ ትጥር ነበር። እውነትም ከደጃዝማች ጀምሮ በቤት ውስጥም ሆነ በጎረቤት ከወይዘሮ ጽጌ በቀር፥ በስራዋ የማያመሰግናት አልነበረም። ባጭር ጊዜው ውስጥ «አሽከር ብሎ ዝም» የሚባል ስም ወጥትሎላት ነበር። ወይዘሮ ጽጌ ግን ምንም ማለፊያ ሰራተኛ መሆንዋን

ልባቸው ቢያውቅ የልባቸውን ስሜት አፋቸው መስክሮ አያውቅም። ይህ እንኩዋ በምነት ላይ የተመሰረተና ልማድ አድርገው የያዙት ጭምር ሆኖ ነው። እንዲያው ከበላዩ ወይዘሮ ጽጌ የተቀጠረ አሽከር የተቀጠረለትን ስራ በትክክል ሰርቶ የተቀጠረበትን ደመወዝ በትክክል ካገኘ ከዚያ አልፎ ማመስገኑ ሆነ ማቆላመጡ የማያስፈልጉ፥ ትርፍ እንገሮች መሆናቸውን የሚያምኑ ናቸው። ‹ላሽከር ሲስቁለት ለበቅሎ ሲወርዱለት ነጥቆ መጋለብ ያምረዋል› እንደሚባለው «ላሽከር ፊት ሲሰጡት፣ ዋዛ ፈዛዛ ሲያሳዩ ደግ አይደለም፥ ይንቃል» ይላሉ። ስለዚህ፥ የሚያጠፉትንም የሚያለሙትንም አሽከሮቻቸውን ባንድነት በተቁዋረጠና በተኮማተረ ፊት የሚመለከቱ በመሆናቸው ዘለግ ያለ ጊዜ አብሮዋቸው የሚቆይ አሽከር የለም። ከዚህ ሌላ፥ በተለይ የደመቀችን ቀንበር ያከበደው፥ የቀጠሩዋት ባልዮው፥ ደጃዝማች አሰፋ በመሆናቸው ነበር።

ወይዘሮ ጽጌ እጅግ ዘመደ ብዙ ስለሆኑ ብዙ ጊዜ፥ ደጃዝማች ካዲስ አበባ ወጥተው በሚሰነብቱበት ጊዜ የቅርብም ይሁን የሩቅ ዘመድ ይሰበሰቡና - መቸም ቤታቸው ሙሉ ነው - እዬተበላ እዬተጠጣ ጨዋታና ውካታ ይሆናል። ከዚያ ጨዋታው ሲደራ የቤቱ እመቤትም ከዘመዶቻቸው ጋር የገዛ ጠጃቸውን በርከት አድርገው ጠጥተው በዚያ ላይ ኮኛክ ወይም ሌላ የፈረንጅ አረቄ አከታትለው ጨምረው ሞቅ ሲላቸው ያዩና፣ ከዘመዶቻቸው መሀከል ሲያሾከሹኩ፥ ባለቤትዋ አዛዡን ጠርተው «ለገሊት ይህን ያክል ቅቤ ለገሌ ይህን ያህል ማር ለገሊት ይህን ያክል ጤፍ ለገሌ ይህን ያክል፥ በርበሬ ስጥልኝ» ብለው በታላቅ ልግስና ለሁሉም እንደየብሶቱ ይዳርጉና ሁሉን ከፍነሩን እዬመጠጠ «እግዜር ለኛ ሲል ያኑርሽ፥ እግዜር መግቢያ አያሳጣን፥ መግቢያችን መሰብሰቢያችን አንቺ ባትኖሪ ማን ይሰበስበን ኖሮዋል? ሊላው ቀርቶ እስበሳችን መገናኘታችንስ ባንቺ አይደል? እግዜር የሁላችነን ልመና ሰምቶ፥ የሁላችነን እንባ አይቶ ላንድ ፍሬ ያብቃሽ» ብሎ እዬተቀባበለ ሲመርቅ ሲሰሙት፣ ደስታና ኩራት ባንድ ላይ ተደባልቀው ከመጠጡ የመለጠ ሞቅ ያደርጋቸዋል! በሁዋላ ብቻ የመጠጡም የከንቱ ውዳሴውም ሞቅታ ሲያልፍ፤ የባላቸው ቁጣ ይታያቸውና ፍራት ይገባቸዋል። መቸም ሊያዝዙትና ሊገዙት የማይቻል አመል ሆኖባቸው ነው እንጂ ወድው አደለም። ሞቅታቸው ካለፈና ዘመዱም በልቶ ጠጥቶ የያዘውን እዬያዘ ከሄደ በሁዋላ ሁልጊዜ ራሳቸውንም ዘመዶቻቸውንም ይወቅሳሉ። ነገር ግን አብሮ የኖረ አመል የሰውነት ክፍል በመሆኑ፥ በመጸጸት የሚገላገሉት ስላልሆነ ተመልሶ ያው ነው። ደጃዝማች ከሄዱበት ተመልሰው በሌሉበት የሆነውን ሁሉ ሲሰሙ መብል መጠጡም ሆነ ስጦታው «ይጎዳኛል» ብለው ሳይሆን፥ የሳቸው እግር

እዬተጠበቀ መደረጉ ብቻ ያሳዝናቸውና፥ የሚበዛውን ጊዜ አኩርፈው እስከ ሁለትና ሶስት ቀን ሚስታቸውን ቅን ሳያነጋግሩ ይቆያሉ። አንዳንድ ጊዜ ግን አልችል ይሉና ቁጣችው በፊታቸው ሲነድ እዬታዬ ምርር ያለ፥ አንጀት የሚቆርጥ ነገር ይናገሩዋቸዋል።

«እኔንኮ የሚገርመኝ» ይላሉ ደጃዝማች። «እኔን የሚገርመኝ ማብላት ማጠጣትሽ፥ ወይም ስጦታ መስጠትሽ አይደለም። ሰው በቤቱ እንኩዋንስ ዘመዱን ባእድ ያበላል ያጠጣል፥ ስጦታም ይሰጣል። ስለዚህ እሱ አይደለም የሚገርመኝ። የሚገርመኝ፥ እግዚአብሔር ሳይፈቅድ ቀርቶ ከኔ ልጅ ባይሰጥሽ፥ የረዥም ጊዜ ምሽቴ ሆነሽ ቤቴ ቤትሽ ሀብቱ ሀብትሽ ሆኖ ሳለ እንደ ሌባ የኔን እግር እዬጠበቅሽ የገዛ ሀብትንሽ መስረቅሽ ነው! ይህ ነው የሚገርመኝ! ያንቺ ዘመንዶች አይደሉም? ምናለ እኔ ባለሁበት ቢመቱና አብረን ብንበላ ብንጠጣ? የተቸገረስ ካለ አብረን እዬተማከርን ብንሰጥ? መቸ ነው ያንቺን ዘመዶች እኔን እንደ ዘመድ ቆጥረው አብረውኝ የሚበሉ? መቸ ነው? መቸ ነው እንደ ጠላት ተሸሽገው መጥተው ቤቴን መዝረፉን የሚተው? » ሲሉ፥ ወይዘሮ ጽጌ አንድ ቃል አይመልሱም። ሁሉንም ውጠው ዝም ይላሉ። ከዚህ ሁሉ የሚያመቸው ደጃዝማች ይህን ምክንያት አድርገው፣ ልጅ መውለድ የማይችሉ በመሆናቸው መውቀሳቸው ነው። በሱም ቢሆን ቢበዛ ያለቅሱ እንደሆነ እንጂ መልስ አይሰጡም።

ወይዘሮ ጽጌ ለባላቸው ኩርፊያም ይሁን ቁጣና ስድብ መልስ የሚሰጡ ሁዋላ ነው። ያውም ቢሆን በቀጥታ ለደጃዝማች አይደለም፤ የለም! ለደጃዝማች አይን ለሚያዩት፥ የደጃዝማች ወገን አድርገው ለሚቆጥሩት ነገር ግን እንደ ደጃዝማች ሊቆጣ፥ ሊሳደብ ሊማታ፥ ለማይችል ደካማ ነው! እንዲያ ያለ ደካማ የደጃዝማች ወገን፥ እንዲያ ያለ በደጃዝማች አይን የሚታይ ደሀ ሲገኝ ወዮለት! የደጃዝማችን ብድር በብዙ እጥፍ ይከፍላል! ወይዘሮ ጽጌ እንዲያ ያለ የደጃዝማች ወገን አድርገው ቆጥረው ቂማቸውን የሚወጡበት ደከማ ምንም ቢሆን አጥተው አያውቁም፤ ባይሆንም እሳቸው ያደርጉታል! በዚያ ጊዜ እንደ ደጃዝማች ወገን ተቆጥራ እዳ ከፋይ የሆነችው ደመቀች ነበረች። ምክንያቱ ደጃዝማች ስለ ቀጠሩዋትና በሳቸው በኩል የመጣች በመሆንዋ ነው እንጂ ሌላ የሳቸው ወገን ተብላ፥ በሳቸው አይን የምትታይበት ምክንያት አልነበረም።

ደመቀች፣ «የውስጥ አሽከር» ትባል እንጂ የማሰራው ስራ አልነበረም። የመቤትዋን ልብስ አጥባ፥ የገላም ይሁን የፊት ውሀ አሙቃ፥ ገላቸውን አንዳንድ ጊዜ፥ እግራቸውን ሁልጊዜ፥ አጥባ፥ ለሳቸው ሆነ፥ ለሚመጣው እንግዳ፥ ሁሉ ቡና አፍልታና

መብል መጠጥ አቅርባ፣ ለብቻቸው ሲሆኑ ተቀምጠው እድነ ሆነ እግራቸውን ተጋድመው እንደሆነ ጀርባቸውን አሽታ፥ ጥዋት ጥዋት ሁልጊዜ መጽሀፋቸውን አቅርባ ሌላም ብዙ ስም አይጠሩ ስራ ሰርታ ነው። መጽሀፋቸውን ደግመው ጨርሰው በቃላቸው ውዳሴ ማርያም መልከ ማርያም፥ ወይም ሌላ መልክ ሲደግሙ፥ ሰፊ ባለግር መስታወት እፊታቸው ታቆምና እሳቸው ባንድ በኩል እዬደገሙ ባንድ በኩል ባንድ በኩል እዬተመለከቱ፥ ጠጉራቸውን በመቀስ አስተካክላ ስታበጥር አንድ ጠጉር እንኩዋ ከመቀሱ አምልታ፥ ሳትተካከል ቀርታ በመስታዋቱ ያዩ እንደሆነ፥ ቁጣቸው እንደሳት ነዶ እ.እ.እ.? ህም -! » ይላሉ በጸሎት ቁዋንቁቃ፥ ያመለጠችውን ጠጉት በጃቸው እያመለከቱ። በግእዝ የተደረሰ ጸሎት በተያዘበት ጊዜ አቁዋርጦ ባማርኛ መናገር ፍጹም ክልክል መሆኑን የንስሀ አባታቸው በጥብቅ ስላስጠነቀቁዋቸው ወይዘሮ ጽጌ ውዳሴ ማርያም፥ ወይም ማናቸውን መልከ በሚደግሙበት ጊዜ ሳይጨርሱ አንድ ነገር ለማለት የተደደኡ እንደሆነ «እ.እ.እ.» በማለት ነበር የሚገልጹት። «እ.እ.እ.» ከጅ ጥቅሻውና ምልክቱ ጋር ምን ማለት መሆኑን በትክክል ተርጉመው የተባሉትን መፈጸም የታዛዦቹ ፈንታ ነው። ቢሳሳቱ ወዮላቸው!

ይህ «እ.እ.እ.» ከልዩ ልዩ የጅና የሌላ ምልክቶች ጋር እንኩዋ የደመቀች እናት፣ ወይዘሮ ሙሉነሽ ጸሎት በያዙ ጊዜ ትእዛዛቸውን ከሚገልጹበትና መልስ ከሚሰጡበት ጋር ከሞላ ጎደል ተመሳሳይ ስለሆነ ደመቀችን እምብዛም አላስቸገራት። እስዋን በጣም ያስቸግሩዋትና ግራ ያጋቡዋት ከነበሩት እንገሮች አንዱ፣ የትእዛዛቸው መለዋወጥ ነው። ወይዘሮ ጽጌ በጣም ቅብጥብጥ ወይዘሮ ስለ ነበሩ ሳያስቡ እንዲሁ አፋቸው እንዳመጣ ትእዛዝ ይሰጡና ካጭር ጊዜ በሁዋላ የሰጡትን ትእዛዝ ረስተው ሌላ፣ እሱን የሚያፈርስ ትእዛዝ ይሰጣል። ስለዚህ «ስሪው አርሺው፣ ውሰጂው መልሺው ጣይው አንሺው ቅጂው አፍስሺው» ሲሉ እስዋ መድከምዋ ሳይቀር ስራው ሳይተናቀር ቀኑ ያልፍና፥ «አልሰራሽም» ብለው ተበሳጭተው የስድብና የርግማን መአታቸውን ሲያወርዱባት የምታደርገው ቅጡ ይጠፋታል። ከዚህ ሌላ መልካም ከሰራች ደስ ብሎዋቸው የሚያመስግኑዋት መስሎዋት ሳያዝዙዋት መልካም የሰራች እንደሆነ ስራውን ባይጠሉ እንኩዋ ሳያዝዙዋት መስራትዋ ብቻ ያስቆጣቸዋል። አንዳንድ ጊዜ ደግሞ ያዘዙዋትን፥ ልክ እንደ ታዘዘችው ሰርታ ሌላው ያልታዘዝሽው ተወዝፎ የቀረ እንደሆነ «ካልታዘዝሁ ምን ቸገረኝ ብለሽ፥ ለግመሽ ነው እንዲህ ወዝፈሽ የተውሽው፥ አንቺ ልግመኛ! » ብለው ይሰድቡዋታል። እንዲያው በማናቸውም መንገድ የምስትሰራውን ሁሉ መንቀፍ ባይችሉም ጥሞዋቸው አይቀበሉትም፤ ቢጥማቸው እንኩዋ «ጣመኝ» ብለው አያውቁም።

ታዲያ ይህ ሁሉ ልማዳቸው ሆኖ ከስዋ በፊት በነበሩት የውስጥ አሽከሮቻቸው ሁሉ ያደርጉት የነበረ ነው እንጂ በተለይ፥ እስዋን ለማስቸገር በለው የፈጠሩት አይደለም። ከዚህ ሌላ፥ ሴት፥ ይልቁንም፣ እመጫት ሴት አይወዱም ነበር። ለወንዶች ብቻ ለሴቶች የሚከፋትን ያክል ከፍተው አያውቁም። ሴቶችን በተለይ እመጫት ሴቶችን መጥላቱም ቢሆን ምክንያቱን እሳቸው፥ ራሳቸው እንኳዋ ሊገልጹት የማችሉ፥ ሁዋላ የመጣ ነገር ነው እንጂ እድሜያቸው ሙሉ አብሮዋቸው የኖረ አደለም። ከዚህ በተረፈ፣ ወይዘሮ ጽጌ ሀይማኖተ ጽኑ፥ እጅግ ኩሩና የገዛ ስጋቸውን ቆርጠው ቢበሉት የማያማቸው ለጋስ እመቤት በመሆናቸው በሰፊው የሚደነቁ ነበሩ።

ደመቀች መጀመሪያ እመቤትዋ እንዲያ መቅበጥበጣቸውና አመላቸው መከፋቱ ስራዋ ባይስማማቸው መስሎዋት ‹ከዛሬ ነገ ያባርሩኛል› እያለች ትፈራ ነበር። ሁዋላ ግን ጊዜ እያለፈ በሄደ መጠን ስራዋን እንደማይጠሉ ባንዳንድ ምልክቶች ስለ ተረዳች አሳብዋ ማረፍ ጀመረ። ለምሳሌ ገላቸውን ለማጠብም ሆነ ጀርባቸውን ለማሸት ከስዋ በቀር የሌላ ሰው እጅ ሲነካቸው አይወዱም። ሌሎች ያፈሉትን ቡና ‹ቀጠነ ወይም ወፈረ› ይሉና እንደ ገና እስዋ እንድታፈላ ከስድብ ጋር ያዝዙዋታል። ይልቁንም ስጋትዋን ያካፈለቻቸው አንዳንድ እዚያ ኖረው አመላቸውን የሚያውቁ ወዳጆችዋ በጠቅላላው አመላቸው እንዲያ አስቸጋሪ መሆኑንና እንዲያውም ከስዋ በፊት ለነበሩት የውስጥ አሽከሮቻቸው አንጻር፥ እስዋ ‹ልውጣ ካላለች እሳቸው ‹ውጪ› እንደማይሉዋት ካረጋገጡላት በሁዋላ ልብዋ ጸጥ አለ። ወይዘሮ ጽጌ ከክፉ አመላልቻው ሁሉ ቢቆጡ ቢሳደቡ ቢራገሙ «ጣሉልኝ ብለው ቢያስደበድቡም ይህን ሁሉ ያልቻሉ አሽከሮች ራሳቸው ይወጣሉ እንጂ፥ «ውጡልኝ» በልው አያውቁም።

ደመቀች መቸም ከዚያ ቤት አንገትዋን አንቀው፥ አውጥተው ካልጣሉዋት በቀር፣ የወይዘሮ ጽጌ አመል ስለ ከፋባት ወይም ስራቸው፥ ስድባቸውና ርግማናቸው ስለ በዛባት መውጣት የማትፈልግባቸው ምክንያቶች ነበሩ። አንዱ የባልዋ ፍራች ነው። ባልዋ ታምራት ተገኘ አዲስ አበባን ልክ እንዳገሩ፥ እንደ ኤልያስ ስለሚያውቀው እስዋን ፍለጋ የመጣና ልትከላከል በማትችልበት ቦታ ያገኛት እንደሆነ እጅዋን አንጠልጥሎ ይወስዳታል። የደጃዝማች አሰፋ ቤት ግን ልክ እንደ ታቦት መቅደስ የታፈረ ስለሆነ፥ ዚያ እስካለች ድረስ የሚደፍራት የለም። ሁለተኛ ልጅዋን ተከስተን ደጃዝማች ይወዱታል። ከዋሉበት ሲገቡ በመንገዳቸው ያገኙት እንደሆነ አንስተው እንደ ልጃቸው ስመው፣ ወደ መቀመጫቸው ይወስዱና ጨዋታው ደስ ይላቸው ስለነበረ፥ «አሜውተኝ» ይሉታል፥ በግብርም ጊዜ እዚያው ግድም ከተገኘ ባጠገባቸው አስቀምጠው ያጎርሱታል። እንዲያውም አንዳንድ ጊዜማ አስበው ልብስ፥ ወይም

መጫወቻ ገዝተው ያመጡለታል። ተከስተም ስለሚወዳቸው አይፈራቸውም። ስለዚህ ደመቀች ይህን ሁሉ ስታይ፥ የትም ብትሄድ ለስዋ የምትስማማ እመቤት ታገኝ እንደሆነ እንጂ ለልጅዋ እንደ ደጃዝማች ያለ የባእድ አባት ልታገኝ የማትችል መስሎ ይታያታል። በዚህ አንጻር የወይዘሮ ጽጌን ክፉ አመል፥ ስድባቸውንና ርግማናቸውን ሁሉ ባንድ ላይ ሰብስባ አስቀምጣ ስትመዝነው ጭራሽ ምንም አደል! ከችቦ ገለባ የቀለለ ሆኖ ታገኘዋለች።

ብቻ እመቤትዋ ሲረግሙዋትም ሆነ ሲሰድቡዋት ዝም ብላ ስትሰማ ቆይታ እጅ ነስታ ከመሄድ በቀር ትንፋሽ ባይወጣትም በድቡና በርግማኑ መሀከል ልጅዋን የነኩባት እንደሆነ ዝም አትላቸውም። ያንጊዜ ትመልስላቸዋለች። እሳቸውም ከጊዜ ብዛት ልጅዋን ሲነኩባት በጣም እንደሚያማት ስላወቁ፥ ለማሳዘን፥ አንጀትዋን ለመቁረጥ ሲፈልጉ ልጅዋን ያነሳሉ። መቸም ወይዘሮ ጽጌ ተቆጥተው ሲራገሙና ሲሳደቡ፥ ቃል መርጠው አያውቁም። ከልባቸው ሳይሆን፥ ከጉሮሮዋቸው በላይ አፋቸው የሚተፋውን እንዲሁ እንደ መጣ በተቆጡት ሰው ላይ መለጠፍ ነው።

አንድ ቀን ባላቸው ሀረር በሄዱበት ዘመዶቻቸው ብዙ ጊዜ እንደሚያደርጉት ተሰብስበው መጥተው በልተው፥ ጠጥተው የብዙ ጊዜ ስንቃቸውን እዩያዙ ከሄዱ በሁዋላ፥ ወይዘሮ ጽጌ የመጠጡና የከንቱ ውዳሴ ሞቅታ እንደ ማለፍ ሲልላቸው መለስ ብለው ዘመዶቻቸውም እሳቸውም፥ ያደረጉት ትውስ ሲላቸው እንዲያ ያለ ነገር በተደረገ ቁጥር ባላቸው ተቆጥተው የሚናገሩት አንጀት የሚቆርጥ ነገር ትዝ ስላላቸው ራሳቸውን መውቀስና ዘመዶቻቸውን መርገም ጀመሩ። መብል መጠጡ እንኩዋ ግዴለም መቸም - ሰው እዘመዱ ቤት ገብቶ «እህል ውሀ» ሳይባል አይወጣም። ነገር ግን ጤፉ አተሩ፥ በርበሬው፥ ቅቤው፥ ማሩ፥ ዘይቱና፥ ሌላው ለሰርግ ማሰረጊያ ለተዝካር ማውጫ ለዝክር መዘከሪያ ለክርስትና፥ ወ.ዘ.ተ. እዬተባለ የተሰጠው፥ ዝርዝሩን ከነድምሩ ባያስታውሱትም በጣም ብዙ ነው፥ ልክም የለው! «አየ -! አሉ ወይዘሮ ጽጌ፥ ብቻቸውን እንደ ተቀመጡ ዝም ብለው ይህን ሁሉ ሲያስቡ ቆይተው ‹አየ - ! ምነው ጌታየ፥ ወይ ለኔ ልብ አትሰጠኝ ወይ እነሱ ወዲያ ጥርግ፥ ሙጥጥ አታደርጋቸው! አየ - ከዚህ ሁሉ ያለ ዘመድ ብቻን መፈጠር እንዴት መታደል ነው! እኔ በነሱ ምክንያት ዘላለም ስሰደብና ስወቀስ የምኖር ምን በወጣኝ ነው? እሳቸው - ገና ሲመጡ ሰይጣን ይሁን ምን «ሹክ» የሚልላቸው ስለማያጡ ይህን ምክንያት አድርገው - እኔ በጀ እሰራው ይመስል ያፉቸው መውቻ «ልጅ አልወለድሽልኝም» ነው! ታዲያ እሱስ ቢሆን ባንተ እጅ አደል ጌታየ? ምን ቸገረህና፥ - በዬቤቱ ተቀጥረው

ለሚኖሩ ገረዶችና ይልሱት ይቀምሱት ቁራሽ እንጀራ አጥተው እዬዞሩ ለሚለምኑት ለማኞች፥ ሳይፈልጉት የምትሰጠውን ልጅ እኔን ነፍገህ ስታስወቅሰኝ ትኖራለህ? አባክህ «ቢቃሽ» በለኝ ጌታዬ እባክህ ላንድ ፍሬ አብቃኝ። ሌላ ምንም አል - አልለምንህ› ሲሉ ልቅሶ እዬተናነቃቸው ደመቀች የተበላበትንና የተጠጣበትን እቃ ስታጥብ ቆይታ ስትመጣ ዳናዋን ስለ ሰሙ አይኖቻቸውን ጠራርገው ፊታቸውን የተቆጡ ለመምሰል ኮስተር አድርገው ጠበቁዋት።

«አችኒ የታባትሽ ሄደሽ ነው ስትፈለጊ የማትገኝ? » አሉ፥ ገና ስትገባ።

«እቃ ሳጥብ ነበር እመቤቴ» አለች፥ እንዳመሰገኑዋት ሁላ ባክብሮት እጅ ነስታ።

«ጣዲያ ብታጥቢ - ቀኑን ሙሉ ነው እቃ የምታጥቢ? እንዲያው ምክንያት ብለሽው ነው እንጂ? »

«ቀኑን ሙሉማ እዚህ ሳሳልፍ ነበርኮ እመቤቴ! »

«ነፍስሽን ያሳልፋትና መቸ አባትሽ ነው- ስታሳልፊ የነበረ? ደሞ ከክፋትሽ ውሸትሽ መባሱ፤ አንቺ ውሸታም! »

‹ኧረ እዚሁ ሳሳልፍ ነው የዋልሁ እመቤቴ! ውሸቴ ከሆነ አባባ አዛዥ - ሌሎችም ይጠየቁ።»

«አዎ፤ አባባ አዛዥ! ‹ያይጥ ምስክርዋ ድንቢጥ› ሂጂ ወግጂ ከፊቴ አንቺ ክፉ አሳባቂ።»

ደመቀች እጅ ነስታ ዘወር ስትል፥

«የኔ ዘመዶችስ የበሉትንም ያልበሉትንም በዬሰአቱ እየሄድሽ ሹክ ትያለሽ፤ ያ ያንቺ ልጅ የሚውጠውን ማርና ቅቤ የሚጠጣውን ወተትስ አንድ እቅን ተናግረሽ ታውቂያለሽ? » አሉ፥ እስዋን ማናደድ ከተሰማቸው ከባድ ጭንቀት የሚያሳርፋቸው መስሎዋቸው።

«ኧረ እዚህ ከማገኘው፥ ከኔ ጋር ከመካፈል በቀር የኔ ልጅ እንኳዋንስ ማርና ቅቤ ሊውጥና ወተት ሊጠጣ ባይኑም አይቶ አያውቅም እመቤቴ! » አለች፥ ቁጣቸው እስኪበርድ ዘወር ብላ ለመቆየት የቃጣችውን ትታ ልጅዋን ስላነሱ ተመለሰችና።

«አዎ፤ ባይኑም አይቶ አያውቅ! እንግዲያስ - መላክ በስውር እዬመገበው ነው እንዲህ - እንደ ተነፋ ፊኛ የተቀበተተ! »

«አንዳንድ ጊዜ እግብር ላይ ጌቶች ከሚያጎርሱትና የኔን ድርሻ ተካፍሎ ከሚበላው በቀር፥ እስቲ በሌላ ጊዜ፥ እንኩዋንስ ማርና ቅቤ ሲውጥ ደረቅ እንጀራ ሴብላ ‹አይቻለሁ› የሚል ሰው ቢገኝ አሁን ልቀጣ! »

«መልኩ እዬመሰከረ! ሰውነቱ እዬመሰከረ! ሌላ ምስክር ፍለጋ መሄድ ያስፈልጋል? ይዘሽው ስትመጪ - ከውሀ አስጥተው እንዳዋሉት ያሳ ግልገል የጠወለገ፥ የለተተ አስቀያሚ እንደ ነበረ ሰው ሁሉ አያውቅም? ደሞ ማርና ቅቤዬን እዬሰረቀች እያዋጠች - ባይኑም አይቶ አያውቅ» ትለኛለች፤ ይች ውሸታም! ሂጂ ወግጅ፤ አሁን ከፊቴ ጥፊ፤ አይንሽን ያጥፋውና! »

«እኔን የቀጠሩኝን የፈለጉትን ይበሉኝ፤ ቢፈልጉም ይቅጡኝ ልጄን ግን በክፉ አይንዎ አይዩብኝ! ልጄን አይንኩብኝ! » አለች ፍትዋ በቁጣ ተለውጦ።

«አዎ፤ ያንቺ ልጅ ታቦቱ አይነካም! ሀ ሀ! እሱም ማርና ቅቤዬን ወተቴን አይንካ! »

«ማርና ቅቤዎን የሚበሉ - ሌሎች ናቸው እንጂ የኔ ልጅ አይደለም! »

«እሰዬ! የኔ ተቆጣጣሪ! ሂጂ እንደ ልማድሽ አሳብቂ። ሀረር አሉልሽ፥ አሁን መሳፈሪያ እሰጥሻለሁ፤ ሌላ ሳይቀድምሽ ሂጅና አሳብቂ! »

ደመቀች ልጅዋን ሲነኩባት መልስ መስጠትዋ የታወቀ ቢሆንም እንደያነለት እመቤትዋን በድፍረት ተናግራቸው አታውቅም። ስለዚህ «ጣልና በልልኝ» ብለው ባያስደበድቡዋት ሳያሳስሩዋት እንደማይቀሩ እርግጠኛ ሆና ትጠባበቅ ነበር። ነገር ግን ወይዘሮ ጽጌ ከስዋ ጋር ጭቅጭቅን ያነሱት አንዳች የሚያስቆጣ ነገር አድርጋ ሳይሆን በዘመዶቻቸው ይሉኝታ ቢስነትና በራሳቸው ግብዝነት ምክንያት ለጊዜው በውስጣቸው ተነስቶ ለነበረው የህሊና ጭንቀት መተንፈስ ይሆን መስሎዋቸው ስለ ነበርና፥ የድፍረት ንግግርዋ ለስዋ ከባድ መስሎ የተሰማትን ያክል ስላልተሰማቸው «ሂጅ ወግጅ ከፊቴ! » ከማለት በቀር ያነለት ምንም አላደረጉዋት።

## ምዕራፍ አስራ አንድ

# ተከስተና ወይዘሮ ጽጌ

ተከስተ ጥቁር መልኩ፥ እያንዳንዱ ልቅም ያለ ባይሆንም፥ ሁሉም ባንድነት ሲታይ፥ ደስ የሚል ፊት ያለውና ሰውነቱ የዳበረ ስለ ነበረ፥ እውነትም ወይዘሮ ጽጌ እንደሚሉት «ማርና ወተት እዬተመገበ» የሚያድግ፥ ሀብታም ልጅ እንጂ፤ ያሽከር ጋር በዶዮ እዬበላ የሚያድግ፥ ያሽከር ልጅ አይመስልም ነበር። ጽዳቱም ስልጡን ሞግዚት ተጠንቅቃ የምትጠብቀው ይመስል ነበር። ምግቡ ያው፥ ከናቱ ጋር ተካፎ የሚበላው ጋሪ በዶዮ ቢሆንም፥ ይተርፍ እንደ ሆነ እንጂ «ያንሳል» አይባልም እስኪጠግብ ይበላል። እናቱ ምንም ያክል ቢደክማት፥ ውሀ አሙቃ ገላውን ሳታጥበው አድራ አታውቅም። ልብሱ ውድ ያልሆነ ተራ፥ አንዳንድ ጊዜም ተቀዶ የተጣፈ ሊሆን ይችላል። ነገር ግን አንድ ቀን «አድፎ አዬሁት» የሚል የለም።

እናቱ በዚያ እድሜዋ፤ የመቤትዋን ቅብጥብጥ አመልና ጊዜ የማይሰጥ አስቸጋሪ ስራ አሸንፋ፥ በዚያ ላይ ልጅዋን በሰውነቱም በጽዳቱም እንዲያ የሰው አይን የሚማርክ አድርጋ በመያዝዋ የሚያውቃት የቤትና የጎረቤት ሰው ሁሉ ይገረም ነበር። እስዋ ግን እመቤትዋን ስታገለግል ቀኑን ውላ ማታውን አምሽታ፥ ፊትዋን ወደ ልጅዋ መለስ ስታደርግ እመቤትዋን ለማገልገል ስትደክም ውላ አምሽታ፥ ልጅዋን ለማገልገል እንደገና መድከም ስትጀምር ነበር ያካልና የመንፈስ እረፍትዋ! ያንጊዜ ነበር የውነተኛ ጸጥታዋና ደስታዋ! ለሚወዱት መድከም እረፍት አደል? የሚወዱትን ማገልገል ደስታ አደል? ስለዚህ፥ ከምታርፍበት ጊዜና ከምትባለው ምግብ የሚበልጠውን ክፍል ለልጅዋ አዬሰጠች፥ አሳምራ፥ ያልፎ - ሂያጅ መንገደኛ አይን የሚማርክ አድርጋ ይዛው ነበር።

ተከስተ በጠቅላላው ጨዋታ ወዳጅ ከመሆኑ በላይ፥ ጎጃም የባላገር ህጻናት የሚጫወቱዋቸውን ብዙ ጨዋታዎች እናቱ እዬነገረችው ያውቅ ስለ ነበረ፥ የሰፈሩ ህጻናት ሁሉ፥ የሀብታሞች ልጆች ጭምር፥ እንደ መሪያቸው አድርገው ያጅቡት ነበር። የህጻናቱ ወላጆችም ልጆቻቸው ሲወዱና በሄደበት ሲከተሉት ሲያይ፥ መውደድ ብቻ ሳይሆን በንቃቱና በብልህነቱ ጭምር እዬተደነቁ ‹ይህ ልጅ የድሀ ልጅ ባልሆነና፥ - እፈረንጅ ትምህር ቤት የሚያገባው ዘመድ ነበረው፤ ወደ ከፍተኛ ቦታ የሚደርስ ለቁም ነገር የሚበቃ ይሆን ነበር!› ይላሉ። እንዲሁ አልፈው ሲሄዱ ከሚያዩት መንገደኞች

እንኩዋ ያለ ስራቸው ቆመው፥ ስሙንና ያባት የናቱን ስም፥ ትምህርት ቤት ይሂድ ወይም አይሄድ እንደሆነና እነዚህን የመሳሰሉትን ብዙ ጊዜ እንግዶች ልጆችን የሚጠይቁዋቸውን ጥያቄዎች ሲጠይቁት ቆይተው፥ ‹እግዚአብሔር ያሳድግህ ከክፉ አይን ይሰውርህ!› በለው ስመውት የሚሄዱ ብዙ ነበሩ። ተከስተን ወይዘሮ ጽጌ ብቻ አይወዱትም ክፉኛ ይጠሉት ነበር። ‹ለምን ይጠሉታል? መልኩ አስቀያሚ ነው? ጽዳት ይጎድለዋል? ጠባየ - ክፉ ነው? ወይስ ሌላ የሚያስጠላ ነገር አለበት?› ብሎ የሚጠይቃቸው ቢኖር እንኩዋንስ ለጠያቂው ለራሳቸውም አጥጋቢ መልስ አያገኙም። ብቻ በአእምሮቸው አሰላስለው የሚጠሉበት ምክንያት ግልጥ ብሎ ታይቶዋቸው ሳይሆን እንዲያው ደመነፍሳቸው አዝዞዋቸው ይጠሉታል። ምናልባት ‹ለምናልባቱ እንዲህ አምሮ የኔ ልጅ አልሆነ? ለምናባቱ እንዲህ አምሮ የሌላ ልጅ ሆነ?› በማለት ይሆን? ይልቁንም ከባላቸው አጠገብ ሲያዩትማ ትእግሥታቸው ሁሉ ሙጥጥ ብሎ ያልቅና የልባቸውን፥ ጥላቻ ባፋቸው አውጥተው እንዳይናገሩ ባላቸውን ያፈሩና፥ የሚያደርጉት ቅጡ ጠፍቶባቸው ሲቸገሩ በውስጣቸው የሚነሳው ሁከት፥ አስከትሎ የሚያያቸው ሰው ቢኖር በፊታቸው ግልጥ ብሎ ቢታዬው! በግብር ላይ፥ ተከስተ ብዙ ጊዜ እዚያ አይገኝም እንጂ አልፎ አልፎ ተገኝቶ ደጃዝማች ይጠሩትና ባጠገባቸው አቁመው ወይም አስቀምጠው ሁለት ወይም ሶስት ጊዜ አጉርሰውት ሲበላ ወይዘሮ ጽጌ ሲያዩ እሳቸው የጐረሱት ይመራቸዋል! እሱም እንዲያ በክፉ አይን ስለሚያዩትና ጠርተውት የቀረባቸው እንደሆነም እሱም እንዲያ በክፉ አይን ስለሚያዩትና ጠርተውት የቀረባቸው እንደሆነም ረግመውና የሚዳብሱት መስለው፥ ሰው ሳያያቸው በቁንጥቻ እርድ አድርገው ስለሚለቁት፥ ይጠላቸዋል። ብቻ እሱ ጥላቻውን እንደሳቸው አይደብቅም። እንኩዋንስ ለሌላ ከጠየቁት ለሳቸውም ይነግራቸዋል። መቸም ልጅ መሆን ከፋቱ ይህ ነው። ልጅ ልክ እንደ እንስሳ የስሜቱ መሳሪያ የስሜቱ መጫወቻ ነው። ‹ይጎዳኝ ይሆናል› ብሎ የሚሰማውን ከማድረግ አይመለስም።

«ና አንተ ወደል እግዚአብሔር ድራሽህን ያጥፋውና! » ይሉታል፤ እናቱን ፍለጋ ወይም የልጅ እግር አያርፍምና ወዲያ ወዲህ ሲሮጥ እሳቸው ወዳሉበት የገባ እንደሆነ።

«እንቢ» ብሎዋቸው ሊሮጥ ሲል ቅርብ እንደሆነ ራሳቸው ለቀም አድርገው፣ ሩቅ እንደሆነ አስይዘው አስመጥተው ይይዙና፥

«ለምን ስጠራህ እንቢ አልህ? » ይሉታል።

«እንዲያው» ይላል፥ አንገቱን ደፍቶ።

«ንገረኝ ሳልመታህ።»

«እንዲያው! »

«መቸም አትወደኝ፤ ከግንድ ያዋድህና! »

«አልወድሁም።»

«እና - የኔ ልጅ ብትሆን አትወድም? የኔ ልጅ ብትሆን እንዲህ - ያልተደረተ ልብስ አለብስህለሁኮ! »

«አልፈልግም፤ አልወድሁም።»

«ለምን ነው የማትወደኝ? »

«ክፉ ነሁ። ትቆጣለሁ፤ ትቆነጥጣለሁ።»

«እንቢ ያንቱ ልጅ አልሆንም፤ አልወድሁም።»

«ደጃዝማችንስ ትወዳቸዋለህ? »

«አዎ ጌቶችን እወዳቸዋለሁ።»

«ለምን? »

«እሳቸው እንዳንቱ አይቆነጥጡኝም፤ ደሞ መጫወቻ ይገዙልኛል።»

«ያቺ ክፉ እናትህ ትሆናለች - ጥልጣል ያውርዳትና እኔን እንድትጠላ የመከረችህ።»

«እስዋ አልነገረችኝም፤ እንዲያው እኔ ነኝ የማልወድሁ።»

«እ፤ አህዮ፤ ‹አልወድሁም አልወድሁም› አንተ ጠላኸኝና መንግሥተ ሰማያት ቀረብኝ! »

«ልቀቁኝ ልሂድ? »

«እኮ ለምን እንደማትወደኝ ንገረኝና እለቅህለሁ።»

«ሁልጊዜ ምንም ሳልልሁ ትቆነጥጡኛለሁ፥ ደሞ - ደሞ ውሽትሁን ስላልበላሁ እንጀራዬን በላህ፤ ማሬን በላህ ትላለሁ።»

«ታዲያ የማነን እንጀራ እዬበላህ ነው እንዲህ - እደል የሆንህ አህዮ? »

»እማዬ ናት የምታበላኝ።»

«አዎ፥ እማዬ የምታበላህ የኔን እንጀራ አደለም፤ ከሰማይ እያወረደች ነው! ሂድ ወግድ፥ ገደል ይሰደድህና፥ አንተ አ - ህያ! » ይላሉ፤ በመጨረሻ በቁንጥጫ ጭኑ እስኪዝል ልም - ዝግ ያደርጉትና እሱም «የታ - ባትሁ፣ አንቱ ውሻ ቡዳ» ብሎዋቸው ጭኑን እያሸና እያለቀሰ ይሮጣል። እስኪረሳው ለሁለትና ለሶስት ቀናት ወደ ወይዘሮ ጽጌ እልፍኝ አይሄድም። ሁዋላ እያደገና ነፍስ እያወቀ ሲሄድ ወይዘሮ ጽጌን መጥላቱ ሳይቀር አጥብቆ ይደፍራቸው ጀመር። አንዳንድ ጊዜ ድንገት ካላገኙት እሳቸው ወዳሉበት ቦታ እንዲያውም ትውር ብሎ መድረሱን ተወ። ድንገት አግኝተውት የተቆጡት ወይም የቆነጠጡት እንደሆነ እንኩዋ እንደ እናቱ ዝም ብሎ ሰምቶ ወይም ድምጹን አጥፍቶ ቁንጫቸውን ቀምሶ መሄድ ነው እንጂ እንኩዋንስ መሳደብ ድምጹን አሰምቶ ማልቀስ የማይፈቅድ መሆኑን ተማረ። ብቻ በሙቱት ቁጥር እናቱ የባጡን የቆጡን፣ አንድ ቀን ተረቱን ሌላ ቀን እውነቱን አውርታ የምትችለውም የማትችለውንም ልታደርግለት ዋሽታ አባብላ አታላ፥ ዝም፣ እስክታሰኘውና እስክታስረሳው ድረስ ያን ቤት ‹፣ጥለን ካልሄድን» እያለ ያስቸግራት ስለ ነበረ፥ ልጅዋን እንዲያ ሆድ ሲብሰው እያዬች ታግሳ በመቀመጥና ‹ደህና መሸሺያ አገኘሁ› ብላ እምነትዋን ሁሉ የጣለችበትን ቤት ጥላ በመሄድ መሀከል መምረጥ አቅቶዋት ቅጥ መላው ጠፍቶዋት ነበር። ሁዋላ፤ ለጊዜውም ቢሆን የተሻለ መስሎ የታያት መቸም ልጅዋ ወይዘሮ ጽጌ ብቻቸውን ወዳሉበት ካልሄደና ባቅራቢያቸው ካላዩት እሱን ፈልገው ለመቆንጠጥ ሲሉ ከቤታቸው ስለማይወጡ እሳቸው ባሉበት አካባቢ ደጃዝማች ቢኖሩ እንኩዋ ጭራሽ እንዳይደርስ ተጠንቅቃ መጠበቁ ነው። ‹ምናልባት ዘለግ ላለ ጊዜ ሳያዩት ከቆዩ እስከ መኖሩም ይረሱት ይሆናል› አለች ባሳብዋ። ከዚያ በተረፈ፥ ማታ ማታ - መቸም ቀን እውጭ ከጉዋደኞቹ ጋር የሚውል - ከስራዋ እስክትመለስ እንደ ልማዱ - እልፍኝ አዳራሽ ማድቤት፥ እየወጣ እዬገባ እዬሳቀ እዬቦረቀ ሲጫወት ማምሸቱ ቀርቶ፥ በጊዜ እቤትዋ እያገባች እዬዘጋችበት ማምሸት በግድ የሚያስፈልግ ሆነ። መቸም እንዲያ ያለ ኑሮ እንኩዋንስ ለልጅ ላዋቂም ቀላል አደል! እንደ እስረኛነት ማለት ነው። ነገር ግን የማይለመድ ነገር ስለሌለ ይለመዳል። ተከስተም ለመደውና፥ ከዚያ በሁዋላ ናፍቆቱ ሁሉ እናቱ ቶሎ መጥታ አገርዋ እንዱዳም

ኪዳነ ምህረት አዋቂዎች ለህጻናቱ ሲያወሩ እዬሰማች ያጠናችውን ተረት እዚያ ልጆች የሚጫወቱትን ጨዋታ በያመትባሉ በዬሰርጉ፥ በዬድግሱ፥ የሚዘፈነውን ዘፈንና የሚደረገውን ሁሉ እስክታጫውተው ሆነ። ከተረቱ ይልቅ እስዋና የንዶዳም ኪዳነ ምህረት ልጆችም አዋቂዎችም ያደርጉት የነበረውን ብታጫውተው ይወድ ስለ ነበረ፥ ብዙ ጊዜ የምታወራው የንዶዳሞን ወሬ ነበር።

እናቱ ኩራዙን አብርታለት፥ የበሩን መዝጊያ ዘግታለ፥ ከሄደች በሁዋላ ተከስተ አልጋው ላይ እንደ ሆነ፥ አንዳንድ ጊዜ እንቅልፍ እዬወሰደው አንዳንድ ጊዜ ነቅቶ፣ እዬተቀመጠም፥ ተመልሶ እዬተደጋገመም፥ ሲጠባበቅ አምሽቶ የሱንም የስዋንም ራት ይዛ እዬሮጠች፥ ስትመጣ ዳናዋን ከሩቅ ይሰማና «እማዬ፥ መጣልሽኝ? » ይላል ከአልጋው ላይ ከተቀመጠ ወይም ከተጋደመበት ዘሎ ተነስቶ ክንዶቹን እንደ ክንፍ ግራ ቀኝ በሰፊው ይዘረጋና። ከዚያ እስዋም ቶሎ የያዘችውን አስቀምጣ፥ እስኪጨንቀው እቅፍ አድርጋ ትስመዋለች። የፍቅርዋ ጥምዋ እስኪረካ ስምጥጥ አድርጋ ስሜትዋ፥ ቅርታዋ ሁሉ የተከሰተን የተዘረጉ ክንዶች አይቶ እንደ ፈራ ሁሉ እስዋ ስትገባ ሁሉም ከበር ተመልሶ ይሸሻል። ከዚያ ቶሎ ገላውን አጥባው፥ ራታቸውን እዬበሉም በልተው ጨርሰው ተቀምጠውም፥ ወደ መኝታቸው ከሄዱ በሁዋላ እሱን እንቅልፍ እስኪወስደውም፥ የንዶዳም ኪዳነ ምህረት ወሬ ይወራል።

አንድ ማታ ከተለመደው ጊዜ የበለጠ አምሽታ የመጣች ስለ መሰለው፥

«ዛሬ ለምን እንዲህ አመሸሽ? እንግዲህ ያገራችነን ወሬ ሳታወሪኝ እንቅልፌ ይመጣብኛል» አለ ያገራቸውን ወሬ ከመጀመራቸው በፊት።

«እመይቴን እስካስተኛ ድረስ ነው፤ ወዲያውምኮ ከዱሮው የበለጠ አላመሸሁም። »

«አንቺ ነሽ የምታስተኛቸው? እሳቸው መተኛት አያውቁም? »

«ማወቅማ ያውቃሉ። አለች ደመቀች፥ ልጅዋ አፉ እንዳመጣው በተናገረው ሳቀችና። «መተኛት ያውቃሉ። ብቻ ጀርባቸውን ሳሻቸው ሰውነታቸው ተፍታቶ ደስ ይላቸውና ቶሎ ይተኛሉ።»

«አዎ፤ እወዳቸዋለሁ።»

«እየረገሙሽ ደሞ - ደሞ እኔን እዬቆነጠጡኝ ለምን ነው የምትወጃቸው? »

«እንተና እኔ ልብሳችነን የምንለብስበት ገንዘብ የሚሰጡን የምበላው ምግብ የሚሰጡት የምኖርበት ቤት የሚሰጡን ይህን ሁሉ የሚያደርጉልን እመቤታችን ስለ ሆኑ ነው የምወዳቸው፤ እንተም ውደዳቸው።»

«እንቢዮ እኔ አልወዳቸውም፥ ክፉ ናቸው። እሳቸው ሙትት ቢሉና ጌቶች ሌላ የማይቆነጥጡ ሚስት አግብተው እሳቸው ዘቡንና - ሌላውን ሁሉ እዬሰጡን እመቤታችን ቢሆኑ ነው የምወደው።»

«ኧረ፥ ኧረ፥ ኧረ! ተው እንደሱ አይባልም፥ ነውር ነው! የማይቆነጥጡ እኔንም የሚረግሙኝ ለኛ ብለው እኛ ደህና እንድንሆን ብለው ነው።»

«እዬቆነጠጡ ሲያሳምሙኝ እንዴት ነው ደህና የምሆን? »

«ቁንጥጫ አሁን ቢያሳምምህ ሁዋላ ደህና ልጅ አድርጎ ያሳድግሀል። ‹ልጅ ካልተቆነጠጠ አታክልት ካልተኮተኮተ፥ ደህና ሆኖ አያድግም› እያሉ ያገራችን ሰዎች እናባባ ሁሉ ልጆቻቸውን እዬቆነጠጡ ነው ያሳደጉን።»

«እኔ እንቢዮ የሳቸውን ቁንጥጫ አልፈልግም፣ ደህና ልጅ ሆኘ ባላድግ ይሻለኛል! እሳቸው ክፉ ውሽታም፥ ቡዳ ናቸው! » ይላል ተከስተ በጣም ተቆጥቶ።

«እሺ ተወው የኔ ጌታ እሳቸው፥ ወዳሉበት ካልሄድን አይቆነጥጡህም» ትላለች፥ በፊቱ ላይ ያለውን እዬሳመችና እያባበለች።

በተረፈ የምታወራለት ሁሉ ከንዶዳም ኪዳነ ምህረት ወጥቶ አያውቅም። የንዶዳም ኪዳነ ምህረትን ወሬ አንድ ማታ የሴቶችን ልጆች ጨዋታ በሌላው ማታ የወንዶች ልጆች ከዚያ የጎበዛዝቱን እዚያ የሽማግሎችንና የባልቴቶችን እዬደጋገመች ብታወራው ከስዋ አይደከማት፥ እሱን አይሰለቸው፤ ሁለቱም በዬለት አዲስ ነው! የንዶዳም ልጆች በተለይ ሴቶች ልጆች የሚያደርጉትን ስታወራው ወሬው እንዶዳም የሚደረገውን ከጉዋደኞችዋ ጋር በትዝታ እንደገና መልሶ አምጥቶ እዚያ ከነሱ ጋር አብራ የምታደርገው ይመስላትና እሱን ብቻ ሳይሆን እስዋንም ደስ ይላት ነበር። ተከስተ የንዶዳም ኪዳነ ምህረትን ወሬ እዬተደጋገመ ብዙ ጊዜ ከመስማት የተነሳ ይልቁንም የልጆችን እንደ ‹አቡነ ዘሰማያት› በቃሉ አጥንቶ ነበር።

«የኛ አገር ሴቶች ልጆች» ትላለች ደመቀች፥ የንዶዳምን ወሬ ከሴቶች ልጆች ስትጀምር። «የኛ አገር ሴቶች ልጆች ቤት ለቤት በመላላክም በስራም እናቶቻቸውን ስለሚረዱ እንደ ወንዶች ልጆች አሜዳ ተሰብስበው መጫወት አይፈቀድላቸውም።»

«ለምንድን ነው የማይፈቀድላቸው? »

«እኔ እንጃ፣ ከጥንት ጀምሮ ልማዱ እንደሱ ቢሆን ነው መሰለኝ - ሴት ልጅ አሜዳ ወጥታ የታዬች እንደሆነ ‹ወንድ ይመስል ሜዳ ለሜዳ የምትዞሪ ምን ፈልገሽ ነው› ብለው ይቆጡዋታል። አንዳንድ ጊዜ እንዲያውም ይመቱዋታል። እና ሴቶች ልጆች እንጨት ለመልቀም፥ ወይም ውሀ ለመቅዳት ካልሆነ ከቤት ወይም ከደጅ አይርቁም። ባንድ ላይ ተሰብሰበው የሚጫወቱት በሰርግ ወይም ባመትባል ጊዜ ነው። ከሁሉም በጣም ደስ የሚለን ቅዱስ ዮሀንስ ሲደርስ ነው። እቤት ቅዱስ ዮሀንስ ሲመጣ እንዴት ደስ ይለና - ል! ገና ክረምት ወጥቶ ቅዱስ ዮሀንስ ሊደርስ ሲል ‹አሽክት› ማፍራትና ‹አክርማ› መዝርዘር ይጀምራል። ያንጊዜ ሴቶች ልጆች ሁላችን፣ አሽክት ለመልቀምና አክርማ ለመቅጨት ወደ ሜዳ ብንሄድ ወላጆቻችን አይቆጡንም። ስለዚህ ባንድ ላይ ሆነን እዬዘፈንንም ለዬብቻም አሽክት ከሜዳ ለቅመን ከሶስት እስከ አምስት እስከ ስድስትም ዘለላ አድርገን በክር ሰክተን ያን በዶቃ፥ ወይም በዛጎል አለፍ አለፍ እያደረግን አቁዋርጠን ሁሉንም ባንድነት እንደ እምረጥነው - በወይን ጠጅ በሰማያዊ፥ ባረንጉዋዴ፥ በቀይ፥ ወይም በቢጫ ቀለም እንነክርና ባንገታችን እናደርጋለን። ደግሞ አክርማ ቀጭተን ካለላ ጋር እያዝጎረጎርን ‹ወፍ እግር እባባ ልብ ፍልጦሽ› እና ሌላም አይነት ‹አጨንቢላ› ሰርተን በክንዳችን እናደርጋለን። አሽክት ባንገታቸው አያደርጉም እንጂ፣ ወንዶቹም አጨንቢላ በክንዳቸው ያደርጋሉ። እንዲያውም ከሴቶች የበለጠ አጨንቢላ የሚያደርጉ ወንዶች ናቸው። ሴቶች ልጆች አንድ ወይም ሁለት አጨንቢላ ብቻ ነው - ለምልክት በክንዳቸው የሚያደርጉ ወንዶች ግን ከጃቸው አንገት እስከ ክርናቸው ግ - ጥም ያደርጉታል።

«ታዲያ እንዲያ በቀለም ባጌጠ አሽክትና በዝንጉርጉር አቸንቢላ አንዳጌጥና መስከረም ጠብቶ ጸሀይ ሲሆን፥ ሜዳውም ሁሉ አደይ አበባውን ለብሶ ያጌጣል፣ ያምራል። ስለዚህ ለቅዱስ ዮሀንስ ዋዜማ ሴቶች ልጆች ሁሉ እዬዘፈርኑ አንግጫ፥ ከመስከ ነቅለን አደይ አበባ ከሜዳው ቆርጠን ሁለቱን ባንድ ላይ ውጥጫ እንወጠጭና፥ ወይም ጉንጉን እንጎነጉንና ያን ይዘን በዬሰው ቤት እዬዞርን በምሰሶውና በወጋግራው እያሰርን ስንዘፍን ማምሸት ነው! አቤ - ት የኛ ቅዱስ ዮሀንስ እንደዚህ አገር አደለም፤

በጣም ግሩም ነው! » ትላለች፥ ያገርዋ ቅዱስ ዮሀንስ ስእሉ ይታያትና አይኖችዋን ቦዘዝ አድርጋ ፊት ለፊት በሱ ላይ ተከላ። «ያን እለት የቅዱስ ዮሀንስ ዋዜማ እለት እንግጫ ልንነቅል እመስክ ስንሄድ ያማሪት ልጆችም እመስክ ስለሌላቸው ወደኛ መስክ እንግጫ ሊነቅሉ ሲመጡ ልጅ በንግጫ ነቀላው ሻማ እንገጥማለን። ስንሽማ ስንሻማ እንቆይና በመጨረሻ ተጣልተን ስንደባደብ ብታይ! »

«ለምን ነው ተጣልታችሁ የምትደባደቡ? እንግጫው ሳይበቃችሁ ጊዜ ነው? »

«የመስኩ እንግጫስ - ተነቅሎም አያልቅ። እንዲያው - እንጂ ከሌላ አገር የመጡ ስለሆኑ፣ እነሱም እኛም መጣላት፣ እንፈልጋለን። ከድሮ - ጀምረው የንዶዳሞና ያማሪት ልጆች በያመቱ፣ በንግጫ ነቀላ እዬተጣሉ ሳይደባደቡ ቀርተው አያውቁም ይባላል! » ስትል ተከሰተ የንዶዳምና ያማሪት ሴቶች ልጆች ተጣልተው ሲደባደቡ ይታዩትና ሲቃ ይዞት ባለበት እንዳለ ይቁነጠነጣል።

«ታዲያ ቅድም እንዳልሁህ የቅዱስ ዮሀንስ ዋዜማ የንግጫና ያደይ አበባ ጉንጉንና ውጥሜችነን ይዘን እዬዘፈን በዬሰዉ ቤት በምሶሰውም በወጋግራውም ስናስር አምሽተን ያን እለት የመንደሩን ቤት ሁሉ ሳናዳርስ ከቀረን በማግስቱም በሳልስቱም እንቀጥላለን። ከቅዱስ ዮሀንስ እስከ መስቀል ሴቶች፥ ትንንሾች ‹ጋሜ ከቁንጮ› ከፍ ከፍ ያሉት ‹ድስት ቅርጽ› ራሳችነን ተላጭተን ባሽክትና ባጨንቢላ አጊጠን ስንዘፍንና ስንጫወት የምንሰነብትበት የሴቶች ልጆች አመትባል ነው። በጣ - ም የድሀ ልጅ ካልሆነች ለቅዱስ ዮሀንስ አዲስ ቀሚስ የማይገዛላት ልጅ አት - አትገኝም! » ትላለች ደመቀች አገርዋ ከጉዋደኞችዋ ጋር ታደርገው የነበረው ትዝ ሲላት ልቅሶ፥ ይመጣባትና ንግግርዋን እያደናቀፈው።

«ለቅዱስ ዮሀንስ ምን እያላችሁ ነው የምትዘፍኑ? » ይላል ተከስተ፥ በናቱ ወሬ ልቡ ተመስጦ ልቅሶ የሚተናነቃት መሆኑን ልብ ሳያደርግ።

«አሁን እንደ ነገርሁህ የንግጫና ያደህ አበባ ጉንጉንና ውጥሜችነን ይዘን በዬቤቱ እንሄድና ያን በዬምሰሶውም በዬወጋግራውም አስረን።

‹ውብ አደይ ውብ አደይ፣ ውብ አደይ አበባ

‹እንቁጣጣሽ ልትል ከኛ ጋር መጥታለች፥ ከፈቱላት ትግባ።

‹ከፈቱላት በሩን፣ እንቁጣጣሽ፣ ልንል መጣን ልጆቻችሁ፤

‹አበባና እማማ አመት አውዳመቱን እንኩዋ አደረሳችሁ፤

‹ከነልጆቻችሁ ከነከብቶቻችሁ፤

‹ለወዲያኛው አመት በቸር ያድርሳችሁ።

‹ምን አባትህ ጉንፋን ምን አባትህ ቁርጥማት ሂድ ውጣ ከቤቴ፤

‹መጥምቁ ዮሀንስ መጥቶዋል መድሀኒቴ።

‹ምስጋና ይንሳህ ጎመን፣ ምስጋና ይንሳህ ዱባ፤

‹ገብስ ይደርስልኛል መስከረም ከጠባ።

‹ውብ አደይ፤ ውብ አደይ፣ ውብ አደይ አበባ፤

‹እንቁጣጣሽ ትበል፤ ከፈቱላት ትግባ› እያልን ነው የምንዘፍን።

«ወንዶችም ልጆችስ የንቁጣጣሽ ለትከናንተ ጋር በዬቤቱ እዬዞሩ አይዘፍኑም? »

«እነሱ የንቁጣጣሽ ለት አይዘፍኑም። ብቻ - እኛ በዬቤቱ እዬዞርን ስንዘፍን አብረውን እዬዞሩ ሲያዩ ያመሻሉ»

«ለምንድ ነው እነሱ የማይዘፍኑት? »

«እኔ እንጃ፤ እንቁጣጣሽ ሴቶች ልጆች ብቻ የሚዘፍኑበት አመትባል ነው ይባላል።»

«ወንዶች ልጆች አመት ባል የላቸውም? »

«ሞልቶዋቸዋል እንጂ! መስቀል፥ ገና፣ ጥምቀት፣ የፋሲካ ‹ሚሻ ሚሾ› ደብረ ታቦር፥ ይህ ሁሉ የወንዶች ልጆች አመትባል ነው። እንዲያውም ከሴቶች ልጆች የበለጠ አመትባል ያላቸው እነሱ ናቸው።»

«ለመስቀል ምን ያረጋሉ? »

«ለመስቀል ደቦት የሚያበጁ ወንዶች ናቸው።»

«ደቦት? ምንድነው ደቦት? የሚበላ ነገር ነው? »

«የሚበላ ነገር አደለም፣ አብዬ! » ትላለች ደመቀች፥ በልጁዋ እዬሳቀች። «ደቦት የሚበላ አደለም፤ እዚህ አገር ‹ችቦ› እንደሚሉት፥ ከቀጫጭን እንጨት ባንድ ላይ ጥቅልል ተደርጎ ታስሮ ደመራ የሚቀጣጠልበት ነው። ታዲያ ግን፥ ‹ደቦት› ያልሁህን ከመስቀል በፊት ባለው ሳምንት አበጅተው፥ በዬቤቱ እየዞሩ ሲያበረክቱዋቸው ቤተሰቦች ነው። ታዲያ፣ የደመራ እለት ኀበዙ ሁሉ ተሰብስቦ የደመራ እንጨት ከዱር ያመጣና፣ ሽማግሌዎች ጭምር ደመራውን ‹አኩዋት አፋፍ› የሚባል ቦታ አለ፤ እዚያ ባደይ አበባ አስጊጠው አያውቅም ይባላል። በማግስቱ ያመዱ እሌላ ቦታ ተደምሮ በሁዋላ ብቻ ገና ሳይጠባ፥ ሽማግሌ ያመዱ እለት ከዶሮ ጩኸት በሁዋላ ብቻ ገና ሳይጠባ፣ ሽማግሌው ኀበዙ ልጁ እንዲያው - ወንዱ ሁሉ ደቦቱን እቤት አቃጥሎ ያበራና፥

‹ኢዮሀደራ፥ ኢዮሀደራ፤

‹መስቀሉ ተገኘ ሲቃጠል ደመራ።

‹እሰይ መስቀል ጠባ፥ መስቀል ጠባ ዛሬ፤

‹እንግዲህ ከጎንደር ሽዋ ከትግሬ፤

‹ከዘመዱ ሁሉ እንሰማለን ወሬ።

‹ካባይ ወዲያ ማዶ ወለጋ ያላችሁ፤

‹በወሎ በሀረር በሁሉ ያላችሁ፤

‹ከረምቱን አሻግሮ፥ ለመስቀሉ ብርሀን እንኩዋ አደረሳችሁ።

‹ኢዮሀደራ፣ ኢዮሀደራ፤

‹መስቀሉ ተገኘ ሲቃጠል ደመራ› እያለ ከዬቤቱ ወጥቶ ወደ ደመራው ሲሄድ፥ አገሩ ሁሉ መብራት ብቻ ሆኖ፥ አቤ - ት! ብታይ ማማሩ! እንዶዳም ብቻኮ አይደለም። አማሪትም፥ ያውያንም እንዲያው እኛ አገር ሆኖ የሚታዬው አገር ሁሉ መብራት ብቻ ሆኖ - ያ ሌሊት ትግንርት የሚታይበት ነው! »

«ታዲያ ያ ሁሉ እሳት ሲቃጠል - ቤቱ ሁሉ አብሮ አይቃጠልም? »

«የለም፥ ደቦቱን በዬቤቱ የሚያቃጥለው ሰው ሁሉኮ ከዬቤቱ ወጥቶ ሜዳ ለሜዳ ነው - ‹ኢዮሀደራን› እዬዘፈነ ደመራው ወዳለበት ወደ አኩዋት አፋፍ የሚሄድ። ታዲያ አሁን እንዳልሁህ፥ ሁሉም ደቦቱን እያበራ እደመራው ሲደርስ፥ ባንድ ላይ ሆኖ ‹ኢዮሀደራን› እየዘፈነ ደመራውን፥ ይዞራል። ከዚያ፣ ያመቱ ባለተራ ሽማግሌ ‹እንጎሮባሽ› ብለው በተቃጠለ ደቦታቸው ደመራውን ሲተኩሱት ያ ሁሉ ሰው እንደሳቸው ‹እንጎሮባሽ› እያለ የተቃጠለ ደቦቱን በደመራው ላይ ያሰፍርበታል። ከዚያ ደመራው ይቃጠልና እሳቱ እስከ ወዲያ ላ - ይ እስከ ሰማይ - ድረስ እዬተግለበለበ ሲወጣና ዙሪያውን በመላሱ አዙሮ ሲገርፍ፥ ሰው ሁሉ ፈርቶ ይሸሻል። ከሩቅ ሲያዩት ግን እንዴት ደስ ይላል! ታዲያ እንዲያ ተቃጥሎ ተቃጥሎ መለስ ሲልና ሰው ሲያቀርብ ልጁ ሁሉ፤ ከነሀሴ መጨረሻ ጀምሮ እየሰራ በክንዱ አድርጎት የቆየውን አጨንቢላ እያወለቀ እደመራው እሳት ውስጥ እዬወረወረ ያቃጥለዋል።»

«ለምን? እንጨቱ ሲያልቅ ጊዜ - እሳት እንዳይጠፋ ነው? »

«አይደለም፤ አጨንቢላ ከልጁ ሁሉ እጅ እዬወለቀ ሲቃጠል፤ ‹በሽታው ሁሉ አብሮ በመስቀል እሳት ይቃጠላል› ስለሚባል ነው። ‹ጌታችን፣ የዬሱስ ክርስቶስ መስከል በሽታውን ሁሉ፣ ክፉውን ነገር ሁሉ ያቃጥላል!› ይባላል። ከዚያ ደመራው ተቃጥሎ አልቆ ፍምና ረመጥ፣ አመድ ሲሆን ልጁ ሁሉ ከየቤቱ ሊጥ በወፍራም ያመጥና፣ ያን፣ በንስትም፤ በሌላ ሰፋፊ ቅጠልም እየጠቀለለ ረመጡ ውስጥ እየፈነዳ ያበስለዋል። ድንችም እንዲሁ እዚያ እዬተዳፈነ ይረመጣል። ከዚያ በሁዋላ ደምራውን የተኮሱት ባለተራ ሽማግሌ፤ ብዙ ወተትና ጠላ ሲያመጡ አዋቂዎች ጠላ እዬጠጡ ጉብሎች የተመረጠ እንጎቻቸውን ድንቻቸውን በልተው ወተታቸውን ይጠጡና የደመራውን አመድ እዬዞሩ ‹ኢዮሀደራን› ይዘፍናሉ።»

«ደመራውን የሚተኩሱት ሽማግሌ አንደኛ ጌቶች - ጌታ ናቸው? »

«አ - ይ! አንደኛ ጌቶች ያለ እንዲያውም በንዶዳሞ የለ! »

«እንግዲያ ለዚያ ሁሉ ሰው ጠላና ወተት ተየት ነው የሚገኙ? »

«ጠላውን - ያመጡ ባለ ተራ መሆናቸውን ስለሚያውቁ አስቀድመው እቤታቸው ያስደርጋሉ፤ ወተቱን ግን፣ ያን እለት ጥዋት በንዶዳም የሚታለበው ወተት ሁሉ ላመቱ ባለ ተራ ሰለሚሰጡ፣ የሌላውን ሰው ወተት አምጥተው ነው ለጉብሉ ሁሉ የሚያጠጡት።»

«እ - ሽማግሌው ደመራውን በጠበንጃ ነው የሚተኩሱት? »

«እንዴት? በጠበንጃ አደለም የሚተኩሱት፥ በተቃጠለ ደቦታቸው ነው የሚተኩሱት። ብቻ ደመራውን ከሁሉ በፊት በደቦታቸው ስለሚያቃጥሉት ነው ‹ተኩሱት› የሚባል። አንዳንድ ጊዜ ደሞ ‹ባረኩት› ይባላል።

«እናንተስ - እንደ ወንዶች እንጎቻና ድንች በልታችሁ ወተት እዬጠጣችሁ - ‹የውሀደራን› አትዘፍኑም? »

« ‹የውሀደራኮ› አይደለም አብዬ፤ ኢዮሀደራ ነው» ትላለች ደመቀች በልጅዋ እዬሳቀች።

«እሺ፤ እሱን አትዘፍኑም? »

«የሴቶች ደመራ ከወንዶች ጋር አይደለም ለብቻ ነው። ሴቶች ሁሉ ደሞ ትልልቆችም፥ ትንንሶችም የቅርብ ጎረቤትች ባንድ ላይ እዬሆኑ፥ የደመራ እለት በዬክፍላቸው፣ ባማካይ ባማካይ ቦታ ወንዶች ይጀምሩላቸውና ያመዱ እለት፥ ወንዶች ወደ ደመራቸው ሲሄዱ፣ እነሱም በዬደመራቸው የተደመረላቸውን በደቦት ያቃጥላሉ። የሴቶች ደመራ እንደ ወንዶች ትልቅ አይደለም። ከዚያ ሴቶች ልጆች አጨንቢላቸውን እናቶች ከቤት ውስጥ ለቅዱስ ዮሀንስ በዬምሰሶው፥ በዬወጋግራውም፥ ታስሮ የሰነበተውን የንግጫና ያደይ አበባ ጉንጉንና ውጥሜ እያወቁለቁ ‹በሽታ፥ ችግር ክፉ ነገር ሁሉ በመስቀል እሳት እንዲህ ተቃጠለ› እያሉ እደመራው እሳት ላይ እዬጣሉ ያቃጥሉታል። ከዚያ ወንዶች እንደሚያደርጉት ወፍራም ሊጥና ድንች አረምጠው በልተው ወተት ይጠጣሉ። ነገር ግን እንደ ወንዶች ‹ኢዮሀደራ› አይዘፍኑም።»

«ለምንድነው የማይዘፍኑ? አያውቁበትም? »

«እኔ እንጃ፥ ማወቅስ ያቁበታል፤ ብቻ ልማድ ስላልሆነ አይዘፍኑም።»

«ወንዶች ልጆች እንጎቻና ድንች በልተው ወተት እዬጠጡ - ‹የውሀደራን› ብቻ ነው የሚዘፍኑ? ሌላ አይዘፍኑም? »

«የውሀደራ» አይደለም አልሁህኮ! «ኢ - ዮ - ሀ -ደ - ራ»

«እሺ፤ «ኢ - ዮ - ሀ - ደ - ራ»

«እ - ንደሱ! ወንዶች ልጆች ‹ኢዮሀደራ› ብቻ አይደለም የሚዘፍኑ ‹ኢዮሀደራ› ለመስቀል ብቻ የሚዘፍኑት ነው። ለገና ለጥምቀት፥ ለደብረ ታቦርና ሌላም አመትባል የሚዘፍኑት ሌላ ነው። ደሞ ወንዶች ልጆች ብዙ አይነት ጨዋታ አላቸው። አዝመራ ፍዬል፥ ጥጃ፥ ላም፥ ሲጠብቁ፥ የማይጠብቁትም ለጨዋታው ሲሉ ወደነሱ ሄደው ባንድ አማካይ ቦታ ይሰበሰቡና በቡድን በቡድን ሆነው ‹ሽመለ - ቀንድዮሽ› ‹ሽመል ግርፊያ› ‹አካንዱራ› ‹ገና› ‹ኩዋስ› ‹ገበጣ› ‹ዶቃ› ይጫወታሉ። ታዲያ አንዱ ቡድን አሸንፎ ሌላው ቡድን የተሸነፈ እንደሆነ ያሸናፊው ቡድን ልጆች የተሸናፊውን ቡድን ልጆች በቅሎ ያደርጉዋቸዋል» ትላለች ደመቀች ጨዋታው ትዝ ሲላት እንደ መስቅ ትልና።

«ልጆች ሰዎች አይሉም? እንዴት ነው በቅሎ የሚያደርጉዋቸው? » ይላል ተከስተ የናቱ፥ ንግግር አልገባው ስላለ ግራ የገባው መሆኑ ከፊቱ እዬታዬ።

«ሰዎችማ ሰዎች ናቸው፤ የጨዋታ በቅሎ ነው እንጂ የውነትዮሽ በቅሎ አይሆኑምኮ። ብቻ - አሸናፊዎች ተሸናፊዎችን ልጆች እንደ በቅሎ ይቀመጡባቸዋል ማለቴ ነው። አዬሀ፥ አሸናፊዎች አስር ጊዜ ያሸነፉ እንደሆነ ተሸናፊዎች ‹አስር እዳ አለባችሁ› ይባላሉ። ከዚያ ተሸናፊዎች እንደገና ተጫውተው እዳቸውን ካላስወረዱ፣ አምሳ ወይም መቶ ክንድ መሬት ይሰፈርና፣ በዚያ ተሸናፊዎች በቅሎ አሸናፊዎች ባለ በቅሎ ሆነው ተቀምጠውባቸው አስር ጊዜ ይመላለሳሉ። ታዲያ እንዲያ አሸናፊዎች በተሸናፊዎች ጀርባ ላይ ተቀምጠው እንደ በቅሎ ‹መጭ› እያሉ ከሁዋላቸው ባርጩሜ ሸንቆጥ እያደረጉና በግራቸው እዬኮለኮሉ ወዲያና ወዲህ ሲመላለሱ ተሸካሚዎች ደግሞ እንደ በቅሎ ‹ቡርፍ - ቡርፍ› እያሉ እያንኩዋረፉ ሲሮጡ ሲጋልቡ ብታይ በሳ - ቅ ይገሉሀል?! በዶቃ ጨዋታ የተረቱት ብቻ፥ እዳቸውን በደቃ ይከፍላሉ እንጂ በቅሎ አይሆኑም።»

«ተከስተ እናቱ የንዶዳምን ልጆች ጨዋታ ስታወራው አሸናፊውች በተሸናፊዎች ደርባ ላይ ተቀምጠው እንደ በቅሎ ሲኮለኩሉዋቸው ይታዩትና፥ እሱ ካሸናፊዎች አንዱ እንደሆነ ሁሉ ደስ ብሎት እዬሳቀ በበቅሎ የተቀመጠ ይመስል ባለበት እንዳለ እግሮቹ ይኮለኩላል።

«አቤ - ት! የኛ አገር ወንዶች ልጆች እንደ ሴቶች ልጆች እቤት ከናቶቻቸው ጋር ስራ ስለማይሰሩ እውጭ ስለሚውሉ አለማቸውን እንዳዩ ነው የሚኖሩ። ለምሳና ለራት ካልሆነ ቤቱን ዘወር ብለው አያዩትምኮ! ከረምቱ ወጥቶ መስከረም ሲጠባማ - እስከ ትሳስ ድረስ - እንዲያውም እቤት አያድሩ፤ ከጎበዞች ጋር እውጭ ሲጫወቱ ነው

የሚያድሩ። በዚያ ወራት፥ ለኛ አገር ጎበዞችና ለወንዶች ጉብሎች ሌሊቱ ሁልጊዜ አመትባል ነው! » ትልና ደመቀች በጸደይ ወራት ያገርዋ ጎበዛዝት ላውሬ ቅራት እውጭ ሲያድሩ እነሱና ትንንሾች ልጆች የሚያደርጉት ሁሉ ስእሉ መጥቶ በፊትዋ ስለሚዘረጋ አይኖችዋን በሱ ላይ ተክላ ስትመለከት ቆይታ፤

«አዬሀ» ትላለች። «አዬሀ ክረምት ሄዶ መስከረም ሲመጣ፥ ጀመሪያ ድንች ከዚያ አተርና ባቄላ ከዚያ ቀጥሎ ዘንጋዳና ማሽላ ስለሚበስል ‹አሳማና ጃርት› የሚበሉት አውሬዎች እንዳይበሉት ጎበዙ ሁሉ እውጭ ማማውን ሰርቶ ሲጠብቅ ነው የሚያድር። ታዲያ እዚያ ያለው ጨዋታ እንዲህ አይመስልህ፥ ግሩም ነው! አዝመራ የሌላቸው ጎበዞች እንኩዋን ለጨዋታው ሲሉ እዚያ ሄደው ነው የሚያድሩ። ወንዶች ጉብሎችም እዚያ ሲጫወቱ እንዲያድሩ ይፈቀድላቸዋል። ታዲያ በዚያ ጨለማ ውስጥ፥ በያዝመራው መሀል ባለው ማማ ስር እሳት ነዶ አተሩና፥ ባቄላው እዬተነኮተ ዘንጋዳውና ማሽላው እዬተጠበሰ እዬተበላ፣ ጎበዞች ዋሽንት እዬነፉ ነው የሚያድሩ። አቤ - ት እንዴት ደስ ይላል መሰለህ! ብታይ ግ - ሩም ነው። ታዲያ እንዲያ እንዲያ ሲጫወቱ የሚበልጠውን ሌሊት አድረው ሊጠባ ትንሽ ሲቀረው ነው የሚተኙ። እኛ፣ ሴቶች ጉብሎች ሁሉ እንዲያ ዙሪያውን በያዝመራው መሀል በጨለማው ውስጥ የነደደው እሳት እንዶዳምን ሁሉ ግምጃ የለበሰ ሲያስመስለው ማየትና የዋሽንቱንም የክራሩንና የመሰንቆውንም ድምጽ ከጉብሎች ዘፈን ጋር መስማት በጣም ደስ ስለሚለን፥ ማታ እደጅ ወጥተን ሲሰሙ ይቆዩና ሲገቡ ‹ምናባታችሁና እናንተ ልጆች እዚህ ልታድሩ አምሮዋችሁዋል? በሉ ኑ ግቡ› ብለው ያስገቡናል። አይ ያንጊዜ ስንጠላቸው ብታይ! »

ደመቀች በጸገይ ወራት እንዶዳም፣ ኪዳነ ምህርት ያተርና የባቄላ፥ የዘንጋዳ የማሽላ የድንች አዝመራ ባለበት መሀከል ሁሉ ሌሊት እሳት ሲነድ በሙሉ እንዶዳም ጨለማው ወደ ብርሀን ሌሊቱ ወደ ቀን የሚለወጥ መምሰላቸውን፥ ጎበዛዝቱ የሚነፉት ዋሽንትና የሚመቱት መሰንቆና ክራር እንዲሁም ጉብሎች የሚዘፍኑት ዘፈርን ቀን ከሚሰማው የዋሽንትም ሆነ የመሰንቆና የክራር ወይም የዘፈን ድምጽ ፍጹም የተለዬ፥ እጅግ የሚያምር መሆኑን፥ ሌሊቱን ሙሉ ሲፈነጥዙ ሳይሰማቸው፥ እንቅልፍ ሳይመጣባቸው፥ ሌሊቱን ሙሉ ሲፈነጥዙ ሲደሰቱ ደስታቸው ከነሱ ተርፎ እቤት የሚያድሩትን ጭምር የሚያደስት መሆኑን፥ እስዋ ለመግለጽ ልጅዋ ለማስተዋል በሚሉበት ቁዋንቁዋ ሳትተርክለት ተከስተ እንዶዳም ከሚፈነጥዙትጉብሎች ጋር ያለ ይመስለውና ለዚያ ሁሉ ደስታ፥ ለዚያ ሁሉ ጨዋታ ተካፋይ የሆነ መስሎ ይሰማውና ባለበት እንዳለ በደስታ ይቁነጠነጣል።

እውነትም ያ ወራት፥ ያ ክረምት ወጥቶ፥ ጸገይ ገብቶ እስኪወጣ ድረስ ያለው ወራት ያ ቀን ሜዳውና ጫካው በልዩ ልዩ አበባ እርሻው በልዩ ልዩ አዝመራ ተዝጎርጉሮ አምሮ የሚታይበት ወራት ያ ክረምትን ወስዶ ጸገይን ላመጣ ፈጣሪ ምስጋናውን በደስታና በጨዋታ በጭፈራና በዝመራ ለመግለጽ እንደ ፈለጉ ሁሉ እንቦሶች ከቀዝቃዛ ጋጣቸው ወጥተው ጸሀይ እዬሞቁ መስክ ለመስክ ሲጨፍሩ የሚታይበት ወራት፥ ያ ወፎችና ንቦች ከዛፍ ወደ ዛፍ፥ ካበባ ወዳበባ እዬተዘዋወሩ ድምጻቸውን አስተባብረው ሲዘምሩ ብራብሮዎች አጊጠው በጉዋድ በጉዋዳቸው እዬሆኑ በዬቁጥቋዋጦዎች ዙሪያ ሲወርቡ ሲያረበርቡ የሚታዩበት ወራት እንዲያው በጠቅላላው ያ ድምሩ ልዩ ልዩ ህብር ባላቸው አዝርእት እጸዋትና ጽጌያት ተጎናጥፎ አዬሩ እኒያ አዝርእት እጸዋትና ጽጌያት በያዝመራቸው መሀከል በተሰሩት ማማዎች ቁጥር እሳታቸውን አንድደው ጨለማው ወደ ብርሀን ሌሊቱ ወደ ቀን ለውጠው እንቅልፍ ሳያምራቸው ድካም ሳይሰማቸው ሲጫወቱ ሲደሰቱ የሚያድሩበት ወራት ያ ከዬማማው ስርና ከዬሳቱ ዳር ባለስንጥርጥይ ስንጥርጥዩን ባላንዲር አንዲሩን ባለክራር ክራሩን ባለመሰንቆ መሰንቆውን ሲጫዋት የኒያ መሳሪያዎች ድምጽ ባንድነት ተዋህዶ በሌሊቱ ጨለማ ብዙ እጥፍ ጊዜ ደምቆ ከጠፈር በላይ ሲያርግ የሰማይ መላእክት የሚጫወቱት አርጋኖር እንጂ የባላገር ጎበዛዝት በባለገር መሳሪያ የሚጫወቱት የማይመስልበት ወራት ያ ከጎበዛዝት ልዩ ልዩ መሳሪያዎችና ከህጻናት ጉሮሮዎች የሚወጣ ድምጽ፤ ባንድነት ሆኖ ተጫዋቾች በማይታዩበት የሌሊት ጨለማ ብቻውን ባዬር ውስጥ ሲዝገመገም የሰማይ፥ መላእክት በሰማያዊ መሳሪያ የሚጫወቱት ልብ የሚመስጥ ሙዚቃ የሚመስልበት ወራት ያ የጎበዛዝት መሳሪያዎችና የህጻናት ድምጽ ባንድነት የሚሰጡት ድምጽ ከሰማይ እንደ መጣ ልብ የሚመስጥ ሙዚቃ ባዬር ውስጥ ሲዝገመገም የመንደሩ ሰዎች ሁሉ በደስታ ተመስጠው ሽቅብ እያንጋጠጡ እዬተመለከቱ ሲሰሙ የሚያመሹበት ወራት ያ ውብ የጸገይ ወራት እዬተመለቱትና ለሚሰሙት የመንደሩ ሽማግሎች ባልቴቶችና ሴቶች ልጆች ጭምር በያመቱ ዞሮ እስኪመጣ የሚናፈቅ አገር ጥሎ ሲሄድ ትዝታው በሄደበት የማይለቅ አብሮ የሚኖር የህይወት ጉዋደኛ ነው!

ደመቀች ያን ሁሉ ጸገይ፥ ገብቶ እስኪወጣ በንዶዳምና በንዶዳም ዙሪያ ባሉት አገሮች ምድሩም አዬሩም ምን እንደሚመስሉና ጎበዛዝቱ ህጻናቱ ባጠቃላይ፥ ልጅ አዋቂው ምን እንደሚያደርግ ለልጅዋ ከተረከችለት በሁዋላ፥ እሱ በስዋ ወሬ ከተዋወቃቸው የንዶዳም ልጆች ጋር ለጨዋታቸውና ለደስታቸው ተካፋይ የሆነ መስሎት ባለበት ባለበት እንዳለ በደስታ ሲቁነጠነጥ፥ እስዋ ያ ሁሉ ሳትጠግበው በውዝፍ የቀረባት የልጅነት ጨዋታ፥ ያ ሁሉ ደስታ፥ ትዝ ብሎዋት፥ ከባድ ቅሬታ ፊትዋን ያጠላውና፥ ያ ሁሉ ደስታ፥ ትዝ ብሎዋት፥ ከባድ ቅሬታ ፊትዋን ያጠላውና

እንባ አይኖቻዋን ይሞላቻውና፥ የታወከ ስሜትዋ እስኪረጋጋ ድረስ ልጅዋ እንዳያውቅባት ስትቸገር ትቆያለች። ከዚያ ሁለት ልጆች ተቃቅፈው ተኝተው ወሬያቸውን ሲቀጥሉ፣ ከስምዋ እሱ ልጅ ስለሆነ እሱን ቀድሞ እንቅልፍ ይወስደዋል። ከዚያ እንዲያ ሰውነቱን አዝንቶ፣ በረዢሙ እዬተነፈሰ ደስ ብሎት እንደተኛ ከራሱ እስከ እግሩ እንደገና እስከራሱ እዬዳሰሰች ቁመቱን እዬለካች ሳይሰማ ትሰማዋለች። ካገርዋ ይዛው ስትመጣ ትንሽ ነበር፤ አሁን አድጎዋል! ያንጊዜ መናገር አይችልም ነበር፤ አሁን ግን የትም አስተካክሎ መቆም እንኩዋ አይችልም ነበር፤ አሁን ግን የትም ሲጫወት ውሎ ይገባል! እንዲያውም በቅርብ ጊዜ አንድ አመት ባልሞላ ጊዜ እዚያው እመንደር ትንንሽ ልጆችን እዬሰበሰቡ ያማርኛ ንባብና ጽህፈት ከሚያስተምሩት ደብተራ ዘንድ መማር ይጀመራል!

ደመቀች ይህን ሁሉ ከገዛ አሳብዋ ጋር ተጫውታ፣ ደስ ብሎዋት ትንሽ ከቆየች በሁዋላ ምንም ልጅ ብትሆን እናት ናትና፥ ወደፊት ልጅዋ ሲያድግ እንዴት አድርጋ እንደምትኖረው ስታስብ መንገዱ ግልጽ ሆኖ አልታያት ይልና ትቸገራለች። «መቸም የመይቴ ጠባይ አይታወቅምና - አንድ ቀን ግልፍ ሲያደርጋቸው ‹ወግጂ› ብለው ካላባረሩኝ እንኩዋ፣ - እስኪያድግ ድረስ - የኔን ምሳና ራት ተካፍለን እዬበላን ልብሱም ቢሆን - ለራሴ ስገዛ ትንሽ ተረፍ አድርጌ ገዝቼ ያን ተካፍለን እዬበላን፥ እስካሁን እንደ ኖርነው ምንም ሳንቸገር እንቆያለን። ብቻ - ካደገ በሁዋላ ያደጉ ልጆች የሚፈልጉትን ምግብና ልብስ መፈለጉ ስለማይቀር ያንጊዜ እንዴት አደርገዋለሁ? እሱም እንደኔ - እዚህ አሽከር ሊሆን ነው? እሱንም እንደኔ - እዚህ አሽከር ሊሆን ነው? እሱንም እንደኔ እመይቴ መመሽ በነጋ ቁጥር - ከፍ ዝቅ እያደረጉ እያዩ ሊሰድቡት ሊረግሙት፣ ነው? አይደረገም! ምንም ቢሆን ልጄ አሽከር አይሆንም! አይዞህ የኔ ጌታ፤ እኔ አሽከር እሆናለሁ፥ እኔን ይሰድቡኛል እኔን ይረግሙኛል እንጂ፥ አንተ አሽከር አትሆንም! አንተ አትዋረድም! ግዴለም እግዚአብሄር ያውቃል! » ትላለች፥ አሳቡን ሁሉ በስዋ ላይ ጥሎ በሰላም የተኛ ልጅዋን እዬሳመችና የስዋንም አሳብ እግዚአብሔር እንዲያስብላት ለሱ አሳልፋ እዬሰጠች። ከዚያ ሌሊቱ ከተገባደደ እስዋንም እንደሱ እንቅልፍ ይወስዳታል።

## ምዕራፍ አስራ ሁለት

# የጨለማ እሳት ወርዋሪ ለጠላቱ መንገድ ይሳያል

ደመቀች ልጅዋ ያማርኛ ትምርህት ከጀመረች በሁዋላ፥ ቀን ቀን ሲማርና ከዚያም በሚተርፈው ጊዜ ከሰፈሩ ህጻናት ጋር ሲጫወት እዩዋለ ወይዘሮ ጽጌ ወዳሉበት መሄዱን ርግፍ አድርጎ በመተው እመቤትዋ እሱን ባዩ ቁጥር በሱ ምክንያት ይናገሩዋት የነበረው ልብ የሚያሳምም መርዘኛ ነገር ስለ ተቀነሰላት በሙሉ ባይሆን በመጠኑ ሰላም አግኝታ ነበር። ነገር ግን ያ ሰላም ረዥም እድሜ አልነበረውም፤ ባቸር ተቆረጠ።

ከደጃዝማች አሰፋ ግቢ አጠገብ የሰፈሩን ህጻናት ሰብስበው እያንዳንዱን ልጅ በወር አምሳ ሳንቲም እያስከፈሉ ያስተምሩ ለነበሩት ደብተራ ደመቀች ስለ ልጅዋ የምትከፍለው ያንድ ወር ሂሳብ ያልተከፈለ መሆኑን አስተማሪው መላልሰው ነግረዋት ስለ ነበረ፥ ደምወዝዋን በተቀበለችበት እለት ልትከፍል ሄዳ፥ ትንሽ ቆይታ ተመለሰች። «ቶሎ እመለሳለሁ» ብላ አስባ የምትሄድበትን ለመቤትዋ አልነገረችም ነበር። ወዲያው እንደ ወጣች ደጃዝማች ገብተው ከምሽታቸው ጋር ተጣልተው ሲቆጡዋቸው ቆይተው ኖሮ እንዲያ ያለ ነገር ሲደርስ ሁልጊዜ እንደሚሆን ሰው ሁሉ ሸሽቶ ወይዘሮ ጽጌ በበኩላቸው የሚቆጡትና ቂማቸውን የሚወጡበት እዩፈለጉ ሲንቆራጠጡ ሲቁነጠነጡ ነበር የደረሰችው።

«አንቺ የታባትሽ ሄደሽ ነው ስትፈለጊ የምትጠፊው? » አሉ ገና ስትገባ ፊታቸው ሁሉ በቁጣ ግሎ።

«ላስተማሪ ገንዘብ ሄጄ ነው እመቤቴ! »

«የምን አስተማሪ ነፍስሽን አይምራትና? »

«ለልጄ አስተማሪ።»

«ልጄ፣ ልጄ፥ ልጄ፥ ሁልጊዜ ልጄ ትለኛለች! ልጅሽ ነው ደመወዝ የሚከፍልሽ? ወይስ እኔ! ሎሌነትሽ ለኔ ነው! ደመወዝ የምከፍልሽ እሱን ጭምር የምመግብ እኔ ነኝ! ይህን ማወቅ አለብሽ! »

«እሺ እመቤቴ! »

«እሺ እመቤቴ ትለኛለች ስታሾብኝ! ይቺ አታላይ ሰባቂ! »

«ኸረ አላሾፍሁም፤ እውነቴን ነው እመቤቴ! »

«አዎ፤ አንቺን እስከ ልጅሽ አሳደግሁ፣ አሹፌብኝ፣ ግዴለም ኧረ የለም፣ ከንግዲህስ አታሾፊብኝም! ያን ልጅሽን እዚህ ግቢ ውስጥ እንዳላየው! ወዲያ ለምትሰጭው ስጭው! እስከ ዛሬ ተሸክሜያለሁ አሳድጌያለሁ! »

«ለማን አባቴ እሰጠዋለሁ? ማን አለኝ! » አለች ደመቀች ሁለት አይኖችዋ ሳይረግቡ ፍጥጥ ብለው ግማሽ በድንዋን በፊታቸው እንደ ቆመች። የተናገረችውን እንዲሁ ደመነፍስዋን ተናገረች እንጂ ምን እንደ ተናገረች አልተሰማትም! «ያን ልጅሽን እዚህ ግቢ እንዳላይ» ሲሉዋት መብረቅ እንደ መታት በድን ሆና ነበር።

እደጃዝማች አሰፋ ቤት ከገባች ጀምራ፥ እዚያ አምስት አመት ስትኖር ስትፈራ የኖረች ወይዘሮ ጽጌ ያነለት ያሉዋትን እንዳይሉዋት ነበር፤ ያ የፈራችው ደረሰ! እዚያ ቤት አምስት አመት ሙሉ ስትኖር ቀን ባሰበችው ቁጥር የሚያስፈራት ሌት ስትተኛ የሚያቃዣት፣ «ልጅሽን ይዘሽ ወዲያ በምትሄጂበት ሂጂ» የተባለች እንደሆነ መሄጃ መድረሻ ስለሌላት በስዋና በልጅዋ ከስዋም ይልቅ ክፉ ነገር ሁሉ ነበር! የምታውቀውም የማታውቀውም ክፉ ነገር ሁሉ ነበር! ያ ቀን ባሰበችው ቁትር የሚያስፈራት ሌት ስትተኛ የሚያቃዣት ክፉ ነገር እንዳይደርስ ነበር ወይዘሮ ጽጌ ምክንያት ፈጥረው ሲሰድቡዋትና ሲረግሙዋት፣ እንደሚመርቁዋት እጅ እዬነሳች ቀን ከሌት፣ «ደከመኝ» ሳትል እዬሰራች አምስት አመት ሙሉ የኖረች። ነገር ግን ያ የፈራችው ያነለት ደረሰ። እንዲያ መብረቅ እንደ መታት በቆመችበት እንዳለች ድርቅ ብላ ቆይታ፥ ወይዘሮ ጽጌ ምን እንዳሉና ያሉት ምን ማለት መሆኑን ማስተዋል ስትጀርም፣ ሮጣ ሄዳ በግራቸው ወደቀች።

«እባክዎ እመቤቴ የዛሬን ይማሩኝ፣ ሁለተኛ አልደግምም» አለች፥ እንዲያ እንደ ወደቀች እግራቸውን ይዛ እንባዋን እያጐረፈች።

«ኧረ ይች ጎረምሳ ልትመታኝ እንው መሰለኝ ኑ ገላግሉኝ! » አሉ ወይዘሮ ጽጌ፥ እያጨበጨቡ። ከዚያ ጭብጨባውን የሰሙ ሰዎች ገብተው በግራቸው ተጠምጥማ ከወደቀችበት በግድ አላቀው ሲያነሱዋት ደመነፍስዋን ልክ እንደ እብድ እዬሮጠች፥ ወጣችና፥ እግቢው ውስጥ ወዳንድ ባሀርዛፍ ሄዳ፥ በግንዱ ተደግፋ ቆመች። አታይ አትሰማ፥ የት እንደሆነች - አታውቅ፣ ፊዛ ደንዝዛ ነበር! ልብዋ እንደ ሌላ አካልዋ ሁሉ ከመደንዘዙ የተነሳ አዘን አልሰማው ብሎ ማልቀስዋ እንኩዋ ቀረ! እንዲያ እንደ ፈዘዘች ቆማ ዘለግ ያለ ጊዜ ከቆየች በሁዋላ፣ «ያን ልጅሽን እዚህ እንዳላየው! » አለ የወይዘሮ ጽጌ ድምጽ በጆሮዋ። «ወዲያ ለምትሰጭው ስጭው! » አለ ደገመና። ከዚያ ትንሽ

በትንሽ ማሰብ ጀመረች። ማሰብ ከጀመረች በሁዋላ ደግሞ የምታስበው ቅጡ ጠፋት፤ ግራ ገባት። ስራ አጥታ ልጅዋን ይዛ ስትንከራተት ልጅዋን ሲርበው ሲደክመው ሲያለቅስ ባልዋ ሲይዛት ሲያባርራት ስታመልጠው፣ ሲይዛት ልጅዋን ሲቀማት ይህን የመሳሰለውና ከዚህ የከፋው የሚያስፈራራ አሳብ ሁሉ ባንድ ላይ ተሰልፎ ባይነ ህሊናዋ ፊት እዬተተራመሰ በራስዋ ውስጥ እዬተንጫጫ ግራ አገባት! ከዚያ ፊትዋን ካጥሩ ወደ ቤቱ መልሳ አጠገብዋ በነበረው ደንጋይ ላይ ተቀመጠችና ያን አምስት አመት የኖረችበትንና ያነለት ወይም በነጋው የምትተውውን ቤት ትመለከት ጀመር። ‹፣አይ ጉ - ድ! ደህና እዚህ ተቀምጬ ማነንም ሳልፈራ ልጄን አሳድጋለሁ ስል እንግዲህ ምን - ምን ሊ - ሊውጠኝ ነው? የታ - የታባቴ ል - ልደርስ ነው? » አለችና እንደገና ሳግ እዬተናነቃት እንባዋን ታጎርፍ ጀመር!

«ምነ፣ ምን ሆንሽ የኔ እናት? » አሉ አዛዥ ተካልኝ የቤቱ አዛዥ ከውጭ ሲገቡ ስታለቅስ ሳላዩዋት ወደስዋ ሄዱና። ሳግ ስለሚተነቃት ልትመልላቸው አልቻለችም።

«እንዴ፤ ምንድነው ነገሩ? እስቲ ንገሪኝ! » አሉ አጠገዋ ተቀምጠው ትከሻዋን ራስዋንም እዬደባበሱና እያባበሉ።

«የም - የምሄድበት ጠፍቶኝ ነው! » አለች ደመቀች ከሳግ ጋር እዬታገለችና እንባዋን በልብስዋ እዬጠራረገች።

«የምሄድበት ጠፍቶኝ? ምን ማለትሽ ነው? »

«እመ - እመይቴ» ል - ልጅሽን እግቢዬ እንደ - እንዳላየው» አሉኝ፤ ስ - ስለዚህ ስለዚህ ወዴት ይ - ይገፔው እንደምሄድ ቅጡ ጠፋኝ።፡»

«እኮ አታልቅሺ! ታዲያ እኔ አባትሽ አለሁልሽ አደለም እንዴ! በይ አሁን ዝምበይ! አይዞሽ፤ የሚስማማሽ ስራ እስከታገኝ እኔ አባትሽ ቤት ትቆያለሽ ምንም አይቸግርሽ! » አሉ አዛዥ የልባቸውን አዘንና ርህራሄ መልካም የሽማግሌ ፊታቸው ወለል አድርጎ እያሳዬ። አዘናቸውን ከፊታቸው ስታይና ያባትነት ማጽናናታችውን ስትሰማ እንባውና ሳጉ ባሰባት። ከስዋ ልብ ተርፎ ለሳቸው ልብ የተሰማውን ብርቱ አዘን ከፊታቸው ስታይ እንባዋንና ሳግዋን መግታት አቃታት! ሁዋላ አዛዥ ተካልኝ በማባበልም በመቆጣትም ጸጥ እንድትል አደረጉዋት።

«አይዞሽ! ልጅሽን ከሆነ እሜቴ ‹አልፈለግም› ያሉት ይዘሽው እኔ ቤት ሆነሽ አንቺ ከዚያ እዬተመላለሽ ስራሽን ትሰሪያለሽ። የኔ ቤት ቤትሽ ነው፤ ባለቤቴ ጌጤም እናትሽ

ነች፤ ግዴለሽም አትከብጅንም አትጨነቂ። የዚህን ቤት ስራ ትተሽ ሌላ ስራ ብትፈልጊም እኔ አባትሽ አገኝልሻለሁ» አሉ አዛዥ የሳቸውን ማባበልና መቆጣት ሰምታ ጸጥ ማለት ስለ ጀመረች ደስ ብሎዋቸው።

«እዚህ ልጄን ጌቶችበደህና አይን ስለሚያዩትና እኔም አንድ ክፉ ነገር ቢደርስብኝ እሳቸው ጋሻ ይሆኑኛል ብዬ - በዚህ ምክንያት ነበር ሁሉንም ችዬ የተቀመጥሁ»

«እኮ የጌቶችን ጥግነት ከፈለግሽ እዚሁ ስራሽን ትቀጥያለሽ። መቸም እሜቴ - ልጅሽን እንደሆነ እንጂ አንቺን አይጠሉ። ይህን ካልፈገሽ - እንኩዋን አንቺ ሌሎችም ስራ አያጡ ‹ስራ ሞልቶዋል› ነው የምልሽ።»

«ከዚህ ብወጣም ምን ስራ አገኛለሁ አባባ? »

«ስራ? ላንቺ? ሆሆ! እንዲያው ሌላውን ሁሉ እንተወውና አሻሻጭስ ብትሆኝ - ባንድ ወር ውስጥ እዚያ ያሉትን ሁሉ ወደ ታች ትተሽ እዚያ ላይ አትሸርሽም? የኔ ልጅ ከስጡንነትሽ ሌላ ውበትሽ የበዛብሽ ቆንጆ ነሽ! በዚያ ላይ ልጅ ነሽ» አሉ አዛዥ፥ ሲሉ በጃቸው ወደ ላይ ወደ ስማይ እያመለከቱ።

«የምን አሻሻጭ? » አለች፤ ሲያባብሉዋትና ሲቆጡዋት ለስለስ እያለ ሲሄድ የነበረው ፊትዋ ክርር፥ ግንባዋ ኩምትር ሲሉ እዬታያት።

«የመጠጥ አሻሻጭ! ሁሉምኮ ሲጀምሩ አሻሻጭ ሆነው ነው የሚጀምሩት። ከዚያ በሁዋላ እንዲህ እንዳንቺ ቆንጆዎችና ስልጡኖች፣ እዚያ ከሚመጡት ሁሉ ተዋውቀው ይላመዱና በአጭር ጊዜ ራሳቸውን ችለው የገዛ መጠጥ ቤታቸውን ይከፍታሉ»

«ኧረ በስመአብ! ምነ ምን አልሁዎ አባባ? አባክዎ እንዲህ ያለውን ነገር ደግመው አያንሱብኝ! »

«እንዴት? ምን መስለሽ? ዛሬኮ ምቾት ያለ ሀብት ያለ እነሱ ዘንድ ነው! ከነሱ መሀከልኮ ከደጃዝማቾች ቢበልጥ እንጂ የማያንሱ ሀብት ያላቸው ሞልተዋል! »

«እንደሚሉት ሊሆን ይችላል፤ ነገር ግን ለኔ የሚሆን አደለም አባባ።»

«ለሌሎች የሆነው ላንቺ የማይሆንበት ምን ምክንያት አለ? ከቆንጆዎች ሁሉ የላቅሽ ቆንጆ ስለሆንሽ ነው? »

ደመቀች ስለጠየቁዋት መልስ ሳትሰጥ አንገትዋን ደፍታ ቆይታ ቆሞ የነበረው እንባዋ እንደገና እዬወረደ ቀና አለችና፥

«ልጅቱ ልጅ አዬ፣ አገሬን ጥዬ የተሰደድሁ ከወንድ ሸሽቼ መሆኑን ነግሬዎታለሁ፤ ከዚህ ቤት ወንዶች ጋር የነበረኝን - ምን ልበለው? ጦርነትም ከማንም የበለጠ እስዎ ያውቃሉ! ታዲያ ይህን ሁሉ እያወቁ - ወንዱ ሁሉ ወደሚሰበሰብበት መጠጥ ቤት ሂጂና እዚያ - የሰከረው ሁሉ ይቀራመትሽ ይሉኛል? »

«ተይው አታልቅሽ ይቅር። እኔ እንኳዋ - እንዲህ ማለቴ አልነበረም፤ ነገሩም ላንቺ እንደ መሰለች ይህን ያክል ክፉ አይደለም። የብዙ መኳዋንንትና ወይዛዝርት ልጆች ወላጆቻቸውን እዬተዉ የብዙ መኳዋንንት ሚስቶች ባሎቻቸውንና ቤታቸዉን እዬፈቱ ‹ይጠቅመናል፥ የመቸናል› ብለው የሚገቡበት መሆኑን ስለማውቅና እንዲያው ከራሳቸው አልፈው ወላጆቻቸውንም፥ ዘመዶቻቸውንም ጭምር ረድተው ልጆቻቸውን ብቻ ሳይሆን የዘመድ ልጆች ጭምር እያስተማሩ አሳድገው ስለሚኖሩ፥ «አንቺም የሰው ፊት ከማየት ድነሽ ዘመድ ለመርዳትና ልጅሽን እያስተማርሽ ለማሳደግ ትበቂያለሽ› መስሎኝ ነው እንጂ እንድትጎጂ ብዬ አልነበረም። ነገር ግን ክፉ ከመሰለሽ ይቅር» አሉ አዛዡ የቅርታ መልክ እዬታዬባቸው።

«እስዎስ የሚጠቅመኝ መስሎዎ ነው እንጂ የሚጎዳኝን እንደማይመክሩኝ አውቃለሁ። ብቻ እኔ - እንደ ነገርሁዎ እፈራለሁ» አለችና አንገትዋን ደፍታ ስታስብ ቆይታ «የምፈራ ባልሆን እንኳዋ» አለችና ቀና ብላ አዛዥን እያሳዬች «የምፈራ ባልሆን እንኩዋ ስራ ባገኝ ቀን ከሌት ሰርቼ ስራ ባጣ ‹ምንተማርያም› እያልኩ እዬለመንሁ ልጄን አሳድጋለሁ እንጂ የሴትኛ አዳሪነት ስራ አልሰራም አባባ። ‹ሴተኛ አዳሪ ሆነች› ተብዬ ወላጆቼ ከሚረግሙኝ ከሚክዱኝ ለልጄም ማፈሪያ ከምሆን፣ ለምኘ ብበላ ይሻለኛል። አገራችን እንዶዳም ሴተኛ አዳሬንት ብርቱ ነውር ነው። ‹አንድ ልጅ ሴተኛ አዳሪ ከሆነች ወላጆችዋ ይክድዋታል፤ እንደ ሞተች ቆጥረዋት አልቅሰው እርማቸውን ያወጣሉ› ይባላል።»

«ይህ እንኩዋ ሞኝነት ነው። ዛሬ የሚያስደብ የሚይዋርድ ድህነት ነው። ሀብት ካለሽ እንደ ምንም ብታገኚው ካንቺ አልፎ ወገንሽን ሁሉ ያስከብራል እንጂ አያዋርድም። ልጅሽም ቢሆን - መቸም ልጅ ከራስ በሁዋላ ነው። ‹ልጅ እንዳይወድቅ

ራስ ይቁም› እንደሚባለው አንቺ ከሌለሽ ልጅሽ ሊኖር አይችልምና መጀመሪያ ለራስሽ ማሰብ አለብሽ።»

«እንጃ እኔስ በኔ የደረሰ ደርሶብኝ ልጄን ቅር የሚያሰኝ ነገር አያግኝብኝ ይህ ብቻ ነው ምኞቴ»

«ይህኮ ያንቺ ብቻ አደለም የናቶች ሁሉ ምኞት ይሄው ነው፤ ብቻ ስህተት ነው»

«እንዴት? »

«መጀመሪያ ከሁሉም የሚቀርብ ራስ ነዋ! ልጅ ከራስ በሁዋላ ነው። ልጅም ቢሆን ካደገ በሁዋላ መጀመሪያ ራሱን ችሎ ነው ወላጆቹን ወደ ማሰብ የሚሄደው። ያውም ካደጉና ራሳቸውን ከቻሉ በሁዋላ እንኳዋ ወላጆቻቸውን የሚያስቡና የሚረዱ ከስንት አንድ ናቸው ይመስልሻል? »

«አባባ፥ የኔ ልጅ እንደ ሌሎች አይምሰልዎ። አሁን እንኳዋ በዚህ እድሜው ሲያስብልኝ ቢያዩት! እሱ ከሚበላ እኔ ስበላ ማየቱ ደስ ያሰኘዋል። ‹ስታድግ ምን ታደርጋለህ?› ብለው ቢጠይቁት የሚነግርዎ ሁሉ ለኔ የሚያደርገውን ነው። እውነቴን ነው፤ ሲያገኙት ይጠይቁት።»

«ይሆናል አንቺ እንደምትይው ይሆናል። ብቻ አሁን የሚለውና ሁዋላ የሚያደርገው አንድ አይሆንም። ሁውላስ መጀመሪያ ራሱን ሁለተኛ ሚስቱን እድላም እንደሆንሽ - አንቺ ሶስተኛ ወይም አራተኛ ብትወጪ ነው! ያውም አሁን እንዳልሁሽ እድላም የሆንሽ እንደሆነ ነው! »

«እንዴት? ለምን? »

«እኔ ምን አቃለሁ? ልጄ! ‹የናትና ልጅ ፍቅርና የኸረት ውሀ፣ ከላይ ወደ ታች እንጂ ከታች ወደ ላይ አይፈስም!› እንደሚሉት ተረት ቢሆን ነዋ! »

«ምን ማለት ነው? »

«ፍቅር እንደ ውሀ ሙላት ከላይ - ካናት ወደ ታች ወደ ልጅ ይወርዳል እንጂ ከታች፣ ከልጅ ወደ ላይ ወደናት እጅግም አይሄድ ማለት ነዋ! »

«ኡም - እንጃ! »

«እንዴት እንጃ! ባንቺ በራስሽ አታይውም? አችኒ ወልደው ለፍተው ያሳደጉሽን እናትና አባትሽን - ትናንት እንዳገኘሽው ልጅሽ ትወጃቸዋለሽ? » ደመቀች አንገትዋን ደፍታ ዝም አለች።»

«አይ፥ እኔ እንኩዋ» አሉ አዛዥ እሳቸውንም አንገታቸውን ደፍተው ሲያስቡ ቆዩና። «እኔ እንኩዋ የዚያን - የመጠጥ ቤቱን ስራ ያነሳሁልሽ - አንቺን ተመችቶሽ ወዲያውም ልጅሽን በደህና ታሳድጊያለሽ ብዬ ነበር። ላንቺ ነውር መስሎ ታይቶሽ ‹ዳግመኛ አታንሳብኝ› ስላልሽኝ አላነሳውም። ብቻ - እንዲያው ለነገሩ የናንተን አገር አላውቅም እንጂ አገር ሴተኛ አዳሬንት ዛሬ እንደ ነውር የሚቆጠር አለመሆኑን ብታውቂ አይከፋም።»

«እሱን መቸም - ዳግመኛ አናንሳው ብለናንል፣ አናነሳውም ነገር ግን - » አለችና አይኖችዋን ሳታረግብ ፊት ለፊት ተክላ ቆይታ ወደሳቸው መለስ ስታደርግ እንባ ሞልተው አዩ።

«አንቺ ልጅ ዛሬ ምን ሆንሽ? ለምን እንዲህ ሆደባሻ ሆንሽ? ብርቱ አልነበርሽም? » አሉ አዛዥ፥ እንደ መቆጣት ብለው።

«የልጄን ነገር ምን እንደማደርግ ቅጡ ጠፋኝ፥ ጨነቀኝ አባባ! »

«ታዲያ ልቅሶ ሆድ ያስብሳል እንጂ ከጭንቀት ያወጣል? »

«እሱስ እውነትዎ ነው። ብቻ - ልጄ በኔ ምክንያት እስከ ዛሬ የተንገላታው አልበቃ ብሎ እኔ ኑሮዬን ስለ ጠላሁ ለኔ እንዲሻለኝ ብዬ አባቱ ቤት ደህና ተቀማጥሎ የሚያሳድገውን ልጄን ያለዳው ያለ ጥፋቱ እስከ ዛሬ ያንገላታሁት አልበቃ ብሎ፥ ጋሬ በዶዮ እዬበላ፥ የተደረተ ልብስ እዬለበሰ በገባ በወጣ ቁጥር እዬተረገመና እዬተደበደበ እስከዛሬ የኖረው እንደ ኑሮ ተቆጥሮ ይህን እንኩዋ ሊያጣነው! ከዚህ የባሰ ሊንገላታ ነው! » አለች አይኖችዋን ሞልቶ የነበረው እንባ ማገጃውን እንደ ሰበረ ሙላት ፊትዋን ዘቅዝቆ እያጥለቀለቀ።

«ተይ ልቅሶ አታብዢ ልቅሶ ደግ አደለም። ወዲያውም - የተጎዳሽ አንቺ ነሽ እንጂ፣ እስከ ዛሬ ልጅሽ ምንም አልተጎዳ! ልወደፊቱም እግዜር ያውቅለታል» አሉ አዛዥ ቁጣው ምንም ያክል እንዳልረዳ ሲያዩ ለስለስ ባለ አነጋገር «ተይ እግዜር አይወድም፥ በከንቱ ራስሽን አትውቀሺ! አንቺ ተጎዳሽ እንጂ እሱ ምንም አልጎደለበት»

አሉ ደገሙና። «እንዲህ እንደኛ የማያውቅ፣ ተከስተን ‹የሚበላውና የሚጠጣው በጥንቃቄ ተመርጦ እዬተሰናዳለት በስልጡን ሞግዚት የሚያድግ የጌታ ልጅ ነው› ይላል እንጂ ያንቺ ልጅ መሆኑን የሚያምን ማነው? ይልቅ ለሱ ብለሽ የተጎዳሽ አንቺ ነሽ። ሁላችነን የምታሳዝኝን አንቺ ነሽ። ከኒህ ክፉ ሴት በቀር በቤቱ ውስጥ ላንቺ የማያዝን የለም። ‹ተቸግሮ የገባን ሎሌ አስቸግሮ መግዛት ይሻላል› እንደሚሉት ተረት፣ ተቸግረሽ አገኙሽና ‹ያታባትዋ ትሄዳለች› ብለው አስቸገሩሽ! ይህ ነው ሁላችነን የሚያሳዝነን።»

«እኔስ መቸም - ‹ይሻለኛል› ብዬ የመረጥሁት ነው፥ ግዴለም። አለች ደመቀች፥ አንገትዋን ደፍታ በግር አውራ ጣትዋ መሬት እዬቆረቆረች። ከዚያ ሁሉቱም ዝም ብለው በዬበኩላቸው ሲያስቡ ቆዩና፣

«ጌቶችኮ ተከስተን በጣም ይወዱታል፣ እንደ ልጃቸው ነው የሚያዩት ደመቁ! » አሉ አዛዥ።

«እንደሱ ይህን ቤት መልቀቅ የማልወድበት ምክንያት ይህ አደል አባባ? ያው እስዎ እንደሚያውቁት፥ ገና ትንሽ ልጅ ሳለ እንኩዋ እያቀፉ ሲያጎርሱት ንፍጡንም ሆነ ለሀጩን በገዛ መሀረባቸው ሲጠርጉለት ሲያንቀባሩት ለማያውቅ ሰው የወለዱት ልጅ እንጂ ያሽከራቸው ልጅ ይመስለዋል? »

«አዎ በጣም፥ ነው የሚወዱት። ታዲያ አሁን ይህን ያነሳሁት አንድ አሳብ በራሴ ውስጥ ብልጭ ብሎብኝ ነው።»

«ምን? »

«ለምን እፈረንጅ ትምህርት ቤት አዳሪ አድርገው እንዲያስገቡልሽ አትለምኛቸው? »

«ዋጋው በጣም ውድ ነው አሉ፤ እኔት አድርገው ያስገቡልኛል? »

«እዚያ ጥበብ ምንስቴር ‹እዝቤክተር ነው? ዲኔክተር› የሚባል የታቸውን ልጅ ያገባ ሰው አለ፤ ምንስቴሩም ወዳጃቸው ንወ። ለነሱ ‹አደራ› ብለው ቢነግሩዋቸው ያለዋጋ ያስገቡልሽ ይሆናል፤ ምን ይታወቃል? »

«አይ - ይህንማ ቢያደርጉልኝ እድሜዬን ሙሉ ባሪያ ሆኘ ያለ ደመወዝ በተገዛሁላቸው! »

«ያደርጉልሻል፤ በግራቸው ወድቀች ለምኛቸው።»

«ደግሞ እመይቴ ‹ሄዳ አሳበቀች› ይሉኝ ይሆናላ! እንዲያውም ባልዋልሁበት ‹አሳባቂ› የሚሉ ስም አውጥተውልኛል! »

«ልጅሽን ከቤቴ አውጭልኝ አሉኝ ብለሽ ብትናገሪ፤ እንዲያው በደፈናው ‹ልጄን ተማሪ ቤት ያሰቡልኝ› ብለሽ ነው የምትለምኛቸው»

«አይዞሽ አትፍሪ ጌቶች ደግ ናቸው። እኔ እንኳዋ ብነግርልሽ ግዴለሽም ነበር፤ ብቻ ነገሩ አንቺ እንደምትነግሪያቸው አይከብዳቸውም ብዬ ነው። አዬሽ? ለማንም ቢሆን፥ ባለጉዳዩን ከመግፋት የባለጉዳዩን መላከተኛ መግፋት አይከብደውም! »

«መቸ ልንገራቸው? »

«ዛሬ ንገሪያቸው፤ ከሄዱበት ሲመለሱ ለብቻ ተቀብለው እንዲያነጋግሩሽ እኔ ነግሬ እጠራሻለሁ።»

«እሽ አባባ እንዲያው - እንጃ! እግዚአብሄር እስዎን ባይሰጠኝ ምን ይውጠኝ ኖሮዋል? »

ደጃዝማች ከዋሉበት ተመልሰው ትንሽ እንዳረፉ፥ አዛዥ ተካልኝ ተስፋ እንደ ሰጡዋት ነግረውላት ተጠራች። ደመቀች እጅ ነስታ ቀና ስትል ደጃዝማችን እንደ ተቆጡ አይኖቻቸውን ፍጥጥ አድርገው ሲመለከቱዋት አይታ ፈራችና፣ የምትናገረው በቃልዋ ስታጠናው የቆየችው ነገር ጠፋት። አዛዥ እንደ ነገሩዋት እያለቀሰች እግራቸው ላይ መውደቁን እንኳዋ ረሳችው! በሁዋላ የተበታተነ አሳብዋን እንደ ምንም ብላ ከዚያም ከዚያም አጠረቃቅማ አንገትዋን እንደ ደፋች ባልተያያዙ ቃልቾ እዬተደናቀፈች በረዢሙ ስትናገር ዝም ብለው ሲሰሙ ቆይተው፥

«እኮ፥ ባጭሩ ተከስተን ትምህርት ቤት እንዳስገባልሽ ነው የምትፈልጊው አደለም? » አሉ ደጃዝማች ፍራትዋን ሲያዩ አሳዘነቻቸውና ፈገግ ብለው።

«አዎን ጌቶች! » አለች አንገትዋን እንደ ደፋች።

«ባዳሪነት ለማስገባት የሚያስከፍሉት በጣም ብዙ መሆኑን አታውቂም? »

«ጌቶች እንዲፍሉኮ አይደለም ለምንስቴሩ እንዲነግሩልኝ ነው።»

«እ - ለዚያውም ቢሆን ለሚኒስትሩ ከኔ ይልቅ አንቺ ብትነግሪው ይሻላል። እኔ ሄጄ ብለምንሽ ከብዶኝ አይደለም፣ አያደርግልሽም ብዬ ነው። እኔ ስነግረው ልጅ ዘመዴ ይመስለውና ‹ለምን ከፍለህ አታስተምርም?› ይለኛል። አንቺ ግን ድህነትሽን ገልሰሽ ብትለምኚው እግዚአብሄር ከረዳሽ የድሆችን ልጆች እያስመሰከሩ ስለሚቀበሉ ያንቺን ልጅም ይቀበልሽ ይሆናል። ‹ድህነትሽን አስመክሪ› የተባልሽ እንደሆነ እኔ ምስክር እሆንሻለሁ። እንዲያውም እኔ የምመክርሽ ሌላ ሰው እንኳዋ ‹ልንገርልሽ› ቢልሽ ‹እሺ› እንዳትይ ነው። አንቺ ራስሽ ሄደሽ የነገርሽ እንደ ሆነ ነው ‹እሺ› የሚልሽ። ግዴለሽም የኔን ምክር ስሚ።»

«እኔ - የት አገኛቸዋለሁ? » አለች፥ በተሰበረ ድምጽ ልቅሶ መጣባትና።

ደጃዝማች ልክ እንደዛዥ ተካልኝ «አይዞሽ ግዴለም አትቸገሪም» ይሉኛል ብላ ተስፋ ስታደርግ ችላ ያሉዋትን የገፉዋት ስለመሰላት ተስፋ ቆረጠችና ስሜትዋ በምሬት ተመረዘ። ደጃዝማች ግን የሚኒስትሩን ጠባይ ስለሚያውቁ «በውነት ጉዳይዋ የሚቃናላት ራስዋ ሄዳ ስትለምን ነው» ብለው በማመን ነበር እንጂ ለስዋ እንደ መሰላት ችላ ብለው ወይም ለግመው አልነበረም።

«ቦታውን ተካልኝ ይሾሽ ሄዶ ያሳይሽና ጥዋት ቀደም ብለሽ ወይም ማታ ሰራተኛ ከወጣ በሁዋላ የሄድሽ እንደሆነ ነው በግላጭ የምታገኚው» አሉ ከዚያ አዛዥ ተካልኝን ጠርጠው ራሳቸው ወስደው የትምህርት ሚኒስቴርን እንዲያሳይዋትና እንዲረዱዋት ነገሩላት።

ደመቀች ያነለት፥ ማምሻዋን ወደ መቤትዋ ጭራሽ ብቅ አላለችም። አምስት አመት ሙሉ ያ፥ ያነለት የደረሰው አመት እንዳይደርስባት የወይዘሮ ጽጌ ብትር ሳያማት ቁጣቸው፥ ርግማናቸው ሳይሰማት ጊዜ የሌለው ስራቸው ሳይከብዳት ሁልጊዜ ታጥቃ ተጠንቅቃ ሰራች። ጽኑ እመም ታማ አታውቅም እንጂ፣ አንዳንድ ጊዜ ራስ ምታትዋ ሲነሳባትና ምችም ይሁን ወይም ሌላ፥ ቀለ ያለ እመም ሲያማት እንኳዋ «እስቲ ተኝቸ ላሳልፈው» ብላ አታውቅም። አምስት አመት ሙሉ ሁልጊዜ ወይዘሮ ጽጌ እንዳቃቤ መላካቸው ሳትለያቸው ጥዋት አስነስታ ማታ አስተኝታ የሚያስፈልጋቸውን ሁሉ አድርጋ፥ ብዞች ያልቻሉትን ከፉ አመላቸውን ችላ ኖረች ይህ ሁሉ ያ ያነለት የደረሰው እንዳይደርስ ነበር፤ ደረሰ! የፈሩት እንዳይደርስ መፍራት ጠንቃቃነት የፈሩት ከደረሰ በሁዋላ መፍራት ጅልነት ነው! ስለዚህ ወይዘሮ ጽጌ ያደረጉትን ካደረጉ በሁዋላ እንደገና

እሳቸውን መለማመጥ ጅለንት ወራዳነት መስሎ ታያትና ምንጣፍዋንና አንዳንድ እቃዋን ጠቅልላ ወዳዛዥ ተካልኝ ቤት ሄደች።

## ምዕራፍ አስራ ሶስት

# ደመቀች በትምህር ሚኒስቴሩ ፊት

ደመቀች ልጅዋንና እቃዋን ይዛ እደጃዝማች አሰፋ ግቢ አምስት አመት ከኖረችበት ቤት ወጥታ አዛዥ ተካልኝ ቤት ያደረች እለት ባይንዋ እንቅልፍ አልዞረም። ካገርዋ ከንዶዳም ኪዳነ ምህረት ወጥታ ማርቆስ ስትደርስ ከዚያ በሁዋላ ወዴት እንደምትሄድ ግራ እንደ ገባት ሁሉ ከደጃዝማች አሰፋ ቤት ልጅዋን ይዛ ወጥታ ወዴት እንደምትሄድ ጠፍቶዋት፣ ዙሪያው ገደል ሆኖባት እንዲሁ እንደ ተጨነቀች እንደ ተወራጨች አድራ እንደ ሳታት ቁዋሚ፣ ገና ሳይነጋ ተነስታ አዛዥን ቀሰቀሰችና «ትምህርት ምንስቴር ይውሰዱኝ» አለቻቸው።

«እንዴ! ጌቶችኮ ‹ከጥዋቱ ቀደም ብላችሁ ሂዱ› አሉ እንጂ ‹ከሌሊቱ ቀደም ብላችሁ ሂዱ› አላሉም? አሁን ገና ሌሊት ነው፤ ሂጂ ተኚ» አሉ አዛዥ ሲያፌዙባት።

«እባክዎ በሁዋላ አናገኛቸውም።»

«ከሁለት ሰአት በፊት አይገቡም፤ ቢሆንም እኛ ባንድ ሰአት እዚያ እንደርሳለን። አሁን ገና አስራ ሁለት እንኩዋአ ልሞላም፤ አስራ አንድ ሰአት ተኩል ነው» አሉ። ባንድ ሰአት እትምህርት ሚኒስቴር ሲደሱ ያጥሩ በር ገና አልተከፈተም ነበር።

አንድ ሰአት ተኩል ላይ፥ አንድ ሰው በትንሽ መኪና መጣና እበሩ ቆሞ ጥሩንባ ይነፋ ጀመር። ከዚያ እውስጥ የሚኖሩት ዘበኝኖችም ሌሎችም ብቅ አያሉ ያችን ትንሽ አቶመቢል ሲያዩ ወዲህ - ወዲያ መሩዋሩዋጥ ስለ ጀመሩ አዛዥ ተካልኝ ራሳቸውን

ዝቅ አድገው ከኦቶመቢልዋ ውስጥ ያሉትን ሰው አዩና፤ «ወላዲታምላክ፣ ወላዲታምላክ ምንስቴሩ ናቸው! » ሲሉ ያ «ምኒስቴሩ» ያሉት ባለ ግርማ ቃል ደመቀችን አስፈራትና ትንቀጠቀጥ ጀመር።

«አይዞሽ አትፍሪ፥ ጠጋ በይና እጅ ንሻቸው፣ ዝም ብለው ለማለፍ የሞከሩ እንደሆነም ከኦቶመቢሉ ፊት ውደቂ! » አሉ ቀስ ብለው።

ደመቀች እዬፈራች እንደ ተመከረችው ወደ ኦቶመቢሉ ጠጋ ብላ እጅ ስትነሳ ሚኒስትሩ በብርቱ መመረርና በብስጭት መልክ ገላምጥዋት ፊታቸውን ከስዋ አዞሩ።

በዚያ ሰአት ቡና እንኩዋ ሳይጠጡ ማልደው መምጣታቸው ከሶስት ሰአት ጀምሮ እንደስዋ የሚረባም የማይረባም አቤቱታ ያላቸውን መቀበሉና የዬለቱን ጥቃቅን ያስተዳደር ጉዳይ ማስተናበሩ በዚያ ላይ ግቢ ሄዶ ሲጠብቁ ወይም ጭራሽ ያላሰቡትን ስራ ሲሰሩ መዋሉ ይህ ሁሉ ስራቸው፣ በጠቅላላው የሚሻሻልበትን ለማሰብና እቅድ ለማቀድ ጊዜ ስለማይሰጣቸው፣ በግላጭ በጸጥታ፥ እቢሮዋቸው ተቀምጠ ትንሽ ለማጥናትና አንዳንድም ያሰቡዋቸውን መሰርታውያን አሳቦች በወረቀት ላይ ለማስፈር ነበር። ያው እንግዲህ ያንለትም መቀረቱ ነው! ሚኒስትሩ ፊታቸውን እንዳዞሩ ይህን ሲያስቡ ቆይተው «ምን - እንደዚህች ያሉት ርጉሞች አያሰሩም! የትም ቢሄዱ የትም ቢሸሹ ከነዚህ ማምለጥ አይቻልም! ከቶ ምን ማድረግ ይሻላል? የሚያይ ሰው እብድ ባይል ይችን ከዚህ ወትቶ መርገጥ ነበር! » እያሉ ባሳባቸው ሲያማርሩ ዘበኖች በሩን ከፈቱ። ደመቀች አዛዥ እንደ መከሩዋት ከኦቶመቢሉ ፊት ወድቃለች።

«ይችን - » ብለው የሚያጠግባቸው ስድብ ፈልገው ሲያጡ፥

«አንሱና ወዲያ ጣሉዋት! » አሉ በብርቱ ቁጣ።

ከዚያ ሁለት ዘበኞች ከወደቀችበት ለማስወገድ ተጋግዘው ሲጎትቱዋትና ወዲያ - ወዲያ ሲያንከባልሉዋት ቆይተው በመጨረሻ ተሸከመው ሲያነሱዋት የመሬቱ ትቢያ በንባዋ እዬተለወሰ በቦካው ጭቃ ፊትዋ ተበክሎ፣ እስዋ መሆንዋ አይታወቅም ነበር! ቢሆንም ያ በንባዋ የቦካ ጭቃ ፊትዋን ያበላሸው ውበትና ደምግባትዋን ይሸሽገው እንጂ ጭንቀትዋን መሸሸግ አልቻለም! ጭንቀትዋ መድረሻ የጠፋት መሆንዋ ከተስፋ መቁረጥ አፋፍ ላይ ቆማ የምትጨብጠው ያጣችና ግራ የገባት መሆንዋ፥ የተበከለችበትን ጭቃ አልፎ ሁሉንም አሸንፎ ይታይ ነበር! ጭንቀትዋ መሄጃ ያጣች መሆንዋ በፊትዋ ላይ በጉልህ ተጽፎ ይነበብ ነበር!

«ምናባቴ ላርግ? ጨንቆኝኮ ነው ጌታዬ! » አለች ዘበኞች ከኦቶመቢሉ ፊት አንስተው ተሸክመው ወዲያ ሲወስዱዋት የተጨነቁ አይኖችዋን ላንድ አፍታ ወደ ሚኒስትሩ ወርወር አደረገችና። እሳቸውም እንዲሁ ላንድ አፋታ እኒያን የተጨነቁ አይኖችና ያን የተጨነቀ ፊት አዩ፥ ዘበኖች ተሸክመዋት ሲሄዱ ያለችውንም ሰሙ።

እንዲህ ያለው ነገር አዲስ አይደለም። በቀን ብዙ ጊዜ የሚደርስ ነው። ከባድም ይሁን ቀላል ችግር የገጠማቸው ሰዎች በሰው ደርሶ የማያውቅ ችግር ወይም በደል፥ የደረሰባቸው መስለው ለመታየትና የባለስልጣንን አሳብ ለመማረክ ከሚፈጥሩት ልዩ ልዩ ዘዴ፣ አንዳንዶቹ በር ይዘው «አናስወጣም፤ ወይም አናስገባም» ይላሉ። ሌሎች ከባለስልጣን እግር ላይ ወድቀው፥ «ረግጣችሁን ሂዱ» ይላሉ። አሁንም ሌሎች እንደ ደመቀች ከኦቶመቢሉ ፊት ይወድቃሉ። በመጨረሻ የሁሉም ጉዳይ ሲመረመር ምን እንኳዋን ከመሀከላቸው ያላግባብ የተበደሉና በጣም የተቸገሩ ቢገኙባቸው የሚበዙት፥ «ተበደልን ተቸገርን» የሚሉት ያን ያክል የሚያበሳጭና የሚያስመርር ሳይሆን ይገኛል! ስለዚህ ይህን የመሰለውን ያቤቱታ ማቅረቢያ ዘዴ የተለመደ ሆነና ባለስልጣኖችን እንደ ሌላው ተራ የጉዳይ ማቅረቢያ ዘዴ ቆጥረውት እጅግም አይከብዳቸውም።

ነገር ግን ሚኒስትሩ ያነለት ከኦቶመቢላቸው ፊት ወድቃ የነበረችዋ ልጅ ዘበኖቻቸው ካስወገዱላቸው በሁዋላ ወደ ውስጥ ለመግባት ኦቶመቢላቸውን ሲያስነሱ እስዋንም ብዙ ጊዜ በፊታቸው ሲወድቁ አስነስተው እያለፉዋቸው እንደሚሄዱት አቤት ባዮች ለመርሳት ቢሞክሩ አልሆላቸው አለ! እስዋን ዘእብኞች ተሸክመው ወዲያ ሲወስዱዋት የተጨነቁ አይኖችዋና የተጨነቀ ፊትዋ በፊታቸው የተጨነቀ ድምስዋ በጆሮዎቻቸው ቀሩ! ኦቶመቢላቸውን እዬነዱ ወደሚያቆሙበት ሲሄዱም አይኖችዋ ፊትዋ ድምጽዋ አብርዋቸው ሄዱ! «ምናባቴን ላድርግ!? ጨንቆኝኮ ነው ጌታየ! » ይላል ድምጽዋ እዬደጋገመ በጆሮዎቻቸው ውስጥ። የተጨነቁ አይኖችዋና ፊትዋም ፊት ፊታቸውን ይሄዳሉ! ኦቶመቢላቸውን አቁመው ወደ ጽህፈት ቤታቸው ለመግባት ደረጃውን ሊወጡ ሲሉ፣ እኒያ አይኖችን ያ ፊት በደረጃው ከላይ ታች ተነጥፈው፥ ሁሉም እዬተሰቀዩ ወደ ላይ የሚያዩዋቸው መሰላቸውና ደረጃውን መርገጥ ፈሩ! ወዲያው ቶሎ መለስ አሉና «አንተ ዘበኛ ያችን - ከኦቶመቢሉ ፊት ወድቃ ‹አላስገባ› ያለችውን ልጅ አምጣት» አሉ። ደመቀች ጭቃን ከፊትዋ እዬጠረገች ወደ ሚኒስትሩ ስትሮጥ ያስቸግሩዋቸው የነበሩት አይኖችዋ ፊትዋ፥ ድምጽዋ ሄዱ!

ከዚያ ይዘዋት እጽህፈት ቤታቸው ገቡና ሲቀመጡ፣ ለመስራት አቅደው የመጡለት ስራ ያነለትም በመቅረቱ ንዴታቸውን በረዢሙ ተንፍሰው አስወጥተው

«በዪ እንግዲህ ከኦቶመቢል ስር የወደቅሽበት ጉዳይ ንገሪኝ፥ ትምህርት ነው የምትፈልጊው? » አሉ የመጡለት ስራ በመቅረቱ ቁጣቸውን ጨርሶ ስላልበረደ ፊታቸው ገና እንደ ከረረ ነበር።

«አዎን ጌታዬ! » አለች ደመቀች፥ አንገትዋን ደፍታ። አንድ ጊዜ ቀና ብላ መቆጣታቸውን ከፊታቸው ስላዬች ሁለተኛ፥ አንገትዋን ለማቅናት አልደፈረችም።

«ባዳሪነት ነው ወይስ በተመላላሽነት? »

«ባዳሪነት ነው ጌታዬ! »

«እህም! - ከየት ነው የመጣሽው? »

«ጎጃም፥ እንዶዳም ኪዳነ ምህርት ከሚባል አገር ነው ጌታዬ! »

«ጎጃም፥ ምን ከሚባል ትምህርት ቤት ነበርሽ? »

«በምንም ትምህርት ቤት አልነበርሁም ጌታዬ! »

«እንግዲያ ገና ልትጀምሪ ነው? »

«ለኔኮ አይደለም ጌታየ! »

«እንዴ! ታዲያ ለማነው? »

«ለልጄ ነው ጌታየ! »

«አንቺ - ለትምህርት የደረሰ ልጅ አለሽ? » አሉ ሚኒስትሩ በመገረም መልክ።

«አዎ ጌታየ! »

«የስንት አመት? »

«የሰባት አመት ነው ጌታየ! »

«እባክሽ የማይታመን ነገር አትናገሪ! አንቺ ስንት አመትሽ ሆኖሽ ነው - የሰባት አመት ልጅ ያደረስሽ? »

«አስራ ዘጠኝ ነው ጌታየ! »

«እንጃ! አትመስይም። ብቻ - እሺ አስራ ዘተኝም ይሁንሽ ባስራ ሁለት አመትሽ ወለድሽው ማለት ነውኮ! እንግዲህ ባስራ ሁለት አመት ለመውለድ፣ ባስራ አንድ አመትሽ ወይም ከዚያ በታች ሳለሽ አገባሽ ማለት ነው! »

«ያገባሁስ ‹በማደጎ› ተብሎ - በዘጠኝ አመቴ ነበር። ብቻ ባስራ አንድ አመቴ - ማላውን አፍርሶ ባስራ ሁለት አመቴ ወለድሁ።

«ይህ ወንጀል ነው! ምህረት የማይገባው ወንጀል ነው! » አሉና ሚኒስትሩ በስጨት ብለው፣ «ታዲያ - እዚህ አገር ለምን መጣሽ? » አሉ።

«ወዲያው - እንደ - እንዳረገዝሁ ታመምሁና ወደ ወላጆቼ ተመለስሁ። በብዙ ጭንቅ ከተገላገልሁ በሁዋላ ደግሞ እንደገና ሊወስደኝ ስለ ፈለገና አባቴም - ፈርተውት በግድ አስረው ሊሰዱኝ ስለ ተስማሙብኝ ወዲህ መጣሁ።

«ግሩም ነው! » አሉ ሚኒስትሩ ከተቀመጡበት ተነስተው ወዲያ - ወዲህ እያሉ። «ታዲያ እዚህ ዘመድ አለሽ? » አሉ ቀጠሉና ቆም ብለው።

«የለኝም ማርቆስ መቃብር ቤት ተሸሽጌ የሰነበትሁባቸው መነኩሲዎች አደራ የሰጡት ነጋዴ እዚህ አምጥቶ በሚያውቃቸው ሰዎች በኩል ግርድና አስቀጠረኝ። እዚያ እተቀጠርሁበት ቤት አምስት አመት ስኖር እስከ ዛሬ፥ ድረስ ምንም አልተቸገርሁም ነበር። የሚሰጡኝን ምግብ ለልጄ ጋር እዬተካፈልሁ ከማገኘው ትንሽ ደመወዝ ቀን አማርኛ ለሚያስተምሩልኝ እዬከፈልሁ ደህና ይዤው እኖር ነበር። አሁን ግን እመቤቴ፣ ‹ልጅሽን ከዛሬ ጀምሮ እቤቴ እንዳላየው› ሲሉኝ ጊዜ የማስጠጋበት ይዠው የምሄድበት አጣሁ» አለች ልቅሶ ያዛትና በተሰበረ ድምጽ።

«ከክፉ ልማዳችን መስዋእቶች አንድዋ ነሽ ማለት ነው! » አሉ ሚኒስትሩ፥ አይኖቻቸውን ቦዘዝ አድርገው፥ ፊት ለፊት በደመቀች ላይ ተክለው። ብቻ ያንጊዜ የሚያዩት እስዋን አልነበረም፤ በሙሉ ኢትዮጵያ እንደስዋ የክፉ ልማድ መስዋእቶች የሚሆኑትን ቁጥር ስፍር የሌላቸው ህጻናት ነበር!

«አባቴ ፈርተው ተስማሙብኝ ያልሽው እንዴት ነው? ለምን ፈሩ? » አሉ ሚኒስትሩ፥ ፍዝዝ ብለው፣ ፊት ለፊት ተተክለው የነበሩ አይኖቻቸውን አሻሽተው ደመቀችን እያዩ።

«እሱ ሀብታም ነው ደግሞ ሀይለኛ ነው»

«ትልቅ ሰው ነው? »

«አ - አዎ፥ ሽማግሌ ነው።»

«ስለዚህ አባትሽ በውድም ይሁን በግድ ሸጡሽ ማለት ነው! ፍጹም ወንጀለኛ ናቸው! ብቻ - እነሱ ለሰሩት ወንጀል እዳ ከፋይዋ አንቺ ሆንሽ! » አሉና አሁንም ዝም ብለው ፊት ለፊት ይመለከቱ ጀመር።

«ታዲያ - ለምን ልጁን እዚያው ጥለሽላቸው አልመጣሽም? » አሉና ቀጠሉና

«እወደዋለሁ፤ ከሱ ተለይቼ - መኖር አልችልም! »

«አዎ አለሙን አስቸጋሪ የሚያደገውም ይህ ነው! እንዲህ በሚጣሉት መሀከል የሚወዱት በሚወዱት መሀከል የሚጣሉት ተሰባጥሮ እዬተገኘ ሰውን፥ ተስፋ በመቁረጥና ተስፋ በማድረግ፥ ህየትን በመጥላትና በመውደድ መሀከል ተወጥሮ ሲሰቃይ እንዲኖር ያደርገዋል! እህ - እንዴት ያለ አለም ነው! » አሉ በረዢሙ ተንፍሰው።

«በይ ነይ፣ እዚያ፣ ተቀመጭና ለምጠይቅሽ መልስ ስጭኝ» አሉ በወንበራቸው ሲቀመጡ፥ ከጠረጴዛቸው ባሻገር ፊት ለፊት፥ ያለውን ወንበር በጃቸው እያመለከቱ።

«ግዴለም፤ እንደ ቆምሁ ለሚጠይቁን እመልሳለሁ፣ ጌታየ! » አለች ደመቀች አንገትዋን እንደ ደፋች መሬት መሬት እያዬች።

«ነይ ተቀመጭ! »

«ኧረ ግዴለም እቆማለሁ! »

«ሳዝሽም እሺ አትይ? » አሉ ሚኒስትሩ ከቅርታ ፈገግታ ጋር፡

«እሺ ጌታየ! » አለች የተደፋ አንገትዋን ወደ ግራ ቀልሳ ከወንበሩ ላይ ስትቀመጥ።

«የልጅሽ ስም ማነው? » አሉ ሹል እርሳሳቸውን በማስታወሻቸው ላይ ደግነው።

«ተከስተ ነው ጌታየ ተከስተ ታምራት።»

«ተከስተ የልጁ ታምራት፥ ያባቱ ስም መሆናቸው ነው? »

«አዎን ጌታየ! »

«ልጁ የተወለደበት አገርስ? »

«እንዶዳም ኪዳነ ምህረት።»

«ወረዳውና አውራጃውስ? »

«ጎዛምን ሲሉ ሰምቻለሁ ወረዳ ወይስ አውራጃ መሆኑን አላውቅም።»

«ጎዛምን ወረዳ ነው አውራጃ ደብረ ማርቆስ ነው፥ ግዴለም እኔ አውቀዋለሁ» አሉ ሚኒስትሩ ከሚስፉበት ቀና ብለው ፍርጥም አሉና።

«እንደሱ ነው መሰለኝ» አለች ደመቀች አንገትዋን እንደ ደፋች።

«እድሚውስ? ሰባት አልሸኝ? »

«አዎ ጌታየ ሰባት ነው።»

«ሊረዳሽ የሚችል ዘመድ የለሽም! »

«የለኝም።»

«መልካም እንግዲህ እስቲ - እግዚአብሄር አንቺንም፣ እኔንም ይርዳን! እኔ ልረዳሽ እሞክራለሁ፤ ፈጻሚው እግዚአብሄር ነው።»

«እስዎ ካሉ ምን ይቸግርዋል ጌታየ? እባክዎ ይርዱኝ» አለች፥ ከተቀመጠችበት ተነስታ ቆማ፥ ለጀመሪያ ጊዜ በድፍረት ሚኒስትሩን ፊት ለፊት እያዬች።

«ህም! ምን ይቸግርዎታል! የምቸገርበትን ምክንያት ብነግርሽ ሊገባሽ አይችልም፤ ብቻ - ብዙ የሚያስቸግር ነገር አለ። የሆነ ሆኖ ከልቤ የምረዳሽ መሆኔን አረጋግጥልሻለሁ። ይህ አይበቃሽም? »

«እስዎ ከልብዎ የሚረዱኝ ከሆነ ይበቃኛል ጌታየ» ኧልች፥ እንባዋን በኩታዋ እዬጠረገች።

እንባዋን ሲያኡ ልባቸው ባዘን ተነክቶ ከተቀመጡበት ተነሱና «አይዞሽ ከልቤ ረዳሻለሁ። በይ አሁን ተቀመጪ እባክሽ ተቀመጪ» አሉ ምንም ሚኒስትር ቢሆኑ ሰው መሆን አለና እሳቸውም አይኖቻቸውን እንባ እንባ ብሎዋቸው።

ደመቀች እጅ እንስታ ስትቀመጥ፥ ሚኒስትሩም እንድ ወገብ በሽተኛ ቀስ ብለው ተቀመጡና፣ ግራ ክርናቸውን ከፊታቸው ባለው ጠረጴዛ ተክለው፥ አገጫቸውን በመዳፋቸው አስደግፈው፣ አይኖቻቸው ሳይረግቡ በደመቀች ላይ ፍጥጥ እንዳሉ ሲታዩ፥ እስዋን አተኩረው የሚያዩ እስዋን የሚያጠኑ ይመስሉ ነበር። እስዋም ላንድ አፍታ ስርቅ አድርጋ አይታ፥ ልብዋ እንደ መሸበር ስላለባት እንደገና አይኖችዋን ወደ መሬት መለሰች። ሚኒስትሩ ግን ምንም እንኩዋ የቦዙ አይኖቻቸው እዚያ እፊታቸው የተቀመጠችውን ያስራ ዘጠኝ ኸምት ልጅ ገር፥ ውብና ደመግቡ ፊት አተኩረው የሚመልከቱ የሚያጠኑ፣ ቢመስሉ በውነት የሚያዩት በዚያ ውበትና ደም ግባት ባስጌጡት መልክ ውስጥ ተሸሽጎ የሚያስጨንቃትን ጨካኝና መጥፎ ችግር ነበር። እንደዚህ በደመቀች ፊት ችግርዋን በስዋ ችግር እስዋን የመሳሰሉትን ሁሉ ችግር እንደ ጉንዳን ሰራዊት እስበሱ ተቆራኝቶ እዬተግተለተለ ባይነ ህሊናቸው ፊት ሲያልፍ ሲመለከቱ ዘለግ ያለ ጊዜ ቆይተው ደከማቸውና ከሚያስጨንቅ፥ ከሚያሰቅቅ የቅዠት እንቅልፍ እንደ ነቁ ሁሉ «እሁ - ! » አሉ አይኖቻቸውን መላልሰው እያርገበገቡ በረዢሙ ተንፍሰው።

«ምን ነበር የምልሽ? እ - አዎ! የእግዚአብሄር ርዳታ ከተጨመረበት እኔ ርዳታየን አላጉዋድልብሽም ነበር ያልሁሽ። አሁንም ያኑ ነው የምደግመው» አሉ ቀጠሉና።

«ደመቀች ተነስታ ጠጉርዋ ምንጣቸውን እስኪጠርግ እጅ ነሳች።

«በይ እንግዲህ - ከሶት ቀን በሁዋላ መጥተ ጠይቂኝ።»

«እዚህ ማን ያስገባኛል? »

«አዎ እውነትሽን ነው፥ ያስቸግርሻ» አሉና ግንባራቸውን ሲያሻሹ ትንሽ ቆይተው «እንዲያውም - ያእልሽበትን ብትነግሪኝኮ እኔ አስፈልግሽ ነበር። ከማን ጋር ነው ያለሽ? »

«እደጃዝማች አሰፋ ቤት ነኝ።»

«አሰፋ አሰፋ! »

«ደጃዝማች አሰፋ ተጫኔ።»

«እ - ! ደጃዝማች አሰፋ ተጫኔ! እሳቸውንማ ደህና አድርጌ አውቃቸዋለሁ፤ እንዲያውም ወዳጇ ናቸው። የስልካቸውን ቁጥርም አውቃለሁ። በይ እንግዲህ የቀናኝ እንደሆነ በሳችወ በኩል አስፈልግሻለሁ።»

ደመቀች ይህን ሚኒስትሩ እዬመላለሱ፣ «የእግዚአብሄር ርዳታ የተጨመረበት እንደሆነ፥ የቀናኝ እንደሆነ ረዳሻለሁ» የሚሉትን ልታስተውለው አልቻለችም። «ፈጻሚው ማን ሆኖ ነው እሳቸው ረዳት የሚሆኑ? ይህን ለመሰለው ጉዳይ ከሁሉ በላይ እሳቸው አደሉም? አባባ አዛዥ እንደ ነገሩኝ ከሆነ ከስፔክተሩም ከዲኔክተሩም የበላይ ሚኒስቴሩ ናቸው! ታዲያ ለምነው የበላይ ያላቸው ይመርል ‹ረዳሻለሁ› የሚሉኝ? እንዲያው ሊፈጽሙልኝ ስላልፈለጉ ነው! አሁን ‹እግዚአብሄር የፈቀደ እንደሆነ ረዳሻለሁ› የሚሉኝ - ሁዋላ ‹እግዚአብሄር ሳይቀናኝ ቀረ› ብለው በእግዚአብሄር ለማመካኘት እንዲመቻቸው ነው፤ ለዚህ ብለው ነው! » እያለች ቆማ በውስጥዋ የምትተቸው በፊትዋ ይነበብ ስለ ነበረ፣ ሚኒስትሩ ትኩር አድርገው ሲመለከቱ ቆዩና፣ -

«ረዳሻለሁ ስልሽ ማመኑ አስቸገረሽ መሰለኝ፥ የጥርጣሬ መልክ አይብሻለሁ» አሉ።

«ኧረ አልጠረጥርም ጌታየ! » አለች ደመቀች ድንጋጤዋ በፊትዋ ጎልቶ እዬታየ።

«ግዴለም ብዙ በደል የደረሰብሽ ነሽና ብትጠረጥሪ አልፈርድብሽም። የወለዱሽን አባትንሽ ለሙሉ እምነትሽ ለጽኑ ተስፋሽ የማይበቁ፥ ጎደሎ ሆነው ስታገኛቸው - እኔን ባእዱን የሰጠሁሽ ተስፋ ከመፈጸሙ በፊት «እመኝኝ» አልልም። ብቻ - የሰጠሁሽን ተስፋ ለማስፈጸም ዋስ የሚሆን ነገር ልንገርሽ። ልጅሽ በመንግስ ሂሳብ አዳሪ ሆኖ እንዲማር ለማድረግ እሞክራለሁ፤ ይህን ማድረግ ባልችል በኔ በራሴ ሂሳብ አዳሪ ሆኖ እንዲማር አድርግልሻለሁ።»

ኧረ አልጠርጠርሁም፤ አምናለሁ ጌታየ» አለች ደመቀች መሬት ስማ ቀና ስትል እንደ ንጋት የበጋ ሰማይ ፊትዋ በደስታ ወገግ ብሎ።

«በይ ሂጂ እንግዲህ! » አሉ ሚኒስትሩ ደስ በማሰኘታቸው የሳቸውም ፊት እንደስዋ በደስታ በርቶ።

ደመቀች መሬት ስማ ቀና ስትል የሚያሳዝኑ ውብ አይኖቾዋ በፊትዋ ዘቅዝቀው የሚመለከትዋትን ሚኒስትር የሚያዩበት ሁኔታ፣ ልክ ጸሎቱ ስለ ተሰማለት አንጋጦ ፈጣሪውን የሚያመሰግን የጻድቅ አይኖች ይመስል ነበር! ከዚያ ዘወር ብላ ለመውጣት ከሚኒስትሩ ጠረጴዛ እስከ በሩ ያለውን ረዢም መንገድ ስትጀምር የሚኒስትሩ አይኖች እንደ ተከተሉዋት የሴትነት ስሜትዋ ነገራትና ጉልበቶችዋ እንደ መብረክረክ ወዲያው ያቆቁዋምዋ ሚዛን እንደ መቃወስ ስላሉባት ፍራት ይዞዋት በሩን ለመድረስ አመት የሚያስጉዝ መስሎ ታያት።

ስለዚህ እንዳትወድ ተጠንቅቃ እዬተራመደ በሩን ለመድረስ ስትናፍቅ በአቶሙቢላቸው ፊት ከወደቀችበት ለማሰወገድ ዘበኞች ሲጎትቱዋት ሲያንከባልሉዋት፣ ሲያነሱ ሲጥሉዋት አበጥራ በሻሽ ያሰረችውን ዞማ ጠጉርዋ እንደ ተፈታ የጥቁር ሀር ነዶ በራስዋና ትከሻዎችዋ ላይ ተመሰቃቅሎ የለበሰችው ቀጭን ጥበብ ኩታ፣ «የሰውነትዋ ውብ ቅርጽ ገልጠህ አሳይ» እንደ ተባለ ሁሉ፥ ከወገብዋ ላይ ግማሹ አግድም ተቀዶ፥ ከዳሌዋ በታች እጭኖችዋ ላይ ወድቆ የሚያማምሩ ባቶችዋን ደረቅ ሳርና ጋሬጣ ጋግጠዋቸው፣ እንዲያ ተጉላልታ እንዲያ ተንገላታ ስትሄድ ከሁዋላዋ አዩና ያን የተጉላላ ውበት ያን የተንገላታ ውበት እበር እስክትደርስ አይናቸውንም አፋቸውንም በሰፊው ከፍተው ከሁዋላዋ ዝም ብለው ሲመለከቱ ቆዩና ከፍታ ልትወጣ የበሩን እጀታ ስትይዝ፥

«እስቲ ቆይ፣ እስቲ አንድ ጊዜ ቆይ የኔ እመቤት! » አሉ፥ ሁለት ሶስት እርምጃዎ ወደ ፊት ተራምደው። ያንጊዜ ደመቀች ልብዋ ከደረትዋ ወጥቶ የበረረ መስሎ ተስማትና፥ ደንዝዛ በሩንም እንደ ከፈተች አንገትዋን ደፍታ ቆመች።

«በሩን ዝጊና ወዲህ ነይ» አሉ ሚኒስትሩ። ደመቀች ደመነፍስዋን እንደ ታዘዘችው በሩን ዘጋች፤ ነገር ግን ከቆመችበት አልተንቀሳቀሰችም።

«ለተበደልሽው በደል ለተሰራብሽ ግብ ተጨማሪ ሆኘ ስላንገላታሁሽ ይቅርታ አድርጊልኝ» አሉ ሚኒስትሩ፥ እስዋ ከቆመችበት ስላልተንቀሳቀሰች እሳቸው ወደስዋ እያመሩ። ደመቀች የስዋን ሴትነትና የሳቸውን ወንድነት አይታ፣ እዚያ ሁለቱ ብቻ በመገኘታቸው ከመፍራትም በቀር አሳባቸውን ስላላወቀች፥ የወባ መነሾ እንዳለበት ሁሉ የሰራ አካላትዋ ይንቀጠቀጥ ነበር።

«ሚኒስትሩ እጃቸውን እደረት ኪሳቸው አግብተው በቀስታ እዬተራመዱ በሩን ዘግታ በቆመችበት ሲደርሱ፥ ከቦርሳቸው አምሳ ብር አውጥተው፥

«እባክሽ ይህን - ይህን ተቀበይኝ» አሉ።

«ምን - ምን ያረግልኛል? » አለች ፍራትዋን ወለል አድርገው በሚያሳዩ ውብ አይኖችዋ መጀመሪያ ገንዘቡን ከዚያ እሳቸውን ተመለከተችና።

«ላቆሰለንው ገላሽ ላሳዘነው ልብሽ ዋጋ ሊሆን ባይችል፥ ለቀደደንው ልብስሽ ዋጋ ሊሆን ይችል ይሆናል! »

«ልጄን ትምህርት ቤት ካስገቡልኝ ይህ ሁሉ ምንም አይደል ጌታየ! እንዲያው እፊትዎ አቅርበው ይህን ያክል ስላነጋገሩኝ - መንገላታት ያሉት በጭራሽ አልተሰማኝም፤ በጣም ደስ ብሎኛል።»

«ይህን የምሰጥሽ በልጅሽ ትምህርት ቤት ፈንታ አደለም፥ ከዚያ ሌላ ነው፤ እኛ ለቀደድነው ልብስሽ ነው» አሉ ባዘነ ፊት፥ የተቀደደ ኩታዋን እዬተመለከቱ። ደመቀች ገንዘቡን ተቀብላ ጫማቸውን ለመሳም ብትሞክር ስለ ከለከሉዋት መሬት ስማ ተነሳች።

«በይ እንግዲህ ሂጂ፥ ቅድም እንዳልሁሽ እኔ አስፈልግሻለሁ» አሉ ሚኒስትሩ።

እስዋ በሩን ዘግታ ስትሄድ ውበትዋ ደም ግባትዋ፥ በዚያ ላይ ከዘበኞቻቸው ያገኘችው መጉላላትዋ መንገላታትዋ፣ ተጨምረው በአእምሮዋቸው ተሰለው ተቀርጸው ቀሩ!

«ወይ ግሩም! መንገላታት መጎሳቆል፣ እንዲህ ያሳምራል? » አሉ፥ እስዋ ከሄደች በሁዋላ ባእምሮዋቸው ተቀርጾ የቀረ ምስልዋን ዝም ብለው ባይነ - ህሊናቸው ሲመለከቱ ቆይተው።

ደመቀች ከዚያ ወጥታ ደረጃውን እዬሮጠች እንደ ወረደች የትምህርት ሚኒስቴርን ግቢ እዬሮጠች አቋዋርጣ አጥሩ በር ስትደርስ አዛዥ ተካልኝን አንድ ድንጋይ ላይ ተቀምጠው ሲጠብቁዋት አገኘቻቸው።

«ቀናሽ? የኔ እናት! » አሉ አዛዥ ደስታዋን ከፊትዋ ሲያዩ፥ እሳቸውም ደስ ብሎዋቸው ተነስተው ወደስዋ እዬሄዱ።

«ሊቀናኝ ነው መሰለኝ አባባ! »

«እንዴት? ምን ማለትሽ ነው? »

«ብችል በመንግሥት ሂሳብ፥ በነጻ እንዲገባልሽ አደርጋለሁ፤ ያለዚያ - እኔ እራሲ ከፍዬም ቢሆን አስገባልሻለሁ አሉኝ። ታዲያ ይህ - መቅናት አይደለም አባባ? »

«ጨርሰውልሻላ! ቀንቶሻል! ነይ ሳሚኝ! »

ደመቀች ከደስታዋ ብዛት የተነሳ ባንገታቸው ወድቃ ያለይሉኝታ ጭንቅ ጭንቅ እስኪላቸው ስማ ስትለቃቸው፥ አዛዥ ደስታና አዘን ተደባልቀው ሊፈጡት በሚችሉ ስሜት ልባቸው ስለ ተነካ፣ አይኖቻቸው በንባ ሞልተው፣ ትንሽ ሲመለከቱዋት ቆዩና፣ «እንኩዋን ደስ ያለሽ! » አሉ።

«እንኩዋን አብሮ ደስ ያለን! » አለች የሳቸውን ሲያዩ የሱዋም አይኖች እንባ ሞልተው።

ከዚያ፥ መንገዳቸውን ወደ ቤታቸው ሲጀምሩ፣ «ምንስቴሩ እንዴት ደግ ናቸው፥ አባባ! ደግሞ አምሳ ብር ሰጡኝ» አለች ደመቀች።

«ምንስቴሩ አምሳ ብር ሰጡሽ? አ - ! እይውልሻ! አላልሁሽም? የኔ ልጅ ቆንጆ ነሽ፤ አንቺ ከፈለግሽ ወንዶችን መውደድ ብቻ ሳይሆን እንዲያመልኩሽ እንዲሰግዱልሽ ልታደርጊ ትችያለች አላልሁሽም? »

«የለምኮ አባባ ለሌላ - ብለው አደለም! ደግ ስለሆኑ አዝነውልኝ ነው! »

«እሱን ግዴለሽም ለኔ ተይልኝ፤ የኔ እናት! ዳኛ ምን ደግ ቢሆን ላዘነለት ቅን ፍርዱን እንጂ ገንዘቡን ሰጥቶ አያውቅም! ገንዘቡን የሚሰጥ ለሚወደው ብቻ ነው! ስለዚህ - ምንስቴሩ ወደውሻል! » አሉ አዛዥ ሲስቁ ጋራ ቀኝ ያፋቸውን ጠርዝ እስከ መጨረሻ ዳርቻው አላቀው።

«አይደለም፥ ደግ ቢሆኑ ነው አባባ! » አለች ደመቀች ትንሽ እንደ ማፈር ብላ።

## ምዕራፍ አስራ አራት

# የምስራች!

የትምህርት ሚኒስትሩ የደመቀችን ልጅ ቢችሉ በነጻ፣ ያለበለዚያ ራሳቸው ከፍለው አዳሪ ትምህርት ቤት ሊያስገቡት ተስፋ ሰጥተው ካሰናበቱዋት አራት ቀኖች አለፉ። ለደመቀች አራቱ ቀኖች አራት አመቶች መስለው ታዩዋት።

«አባባ ምንስቴር ቃሉን ያጥፋል? » አለች ደመቀች፥ ባምስተኛው ቀን ጥዋት ወደ ስራዋ ለመሄድ ታጥቃ ተነስታ።

«እንዴት? » አሉ አዛዥ።

«ምንስቴሩ ሂጂ ‹እኔ አስፈልግሻለሁ› ካሉኝ ይሄው ዛሬ አስምተኛ ቀን ነው፤ ነገር ግን አላፈልጉኝም። ታዲያ ይህ - ምን ይባላል? »

«ባራት ቀን ውስት አስፈልግሻለሁ ብለውሽ ኖሮዋል? »

«ከሶስት ቀን በሁዋላ ጠይቂኝ ካሉ በሁዋላ እንደገና መልሰው ‹እኔ አስፈልግሻለሁ› አሉኝ። ብቻ - የሚያስፈልጉብኝን ቀን አልቆረጡም።»

«ታዲያ ቀን ካልቆረጡ ‹ቃል አባይ› የሚያሰኛቸው፥ ምኑ ነው? ወዲያውምኮ ሚኒስቴር በቃሎ ቆሞ ባይገኝ ‹ረሳ፣ ሳይመቸው ቀረ ይባላል እንጂ ‹ቃል አባይ› አይባልም» አሉ አዛዥ፥ የሽማግሌ ፊታቸውን ባሽሙር ፈገግታ በርቶ።

«እባክዎ አይቀልዱ አባባ፥ እኔን ጨንቆኛል።»

«ምንስቴሩ መንግሥት በነጻ ካላስተማረልሽ እኔ ከፍዬ አስተምርልሻለሁ» ብለው ሙሉ ተስፋ ሰጥተውሻል። ታዲያ ተስፋ የለሽን ይጭነቀው እንጂ አንቺን ባለ ሙሉ ተስፋዋን ለምን ይጨንቅሻል? »

«እንዲያውም ተስፋው ነው መሰለኝ እንዲህ ያስጨነቀኝ ተስፋ ባይሰጡኝ ኖሮ ምናልባት አንድ ጊዜ አዘኘ ረሳው ነእብር ይሆናል።»

«የለም ተሳስተሻል፥ ልጄ! ተስፋማ መልካም ነው፥ ተስፋ የሌለው ሰው ህይወቱ ባዶ ነው! ወዲያውም በምንስቴሮች ዘንድ አራት ቀን ብዙ፣ አይደለም፤ ሶስት ወር አራት ወር ደጅ የሚጠኑ አሉ! »

«ሶስት አራት ውር? »

«እንዴታ! ሶስት አራት ወር! ኧረ ከዚያም የበለጠ! ብቻ አንቺ ሶስት አራት ወር ደጅ ያስጠኑሻል? ማለቴ አይደለም።»

«እንዴት? ሌላውን ያን ያክል ደጅ ካስጠኑ እኔንስ ቢሆን እንደ ሌላው ‹ደጅ ጥኚ› ሳይሉ ይቀራሉ? » አለች ደመቀች እንደ መፍራት ብላ።

«የለም አንቺን ደጅ አያስጠኑሽም።»

«እንዴት? ለምን? »

«ቆንጆ ነሻ! ቆንጆ ደጅ ያስጠናል እንጂ ደጅ ይጠናል? » አሉ አዛዥ አፋቸውን እስከ መጨረሻ ከፍተው እዬሳቁ።

«አባክዎ አይቀልዱ አባባ፥ በዚህ ሰሞን የሰነበትሁትን ጭንቅ ብነግርዎ» ብላ ላዛዥ መንገር የፈለገችውን ሳትነግር ከመቤትዋ የተላከ አሽከር እዬሮጠ መጥቶ «ትጠሪያለሽ» ስላላት ቶሎ ወደ መቤትዋ ሄደች።

«የኛ እመቤት! ቀስቃሽ ተልኮ ካልቀሰቀሰሽ ከመኚታሽ አትነሽም ማለት ነው! ግዴለም እድኒህ እንደ ቀለድሽብኚ የምትቀሪ ብትሆኚ ይቆጨኚ ነበር! » አሉ ወይዘሮ ጽጌ፣ ወደጉዋሮ ለመሄድ ወፍራም ቡልኮዋቸውን ተከናንበው አልጋቸው ጫፍ ላይ እንደ ተቀመጡ።

«ወዲህ ለመምጣት ስወጣ ነውኮ አሻግሬ የደረሰብኚ እመቤቴ! »

«አዎን እመቤቴ ወዲህ ስትመጣ በመንገድ ነው ያገኘሁዋት።» አለ መላከተኛው አሻግሬ ከውሸት ተንሽ ጨመር አድርጎ።

«ዝምበል አንተን የጠራህ የለም አንት - » አሉና እንደሱ ሳይጠሩት ለሚመሰክር የሚስማማ ስድብ አጥተው ሲፈልጉ ቆይተው «ለመሆኑ» አሉ ግንባራቸውን ኮስተር፥ ቅንድባቸውን አንዱን ከፍ ሌላውን ዝቅ አድርግው አጣመው፥ አሻግሬን ትተው ወደ ደመቀች ዘወር አሉና። «እንዲያው ለመሆኑ አንቺ እዚያ - እተካልኚ ቤት እንድታድሪ የፈቀደልሽ ማነው? » ደመቀች አንገትዋን ደፍታ በግር አውራ ጣትዋ መሬት እዬቆረቆረች ዝም አለች። -

«ንገሪኝ እንጂ! ለምን ተናገራችሁኝ ለምን ተደፈርሁ ብለሽ ጠግበሽ፣ ያ ትቢትሽ ኩራትሽ ሆድሽን እንደ ጥሬ ሽንብራ ነፍቶት አደለም? »

«ለምን ተናገሩኝ ብዬ ወይም ኩራት ነፍቶኝ አደለም። ብኮራ ግርድና ባልተቀጠርሁ እመቤቴ! ወዳባባ አዛዥ ቤት የሄድሁ ‹ልጅሽን ከዚህ ቤት አስወግጂ› ሲሉኝ ጊዜ ነው።»

«ታዲያ - ‹ልጅሽን አስወግጂ› ብልስ - አንቺን ‹ወግጂ› ብዬሻለሁ? »

«እስከ ዛሬ ብቻውን ሆኖ አያውቅም። ስለዚህ እንዳያለቅስ ብዬ ነው።»

«አዎ የሜቴ ልጅ ብቻውን የሆነ እንደሆነ ሞት ሰርርቆ ይወስደዋል! አሁን ወደ ነበርሽበት እንድትመልሽ! ያን ርጉም ልጅሽንም እንድታመጪ! በንጀራዬ፥ በማር በወተቴ አሳድጌ በጉልበቱ ሳይከፍለኝ እንዲያው እንዲሁ - አይሄድም! ከንቱ ሳልመሰገን ‹እግዜር ይስጥሽ› ላልባል፥ ላልተወለድሁት ላልተዘመድሁት ባእድ ገንዘቤ ባክኖ አይቀርም! መቸም ‹የኔ እጅ አመድ አፋሽ› ነው አብቼ አጠጥቼ፥ ‹ያች ክፉ› እንጂ ‹ያች ደግ› የሚለኝ የለ! ‹ክፉ› መባል አንሶኝ ደግሞ ‹ቂል› አልባልም! » አሉ፥ ሲነሱ ግንባራችውን በውሸት ኩስትር አድርገው። ታዲያ፥ በደመቀች ላይ ያደረጉት ባላቸው ሰምተው ስለ ተቆጡዋቸውና እሳቸውም ስለተጸጸቱ ልጅዋን ይዛ ወደ ነበረችበት እንድትመለስ መንገድ ለመክፈት ነው እንጂ ያ ያሉት ሁሉ የውነተኛ ስሜታቸው ሆኖ አልነበረም። ደመቀች አንገትዋን እንደ ደፋች ምንም ሳትመልስ ዝም ባል ስትሰማ ቆይታ ውሀ ይዛ ተከተለቻቸው።

ከጉዋሮ ሲመለሱ፥ አዛዥ ተካልኝን ሴት እልፍኝ በራፍ ቆመው አገኙዋቸው። አዛዥ ወይዘሮ ጽጌ በደመቀች ላይ ያወረዱትን የቁጣ መአት የሰሙ አሽከሮች ነግረዋቸው አዝነው ነበር።

«አ - ! » ጌታው እንኩዋን ለዚህ አበቃህ! » አሉ ወይዘሮ ጽጌ አዛዥን፥ እዚያ ቆመው ሲያዩዋቸው።

«ለምኑ እመቤቴ? » አሉ አዛዥ እጅ ነስተው ቀና ሲሉ።

«የኛን አሽከሮች ለማስኮበሉ! »

«ምን አሽከር አስኮበለልሁ እመቤቴ? »

«ደመቀችና ልጅዋ ከኛ ቤት ወጥተው መኖሪያቸው አንተ ቤት መሆኑን ሰማን! »

«ደመቀች ማደሪያዋ ብቻ እኔ ቤት ሆነ እንጂ ስራዋም መኖሪያዋም እዚሁ ነው። ላዳኙም ቢሆን የልጅዋን እዚህ መኖር እመቤቴ ስላልፈቀዱና የምታስጠጋበት ስላጣች፥ እኔ ዘንድ አስጠግታ ብቻውን እንዳይሆን አብራው ታድራለች። ታዲያ ይህ - የመቤቴን ሎሌዎች ማስኮብለል ይባላል? ይች ልጅ ገና ራሱን ያልቻለ ህጻን ይዛ ስትንገላታ አደጋ ቢደርስባት ብዬ ነው መጠጊያ የሰጠሁዋት።»

«ለኔ ስም አዝነህ! ሀ - ሀ! የሆነ ያልሆነውን ማሞጣሞጡን በተውኸኝና ለኔ ስም ማዘህን በቀረብኝ! »

«አዛዥ ተካልኝ የወይዘሮ ጽጌን ስድብ ሲሰሙ፣ ለጊዜው ራሳቸውን በሀይል እንደ ተገጨ ደንዝዞ፥ ምንም ሳይናገሩ አፋቸውንም አይኖቻቸውንም በሰፊው ከፍተው ቆይተው ድንጋጤው ሲያልፍላቸው፣

«እንዲያ ነዋ! እንዲያ ነው እንጂ! ከጉልምስና እስከ ሽምግልና ካገለገልሁበት ቤት ካገለገልሁዋቸው እመቤት ከዚህ የተሻለ ‹አሞጣሙዋጭ› ከመባል የተሻለ የማእረግ ስም ወዴት ይገኛል? ላገልግሎቴ ለሽምግልናዬ የሚገባኝ የሚስማማ ስም ነው፥ እግዚአብሔር ይስጥልኝ! ህ! እኔ ተካልኝ ነኝ አሞጣሙዋጭ? እኔ ተካልኝ አሞጣሙዋጮችን የምጸዬፍ እንጂ አሞጣሙዋጭ አይደለሁ! ብቻ ህይወቴን በገዛ እንጂ ባሳለፍሁ! እርስዎም ብዙ ዘመን አብሬዎ በቅርብ እያገለገልሁዎ ስኖር ባያውቁኝ፥ ጉድለቱ የኔ አደለም፥ ለማወቅ ችሎታ የጎደለው ነው! ለዚህች ልጅም ያለዎ የተሳሳተ አሳብ ስለኔ ማኖር የማይችሉትን አምስት አመት ችላዎ መቀመጥዋ ነው። ይህ ብቻ ጥፋትዋ! አሁንም ቢሆን እስዎ ካልፈልጉዋት እግዚአብሄር ጤናዋን አይንፈጋት እንጂ፥ ደከማ የለት እንጀራዋን የምታገኝበት ስራ አታጣም። እስዎ ግን እንደስዋ ያለች አሽከር ‹አገኛለሁ› ብለው ያስቡ እንደሁ ተሳስተዋል! » አሉ አዛዥ ቁጣቸው በልባቸው ያነደደው እሳት ጢሱን ባፍንጫቸው ሲያትጎለጉል ነበልባሉ ባይኖቻቸው ሲያንቀለቅል እዬታዬ።

ወይዘሮ ጽጌ እንዲያ ያለ፣ ያልለመዱትና ያልጠበቁት የድፍረትና የዘለፋ አነጋገር ተከታትሎ ካሽከራቸው አፍ ሲወረወርባቸው በድንጋጤ አፋቸውንና አይኖቻቸውን በሰፊው ከፍተው ከመስማት በቀር ምንም ለማለት አልቻሉም።

ወይዘሮ ጽጌ፥ እስከዚያ ቀን ድረስ የሚያውቁት አሽከር፥ ምንም ትልቅ ምንም ሽማግሌ ቢሆን እንኩዋንስ ሲሰድቡት ቢመቱትም እጅ ነስቶ፥ መሬት ስሞ መሄድ ነው እንጂ፥ ያነለት አዛዥ እንዳደረጉት አንገቱን አቅንቶ ደረቱን፥ ነፍቶ እመቤቱን ወይም ጌታውን የሚዘልፍና የሚሰድብ አሽከር ገጥሞዋቸውም ከገጠመው ሰው ሰምተውም አያውቁ። ስለዚህ ካሽከራቸው አፍ የወጣውን ዘለፋ ከግዜር የተላከ ነቢይ በፊታቸው ቆሞ እንደሚዘልፋቸውና እንደሚገስጻቸው ዝም ብለው ሲሰሙ ቆይተው አዛዥ ወጥተው ካይናቸው ከጠፉ፣ በሁዋላ በረዢሙ ተንፍሰው «ወይ ጊዜ! ሰደበኝኮ! ጊዜ የማያመጣው የለም! » አሉና ወደ ደመቀች ዘወር ብለው «አንቺ ያን ልጅሽን ይዘሽ ዛሬ ወደ ነበርሽበት እንድትመለሺ! ያለዚያ እኔ የማደርገውን ታያለሽ ልብ አድርጊ! » አሉ።

አዛዥ በበኩላቸው ከወይዘሮ ጽጌ ዘንድ እንደ ወጡ «ስልክ ቤት» ወደሚባለው ክፍል ገብተው እመቤታቸውን የተናገሩት የድፍረት አነጋገር ልባቸው እንደ ዝሆን ገዳይ በወኔ ተሞልቶ ከሞቅታቸው የተነሳ እዚያ የነበሩትን ሰዎች ከመጤፍ ሳይቆጥሩ እጆቻቸውን በግራና ቀኝ ታፋዎቻቸው ላይ አሳርፈው ወዲያ - ወዲህ እዬተንጎራደዱ ይፎክሩ ጀመር! «ምነው እኔ ተካልኝ! » አሉ። «እኔ ተካልኝ፤ አገር እሾማለሁ አልል! አገር መግዛቱ እንኩዋንስ ለኔ ለነሱም ቀርቶዋል! ለምኑ ነው ሲያዋርዱኝ የምለማመጠው? ቀን ከሌት ሰርቼ ላቤን አንጠፍጥፌ ለማገኘው የተራ ወታደር ደመወዝና ለዚያ አንድ ጋሻ መሬት ነው? ለዚያ ነው ከሽመገልሁ ሁለት ጠጉር ካበቀልሁ በሁዋላ - ‹አሞጣሙዋጭ› ተብዬ የምሰደበው? የለም! አልሰደብም! እንዲህ ልክ ልካቸውን እነገራቸዋለሁ! »

«ምን ሆኑ አባባ አዛዥ? ለማነው ልክ ልኩን የሚነግሩት? » አለ ስልክ ጠባቂው ልጅ፣ ሁኔታውን ሁሉ አስገርሞት።

«እ? ደህና ነኝ! ምንም አልሆንሁ! » አሉ አሳባቸውን ትንሽ ሰብሰብ አደረጉና።

አዛዥ አሳባቸው በቁጣና በወኔ ከተደበላለቀበት ገና ጨርሶ ሳይጠራ ስልክ ስለ ተደወለ፣

«አሎ፣ አሎ! » አሉ ቶሎ ስልኩን አንስተው። ካሳባቸው መታወክ የተነሳ፥ ስልክ ማንሳቱ የስልከኛው ፈንታ መሆኑን ረስተውታል።

«አዎ ልክ ነው፥ የደጃዝማች አሰፋ ተጫኔ ቤት ነው። አዎ አለች። እ? አዎ አዎ። መቸ? ቅዳሜ ከስባት ሰአት በፊት? እሺ እነግራታለሁ። ኸረ ግዴለም አልረሳም፥ አሁን እነግራታለሁ ትመጣለች! ስሜ? ስሜ አዛዥ ተካልኝ ነው» አሉና ስልኩን ዘግተው ለትንሽ ጊዜ ምንም ሳይናገሩ ፊታቸው ፈገግ ብሎ አይኖቻቸውን ፊት ለፊት አተኩረው፥ ሲመለከቱ ቆዩ። እንዲያ አይኖቻቸውን ሳያረግቡ ፊት ለፊት አተኩረው ሲመለከቱ በውስጣቸው ልዩ ልዩ አሳቦች እንደሚለዋወጡባቸው በፈገግታ ከበራ ፊታቸው ይነበብ ነበር።

«ምን ሰሙ አባባ? » አለ ስልከኛው ህብሩ የሚለዋወጥ ፊታቸውን ሲያይ፥ የሰሙት ወሬ ክፉ ይሁን በጎ መገመት አቅቶ።»

«እ? ምንም አደል አይዞህ መልክቱ ለኔ ቤት ነው፤ ልሂድና ልንገር። የተፈለግሁ እንደሁ ‹ወደ ቤቱ ሄዱዋል› በልና ቶሎ ሰው ላክብኝ። ብለው ወደ ቤታቸው ሮጡ።

አዛዥ እቤታቸው ቆይተው ሲመለሱ ደመቀችን አዝና ተክዛ አገኙዋት።

ደመቁ ዛሬ ጥቂት እንግዶች ስለ ጋበዝን አንቺም በጊዜ ተሰናብተሽ ውቺና ራት አብረን እኛ ቤት እንድንበላ» አሉ።

«የለም አይሆንልኝም አባባ፤ እመይቴ በጣም ተቆጥተዋል።»

«በጊዜ ተያቸው» ያልሁሽ አንዱም ለዚህ ነውኮ! በከንቱ የተቆጣ ሰው በከንቱ፥ የተቆጣ መሆኑን የሚገነዘበው ብቻውን ሆኖ ለማመዛዘን ሲችል ነው! ስለዚህ የተቆጡበት ከንቱ መሆኑን ለማመዛዘን እንዲችሉ እስቲ እድል፣ እንስጣቸው! »

«ዛሬ ልጅሽን ይዘሽ ወደ ነበርሽበት ያልተመለሽ እንደሆነ የማደርገውን ታያለሽ አሉኝ።»

«አሉ? ግዴለም ‹እንኩዋንስ ከፎከረ ከወረወረም ያድናል!› የሚባለውን ታውቂ የለም? ግዴለም ዝም ብለሽ ነይ። ይህን ሰሞን እንዲህ - ያቅበጠበጣቸውን ደርሸበታለሁ ሰምቻለሁ! »

«ምንድር ነው? »

«አንቺን ያደረጉሽን - ማን እንደ ነገራቸው እንጃ - ጌቶች ሰምተው፥ በጣም ነው አሉ የተቆጡዋቸው። ‹እንዴት አንድ ልጅ፥ ያውም የጥሩ ሰራተኛሽን ልጅ፥ ከበደኝ

ከቤቴ አስወጪልኝ ብለሽ እንዲህ ያለ መሳቂያ መሰደቢያ ነገር ታደርጊያለሽ› ብለው - በጣም ነው አሉ የተቆጡ! ይውልሽ ይህ ነው ምሥጢሩ» አሉ ወደ ጆሮዋ ጠጋ ብለው። ደመቀች አዛዥ ያወሩዋትን ስትሰማ በስዋ ምክንያት ደጃዝማች መቆጣታቸው ይብሱን ቀንበርዋን የሚያከብደው መስሎ ተሰማትና ስጋት አደረባት። ስለዚህ እንደ ማዘን ብላ፥ አንገትዋን ደፍታ ስታስብ ቆይት፥ «እስዎ ለመሆኑ ዛሬ ራት ግብዣ የሚያደርጉት ምን አለብዎ? » አለች፥ ቅርታዋ ከፊትዋ ሳይጠፋ ቀና አለችና።

«ብዙ ድግስ እንኳዋ አንደግስም። እንዲያው ትንሽ ነገር አድርገን ጌጤና እኔ የተጋባንበትን ያርባ አመት መታሰቢያ እናከብራለን። ስለዚህ - ‹አሞኛል› ብለሽ አመካኝተሽ በጊዜ ውጪ፤ እኔም ከጌቶች ተሰናብቼ በጊዜ ነው የምወጣ።»

«አዛዥ እንዳሉት በጊዜ ከጌታቸው ተሰናብተው ወጥተው ባልተቤታቸው ባሰናዱት መጠነኛ መብልና መጠጥ ላይ አስገዝተው ጨምረው ጎረቤታቸውን ህጻናቱ ሳይቀሩ ጠርተው ደመቀች እስክትመጣ ጠላ እዬተጠጣ ይዘፈን ነበር። ወዳጃቸው አዝማሪው ውቤም አስጠርተውት መጥቶ እዚያ ነበር።

አዝማሪው ውቤ፥ የዱሮው ቀኝ ጌታ ውቤ አጎናፍር የቀጨኔ መድሀኔ አለም ደብተራ ነበር። እሱ «በቅኔ ይሁን በዜማ ወይም ባቆቋዋምና በመጻሕፍት ትርጉዋሜ፣ ከቀጨኔ ደብተሮች ሁሉ እበልጣለሁ እንጂ አንሳለሁ አይልም። ነገር ግን ማንም የማይከደው ካህናቱ ሳይቀሩ ‹አዎን፣ አሜን› ብለው የተቀበሉት በድምጽ ማማር የማይተካከሉት መሆናቸውን ነው። ቀኝ ጌታ ውቤ፤ ላገልግሎት ከተሰጠው ኩርማን ጋሻ የማደሪያ መሬት በቀር ሌላ ሀብት አልነበረውም። እሱም ቢሆን «መሬት አለኝ» ለማለት ያክል ካልሆነ ከችግር አውጥቶ አያውቅም። ባመት አንድ ጊዜ ጊዜ ገንዘብ ሊሰበስብ ወደ ጢሰኞቹ ሲሄድ አንዱ በሬው ሞቶ ሌላው ማርሻው ተሰብሮ፣ ደግሞ ሌላው ወገሉ ተሰርቆ እንዲሁም ሌላው ዘር አጥቶ ሳያዘምሩ ስለቀሩ የደረሰባቸውን ችግር በሰው ደርሶ የማያውቅ አስመስለው ሲነግሩት አስተዛዝኖዋቸው «በሉ ግዴለም ከርሞ የዘንድሮውን ጭምር ትሰጡኛላችሁ» ብለው ባዶውን ይመለስና እሱም በፈንታው በጢሰኞቹና በሱ የደረሰውን ችግር እዬተረከ ወደ ብድሩ ይገባል። በሁዋላ እንዲያውም «ይግረምህ» ብለው፣ የቀጨኔ አለቃ ያችኑ ኩርማን ጋሻውን ላንድ ዘመዳቸው ስለ ሰጡበት በብስጭት አፉ አልፎ ኖሮ፣ «አለቃህን ደፍረሃል አዋርደሃል» ሲወጣ፥ እንኩዋን ላገልግሎት ለመሳለምም የቤተክርስቲያንን ቅጽር ላይረግጥ ምሎ እስር ቤት ሳለ መሰንቆና ክራር ምት ተምሮ ስለ ነእብረ በዘፋኝነት አገር ፍቅር ማህበር

ውስጥ ተቀጠረ። እዚያም አልቀናውም። አንድ አመት ያክል ውቤ» እዬተባለ ደስ ብሎት የሚያስተናግዳቸውንም ሁሉ ደስ አሰኝቶ እንደቆዬ ስላገር ፍቅር ተጫዋቾች ሲወራ ካለቃው ስም የሱ ስም መቅደም ስለ ጀመረ፣ አለቃው እዬተከታተለ ያስቸግረው ጀመር። ለበላይ አቤት ማለቱም ችግሩን ከማክበድ በቀር አላቃለለትም። ስለዚህ ዳኝነት ለብርቱ እንጂ ለደካማ አለመሆኑን አምኖ እዚያው የቆዩ እንደሆነ ከቀጨኔ አለቃ ጋር ተጣልቶ የደረሰበት እንዳይደገም ሰግቶ፣ ዳግመኛ የማንም ጭፍራ ላይሆን ወስኖ ስራውን ለቀቀ።

አዝማሪው ውቤ ተደጋግሞ፣ ከደረሰበት በደል የተነሳ የሰማይና የምድርን ባለሥልጣኖች አጥብቆ የሚያማርር አለም ከውበትዋ ክፋትዋ ጐልቶ የሚታየው ስለ ነበረ፥ ያን ለመግለጽ የሚገጥማቸውን የሀዘን ግጥሞች በንጉርጉሮ ሲጫወት ልብ ይነካ ነበር! ያሳዝን ነበር! በሌላው ጊዜ ግን ጨዋታና ቀልድ ወዳድ ጨዋታውን በዘፈን ግጥም መክፈት ልምድ አድርጎ የያዘ ተወዳጅ ተጫዋች ነበር። ታዲያ ሰው ሁሉ ያን ጎን ትቶ እንጉርጉሮውን ስለሚወድ «አልቃሽ ውቤ» ይለው ነበር። እሱም «አልቃሹ» ሲሉት «አቤት» አይበል እንጂ ያን ስም ለሱ ተስማሚ ባይሆንም በዝምታ ተቀብሎ ይኖር ነበር።

አንዳንድ አድናቂዎቹ ደግሞ «ፈላስፋው አዝማሪ» ይሉት ነበር። አዝማሪው ውቤ፥ ግጥሙ ታሪክ - ጠቀስ የምሁር ግጥም ድምጹ ጎርነን ብሎ ወደር የሌለው ከመሆኑ ሌላ በሱ፥ ደረጃ ያሉ፥ እውቅ አዝማሪዎች የሚጠይቁትን ያክል ዋጋ ስለማይጠይቅ፣ ከሌሎች አዝማሪዎች የበለጠ፣ ብዙ ሰው የሚወደው ነበር። እንዲያውም እጉዋደኞቹና እወዳጆቹ ቤትማ እንኩዋንስ ዋጋ ሊጠይቅ ባይጋብዙትም ራሱን ጋብዞ ሄዶ ይጫወታል።

ደመቀች አዛዥ እንዳተማሩዋት «አመመኝ» ብላ ከወይዘሮ ጽጌ ተሰናብታ፥ አጥሩን እስክትወጣ እውነት የታመመች ለመምሰል አንገትዋን ደፍታ፣ እግሮችዋን እያወላገደች ስትጎተት ቆዬችና አጥሩን ከወጣች በሁዋላ ተኩሶ እንደ ሳትዋት ፌቆ እዬዘለለች አዛዥ ቤት ገባች። እዚያ ዘፈኑ ደምቆ አዛዥም የማያውቁበትን እመሀል ገብተው ሲዘፍኑ ስለ ደረሰች እሳቸውን ደስ እንዲላቸው አብራ ትዘፍን ጀመር።

ደመቀች ስትደርስ፥ ዘፈኑ በቀናቃኝና በተቀባዮች መሀከል እዬተመላለሰ ባረብራቦና በውዝዋዜ ደረጃ ነበር። ከዚያ እዬሞቀ እዬሞቀ ሄዶ ካረብራቦና ከውዝዋዜ ወደ እስክስታ፥ ከዚያው ወደ ዳንኪራ ሲተላለፍ ሁሉም በያለበት እንደ ባላውሌ እያገሳ እስኪያልበው ዳንኪራ ይመታ ጀምር። ከዳንኪራ በሁዋላ ብዙዎች ወደ መቀመጫው

እንኩዋ ለመድረስ ደከሞዋቸው እዬሳቁ እዚያው ሽብርክ ሲሉ ሌሎች ብዙ ምእራፍ እንደ ሮጡ ሁሉ ከላይ ከላይ እያቃተታቸው በዬቆሙበት እንዳሉ ላባቸውን ይጠምቁ ጀመር።

«እንዲህ አንድ ጊዜ ዝም በሉና ለዛሬው ደስታችን ምክንያት የሆነው ነገር ይገለጽ» አሉ አዛዥ ሰዎች ዝም እንዲሉ ደጋግመው አጨብጭበው። ዳንኪራ ሲመቱ ቆይተው ስለ ደከማቸው ትንፋሻቸው ቁርጥ ቁርጥ ይል ነበር።

«ዛሬ እዚህ ተሰብስበን የምናከብረውን የደስታ በአል የምናውቀው ውቤ ጌጤና እኔ ብቻ ነን። ለቀራችሁት ሁሉ እስካሁን ምስጢር ነው። ይህ የደስታ በአል እጅግ ትልቅ ስለሆነ እንደ ተራ ነገር ብቻውን መጥቶ አይገልጽም። ካሳቾች ጋር ባሳሳቾች ታጅቦ መጥቶ ነው የሚገለጽ። በነዚህ ወረቀቶች» አሉ አዛዥ አራት አነስ አነስ ብለው የተቆረጡ ወረቀቶች ከራሳቸው በላይ ከፍ አድርገው ይዘው እያሳዩ። «በነዚህ ወረቀቶች አራት የደስታ በአሎች ተጥፈዋል። ሶስቱ አሳሳቾ የቀልድ የደስታ በአሎች አንዱ ዋናው እውነተኛው እይደስታ አበላችን ናቸው። ሶስቱን የቀልድ በአሎች ጌጤና እኔም እናውቃቸው፤ ውቤ ፈጥኖ የጣፋቸው ስለሆኑ እኛም ገና ከናንተ ጋር ነው የምንሰማቸው። አሁን አራት ልጆች እንመርጥና አራቱም እያንዳንዳቸው እንደ እጣ አንድ ወረቀት ከውቤ እጅ በመዘዙ ቁጥር የመዘዙት ወረቀት ይነበባል። እውነተኛው የደስታ በአል የተጣፈበትን ወረቀት የመዘዘ ልጅ ያንድ ብር ሽልማት ከኔ ይቀበላል! » አሉና ወዲያው አራት ልጆች ተመረጡ። ካራቱ አንዱ የደመቀች ልጅ ተከስተ ነበር። ከዚያ አዝማሪው ውቤ ወረቀትችን ከዛዥ እጅ ተቀብሎ እንደ እጣዎች ያደበላለቃቸው ለመምሰል እጆቹን ሲያገለባብጥ ቆዬና ወደ መጀመሪያው ልጅ ሲዘረጋለት ልጁ እንዱን ወረቀት መዝዞ እንዲያነበው ላዝማሪው ውቤ መልሶ ሰጠው። በዚያ ወረቀት የሚከተለው ተጽፎበት ነበር።

«እኛ ግርማዊ አዛዥ ተካልኝ እግዚአብሔር በቸርነቱ ቅብአ መንግስት ተቀብቶ ሲያንግሰን ለዚህ ታላቅ ክብር ላበቃን ጌታ የምንከፍለው ዋጋ እንደዚያው ታላቅና አዲስ ስራት መመስረት መሆኑን ተገንዝበን አለም ከተፈጠረበት ጀምሮ እስካሁን ጌታ በገገርነት ሎሌ በተገገርነት ሀብታም በምቾት ድሀ በድህነት እዬኖረ ጌታና ሀታም ተገገርነትና ድህነትን ሎሌና ድሀ ገገርነትንና ምቾትን ሳይቀምሱ ስምንተኛው ሺህ ደርሶ እለተ ምጻት እዬቀረበ ስለ መጣ፥ ከዛሬ ጀምሮ በዚህ በተረፈው ጊዜ ሎሌ የገዚነትን ጌታ የተገገርነት ድሀ የምቾትን ሀብታም የድህንትን ቦታ ተለዋውጥው ይዘው እንዲኖሩ አውጀናል። ስለዚህ ዛሬ ይህን ቀን በዘፈንና በደስታ እንድታከብሩት አዘናል።

አዝማሪው ውቤ የጻፈውን የቀልድ አዋጅ አንብቦ ሲጨርስ የተሰበሰቡት ሁሉ ይስቁ ጀመር። አዛዥም መሳቃቸው ሳይቀር አዝማሪውን ሲሰድቡና ሲረግሙ ቆይተው፣ «እንዲህ ያለ የግዚአብሄርን ህግጋት የሚያፈርስ ነገር እንዳንተ ካለ ሰይጣን እንጂ ከኔ እንደማይወጣ ሰውም እግዜርም ያውቃል» አሉ። ከዚያ ሁለተኛው ልጅ የመዘዘውን ወረቀት ሲሰጠው አዝማሪው የሚከተለውን ያነብ ጀመር።

«እኛ ብጹእ እምብጹእን አዝማሪው ውቤ «አቡነ ሀራ» ተብለን በሊቀ ጳጳሳቱ መንበር ስንቀመጥ ከፍጥረት ሁሉ ተለይቶ የሰው ዘር ብቻ ጋብቻ በተባለ የባርነት ቀንበር ስር ተጠምዶ ተጨቁኖ መኖሩን ይህም ከፍጥረት ህግ ውጪ መሆኑ ሱባኤ ገብተን በጾምና በጸሎት ብዛት ስለ ተገለጸልን ከዛሬ ጀምሮ ወደ ፊት ወንዶችና ሴቶች ሁሉ ያላንዳች ገደብ፣ እንደ ሌሎች ፍጥረቶች በፈለጉት ጊዜና በፈለጉበት ቦታ ከመረጡት ጋር በግብረ ስጋ እንዲደሰቱ በዚህ መንፈሳዊ አዋጅ ሙሉ ነጻነት ሰጥተናቸዋል። ስለዚህ ዛሬ እዚህ የተሰበሰባችሁ ሁሉ ይህን የነጻነት በአል በደስታና በዘፈን እንድታከብሩ ፈቅደንላችሁዋል! » ብሎ ሲጨርስ ሳቅ ውካታ ሆነና እዚያ ከተሰበሰቡት የሚበዙት በጋብቻ የተሳሰሩ ስለ ነበሩ እነሱ ሁሉም የጳጳሱን መንፈሳዊ አዋጅ የሚደግፉ መሆናቸውን ገለጹ።

አዝማሪው ውቤ ከሶስተኛው ልጅ የተቀበለውን ወረቀት ማንበብ ሲጀምር ብቻ ጫጫታው ጸጥ አለ።

«አዋጅ አዋጅ» ይላል ሶስተኛው ወረቀት። «አዋጅ አዋጅ፥ አዋጅ እኛ ግርማዊት እቴዬ ጌጤ የሴቶችና ወንዶች ትክክል ተፈጥረው ሳለ የተመደባለቸው ያልተመዛዘነና ፍትርት የጎደለው የተግባር ድርሻ አለም ከተፈጠረ ጀምሮ እስካሁን ዘመናት እያለፉ ዘመናት ሲከታተሉ ሰባት ሽህ አመታት ሙሉ አንድ ጊዜ እንኩዋ ያልተሻሻለ በመሆኑ እጅግ ስናዝንና ስንቆረቆር መኖራችነን እግዚአቤር አውቆ የቲዬነቱን ስልጣን ስለ ሰጠን በተሰጠን ስልጣን ከዚህ የሚከተለውን አውጀናል። - ሴቶች እስከዛሬ በቤት ውስጥ የሚፈጽሙት የቤተሰባቸውን መብል መጠጥ የማሰናዳቱና በጠቅላላው የቤት አጠባበቁ ተግባር ሁሉ ልጅ አርግዞ አምጦ የመውለዱና አጥብቆ የማሳደጉ ተግባር ጭምር የወንዶች ተግባር እንዲሆን እንዲሁም ወንዶች ከቤት ውጪ የሚፈጽሙት ተግባር ሁሉ በቤት ውስጥ ቀን ከሌት የሚፈጽሙት ተግባር ጭምር የሴቶች ተግባር እንዲሆን ወስነናል! ይህን አዋጅ ተላልፈው የተገኙ ሴቶችም ሆኑ ወንዶች አይቀጡ ቅጣት ይቀጣሉ! ይህ አዋጅ፥ ከተነገረበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል! » ይህ የወይዛዝርት ጌጤ አዋጅ ተነቦ ሲያልቅ ውካታውና ጭብጨባው ካለፉት የቀልድ አዋጆች የላቀ

እጅግ የሞቀና የደመቀ ሆነ። ወይዘሮ ጌጤ ብቻ ከማፈራቸው ብዛት የተነሳ ብዙ መሳቅ እንኳዋ አልቻሉም።

አዛዥ ያስጻፉትን አራተኛውን ወረቀት ተከስተ ካዝማሪው ውቤ እጅ መዝዞ፣ እንዲያነበው መልሶ ሰጠውና አዝማሪው ከዚህ እንደሚከለው ያነብ ጀመር።

«የድሀን እንባ እያንዳንዱን ጠብታ የሚቆጥርና የሚሰፍር ጌታ፣ ደመቀች አምስት አመት ስታፈስ የኖረውችውን እንባ እየተቀበለ አጠራቅሞ አሁን መስፈሪያው ስለ ሞላ ልመናዋን ሰምቶ ልጅዋን ተከስተን መንግስት ባዳሪነት እንዲያተምርላት የወሰነበት ቀን በመሆኑ ዛሬ ይህን ታላቅ ደስታ ከስዋ ጋር የምናከብርበት ቀን ነው» ብሎ የመጨረሻው ቃል ገና ካፉ ወጥቶ ሳያልቅ «ይህ ነው ቁም ነገሩ! » እሱ አዛዥ አቋዋርጠው «ሌላው ሁሉ ውቤ የከሰለው ቀልድ ነው! ይህን ታላቅ ደስታ አብረን እንዳከብር ነው ትልቅ ትንሹ እዚህ የተሰበሰብን። ደመቀች የምስራች! እንኳዋን ደስ ያለሽ! ዛሬ ጥዋት ከተፈሪ መኮንን ትምህርት ቤት ስልክ ደውለው «ተከስተ ታምራት የሚባለው ልጅዋ እዚህ አዳሪ ሆኖ እንዲማር መንግስት ስለፈቀደ ቅዳሜ ጥዋት ይዛው እንድትመጣ ለደመቀች ንገሩት» ስላሉኝ ጎረቤቶቻችን ሁሉ አንቺንና ልጅሽን የሚወዱ ሁሉ የድስታሽ የደስታችን ተካፋዮች እንዲሆኑ ነው እይተሰበሰቡ! ጌጤና እኔ የተጋባንበትን ያርባ አመት መታሰቢያ ለማክበር አደለም! » እሉ ቀጠሉና።

ትልቅ የምሥራች እንደ ትልቅ መርዶ ልብ ይመታና ለጊዜው ያፈዛል፤ ያደነዝዛል እልልታውም ሆነ ዋይታው የሚመጣ ትንሽ ቆይቶ መፍዘዝና መደንዘዙ እያለፉ ደስታው ወይም አዘኑ እዬተሰማ ሲሄድ ነው። ደመቀች ለጊዜው ደንግጣ፥ አይኖችዋ ፍጥጥ ብለው ዝም ብላ ቆዬች። ሁዋላ ብቻ ድንዛዜው አልፎ ደስታው በሙሊ ሲሰማት የደስታ እንባዋ በግራ ቀኝ ጉንጮችዋ እዬወረደ ባዛዥ አንገት ተጥምጥማ ፊታቸውን ሁሉ ትስም ጀመር!

አዛዥ እንደ ምንም ብለው ከደመቀች ተላቀው እንድ ጀማሪ ቅኔ ቆጣሪ ቀኑን ሙሉ ሲቸገሩ ውለው የገጠሙዋቸውን የመሀይም ግጥሞች ለሚዘፍኑት ነገሩና የደከማቸው ተቀምጠው ጠላ ሲጠጡ የበረቱት ሴቶችም ወንዶችም በቀናቃኝና በተቀባዮች መሀከል እዬተቀባበሉ ይዘፍኑ ጀመር።

ዘፈኑ ደምቆ ሲዘፈን ደመቀች ደስታዋን እንጂ ዘፈኑን ኣታይም ኣትሰማም ነበር! ተከስተን አቅፋ አንድ ጊዜ ወደ ቀኝ እንድ ጊዜ ወደ ግራ እያዞረች እዬሳመች ያልተያያዙ ነገሮች ስትለፈልፍ ያበደች ወይም የሰከረች ትመስል ነበር!

«አዬ እናቴ፣ ኪዳነ ምህረት! አዬ እናቴ የደንጋያላይቱ! እውነት አልተውሽኝም! እውነት አብርሽኝ ተሰደሻል! እንኩዋን ልመናዬን ሰማሽኝ! እንኩዋን እልሜን እውን አደረግሽልኝ! እንኩዋን ልጄ ትምህርት ቤት ገባልኝ እንጂ እንግዲህስ የሆነው ቢሆን ግዴለኝም ገባህልም እንኩዋን አንተ መጠጊያ አገኘህልኝ እንኩዋን ‹ልጅሽን አሳዝዬ አባርርሻለሁ› መባሉ ቀረልኝ እንጂ እንግዲህስ አልፈራም! እንግዲህስ ማንም አያስፈራራኝ! ማንም አያዋርደኝ! » እያልች ምስጋናዋንም ፉከራዋንም ባንድ ላይ አደበላልቃ - ሰምተው ላይመልሱላት - «ለናቴ የደንጋየላይቱና» ለተከስተ ስትለፈልፍ ቆዬች። ከዚያ የደስታው ስካር በረድ እያለ ሄዶ አእምሮዋ በትክክል ማሰብ ሲጀምር የስዋ የድሀይቱ የገረዲቱ ልጅ ተፈሪ መኮንን ትምህርት ቤት መግባቱ ይህ «ይቻል ይሆናል» ብላ ባሳብዋ እንኩዋ አግብታው የማታውቅ ነገር፣ ይህ ትልቅ ነገር፣ በሙሉ ትልቅነቱ በሙሉ ግርማው ተስሎ እፈትዋ ቆሞ ስለ ታያት፣ ልጅዋን እንዳቀፈች በሙሉ ግርማው ተስሎ እፊትዋ ቆሞ ስለ ታያት፣ እሱን ባይነህሊናዋ ትመለከት ነበር። እዚያ ዘፈን እዚያ ጫጫታ እዚያ ውካታ ውስጥ ሆና እዚያ ውስጥ እንዳልሆነች ብቻዋን እንደሆነች ሁሉ ያን የሚያስገርም ትልቅ ነገር ብቻ እዬተመለከተች ትገረም ነበር! ተከስተን ደስ ያሰኘው ደግሞ ሌላ ነበር። ለተከስተ እናቱ የሱ ትምህርት ቤት መግባት በደስታ አስክሮዋት እሱን እዬሳመች የምትለፈልፈው ስለሱ ትምርት ቤት መግባት ደስታውን ለመግለጽ ትንሽ ትልቁ ትምህርት ቤት የሚገባ መሆኑ ይህ ሁሉ ምኑም አልነበር! ለተከስተ እናቱ አቅፋው እንደ ተቀመጠች፣ ከዚህ ሁሉ የበለጠ የልጅ ልቡን በደስታ ያስጨፍረው የነበረ ከዚህ ሁሉ አኩርቶት ከቁመቱ በላይ አንጠራርቶት የነበረ ከሶስቱ ጉዋደኖቹ ጋር እጣ ሲመዙ ከሁሉም አሸናፊ ሆኖ አንድ ብር መሸለሙ ነበር!

እንዲያው በዚያ ዘፈንና ጫጫታ፣ በዚያ ውካታ መሀል እናትና ልጅ ከዬግል ደስታቸው ጋር ሲጫወቱ «በቃሽ እንግዲህ ልጁን አታስጨንቂው ከጉዋደኞቹ ጋር ይጫወት! » አሉ አዛዥ ተከስተን አጭንዋ አሰስተው ደመቀችን ከተቀመጠችበት ሲያስነሱ። ከዚያ ጎረቤት ደመቀችን «እንኩዋን ደስ አለሽ እንኩዋን ደስ አለሽ! » እያለ ሲንጫጫ ቆይቶ ሁሉም ቦታውን ያዘና ራት ቀረበ።

ከራት በሁዋላ ጠጅ ለሚጠጣ ጠጅ ጠላ ለሚመርጥ ጠላ እዬጠጣ እዬተጣጣ አዝማሪው ውቤ በግል ቅዋንቁዋው ደስታውን መግለጽ ሲጀምር እንደ ተለመደው እንዲያ ባለ የጭዋታ ጊዜ ግጥም ላዝማሪ መስጠት የሚፈልጉ ተጠንቅቀው ይጠብቁ ጀመር።

«እሰይ ና ወዳጄ እሰይ ናማ ምነው» አለ አዝማሪው ውቤ፥ የመሰንቆው ቅኝት ልክ እስኪገባ እዬመላለሰ።

«እሰይ ና ወዳጄ፣ እሰይ ናማ ምነው
ያዘን ደስ ሲለው ደስታው ደስታችን ነው።

«ተላላፊ ነወይ ደስታ እንደ በሽታ
ተጋባብን በኛም የደመቀች ደስታ።

«ለምን ደስ አይለን ደስ ይበለን እንጂ
እርሙን ቅን ፍርድ ሲፈርድ የማርያም ልጅ።

«ቀኝህን ለጠፋህ ስጠው ግራህን
ኩታህን ለቀማህ ስጠው ቀሚስህን
አጥብቀህ ውደደው የሚጠላህን
ከልብህ መርቀው የሚጠላህን
ይቅርታ ለምነው የበደለህን

«ከሌለው ተወስዶ ላለው ይጨመረው»
እያለ ግልብጦሽ ይፈርድ የነበረው
ዛሬስ ቅን ፈረደ ከቶ ማን መከረው?

«አለምን ከሰራ እስከ ዛሬ ማታ
ለጌቶች ነበረ የግዚአብሄር ርዳታ፣
ዛሬ በደመቀች አስማቱን ከፈታ
መስማት ከጀመረ የድሀ አቤቱታ፣
ደረሰ መስለኝ አሁን የኛ ፈንታ
ድሀ ደስ ይበልህ ተነስ ላሌ ምታ! »

እያለ ውበት ባስጌጠው ፈገግታ እንደ አንዲር በሚዝገመገም ላሄያማ ድምጽ ደስታውን ሲገልጽ፥

ውዱ ገብረ ጻድቅ የሚባለው ካዛዥ ጎረቤቶች አንዱ፥ «አንካ ተቀበል ሊቀመኩዋስ! » አለና አንዱን ግጥም ገጥሞ ሌላውን እስኪያስብ «ድግመው» እያለ የሚከተሉትን ግጥሞች ላዝማሪው ነገረ።

«ሰነፍ በስንፍናው ሲቀርበት ሀብት፣

ፈሪ እብከንቱ ድል ሲቀርበት

እግዜር እግዚአብሄርን ባይወርድለት፣

ከየት ይገኝ ኖሮዋል ከቶ ምክንያት?

ሰነፉና ፈሪው ጅሉ እንኩታኩቱ፥

ሳይሞላለት ሲቀር ውጥንቅጥ ምኞቱ፣

ምንጊዜም ልማድ ነው እግዜርን ማማቱ።

እግዜሀር ችሎት አርጎ ነው ሰውን አስከትቶ

በድሀ ላይ ሲፈርድ ለሀብታም አድልቶ፣

አዬሁ ሰማሁ የሚል ይኖር ይሆን ከቶ?

አዬሁ ሰማሁ የሚል እዚህ አለ እንደሆነ እስቲ አሁን ይናገር ይመስክር ተነስቶ።

«ሊቀመኳስ እንካ ተቀበል! » አለ ዳምጤ በልሁ የሚባለው ሁለተኛው ያዛዥ ጎረቤት። አዝማሪው ውቤ ብርሌ ጠጁን «ፉት» ብሎ አስቀመጠና የዳምጤ በልሁን ግጥም ተቀበለ።

«እኛምኮ እግዜርን የምንወቅስበት ዋና ምክንያቱ፣

አርጎ ከፈጠረን ሀብታንምና ድሀ፥ ደካማና ብርቱ፥

ግፍ ሲሰራ እያዩ ባለ መፍረዱ ነው ዝም በማለቱ።

ችሎት ተቀምጦ እዬመረመረ ፍርድ ቢሰጥማ

ሀብታም ድሀ ሳይል ወይ ብርቱ ቢሰጥማ፥

ሀብታም ድሀ ሳይል ወይ ብርቱ ደካማ፥

ይመስገን ነበር እንኩዋንስ ሊታማ።»

«ሊቀመኩዋስ በል እንካ ከኔም ተቀበል! » አሉ አቶ ፈረደ መንፈቁ ሀዲሳትና ብሉያት መጻሀፍት ጠንቅቀው የሚያውቁ ያራዳ ጊዮርጊስ ደብተራ ነበሩ። ስማቸው ሊቀ ጠበብት ፈረደ በሻው ነበር። በመጻሀ ትርጉዋሜ ከካህናቱ ጋር ስላልተስማሙ የጊዮርጊስ ካህናት «መናፍቅ» የሚል ቅጽል ስም ሰጥተው አባርረዋቸው ህዝቡ «ፈረደ መንፈቁ» ይላቸዋል። ስለዚህ ፈረደ መንፈቁ ከቤተክርስቲያን አገልግሎትም ከካህናት ማህበርም ተለይተው የንግድ ስራ እዬሰሩ የሚኖሩ ናቸው።

«ተቀበል ሊቀ መኩዋስ! » አሉ ደገሙና። አዝማሪው ጉሮሮውን ጠጅ ለቅልቆ ብርጭቆውን ቁጭ አድርጎ «ይዣለሁ› ሲል

«መጻሕፍት ሁሉ ባንድነት ተስማምተው እንደሚነግሩነ፣

እግዜር ችሎት አርጎ እንደየስራቸው፣ ፍርድ የሚሰጠነ፣

ይችም አለም ስታልፍ በምጻት ነው እንጂ መች ዛሬ ሆነ?

አሁን ችሎት አርጎ፣ ለሁሉ እንደ ስራው ፍርድ ከሰጠማ፣

በእለተ ምጻት ምን ሊያደርግ ይመጣል በመለኮት ግርማ?

የገዛ ራሱን ፍርድ እንደገና ደግሞ በይግባኝ ሊሰማ?

ይህ ከንቱ ወሬ ነው መንገድ የለቀቀ

ባልቴት የሚያወራው ምድጃውን ከብቦ እሳት እዬሞቀ!

«እግዜር ሰውን ፈጥሮ የወቀትን እስትንፋስ ‹እፍ› ሲል ባፍንጫው፣

ነጻነት ሲሰጠው ለመስራት እንዲችል ሰው ሁሉ እንደ ምርጫው

ህግን ሲሰራለት ምስክር ይሆን ዘንድ ለሁዋላ መቀመጫው

ድሮውን ተናግሮዋል በምጻት መሆኑን የሱ ፍርድ መስጫውን።

«እስከ ምጻት ድረስ ከፍጥረት ለይቶ ለሰው ያካፈለው፣

እውነተኛ ዳኛ ጉቦ የማይበላ አድልዎ የሌለው

ባንሰማ ነው እንጂ ህሊና ነበረ በውስጣችን ያለው» አሉ ወደ መጨረሻ ሲደርሱ ህሊና በአካል እፊታቸው እንደ ቆመና እንደሚያማጥኑት ሁሉ አይኖቻቸው ፊት ለፊት ትኩር፣ ፊታቸው ኩስትር ስሜታቸው ምርር ብለው። አቶ ፈረደ መንፈቁ ሲጨርሱ፣ እዚያ የተሰበሰቡት ሁሉ ፊታቸውንና ሌላ ሁኔታቸውን ተመልከተው ይስቁ ጀመር። ከዚያ አዝማሪው ውቤ ቀጠለ።

«አየ አቶ ፈረደ ብልህ ናቸው ስንል፣ ለካስ ሞኝ ናእው.

ውሸትና ስርቆት መግደልና ቅሚያ የሆነ ኑሮዋቸው.

ደጋግመው ደጋግመው የተመላለሱ በወንጀል ስራቸው፣

ገና ድሮ ድሮ ታሞ ተሰቃይቶ ሞቶ ህሊናቸው፣

የነበረበቱ ቦታው እንኩዋን ፈርሶ ጠፍቶ ከውስጣቸው፣

ከወዴት መጥቶ ነው? ወዴትስ ሆኖ ነው የሚፈርድባቸው?

እንዲያውስ እግዚአብሄር ከህሊና በቀር፣ ምን ከንቱ ፈጠረ?

ወይ ከሁሉ አልጠፋ ወይ በሁሉ አልኖረ

ታዛገሮቹን ሁሉ በጸጸት ሰንሰለት፣ አስሮ እያስቸገረ፣

ለማይታዘዙት የግፍ መፈጸሚያ አድርጎ ያኖረ?

«ይልቅ ከንቱ አንድከም የትም ላያደርሰን ይህ ሁል ፍልስፍና

አንተወው ግዴለም ድሀ በራብ ይሙት ሀብታምም በብስና

ለበዳይ ይፈረድ ተበዳይም ይካስ ይቀጣ እንደገና

መቸም ያለም ስራት እብድ እንዳደራው ድር ውትብትብት ነውና።

«ይህ የወንበዴ አለም የወንበዴዎችን ስራት ተከትሎ፣

ደካሞችን ረግጦ ሀይለኞችን አዝሎ

ያም ቢጮህ ያም ቢጮህ ይቀጥል ወደ ፊት ይጉዋዝ ዝም ብሎ

«ይህ ለመቀበል ብሎ የሚኮራ ደሙ የሚፈላ፣

ታግሎ መለወጥ ነው መንገድ የለም ሌላ።

ነገር ግን አንደኛ ደሙ የማይፈላ የረጋ ቀዝቅዞ፣

አለሙን እንዳለ እስከ ጉስቁልናው እስከ ግፉ ይዞ

ጥቃት እንዳያስቆጨው ምክንያት በመፍጠር መንፈስን አብዞ

ግፍ እንዳያሰቃይ በጌሸዋማ ጠላ ራስን አፍዝዞ፣

ቀን እየሰከሩ ሌሊት እዬተኙ፣ መቀጠል ነው ጉዞ።

ሀ.ሀ.ሀ እንዲያ ነው! መጠጣት መተኛት ማለምና መስከር

ስካር መልካም ነገር እልም መልካም ነገር፣

እግዜር የነሳኝን፣ ያደርጉልኛል ጌታ ያስገዙኛል አገር።

ባልገዛ ባልነዳ ባላዝዝ ባልናዘዝ ስሰክር ተሹሜ፣

ወዳጆቼን ባልሾም ጠላቶቼን ባልሽር ስተኛ በህልሜ

የዚችን አለም ጣም፣ ሳልቀምስ እሞት ነበር፣ በድሜዬ ፍጻሜ።

ጨምሩልኝ ከጠጁ ልስከርና ልንገስ

ዙፋን ይዘርጋልኝ ልብስ መንግሥት ልልበስ

ጮማ ነመን ይሁን ጠጅ እንደ ውሀ ይፍሰስ

ድሆችን ላበልጽግ ሀብታሞችን ላደህይ የልባችን ይድረስ።

አምጡ! ስጡ! ጠጡ! አምጡ! አምጡ!

ጠጡ - ጠጡ - ጠጡ - ጠጡ - ጠጡ - ጠጡ» ሲል መሰንቆውን ዳንኪራው ምታ ቃኝቶ ሁሉንም

ተነስቶ «ጠጡ - ጠጡ - ጠጡ - ጠጡ - ጠጡ - » እያለ እስኪያልበው ዳንኪራ መትቶ የሚወድቀው እዬወደቀ የቆመው እንደ ቆመ ከላይ ከላይ እዬተነፈሰ ሳቅና ውካታ ሆነ። ከዚያ ያዛዥ ቤት ጠላና ጠጅ ስላለቀ እዚያ ከነበሩት ብዙዎች እንደያቅማቸው አዋጥተው ጠላም ጠጅም፣ አረቄም ተገዛና ጨዋታው ደስታው ውካታው ቀጠለ።

ወንዶች በግጥሙ ውድድር ላይ ሲከራከሩ ሴቶች ደመቀችንና ሀር የሚያጣ መሆኑ ባንቺ ታዩ! » አለች አንድዋ ደመቀችን እቅፍ አድርጋ ይዛ እዬሳመች።

«እግዝእትነ ማርያምን እንዴት አርገሽ ብትለምኛት ነው እባክሽ እንዲህ በገሀድ የረዳችሽ? » አለች ሌላዋ

ከፊተኛዋ እቅፍ ጎትታ ወስዳ።

«ነይ እስቲ እባክሽ ንገሪኝ ምንስቴሩን እንዴት ብለሽ ነው የነገርሻቸው? አልፈራሻቸውም? ሽማግሌ

ናቸው? ወይስ - እኔ እምንስቴር ፊት ቅርቤ መናገር የምችል አይመስለኝም እንዲያው እንኳ የምናገረው የሚጠፋኝ ይመስለኛል! አንቺ - እንዲያው አይን አውጣዋ ነሽ! » አለች ሶስተኛዋ ደመቀችን ነጥቃ ወስዳ። ደመቀች ለተጠየቀችው መልስ ሳትሰጥ ሌላዋ ቀምታ ወሰደቻት። ከዚያ ደግሞ ሌላዋ፣

«ናስቲ የኔ አባት! እኔ ይህ ልጅ ትልቅ ሰው የሚሆን መሆኑን ገና ከፊት ጀርሞ ሰውነቴ ይነገረኛል። እዩት እንዲያው ግንባሩኮ ያስታውቃል! » አሉ ከጎረቤት ባልቴቶች አድንዋ ተከስተን ሳብ አድርገው ይዘው እዬሳሙ።

«ምን አንቱ ብቻ! የማያውቁት ታላልቅ ሰዎች እንኳዋ አልፈው ሂደ ያዩት እንደሆነ ቆመው እንደ ጉዋደኛ ሳያነጋግሩት አይሄዱም! እንዲያው እንጂ! እዝጊሀር እድሜ ሰጥቶት ሲያድግ ምን እንደሚሆን ያዩ! » አለች ሌላዋ።

በግጥሙ ውድድር፣ እግዚአብሄር እየወቀሱ የገጠሙትና ወቃሾችን እዬተቃወሙ የገጠሙት ለያሳባቸው ደጋፊ ማስረጃ እያእምጡ አንዱ ማስረጃ ሌላው አፍራሽ ማስረጃ እያቀረበ ሁሉም በዬበኩሉ «አሸነፍሁ» እንጂ «ተሸነፍሁ» የሚል ባለመኖሩ ክርክሩ መጨረሻ የሌለው መሆኑንና ጊዜውም መጠጡም መገባደዱን ስላዩ አዝማሪው ውቤ እንዲያ ካለ ጨዋታ በሁዋላ የሚያሳርግበትን «ሞሪኝ» የሚለውን እንጉርጉሮውን ማሰማት ጀመረ። «ሞሪኝ» ምንም ሌላ አዝማሪ የማይካፈለው አዝማሪ ውቤ የፈጠረው የሱ የግሉ ነው!

«ሞሪኝ መሰንቆየ ሞሪኝ ጉዋዴ ሞሪኝ እከተልሻለሁ፣

መቸም ያንቺ እስረኛ ምርኮኛሽ ሆኛለሁ።

«ሞሪኝ ልከተልሽ በሄድሽበት ቦታ፣

አንች የምትሰጭኝን የልብ ደስታ፣

ካንች የማገኘውን የመንፈስ ጸጥታ

ከማንም አላገኝ በምንም ሁኔታ

«ሞሪኝ መሰንቆዬ እንሳፈር ባዬር ላይ

ልጆች ርቦዋቸው እናቶች ጨንቆዋቸው ሲላቀሱ እንዳናይ።

«ሞሪኝ መሰንቆየ ልከተልሽና እንሂድ ወደ ሌላ፣

በማይታይበት እንደ ዱር አራዊት ሰው ለሰው ሲበላ።

«ሞሪኝ ጉዋዴ ሞሪኝ ጥለት እንሰደድ ከዚህ እንነሳ

ትንሹን ትልቁ በማያድንበት እንደ ባህር አሳ።

«ክንዱ ላልበረታ ልቡ ላጨከነ.

አመጽን እንዳያይ አይኑን ላልጨፈነ

ግፍ ከሚሰሩት ጋር አብሮ ላልዘፈነ

በዚህ ማህበር ቦታ የሌለው ከሆነ

ሞርኝ ከዚህ እንሂድ እያንጎራጎርነ።

«አንዳንቺና እንደኔ ስስ ቆዳ ያላቸው

የሌሎች መከፋት የሚያስለቅሳቸው

የሌሎች ደስታ የሚዘፍናቸው

በዚህ ማህበር ቦታ ስለማይኖራቸው

ሞሪኝ መሰንቆየ፥ እንሂድ ወደ ሌላ ጣጥለንላቸው።

«ሞሪኝ ወዳገርሽ ወደ መጣሽበት

ወደ ሙዚቃ አለም ህብረት ወዳለበት።

«ሞሪኝ ልከተልሽ ወደ ሙዚቃ አለም

እዚያ ህብረት እንጂ መለያየት የለም።

«ጽናጽል ከበሮ እንቢልታ፣ ዋሽንት

ጥሩንባ በገና ክራር፣ መለከት።

«አንቺም ከነሱ ጋር ባንድ ላይ ሆናችሁ

ምንም ልዩ ልዩ ቢሆን ፍጥረታችሁ

የህብረት የሰላም፣ አለም ፈጠራችሁ።

«አየ ጉድ! አየ ጉድ! የማይገኝ ነገር ከንቱ መመኘቴ!

ባገኝማ ኖሮ እንደ ፍላጎቴ

ከናንተ አንዱን በሆንሁ ቀርቶ ሰውነቴ!

«ኦ ሞሪኝ ጉዋዴ ሞሪኝ! ሞሪኝ ጉዋዴ! ሞሪኝ - ሞሪኝ ሞሪኝ! » ሲል መስንቆውን በዳንኪራ ሞት ቃኝቶ ሴት ወንዱ ህጻናቱ ጭምር «ሞሪኝ ሞሪኝ ሞሪኝ - » እያሉ ባንድ ላይ አብረውት ዳንኪራ መቱና ሳቅ ውካታ፣ ሆነ። ወዲያው ሌሊቱ ተገባዶ ስለ ነበረ እንደገና ሁሉም ደመቀችን «እንኩዋን ደስ አለሽ! » እያሉ ወደየቤታቸው ሄዱ።

ከሌሊቱ የተረፈው ደመቀች አይኖችዋን ሳታለብስ ነጋ። ልጅዋን አቅፋ ስትጋደም። ልዩ ልዩ አሳብ ከበባት። መጀመሪያ ለዚያ ሁሉ ጨዋታ ለዚያ ሁሉ ደስታ ምክንያት የሆነው የስዋና የልጅዋ ደስታ መሆኑ አንድ ቀይ ሳንቲም ሳታወጣ አዛዥና ሌሎች የጎረቤት ሰዎች፣ የድሀ ገንዘባቸውን አዋጥተው ያ ሁሉ መጠን እንደ ውሀ ሲፈስ ሌሊቱ የተገባደደ እስዋን ደስ ለማሰኘት መሆኑ ይህ ሁሉ ታሰባትና ከልብዋ የተነሳው የደስታ ሙቀት በሰውነትዋ ሁሉ ሲሰራጭ ሰውነትዋን ሁሉ ሲወረው ተሰማት። ልብዋ በጣም ተነካ። «ለካ - በባዕድ መሀከል አደለሁም! ለካ በዘመድ መሀከል ነኝ! » አለች አይኖችዋን በጨለማ አፍጥጣ ደስ ብሎዋቸው ሲጨፍሩ ያመሹትን ሰዎች ሁሉ አንድ ባንድም ባንድ ላይም ባይነህሊዋ ሲያልፉ ዝም ብላ ስትመለከት ቆየችና። ከሁሉም ጎልተው አዛዥ ተካልኝ ታዩዋት። አዛዥ አንዳንድ ጊዜ እድሜ የከበደው አንገታቸው ከትከሻቸው መሀከል ወደ ፊት ደፋ ብሎ ጎበጥ ጎበጥ እያሉ ሲሄዱ፣ ሌላ ጊዜ አፋቸውን እስከ ጆሮ ግንዳቸው ከፍተው እንጥላቸው እስኪታይ ሲስቁ ታዩዋትና እስዋም እንደ

ተጋደመች ትንሽ እንደ መሳቅ ብላ «አየ - ደግ ናቸው እግዜር የሰጠኝ አባት! » አለች በመሳቅዋ የህሊና ወቀሳ ተሰምቶዋት። ወዲያው የሰጠኝ አባት! » አለች በመሳቅዋ የህሊና ወቀሳ ተሰምቶዋት። ወዲያው ያዝማሪ ውቤ ጣቶቹ በመሰንቆው ዜማ ተከትሎ ሲወርድ ታዩዋትና «ግሩም ነው! እንዴት ግሩም የሆነ ሰው ነው! » አለች እንደ ተጋደመች ራስዋን እዬወዘወዘች።

ከዚያ አይኖችዋን በጨለማ እንዳፈጠጠች አሳቡን ሁሉ ለስዋ ጥሎ በሰላም የተኛ ልጅዋን ከላይ ታች ከታች ላይ ለሰስ አድርጋ እዬደባበሰች እንዲያ ከልዩ ልዩ አሳብ ጋር ስትጫወት «እ - እመዬ! » አለ ተከስተ በንቅልፍ ልቡ «ታመልጥሀለች» እንደ ተባለ ሁሉ ያቀፈበትን እጁን ጠበቅ አድርጎ። «አብ - ዬ! » አለች እስዋም እንቅፋትዋን እንደሱ ጠበቅ አድርጋ። «እም - ! » አለና ሰላማዊ እንቅልፉን ቀጠለ!

እንዲያ በጨለማ አይኖችዋን አፍጥጣ ልጅዋን በዳበሰች መጠን ትምርት ቤት ከመግባቱ ጋር የተያያዘው መልካሙ ክፉው ያለፈው የሚመጣው የቅርቡ የሩቁ አሳብ ሁሉ ሊበጠስ እንደማይችል የዱር አረግ አንዱ ሌላውን እዬሳበ እስበሱ ተጠላልፎ፣ ባንድ ላይ ተቆላልፎ እዬተግበሰበሰ መጣባት! መጀመሪያ ያ የምትዳብሰው ልጅ ያ የስዋ የምኪንዋ የገረድዋ ልጅ እንደ ጌቶች እንደ ሀብታሞች ልጆች የጌቶች ልጆች ጋር ባዳሪነት ተፈሪ መኮንን ትምህርት ቤት የመግባቱ አሳብ ልብዋን ኩራት በተቀላቀለበት ደስታ አሞቀው፤ አኹበረበረው! እስከ ተኛበት አልጋ ከመሬት በላይ አሞቀው በላይ ከፍ ያለች መስሎ ተሰማት! ብቻ ይህ የደስታና የኩራት ስሜት ብዙ አልቆዬም። ቶሎ ጠፋና ሌላ አሳብ መጣ! ከጥቂት ቀናት ከሶስት ቀናት በሁዋላ እዚያ አልጋ ላይ እንዲያ አቅፋ የምትዳብሰው አለመኖሩ ከሶስት ቀናት በሁዋላ እዚያ አልጋ ላይ በዚያ ልጅ ፈንታ ጉልበትዋን አቅፋ ብቻዋን የምትተኛ መሆንዋ ከሶስት ቀናት በሁዋላ ተከስተ ልጅነቱ ባይቀር፣ ያልጋ የምግብ፥ የጨዋታ፣ ጉዋደኝነቱ የሚቀር መሆኑ፥ ከሶስት ቀናት ጀምራ ሰባት አመታት ሙሉ ላጭር ጊዜ እንኩዋ፥ ሳይቀር የኖረውን ልጅዋን እንደ ቤተ ክርስቲያን ሳሚ ከሳምንት አንድ ቀን እሁድ እሁድ ብቻ በማየት የምትወሰን መሆንዋ ይህ ሁሉ ታሰባትና፥ ፍራት ገባት፤ ልጅዋ ተሸበረባት! ሰባት አመታት ሙሉ እስዋና እሱ ባንድ ላይ ተደምረው አንድ አካድ አንድ ነፍስ ሆነው ይኖሩ ነበር። አሁን ድንገት እሱ ከስዋ ሲነጠል እሱ ሲቀነስ፣ ጎዶሎ የሆነች በውስጥዋ ባዶነት የተፈጠረ መስሎ ተሰማት! ሆድዋን ባር ባር አለው። ደግሞ ከሱ የባሰ አለ እንጂ! ተከስተ የድሀ ቅምጥል ነው። «ራበኝ ይልና ደፋ ቀና ብላ የሚወደውን ስለምታውቅ ቶሎ ያኑ ያላትን እንደሚወደው አድርጋ አሰናድታ ልታጎርሰው ስትቀርብ ልቡ እዬወደደ ጎምዥቶ

ጉሮሮው ምራቁን አስር አስር ጊዜ እየዋጠ ሆዱ «የህል ያለህ! » እያለ፥ እዬጮኸ ድንገት ግንባሩን በውሽት አጨማዶ ከንፈሩን አኾመድሙዶ «እምቢ አልበላም እምቢ አልፈልግም! » ይላል። እንድትለምነው እንድታባብለው እዬሳመች እንድታቆላምጠው ነው። እስዋም ይህን አመሉን አውቃ ምግቡን ወደ ጎን ታስቀምጥና ከጉልበቱ ጀምራ ወደ ላይ እስከ ግንባሩ፥ ከግንባሩ እንደገና ወደ ታች እስከ ጉልበቱ፥ እስከግሩ አካላቱን ሁሉ እዬሳመች ስትለምነው ስታባብለው ልቡ በደስታ እዬዋኘ መብላቱ ይጀምራል። የሚወዱት እንዲያ በፍቅር ሲጨነቅ እንዲያ ሲለማመጥ እንዲያ ታቦቱን ሁሉ እዬጠራ ሲያማጥን እንዴት ደስ ይላል! እንዳንዴት ይጥማል! ተከስተ የሚወዳት እናቱ ፍቅርዋን በመጨነቅ በመለማመጥ በመሳም ስትገልጽ ከላዩ ብዙ ጊዜ፥ ቢርበው እንኳዋ አይበላም። ከሶስት ቀናት በሁዋላ «ብላልኝ» ብሎ ማን ይለምነዋል? ማን ይጨነቃል? »ልጄ በራብ ይሞታል? ልጄን ራብ ይገለዋል? » አለች ይህን ሁሉ ስታስብ ቆይታ። እንዲያውም ልጅዋ ትምህርት ቤት እንዲገባላት ሚኒስትሩን ደጅ መጥናትዋ፥ መሰንበቻዋን ለማታውቃቸው ታቦቶች ሁሉ መሳልዋ የሚገባ መሆን አለመሆኑን ማወቅ ተሳናት፤ ግራ ገባት!

እንዲያ ብዙ ስትቸገር ከቆየች በሁዋላ፣ አንድ የምትጽናናበት አሳብ ያገኘች መሰላት። «ከድሆች ልጆች ይልቅ ተቆላምጠው የሚያድጉ የጌቶች ልጆች ናቸው። ታዲያ ለነሱ የሆነው ለኔ ለድሀዋ ልጅ የማይሆንበት፥ እነሱ የለመዱትን እሱ የማይለምድበት ምን ምክንያት አለ? ግዴለም ለጊዜው ብቻ! እኔም እሁድ እሁድ አልለዬውም! » እያለች እንደ ተንቀላፋ ፊቱን ሁሉ ትስመው ጀመር።

እንዲያ ፊቱን እዬሳመች አካላቱ ለሰስ አድርጋ ስትዳስስ ሽልብ አደረጋት። ብቻ አይኖችዋ ገርበብ ቢሉም ጨርሰው አልተከደኑም። ተከስተን የሚዳብሰው እጅዋም መዳሰሱን ጨርሶ አላቆመም፤ ትንሽ ትንሽ ይነቃነቅ ነበር። እንዲያ በንቃትና በንቅልፍ መሀከል እንዳለች ያን ከንቃት ወደ እንቅልፍ አለም የሚወስደውን ቀጭን መንገድ እንደ ያዘች ተከስተ በውስጥ ጥሩ ዝንጉርጉር ሸሚዝ፣ በላይ አዲስ ካኪ ኮትና ቁምጣ ሱሪ ለብሶ በግሩ ጥሩ ጥሩ ሹራብና ጫማ አድርጎ አጊጦ ይመጣና እፊትዋ የሚቆም ይመስለታል።

«እንዲህ ያለ ጥሩ ልብስና ጫማ ማን ሸለመህ? » ትለዋለች።

«አቡ በሽር» ይላላ ተከስተ። አቡ በሽር እዚያው እነሱ ሰፈር የሚኖሩ እመሀል አራዳ ትልቅ የልብስ ሱቅ ያላቸው፥ ሀብታም ነጋዴ ናቸው።

«እሰይ የኔ ልጅ በጣም ተስማምቶሀል፥ በጣም አምሮብሀል! » ብላ አቅፋ ስትስመው እቅፉዋን ጉም እንዳቀፈ ሁሉ ባዶነት የሚሰማው፣ ከንፈርዋ የሱን ከንፈር ሳይነካ ብቻውን የሚጮህ ይመስላታል።

«ሳቅፍህና ለስምህ የነካሁህ የማይመስለኝ ለምነው? » ትለዋለች።

«ያቺን ልጅ ስለልሆንኩ ነው። ላቡ በሽር ሰጥተሻቸው የሳቸው ልጅ ሆኛለሁኮ። ይህን ልብስና ጫማ የሰጡኝም የሳቸው ልጅ ስለሆንሁ ነው» ወዲያው፥ አቡ በሽር በሰላም ልብሳቸውና ጥምጣማቸው ፈንታ የክርስቲያን ቄስ ልብስና ጥምጥም ለብሰው ይመጡና «ልጄን ልትወስጅብኝ ነው አቅፈሽ የምትስሚው? » ብለው ከቅፍዋ ነጥቀው ይወስዱባታል። ይዛ ለማስቀረት ተከትላቸው ስትሮጥ በሰዋና ልጅዋን ይዘው በሚሸሹት ባቡ በሽር መሀከል፣ ሜዳ የነበረው መሬት ድንገት ልታሻገረው የማትችል ሰፊ ጉድባ ይሆንና የሚያግዳት ይመስላታል። እዚያ ጉድባ አፋፍ ላይ ቆማ፣ «አቡ በሽር አቡ በሽር የሚፈልጉን ሁሉ እከፍላለሁ እባክዎ ልጄን ይመልሱልኝ» እያለች ስትጮህ ተከስተም እጁን ከራሱ በላይ እያራገበ «እመዬ ተለያዬን እንግዲህ አንገናኝም! » ሲል እሱንና አቡ በሽርን ነጭ ጉም እመሀል አልቦ መጥቶ ይሸፍናቸውና እዚያ ውስጥ ይጠፋሉ!

ያንጊዜ፥ ዋ - ይ! ልጄን ወሰዱብኝ! » ብላ ጮሀ ስትነሳ፥ ተከስተም ደንግጦ ተነስቶ፣ «እመዬ ምን ሆንሽ? እመዬ፥ እመዬ» ይል ጀመር፥ ባንገትዋ ተጠምጥሞ።

«በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ? አለህ? አብዬ? አብዬ አለሁ አለች እስኪጨንቀው ወገቡን አጥብቃ ይዛ።

አለሁኮ እመዬ፣ ማን ወሰደኝ መስሎኝ ነው? እኔ አለሁ። ብቻ አጥብቀሽ አትያዢኝ አሳመምሽኝ! » አለ ተከስተ ዳግመኛ እንዳያመልጣት ወገቡን ከመጠን ያለፈ አጥብቃ ስለ ያዘችው ጭንቅ ጭንቅ ብሎት።

«ቅዠት ነው መሰለኝ በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አለች እንደገና። ፍራቱ ከውስጥዋ አልወጣ ብሎ፥ ወገቡን እንደ ያዘች ስትንቀጠቀጥ ብዙ ቆዬች። ወዲያው ነግቶ ስለ ነበረ ወፎች ይንጫጩ ጀመር።

ደመቀች ህልም በሚታመንበት አካባቢና ቤተሰብ ውስጥ ተወልዳ ያደገች ስለ ነበረች ህልም በጣም ታምን ነበር። ምንም እንኩዋ የተወለደችበትን አካባቢና ቤተሰብ የለቀቀች ገና አስራ አራት አመት ተካልሎ ሳይመላት ቢሆን በዚያ የልጅነት እድሚዋ

ስለ ህልም ስለ ሌሎች ቁጥር፥ ስፍር የሌላቸው አምልኮዎች - ከነትርጉዋሜያቸው - በቤተሰብዋ ውስጥ ይሁን ከዚያ ውጪ፥ እዬሰማች ያጠናችው ባእምሮዋ ውስጥ እንደማይተፋ ሆኖ ተቀርጾ በህይወትዋ እስከ ብዙ ጊዜ ድረስ ክፉው በጣም ሲያስፈራት መልካሙ ደስ ሲያሰኛት ትኖር ነበር። ለምሳሌ፥ ህልም በተለይ፥ እንጋት ላይ - ከንቅልፍ ወደ ንቃት በሚሸጋገሩበት ጊዜ - የሚታይ ህልም ትርጉዋሜው ከታወቀና ተከታትሎ ከጠበቁት፥ «የማይስት ራእይ ነው» እዬተባለ የሚነገረው አጥንታ፣ አምናበት ትኖር ስለ ነበረ፥ ያ ስለ ጠላችውና ስለ ፈራችው - እንዳይደርስባት - «ቅዠት» ያለችው፥ እንጋት ላይ የታየት ህልም ወይም ራእይ፣ ያስፈራትንና ያስደነገጣትን ያክል በሙሉ ህይወትዋ ምንም ነገር አስፈርቶዋትም አስደንግጦዋትም አያውቅ!

## ምዕራፍ አስራ አምስት

# ያራዳ ልጅ!

ስለ ተከስተ ትምህርት ቤት መግባት የደስ ደስ የተጠጣው ያዛዥና ሁዋላም ጎረቤቶች የገዙት መጠጥ ዘፈኑ ጭዋታው፣ ውካታው ካንድ የድሀ ሰርግ አያንስም ነበር። ከመጠጡ ጋር ደስታውና ጭዋታው እዬጣመ ሳይታወቅ ሌሊቱን አገባዶት በነጋው፥ ጥዋት አዛዥና ባለቤታቸው ወይዘሮ ጌጤ እንቅልፍ ስላልጠገቡ፥ ደመቀች እንዲያውም ስላልቀመሰች ሁሉም ደክመው፣ ፈዝዘው ነበር። ቢሆንም አዛዥ ጌታቸው ከመነሳታቸው ቀድመው እግዝቢ መገኘትና ሰዎችን በዬስራቸው ማስማራት ስለ ነበረባቸው እድላቸውን እያማረሩ ተነስተው እጃቸውን ታጥበው፥ በዚያ ፊታቸውን አባብሰው እንጀራ ባዋዜ ቀርቦ እዬቀረሱ ወይዘሮ ጌጤና ደመቀች ጭምር ቡና ሲጠጡ፣

«አባባ ዛሬና፣ ነገ ለልጁ የሚያስፈልገውን ሁሉ ለመግዛት ገብያ እውላለሁ፣ ቅዳሜም ይገዬው ወደ ትምህርት ቤት እሄዳለሁ፥ ታዲያ - ሶስት ቀን ሙሉ ስጠፋ እመይቴ ምን ይሉ ይመስልዎታል? » አለች ደመቀች።

«እሳቸው የሚሉትን፣ ሲሉት ካልሆነ አስቀድሞ ማን ሊያውቅ ይችላል ልጄ? አሉ አዛዥ ትንሽ እንደ መሳቅ ብለው።

«እንዳልሰናበታቸው - አይፈቅዱልኝም፤ ምን ይሻላል? »

«ዝም ብለሽ ሂጂ! ዝም ብለሽ ሂጂና ምክንያቱን ሁዋላ እነግራቸዋለን። መቸም ያው - ስድባቸውና ርግማናቸው ነው፣ እሱን ታግሰሽ ልብሽን አስፍተሽ መቀበል ነው። »

«በስድብና በርግማን ብቻ የሚያልቅ ከሆነስ ግዴለም።»

«ከዚያስ አያልፉም። ግዴለሽም ለራሳቸው ሲሉ ከዚያ አያልፉም።»

«ለመሆኑ - እኔ ገብያውን አላውቅ፣ ማን ይረዳኛል አባባ? » አለች ደመቀች፥ እዩፈራች።

«እኔ አሁን - ጌቶን ቁርስ አብልቼ ሰዎችን በዬስራቸው ካሰማራሁ በሁዋላ ምን እሰራለሁ? ተሰናብብቸ አብሬሽ እሄዳለሁ ብቻ - እኔ የህሉን የማሩን፣ የቅቤውንና እንዲሁም ለምግብ የሚሆነውን ሌላ ሌላውን ገብያ ነው እንጂ፣ ይህን የሱቃ - ሱቁን ገብያ እጅግም አላውቅም። ለመሆኑ ምን ለመግዛት ነው ያሰብሽው? »

«ካኪ ኮትና ሱሪ ሸሚዝ፣ የውስጥ ልብስ የላይ ሹራብ ጫማና የግር ሹራብ መሀረብ፣ አንድ ሻንጣ እነኒህን የመሳሰሉትን ነው፣ አባባ።»

«ለዚህ ሁሉ ገንዘብ ታገኛለሽ? »

«ምንስቴሩን የሰጡኝና - እኔም ትንሽ ገንዘብ ለምንም ለምን ብዬ - ቆጥቤ ያስቀመጥሁት ነበር አባባ።»

«ታዲያ ቢሆንስ - እንዲያው አያርገውና ብትታመሚ ለመድህኒት መግዣ እንኩዋ ትንሽ ማስቀረት አይገባም ልጄ? »

«እዚያ ያለው ሁሉ ከዚህ ያነሰ ያለው አይገኝም» አሉ፤ ታዲያ አብሮዋቸው ከሚኖር ጉዋደኞቹ ያነሰ መስሎት እንዳይዝን ነዋ አባባ! ደስ እንዲለው ብዬ ነው። ለኔስ ከሱ ደስታ የበለጠ ምን ደስ የሚያሰኝ ነገር አገኛለሁ? »

«ይህ እንኩዋ - እንዲያው ከንቱ ነው! ብቻ - ብለሽዋልና ይሁን። እንደኔ፥ እንደ ሞኙስ ቢሆን፣ ልጅም ከራስ ወዲያ ነው! ግንዱ ከሌለ ቅርንጫፉ አይኖርም! » አሉና አዛዥ ደመቀች መስል ስላልሰጠቻቸው፤ እሳቸውም ዝም ብለው ሲያስቡ ቆይተው

«ኮትና ሱሪ ታዬ ይሰፋልና ለሌላውም ቢሆን - ከሱ የተሻለ፣ የገበያው ውስጥ - አወቅ አይገኝም። ግዴለም እሱ ሳይረዳን አይቀርም» አሉ።

ታዬ፥ ያዛዥ ታናሽ እት ልጅ ነው። እናቱ በልጅነቱ ሞተው፣ ያሳደጉትም መኪና ስፌት እንዲማር አድርገው ራሱን ያስቻሉትም አዛዥ ናቸው። ነገር ግን መሰላል ሆነው በደረሰበት ካደረሱት በሁዋላ፥ እሳቸውን ገለል አድርጎ፥ ባስተማሩት ስራ በጎ አዳሪ ሆኖ የሚኖር ነው።

አዛዥ ጌታቸው ተሰናብተው ተመልሰው ከደመቀችና ከተከተ ጋር አራዳ እታዬ ሱቅ ሲደርሱ፥ እሱ ከሁለቱ ሰዎች ጋር ቁጭ ብሎ ይጫወት ነበር። ከጭዋታ ተካፋይ ሳይሆኑ እንዲሁ ትንሽ ራቅ ብለው ቆመው ተላላፊውን የሚመለከቱም ሁለት ሰዎች ነበሩ። ሁለት የታዬ ቅጥረኖች መኪና ይሰፉ ነበር።

«ኧረ! አባባ ዛሬ ምን እግር ጣለዎ? » አለ ታዬ፥ አዛዥ ከበመቀችና ከተከስተ ጋር ሲገቡ፣ ከተቀመጠበት ተነስቶ። ምንም አፉ ላዛዥ ቢናገር አይኑ በደመቀች ላይ ነበር።

«ሽማግሌ አባትን ይጠይቁታል እንጂ ‹አልጠዬቅህ› ተብሎ ይወቀሳል? » አሉ አዛዥ ትንሽ ፍርጥም ብለው።

«እሱስ እውነት ነው። መቸም - ያዲስ አበባ ነገር ባሰቡት የማያውል ሆኖ ነው እንጂ መቸም ለመጠዬቅ ሳላስብ ውዬ አላውቅም።»

«በል ግዴለም እናንተ እኔ ተለያይተን አንለያይም። ይልቅስ አሁን ላስቸግርህ ነው የመጣሁ።»

«ምን አለ! መቸስ የስዎ ችግር ችግሬ አደል? »

«ይህ ልጅ፣ ይህ የደመቀች ልጅ ቅዳሜ ተማሪ ቤት ስለሚገባ ካኪ ሱሪና ኮት አንተ በደህና ዋጋ እንድትሰፋለትና፥ ሌላም ብዙ የምንገዛው ነገር ስላለ የዛሬን ስራ ስራ ፈተህ በደህና ዋጋ ከሚገዛበት እንድትወስደን ነው።»

«ኮትና ሱሪውን - ምናለ እንሰፋለታን፤ ሌላውን ለመግዛት ግን - ዛሬ ብርቱ ስራ ስላለብኝ የምችል አይመስለኝም፤ አዎ አልችልም አባባ በጣም ዝናለሁ፤ በምችልበት ቀን ቢኖር ኖሮ ደስ ይለኝ ነበር» አለ ታዬ ውሸቱን።

«ታዬ ደመቀችኮ ልጇ ናት! ለስዋ የምታደርገው ለኔ እንደ ምታደርገው ነው! አዩሀ ይህቺ ልጅ ጦም አድራ፣ እንደ ልጆች ጌጥ ሳያምራት ያላትን ትንሽ ገንዘብ ሁሉ ለልጅዋ በሚያስፈልገው ላይ ለማዋል ስትፈልግ፣ ገብያውን ባለማወቅ የድሀ ገብዘብዋ መውጣቱ ሳይቀር፣ ለተፈለገው ነገር ሁሉ ሳይደርስ ቢቀር የሚያሳዝን ይሆናል! የስዋ አዘን አዘኔ ነው! መቸስ ብሞት - ‹ሰው ምን ይለኝ› ብለን፣ አንድ ቀን ስራ መፍታትህ ይቀራል? ያን ለዚህ አድርግልኝ! »

«ኧረ ጠላትዎ ይሙት! ምን ባሉ ይሞታል? ዛሬ ብርቱ ስራ ባይኖረኝ ምን ቸገረኝ ነበር። የምትፈሉት እቃ የሚገኝበትን ሱቅ ለማሳዬት ከሆነ፥ ከኔ የተሻለ የሚያውቁ አሉ። እሱ ወንድሜም - የድካሙን ዋጋ ከከፈላችሁት ያሳያችሁዋል» አለ ታዬ ቀስ ብሎ እዚያ ቆመው አላፊ አግዳሚው ከሚመለከቱት ወዳንዱ ባገጩ እያመለከተ።

«በል ደህና ግዴለም! ኮትና ቁምጣ ሱሪውን አንተ በስንት ትሰፋልናለህ? » አሉ አዛዥ መቀየማቸው ከፊታቸው እዬታዬ።

«አንድ ሙሉ ነው? »

«ሁለት» አለች ደመቀች።

«ስንት ገንዘብ አላት? » አለ ታዬ አሁንም አፉን ላዛዥ እያናገረ አይኖቹን እደመቀች ላይ ተክሎ።

«ወጀው ጉ - ድ! ‹ልብስ ሽጥልን› አልነህ እንጂ ልጅ እንዳርልህ አላልነህ! ያላትን ገንዘብ ምን ያጠያይቅሀል? ጨርቁን አስመርጠንና ዋጋውን ንገረን! » አሉ አዛዥ ከመቀየምም አልፈው እንደ መቆጣት አሉና።

«መክፈል ከምትችለው ገንዘብ ጋር ተመጣጣኝ የሆነ ልብስ ለማቅረብ ብዬ ነውኮ አባባ» አለ ታዬ፥ አዛዥ መቆጣታቸውን ሲያይ፣ የተቋዋጠረ ፊቱን ፈታ ለማድረግ እዬመከረ።

«በል ደህና ደህና ጨርቅ ከያይነቱ አሳዬንና ለመረጥነው የጠዬቅኸውን ዋጋ እንከፍልሀለን፥ ‹የዋጋ ቅናሽ አድርግልን ይሉኛል› ብለህ እንደሆነ - ጨምዳዳ ፊትህን አስቀድመህ እንዲህ ኮሶ እንዳገሳው ሽማግሌ የባሰውን ያጨማደድኸው አይዞህ፥ አንጠይቅህም! » አሉ አዛዥ፥

ታዬ ጥፋቱን ስለ ተገንዘበ፥ ያዛዥን መራራ ስድብ ከህሊና ወቀሳው ጋር፥ ባንድ ላይ ምንም ሳይተነፍስም ዝም ብሎ ዋጠና ተነስቶ አራት አይነት ካኪ አቀረበላቸው። ከዚያ ተከስተ የወደዳቸውን ሁለት አይነቶች መርጠው፣ ታዬ መጀመሪያ በጠራው ዋጋ ለነጋው አስር ሰአት ላይ ሊያደርስላቸው ተስማምተው ወጡ። ከዚያ ሌሎች፣ እቃዎች የሚገኙባቸውን ሱቆች እንዲያሳያቸው ታዬ ያመለከታቸው ሰው ፈቃደኛ ስላልሆነ፥ እዚያው አብሮት ቆሞ ባዛዥና በታዬ መሀከል የሆነውንና ያዛዥን ተቀይሞ መውታት ይመለከት የነበረው በሻህ ዘለሌ፥ ተከትሎዋቸው ወጥቶ ሊረዳቸው ፈቃደኛ መሆኑን ገለጸላቸው።

«ኑ ከኔ ጋር፥ እኔ እስከ ሰባት ሰአት ስራ የለኝም፥ ረዳችሁዋለሁ፥ አባቴ» አለ በሻህ። ነገር ግን መቸም ሳይጠዬቅ፥ «አገልግሎት ልስጥ» የሚል ሁሉ መጠርጠሩ አይቀርምና፥ አዛዥ ሰውዬውን ጠረጠሩት። ብቻ ማማረጫ ስላልነበራቸው፥ ልባቸው መስጋቱ ሳይቀር በሻህን ባፋቸው እያመሰገኑ ተከትለው ሄዱ።

በሻህ ዘለሌ፥ በገበያ አካባቢ የራሳቸው መደበኛ ስራ ሳይኖራቸው የሌሎችን ስራ መከታተልን ስራና መኖሪያ አድርገው ከያዙት እንዲሁ በድምር «ያራዳ ወይም ያዲስ ከተማ ልጅ» በመባል ካልሆነ፥ በዬግል ስማቸው ማንም ሳያውቃቸው ሁሉንም ስም ከናባቱ ከነግብሩ በዝርዝር ከሚይውቁት አውታታዎች ጋር የኖረ በመሆኑ፥ የገብያውን ውስጠ ምስጢር ደህና አድርጎ የሚያውቅ ነበር።

«አሁን ምን መግዛት ነው የምትፈልጉ? » አለ በሻህ እናዛዥ ከታዬ ሱቅ ወጥተው ተከትለውት ሲሄዱ።

«ለዚህ ልጅ የሚሆን ጫማ፥ የውስጥ ልብስ፥ ሸሚዝ ሹራብ፥ ሻንጣና እንዲህ እንዲህ ያሉትን ነው፥ አደለም? » አሉ አዛዥ፥ ወደ ደመቀች ዘወር ብለው። ደመቀች አዎታዋን ለመግለጽ ራስዋን ወደ ላይ ገፋች። በሻህ ቆም ብሎ ትንሽ ሲያስብ ቆዬና፥ እዚያው አራዳ ውስጥ ‹ፓፓንድሩስ› ወደሚባል ነጋዴ ሱቅ ይዞዋቸው ሄደ።

«እስቲ - አንድ መጠነኛ ሻንጣ፥ ሙሴ ፓፓንድሩስ! » አለ በሻህ እዚያ እንደ ገቡ። እዚያ ሱቅ ውስጥ ልዩ ልዩ እቃ ለመግዛት የተደረደሩት ገብያተኖች በርከት ያሉ ነበሩ። ነገር ግን ለሁሉም እቃ እያቀረቡ የሚያሳዩም፥ በዋጋ እዬተከራከሩ የሚሸጡም፥ የፓፓንድሩስ ኢትዮጵያውያን ቅጥረኞች ናቸው እንጂ፣ ፓፓንድሩስ ራሱ፣ እንደ ታዛቢ ቆሞ ሲጋራውን እያጤሰ ከመመልከት በቀር አንድ ቃል አይተነፍስም። ባሻህ ሻንጣ ሲጠይቀው ፊቱ እንደ መቅላት አለና እንዳልሰማ ሌላ ሌላ ያይ ጀመር።

«አንድ መጠነኛ ሻንጣ፥ ሙሴ ፓፓንድሩስ! » አለ ደገመና ፓፓንድሩስ ወደ ቆመበት ቀረብ ብሎ። ፓፓንድሩስ አሽከሮቹ እያሉ በቀጥታ መጠየቁን እንደ ስድብ ቆጥሮት በጣም ተናዶ፣ እንዳይናገር ከባሻህ ጋር መናገሩን እንደ ውርደት ከመቁጠሩም ሌላ፣ የቁጣ ስሜቱን ለመግለጽ የሚበቃ ቃል አጥቶ አፉን እዬመጠጠ ምራቁን ሲውጥ፣ ካሽከሮቹ አንዱ ከሩቅ አዬና ወደ ባሻህ መጣ።

«ምን ትፈልጋለህ? » አለ አሽከሩም የጌታውን ቁጣ እንደ ተጋባበት ሁሉ ትንሽ እንደ መቆጣት ብሎ።

«አንድ መጠነኛ ሻንጣ እንፈልጋለን፤ ሌላም ብዙ እቃ እንገዛለን፤ ብቻ መጀመሪያ እስቲ ሻንጣውን አስዬን።»

«ታዲያ ድሮውንስ ወደኛ አትመጣም ኖሮዋል? ወደሳቸው ምን ወሰደህ! ና ከኔ ጋር! » አለና ቅጥረኛው እሱ ወደሚሸጥበት ወስዶ ሶስት መጠነኛ ሻንጣዎች ለምርጫ ሲያቀርብ ደመቀች ደስ ያላትን መርጣ ዋጋውን ብትጠይቅ «ሰላሳ አምስት ብር» አላት።

«እባክህ እውነተኛውን ዋጋ ተናገር! ይህ ሰላሳ አምስት አውጥቶ የቆዳ ሻንጣ ምን ሊያወጣ ነው? ይህ መናኛ የካርቶን ሻንጣ ካስራ አምስት ብር በላይ አያወጣም» አለ ባሻህ። ፓፓንድሩስ ምንም እንኩዋ የቆመበት ቦታ ራቅ ያለ ቢሆን አሳቡም ሆነ አይኖቹና ጆሮዎቹ በሻህን ይከታተሉ ስለ ነበር፥ የተናገረውን ሲሰማ፥ ያ ንግግር ከቅድሙ ድፍረት ጋር ተጨምሮ ያስነሳበት ቁጣ መግታት አቅቶት፥ የወባ መነሾ እንደ ተቀሰቀሰበት ሰው እዬተንቀጠቀጠ መጣና -

«ኢኛ ባዚ ጭቅጭቃት አይፋልጉም! ይፋልጋል ግዚ ገዛል፤ አይፋልጋል ግዜ ሄዳል! » አለ እንደ ብራቅ ጆሮ በሚያደነቁር ጩኸት። እዚያ ያሉት ገበያተኞች ሁሉ በዬጃቸው የያዙትን እቃ እንደያዙ ደንግጠው አንደ ጊዜ ፓፓንድሩስ አንድ ጊዜ ባሻህን ይመለከቱ ጀመር።

«ኢኛ ባዚ ጭቅጭቃታ አይሸጡም፤ ጭቅጭቃታ ፋልጋል ግዜ፣ ጭቅጭቃታ አሌ ሱቅ ሄዳል ውሬ! አውን ወጣ! » አለ ደገመና በዚያው በሚያደነቁር ጩኸት፤ የሚንቀጠቀጥ እጁን ወደ መውጫው ቀስሮ፣

«እኮ ታዲያ ለምን ይቆጣሉ? ገብያ ሁልጊዜም ተከራክሮ ነው። ወዲያውምኮ በገንዘባችን ልንገዛ ነው እንጂ ልንለምን አመልጣንምና እንደ ለማኝ ‹ወግዱ ውጡ› አንባልም! »

«ሳንጣ ምን ታውቃል አንተ! ሳንጣ ምን ታርጋል! አንታ ታውቃል ከሻ! ከሻ እሌ ሱቅ ሄዳል! ውጡ! » አለ ፓፓንድሩስ እጁን ወደ በሩ እንደ ቀሰረ።

ባሻህ እንደ መሳቅ ብሎ እናዛዥን ይዞ ለመውጣት ወደ በሩ ሲያመራ፥

«ምናባት ኩሻሻ፣ ውሻ! » አለ ፓፓንድሩስ መጸየፉን ለመግለጽ ከፍነሩን አሸራምሞ።

«እንዴ! ማነው ቆሻሻ ውሻ? » አለ በሻህ ዘወር ብሎ።

«አንታ ነው ውሻ! » አለ ፓፓንድሩስ ከንፈሩን እንዳሸራመመ የቀኝ ጠቋዋሚ ጣቱን ወደ በሻህ ቀስሮ።

በሻህ ዳግመኛ አልተናገረም፤ ቁጣው ብቻ እንደ እሳት እብሬቱ እዬነደደ ከሄደበት ተመልሶ ፓፓንድሩስ የመሸጫውን ጠረጴዛ ከውስጥ ተመርኩዞ እንደ ቆመ በተለማጭ ከዘራው ትከሻውን ሲለምጠው፣

«አይ -! » ብሎ ባለበት ሽብርክ አለ ፓፓንድሩስ። ከዚያ ቀና አለና ወደ ጉዋሮ በሚያስወጣው በር ሊወጣ ሲሮጥ በሻህ የመሸጫውን ጠረጴዛ ዘልሎ ተከትሎ ሁለት ጊዜ መላልሶ ጀርባውን እንደ ወቃው ወጣና በሩን ዘግቶ ጠፋ።

«አምባጉዋሮ በተነሳበት ቦታ ፖሊሶች የደረሱ እንደ ሆነ እዚያ ያገኙትን ሁሉ በምስክርነትም፣ በተባባሪነትም ስም እዬያዙ ስራ ያስፈታሉ» ይባል ስለ ነበረ፣ ያንጊዜ እፓፓንድሩስ ሱቅ የነበረው ገብያተኛ ሁሉ ሸሽቶ፣ ከሰራተኞቹ ሌላ እሱቁ ውስጥ የሚታዩት አዛዥና ደመቀች ከነልጅዋ ብቻ ነበሩ።

«ይህ ጥጋበኛ ‹ቆሻሻ ውሻ› ይበለኝ? ግን እውነቱ ነው ስድብ የሚገባን ሕዝብ ነን! በገዛ አገሩ ሀብት ‹የበይ ተመልካች፤ የሚሆን ህዝብ ባገሩ ቦታ አጥቶና ትርፍ ሆኖ የሚሰደድ ባእድ ሁሉ አገልጋይ ሎሌ የሚሆን ሕዝብ ካልተሰደበ ማን ይሰደብ? » አለና በሻህ ራሱን እዬወዘወዘ ፓፓንድሩስን ደብድቦ ካባረረበት ተመልሶ እናዛዥን ይዞ ወጣ። የፓፓንድሩስ ሰራተኞች ጌታቸው ሲደበደብ እንኩዋንስ ሊረዱት ለመገላገል አልሞከሩም፤ ነገሩ ያልጠበቁት ድንገተኛ ስለ ሆነባቸው ሁሉም ፈዘው ነበር።

«ይህ - መሬት የተፋው ወሮበላ ጌታ፣ ፓፓንድሩስን እንዲያ አድርገው ሲደበድባቸው ሁላችንም ዝብ ብለን የተመለከትን ምን ሆነን ነው እባካችሁ? አሁን እንግዲህ እሳቸው ምን ይሉናል? ከንግዲህ ከሰዎች አይቆጥሩንም! » አለ ከፓፓንድሩስ ሰራተኞች አንዱ፥ እነ በሻህ ከሄዱ በሁዋላ።

«እባክዎ ዝም በል፣ መሬት የተፋው ጥጋበኛ ይህ - ወደል ፈረንጅ ነው። እኛን ብቻ ሳይሆን እዚህ ሱቅ የሚገባውን ሁሉ እንደ ትል እዬተጸዬፈ አፉ እንዳመጣው ሲሳደብ ለምዶ አበሻ ሁሉ አንድ አለመሆኑን ከእንግዲህ ይማራል! እኔ መቸም ደስ ብሎኛል! » አለ ጉዋደኛው።

ከፓፓንድሩስ ሰራተኞች አንዱ፥ በሻህን ሌላው ጌታውን ጥፋተኛ አድርገው በመከራከር ላይ እንዳሉ፥

«ኤ፥ ገረማሪያ! » አለ ፓፓንድሩስ፥ የሩዋሮውን በርመዝጊያ ከውጭ ጠጋ ብሎ። ገብረማርያም ከሰራተኖቹ አንዱ ነው።

«አቤት ጌታ ፓፓንድሩስ! »

«ኩፉ ሰው ሄዱ? »

«አዎ ሄደ፥ ጌታ ፓፓንድሩስ።»

«ባኮ ገረማሪያም ውነት ንጋር፤ ክፉ ሳው ሄዱ ግዜ ሄዱ ንጋር አልሄዱ ግዜ አልሄዱን ንጋር፤ አልሄዱ ግዜ ሄዱ አትንጋር! »

«እውነት፥ አባቴ ይሙት ሄደዋል ጌታ ፓፓንድሩስ» ብለው ገብረማርያም የበሻውን መሄድ በመሃላ ካረጋገጠለት በሁዋላ ፓፓንድሩስ የጉዋሮውን በር መዝጊያ በትንሹ ከፈት አደረገና ራሱን አስገብቶ ቢያይ እውነትም እሱቅ ውስጥ ከሰራተኞች በቀር ማንም አልነበረም። ከዚያ በሩን፥ በሙሉ ከፍቶ ሲገባ ሰራተኞቹ ሁሉ በሱ መመታት ያዘኑ ለመምሰል አንገታቸውን እዬደፉ ቆመው ስላዬ፣ እረፍት ተሰምቶት፣ ሲደእብደብ በመመከት፥ ወይም አጠፋውን በመመለስ ፈንታ የሮጠ ፈርቶ አለመሆኑን የሚያሳምንበት መላ እዬፈለገ እጁን እኪሱ ውስጥ አድርጎ ወዲያ - ወዲህ ሲል ቆዬ። ከዚያ፥

«አይ ልጆች» አለ ቆም ብሎ። «ኩፉ ሰው ሳይጣን፥ ኤኛ ደሞ ሳይጣን፥ ሁለቱ ሰይጣን ይሆናል ግዜ፣ ኤኛ በጣም በጣም ኩፉ ስራ ይሰራል ነበር፣ ኤኛ ክፉ ሰው

በሽጉት ይገላል ነበር! ግን ኤኛ ከፉ ስራ ይሰራል አይፈልጉም። ይሻላል ከፉ ሰው ሰይጣን ይሆናል ጊዜ ኤና ማንፉስ ቅዱስ! »

«እውነት ነው፤ ያ ክፉ ሰው የሰይጣን ስራ ሲሰራ እርስዎ ዘወር በለው መቆየትዎ የመንፈስ ቅዱስ ስራ ነው። እሱ የሰይጣን ስራ ስለ ስራ እርስዎ ቢገድሉት ኖሮ፣ ይህ ሱቅ ይዘጋና ጉዳቱ ለርስዎ ብቻ ሳይሆን እኛ ጭምር ስራ አጥተን እንጎዳ ነበር» አለ ገብረማርያም ሲያሾፍበት።

«ል - ክኖ! አንታ ገብቶዋል፤ ውሬ ገረማሪያም! » አለ ፓፓንድሩስ፥ በፈጠረው መላ ሰራተኞቹን ማሳመን የቻለ መስሎት ፊቱ በደስታ በርቶ።

በሻህና አዛዥ ከፓፓንድሩስ ሱቅ ወጥተው ሳይነጋገሩ ትንሽ ራቅ እንዳሉ፣

«እስቲ አንድ ነገር ልጠይቅ ልጄ» አሉ አዛዥ፥ ፓፓንድሩስን በሻህ ሲደበድበው ሁኔታው ሁሉ ትዝ ስላላቸው እንደ መሳቅ አሉና። «ያን ፈረንጅ -እንዲያ እንደ ወደል አህያ በዱላ እዬደወልህ ስትነዳው፥ ዝም ብሎ ፊት ፊትህን ለመሮጥ ኖሮዋል - እንዲያው ምንም ሳንለው ገድሎ የገባ ይመስል ያን ያክል፥ ‹አካኪ ዘራፍ› እያለ የፈከረብን? »

በሻህ ዝም ብሎ ፈገግ ከማለት በቀር የሚመልሰው አልነበረውም።

«ይገርማ! ‹አህያ ሲያከላላ መድህኒቱ ዱላ› እንደሚሉት መድህኒቱን አቅምሰህ ልክ አገባኸው! » አሉና አዛዥ ከባሻህ አሁንም መልስ ስላጡ፣ «ለመሆኑ ድሮም እንዲህ ነው? ወይስ ዛሬ በጥዋቱ ሰክሮ ይሆን ገና ከመግባታችን በስድብ የተቀበለን? ‹እቃ እንግዛ› ከማለት በቀር እስቲ ምን አልነው? »

«አሽከሮቹ እያሉ እሱ ‹እቃ አሳዬን› መባሉን እንደ ውርደት ቆጥሮት ነዋ! አሽከሩ ‹እኛ እያለን ለምን ወደሳቸው ሄድህ› ሲል አልሰሙትም? »

«ኧረ ያሰፋ ያለህ! ደሞ በነጋዴ ቤት ይህ አለ? እኛንስ እስቲ ይሁን፤ ታላላቅ ሰዎች ቢመጡም ‹አሽከሮቼን ጠይቁ› ሊላቸው ነው? »

«ሹሞች ካልሆኑ ይላል። ሹሞች ሲመጡ ግን፣ ሰው በሚቆምበት እንኳዋ አይቆሙም፤ ቶሎ ወደ ጉዋዳ ይዞዋቸው ገብቶ ቡና፥ ወይም ሌላ የመረጡትን መጠጥ እዬጋበዘ እዚያው ድረስ የሚፈልጉትን እቃ አቅርቦ በቅናሽ ዋጋ ይሸጥላቸዋል፤ ‹እሺ›

የሚሉ ከተገኙ እንዲያውም አንዳንድ ነገር ‹ለሚቴ ወይም ለልጆች› ብሎ ይሰጣል! እንዲህ ባያደርግ እንዲህ ባልሆነ አባቴ! »

«እንዲያ ነው? እ - ! ‹በጠባቂው የተማመነ በግ ላቱን ውጪ ያሳድራል!› እንደሚሉት መሆኑ ነው! » አሉ አዛዥ።

ከዚያ፣ አዲስ ከተማ ተሻግረው ወደ አህመድ አሊ ሱቅ ሄዱ። አህመድ አሊ ሞላላ ቁፍጣውን ደፍቶ ረዥም፥ ኮቱን እስከ ጥንቁሩ ቆልፎ ሁለት እጆቹን ወደ ሁዋላው በጀርባው አስተሳስሮ፣ ከመሸጫው በስተሁዋላ ወዲያና ወዲህ እዬተመላለሰ ሽርሽር ይላል። ገብያተኞችን የሚያገለግሉ ሁለት የህንድ ቅጥረኞች ናቸው።

«ምሊካን፥ ሻንጣና የልጅ ልብስ በያይነቱ እንፈልጋለን፤ እስቲ - መጀመሪያ ሻንጣ አውርድልንና እንምረጥ» አለ በሻህ ወዳንደኛው ቅጥረኛ ሄዶ።

«ሚን አይናድ? ይልቅ ሾይ ድንሽ? » አለ ሚሊካን።

«መሀከለኛ።»

ሚሊካን፥ ሁለት ልዩ ልዩ ቀለም ያላቸው መጠነኛ ሻንጣዎች አውርዶ እመሸጫው ላይ እየከፈተ ውስጣቸውን ካሳዬ በሁዋላ፣ እንደ ገና ዘግቶ ሁለቱንም በሙሉ ሀይሉ ሁለት ሁለት ጊዜ በጡጫ መታና ጥርሱን እንደ ነከሰ በሻህን ፍጥጥ አድርጎ አዬው። ብርታታቸውን ማስመስከሩ ነው።

«ጥሩ ነው፤ በል የሁለቱንም ዋጋ ንገረን፤ ዋጋው የሚስማማንን እንድንገዛ።»

«የውለድ ቫጋ አንድ ነው፤ ኡሉድ ቫጋ የላም።»

«ስንት? »

«አያ ስድስድ።»

«አትቀንስም? »

«ሹሳድ አያምስድ፤»

«ምነው ይህ አይነት ሻንጣ አስራ አምስት አልነበረም? »

«እሱ ፈድናው፤ አኡን ያለም። ባድፋልግ ደው! » አለና ሚሊካን ሻንጣዎቹን አነሳ። ከዚያ በሻህም እናዛዥን አስከትሎ እዚያው አጠገብ ወደ ሁሴያን ዮሴፍ ሱቅ ሄዱ።

ሁሴይን ዝጉርጉር ጃዊውን አገልድሞ፥ በዚያ ላይ ግራጫ መሳይ ኮት ደርቦ፥ ያገለደመውን የመስለ ጃዊ በራሱ ከበድ አድርጎ ጠምጥሞ፣ ከመሸጫው ጀርባ፣ ሱቁንና መኖሪያ ቤቱን በሚያገናኘው የተዘረጋ በር ፊት ወንበሩን ተክሎ፣ ጫቱን እያላመጠ ተቀምጦዋል። በሻህ፣ ሁዋላ ለናዛዥ እንደ ነገራቸው፥ ባለባበሱ ሹም የሚመስል ሰው፥ ወይም መልከ ቀና ሴት ካላዩ፥ ሁሴይን ከወንበሩ ጋር እንደ ተቸነከረ ሁሉ ከተቀመጠበት አይንቀሳቀስም! ገብያተኞችን የሚያስተናግዱ ሁለት ኢትዮጵያውያን ልጆች ናቸው። ሁሴይን ደመቀችን ሲያይ ፊቱ በቅጥበት ፈገግ አለና፥ ከተቀመጠበት ተነስቶ፥ ከልጆቹ ያንዱን ቦታ ቀምቶ፣ መሸጫውን በሁለት እጆቹ ተመርኩዞ ወደ ፊት ቀረብ አለና፥

«ትፈልግኪ ሚን? እመይታ! » አለ፥ አፉን ግራ ቀኝ እከ ጆሮ ግንዱ አላቅቆ።

«ሻንጣና የልጅልብስ እንፈልጋለን፥ ሸህ ሁሴይን። መጠነኛ ሻንጣና ለልጅ የሚሆን ሸሚዝ፥ ሹራብ፥ የውስጥ ልብስ፥ የግር፣ ሹራብ፥ መሀረብ አለ? » አለ በሻህ፥ ደመቀች ለተጠዩቀችው መልስ።

ሁሴይን ባሻህን ሳይጠዩቅ መልስ በመስተቱ ገላመጠና ወደ ደመቀች ዘወር ብሎ «አሌ ሳንጣ፣ አሌ ሸሚዝ፣ አሌ ሱራብ፥ አሌ ውስት መለብስ አሌ ሱራብ ኤግር፥ ወአሌ ማራብ፥ አሌ ኩሉ አማይታ! » አለ፥ ግራ ቀኝ እስከ ጆሮ ግንዱ በተለቀቀ አፉ፥ በጥርስ ፈንታ የሞላው የጫት አተላ እያሳዩ።

«እስቲ ሁሉም ይውረድልንና እንምረጥ» አለ በሻህ።

«አውራድ ኤንታ! ሚናበተከ ትርጉም ትሹፍ! » አለ ሁሴይን ቦታውን ስለ ተቀማ ወደ ጎን ቆሞ የሚመለከተውን ልጅ ተቆጥቶ። ልጁ ወዲያው በመሳላል ወጥቶ የተጠዩቁትን እቃዎች ሁሉ ከያሉበት አጠረጋቅሞ አወረደና በመሸጫው ላይ ደረደራቸው። ሁሴይን ያቀረባቸውን እቃዎች ሁሉ ተከስተ በጣም ወደዳቸው። እውነትም በተለይ ሸሚሾቹ በጥም ጥሩዎች ነበሩ። ነገር ግን ዋጋቸው እጅግ ውድ ስለሆነ፥ ከደመቀች የመከፈል አቅም ጋር የማይቀራረብ ሆነ።

«እስቲ መጀመሪያ የዚህን ዋጋ ይንገሩኝ» አለ በሻህ፥ አንዱን ሸሚዝ አንስቶ።

«ውሳድ ቢትማንያ።»

«ኧረ ያሰፋ ያለህ! አንድ የልጅ ሸሚዝ ሰማንያ ብር? » አሉ አዛዥ አይኖቻቸውን በጥፍ አውጥተው። ደመቀችም ደነገጠች።

«እሱ እንኩዋ ስምንት ብር ማለቱ ነው፤ ቢሆንም ውድ ነው» አለ በሻህ። ከዚያ ወደ ሁሴይን ዘወር ብሎ፣ «ከዚህ አይወርድም? » አለ። ሁሴይን አንገቱን ነቅነቀና «ጡሩ ናጋር ትፈለግኪ ጡሩ ጋጀብ ትከፈልኪ! ወላሂ ሁሴይን ናጋ ኩሉ ጡሩ እመይታ! » አለ በሻህን ትቶ ደመቀችን እያዬ። በያንዳንዱ እቃ ላይ ብዙ ተከራከረው ሁሴይን ካለው ምንም ያክል ቅናሽ የማያደርግ ስለሆነ ትተውት ወጡ።

«ከንግዲህ ወዲያ መዞር ከድካም በቀርም ምንም አይረባንም፤ ገብያው ከሞላ ጎደል ያው ያዬነው ነው» አለ በሻህ፥ ከሁሴይን ሱቅ እንደ ወጡ።

ባይሆን - የሚስብ የሚብሰውን በውድም ቢሆን ገዝተን ሌላውን መተው ነው እንጂ መቸስ ምን እናደርጋለን? » አሉ አዛዥ ማዘናቸውን በሚገልጽ አስተያየት ደመቀችን እዬተመለከቱ። ደመቀች አዛዥ ያሉትን ስትሰማ በጣም አዝና ልጅዋን እያዬች ዝም አለች። ተከስተ የሁሴን ሸሚዞች ሳይገዙ በመቅረታቸው ሊያለቅስ ምንም አልቀረው።

«እ - ! እስቲ ሁለት ያክል ሱቆች አሉ፤ መጀመሪያ እነሱ እንያቸው። እቃ መጥቶላቸው እንደሆነ - እንዲያውም እነሱ ይሻላሉ። ብቻ ባለፈው ሳምንት ምንም አልነበራቸው! » አለ በሻህ የደመቀችንና የልጅዋን ቅርታ እያዬ ዝም ብሎ ሲያስብ ቆዬና። ከዚያ ወደ «ጣሂር ሙደስር» ሱቅ ሄዱ። እዚያ ሲደርሱ ከሱቁ ማነስ ሌላ የሰው ብዛት «የመንቀሳቀሻ ያለህ! » ያሰኛል።

ጣሂር ሙደስር ካንደኛ ደረጃ ትምህርታቸውን አስጥሎ ያመጣቸውን ያስራ አራትና ያስራ ሁለት አመት ልጆቹን ቀኙና ግራ አድርጎ እሱ የመሸጫውን መሀከል ይዞ ያን ሁሉ ገብያተኛ ያስተናግዳሉ።

እነበሻህ ገብተው ተራ እስኪደርሳቸው ብዙ ከጠበቁ በሁዋላ ያስራ ሁለት አመቱ ልጅ የሚያስተናግድበት ክፍል ነጻ ስለሆነ፥ ወደዚያ ቀረብ አሉና «እስቲ አንድ መሀከለኛ ሻንጣና ለዚህ ልጅ የሚሆን - ሸሚዝ፥ ሹራብና - ሌላ ሌላም እንፈጋለን፤ መጀመሪያ ሻንጣውን አሳዬን፣ ሙስታፋ! » አለ በሻህ ተከሰተን አስቀድሞ ሙስታፋ

ተከተን አፍሮ አይኑ ማረፍያ እስኪያ። ትኩር አድርጎ አዩና «ሻንታውን ለሱ ነ - ው? » አለ፥ ‹ነ ን በረዢሙ አዚሞ።

«አዎ፤ ለሱ ነው» አለ በሻህ።

ከዚያ ሙስተፋ መሰላሉን ሻንጣዎች በተራ ወደ ተደረደሩበት ሳብ አድርጎ በዚያ እዬሮጠ ወጣና ሁለት መጠነኛ ሻንጣዎች ይዞ ተመልሶ ሁለቱንም በዬተራ እዬከፈተ ውስጣቸውን ካሳዬ በሁዋላ እንደ ገና ዘግቶ የህጻን አካሉ ሊደርስ እስከሚችልበት ድረስ እዬተንጠራራ በትንሽ ጡጫው መታና «እኒያውላችሁ! አንስታችሁ ብትወረወሩውቸው በላያቸው ቆማችሁ ብትዘሉባቸው ‹ይበላሻሉ› የማይባሉ ለዘላለም እንዳማረባቸው የሚኖሩ ወርቅ የመሰሉ ሻንጣዎች! » አለ፥ በተባ አንደበትና በውነተኛ የነጋዴ አቀራረብ። አዛዢና ደመቀች የቀረቡላቸውን እቃዎች ትተው የዚያን ትንሽ ልጅ አነጋገር አቀራረብ እያዩ ይስቁ ጀመር።

«ቀልድ እንዳይመስላችሁ! የትም ብትሄዱ እነዚህን የመሰሉ ሻንጣዎች አታገኙም! » አለ ሙስታፋ።

«በል ስብከትህ ይብቃና ያንዱን ዋጋ ንገረን። አለ በሻህ።

«ሁለቱን አትገዙ - ም? እነዚህ የመጨረሻዎች ናቸው፤ ዳግመኛ የነዚህ አይነት ሻንጣ አይመጣ! »

«ግዴለም አንዱ ይበቃናል።»

«እኔ ለናንተ ብዬ ነው እንጂ ምን ቸገረኝ! የትኛውን ትፈልጋላችሁ! »

«ጅግራ ቀለሙ ይሻላል፤ እድፍ ይችላል» አለች ደመቀች።

«በል ዋጋውን ንገረን» አለ በሻህ።

«ስንት ትከፍላላችሁ? »

«አንተ ንገረን እንጂ! »

«የመጨረሻው - ሰላሳ ብር።»

«እባክህ አትቀልድ እውነቱን ንገረን! »

«እሌላ ጋ ካርባ ባነሰ ብታገኙ ምላሴን! እኛም አሁን በሰላሳ የምንሸጠው የተረፉት እነዚህ ብቻ ስለሆኑ ለማጣራት ነው፤ ወዲያውም ለናንተ ስለሆነ ነው! » ሲል አዛዥ ቀና ብለው እመስቀያው ላይ የተደረደሩትን ብዙ፤ የነዚያን አይነት ሻንጣዎች አዩና ይስቁ ጀመር። ሙስታፋም ያዛዥን አይኖች ተከትሎ ሄዶ ውሸቱን አዬና፣ ትንሽ እንደ ማፈር ብሎ ፍርጥም አለ። በሻህ ከሙስታፋ ጋር የጀመረው የውጣ - ውረድ ክርክር እንደማያዛልቀው ሲያይ ወዳዛዥ ዘወር ብሎ፥

«ግዴለም ጥሩ አጋጣሚ ነው፤ እስቲ እንቆይና አሁን፥ ከስድስት ሰአት በሁዋላ ገብያተኛው ቀለል ሲ፣ ከባለቤቱ ጋር ብንነጋገር ይሻላል» አለ።

እውነትም ትንሽ እንደቆዩ ስድስት ሰአት ሆነና ሱቁን ሞልቶት የነበረው ገብያተኛ ቀለል እያለ ስለ ሄደ በሻህ፣ ሙስተፋ ያቀረበለትን ጅግራ ቀለም ሻንጣ እንደ ያዘ፥ ወደ ጣሂር ሙደስር ቀረብ ብሎ፥ «ጤና ይስጥልም አቶ ጣሂር፤ እስቲ እባክዎ የዚህን ሻንጣ ዋጋ ይንገሩኝ፤ መጨረሻውን» አለ።

«መጨረሻ ዋጋው ሰላሳ ነው፤ ልጁ አልነገረ - ህ? » አለ ጣሂር ‹ረ› ን ዘለግ አድርጎ አዚሞ።

«እሱስ ነግሮናል፤ እውነት አልመስለን ስላለ ወደስዎ መጣን እንጂ! »

«ይሁን ሀያ ዘጠኝ! »

«እባክዎ እውነተኛውን ይንገሩኝ።»

«ቢሻው ሀያ ስም -! »

«መጨረሻውን? »

«ሀያ ሰባ አትወስዱ -? »

«ጭራሽ አልተቀራረብንም! »

«ግዴለ፤ ብሎት በሀያ አም - ስ! » በሻህ ምንም ሳይመልስ ዝም ብሎ አለመስማሙቱን ራሱን በመወዝወዝ ብቻ መግለጽ ሲጀምር፥

«እሺ በስንት ትገዙ? » አለ ጣሂር።

«አቶ ኑር ሀሰን በቸ መጡ? » አለ በሻህ፥ ለተጠዬቀው መልስ በመስጠት ፈንታ።

«ኑር ሀሰን? ማናቸው ኑር ሀሰን? እኔ ኑር ሀሰን የሚባል ሰው አላቅ! » አለ ጣሂር፥ በጣም ደንግጦ በሻህን ትኩር አድርጎ እያዩ።

«የበርበራውን ኑር ሀሰን መቸ አጡዋቸው? ለኔም ወዳጄ ናቸው።»

«እኔ አንተንም፥ እሳቸውንም አላውቅ! »

«አቶ ጣሂር፥እኔ ብዙ እቃ እገዛለሁ፤ ስለዚህ በደህና ዋጋ ይሸጡልኝ? »

«ከስሬ ልሸጥል - ህ? »

«ከሰው እንዲሸጡልኝ አልፈልግም፤ ሳያተርፉ እንዲሸጡልኝ እንኳዋ አልፈልግም፤ ብቻ ‹ከመጠን ያለፈ ትርፍ አይጠይቁኝ› ነው የምል! ምክንያቱም ይህ እቃ በስንት እንደሚገዛ ከየት እንደሚመጣ ማን እንዲያመጣው አቶ ኑር ሀሰንን ጭምር ይህን ሁሉ ዝርዝር ስለማውቅ ነው! » አለ በሻህ፥ ሰው እንዳይሰማው ወደ ጣሂር ጆሮ ቀረብ ብሎ።

«አንተ ቡዳ ሰው ነህ! ምን ምን ትፈልጋለህ? የምትፈልገውን ጻፍና ስጠኝ! » አለ ጣሂር፥ ከበሻህ በቀር ሌላ ሰው እንዳይሰማው ድምጹን ዝቅ አድርጎ። ከዚያ በሻህ የሚፈልጉትን እቃዎች ከደመቀች እዩጠየቀ፣ አራት ሸሚዞች አንድ በላይ የሚለበስ ሹራብ ሁለት ጥንድ የውስጥ ልብሶች ሁለት ጥንድ ጥቁርና ጠይም የቆዳ ጫማዎች አራት ጥንድ የግር ሹራቦች ሁለት ጥንድ የሌሊት ልብሶች ስድስት መሀረቦች አንድ መጠነኛ ሻንጣ በዝርዝር ጽፎ ሲሰጠው ጣሂር ልቡ እዩተሸበረ እቃዎችን ከያሉበት አጠረቃቅሞ አቅርቦ በጣም በርካሽ ዋጋ ሸጠለት። በሻህ ወደ ጣሂር ጆሮ ቀረብ ብሎ የነገረውን ከነገረው በሁዋላ፥ ያን ትግስት የሚያስጨርስ ክርክሩን ትቶ ጭራሽ ሌላ ሰው ስለሆነና ያን ሁሉ እቃ ከተመኙት እንኩዋ በጣም ዝቅ ባለ ዋጋ ሰለ ሰጣቸው አዛዥና ደመቀች ምክንያቱ አልገባቸው ብሎ የመገረም አይን ተለዋወጡ።

ከዚያ የገዙትን እቃ ሰብስበው በሻንጣው ከተው ጣሂርን አመስግነው ወጡና እዩተጫወቱ አራዳ ሲደርሱ «ኧረ - ! አሁንስ» አሉ አዛዥ፤ «አሁንስ ትንሽ አርፈን እህል የምንቀምስበት በቅርቡ የሚገኝ ቢሆን እወድ ነበር! ሽማግሌኮ ጭንቅ አይችልም! ከወጣቶች ጋር ገና በጥዋት የተጠመድሁ - ምንተ እፍረቴን ልወድቅ ነው! »

«በሞትሁት! ደከመዎ አባባ? » አለች ደመቀች፥ እውነት መስሎዋት። ያዛዥ አላማ በሳቸው ድካም አመካኝተው በሻህን ለመጋበዝ ነው።

«ሞልቶ! እዚሁ አስር እርምጃ ሳንራመድ መብል ቤት ብቻ ነው! » አለ በሻህ፥ መብል ቤት ወደ ሞላበት አገጩን እያመለከተ። ከዚያ ዶሮ፥ ማነቂያ ውስጥ «መገናኛ» ወደሚባል መብል ቤት ይዘዋቸው ሄደ።

መብል ቤቱ በሰው ጥቅጥቅ ብሎ ሞልቶ እንኳዋንስ ተጨማሪ ሰው የሚያስቀምጥ አንድ እግር የሚያስቆም ቦታ ያለ አይመስልም። የዚያን ሁሉ ሰው ጫጫታ ሁሉም ባንድ ላይ እንዲጮህ ታዝዞ የሚጮህ እንጂ፣ እስበሱ እዬተደማመጠ የሚነጋገር አይመስልም! ይልቁንም ያ ተሰብስቦ የሚንጫጫው ሁሉ ወንድ ብቻ ስለሆነ ደመቀች ፈርታ እግሮችዋ ወደ ሁዋላ ይስቡዋት ጀመር።

«አይዞሽ አትፍሪ የኔ እህት፤ ቤታችን ነው! እኔን ተከተሉኝ» አለና በሻህ ዳርዳሩን ይዞዋቸው አልፎ ወዳንድ ትንሽ ጉዋዳ አሰባቸው። እንዲያ ያሉት ጉዋዳቸው ምሳም ይሁን ራት እዬበሉ በጸጥታ ልዩ ጉዳይ መነገጋገር ወይም የሴት እንግዳ መጋበዝ ለሚፈልጉ ሰዎች የተሰናዱ ናቸው።

በሻህ፥ ወንበሮችን ከዬማእዘኑ ሰብስቦ ባንድ ጠረጴዛ ዙሪያ ደርድሮ እንግዶቹን አስቀመጠና ወጣ።

«ምን - ሁሉ ቤቴ ነው እባክሽ? ለካስ ‹ያራዳ ልጅ› ማለት እንዲህ እንደሱ ያራዳን ጉዋዳ ሁሉ በር ሳይመታ እንዲገባ የተፈቀደለት ማለት ነው! » አሉ አዛዥ፥ በሻህ ከወጣ በሁዋላ እንደ መሳቅ ብለው።

«እኔንም ገርሞኛል! ደግሞ በዬደረሰበት ትንንሾችን ልጆች ሳይቀር በዬስማቸው ማወቁስ አይገርምዎም? » አለች ደመቀች። ወዲያው ጥዋት ታዬ፥ የድካም ዋጋ ስለ መክፈል የተናገረው ትዝ አላትና «አባባ ጋሽ ታዬኮ ‹የድካም ዋጋ ትከፍላላችሁ› ሲል ሰምቻለሁ፤ ታዲያ - ስንት እንክፈለው? » አለች።

«እኔም ‹ይከፍሉሀል› ሲል ሰምቻለሁ፤ ብቻ እሱን አደለም፤ ሌላውን ያን ‹እንቢ› ያለውን ነው። ለዚህስ - አሁን ምሳውን ካበላነው አንድ ብር የሚበቃው ይመስለኛል። »

«ኧረ እንጃ! ‹አነሰኝ› ይል ይሆናል፤ አባባ! ወዲያውምኮ እሱ ባይኖር ኖሮ ብዙ ገንዘብ መክሰራችን አይቀርም ነበር፤ ምናልባት እንዲያውም - ምንም ሳንገዛ እንቀር ነበር! »

«እሱስ እውነትሽ ነው፤ ብቻ - ከሌሎች ያተረፍነውን ሁሉ ለሱ ሰጥተን ዞሮ ዞሮ ያው ኪሳራ እንዳይሆንብን እንጂ! »

«አይ ከዚያም ወዲህ! ሶስት ብር ብንሰጠው - ምን ይመስልዎታል? »

«ሶስትስ -» ብለው አዛዥ ሊናገሩ ያሰቡትን ሳይናገሩ በሻህ አንድ ቅብጢ አሳላፊ አስከትሎ ተመልሶ «በል ያለህን ሁሉ ንገራቸውና ጌታ የመረጡትን ይዘዙ» አለ። ከዚያ አሳላፊው እንደ ልማዱ ውዱን ርካሽ ተራውን ልዩ አስመስሎ፣ በሚያስጎመዥ ቁዋንቁዋው እቤት ያለውን የመብልና የመጠጥ ዝርዝር በቃል እንደ ተጠና ድጋም እንበለበለ!

«ቀይና አልጫ ወጥ፣ ሁሉም እንደ ጌታ ልጅ ወተት ብቻ እዬተመገቡ በጥንቃቄ አድገው፥ ዛሬ ጥዋት ከታረዱ ጥቦቶች፣ የወጥ ቤቶች አለቃ ራሱ የሰራው! ከጌቶች ከራሳቸው ያትክል ቦታ ሙሽራ ሙሽራውን ብቻ ተቀንጥሶ በማረቀ ንጥር ቅቤ አብዶ የተሰራ ጎመን! አንድ «ያልታጠበ እጅ አይንካኝ» የሚል ያዳ ነጭ እንጀራ! ይህ ሁሉ ባንድ ላይ ላንድ ሰው፥ ሁለት ብር ብቻ!! መጠጥ ለሚፈልግ ካገው ምድር ማር ብቻ የተጣለ አንዱን ሲጠጡት ሙሉ አገው ምድርን የገዙ የሚያስመስል በሰባት ማጣሪያ ሰባት ጊዜ የተጣራ ጠጅ ግሩም የሆነ ጠላ አለ። ጠጁ በብር አራት ብርጭቆ፣ ጠላው በብር ስድስት ነው! » አለ አሳላፊው፥ ለደንቆሮ ይናገር ይመስል ድምፁን ከፍ አድርጎ።

ደመቀች፥ መብልና መጠጥ አሰናድተው የሚያቀርቡ ሰዎች፥ መሰናዶዋቸውን ተጋባሾ ሲያመሰግኑላቸው እንጂ፥ ራሳቸው እንዲያ አድርገው ሲያመሰግኑ ለጀመሪያ ጊዜ መስማትዋ ስለሆነ፣ ልታግደው የማትችል ሳቅ መጥቶባት፥ እንዳትስቅ ነውር መስሎዋት እንገትዋን ደፍታ አፍዋን፥ በኩታዋ አፍና ትጨነቅ ነእብር።

«በል አሁን የቆጠርኸውን መብል ሁሉ ለሁላችን ያገው ምድሩን ማር ጠጅ ለሶስታችን ለልጁ - ሎሚናት አለ እንደሆነ አምጣልን» አሉ አዛዥ። አሳላፊው ከወጣ በሁዋላ በሁኔታው ሁሉም ይስቁ ጀመር።

የቀልድ በሽታ ያለበት ልጅ ነው፥ ‹ተው› ቢሉትም አይሰማ» አለ በሻህ።

«መልካም ነው እንጂ፤ ያጫውታል! » አሉ አዛዥ።

የታዘዘው ሙብልና መጠጥ ቀርቦ እዬተመገቡ ሲጫወቱ፥ እዚያ ሙብል ቤት ከገቡ ጀምሮ በሻህ ሲያደርግ ያዩት ሁሉ ከቤት ጋር ግንኙነት ያለው የሚያስመስል ስለ ነበረ -

«የዚህ ሆቴል ባለቤት ዘመድህ - ናቸው? » አሉ አዛዥ።

«የስጋ ዘመድ» ማለትዎ እንደሆነ አደሉም፤ ብቻ አባታችን ናቸው»

«እንዴት? » አሉ አዛዥ የበሻህ አነጋገር ትርጉም ስላልገባቸው።

«ይህ ቤት በጠላት ወረራ ጊዜ አርበኞች ከዬጫካቸው የውስጥ አርበኞች ከዬቤታቸው ጫማ ጠራጊዎችና ወሮበላዎች ከዬበረንዳቸውና - ከዬስርቻቸው ባንድ ላይ ተገናኝተው ገንዘብ ያለው ከፍሎ፥ የሌለው ካለው የተረፈውን ፍርፋሪ በልቶ ጠግቦ፣ ተጫውቶ አርበኞች በዬክፍላቸው የሚደረገውን ትግል አውርተው የውስጥ አርበኞች የሚያውቁትን የጠላት ምስጢር፥ ያገኙትን መሳሪያና ጥይት ሰጥተው ይለያዩበት የነበረ ቤት ነው። ስለዚህ፣ እኔና በዚያ ጊዜ እንደኔ ወሮበሎችም ጫማ ጠራጊዎችም የነበርነ ያራዳ ልጆች ሁሉ፥ ገንዘብ ስናገኝ ከፍለን ስናጣ ካላቸው የተረፈውን ፍርፋሪ የስህንም የድስትም ጥራጊ በልተን፥ ክፉ ቀን ያሳለፍንበት ቤት ስለሆነ፣ ‹ቤታችን› እንለዋለን፤ ባለቤቱ አቶ ማንደፍሮ ባንቴንም ‹አባታችን› እንላቸዋለን! »

«ይገርማል! እና - ባለቤቱ አሁን በይህወት አሉ? »

«አሉ እንጂ! አሉ። ኧረ ገና ‹ብዙ ጊዜ ይኖሩልናል› ብለን ተስፋ እናደርጋለን! አቶ ማንደፍሮ ባገራችን ትምህርት በጣም የላቁ፣ የውጭ ቋንቋዎች የሚያውቁ በጣም የተማሩ ሰው ናቸው። ከጠላት ወረራ በፊት በትምህርት ከዚያም፥ እዬተላኩ ያልደረሱበት የፈረንጅ አገር የለም። በጠላት ጊዜ ታስረው ከተፈቱ በሁዋላ ይቺን ሆቴል ከፍተው ለብዙ ሰው ቀን አወጡ። ሆቴልዋን ሲከፍቱ ‹መገናኛ› ብለው ሰይመዋት ስለ ነበረ ጣሊያኖች ‹ምን ብታስብ ነው እንዲህ ያለ ስም ያወታህለት› ብለው ዘግተውባቸው ነበር። ሁዋላ ባማላጅ ሀይል፣ ስም እንዲለውጡ ተደርጎ ተከፈተችላቸው።»

«አንተ ታዲያ - » አሉና አዛዥ ወሮበላ፣ ወይም ጫማ ጠራጊ የነበረ መሆኑን መጠየቁ ‹ያስቀመው ይሆናል› ብለው ሰግተው መልሰው ዝም ሲሉ በሻህ አሳባቸውን ቶሎ ከግንባራቸው አነበቡና -

«አዎ፤ ያን ጊዜ እኔ በዬተራ ጫማ ጠራጊም ወሮበላም ነበርሁ። ከጠላት በፊት በሚሲዮን ትምህርት ቤት እማር ነበር። አባቴ ማይጭው ሄዶ ሲቀርና እናቴም ባሙቱ ጥላኝ እሱን ስትከተል፣ ምንም እንኳዋ ትምህርቴን ባልጨርስ ያው የተማርሁት ያክል ረድቶኝ ላጭር ጊዜ ያንድ ጣሊያን ነጋዴ የሂሳብ ረዳትና መዝገብ ገልባጭ ሆኘ ሆዴን ደህና ተመችቶት ነበር። በመጠኑ የወር ደሞዝም ነበረኝ። ብቻ እሱ አሁን እንዳልሁት ላጭር ጊዜ ነው፤ ትቸው ወጣሁ።»

«ታዲያ ከተመቸህ - ለምን ትተኸው ወጣህ? »

«ሆዴን ነውኮ ‹ተመቸው› ያልሁ አባቴ፥ እኔን አደለም! »

«ደሞ ባንተና በሆድህ መካከል ልዩነት አለ? » አሉ አዛዥ እዬሳቁ።

«እኔም ሆዴና እኔ ልዩ መሆናችነን የተረዳሁ ያን ጊዜ ነው! »

«እንዴት እባክህ? »

«ያ ጣሊያን፥ ሆዴን እንደ ውሻ እዬሞላ እንደ ውሻ እንጂ እንደ ስው እንደማይመለከተኝ ሳይ፣ ልቤ ተቀይሞ፥ መንፈሴ ታውኮ ‹ሁሉስ ቢቀር ምናባቱ!› ስል ከሌላ ወገን የምበላው ማካሮኒና የምጠጣው ቪኖ በመሀከል ገብቶ ስንቅር ይልና፣ ወደ ማመንታት ይመራኛል። ያን ጊዜ ሆዴ የራሱን መሙላት እንጂ የኔን ውርደት የኔን ማዘንና መበሳጨት ከጉዳይ የማይጽፍ መሆኑ ተረዳሁ። ስለዚህ ለካስ ሆዴና እኔ ልዩ ነን! ለካስ ሆዴ የኔ ሲመስለኝ ባእድ ነው› ብዬ ታዝብሁት።

«መቸም ሆድ ከባለቤቱ ልዩ መሆኑን ገና ዛሬ ካንተ መስማቴ ነው! ብቻ እስቲ ይህም ሁሉ ይሁን፥ ሆድህን እንዲያ እስከ መታዘብና ‹የኔ አደለህም› ብለህ መካድ ድረስ የተመረርህ ያ ጣሊያን ምን ቢያደርግህ ነው? »

«ጣሊያኑ በተለይ በኔ ላይ ያደረገው ይልቁንም ካለፈ በሁዋላ መለስ ብሎ ሲያዩት፣ ይህን ያክል የሚያስመርር አይመስልም። ይንቀኛል፣ ይጸየፈኛል፤ ይጠላኛል። ለምሳሌ የጣሊያን ልጆች የሚለብሱትን አይነት ልብስ ወይም ጫማ በገንዘቤ ገዝቼ ስለብስ ወይም ሳደርግ ያዬ እንደሆነ ልክ ጣሊያንነቱን እንደ ወሰድሁበት ሁሉ አይኑ ደም እስኪለብስ ይቆጣል! ታጥቢ ጠጉሬን ተከርክሜና አበጥሬ ነቃ ብዬ ሲያየኝ ያኮርፍና አያነጋግረኝም። ስለዚህ በውነቱ በኔ የደረሰው እንዲህ እንዲህ ያለ ከስሶ የማይካሱበት ብቻውን ተሰብስቦ ሚዛን የማይሞላ ጥቃቅን ነው። ነገር ግን ይህን በኔ

የደረሰውን ሌሎች ጣሊያኖች በሌሎች ኢትዮጵያውያን ላይ ከሚያደርጉት ገደል ገደል የሚያካክል በደል ጋር ባንድ ላይ ደምረው ሲያዩት፣ በኔ የደረሰው ጥቃትን በሌሎች የደረሰው ትልቅ እብደል ዘርፍና ቅርንጫፍ መሆኑን ሲረዱት ዛሬ የደረሰብኝ ጥቃትን ነገር ለሚደርስብኝ ትልቅ በደል ዋዜማ መሆኑ በርግጥ ሲታወቅ፥ ያን ጊዜ ያው ጥቃቅኑም ሊሸከሙት የማይቻል ከባድ ይሆናል። ይልቁንም አንድ ጊዜ ‹ተንቁያለሁ፥ ተጠልቻለሁ ተብድያለሁ› በሚል ስሜት ልብ ከቆመና ጊዜ ልቤ ቆመና፣ መንፈሴ ነቃና እስከዚያ ድረስ አይቸው ሰምቸው የማላውቀውን ክፉ ነገር ሁሉ አይ፣ እሰማ ጀመር! በወጣሁ ቁጥር በዬጥቃቅኑ ምክንያት ኢትዮጵያውያን ሲሰደቡ፥ ሲመቱ፣ ሲታሰሩ፥ ሲገደሉ፥ የማላይበትና የማልሰማበት ቀን ጠፋ። ከዚያ ወዲያማ ምን ልበልዎ! እንዲያው ሙሉ አካሌ ለመልካም ነገር ተዘግቶ ክፉ ነገር ብቻ ግፍ ብቻ አመጽ ብቻ ለማየት፣ ለመስማትና ለማሽተት እንደ ተከፈተ ሁሉ፥ የወራሪዎችን ግፍና አመጽ ብቻ ይታዬኝ ይሰማኝ ይሸተኝ ጀመር። ስለዚህ ሆዴን ድል አድርጌ ሁሉንም ጣጥዬ ወሮበላኔትን ገባሁ! »

«ቆዩኝ እስቲ! መቸም - ባንተ የደረሰው በደል ‹ቢከሰሱ የማያስከስስና ተሰብስቦ ሚዛን የማይሞላ ነው› ብለሀል፥ ታዲያ ባንተ የደረሰው ሳይሆን በሌሎች ሲደርስ ያዬኸው በደል ነው - ከምኞት ጦም አዳርን ያስመረጠህ ማለት ነው? » አሉ አዛዥ አፋቸውን ከፍተው የበሻህን ወሬ ሲሰሙ ቆይተው።

«አ - ይ፥ ይህን ያክልም ጻድቅ አያድርጉኝ፥ አባቴ! ‹በኔ የደረሰብኝ ግፍ በሌሎች ሲደርስ ካዬሁትና ከሰማሁት ጋር ሲመዛዘን ትንሽ ነው› አልሁ እንጂ፥ ‹እኔ ምንም ሳልሆን፥ ሌሎች ስለ ተበደሉ ምኞቴን ትቼ ወጣሁ› ማለቴ አይደለም! ወዲያውም - የመንፈስ ጸጥታና የህሊና እረፍት በሌሉበት ሆድ ስለ ሞላ ብቻ ምኞት ሊኖር አይችልምኮ፥ አባቴ! ቅድም እንዳልሁዎ ያ ጣሊያን እንደ ሰው ሳያዬኝ፣ እንደ ትል ሲጸየፈኝ ሲንቀኝ እንደ ጣልያን ልጆች ለበስሁ ብቻ ሲያኮርፈኝ ሳይ መንፈሴ ታወከ፣ ህሊናዬ እረፍት አጣ። ስለዚህ ይህ ሁሉና በሌሎች ላይ ሲደረግ ያዬሁት ትላልቅ ግፍ ባንድ ላይ ሆኖ - ወደ ወሮበላነት ያባረረኝ!

«እንጂ! ይሆናል። እንደኔ እንደ ሞኙ ቢሆን ግን - ቅድም እንዳልኸው ከስሶ የማይካሱበትና ‹ይህን ተበደልሁ› ብሎ ስም የማይሰጥት በደል ተበደል ተቆጥሮ ወደ - ወሮበላነት የሚያባርር አይመስለኝም! » አሉ አዛዥ እንደ መሳቅ ብለው።

«በደል ወይም ግፍ ‹አገሌ› ተብሎ የሚጠራበት ስም ስለሌለው በደል ወይም ግፍ መሆኑ አይቀርም፣ አባቴ! እንዲያውም ባጠቃላይ ያራዳ ወሮበላ ሁሉ ‹አገሌ› ተብሎ የሚጠራበት ስም የሌልው ግፍ ወይም በደል ያባረረው ነው! እያንዳንዱን ወሮበላ ይዘው ‹ምን ግፍ ተሰርቶብህ ነው ወሮበላ የሆንህ?› ብለው ቢጠይቁት የሚነግርዎ የተለያዩ ምክንያት ‹አበጀህ› የሚያሰኝና ጎልቶ የሚታይ ግፍ ላይመስል ይችላል። እንዲያውም ይግረምዎና ላብዛኛው ወሮበላ የተሰራበት ግፍ ምን እንደሆነና ማን እንደ ሰራበት ለራሱም ግልጽ አደለም! ብቻ ሁሉም ግፍ ያባረረው በግፍ ላይ የሸፈተ መሆኑን አእምሮው ሳይሆን ደመ - ነፍሱ እዬነገረው ግፍን አጥብቆ ሲጠላ ግፍን በያገኘበት ሲቃወም ያገኙታል።»

«እንዴት? የተሰራበት ግፍና ግፍ የሰራበትን ካላወቀ እንዴት ‹ግፍ ተሰራብኝ› ይላል? ማነንስ ይወቅሳል? »

«አሆ - ! ይህ በጣም አስቸጋሪ ጥያቄ ነው! » አለ በሻህ። «አዩ? » አለ ደገመና። «አዩ? ለምሳሌ አንዱ ከማያውቃቸው እናትና አባት ተወልዶ አራዳ ተጥሎ ሲያገኝ እዬለመነ ሲያጣ እዬሰረቀ ያደገ ነው። ሌላው ከሚያውቃቸው እናትና አባት ቢወለድም ራሱን ሳይችል ጥለውት ይሞቱና እድሜ ላራዳ እዬለመነም እዬሰረቀም ያደገ ነው። ደግሞ ሌላው እንኩዋንስ ልጅ ሊያሳድጉ ለራሳቸውም ይልሱት - ይቀምሱት ካጡ ድሆች ይወለድና ገና ለመለመን ያክል አፉን ሲፈታ ‹ሂድ ራስህን አውጣ!› ብለው ያስወገዱት ነው! እንግዲህ፣ በዚህና ይህን በመሳሰለው ልዩ ልዩ ሁኔታ ወሮበሎች የሆኑ ያራዳ ልጆች የተሰራባቸው ግፍ እንኩዋንስ ለሌላው ለነሱም ለራሳቸው ግልጽ ብሎ በጉልህ ላይታያቸው ይችላል! ግፍ የሰራባቸውም ሰው ይሁን እግዚአብሄር መፍረዱ ያስቸግር ይሆናል! ብቻ እነሱ ሳያጠፉ የሚኖሩትን አይነት ኑሮ እንዲኖሩ፣ ‹ይግባኝ› የሌለበት ፍርድ የተፈረደባቸው መሆናቸው ደመ - ነፍሳቸው እዬነገራቸው እንዲህ ባለው የግፍ ፍርድ ላይ ሸፍተው ግፍ የሚሰራ ሲያዩ ለመቃወም ግፍ የተሰራበት ሲያዩ ለመርዳት ቀድመው ይገኛሉ! »

በሻህ የተናገረው እጅግም ግልስ ስላልሆነላቸው፣ አዛዥ ንግግሩን ትንሽ በትንሽ ወደ ሌላ ለመምራት አስበው - «ይገርማል! ታዲያ ያራዳ ልጅ ሁሉ ጣልያኖች እንዲህ - እንዳንተ ይጠላ ነበር ማለት ነው? » አሉ።

«እንዴታ! ብቻ ያራዳ ልጅ ጣልያኖችን የጠላው በጣሊያንነታቸው ሳይሆን ያገር ፍቅር ምን መሆኑን አውቆ ሳይሆን ቅድም እንዳልሁት ይሰሩት በነበረው ግፍ ነው። ምናልባት እስዎም እንደሚያውቁት በንግሊዝና በኢትዮጵያ የጦር መኮንኖች መሀከል የሆነው ግጭት ለዚህ ምሳሌ ሊሆን ይችላል።»

«በንግሊዝና በኢትዮጵያ መኮንኖች መሀከል ግጭት ሆኖ ኖሮዋል? እንግሊዞች የኛ ረዳቶች አልነበሩ? »

«እኛን ወይስ ራሳቸውን ለመርዳት መሆኑን እንጃ እንጂ፣ ጣሊያንን እምቃወማቸው እውነት ነው። ብቻ ጣልያኖች ቢቃወሙም ለክፉ ስራቸው ለንቀታቸው ‹ወራሾች እንሁን› አላሉ ከኢትዮጵያ መኮንኖች ጋር ግጭት ደርሶ ነበር። አዲስ አበባ ተቀምጠው እንዴት ሳይሰሙ ቀሩ? »

«ሳልሰማ የቀረሁ እንኩዋ አይመስለኝም፤ ብቻ ባለ ስራ ስለሆንሁ ሌላ ሌላውን ሳስብ እሱን ባሳቤ አላቀዬሁት ይሆናል። እንዴት ኖሮዋል? »

«ጣሊያኖች ለቀው እንግሊዞች እንደ ገቡ፣ እነሱም እንደ ጣሊያኖች ኢትዮጵያውያንን ለመጸየፍ እነሱም፣ ቦታ ለይተው ኢትዮጵያውያንን ‹ወዲህ አትድረሱ ከዚያ ተመለሱ› ለማለት ቃጡ። ያንጊዜ እንደሚያውቁት ከዬደኑ ከዬስደቱና ከዬስር፣ ቤቱ የተመለሰው የኢትዮጵያ ሱታ ሱታ የጦር መኮንን፣ ገና ያገር ፍቅርና የክብር ስሜት በዬልቡ እዬፈላ የሚያስበርድበት አጥቶ ይቅበጠበጥ የነበረበት ጊዜ ነው! ታዲያ ያንጊዜ በርዳታ ስም የመጡ እንግዶች ለገዛ ቤቱ ‹እንግዳ እናርግህ› ቤቱን ይዘው ‹እጥግ ይነጠፍልህ› ለማለት ሲቃጡ እዬና፣ ‹አካኪ ዘራፍ!› ብሎ ደንፍቶ ተነሳ! አየ - ያንጊዜ ያራዳን ልጅ ባዩ አባቴ! ያንጊዜ ጫማ ጠራጊ የጫማ መጥረጊያውን ደረጃ አዳሪ የበሀር ዛፍ መንደውን እንደ ጎራዴ እዬመዘዘ በሰው ቤት ገብቶ ባለቤቱን ጥገኛ ሊያደርግ የሞከረውን ጥጋበኛ እንግዳ ሊቀጣ ከሱታው መኮንን ጎን ተሰልፎ መጣልዎታ! » አለ በሻህ፣ እያንዳንዱ ቃል ካፉ ሲወጣ ያንጊዜ እዬፈከሩ ለግጥሚያ ከተሰለፉበት መኮንኖችና ወሮበሎች መሀከል እንደ ሆነ ሁሉ ትከሻዎቹ ወደ ላይ ነፋ አይኖቹ ሰፋ እያሉ።

«ታዲያ በምን አለቀ እባክህ? » አሉ አዛዥ ከደመቀች ጋር ሁኔታውን እያዩ ሲስቁ ቆይተው።

«ምን - ከዚያ ወዲያማ፣ ያገርዎ ልጅ ለጠላቱ የማይቀመስ፣ መራራ ኮሶ መሆኑ ሲታወቅ የታለመው ከሸፈ፣ የተቃጣው ታጠፈና፣ ሰላም ሆነ! ወዲያው እንደሚያውቁት እንግሊዞች ምንም ያክል ሳይቆዩ ለቀው ሄዱ፣ ቤትም ባለቤትም ሆነ! » አለ በሻህ የግጭቱን ወሬ ቸርሶ የሰላሙን ሲጀምር ፊቱ ትንሽ በትንሽ ከሞቅታ ወደ ቅርታ ሲለወጥ እዬታዬ። «አሁን እንኩዋ ከመንገድ ወጥቼ ይህን ያክል የለፈለፍሁት» አለ አንገቱን ደፍቶ፣ ትንሽ ዝም ብሎ ከቆዬ በሁዋላ። «አሁን ይህን ያክል የለፈለፍሁት ያራዳ ልጅ ጣልያኖችን የጠላ በጣሊያንነታቸው ሳይሆን፣ ይሰሩት በነበረው ግፍ መሆኑንና ግፍ፣ ሰራውን ሁሉ የሚጠላ መሆኑን ለማስረዳት ብቻ ነው። ዛሬም ቢሆን በኢትዮጵያውያን መሀከል ግፍ የሚሰራ ቢኖር፣ ከጣሊያኖች ያላነሰ እንደሚጠላው ይመኑኝ። ግፍ ኢትዮጵያዊ ስለ ስራው ግፍ መሆኑ አይቀርም፥ አባቴ! »

«እንዴታ! እንዲያውስ - ወገንን ወገን የሚያሰኘው ስራው ነው እንጂ ሌላ ምን አለ? » አሉና አዛዥ የበሻህ ወሬ አሰረስቶዋቸው የነበረውን ጠጅ አንስተው ወዳፋቸው ሲወስዱ ጣሂር ሙደስር ባንድ ሻንታ ላይ ያን ያክል ሲከራከር ውሎ በሻህ ቀረብ ብሎ ካነጋገረው በሁዋላ ድንገት የተለወጠው ትዝ ስላላቸው፥ ብርጭቆው ከንፈራቸውን ሳይነካ መልሰው አስቀምጠው፥ «አንድ ነገር! » አሉ። «አንድ ሲከነክነኝ የቆዬ ነገር - ምናልባት ምስጢር አደለ እንደሆነ ልጠይቅህ እባክህ? »

«ምን? መቸም ምስጢር መሆን አለመሆኑን የማውቀው ከሰማሁት በሁዋላ ነው።»

«ያ፣ እቃውን የሸጠልን ነጋዴ መጀመሪያ ያን ያክል ችክ ብሎ ሲከራከር ቆይቶ፣ ቀረብ ብለህ ካነጋገርኸው በሁዋላ ጭራሽ ተለውጦ ሌላ ሆኖ የገዛነውን ሁሉ እንዲያው - ከተመኘነው እንኩዋ ባነሰ ዋጋ ነው የሸጠልን! ምን ብትለው ነው እንዲያ የገረመ? »

«እ - ! እውነትም ምስጢር ነው። ብቻ ብነግራችሁም ግዴለ። ያ ያያችሁት፥ የጣሂር ሱቅ የሞላው የውጭ አገር እቃ፣ አብዛኛው ተደብቆ የገባ ‹አጉራ ዘለል› እቃ ነው። እኔና አንዳንድ ጉዋደኞች ጣሂር ባጉራ ዘለል እቃ መነገዱን ብቻ ሳይሆን ከየት እንደሚመጣለትና ማን እንደሚያመጣለት ጭምር እናውቃለን። ለምሳሌ - ‹የበርበራው ኑር ሀሰን መቸ መጡ?› ያልሁት እቃ የሚያመጡለት እሳቸው እንደሆኑ ማወቄን ለመግለጽ ነው። እና - ይህን ነው የነገርሁት።»

«ኧረ ያሰፋ ያለህ! እና የተሰረቀ እቃ ነው የገዛን? » አሉ አዛዥ፣ ያኔውኑ በሌብነት የሚያዙ መስሎዋቸው በጣም ደንግጠው። ደመቀችም ደነገጠች።

«ቀረጥ ሳይከፈልበት የገባ ነው» ማእልቴ ነው እንጂ የገዛው እቃ ነውኮ! ስለዚህ ገዢዎችን የሚያሰጋ አደለም፤ አይዞዎ! » አለ እዮሳቀ።

«አየ ጉ - ድ! ምን የተረገመ ነው? እባክህ! ህግ ሳይተላለፍ ቤንግድ ምን ቸገረው ነበር? »

«ህግኮ ሰው ሁሉ ዘንድ የሚከበረው የሁሉን መብት በትክክል እስከ ጠበቀ ድረስ ነው፥ አባቴ! ያለዚያ የተጠቀሙበት ብቻ ይታዘዙታል፤ የተጎዱት ያምጹበታል! ጣሂርና ግብራበሮቹ ‹መብታችን በህግ አልተጠበቀልንም› ብለው ህገ ወጥ ስራ ቢሰሩ አይግረምዎ! እኔ ደጋፊያቸው ነኝ። ስለዚህ ነው ህገ ወጥ ስራቸውን እያወቅሁ ለባለስልጣኖች የማልገልጽባቸው! »

«ህግ ማክበር መልካም ነው፥ ልጄ! ህግ ካልተከበረ እንኩዋንስ ለንብረታችን ለህይወታችን ምን ዋስ አለው? »

«የሁሉን መብት ትክክል የሚጠብቅ ህግማ እርስዎ እንዳሉት በሁሉም መከበር አለበት። ነገር ግን ግፈኖችንና ተንኮለኞችን ብቻ የሚጠብቅ ሲሆን፥ እሱም ግፈኛ እሱም ተንኮለኛ መሆኑ ነውና፥ እንዲያ ባለው ህግ ላይ የሚያምጽ ቢኖር አጥፊ አደለም፤ አልሚ ነው! ሊመሰገን እንጂ ሊነቀፍ የሚገባው አደለም! ለምሳሌ፣ እግዚአብሄር በጣሂር ሙደስር አድሮ የሚሰራውን ህገ ወጥ ስራ እንዲሰራ ባያደርግ ኖሮ ዛሬ የገዛነው እቃ ሁሉ ለመግዛት ይቺን እቴን ከዚህ ሁሉ ውበትና ደም ግባትዋ ጋር ሸጠን እንኩዋ መክፈል እንችል ኖሮዋል? » አለ በሻህ እንደ መሳቅ ብሎ፣ ደመቀችን የጎድን እዮተመለከተ። ደመቀች ፍርጥም ብላ አንገትዋን ደፋች።

«እስቲ ቆይ እባክህ፣ አንድ ያልገባኝ ነገር አለ! ‹ህጉ ሁሉን እኩል አይጠብቅም› ያልኸው አልገባኝም። እኔ የሰማሁት ‹ህጉ ምንም ልዩነት አያረግም ሁሉን እኩል ይጠብቃል› ሲባል ነው። እንዲያውም ‹ደሀና ሀብታም እኩል ይሁን› ስለ ተባእል ነው ብዙ ትላልቅ ሰዎች ሲያማርሩ የምሰማ! »

«አዎ፣ ህጉ ልዩነት አያረግም፤ ልዩነት ባለማድረጉም ሁልጊዜ ልዩነት እንዲኖር ያደርጋል» አለ በሻህ ያሽሙር ሳቅ እዮሳቀ።

አዛዥ ግራ ገብቶዋቸው ምንም ሳይናገሩ ዝም ብለው አተኩረው ያዩት ጀመር።

«አዬ አባቴ? » አለ በሻህ፣ አዛዥን ግራ ሲገባቸው አዬና መሳቁን ትቶ ፊት ትንሽ በትንሽ ክርር ወደ ማለት እዬተለወጠ። «አዩ? ለንግድም ሆነ ለሌላ ልዩ ልዩ ዘመናዊ ስራ ኢትዮጵያውያን አዲስ መጪዎች ናቸው። በዚህ ሁሉ ስራ ደርጅተው ቦታውን ይዘው የቆዩ የውጭ አገር ሰዎች ናቸው። አሁን ኢትዮጵያውያን ‹እንግባ› ቢሉ፣ ቀድመው ቦታውን ይዘው፣ ደርጅተው የቆዩት ባእዶች በሩን ግጥም አድርገው ዘግተው ‹አትገቡም› አሉዋቸው! ኢትዮጵያውያን ላገራቸው ሀብት ላገራቸው፣ ስራ ሙሉ ባለቤቶች መሆናቸው ቀርቶ ተካፋዮች እንኳዋ እንዳይሆኑ በር ተዘጋባቸው! ህጉ ስር ሰዶ፣ ደርጅቶ የቆመውና ለግሩ መቆሚያ ያጣው ብርቱውን ደካማው የተንኮሉ ሊቅና ተማሪ ሁሉም ባንድ ላይ ተደባልቆ እንዲታገልና ያሸነፈ ብቻ ሰርቶ እንዲበላ የተሸነፈ እንዳይሰራም እንዳይበላም ፈረደ! ምን ማለት ነው? ቦታውን ገብያውን ብርቱዎ እንደ በረቱ ደካሞች እንደ ደከሙ እንዲቀሩ ማለት ነው! በሌላ አነጋገር ኢትዮጵያውያን ላገራቸው ሀብትና ላገራቸው ስራ ተካፋዮች እንኳዋን እንዳይሆኑ በነሱ ላይ የተፈረደ ፍርድ ነው! አዩ! ለውድድርም ለፍልሚያም ለትግልም፣ ስራት አለውኮ! ተወዳዳሪዎች ተፋላሚዎች ታጋዮች መሳሪያ ያላቸው ተመጣጣኝ የሆኑ መሆን አለባቸው? ባልተመጣጠኑና ተመጣጣኝ መሳሪያ በሌላቸው ተወዳዳሪዎች መሀከል ውድድር እንዲሆን የሚያዝዝ ህግ አደለም፤ የብርቱዎችን ጥቅም ብቻ የሚጠብቅ የብርቱዎች ጋሻ ነው! »

«ቆይ እስቲ! አሁን በስራና በንግድ እንዲሁም ይህን በመሳሰለው፥ በሌላው ስራ ሁሉ ኢትዮጵያውያኖችን የሚረዳና የሚያስቀድም ህግ የለም? » አሉ አዛዥ ገርሞዋቸው።፡

«ምን ርዳታ! ደግሞ የምን ቅድሚያ! »

«ኧረ ያሰፋ ያለህ! ታዲያ ከጣሊያ ጋር ምን አዋጋን? እሱስ ቢሆን - ‹የኢትዮጵያን ህዝብ አርጄ ልብላ› አላለ! ሀብቱንና ስራውን ከኛ ቀምቶ ለራሱ ህዝብ ሊያደርግ ስለ ፈለገ አልነበረም የተዋጋነው? » አሉ አዛዥ ባቁዋራጭ መንገድ ነገሩን አጠቃለው።

«ነበራ፣ አባቴ! ነበር! »

«ወይ ግሩ - ም! እንግዲያስ እነዚያ እነ - ጣረሞት ነው? ማነው ያልኸው ያ ኢቃ የሸጠልን! »

«ጣሂር ሙደስር» አለ በሻህ፥ እንደ መሳቅ ብሎ።

«አዎ እሱ! እንግዲያስ በነሱ አይፈረድም! » አሉና አዛዥ አንገታቸውን ደፍተው ሲያስቡ ቆይተው «እንጃ! እንዲያው - ማመኑኮ ያስቸግራል! » አሉ እንደገና በሻህን አተኩረው እያዩ።

«እንዴት ማመኑ ያስቸግራል? መቸም የሰሙትን እንደሆነ እንጂ ባይን ያዩትን ማመን አያስቸግርም! ለምሳሌ ያክል፣ ዛሬ ይህ እቃ ለመግዛት ስንዞር በመጨረሻ፣ ከጣሂር ሙሰደር ሱቅ እስከንገዛ ድረስ ያዬናቸው ሱቆች ሁሉ የግሪኮች የህንዶች፣ ያረቦች፣ አደሉም? እኒህ ካዬናቸው ሌላ፣ ከነዚህ ካራዳ ጀምሮ እስካዲስ ከተማ፣ ከዚያ በዬጠቅላይ ግዛቱ የሚታዬው ዋና ዋና ሱቅ ሁሉ ከዚያ አለፍ ስንል ያምጨና የላኪ ስራ የቤትና የመንገድ ስራ የጋራጅና የትናንሽ ፋብሪካ ስራ እንዲያው በጠቅላልው ለዘመናዊ ኑሮ የሚያስፈልገው ስራ ሁሉ ያለው በውጭ አገር ሰዎች እጅ አደለም! »

«ይህ እውነትም የሚያስገርም ነው! ካንድ ባእድ ተዋግተውን ያስቀረነውን ሀብትና መብት - ያውም ሳንገደድ - በፈቃዳችን ለብዙ ባእዶች አከፋፍለን ስንሰጥ አያገርምም? በውነት የሚያስገርም ነው! » አሉ አዛዥ ጥያቄያቸውን ራሳቸው መልሰው።

«እንደሱ ነው፤ ግሩም አድርገው አመጡት፣ አባቴ! » አለ በሻህ ጠጁን ጨልጦ ብርጭቆውን ሲያስቀምጥ።

ከዚያ አዛዥ የኪስ ሰአታቸውን አውጥተው አይተው፣ «ኡ - ! ጊዜ እንዴት ያልፋል አባካችሁ? ሳይታወቀን ሰአቱ እኛን እዚህ ትቶን ሄዶዋል! በል እንግዲህ ስለ - ርዳታህም ስለ ጭዋታህም እግዚአብሄር ይስጥህ ልጄ! ለወደፊቱ እንተዋወቅ፤ ቤቴ ገዳም ሰፈር ከደጃዝማች አሰፋ ዳምጤ ግቢ አጠገብ ነው። ከኔ አንተ ህጻን ነህና እዬመጣህ ጠይቀኝ። ሽማግሌ በሌላ ባይሆን በምክሩና በጸሎቱ ይረዳል። እስቲ እንግዲህ ‹ደፈራችሁም› አትበልና - ስለ ድካምህ የምናደርገውን ንገረን።»

«ተመራርቀን ከመሰነባበት በቀር ምን የምታደርጉት ነገር አለ? ምሳ ጋብዛችሁኛል እግዚአብሄር ይስጥልኝ፤ መቸም ጫዋታው የጋራ ነው! » አለ በሻህ፥ መጀመሪያ አዛዥን ከዚያ ደመቀችን እያለዋወጠ ተመልከቶ።

« ‹የስራ የደከመ ለድካም ዋጋ ይገባዋል!› ይላል መጣፉ ሲሉ ሰምቼ ነውኮ! » አሉ አዛዥ ትንሽ እንደ መሳቅ ብለው።

«እንዲያው በከንቱ ስዞር የማሳልፈውን ጊዜ ከናንተ ጋር እዮተጫወትሁ ስላሳለፍሁት ደስታ እንጂ ድካም አልተሰማኝም፤ በዚያ ላይ ምሳየን አበላችሁኝ። እንዲያውም - እንዲህ ያለውን እድል ደጋግሞ የሚያጋጥመኝ ቢሆን እግዜርን እንዴት ባመሰገንሁት! » አለ በሻህ ፈገግ እንዳለ ደመቀችን የጎድን እያዩ። ደመቀች አስተያየቱን ስታይ ለመናገር ስታስብ የቆየችው ለጊዜው ለጊዜው እንደ መበታተን ቢልባትም እንደ ምንም አጠረቃቀመችና፥

«እባክህ ታሽ፥ ለድካምህ ዋጋ የሚሆን ነገር ለማድረግ ባንችልም፣ ባይሆን እኛን ደስ እንዲለን ትንሽ - ለውህ የሚሆን ነገር እናድርግ። እባክህ እሺ በለን» አለች አይኖችዋ የሱን አይኖች ማየት ስለፈሩ ወዲያ - ወዲህ እየሮጡ።

«የለም የኔ እህት፥ አሁን እንዳልሁት ደስታ እንጂ ድካም አልተሰማኝም። ወዲያውም ያንድ ቀን ነጻ አገልግሎት ለተቸገሩ ሰዎች ለመስጠት ለጊዮርጊስ የገባሁት ቃል ኪዳን ስለ ነበረብኝ፥ ዛሬ ለናንተ ያደረግሁት መጠነኛ ርዳታ ያን የገባሁትን ቃል ኪዳን ለማስወረድ የተደረገ ነው» አለ በሻህ፥ ያሽሙር ፈገግታ ፈገግ ብሎ አዛዥንና ደመቀችን እያለዋወጠ እያዬ።

«እንዲያ እንጂ! ከጊዮርጊስ ጋር የቆሎ ጉዋደኞች ሆናችሁ ነው የጋራ ቃል ኪዳን የገባችሁ? ‹ምን እናድርግ› ብላችሁ? » አሉ አዛዥ እዮሳቁ።

«ቅድም እንደ ነገርሁዋችሁ ያራዳው ጊዮርጊስ እውር እድል ከየትም አጠረቃቅሞ የጣለበትን ያራዳ ልጅ ለማስተዳደር - ሲቀሙም፥ ሆነ ሲሰርቁ ሊጠብቃቸው እነሱም በበኩላቸው ሞልቶ ከተረፋቸው ካልሆነ እንኩዋን ካጡ ከነጡ ካላቸውም ቢሆን፣ ያላቸው ለመተዳደሪያ ብቻ የሚሆን ከሆነ፥ እንዳይሰርርቁም እንዳይቀውም ቃል ኪዳን ገብተዋል። እንዲሁም ሞልቶ ከተረፋቸው ከወሩ ሀያ ዘጠኝ ቀን የቀሙትንና የሰረቁትን ለራሳቸው አድርገው በሰላሳኛው ቀን የሚያገኙትን ያንድ ቀን ገቢ፥ ለጣን ለመብራትና ደጀ - ሰላም ለወደቁት መተዳደሪያ እንዲሆን ለጠባቂያቸው ላራዳው ጊዮርጊስ ግብር ሊከፍሉ ነገር ግን ከወሩ በሰላሳኛው ቀን በለስ ባይቀናቸውና የሚሰረቅም የሚቀማም ሳያገኙ ቢቀሩ ያንድ ቀን ነጻ አገልግሎት ለተቸገሩ ሰዎች ሊሰጡ፣ ጊዜ የማይሽረው ቃል ኪዳን ገብተዋል። ስለዚህ - እኔም ባለፈው ወር ሰላሳ የማይሽረው ቀርቶ ግብሬን ስላስታጎልሁ ያራዳ ልጅ እንደ መሆኔ በገባሁት ቃል ኪዳን መሰረት ያንድ ቀን ነጻ

አገልግሎት ለናንተ መስጠቴ ነው። ይህን ነጻ አገልግሎት መቸም ቃል ኪዳን የገባሁት በመሆኑ ዛሬ ባይሆን ነገ ለናንተ፣ ባይሆን ለሌላ መስጠቴ አይቀርም ነበርና፣ ነኩዋን ለናንተ ሆነልኝ! » አለ ፈገግ፣ እንዳለ አዛዥሮንም ደመቀችንም በቀልድ አይን እያዩ።

ላዛዥና ለደመቀች የበሻህ ሁኔታ ሁሉ ምስጢር የከበበው ሆነባቸው። ባጠቃላይ ጥንቃቄ ያልተደረገለት ሰውነቱና አለባበሱ እውነት እሱ እንደሚለው ካራዳ እውነታዎች አንዱን አስመስለው ያሳዩታል። አነጋገሩ ጭዋነቱና ለገንዘብ የማይሳሳ መሆኑ ግን ያን መስሎ የሚታዬውን የሚያስተባብሉ ናቸው። ስለዚህ ምን አይነት ሰው መሆኑን ማወቅ መገመት እንኩዋ ስላልቻሉ እግዚአብሔር ለርዳታ የላከላቸው ሰው መሆኑን አምነው፣ እንዲያው እንዲሁ አመስግነው ሲወጡ፣ በሻህ እስከ ሆቴሉ በር ድረስ ሸኝቶዋቸው ካይኑ እስኪጠፉ እዚያው ቆሞ ሲመለከታቸው ቆይቶ፣ «ወይ ግሩ - ም! እንዴት ተጠንቅቆ የሰራት ልጅ ነች!› አለ።

## ምዕራፍ አስራ ስድስት

## ባሻህ ማነው?

### <u>1 ወሮበላው በሻህ</u>

በሻህ ዘለሌ በልጅነቱ በፈረንሳይ የካቶሊክስ ሚሲዮን ትምህርት ቤት እዬተማረ ያደገ ነው። እዚያ በመጨረሻው ክፍል ደርሶ ሊመረቅ ትንሽ ሲቀረው አባቱ ማይጨው በጦርነት እናቱ አዲስ አበባ በተስቦ በሽታ፥ ተከታትለው ሞተው መኖሪያ ስላጣ፣ ትምህርቱን አቁዋርጠው ላንድ የጣሊያን ከበርቴ ነጋዴ ተቀጥሮ ይሰራ ጀመር።

ትምህርቱን ባይጨርስም ፈረንሳይኛ ደህና አድርጎ ከመናገሩ ሌላ የሂሳብ ችሎታ ያለው ስለ ነበረ በሂሳብ ክፍል ረዳት ሆኖ እዬሰራ አንድ የሚኖርበት ክፍል እዚያው እጣሊያኑ ግቢ ውስጥ ተሰጥቶት ፓስታ እክሲጠግብ እዬበላና ቪኖ እንደ ልቡ እየጠጣ በዚያ ላይ መጠነኛ ይሁን እንጂ የወር ደመወዝ እያገኘ ይኖር ነበር። ነገር ግን እሱ እንደሚለው ‹እሱ ሆዱን እንደ ውሻ እዬሞላ ጣሊያኑ እንደ ውሻ እንጂ እንደ ሰው እንደማይመለከተው እንደሚንቀውና እንደሚጸዬፈው› ቢቀር ሲያይ ልቡ ተቀይሞ

ታመመና፣ መንፈሱ ሸፈተና ‹ሁሉስ ቢቀር ምናባቱ!› ብሎ ሁሉንም ጣጥሎ ማደሪያውን ከደረጃ አዳሪዎች ጋር አድርጎ ጫማ ጠራጊ ሆነ።

መቸም ጫማ ድርገው የሚያልፋትን ሁሉ እያባረሩ ከላይ ታች፣ ከታች ላይ፥ እየሮጡ እዬተጣደፉ ባለጫማዎች ቢወዱም ባይወዱም ጫማቸውን ተሻምተው እያቀፉ ለሚጠርጉ ልጆች የጫማ ጠራጊነት ስራ በዋጋውም በጉርሻውም ብሎ ሌላው ቢቀር ጦም አያሳድርም። ብቻ እንዲያ ያለው ስራ ልባቸው ከኩራት ህሊናቸው ከይሉኝታ ስሜት ነጻ ለሆነ ልጆች ነው እንጂ እንደ በሻህ ‹በንቀት አይን ከመታየት ሁሉስ ቢቀር ምናባቱ!› ብለው መኖሪያ ቤታቸውንና መተዳደሪያ ቀለባቸውን ጥለው ለሚሄዱ ኩሩ ጎረምሶች የሚሆን አይደለም። ስለዚህ በሻህ እጣልያኑ ቤት ሳለ በቆጠበው ትንሽ ገንዘብ የጫማ መጥረጊያ ሙሉ መሳሪያ ገዝቶ፣ ለመስራት ከጀመረ በሁዋላ ጭራሽ የማይገጥመው ጭራሽ የማይዋጥለት መሆኑን ሲያይ ስራውንም መሳሪያውንም እዚያው የጫማ ጠራጊነት ስራ ለሚጥማቸውና ለሚዋጥላቸው ልጆች ጥሎ፥ የማጅራት መቺዎችና የቀማኞች ማህበርተኛ ሆነ። እዚያ በድሜውም ሆነ በውቀቱ ከብዙዎቹ ቀደም ያለ ስለ ነበረ ከተራ ማህበርተኛነት ወደ መሪነት ለመራመድ ብዙ ጊዜ አልወሰደበትም።

በሻህ ማጅራት መቺዎችና የቀማኞች ማህበር መሪ እንደ ሆነ፥ የማህበሩ አላማም ወዳላማው መድረሻ መንገድም ፍጹም ተለወጡ። አላማው ወራሪ ጠላትን መጉዳት መድራሻ መንገዱ የጣሊያን ሰላዮች የሆኑትን ኢትዮጵያውያን ሲመች ራሳቸውን ጣልያኖችም ጭምር ማጅራት ማጅራታቸውን እዬመቱ በዬድልድዩ ስር በዬወንዙ ዳር እንዲሁም በልዩ ልዩ ሰዋራ ቦታዎች መድፋትና ገንዘባቸውን መቀማት ሆነ።

ጣልያኖች የጫካ አርበኞችና በከተማም በገጠርም፣ የሚኖሩ የውስጥ አርበኞች እዬተገናኙ መሳሪያ የምስጢር መረጃ የሚለዋወጡ መሆናቸውን ስላወቁ የውስጥ አርበኞች መስለው ከጫካ አርበኞችና ከውስጥ አርበኞች ጋር ተደባልቀው የሁለቱንም ምስጢር እዬቀዱ እንዲያቀብሉዋቸው ብዙ ገንዘብ የሚከፍሉዋቸው ሰላዮች አድርገው ነበር። እኒያ የጣሊያን ሰላዮች ከጫካና ከውስጥ አርበኞች ጋር ከሚገናኙባቸው ቦታዎች አንዱ ‹መገናኛ› የሚባለው ያቶ ማንደፍሮ ባንቴ ምግብ ቤት ነበር። ሰላዮች ጥይትና የጅ ቦምብ፣ ጠመንጃና ገንዘብ ውስጥ ለውስጥ ከጣሊያኖች እዬተቀበሉ አምጥተው ላርበኞች ይሰጡና፣ በዚያ ላይ መጠጥ በርከት አድርገው ይጨምሩዋቸውና አርበኞችን መሳሪያና ገንዘብ ማግኘቱ ከመጠጡ ጋር ባንድ ላይ ተደባልቆ በደስታ ሲያሞቃቸው በደስታ ሲያሰክራቸው እንኩዋንስ የተጠዬቁትን ያልተጠዬቁትን ሁሉ አውጥተው ለሰላዮች ይዘረግፉላቸዋል። ጣሊያኖች በዚህ አሆሁዋን ከሰላዮቻቸው ባገኙት መረጃ

መሰረት በዬጊዜው በዬቦታው የባንዳ ሰራዊታቸውን ባርበኞች ላይ እያዘመቱ ብዙ አርበኞችን ፈጅተዋል፤ ብዙ የውስጥ አርበኞችን ገድለዋል፤ ያልገደሉዋቸውንም ወህኒ ቤት አግብተዋል።

እንዲህ ያሉትን የተጎሳቆሉ ሰላዮች እንዲህ ያሉትን በወገኖቻችው ደም የሚነግዱ ሆድ አምላኩዎች ነበር፣ በሻህና ወሮበሎች ጉዋደኞቹ እዬተከታተሉ በገቡበት ገብተው፣ በወጡበት ወጥጠው እያደኑ፣ ያን የደም ዋጋ ገንዘባቸውን የሚቀሙዋቸውና ማጅራታቸውን እዬመቱት በዬወንዙ ዳርም፥ በዬድልድዩ ስርም፣ እዬጣሉት ይገኝ የነበር! በኢትዮጵያውያን ሰላዮችና በጣሊያን ባለሥጣኖች መሀከል አገናኝዎች የሆኑትን ጥቂት ጣሊያኖችም በሻህና ጉዋደኞቹ ገድለዋቸው ሬሳቸውን፥ በመንገድ ዳር እዬወደቀ ተገኝትዋል። ያጊዜም ፋሽስቶች የተደራጀ የውስጥ ጠላት ለመነሳት የጀመረ መስሎዋቸው ፈርተው ‹ካርበኞች ጋር ይላላካሉ› ተብለው ተጠርጥረው ይከታተሉዋቸው የነበሩትን ብዙ ንጹሀን ኢትዮጵያውያን ከያሉበት እዬለቀሙ ድራሻቸውን አጠፉት። ያን ሲያዩ በሻህና ጉዋደኞቹ ጣልያኖችን መግደል ትተው ዘመቻውን ተበቃይ በሌላቸው ኢትዮጵያውያን ሰላዮች ላይ ብቻ አደረጉ።

አንድ ማታ የጫካና የውስጥ አርበኞች ‹መገናኛ› ምግብ ቤት ባንድ ልዩ ጉዋዳ፥ ውስጥ ተሰብስበው ራት የሚበሉ መሆናቸውን አንድ ምግብ ቤቱ ውስጥ አዋቂ አሳላፊ ለበሻህና ለጉዋደኞቹ ነገራቸው። በሻህና ወሮበሎቹ ጉዋደኞቹ ከመገናኛ ምግብ ቤት የማይለዩ ገንዘብ ሲያገኙ ከፍለው ሲያጡ፥ ለንግዶች ከተሰናዳው የሚተርፈውን በልተው የሚሄዱ ደንበኖች ስለሆኑ፣ ከባለቤቱ ካቶ፥ ማንደፍሮ ጀምሮ ሰራተኞች ሁሉ እንደ ቤት ሰዎች ያዩዋቸው ነበር።

ያነለት፣ በሻህና ጉዋደኞቹ በወጥመዳቸው አልገባላቸው ብሎ አስቸግሮዋቸው ሲያደቡትና ሲከታተሉት የቆዩ ሰላይም የውስጥ አርበኛ መስሎ እዚያ ካርበኞች ጋር ነበር።

«ጎበዝ! ዛሬ የኔ ነፍስ ቀድማ ካልወጣች፣ ይህ ቡዳ ይህ በገዛ ወገኖቹ ደም የሰባ ቦርጫም፣ ከነፍሱ ላያመልጠኝ ቃል ለምድር ለሰማይ! » አለ በሻህ ለጉዋደኞቹ ቀስ ብሎ።

«ማላው ይድረሰኝ! ይድረሰኝ! ይድረሰኝ.......! » ተባባሉ፥

የጫካና የውስጥ አርበኞች በልተው ጠጥተው የሚለዋወጡትን መሳሪያና ምስጢር ተለዋወጡ፥ ተመራርቀው እንደ ተለመደው አንድ ባንድ በጉዋሮ እዬወጡ

በተለያዩ መንገዶች ተበታተኑ። ያንጊዜ በሻህ ሰላዩ የወጣበትን ተሸሽቶ ተመለከተና ሮጦ ያቶ፥ ማንደፍሮን መኖሪያ ቤት ዞሮ፣ ከዝንቦ ጥላ ስር የማእዘን ከምር ስላገኘ ያን ተጠግቶ ጠበቀው፡ ከዝንቦው ውጪ የጨረቃዋ ብርሀን እጅግ ደማቅ አንድ የጤፍ ፍሬ ብትወደቅ የሚያስለቅም ነበር! ስላዩ፣ ያገኘው ምስጢር በመንገድ ሳይጠፋበት ቶሎ ለማድረስ እንደ ፈለገ ሁሉ ባቶ ማንደፍሮ የመኝታ ቤት ጀርባ የምታልፈውን ቀጭን መግነድ ይዞ ጥድፍ ጥድፍ፥ ሲል፥ በሻህ ከሁዋላው ማጅራቱን ብሎ በግንባሩ ከነቸረው። ወዲያው ከባድ ዱላ እዚያው እማጅራቱ ላይ ደገመው። ያ ሰላይ እኳዋንስ ሲጮህ ሳይተነፍስ፥ እንኩዋንስ ሸሽቶ ለማምለጥ ሲሞክር ሳይንቀሳቀስ እዚያው በተደፋበት ዝም እንዳለ ቀረ! በሻህ ቶሎ ብሎ ከተደፋበት ሲገለብጠው ካፉም ካፍንጫውም የሚወጣው በትንፋሽ ፈንታ ደም ብቻ ነበር! ሞቶዋል! ከዚያ ሬሳውን ቶሎ ቶሎ እያገላበጠ በርብሮ ያገኘውን ገንዘብ ይዞ፥ በዶሮ ማነቂአይ የቤት ጫካ ውስጥ ገብቶ ጠፋ! አስፈላጊ ቢሆን ደጀን ሆነው ለመርዳት ባቅራቢያው ተሸሽገው ይጠብቁ የነበሩት ጉዋደኞቹም ብቻቸውን ያለ ችግር መልክቱን መፈጸሙን ሲያዩ ከተሸሸጉበት እዬወጡ በተለያዩ መንገዶች ሮጡ።

ያንጊዜ አቶ ማንደፍሮ ራታቸውን ከበሉ በሁዋላ ብዙ ጊዜ እንደሚያደርጉት ከፎቅ መኝታ ቤታቸው ውስጥ ገብተው መብራት፥ አጥፍተው የተከፈተ መስኮታቸውን ተደግፈው ወደ ውጪ እዬተመለከተቱ አዬር ይቀበሉ ነበር። በሻህ ከመስኮታቸው ስር ሮጦ ወጥቶ ሰላዩን ማጅራቱን መትቶ ሲጥለውና ወዲያው በዱላ ሲደግመው ሲያዩ ልክ የሳቸው ማጅራት እንደ ተመታ ሁሉ ራሳቸው ደንዝዞ፥ አይናቸው ፈዝዞ ባሉበት ድርቅ ብለው ቀሩ! ድንጋጤያቸው አልፎ ማየት ሲጀምሩ ማጅራት መቺው ተሙቶ የወደቀውን ሰው በርብሮ ያገኘውን ከወሰደ በሁዋላ ቀና ብሎ ዙሪያ ገባውን ተመልክቶ ሲሮጥ በሻህ መሆኑን አወቁ። ከዚያ፣ ሰው እንዳይሰማ ቀስ ብለው መስኮታቸውን ዘግተው እንዲሁም እርምጃቸውን ሰምቶ የሚወጣ ጎረቤት የተሰራውን ወንጀል እንዳያይ የፈሩ ይመስል፣ በግር ጣቶቻቸው ጫፍ እያጠቀሱ ቀስ ብለው ሄደው አልጋቸው ላይ ተጋደሙ! ያን ሌሊት እንኩዋንስ እንቅልፍ ባይናቸው ሊዞር ልብሳቸውን ሳያወልቁ እንዲሁ እንደ ተወራጩ አደሩ!

አቶ ማንደፍሮ በሻህ የፈረንሳይ ቁዋንቁዋ የሚናገር መሆኑን ሰምተው ካነጋገሩት በሁዋላ የቁዋንቁዋ እውቀት ብቻ ሳይሆን ከድሜው ቀድሞ የበሰለ አእምሮና የተመዛዘነ አስተያየት ያለው መሆኑን ሲያዩ ጉዋደኝነቱን፣ ከወሮበሎች ጋር ያደረገበት ምክንያት አልገባቸው ብሎ ይቸገሩ ነበር። ብዙ ጊዜም፥ ከወሮበሎች ማህበር ወጥቶ በጽህፈት ቤታቸው ውስጥ እሳቸውን ቢረዳ ደስ እንደሚላቸው በተዘዋዋሪ መንገድ

አስተያይተውር ነበር። ነገር ግን ያኑ ያለበትን ቦታ እንደሚወድና ለምንም ነገር እንደማይውጠው ሲረዱ፣ ‹ያለ ተቆጣጣሪ እንደ ልቡ መቦረቅ ቢወድ ነው› ብለው ተዉት። ብቻ ምንም የልጅነት ጠባይ ይዞት ወሮበሎችን ጉዋደኝነት ቢወድ ያን ማታ ሲያደርግ ያዩት ‹ያደጋል› ብለው እንኩዋንስ ሊያምኑ አይጠረጥሩም ነበር።

ሰሞኑን በሻህና ጉዋደኞቹ፥ ገንዘብ ሲያገኙ ሁልጊዜ እንደሚያደርጉት፣ አቶ ማንደፍሮ ቤት ውድ፥ መብልና መጠጥ እያመረጡ ሲበሉና ሲጠጡ፣ ላሳላፊዎችና ለወጥ ቤቶች በታላቅ ልግስና ጉርሻ ሲሰጡ ሰነበቱ።

ወንጀሉ በተሰራ ባራተኛው ይሁን ባምስተኛው ቀን በሻህ እንደ መሰንበቻው እዚያው መገናኛ ምግብ ቤት ምሳውን በልቶ ሲወጣ አቶ ማንደፍሮ ከሩቅ ስላዩት፣ አስጠርተው ወደ ጽህፈት ቤታቸው ይዘውት ገቡ። እዚያ መጀመሪያ እሱን አስቀምጠው ሲጋራ ስጥተው ካቀጣጠሉት በሁዋላ እሳቸውንም ተቀምጠው ሲጋራቸውን አቀጣጠሉና፣

«አዎ፤ ሰሞኑን - እነዚህ እሰፈራችን - እንዲያውም ከኔ መኖሪያ ቤት ጉዋሮ ነው - አንድ ሰው ተገድሎ ወድቆ ስለ ተገኘ ፖሊሶች ሲያስቸግሩን ነው የሰነበቱ፤ ሰምተሀል? » አሉ አይኖቻቸውን ሽቅብ ወደ ጣራው ከሚመለከቱበት ወደሱ መልሰው።

«አዎ፤ ሰምቻለሁ» አለ በሻህ የሲጋራውን ጢስ ውጦ እስኪመልስ ትንሽ ዝም ብሎ ቆይቶ።»

«ፖሊሶች - ‹እዚህ ቤት ከቤት ተያይዞ በተሰራበት ሰፈር ሰው ገድሎ ሳይታይ ሊሄድ የሚችል ነፍሰ - ገዳይ አይኖርምና፥ ገዳዩን ማውጣት አለባቸው› ብለው ነው ሲያስቸግሩን የሰነበቱ። ስለዚህ - ጉዳዩን በግድ ማውጣት ይኖርብናል! » አሉ፥ በሻህን ፊት ለፊት አተኩረው እያዩ።

«ገዳዩን የሚያውቅ ካላ - ማውጣት ነው እንጂ! » አለ በሻህም፥ ፊት ለፊት አተኩረው የሚያዩትን አይኖች መልሶ አተኩሮ እያዬ።

«እኔ አውቀዋለሁ! » አሉ አቶ ማንደፍሮ።

«ታዲያ ካወቁት ፖሊሶች ያን ያክል ሲያስቸግሩዋችሁ ለምን አልነገሩዋቸውም? »

«የገደለበት በቂ ምክንያት እንዳለው ቀድሞ እሱን ራሱን መጠዬቅ ተገቢ ስለ መሰለኝ! »

«እ - ! ይህም ጥሩ አሳብ ነው፤ ይጠይቁት! »

«ይኸው መጠዬቁ ነውኮ! አንተ ነህ የገደልኸው! ለምን ገደልኸው? »

«እኔ መግደሌን የት አዩ? » አለ በሻህ፥ ፊቱ የድንጋጤ ይሁን ወይም የሌላ ትንሽ ምልክት እንኳዋ ሳያሳይ።

አቶ ማንደፍሮ ተሸሽቶ፥ ነፍስ መግደሉ ለመጀመሪያ ጊዜ ሲገለጽበት፣ ፊቱ ትንሽ የድንጋጤ ምልክት ትንሽ፣ ለውጥ እንኳዋ አለማሳዬቱ አስገርሞዋቸው ዝም ብለው ሲመለከቱት ከቆዩ በሁዋላ ሰላዩን ሲገድል ማየታቸውን ለማስመን ያደረገውን ሁሉ ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻ በዝርዝር ተረኩለት። «የሚያስገርመው » አሉ ቀጥለው። «ለሁሉም የሚያስገርመው ገድለህ ለመዝረፍ ከመጎምዠትህ ብዛት የተነሳ እንዲያ ያለ ክፉ ወንጀል ከመስራት በፊት ተመልካች መኖር የመጣ አይመስልም! ፊት ልታደርገው ይገባህ የነበረውን ቀና ብለህ ዙሪያ ገባውን የተመለከተህ ሰውዬውን ገድለህ ሬሳውን እያገላበጥህ ያገኘኸውን ከዘረፍህ በሁዋላ ነው። ያን ጊዜ እኔም ያዬሁህ! ያንጊዜ ደማቅ ጨረቃ ስለ ነበረች ልክ አሁን እፊቴ ተቀምጠህ እንደማይህ መልክህን በቁጥር ልቅም አድርጌ አዬሁ! እና - መቸም እጅህን መስጠቱ ይሻል እንደሆነ ብታስብበት መልካም ነው። ይልቁንም የገደልህበት ምክንያት እንዳለህ ምክንያቱን ገልሰህ በፈቃድህ እጅህን መስጠቱ ቅጣቱን የሚያቀለው እንደሆነ ከህግ አዋቂዎች ጋር መመካከሩም ይጠቅማል። ባይሆን እንኳዋ ከህግ አዋቂዎች መለሚሰጡህ ምክርና ሌላ የሚያደርጉልህ አገልግሎት ቢኖር ለዚያ የሚያስፈልገውን ገንዘብ እኔ ልርዳህ።»

በሻህ ዝም ብሎ በጥሞና ሲሰማ ቆይቶ «እስቲ እባክዎ አንድ ሲጋራ አለዎ እንደሆነ ይጨምሩልኝ» አለ። ከዚያ የሰጡትን ሲግራ ሲያቀጣጥሉት ጠለቅ አድርጎ ስቦ ጢሱን ካስወጣ በሁዋላ «የገደልሁን ሰው እኔ እንደማውቀው ቢያውቁት ኖሮ እንኩዋንስ ‹ሲገድለው አዬሁ› ብለው ለፖሊስ አሳልፈው ሊሰጡኝ ከኔ ጋር ተባብረው ለመግደል አይንዎን አያሹም ነበር! » አለ አይኖቹን ባይኖቻቸው ላይ እንደ ተከለ ትንሽ ፈገግ ብሎ።

«ተሳስተህል! ምንም ይሁን ምንም አይነት ወንጀል ይስራ እንዲህ እንዳሁኑ ግድ አስፈላጊ ከሆነብኝ፣ ሲሰራ ያዬሁትን ወንጀል ለባለስልጣን እነግር እንደሆነ እንጂ፣ እኔ

በባለስልጣን ፈንታ ተተክቼ የባለስልጣን ሙብት ቀምቼ ሰው ስገድል የምገኝ አይምሰልህ! »

«ባለስልጣን የሚሉት፥ ከወንጀል ሰሪው የበለጠ ወንጀለኛ ቢሆንስ? ወንጀል ሰሪውን የወንጀል ስራ የሚያሰራው ‹ባለስልጣን› የሚሉት ቢሆንስ? »

«እንዴት? ምን ማለትህ ነው? አልገባኝም! »

«እንግዲህ ይስሙኝ ልንገርዎ» አለ በሻህ በቁጣ በሚንቀጠቀጥ እጁ የማስታወሻ ደብተሩን ከኪሱ አውጦ እያዩ። «እንዲያውም ስገድል ያዩኝን ሰው ብቻ አደለም የገደልሁ። ከሱ ሌላ አሁን ብቅርቡ እንኩዋ ፈለቀ እሸቴ፣ ደሴ ታምራት ተካ፥ ጉተማ፥ ሙሉነህ፣ መልኬ፥ የሚባሉትን ሰዎች ገድያለሁ! » አለ፥ ጉዋደኞቹ የገደሉዋቸውንም እነሱን ለመሸፈን እሱ የገደላቸው አስመስሎ። «ደግሞ» አለ ቀጠለና። «ደግሞ ገና ሳለሁ፥ አደፍርሰውና ተፍራ ባልቻ የሚባሉት ቀርተውኛል። እነሱንም ላልምራቸው ይህ ወር ሳያልቅ በገቡበት ገብቼ፥ በወጡበት ወጥቼ ልደፋቸው ምያለሁ! » አለ፥ በቁጣ የሚንቀለቀሉ አይኖቹን ከማስታወሻ ደብተሩ አንስቶ ወዳቶ ማንደፍሮ ወርውሮ።

«እንዴት! ምንድነህ አንተ? ሰው የመግደል ሱስ ያለብህ በሽተኛ ነህ ማለት ነው? »

«አዎ፤ በሽተኛ ባልሆንም፣ እንዲያው ያሉትን ሰዎች የመግደል ሱስ፣ የመበቀል ሱስ ያለብኝ ሰው ነኝ።

« ‹እንዲያ ያሉትን ሰዎች!› እ? ‹እኒያ ሰዎች› ምንድናቸው እባክህ? እኒያ ሰዎች ከሰው ሁሉ ተለይተው እንዲህ እንዳንተ በቀላሉ ለተጠሙና የበቀል ሱስ ላለባቸው ለበቀል ሱሳቸው ማርኪያ እንዲሆኑ የተፈተሩ ናቸው? » አሉ አቶ ማንደፍሮ ወንበራቸውን ወደ ሁዋላ ተደግፈው ከተቀመጡበት ወደ ፊት መጥተው በቁጣ የሚነዱ አይኖቻቸውን በበሻህ ላይ ተክለው።

«አደለም፤ እንደሱ አደለም። ያ ስገድለው ያዩትና ከሱ በፊት የገደልሁዋቸው ወደፊትም ለመግደል የምከታተላቸው ሰዎች የጣሊያን ሰላዮች ናቸው! እኒያ ሰዎች የውስጥ አርበኞች ሳይሆኑ የውስጥ አርበኞች መስለው ከጫካ አርበኞችና ከውስጥ አርበኞች ጋር ተደባልቀው ያርበኞችን ምስጢር ለጣሊያኖች እንዲያቀብሉ የተገዙ ሰላዮች ናቸው። ጣሊያኖች ከነሱ ባገኙት የምስጢር መረጃ መሰረት የባንዳ ሰራዊታቸውን በጫካ አርበኞች ላይ እያዘመቱ በልዩ ልዩ ጊዜና በልዩ ልዩ ቦታ በተደረጉ

ጦርነቶች ስንት አርበኞችና ስንት ባንዳዎች ያለቁ ይመስልዎታል! በኒያ ሁሉ ጦርነቶች ያለቁትን አርበኞችና ባንዳዎች ስንት እንደሆኑ የሚያውቁ የወደቁበት፥ መሬትና የበሉዋቸው አራዊት ብቻ ናቸው! እኒያ ሰላኦች በሰጡት የምስጢር መረጃ መሰረት እዬተያዙ ወህኒ ቤት የገቡትና እዬተገደሉ እንደ ጥራጊ ባንድነት ተሰብስበው በሰፋፊ ጉድጉዋዶች የተጣሉት የውስጥ አርበኞች ስንት እንደሆኑ የሚያውቁ የታሰሩባቸው ወህኒ ቤቶችና የተጣሉባቸው ጉድጉዋዶች ብቻ ናቸው። ታዲያስ! እንዲያ ያሉትን በሰው ነፍስ የሚነግዱ ሆድ አምላኩዎች የመግደል ሱስ የተቀደሰ ሱስ አደለም? እንዲያ ያሉትን በወገኖቻቸው ደም የሚኖሩ ቡዶች በመበቀል ሱስ የተባረከ የበቀል ሱስ አደለም? እንዲያ ያለውን ወንጀል የሚያስሩት የጣልያን ባለስልጣኖች መሆናቸው እዬታወቀስ - ወንጀል የሰሩትን ወንጀል ላሰሩዋቸው ባለስልጣኖች ማጋለጥ ምን ለማግኘት ነው? ይበሉ ይንገሩኝ እስቲ! ይንገሩኝ እንጂ! » አለ በሻህ የደም ስሮቹ በግንባሩ ግትር ትር ብለው የኒያን ሰላዮች ማጅራት የኔውኑ እንደሚመታ ሁሉ ያቶ ማንደፍሮ ጠረጴዛ በብርቱ ሲቃ እስኪነቃነቅ በቡጢ መትቶ።

አቶ ማንደፍሮ ሁለት ክርኖቻቸውን በጠረጴዛቸው ላይ ተክለው ራሳቸውን በሁለት መዳፎቻቸው ላይ ደፍተው በሻህ ከመራራ ስሜት ጋር እዬተበሳጨ የሚተርከውን የሚያሳዝንም የሚያበሳጭም የሰላዮች ታሪክ ዝም ብለው ከመስማት በቀር እንኩዋንስ ሊናገሩ የሚተነፍሱ አይመስሉም ነበር! የተደገፉትን ጠረጴዛ ያን ያክል በጡጫ ሲያነቃንቀው እንኩዋ ራሳቸውን ደፍተው ከተቀመጡበት ቀና ብለው ቆይተው ቀና ሲሉ፣ እንባአቸው በጽኑ ሀዘን ከመቁሰሉ የተነሳ ደም የለበሱ አይኖቻቸው እንባ ሞልተው ነበር።

«እባክህ እባክህ ልጄ» አሉ በኒያ እንባ በሞሉ ጐሽ አይኖቻቸው በሻህን እያዩ። «የተገደሉት መቸም ተገድለዋል ከእንግዲህ አይመለሱ! እባክህን ባይሆን ያልተገደሉትን አትግደላቸው! »

«እንዴት? ለምን? » አለ ያን ያክል ተቆጥተው የነበሩት ልቅሶ እስኪመጣላቸው ድረስ ማዘናቸውን ሲያይ የሱም በቁጣ ግሎ የነበረ ስሜቱ እንደ መብረድ ብሎ።

አቶ ማንደፍሮ ወዲያው አልመለሱለትም። የተመረዙ አይኖቻቸው በላዩ እንዳሳረፉ ግንባራቸውን ቁጥር ፈታ እያደረጉ ዝም ብለው ቆዩ። «አዬህ ልጄ» አሉ፥ መሀረማቸውን ከኪሳቸው አውጥተው አይኖቻቸውን አዬጠአረጉ። «አዬህ? ይህ መቅሰፍት ይህ ያንድ የኢትዮጵያ ልጆች ወንድማሞች አርበኞችና ባንዳዎች ሰላዮቻ

ጠረ - ሰላዮች ሆነን ተከፋፍለን እስበሳችን እዬተዳደርን መተላለቅ ይህ መቅሰፍት ጠላት አገራችነን ሲይዝ እኛ የሱ ባሮች መሆናችን ያመጣብን መቅሰፍት ነው! መቸም ሰው ከነጻ ሰውነት ወደ ባርነት ደረጃ ከወረደ የፈቃድ ጌታ መሆኑ ቀርቶ የገዥ ጌታውን ፈቃድ ፈጻሚ ብቻ የገዥ ጌታው መሳሪያ ብቻ መሆኑ የታወቀ ነው! ጠላታችን ባገራችንና በኛ ላይ በገዥነት እስካለ ድረስ እኛ በውድም በግድም አርበኞች ባንዳዎች ሰላዮችና ጠረ - ሰላዮች እዬሆን እስ በሳችን እዬተዳደን መተላለቃችን የማይቀር የሚቀጥል፣ ነው! የጠላታችን አይነተኛ አላማም ይህ ነው! የጠላታችን አይነተኛ አላማ የራሱን ሰው ቆጥቦ እኛን በልዩ ልዩ ስም አሰልፎ እስ በሳችን እንድንተላለቅ እያደረገ እዚህ መሬት ሲለቀቅለት መሬት ጠብቦት መድረሻ ያጣ ህዝቡን ካገሩ እያመጣ በሚያልቁት ኢትዮጵያውያን ቦታ መተካት ነው! እንዲህ እስበሳችን ተላልቀን ባገራችን በኛ ፈንታ ሌላ ሲተካ ነዋሪው ህዝብ ብቻ ሳይሆን አውሮፓውያን ባሜሪካና ባውስትራሊያ እንደ ያዙዋቸው አገሮች ያገራችን ስምዋ እንኳዋ ጠፍቶ ሌላ ይሆናል! ታዲያ - የጠላታችን አልማ ይህ መሆኑ ሲታወቅ ምንስ ብርቱ በደለኞች ቢሆኑ ኢትዮጵያውያንን መግደል ይህ የጠላታችን ርኩስ አላማ ፍጻሜ ቢያገኝ መርዳት አደለም? የጠላት መሳሪያ መሆን አደለም? መቸም ባለማወቅ ካልሆነ፥ አወቀህ የጠላት መሳሪያ መሆን እንደማትፈልግ እርግጠኛ ነኝ! »

«የምበላው እንጀራ ባጣ እንኳዋ የንጨት ስርና ቅጠል እዬበላሁ የጠላት መሳሪያዎች የሆኑትን አጠፋለሁ እንጂ፥ የጠላት መሳሪያ አልሆንም! » አለ በሻህ ከስሜት ጋር።

«አውቀህ የጠላት መሳሪያ እንደማትሆን አውቃለሁ። ብቻ እስካሁን ያደረግኸውና ‹ወደፊት አደርጋለሁ› ያልኸው አሁን እንደ ነገርሁህ የጠላትን የረዥም ጊዜ አላማ የሚረዳ ስለሆነ ካልተውኸው የጠላት መሳሪያነት ነውኮ! »

በሻህ አንገቱን ደፍቶ እዬተከዘ ሲያስብ ቆዬና «እውነትም ነው» አለ ለራሱ እንደሚናገር ሁሉ በዝቅተኛ ድምጽ። ከዚያ ከባድ ቅርታ ያጠለለው ፊቱን ወዳቶ ማንደፍሮ ቀና አድርጎ፥ «ከንግዲህ» አለ። «ከዛሬ ጀምሮ ጠላታችን ባገራችን መሬት እስካለ ድረስ ለሕይወቴ ስከላከል ሊደርስ ከሚችለው በቀር ያንድ ኢትዮጵያዊ ነፍስ ላላጠፋ ማላ ይሁንብኝ! »

አቶ ማንደፍሮ፥ በሀዘን ጠልሞ የነበረ ፊታቸው እንደ በጋ ጎህ በደስታ ወገግ ብሎ ጠረጴዛቸውን ዞረው ሄደው እስኪጨንቀው እቅፍ አድርገው ይዘው ይስሙት ጀመር!

በሻህም የሳቸውን፥ ሁኔታ ሲያይ ልቡ ተነከቶ ያለቅስ ጀመር! ከዚያ ቀን ጀምረው ነው አቶ ማንደፍሮ በሻህ አባትና ልጅ ሆነው የቀሩ!

## 2. የዉስጥ አርበኛው በሻህ

በሻህ ኢትዮጵያውያን ሰላዮችን እያደነ ላይገድል ላቶ ማንደፍሮ ከማለላቸው በሁዋላ ጠላት፣ ኢትዮጵያን ለቆ እስኪወጣ ድረስ፣ እሱና ‹ወሮበሎች› ጉዋደኞቹ፥ ዘመዶቻቸውን በበጣሊያኖች በሆኑት ነገኦች ላይ አደረጉ።

ጣሊያኖች ማጥቃት ለበሻህና ለጉዋደኞቹ - አላማቸው አንድ እስከሆነ ድረስ - አስቸጋሪ አልነበረም። እንዲያውም ኢትዮጵያን ሰላዮችን እያደኑ ከመምታትና ከመቀማት እጅግ የቀለለ ነበር። ምንም እንኩዋ በጣሊያኖችና በኢትዮጵያኖች መሀከል የጋብቻም ሆነ የግብረ ዝሙት ግንኙነት እንዳይኖር ቀዋሚ የመንግሥት ትእዛዝ ቢኖር መቸም በተለይ በወጣቶች ዘንድ ከመንግሥት ትእዛዝ የፍትወት ስጋ ትእዛዝ አሸናፊ መሆኑ የታወቀ ስለሆነ መሸት ሲል የጣሊያን ወታደሮችና ሰላማውያን ወጣት ጣሊያኖች ሴት፥ ፍለጋ ብዬ፣ መንገዱ ማእዘንና በዬስርቻው ብቻ ብቻውን ቆመው አይናቸው ሲቃብዝ ሴት አዳኞች መሆናቸውን በሻህና ጉዋደኞቹ ያውቃሉ።

‹ሲኞሬ ቮለሬ ቤላ፥ አንቺ?› ይለዋል በሻህ፥ ወይም ከጉዋደኞቹ አንዱ ቀስ ብሎ ብቻውን ወደ ቆመው ጣሊያን ጠጋ ይልና። ‹ቤላ አንቺ› በጣሊያን አማርኛ ‹ጥሩ ሴት› ማለት ነው። ከዚያ፥ በጠባብ መንገድ መርቶ እሴተኛ አዳሪዋ ቤት አድርሶት ጉርሻውን ከተቀበለ በሁዋላ ዘወር ብሎ ተሸሽጎ ይቆይና ጣሊያኑ በየሄደበትን ጉዳይ ፈጽሞ ሊወጣ ከተሸሸገበት ወጥቶ ማጅራቱን መትቶ በግንባሩ ይደፋዋል! የተገደለው ጣሊያን ወታደር እንደሆነ ሁልጊዜ ሰላማዊ እንደሆነ ብዙ ግዜ ሽጉት ስለሚኖረው ወሮበሌ ቶሎ ሽጉጡን እጅ እያደርግና ከዚያ ይብዛም ይነስ በኪሱ ያገኘውን ገንዘብ በርብሮ ይወስድና መንገዱን ለውጦ የውሀ ሽታ ይሆናል! እንዲያ እንደ በግ እዬተሳበ ሄዶ የሚታረደው ጣሊያን መቸም ተመልሶ ማን እንዳረደው አይናገር! በዚያ አይነት መንገድ እዬተከታተሉ ያን አይነት ሞት የሞቱት ጣሊያኖች ብዙ ነበር።

መቸም ወሮበላ ለለት ማደሪያው እንጂ፣ ለሁልጊዜ መኖሪያው ‹ላገሩ ያስባል› ተብሎ ስለማይገመት በሻህና ወሮበሎች ጉዋደኞቹ በወሮበላነት ስማቸው ተሸሽገው ይሰሩት የነበረ የውስጥ አርበኝነት ስራ እጅግ የሚያስደንቅ ነበር! ከገደሉዋቸው ብዙ ፋሽስቶች ሌላ የመሳሪያ ማከማቻዎችን መጠገኛዎችንና ጋራጆችን ሲያቃጥሉ የስልክ፣ የሙብራትና የውሀ መስመሮችን እያበላሹ ሲያስቸግሩ እንኩዋን የሚያውቅባቸው

የሚጠረጥራቸው አልነበረም። እነሱ በሰሩት እዬጠረጠሩ ተልፈገው የሚያዙ ‹ላገራቸው ነጻነት ተቆርቆዋሪዎች ናቸው› የሚበሉት የፖለቲካ ሰዎች ነበሩ።

ከእለታት አንድ ቀን በሻህ ከወሮበሎች ጉዋደኞቹ አንዱን የጣሊያን ሰላይ መሆኑን ከሚያውቀው ሰው ጋር ተቀምጦ ሲነጋገር አዬው ያ፣ እቅዳቸውን ትቶ ማንደፍሮ እስኪያስለውጡዋቸው ድረስ እነ በሻህ ሊገድሉት ይከታተሉት የነበረው ተፈራ ባልቻ ነበር! በሻህ ሁለቱን ባንድ ላይ ተቀምጠው ከማግኘቱ ይልቅ እሱን ሲያዩ መደንገጣቸው፣ እንደሚገበያዩ በጣም አስጠረጠረው።

ከዚያ፥ ወዲያው ተመልሶ ጉዋደኞቹን ከያሉበት እዬፈለገ አጠራቅሞ ከከተማ ዳር ወዳንድ ጫካ ወስዶ ያዬውንና የጠረጠረውን ከነገራቸው በሁዋላ «ጎበዝ» ምናልባት ወንድማችን እኔ የጠረጠርሁትን ለማድረግ እኛን ለመሸጥ አላሰበም ይሆናል። ብቻ አሁን እኛ ባለንበት ሁኔታ መጠርጠርና የጠረጠርነው እድናይደርስብን የሚያስፈልገውን እርምጃ መውሰድ የሚገባ ነው። ‹ያልጠረጠረ ጠመነጠረ› የሚሉት ተረት እንዳይደርስብን ሳንመነጠር ዛሬውኑ ካዲስ አበባ ወጥተን እንደር! »

«ከዚህ ወጥተን ወዴት እንሄዳለን? » አለ ከጉዋደኞቹ አንዱ።

«አንደኛ ላሉ፥ ወዳርበኞች ከመሄድ በቀር፥ ሌላ ምን መሸሻ ይኖራል? »

«በሻ የጠረጠረው ልክ ኖሮዋል! ከማግስቱ ጀምሮ እስከ ብዙ ቀን ድረስ የፋስሽት፣ የፖሊስ ሀይል፥ አዲስ አበባ ውስጥም ካዲስ፥ አበባ ውጭም፥ ‹በሻህና ጉዋደኞቹ ለሄዱባቸው ይችላሉ› ተብለው በሚጠረጥሩት ቦታዎች ሁሉ፥ በግር በፈረስ ፈልጎ ሊያገኛቸው አልቻለም፣ ያንጊዜ እነሱ ካዲስ አበባ ወጥተው ለማደር እንደ ወሰኑት እለቱን ወጥተው፥ ጉዋዝ መዘዝ የላቸው፣ ቀን ከሌት ገስግሰው ግንደበረት ካርበኞች ጋር ተጨምረዋል!

## 3. አርበኛዉ በሻህ

ብዙ ጊዜ ጣሊያኖች የሚልኩዋቸው ሰላዮች አርበኞች ለመሆን የሄዱ መስለው ካርበኞች ጋር ተጨምረው መሪዎችን ለመግደል፥ ወይም ሌላ ጣሊያኖችን የሚረዳና አርበኞችን የሚጎዳ ተንኮል ለማድረግ ሲሞክሩ፣ የተደረሰባቸው በመሆኑ አዲስ ገቢዎች ሁሉ ምንነታቸው እስኪታወቅ ለብቻ ሆነው ሲጠብቁ እንዲቆዩ ጥንቃቄ ይደረግ ነበር። ስለዚህ በሻህና ጉዋደኞቹ ካዲስ አበባ ሸሽተው ካርበኞች ጋር ሲጨመሩ ተስፋ እንዳደረጉት አርበኞች እጃቸውን ዘርግተው አልተቀበሉዋቸውም። ለጥቂት ቀናት እንደ

እስረኞች እጃቸውን ዘርግተው አልተቀበሉዋቸውም። ለጥቂት ቀናት እንደ እስረኞች ለብቻ አንድ ሳምንት ባልሞላ ጊዜ ውስጥ መሳሪያና ወሬ እንዲያመጣ አዲስ አበባ ተልኮ የነበረውን የሚያስደንቅ የምስጢር ዘመቻ ከተደረገውም የበለጠ እዬተነጋነነ ሲወራ ሰምቶ መጥቶ ሲናገር በሻህና ጉዋደኞቹ ለብቻ ከሚጠበቁበት ተለቀው፣ ያርበኞች መሪዎች ባንድ ላይ ባሉበት ቀርበው ታሪካቸውን ራሳቸው እንዲገልጹ ተጠዬቀ። እዚያ፥ በሻህ ተጨማምሮ እዬተጋነነ የተወራውን ቀንሶ እውነቱን ነገራቸው። ብቻ፥ እውነቱንም ህልም እንጂ እውን የሚመስል አልነበር! ወዲያው በሻህ መትረዬስ ጉዋደኞቹ እያንዳንዳቸው ምኒሽር ጠመንጃ ከበቂ ጥይት ጋር ተሸልመው ሲወጡ፣ እኒያን ተጠርጥረው በዘብ ሲጠብቁ የሰነበቱ ‹ወሮበሎች› እዚያ የነበረው አርበኛ ሁሉ ከብቦ፥ እያንዳቸው አንዱ ካንዱ እዬተናጠቀ፣ አቅፎ፣ ስሞ ተሸከሞ አልጠግባቸው አለ!

መቸም ሰሞኑን፥ እዚያ ባርበኞች ሰፈር፣ ከያፉ ነገር ሲነገር የሚሰማው ካዲስ አበባ የመጡት ጀግኖች በተለያዩ ቡድኖች ውስጥ የተመደቡ መሆናቸው ሲነገራቸው ሁሉም ከበሻህ የማይለዩ መሆናቸውን አስታወቁ።

«የለም፥ እኛ ምንም ቢሆን ከበሻህ አንለይም! » አለ አንዱ።

«ከበሻህ ሞት ብቻ ነው የሚለዬን! » አለ ሁለተኛዉ።

«ማነን ብለን መጣንና ከበሻህ እንለያለን? » አለ ሶስተኛው ሌሎችም እንዲሁ በተለያዩ ቃላት፣ ከበሻህ የሚለያቸውን ድልድል የማይቀበሉ መሆናቸውን ገለጹ።

እውነትም ‹ማነን ብለን መጣንና ከበሻህ እንለያለን?› እንዲለው አንዱ እኒያ ያራዳ ወሮበሎች በሻህን ብለው በሻህን ተከትለው መጡ እንጂ፥ ሌላ ነገር ፈልገው አልመጡም። ለጤናቸው፥ ለትምህርታቸው ለልብስ - ጉርሳቸው በጠቅላላው ለኑሮዋቸው አስቦላቸው የሚያውቅ አገር ስላልነበራቸው ያገር ፍቅርም አልነበራቸውም! ስለዚህ የማያውቁት ያገር ፍቅር አስገድዶዋቸው አልመጡም! እነሱ የመጡ በሻህን ብለው በሻህን ተከትለው ነው! በሻህ ተቀምቶ ይሁና ተስርቆ የሚገኘውን ገንዘብና ሌላ ሀብት ‹ለኔ› ከማለት ‹ለናንተ› የሚል በመሆኑ ከነዚህ ሌላ፥ በሻህ ሲናገር የሰሚውን አሳብና ስሜት እንደ መስኖ ውሀ በመራው ስቦ የሚወስድ እንደ መሆኑ በዚያ ሰሚውን ለማሳመን በታደለ አንደበቱ ጣሊያን የግፈኞች ግፈኛ መሆኑን ስላሳመናቸው እነሱ ራሳቸው የግፍ ስደተኞች በመሆናቸው ግፍን ሊቃወም በሻህን ተከትለው መጡ እንጂ ለኢትዮጵያ ነጻነት ሊዋጉ ወደ አርበኝነት አልመጡም!

በሻህም ከነሱ መለየት እንደማይወድ ለመሪዎች አስታወቀ። ስለዚህ በነሱ ላይ ሌሎች አስራ አምስት አርበኞች ተጨምረውለት ያንድ ቡድን አለቃ ሆነ።

በሻህ፣ ባርበኝነት በቆዩበት ጊዜ፥ ትልቅ ጦርነት ሆኖ የሱን ቡድን በተሰለፈው ግንባር ወይም አርበኞች በሙሉ የማይሰለፉበት ‹መጠነኛ ጦር መጣ› ተብሎ የበሻህ ቡድን የተላከ እንደሆነ መቸም ‹ድል ያደርጋል እንጂ ድል ይሆናል› አይባል! ጦርነቱ እንደ ቁዋያ እሳት ይቃጠልና ወላፈኑ በሩቅ ያሉትን ሳይቀር እዬተገረፈ ሲያባርር እኒያ የውቤ በርሀ ማጅራት መቺዎች እኒያ የሌሊት፥ ዛሮች እዬዘለዘለ፥ እመሀል የገቡ እንደሆነ ‹አለቁ› ሲባል ምንም ሳይሆኑ ጠላታቸውን ጨርሰው ይወጣል! እኒያ ተርቦች እመሀል ገብተው ላይና ታች ቀኝና ግራ እዬተዋነቡ ጠላታቸውን ሲነድፉ ይይዘውን ያደርገው፥ ያሳጡታል! ተርበን አልሞ ማን መትቶ ያውቃል? ዛርንስ ማን ገድሎ ያውቃል?

የበሻህ ወሮበሎች በገጠሙበት ጦርነት የፈጁትን ፈጅተው የተሸንፈውን አሻሽተው እነሱ ምንም ሳይሆን ስለሚወጡ ‹ዛሮች› የሚባል ስም ወጥቶላቸው ነበር! ካርበኖች መሀከል የነበረ ገጣሚ ሲያወድሳቸው እንዲህ አለ።

«ያው መጣ እዚያ ማዶ ባንዳ፥ ሲግተለተል መድፉን በግፍ ጭኖ፣

ዛሮች የሄዱበት ዛር አንዱ ይበቃል፣ እንኩዋስ ብዙ ሆኖ።

አየ ባንዳሞች ዛር እዋጋ ብሎ፣ በገዛ እጁ ይስቃል፣

ዛር ይገድላል እንጂ፣ መች ተገድሎ ያውቃል?

ባንዳ መትረየስን አንድደህ አፍላበት ቡና በጀበና፣

መቸም ተተኩሶ ዛር አይገድልምና።

ባንዳ ጠመንጃህን ሰብረህ አንድድና ንፍሮ ቀቅልበት፣

መቸም አትችልና ዛር ልትገድልበት።

ያው መጣ እዚያ ማዶ ባንድ ሲግበሰበስ።

መድፉን መትረዬሱን አስጭኖ ባጋሰስ

ንገሩት ለበሻህ፣ እንዲያ እንደ ልማዱ ተረክቦት ይመለስ።

ወርደህ ተረከበው፥ በሱ እንደ ልማድህ ከዛሮችህ ጋራ።»

ያ ያርበኝነት ኑሮ ለኒያ ለበሻ ዛሮች፣ ተኑሮ የማይጠገብ፣ ግሩም የሆኑ ኑሮ ነበር! ብቻ እንደማይጠገበው ግሩም ነገር ሁሉ ቶሎ አለቀ ፋሽስቶች ድል መሆናቸውና የኢትዮጵያ መንግስት በእንግሊዝ እዩተረዳ ወደ ስልጣኑ በመመለስ ላይ መሆኑ ደምቆ ይወራ ጀመር። ያን ጊዜ ባርበኞችና በውስጥ አርበኞች በስደተኞችና በግዞተኞች መሀከል የነበረው ደስታ የደስታን ዳር ድንበር ሁሉ ያለፈ ነበር! ያ ወሬ ከኢትዮጵያውያን መሀከል ደስ ያላሰኛቸው፥ የበሻህ ወሮበሎች ብቻ ነበር! ለበሻህ ወሮበሎች ‹ኢትዮጵያ ነጻነት› የሚሉት ነገር እንዲያው ትርጉም የሌለው ባዶ ቃል ነው! ስለዚህ ኢትዮጵያ ነጻ ብትሆን ባትሆን የራስዋ ጉዳይ ነው! የነሱ ጉዳይ አደለም! ኢትዮጵያ ነጻ ስለሆነች ‹እነሱ ነጻ ሆኑ፥ የነሱ ጦርነት አለቀ› ማለት አደለም፤ የነሱ ጦርነት የሚቀጥል ነው! ጣሊያን ኢትዮጵያን ከመያዝዋ በፊት፣ አገራቸው አራዳ ሳሉ ሳይወዱ በግድ፥ ኑሮ አስገድዶዋቸው ሲሰርቁ ሲቀሙ፣ ማጅራቱ ሲመቱ ተይዘው ሲታሰሩ ሲደበድቡ ተፈትተው እንደ ገና ወደ ወንጀል ስራቸው ሲገቡ ሁልጊዜ በጦርነት የኖሩ ናቸው! አሁን ወዳገራቸው ወዳራዳ ሲመለሱ፣ መኖር ካልቀረ ያው መኖር የሚያስችላቸው ጦርነት የማይቀር የሚቀጥል ነው! ስለዚህ ለጦርነት ጦርነት ካራዳው ጦርነት ያን የጫካዉን ያን ያርበንነቱን ጦርነት በጣም ወደውት ስለ ነበረ፥ ያ ሁሉን ደስ ያሰኘው ወሬ የንሱን አሳዘናቸው!

ያራዳው ጦርነት ጨለማ ለብሰው ሰው እንዳያያቸው እዩፈሩ የሚዋጉበት ነው! ያርበኝነቱ ጦርነት ቀን ለቀን ጀግንነታቸው ሰው ሲያይላቸው እዩኮሩ የሚዋጉበት ነው! ያራዳው ጦርነት በሰረቁ በቀሙና ማጅራቱ በመቱ ቁጥር የሚረገሙበት፣ ያርበኝነቱ ጦርነ በገደሉ ማጅራት በመቱ ቁጥር የሚሸለሙበት ነው! ያራዳው የሚያስከስስና የሚያስወቅስ፣ ያርበኝነቱ የሚያስወድስና የሚያሞግስ ነው! አየ ጉ - ድ! ምን ጣሊያኖች ባልወጡና ያርበኝነቱ ጦርነት ለሁልጊዜ የሚቀጥል በሆነ! ያ በሆነ እንዴት ደስ ባላቸው ነበር! ብቻ ምን ይሆናል? ማለቁ ነው። ስለዚህ ያ ደምቆ የተወራው ወሬ እዚያ ለነበሩት አርበኞች ሁሉ ለብሻህ ጭምር ትልቅ የምስራች የነበረውን ያክል ለወሮበሎች መርዶ ነበር! ወዲያው ኢጣሊያ ወጥታ ኢትዮጵያ ነጻ ሆና የኢትዮጵያ መንግስ ወደ ስልጣኑ ተመለሰ።

መቸም ክፉ ነገር ሲደርስ የሚያልፍ ሲያልፍ ተመልሶ የሚመጣ አይመስል! ፋሽስቶች ኢትዮጵያን በያዙ ጊዜ በስደት በግዞት ባርበኝነትና በውስጥ አርበኝነት ውስጥ ሆነው ይቸገሩ የነበሩት ኢትዮጵያውያን ሁሉ ያ ችግር ያ መከራ የደረሰባቸው ላገራቸው

ሊሰሩት ይገባቸው የነበረውን ባለመስራታቸው መሆኑን ተገንዝበው ስለሰሩት ክፉና ስላልሰሩት መልካም ተጸጸተው ራሳቸውን እዬወቀሱና እስበሳቸው እዬተወቃቀሱ ባንድ ታምር አገራቸው እንደገና ነጻነትዋን የምታገኝ ብትሆን የራሳቸውን ጥቅም ወደ ሁዋላ ብለው ላገራቸው ጥቅም ቀን ከሌት የሚደክሙ እንደሚሆኑ ይምሉ ቃል ኪዳን ይገቡ ነበር! ነገር ግን እኒያ በችግር በነበሩ ጊዜ አገራቸው እንደገና ነጻ ብትሆን ከራሳቸው ጥቅም የስዋን ጥቅም እንደሚያስቀድሙ ይምሉ ይሳሉ ቃል ኪዳን ይገቡ የነበሩት ሁሉ ፋሽስቶች ድል ሆነው ኢትዮጵያ ነጻ ከሆነች በሁዋላ ከዬነበሩበት የችግር ቦታ ሲመለሱ ያን ሁሉ ረሱና በጠላት እጅ ተመትታ ደምታ ቆስላ፥ የነበረች አገራቸውን ቁስልዋን ለማዳንና ልማትዋን ለማፋጠን በማሰብ ፈንታ እንዲያውም እስዋ በደለኛ እንደ ሆነች ሁሉ ከስዋ ካሳ ፈላጊዎች ሆኑ!

እኒያ በችግር በነበሩ ጊዜ ከራሳቸው ጥቅም ያገራቸውን ጥቅም ለማስቀደም ይምሉ፣ ይሳሉ ቃል ኪዳን ይገቡ የነበሩ ስደተኞች አርበኖችና የውስጥ አርበኞች ፋሽስቶች በዬከተማው የሰሩት ቤት የፋሽስት ገበሬዎች በዬገጠሩ ያለሙት መሬትና ያረቡት ከብት ጠላት አቁስሎ ለተዋት አገራቸው ማገገሚያና ላልለማ ሀብትዋ ማልሚያ እንዲሆን በማሰብ ፈንታ እሱን ለመከፋፈል ቅድድሞሽ ትግል፥ ላይ እንደ ትልቅና ትንሽነታቸው ወይም ለባለሥልጣን እንደ መቅረብና መራቃቸው መጠን አንዱ ብቻ መሬት አንዱ አንድ ጋሻ መሬት ከዚያ አንድ ጋሻ ለሁለት ከዚያ አንድ ጋሻ፥ ላራት ከዚያ ገንዘብ ተካሱ! በዚያ ላይ እስበሳቸው እዬተመሰካከሩ ሽልማቱን ተከፋፈሉ! ስደተኛነት አርበኛነትና፣ የውስጥ አርበኛነት ለካሳና ለሽልማት ብቻ ሳይሆን ባስተዳደርና ባገር ግዛትም ለስራ የሚያስመርጡ የደረጃ እድገት የሚያሰጡ ሆኑ! በትምህርት መመረቅና ስራ ማወቅ ሁለተኛ ደረጃ ያዙ!

እመጀመሪያ ላይ ከኒያ ከስደተኞች ካርበኞችና ከውስጥ አርበኖች መሀከል ጥቂቱ በጣም ጥቂቱ ብዙሀኑ የችግር ጉዋደኖቻቸው ዘርፈው ገፍፈው ወደዬነበሩበት የችግር ቦታቸው ለመመለስ እንደ መጡ ሁሉ ባገራቸው ለመኖር እንዳልመጡ ሁሉ በሚዘረፈው ሀብትና ንብረት ላይ ሲተናነቁ፣ ሲዋደቁ ስያዩ ልባቸው ተቀዬመ ታመመና ለምኑም ለምኑ ተካፋዮች ሳይሆኑ፤ የሩቅ ታዛቢዎች ሆነው መቆየቱ የሚሻል መሰላቸው። ብቻ እነሱም የሩቅ ታዛቢዎች እንደ ሆኑ ብዙ አልቆዩም። ዘረፉ የማህበሩ ጠቅላላ ስራት ከሆነ መዝረፍ የማይፈልጉትን ጎትቶ፣ ከዘራፊዎች ጋር ስለሚጨምራቸው መጀመሪያ ተቀይመው ለማናቸውም ነገር ተካፋዮች ላለመሆን አስበው የነበሩት እንኩዋ ቀስ እያሉ ከብዙሀኑ ተጨመሩ። ‹ለምን አሰባችሁን ለወጣችሁ?› ተብለው ሲጠብቁ ‹ያባትህ ቤት ሲወረር አብረህ ውረር› የሚለውን

ዘይቤ አስታውሰን ነዋ! » እያሉ ይቀልዱ ጀመር! አንዳንዶቹ ለካሳውና ለሽልማቱ ተካፋዮች መሆኑን ትተው በመንግስት መስሪያ ቤቶች ገብተው አገራቸውን ለማገልገል ብቻ ወሰኑ። ከነዚህ አንዱ በሻህ ዘለሌ ነበር።

በሻህ ‹ካሳ› የሚሉትን ነገር ቢጠላም ላርበኝነትና ለውስጥ አርበኝነት የሚሰጠውን ሽልማት ቢያገኝ ባልጠላ ነበር። ነገር ግን የጣሊያን ሰላዮች እንደ ነበሩ ደህና አድርጎ የሚያውቃቸው ሰዎች የውስጥ አርበኞች መሆናቸውን መሳሪያና ገንዘብ ውስት ለውስጥ ከጣሊያን እዬተቀበሉ ይሰጡዋቸው የነበሩ አርበኞች እዬመሰከሩላቸው ሲሸለሙ ሲያዩ ከነሱ ጋር ተሰልፎ መሸለሙ ቀፈፈው አስጸዬፈው፥ ከነሱ ጋር ተሰልፎ መሸለሙ እነሱን የሚያደርገው መስሎ ታዬውና ሽልማቱንም ተወው!

አርበኞች አዲስ አበባ ገብተው ሰልፋቸውን ካሳዩ በሁዋላ፣ በሻህ ወሮበሎች ጭፍሮቹን አስከትሎ ወደ አቶ ማንደፍሮ ቤት ሄደ። ከሱ ጀምሮ፥ ሁሉም የለበሱት ልብስ በቅቤ ጠልቆ፣ በጸሀይ የደረቀ፥ የላምነት እንጂ፥ ጨርቅ ስለማይመስል የራስና የፊት ጠጉራቸው ከመጠን በላይ አድጎ፣ የነበሩበትን ጫካ እንጂ የሰው ጠጉር ስለማይመስል እንዲሁ ባጠቃላይ ሲታዩ አንዳንድ፥ ጊዜ ሌት በቅዠት መጥተው የሚያስፈራሩ ክፉ መናፍስት እንጂ ሰዎች አይመስሉም ነበር!

እኒያን የላም ነት የለበሱና ጫካ የተሸከሙ የሚመስሉ ልዩ ፍጥረቶች በመንገድ ያገኛቸው ሁሉ ፈርቶ እግሩ መንገዱ እዬለቀቀ እይኑ እነሱን እዬተከተለ አቶ ማንደፍሮ ቤት ደርሰው ጠመንጃቸውን፥ እንዳነገቱ ግቢውን ሲወሩት እዚያ የነበሩት ሁሉ አቶ ማንደፍሮ ጭምር ደንገጡ። ከዚያ በሻህ ቀድሞ ሌሎች እሱን ተከትለው ያቶ ማንደፍሮ ጉልበት ለመሳም ሲሄዱ ልባቸው ፈርቶ ለመሸሽ ቃጥተው ነበር። ነገር ግን ከድንጋጤያቸው ብዛት የተነሳ እግሮቻቸው፥ በቆሙበት እንደ ተተከሉ ስለ ቀሩ፥ ቁልቁል ከመመልከት በቀር ምንም ለማድረግ አልሞከሩም። መጀመሪያ በሻህ ጉልበታቸውን ስሞ ቀና እንዳለ ከንፈሮቹ ፊቱን የሸፈነው ጫካ ግራና ቀኝ ገለል አድርገው ከዚያ መሀከል ነጭ ጥርሱ ብልጭ ሲል፣ በሻህ መሆኑን አወቁ! አየ ያንጊዜ ያቶ ማንደፍሮን ደስታ ያዬ! የዚያን ጊዜው ያቶ ማንደፍሮ ደስታ ስካር እንጂ ደስታ አይባልም። ደስታቸው ከደስታነት አሎ ስካር ሆነና ስካራቸው ቅድም በሻህን እንደ ጣረ ሞት መፍራታቸውን መጸየፋቸውን አስረሳቸውና፥ አሁን ከነቅቤው ከነድፉ አቅፈው እያገላበጡ ይስሙት ጀመር! ከዚያ ሌሎችንም እንዲሁ እያቀፉ ሳሙዋቸው።

«እንኩዋ እግዚአብሔር አተረፋችሁ፣ ‹እነሞት እንቢ!› እንኩዋ ከዚያ ጨለማ አውጥቶ ስለነጻነት ብርሃን አበቃችሁ» አሉ፣ ከድንጋጤያቸው ሲወጡ አይኖቻቸው በደስታ እንባ እዬዋኙና ሁሉንም አንድ ባንድ ከግር እስከ ራሳቸው እያዩ። ወዲያው አንድ የተለዬ ክፍል እንዲሰናዳ አደረጉና እዚያ ይዘዋቸው ገብተው ትልቅ ድግስ ትልቅ በአል አደረጉላቸው። እምግብ ቤታቸው ከሚሰናዳው ሌላ ሽንጥ ስጋ ተገዝቶ እዬተበላ፣ ጠጅ በግፍ እየተጠጣ ፋሲካ ሆኖ ዋለ። ከግብዣው በሁዋላ ለሁሉም፥ ፍል ውሀ ሄደው የሚታጠቡበት ጠጉራቸውን የሰው ጠጉር የሚያስመስሉበት ልብስ የሚለውጡበትና ለለት ምግብም ማረፊያም የሚሆን ገንዘብ ሰጥተዋቸው ተሰነባበቱ።

## 4. የመንግስት ሰራተኛዉና ባለ ትዳሩ በሻህ

«አሁን እንግዲህ - ምን ለማድረግ ነው የምታስበው? » አሉ አቶ ማንደፍሮ በሌላው ቀን። በሻህ አንድ ክፍል ቤት ሰጥተው ምግቡንም እዚያው እሳቸው ቤት እዬተመገበ ነበር የሰነበተ።፡

«የማገኝ ከሆነ የመንግስት ስራ መስራት ነው የምፈልገው አባባ» አለ በሻህ።

«ስራ አይገድም ዛሬ አገራችን ስራ፣ የሚሰራ እው ድሀ ናት፣ እንጂ የስራ ድሀ አደለችም። በመረጥኸው መስሪያ ቤት ስራ አታጣም።»

«የማገኝ ከሆነ፣ በገንዘብ ሚኒስቴር ውስጥ መስራት ነው የምፈልግ። ከጣሊያኖች ጋር እሰራ የነበረ የሂሳብ ስራ ስለሆነ፥ በመጠኑም ቢሆን፥ የሂሳብ ስራ ልምድ አለኝ።»

«ሌላዉ - የምመክርህ ነገር» አሉ አቶ ማንደፍሮ እንዴት እንደሚቀበላቸው ስላላወቁ እያመነቱ፣ «ሌላዉ የምመክርህ ነገር ስራ እንደ ያዝህ የምትስማማህና በመጠኑም ቢሆን ትምርት ያላት ልጅ ፈልገህ አግብተውህ ትዳር እድንትይዝ ነው። ትዳር መልካም ነው ልጄ። ትዳር ይሰበስባል፤ ይቀጣል። ‹የትዳርን ያከል አባት እናት አይቀጡም› ይባላል። ወዲያውም ያስከብራል።»

«እኔም ያሰብሁት እንደሱ ነው አባባ» አለ በሻህ።

አቶ ማንደፍሮ እንዳሉት፥ - የሹመቱ ቦታ ለጥቂቱ ይቆጠብ እንጂ - ስራ ተርፎ ‹የሰራተኛ ያለህ!› የሚባልበት ጊዜ ስለ ነበረ፣ በሻህ ማመልከቻውን እንዳገባ በገንዘብ ሚኒስቴር ውስጥ ተቀጥሮ 145 ብር የወር ደመወዝ ተቆረጠለት። በዚያ ላይ ከስራው ሲወጣ፣ ያቶ ማንደፍሮን መጻህፍት በያይነታቸው ተራ እዬሰጠ በስራት መዝግቦ

ለማስቀመጥ 125 ብር ሊከፍሉት ስለ ተስማሙ፣ ከኰልቱ 300 ብር የወር ደመወዝ አገኘ ማለት ነው። 300 ብር በዚያ ጊዜ፣ የክፍል ዲሬክተር ደመወዝ ነው። መቸም አቶ ማንደፍሮ በምክንያት በሻህን ለመርዳት ብለው ነው፥ እውነት ስራው የሚያስፈልጋቸውና ያን ያክል ደመወዝ የሚከፍልበት ሆኖ አደለም። የሆነ ሆኖ፣ በሻህ፥ ከገንዘብ ሚኒስቴርና ካቶ ማንደፍሮ ራሱን የሚያስችለው ደመወዝ እያገኘ ቤት ተከራይቶ ምሽት አገባና፥ አገሩን እያገለገለ የክብር ኑሮ እንደሚኖር ባለጽኑ ተስፋ ሆነ። ብቻ ተስፋ አንድ ነገር የተስፋ፥ ፍጻሜ ሌላ ናቸው!

በሻህ፥ ፋሽስቶች ኢትዮጵያን ከመያዛቸው በፊት፣ ገና ከፉና በጎለመለዬት ያልበቃ ስለ ነበረ የመንግስት አስተዳደር እንዴት እንደ ነበረና የህዝቡ መብት ምን ያክል ይከበር እንደ ነበረ አጣርቶ ባያውቅም ጠላት በስልጣን በቆዬበት ጊዜ፥ በኢትዮጵያውያን ላይ ሲደረግ ያዬው ያመጽ ስራ ሁሉ የነጻነት አለመኖር ያስከተለው መሆኑን ስላወቀ ነጻነት ከሁሉ የሚበልጥ ውድ ነገር መሆኑን አመነ። ስለዚህ ለዚያ፥ ከሁሉ ለሚበልጥ ውድ ነገር ለዚያ ከጥቃት ከውርደት ከንቀት፥ ሁሉ ለሚያድን ውድ ነገር፥ ታጥቆ ለመስራት ቆርጦ ከሱ የበለጠ የነጻነትን ትርጉምና ዋጋ የሚያውቁ ድግሞ የሱን እጥፍ የበለጠ እንደሚሰሩ አምኖ ነበር ስራውን የጀመረ! ነገር ግን የተመደበለትን ስራ እዬሰራ ትንሽ እንደ ቆዬ ስለ ሰራተኞችም ሆነ ስለ ስራው አሰራር የነበረው እምነት እዚያ ሲደረግ ከሚያየው ከውነቱ ጋር ፍጹም የተለዩ ሆነበት! ለስራው ከተመደበው ጊዜ የሚበልጠው ከስራው ጋር ዝምድና ለሌላቸው ባእድ፣ ለሆኑ ጉዳዮች ነው የሚውለው። የበላይ ሹሞች ግቢ ቆይተው ሲመለሱ ለግል፣ ጉዳያቸው በቀጠሮ የሚመጡትን የውጭ ሰዎች ሲያነጋግሩ ከነሱ በታች ያሉት ሰራተኞች በያንዳንዱ ክፍል ተሰብስበው ተቀምጠው ቡና እዬጠጡ ጣሊያኖች ትተውት ከሄዱት ንብረት ማን ምን እንደ ደረሰውና ማን ስአት እንዳለው ሲያወሩ፣ አባቶቻቸው በጦር ሜዳ ወይም ባርበኝነት የሞቱባቸው እንዴት ቢያደርጉ ካሳ እንደሚያገኙ ሲማከሩ ጊዜው ይገደባል! ስለዚህ ለስራው የሚተርፈው ጊዜ እያጠረ፣ በለቱ ሊፈጸሙ የሚገባቸው ጉዳዮች ለማግስት ለሳልስት፣ ለሳምንት ለወር፣ ከዚያም በላይ እስከ ታች ሁሉንም ጠላቸው፤ ናቃቸውና መስሪያ ቤቱን ጥሎ ለመሄድ ወሰነ። ከዚያ ወደ ግንድ ሚኒስቴር፥ ደግሞ ከዚያ ወደ ትምህርት ሚኒስቴር መጨረሻ ወደ ማዘጋጃ ቤት እዬተዘዋወረ አጫጭር ጊዜ ሰርቶ ሁሉንም አዬ። ነገር ግን አንዱ ከሌላው ባይብስ የማይሻል ሆኖ ስላገኘው ለመንግስት ስራ ተስፋ ቆረጠ። በጋብቻ ኑሮውም አልቀና!

የበሻህ ምሽት፥ ፋናየ ከፋሽስት ወረራ፣ በፊት እቴዬ መነን ትምህርት ቤት ፈረንሳይኛና በዚያ ጊዜ ይሰጥ የነበረውን ትምህርት ስትማር ቆይታ፥ በወረራው ጊዜ

በካቶሊክ ሚሲዮን ትምህርት ቤት ገብታ ትምርትዋን ስትቀጥል የቆዬች በፊት መልክዋ ሆነ በደም ግባትዋና በቅርጽዋ እጅግ የተዋበች መሆንዋን የሚያውቁት ሁሉ የሚያደንቁላት፥ ወጣት ወይዘሮ ነበረች። እስዋም ውበትዋን ስለምታውቅና ያድናቂዎችዋ ምስክርነት ስላረጋገጠላት የገዛ ውበትዋ ፍቅር አድሮባት፥ ከገዛ ውበትዋ ጋር ፍቅር ወድቃ ከቀኑ የሚበልጠውን የምታሳልፈው ከሱ ጋር ስትጫወት ስለ ነበረ፥ ለቤትዋና ለባለቤትዋ ጥንቃቄ የሚተርፈው ጊዜ ያጥር ነበር። ከወንዶቹ ውበትዋን ሲያደንቁ ሲያወድሱዋት ሲያመግሱዋት መስማቱ የሚሰጣትን ደስታ ያክል፣ ሌላ የምትፈልገው ያለ አትመስልም ነበር።

በሻህ ጥዋት ለስራ ሲወጣ፣ ልዩ ልዩ አይነትና ቁርጥ አካላቸው ልብሶችዋ ሶስት አራቱን ይዛ መኝታ ቤት ውስጥ ገብታ ቆልፋ፥ እዚያ ካለው ረዥም መስታዋት ፊት ትቆምና አንዱን አውልቃ ሌላዉን ለብሳ ስታይ ደግሞ ያን አውልቃ ሌላዉን ለብሳ ስታይ እንዲሁ እያወለቀ እዬለበሰች ካዬች በሁዋላ በመጨረሻ ከሁሉም ያማረባት የመሰላትን ትለብሳለች። ከዚያ ጠጉርዋን በሻሽ ተሸፍኖ ከታሰረበት ትፈታና ዙሪያ ጥምጥም ሰርታ ታየዋለች። ከዚያ ያን ፈትታ አንድ ጊዜ በግራ አንድ ጊዜ በቀኝ ጐን እያለዋወጠች ከፍላ ታበጥርና የተዘረጋ ያሞራ ክንፍ አስመስላ ትሰራዋለች። ደግሞ ያን አፍርሳ ወደ ግንባርዋ ታበጥርና ባርኔጥዮሽ ሰርታ ታየዋለች። እንዲሁ ጠጉር የሚሰራባቸውን ዘዴዎች ሁሉ እያለዋወጠች እዬሰራች ካዬች በሁዋላ፥ ለለቱ ከሁሉም ያማረባት የመሰላትን መርጣ ትሰራዋለች። ፋና ለብሳው ወደ ውጪ አትወጣም እንጂ ቤት ለቤት የምትለብሰው የወንድ ሱሪ ነበር። እንዲያውም እቤት እቤት ውስጥ ከወንድ ሱሪ በቀር ሌላ ልብስ መልበስ አትወድም። ነጠላ እንኩዋ በላዩ አትጥልበትም! እጅጌ - የለሽ አንገተ - ክፍት ሸሚዝዋን ለብሳ ያን ከገላዋ ጋር ጥ - ብ - ቅ ብሎ የተሰፋ ሰሪዋን ታጥቃ ኮራ ያሉ ደረትዋና ዳሌዋ ከሽንቅጥ ወገብዋ ጋር እንዴት ውብ ሆነው እንደ ተዋደዱ እንዴት ተስማምተው እንደ ተዋሀዱ ከመስታወቱ ፊት ቆማ ያን እጹብ ድንቅ ውበት እያዬች ስትገረም ስትደነቅ ቆይታ ደስ እያላት እዬኮራች ሱሪዋን አውልቃ ታስቀምጥና፣ ለለቱ የመረጠችውን ልብስ ለብሳ፣ ቦርሳዋን ይዛ ወደ ገብያዋ ጭ - ል - ጥ ነው! የምትገዛው ነገር ባይኖራትም ድንገት እክል ደርሶ ካላሰናከላት ገብያውን ሳትሳለመው አትውልም! ገብያ መሄድ ከለት ተግባርዋ አንዱ ነው! እዚያ በዬሱቁ መስኮት እዬቆመች ልብሱን ጌጡን ጫማውን የቤት እቃውን እንዲያው ገብያ መሄድ ከለት ተግባርዋ አንዱ ነው! እዚያ በዬሱቁ መስኮት እይዬቆየች ልብሱ ጌጡን ጫማውን የቤት እቃውን እንዲያው ገበያ ያፈራውን ሁሉ ስንቱን! ስታይ አንዳንድ ጊዜም - ላትገዛ - እዬገባች በዋጋ ስትከራከር ቀኑም እንደስዋ የለት ተግባሩን ስለማይረሳ ይሄዳልና ሄዶ

ታገኘዋለች! ከዚያ እዬቸኮለች እንደ ሄደች እዬቸኮለች ስትመለስ ብዙ ጊዜ በሻህ ከመግባቱ ትንሽ ቀደም ብላ አንዳንድ ጊዜ ትንሽ ዘግየት ብላ ትደርሳለች። ብቻ ትንሽ ብትቀድም ትንሽ ብትዘገይ ምንጊዜም ቢሆን በሻህ ለምሳ የበሰለ ወጥ መብላቱ ቀርቶዋል! ከዋለችበት ስትመለስ ረጋ ብላ ለብሳው የዋለችውን ልብስ አውልቃ ሱሪውን ታጥቃ፣ ከመስትዋቱ ፊት ቆማ ውበትዋን ከፊትዋም ከሁዋላዋም እያዬች አድንቃ፥ ከዚህ በሁዋላ ነው፥ ሰራተኛዋን ወጥ እንድትሰራ የምታዝዛት። ስለዚህ ወጡ ገና መፍላት ሲጀምር ወጥቶ ይቀርብለትና በሻህ ያን በልቶ እያቃረው ወደ ስራው ይሄዳል ወይም ሳይደርስ ይቀርና ጭራሽ ሳይበላ ይሄዳል።

የበሻህና የፋናየ ሰራተኛ ያበሻ ወጥ አታውቅም እንጂ የጣሊያን ወጥ ስራ አዋቂ ጥሩ ሰራተኛ ነበረች። እስዋ አስባ ስትሰራ በሻህ ጥሞት ተስማምቶት ይበላ ነበር። ነገሩ ሁሉ የተበላሸ ፋናየ፣ ያበሻ ይሁን የፈረንጅ ወጥ ስሙን ካልሆነ ስራውን የማታውቀውን በሻህ ፊት የምታውቅ ለመምሰል ብች ‹ይህን ለምን ሰራሽ? ያን ለምን አልሰራሽ?› እያለች መዘባረቅ ከጀመረች በሁዋላ ነው። ሰራተኛዋ የበግ ወይም የዶሮ ‹አሮስቶ› ሰርታ ያቀረበች እንደሆነ።

« ‹ቦሌቶ› አትስሪውም ኖሮዋል? ለምን ‹አሮስቶ› ሰርሽው? » ትላታለች። በማግስቱ ‹ቦሌቶ› ሰርታ ስታቀርብ ‹አላካቻቶሬ› ብትሰሪው ምን ቸገረሽ ኖሮዋል? » ትላታለች።

‹አላካቻቶሬ› ሰርታ ስታቀርብ፥

«አንቺ እንዲያው - ያለ በግና ያለ ዶሮ ሌላ አታውቂም? ለምን ‹ፓስታ አልፉርኖ› አትሰሪ? » ትላታለች። ‹ፓስታ አልፉርኖ› ሰርታ ስታቀርብ፥

« ‹አሁን - ፓስታ ሳልታታ አልቡሮ ብትሰሪው ሳይቸግርሽ!› » ትላታለች። ከዚያ በሁዋላ፥ ሰራተኛዋ ቸገራትና ከመስራትዋ በፊት የሚሰራውን የምግብ አይነት እመቤትዋ እዬነገረቻት ብትሰሪ የሚሻል መሆኑን አመልክታ፥ በዚህ ሁለቱ ተስማሙ። እንገር ግን ፋናየ መጀመሪያ ከውበትዋ ጋር መጫወቱ ከዚያም ወደ ገበያ መቸኮሉ እያስረሱዋ ለምሳ ምን ወጥ መስራት እንደሚገባ ሳትናገር ስለምትሄድ ሰራተኛዋ ሌላ ስራዋን ሁሉ ታጠናቅቅና እክፍልዋ ውስት ተቀምጣ፥ የመቤትዋን መምጫ መንገድ በመስኮት እያስወጣች እያዬች ስትጠብቅ ትውላለች።

በመሀከሉ በሻህ ጠባም ተቸገረ። የሚቀርብለትን ያልበሰለ ወጥ ዝም ብሎ ሲበላ ድሮ የሚያውቀው ብርቱ ቃር እያመመው ቃሩን፣ ፈርቶ ሳይበላ ሲሄድ እዬበራው

ችግሩን ካፉ አውጥቶ ለምሽቱ እንዳይናገር ስሜትዋን የሚቆስልና የሚያስቀይማት እዬመሰለው የሚያደርገው ቅጡ ጠፋው። ታዲያ ነገሩ እንዲሁ ታፍኖ በቆዬ መጠን ቂም ሆነና ውስጥ ውስጡን ይጠላት ጀመር! ውስጥ ውስጡን እንዳልበሰለ ወጥ ታቅረው ጀመር!

ፋናየ በበኩልዋ ገብቶ ቁጭ ሲል፣ ያን ጊዜ እግዚአብሄር አሳምሮ የሰራውን ሰውነትዋን እንዲያ ተጨንቃ ተጠብባ፥ ይበልጡን አሳምራ፥ በፊቱ ወገብዋን እዬሽረሽረ ያለጉዳይዋ ከወዲህ ወዲያ ከወዲያ ወዲህ እዬተመላለሰች እ - ፍ - ስ አድርጎ በጭኑ ላይ አስቀምጦ ውበትዋን እያደነቀ እንዲያቀብጣት እንዲያቆላምጣት እንዲያመልካት፣ ስትፈልግ፣ እሱ አንድ ትንሽ ፈገግታ እንኩዋ ነፍጎዋት ኮሶ ያገሳው ይመስል ፊቱን አከፍቶ ‹እንዳትናገር› የተባለ ይመስል አፉን ዘግቶ ስታዬው ግ - ል - ፍ ይላትና ‹ጫማሽን አውልቀሽ አፍን - ጫውን በለሽው ሂጂ!› የሚላት ሰይጣን ይመጣባታል! ብቻ ጊዜያዊ ግልፍታ ነው እንደሱ ተከድኖ ታፍኖ የሚፈላ መራራ ቂም አደለም! ግልፍታዋ ሲያልፍ ከሱ መልስ አታገኝም እንጂ ወደ ማባባልዋ ትመለሳለች!

አንድ ቀን በሻህ እመስሪያ ቤቱ ሰርቶ አለቃው እንዲፈርምበት ያቀረበለት ጉዳይ እዚያ በጠረጴዛው ላይ ተቀመጦ ደጅ ሲጠና ስማንት ካለፈ በሁዋላ በመጨረሻ እንዲያውም ‹ጠፋ› ስለ ተባለ በዚያ ሲበሳጭ ቆይቶ ወደ ቤቱ ሲሄድ፥ ምሽቱ ከሄደችበት ባለመመለስዋ ምሳ ገና አለመሰናዳቱን ሰራተኛው ነገረችው። ያን ጊዜ ብስጭቱ ወደ ብርቱ ቁጣ ተለወጠና፣

«እስዋ ባለመኖርዋ ምሳ የማይሰራበት ምክንያት ምንድነው? እስዋን ኖሮዋል ለምሳ የምትሰሪያት? » አለ በሻህ አይኖቹ በቁጣ እንደ ትንታግ ቀልተው ሰራተኛዋን ሊመታ እዬቃጣ። ታዲያ መስሪያ ቤት ካበሳጨው ነገር ጋር ተጨምሮ ያን ያክል አስቆጣው እንጂ፣ ምሽቱ በጊዜ ባለመግባትዋ ምሳ ሳይበላ ወደ ስራው ተመልሶ መሄድ አዲስ አልነበረም፤ የተለመደ ነበር።

«ኸረ አደለም ጌታየ የምሰራውን - እንዲነግሩኝ - ብዬ ነው» አለች ሰራተኛዋ ደንግጣ እዬተንቀጠቀጠች።

«እ - ! የምትሰሪውን እንድነግርሽ! እስዋ እያስተማረችሽ ልትሰሪ ነው በደመወዝ የተቀጠርሽ? » ሰራተኛዋ በሻህን እንዳያንለቱ ሲቆጣ አይታው አታውቅም! እቤት እንደያንለቱ ተቆጥቶም አያውቅ!

ያች ፍራት የሚያንቀጠቅጣት ሰራተኛ ወደ ማድ ቤትዋ ተመልሳ ምን እንደምትሰራ መወሰን ተስኖዋት ስትርበተበት ፋናየ ደረሰችና በሻህ ወዳለበት ሳትሄድ በቀጥታ ወደ ማድ ቤት ሄደች። እዚያ በጣም፥ መቆታቱን ስትሰማ እንደ ልማድዋ ለብሳው የዋለችውን ልብስ አውልቃ ሱሪዋን ለመታጠቅ ወደ መኝታ ቤት በመግባት ፈንታ፣ ወደሱ ሄደች።

«በሹ፥ በሽዬ፥ ዛሬ ምሳህን ምን ትበላ? » አለች፥ ወንበሩን ወይ ሁዋላ ተደግፎ በተቀመጠበት በሩን በከፊል ከፈት አድርጋ፣ አንገትዋን አስገባችና። አብርወ እንደዋሉ ሁሉ «ሰላም» እንኳዋ አላለችም! ለጠዬቀችው መልስ በመስጠት ፈንታ፣

«ስሚ» አለ በወንበሩ ተንጋሎ ከተቀመጠበት ተቃንቶ ቁጭ ብሎ።

«ወዬ» አለች ፋናየ በከፊል የከፈተችውን በር ገብታ ወደ ሁዋላ ዘጋችና።

«በተፈጥሮ ወንድ ያልሆንሽውን ሱሪ ታጥቆ መወላገዱ ብቻ ወንድ አድርጎ የወንድ ተግባር ሊያስፈጽምሽ እንደማይችል መቸም የታወቀ ነው! በትምህርት የሴቶችን ተግባር አውቀሽ እንደማትሰሪ ደግሞ - ይኸው፣ ታወቀልሽ! ታዲያ እንግዲህ - እኔና አንቺ ምንና ምን ተብለን ነው እዚህ ቤት አበርን የምንኖር? » አለ በልቡ ውስጥ ተዳፍኖ የቆየውን የጥላቻና የቂም እሳት የለቱ ቁታ አቀጣጥሎት በፊቱ ሁሉ ላይ ሲነድ እዬታዬ።

«እኔ እንጃልህ! ምንና ምን ተብለን እንድንኖር ኖሮዋል ያገባኸኝ? ጌታና ገረድ ሆነን እንድንኖር አስበህ ኖሮዋል? አሳብህ እሱ ኖሮ እንደሆነ በጣም ተሳስተሀል! እኔ ስፈጠርም ስማርም ለግርድና የተመደብሁ አደለሁ! እኔ ፋናይቱ ግርድና ቢቀርብኝ ሌላው ሴትነት ታውቃለህ? ጥሩ ሴት! » አለች በብርቱ ቁጣ ግራ ቀኝ እጆችዋን በዳሌዋ ላይ አድርጋ ራስዋን እዬነቀነቀች።

«አይዲያ! አላዬን ጥሩ ሴት! ሴቱ ሁሉ እንዳንቺ ከሆነ ወዲያ በጠበል» አለ ከንፈሩን አበላልጦ።

«እላዬን ወንድ እቴ! ወንዱ ሁሉ እንዳንተ ከሆነ በጠበል ወዲያ! » አለች ፋናየ መልሳ።

«እ - ንዲያ ነው እንጂ! » አለና በሻህ ሊመታት ሲነሳ ሮጣ፥ ወጣች።

«እቃሽን ለመውሰድ ካልሆነ፥ ‹ቤት አለኝ› ብለሽ ወዲህ እንዳትመለሺ» አለ ተከትሎዋት ወጥቶ።

«ያቡን አማልጅ ይዘህ ብትመጣ፥ እኔ ፋናይቱ ወደዚህ ቤት አልመለስም! አንተም ቤትህም እክ እ - ትፍ» አለች ፋናየ፥ ወገቡዋን በሁለት እጆችዋ እንደ ያዘች፥ ተንጠራርታ አንገትዋን በሀይል ወደ ፊት ወርወር አደረገችና።

በሻህ ከምሽቱ መለያየቱን ላቶ ማንደፍሮ ሲነግራቸው በጣም አዘኑ።

«መልከ መልካም ከመሆንዋ በላይ፥ ትምህርት ያላት መሆንዋን ስትነግረው፣ ‹መልካም እድል አጋጠመህ› ብዬ ደስ ብሎኝ ነበር። ለመሆኑ ለመለያየት የሚያደርስ ምን ችግር ተፈጠረ? እኔ ለመርዳት የምችልበት መንገድ ይኖር ይሆን? » አሉ አቶ ማንደፍሮ የሳቸውን፣ አማላጅነት ወይም የገንዘብ ርዳታ ፈልጎ የነገራቸው መስሎዋቸው።

«የለም እግዚአብሄር ይስጥልኝ አባባ፤ እስዎ የሚረዱበት ምንም መንገድ የለ። የስዋ ትምህርት የናቶችዋ የሆነውን ሁሉ አስንቆ፥ ያባቶችዋን የሚያስመኝ፣ ከንቱ ትምህርት ነው። ‹መልከ› ያሉት ደግሞ - እኔ እንጃ? ምናልባት የኔ አስተሳሰብ ጊዜ ያለፈበት እንደሆነ እንጂ፥ እንደኔ አስተሳሰብ ከሆነ የሴት መልከ ‹ጥሩ› የሚባለው ከሙሉ የሴትነት ጠባይ ጋር ሲሆን ነው። የሴትነት ጠባይ የጎደለው ጥሩ የሴት መልከ ደም በውስጡ እንደማይዘዋወርበት ቀዝቃዛ ጥሩ የሴት ምስል ነው! እስዋ አድርጎትዋና ሁኔታዋ ሁሉ ወይም አሁን እንዳልሁዎ ጠባይ ወንድ ለመምሰል ስለሆነ እንጂ፣ ሴት አልመስለኝ አልች ገባች!

«እንዲያማ - አንተ ነህ ያልፈልገሁት! »

«አዎ፤ እኔ ያልፈልገሁዋት። እኔ በሴትነትዋ አምና፥ በሴትነትዋ ኮርታ በሁኔታዋ በጠባይዋ ሁሉ የሴትነት ክብርዋን ለማስከበርና የሴትነት ውበትዋን ለማይወደድ የምትጣጣር ሴት እንጂ ወንድ ለመምሰል የምትጣጣር ሴት ወንድ ስለምትመስለኝ አልወድም፤ ይገርምዎታል አባባ። እንኩዋንስ እስዋን እንደስዋ የሚለብሱና እስዋ የምታደርገውን አንዳንድ ነገር የሚያደርጉ ሴቶች እንዲሁ በሩቁ ሳይ እጠላ ጀመር! »

## 5. ‹የጨለማዉ ንጉስ› በሻህ

በሻህ ከምሽቱ እንደ ተለያዩ፥ የመንግሥት ስራም ለቅቆ፣ አቶ ማንደፍሮን እዬረዳ፣ ፊት ይከፍሉት በነበረው ላይ 25 ብር ጨምረው 150 ብር የወር ደመወዝ እዬተሰጠው ምግቡና ማደሪያው እዚያው ሆኖ፥ ከሳቸው ጋር ተቀመጠ።

አቶ ማንደፍሮ የከበባቸው አባሎች ከሆኑት ጉዋደኞቻቸው ጋር ማታ ማታ እዬተሰበሰቡ በልዩ ልዩ ያገርም ያለምንም ጉዳዮች፥ ላይ ሲነጋገሩና ሲከራከሩ በሻህ እዬተከታተለ የሚስማቡባቸውን ፍሬ ነገሮች ጽፎ በዬማህደራቸው ማስቀመጥ ከስራው አንዱ እንዲሆን ስለ ተደረገ ያንጊዜ ያገኘውን ያክል ትምህርት ከዚያ በፊትም ሆነ ከዚያ በሁዋላ አግኝቶ አያውቅ! በዚህ ላይ አቶ ማንደፍሮ መጻህፍት ቤት ውስጥ ካገኛቸው ልዩ ልዩ መጻህፍት ብዙ ተማረ። በተለይ ባንዳንድ አገሮች በክፉ ስራተ - ማህበራቸው ላይ ያመጹ ሽፍቶች ስለ ሰሩዋቸው የሚያስደንቁ ስራዎች የተጻፉ መጻህፍት አግኝቶ ሲያነብ ልቡ በጣም ተማረከና ራስ የመሸፈት ምኞት አደረበት! በፋሽስት ወራር ጊዜ ባደራ የተቀበሉትን ስልጣን ላገር መጉጃና ለግል ጥቅማቸው ማሳደጊያ የሚያደርጉትን ሁሉ መቅጣት!

ይህ የመሸፈት ምኞቱ እዬዋለ ሲያድር እዬበረደና እዬተረሳ በመሄድ ፈትና፣ ባሳቡ ቅርጽ እያበጀ፣ መልክ እዬያዘ ይሄድ ጀመር። ነቅቶ ሳለ ባሳቡ ሲተኛ በልሙ የሚታየው ወሮበሎች ጉዋደኞቹን አደራጅቶ፣ በዬመስሪያ ቤቱ ሲዞር በወደቀ አስከሬን ላይ እንደሚረፋረፉ ጆፎ አሞሮች፥ ጣሊያን ትቶን በሄደው ንብረትና ባገር ሀብት ላይ ሲረፋረፍ የተመለከታቸውንና እንደሱ የተመለከቱትን የነገሩትን ሹሞችና ሰራተኞች መቅጥት! ከውቀትና ከችሎታ ይልቅ የዝምድና ሀረግ ስበው ወይም ልዩ ጥቅም ይዘው የሚቀርቡትን ለስራ ሲመርጡ የተመለከታቸውን ባለስልጣኖች መቅጣት! ፍርድን ለገንዘብ ወይም፣ ለሌላ ልዩ ጥቅም የሚሸጠውን ዳኞች መቅጣት! ባጠቃላይ እንዲሁ ያሉትን ባገር ሀብትና በመንግስት ስራ እንደ ግል ወረታቸው የሚነግዱትን በደለኞች ሁሉ እንደየበደላቸው መጠን መቅጣት ነበር! እንዲያ ያሉትን በደለኞች ሁሉ እንደዬበደላቸው መጠን፣ እንዳይሞቱ አድርጎ ማ - ጅራቱን ማጅራታቸውን እዬመቱ ወይም አገርና ህዝብ ለመበደል የተቀበሉትን ዋጋ እዬቀመሱ ወይም ቤት ንብረታቸውን እዬዘረፉ ያን አይነት ቅጣት የተቀጡበትን ምክንያት ዝርዝር አድርጎ ጽፎ በልብሳቸው እያጠበቁ፣ ቀይም በቤታቸው ግድግዳ ላይ በስተውጪ እዬለጠፉ መተው! እንዲህ የተደረገ እንደሆነ - እንደ በሻህ አስተሳሰብ - ‹ከሚደርስባቸው ጉዳት በላይ፣ አስጸያፊ ነው ራሳቸውን ገልጾ ለሰው ሁሉ ስለሚያሳይባቸው፣ እንዲያ ያለ ስራ ደግመው

አይሰሩም፤ ሌሎችም ያን የመሰለ ጉዳትና ውርደት እንዳይደርስባቸው ክፉ ከመስራት ይቆጠባሉ!›

በሻህ ይህን አሳብ ካስራ አስምት ቀና በላይ ሲያወጣ ሲያወርድ፣ ሰንብቶ አንድ ቀን ላቶ ማንደፍሮ ሲነግራቸው፣ መጀመሪያ ‹የልጅ አሳብ ነው› ብለው ሳቁ።

አቶ ማንደፍሮ ከፋሽስት ወራራ በሁዋላ የኢትዮጵያ መንግስት ወደ ስልጣኑ ሲመለስ የትምህርት ሚኒስትር የሆኑት ባለስልጣን፣ ለትምርት አመራር አማካሪዎች እንዲሆኑ መርጠው ከሰበሰቡዋቸው የኢትዮጵያ ሊቃውን አንዱ ነበሩ። እኒያ ሚኒስትር ‹ከጥንታዊው የኢትዮጵያ ትምህርትና ባህል፣ የሚጠቅመው እዬተያዘ፣ የሚጎዳው እዬተጣለ የሚሻሻለው እዬተሻሻለ ዘመናዊ፥ የጥበብ ትምህርት በዚያ ላይ ተመስርቶ የጎደለውን እዬሞላ የሚሄድ መሆን አለበት› ብለው የሚያምኑ ስለ ነበሩ፣ አቶ ማንደፍሮንና እንደሳቸው ጠለቅ ያለ የኢትዮጵያም የውጭም አገር ትምህርት ያላቸውን በርከት ያሉ ሊቃውንት ላማካሪነት ቀጥረው ነበር። ነገር ግን በትምህርት አመራር ምክር ቤት ውስጥ ከነበሩት የሚበዙት ጥንታዊዉን የኢትዮጵያ ትምህትም ባህልም፥ ስለሚያውቁ የሚንቁ ዘመናውያን ስለ ነበሩና እነሱ ‹ኢትዮጵያ ቶሎ ዘመናዊት አገር እንድትሆን ከጥንታዊዉ ትምህርትዋና ባህል ገልብጣ መያዝ ያስፈልጋታል› ብለው ባንድ ላይ፣ የበርሀ አውሎ ንፋስ እንዳስነሳው ደረቅ አሸዋ ድምጻቸውን ሲያንጫጩ፣ እንኩዋንስ እናቶ ማንደፍሮን ሚኒትሩንም አንደንግጠው ዝም አሰኙ። ያን የዘመናውያን አሳብ መንግስቱም የሚደግፈው ስለ ነበረ፣ ሚኒስትሩ ወደ ሌላ ስራ ተዛወሩ። አቶ ማንደፍሮ ከሊቃውንቱ የሚበዙት በመንግስት አዝነው ‹እግራቸውን ከዚያ ደረቅ አሸዋ እያረጋፉ ጥለው ወጡ! ‹አቶ ማንደፍሮ ከጉዋደኞቻቸው ጋር ክበባቸውን አቆቁመው ምግብ ቤታቸውን እዬተቆጣጠሩ ተቀመጡ። እንዲያ በመንግስት አዝነው ተስፋ በመቁረጥ አፋፍ ላይ በተቀመጡበት ጊዜ ነበር በሻህ የሚያደፋፍሩት መስሎት፥ የሽፍትነት አሳቡን ያካፈላቸው።

«ህእ! ‹የልጅ አሳብ ነው› አሉ? የልጅ አሳብ አደለም፤ ያዋቂ አሳብ ነው አባባ! » አለ በሻህ ‹የልጅ አሳብ ነው› ብለው ሲስቁ ትንሽ ቅር ያለው መሆኑ ከፊቱ እዬታዬ።

«እሺ ‹የልጅ አሳብ ማለቴን ከጠላህብኝ የተቸገረ ይይዘውን ያጣ አዋቂ፣ ከንቱ ልበለው! » አሉ አሁንም እዬሳቁ።

«የለም የልጅ አሳብም የጨነቀው አዋቂ ከንቱ ምኞትም አደለም አባባ፤ እንዲህ ሆኖ ሊቀጥል ስለማይችል አንድ ነገር መደረግ አለበት! »

«እኮ ታዲያ - ሹማምትና ሰራተኞች ተግባራቸውን በትክክል ሳይፈጽሙ ወይም ሲበድሉ የሚቀጣ መንግስት ነው እንጂ አንተ ነህ? »

«መንግስት ማነው? መንግስት ማለት - ሚኒስትሮች ዳኞች፣ የጦር አለቆችና፣ - እነሱን የመሰሉት ለመንግስቱ ስራ ሁሉ አላፊቱን የያዙት አደሉም? ታዲያ በደለኞች እነሱ ራሳቸው እነሱ ራሳቸው ሲሆኑ ከነሱ፣ በላይ የሚቀጣ ማን ኖሮ ‹አቤት› ይባልባቸዋል? ከነሱ በላይ - እናንተ እዚህ እዬተሰበሰባችሁ ሁልጊዜ ስትነጋገሩ እንደምሰውማ ከሆነ - ህዝብ ነው። ህዝብ ማለት ደግሞ እኛ ነን። ወይስ - በኔ አፍ ስለ ተነገረ ብቻ ነገሩ ተለውጦ ሌላ ይሆናል? »

«ከሹማምንትም ሆነ ከሰራተኛ ሁሉ የበላይ ህዝብ መሆኑ የመንግስቱን ስልታን የያዙት ሹሞችና ሰራተኞች ተግባራቸውን በሚገባ ሳይፈጽሙ ቢቀሩ ለመቅጣት የመጨረሻ መብት ያላቸው ህዝብ መሆኑ የማያጠያይቅ እውነት ነው። ነገር ግን ህዝብ ማለት ጠቅላላው ህዝብ ማለት ነው እንጂ አንተና እኔ ብቻ አደለንም፤ ወይም አንተና ሁለት ፍሬ ጉዋደኞችህ ብቻ አደላችሁም። ብቻ ችግሩ ጠቅላላው ህዝብ መንግስቱን ከሚያስተዳድሩት ባለስልጣኖች የበላይ መሆኑን እስኪያውቅና ተግባራቸውን ባይፈጽሙ ተባብሮ የመቅጣቱ አላፊነት የሱ ብቻ መሆኑን ተምሮ እስኪረዳ ገና ብዙ ያስፈልጋል። ይህ ነው ችግሩ፤ ለዚህም ነው - ‹አሳብህ ሊሆን የማይችል፣ የልጅ አሳብ ወይም ያዋቂ ሰው ከንቱ ምኞት ነው› ያልሁህ።»

«ሊሆን የማይችል አደለም፥ ሊሆን የሚችል ነው፤ ሲያስቡ ትንሽ ቆይተው «ሊሆን የሚችል አደለም እንጂ፣ ሊሆን ቢችል አንኩዋ በጣም ከፉ ነው» አሉ።

«እንዴት? »

«አላማህን አደለም ‹ከፉ ነው› ያልሁ። አላማህ ግብህ፥ መልካም መሆኑን አውቃለሁ። ነገር ግን ለመልካም አላማም ቢሆን ማጅራቱ መምታት ማቁሰል፣ መቀማት መዝረፍ መግደልም ሊደርስ ይችላል፤ ይህ ሁሉ በጣም ከፉ ስራ ነው። ‹ከፉ መንገድ እመልካም ግብ አያደርስም ልጄ! ከፉ ስራ እድኑ ተኮስቱ ጥይት አላማውን ይገላል! ‹ከፉ ስራ ስርቶ መልካም ውጤት አገኛለሁ› ማለት እንክርዳድ ዘርቶ ስንዴ ለማምረት እንደ መመኘት ነው! ደግሞስ - » አሉ፤ አሁንም ትንሽ ዝም ብለው ሲያስቡ ቆይተ «እኒያ» ጉዋደኞቼ፣ ያልካቸው ይህን ከፉ ስራ አብረውህ የሚሰሩት ሁሉ አላማቸው ካንተ መልካም አላማ ጋር አንድ መሆኑን እንዴት ታውቃለህ? ከፉ አላማ

ያላቸው ይህን ከፉ ስራ ለከፉ አላማቸው የሚያውሉ አለመሆናቸውን እንዴት ታውቃለህ? »

«ብዙዎችን - ራሴን የማውቀውን ያክል ደህና አድርጌ አውቃቸዋለሁ። ላርበኛነት ከመውጣታችን በፊት እዚህም ባርበኝነትም አላማየን፣ አላማቸው አድርገው አብረውኝ የሰሩ፣ በጣም የማምናቸው ናቸው። ሌሎች አላማችን እዬተገለጸላቸው ሲያምኑበት በብርቱ ጥንቃቄ የሚመረጡ ናቸው።»

«መጀመሪያ - ሁሉም፥ ‹ላማህ አላማችን ነው› እያሉ ምለው ተገዝተው ነው የሚገቡ! ነገር ግን ሲያስቡ ነው! ማንም ቢሆን፥ የግል ጥቅሙን ካላዬ ያገሩን ደህንነትና የህዝቡን መብት ብቻ አላማ አድርጎ ለነሱ ብቻ ብሎ እንዲህ ያለ የእስራት የመሰቃየትና፣ የሞት አደጋ ሁሉ ተሰብስቦ የከበበው ስራ ለመስራት ወዶ የሚገባ የለም! ያገርን ደህንነትና የህዝብን መብት ለማስከበር ብቻ ብሎ እንዲህ ያለ አደጋ የከበበው ስራ ለመስራት ለሚያምንበት አላማ ህይወቱን የሚሰጥ ሰማእት መሆን፣ በሻህ ዘለሌ መሆን ያስፈልጋል! ነገር ግን ሰው ሁሉ እንዳንተ አይምሰልህ ልጄ! እኒያ ‹አላማህ አላማችን!› እያሉ የሚሰበስቡት ሁሉ ሲያብሉ ነው! አንዱ ማጅራት መትቶ ገንዘብ ለመቀማት እንዱ ቤት ንብረት ለመዝረፍ ሌላው ቂም የያዘበት አለ እንደሆነ ቂሙን፣ ለመወጣት ደግሞ ሌላዉ የሚቀናበት እንደሆነ፥ እሱን ለማጥፋት እንዲህ ለተለያዩ አላማቸው የሚሰበሰቡ ናቸው! ታዲያ ለዚህ ሁሉ ሌሎች ለከፉ አላማቸው የሚሰበሰቡ ናቸው! ታዲያ ለዚህ ሁሉ ሌሎች ለከፉ አላማቸው ለሚሰሩት ከፉ ስራ ሁሉ ባለዳው አንተ ትሆናለህ! ከዚህ በሁዋላ መውጣ ብትፈልግ እንኩዋ አትችልም! ካንድ ወገን እኒያ ጥቅማቸውንና ኑሮዋቸውን በዚያ ከፉ ስራ ላይ የመሰረቱ ሁሉ አይለቁህም። ከሌላ ወገን ስራው ራሱ ያስርሀል። ከፉ ስራ አለ መስራት ነው እንጂ፥ ከተሰራ ከፉ ነው፤ አይለቅም። እስረኛ ያደርጋል! ስለዚህ ይህን ከፉ ስራ ባትጀምረው ይሻላል» አሉ አቶ ማንደፍሮ።

በሻህ ‹ላመነበት እንደ ሰማእት ህይወቱን የሚሰዋ› ለመሆኑ ያቶ ማንደፍሮ ምስክርነት ሲሰማ ከሰዎች ተራ ወጥቶ በእማእታት ተራ የቆመ መስለውና የሰማእታት ጉዋደኛ የሆነ መሰለውና የደታና የኩራት ስሜት በሰራ አካላቱ ተሰራጭቶ ሞቅ ሲያደርገው ተሰማው። እንዲያ ባለ ስሜት ውስጥ እንዳለ አንገቱን ደፍቶ፣ አቶ ማንደፍሮ ያሉትን ሲያሰላስል ቆይቶ፣ ያን ‹አደጋ ሁሉ ተሰብስቦ የከበበውና መንገድ

እንዳይከተል› የመከሩትን ምክር ‹ላመነበት ይህወቱን የሚሰዋ ሰማእት› በመሆኑ ያመሰገኑት ምስጋና አሸንፎ፣ ያሰበውን፥ እግቡ እንዲያደርስ ገፋፋው።

«ቅድም - ‹ከፉ መንገድ እመልካም ግብ አያደርስም አሉኝ›፥ አባባ! » አለ ፈገግ ብሎ ቀና አለና።

«አዎ፤ ታዲያስ? » አሉ አቶ ማንደፍሮ፥ ‹ምን ልታመጣ ይሆን? » በሚል አስተያየት ፈገግ ያለ ፊቱን አተኩረው እዬተመለከቱ።

«ነጻነት መልካም ነው፤ ጦርነት ግን - መግደል ማቁሰል፣ መዝረፍ፥ መግፈፍ ይህን ሁሉ ስለሚያስከትል - ከፉ ነው! አደለም? »

«ልክ ነው! »

«ታዲያ - ያ ከፉው ጦርነት ተደርጎ በመገደል በማቁስል መሳሪያ በመግፈፍና ንብረት በመዝረፍ አደለም - ያ መልካሙ ነጻነት የተገኘ? »

«አ - ! እሱ ሌላ ነው! እሱ ካጥቂ፣ ለመከላከል የተደረገ ጦርነት ነው! ጦርነት ከፉ ስራ ቢሆን፣ ካጥቂ ለመከላከል የሚሰራ ከፉ ስራ ሁሉ የተባረከ ከፉ ስራ ነው! » አሉ አቶ ማንደፍሮ እንደ መሳቅ ብለው።

«ቀልድ አይምሰልህ፣ እውነቴን ነው» አሉ ቀጠሉና፣ «ለማጥቃት የሚደረግ ጦርነት እብሪት የሚወልደው ለመከላከል የሚደረግ ጦርነት የተፈጥሮ ህግ የሚያስገድደው ናቸው! »

«እንዴት? »

«ለመከላከል የሚደረግ ጦርነት የተፈጥሮ ህግ የሚያስገድደው መሆኑን ማሰብና በሚችሉ ሰዎች ብቻ ሳይሆን በደመ ነፍስ በሚመሩ ህጻናትና እንስሳት ተመልክቶ መረዳት ይቻላል። ለምሳሌ የሚነድ እሳት ይዘህ ወዳንድ ህጻን ብትቀርብ ለመከላከል ትናንሽ እግሮቹንና እጆቹን ሲያወራች ታያለህ። ዱላ ይዘህ አንድ ውሻ ለመምታት ብትነሳ ፈሪ እንደሆን ሲሸሽ ደፋር እንደሆን ሊነክስህ ጥርሱን እያገጠጠብህ ታያለህ። እንዲሁም ከመንገድ የወጣ ጉዳት ልታደርስባቸው መፈለግህን ካወቁ በሬ ሊወጋህ ቀንዱን ሲያዞርብህ በቅሎ ልትረግጥህ የሁዋላ እግሩዋን ስታነዝርብህ ታያለህ። እጽዋት እንኩዋ ርሀብ ጥም ብርቱ ሀሩርና ቁር ጉዳት እንዳያደርሱባቸው በሳር በቅጠላቸው ሲከላከሉ ታያለህ። እንዲህ ሰው ብቻ ሳይሆን ህይወት ያለው ፍጥረት ሁሉ ካጥፊ

ለመከላከል ለመኖር የማያቋዋርጥ ጦርነት እንዲያደርግ የተፈጥሮ ህግ የጣለበት ግዴት ነው ማለት ነው! » አሉ እንደገና ሳቅ ብለው።

«እኔ ላምድረግ ያሰብሁትም እስዎ ካሉት የተልዬ አደለምኮ፤ አንድ ነው! »

«እንዲደት አንድ ይሆናል? »

«የኢትዮጵያ ህዝብ በገዛ አገሩ እንደዬችሎታው ሰርቶ የመኖር ህግ የሚፈቅድለትን ትክክለኛ ፍርድ የማግኘት ለሚከፍለው ደመወዝ ተገቢ አገልግሎት የማግኘት መብቱን በሚቀሙት አጥቂዎች ላይ የሚደረግ ጦርነት አሁን ካሉት ጦርነት ጋር አንድ አደለም? አንድ ነውኮ! አጥቂዎች ኢትዮጵውያን መሆናቸው ብቻ ክፉ ስራቸውን መልካም አያደርገውም! » አለ በሻህ በስጨት ብሎ። ሁኔታው ሁሉ ያቶ ማንደፍሮን ምክር ተቀብሎ ያሰበውን የሚተው አይመስልም ነበር። አቶ ማንደፍሮ ‹ውሎ አድሮ፥ ብስጭቱ እያለፈለት ሲሄድ አሳቡን ይለውጥ ይሆናል› ብለው ያነለት ምክሩንም ሆነ ክርክሩን አለ መቀጠሉ የሚሻል ስለ መሰላቸው ዝም አሉ። ነገር ግን ውሎ አድሮ በማግስቱም በሳልስቱ በሳምንቱም ሳያዩት ስለ ሰነበቱ ቢያስጠይቁ ቤቱ ሳይከፈት ተዘግቶ መሰንበቱን ሰሙ። ወዲያው በተመሳሳይ መክፈቻ አስከፍተው ቢያዩ በሻህ የለም! አንድ የተዘጋ አንቨሎፕ ብቻ በጠረጴዛው ላይ ማስመሪያ ተጭኖበት ይታያል። በላዩ ‹ለክቡር አቶ ማንደፍሮ ባንቴ? ተብሎ ተጽፎበት ይታያል። ማንደፍሮ ቀ - ስ ብለው እንደ ታቦት በጥንቃቄ አነሱና እሽቱን ከፍተው እነበቡት።

«ክቡር አባቴ አቶ ማንደፍሮ ባንቴ፣ም

«ተገናኝተን ቡራኬዎን ተቀዬል ሳልሰናበትዎ በመሄዴ በጣም አዝናለሁ። ወደ ወላጆቼ አገር ወደ መንዝ፣ ሂጄ፥ የማውቃቸውን ዘመዶቼን ለመጠዬቅና ከማላውቃቸው ለመተዋወቅ ማሰብ የጀመርሁበት ጊዜ ቆየት ብሎቃል። አሁን ባጋጣሚ ከዚያ የመጡ፣ የማውቃቸው ሰዎች አግኝቼ፣ ‹መሄድ ካሰብህ እኛ እናደርስሀለን› አላሉኝ ተሰናብቸዎ ለመሄድ ብመጣ ወጥተው ቆዩኝ። እስኪመልሱ እንዳልጠብቅም የሚወስዱኝ ሰዎች ሊያመልጡኝ ሆነ። ስለዚህ በዚች ደብዳቤ ልሰናበትዎ ተገደድሁ።

«ክቡር አባቴ ሆይ እስከ ዛሬ ድረስ በኑሮም በምክርም፣ ያደርጉልኝን ያባትነት ርዳታ እኔ መቸም የምመልስበት አቅም ስለሌለኝ እግዚአብሔር እንዲመልስልዎ ጠዋት ስነሳ ማታ ስተኛ የማላስታጉለው ጸሎቴ መሆኑኑ ስገልጽልዎ እንዲያምኑኝ

እለምንዎታለሁ። የምሄድበት አገር ምንም ተወልጄ ባላድግበት አገሬ ነውና ትንሽ እዚያ ቆይቼ የምችለውን ያክል ካገሩም ከህዝቡም ለመተዋወቅ አስቤአለሁ። ደህና ብመለስ ከርስዎ በፊት ሌላ ለማየት አልሄድም፣ እንዳይረሱኝ እለምንዎታለሁ።

የመንፈስ ልጅዎ፣

በሻህ ዘለሌ።»

አቶ ማንደፍሮ ደብዳቤውን ባንድ እጃቸው እንደ ያዙ በሁለተኛው ጠረጴዛውን ተመረኰዙና አይኖቻቸውን ሳያረግቡ ፍት ለፊት ቦዘዝ አድርገው ተክለው በሻህ መጨረሻ በጽህፈት ቤታቸው ተገናኝተው ስለ ሽፍትነት ሲከራከሩ ግንባሩን ኵስተር እዩተበሳጨ ሲናገርና በሻህ ያነለት በመበሳጨቱ ተጸጽቶ ከቅርታ ፈገግታ ጋር ያን ደብዳቤ ሲጽፍ ሁለት የተለያዩ በሻህዎች ባይነ ህሊናቸው ፊት ታዩዋቸው! እንዲያ እኒያን ሁለት በሻህዎች ባይነ ህሊናቸው ፊት እንዳሉ ሲያዩ ዘለግ ያለ ጊዜ ቆይተው ድንገት ከንቅልፋቸው እንደ ተቀሰቀሱ አይኖቻቸውን እየመላለሱ አርገበገቡና፥

«እቃውን ሁሉ ይዞ ሄዶ ይሆን? » አሉ፥ በሩን ከፍቶላቸው ባጠገባቸው ወደ ቆመው ሰው ዘወር ብለው።

«አይመስለኝም ጌታየ፤ እዚህ ከሚታየው አብዛኛው ዱሮ ያልነበረ እሱ ያመጣው ነው።»

«እንግዲህ እዚህ ቤት ማንም እንዳይገባ አደራህ። እሱ እስኪመለስ ወይም ከሱ እስክንሰማ ተቆልፎ ቁልፉ ባንተ እጅ ይቆይ» አሉ፥ ሲወጡ።

አቶ ማንደፍሮ የበሻህን የስንብት ደብዳቤ ካነበቡ በሁዋላ ሁለት ወራት አልፈው በሶስተኛው አጋማሽ ላይ፣ አንድ ማታ፥ ባራትና በምስት ሰአት መሀከል የሙሉ ዶሮ ማነቂያ ሰፈር የቤቱም የመንገዱም፥ መብራት ጠፍቶ ሰፈሩን ከባድ ጨለማ ዋጠው! በሰፈሩ ሱቆች የተገኘው ሻማ፥ ለፈላጊው ሁሉ ሊበቃ ስላልቻለ እንዳቶ ማንደፍሮ ምግብ ቤት ብዙ በሚያስተናግዱ ሆቴሎች መጠጥ ቤቶችና ልዩ ልዩ የመዝናኛ ቦታዎች ከሌሎች የባሰ ችግር ተፈጠረ።

«ምነው እባካሁ ለምን ዝም ትላላችሁ? መብታ ሀይል ለድንገተኛ ክፍል ደውላችሁ ሰፈራችን በሙሉ ጨለማ ውስጥ መሆኑን አትነግሩም? » አሉ አቶ ማንደፍሮ በድምር ሰራተኞቻቸውን ተቆጥተው።

«ሞክረን ነበር፤ ስልኩ አይሰራም ጌታዩ። የኛ ብቻ ሳይሆን የጎረቤቶቻችን ስልክም አይሰራ» አለ የምግብ ቤቱ ስራ አስኪያጅ። ያን ሌሊት የዶሮ ማነቂያ ነዋሪዎች ብቻ ሳይሆኑ የጎላ ሰፈር ነዋሪዎችም መብራትና ስልክ አልነበራቸውም! ያን ሌሊት በዶሮ ማነቂያና በጎላ ሰፈሮች የሚሰራውን ክፉ ስራ የሚያይ እንዳይኖርና ለርዳታ ቢጠራ ሰምቶ የሚደርስ እንዳይኖር የመብራትና የስልክ መስመሮች ተቆርጠው ነበር!

በማግስቱ ዶሮ ማነቂያ ‹ብዙአዬሁ መራዊ› የሚባል የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የፓስፖርት ክፍል ሰራተኛ ጎላ ሰፈር፣ ‹አራጋው ተወንድ በላይ› የሚባል ባገር ግዛት ሚኒስቴር ውስጥ የውጭ አገር ዜጎች መቆጣጠሪያ ክፍል ሰራተኛ ማጅራት ማጅራታቸውን እዬተመቱ በዬደጃቸው ወድቀው መገኘታቸው ተወራ። ብቻ ሁለቱም አልሞቱም። ማጅራታቸውን የተመቱበት ምክንያት በጉልህ ተጽፎ በዬኮታቸው ላይ ተጣብቆዋል።

‹ብዙአየሁ መራዊ› ይላል ጽሁፉ። ‹ትናንት የኢትዮጵያን የነጻነት ክብር ገፈው ሀብትዋን ዘርፈው ህዝብዋን ፈጅተው የሰውና የሀብት ድሀ ያደረጉትዋ ጠላቶችዋ ፋሽስቶች በጦር ሜዳ ድል ተመትተው ሲወጡ ተመልሰው ለመግባት ላላቸው ከንቱ አላማ፥ መንገድ እንዲያዘጋጁላቸው ወደ ሁዋላ ትተዋቸው ከሄዱት ብዙ ወገኖቻቸው ጉቦ እዬተቀበልህ እዚህ ተቀምጠው ኢትዮጵያን የሚጎዳና ጠላቶችዋን የሚረዳ የስለላ ስራቸውን እንዲሰሩ ከባለስልጣኖች ጋር ተሻርከህ የመኖሪያ ፈቃድ እንዲሰጣቸው ማድረግህ በማያወላዋል ማስረጃ ስለ ተረጋገጠ ይህ የማስጠንቀቂያ ቅጣት ተፈርዶብሀል! ይህንና ይህን የመሳሰለ ርኩስ ስራህን ባትተው ወደፊት ሞት ይጠብቅሀል!

የኢትዮጵያ ክብርና ጥቅም ዘበኞች።›

‹አራጋው ተወንድ ባላይ› ይላል ባራጋው ኮት ላይ፥ የተጣበቀውና በቤቱ ግድግዳ በስተውጭ፣ የተለጠፈው ጽሁፍ ‹ከጠላት ወረራ በፊት ብዙ ዘመን በኢትዮጵያ ተቀምጠው በልዩ ልዩ ስምና መልክ ሀብትዋን ሲዘርፉ ከነበሩና ሁዋላም ወራሪው ጠላት የመንግስቱን ስልጣን ይዞ በቆዩበት ጊዜ የሱ ተባባሪዎች ሆነው ብዙ፣ ኢትዮጵያውያንን ካሳሰሩና ካስገደሉ የውጭ አገር ሰዎች ጉቦ እዬተቀበልህ ተራ የመኖሪያ ፈቃድ ብቻ ሳይሆን የበደሉዋት አገር የኢትዮጵያ ዜግነት እንዲኖራቸው ያደረግህ መሆንህ ስለ ተረጋገጠ ማጅራትህን ተመትተህ አገርህን ኢትዮጵያን ሸጠህ ያፈራኸው ንብረትህ እንዲወረስ ተፈርዶብሀል!

የኢትዮጵያ ክብርና ቅቅም ዘበኞች።›

ያን ሌሊት በዶሮ ማነቂያ በጎላ፣ ሰፈር የደረሰው አደጋ፣ ከቁም ነገር ስላልተጻፈ ይሁን ወይም ተሸሽጎ እንዲቀር ስለ ተፈለገ፣ በራዲዮም በጋዜጣም ለህዝብ አልተገለጸ። ታዲያ መቸም የተሸሸገ ነገር እንደ ተሸሸገ በሽታ በተሸሸገ መጠን ከፍቶ አንዳንድ ጊዜም መልኩን ለውጦ ስለሚገለጽ የዚያ ሌሊቱ የወንጀል ስራም፣ በከተማው ውስጥ ከያፉ ወደዬጆሮው ሲተላለፍ ከተነባእተ እዬራቀ በሄደ መጠን በተሰራው ላይ ያልተሰራው እዬተጨመረበት በዝቶ ከፍቶና መልኩን ለውጦ ሲወራ ሰነእብተ።

‹ጎላ ሰፈርና ዶሮ ማነቂያ የተሰራውን ሰምታችሁዋል?› ይላል አንዱ የሚያውቃቸው ሰዎች ሰብሰብ ብለው በቆሙበት ወይም በተቀመጡበት ይሄድና።

‹ምን ተስራ?›

‹የፈረንጅ ሰላዮች የሆኑ፣ ሁለት ያገር ግዛት ሚኒስቴርና የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ሰራተኞች የስለላ ዋጋቸውን ብዙ ብዙ ብር በጨለማ ከፈረንጆች ተቀብለው እዬተሸከሙ ወደቤታቸው ሲሄዱ፥ ፖሊሶች ተከታትለው ሁለቱንም ጉሮሮዋቸውን እያነቁ በየቤታቸው በራፍ ጥለው ገንዘቡን በሙሉ ዘረፉት አሉ! የታነቁት ሰዎች ይሞቱ ይዳኑ አይታወቅም፤ ያጣጥሩ ነበር ይባላል!›

‹እሰይ! ጥሩ አደረጉ ብቻ - ዘራፊዎች ፖሊሶች መሆናቸው እንዴት ታወቀ?›

‹እያነቁ በጣሉዋቸው ሰላዮች ላይ ጽፈው ትተውት የተገኘ ጽሁፍ ‹ዘበኞች› ይላል። ዘበኞች ማለት - ፖሊሶች ማለት አደለም?›

‹እ - ! ልክ ነው!›

‹እዚያ አራዳ ጉድ ሲወራ ሰምቼ መጣሁ!› ይላል ደግሞ ሌላው ለወዳጆቹ።

‹ምን?›

‹ከመንግስት ግምጃ ቤት ገንዘብ አልቆ የሁለት ይሁን የሶስት ወር ደመወዝ ለፖሊሶች ሳይከፈል ስለ ቆዬ፣ ፖሊሶች በዬሰው ቤት እዬገቡ እዬዘረፉ፣ «ደመወዛችነን ስንቀበል እንከፍላለን» ብለው የጻፉትን በዘረፉት ቤት ላይ ለጥፈው ይሄዳሉ አሉ!›

«እንዴት! ዘራፊ የሚይዘው ፖሊስ መዝረፉ አነሰና - ደግሞ «ዘረፍሁ» እያለ ማስታወቂያ ያወጣ ጀመር? አይመጣ ጉድኮ የለም!?

መሰንበቻቸውን እንዲህ ያሉና ከነሱ የባሱም ያነሱም እውነት የማይመስሉ ልዩ ልዩ ወሬዎች በከተማው ሲወሩ ሰነበቱ። ብቻ የሚለያዩበት ቢኖር በተሰራው ወንጀልና ባሰራሩ ነው እንጂ፣ ሰሪዎች ፖሊሶች በመሆናቸው ሁሉም ይስማሙ ነበር!

ዶሮ ማነቂያና ጎላ ሰፈር የተሰራው ወንጀል፣ ወሬው ከሰው አፍ ሳይደርስ ገና በትኩስነቱ እንዳለ ቂርቆስና ተክለ ሃይማኖቶ ሰፍሮች እንደ ጎላ ሰፈርና እንደ ዶሮ ማነቂያ የመብራትና የስልክ መስመሮች ተቆርጠው ሶስት ሰዎች ማጅራት ማጅራታቸውን እዬተመቱ አንዱ በመንገድ ሁለቱ በዬቢታቸው ውስጥ እንዳሉ እጅና እግራቸውን ታስረው አፋቸውን ታፍነው፥ ገንዘባቸውን ተዘርፈው ተገኙ። ነገር ግን ቂርቆስና ተክለ ሃይማኖት ማጅራታቸውን በተመቱት ሰዎች ልብስ ላይም ሆነ በተዘረፉት ቤቶች ግድግዳ ላይ የቅጣቱን ምክንያት የሚገልጽ ጽሁፍ አልነበረም።

ከዚያ በሁዋላ፥ በዬሳምንቱ ከዚያ በያምስተኛው፥ እከዚያ በያራተኛው ቀን በዬሶስተኛው ሌት በሁለት ወይም በሶት ሰፈሮች የመብራትና የስልክ መስመሮች እዬተቆራረጡ፣ ሰዎች ማጅራታቸውን ተመትተው ገንዘባቸውን ተቀምተው በዬመንገዱና፥ በዬደጃቸው ወድቀው መገኘታቸው የቤትና የውጭ ንብረት መዘረፉ የተለመደ የከተማው የኑሮ ስራት ልሆን ምንም አልቀረው! ሰዎች ማጅራታቸውን ይመታል፤ ገንዘባቸውን ይቀማሉ፤ ቤታቸው ይዘረፋል፤ አቶሞቢላቸው ደህና ሲሄዱ ውለው ማታ እጋራዣቸው ገብተው ከቆሙበት ሌሊቱን ከፊት መብራታቸው ወልቆ እውሮች ሆነው፣ ከስር ጎማቸው ሄዶ ሽባዎች ሆነው፣ ከውስጥ ባትሪያቸው ተወስዶ ቀዝቃዛ ሬሳዎች ሆነው ይገኛሉ! ነገር ግን ሰዎች ማጅራታቸውን የሚመቱበትና ቤት ንብረት የሚዘረፍብት ምክንያት እንደ መጀመሪያ ጊዜ ተጽፎ የሚታዬው አልፎ አልፎ በጣም፥ አልፎ አልፎ ከስንት አንድ ነበር።

ከዚያ ዘረፋው ከሰዎችና ከቤቶች አልፎ፣ ወደ መብራት ስልክ ሽቦዎች አምፑሎችና ስኒዎች ተራመደ። የስልክና የመብራት ምሰሶዎች ሽቦዎቻቸው እዬተቆረጡ አምፑሎቻቸውና ስኒዎቻቸው እዬተነቀሉ ከላያቸው ተወስደው ምልምላቸውን ተገትረው ይታዩ ጀመር! ወዲያው ዘራፊዎችና ማጅራት መቺዎች የታጠቁ ወንበዴዎች እንጂ ፖሊሶች አለመሆናቸው ታወቁና፣ ፖሊሶችን በከንቱ ያማው ሁሉ እግዜር «ይቅር» እንዲለው የቃልም የህሊናም ጸሎቱን ያደርግ ጀመር! ከዚያ በሁዋላ ፖሊሶች ይወቀሱበት የነበረው ‹ይዘርፋሉ› ተብለው ሳይሆን እኒያ የታጠቁ ወንበዴዎች የመብራትና የስልክ መስመሮች ቆርጠው በሚዘርፉባቸው ሰፈሮች ጩኸት ሲሆን ጩዋሂዎችን ለማገዝና ዘራፊዎችን ለመያዝ ፈጥነው ባለመድረሳቸው ነበር።

ፖሊሶች፥ ወንበዴዎችን ከሰላም ሰዎች ለይቶ ለመምታት መብራት ስለሚያስፈልግና ተጨማሪ ረዳት ቢያስፈልግ ከጣቢያ ለመጥራት ስልክ ስለሚያስፈልግ እነዚህ በተቆረጡባቸው ሰፈሮች መግባት አይወዱም ነበር። ስለዚህ ጩኸቱን ቢሰሙም ያልሰሙ፥ የሚመስሉበት ጊዜ ይበዛ ነበር! ወንበዴዎችም ልባቸውን ሞልተው የወንጀል ስራቸውን የሚፈጽሙ ይሁኑ ተማምነው ነበር! እዬዋለ እያደረ ግን፥ የሰው ይሁን ወይም የገዛ ህሊናቸው ወቀሳ እዬበዛ ሲሄድ እያንዳንዱ የፖሊስ አባል እንደ ጠመንጃውና እንደ ሽጉጡ ባትሪም መዛያ የተለመደ ሆነና ወንበዴዎች መብራት አጥፍተው የሚያስጮሁበት ሰፈር፣ ፖሊሶች ባትሪያቸውን እያበሩ ይደርሱ ጀመር።

አንድ ሌሊት ካራት ሰአት በሁዋላ፣ ከዚያ በፊት በሌሎች ሰፈሮች እንደ ደረሰው ሩፋኤል ሰፈር የመብራትና የስልክ መስመሮች ተቆርጠው ምንም የማይታይበት ምንም የማይሰማበት የጨለማ አለም የሲኦል አለም ሆነ!

‹ዛሬ የጨለማው ንጉስ ዘመቻውን፥ እኛ ሰፈር አድርጎዋል ማለት ነው!› አለ አንድ የሰፈሩ እዋሪ፣ አብሮት ለነበረው!

‹ዛሬ ደግሞ እግዜር የፈረደበት ባለ ተራ ማን ይሆን? አለ ሌላው። ‹የጨለማው ንጉሥ› ለወንበዴዎች መሪ ህዝቡ ያወጣለት ስም ነበር።

ትንሽ ቆይቶ፣ ካንድ ሀብታም ሰው ቤት ጩኸት ተሰማና፣ ያን ጩኸት መጀመሪያ የቅርብ ጎረቤት ከዚያ የሩቅ ጎረቤት እዬተቀባበለ ሲያስተጋባ ሰፈሩ በሙሉ ጩኸት በጩኸት ተደባልቆ እዚያ ሰፈር እያንዳንዱ ቤት ወራሪ የገባ መሰለ! ይህ ዘዴ ይህ አንድ ሰው ቤት ጩኸት ሲሰማ ከተነሳበት እስከ ሩቅ ድረስ እዬተቀባበሉ መጮህ ወንበዴዎች በዬሰፈሩ መብራትና ስልክ እዬቆረጡ ወንጀል መስራ ከጀመሩ በሁዋላ ህዝቡ ፖሊስ ለማንቃት የፈጠረው ዘዴ ነበር! ስለዚህ ያን ሌሊት ፖሊሶች ጩኸቱን ሲሰሙ በርከት ብለው ባትሪያችወን እያበሩ ወንጀሉ ወደ ሚሰራበት ቤት ደርሰው ወንበዴዎችን ከቤ ውስጥ እንዳሉ ከበቡዋቸው። ፖሊሶች ከደረሱ በሁዋላ የሰፈሩ ህዝብም ልጅ አዋቂው እዚያ የሚሆነው ለማየት ተሰበሰበ። የቤቱን ባለቤቶች ወንበዴዎች ይዘው ሲያስሩዋቸው ሁለት ሰራተኞች አምልጠው ወጥተው በታም ደንግጠው ስለ ነበር ወዲያ - ወዲህ እዬተርበተበቱ ለጠየቁዋቸውም ላልጠየቁዋቸውም የባጥ የቆጡን ይቀባጥሩ ነበር!

‹ሁሉም ጠበንጃ የያዙ ናቸውኮ! ሁሉም ካይናቸው በቀር ፊታቸውን በጨርቅ ሸፍነው ከዚያ ከጠበንጃቸው ጋር - ጋኔኖች እንጂ ሰዎች አይመስሉም! ጌቶችንና እሜቴን ልጆችን ጭምር ሲያስሩ ብታዩዋቸው! ውይ ማስፈራታቸው! ወይ እድሌ! ምን ያረጉዋቸው ይሆን? ይገሉዋቸው ይሆን? ባልገደሉዋቸው እንጂ የሚያምኑት ቅዱስ ሩፋኤል ነፍሳቸውን ባዳነው እንጂ፥ ገንዘባቸውንስ ግዴለም ባርኮ ቀድሶ ይስጣቸው፤ ገንዘብ ጤዛ ነው፤ ዛሬ ቢጠፋ አድሮ ይተካል!› እያለች እንደ እብድ ብቻዋን ትቀባጥር ነበር አንድዋ ወዲያ ወዲህ እዬተመላለሰች።

ከዚያ «እናንተ እዚህ ቤት የገባችሁ ሰዎች ተጠንቀቃችሁ ስሙ» አለ አንድ ከፍ ያለ ድምጽ ከጨለማው ውስጥ። ፖሊሶችን የሚመራው ያምሳ አለቃ ነበር። «ተጠንቀቃችሁ ስሙ። ባለቤቶችንና ልጆችን ሁሉ ጉዳት ሳይደርስባቸው በደህና እንዲወጡ፣ እናንተም በሰላም እጃችሁን እንድትሰጡ፣ ጥሪ እናደርጋላሁዋለን። ባለቤቶቹ ከልጆቻቸው ጋር በደህና ከወጡና አንተም በሰላም እጃችሁን ከሰጣችሁ ምንም እንደማይደርስባችሁ ቃል እንሰጣችሁዋለን» ብሎ ንግግሩን ከመጨረሱ ወንበዴዎች ከውስጥ አን ጥይት ተኮሱ። የንቢታ ምልከት መሆኑ ነው! ብቻ ተኩሱ የንቢታ ምልክት እንደ መሆኑ ከራስ በላይ የተተኮሰ ስለ ነበረ በሰው ጉዳት አላደረሰም። ከዚያ ፖሊሶች እሰረኞች ጉዳት እንዳይደርስባቸው ወንበዴዎችን ማጥቃት የሚችሉበትን ወንበዴዎች የሞት ወይም የመቁሰል ጉዳት ሳይደርስባቸው ከበባውን ጥሰው የሚያመልጡበትን ዘዴ፤ በዬበኩላቸው እያሰላሰሉና እዬተመካከሩ - አይን ላይን መቸም አይተያዩ - በመንፈስ ፍጥጫ ላይ እንዳሉ፣ አንድ ከሁዋላ ግልጥ የሆነች ካሚዮን እዬበረረች እዚያ ወንበዴዎች በተከበቡበት ቤት ደረሰች። ሰሌድዋ ‹ፖሊስ› ይላል። ወዲያው አንድ የፖሊስ ሻምበልና ነጂው ከፊት አራት የተራ ፖሊስ መለዮ የለበሱ ሰዎች ከሁዋላ ሲወርዱ ከበው የቆዩት ፖሊሶች የባትሪ መብራታቸውን ላንድ አፍታ ከያቅጣጫው አሰፈሩባቸው። መለዮዋቸው ያስተዋውቃቸዋል እንጂ መቸም ፖሊሶች ሁሉ አይተዋወቁ!

«መሳሪያ አላቸው? » አለ አዲስ መጪው ሻምበል።

«አዎ ጌታየ የታጠቁ ናቸው» አለ እዚያ የቆየው ያምሳ አለቃ አዲስ መጪውን ባያውቀውም መለዮው የበላዩ ስለሚያደርገው ሰላምታ ሰጥቶ።

«ስንት ይሆኑ ይመስለሀል? »

«አምትም ስድስትም ይላሉ። የቤቱ ሰራተኞች ደንግጠው ቁጥራቸውን በትክክል ያስትዋሉ አይመስልም። ባለቤቶችን እስከ ልጆቻቸው እውስጥ ይዘዋቸዋል አሉ።»

«እጃቸውን እንዲሰጡ ጠይቃችሁዋቸዋል? »

«አዎን ጌታየ፤ ነገር ግን የሰጡን መልስ ጥይት መተኮስ ነው፤ ተኮሱብን! »

«ተኮሱባችሁ! እ? ቆይ ግዴለም እኒህ ወሮበሎች፣ ከነናቸው ያገኙታል! » አለና ሻምበሉ ‹እህ፣ እህ እህ! » አለ ሶስት ጊዜ ድምጹን ከፍ አድርጎ፣ ማስጠንቀቂያውን ጮሆ ከመስጠቱ በፊት ጉሮሮውን እንደሚያጠራ ሁሉ።

«እናንተ እዚህ ቤት የገባችሁ - ሽፍቶች» አለ ቀጥሎ። «መጀመሪያ በገዛ ቤታቸው ያሰራችሁዋቸውን ባለቤቶች ከነልጆቻቸው አንዳች ጉዳት ሳይስደርስባቸው ለቃችሁዋቸው እንዲወጡ። ሁለተኛ እናንተ፥ ሁላችሁም፣ የመሳሪያችሁ አፈሙዝ ወደላይ እያደረጋችሁ ሁለት እጃችሁን ከራስችሁ በላይ እዬዘረጋችሁ እንድትወጡ ይህን የመጨረሻ ጥሪ አሰማችሁዋለሁ። ይህን ጥሪ ከሰማችሁ በሁዋላ ካንድ ጀምሬ ቀስ እያልሁ እስከ አምስት እስቆጥር ድረስ ትእዛዝዙን ባትፈጽሙ ባላችሁበት በቦምብ የምንጨርሳችሁ መሆኑን እናስታውቃችሁዋለን! »

«እንዴ! እንዴት! ባለቤቶን ጭምር? ይህማ እንዴት ይሆናል? ይህ ጉድ ነው! ይህማ እብደት ነው! » እያለ እዚያ የተሰበሰበው ህዝብ ሁሉ እስበሱም ለዬራሱም ቀስ ብሎ የሚያጉረመርመውና የሚያኩተመትመው ባንድ ላይ ሆኖ አዬሩን ሞልቶት፣ በጢስ ተረብሾ ከቀፎው የወጣ የንብ ሰራዊት ‹ህም - ታ› ይመስል ነበር!

«ዝም በሉ፤ ልቁጠርበት! » አለ ሻምበሉ፥ በወፍራም ድምጹ አንደ ነበር አጉራርቶ። ያንጊዜ ህዝቡ፥ ‹ቦምቡ ሊጣልብህ ነው› እንደ ተባለ ሁሉ ፈርቶ ጭጭ ርጭ አለ። ብቻ የሻምበሉ ትእዛዝ ህዝቡ ጭንቀቱን ወደ ውጭ እንዳይተነፍስ የሚከለክል እንጂ ጭንቀቱን የሚያስወግድ ስላልነበረ ሁሉም ጭንቀቱን በዬጉሮሮው ውጦ ሲያምጥ የቆዬበት እያንዳንዱ ንኡስ ደቂቃ አመት፣ ‹ቦምቡ ሊጣልበት ነው› ብሎ የሚጠብቀው የባሰውን፣ ያምጥ ጀመር! ያ ጭንቀት ከህዝቡ ተርፎ፣ ምድሩንም አዬሩንም እስኪፈነዱ የወጠራቸው ይመስል ነበር!

«አ - ንድ! » አለ ሻምበሉ እንደ ገመምተኛ እያዘገመ። አቤት ያንጊዜ የነበረው ጣር! ያንጊዜ ከትንንሽ ልጆች በቀር ላብ ያልዋጠው ባይውጠው ሊያልበው ያልቃጣው

ሰው አልነበረም! ትንንሽ ልጆች ብቻ ቦምቡ ቶሎ ፈንድቶ እስኪያዩትና እስኪሰሙት ቸኩለው ነበር። «ሁ - ለ - ት! » አለ ሻምበሉ፥ አሁንም ፊደሎችን እዬቆጠረ። እግዚኦ -! የሩፋኤል ያለህ! ከዚያ ትንሽ ቆይቶ «ሶ - ስት! » ከማለቱ እስረኞቹ ሆነው የቆዩት ባልና ምሽት ከልጆቻቸው ጋር ብቅ ሲሉ የቤቱን በራፍ በርቶ በሚጠብቀው የፖሊሶች የባትሪ መብራት ታዩ! አየ ያንጊዜ የህዝብ ደስታ! ያን ጊዜ የህዝቡ ደስታ እሁታው እሰይታ፣ ጫጫታው፣ የሻምበሉን ትእዛዝ ጥሶ በጨለማው ውስጥ ሲያስተጋባ ከሩቅ ይሰማ ነበር! የቤቱ እመቤት፣ የነበሩት ጭንቅና ከዚያ ጭንቅ የመገላገላቸው ደስታ ባንድነት ሆነው ከፈጠሩት ድብልቅ ስሜት የተነሳ ጥርሳቸው ብቻ ሳይሆን ፊታቸው ሁሉ እዬሳቀ አይኖቻቸው በንብ ውሀ ይታጠቡ ነበር! ባልዬውም የሚንቀጠቀጥ ድምጻቸውን ከፍ አድርገው ለፖሊሶችና ለህዝቡ ምስጋናቸውን ሲገልጹ ልባቸው በደስታ የተነካ መሆኑ ይታወቅ ነበር!

«በቃ እንግዲህ ዝም በሉ! » አለ ሻምበሉ በጫጫታ፥ መሀል እንደ ቅድሙ አጉራርቶ። ህዝቡም ‹ዋ ትተነፍስና!› እንደ ተባለ ህጻን ሁሉም ትንፋሹን ውጦ ጭጭ ኧለ። እዚያ ሻምበሉ ቆጥራውን ካቆመበት ለመቀጠል ‹አ - ራ -› ብሎ ገና ‹ትን› ሳይጨርስ አራት ወንበዴዎች እንደ ታዘዙት የጠመጃቸውን አፈሙዝ ወደ ላይ አድርገው እጆቻቸውን ከራሳቸው በላይ እዬዘረጉ ወጡ። እዚያ የተሰበሰበው ህዝብ ስጋቸውን እንደ ገና ፍሪዳ ተቀራምቶ ቢበላው በወደደ! ‹አይናችሁ ይፍሰስ! አፈር ብሉ! ድራሻችሁን ያጥፋው! ርጉሞች! ሰይጣኖች! ቡዶች!.....› እያለ ርግማኑንና ስድቡን ያላወረደባቸው አልነበረም!

«በሉ ቶሎ መሳሪያቸውን ግፈፉና ሁለት ሁለቱን በጅ ሰንሰለት አቆራኝታችሁ እመኪናዋ ላይ ጫኑዋቸው» አለ ሻምበሉ። ወዲያው አብረውት የመጡት አራት ሰዎች የወንበዴዎቹን መሳሪያ ገፍፈው፣ እነሱን እያዳፉ ሲያመጡ፣ ነጂው ከመኪናው ውስጥ ሁለት ባለጣምራ ቀለበት የጅ ሰንሰለቶች አምጥቶ ሁለት ሁለቱን እያቆራኘ በቅጽበት እመኪናዋ ላይ ጫኑዋቸው። አየ ቅልጥፍና አየ ስልጥንና ያለቃው ትእዛዝ አሰጣጥ የጭፍሮች ትእዛዝ አፈጻጸምና እይስረኞች መተባበር ሁሉም በቃል ተጠንቶ በመድረክ ላይ የሚታይ ትያትር ይመስላ! ያ አይነት አሰራር ቀድመው መጥተው እዚያ ለቆዩት ፖሊሶች እንግዳ ሆነባቸውና ግር አላቸው። በነዚህ ራሳቸውን ከጥንት ‹ከስብስቴ› ጊዜ ተርፈው የቀሩ አድርገው ቆጠሩት!

ሻምበሉ ለባለቤቶቹ የጅ ሰላምታ ሰጥቶ፣ «እንኩዋን እግዚአብሄር አተረፋችሁ» ካላቸውና ትንሽ ሲያጽናናቸው ከቆየ በሁዋላ በማግስቱ ጠዋት ሶስተኛ ፖሊስ ጣቢያ ሄደ ቃላቸውን እንዲሰጡ ነግሮዋቸው «በል ንዳ ወደ ጣቢያ» አለ እመኪናው ውስጥ ሲገባ።

«ሻምበል - ጌታየ፤ ጣቢያ ድረስ አብሬ ልሂድ መኪና የለኝም» አለ ወንበዴዎችን ከበው የቆዩት ፖሊሶች ያምሳ አለቃ ቀረብ ብሎ።

«እሁዋላ ግባ» አለ ሻምበል።

ያምሳ አለቃው በመኪናዋ ሁዋላ የተቆራኙት ወንበዴዎችና ጠባቂዎቻቸው ባሉበት ገብቶ ሲቀመጥ ከጠባቂዎቹ አንዱ ቦታውን ለቅቆ አስቀመጠውና እሱ በሁዋላው ከመኪናው ጠርዝ ላይ ተቀመጠ።

«እግዚአብሄር ያክብርልኝ። ብቻ - አንተን ይመችህል? እንዳትወድቅ እንጂ! » አለ ያምሳ አለቃው፣ ተመቻችቶ ሲቀመጥ።

«ደህና ነ፤ ተመችቶኛል ጌታየ» አለ አስተናጋጁ።

ከዚያ ያች ካሚዮን በገዛ ቤታቸው እስረኞች የነበሩትን ባልና ምሽት ከብቦ የሚጫጫውን ብዙ ህዝብና ፖሊሶችን ኢዚያው ትታ በመጣችበት ፍጥነት ከሩፋኤል ወደ መስፍን ሀረር ጎዳና በረረች። እንዲያ እዬበረረች አውራ ጎዳና ልትገባ ትንሽ ሲቀራት ከፊት ይሁን ከጎን ‹ይህ መጣባት› የሚባል ነገር ሳይኖር ድንገት ጎማዎችዋ ‹ስ - ጢ - ጢ - ጢጥ› ብለው ቀጥ አለች። ወዲያው ያ ለምኖ የገባው ያምሳ አለቃ ላንድ ቅጽበት ነው። ከዚያ በሁዋላ አእምሮው ተሰወረ። እንዲያ አእምሮው እንደ ተሰወረ ቆይቶ ነፍሱን ሊገዛ አንድ የንጨት ጉራጅ ተንተርሶ ከመንገዱ ዳር ተኝቶ አገኘ! ‹እልም ይሆን? ወይስ እውን?› አለ በልቡ። መሬትዋ ትዞር ነበር። በትምርት ቤት መሬት እንደምትዞር የተማረው እውነት መሆኑን ገና ያን ሌሊት ተረዳ! ከዚያ ተንስቶ ማዞሩ እስኪያልፍለት ተቀምጦ ቆይቶ እያዘገመ። መኪናዋም በውስጥዋ የነበሩት ሰዎችም፥ ወደዚያ ወይም ወደ ሌላ ፖሊስ ጣቢያ አልሄዱም። የት እንደ ደረሱ ከነሱ በቀር የሚያውቅ አልነበረም!

ሩፋኤል ተከበው የነበሩት ወንበዴዎች ከተከበቡበት ወጥተው የደረሱበት ደብዛው በመጥፋቱ ፖሊሶች ግራ ገብቶዋቸው የጠረጠሩትን ሁሉ ለምርምራ እዬያዙ

ሲያስሩና ሲፈቱ፣ ህዝቡ ወንበዴዎች በሰሩት ላይ ያልሰሩትን አስደናቂ ስራ እዬጨመረ ሲያወራ ያ፤ የሩፋኤል ወሬ ገና ባፍላው እንዳለ ያዲስ ከተማው ወሬ ተጨመረበት!

ሩፋኤል ተከበው የነበሩት ወንበዴዎች ከመለጡ በኋላ ባራተኛዉ ሌሊት አምት ወንበዴዎች አዲስ ከተማ ያው እንደ ልማዳቸው የመብራትና የስልክ መስመሮችን ቆርጠው፣ አንድ ነጋዴ ቤት በገቡበት ጨኸት ሆነና ተከበው። ወንበዲዎች ሲገቡ ባለቤቶቹ አልተኙ ኖሮ፥ አምልጠዋቸው፣ በልማቸው እንደሚያደርጉት፣ እቤት ውስጥ የሰው መያዛ አላስቀሩም ነበር። ፖሊሶች ከሰፈሩ ህዝብ ጋር ቤቱን እንደ ከበቡ፣ በሰላም እጃቸውን የማይሰጡ ከሆኑ እውስጥ፣ እንዳሉ ቤቱ የሚቃጠል መሆኑን አስታወቁዋቸው።

«ስሙ፣ ስሙ እናንተ እዚህ ቤት» ያላችሁ ሰዎች! እጃችሁን በሰላም እንድትሰጡ የሰላም ጥሪ እናደርግላችሁዋለን። እጃችሁን በሰላም የማትሰጡ ከሆነና ግን እውስጥ እንዳላችሁ ቤቱን እንድናቃጥልና መንግስት ለባለቤቶቹ የንብረታቸውን ዋጋ እንዲሰጥ አዲስ ቀዋሚ ትእዛዝ የተሰጠ ስለሆነ ትእዛዙን የምንፈጽም መሆናችነን እናስታውቃችዋለን! » አለ የፖሊሶች ሹም ድምጹን እክፍ አድርጎ። ከዚያ ለጥቂት ደቂቃዎች ፖሊሶች የወንበዴዎችን መልስ በመጠበቅ ወንበዴዎች ፖሊሶች ቀጥለው የሚያደርጉትን እርምጃ በመናፈቅ ያን ቦታ የሚያስጨንቅ ከባድ ዝምታ፣ ቆዬ! ከዚያ ፖሊሶች ከቤቱ ፊትና ሁዋላ እሳት ማቀጣጠል ጀመሩ። ወዲያው ወንበዴዎች የቃጠሎውን ድምጽ ሲሰሙን በተዘጋው መስኮት የብርሀን ጭላንጭል ሲያዩ እውነት ያሉበት ቤት መቃጠል የጀመረ መስሎዋቸው ቶሎ ቶሎ የጠመንጃውን አፈሙዝ ወደ ላይ እያደረጉ ወጥተው እጃቸውን ሰጡ።

በማግስቱ ማታ ሁለት ሰአት ላይ ወደ አዲስ ከተማ ፖሊስ ጣቢያ ስልክ ተደወለ።

«ሀሎ፤ ሻምበል ጠና በቃሉ» አለ ያዲስ ከተማ ፖሊስ ጣቢያ አዛዥ ስልኩን አስንቶ ፡

«ሻምበል ጠና በቃሉ ጀነራል ጣሰው ነኝ ካዲስ አበባ ፖሊስ መምሪያ።»

«አቤት ጌታየ! » አለ ያዲስ ከተማው ጣቢያ አዛዥ ደንግጠጦ ተነስቶ።

«ትናንት ሌሊት እዚያ እናንተ ሰፈር ስለ ተያዙት ወንበዴዎች ጉዳይ ነው። ስንት ናቸው? »

«አምስት ናቸው፥ ጌታዬ! »

«መቾም የመጀመሪያውን ምርመራ እስካሁን ሳታደርጉ አልቀራችሁ! » አለ ጀነራሉ።

«አዎን ጌታዬ፤ ወዲያው ተይዘው እንደ መጡ፤ ሌሊቱን ነው ያደረግን።»

«ታዲያ ምን አገኛችሁ? ለምን ተቀጥረው እንደሚሰሩ ትንሽ ፍንጭ አሳዩ? »

«ያው - ለዘረፉ የገቡ መሆናቸውን ከማመን በቀር፣ ለጊዜው ሌላ ነገር አልነገሩንም። ዛሬና ነገ ተሰናድተን ከነገ ወዲያ ጀምረን ጠበቅ ያለ ምርመራ ልናደርግ አስበናል፤ ውጤቱ የሚታወቀው ከዚያ ወዲህ ነው ጌታየ! »

«ህእ! ተራ ወንበዴዎች መስለህልኮ! ተራ ወንበዴዎች አደሉም፤ የውጭ ጠላት ገዝቶ ያዘመተብን እጅግ አደገኞች የሆኑ ምንድኞች ናቸው፤ እኛ እዚህ መረጃ ይዘናል። አሁን እንዲህ አድርግልኝ። መቶ አለቃ መልካሙ ዴንሳን ታውቀው የለም? »

«መቶ አለቃ መልካሙ ዴንሳ? የምንተዋወቅ አይመስለኝም ጌታየ! »

«መቶ አለቃ መልካሙ በቅርቡ በጠላት ሰርጎ - ገቦች ምርመራ ሰልጥኖ የመጣ መኮንን ነው። እሱን ከቡድኑ ጋር መኪና ጭምር አሁን አልክልሃለሁና ወንበዴዎቹን በሱ እጅ ስደድልኝ። ትናንት የተመረመሩበትን ስነድም እዚህ ከያዝን መረጃ ጋር ለማእንጻጸር ስለምንፈልገው ቢመችህ አንተ ራስህ ይዘህልኝ ከሱ ጋር ና፤ እዚያ አስቸኩዋይ ስራ እንዳለህ ግን በምክትልህ ወይም - በሌላ በምታምነው የፖሊስ አባል እጅ ላክልኝ» ብሎ ጀነራሉ፥ መልስ ሳይጠብቅ ስልኩን ዘጋ።

እኩል ሰአት ባልሞላ ጊዜ ውስጥ መቶ አለቃ መልካሙ ዴንሳ ያዲስ አበባ ፖሊስ አዛዥ እንዳለው በትልቅ የፖሊስ ሰራዊት መኪና ከቡድኑ ጋር አዲስ ከተማ ፖሊስ ጣቢያ ደረሰ። ወዲያው ከሻምበል ጠና በቃሉ ጋር ከተዋወቁ በሁዋላ፣ እስረኞችን ተረክቦ በጅ ሰንሰለት እስበሳቸው እያቆራኘ በመኪናው ጭኖ፣ የተመረመሩበትን ሰነድ የያዘው የሻምበል ጠና በቃሉ ምክትል ጭምር ካዲስ ከተማ ፖሊስ ጣቢያ ተነሱ። ነገር ግን አዲስ አበባ ፖሊስ አዛዥ ጽህፈት ቤት አልደረሱም! በመንገድ የውሀ ሽታ ሆኑ! የሻምበል ጠና በቃሉ ምክትል ብቻ ከነነፍሱ ከመግነድ ዳር ወድቆ ተገኘ!

ወንበዴዎች መብራት አጥፍተው በመንገድ እቤት ውስጥ ወይም ከቤት ውጪ በሌላ ቦታ ማጅራቱ ሲመቱና ገንዘብ ሲቀሙ አንኩዋንስ ሊያዙ ያን ወንጀል መስራታቸውንም አደጋው ከደረሰባቸው ሰዎች በቀር የሚያውቅም አልነበረም። በማግስቱ ማጅራታቸውን የተመቱት ወይም ገንዘባቸውን የተቀሙት ሰዎች

የደረሰባቸውን አደጋ ሲያወሩ ብቻ ነበር ወሬው እዬተዛመተ ተስፋፍቶ የከተማው ህዝብ የሚሰማው። ቤት በሚዘርፉት ቤት የሚገቡ በቤቱ ሰዎች ላይ ድንገት አደጋ ጥለው የሚጮህ እንዳይኖር አሰናድተው በያዙት መለጎሚያ ኩዋስ የሁሉንም አፍ ይለጉሙና ባንድ ላይ አጉረው፣ በጠመንጃ አፈሙዝ እያስጠበቁ ነበር የዘረፉ ስራቸው ስራቸውን የሚሰሩ። እንዲያ የቤቱን ሰዎች ሁሉ እንዳይቀሳቀሱ እጅ እግራቸውን አሰው እዳይናገሩ ለጉመው ያላንዳች፣ አደናቃፊ በርብረው ሊያገኙ የቻሉትን ራሳቸው የቀረ ቢኖር፣ በማስፈራራት፥ ባለቤቶች እያሳዩዋቸው እጅ ያደረጉትን ሰብስበው ይዘው ከሄዱ በሁዋላ፣ ወሬው ብቻ ይሰማል!

ነገር ግን አንዳንድ ጊዜ አደጋ፥ ሲጥሉ ከቤቱ ሰው ቶሎ ነቅቶ ያመለተ ወይም ባጋጣሚ እውጭ የቆዬ ሰው ኖሮ ሲጮህ በዶዋቸውን ወይም፥ በቅርብ ያገኙትን ብቻ ይዘው ያመልጣሉ። ፖሊስ ከከበባቸው በሁዋላም በሚያስደንቅ ጀግንነት ተታኩሰው ወይም በሩፋኤልና ባዲስ እከተማ እንዳደረጉት በረቀቀ ዘዴ ከተከበቡበትና ከታሰሩበት ውስጥ እሚያመልጡበት ጊዜ ብዙ ነበር! ከተከበብቡበትም ሆነ ከታሰሩበት ተታኩሰው ውይም በዘዴ ማምለጥ ሳይችሉ ይቀሩና ፖሊስ ጣቢያ ታስረው በሚመረመሩበት ጊዜ፥ ምንም ያክል ቢያስቃዩዋቸው ያን ሁሉ ‹አይቻል ችለው› ዝም ነው እንጂ ‹እነሱን መርምረን ስለ ድርጅታቸው ወይም ከነሱ ቡድን ውጪ ሊኖሩ ስለሚችሉ ሌሎች ቡድኖች ይህን ፍንጭ አገኘን› የሚሉ መርማሪዎች አልነበሩም!

እኒያ ወንበዴዎች በስቃይ ብዛት የማይገበሩ ቆራጦችና ቸካኞች ከመሆናቸው ሌላ፣ እዚያው ከተያዙት ከብድናቸው አባሎችና ከቡድኑ መሪ በቀር ምንም የሚያውቁት ስላልነእብረ በስቃይ ብዛት የሚያወጡት ምስጢርም አለነበረ! እርግጥ፣ እነማን መሆናቸውን አይወቁ እንጂ በሌሎች ክፍሎች እንደነሱ ማጅራት የሚመቱ ገንዘብ የሚቀሙና ቤት የሚዘርፉ ሌሎች ቡድኖች መኖራቸውን ሰምተዋል፤ ማን መሆኑን አይወቁ እንጂ እንደ እግዜር ሳይታይ እዚያ ላይ ሆኖ የነሱንና የሌሎችን ቡድኖች ስራ አስተባብሮ የሚመራ ሁሉም የሚያውቅና ሁሉን የሚችል ግርማው የሚያርእድ አንድ ‹የጨለማው ንጉስ› የሚሉት መኖሩን ሰምተዋል፤ ነገር ግን እነዚህን እንኩዋ ሰው ሁሉ የሚያውቃቸውን ምን ቢገረፉ ምን ቢሰቃዩ፣ በጆሮዋቸው የሰሙትን ባፋቸው ወይ ትንፍሽ!

መቸም የኒያ ወንበዴዎች ጭካኔ ቆራጥነታቸው ጀግንነታቸው ዘዴያቸው ድርጅታቸው፣ ይህ ሁሉ እንከን የሌለው እጅግ የሚያስደንቅ ነበር! ነገር ግን ድርጅታቸው የተመሰረተበትን አላማ ፈጽመው ሰለሳቱ፣ እነሱ ‹ለኢትዮጵያ ጥቅምና

ክብር ዘብ የቆሙ› መባላቸው ቀርቶ ‹ጨካኝ ወንበዴዎች› ስራቸው ‹አስቀያሚ፥ እርቃንኑን የጣለ ውንብድና› ተባለ!

## 6. ድል የተመታዉ በሻህ

የበሻህ የሽፍትነት ድርጅት ከተቋዋዋመ ባንድ አመት ውስጥ እኒያ ወንበዴዎች ነፍስ አላጠፉም እንጂ፣ አንድ መቶ ሰላሳ፣ አምስት ሰዎች ማጅራታቸውን እዬመቱ፥ ጥለው ገንዘባንቸውን ቀምተዋል፤ አምሳ ሁለት ቤቶች ዘርፈዋል፤ ሀያ ሶስት ሰዎች በቂም በቀልና በውር ቅናት ማጅራታቸውን እዬመቱ ጥለዋል! ነገር ግን እነዚህ ሁሉ ውስጥ አገርና ህዝብ በመበደላቸው ማጅራታቸውን ተመትተው ገንዘባቸው እንዲወረስና ቤታቸው እንዲዘረፍ፣ ጠቅላይ መምሪያው የፈረደባቸው ዘጠና አምስት ሰዎች ሲሆኑ ፍርዱ የተፈጸመባቸው ስምንት ብቻ ነበሩ!

ድርጅቱ ቅጣቱን እንዲፈጽሙ በተመደቡት በታች፣ ቡድኖች ደረጃ፣ የታቀደለትን መንገድ ስቶ ያልታቀደለትን አደገኛ መንገድ እንደ ተከተለ በሻህ ሲያይ የጠቅላይ መምሪያው አባሎች የሆኑትን ጉዋደኞቹን እዬሰበሰበ እንዲያ ያለ፣ የውንብድና ስራ በመስራቱ አዘኑንም ቁጣውንም ከመግለጽና ያን የውንብድና ስራ ደግመው የሚሰሩ ቢኖሩ ብርቱ ቅጣት የሞት ቅጣት፣ ጭምር እንደሚቀጡ፣ ማስጠንቀቂያ ከመስጠት ቦዝኖ አያውቅም። ነገር ግን ምክሩም ቁጣውም ማስፈራራቱም በሙሉ ክብደታቸው ከጠቅላይ መምሪያው አባሎች አልፈው ቅጣቱን ለሚፈጽሙት ለታች፣ ቡድኖች አባሎች አልፈው ቅጣቱን ለሚፈጽሙት ለታች ቡድኖች አባሎች ስለማይደርሱ፣ ከውንብድና ስራቸው ሊገቱዋቸው አልቻሉም።

የድርጅቱ አቋዋም፣ ላገርና ለህዝብ አገልግሎት በመሀላ የተቀበሉትን ስልጣን፥ መልሰው ለህዝብ መጉጃና ለግል ጥቅማቸው ማሳደጊያ የሚያውሉትን ባለስልጣኖችና ሰራተኞች ለመቅጣት እንዲመች፣ አዲስ አበባ ባራት አበይት ክፍሎች፣ (ምስራቅ ምእራብ፣ ሰሜን፣ ደቡብ) ተከፍላ ለያንዳንዱ አቢይ ክፍል አንድ አላፊ የተደረገበት ነበር። አራቱ ያበይት ክፍሎች አላፊዎች በበሻህ ሰብሳቢነት የጠቅላይ መምሪያው አባሎች ናቸው። ከዚያ፣ እያንዳንዱ አቢይ ክፍል በብዙ ንኡሳን ክፍሎች ይከፈልና በያንዳንዱ ንኡስ ክፍል ውስጥ የሚኖትን በደለኞች (የመንግሥት ሹሞች ወይም ሰራተኞች) የሚቀጣ፣ አንድ የንኡስ ቀጪ ቡድን ተቋቁሞዋል። ቡድኑና ያቢይ ክፍሉ አላፊ የሚገናኙት በቡድኑ አለቃ በኩል ብቻ ነው። በተረፈ የያንዳንዱ ቡድን አባሎች ከስበሳቸውና ከቡድናቸው አለቃ በቀር ከሌሎች ቡድኖች ወይም ከጠቅላይ መምሪያው አባሎች ጋር አይተዋወቁም።

ይህ አይነቱ ያደረጃጀት ስልት ያንድ ቡድን አባሎች ድንገት በፖሊስ እጅ ቢወድቁና የሚመረመሩ ቢሆኑ ወደ ሌሎች ቡድኖችም ሆነ ወደ ጠቅላይ መምሪያው አባሎች መምራት ስለማይችሉ ያንዱ ወይም የሌላው ቡድን አባሎች በፖሊስ መያዝ ሌሎችን ቡድኖች እንዳያሰጋና በጠቅላላው የድርጅቱን ስራ እንዳያሰናክል የታቀደ ነበር። ነገር ግን ከሌላ ወገን እኒያ፣ ቅጣቱን ሊፈጽሙ የተመደቡት የታች ቡድኖች ከጠቅላይ መምሪያው ሩቅ መሆናቸው ከጥብቅ ቁጥጥሩም ስላራቃቸው ስራቸው ሁሉ ድርጅቱ የተቋዋቋዋመለትን አላማ መሳት ብቻ ሳይሆን ላላማው ፍጹም ተቃራኒ ሆነ። በሻህ ከሩቅ የሚጮኸው ጩኸት ቁጣዉ፣ ማስፈራራቱ ሁሉ የዘረፋ ላበይት ክፍሎች አላፊዎች የሚሰጠው ትእዛዝ ከያንዳንዱ ያቢይ ክፍል አላፊ ለያንዳንዱ የቡድን መሪ ከዚያ ለቡድኑ አባሎች ሲደርስ ያ ከፊቱ ባይን ሲያዩትና ከድምጹ በጆሮ ሲሰሙት የሚያንቀጠቅጠው የበሻህ ቁጣ በመንገድ ቀርቶ ትእዛዙ ብቻ ስለ ነበር የሚደርሳቸው ፈርተው ከማድረግ የሚታገዱበት ነገር ምንም አልነበረ። መቸም ቁጣ ፊት ለፊት እንጂ ቁጣ በመልክት ይህን ያክል አያስፈራ! ስለዚህ እኒያ ዘረፋ የለመዱ ወንበዴዎች እንኩዋንስ የሞት ፍርድ ብቻ «የሞትና የኩነኔ ፍርድ ባንድ ላይ ነገ እዚህ በመሬት ይፈረድባችሁዋል» ተብሎ ከሩቅ ቢላክባቸው ዘረፋቸውን የሚተዉ አልነበሩም!

በሻህ እኒያን ወሮበሎች መጀመሪያ ድርጅቱን ሲያቋቁም ወዳቀደው መንገድ ለመመለስ ያደረገው ጥረት ሁሉ ከንቱ ድካም ብቻ መሆኑን ሲያይ እንደ ዛተው ለመቀጣጫ ያክል ጥቂቱን በሞት ለመቅጣት አስቦ ነበር። ነገር ግን እነሱን ማስገደል በደረሰው የንብረት ጥፋትና ያካል ጉዳት ላይ የነፍስ ማጥፋት ከመጨመር በቀር ምንም ቢሆን የቀሩትን መጀመሪያ ወዳቀደው መንገድ የማይመልሳቸው መሆኑን ስለ ተረዳ ተስፋ ቆርጦ ድል መሆኑን አምኖ ከመቀበል በቀር ሌላ የተሻለ ማማረጫ አልነበረውም!

ድል መሆንን አምኖ መቀበል ለበሻህ ለዚያ ኩሩ ጀግና እጅግ መራራ ነበር። ነገር ግን ከሱ የተሻለ ማማረጫ ስላልነበራቸው ያን መራራ ነገር ተቀብሎ መዋጥ ነበረበት!

ከዚያ በሁዋላስ? ከዚያ በሁዋላ ምን ያድርግ? ማጅራታቸውን እዬተመቱ ገንዘባቸውን ለተቀሙትና ቤት ንብረታቸውን ለተዘረፉት ሁሉ አላፊው እሱ መሆኑን አስታውቆ እጁን ለፖሊስ ይስጥ፣ ወይስ ይሽሽ? እኒያ ወንበዴዎች ላደረሱት ያካል ጉዳትና የንብረት ጥፋት አላፊው እሱ መሆኑን አስታውቆ፣ እጁን ቢሰጥ፣ ወህኒ ቤት ገብቶ ሲሰቃይ ከመኖር ወይም እዚያ ከመሞት በቀር ቤት ንብረታቸውን ለተዘረፉት፥ የተዘረፈ ንብረታቸው ይመለስላቸዋል? ወይስ ማጅራታቸውን ለተመቱት ካሳ

ይከፈላቸዋል? ከየታባቱ መጥቶ? ታዲያ የሱ ወህኒ ቤት ገብቶ መሰቃየት ወይም መሞት ማነን ይጠቅማላ? ማነንም!

ይህን እጇን በመስጠትና በመእሽ መሀከል ባሳቡ የተነሳውን ክርክር መቁረጥ አቅትቶ ሰሞኑን ሲጨነቅ ሰንብቶ፣ በመጨረሻ ድርጅቱን አፍርሶ ለመሸሽ ወሰነ! ብቻ ያን ውሳኔ እስኪወስን ሰሞኑን ያላለፈውን የመሰልው ጭንቅ እስከዚያ ድረስ በኖረው ህይወቱ ደርሶበት አያውቅም! ይደከመዋል እንጂ ራብ ወይ እንቅልፍ አልነበረው፤ እንዳይደከመው መብላት ፈልጎ እህል ሲጎርስ ጉሮሮው አይውጥለት፤ ሊተኛ ገደም ሲል ከሚያስፈራራ ቅዠት በቀር የሚያሳርፍ እንቅልፍ አይመጣልት፤ እንዲያው ተንገላቶ እንዲያው ከስቶ ከስቶ በሱ ፈንታ የሱ ጥላ ብቻ ቀረ! ለመተኛት አይኖቹን ለብስ ሲያደርግ በሱ ንብረቱን የተዘረፈውና ማጅራቱን ተመቶ ባፍ ባፍንጫው ደሚ የሚጎርፈው ሁሉ ባንድ ላይ ራቁቱን የጣረሞት ሰራዊት መስሎ፣ ሁሉም ረዣዥም ጥፍሩን አሹሎ፣ ‹አታምልጠንም አንተ ወንጀለኛ! አንለቅህም አንተ ወንጀለኛ!› እያለ ሊቀራመተው ዙሪያውን ከቦ ሲንጫጫበት በርግጎ ተንስቶ ይወጣና ቅዠቱ፥ ያወከው ሰውነቱ ጸጥ እስኪል፣ ወዲያ ወዲህ ሲዘዋወር ይቆያል። ያ የሚያስፈራራ ቅዠት እንዳይመጣበት መተኛቱን ትቶ ቁጭ ሲል አቶ ማንደፍሮ መጥተው መልካቸውን እያለዋወጡ ባይነህሊናው ፊት ቁጭ ይሉበታል!

‹ሊፈጸም የማችይል የልጅ አሳብ ነው!› ይሉታል፥ ጥርሳቸውን ብቻ ሳይሆን ፊታቸውን ሁሉ በፌዝ ሳቅ እዬሳቀ።

‹አሁን «አላማህ አላማችን» እያሉ የሚሰበሰቡት ሁሉ ሲያብሉ ነው፤ እውነት አይምሰልህ። አንዱ ገንዘብ ለመቀማት፥ ሌላው ቤት ለመዝረፍ ደግሞ ሌላው ያቄመውንና የቀናበትን ለማጥፋት የሚሰበሰቡ ናቸው። ታዲያ ለዚያ ሁሉ፣ እነሱ ለክፉ አላማቸው ለሚሰሩት ወንጀል ባለዳው አንተ ትሆናለህ!› ይሉታል፤ የፌዝ ሳቅ ይስቅበት የነበረ ፊታቸው፣ ቀላል ደመና እንዳመጣባት ጸሀይ በቅርታ ደብዘዝ ብሎ።

ከዚያ ያን መናጢ ድርጅት ለማቋዋቋማው ማሰቡን ሲነግራቸው በብርቱ ተቃውመው የሰጡት ምክርና ማስጠንቀቂያ ሁሉ አንድ ባንድ ትዝ አለውና፣ ‹እንዴት ትልቅ አዋቂ ናቸው! ትልቅ ነቢይ!› አለ፥ ድምጹን አስምቶ፥ ራሱን እዬወዘወዘ። ያስብ እንጂ፣ አልመሰለውም ነበር!

በሻህ ውሳኔውን ካደረገ በሁዋላ ወዲያው የመምሪያው አባሎች ለሆኑት አራት ጉዋደኞቹ ሲነግራቸው ድንገት የወረደ፥ የበራ መብረቅ የተቀመጠበትን መሬት

ከስራቸው የገለበጠው መሰላቸውና ሁሉ በያሉበት እንዳሉ አይንቀሳቀሱ አይተነፍሱ፥ የከረሩ አይኖቻቸውን በሱ ላይ አፍጥጠው ብቻ ድርቅ ብለው ቀሩ!

«የኒያ ከፉ ሰዎች ከፉ ስራ፥ እንደ ተተኮሰ ጥይት አላማችንን ገደለው! » አለ እብሻህ በሻከረ ድምጽ፤ ስራቸው መበላሸት ከጀመረ ጀምሮ በጆሮው ውስጥ ሲጮህበት የኖረውን ያቶ ማንደፍሮን ማስጠንቀቂያ እንዲሁ ሳያስበው ድንገት መጣበት፤ ከዚያ ንግግሩን ለመቀጠል ቢሞክር ስላቃተው እሱን ትቶ ትንፋሽ እስኪርቀው ስቅስቅ ብሎ አለቀሰ። የሱን ልቅሶ ሲያዩ ጉዋደኞቹም ከድንጋጤያቸው ወጥተው አብረውት ያለቅሱ ጀመር።

«እንግዲህ» አለ ከመሪር ልቅሶ በሁዋላ የሚከተለውን ጊዜያዊ ሰላም አግኝተው ሁሉ ጽጥ ማለት ሲጀምሩ አይኖቹንም አፍንጫውንም በመሀረቡ እዬጠራረገ። «እንግዲህ ከዚህ - ድርጅት ጋር ግንኙነት እንደ ነበረን ምስክር ሊሆን የሚችለውን ማናቸውንም ነገር አቃጠልን አጥፍተን ዛሬውኑ ካዲስ አበባ ወጥጠን ላጭር ጊዜ አንድ ወይም ሁለት ወር ያክል ለብቻዬ ውጪ መቆየት ይኖርብናል» አለና ትንሽ ዝም ብሎ ሲያስብ ቆይቶ «ለመሆኑ በንኡስ ክፍሎች የቡድን አባሎች እጅ በኛ ላይ ምስክር ሆኖ የሚያስጠይቅ የተጻፈ ነገር ይኖራል? » ብሎ ጠዬቀ።

«በደለኞች ማጅራታቸውን የሚመቱበትና ቤታቸው የሚዘረፉበት ምክንያት ተዘርዝሮ የተጻፈባቸው ወረቀቶች ካልሆኑ፥ ሌላ ምንም የለ» አለ ካራቱ ጉዋደኞቹ አንዱ። ሌሎችም ጉዋደኛቸው ያለው ልክ መሆኑን በዬራሳቸው ምልክት አሳዩ።

«ከሱ በቀር ከመሀከላችን ያንዳችን ስም ያለበት፥ በጽሁፍ የሆነ ነገር ወደ ታች ቡድኖች የተላለፈ የለም? » አለ በሻህ፥ ከመሀከላቸው ከሱ በቀር የሚስፍ አለመኖሩን ቢያውቅም ለማረጋገጥ ያክል።

«ምንም የለ። ትእዛዝ ከኛ ወደ ታች ሲተላለፍ ወይም ምልክት ከታች ወደኛ ሲአልክ፣ ያው - እንደ መመሪያው በቃል እንጂ በጽሁፍ የሚደረግ ነገር የለም።»

«ጥሩ ነው። እንግዲህ እኔ ወደ መንዝ ሄጄ እቆያለሁ። እናንተም ከአዲስ አበባ ውቺ ቅርቡም ይሁን እሩቅ ለየብቻ ወደ የዘመዱ ሄዳችሁ ቆዩ» አለ በተሰበረ ድምጽ ልቅሶ እንደገና መጥቆበት ምራቁን እዬመላለሰ እዬዋጠ።

«ያንተ እንጂ የኛው ግዴለም፣ አያስቸግርም» አለ አንዱ አንገቱን ደፍቶ ተቀመጠ፥ ለመስማት በሚያስቸግር ዝቅተኛ ድምጽ።

ከዚያ አንዳቸው ወይም ሁሉ በያዙ ለዚያ አንድ፣ አመት ሙሉ ለተሰራው ወንጀል መሪዎች ወይም ተባባሪዎች ለመሆናቸው ምስክር ወይም ምክትል ሊሆን የሚችል የመሰላቸውን ሁሉ አጥፍተው እዬተቃቀፉ ተሳስመው ሲለያዩ ‹እንገናኛለን! እንገናኛለን!› ተባባሉ።

በሻህ እንዳለው፣ ወደ መንዝ ሄደ። አራቱ ጉዋደኞቹ ግን፥ ካራዳ በቀር ሸሽተው የሚጠጉበት በቅርብም ይሁን በሩቅ ዘመድ ስላልነበራቸው እዚያው አራዳቸው ቀሩ!

በሻህ ሁለት ወር ያህል መንዝ ቆይቶ ሲመለስ፣ ከፖሊሶች ጋር እንደ ተቃጠሩ ሁሉ ወዲያው ተቀብለው ወደ ጣቢያቸው ወሰዱት። እዚያ መርማሪዎች ብቻ በሚያውቁት የምርመራ ዘዴ ሁሉ ሶስት ወር ሲያሰቃዩት ቆይተው ‹የጨለማው ንጉስ› ይባል የነበረው የወንበዴዎች መሪ እሱ፣ ለመሆኑ መስክር ሆኖ ለፍርድ ቤት ሊቀርብ የሚችል ማስረጃ ከሱ አፍ ይሁን ከጽሁፍ ወይም ከሌላ ሰው ሊያገኙ ስላልቻሉ ደቁዋቁሰው አልወስውሰው ለቀቁት! ከሶስት ወር በፊት እዚያ ፖሊስ ጣቢያ ሲገባ ያዬው ሰው ተመልሶ ሲወጣ ‹እሱ ነው› ቢሉት ‹አደለም› ብሎ ባንገቱ በተወራረደ! የተላጨ ራሱ በጎፈረ ፊቱ ተውጦ እንደ ደጋን ጎብጦ፣ ስጋው አልቆ ደሙ ደርቆ አጥንቱ ደቆ በምርኩዝ ተደግፎ እዬተልወሰወሰ ከጣቢያ ሲወጣ ላዬው፣ ለሰው ማስፈራሪያ የተፈጠረ ጉድ እንጂ ሰው አይመስልም ነበር!

መቸም ሰው መንፈሱን አፍርሶ መስራ አይቻል እንደሆነ እንጂ፣ አካሉ እንደ ማናቸውንም ህጻን አፍርሰው የሚሰሩት ነገር ነው! እንዲህ ባይሆን ኖሮ፥ በሻህ እንዲያ ከሰውነት ተራ ከወጣ በሁዋላ እንዲያ ለሰው ማስፈራሪያ እንዲሆን የተፈጠረ፣ በሶት እግር የሚሄድ ጉድ ከመሰለ በሁዋላ ተመልሶ ሰው ባልሆነ ነበር!

ከፖሊስ ጣቢያ እንደ ወጣ ሁለቱ ደካሞች እግሮቹ ያን ያለቀ ሰውነቱን እንኩዋ መሸከም አቅቶዋቸው፥ ወፍራም ምርኩዝ ሶስተኛ እግር ሆኖ እየረዳቸው ትንሽ ሄዶ ሲቀመጥ አርፎ ቆይቶ ደግሞ ትንሽ ሄዶ ሲቀመጥ እንዲህ እዬተቀመጠ እዬተነሳ ረዥም ጊዜ ተጉዞ እንደ ምንም አቶ ማንደፍሮ ግቢ ደረሰ። እሳቸው እግቢያቸው ውስጥ ከምግብ ቤታቸው ስራ አስኪያህ ጋር ቆመው ይነጋገሩ ነበር። በሻህ ምርኩዙን በሁለት እጆቹ ጨብጦ ጐብጦ እዬተልወሰወሰ ወደሳቸው ሲሄድ ከመንቀሳቀሱ በቀር መቃብር ተጸይፎ የተፋው አስከሬን እንጂ ህይወት ያእልው ሰው አይመስል ስለ ነበረ፥ ፈሩት!

«እባክዎ ይማሩኝ አባቴ፥ በድዬዎታለሁ! » አለ እግራቸው ዘንድ! » አሉ አቶ ማንደፍሮ። ደንግጠው እንዲሁ ባፋቸው የመጣውን ተናገሩ እንጂ ባጠገባቸው

የወደቀው ሰው ማን እንደሆነና ምን እንደ ተናገሩ አያውቁም ነበር። ሰራተኛው ቶሎ ሄዶ ከተደፋበት ሲያቀናው ብቻ ምንም ከሰውነት ተራ ቢወጣ፣ ምንም ለማስፈራሪያ የተፈጠረ ጉድ እንጂ በሻህን ባይመስል በሻህ መሆኑን አወቁ።

«እንዴ! እብሻህ ልጄ! አንተ ነህ እንዲህ የሆንህ! » አሉና ሮጠው ሄደው ምርኩዙን እንደ ተደገፈ አጎንብሶ በቆመበት አንገቱም አቅፈው ኡስሚት ጀመር። ከዚያ መሳማቸውን ትተው ስጋው አልቶ ጠጉር ብቻ የተተካበትን ፊቱን እንደ መስታወት ፊት ለፊት ይዘው እያዩ፣

«ምን እንዲህ አደረገህ? ጽኑ እመም ታመህ ኖሮዋል? » አሉ።

«አዎ፤ ጽኑ እመም ታምሜ ነበር» አለ ባሻህ። ያሳለፈው ጽኑ ስቃይ ተመልሶ መጥቶ ባይነህሊናው ስለ ታዬው አይኖቹ እንባ ሞልተው ከንፈሮቹ ይንቀጠቀጡ ነበር።

እንዲያ እንድ ያዙት ሁኔታውን ሁሉ ሲያዩ በጣም አዝነው፥ ልባቸውም እንጀታቸውም በውስጣቸው የሚላወሱ መስሎ ተስማቸውና ወዲያው የሳቸውም አይኖች እንባ ሞሉ።

«እባክህ ክፍሉን አስከፍትለትና እዚያ ይረፍ» አሉ በሻህን ማየቱ ስላሰቀቃቸው አይኖቻቸውን ከሱ ወደ ስራ አስኪያጁ ዘወር አድርገ።

«ይቅር ለእግዚአብሄር ካላሉኝ ማረፍ አልችልም። እባክዎ ‹ይቅር ለእግዚአብሄር› ይበሉኝ! » አለ በሻህ አንገቱን እንደ ደፋ።

«እኔን ምን በደልኸኝ? የበደልህ ሌሎችን ከሌሎችም የበለጠ ራስህን ነው፣ እኔን ምንም አልበደልኸኝ»

«አዎ ግን የስዎን ምክር ብሰማ ኖሮ፥ ሌሎቹንም ራሲነም አልበድልም ነበር። አስበው፥ ተቸግረው የሰጡኝን ምክር አክብሬ ሳልቀበል መቅረቱ ብርቱ በደል ነውና፣ ይማሩኝ፥ አባክዎ። ወደ ፊት ከምክርዎ ይሁን ከትእዛዝዎ አልወጣም» አለ በሻህ ምርኩዙን ጥሎ እግራቸውን ለመያዝ እዬሞከረ።

«ተው ተው፣ ይቅር ለእግዚአብሄር! አሁን ሂድና እረፍ፤ ሲሻልህም ሁሉንም እንነጋገራለን» አሉ አቶ ማንደፍሮ እግራቸውን ለመያዝ ካጎነበሰበት አቃንተው።

ያ ከሰውነት ተራ ወጥቶ፣ አቅሙ ሁሉ ጥሎት ሸሽቶ፣ አጎንብሶ በምርኩዙ እርዳታ እዬተጎተተ የመጣው በሻህ አቶ ማንደፍሮ እንደ ወላድ አስተኝተው በጥንቃቄ ስለ

ተንከባከቡት ካንድ ወር ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ የደረቀ ደሙ እንደገና ሞልቶ የደቀቀ አጥንቱ እንደገና ጸንቶ ስጋ ለብሶ ያለ ምርኩዝ ርዳታ በሁለት እግሮቹ ቀጥ ብሎ ቆሞ የሚሄድ በሻህ ሆነ! ከዚያ በሁዋላ የሽፍትነት ድርጅቱን ለማቋዋቋዋም ከመሄዱ በፊት ስራና ደመወዙን መልሰውለት እዚያው ከሳቸው ጋር ነዋሪ ሆነ። እዚያ እንዳለ ነበር፥ አዛዥ ተካልኝና ከደመቀች ጸሀይ እስከ ልጅዋ የተገናኙ።

## ምእራፍ አስራ ሰባት

# የተከስተ ተፈሪ መኮንን ትምርት ቤት መግባት

ደመቀች ልጅዋ ትምርት ቤት እንዲገባ የተፈቀደለት መሆኑን ረቡእ ወደ ማታ ከሰማች ጀምራ እስከ ቅዳሜ ጥዋት ድረስ ያላትን ትንሽ ገንዘብ እያወጣች ተከስተ ‹እወደዋለሁ› ያላትን ልብስና እቃ ስትገዛ ፍልውሀ ወስዳ አስታጥባ ጠጉሩን ስታስረከርክም ማታ ታጥቦ መተኮስ የሚያስፈልገውን ልብስ እያጠበች ስትተኩስ የድሀ ገንዘብዋ ሲወጣ ትንሽ አይከብዳትም፤ ድካም አይሰማት ተከተ፣ አንዳንድ እንገር ሲገዛለት ደስ ባለው ቁጥር አብራ ደስ እንዳላት እንዲሁ ለልጅዋ የሚሆን ነገር ‹ይገኛል› ወይም ‹ይደረጋል› ወደ ተባለው ቦታ ሁሉ ደስታ እንደ መኪና ሲነዳት ሰነበተች።

‹በጣም ለሚወዱት የማድረግ መስዋእትነት ከማይደረግለት ይልቅ ያድራጊውን ልብስ ደስ ያሰኛል› የሚሉት አሰት አሰት አይደለም። ደመቀች ላንድ አሮጌ ልብስዋ መለወጫ ሳይኖራት ድንገት እመቤትዋ ቢያባርርዋት ላንድ ቀን ስንቅ የሚሆን እንኩዋ ሳታስቀር ያላትን ሁሉ ሙጥጥ አድርጋ አውጥታ በገዛችለት ልብስና ልዩ ልዩ እቃ ልጅዋን በጣም ደስ ሲለው ማየት የሰጣት ደስታ ይህን ያክል ነው የማይባል ቅጥ መጠን ያጣ ነበር።

ምንም እንኩዋ የምትርት ሚኒስትሩ የሰጥዋት ተስፋ የተረጋገጠና የማያወላውል ቢመስልም፥ ተስፋዉ እጅግ ከፍተኛ በመሆኑ እንዲሁ ትልቅ ተስፋ እንዲሁ ሊደርስ የማይችል ጥሩ እልም ሆኖ እንዳይቀር ልብዋ በምስጢር እዬሰጋ በስተፋ ፈንታ ቁርጡን የምትሰማበት ቀን ደርሶ ካላዬች ማመን አቅትዋት ያን ቀን የሞት፣ ወይም የህይወት ፍርዱን ለመቀበል እንድ ተቀጠረ ወንጀለኛ ፍራት በተቀላቀለበት ናፍቆት ትጠባበቅ ነበር። አሁን ያ ቀን የምሥራቹን ይዞ ስለ ደረሰ ደስታዋ ቃል ሁሉ ተሰብስቦ ሊገልጸው

የማይችሉ እንዲያው እንዲሁ ድህነትዋን ረስታ እንደ ሀብታም ተከስተን ደስ የሚያሰኝ የመሰላትን ሁሉ ልግዛ ስትል ድካም ሳይሰማት እረፍት ሳያምራት ጠቅላላ ሁኔታዋን በማየት ብቻ ሊገመት የሚችል እጅግ ትልቅ ነእብር።

ቅዳሜ ጥዋት አዛዥ ጌታቸው ግቢ ሄደው ሰራተኞችን በዩስራቸው አሰማርተው ከጌቶች ተሰናብተው እስኪመለሱ ደመቀች የመጨረሻውን መሰናዶ ታሰናዳ ጀመር።

ያነለት ወደ ትምርት ቤት ሲሄድ እንዲለብሰው ተመርጦ ከተቀመጠው በቀር የተከስተ ልብስ እዩታጠበ ተተኩሶ አምሮ ማታ በሻንጣ ተከቶዋል። አሁን የቀረው አልብሳ አስጊጣ፣ ወደ ትምርት ቤት ወስዳ አስረክባ መመለስ ብቻ ነው። ስለዚህ እንደ ልማድዋ እያባበለች በታቦቱ ሁሉ እያማጠነች ቁርሱን አብልታ፣ አፉንም እንጁንም አጥባ ስታበቃ፣ ከጣሄር ሙደስር የገዛችለትን ዝጉርጉር ሽሚዝ ዝጉርጉር የግር ሹራብና ቀይ ጫማ በዚህ ላይ ከታዩ በፈታዱ የገዛችለትን ጥሩ ሆኖ ተስፍኖ የተተኮሰ ካኪ ኮትና ቁምጣ ሱሪ አልብሳ ጠጉሩን ጥሩ አድርጋ አበጥራ አሳምራ እንደ መስታወት እፊትዋ አቁማ ስታየው ሌላ መሰላት! ያ እኒያ አጊጦ እንዲያ አምሮ እንዲያ ተውቦ እፊትዋ የቆመው ልጅ የስዋ የድሀዋ ልጅ ተከስተ መሆኑን ማመን አቃታት።

ብቻ ያን የመስለ ልብስ አሰፍታ ያን የመስለ ጫማ ግዝታ ጠጉሩን አስከርክማ እንዲያ አድርጋ ያስጌጠች የመጀመሪያ ጊዜዋ ቢሆንም ያ ሁሉ ጨርሶ አዲስ አልመስላት አለ። ያነለት የለበሰውንና ያጌጠውን ጌጥ ከዚያ በፊት ለብሶና አጊጦ ያዩችው መስሎ እዩተሰማት አእምሮዋን ከነከነው። ግን ‹መቸ? የት? እድኔት ሆኖ ሊሆን ይችላል?› ለነህ ጥያቄዎች መልስ መስጠት የሚያስቸግር ሆነባትና አይኖችዋን በልጅዋ ላይ እንደ ተከለች ላጭር ጊዜ ዝም ብላ እነሱን ባሳብዋ ስታወጣ ስታወርድ ትንሽ በትንሽ ያዩችበት ጊዜና ቦታ ትዝ እያሉዋት ሄዱ። ትምርት ቤት እንዲገባ የተፈቀደለት መሆኑን የምስራች በሰማችበት እለት ሌሊት እንጋት ላይ፣ በታያት ቅዠት ነበር ልክ ያለነት የለበሰውን ልብስ ለብሶ ያነለት ያደረገውን ጫማ አድርጎ እንደያነለቱ ጠጉሩን ተከርክሞ፣ አጊጦ ያዩችው!።

ያ፣ ረቡእ ሌሊት እንጋት ላይ የታያት ቅዠት ምንም እንኩዋ በጊዜው ከመጠን ያለፈ አስፈራርቶ ቢያንቀጠቅጣት በተከተሉት ቀናት - አሙስና አርብ - ለልጅዋ የሚያስፈልገውን መሰናዶ ለማጠናቀቅ ጊዜ አልበቃ ብሎ ስትሮሩዋጥ ነፍስ ስላልነበራት የመሰንበቻው ያሳብና የስራ ብዛት ውጦት ሸሽጎት ነበር። ነገር ግን ‹መሰል መሰሉን ያስታውሳል› ነውና እንዳጋጣሚ ተከስተ ያነለት የለበሰው ልብስ ያደረገው ጫማ አለባበሱ፥ የጠጉሩ አከረካከምና ባጠቃላይ አቁዋቁዋሙ ማማሩ እንዲያው ሁኔታው

ሁሉ ልኮ በቅዠትዋ ያዬችው መሆኑ ታወሳት! ስለዚህ ያን ባሳብና በስራ ብዛት ውስጥ ተሸሽጎ ተረስቶ የቆዬውን የሚያስፈራራ ቅዠት ያን አቡበሽር ልጅዋን ከቅፍዋ ቀምተው ሲወስዱባት ያዬችውን ቅዠት ያን አቡበሽር ልጅውና ከቅፍዋ ቀምተው ሲወዱባት ያዬችበትን ቅዠት ያን ልጅዋን ከቀማኛው ለማስመለስ እያማጠነች ተከትላቸው ስትሮጥ ድንገት በሰዋና በቀማኛው መሀከል ልትሻገረው የማትችል ሰፊ ጉድባ አፉን ከፍቶ ሲከለክላት ያዬችበትን ቅዠት ያን ተከስተ ‹እመዬ ተለያዬን ከንግዲህ አንገናኝም!› እያለ እጁን እያርገበገበ በነጭ ጉም ውስጥ ገብቶ ግርማዉ መልሶ ያዬችብትን ቅዠት ያን የሚያስፈራራ ቅዠት በሙሉ ግርማው መልሶ አምጥቶ ስላሳያት እንደገና ፍራት ያዛትና ከፊቱም የባሰ ፍራት ገባትና ተከስተን ከቆመችበት ስባ በቅፍዋ ይዛ እዬተንቀጠቀጠች ትስመው ጀመር! እሱን መሳም ከፍራትዋ የሚከለክላት ይመስል፤ ያስጨነቀች ትስመው ጀመር! እንዲያ በቅፍዋ አጥብቃ ይዛ እያስጨነቀች ስትስመው «እመዬ» አለ እሱም አገትዋን እንደ ያዘ።

«በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ! » አለች «አቤት» በማለት ፈንታ። ፍራቱ አእምሮዋን አደንዝዞት ሰል ነበረ፣ አልሰማችውም።

«እመዬ» አለ ደገመና። አሁንም አልሰማችውም።

«እመዬ ምን ሆነሻል? »

«እ? ም - ምንም አልሆንሁ» አለች ከንቅልፍዋ እንደ ቀስቀሰዋት ብንን ብላ።

«ዛሬ ሄጄ እዚያው ልቀር ነው? ካችኒ ጋር አልመለስም? »

«እ? » አለች አሁንም አሳብዋን ገና ማጠቃለል ስላልቻለች።

«ዛሬ ሄጄ እዚያው ልቀር ነወይ? ካንቺ ጋር ተመልሼ አልመጣም ወይ? » ነው ያልሁሽ አትሰሚኝ? »

«እ - ! አዎ፤ ዛሬ እዚያው ትቆያለህ፤ በሌላ ጊዜ መምጣት ስትፈልግ አመጣሀለሁ።»

«እባክሽ እመዬ፣ ዛሬ ተመልሼ ልምጣና በሌላ ቀን ሄጄ እዚያው ልቅር! »

«ዛሬስ እዚያ ብትቆይ ይሻላል፥ የኔ ጌታ! ያለዚያ ላንተ የተባለውን ቦታ ለሌላ ልጅ ይሰጡብንና ዳግመኛ ቦታ ሰለሚገኝ፥ ያ ጥሩ ትምርት ቤት ይቀርብሀል።»

«ይቅርብኝ፣ ለሌላ ልጅ ይስቱት፣ እኔ እዚያ መሄድ አልፈልግም! » አለ ተከስተ የናቱን አንገት እንደ ያዘ እያለቀሰ።

ተከስተ መሰንበቻውን ሲገዛለት የሰነበተው ልዩ ልዩ ልብስ፥ ጫማው ሻንጣው እንኩዋንስ እንደሱ ላሉ የድሀ ልጆች ለብዙ የሀብታም ልጆች የሌላቸው በመሆኑ ያን ይዞ ከናቱ ለሚለይ መሆኑን ሳያስብ በደስታ ሰክሮ የህጻን ልቡ ደስታውን አልችለው ብሎ ቀን በውኑ ሌት በልሙ እሱን ብቻ ሲያይ ከሱ ጋር ብቻ ሲጫወት ሰነበተ። በመጨረሻ ያ ሁሉ ጥሩ ነገር፣ መሆኑን ሲያስተውል፥ ያን ሁሉ ይዞ ያነለት ከናቱ መለየት ቁርጥ መሆኑን ሲያውቅ በጣም፥ ጨነቀው። የተገዛለትን ልብስና እቃ አንኩዋ ከናቱ የሚለዬው እሱ እንደሆነ ሁሉ የወደደውን ያክል ጠላው።

ልጅዋ ሲያለቅስ ስታየው ደመቀችም ልቅሶ መጥቶባት እንዳታለቅስ ይባባል ብላ ፈርታ ልቅሶዋን ለመዋጥ እዬታገለች ወዲያው ሁኔታዋን እንዳያይ አድርጋ ፊቱን በደረትዋ አስጠግታ፣ እንባውን እዬጠረገች ታባብለው ጀመር።

«እኔ አልፈልግም፤ ካንቺ ጋር መሆን ብቻ ነው የምወደው።»

«እኔኮ አልለይህም፤ እዬመጣሁ አደለሁምኮ! »

«አንቺ እምትመጪ እሁድ እሁድ ብቻ ነው።»

«ከፈለግህ ሌላ ጊዜም እመጣለሁ።»

«እኔ ካንቺ ጋር ሆኘ ገዳም ሰፈር መማር ይሻለኛል።»

«እሺ የኔ ጌታ፤ አሁን እየውና፥ ላንድ ሳምንት እዚያው ሆነህ እዬውና ካልወደድኸው መልሼ አመጣለሁ።»

«ላንድ ሳምንት ብቻ? ከዚያ በሁዋላ ተመልሼ እመጣለሁ? »

«ካልወደድኸው መልሼ አመጣሀለሁ።»

ደመቀች እንዲህ ልጅዋን ስታባብል፣ ያ ሲያስፈራራት ሲያንቀጥቅጣት የቆዬው ቅዠት ከራስዋ ባይጠፋም፣ ማስፈራራቱን ማንቀጥቀጡ ቀረ። ከዚያ ያን ክፉ፥ ያን ጨካኝ ቅዠት ያሰበች፥ ያሰላሰለች እንደ ሆነ በዚያ በሚያንቀጠቅጥ ግርማው ተመልሶ እንዳይመጣበት እሱን ለመርሳት የሚረባውንም የማይረባውንም ለልጅዋ ስታወራ የሱን መልስ ሳትጠብቅ እንዲሁ ስትለፈልፍ አዛዥ ከጌታቸው ግቢ ተመልሰው ወደ ተፈሪ መኮንን ትምህርት ቤት ይዘዋቸው ሄዱ።

አዛዥ፥ ተፈሪ መኮንን ትምህርት ቤት የት እንዳለ ያውቃሉ እንጂ፥ እንኳዋንስ ግቢውን ከውጭ አጥሩንም ቀርበው አይተውት አያውቁም። ስለዚህ ከውጭ አሩንም ቀርበው አይተውት አያውቅም። ስለዚህ በምእራብ እበር ሲደርሱ በሩ እንደተዘጋ ያን ሰፊ አገር አስገብተው አዩና ወዳንድ እንገዳ አለም የመጡ መሰላቸው። እውነትም ገዳም ሰፈር ለሚኖር ሰው እንደ ተፈሪ መኮንን ትምርት ቤት ያለ ቦታ እንግዳ አለም ነው።

የተፈሪ መኮንን ትምርት ቤት ከታች የቀበና ኸረት ረግጦ ከላይ የጌን ባትክልት ያጌጠ ጋራ ተንተርሶ በዙርያውና በውስጡ የበቀሉ ለምለም እጽዋት አጠልለውት ከራስጌው ኮረብቶች የሚፈልቁ በራድ ምንጮች ያለማቋዋረጥ እያጠጡት ዘወትር እዬተከረከመ ከሚከፈከፍ ለምለም ሰርዶና ልዩ ልዩ ቀለም ካላቸው ምርጥ አበቦች ተሰባጥሮ አምሮ በተሰራው ምንጣች ላይ በሰላም ተኝቶ ሲታይ፥ ያ ጠቅላላ ሰላም ለሚያዩት ሁሉ ሰላምን ይሰጣል። ያን ጠቅላላ ልምላሜ ማየቱ ብቻ ያይጠጡ ጥም ይቆርጣል። ያ እግዜር በፈጠረው ውበት ላይ ሰዎች ጨምረው ያሳመሩት ቦታ ውበቱ ልምላሜው ሰላሙ ባንድ ላይ ላዘነ ልብ ደስታ ለታወከ መንፈስ ጸጥታ ይሰጥና ለጊዜው ከዚያ ውጭ ያለውን መጥፎ ነገር ሁሉ ያስረሳል።

እዚያ እንዲያ በሚያምር ሰፊ ግቢ ቅዳሜ ትምርት ስላልነበረ፣ የጅኩዋስ ቴኒስና፣ ሌላም ልዩ ልዩ ጨዋታ በዬጉዋዳቸው የሚጫወቱት ቁጥራቸው እጅግ የበዛ ተማሪዎች እነደመቀች ከቆሙበት ከፍተኛ ቦታ በሩቅ ለሚመለከት ያን ጠቅላላ ሰላም ያን ጸጥታ እንዳያውኩ ‹አትናገሩ› የተባሉ ይመስል ድምጽ እንደሌለው ስኒማ እንቅስቃሴያችወና ሩጫቸው ብቻ ይታያል እንጂ ድምጻቸው አይሰማም።

አዛዥ ደመቀችና ተከስተ የሄዱለትን ጉዳይ ረስተው ያን እንግዳ አለም እንዲሁ ከውጭ አይተው ለመመለስ እንደ ሄዱ ሁሉ የበሩን መዝጊያ ተደግፈው ዝም ብለው እያስገቡ ሲመለከቱ ብዙ ከቆዩ በሁዋላ፣

«ግሩም አይደለም፥ ደመቁ? እዚህ መኖር ሳይሞቱ መጽደቅ አይደለም? » አሉ አዛዥ ወደ ደመቀች ዘወር ብለው።

«ግሩም ነው አባባ! » አለች ደመቀች።

ከዚያ አዛዥ እዬፈሩ የበሩን መዝጊያ ቀስ አድርገው ከፊቱና ከቤታቸው ጥግ ተቀምጠው ገበጣ ወደሚጫወቱ ሁለት ዘበኞች ሄደው ሰላምታ ሰጡ።

«ምን ይፈልጋሉ ሽማግሌ? » አለ ከሁለት ዘበኞች ልጅግሩ።

«ምን እንርዳዎ ጌታ? » አሉ ሽምግል ያሉት ዘበኞች የጉዋደኛቸው ጥያቄ ትህትና የጎደለው መሆኑን በማየት ቶሎ አርመው።

«ተማሪ ቤት የሚገባ ልጅ የን መጥተን የሚቀበሉትን ቦታ አንድታመለክቱን ለመለመን ነው ጌቶች! »

«ከዚያ ፊት ለፊት ከሚታየው ጥርብ ድንጋይ ቤት በስተሁዋላ ነው» አሉ ሽማግሌው ዘበኛ ጥርብ ደንጋዩን ቤት ባገጫቸው አመልከተው።

«ከጥርብ ደንጋዩ ቤት ሁዋላ ብዙ ቤቶች ይታያሉ፤ የትኛው ይሆን? »

«ሂዱና እዚያ ተይቁ፤ አታጡትም» አለ ልጅግሩ ዘበኛ እንደ መቆጣት ብሎ።

« ‹አላዋቂ ፎገራ ዱሩ ነው› የሚሉት ሆኖብኝ ነዋ፣ ልጄ! » አሉ አዛዥ ትንሽ እንደ መሳቅ ብለው።

«ሀ - ሀ - ሀ - ሀ .....ሀ - ሀ - ሀ - ሀ - ደሞ የፎገራን ዱር ተማሪ ቤት ምን አመጣው? እሱም ተማሪ አመጣው? እሱም ተማሪ ቤት ሊገባ ነው? ሽማግሌ! » ብሎ ልጅግሩ ዘበኛ ከባጥ በላይ ሲስቅ፣ ሽማግሌው ዘበኛ በቁጣ መልክ ገላመጡትና «ኑ ላሳያችሁ» ብለው ተነሱ። አዛዥም የወጣቱ ዘበኛ ብልግና አስገርሞዋቸ ቅንድባቸውን ላይና ታች አጣመው በንቀት አይን ትንሽ አይተውት፥ ደመቀችንና ተከስተን ጠርተው ሊመሩዋቸው የተነሱትን ዘበኛ ተከትለው ተከስተን የሚቀበሉት ሹሞች ወዳሉበት ሄዱ።

እንግዶቹ በዚያ ሰፊ ሜዳ ሞልቶ ልዩ ልዩ ጨዋታ የሚጫወተውን ተማሪ አልፈው ሲሄዱ የሚጣራው ሁሉ እነሱን ለማሳዬት ነው የሚጣራ፣ የሚስቅ ሁሉ በነሱ የሚስቅ እዬመሰላቸው ጉልበታቸው ሲብረከረክ እግራቸው የፈልጉትን ትቶ ያልፈልጉትን ሲረግጥ ያን ግቢ ማቁዋረጡ እንደ ወር ጎዳና ረዝሞባቸው በመጨረሻ ወደ ሚፈልጉት ቦታ ደረሱ።

«የዲኒክተሩ ቢሮ ያው ነው፤ ብቻ ፈረንጅ ናቸው። አፋቸው ካላወቁ ወደ ምክትል ዲኒክተሩ ቢሄዱ ይሻላል እሳቸው አበሻ ናቸው» አሉ ዘበኛዉ ጽህፈት ቤት አዳራሽ እንደ ገቡ፣ የሁለቱን ሽምማንት ጽህፈት ቤት በጃቸው ላዛዝ እያመለከቱ።

«እንዲያውም ፈረንጅ እጣችን አደለም፤ ጉዳያችነን ከፈጸሙልን የኛው አበሻው ይሻሉናል» አሉ አዛዥ ፈረንጅ የሚባለውን ስም ሲሰሙ የፓፓንድሩስ ቁጣ ትንሽ ትዝ ስላላቸው።

ምክትል ዲረክተሩ እድሜያቸው ወደ አምሳ የተጠጋ መልከ ቀና ሲናገሩ፣ ፈገግ ብለው የሚናገሩ ፊታቸው እንግዳ ተቀባይ የሆነ ናቸው። ባጠገባቸው ከጽህፈት ጠረጴዛቸው ባሻገር ባምስት በስድሳ አመት መሀከል የሚሆኑ አጠር ወፈር ብለው ጠጉራቸውን ሽበት ያሰረገው ፊታቸውንም እንደ ሌላ አካላታቸው ጎላ ያለ በብርቱ ቁጣ እዬጮሁ ይናገራሉ። የተማሪዎች ሞግዚት ናቸው። ሌሎች ሰራተኞችም እዚያ ነበሩ።

«ወይ እነዚህ ሰይጣኖች እገሌ፣ እገሌ፣ ሳይባል በሙሉ መቀጣት አለባቸው፤ ያለዚያ እኔ የስንብት ማስታወቅያየን አቀርባለሁ። ሞግዚት ተብዬ አባት ተብዬ በማሳድጋቸው ልጆች ዘወትር እዬተደበደብሁ አልኖርም» አሉ ሞግዚቱ።

«አቶ ተሾመ እኔ ስናገር አብረውኝ እየተናገሩ ስልሰሙኝም እንጂ፣ እኒኮ ተመርምሮ ይህን የሰይጣን ስራ የሰሩት ሲገኙ ‹አይቀጡ› አላልሁም። መቸም ባንድ መኝታ፣ ቤት የሚያድሩት ስድሳ ወይም ሰባ ልጆች ባንድ ላይ ተሰብስበው ይህን ጭቃ አልቀቡዎትም። እስዎም ‹አንዱ መብራት ሲያጠፉ ሁለት ወይም ሶስት የሚሆኑት በጨለማ ከበው ጭቃውን ቀቡኝ› ነው የሚሉት። እንግዲህ ይህን የተንኮል ስራ የሰሩት ከሶስት ወይም ካራት አይበልጡም ማለት ነው። ስለዚህ ሁለት ሶስት ቀን ይታገሱና መርምረን ብናገኛቸው ብርቱ ቅጣት ይቀጣሉ፤ ባናገኛቸው ግን የሚያደርገውን እንወስናለን።»

«አዎ፤ ‹የሚደረገውን እንወስናለን።› የሚደረገውን ተወስኖ አያውቅም እንጂ ይህን ከማለት ቦዝናችሁ አታውቅም። ለኔ መደለያ የተፈጠረ ቁዋንቁዋ ነው። ሁልጊዜም እንዲህ እያላችሁ ነው የምትደልሉኝ» አሉና አቶ ተሾመ ጭቃ የተበከለ ልብሳቸውን እያገላበጡ ሲያዩ ብስጭቱና አዘኑ እንደገና አፍንባቸው «እስቲ እባካችሁ ተመልከቱ! » አሉ ኮቱን ባንድ እጃቸው ሱሪውን በሁለተኛው አንጠልጥለው እዚያ ላሉት ሰዎች ሁሉ እያሳዩ። «እስቲ ተመልከቱ! እነዚህ ልጆች ሁሉም የወለድሁዋቸው ልጆች ነው የሚመስሉኝ እያንዳንዳቸው ሲታመኡ ታምሜ ሲከፋቸው ከፍቶኝ ደስ ሲላቸው ደስ ብሎኝ የምኖር አባታቸው ነኝ፣ ታዲያ ልጅ ባባቱ ይህን የመሰለ የክፋት ስራ ይሰራል? » አሉ ሞግዚቱ እዚያ የተሰበሰቡትን ሰዎች ያዘን መግለጫ ከያፋቸው ለመስማት እዬተጠባበቁ። እውነትም ተማሪዎች በሞግዚትነታቸው ላይ ያን የመሰለ

ከፉ ስራ መስራታቸው የሚያሳዝን ነው። ነገር ግን ልብሱ የተቀባው ጭቃ ብቻ ሳይሆን አልፎ አልፎ ከሰል ጭምር ተቀብቶ ነበርና ከሩቅ ሲያዩት አላዋቂ የሳለው የሚያስቅ ስእል ስለሚመስል እዚያ የነበሩት ሁሉ ምክትል ዲሬክተሩ ጭምር አፋቸውን እዬያዙ እንባቸው እስኪወርድ ይስቁ ጀመር። አቶ ተሾመ ‹ያስተዛዝኑኛል› ብለው በደላቸውን ያሳዩዋቸው ሰዎች በማስተዛዘን ፈንታ ስለሳቁ ቁታና መገረም ባንድ ላይ የሚናገሩትን አሳጥተዋቸው አፋቸውን በሰፊው ከፍተው ዝም ብለው ቆሙ።

«ይቅርታ ያድርጉልኝ አቶ ተሾመ፤ በከሰሉና በጭቃው ነው እንጂ በርስዎ ለመሳቅ..... ገልጌ አይደለም» አሉ ምክትል ዲሬክተሩ ተነስተው ቆመው እንባቸውን እዬጠረጉ።

«ተበደልሁ ብዬ አቤት ስለዎ ከመሳቅ የተሻለ ሌላ ምን ፍርድ ይሰጡኛል? መልካም ዳኝነት ነው፤ የማይገኝ ዳኝነት! » አሉ ሞግዚቱ እንደ ተቆጡ።

«እባክዎ ሁለት - ሶስት ቀን ይታገሱኝ በዚህ ጊዜ ውስጥ ይህን መጥፎ ስራ የሰሩትን ተንኮለኞች አግኝቼ እንዲቀጡ ባላደርግ ከዚያ በሁዋላ ይቀየሙኝ።»

«እስቲ ሊታይ አይደል! » አሉና ሞግዚቱ እያጉረመረሙ ፈንጠር በለው ሲቆሙ ዘበኛው ወደ ምክትል ዲሬክተሩ ቀረብ ብለው አዲስ ተማሪ ይዘው ስለሚጠባበቁት እንግዶች ነገሩና አዛዥ ደመቀችና ተከስተ ቀረቡ።

ምክትል ዲሬክተሩ እንግዶችን ደስ በሚያሰኝ ፊት ተቀብለው የልጁን ስም እድሜውን የትምርቱን ደረጃ የተወለደበትን አገር የወላጆቹን ስምና አድራሻ፣ የሚከፍልለት መንግስት መሆኑንና ይህን የመሳሰለውን የተለመደ ዝርዝር ቶሎ ቶሎ ጽፈው ተከስተን አቶ ተሾመ እንዲረከቡ አደረጉ።

እንግዶቹ አቶ ተሾመን ተከትለው ከጽህፈት ቤቱ አዳራሽ እስኪወጡ ደመቀች ሻንጣውን ይዛ ነበር። ከዚያ ወጥተው ተማሪዎች ወደሚተኙበት ህንጻ ቀረብ ሲሉ፥

«በሉ እንግዲህ ተመለሱ! ሻንጣውን ለልጁ ስጭው እቱ! » አሉ አቶ ተሾመ ቆም ብለው አዛዥንና ደመቀችን እያዩ።

«ሻንጣውን ላድርስለት እንጂ! ወዲያውም የሚተኛበትን ልዬው! » አለች ደመቀች።

«ከዚህ ማለፍ አይፈቀድም።»

«እናቱ ነኝኮ! »

«ብትሆኝም አይፈቀድም። እንኩዋንስ ለሴት ለወንድም አይፈቀድም። ዛሬ እሱ እንግዳ ስለሆነ ነው እንጂ ተማሪዎች ራሳቸው በመኝታ ጊዜ ካልሆነ ቀን መኝታ ቤት እንዲገቡ አይፈቀድላቸውም። በል አንተ ሻንጣህን ተቀበል! » አሉ ሞግዚቱ ስልጣናቸውን አጉልቶ በሚያሳይ መልክና አነጋገር።

«እመዬ አልፈልግም ይቅርብኝ» አለ ተከስተ የናቱን ልብስ በሁለት እጁ ይዞ እያለቀሰ።

«ያዝ እንጂ ምን ያስለቅስሀል! » አሉ አቶ ተሾመ በቁጣ።

«እባክዎ ጌታዬ ትንሽ ይቆይ ፈርቶ ነው» አለች ደመቀች ልጅዋ ሲያለቅስ ስታይ እስዋም እንባዋ መጥቶባት።

«አዎ ፈርቶ! በመጀመሪያው ቀን ሁሉም እንዲሁ ሰው የሚፈሩ ይመስላሉ፤ በሁለተኣኘው ቀን ‹እንስደባችሁ›፤ በሶስተኛው ‹እንምታህቼ› እስኪሉን ድረስ» አሉና አቶ ተሾመ ሻንጣውን ከደመቀች ተቀብለው ላንድ ተከታያቸው ሰጥተው የተከስተን እጅ በግድ ከናቱ አላቀው እያለቀሰ ይዘውት ሲሄዱ «እመዬ እንግዲህ ተለያዬን አናገኝም! » አለች ዘወር ብሎ። ደመቀች የልጅዋን ሁኔታ ስታይ ስቅቅ ብላ ታለቅስ ጀመር። ከስዋ ተለይቶ የሄደበት ሁኔታና ‹እመዬ ተለያዬን አናገናኝም› ያለው ቃል የረቡእ ጥዋቱን ቅዠት አስታውሳትና ፍራት እንደ ብርቱ ብርድ እልብዋ ውስጥ ገብቶ እያንቀጠቀጣት ስታለቅስ አዛዥ ቢቆጥዋትም እልብዋ ውስጥ ገብቶ እያንቀጠቀጣት ስታለቅ አዛዥ ቢቆጥዋትም ቢያባብልዋትም መጽናናት አቃታት። ከዚያ ግቢውን የሞላው ተማሪ ልቅሶዋን እንዳያይ አፍዋን በኩታዋ አፍና ሳግ እዬተናነቃት አትሩን ወጥታ አንድ ድንጋይ ላይ ተቀምጣ ልቅሶዋን ስትቀጥል፥

«እንዲያውኮ ለስሚው ግራ ነው! መንግስት ልጁን እያስተማረ ሊያሳድግ ሲወስድለት ‹እልል› በማእልት ፈንታ የሚያስለቅስ አለ? » አሉ አዛዥ እንደ መቆጣት ብለው።

«እውነ.......እውነትዎን ነው፤ አባ......አባባ! ብቻ ፈራሁ» አለች ደመቀች ንግግርዋን ሳግ እያቁዋረጠው።

«ልጅሽ ተማሪ ቤት ገባ እንጂ አልታሰረ! ለምን ትፈሪያለሽ? »

«እንጃ እንደ ዛሬው ባብቸ አላውቅም፤ ልጄ ምን ሊሆንብኝ ይሆን? በቀደም ጥዋት.....» አለችና ጥዋት ያዬችውን ቅዠት ለአዛዧ ልትነግር ስትሞክር እሳቸውም ‹ምን ልትነግረኝ ነው› ብለው ሲጠብቁ ወዲያው የቅዠት ስእል በአይነ ህሊናዋ ፊት ቆሞ ሳላስፈራራት መልሳ ዝም አለች።

«እ......! ‹ልጄ ምን ይሆንብኝ ይሆን?› ላልሽው ልጅሽ እንዲህ ባለ ገነት ሲገባ ደስ ብሎት እዬተማረ ያድጋል እንጂ ምንም አይሆን። ይልቅ ትሰሚኝ እንደሆነ ልምከርሽ፣ አንዳንድ ጊዜ የሽማግሌ ምክር መስማት መልካም ነው። ማንም ቢሆን ለልጁ ከዚህ የበለጠ የሚያደርግ የለም፤ ልጅሽን ጥሩ መንገድ አስይዘሽዋል። ከንግዲህ ወዲያ ራሱን አይጥልምና አንቺም ራስሽን እንዳይጥ፣ ለሱ ከምታስቢው ቀንሰሽ ለራስሽ አስቢ።»

«አይ.....አባባ! እንዴት አላስብ? ከኔ ሌላ ማን አለው? ለኒስ ማን አለኝ? »

«እሱን መንግሥት ከሚያስብላቸው ጋር ጨምረሽዋል፤ ከንግዲህ ወዲያ የመንግስት ነው፤ ያንቺ አይደለም! ላንቺ ግን ያላንቺ ሌላ የሚያስብልሽ የለም። በይ አሁን ተነሺ እንሂድ በርጋታ እንነጋገርበታለን።»

«እኒህ ሞግዚቱ ጨካኝ ናቸው፤ የልጆች አሳዳጊ መሆን የሚገባቸው አይደሉም አባባ! » አለች ደመቀች መንገድ ሲጀምሩ ተከስተን እያለቀሰ አንጠልጥለው የወሰዱበት ሁኔታ ታያትና።

«እውነትሽ ነው፤ የልጆች አሳዳጊ የሚሆኑ አይደሉም፤ የሚናቁ አነብናቢ አይነት ናቸው። የልጆች አሳዳጊ መሆን የሚገባው መከበርና፣ መታፈር የሚያውቅ፣ ምሳሌነቱን ሊከተሉት የሚገባ ሲሆን ነው። እኒህስ....እንጃ! እንዲያው.......ለሞግዚትነት ሳይሆን ለመጭዋቻነት ያስቀመጥዋቸው ናቸው መሰለኝ! » አሉ አዛዧ እንደ መሳቅ በለው።

## ምእራፍ አስራ ስምንት

# ዱብእዳ

«እመቤታችን ልክ፥ ‹ግልገልሽን እንቀማሽ› እንደ ተባለች አራስ ነብር ተቁዋጥረው ተቀምጠው እንኩዋንስ ለማነጋገር ለማየት፥ ያስፈራሉ፤ ስለዚህ ፈርቼ ሳልነግራቸው መጣሁ» አሉ አዛዥ ደመቀች ስራዋን ትታ የሰነበተችበት ለወይዘሮ ጽጌ አስረድተው እንዲቀበልዋት ለመለመን ከሄዱበት ተመልሰው።

«እንኩዋን አልነገርዋቸው! እንዲህ በተቆጡበት ጊዜ ቢነግርዋቸው ኖሮ እንኩዋንስ፥ እኔን ሊያማልዱ፣ ለራስዎ አማላጅ ፍለጋ ይሄዱ ነበር! ብቻ ምን ሆነው ይሆን? » አለች ደመቀች።

«ምን አውቃለሁ እባክሽ! የህታቸው፥ የወይዘሮ ብርቄ ልጅ ከነጋ ሁለተኛ ጊዜ መምጣቱ ነው አሉ፤ በቆይታ አነጋግርውት ሲወጣ፣ ገብቸ እጅ ብነሳ የሰደብሁዋቸው ይመስል ሲገላምጡኝ ጊዜ ቀስ፥ ብዬ ወደ ሁዋላ ሸሸሁ። ምን ብሎዋቸው እንደ ሄደ እግዜር ይወቀው! »

«ማነው እሱ? »

«ሻምበል ዳኘ ይባላል፥ የፖሊስ ሹም ነው። አታውቂውም? »

«ስሙን ሰምቻለሁ ይመስለኛል፤ ይሄ.... ‹ጥቁር ፋሽስት› የሚሉት አይደለም? »

«አዎ፤ እንዲያ ይሉታል። ብቻ ለምን እንደሆነ አላውቅም፤ መቸም እኔ ሳውቀው፥ በጣም ደግ ነበር፤ እዚሁ እኛ ያሳደግነው ነው።»

«እስዎ የሚያውቁት ድሮ ይሆናል፥ ከዚያ ወዲህ አይለወጥም? »

«የሰው ነገር ምኑ ይታወቃል? ተለውጦ ይሆናል! » አሉ አዛዥ።

ከዚያ ሁለቱም ትንሽ ዝም ብለው ቆዩና፥ «እኮ ታዲያ መጨረሻው ምን ይሁን? ዝም ብዬ ሄጄ፥ እጅ ልንሳና - የሚሉኝን ልስማ? » አለች ደመቀች።

«እስቲ - ትንሽ ቆይ፥ ፊታቸውን አይተን ነው።»

«ጌቶች ቢኖሩ - ምናልባት ይነግሩልኝ ነበር። መቸ ነው የሚመለሱ? »

«እሳቸውስ ሁልጊዜም ሀረር ከሄዱ ቶሎ አይመለሱም። ዋና ንብረታቸው እዚያ ስለሆነ የቤቱም ሆነ የርስቱ ጣጣ አይለቃቸውም። ኧረ አሁን ትንሽ ቁጣቸው በረድ ሲል ፊታቸውን አይቼ እኔ እነግራቸዋለሁ! ግዴለሽም፥ ያንቺ አለመኖር ምን ያክል እንደሚያጎል ተረድተውት ሰንብተዋል! »

«እንዲያው ለመሆኑ አባባ! » አለች ደመቀች በጠቅላላው የመቤትዋ ታያትና «እኔስ መቸም እስከ ዛሬ የጠበቀኝ አምላክ ወደፊትም መውደቂያ አያሳጣኝ ይሆናል! እሳቸው እስከ መቸ እንዲህ ራሳቸውንም ሰውንም ሲያስቸግሩ ይኖራሉ? አምስት አመት ሙሉ አብሬያቸው ስኖር፥ ዘመዶቻቸው በሚሰበሰቡበት ጊዜ በመጠጥ ብዛት ሞቅ ብሎዋቸው ራሳቸውን ሲረሱ ካልሆነ፥ አንድ ቀን ግንባራቸው ተፈቶ ሲስቁ ሲጫወቱ አይቻቸው አላውቅም! ሁልጊዜ ግንባራቸውን ቁዋጥርወ እንደ ተቆጡ እንደ ተነጫነጩ ናቸው። ከጌቶች ጋር እንኩዋ ሁለት ሶስት ቃል ተነጋግረው ሁልጊዜም፥ ማሳረጊያው ልቅሶ ነው! ታዲያ እንዲህ ያለው ምን ባህሪ ነው? አሁንማ ሁልጊዜ የሚቆዋጥሩት ግንባራቸው ለምዶበት፥ እዚያው እንደ ተቁዋጠረና ያለ እድሜያቸው አሮጊት አስመሰላቸው»።

«እውነትሽን ነው፤ ያሳዝናል! ታዲያ ፊትኮ እንዲህ አልነበሩም፤ ደስ ብሎዋቸው እንኩዋንስ የቅርባቸውን ደርሶ ሂያጁን ሁሉ፥ ደስ የሚያሰኙ፣ ዘንካታ እመቤት ነበሩ! ገና ከጌቶች ሲጋቡ ጀምሬ ነው የማውቃቸው። ከዚህ ከሹመት፥ ጎፉ ሄደን እስክንመለስ ሁሉ ደህና፥ ነበሩ፤ ተመልሰን ከመጣን ነው የተለወጡ! »

«ታዲያ ምን ነካቸው? »

«ዘመዶቻቸው ናቸው።»

«እንዴት ዘመዶቻቸው? »

«አንድ ክፉ ውርደት እንዲደርስባቸው አደረጉዋቸውና፥ ከዚያ ወዲህ ተመልሰው እሳቸው ሳይሆኑ ቀሩ።»

«አበስኩ - ገበርኩ! እመይቴ? ውርደት? የምን ውርደት? አባባ! »

«እባክሽ መቸም በባልና ምሽት መሀከል ዘመድ ከገባ ሰላም ከዚያ መውጣት አለበት! ጌቶችም የሜቴም ዘምዶች ደጎች አይደሉም። የሁለትም ወገኖች ተቆርቁዋሪዎች የመምሰል ዋጋቸውን ለመክፈል በሁለቱ አሳብ የሚቆረቁር ነገር

በዬጊዜው ሲተክሉ ሲተክሉ ተዋደው ተስማምተው የሚኖሩትን ባልና ምሽት ልብ ለልብ እንዲሻካከሩና እስበሳቸው እንዲጠራጠሩ አደረጉዋቸው። የጌቶችም ዘመዶች ይመጡና ‹ፍሬ ማትሰጥ መካን ሴት አብተህ ስምህም የደከምህበት ሀብትም ጠፍቶ እንዳይቀር ወይ እስዋን ፈተህ ሌላ አግባ ያለዚያ ወላድ ሴት በጎን ማስቀምጥ አለብህ› ይሉዋቸዋል። አንዳንዶቹ እንዲያውም ‹ይህን ካላደረግህ የዝምድና ማሰርያችነን ቆርጠን እንጥላለን› ብለው ያስፈራሩዋቸዋል። የሜቴ ዘምዶች ይመጡና ‹ልጅ ካልወለድሽ ለባልሽ ፍቅርም ሆነ ለህብቱ ንቁል ነሽ። ስለዚህ እንደ ምንም ብለሽ ልጅ ማግኘት አለብሽ› ይሉዋቸዋል። ስለዚህ ጌቶች፥ እሜቴን አሁንም ቢሆን ስለሚወዱዋቸው ለስማቸውም ሲሉ ‹የረኸም ጊዜ ሚስቴን ሞት ይለዬኝ እንጂ አልፈታም› አሉ። ነገር ግን እኒሁ ዘመዶቻቸው ‹ወላዶች ናቸው› እያሉ በዬጊዜው እያለዋወጠው የሚያመጡላቸውን ሴቶች እዚያው ከነሱ ጋር እያስቀመጡ እነሱን ጭምር መቀለባቸው አልቀረም።

«እንዲሁ የሜቴ፥ ዝመዶች» መለኩሴ ይሁን ጠንቁዋይ ወይም ቃልቻ እዬሰበሰቡ እያመጡ አንዳንድ ጊዜም፥ ጌቶች በሌሉበት እሜቴን፥ ራሳቸውን እዬወሰዱ ገንዘባቸውንም ስማቸውንም አስጠፍተው ሁሉም የማይሆን ሲሆን ጊዜ፥ በመጨረሻ - የተሰራውን እዚህ አገር ከባልና ምሽቱና ከወይዘሮ ዘርፈሽዋል ውጪ፥ እኔ ብቻ ነኝ የማውቀው ደመቁ! »

«ከጠረጠሩኝ አይንገሩኝ፥ አባባ! »

«ጠርጥሬሽ አይደለም፥ ደመቀች፥ ደመቁ ማስጠንቀቄ ነው! »

«የለም የለም አባባ ይህን ያክል ከባድ ምስጢር ከሆነ ባይነግሩኝ ይሻለኛል፤ ይከብደኛል እንጂ ምንም አያረግልኝ።»

«የለምኮ ጠርጥሬሽ አይደለም፤ አንችን መጠርጠር ራሴን መጠርጠር መሆኑን መቸ አጣሁት? ግዴለም፥ እነግርሻለሁ። እንዲያውም አሁን ሳልነግርሽ ብቀር ምናልባት ከተሰራው የበለጠ የተሰራ ይመስልሽ ይሆናል።»

«ወይዘሮ ዘርፈሽዋል ታውቂያቸዋለሽ? » አሉ አዛዥ፥ ሁለቱም ትንሽ ዝም ብለው ከቆዩ በሁዋላ።

«አላውቃቸውም።»

«አዎ፤ አታውቂያቸውም፤ ይህ መጥፎ እንገር ከደረሰ በሁዋላ መጥተው አያውቁም። ከፊት ግን ከዚህ አይወጡም ነበር።

«ወይዘሮ ዘርፈሽዋል አምቦ አጠገብ የቤተሰቡ ሰፊ ርስት አለ፤ እዚያ የሚኖሩ የሜቴ አክስት ናቸው። ቅድም እንዳልሁሽ፥ አባይ ጠንቁዋይ ሁሉ ምንም ለማድርግ እንዳልቻለ ከታወቀ በሁዋላ፥ እኒህ ሴትዮ ሌላ ዘዴ ፈጠሩ። እሳቸውን ተጠግታ የምትኖር አንዲት ሴት ነበረች። ያች ሴት፥ እዚያው አገር ካንድ ድሀ ባላገር ማርገዝዋን ሲያውቁ፥ ወዲያው እዚህ መጥተው እሜቴን እንዲያረግዙ አደረጉ።»

«እንዴት? ምን ማለትዎ ነው አባባ! »

‹አረገዝሁ› እንዲሉ አደረጉ ማለቴ ነው። ያንጊዜ እዚህ ቤት የነበረው ደስታ እንዴት አድርጌ በምን መስዬ ልገልጽልሽ እችላለሁ! የጌቶችን ሁኔታ፥ እንዴት አድርጌ ላሳይሽ እችላለሁ! ብቻ ጽንሱ እያደገ ሲሄድ አንዳንድ ቀን ወደ ላይ አንዳንድ ቀን ወደ ታች ሆኖ እዬታዬ፥ ‹ምናልባት ዘግይቶ የመጣ ስለሆነ ለህይወታቸው ያስፈራ ይሆን?› የሚል ስጋት ከጌቶች ጀምሮ በሁላችን አደረ። ያች ሴት የምትወልድበት ቀን ሲደርስ እሜቴም አክስቴ ዘንድ ነው የምወልድ ብለው፥ እዚህ ሀኪም ቤት እንዲገቡ ቢለመኑ ሌላው ቀርቶ፥ ጌቶች አብርዋቸው ለመሄድ ቢለምኑ እንኩዋ ‹እምቢ› ብለው ወደ ወይዘሮ ዘርፈሽዋል ሄዱ። እዚያ ያች ባላገር ሴት የወለደች እለት የወይዘሮ ዘርፈሽዋል ታማኝ አሽከርና የስጋ ዘመዳቸው፥ ‹ሌሊት እንቁ እጫካ ውስጥ ቀበርሁዋት› ብሎ በማላ ስላረጋገጠላቸው፣ እሜቴ ዘጠኝ ወር ያረገዙትን ጨርቅ አውጥተው ጥለው የሴትዬዋን ልጅ ወለዱ» አሉ አዛዥ እንደ መሳቅ ብለው፤ «በማግስቱ› አሉ ቀጥለው።

«በማግስቱ እሜቴ በደህና ወንድ ልጅ መገላገላቸውን መላክተኛ መጥቶ ሲነግረን ጌቶችን ተያቸው፥ እኛ ሁላችን የሆነውን ብታይ ‹የቤቱ ሰው በሙሉ አበደ› ትያለሽ! ከዚያ ጌቶች፥ እንኩዋንስ እህል ለመቅመስ ልብስ ለመለወጥ ደስታው አላስችል ብሎዋቸው ወዲያው ተነስተው ሄደው እሜቴንም ህጻኑንም አመጡዋቸው። ብቻ እሜቴ፥ ጣጥባት ስላልቻሉ ህጻኑን ራብ እንዳይገለው ተፈርቶ ሳለ በሁዋላ አንዲት ሴት አኪም መጥታ አይታ፥ ምግብ አዘዘችለትና ዘመዶች ይሰበሰቡና ‹አቤ - ት፥ እንዲያውኮ ከራስ ጠጉሩ እስከግር ጥፍሩ - ቁርጥ አባቱን ነው! እንዲህ ነው አባት እስካሉ አስመሎ ወደ ማለት!› ሲሉ፥ መቸም....... ‹ምኞት ባለበት ማሳመን አያቅት› እንደሚባለው፥ ጌቶች የሁልጊዜ ምኞታቸው፥ ልጅ ማግኘት ስለ ነበረ፥ እውነት መስሎዋቸው የደስታ እንባ አይናቸውን ይሞላዋል። ሶስት ወር ይህ ቤት ፍጹም የደስታ ቤት ሆነ። ከዚያ

በሁዋላ አንድ ቀን አንድ ሰው የመርዶ ደብዳቤ ይዞ መጣ። ለካ ያችን ‹ታንቃ ጫካ የተቀበረች› የተባለች ሴት ያ የወይዘሮ ዘርፈሽዋል ዘመድ እግዜርን ፈርቶ በመግደል ፈንታ እንዳትመለስ አምሎ ወደ ሩቅ አገር ሰዱዋት ኖሮ፥ እዚያ ቆይታ ትመለስና፥ ከልጅ አባትዋ ጋር ተመካክራ ወይዘሮ ዘርፈሽዋልንም እሜቴንም ጌቶችንም በወንጀል ልትከስ መነሳትዋን ለጌቶች ዘመድ ጻፈላቸው። የዚያን ጊዜ ድንጋጤያቸው ይህ ነው አይባልም። በውነት ቢወግዋቸው ደም አይወጣቸውም! ከዚያ ወዲያማ ምን ልበልሽ ለሴትዮዋና ለጅ አባትዋ ሲባል እዚያው አገር ነገሩን ላወቁት ሰዎች አፍ መዝጊያስ ሲባል ከአስር ሺ ብር በላይ ተከፍሎ ‹ዝም ይባል› ተባለና ዝም ተባለ! »

«ልጁስ? » አለች ደመቀች፥ መጨረሻውን ለመስማት ቸኩላ ከላይ ስትተነፍስ ቆይታ።

«ልጁማ ወይዘሮ ዘርፈሽዋል እንዲያሳድጉት ሄዶ እዚያ ሞተ ተባለ።

«እውነት ሞተ? »

«ለወላጆቹ አሉ፤ ለኛ ግን ሞተ! » አሉ አዛዥ ቅርታ፥ ያጠለለው ፊታቸውን ወደ ደመቀች መለስ አድርገው።

«እግዚኦ መሀረነ ክርስቶስ - ! ምንድን ናቸው እኒህ? አባባ! ሰው አናቸው? » አለች ደመቀች የተደፋ ራስዋን በሁለት እጅዋ እንደ ያዘች አይንዋን ብቻ ቀና አድርጋ አዛዥን እያዬች።

«ሰው ናቸው እንጂ፥ ልጄ! ሰው ባይሆኑ፥ የሰውነት ድካም ባይኖራቸው እንዲህ ያደርጉ ኖሮዋል? »

«እንዴት? »

«ሰው በመሆናቸው፥ ባላቸውን ስለ ወደዱ፥ ሀብት ስለ ወደዱ፣ «እንደ ምንም አድርገሽ ልጅ ካላመጣሽ የባልሽን ፍቅርም ሀብቱንም፥ ታጫለሽ› ሲልዋቸው ጊዜ፥ ፈርተው እንዲያ ያለ ክፉ ስራ ሰሩ።።»

«እንጃ! እንዲህ ያለው ያውሬ፥ ስራ እንጂ፥ ‹የሰው ስራ› ሊባል የሚችል አይመስለኝም! እረ እስቲ እይሳቸውን እንተወውና ይህ ሁሉ ከሆነ በሁዋላ፥ ጌቶች ምን ያክል ታጋሽ ቢሆኑ ነው ምሽት አርገው የሚያኖርዋቸው? »

«የሳቸው መቸም የሚያስገርም ነው! ለጊዜው ‹እንከሳለን› ካሉት ሰዎች ጋር እርቅ እስኪሆን ድረስ እንቅልፍም ምግብም ‹እምቢ› ብልዋቸው በጣም ታውከው ነበር፤ በመጨረሻ እንዲያውም ታመው ሀረር ወረዱ። ከዚያ ሲመለሱ በጣም ደህና ሆነው አሳባቸውና ጭንቀታቸው ሁሉ ለሚቴ ብቻ ሆነ። ከዚያ ከፉ ነገር በሁዋላ ያልተመለሱ እንደ ተለወጡ የቀሩ እሜቴ ናቸው። እሜቴ ሰው የማይወድ ተጠርጣሪ ጨካኝ፥ ቅድም አንቺ እንዳልሽው ከዘመዶቻአቸው ጋር መጠጥ ባሞቃቸው ጊዜ ሲስቁ፥ ሲጫወቱ ይታያሉ እንጂ፥ በሌላ ጊዜ ከመጣፋቸው ጋር ካልሆነ ከሰው ጋር መናገር የማይወደ ሆኑ። በተለይ ሴት - ግድ ሆኖባቸው ነው እንጂ - እዚህ በኢት እንድኖር አይወዱም። ልጅ ያላት ሴትማ ማየቱ ብቻ ያሳምማቸዋል። ለምሳሌ አንቺ በጌቶች በኩል ባትመጪና በሁዋላም በስራሽ ባታሸንፊያቸው እንኩዋንስ ይህን ያክል ጊዜ አብረሻቸው ልትኖሪ አንድ ቀን ከልጅሽ ጋር እፊታቸው ቆመሽ ሊያዩሽ ባልወደዱ። እንዲያው እንጃ፥ እሳቸው ልጅ ፈልገው ሲያመጡ ጊዜ ነው መሰለኝ - ልጅ ያላት ሴት አይወዱም! ታዲያ አታምኝ ይሆናል፤ ብቻ የምወደው ጌታየ አሰፋ ይሙት እልሻለሁ፤ ይህ ሁሉ ከዚያ መጥፎ አደጋ በሁዋላ የመጣ ነው እንጂ፥ ከዚያ በፊት ሌላ ነበሩ! አንጃ! ምናልባት ያንጊዜ ሲደነግጡ ምናምን - ለክፍላቸው እንደሆነ ማን ያውቃል! »

«ተከስተን ሲያዩ አይናቸው ደም እንደሚለብስ ደህና አድርጌ ተመልክቻለሁ። ነገር ግን ‹የኔን ማርና ቅቤ እዩሰረቅሽ አብልተሽ ነው ያሳደግሽው› እያሉ ብዙ ጊዜ ስለሚናገሩ በተለይ በሱ ላይ የንፍገት ስሜት ያደረባቸው ይመስለኝ ነበር እንዲህ በጠቅላላው ልጅ የሚያስጠላ ቁራኛ የያዛቸው መሆናቸውን አላወቅሁም። ብቻ ይህን ሁሉ እስከ ዛሬ ለምን አልነገሩኝ? አባባ።»

«እንዲህ ያለው ነገር ምን ተብሎ ይነገራል ልጄ? ዛሬ ምኮ ድንገት ሳላስበው መመለስ በማልችልበት ቦታ ስለ ደረስሁ፥ እስከ መጨረሻው መሄድ ግድ ሆኖብኝ ነው እንጂ፥ ልነግርሽ ፈልጌ አልነገርሁሽም።»

«እሱስ እውነት ነው» አለች ደመቀች። ከዚያ ሁለቱም ትንሽ ዝም ብለው እንደ ቆዩ፥ አዛዡ በመስኮት አስወጥተው አይተው፣

«የምን ፖሊሶች ናቸው? » አሉ፥ እንደ መደንገጥ ብለው ተነሱና። ደመቀች አብራቸው ተነሳች። ወዲያው በሩን ከፍተው ሲወጡ እስዋም ተከትላቸው ወጣች።

«ያቶ ተካ ተስጤ ቤት ይማዶል? » አለ ከፖሊሶች አንዱ።

«አዎ ያዛዥ ተካልኝ ገስጤ ቤት ነው» አሉ አዛዥ ፖሊሱን አርመው።

«አዛዥ ተካልኝ እስዎ ነዎ? »

«እኔ ነኝ።»

«ወይዘሮ ደመቀች ጸሀይ የሚባሉ ሴት እዚህ አሉ? »

«እ? ወይዘሮ - » አሉ አዛዥ፥ የደመቀችን ስም በመጥራት ፈንታ አይን አይንዋን እያዩ።

«ደመቀች ጸሀይ እኔ ነኝ» አለች እስዋ፣ ቶሎ ብላ።

«ሶስተኛ ፖሊስ ጣቢያ ይፈልጋሉ» አለ ፖሊሱ።

«ለ - ለምን? » አሉ አዛዥ ደንግጠው።

«ለጥያቄ ነው ይመለሳሉ፥ ይምጡ እንሂድ።»

«ለጥያቄ ከሆነ - የምትጠይቅዋትን እዚይ አትጠይቅዋትም? »

«ጥሩዋቸው ተባልን እንጂ ጠይቁ አልተባልንም፥ ጌታየ።»

«እስቲ እባካችሁ እባካችሁ እቤት እንግባና እንነጋገር።»

«የለም ሌላ የታዘዝነው ስራ ስላለ እንቸኩላለን።»

«ለሌላኮ አደለም እስዋ ልብስ እስክትለውጥ እደጅ ከምትቆሙ ብዬ ነው።» ፖሊሶች እስበሳቸው ተያይተው እናዛዥ እንዳይሰሙ ድምጻቸውን ዝቅ አድርገው ትንሽ ሲነጋገሩ ቆይተው ጠመንጃቸውን እያወረዱ በጅ በጃቸው ይዘው ገብተው እንደ ተቀመጡ፥ ወይዘሮ ጌጤ ስላልነበሩ ደመቀች፥ ማንቆርቆርያ ሙሉ ጠላ አቅርባ፣ ለነሱም፥ ለአዛዥም እዬቀዳች ከሰጠች በሁዋላ የተረፈውን እፊታቸው አስቀምጣ ልብስ በመለወጥ ፈንታ አብራቸው ተቀመጠች። አዛዥ ገና አንዱን እንደ ያዙ ፖሊሶች ቶልቶሎ ሁለት ሁለት ጠጥተው ሶስተኛውን ሲይዙ «እባካችሁ ጌቶቼ፥ መቸም ስራ ሆኖባችሁ ነው እንጂ እንደ ሁላችን ምሽት እህት - እናት ሳይኖራችሁ አይቀርም! እኔ ስራችሁን የሚያሰናክል ነገር አድርጉልኝ አልላችሁም። የምለምናችሁ የተፈለገችበትን ምክንያት እንድትነግሩኝ ብቻ ነው» አሉ አዛዥ።

«እኛ ምኑን እናቀዋለን አባቴ፥ አምጡ ሲሉን መውሰድ ነው እንጂ! » አለ አንደኛው ጉዋደኛውን እያዬ።

«አዎ፥ እኛ እምናቀው ትንሽ ነው። ብቻ - ነገሩ ከዚሁ ከቤታችሁ የተነሳ ሳይሆን አይቀርም» አለ ሁለተኛው።

«እንዴት? » አሉ አዛዥ።

«ሻምበል ዳኘ እዚህ እናንተ ግቢ ሁለት ጊዜ እዬተጠሩ ገብተው ሲነጋገሩ ብዙ ከቆዩ በሁዋላ ነው እኛ ወደዚህ የተላክነ። መጀመሪያ ጥዋት ሲጠሩ፣ አብሬያቸው መጥቸ እሳቸው ሲገቡ እኔ እውጭ ቆዬሁ። ሁለተኛ ሲጠሩ ‹የተፈለግሁ እንደሆነ ቅድም በሄድንበት ቦታ ነኝና መጥተህ ንገረኝ› ብለውኝ ሄዱ፣ ለዚህ ነው የነገሩ መነሻ እዚህ ሳይሆን አይቀርም ማለቴ። ገምቼ ነው በርግጥ የማውቀው ነገር ኖሮ አደለም» አለ ዘበኛው።

«እግዜር ይስጣችሁ ጌቶች እግዜር ይስጣችሁ ለመሆኑ እዚያ እጣቢያው ይችን ልጅ ምን ያረግዋት ይመስላችሁዋል? »

«መሰንበቻውን እዚህ ግቢ የሆነ ነገር አለ? » አለ አንዱ ዘበኛ።

«ኧረ የለም! » አሉ አዛዥ ደመቀችን እያዩ።

«የለም» አለች ደመቀችም።

«እንግዲህ ምንም አይሉሽ አይዞሽ፥ አትፍሪ! ብቻ ሲጠይቁሽ ልብሽን ሞልተሽ ሳሽበሪ፣ እያሰብሽ መመለስ ነው። እነሱ ለማደናገር ይፈልጋሉ፤ አንቺ ያኑ መጀመርያ የተናገርሽውን እውነቱ ብቻ መናገር ነው እንጂ ቃል አለመለዋወጥ ነው። አሁን ተነሽ እንሂድ» አለ ዘበኛው ብርጭቆውን አስቀምጦ። ከዚያ አዛዥ ጭምር ወደ ሶስተኛ ፖሊስ ጣቢያ ሄዱ። እዚያ ሲደርሱ ደመቀችን አስገብተው እሳቸውን ውጭ አስቀሩዋቸው። ያነለት ሁለተኛ አላዩዋትም። አዛዥ እዚያ ቆመው የሚወጣ የሚገባው ሁሉ ደመቀች የሆናቸውን የሚያውቅ እዬመሰላቸው ሲጠይቁ አምሽተው፥ ምንም ወሬ ስላጡ እንደገና ወደ ቤት ተመልሰው ምንጣፍ ልብስና ራት ወስደው ለፖሊሶች አስረከቡ። ይድረሳት አይድረሳት እግዜር ይወቀው!

ደመቀች ልጅዋን ተፈሪ መኮንን ትምህርት ቤት አስገብታ እንደ ተመለሰች ሶስተኛ ፖሊስ ጣቢያ ከሄደችበት ጀምሮ ምሳና ራት እያስያዙ በቀን ሁለት ጊዜ እጣብያው

ሳይደርሱ ቀርተው አያውቁም። ነገር ግን እንኩዋንስ ተገናኝተው ሊያነገግሩዋት እንኩዋንስ ባይናቸው ሊያዩዋት ርግጠኛ ወሬዋን የሚነግራቸው ስላጡ ‹ደርሶባት ይሆናል› ብለዋል ብለው ያላሰቡት ክፉ ነገር የለም። የወሰዱትን ምግብ ከፍተው አስመርምረው ስምዋን ጭምር ለተቀባዩ ፖሊስ ይሰጡና፥ እዚያ ቆመው ታስሮ የሚመጣውን ታስሮ ሲመረመር ሰንብቶ የሚለቀቀውን ከምርመራ በሁዋላ በዝግ ካሚዮን ወደ ፍርድ ቤት የሚሄደውን ሲመለከቱ ቆይተው እዚያ መሀከል አለመኖርዋን ሲያረጋግጡ ግራ እንደ ገባቸው ነገሩ ከለት ወደለት እንደ ጨለመባቸው ይመለሳሉ። ሻምበል ዳኘ፣ እጽህፈት ቤቱ በሚገኝበት ጊዜ ሊያዩት ሲጠይቁ፣ ምክንያት እዬፈጠረ እንዳይገቡ ያስከለክላቸዋል። ነገር ግን ደመቀች ከታሰረች ጀምሮ ቢያንስ በቀን አንድ ጊዜ ወይዘሮ ጽጌን ሳያይ ስለማይውል እመቤታቸውን በመፍራት ‹አዩኝ አላዩኝ› ሰላምታ እንደሚሰጡት ቀረብ ብለው የጠየቁት እንደሆነ ነገሩን ከችቦ ገለባ አቅሎ የማታለል መልስ ሰጥቶዋት ይሄዳል።

«ማን ነች እሰዋ? አ.....! አዎን አዎን ደመቀች! ስራ ስለበዛ ተራዋ አልደርስ ብሎ ይሆናል እንጂ፥ እሰዋኮ ምንም የለባትም! ለጥያቄ ብቻ ነው የሄደችው፣ ዛሬ ያለዚያም ነገር ትለቀቃለች! » ይላቸዋል አንድ ቀን።

«አልተለቀቀችም እንዴ! እስቲ አሁን ስሄድ እጠይቃለሁ» ይላቸዋል በሌላው ቀን።

«ይች ሴት ተለቀቀች? » ይላል ደግሞ በሌላው ቀን ገና፥ ሊጠይቁት ወደሱ ማምራታቸውን ሲያይ።

እንዲሁም የፖሊስ ጣቢያዎችንና ፍርድ ቤቶችን እናውቃለን ለሚሉ ሰዎች ሲያዋዩዋቸው የሚነግሩዋቸው ሁሉ እስበሱ የሚፋለስና ይይዙትን አሳጥቶ ተስፋ የሚያስቆርጥ እንጂ መውጫ መንገድ የሚያሳይ ትንሽ የተስፋ ጮራ ያለው አይደለም።

«መቸም በልማዱ ፖሊሶች ቀላሉን ነገር ከባድ አስመስለው ነው የሚናገሩ፤ ስለዚህ ሻምበል ዳኘ እንዲህ ከነገረዎ ቀላል ቢሆን ነው የሚናገሩ፤ ስለዚህ ሻምበል ዳኘ እንዲህ አቃልሎ ከነገረዎ ቀላል ቢሆን ነው» ይላቸዋል አንዱ።

«አሄ - ! ፖሊሶች የሚሉትን ያምናሉ? እነሱ ንጹሀን ወንጀለኛ ለማድረግ የሰሩትን ሰርተው እግባቸው እስኪደርሱ ‹ነገሩ ቀላል ነው እያሉ እርስዎ መከላከያ መንገድ እንዳይፈልጉ ማቦዘኛ ዘዴያቸው ነው» ይላቸዋል ሌላው።

«እንዴ - ! ፖሊሶችኮ ያሰሩትን ሰው ካርባ ስምንት ሰአት በላይ ለፍርድ ቤት ሳያቀርቡ በጃቸው ሳያቆዩት በህግ ተከልክለዋል። ስለዚህ ይች ልጅ ይህን ያክል ቀን ፖሊስ ጣቢያ መታሰርዋን ለፍርድ ቤት የሚያመለክትላት ዘመድ ቢኖር የፖሊስ ባለስልጣኖችን አስቀጥቶ አሁን ያስፈታት ነበር! » ይላቸዋል ግሞ ሌላው።

«አሆ - ! ‹ሞት ያማራት አይጥ የድመት አፍንጫ ልትልስ ትሄዳለች› የሚሉት ነው፤ የፖሊስ ባለስልጣኖችን መክሰስ በዚች ልጅ የባሰ ችግር እንዲደርስባት ማድረግ ነው። ይልቅ ዘመድ የሆነ ሰው እንደ ምንም ተቸጋግሮ ከነሱ ጋር መስማማት ነው» ይላል አሁንም ሌላዉ።

አዛኙ፣ ይህን ሁሉ ከያፉ ከሰሙ በሁዋላ አሳባቸው የባሰውን መሰብሰቢያ ያጣ ብትን ይሆንባቸውና፥ ማነኛውን እንደሚይዙ ግራ ይገባቸዋል። በደመቀች እስራት ወይዘሮ ጽጌ ያሉበት መሆናቸውን መጀመሪያ የወሰድዋት ፖሊሶች ከነገሩዋቸውም ሌላ፣ ሻምበል ዳኘ ለብዙ ጊዜ ግቢያችውን ረግጦት የማይውቀውን በዬቀኑ እየመጣ በቆይታ መነጋገሩ፥ አንድ ማስረጃ ሊሆን የሚችል ነው። ብቻ ደመቀች በልጅዋ ትምህርት ቤት መግባት ምክንያት ሳትሰናበት ስራዋን ከማስታጎልዋ ሌላ በፖሊስ ያን ያክል ቀን የሚያሳስር ወንጀል ‹ትሰራለች› ተብላ የማትጠረጠር መሆንዋን ስለሚያውቁ ሳትሰናበት በመሄድዋ ብቻ ‹በፖሊስ ያሳስሩዋታል› ብለው ማመኑ አስቸገራቸው። ስለዚህ ደመቀች የታሰረችበትን ምክንያትም ሆነ የምትፈታበትን መንገድ ለማግኘት የደከሙት ድክምና እናውቃለን ከሚሉት የተቀበሉት አሳብ ሁሉ እንደ ተቀላቀለ ብርቱ መጠጥ ራስ የሚያዞር እንጂ፣ ምንም የማያሳይ ስለሆነ፥ ሁሉም «ቀን ይፍታው» ብለው ትተው በቀን ሁለት ጊዜ ምግብ እዬወሰዱ ለፖሊሶች ‹አደራ› እያሉ እያስረከቡ ዝም ብለው ይጠባበቁ ጀመር።

አንድ ቀን ጥዋት ወይዘሮ ጽጌ ከግራና ቀኝ መከዳዎች መካከል በተነጠፈ ፍራሽ ላይ ተቀምጠው እፊታቸው ባትሮንስ ፈንታ አንድ መከዳ አስቀምጠው በዚያ ላይ ዳዊታቸውን ዘርግተው ሲደግሙ፥ ወይዘሮ ማረክሻቸው ገብተው ‹ዳኛቸው መጥተዋል› አሉ። ወይዘሮ ማረክሻቸው፥ ከወይዘሮ ጽጌ ድሆች ዘመድ አንድዋ ናቸው። ደመቀች መምጣት ከተወች ጀምረው፥ ወይዘሮ ጽጌን የሚረዱ እሳቸው ናቸው።

«እህህ! » አሉ ወይዘሮ ጽጌ በራሳቸው ጠቅሰው። ‹ግባ በይው› ማለታቸው ነው። ሻምበል ዳኘ፥ መለዮውን በጁ እንደ ያዘ ገብቶ ሁለት እግሮችን ገጥሞ ባንገቱ ብቻ እጅ ሲነሳ፥ ወይዘሮ ጽጌ ላንድ አፍታ ቀና ብለው አይተው «እህህ! » አሉ

ባገጫቸው መቀመጫውን ለሻምበሉ እያሳዩ። ከዚያ ቀጥሎ ባለው መዝሙር ለመድረስ የቀራቸውን ለማየት ብራናውን ገልበጥ ገልበጥ አድርገው ባሳቸው ቆጠሩና መጀመሪያ አንዳንድ መስመር ከዚያ፥ ሁለት ሁለት፥ ከዚያ ሶስትም፥ አራትም፥ መስመር እዬዘለሉ ቶሎ ጨርሰው ዳዊታቸውን አጥፈው፥ ተሳልመው ተቀመጡና ምራቃቸውን በጃቸው ላይ «ትፍ - ትፍ» እያሉ ፊታቸውን እያባበሱ አንገታቸውን ደፍተው ከንፈራቸውን ሲመጣጥጡ ትንሽ ቆይተው፥

«ታዲያስ? » አሉ ሻምበል ዳኘን ቀና ብለው እያዩ። ከመበቀል ፍላጎታቸው ጽናት የተነሳ መጀመሪያ ‹እንዴት አደርህ› ማለት የሚገባ መሆኑን እንኳዋ ረስተውታል።

ሻምበል ዳኘ፥ ለተጠዬቀው መልስ በመስጠት ፈንታ አንድ ጊዜ ወይዘሮ ማረከሻቸውን አንድ ጊዜ ወይዘሮ እያዬ ዝም አለ። ከዚያ ወይዘሮ ማረከሻቸው ፊት መናገር አለመፈለጉን ተረድተው።

«እስቲ አንድ ጊዜ ዳኛቸውን ለብቻ ላነጋግረው እትዬ» አሉ ወይዘሮ ጽጌ ወይዘሮ ማረከሻቸው እንዳይቀዬሙ ለማባበል ያክል ትንሽ ፈገግ ብለው። ወይዘሮ ማረከሻቸውም ምንም ቢደኸዩ፥ መልካም አስተዳደግ የሚሰጠው ጸጋ ገና ያልተለያቸው ስለሆኑ «ኸረ እሱን ሳይ ጊዜ ልነግርለት ትመለስሁ እንጂ እኔም ማድቤት የማሰራው ብዙ ስራ ስላለኝ ወደዚያ መሄዴ ነው! » አሉ መቀየማቸውን ላላማሳዬት እውነት የሚመስል የውሸት ፈገግታ ፈገግ ብለው።

«አልሆነልንም እማማ፥ በጣም አዝናለሁ! » አለ ሻምበል ዳኘ፥ ማረከሻቸው ከወጡ በሁዋላ አንገቱን ደፍቶ ግንባሩን ሲያሽ ከቆዬበት ቀና ብሎ አክስቱን እያዬ።

«እንዴት! » አሉ ወይዘሮ ጽጌ ቁጣቸው በፊታቸው ሲነድ እዬታዩ።

«እንዴት! ትናንት ተስፋ አለን አላልኸኝም ነበር? » አሉ ቀጠሉና።

«መስሎኝ ነበር፤ ነገር ግን እንዲያው ከንቱ ድካም ነው ዛሬ ደግሞ እንደገና ወደዚያው ወደ ስነበትነበት ተመልሰን! »

«እጃችሁ ላልቶ ነዋ! አዎ እጃችሁ ላልቶ ነው እንጂ፥ እጃችሁ ጠበቅ ቢል እንኳዋንስ ምልክት ከተገኘ በሁዋላ ወደ ስነበታችሁበት ልትመለሱ እህን ጊዜ - ሁሉም ያልቅ ነበር።»

«የለም እማማ እጃችን አላላም፤ እንዲያውም ከዚህ የበለጠ የመጨረሻ እንጀል በሰሩት ሰዎች የምናደርገውን የምርመራ ዘዴ ሁሉ አድርገናል፤ ምንም የቀረን የለ። ብቻ - እርስዎ ‹ምንም ቢሆን ሌላ ሰው ሊወስደው አይችልም› አሉኝ እንጂ እኔ ‹ሌላ ሰው ወስዶታል› ነው የምል፤ እሱዋ አልወሰደችም።»

«ታዲያ እንዴት ነው ትናንት ምልክት አግኝተናልና ተስፋ አለን ያልኸኝ? »

«ትናንት መርማሪዎች ያለ - መጠን ሲጨክኑባት ‹ጊዜ አስቤ ነገ ልናገር› ብላ ነበር። ስለዚህ ‹ያኑ የፈለግነውን ልትነግረው ነው› ብሎ አምኘ ለርስዎ ይህን ያክል አልገለጽሁልዎም እንጂ፥ በጣም ደስ ብሎኝ ነበር።

«እየውህልህ! እጃችሁ ጠበቅ በማድረጋችሁ ምልክት አግኝታችሁ ነበር! ነገር ግን እውነቱ እስኪወጣ በዚያው በመቀጠል ፈንታ ስለተዋችሁዋት እንደገና ወደ ሁዋላ ተመልሳለች! »

«ያልወሰደችውን ‹ወስጃለሁ› እንድትል ከሆነ አላምችን ይህን ማድረግ አሁን እንችላለን። ነገር ግን የጠፋውን ሀብት ለማግኘት እንደሆነ የወሰደውን መፈለግ አለብን፤ እስዋ እንዳልወሰደችው እርግጠኛ ነኝ።

«ያልወሰደ ሰው ‹አስቤ ልናገር› ይላል? »

« ‹ስቃዩ ስለ በዛብኝ ለማረፍ ብዬ ነው እንጂ እንኩዋንስ› «ጠፋ» የተባለውን እቃ ልወስድ እኒያ ያለ እቃ መኖሩንም አላውቅ፤ «ባትወድጅጂም ወስድሁ በይ» ካላችሁኝ ይህኑ ቃሌን ጻፉልኝና ተሰቃይቼ እንዳልሞት እኛን በመጥፎ ቦታ ከማቆም በቀር ጥቅም ለፍርድ ቤት ማቅረብ እኛን በመጥፎ ቦታ ከማቆም በቀር ጥቅም የሌለው ነገር ነው። ይልቅ ሌላ የሚጠረጥሩት አለ እንደሆነ በከንቱ እስዋ ላይ የምናጠፋውን ጊዜ እዚያ ላይ ብናውለው ይሻላል።»

«ለጌጤና ለልብሴ ብቻ ሳይሆን ለኔስ ለራሴ ቢሆን ከስዋ በቀር ሌላ ማን ጠባቂ ነበረኝና ማነን ልጠረጥርስ? እኔንስ እግዜር ቢጠብቀኝ ነው እንጂ አንድ ነገር ብታደርገኝ መቸም - በጅዋ ነበርሁ! አምስት አምት ሙሉ የሰይጣን ቁራኛ ሆና ተቆራኝታኝ ላባርራት ከቆረጥሁ በሁዋላ ያዞረችብኝ አስማት ልቤን እንደ ውሀ ያፈሰውና እንዲያው በቃ እሱዋ የሄደች እንደሆነ መኖር የማልችል መስሎ ታይቶኝ

መልሼ እተወዋለሁ። ስለዚህ - እስዋ ከገባች ጀምሮ ከስዋ በቀር በጌጤ አጠገብ የሚደርስ የለም።»

«እስዋ ብትወስደው እስከ ዛሬ እናገኘው ነበር፤ ይመኑኝ እማማ! »

«እስቲ አንድ ነገር ልጠይቅህ።»

«ምን? »

«ልጅዋን ተማሪ ቤት ስታስገባ የራስ የደጃዝማች ልጆች የማያገኙትን ልብስና እቃ ገዝታለታለች እሱ፣ እኔ የምሰጣት ደመወዝ - ያውም የዛሬ ሁለት ነው? ወይስ አንድ አመት - ሰባት ብር ሆነላት እንጂ ከዚያ በፊት ከልጅዋ ጋር ሆድዋን ችዬ፥ አምስት ብር ነበር፤ ከየት አምጥታ ነው ያን ሁሉ ነገር የገዛችለት? የኔን ጌጥ ሽጣ አደለም? »

«በሱም ደርሰንበታል እማማ። የትምርት ሚኒስትሩ፣ አምሳ ብር ‹ለልብስ መግዣ ይሁንሽ› ብለው ሰጥተዋታል፤ በዚያ ላይ እሱዋ የቆጠበችው ሀያ ሁለት ብር ከአምሳ ሳንቲም ተጨምሮ በሰባ ሁለት ብር ካምሳ ሳንቲም ለልጅዋ ልብስና እቃ ገዝታለች። ይህ እውነት ነው።»

«ማን አለ? »

«እስዋ።»

«እንግዲህ እስዋ የምትለው ሁሉ፥ ልክ እንደ እግዜር ቃል እውነት ነው ማለት ነው! »

«የለም እስዋ ‹ይህን አለች› ማለቴ ነው እንጂ፥ እውነት ለመሆኑማ እኛ ባለን የማጣሪያ ዘዴ አጣርተን አረጋግጠናል። የነገረችን ሁሉ እውነት ሆኖ ነው ያገኘነው እማማ። ስለዚህ ነው ጌጥዎን የወሰደው ሌላ ሰው መሆን አለበት የምልዎ።»

«ለመሆኑ ምንስትሩ ምናቸው ሆና አምሳ ብር ይሰጥዋታል? »

«ልጅዋን ትምርት ቤት እንዲያስቡላት ልትለምን ሄዳ፥ ዘበኞች ሲያንገላትዋት ልብስዋ መቀደዱን ስላዩ፥ እነሱን ተቆጥተው ልብስ እንድትገዛበት ሰጡዋት»

«እሺ! » አሉ ወይዘሮ ጽጌ፥ የህታቸው ልጅ ‹ጠፋ የተባለውን ጌጥ ደመቀች መስረቅዋን አመነች› ሲለኝ መጣ ብለው በደስታ ሲጠባበቁ ንጹህነትዋን ስለ መሰከረ

በጣም ማዘናቸው በፊታቸው ጎልቶ እዬታዬ። «እሺ ይሁን እስዋን ንጹህ ነች አልህ፤ እኔም ሌላ የምጠረጥረው የለኝ! እንግዲ ያ ሁሉ ጌጤ ለክፉ ቀን ይሆነኛል ብዬ ተስፋ የቆረጥሁት ጌጤ፣ ከልጅነቴ ጀምሬ ያፈራሁትን ገንዘብ ያጠፋሁበት ጌጤ እንዲሁ ጠፍቶ ይቅር ማለትህ ነው? እንዲያው ቢያንስ ቢያንስ ከአምሳ ሽህ ብር በታች የሚገመት አደለምኮ! ምነው ዳኛቸው እናት ህኮ ነኝ! እንዲያው ገንዘቡን ትተን ጥቃቱ ብቻ ከኔ ያነሰ ሊሰማህ አይገባምኮ» አሉ ወይዘሮ ጽጌ እንባቸው አይኖቻቸውን ሞልቶ።

«ይች ሴት አስራ ሰባት ቀን ታስራ በጥብቅ እንድትመረመር ማድረጌ እርስዎ ሌላ ሰው አልሰረቀኝም ስላሉ የልብዎ እንዲያደርስና እንዲሁም ጉዳትዎ ጉዳቴ ጥቃትዎ ጥቃቴ መሆኑ ስለ ተሰማኝ ነው እንጂ ካርባ ስምንት ሰአት በላይ እስረኛ መያዝ ከስልጣኔ በላይ ነውኮ እማማ! በዚህ ብከሰስ ብርቱ ቅጣት ተቀጥቼ ስራየን አጣለሁ! ነገር ግን የራሴ ጉዳይ ስለሆነ በስልጣኔ ሰቼ የበላይ ባለስልጣን የሚሰራብኝን ለመቀበል ቆርጬ ነው።»

«መቀጣትና ስራ መልቀቅማ ለምን? እሱንስ እግዜር አያርገው! እንግዲህ ምን ይሁን? »

«ምንም እንኳዋ እኔ እስዋ እንዳልሰረቀች ርግጠኛ ብሆን፥ እርስዎ ከስዋ በቀር ሌላ የምጠረጥረው የለኝም ካሉ፥ እስዋን ወይጀለኛ አድርጎ ፍርድ ቤት ለማቅረብ ሁለት መንገድ ብቻ ነው ያለ። አንዱ ራስዋ በምርመራ ስታምን ሁለተኛው ምስክር ሲመሰክርባት ነው። መቸም ራስዋ ታምናለች ብሎ ማሰብ ከንቱ ነው። የተደረገው ሁሉ ተደርጎ ውጤቱ የነገርሁዎ ነው። ስለዚህ አሁን የቀረን እቤት ያሉትን ሁሉ ወስዶ በጥብቅ መመርመር ነው፣ ከነሱ መሀከል ሶስት እንኳዋ የሚመስከሩባት ብናገኝ ፍርድ ቤት ልናቀርባት እንችላለን።»

«ማለፍያ ነው። የሰዎችን ስም ተካልኝ ያስጽፍህና ሄደው ይመርመሩ ራሱ ተካልኝም ቢሆን - ይመርመር እንዲያውም አብሮዋት እዬዞረ እቃ ሲገዛላት የሰነበተ እሱ ነው አሉ፤ ከዚህ ወጥታ እይተቀመጠችም እሱ ቤት ነው» አሉ ወይዘሮ ጽጌ፥ የህታቸው ልጅ በመጨረሻ የመጣው አሳብ ወደ ሞት አፋፍ በደረሰ ተስፋቸው፥ ህይወት ስለዘራበት ባዘን ጨልሞ የነበረ ፊታቸው ወገግ ብሎ።

አዛዥ ተካልኝ፥ የቤቱን ሰዎች ስም ለሻምበል ዳኘ ካስጻፉ በሁዋላ፣ መጀመሪያ ተመርማሪው እሳቸው ሆኑ። ወደ ሶስተኛ ፖሊስ ጣቢያ ተጠርተው እሻምበል ዳኘ

ጽህፈት ቤት ሲገቡ ሶስት የፖሊስ መኮንኖች አንድ ቃል ተቀባይ ጸሀፊ ይዞ ተቀበላቸው።

«አዛዥ» አለ ሻምበል ዳኘ አዛዥ ተካልኝ ገብተው እንደ ተቀመጡ። «አዛዥ፣ እስዎ በጣም የማከብርዎ አባቴ ነዎ። ስለዚህ ነው ወደ ሌሎች መርማሪዎች ሰድጀዎ፣ እርስዎንም እኔንም የሚያሳዝን ነገር ዳንዳይደረግ እኔ በቀጥታ እንድጠይቅዎ የወሰንሁ። ለምጠይቅዎ ሁሉ የማይለወጥ እውነተኛ መልስ እንዲሰጡኝ እለምንዎታለሁ። ያለዚያ ተግባሬ አስገድዶኝ ለዚህ ወደ ተሰናዱ መርማሪዎች እስድዎና ሁላችነንም የሚያሳዝን ነገር ይደረጋል።»

«አዛዥ ተካልኝ ወደ ሶስተኛ ፖሊስ ጣቢያ ሲጠሩ፥ የሚጠዬቁትን ነገር በትክክል አይወቁ እንጂ፣ በጠቅላላው ከደመቀች እስራት ጋር የተያያዘ መሆኑን የስራ ቤቱን ስም ዝርዝር ሲሰጡ ገምተው ስለ ነበረ፥ ሳይሸበሩ በሙሉ ርጋታ የሚጠዬቁትን እዬሰሙ መልስ ይሰጡ ጀመር።

«ይህን ያክል ስለ ተቸገርህልኝ እግዚአብሔር ልጄ፤ እንኩዋንስ ዛሬ ሁለት ጠጉር ባበቀልሁበት ጊዜ ድሮም ቢሆን ‹ተካልኝ ይዋሻል› እንዳልተባልሁ አንተም ታውቃለህ። ስለዚህ የማውቀውን እናገራለሁ የማላውቀውን ‹አላውቅም› እላለሁ አሉ።

«ደመቀች ጸሀይ የምትባለዋ የሜቴ፥ ወይዘሮ ጽጌ አሽከር እዚህ ለጥያቄ እስክትመጣ ድረስ አምስት አመት እግቢያቸው ውስጥ ቤት ሰጥተዋት ስትኖር፥ ድንገት ለሳቸውም ሳትነግር የሰጥዋትን ቤት ትታ ከስዎ ጋር ትቀመጥ ጀመር። ይህ የሆነበት ምክንያት ያውቁታል? »

«እመቤቴ ተቆጥተው ‹ልጅሽን ከቤቴ አስወጭልኝ› ስላልዋት ግራ ገብትዋት ስታለቅስ አግኝቻት ‹እኔ ቤት ተቀምጠሽ ከዚያ እዬተመላለስሽ ስሪ› ብዬ እኔ ነኝ የወሰድሁዋት።»

«እዚህ ለጥያቄ ከመጥራትዋ በፊት አንድ ሳምንት ያክል ሌት እስዎ ቤት እያደረች ቀን ‹እዚህ እሄዳለሁ› ብላ ሳትሰናበት ስራዋን በጭራስ ትታ በዬልብስ ሰፊውም በየወርቅ ሰሪውም ሱቅ ስትዞር መሰናበትዋን ተረድተናል፤ መቸም ወደ ወርቅ ሰሪ ሱቅ የሚሄዱ ወርቅ ኖሮዋቸው የሚሸጡ፣ ወይም ብር ኖሮዋቸው ወርቅ የሚገዙ ሀብታሞች ናቸው፤ እስዋ ለምን እንደ ሄደች ያውቃሉ? »

«አንድ ሳምንት ስራ አልፈታችም፤ ስራ የፈታች ከሮብ ማታ ቅዳሜ እዚህ እስከትመጣ ድረስ ነው። ልጅዋ ተማሪ ቤት እንዲገባ ተፈቀደለት ሀሙስና አርብ የሚያስፈልገውን ልብስ ስትገዛ ቅዳሜ፥ ጥዋት ተማሪ ቤት ስታስገባ ሰነበተች። ወርቅ ሰሪ ሱቅ አልሄደችም።»

«አለመሄድዋን እንዴት ያውቃሉ? »

«ላይን ቅጥበት አልተለዩሁዋትም።»

«አምስት አመት የሜቴ የቅርብ አሽከር ሆና ትሰራ ልብሳቸውንም ሆነ ጌጣቸውን ሲፈልጉ የምታቀርብ ሳይፈልጉ የምታስቀምጥ እስዋ ብቻ አልነበረችም? »

«እስዋ ብቻ ናት።»

«ልብስ ወይም ጌጥ ቢጠፋ፥ መቸም ከስዋ በቀር ሌላ የሚጠዪቅ የለም! »

«ልክ ነው፤ ብቻ እሜቴ ካላዘዙበት እስዋ ቅቤ፥ ባፍዋ ቢያስቀምጡ የማይቀልጥባት በጣም ጠንቃቃ ናት! »

«እሜቴ የሚያዙበትን ላልሁም፤ እስዋ አስቀምጭ የተባለችው ቢጠፋ ነው ያልሁ! »

«እሱም እውነት ነው፥ አስቀምጭ የተባለችው እቃ ቢጠፋ ሌላ የስራ ተካፋይ ስለሌላት ተጠያቂዋ እስዋ ብቻ ናት። እንገር ግን ያው ጌታየ እንደምታውቀው የቤቱ አዛዥ ስለ ሆንሁ ሁሉንም አውቃለሁ። ይቺ ልጅ እንኩዋንስ ብርቱ እቃ እለት ተበልቶ ተጠጥቶ የሚያልቅ እህል ውሃ ‹ይጠፋባታል› ብሎ ሰይጣን የማይመሰርክርባት፣ ጠንቃቃ ናት! »

«እባክዎ ለጠዪቅሁዎ ብቻ ይመልሱ።»

«እሺ - እሺ ለጠዪቅኸኝ ብቻ የመለስሁ መስሎኝ ነው።»

«አሁን ተጠንቅቃ እንድትጠብቅ የተቀበለችው በጣም ከፍተኛ ዋጋ ያለው የሜቴ እቃ ስለ ጠፋ ከግቢያቸው ወጥታ በቀጥታ የገባች እርስዎ ቤት ከሆነና ከዚያ ጀምሮ ‹ላይን ቅጥበት አልተለዩሁዋትም› ካሉ ያን እቃ የት ወስዳ እንደ ሸሸገችው ወይም ለማን እንደ ሸጠችው ያውቃሉ? »

«ምን? ደመቀች የሜቴን እቃ አውጥታ መሸሽግ? እንዲያውም መሸጥ? ተው እንዲህ አትበል እጠላሀለሁ! » ሲሉ አዛዥ ፊታቸው በቁጣ ተለዋውጦ እዚያ ያሉት መኮንኖችም ቃል ተቀባዩም ይስቁ ጀመር። ሻምበል ዳኘም ሳቅ መጥቶባቸው፥ ላለማሳዬት ራሱን በጠረጴዛው ላይ ደፍት ትንሽ ቆይቶ ኮስትራ ፊቱን እንደገና ቀና አደረገና «ለጠየቅሁዎ ይመልሱ አዛዥ» አለ።

«ለመሆኑ የሜቴ ከፍተኛ ዋጋ ያለው ምን እቃ ነው። የጠፋቸው? » አሉ አዛዥ ግልፍታቸው አልፎ እንደገና ዘና ብለው።

«ጌጣቸው፤ ካምሳ ሽህ ብር በላይ የሚገመት ጌጣቸው በሳጥን እንዳለ ጠፋ! »

«የሜቴ ጌጥ ጠፋ? » መቸ? »

«እስዋ ስራዋን ትታ ስትጠፋ ጠርጥረው ሁልጊዜ የሚቀመጥበትን ቦታ ቢያዩ አጡት። ከዚያ በሁዋላ ቤቱ በሙሉ ተበርብሮ ጠፋ።

አዛዥ አንገታቸውን ደፍተው ግንባራቸውን እዬቁዋጠሩም እዬፈቱም ሲያስቡ ቆይተው ቀና አሉና «እሜቴ ዘወትር እዬተለዋወጡ የሚያደርግዋቸው ልዩ ልዩ ጌጦች የሚቀመጡበት ደብዘዝ ባለ ዳማ ከፋይ የተሸፈነ ሳጥን አለ። ሌላው ቁልፉን ከሳቸው በቀር ማንም የማይነካው ባረንጉዋዴ ከፋይ የተሸፈነ መሀከለኛ መጠን ያለው የጌጥና - የሌላም አንዳንድ ነገር ሳጥን ነው፤ የትኛው ነው ጠፋ የተባለ? »

«ባረንጓዴ ከፋይ የተሸፈነው ሳጥን በውስጡ ካለው ሀብት ጋር! »

«እሱስ ካምሳ አደለም፥ ከመቶ ሽም ይበልጣል። ብቻ - ታዲያ ያን ሳጥን ያስቀመጠችው ደመቀች ኖራለች? »

«የሜቴን ጌጥ የሚያስቀምጥ ሌላ ምን አለ? እስዎምኮ ለዚህ ስራ አላፊ እስዋ ብቻ ነች አሉን! »

«አዎን ብያለሁ፤ ብቻ ይህን ማለቴ አልነበረም፥ ሌላውን ነው።»

«እንዴት ሌላውን? »

«የዘወትሩን ጌጥ ማለቴ ነበር። ለመሆኑ በዚህ ነው ደመቀች ከሁለት ሳምንት በላይ የታሰረች? »

«ለጥያቄ መጣች እንጂ አልታሰረችም፤ ተራዋ ሲደርስ ተጠይቃ ትለቀቃለች።»

«እኔ ዛሬ መጥቼ ተራየ ሲደርስ ከሁለት ሳምንት በላይ እዚህ ተቀምጣ ‹ተራዋ› ባይደርስ ነው፤ የምትለው..... ማመን ያስቸግረኛል፤ ብቻ......» ብለው አዛዥ ሊቀጥሉ ሲሉ.... «ቢያምኑ ባያምኑ የራስዎ ጉዳይ ነው፤ አሁን ለተጠየቁት ብቻ መልስ ይስጡ፤ ትርፍ ነገር ጣልቃ ማግባቱ ይበቃል! » አለ ሻምበል ዳኘ፥ በቁጣ ፊቱን አኮማትሮ። እንዲያ ፊቱን አኮማትሮ እዬተቆጣ ሲናገር አዛዥ ትኩር አርገው ሲመለከቱ ቆዩና፥

«ስማኝ እስቲ ስማኝ! » አሉ እንደ ሻምበል ዳኘ በመላ ሳይሆን በውነተኛ ቁታ ሰውነታቸው ሁሉ ግሎ። «ምን የሚታመን ነገር አዬሁ ሰማሁ ብዬ ልመን? አላምህም! በተናገርኸው ሁሉ አንድ እውነት የለበትም! ከሁሉ አስቀድሞ ይህን እቃ ደመቀች ጭራሽ አታውቀውም! ገና እሱዋ ከመግባትዋ በፊት እሜቴ ራሳቸው ‹እንዳይጠፋብኝ የጌቶች ሽልማት በሚቀመጥበት የብረት ሳጥን አስቀምጥልኝ› ብለው ቆልፈው ሰጥተውኝ እኔ ነኝ ያስቀመጥሁት። ተዚያ ‹ቤቱ ተበርብሮ እቃው ተፈልጎ ጣፋ› አልኸኝ! ምነው እኔ የማስተዳድረው ቤት እዬተበረበረ የጠፋው እቃ ሲፈለግ እኔ የት ኖሬያለሁ? እሜቴ ጠይቀውኛል? አንተ ጠይቀኸኛል? ተዚያ ደመቀች ወርቅ ልትሸጥ በዬወርርቅ ሰሪው ሱቅ ስትዞር መሰንበትዋን ‹ተረድተናል› አልኸኝ! ይህ ሁሉ አንድ እውነት አለበት? ይህ ሁሉ፥ ይህሽን ልጅ ደም፥ ደም ተፍታ ባገኘለገለች፥ ለማስቸገር ተፈትሎ የተሰራ እንጂ አንተም ራስህ ‹እውነት ነው› ብለህ እንደማታምን አውቃለሁ! ታዲያ አንተ የምታምነውን እኔን ‹ካላመንህ› ብለህ ትቆጣለህ! የለም! እውነቱን እኔ አውቄዋለሁ ልንገርህ! እሜቴ ባልታወቀ ምክንያት ይችን ድሀ ለመበደል አንተ ስልጣንህን መከታ አድርገህ እስቸውን ደስ ለማሰኘት የጀመራችሁት ነው! መቸም እግዜር ለብርቱ ነውና፥ ያዘልቅላችሁ ይሆናል! በል እንግዲ ወደዚያ ወደምትፈክርበት ወደዚያ፥ ማስፈራሪያህ ስደደኝ፥ እኔ ተካልኝ አልፈራም! » አሉና ላባቸውን ከግንባራቸው እዬጠረጉ ወደ ቃል ተቀባዩ ዘወር ቢሉ፥ አዛዥ ወደ መጨረሻ የተናገሩትን እንዳይጽፍ ምልክት ተሰጥቶት ኖሮ፥ እጁን በጠረጴዛው ላይ አመሳቅሎ አኑሮ! አንገቱን ደፍቶ ተቀምጦ አዩት። «ለምን የተናገርሁት አይጣፍ? በንጉስ ይጣልፍኝ! » አሉ።

«ተጽፎዋል፤ ግዴለም ይጻፋል፤ አሁን ይሂዱ በቃ! » አለ ሻምበል ዳኘ አንገቱን ከደፋትበት ሳያቃና። አዛዥ ከተቀመጠበት ተንስተው ለመሄድ ቢሞክሩ ብርቱ ትኩሳት ታሞ እንደ ሰነበተ ገገምተኛ ጉልበታቸው እዬተብረከረከ አቃታቸው። ከዚያ ቃል ይቀበል የነበረው ጸሀፊ ረድቶዋቸው ተነስተው እዬተንቀጠቀጡ ወጡ።

አዛዥ፣ ከሶስተኛ ፖሊስ ጣቢያ እንደ ተመለሱ፣ ለስረኛዋ ራት እንዲሰናዳ፥ ለባለቤታቸው ለወይዘሮ ጌጤ ነግረው ወጡና ሻምበል ዳኘ ወደዚያ ወሬው እንደ ገሀነም ወደሚያስፈራው የምርመራ ክፍል ‹ይሰደኛል› ብለው ርግጠኛ ሆነው ሳለ የጫኑበትን ያን ያክል ከባድ ነውር ሁሉ ዝም ብሎ ተሸክሞ የለቀቃቸው በምን ምክንያት እንደሆነ አልገባቸው ብሎ በትንሽ ግቢያቸው ውስጥ ወዲያ - ወዲህ እዬተመላለሱ ራሳቸውን ይበዘብዙ ጀመር። ‹ምንም ቢሆን በስራ ጉዋደኖቹ ፊት ጉዱን አውጥቸበት እንዲያ አጋልጨው አይለቀኝም፤ ምን አይነት ቅጣት እንደሚቀጣኝ ተማክሮም ይሁን ብቻውን እስኪወስን ነው የለቀቀኝ!› ይላሉ አንድ ጊዜ ባሳባቸው። ‹ይህን ለማድረግ መልቀቅ ያስፈልግ ኖሮዋል? ይህን ለማድረግ ቢያስብ ኖሮ፥ «ያዝና እዚያ አቆዬው! » ብሎ ወዲያው በፈላ ደሙ የፈለገውን ቅጣት ወስኖ አይፈጽምብኝም ኖሮዋል? እንጃ፤ አልገባኝም!› ይላሉ ሌላ ጊዜ። እንደሆነ የሚፈጽምባቸው ስቃይ ከሚያውቁ ሰዎች እንደ ሰሙት በዬደረጃው ተሰልፎ ይታያቸውና ‹ግዴለም የመጣው ይምጣ፤ እኔ ተካልኝ ልኩን ነግሬዋለሁ!› ይላሉ።

እንዲህ እጆቻቸውን ወደ ሁላዋ በጀርባዋ አስተሳስረው ወዲያ ወዲህ እየተመላለሱ መታረቅ የማይችሉትን ልዩ ልዩ አሳቦች በራሳቸው ውስጥ ሲያሙዋግቱ አንዲት እድፋም ልብስዋ የተቀዳደደ ደምዋ እስከ መጨረሻው ጠብታ ከውስጥዋ ተመጦ የወጣ ፊትዋ ጠል እንዳጣ ስር የገረጣ፣ ጠጉርዋ እንደ ደረቅ ጭራሮ የተንጨበረረ እንዲያው በጠቅላላው፥ አንዳንድ ጊዜ በቅዠት የሚታይ ዛር እንጂ፥ ሰው የማትመስል ፍጥረት እያነከሰች መጥታ ወዳጥሩ በራፍ ስትቀርብ አዩና፥ ቆመው ይመለከቱ ጀመር። ሴትዮዋ ያጥሩን በር መዝጊያ ከፍታ ስትገባ ሁኔታዋ ሁሉ ከቅድሙ የበለጠ ጎልቶ ስለ ታያቸው በጣም ቶሎ ሳንቲም ሰጥተው ለማሰናበት ኪሳቸውን ቢዳብሱ ሳንቲም ተሰቀው አጡ። ከዚያ ወደ ቤት ዘወር ብለው፥ «ጌጤ ጌጤ እባክሽ ቶሎ አንድ እንጀራ አምጪ! » በለው እንደገና መለስ ቢሉ ለማኝዋ አይኖችዋ እንባ ሞልተው አንካሳ እግርዋ እንደ ልብ አላስሄዳት ብሎ ደፋ ቀና እያለች፥ መጣችና በቆሙበት ልትደርስ አስር ሜትር ያክል ሲቀራት «አባባ! » አለች። ደመቁ ልጄ! አንቺ ነሽ? » በለው አዛዥ እጆቻቸውን እንደ ክንፍ ግራ ቀኝ ዘርግተው እዬሮጡ ሄደ

ታቀፍዋት። ከዚያ ተያይዘው ይላቀሱ ጀመር። «እግዞ! እግዞ! ሰው ባስራምት ቀን እንዲህ ይሆናል? ምን ቢያረጉሽ እንዲህ ሆንሽ? »

«ግዴለም ደህና ነኝ አባባ፤ ልጄ ደህና ነው? ልጄን አዩልኝ? »

«እሱስ ደህና ነው፥ አንቺ ነሽ እንጂ።»

«መቸ አዩት? »

«አንቺን በወሰዱሽ ማግስት እሁድም፥ ከዚያ ወዲህ በነበረው እሁድም እኔና ጌጤ ሄደን ነበር፤ በጣም ደህና ነው» አሉና እንደ ገመድ ሲቁዋጠር ሲፈታ የሰነበተ አጥንት እንዳልተፈጠረበት የሚልወሰወስ ደካማ ክንድዋን ተጠንቅቀው ይዘው «ጌጤ ነይ ጉድ እይ! ጌጤ ነይ ጉድ እይ! » እያሉ ይዘዋት ገቡ።

## ምእራፍ አስራ ዘጠኝ

# የህገወጦች ህግ

ደመቀች፥ ሶስተኛ ፖሊስ ጣቢያ መታሰርዋን አዝማሪዉ ቤት ሰምቶ ለጉዋደኛው ለበሻህ፥ ዘለሌም ነግሮት ስለ ነበረ ሁለቱ በዩጊዜው እዩመጡ አዛዥን ይጠይቁ ነበር።

በተፈታች ሳልስት አዝማሪው ውቤ አንድ ማንቆርቆሪያ ጠላ የደስ ደስ መጥቶ ከባለቤታቸውና ከደመቀች ጋር እዩወጡ፥ ሲጫወቱ በሻህ ዘለሌ መጣ።

«ያው ደግሞ አንዱ ዘመዳችን ደመቁ፤ ከታሰርሽ ጀርሞ አንድ ቀን መጥቶ ሳይጠይቀኝ ቢቀር፥ በሁለተኛው አይቀርም! በሻህን ታስታውሽዋለሽ? » አሉ አዛዥ በሻህ ገብቶ ለሁሉም የጅ ሰላምታ ሲሰጥ፡

«ውለታው የሚያስረሳው ነው? አባባ! እንኩዋንስ - በሶስት ሳምንት እድሜዬን ሙሉ አልረሳውም! » አለች ደመቀች ለመነሳት ብትሞክር ሰላቃታት በተቀመጠችበት ጉዋያ እንደ ሰበራት እዩተልወሰወሰች።

«እግዜር ይስጥልኝ፥ እንዲህ አገልግሎት ልማስረሳ ወይዘሮ እንኩዋንስ አንድ ቀን የድሜዬን ሙሉ ሳገልገል ብኖር እንደ ተገለገልሁ እንጂ እንዳገልገልሁ አልቆጥረውም።

ኧረ ለመሆኑ! ያ ሁሉ ደም የት ሄደ? እኒያ ፖሊሶች ቀድተው ጠጡት? » አለ በሻህ፥ እጅዋን እንደ ያዘ፥ ጠል እንዳጣ ተክል የጠወለገ ፊትዋን ዘቅዝቆ እያዩ።

አዝማሪው ውቤ በሻህ ዘለሌ፥ ስራቸው እዩቅል ይሁን እንጂ ብዙ ጊዜ አብረው የሚታዩ በምክር ሆነ በስራ የሚረዳዱ እጅግ የሚዋደዱ ጉዋደኞች ናቸው። ብቻ የስበሳቸውን ፍቅርና አክብሮት በዩልባቸው ይዘው፥ ባፋቸው ሲሰዳደቡና አንዱ ሌላውን ነውር ጎልጉሎ ሲያወጣ ለሁልጊዜው ተቆራርጠው የሚቀሩ እንጂ አድረው የሚገናኙ አይመስሉም።

«ኧረግ ኧረግ፣ ኧረግ! እንዲያውስ ጨዋታ በማን አፍ ያምራላ! በሻህን ደህና አድርገህ አታውቀውም መሰለኝ፥ ውቤ! » አሉ አዛዥ የሁለቱን በጣም ቅርብ ወዳጅነት ስላላወቁ።

«እንደ በሻህ ደህና አድርጌ የማውቀው ሰው የለም፥ አባባ አዛዥ። ብቻ፥ እኔ የማውቀው በሻህ ዘለሌ ሰባዊ ስሜት የሌለው የማጅራት መችዎችና የሌቦች ሰራዊት ጠቅላይ አዛዥ ነው እንጂ የጨዋታ ሰው አደለም።»

«አ - ይ! ይህ እንኩዋ አይመስለኝም! » አሉ አዛዥ፥ ራሳቸውን እዩወዘወዙ። በሻህ አዝማሪው ውቤን በማጎጠጥ አይን እንድ ጊዜ የጎድን ገረፍ አድርጎ፥ «እንግዲህ ጀመረ ይህን..... ጅራፍ ምላሱን ያጮህ! » አለና ወንበር ሳብ አድርጎ ተቀመጠ።

«እስቲ እንዲያው ለምሳሌ ያክል፣ አለቃ መዝሙርን ‹ምን አደረግሀቸው› ብለው እሱን ራሱን ይጠይቁት። እኔ እንዳልናገር ‹ዋሽህ ወይም ምስጢር አወጣህ› ይለኛል» አለ አዝማሪው ውቤ።

«ለመሆኑ አለቃ መዝሙር ማናቸው? » አሉ አዛዥ ሲስቁ ቆይተ።

«አለቃ መዝሙር የሱ አለቃ ናቸው። ግፍ ሰሩብኝ ብሎ እንደ ሴት ሲያለቅስ ስላስካስሁት ይዩትልዎ በማስመገን ፈንታ ስሜን፣ ያከፋል» አለ በሻህ አሁንም አዝማሪው ውቤን የጎድን እያዩ።

«እንዴት አድርገህ አስካስኸው? በሽምግልና ነው? »

«የዚያኑ ያክል ነው፤ አዎ በሽምግልና ሊባል ይቻላል» አለ በሻህ ፍርጥም ብሎ።

«ግሩም ሽምግልና! » አለ አዝማሪው ውቤ ከልቡ እዩሳቀ።

«እንዲህ ነው፤ አዝማሪው ውቤ ወደ አዝማሪነት ደረጃ ከማደጉ በፊት ገና እዚያ መድህኔ አለም ዲያቆን ነው? ወይስ - ደብተራ ሳለ እኒህ አለቃ የማደርያው መሬቱን ሲወስዱበት ጊዜ መቸም ይህ ክፍት አፉ ለዘፈንና ለልቅሶ ብቻ ሳይሆን እንደሚያዩት ለስድብም የሰላ ነው፤ ሰድቦዋቸው ኖሮ በክብረ ነክ አመት አሳስረው አልፍተውታል። በዚህ ‹ፍርድ ጎደለብኝ› እያለ ሲያለቅ አይቼ ግፍ የተሰራበት መሆኑን ለ - ልጆች ስለ ነገርሁዋቸው አለቃ እብብዙ ርስታቸው ከሰፋሪው ጢሰኛ በርከት ያለ ገንዘብ ሰብሰበው ሲመለሱ፣ ልጆች እመንገድ ጠብቀ ካለቃ ገንዘቡን ተቀብለው - ‹ያውልህ ካሳህ ብለው ሰጡት። ታዲያ ይዩትልዎ በዚህ እዬዞረ ስሜን ያከፋል።»

«ምን ያክሉን ወስዳችሁ ምን ያክል ሰጣችሁኝ? » አለ አዝማሪው ውቤ።

«እኔ በደልህን ከመንገርና ካሳ የሚገባህ መሆንህን ከማመልከት በቀር እንኩዋንስ ገንዘብ ልወስድ ልጆች ገንዘብ ልውሰድ ልጆች ገንዘብ ሲወስዱ ኖሪያለሁ? ነገር ግን ካሳ ማግኘት በሁዋላ ነግረውኛል።»

« ‹ልጆች የምትላቸው የማን ልጆች ናቸው? » አሉ አዛዥ በሻህን እያዩ።

«ሌቦችንና ቀማኞችን የሱን ጭፍሮች ነዋ! » አለ አዝማሪው አቁዋርጦ።

«ኧረ ያሰፋ ያለህ! የሌቦችንና የቀማኞችን ዘረፋ ነው እንዲህ እንደ ተቀደሰ ስራ በመልካም ስም አጎናጥፈው የምትነግረን? » አሉ አዛዥ እንደ መሳቅም እንደ መገረምም ብለው።

«ይዩትልዎ በሻህና በወሮበሎች ጉዋደኞቹ ቁዋንቁዋ ማጅራት መቺዎች ቀማኞችና ሌቦች «ልጆች» ይባላሉ፤ መቀማትና መስረቅ «መቀበል» ይባላሉ! » አለ አማሪው ውቤ። አዛዥ ባለቤታቸውና ደመቀች ይስቁ ጀመር። በሻህም አብሮ ሲስቅ ቆይቶ።

«እንዲህኮ ነው፤ ምክንያቱን ልንገርዎ አባቴ። መቀማት ይሁን መስረቅ ከሌሎች ልዩ ልዩ የሰው ገንዘብ መውሰጃ ዘዴዎች ምንም ያክል ልዩነት ያላቸው። ‹ማጅራት መቺዎች ቀማኞችና ሌቦች› የሚባሉትም ያው እንደ ሌሎች በልዩ ልዩ ስም በሰው ገንዘብ የሚኖሩ ሰዎች ናቸው። ልዩነታቸው የስም ልዩነት ብቻ ነው። ባልታወቀ ምክንያት ቅምያና ስርቆት ከሌሎች፥ የሰው ገንዘብ መውሰጃ ዘዴዎች ሌባና ቀማኛ ማጅራት መቺ፥ ከሌሎች በሰው ገንዘብ የሚኖሩ ሰዎች የበለጠ ለሰሚ ጆሮ ይቀፋሉ፤

ስማቸው ለጆሮ አይጥምም። ስለዚህ ‹ግብራቸው ሳይሆን ስማቸው ብቻ ከሆነ አስጠልቶ ወንጀል ያደረጋቸው ይለወጥ› የተባለበት ምክንያት ይህ ነው» አለ ያሽሙር ፈገግታ ፈገግ ብሎ።

«አይደለም ልጄ! የክፉ ስራም የክፉ ሰሪም፥ ስማቸው ብቻ አይመስልህ የሚጠላው። ስራውም ሰሪውም ጭምር ነው! »

«አ..... ! በጠቅላላው ክፉ ስራና ክፉ ሰሪ የሚጠላና የሚጠፋ ከሆነ ከኔ የበለጠ ከርስዎ ጋር የሚስማማ አያገኙም። ነገር ግን በመልካም ስም የተሸፈነ ክፉ ስራ በመልካም ስም ከተሸፈነ ክፉ ሰሪዉ ጋር እስካለ ድረስ፥ ስሙ ለጆሮ የማይጥመውን ብቻ ማጥፋት፥ ምንም ቢሆን የማይቻል ነው። ስለዚህ ወይ የስምን ነገር ወደ ጎን ትቶ በጠቅላላው ክፉ ስራንና ክፉ ሰሪን ጨርሶ ማጥፋት ያለዚያ ለባለ ክፉ ስም መልካም ስም ሰጥቶ ሁሉንም አሁን እንዳለው መተው ነው። እንዲያውም ለሰሚው ጭራሽ ግራ የሚመስል ነገር ግን እውነተኛ ነገር ልንገርዎ፥ አባቴ። በልዩ ልዩ መልካም ስም የተሸፈነ ክፉ ስራ ከሰሪው በክፉ ሰሪው ላይ የበለጠ ክፉ ሰሪ መኖሩ በመጨረሻ በጠቅላላው ክፉ ስራንም ክፉ ሰሪውንም ያጠፋዋል።»

«ይህን ከጥልቅ ሀይቅ የጠለቀ ፍልስፍና ይሰማሉ? አባባ አዛዥ! የማጅራቱ መቺዎች የቀማኞችና የሌቦች ሊቃውንት ተመራምረው ይዩትልዎ እንዲህ ያለ የጠለቀና የረቀቀ ፍልስፍና ላገር ያበረክታሉ! እጡብ ድንቅ ይበል ይበል! » አለና አዝማሪው ውቤ እዬሳቀ ያጨበጭብ ጀመር።

«አዎ ‹ይበል ይበል› አልቃሾ! አለቃህ በሰበሩብህ የግፍ ስራ ላይ የልጆች ቅምያ በሳቸው ላይ ልጆች ባይኖሩ አመት ሙሉ ወህኒ ቤት ለፍተህ እንዲሁ ሳትካስ እንዳለቀስህ አትቀርም ኖረህል! » አለ በሻህ ከመናደዱ የተነሳ አዝማሪው ውቤን እንደሚያንቅ ከተቀመጠበት ለመነሳት ቃጥቶ። እዚያ ያሉት ሁሉ ሁኔታውን አይተው ሲስቁ ጊዜ በሻህም እንደገና አብሮዋቸው ይስቅ ጀመር።

ደመቀች የልጅዋን እቃ ስትገዛ በሻህ ያደረገላት ርዳታና በሁዋላም በመገናኛ ሆቴል ምሳ ሲበሉ በሱ ላይ የተመለከተችው ፍጹም ጨዋነትና ባህሪ ያንለት፥ አዝማሪው ውቤ፥ ካወራበት ጋር አልሰማማላት አለና አሳብዋን ከነከነው። ይልቁንም በሻህ ራሱ፥ አዝማሪው ውቤ የወንጀለኞች አለቃ አስመስሎ ሲያወራበት አለ ለማለትና ንጹህ መሆኑን ለማሳዬት በመሞከር ፈንታ ወንጀለኞችንና ስራቸውን ለመደገፍ ሲከራከር በማዬትዋ የባሰውን ግራ ገባት። ስለዚህ ለማጣራት ፍለጋ፥ «መቸም»

አለች። «መቸም አሁን የምትሉት ሁሉ እንዲያው ለጨዋታ ያክል ነው እንጂ እውነት ሆኖ አደለም! »

«ምኑ? » አለ አዝማሪው ውቤ።

«ለምሳሌ አሁን አንተ፥ ስለ ጋሼ በሻህ ስትለው የቆዬኸው ሁሉ እውነት አይመስለኝም።»

«እንዴት? አነሰ ወይስ በዛ? »

«እንጃ! ጋሼ በሻህ..... ክፉ ስራ የሚሰራ አይመስለኝም! »

«በይ ዝም በይ፤ በሻህን አታውቂውም! ሰው መሰለሽ? ሰይጣንኮ ነው! ወንጀሉም ሆነ ሌላ ተንኮሉ እንደ ሌሎች ጉዋደኞች ከተወለደ በሁዋላ የተማረው አደለምኮ አብሮት ተፈጥሮ አብሮት የተወለደ ነው! አዬሽ? ገና በናቱ ሆድ ሳለ እዚያ አምባጉዋሮ አንስቶ እናቱን ‹ካልገደልሁ› ብሎ በጣም አስቸግሮ በስንት ጭንቅ በሀኪም ርዳታ በሰባት ወሩ አውጥታ ጣለችው። ከዚያ ያችው ያመጸኞች ሞግዚት አራዳ ተቀብላ አሳድጋው ያውልሽ አሁን..... የወንጀል ስራውን እንደ ሌሎች ወንጀለኞች በስውር መስራ አልበቃሽ ብሎ የወንጀለኞችና የወንጀል ስራቸው ጠበቃ መሆኑም አላጠግበው ብሎ የወንጀል ሀዋርያ ሆኖ፥ ፍልስፍናውን በገሀድ እዬዞረ ይሰብካል። ታዲያስ! እንዲህ ያለውን ሰው ነው ‹ክፉ ስራ የሚሰራ አይመስለኝም› የምትይው? »

«ታዲያ ይህም ሁሉ እውነት ነው? » አለች ደመቀች ትንሽ እንደ መሳቅ ብላ፥ አንድ ጊዜ አዝማሪው ውቤን፥ አንድ ጊዜ በሻህን እያለዋወጠች እያዬች።

«ያዝማሪው ግጥማ - ግጥም ተቀንሶለት በሰባት ወር መወለዴ እውነት ነው! » አለች በሻህ ትንሽ እንደ መሳቅ ብሎ። ሌሎቹ አዝማሪው ውቤ ጭምር በጣም ሳቁ።

«የወንጀለኞች አለቃ መሆንህሳ! » አለ አዝማሪው ውቤ፥ አይኑን ወደ በሻህ ፍጥጥ አድርጎ።»

«ልጆች አንድ ጊዜ መሪያቸው አድርገው መርጠውኝ ነበር፥ ብቻ እሱም ዱሮ ያለፈ ታሪክ ነው። ‹ወንጀለኞች፥ ወንጀለኞች› እምትሉዋቸው እንዲያ የልማድ አነጋገር ነው እንጂ ሌላውን ትልልቁን ወንጀለኞች እንተውና ካንተ እኩዋን ካልቃሻሙ የክፉ አደሉም! አንተ ዱሮ፣ ጠንቁዋይ ደብተራ ሳለህ ራስህን በድህነት እዬቆራመድህ ሌሎችን

በውሸት ‹ሀብታም አደርጋችሁዋለሁ› እያልህ እያታለልህ በቀላሉ የማይታለሉትን ‹መአት አመጣችሁዋለሁ› እያልህ እያስፈራራህ የሰው ገንዘብ ትዘርፍ አልነበርም? ከዚያ አልቃህ ካባረሩህ በሁዋላ ሌላ ማታለያ ፈጥረህ አሁን ፈሪውን ደፋር ከፉውን ደግ መጥፎውን ሸጋ አስመስለው በውሸት ግጥም የምታወድሳቸውን ሰዎች ልብ እዬነበዝ ራሳቸውን እያፈዘዝህ የማይሸንገሉትን ‹ዞሬ እሰድባችሁዋለሁ› እያልህ እያስፈራራህ የሌሎች ገንዘብ ትበላ የለም? መኖሪያህ ይህ አደለም? ብቻ ባንተ ቁዋንቁዋ ይህ ወንጀል አይደለም! ይልቅ ይህን ተውና ሌላ ወሬ አምጣ፤ ላንስማማ በከንቱ ጉንጫችነን እናልፋ! » አለ በሻህ ስሜቱ ከቀልድ ወደ ምር ሲለወጥ በፊቱ እየታዬ። የበሻህን ስሜት ከፊቱ አይተው ሁሉም ዝም አሉ።

«ምን አደረግሽ ብለው ነው ፖሊሶች ይህን ያክል ጊዜ ያሰሩሽ? » አለ ቀጠለና ወደ ደመቀች መለስ ብሎ።

«እመቤታችን በጣም ብዙ ዋጋ ያለው እቃ ‹ጠፋብኝ› ብለው እስዋን ስለ ጠረጠረዋት አሳስረዋት ነበር» አሉ አዛዥ ደመቀች አንገትዋን ደፍታ ዝም ማለትዋን አይተው።

«እንዲሁ በጥርጣሬ! »

«ያውም እቃው ሳይጠፋ።»

«እንዴት? »

«ገና ድሮ፥ ደመቀች እንኩዋ ሳትመጣ እንጂ! ቢያንስ ቢያንስ ሰባት አመት ሳይሆን አይቀርም - ይህ እቃ ራስጌያቸው ቁልፍ በሌለው ቁምሳጥን ከሚቀመጥበት ከሳቸው ጋር ተመካከረን የጌቶች ልሻን በሚቀመጥበት የብረት ሳጥን እንድቆልፍበት ሰጥተውኝ እዚያ ይኖራል። ረስተውታል መሰለኝ እንጂ፥ አንስተውብኝ እንኩዋ አያውቁም! አሁን ምን ሰይጣን እንደ መከራቸው አይታወቅም። ጠፋብኝ ብለው የህታቸውን ልጅ አስጠርተው ታራ እዬተሰቀዬ እንድትመረመር ‹አደራ› ብለውት ያው - እንደምታይዋት አርጎ ለቀቃት» አሉ አዛዥ በትካዜ ፊት ደመቀችን እዬተመለከቱ። ያዛዥ አዘንና ትካዜ የተቀበለችውን ስቃይ አስታወሳትና ደመቀች አንገትዋን ደፍታ እንደ ተቀመጠች እንባዋ ጉንጭዋን ሳይንካ እንደ መስከረም ዝናም ደቦል ደቦል እዬሆነ እመሬት ይወድቅ ጀመር።

«በመጨረሻ እንዴት ተለቀቀች? » አለ በሻህ ደመቀችን ስታለቅስ ሲያይ ስሜቱ ታውኮ በሻከረ ድምጽ።

«በመጨረሻማ - እኔም እንዲህ እንደሰዋ ታስሬ፥ እንድመረመረ ተመክሮ ኖሮ እግዚአብሄር ይስጠው፥ ወደዚያ ወደ መመርመሪያቸው ከመስደዱ በፊት፥ ጉዋደኞቹንና አንድ ጣፊ ይዞ እዬጠዬቀኝ ስነግረው ጊዜ እሱም ጉዋደኞቹም በመሀላቸው መብረቅ እንደ ወደቀ ደንግጠው ደርቀው ዝም አሉ። እሱማ - መቸስ ምን ልበልህ! ቀና ብሎ ማየቱንም ፈርቶ፥ ራሱን በጠረጴዛው ላይ እንደ ደፋ ‹ሂድ በቃ› አለ። እስዋም ወዲያው ተለቀቀች።»

«ይኸ ‹እሱ› የሚሉት ማነው? »

«ያው የህታቸው ልጅ ነዋ! ሻምበል ዳኘ ይባላል! »

«ኧረግ! ይኸ ‹ጥቁር ፋሺስት› የሚሉት? እሱ የታቸው ልጅ ነው? »

«እንዲያው እናቱ ይውለዱት እንጂ ያሳደጉት እመይቴ ናቸው! »

«ለመሆኑ ክፋት የቤቱ ነው ማለት ነው! » አለ በሻህ በመገረም።

«እመቤታችሁስ ይህ ሁሉ ከሆነ በሁዋላ ምን አሉ? » አለ ወዲያው ቀጠለና።

«አምጥቼ እፊታቸው ላስቀምጥላቸው፥ ‹ለካ አንተ ዘንድ ኖሮዋል! ረስቸው!› አሉና ወዲያው ከፍተው አንዳንዱን እያወጡ ትንሽ ሲመለካከቱ ቆይተው እንደገና ቆልፈው ራስጌያቸው ዱሮ፥ በሚቀመጥበት ክፍት ቁም ሳጥን አስቀመጡት። በጣም ገረመኝ፣ በተደረገው ሁሉ በደል ትንሽ እንኩዋ የመጸጸት ምልክት በፊታቸው አለመታየቱ፥ ነው! » ከዚያ ሁሉም ዝም ብለው ሲተክዙ ቆዩና፥

«ለመሆኑ እውነት እቃው ብዙ ዋጋ ያለው ሆኖ ነው? ወይስ እንዲያው ይችን ድሀ ለማስቸገር የተጐዱ መስለው ለመታየት ያደረጉት ዘዴ ነው? » አለ በሻህ።

«እቃውስ በጣም ብዙ ዋጋ ያለው ነው! እንዲያውም እሳቸው ‹አምሳ ሽህ› ይበሉ እንጂ..... ከሙቶ ሽ እንኩዋ ሳይበልጥ አይቀርም! ጥምዙና ሌላው ልዩ ልዩ መልክ ያለው ወርቅ ብቻ አምሳ ሽህ ብር ሳያወጣ አይቀርም! »

«ይህን ያክል ገንዘብ ከየት አመጡት? »

«አየ ልጄ! ጌታ ከድሀ እንጂ ከየት ያመጣል? ረዥም ጊዜ ጎፋን ገዝተዋል። የጎፋ ህዝብ እንኩዋን ገንዘቡን ቆዳውን ቢገፉት የማያመው ደግ ህዝብ ነው! ከዚያም በላይ ባለ ብዙ ርስት ናቸው! »

«ግሩም ነው! ታዲያ እኒህ ያሉት በድሀ ገንዘብ መልሰው ድሀ የሚያሰቃዩት፥ ብዙ ህዝብ ይበላው ይታከምበት አጥቶ በራብና በበሽታ ሲያልቅ መቶ ሽህ ብር አገልግሎቱን እንዳበቃ ሰባራ እቃ የትም ጥለው ‹ረሳው› የሚሉት እንዲሁ ‹ሰው ማሰቃየት አማረኝ› ብለው እያሳሰሩ የሚያሰቃዩት በህግም ሆነ በሰው ፊት ወንጀለኛ አደሉም! በህግም በሰው ፊትማ ዋና ወንጀለኛ ሲርበው ከተረፈው ወስዶ የበላ ነው! ታዲያ እንዲህ ያለው ህግ ህግ ነው? ሰዉስ ሰው ነው? የሞት ፍርድ ይፈረድባቸዋል፤ ሞት ቢቀር ግን ለደካማ ማጥቂያ መሳሪያ ያደረጉት ሀብታቸው እንደ ሚወረስና የተጠቁት እንደሚካሱ የማይጠረጠር ነው» አለ በሻህ ወደ መጨረሻው ትንሽ እንደ መሳቅ ብሎ።

«አንተና ማጅራት መቺዎችህ፥ በዳኝነት ወንበር ተቀምታችሁ፥ ህጋችነን ባራዳ ህግ ለውጣችሁ እስከትፈርዱ ህጋችን ህግ ነው! » ብሎ አዝማሪው ውቤ ለመሄድ ተነሳ። ከዚያ ሁሉም እዬሳቁ ሲሰነባበቱ፥

«አይዞሽ የኔ እመቤት አንቺም ትካሽ ይሆናል! » አለ በሻህ ደመቀችን የጎድን እያዩ እጅዋን ጥብቅ አድርጎ ይዞ።

አዛዥ እመቤታችን ለአስተርዮ ማርያም የሚዘከሩት ዝክር ለግቶ ስለ ነበረ ወደ ስራው ለመሄድ ሲነሱ ሰአታቸውን አውጥተው አይተው «አቤት አቤት! ጊዜው እንዴት ሂድዋል! እምቸም እሜቴ ‹እቤትህ ዋልህ› ብለው ይገሉኛል! ትላንት ያሉኝን አልነገርሁሽምኮ» አሉና እየቸኮሉ ሄዱ።

## ምእራፍ ሀያ

# አስተርዮ ማርያም

ያስተርዮ ማርያም ዝክር መቸ፥ ወይም በምን ምክንያት እንደ ተጀመረ ይረሳ እንጂ፥ በችግር ይሁን በድሎት ጊዜ ሊታጎል የማይችል፥ በሴት በኩል ከትውልድ ወደ ትውልድ እዬወረደ መጥቶ ወይዘሮ ጽጌ ከናታቸው የወረሱት የግዝት ዝክር ነበር።

ያስተርዮ ማርያም ዝክር እንደ ወይዘሮ ጽጌ ጊዜ ዝነኛ ሆኖ አያውቅም። ከቀደሙት እናቶታቸው እንደ ጊዜውና እንዳያቅማቸው ሰፋም ጠበብም አድርገ የሚዘክሩ ነበሩ። በወይዘሮ ጽጌ ጊዜ ግን ከድግሱ ብዛት ሌላ፥ ድግሱን የሚጋበዙት እነማን እንደሆኑ ለግብዣው የሚሰናዳው ምን እንደሆነና ተጋባዦች የሚስተናገዱበት ስነስራት የማይለወጥ ሁልጊዜም አንድ አይነት ስለ ነበረ ወይዘሮ ጽጌ በመልክ ይሁን በስም በሚያውቁዋቸውና የዝክርን ወሬ በሚከታተሉ ሰዎች ዘንድ በጣም እዬተደነቀ ይተረክላቸው ነበር።

ወይዘሮ ጽጌ አዲስ አበባ ሲኖሩ፥ የሚጋብዙዋቸው በሶስት የተከፈሉ ናቸው። እነሱም አንደኛ የንጦጦ ማርያና ያራዳ ጊዮርጊስ ካህናት በሙሉ ሁለተኛ ወይዘሮ ጽጌ ‹የኔ ቢጤዎች› የሚሉዋቸው ድሆች፥ በሽተኞችና ከልዩ ልዩ የኢትዮጵያ ጠቅላይ ግዛቶች፤ ለሙግትም ይሁን ለምስክርነት አዲስ አበባ መጥተው ስንቃቸውን ከጨረሱ በሁዋላ ለማኞች የሚሆኑ ሰዎች ሶስተኛ በጠቅላላ ስም ‹ዘመድ› ተበልው የሚጠሩት ናቸው። ለሁለቱ አድባራት ካህናት ከበግና ከዶሮ ሌላ ሁለት ለኔ ቢጤ ሁለት ለዘመድ፥ አንድ በድምር አምስት የሀረር ሰንጋዎች ይታረዳሉ። በመጠጥ በኩል፥ ለያንዳንዱ ደብር ካህናት አንድ ጋን ጠጅ፥ ሁለት ጋን ጠላና አስር ጠርሙስ ኮኛክ ለኔ ቢጤ ሶስት ጋን ጠላ ተመድቦዋል። ለዘመድ ግን የመጠጥ ወሰን አልተደረገም። በዚያ ላይ ሁለት መቶ አምሳ ብር ተመንዝሮ ላንድ ሽህ የኔ ቢጤ ለያንዳንዱ ሀያ አምስት ሳንቲም እንዲመጸወት ተመድቦዋል። አስተርዮ ማርያም ረቡ፥ ወይም አርብ ቀን የዋለች እንደሆነ በለቱ ለቀዳስያን ተብሎ የጾም ድግስ በሰፊው ተሰናድቶ፥ ወይዘሮ ጽጌ እንጦጦ ማርያም ሄደው አስቀድሰው ለካህናቱ ከሰጡ በሁዋላ ዋናው ድግስ በማግስቱ ይሆናል።

ከዚህ ሁሉ የወይዘሮ ጽጌን ዝክር የበጎ ምግባር ጥሩ ምሳሌ አድርጎ በያፉ የሚያስተርክላቸው፥ በተለይ ‹የኔ ቢጤ› ለሚሉት ያደርጉት ነው። የዘመዱ ግብዛ ሁልጊዜም ካህናቱና የኔ ቢጤው ተጋብዘው ከተመለሱ በሁዋላ ጀምሮ እስከሚከተሉት ሶስትና አራት ቀኖች ድረስ ይቀጥላል።

በመጀመሪያ ከወይዘሮ ጽጌ እጅግ ሰፊ ግቢ፥ ባንዱ ክፍል፣ አዳራሽ ድንኩዋኖች ባንድ ተቀጣጥለው ተተክለው የሁለቱ አድባራት ካህናት ለዬብቻ ባያጋፉሪያቸው እንደ የማእረጋቸው ገብተው ተቀምጠው የተመደበላቸውን ድግስ ይጋብዛሉ። ካህናቱን እንደ ወይዘሮ ጽጌ ሆነው የሚጋብዙና ምንም ነገር እንዳይጎድል የሚያስተናብሩ ባለቤታቸው ደጃዝማች እሳቸው ከሌሉ ባለቁርጦቻቸው የሆኑ ታላላቅ ሰዎች ናቸው። ካህናቱ በድንኩዋኑ ውስጥ ሲጋበዙ፥ ከሌላ ወገን ድንኩዋን ባልተተከለበት ክፍል ያን ሰፊ ሜዳ፥ የሞላውን የኔ ቢጤ ለማስተናገድ የተመደቡት ሰዎች ቦታ ቦታውን ይዞ እንዲቀመጥ ያደርጉታል። ከዚያ ሁሉም ሰጥ ጸጥ ሲል ወይዘሮ ጽጌ ልክ እንደ ተራ ሳላፊ አንገትዬው ሰፊ፣ እጅጌ - የለሽ ቀሚሳቸውን አጠር አድርገው ታጥቀው በዚያ ላይ ቀጭን ኩታቸውን በወገባቸው ዙሪያ ጠቅለል አድርገው አደግድገው ጫማቸውን አውልቀው ባዶ እግራቸውን ይሆኑና እንጀራንው በዬንቅቡ ቅይና አልጫው ወጡ ለዬብቻ በያፍላሉ ሙዳ ሙዳ ሆኖ የተቆረጠውን ስጋ በዬጥራሩ ጠላው በማንቆርቆሪያ እዬተሞላ ለዚያ መጠጫ ኩባያው የሰው ቁመት እስቲያክል እዬተሰካ፥ ያን ሁሉ ተሸክሞ የተከተላቸውን ሰራዊት በሁዋላቸው አሰልፈው ብቅ ሲሉ ያ ሁሉ የተራበ ሆድ እልል እንደሚል ሁሉ በያለበት ሲንጫጫ ‹ባለሆዱ› ብቻ ሳይሆን ለዬጎረቤቱ ይሰማል። ያ ሁሉ አፍ ገና ሳይጎርስ ምራቁን ማላመጥ ያ ሁሉ ግሮሮው ገና ሳይጎርስ መዋጥ ይጀምራል። ከዚያ ‹ስለ አስተርዮ› ማርያም እያሉ ለያንዳንዱ የኔ ቢጤ እንጀራ ቀይ በግማሽ አልጫ ወጥ ያውጡለታል ከዚያ ላይ ሙዳ ስጋ ይደርቡለታል። ከዚያ በረዥም ኩባያ ጠላ ሞልተው ባንድ እጁ አስይዘው በሌላው ሀያ አምስት ሳንቲም ይሰጡታል። እንዲህ እያደረጉ እስከ መጨረሻው የኔ ቢጤ ዝክራቸውን እስኪያዳርሱ ቀኑ ይገባደድና ያን ያክል የቆዩትን ድሆች ራብ በህል ፈንታ አንጀታቸውን በልቶ ሄደ ወይዘሮ፥ ጽጌም ካጎነበሱበት ወገባቸውን ቀና አድርገው መሄድ አቅትዋቸው በደጋፊ ገብተው አልጋቸው ላይ ይወድቃሉ። ብቻ ከዚያ ሁሉ ድካም በሁዋላ አስተርዮ ማርያም ከገሀነም ጣርና ጋር የምታሳርፋቸው መሆንዋ ‹በላኤ ሰብን› እንኩዋ እፍኝ ውሀ ላንድ በሽተኛ በስምዋ ስለሰጠ ያስማረች ማርያም በስምዋ ያን ያክል ትሩፋት ለሰሩት ለሰቸውማ የምታውርሳቸው ሰማያዊ ሀብትና ድሎት መመጠኛ የማይኖረው መሆኑ አልጋቸው ላይ እንደ ተጋደሙ ሲታሰባቸው መንፈሳዊ ደስታ ልባቸውን ይመስጠውና አስተርዮ ማርያም ያንጊዜውኑ አቅፋ ወደ ሰማይ ሰማያት ይዛቸው የምታደርግ መስሎ ይሰማቸውና ድካሙ ሁሉ ትቶዋቸው ሸሽቶ የጎበጠ ወገባቸው ቀንቶ ካልጋቸው ዘለው ተነስተው ፊታቸው እንደ ንጋት ሰማይ ወገኑን እያሳዬ ዘመዱ ወደ ሚጋበዝበት ይሄዳሉ። ከዚያ፥ «አዬ...... ! እንዲያ ሲደክሙ ውለው ትንሽ እንኩዋ እንዳያርፉ አሁን ለምን መጡ? » ይላቸዋል አንዱ።

«ያላዬ አያምንኮ እናንተ! እንኩዋ ቀኑን ሙሉ አንድ ሰአትስ እንዲያ እንደሳቸው ሊሰራ የሚችል ማነው? » ይላል ሌላው።

«ያስተርዮ ማርያም ሀይል ነው እንጂ የሳቸው መሰላችሁ? » ይላል ደግሞ ሌላው።

«ግሩምኮ ነው! እንኩዋንስ እንዲህ ያሉ ለስላሳ እመቤት ማንስ እድሜውን ሙሉ በስራ የኖረ በስራ የደነደነ ጤነኛ ሰው፥ እበሽተኞች መሀከል ገብቶ ያን ያክል ቀኑን ሙሉ ሲለፋ፥ እንዲያው ትንሽ ስቅቅ የማይለው አለ? ይኸ በውነት የጻድቃን እንጂ ያለማዊ ሰው ስራ አደለም! » ይላል አሁንም ሌላው ለጉዋደኞቹ ወይዘሮ ጽጌ እንዲሰሙት ድምጹን ከፍ አድርጎ።

ወይዘሮ ጽጌ እንዲህ ከያፉ የሚሰሙት አድንቆትና ውዳሴ፥ ልባቸውን በደስታ እያሰከረው ሲዘዋወሩ መሬት ለቀው እንደ መላክ ባዬር ላይ የሚሰፉ ይመስላቸዋል። በድካም ፈትና አዲስ ሀይል ይሰማቸዋል! ድካሙ ሁሉ ከዬሸሸበት ከዬተሰደደበት ተሰብስቦ ሳምንት የሚያስተኛቸው ለዝክሩ የተደገሰውን ድግስ ዘምድ ወዳጅ፤ ከለቱ እስከ ሳልስቱ ወይም ከዚያ በላይ በምሳም በራትም ጊዜ እዬተሰበሰበ ጨርሶ መምጣቱን ሲያቁዋርጥ ነው።

የዚያ አመት ያስተርዮ ማርያም ዝክርም እንደዚያው እንደ ተለመደው ሆኖ ተዘክሮ አለፈ። ከተለመደው የጎደለ ነገር ቢኖር የደጃዝማች አሰፋ አለመገኘት ብቻ ነው። ደጃዝማች ወደ ሀረር የሄዱበት ጉዳይ ስላላለቀላቸው ሰንጋዎችን ቀደም አድርገው ልከው፣ ለዝክሩ የማይደርሱ መሆናቸውንና ምንም ነገር እንዳይጎድል ‹አደራ› ብለው ለባለቤታቸውም ለወዳጃቸውም ጽፈው ስለ ነበረ የሳቸው አለመኖር ቢኖሩ ያደርጉት ከነበረው ያጎደለው ነገር የለም።

የደጃዝማች አሰፋ ቤት በሰፊ አጥር የተከበበ፥ አሽከሮች ከሚኖሩባቸው ቤቶች በጣም ፈንጠር ብሎ ከሁዋላ ወገን አጥሩን ተጠግቶ የተሰራ ነው። ትንሽ የሚቀርበው ወጥ ቤቱ ብቻ ነው። ደጃዝማች ሀረር ከሄዱ ጀምሮ እዚያ ቤት ከወይዘሮ ጽጌ አጠገብ ወይዘሮ ጽጌና ወይዘሮ ማረከሻቸው የሚያድሩበት ቤት አንድ ይሁን እንጂ የመኝታ ክፍሎቻቸው የተራራቁ ናቸው።

ለዝክሩ ከተደገሰው ድግስ የተራራፈውን እዬበላ እዬጠጣ፥ ሲጫወት የሰነበተው ዘመድ ወዳጅ መምጣቱን ካቆመ በሁዋላ ወይዘሮ ጽጌም የቤቱ ሰውም ደክመው ስለ ነበረ በጊዜ ግብር እዬገባ ሁሉም በጊዜ ወደዬማደሪያው ይሄዳል።

ያስተርዮ ማርያም ዝክር በዋለ ባምስተኛው ቀን ማታውን አዛዥ ተካልኝም አሽከርም ሁሉ እዬተሰናበቱ ከሄዱ በሁዋላ ወይዘሮ ጽጌ ወይዘሮ ማረከሻቸውን አስከትለው ወደ ጉዋሮ ደርሰው ተመልሰው አልጋቸው ውስጥ እንደገቡ ወይዘሮ ማረከሻቸው በሽቱ ገላቸውን ሲያሻሹዋቸው ከሩቅ የሚጎሰም ከበሮ የመሰለ ድምጽ ሰሙ።

«ዛሬስ ይህ ቃልቻ ድቤ መምታቱን በጊዜ ጀመረ» አሉ ወይዘሮ ማረከሻቸው።

«ጀመረ? እስቲ ከዚያ ቁም ሳጥን ውስጥ ጥጥ ፈልገሽ ስጭኝና እስካንቀላፋ ጆሮዬን ልወትፈው፤ አንድ ጊዜ እንቅልፍ ከወሰደኝ እንኩዋንስ እዚያ ሆኖ ድቤ መምታት አጠገቤ መጥቶ ጠመንጃ ቢተኩስ አልሰማውም! » አሉ ወይዘሮ ጽጌ።

«እኔስ ጆሮዬን መወተፍም አያስፈልገኝ፤ አሁን ሄጄ እስክወድቅ ቸኩያለሁ፤ አይኔን እንኩዋ መግለጥ አቅቶኝ እውር ድንብሬን ነው የምንገላጀጅ» አሉ ወይዘሮ ማረከሻቸው እግራቸው የፈለጉትን ያልፈለጉትን እየረገጠ ጥጥ ፍለጋ ሲሄድ።

«ወይዘሮ ማረከሻቸው ‹ጠፋ› ተብሎ የነበረው የወይዘሮ ጽጌ ጌጥ ከተቀመጠበት ቁልፍ የሌለው ቁም ሳጥን ጥጥ ፈልገው አምጥተው ወይዘሮ ጽጌ አይናቸውን እንቅልፍ ከብዶት እዬተስለመለመ ከፍ ያለ መከዳቸውን ተንተርሰው በጀርባቸው እንደተኙ ግራ ቀኝ ጆሮዋቸውን ወትፈውላቸው መብራቱን አጥፍተው ወደ መኝታቸው ሲሄዱ ያ በሩቅ የሚጎሰም ከበሮ ይመስል የነበረው ድምጽ በጣም ቅርብ ሆኖ ተሰማቸው። ነገር ግን እሱን ላለመስማት እንደ ፈለጉ ሁሉ ቶሎ ብለው ወደ መኝታቸው ሮጡ።

ከሌሊቱ ስምንት ሰአት ግድም ሲሆን እነ ወይዘሮ ጽጌ ከተኙበት ቤት ራቅ ብለው በር ከሚጠብቁት ዘበኞች አንዱ ጉዋደኛውን ጠርቶ፥

«እሜቴ ምኝታ ቤት ከተከፋቹ መስኮት በላይ መብራት ይታያል። እስቲ ሂድና እይና ና» አለ።

«መብራት ሳያጠፉ ተኝተው ይሆናል እንጂ፥ አሁን ምን ‹ይመጣ› ብለህ ነው? » አለ ጉዋደኛው ቤቱን ዞሮ አይቶ ለመመለስ ሲነሳ፤

«እሱስ ይሆናል ብቻ ቀደም ብሎ ያልነበረ ስለ መሰለኝ ነው እንጂ።»

የመብራቱ ብርሃን ከውጭ ወደ ውስጥ የሚዘጉት የመስኮት መዝጊያዎች በሚገናኙበት ቀጭን መስመር ላይ እሰከታች ይታያል። ነገር ግን የመስኮቱ መዝጊያዎች

የሚገናኙበት ቀጭን መስመር እውስጥ መብራት መብራቱን ለማሳዬት ያክል እንጂ፥ ከውጭ እውስጥ ምን እንዳለ ለማሳዬት አይበቃም። ስለዚህ ዘበኛው እንደ ሚተኩስ ሁሉ አንድ አይኑን ጨፍኖ በሌላው በዚያች ቀጭን መስመር አስገብቶ ለማሳየት ቢሞክር ስላቃተው ባይኑ ፈንታ አንድ ጆሮውን ደቅኖ ድምጽ ለመስማት ያድምጥ ጀመር። ምንም ድምጽ የለም፤ ሁሉም ጸጥ ሰጥ ያለ ነው!

«ከመብራት በቀር ምንም የለ» አለ ወደ ጉዋደኛው ተመልሶ። ነገር ግን በዚያው ጊዜ በወይዘሮ ጽጌና በወይዘሮ ማረከሻቸው ምኝታ ቤቶች መብራት ብቻ አይደለም የነበረ። ሁለቱም በወሬ እንደሆነ እንጂ ሲሰራ አይተውት የማያውቁ ስራ ይሰራ ነበር!

አምስት እንግዶች ከንግዳ ቤት በኩል የወይዘሮ ጽጌን ምኝታ ቤት ቀስ ብለው ከፍተው ገብተው መብራት አበሩ። እንግዶቹ ራስ ራሳቸውን በጨርቅ አስረው ፊታቸውን እስከ አይናቸው ስር በመሀረም ሸፍነው ሁሉም፥ ልብሳቸው ላይ የስጋ አራጅ መለዮ የመሳሰለ ነገር ደርበው በፊታቸው ላይ ካይናቸው በቀር ሌላ ነገር ስለ ማይታይ ከጨርቅ ብቻ የተሰሩ አይን ያላቸው በጣም የሚያስፈሩ ምስሎች እንጂ ሰዎች አይመስሉም።

ወዲያው እንደ ገቡ፥ ከመሀከላቸው አለቃ የሚመስለው ከኪሱ፥ ብጣሽ ወረቀት አውጥቶ አይቶ፥

«የዚህ ክፍል ምእራብ ያ አይደለም? » አለ፥ በጣም በዝቅተኛ ድምጽ በምእራብ በኩል ያለውን በር እያመለከተ።

«አዎ ነው» አለ ሌላዉ እንድ እፊተኛው በሹክሹክታ።

«ሴትዮዋ የተገኙት በዚያ አልፎ አልፎ በሚገኘው ክፍል ነው ፍጠኑ» ሲል አለቅዬው እንዲሁ በሹክሹክታ ካምስቱ ሁለቱ በጥፍራቸው እዬቆሙ ወደ ወይዘሮ ማረከሻቸው ክፍል ሄዱ።

ወይዘሮ ጽጌ የጥቁር ሀር ክምር የመሰለ ጠጉራቸውን የተሸከመ ራሳቸው ከፍ ባለ መከዳ ላይ ከግራ ወደ ቀኝ ትንሽ ዘንበል ብሎ አርፎ በንቅሳት ያጌጡ አንገት ደረታቸውን ‹እዩልኝ› ለማለት እንደ ፈልጉ ሁሉ፥ የለበሱትን ልብስ ወደ ታች ገፋ አድርገው ሁለቱ ራቁት ክንዶቻቸው በግራ ቀኝ ጎናቸው ዛል ብለው ወድቀው አይኖቻቸውና ከንፈሮቻቸው ገርበብ ብለው እንደ ተከደኑ ፊታቸው ሊስቁ እንደሚፈልጉ በፈገግታ ተውቦ፥ በጀርባቸው ተኝተው ሲታዩ፥ በጣም ያምሩ፥ በጣም

ያሳዝኑ ነበር። እንግዶቹ፥ የኒያ ወይዘሮ ውብትና፥ የተኙባት ሁኔታ ስራቸውን እንዳስረሳቸው ሁሉ ዝም ብለው ቆመው ሲመለከቱ፥

«ምን ትጠብቃላችሁ? » አለ አለቅዬው፥ እንደ መቆጣጥ ብሎ። ከዚያ አንዱ ከመብራቱ ጋር ሲታይ አይን የሚያጥበረብር የተመዘዘ ሻምላውን በወይዘሮ ጽጌ ደረግ ላይ ባለ ሁለት ነጠብጣብ ትልቅ ኩዋስ ይዞ ወደ ወይዘሮ ጽጌ ቀረብ አለና፥ አፋቸውን ቀስ ብሎ ለመክፈት ቢሞክር በንቅልፍ ልባቸው ራሳቸውን ቀኝና ግራ እያዘዋወሩ ስላስቸገሩት አውራ ጣቱን አፋቸው ውስጥ አግብቶ በሀይል ሲከፍት ነቁ ነገር። ግን፥ ከመጮሀቸው በፊት፥ ያን ትልቅ ባለጥብጣብ ኩዋስ አጉርሶ፥ ጥብጣቦችን በጆሮዎቻቸው ግርጌ አዙሮ እማጅራታቸው ላይ ቋጠረ። ከዚያ እጆቻቸውን ወደ ሁዋላ አዙሮ መስቀልኛ አሰረና በላያቸው እንዲተኙባቸው ካደረገ ብሁዋላ፥ እንዲያ በጆቻቸው ላይ በጀርባቸው እንደ ተኙ ከታች እግሮቻቸውን ገጥሞ ከላይ በደረታቸውና ወደ ሁዋላ በታሰሩት እጆቻቸው ላይ ጀመሬ ገመድ አሳልፎ፥ እንዳይንቀሳቀሱ፥ እንዳይላወሱ አድርጎ ካልጋው ጋር አሰራቸው። ካካላታቸው ሁሉ፥ ላይ ታች፥ ግራ ቀኝ እንዲሮጡ ነጻነት የነበራቸው አይኖቻቸው ብቻ ነበሩ።

ወይዘሮ ጽጌ፥ በላያቸው የተንጠለጠለውን ሻምላ እያዩ፥ ያሉበት ደቂቃ አልፎ ሌላው ሲከተል፥ ወርዶ በሆዳቸው የሚጠልቅ መስሎዋቸው እሱን ብቻ እዮጠበቁ፥ እግሮቻቸው ካልጋ ጋር ሲጠፈሩ፥ እጆቻቸው የሁዋሊት ዞረው ሲታሰሩ አፋቸው ሲለጎም ሰራተኛውን ከመርዳት በቀር ለመከላከል አልሞከሩም።

ይህ ሁሉ ከሆነ በሁዋላ እጆቹን ወደ ሁዋላ በጀርባው ላይ አስተሳስሮ ቆመ፤ ትእዛዝ የሚሰጠው ሰው፥

«ያን ቁም ሳጥን ክፈተው! » አለ ወይዘሮጽጌን ሲያስርና ሲለጉም የቆየውን ሰው። ያ ቁልፍ የሌለው ቁም ሳጥን ሲከፈት ሁለት መጠነኛ ሳጥኖች ታዩ።

«አረንጉዋዴ ከፈይ የተሸፈነውን ሳጥን አምጣ» አለ አዛገፑ።»

«ክፈተው» አለ፥ ሳጥኑ መጥጦ እወይዘሮ ጽጌ ጎን እንደ ተቀመጠ።

ሳጥኑን ያመጣው ሰው በሀብል የተሰኩ ብዙ መክፈቻዎች ከኪሱ አውጥቶ እያለዋወጠ ሲሞክር ከቆዬ በሁዋላ ባንዱ ከፈተው። ወዲያ አዛገፑ ቀረብ ብሎ ከወርቅ ከብር ከሉልና እንዲሁም ከልዩ ልዩ የከበረ ድንጋይ አምባር ድሪ አሸንክታብ ቀለበትና መስቀል ጉትቻ እንዲሁም ሌላ ጌጥ ሆኖ የተሰራውን ለብቻ መርጦ አስቀመጠ። ከዚያ ተጠምዞ ተድበልብሎ፥ ተሞልሙሎ ተጠፍጥፎ የተቀመጠውን ወርቅ ሰብስቦ ባንድ

ከረጢት ከተተና ጌጥ ሆኖ የተሰራውን ሁሉ፣ እንደገና በሳጥኑ አግብቶ ቆልፎ፥ ወደ ነበረበት ቁም ሳጥን መልሶ አስቀመጠ። ከዚያ መጣና በከረጢት ከተተውን ወርቅ አንስቶ ለጉዋደኛው አስይዞ፥

«እሜቴ ይህ ሀብት እስዎና፥ እኔ የጋራ ክፉ ስራ የሰራንበት የክፉ ዋጋችን ነው። በዚህ ሀብት ምክንያት ሳላውቅ የወንጀልዎ ተካፋይ ሆኛለሁ። የወንጀልዎ ተካፋይ ከሆንሁዎ ወንጀል ለሰራሁበት ህብት ተካፋይ የማልሆንበት ምክንያት የለም። ስለዚህ ድርሻዎን ትቼ ድርሻየን ወስጃለሁ። በዚህ ሀብት ምክንያት የወንጀል ተካፋይዎ ማን እንደሆነ ስለሚያውቁ፥ ከዚህ በፊት እንዳደረጉት ሌላ ሰው እንዳያስቸግሩ አደራ፥ ጤና ይስጥልኝ» አለና ከወይዘሮ ማረከሻቸው ጋር የቆዩትን ጉዋደኞቹን አስጠርቶ በመጡበት ተመልሰው ሄዱ።

ሲነጋ አዛዥም አሽከሮችም ቢመጡ፥ እንኩዋንስ የወይዘሮ ጽጌ የወይዘሮ ማረከሻቸው መስኮት አልተከፈተም። ደመቀች መምጣቷን ከተወች ጀምሮ መሰንበቻውን ወይዘሮ ማረከሻቸው ከሁሉም ቀድመው ተነስተው መጀመርያ የራሳቸውን ሁዋላ የወይዘሮ ጽጌን መስኮት ከፍተው፥ ወይዘሮ ጽጌ ሲነሱ ጉዋሮ አድርሰው መልሰው መጻህፎቻቸውን አቅርበውላቸው ካዛዥ እንኩዋ ቀድመው እውጭ ይገኙ ነበር።

«የመሰንበቻውን የንቅልፍ ውዝፍ ማውጣታቸው ነው! ትንሽ ይቆዩ አትቀስቅሱዋቸው» አሉ አዛዥ። ከዚያ አሽከሮች የውጭ የውጪውን ስራ ሲሰሩ እንዲቆዩ አድርገው ሲጠብቁ ሰአት ሰአትን እዬተከተለ ያልፋል። የወይዘሮ ጽጌና የወይዘሮ ማረከሻቸው መስኮቶች ግን ጭራሽ አይንቀሳቀሱም! ‹ምን ሆኑ?› አሉ በሁዋላ መጀመርያ ለሰስ አድርገው በሁዋላ በሀይል ይመቱ ጀመር። ድምጽ የለም! ከዚያ ስጋታቸው ወደ ብርቱ ፍራት ወደ መሸበር ተለውጦ፥ አሽከሮችን ጠርተው መስኮት እዬሰበሩ ቢገቡ ሁለቱን ወይዘሮዎች ታስረው ተለጉመው እንደማይንቀሳቀስ ሬሳ በያልጋቸው ላይ ደርቀው አገኙዋቸው።

«ቶሎ ስለት ነገር ፈልጉና አምጡ! ቶሎ ስለት ነገር! » አሉ አዛዥ ደንግጠው እዬተርበተበቱ። ስለት ፍለጋ ሩቅ ከመሄድ የጥብጣብና የገመድ ቁዋጠሮ መፍታት የሚቀርብ መሆኑን ድንጋጤያቸው አስረስተዋቸዋል! እንዲሁ ገመዱን ይሁን ጥብጣቡን ሳይነኩ በመ. ቤታቸው ዙርያ እዬዞሩ ‹ስለት› ሲሉ ከሌላው ክፍል ወይዘሮ ማረከሻቸውን የፈታው አሽከር መጥቶ ወይዘሮ ጽጌንም ፈታቸው።

አዛዥ፥ ወይዘሮ ጽጌ ከተፈቱ በሁዋላ፥ እጅ እግራቸውን ማንቀሳቀስ አፋቸውን፥ መሰብሰብ አቅቱዋቸው ተጎሳቁለው ሲያዩዋቸው ጊዜ እንያን እንደ ታቦት ይፈሩዋቸው ያከብሩዋቸው የነበሩ ወይዘሮ አቅፈው ይጮሁ ጀመር። «እኔን ይሰሩኝ፥ እኔን ይገንዙኝ እኔን ያንገላቱኝ እመቤቴ! » እያሉ ሲያለቅሱ ወይዘሮ ጽጌም ያዛዥን አንገት አቅፈው በጣም አለቀሱ።

የቤቱ ሰው፥ ወይዘሮ ጽጌንና ወይዘሮ ማረከሻቸውን ከቦ ቆሞ ሲያለቅስ፥ «አገኘሁት፥ አገኘሁት! » አለ አንዱ አሽከር እዬሮጠ መጥቶ።

«ምኑን? ሌባውን? » አለ ሌላው።

«ሌባው - ሌቦች - የገቡበት በንግዳ ቤት በኩል ነው! »

ከዚያ አዛዥም ሌሎችም አሽከሮችም ወደ እንግዳ ቤት ቢሄዱ ከወለሉ ንጣፍ ብዙ ሳንቃ ተእንስቶ ሥፊ ጉድጉዋድ አፉን ከፍቶ ይታያል። ወይዘሮ ጽጌና ወይዘሮ ማረከሻቸውም ተደግፈው እያነከሱ ለማየት መጡ።

«ሩጥና ሽጉጤን አምጣ አንተ! » አሉ አዛዥ።

«ለምን? » አሉ ወይዘሮ ጽጌ።

«እገባለሁ፥ ሌቦች አልወጡም፤ እዚህ ነው ያሉ! »

«እንዴት? »

«እዚህ ከገቡ በየት ይወጣሉ! »

«ባይሆን ሌላ ሰው፥ እጣን ሰው ይግባ።»

«የለም እኔ ነኝ የምገባ» አሉና አዛዥ ሽጉጣቸውን አቀባብለው መብራት የያዘ ሰው አስከትለው እጉድጉዋዱ ውስጥ ገቡ። ሌሎች አሽከሮች፥ አዛዥ ሌቦች አግኝተው ጦርነት የገጠሙ እንደሆኑ ለርዳታ ለመድረስ መሳሪያቸውን ይዘው፥ እጉድጉዋዱ አፍ ተሰልፈው ይጠባበቁ ጀመር። አዛዥና መብራት የያዘው ሰው ሌቦች የሰሩትን መንገድ ተከትለው ካጥር ውጭ ወጡ። ከዚያ ዞረው በበር በኩል ተመልሰው ሌቦች ካጥር ውጭ ጀምረው ውስጥ ለውስጥ እዬቆፈሩ መጥተው እንግዳ ቤት ሲደርሱ ሳንቃውን አፍርሰው መውጣታቸውን ባስረዱ ጊዜ ሰው ሁሉ ተገረመ። ‹ከመሬት በታች ያን መንገድ ለመስራት ስንት ሌሊት ፈጀባቸው እግዜር ይወቅ›

«እህ..... ለካ ‹ያ! የቻልቻ ድቤ!› የልነው ሌቦች ሲቆፍሩና ግንብ ሲንዱ ሰምንተን ነው! » አሉ ወይዘሮ ማረከሻቸው።

ከዚያ በሁዋላ አዛዥ፥ ለደጃዝማች አሰፋ ቴሌግራም አስተላልፈው ወዲያው ሶስተኛ ፖሊስ ጣቢያ ሄደው የመቤታቸው ሀብት መዘረፉን አስጽፈው ተመለሱ።

ደጃዝማች የጀመሩትን ጉዳይ እንኩዋ ሳይጨርሱ ቴሌግራሙ እንደ ደረሳቸው ተነስተው መጡ። ባለቤታቸውም አዛዥ የሆነውን ሁሉ የሌቦች አለቃ በመጨረሻ ወርቁን ይዞ ሲሄድ የተናገረውን ጭምር ከነገርዋቸው በሁዋላ ብዙ ሲያስቡ ቆይተው «ይገርማል! አሁን የነገራችሁኝ ሁሉ ተሰብስቦ የማይታመን ነገር ወደ መጠርጠር ነው የሚመራኝ! » አሉ ደጃዝማች።

«ምን አሉ ወይዘሮ ጽጌ።

«እንጃ! መናገሩም ያስቸግራል! እስቲ እባክህ በላይነህን ካለበት በስልክ ፈልግና ቶሎ እንዲመጣ አድርግልኝ» አሉ ወደ አዛዥ ቀና ብለው። አቶ በላይነህ የምሩ ነገረ ፈጃቸው ናቸው። አዛዥ ወደ ስልክ ቤት ከሄዱ በሁዋላ፥

«አዬሽ ጽጌ፥ ድንግል አንቺና ተካልኝ እንደ ነገራችሁኝ የማላውቀው ቢኖር ኖሮ ከዳኛቸው በቀር ሌላ ሰው ባልጠረጠርሁ ነበር! ብቻ ዳኛቸውን ስለማላውቀው ባንቺና በኔ ላይ ይህን ስራ ይሰራል ብዬ አላምንም» አሉ ደጃዝማች።

«በዚህ እግዚአብሄር ይኮንነኝ እንጂ፥ እኔ ሌላ ሰው ወሰደው አልልም፥ ወርቁን የወሰደው እሱ ነው። ደመቀችን ፈቶ ከለቀቀ በሁዋላ እዚህ መጥጦ ስድብ ቀረሽ የወረደብኝንና የዛተብኝን ዛቻ ባይሰሙ ነው» አሉ ወይዘሮ ጽጌ።

## ምእራፍ ሀያ አንድ

# ከፉ አጋጣሚ እየጠሉት ያስጠላል

ደመቀች አስራ አምስት ቀን ያክል፣ አዛዥ ቤት ካገገመች በሁዋላ ሙሉ ጤና አግኝታ ደምዋ ተመልሶ፥ በርትታ፥ ያዛዥን ባለ ቤት ወይዘሮ ጌጤን በቤት ስራ ትረዳ ጀመር። ወደ ፊት እድልዋ ወዴት እንደ ሚመራት እሱ እንጂ፥ እስዋ አታውቅም። ካገርዋ ከመጣች ጀምራ፥ ከደጃች አሰፋ ሰፊ ግቢና ካካባቢዋ በቀር ሌላ ቦታ አታውቅ፥

ከደጃች አሰፋ በቅርብ ካሉ ጎረቢቶች በቀር ሌላ ሰው አታውቅም አዲስ አበባ አምስት አመት ተቀምጣ ላገሩ እንግዳ ለሰዉ ባዳ ነበረች። አምስት አመት ከኖረችበት ጠባብ አለም ውጭ አንዳንድ ቦታዎች ያዬችና አንዳንድ ሰዎች ያወቀች ልጅዋን ትምርት ቤት ባስገባችበት ጊዜ ስትዘዋወር ነው። ስለዚህ ስራ ወዴት እንደሚፈለግና ማን እንደሚፈልግላት ስታስብ አሳብዋ ዞሮ ዞሮ የሚያርፍበት ስለሚያጣ በባዶ አለም ብቻዋን ያለች ይመስላትና ፍራት ይይዛታል። በቅርቡ ምናልባት አዝማሪው ውቤና በሻህ ዘለሌ ናቸው። ነገር ግን ከሶስተኛ ፖሊስ ጣቢያ በተፈታች ሳልስት ካዬችው በሁዋላ ብቅ ብሎ ስለማያውቅ አዝማሪው፥ ውቤም መላልሳ እዬነገረችው እንደገና በጠዬቀችው ቁጥር የሚሰጣት መልስ ‹ረሳሁት› ስለሆነ ተቀይማ መጠዬቁን ተወች።

አንድ ቀን አዛዥ መድሀኒት ጠጥተው እቤት በዋሉበት ደመቀች ከባልተቤታቸው ጋር ምሳ ስታሰናዳ፥ «ደመቁ እባክሽ ነይ አጫውችኝ» አሉ።

«እዚያ ከስራ - የቤቶች ጋር ጭቅጭቅ ለምደው ዝም ብሎ መቀመጡ ጭንቅ ይሆንባቸዋል! እባክሽ ሂጂ አጫውቻቸው እኔ እጨርሰዋለሁ» አሉ ወይዘሮ ጌጤ። ደመቀች ትሰራ የነበረውን ድሮ ወጥ ለወይዘሮ ጌጤ አስረክባ፥ እጅዋን ታጥባ አዛዥን ለማጫወት ሄዳ አጠገባቸው ተቀመጠች።

«ተከሰተ እንደምን ነው? እኔ እንዳልሁሽ ደህና ሆኖ አላገኘሽውም? » አሉ አዛዥ ትናንቱን የተከስተን ምሳ ይዛ ሄዳ አይተው ስለ ነበረ።

«ተከስተ ደህና ነው፤ በጣም ደህና ነው አባባ! ተለይቸው ስሰነብት ጊዜ ነው መሰለኝ፥ በዚህ ባጭር ጊዜው ያደገ መስሎ ታየኝ።»

«ያድጋል እንጂ ሲመቸው ለምን አያድግ? »

«አዎ የተመቸው ይመስላል። ትምርት ቤት የገባ እለት ጥዋት ለመሄድ ስንሰናዳ ‹አልሄድም› ብሎ እያለቀሰ ሲያስቸግረኝ ጊዜ ‹ለጥቂት ቀን እየውና ካልወደድኸው መልሸ አመጣሀለሁ› ብዬው ነበር። ትናንት የሚለውን ለመስማት ብዬ ‹ልውሰድህ? ብለው አንቄ በግድ የምወስደው መስሎ ፊቱ ባንድ ጊዜ ተለዋወጠና ተነስቶ ሊሮጥ ሞከረ። በሁዋላ እጁን ይዤ ቀልዴን መሆኑን ስነግረው ብቻ ደስ ብሎት ይስቅ ጀመር። »

«አዎ ይመቸዋል፡ አፈርና ውሀ የሚመገበው እንጨትና ሳር ተመችቶት እንዲያ የሚያምርበት ቦታ - ምግብ እያማረጠ እዬተመገበ እዚያ የሚኖር ሰው ቢመቸውና - ቶሎ ቢያድግ ያስገርማል? » አሉ አዛዥ እንደ መሳቅ ብለው ደመቀችን እያዩ።

«እውነት ነው» አለች እሰዋም ትንሽ ሳቅ ብላ።

«እሱ እግዚአብሄር ጤና ያድርገውና ትምርቱም ይቅናው እንጂ ከንግዲህ አያሳስብሽም። ይልቅ ከንግዲህ የምታሳስቢ አንቺ ነሽና ለሱ፥ ከምታስቢው ትንሽ ቀነስ እያረግሽ ለራስሽ - ማሰብ ነው! » አሉ አዛዥ በትካዜ ድምጽ አይናቸውን ከደመቀች አንስተው ሳይረግቡ ሌላ ሌላ እያዩ። ደመቀች አልመለሰችም። ከዚያ አይኖቻቸውን ከወሰዱበት እንደገና ወደስዋ መለሱና «ደመቁ አንድ ነገር ልለምንሽ! » አሉ።

«ምን? »

«ቀደምሽ እሺ በይኝና።»

«የማልችለውስ የሆነ እንደሆነሳ? »

«እንኩዋንስ የማትችይውን ብትችይውስ የማይስማማሽ ከሆነ ‹አድርጊልኝ› እልሻለሁ? »

«ታዲያ የምችለው ከሆነ ልጅዎ ነኝ፤ ይዘዙኝ እንጂ ለምን ይለምኑኛል? »

«ለምኜ ከሆነልኝ አዝዤ እንዳስረደግሁት በቆጠርሁት! »

«እሺ።»

«ሙት በይኝ።»

«ተካልኝ ይሙት! »

«ካሳሁን አብጤን ታውቂው የለም? » አሉ አዛዥ ከምን እንደሚጀምሩ ችግሮዋቸው አንገታቸውን ደፍተው ትንሽ ስያስቡ ቆዩና።

«እንጃ! የማውቃቸው አይ - መስለኝም» አለች መፍራትዋ በፊትዋ እዬታዬ። እከዚያን ያክል ዳርዳርታ በሁዋላ የካሳሁን አብጤን ስም በማንሳታቸው ብቻ የሚጠይቁዋት ምን መሆኑን ጠርጥራ ልብዋ በጣም ተሸብሮ ነበር።

«ካሳሁን አብጤን ካላወቅሽማ - ‹ማነን አውቃለሁ› ልትይ ነው? ያ - ዘለግ ያለ መልከ መልካም ሱፍ ለባሽ - ካሳሁን አብጤ ጠፋሽ? ለጌቶችም ለሜቴም ወዳጅ ስለሆነ፥ ከቤታችንኮ ተለይቶ አያውቅም። እንዲያውም ብዙ ጊዜ ግብር ከተመለሰ በሁዋላ ሲመጣ፥ ቡና አልፍተሽ የምትሰጭው አንቺ ነሽ! »

ደመቀች፥ አቶ ካሳሁ አብጤን ደህና አድርጋ ታውቃቸዋለች ብቻ ብዙ ጊዜ ቡና እያፈላች መስጠትዋ ታዝዛ እንጂ ወዳ አልነበረም። አቶ ካሳሁን ደመቀች ከምትፈራቸውና ከምትጠላቸው ሰዎች አንዱ ነበሩ። አዛዥ እንዳሉት አቶ ካሳሁን ለደጃዝማች አሰፋና ለወይዘሮ ጽጌ ወዳጅ ስለሆኑ፥ ብዙ ጊዜ ወደነደጃዝማች ቤት መሄድ ከሚያዘወትሩት ሰዎች አንዱ ነበሩ። በተለይ ወይዘሮ ጽጌ፥ ‹መንፈሳውያን፥ ናቸው› የሚባሉትን ሰዎች ማቅረብ ስለሚወዱና፣ አቶ ካሳሁን ቤተክሲያን አዘውትረው ስለሚስሙ፥ እዚያ ከመተያየት ብዛት መጀመሪያ ከወይዘሮ ጽጌ ሁላ በሳቸው ሳቢያ ከባለቤታቸው ከደጃዝማች አሰፋ ጋር ተዋወቁ ወዳጅነታችወ በዚያ የጀመረ ነው። አንድ ቀን አቶ ካሳሁን ከወይዘሮ ጽጌ ጋር ሲጫወቱ ቆይተው ለመሄድ ሲነሱ በልማድ በወዳጆች መሀከል እንደሚደረገው፥

«እመቤቴ፥ ነገ ጠዋት መድሀኒት ስለምቀምስ፥ ተሰናብቸዎታለሁ» አሉ።

«እ - ! ነገ መድሀኒት ልትጠጣ ነው? ማለፊያ እንጂ ማለፊያ ነው። ያስቀጥህ ያሽርህ! » አሉ ወይዘሮ ጽጌ፥ እንደ መሳቅ ብለው።

«አሜን እመቤቴ አሜን። ማለፊያ አድርጎ፣ እንደሚያስቀምጠኝ ርግጠኛ ነኝ፥ ማለፊያ አድርጎ የማሻሩ ፈንታ ግን - እንደ ሁልጊዜው የመቤቴን ፈንታ ነው! » አሉ አቶ ካሳሁን ላለፈው ምስጋናቸውን አስቀድመው የሚከተለውን እንዳይረሳ የማያሳስቡ መሆናቸውን በሚገልጽ ያነጋገርና አስተያየት ስልት።

በማግስቱ ርፋድ ላይ ወይዘሮ ጽጌ ላቶ ካሳሁን፥ የላኩትን የኮሶ ምሳ፣ አስር ነጭ እንጀራ በጥልፍ መሶብ አንድ ወንድ አሽከር ጃዊ ቀሚስ አልብሶ በራሱ ተሸክሞ፥ አንድ ድስት ዶሮ ወጥና አንድ ገንቦ ጠጅ ወጡን በሁለት እጆችዋ ጠጁን በጀርባዋ ደመቀች እንዲሁ ጃዊ ቀሚስ አልብሳ ተሸከማ፣ ወደ አቶ ካሳሁን ቤት ሄዱ። ያቶ ካሳሁን ቤት እዚያው ገዳም ሰፈር ቅርብ ነበር። ደረሱ እሽከር ነግሮላቸው ሲገቡ፣ አቶ ካሳሁን በልማዱ ኮሶ የጠጡ መኩዋንንት እንደሚያደርጉት ሱሪ ሳይታጠቁ ወፍራም ጋቢያቸውን ብቻ ለብሰው እተነጠፈ ድንክ አልጋቸው ላይ ቁጭ ብለው ነበር። እዚያ መላከተኞች ከመቤታቸው የተላከውን ምሳ አቶ ካሳሁን ፊት አቅርበው አሳይተው

ደመቀች ጠጁንም እንጀራና ወጡንም ቀምሳ ካስረከበች በሁዋላ ባለቤቱ አንዳንድ ብርሌ ጠላ አዘውላቸው ተቀምጠው ጠጥተው ሊሄዱ ሲሉ፥

«እቲ - አንተ እውጭ ቆይ ደመቀች ለሜቴ የምትነግርልኝ መልእክት አለኝ ልንገራት» አሉ አቶ ካሳሁን ከደመቀች ጋር የመጣውን አሽከር። አሽከሩ እጅ ነስቶ ከወጣ በሁዋላ፥

«ነይ ወዲህ» አሉ እድንኩ አልጋቸው ላይ እንደ ተቀመጡ፣ የውስጥ ግለታቸው ጸዳሉን በፊታቸው ሁሉ ላይ እያበራ። ደመቀች ከተቀመጠችበት ተነስታ ወደሳቸው ለመሄድ ከቃጣች በሁዋላ ሁኔታቸውን ስታይ መልእክት ለመንገር የፈለጉ ስላመሰላት ወደ ፊት የቃጣችውን እርምጃ ገታችና ቆመች።

«ነይ እንጂ! » አሉ እንደ ተቀመጡ ቀኝ እጃቸውን ዘርግተው።

«እዚህ እንዳለሁ ይንገሩኝ እሰማለሁ» አለች። ፈርታ ትንቀጠቀጥ ነበር።

ወዲያው በፍትወት ግፊት ከተቀመጡበት ተወርውረው ተነስተው እጅዋን ሲይዙዋት አቅምዋን ሁሉ አጠራቅማ ነጥቃቸው ለማምለጥ ሞከራ ነበር። ነገር ግን ከስዋ አቅም የሳቸው አሸነፈና፥ ስበው አልጋቸው ላይ ጣሉዋት። እዚያ፥ ያ ቅድም በፊት ለፊታቸው ተቀምጣ ሲያዩዋት ጭዋነታቸውን አስረስቶ ተራ የብልግና ስራ እንዲሰሩ ያደረጋቸው ውበትዋ ሁሉ ጠፍቶ ፊትዋ ኩምትርትር ጠጉርዋ ጭብርር ብሎ፥ ያቆሰሉት አውሬ መስላ አካላታቸውን ሁሉ በጆችዋ አዬቡዋጠጠችና በግሮችዋ እዬረገጠች ስትታገላቸው በስዋ ሀይል፥ ላይ ሌላ ሀይል ያውሬ ሀይል እንደ ጨመረች ሁሉ አባተቻቸው! እንዲያ ሲታገሉ፥ ጋቢያቸው ከላያቸው ወድቆ እርቃናቸውን ቀሩ። ከዚያ በሁዋላ በውስጣቸ ይነድ የነበረው የፍትወት ስሜት ቀዝቃዛ ውሀ እንዳፈሰሉበት እሳት ጠፍቶ በሱ እፍረትናእልክ ተተኩና ትግላቸው ሁሉ ላለመሸነፍ ብቻ ስለ ነበረ ቡጭጫውንም ርግጫውንም ችለው እንደ ምንም አንድ እጅዋን አናጥለው በሁለት እጆቻቸው ይዘው በብርቱ ጭካኔ ሲጠመዝዙት፣

«ዋ - ይ! መጮሄ ነው! እጮሀና ይዋረዳሉ! ይልቀቁኝ፤ ድም - ድምጤን ከፍ አድርጌ ሳልጮህ! » አለች ከመሙ ይልቅ ንዴቱ እያስለቀሳት። አቶ ካሳሁንም የምኞታቸው አለመፈጸምና ውርደታቸው ባንድ ላይ ሆነው በጣም አናደዋቸው እርቃናቸውን እንደ ቆሙ፥

«ሂጂ ወዲያ ውጪ! » አሉና ጠምዘው በያዙት እጇዋ በሀይል ወደ ፊት ገፍተው እወለሉ ላይ በግንባርዋ ደፉዋት! ደመቀች ከወደቀችበት ተነስታ እንኩዋንስ አንድ ቃል ልትናገር ዘወር ብላ ሳታያቸው፥ አውጭኝ - ነፍስዋን እየሮጠች ወጣች። ብሮዋት የነበረው ልጅ ስለ ዘገዬችበት ከግቢው ወጥቶ ካጥር፥ ውጭ ወዲያ - ወዲህ እዬተን ሸራሸረ ይጠብቃት ነበር። ካጥር ውጭ መሆኑ በጃት። እንዲያ እንደተንገላታች ሳያይት ትንፋሽዋ ጸጥ እስኪል በቅጡ፣ ለማድረግ ጊዜ አገኘች። አቶ ካሳሁን ፊት ከፍትወት ሁዋላ ከልክና ከፍረት ብዛት የተነሳ ራቁታቸውን ሲታገሉ መቆዬታቸው አልታወቃቸውም ነበር። ራቁት መሆናችውን ያዩ ደመቀች ወጥታ ከሄደች በሁዋላ ነበር!

ስለዚህ፥ ደመቀች አቶ ካሳሁን አብጤን እስከዚህ ድረስ ነበር፥ ደህና አድርጋ፥ የምታውቃቸው። በሌላው ሰው ሁሉ ዘንድ የሚታወቁበትን መንፈሳዊ መልካቸውን ብቻ ሳይሆን በሌላው ሰው ሁሉ ዘንድ የማይታውቀውን ውስጣዊ፥ ያውሬ ባህሪያቸውን ጭምር ነበር ደህና አድርጋ የምታውቅ!

«አ - አዎ፤ ስማቸውን ከመልካቸው ጋር ሳላገናዝብ ቀርቼ ነው አሁን አውቅሁዋቸው፥ አባባ! » አለች ውሸትዋን።

«ታዲያ እሳቸው ምን ሆኑ? » አለች ቀጠለችና ሊነግሩዋት ያሰቡትን የጠረጠረች እንኩዋ ሳትመስል።

«ምንም አልሆነ አቶ ካሳሁን፥ ‹አንቱ› የተባለ ሀብታም ከመሆኑ ሌላ፥ በጣም ደግ ሰው፥ ሀይማኖተኛ ነው። ሚስቱ ከሞተች ጀምሮ፥ ብዙ ወይዘሮዎች አዬተመኙት፥ ከሴት ሴት ሲያማርጥ ከ - ሁለት አመት የበለጠ ብቻውን ኖረ። አሁን - አንቺ እሜቴን ትተሽ መውጣትሽን ስለ ሰማና - የጭዋ ልጅ መሆንሽን ስለሚያውቅ ‹ካልዳርህልኝ› ብሎ ሲያስቸግረኝ ነው የሰነበተ። ስለዚህ መቸም ሰው የመሆን ትርፉ ቤትና ንብረት የሚሰጡትን ደስታ ከሚወዱት የኑሮ ጉዋደኛ ጋር እዬተካፈሉ መኖር ነውና እሱን ብታገቢው ደስ አሰኝቶ ያኖርሻል። በደልሽን ቆጥሮ እግዚአብሄር የላከው ሰው ነው፥ አትግፊው ልጄ» አሉ አዛዥ። ደመቀች አንገትዋን ደፍታ በግር አውራ ጣትዋ መሬት እዬቆረቆረች ዝም አለች።

«በይኮ! » አሉ አዛዥ ሲጠብቁ ቆይተው መልስ ስላጡ።

«ምን ልበል? »

«እሺ በይ! »

«ባያምሉኝ መልካም ነበር፥ አባባ! »

«እንዴት? ለምን? »

« ‹ይሁን› እንዳልል ጭራሽ የማልችለው ስለሚመስለኝ ‹አይሆንም› እንዳልል በርስዎ ‹አሉኝ› ብዬ እምነቴን ሁሉ ባሳረፍሁብዎ አባቴ መማሉ እኒህ ሁለት ክፉ ነገሮች አስጨነቁኝ።»

«በኔ መማልሽ እንኩዋ እዚህ ውስጥ ተራ የሚገባ አደለም። ሰውዬውን ካልፈቀድሽ ‹መሀላ አፈረስሽ› ብዬ አልቀዬምም። ብቻ ‹ጭራሽ የምችለው አይመስለኝም› ያልሽው ነው የማይገባኝ። ምኑን ነው የማትችይው? ባል አግብቶ ቤት ንብረት መያዙን፥ እመቤት መሆኑን ነው የማትችይው? »

«እንዴት አድርጌ ብነግርዎ ችግሬን እንደሚረዱልኝ አላውቅም፥ አባባ። በቅላ ስናገረው እንኩዋንስ ሌላ ሰው እኔን ራሴንም አያስረዳ። ብቻ ከተወለድሁበት መንደርና ካካባቢ በቀር፥ ሌላ አለም መኖሩን አላውቅ ልጅቱ ልጅ አዝዬ፥ ‹ሊደርስ የሚችለው ክፉ ነገር ይድረስብኝ› ብዬ፥ ስሙን እንኩዋ ሰምቼው እማላውቀው ነገር አዲስ አበባ ድረስ ከጎጃም የተሰደድሁ ከባል ሽሽቼ መሆኑ ከሚያስፈራው ነገር ሁሉ ባል የምፈራ መሆኔን ሊያስረዳ ይችል ይሆናል።»

«ከባልሽ ሽሽተሽ መምጣትሽን ነግረሽኛል። ነገር ግን አንድ ባል ስለ ተጣላ፥ ባል ሁሉ ሊጠላ አይኖርም፥ ልጄ! »

«እንጃ! ለኔ ባል ሲባል ያው፥ እኔ የማውቀው ሞትን የሚያስመርጠው መስሎ ነው የሚታዬኝ! እንኩዋንስ ባል፥ ስለ ወዳጅ ፍቅር ሴቶች የሚያስወሩት ሁሉ እውነት አይመስለኝም። እስከ ዛሬ የገጠመኝ ሁሉ ሲያወሩ እንደምሰማው ሳይሆን ያው - ዱሮ እንደማውቀው ጉሮሮ እያነቀ፣ እጅ እዬጠመዘዘ ጠጉር እዬጨመደደ የሚያሰቃይ ወንድ ነው። እዚህ ግቢ አምስት አመት ስኖር ያሳለፍሁትን ጭንቅ ስለሚያውቁት ለርስዎ መንገር አያስፈልገኝም። ስለዚህ - ለባል ገና ልቤ አልሻረምና የማይቀየሙኝ ከሆነ ቢቀር ይሻላል፥ አባባ።»

«እኔስ ልቀየምም። ብቻ አንቺ ገና ምኑንም ሳታውቂ በልጅነትሽ ክፉ አጋጣሚ ስለ ደረሰብሽ ‹ክፉ አጋጣሚ አይጠሉትን አስጠልቶ ይቀራል› እንደሚሉት ሁልጊዜ ያው መስሎሽ የወንድ ጉዋደኝነት ጠልተሽ እንዳትቀሪ ነው የምመክርሽ። የኛ ቤት ጎረምሶች ያስቸግሩሽ የነበረውንም ከቁም ነገር አለመጣፍ ነው። እነሱ አእምሮ የሌላቸው ወጠጤዎች ናቸው» አሉ አዛዥ ቅር ያለው ፊታቸውን ቀና አድርገው ጣራውን እዬተመለከተኡ።

«ይቅርታ ያድርጉልኝ አባባ» አለች ደመቀች አንገትዋን ደፍታ ስታስብ ቆይታ። «ይቅርታ ያድርጉልኝ። ‹የሰው ነውር መግለጽ አይገባም› ብዬ ለስዎ እንኩዋ ላባቴ ሳልገልጽልዎ የቆየሁት ነገር ነበር። አሁን ግን ‹ፈቃድዎን እፈጽማለሁ› ብዬ ከማልሁልዎ በሁዋላ የተቸገርሁበትን ምክንያት ተረድተው ምህረት እንዲያደርጉልኝ ያን ሸሽጌው የነበረውን ነገር መናገር አለብኝ። አቶ ካሳሁን አብጤን የማላውቃቸው ለመምሰል የሞከርሁ ሳብል ነው፤ ድህና አድርጌ አውቃቸዋለሁ። ‹የኛ ቤት ጎረምሶች› ካሉዋቸው የባሱ ክፉ ሰው ናቸው። እሜቴ የላኩላቸውን ምሳ ይዤ እቤታቸው ብሄድ ‹በግድ ካልደፈርሁሽ› ብለው ያደረሱብኝ ስቃይ እስከ ዛሬ ከማንም ደርሶብኝ አያውቅ! በግድ ፈቃዳቸውን ሊያስፈጽሙኝ እንዳልቻሉ ሲያውቁ ክንዴን ጠምዘው ወርውረው፥ እወለሉ ላይ ሲጥሉ› እዚህ እማጠፊያዬ ላይ ተናግቶ ብዙ፥ ቀን ስራ አላሰራኝ ብሎ ነበር» አለች፥ ተናግቶ የነበረውን ማጠፊያዋን ላዛዥ እያሳዬች። «ስለዚህ አቶ ካሳሁን ለስዎ እንደሚመስሉዎ፥ ደግ ጭዋም አደሉም።»

«አቶ ካሳሁን እንዲህ አደረገሽ? አንቺን? አሉ አዛዥ መከዳቸውን ተደግፈው ከተጋደሙበት ተቆጥተው አይኖቻቸውን፥ በጥፍ አውጥተው ተነስተ ቁጭ ሲሉ።

«እባክዎ አይቆጡ፥ አባባ! እስከ ዛሬ ድረስ ለማንም ተንፍሸው የማላውቀውን ዛሬ የነገርሁዎ ‹ከፈቃዴ ወጣሽ› በለው እንዳያዝኑብኝ ነው እንጂ እንዲቆጡ አይደለም።»

«ታዲያ ባንቺ፥ በልጄ ላይ እንዲህ ያለ የባለጌ ስራ ከሰራ በሁዋላ እንዴት ቢደፍረኝ ነው - » ብለው ሳይጨርሱ፥ በር በሀይል ተመታና ደመቀች ቶሎ ተነስታ ለማየት ሄደች። አዝማሪው ውቤ ነበር። ስተከፍትለት ገብቶ ለስዋም፥ ለዛዥም ሰላምታ፥ ከሰጠ በሁዋላ፥

«ምን ሆኑ? » አለ አዛዥን አለወትሮዋቸው አልጋቸው ላይ ቁጭ ብለው ስላያቸው።

«ደህና ነኝ፤ መድህኒት ቀምሼ ነው» አሉ አዛዥ።

«ያስቀምጥዎ ያሽርዎ» አለ ለመቀምጥ ወንበር ወዳለበት እያመራ።

«አሜን» አሉ አዛዥ። ከደመቀች ጋር ሲነጋገሩ በቆዩበት ጉዳይ ስሜታቸው ገና እንደ ታወከ ስለ ነበረ አዝማሪው ውቤን እንደ ድሮው በፈገግታ አልተቀበሉትም። ደመቀችም ቅር ያላት ላለመምሰል ፊትዋ ተቋዋጠረ ጥርስዋ ብቻ በግድ ተገልጦ የሚያሳዬው ፈገግታ ከተቋዋጠረ ፊትዋ ጋር አልስማማ ብሎ እንደ ተውሶ ልብስ አላማረባትም።

«ምን ሆናችሁዋል? ተጣልታችሁ ኖሮዋል? ሁለታችሁም የኮረፋችሁ ትመስላላችሁ» አለ አዝማሪው፥ ወንበር ሳብ አድርጎ ሲቀመጥ።

«ኧረ ደህና ነን! ደሞ እኛን ምን የሚያጣላን ነገር ይኖራል? » አሉ አዛዥ። ደመቀች ምንም ሳትመስል በፊት ለፊቱ ተቀመጠች።

«እ እ፥ አልመስለኝም አልመሰለኝ.... ም፥ ተኩዋርፋችሁዋል! » አለና ኩርፊያውን ለማባረር እንደ አንዲር በሚዝገመገም ወፍራም ድምጽ ያቆረቆረው ጀመር።

«ኩርፊያ ምናባቱ ይሂድ ወዲያ ይውጣ፥

መሰንቆውን ይዞ አዝማሪው ሲመጣ።

የኩርፊያ በሽታ ሲገባ በቤቱ፥

ያዝማሪው ዘፈን ነው ፍቱን መድህኒቱ።

ፍቅር ባለበት ቤት ሲገባ ቅርታ፥

የተቋዋጠረ ልብ አዝንናቶ እሚፈታ፥

ፍቱን መድህኒት ነው ያዝማሪው ጭዋታ።

ደመቀችና አዛዥ ኩርፊያችሁን እርሱ፥

ዛሬ ነው የኛ ቀን እንጨፍር ተነሱ፥

ነገሜ ነገ ነው የሚያስብ ለራሱ «አለና ዘፈኑን ሲጨርስ፥

«በሉ ተነሱኮ! » አለ እሱ ከተቀመጠበት ተነስቶ አዛዥን አንስቶ ሊያስጨፍር ወደ ተገደሙበት ጆቹን ዘርግቶ እዬሄደ።

«ተው እዚያው ሁን አንተ፥ ከይዚ! » አሉ አዛዥ ከልባቸው እዬሳቁ፥ እሳቸውም ለመከላከል እጆቻቸውን ወደሱ፥ ዘርግተው። ከዚያ እወንትም አዛዥንና ደመቀችን ቅር አሰኝቶዋቸው የነበረው ነገር ለጊዜው ተረሳና ሁሉም ይስቁ ጀመር።

«ያ ሌባ መሰንበቻውን ወዲህ አልመጣም? » አለ አዝማሪው ውቤ ከሳቅ በሁዋላ ወደ ወንበሩ ተመልሶ ሲቀመጥ።

«የምን ሌባ ልጄ! » አሉ አዛዥ።

«ያ በሻህ።»

«እ! አንድ ቀን እዚህ በስድብ አስመርረህ ከሰደድኸው በሁዋላ ጭራሽ ብቅ ብሎ አያውቅም። እኔስ ያነለት እንዲያ ስትሰዳደቡ ትጣላላችሁ ብዬ ፈርቼ ነበር።»

«አንጣላም፥ በጣም ወዳጄ ነው፤ ያልተሰደደብን እንደሆነ ነው የምንጣላ» አለ እንደ መሳቅ ብሎ «ይልቅ» አለ ቀጠለና። «ይልቅ አሁን ጠፍቶኝ ተቸግሬያለሁ። ያነለት፥ ከዚህ እንደ ወጣን፥ በደመቀች ላይ በተሰራው ግፍ ተበሳጭቶ መንገደኛው ሁሉ እዬሰማ የፖሊሱን ሹምም እዚህ የናንተን እመቤትም ስም እዬጠራ መሳደብ ስለ ጀመረ ‹ተው አይገባም› ብለው በኔም ተቆጥቶ ሄድሁ ብጠይቅ ‹አዬነው› የሚለኝ ሳጣ ጊዜ ‹ምናልባት - ደህና ባይሆን ይሆን?› ብዬ ሰጋሁ።»

«ቤት የለውም? እቤቱ መጠዬቅ ነበራ! »

«ዱሮ ሚስትም፥ ደህና ቤትም ነበረው። አሁን፥ እዚያ - አቶ ማንደፍሮ ግቢ ብቻውን ባንድ ክፍል ውስጥ ነው የሚኖር። ታዲያ በሌለበት፥ የሄደበትን ሆነ ብሎ ካልተናገረ የሚያቅ የለም።»

«ከከተማው ቢወጣ ይሆናል፤ ክፉ ነገር ቢደርስበት ኖሮ፥ መቸም የክፉ ነገር ወሬው አይሰወር፤ ይሰማ ነበር! »

«ክፉ አይድረስበት እንጂ ሌላውስ ቢሻው! በሻህን ቢለምዱት ይወዱታል፥ በጣም ጥሩ ሰው ነው፥ አባባ አዛዥ። ለዚህ ነው፥ የደመቁን ልጅ ልብስ የገዛችሁ እለት

አብራችሁ መዋላችሁንና ምሳ አብራችሁ መብላታችሁን ስለ ነገረኝ በቅጡ፥ እንድትተዋወቁ ደመቁ፥ መታሰርዋን እንደ ሰማሁ ይዤው የመጣሁ! »

«በጣም አንተዋወቅም ለመጀመርያ ጊዜ የተገናኘን አሁን እንዳልኸው ደመቀች ለልጅዋ፥ የተማሪ ቤት እቃ ስትገዛ ነው። ያነለት የደከመልን ድካምና ያደረገልነን ርዳታ እንኩዋንስ ለማይታወቁ እንግዶች ለብዙ ቀን ወዳጆች የሚያደርጉት ጥቂት ናቸው። ስለዚህ - እንዴት እግዜር የባረከው ሰው ቢሆን ነው?› እያልን ደመቁም እኔም ስንገረም ነበር! ብቻ - ያነለት እዚህ ስትከራከሩ ወንጀለኞችን እያሞገሱ ሲናገር ሰምቼ ግራ ገባኝ። መቸም ያነለት አንተ እንዳልኸው እውነት የወንጀለኞች አለቃ ከሆነ በጎ ቢሰራም ከፉ ነው! »

«የወንጀለኞች አለቃ ነበር እንጂ አሁንኮ አደለም።»

«አዬህ ልጄ ሌብነትንና ቅሚያን የመስለ የወንጀል ስራ ከፉ ሱስ ነው! እንዲህ ያለውን የወንጀል ስራ የለመዱ ሰዎች እንኩዋንስ ሲቸግራቸው ባይቸግራቸውም አጋጣሚ ካገኙ ይመለሱበታል። አስቀድሞ ሌብነትም ሆነ ቅሚያ ከፉ ስራ መሆኑን አውቆ አለመልመዱ፥ ከሱ መራቅ ነው ደጉ።»

«በሻህኮ ሌብነትም ይሁን ቅሚያ ወይም እነሱን የመሳሰሉ የወንጀል ስራዎች፥ ከፉ መሆናቸውን ደህና አድርጎ የሚያውቅ በጣም የተማረና - ምን ልበልዎ? ሊቅ ነው! እሱ እንደሚለው የወንጀል ስራ ሰለሚጠላ፣ ወንጀልን ለመቃወምና ለማጥፋት ነበር፥ የወንጀለኞች አለቃ የሆነ። ‹ትንሽ እሾህ በትልቅ እሾህ ይወጣል› እንደሚሉት ‹ወንጀልን ለማጥፋት በወንጀለኞች ላይ ከነሱ የበለጡ ሀይለኞች ሊኖሩ ያስፈልጋል› ብሎ ያምን ነበር። ብቻ የማይሆንለት መሆኑን ከተረዳ በሁዋላ ሁሉንም ጥሎ ወጣ።»

«ዱሮውንም የማይመስል ነገር ነው እንጂ! ወንጀል እዬሰራ፥ ‹ወንጀል እጠላልሁ፥ ወንጀል አጠፋለሁ› የሚልህን ሰው ታምነዋለህ? ይህ እንዲያው - ትርጉም የሌለው ከንቱ፥ ነገር ነው።»

«ትርጉም የሌለው እንኩዋ አደለም አባባ አዛዥ! »

«እንዴት? አንተም የሱ ግርፍ ነህ መሰለኝ! »

«አደለሁም፡ ብቻ አማኙና ተከታዩ ባልሆንም የሚለው ትርጉም ያለው መሆኑን አምናለሁ። በሻህ እንደሚለው ሌብነት፥ ቅሚያ ማጅራት መምታትና እነሱን

የመሳሰሉትን ግልጽ ወንጀሎች፥ ሀብትና ጉልበት ከሚሰጡት መብት ከክፉ የማህበር ስራት ካድላዊ ህግ፥ ከግፈኛ ስልጣንና እነዚህ ከመሰሉት በልዩ ልዩ ህጋዊ ስም ከተሸሸጉት ክፉ ስራዎች የሚወለዱ የነሱ ልጆች ናቸው። እነዚህ በልዩ ልዩ ህጋዊ ስም የተሸሸጉ ክፉ ስራዎች ወይም ወንጀለኞች ባይኖሩ ኖሮ ግልጽ ወንጀሎችም ባልነበሩ! ስለዚህ ግልጽ ወንጀሎችን ለማጥፋት እነሱኑ ማለት ግልጽ ወንጀሎችን መሳሪያ አድርጎ ወላጆቻቸውን፥ የተሸሸጉትን ወንጀሎች መቃወምና ማጥፋት ያስፈልጋል! ወይም በሌላ አነጋገር፥ ለምሳሌ በሀብታቸውና በጉልበታቸው አስፈራርተው ወይም አባብለው የድሆችን ጥቅምና መብት የሚቀሙት ሰዎች እንዲህ ላለው ክፉ ሥራ መሳሪያቸው የሆነውን ሀብት የተቀሙ ወይም የተሰረቁ እንደሆነ የተበደለ ሊያስክስ፥ የተቀማ ሊያስመልስ በዳኝነት ወንበር የተቀመጠ ዳኛ ፍትህን፥ የተቀማ ወይም የተሰረቀ እንደሆነ የህዝብ ጉዳይ ሊያስተዳደር ስልጣን የተቀበለ የመንግስት ሹም ወይም ሰራተኛ ያን ስልጣን ለሰው ማጥቂያና ለግል ጥቅም መጠበቂያ ማድረጉ ሲረጋገጥ አናቱን ወይም ማጅራቱን ‹ቂው› ያደረጉት እንደሆነ እንዲያ ያለ ቅጣት የደረሰበት ደግሞ እንዳይደርስበት ያልደረሰበት እንዳይደርስበት ይፈራና፥ ሁሉም በህጋዊ ስምና መልክ ተሸሽጎ የሚሰራውን ሸሽግ ወንጀል ከመስራት ይታገዳል። በዚህ መንገድ በህግ ስም የሚፈጸመው ወንጀል ሁሉ ሲጠፋ ፍትህ ይገኝና ግፍ ይጠፋና ሁሉም፥ ለነጻ ህዝብ ከሚገባው ጥቅምና መብት ድርሻ ድርሻውን ያገኝና ከዚያ በሁዋላ ሌብነት ቅሚያ፥ ማጅራት መምታት ሁሉም አውቀው ይጠፋሉ! ይዩትልዎ! በዚህ ዘዴ ወንጀልን ለማጥፋት ነበር በሻህ የወንጀለኞች ጠቅላይ መሪ የሆነ! » አለ አዝማሪው ውቤ የበሻህን አሳብ እንደ መሰለው ተርጉሞና በቀልድ ቀለም ኩዋኩሎ ላዛዥ ሲተርክ እንደ መሳቅ ብሎ።

«እባክህ ይህ ያልከው ሁሉ እውነት ነው፥ ወይስ ተረት? » አሉ አዛዥ ያን ተረት እንጂ እውነት የማይመስል ታሪክ ዝም ብለው ሲሰሙ ቆይተው።

«የምን ተረት! እውነት ነው እንጂ! »

«እ - ሺ እስቲ! ታዲያስ? » አሉ አዛዥ ‹እውነት ነው› ብለው ባያምኑም የታሪኩን መጨረሻ መስማት ስለ ፈለጉ።

«ታዲያማ - በህግ አጥር ውስጥ ተሸሽገው ክፉ ስራ ለሚሰሩት ወንጀለኞች መቅጫ ህግ ወጣ! አዲስ አበባ ባራት ይሁን በስንት ክፍል ተከፍላ፣ ለያንዳንዱ ክፍል፥ አንድ የቀጪ ቡድን አለቃ ተሾመ! ቅጣት በያይነቱና በዬደረጃው የተፈረደባቸው ሰዎች

ዝርዝር ተሰናድቶ ፍርዱን በዬክፍላቸው ለሚያስፈጽሙ አለቆች ዝርዝር ተሰናድቶ ፍርዱን በዬክፍላቸው ለሚያስፈጽሙ አለቆች ተሰጠ። መቸስ - ድርጅቱና ያሰራሩ ዘዴ የሚያስገርም ነበር! »

«ትቀልድብኛለህ መሰለኝ! » አሉ አዛዥ አዝማሪው ሲያወራ ያሽሙር ፈገግታ በፊቱ ይታይ ስለ ነበረ።

«ልሙትልዎ እውነቱን ነው። ቀንሼለት እንደሆነ እንጂ አልጨመርሁበትም።»

«ታዲያ ይህ ሁሉ ሲሆን ቦሊሶች ሊያገኙት አልቻሉም? »

«በጭራሽ! ያውም ውሎው ከነሱ ጋር ነበር፤ ብቻ አያውቁትም። በድርጅቱ ውስጥ ላሉት ሁሉ ጠቅላይ መሪ ሆኖ እያንዳንዳቸው የመማሩበትን ደንብ እዬሰራ ሲሰጥ ከዋናቹ አለቆች በቀር እንኩዋንስ ፖሊሶች ሌሎች ጭፍሮቹ አያውቁትም፤ ‹የጨለማዉ ንጉስ› የሚባል ሀይለኛ መሪ እንዳላቸው ብቻ ነበር የሚያቁ! »

«አህ፥ ቆዩኝ እስቲ! ያ - ‹የጨለማ ንጉስ› የሚባለው ሌሊት ሌሊት ሙብራትና ስልክ እዬቆረጠ አዳሜን ሁሉ የከተማውን ሰው ሁሉ ቦሊሱን ሳይቀር ሲያስጨንቀው፥ የንሽርት ውሀውን ሲያስፈስሰው የነበረ፥ ይህ በሻህ ነው ልትለኝ ነው? » አሉ አዛዥ፥ ተገርመው፥ ‹ይህ በሻህ› ሲሉ አዝማሪው በሻህ እንደ ሆነ ሁሉ አገጫቸውን ወደሱ አሹለው።

«ይህ እብሻህ! » አለ አዝማሪዉ፥ እዙም አገጩን ወደ ሳቸው አሹሎ እዬሳቀ።

«ይገርማል! እውነትም አንድ እቅን እንዳልሽው፥ ሰው አደለም ሰይጣን ነው! »

«ስቀልድበት ነው እንጂ፥ በሻህ ሰይጣን አደለም፤ ትልቅ ሰው ነው አባባ። እንደ በሻህ ያለ ትልቅ ሰው ብዙ አይገኝም። በጠላት ወረራ ጊዜ ያራዳን ወሮበሎች በደንብ አደራጅቶ በውስጥ አርበኝነት ጣሊያኖችንና ኢትዮጵያውያን ሰላዮቻቸውን እዬገደለ፥ የመሳሪያ ማከማቻቸውን እያቃጠለ፥ የሙብራት፥ የውሀና፥ የስልክ መስመራቸውን እያበላሸ ሲያስጨንቃቸው ብዙ ጊዜ ቆይቶ ደርሰውበት ሊይዙት ሲሉ አምልጠዋቸው ጫካ ካርበኞች ጋር ተጨመረ። እዚያ ባርበኝነት ደግሞ ወሮበሎች ጭፍሮቹን እዬመራ ይሰራው የነበረውን የጀብድ ስራ አብረው የነበሩ አርበኞች ሲተርኩት ቢሰሙ ይገረማሉ! በሻህ ከጭፍሮቹ ጋር በተሰለፈበት ግንባር ሁሉ ጠላትን ድል እየመታ፥ መሳሪያውን ማርኮ መመለሱ አንድ ቀን የማስይስ የተለመደ በመሆኑ ካርበኞች ጋር

የነበረ ገጣሚ ‹ገጠመለት› ብለው ከነገሩኝ የማስታወሳቸውን ሁለቱን ብቻ ልንገራችሁ።

1 ያው መጣ እዚያ ማዶ ባንድ፥ ሲግበሰበስ፥

መድፉን መትረየሱን፥ አስጭኖ ባጋሰስ፥

ንገሩት ለበሻህ እንዲያ እንደ ልማዱ፥ ተረከቦት ይመለስ›

ብሎ አዝማሪው ሁለተኛውን ሊቀጥል ሲል፥

«እሰይ ልጄ! እግዜር ይባርከው! » አሉ አዛዥ ሲቃ ይዞዋቸው ከተጋደሙበት ተነስተው ቁጭ አሉና። አዝማሪው ውቤና ደመቀች ያዛዥን ሁኔታ አይተው ይስቁ ጀመር።

‹2 ያው ፋሽስት መጣ መሳሪያውን ጭኖ እያጤሰ አጉዋራ

ወርደህ ተረከበው በሹ እንደ ልማድህ ከጭፍሮችህ ጋራ የሚል ነበር፥ ሁለተኛው ግጥም። «በዚያ ላይ» አለ አዝማሪው ቀጠለና። «በዚያ ላይ በሻህ ግፍ የማይወድ ደግ አዋቂ ያለውን ራሱ ጦም አድሮ ለሌላው መስጠት የሚወድ ቸር ነው።»

«አሁን ያልኸውን ሁሉ መሆኑን ነው እንጂ የማናውቅ ደግነቱንስ ደመቀችና እኔም አይተን አድንቀናል። አድን ቀን እንኩዋ አይቶን ለማያውቅ እንግዶች ስንቸገር ስላዩ ብቻ እኛን ለመርዳት ቀኑን ሙሉ ይዞት ሱቅ ለሱቅ ያን ያክል ሲንከራተት መዋሉ አስገርሞን ‹ምን አይነት ሰው ነው?› እያልን እስዋን እኔ ስንነጋገር ነበር። እንዲህ ያለ ሰው መሆኑን ሳናውቅ ስላገለግሎቱ ‹አንድ ብር እንስጠው፥ ወይስ እንጨምርለት?› እያልን ደመቁና እኔ ስንከራከር ነበር «አሉ አዛዥ እዬሳቀ። ደመቀችም ክርክራቸው ትዝ አላትና ትስቅ ጀመር።

«ያ - ‹የመንግስት ሹሞች ለመቅጣት አቆቁዋመው› ያልኸው ድርጅት መጨረሻው ምን እንደ ሆነ አልነገርኸንምኮ» አሉ አዛዥ ሁሉም ትንሽ ዝም ብሎ ከቆዩ በሁዋላ።

«እ - ! እሱማ ቅጣቱንስ ለመፈሰም የተመደቡት ሰራተኞች በተለይ እታች ያሉት አላማቸው፥ ቀምቶ ይሁን ሰርቆ ወይም ማጅራት መትቶ ገንዘብ ማግኘት ብቻ ሆነና እንዲቀጡ ከተፈረደባቸው ሹሞች ባንዳቸውም ፍርድ ሳይፈጸም ቤት ንብረታቸው የሚዘረፍና ማጅራታቸውን እዬተመቱ ወድቀው የሚገኙት ሀብት ስላላቸው ብቻ

ያልተፈረደባቸው ንጹሆች ሆኑ። እንዲያ ያለውን ክፉ ስራ ታጥቀው የቆሙ ሆኑና እንዳልተሳካለት ተረዳ። ስለዚህ ተስፋ ቆርጦ ሁሉንም ትቶ ሲወጣ፥ እሱ ያቆቁዋመው ድርጅትም ፈረሰ።»

«ታዲያ አሁን - እሱ ትቶ ቢወጣስ - መቸም ሰዎችን ይዞ አልወጣ፤ ቀማኞችና ሌሎች ወንጀለኞች ዛሬም አሉ፤ ከነሱ ጋር ግንኙነት የለውም ይመስልሀል? »

«ግንኙነት ማለት በስራቸው መተባበር እንደሆነ ጭራሽ የለውም። ብቻ ፊት ላቆቁዋመው ድርጅት ከሱ ጋር የመምሪያው አላፊዎች አድርጎዋቸው የነበሩትንና በዚያው ስራቸው የቀጠሉትን መቸም ስለሚተዋወቁ የሚሰሩትን ቢያይ እንኩዋ የሚያጋልጣቸው አይመስለኝም። እንዲያውም አንዳንድ ከመንገዳቸው ወጥተው በሰው አፍ ላይ ግፍ የሚሰሩ ሲያይ፥ ሳይነግራቸው የሚቀር አይመስለኝም። ይህን የምልበት ለምሳሌ በቀደም እዚህ ስንጫቃጨቅ እንደ ሰሙት የኔ አለቃ የነበሩት አለቃ መዝሙር በኔ የሰሩትን ግፍ ካወቀ በሁዋላ፥ ላንዳንዶቹ፥ ነግሮዋቸው ነው - በርስታቸው ከሚኖሩት ጢሰኞች የሰበሰቡትን ገንዘብ አሸክመው ሲመጡ ቀምተው - ለኔም ያካፈሉኝ።»

«ይገርማል! » አሉ አዛዥ ሁሉም ትንሽ ዝም ብለው ቆይተው። «ደመቁ፥ በሻህ የልጅሽን ልብስ የገዛልን እለት አብረን ምሳችነን እዬበላን ጣሊያኖች በኢትዮጵያውያኖች ላይ ይሰሩት ስለ ነበረው ግፍ ሲያጭውተን፥ ‹ያንጊዜ አንተ ምን ትሰራ ነበር?› ብዬ ስጠይቀው ስራ ምን እንደ ነበረ የነገረንን ታስታውሻለሽ? »

ደመቀች አዎታዋን በራስዋ ምልክት አሳዬች።

«ያነለት ጣሊያኖች ኢትዮጵያኖችን ያደርጉዋቸው የነበረውን ሁሉ ሲያጭውተን ‹ያንጊዜ ምን ትሰራ ነበር?› ብዬ ብጠይቀው፥ መጀመሪያ የጣሊያን አሽከር ከዚያ በዬተራ ጫማ ጠራጊና ወሮበላ የነበረ መሆኑን ይህን - ትንሽ ትንሹንና ክፉ ክፉውን ነው እንጂ የነገረን የውስጥ አርበኛና አርበኛ ሆኖ ስለ ሰራው ወይም አሁን አንተ ከነገርኸን የሚያስገርም ነገር ሁሉ ስላንዱ ጨርሶ አላነሳ! ሌሎች ይናገሩለታል እንጂ እሱ አይናገረውም! » አሉ አዛዥ ከልባቸው እዬተገረሙ። ደመቀችም አዝማሪው ውቤን ተቀይማው ስለ ነበረ ስሜትዋ በቃል አልገለጸችም እንጂ ስለ በሻህ የተረከው ታሪክ በዚያ በተጎሳቆለ ሰውነቱና በትህትናው ውስጥ ትልቅነቱን በጨካኝ ማጅራት መቺ ስሙ ውስጥ ሰባዊ ርህራሄ ያለው ደግ መሆኑን ባይነ ህሊናዋ ፊት አስቀምጦ

እያሳያት ልብዋ ተማርኮ ዝም ብላ በውስጥዋ ታደንቅ ነበር! ነገር ግን አዝማሪው ውቤ ስትጠይቀው ‹ረሳሁት› ስለሚላት ለችግርዋም፥ ለልመናዋም ዋጋ ያልሰጠ መስሎ ስለ ተሰማት ልብዋ ተቀይሞ፥ ያነለት ሲገባ ሰላምታ ሰጥታው በፊት በፊቱ ተቀምጣ ካዛዥ ጋር ሲጫወቱ ዝም ብላ ከመስማትና የሚያስቅ ነገር ሲናገር ወይም ሲያደርግ ከመሳቅ በቀር አንድ ቃል አልተነፈሰችም።

«አዎ ስለ መልካም ስራው እንኩዋንስ እሱ ሊያነሳ ሌላ ሰው ሲያነሳባት አይወድም። ዛሬ የነገርኩዋችሁን እንዳትነግሩት አደራ፥ ይጣላኛል። እስቲ እንግዲህ ልሂድና ልፈልገው። ድንገት የመጣ እንደሆነ የምፈልገው መሆኔን ንገሩልኝ» አለ አዝማሪው ሲነሳ። ከዚያ ላዛዥም ለደመቀችም የጅ ሰላምታ ሰጥቶ ሊወጣ እበር ከደረሰ በሁዋላ፥ «አየ አየ የኔ ነገር! የመጣሁለትን አይነተኛ ነገርኮ ረስቸ ልሄድ! ደመቀች» አለ እንደገና ተመልሶ።

«አቤት» አለች ደመቀችም ወደ ወይዘሮ ጌጤ ለመሄድ መንገድ ከጀመረች በሁዋላ እንደገና መለስ ብላ።

«የምትወጅው መሆኑን እንጃ እንጂ ስራ አግኝቼልሽ ነበር» አለ መቀየምዋን ስላላወቀ እንደ ሁልጊዜው ፈገግ ብሎ።

«ምን ስራ? » አለች ደመቀች መርዶ ያረዳት ይመስል ደንግጣ።

«ምን አይነት ስራ? » አሉ አዛዥም ከስዋ ተቀብለው፥ ከተጋደሙበት ቀና አሉና።

«ፍል ውሀ ሀኪም ቤት የጽዳት ስራ። የወር ደመወዙ ሀያ አስምት ብር ነው። ‹ይስማማኛል› የምትህ የሆንሽ እንደሆነ ነገ ጥዋት ይገቺሽ እሄዳለሁ፤ መቸም እኔ ደህና መስሎኛል። ቅዳሜ ቀኑን ሙሉ የማትስሪ ከመሆንሽ ሌላ በተረፉት ቀኖችም ግማሽ ቀን ብቻ ነው የምትሰሪ።»

አዝማሪው ውቤ የስራውን አይነት ሲዘረዝር ድንጋጤዋ አልፎ ደስታ ቅያሚዋን አባሮ በደረትዋ ውስጥ ዳንኪራ ያስመታው ጀመር። ደስታዋን የምትገልጽበትም ሆነ እሱን የምታመሰግንበት ቃል አጥታ ከንፈሮችዋ እዬተንቀጠቀጡ፥ አይኖችዋ አፎቻቸውን በመላው የደስታ እንባ እዬዋጉ ዝም ብላ ስታየው ቆየችና፥

«ጋሽ እባክህ ማረኝ፥ ተቀይሜህ ነበር! » አለች አይኖችዋን በጅጌዋ እዬጠራረገች።

«ለምን፥ እባክሽን? » አለ አዝማሪው ውቤ።

«በዬጊዜው ስጠይቅህ ‹ረሳሁ› ስትለኝ ጊዜ ‹ችግሬን ከጉዳይ ባትጥፈው ነው› ብዬ እንጃ - ሆድ ሲብሰኝ ጊዜ ነው መሰለኝ - ተቀይሜህ ነበር»

«እግዜር ይስጥልኝ፤ ይህስ ይቅርታ የሚያስለምንም አደል፥ ለኔ ትልቅ ክብር ስለሆነ እንዲያውም የሚያኮራኝ ነው! » አለ አዝማሪው ባሽሙር ፈገግ ብሎ።

«ምኑ? »

«በቁምነገራም ሰዎች ተራ ገብቼ የሚታዘንብኝ መሆኔ ትልቅ ክብር ነው! »

«እባክህ አትቀልድ ምን ያክል ውለታ እንደ ዋልህልኝ ለኔ እንጂ ላንተ አይሰማህ ይሆናል! በጣም ነው ጨንቆኝ የነበር። ከጭንቅ እንዳወጣኸኝ እግዚአብሔር ጭንቅ አያሳይህ! »

«ጭንቅ አያሳይ? ይግረምሽና ጭንቁን ማሳዬት ብቻ ሳይሆን እጅ እጅ እስኪለኝ አጥግቦኛል! » አለ አዝማሪው ፈገግ እንዳለ።

«ትልቅ ስራ ነው የሰራኸው እግዚአብሄር ይባርክህ ልጄ! » አሉ አዛዥም።

## ምእራፍ ሀያ ሁለት

# የማይበላ ካሳ

ደመቀች፥ ካገርዋ ከመጣች ጀምራ አምስት አመት የወይዘሮ ጽጌ ገርድ ሆና ስትኖር መጀመሪያ በወር አምስት ብር ከዚያ ሰባት ብር ታገኝ የነበረችው ፍል ውሀ ሀኪም ቤት የጽዳት ስራ ለምስራት በወር ሀያ አምስት በር በመቀጠርዋ ባንድ ጊዜ ከድህነት ወጥታ በሀብታሞች ተራ የገባች መስሎ ስለ ታያት በጣም ደስ አላት።

በሁዋላ ብቻ እያደር፥ ለቤት ክራይ ለዱቄት፥ ስጋ፥ ቢቀር ለክክ፥ ቅቤ ቢቀር ዘይት፥ ኤሌክትሪክ ቢቀር ለኩራዝ ለቅመማ ቅመም ለማገዶ ለውሀና ይህን ለመሳሰለው

ለዝቅተኛ ኑሮ አስፈላጊ ለሆነው ጥርቃሚ ነገር ሁሉ የሚያስፈልገውን ወጪ ስታስበው ጊዜ ከሀያ አምስቱ ብር የሚተርፈው ወይዘሮ ጽጌ ይህን ሁሉ ችለው ይሰጥዋት ከነበረው ሰባት ብር ቢያንስ እንጂ የማይበልጥ ሆኖ አገኘችውና በደስታ ሞቆ የነበረው ስሜትዋ በቅራታ ቀዝቀዝ ማለት ጀመረ።

ቤት ተከራይታ ለብቻዋ መቀመጥ ስታስብ ከወጪው፥ መክበድም የባሰ የሚያስፈራ ነገር ታያት። የልጅ አባትዋ ታምራት ተገኝ አዲስ አበባን በጋ በጋ ቢያንስ አንድ ጊዜ ሳይረግጠው፥ እንደማይቀር የታወቀ ስለሆነ ምናልባት ጠይቆ፥ ቤትዋን ያገኘው እንደሆነ አንቆ እንደሚወስዳት አይጠረጠርም። እሱ እንኳዋ አምስት አመት ሙሉ ፈልጎ ስላጣት ተስፋ ቆርጦ ረስቷት እንደሆነ የከተማዉ ሴት አዳኝ ሁሉ ብቻዋን በባዶ ቤት ሲያገኛት እንዳይምራት የታወቀ ነው! ለደመቀች እስከ ብዙ ጊዜ ድረስ ወንድ ሲባል ከታምራት ተገኘ የተለዩ የወንድና የሴት ግንኙነት ሲባል በሱና በስዋ መሀከል ከነበረው ግንኙነት የተለዩ እምስሎ አይታያትም ነበር። ስለዚህ ይህን ሁሉ ስታስብ ከስምንት አመት በፊት ታምራት ተገኘ በጫጉላ ቤት ብቻዋን ይዞ በፈጣሪ አምላክና በተፈጠሩ ቅዱሳን ሁሉ እያማጠነችው እያወገዘች እንደ ተራብ የዱር አውሬ በጽኑ ጉምዥት ሰውነትዋን ያብጠለጠለው ትዝ አላትና ያን ጊዜ ታምራት ተገኘም፥ ሴት አዳኙ ወንድ ሁሉም ባንድ ላይ ተሰብስበው የሚቀራመትዋት መስልዋት ብርቱ ርእድ እልብዋ ውስጥ ገብቶ ያንቀጥቅጣት ጀመር። ስለዚህ ብትጮህ አዛዥ ሰምተው እንዲደርሱላት ባጠገባቸው የሚከራይ ቤት ካላገኘች ምን ማድረግ እንደምትችል ቅጡ ጠፋት። አዛዥን ያማከረቻቸው እንደሆነም አብራቸው እንድትቀመጥ የሚጠይቅዋት መሆናቸውን በርግጥ ስለምታውቁ ጥያቄያቸውን ብትቀበል፥ የምትከብዳቸው፥ ባትቀበል የምታሳዝናቸው መሰላትና እጅግ ተቸገረች። ብቻ ሁልጊዜም ቢሆን ሲጨንቃት ዙርያው ጨለማ ሲሆንባት መንገድ መሪዋ አዛዥ ስለሆኑ መጠዬቅ ነበረባት።

«አባባ ለከፋውም ይሁን ለደጉ፥ ካጠገብዎ መራቅ አልፈለገም፤ ስለዚህ በጎረቤት አንድ ትንሽ ቤት የሚያከራይ ሰው ያውቃሉ? » አለች አዛዥም እስዋም ወደ ስራቸው ለመሄድ ቀደም ብለው ተነስተው ቡና ሲጠጡ።

«ያለሽበት ቤት ምን አለሽ? » ደመወዙ ገና መጥቶ ሳትበይው በወሬ አወፍሮሽ ጠበበሽ? » አሉ አዛዥ እንደ መሳቅ ብለው።

«እኔስ እዚህ ከምተኛበት ክፍል የበለጠ የትም ብሄድ አላገኝ። ነገር ግን እንግዳ፥ የሚቀበሉበት ትርፍ መኝታ ቤት ስለሌለዎ አሁን አልቸገርምና፥ ተቸግሮ ለሚመጣ እንግዳ ይሁን ዘምድ ልልቀቅ ብዬ ነው።»

«ባለቤት አስወጥቼ ልግባ የሚል እንግዳ አይመጣም፤ ቢመጣም አንቀበለው፣ አንቺ ቤትሽ ነውኮ! »

«እሱስ እውነት ነው፥ ብቻ........»

«ብቻ ምን? »

«እሺ እዚሁ....... እሆናለሁ። ነገር ግን እባክዎ አንድ ነገር ልለምንዎ እሺ ይበሉኝ።»

«ደግሞ አንቺ ለምነሽ ‹እንቢ› እላለሁ? »

«እግዚአብሄር ይስጥልኝ አባባ! መቸም ቤትዎ የምኮራበት ቤቴ ገንዘብዎ፥ ገንዘቤ፥ ነው፤ የኔም የስዎ ነው። አሁን እንደ ሚያውቁት በርስዎ ጥግ ሀያ አምስት ብር ደመወዝ ስላገኘሁ...... ዞሮ ዞሮ ያው ለራሴ ነውና በዬወሩ እንዳቅሜ እንድረዳ ቢፈቅዱልኝ...... በጣም ደስ ይለኛል» ብላ አይኖችዋን ወደሳቸው ቀና ብታደርግ ፊታቸው በቅጥበት ተለውጦ አዬችና ደነገጠች።

«እግዞ ማረነ ክርስቶስ! አባትሽ ነኝ ሲመስለኝ ባዳነቱን ነገርሽኝ! በይ እንግዲህ ቤትሽን ፈልጊ! » አሉ ቡናቸውን ሳይጨርሱ ቀስ ብለው እመሬት አስቀምጠው።

ደመቀች ከድንጋጤዋ የተነሳ ምራቅዋ ካፍዋ ደርቆ አይኖችዋ መርገብገቡን ረስተው ክርር ብለው ባዛኙ ላይ እንደ ተተከሉ እዚያው ቀሩ። ወይዘሮ ጌጤም ለጊዜው ደንግጠው መሬት መሬት እያዩ ዝም አሉ።

«እኔም እንጀራ ሽቃጭ ዬመስላል? » አሉ አንገታቸውን ደፍተው ከቆዩበት ቀና ብለው ደመቀችን በቁታ አይን እዬተመልከቱ።

«ግዴለም ባታውቂኝ ነው! » አሉ አይናቸውን እንደ ገና ከስዋ አስንተው ሳያረግቡ እጣራው ላይ ሰቅለው ያለፈ ጌትነታቸውን ትዝታ እያዩ። «አዎ ባታውቂኝ ነው፤ ብታውቂኝም ጊዜ ከመሸብኝ በሁዋላ አውቀሽኝ ነው! ያው ጌጤ ትታዘብ «ማተብ ለዬቅል ነው› ለራት ይሁን ለምሳ በገበታችን አብሮን ይሰለፍ የነበረው ብቻ

ካስር ካስራምስት አንሶ ያውቅ እንደሆነ! ዛሬም ቢሆን እግዚአብሄር ይመስገን እድሜ ለጌታየ የወር ደመወዝ አለኝ በዚያ ላይ ጋሻ መሬት አለኝ እኔ ተካልኝ እንጀራ ሳልሸቅጥ እንደ ኮራሁ ነው ወደ መቃብሬ የምሄደው! » አሉ አሁንም ቁጣቸውን በሽማግሌ ፊታቸው ሲነድ እዬታዬ።

«ዛሬ ምን ሆነዋል? ልጅቱ የተናገረችውኮ ይህን ያክል አስቆጥቶ ያለፈ ታሪክ የሚያስቆጥር አደለም! ‹ይፍቀዱሉኝና ለኔ ከሚደረግልኝ ወጪ ትንሽ ልርዳ› ነው ያለች! የወለዱት ልጅሽ እንዲህ ቢል አስቆጥቶ ይህን ያክል ያናግራል? የማይፈቅዱ ከሆነ ‹አልፈቅድም› ቢሉ አይበቃም? » አሉ ወይዘሮ ጌጤ፥ ድንጋጤያቸው ሲያልፍ ባለቤታቸው በማይበቃ ምክንያት ያን ያክል በመቆጣታቸው እንደ ማፈርም እንደ መገረምም ብለው።

ወይዘሮ ጌጤ ባላቸውን ሲገስጹ ደመቀች ከድንጋጤዋ ወጥታ አእምሮዋን ገዛችና፥

«አባባ ማነኛውም ነገር ሁሉ ያገኘሁት ስራ ጭምር ይቀራል እንጂ እርስዎ እንዲቀዬሙኝ አልፈልግም! ሆነ ብዬ አደለም፤ ንግግር ባላውቅ ነው ያስቀዬምሁዎ! ለመሄዱ ቤት ባገኝም ባ - ባላገንም እሄዳለሁ፤ ብቻ - ብቻ እባክዎ ይማ - ይምሩኝ እባክዎ ይቅር ይበሉኝና ልሂድ! » ብላ እያለቀሰች ምንም እንኩዋ በሁለት እጃቸው ለመከላከል ቢሞክሩ አሸንፋ በግራቸው ወደቀች።

መሸነፍ ይልቁንም ተሸንፎ ማልቀስ የተሸነፉት ያሸነፉትን መልሰው ድል የሚያደርጉበት ብርቱ መሳሪያ ነው! ደመቀች እንባዋን በግራ ቀን ጉንጮችዋ እያጎረፈች በግራቸው ላይ ስትወድቅ አዩና አዛዥ በልባቸው ድንገት የተቃጠለው የቁጣ እሳት ድንገት ጠፍቶ ወዲያው ማዘን ወዲያው መጸጸት ወዲያው ራሳቸውን መውቀስ ጀመሩ።

«አንቺ ማሪኝ ልጄ፥ እኔ ነኝ በደለኛ ጌጤ፥ እውነቱዋ ነው አንቺ ምንም አላጠፋሽም! እንዲያው በገሻ ከንቱነቴ ነው ያስቆጣኝ ማሪኝ! » አሉ ከወደቀችበት ለማንሳት እዬታገሉ። ሲያባብልዋት ጊዜ የባሰውን ሆድ ባሳትና ስቅቅ ብላ ታለቅስ ጀመር።

«ልቅሶው ይበቃል እንግዲህ ደመቀች! ከኔ ጋር ተመካክረን የምትችይውን ትሰጭኛለሽ! » አሉ ወይዘሮ ጌጤ።

«አዎ፥ ልሂድ አትበይ እንጂ፥ ከጌጤ ጋር ተማክራችሁ የምትችይውን ትከፍያለሽ! » አሉ አዛዥም ምሽታቸው ያሉትን ተቀብለው። ደመቀች ከወደቀበት ተነስታ ፊትዋን በነጠላዋ በነጠላዋ እዬጠረጠረች ያዛዥንም የወይዘሮ ጉልበት ሳመች።

አዛዥ ጌታቸው ደጃዝማች አሰፋ ጎፉን ብዙ አመት በገዙበት ጊዜ እንደ ሌሎች መኩዋንንታቸው ከሰጥዋቸው ማለፊያ ግዛት ሌላ፥ የጌታቸው ሙሉ ቤት አዛዥና ባለሙዋል በመሆናቸው፥ ያገኙት የነበረ መተያያ ያማልዱኝና ልዩ ልዩ በረከት ‹አንቱ› የተባሉ ጌታ አድርጎዋቸው ይኖሩ ነበር። በዚያ ጊዜ ለራትም ይሁን ለምሳ እቤታቸው ግብር ይበላ የነበረው እሳቸው እንዳሉት አስር አስራ አምስት ብቻ ሳይሆን ከዚያም ይበልጥ ነበር። ነገር ግን፥ ያ ሁሉ ትዝታውን ብቻ ትቶላቸው አልፎ አዲስ አበባ ባምሳ ብር የወር ደመወዝና አዳ ውስጥ ካንድ ጋሻ ለም መሬት በሚያገኙት ገቢ ከተወሰኑ በሁዋላ የወይዘሮ ጌጤ ብርታትና ጥሩ የቤት እናትነት ባይጨመርበት ኖሮ በሚኖሩበት ለጋስነትና ደግነት መኖር ባልቻሉ ነበር። ወይዘሮ ጌጤ ባላቸው ሳያውቁ ከዳ ከሚያገኙት ልዩ ልዩ እህል ጠላ ጠምቀው አረቄ አውጥተው በውጭ እያሸጡ፥ በወር የሚያገቡት ገቢ ካዛዥ ደመወዝ ይበልጣል። ስለዚህ በቤት ውስጥ አዛዥን የሚያሳስብ ችግር ኖሮ አይውቅም። አዛዥ ዱሮ እንደ ለመዱት ያገኙትን ሁሉ ይዘው ገብተው ‹እባካችሁ ምሳ ወይም ራት ሳትበሉ አትሂዱ› እያሉ እዬለመኑ እንግዶቻቸውን አብልተው፣ አጠጥተው ሲያሰናብቱ ከተለመደው ምንም አለመጉደሉን እንጂ ከየት እንደመጣ ምስጢሩን ስለማያውቁ በወር ደመወዛቸውና በጋሻ መሬታቸው ብቻ የሚኖሩ እዬመሰላቸው ከምስጋናው ትንሽ እንኩዋን ለባልቴታቸው ለወይዘሮ ጌጤ ሳያካፍሉ ‹እድሜ ለጌታየ› እንዳሉ ይኖራሉ። እሳቸው ባይሆኑ ምሽታቸው እንጀራ ባይሆነ አረቄና ጠላ ሸቅጠው በሚያገኙት ገቢ ባይሆን በሚኖሩበት ሁኔታ መኖር የማይችሉ መሆናቸውን ቢያውቁ ኖሮ ለደመቀች ያቀረበችውን አሳብ እንደ ውርደት ቆጥረውት ‹እንጀራ ሳልሸቅጥ እንደ ኮራሁ ወደ መቃብሬ እሄዳለሁ› ብለው ብዙ ጊዜ ካፋቸው ሲወጣ ተሰምቶ የማያውቀውን የብሪት ቃል ባልተናገሩ ነበር! ብቻ አዛዥ፥ እንደ እውነተኞች እንደ ቅኖች ሁሉ በሳቸውም ይሁን በሌሎች ላይ ክፉ የተሰራ መረዳቱም ቁጣቸውን መግታት የማይችሉ፣ እሳቸው ክፉ ሲሰሩ መረዳቱም ተጸጽቶ ንስሀ መግባቱም የማይከብዳቸው ስለ ነበሩ ቶሎ እንደ ተቆጡ ቶሎ ተጸጽተው ደመቀችን ይቅርታ ለመኑና ሰላም ሆነ።

ወይዘሮ ጌጤና ደመቀች ተመካክረው በወር አስር ብር እንድትከፍል ተስማሙ። አስር ብር ደመቀች ለብቻዋ ቤት ተከራይታ ብትቀመጥ ኖሮ ከምታውጣው በጣም ያነሰ ነው። ለወይዘሮ ጌጤ ግን፥ አንድ ቀዳዳ ይደፍንላቸዋል። በዚያ ላይ ደመቀች

ቅዳሜ ፍል ውሀ ሀኪም ቤት ስራ ስላልነበራት የቤተሰቡን ልብስ እያጠበች ባዘቦቱ ከስራዋ ስትመለስ ወይዘሮ ጌጤን በቤት ስራ እዬረዳች ‹ጎዱኝ ጎዳችን› የማለት ስሜት በመሀከላቸው ሳይኖር ሁሉንም ደስ ብልዋቸው ተቀመጡ።

አንድ ቅዳሜ ወይዘሮ ጌጤ ገበያ በሄዱበት አዛዥም ከደጃዝማች ግቢ ገና ሳይመለሱ፥ ደመቀች የሳምንት ልብስ አጠባዋን ቀደም ብላ ጨርሳ እደጅ እንደ ተቀመጠች፥ ቀጥላ የምትሰራውን ስታስብ በሻህ ዘለሌ፣ መጣ።

«እንኩዋን ደስ አለሽ፤ ጥሩ ስራ ማግኘትሽን ሰማሁ! » አለ በሻህ ገና ያጥሩን በር ሲገባ።

«እንኩዋን አብሮ ደስ አለን» አለች ደመቀች ከተቀመጠችበት ተነስታ ሰላምታ ለመስጠት ወደሱ እያመራች።

«መቸም አዝማሪ የማይገባበት የለ! ያ አልቃሻም ነው አሉ ያገኘልሽ! »

«ጋሼ ውቤ ነው ያገኘልኝ።»

«አዎ፥ እሱ አወዳድሶም፥ አለቃቅሶም እንኩዋንስ ራሱን ይሄው ዘመድ ለመርዳት ቻለ። ዛሬ ከሁሉም አዝማሪ መሆን ይሻላል! » አለ በሻህ ትንሽ ፈገግ ብሎ።

«ወደዚህ ብቅ ካልህ ብዙ ግዜ ሆነኮ ጋሼ፥ በጤንነት ነው? » አለች ደመቀች ስላዝማሪው ውቤ የተናገረውን ወደ ጎን ትታ።

«ደህና ነኝ፣ ሩቅ አገር - ጅቡቲ ሄጄ፥ ትናንት ማታ ነው የተመለስሁ፤ አንቺስ በረታሽ? ደምሽ ተመልስዋል? »

«እግዜር ይመስገን ደህና ነኝ» አለች አይንዋን ከሱ ላይ አንስታ መሬት አያዬች።

«በዱሮ እመቤትሽ የደረሰውን ጉድም ሰማሁ።

«ማን ነገረህ? »

«ጅቡቲ ከመሄዴ በፊት ጀምሮ፥ የከተማው ሰው የሚያወራው እሱን ብቻ ነበር። ከተመለስሁ ግን ምንም አልሰማሁ።»

«አዎ አሁን ወሬው፥ ቀዝቅዞዋል። እንዲቀዘቅዝ ያደረጉትም ባለቤቶቹ ናቸው። »

«እንዴት? »

«አልተከታተሉትም፤ ሌቦች ቤቱን ቀደው የሜቴን ወርቅ ሁሉ እንደ ወሰድዱ፥ በነጋው አባባ ሶስተኛ ፖሊስ ጣቢያ ሄደው ካስጻፉ በሁዋላ ሁለተኛ ያነሳው የለም።»

«ለምን? ገንዘብ ስለ ተረፋቸው ነው? »

«አደለም፤ መጀመሪያ እሜቴና ጌቶች ስላልተስማሙ ነው። በሁዋላስ ቢስማሙም - እንጃ የተቸገሩበት ነገር አለ መሰለኝ።»

«ምን? »

«መጀመሪያ እሜቴ፥ ‹ወርቄን የሰረቀኝ ሻምበል ዳኘ ነውና እሱ በቀጥታ ይከሰስ› አሉ፤ ጌቶች ግን ይህን አላመኑም ነበር። በሁዋላ እሳቸውም ወደ ማመኑ አዘነበሉና ለጠበቃቸው ቢያማክሩት ‹በቂ ማስረጃ ሳይኖር አንድ ትልቅ የፖሊስ ባለስልጣን በንዲህ ያለ ወንጀል ከሶ መርታት ያልተቻለ እንደሆነ ብርቱ ቅጣት ያስከትላል› አላቸው ይባላል። ሻምበል ዳኘ ደግሞ በጎን ይህን ሁሉ ሰምቶ፥ በጣም ተቆጥቶ እንዲያውም ‹እከሳለሁ› እያለ ይገላገል ነበር አሉ። ለምን እንደ ተወው አላውቅም። ብቻ ጌቶችንም እሜቴንም እቤታቸው ድረስ ኄዶ እስኪ በቃቸው ድረስ ሙልጭ አርጎ መሳደቡ ርግጥ ነው። ታዲያ እየውልህ ‹ሌቦችን አስፈልጉልን ብለው ፖሊሶች እንዳይነግሩ የፖሊሶችን ሹም መጠርጠራቸው አስቀድሞ ስለ ተወራ፥ ከሱ ጋር በመጣላታቸው እሱን ደፍረው እንዳይከሱ ምንም እንኩዋ እሱ መስረቁን ቢያምኑ ዳኞቹን ለማሳመን የሚበቃ ማስረጃ ስለሌላቸው ዞርያው ገደል ሆኖባቸው ዝም ብለው ተቀምጠዋል ይባላል! »

«ለመሆኑ እነሱ ‹ጥቁር ፋሽስት› እንደ ሰረቃቸው በርግጥ ያውቃሉ? »

«እንደ እሜቴማ ከሆነ፥ ‹እያየሁት ነግሮኝ ስለሆነ ወርቄን የወሰደብኝ ቅምያ ነው እንጂ ስርቆት እንኩዋ አይባልም› ነው የሚሉት።»

«ምን ማለት ነው? ወርቄን ሲወስድ ባይናቸው አይተውት ወይስ እሱ ‹እኔ ነኝ የወሰድሁት› ብሎ በገዛ አፉ ነግሮዋቸው ነው የወሰደው ማለት ነው? »

«የዚያኑ ያክል ነው! »

«እንዴት እባክሽ? ይህ ግሩም ነው! » አለ በሻህ እዬሳቀ።

«እኔን ባሰት ‹ሰርቃለች› ብለው አሳስረው ያን ያክል..... ግፍ እንደተሰራብኝ ካደረጉ በሁዋላ፣ አባባ ሄደው ተሰረቀ የተባለው ጌጥ በሳጥን ውስጥ ተቆልፎበት ከመከፈቻውም በሜቴ በራሳቸው እጅ እንዳለ እቤታቸው ከተቀመጠበት ያልተንቀሳቀሰ መሆኑን በጉዋደኞቹ ፊት ሲመከሩበት ሲያጋልጡት ጊዜ ከዚያ ተቆጥቶ ወደ እሜቴ ሄዶ ‹እንዲህ ላለው ክፉ ስራ እኔን ጭምር ተካፋይ እንዳደረጉኝ አይቀሩም፤ በዚህ ሳይጠፋ «ጠፋ» ብለው ግፍ ባሰሩበት ሀብትዎም እግዜብሄር በላተኛ እንደሚያዝበት አይጠርጥሩ› ብሎ በብዙ ሰው ፊት ዘልፍዋቸው መሄዱ መቸ ርግጥ ወርቁን ሲወስድ ‹የጋራ ግፍ የሰራንበት ሀብት ስለሆነ ድርሻ ድርሻችንን መካፈል ያስፈልጋል! የግፍ ስራዎ ተካፋይ ማን እንደ ሆነ ስለሚያውቁ አሁን ደግሞ ሌላ ሰው እንዳያስቸግሩ አደራ!› ብልዋቸው መሄዱን እሜቴ እዬማሉ ይናገራሉ አሉ። ይህ ሁሉ እውነት ከሆነ አንተስ ብትሆን ከሱ በቀር ማን ወሰደው ትላለህ? ሲወስድ ባይንህ ባታይስ...... ምለህ ‹እሱ ነው› አትልም? »

«እኔ ብሆን፥ ምዬ ‹እሱ ነው› ከማለቴ በፊት መጀመሪያ ተቆጥጦ መጥጦ ተናገረ የተባለውን ሁሉ ሲናገር «የሰማ ሰው ኖሮዋል ወይ› ብዬ እጠይቅ ነበር! ለመሆኑ እንዲህ አድርጎ የሚያዝበትን ወጥመድ ሁሉ አሰናድቶ ለሚይዙት ሰዎች ሰጥቶ ለመስረቅ የሚሄድ ሌባ አለ? » አለ በሻህ እዬሳቀ።

«እንዴት? ያልኸው አልገባኝም፥ ጋሼ።»

«እብድ ካልሆነ አንቺ ቅድም እንደ ነገርሽኝ መጀመሪያ ተቆጥጦ መጥጦ የተናገረውን ጠቅሶ፥ ከዚያ ጊዜ እንደ ፈከርሁ አሁንም ሀብትዎን የዘረፍሁ እኔ ነኝና ሌላ ሰው እንዳያሙ» ብሎ የሚሰርቅ ሌባ የለም፤ የዱሮ እመቤትሽን ወርቅ የሰረቀው፥ ወይም ያሰረቀው ጥቁር ፋሽስት በቁጣ ብዛት የዛተውን ዛቻ የሰማ ሰው ነው። ብቻ እንዲያ ያለው ሌባ በጣም ዘዴ አዋቂ ጎበዝ ሌባ ነው።»

«ያንለት ሲሳደብም ሲዝትም የሰሙ፥ አባባ እንደ ነገሩኝ እሳቸውና ወይዘሮ ማረከሻቸው ደግሞ፥ አንዳንድ የቤት አሽከሮች ቢኖሩ ነው። ታዲያ.....»

«ታዲያማ ወይ አዛዥ፥ ያለዚያም - ይሆናሉዋ?! » አለ በሻህ አሁንም እዬሳቀ።

«አየ...... ! አባባ ደግሞ እንዲህ ባለው ይጠረጠራሉ? በል እንግዲህ ዝም በል፤ ባታውቃቸው ነው! » አለች ደመቀች፥ እንደ ማዘን ብላ። በሻህ ሲስቅ ቆዬና፥

«ካዛዝ በቀር ለማንም እንዳትነግሪ ማይና አንድ ምስጢር ልንገርሽ። ለሳቸውም ቢሆን የምትነግሪያቸው አምለሽ ነው! » አለ።

«የለም ምስጢር ነው የምትነግረኝ? እኔ ምስጢር መስማት አልፈልግም ጋሼ» አለች ደመቀች ስላዛዥ በተናገረው የቅያሜ ስሜትዋ ገና በፊትዋ እዬታዬ።

«ንጹህ ሰው ከማማት እንድትድኑ የዱሮ እመቤትሽን ወርቅ ማን እንደ ሰረቀው ልንገርሽና ላዛዥም ንገሪያቸው። ብቻ ከሁለታችሁ በቀር ማንም እንዳያውቅ ምለሽ ለሳቸውም የምትነግሪያቸው አምለሽ ነው።» ደመቀች ደንግጣ የምትለው ጠፋትና ዝም ብላ ታየው ጀመር።

«በይኮ» አለ በሻህ ፈገግ እንዳለ።

«ምን ልበል? »

«ለማንም አልናገርም፥ አዛዥም ለማንም ላይናገሩ ቃል ሳይገቡ አልነግራቸውም በይ። በታቦት እንድትምይ አልፈልግም አምንሻለሁ።»

«ለማ - ለማንም አልናገርም» አለች ደመቀች ደንግጣ በልብዋ የተነሳው ሽብር ንግግርዋን እያደናቀፈው። በሻህ ከምን እንደሚጀምር ጠፍቶት አንገቱን ደፍቶ ሲያስብ ቆዬና እንደገና ቀና ብሎ ሰማዩን እዬተመለከተ፥

«እኒህ ክፉ ሴት» አለ። «እኒህ ክፉ ሴት፥ ባንቺ የሰሩትን ግፍ ያንለት አዛዥ ሲናገሩ በጣም አዝኘ፥ በጣም ተናድጄ ምንም ቢሆን ሳልበቀላቸው ላላርፍ ቆርጨ ነበር። ያንለት ያልሁትን አታስታውሽ ይሆና እንጂ፥ ‹ባራዳ ህግ እንዲህ ያሉት የሞት ፍርድ ይፈረድባቸዋል፤ ሞት ቢቀር ግን ለደካማ ማጥቂያ እምሳሪያ ያደረጉት ሀብታቸው እንደሚወረስ አይጠረጠርም› ብዬ ነበር። ታስታውሻለሽ! » ሲል በሻህ አዎንታዋን ራስዋን ወደ ላይ በመግፋት አመለከተች።

«ቀልዴን አልነበረም፥ የምሬን ነበር» አለ። «ላስገድላቸው ያ ቢቀር ላሰርቃቸው ቆርጨ ነበር ከዚህ የሄድሁ። ልብ አርጊ፥ ላንቺ ብዬ አደለም፤ እንዲያው ግፉ አንገፍግፎኝ አብግኖኝ ነው። ብቻ ደሜ ፈልቶ ከዚህ እንደ ሄድሁ እንዲህ ያለውን ስራ የሚሰሩትን ሰዎች ፍለጋ ከተማውን ሁሉ አዳርሼ ላገኛቸው አልቻልሁም። ይገርምሻል! ዱሮ ሳልፈልጋቸው በዬቀኑ ሳላያቸው የማልውለው ሆነ ብለው ከኔ እንደ ተሸሸጉ ሁሉ

መሰንበቻውን ብፈልግ ሁሉም ጠፉኝ። ሁዋላ በስድስተኛው ይሁን በሰባተኛው ቀን አንዱን አግኝቼ ስፈልገው የሰነበትሁበት ጉዳይ ባዋዬው፥ስቆ «ተቀድመሀል! » አለኝ።

«ምን ማለት ነው? አልገባኝም! » አለች ደመቀች።

«በዱሮ እመቤትሽ በጣም ከሚቀኑና ወርቃቸውን አሰርቀው አሽጠው ከዋጋው ለመካፈል ካቀዱ ብዙ፣ ምስጢር ከሚያውቁ ሰው ጋር ተዋውለዋል ማለት ነዋ! እይውልሽ፥ እኒያ ቀናተኛ ምስጢር አዋቂ የወይዘሮ ጽጌ ጌጥ ያለበት ሳጥን ከተቆለፈበት ወጥቶ ራስጌያቸው ቁልፍ በሌለው ቁም ሳጥን ውስጥ መቀመጡን የሚያውቁ ናቸው። ከዚህ ሌላ ከወርቅና፥ ከልዩ ልዩ የከበረ ድንጋይ የተሰራውን ጌጥ ሁሉ የሰሩት አዲስ አበባ የሚኖሩ የጌጣጌጥ፥ ሰራተኞች ስለሆኑና እዚህ አገር፥ ለመሸጥ የተፈለገ እንደሆነ የማን መሆኑ ሊታወቅ ስለሚችል እሱን ትቶ ባለቤቱ የማይታወቀውን ወርርቁን ብቻ መውሰድ የተሻለ መሆኑን ሌባው ‹ጥቁር ፋሽስት ነው እንዲባል› እሱ በቁጣ ተገፍቶ የተሳደበውንና የዛተውን እንዲሁም የቤቱን አከፋፈል በውስጡ የሚተኙት የት እንደሚተኙ ዘበኞች የት ሆነው እንደሚጠብቁ፥ ሌላም ሌላውንም የውጭ ሰው ሊያውቀው የማይችለውን ለሌባ፥ አስፈላጊ ዝርዝር ሁሉ የሚያውቁ ናቸው! » አለ በሻህ፥ ፈገግ እንዳለ የደመቀችን አይን ጠልቆ እያዩ። ይህ የሚለው ሁሉ ‹ከዚህ በቀር› የማይባል ልክ አዛዥን የሚመስል ስለሆነ ደመቀች ደንዝዛ በድን ሆና አፍዋን ብቻ ከፍታ ዝም ብላ ታየዋለች።

«አሁን ማን እንደሰረቀው ያለ ጥርጥር ታውቂዋለሽ! » አለ በሻህ።

«የለ - የለም አላውቅም» አለች ላብዋን ከግንባርዋ በመዳፍዋ እዬጠረገች።

«ይህን ሁሉ ከነገርሁሽ በሁዋላ ማወቅ አትችይም? »

«የለ - የለም።»

«ወይዘሮ ማረከሻቸው የሚባሉት የዱሮ እመቤትሽ ዘመድ ናቸው! » ሲል በሻህ ተጭኖዋት የቆየውን ከባድ ሸክም ከላይዋ አንስቶ እንደ ጣለላት ሁሉ «እሁ……! » ብላ በረዥሙ ተንፍሳ እንደምትስቅ አፍዋ ግራና ቀኝ እስከ መጨረሻው ተከፍቶ ከንፈሮችዋና ጉንጮችዋ እዬተንቀጠቀጡ የደስታ እንባ ይዝረከረካት ጀመር።

«ምን ሆንሽ? » አለ በሻህ ስታለቅስ አዬና።

«ደህና ነኝ፤ ደስ ብሎኝ ነው። አባባን ልትል መስሎኝ ጨንቆኝ ነበር፤ አሁን በጣም ደስ አለኝ።» በሻህ ይስቅ ጀመር።

«በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ! ወይዘሮ ማረከሻቸው የታቸውን ሀብት? በዚያ ላይ እቤታቸው ተቀምጠው እንጀራቸውን እዬበሉ እንዴት እንዲህ ያለውን ስራ ይሰራሉ? »

«ድህ ከባእድ ይልቅ በሀብታም፥ ዘምዱ መቅናትና ከቻለ በማናቸውም መንገድ ከሀብታም ዘመዱ ሀብት መካፈል መፈለጉ የታወቀ ነው።»

«ብቻ እሳቸውኮ ሁልጊዜም ቢሆን በሜቴ ርዳታ የሚኖሩ ‹ሞትሽን ለኔ ያርገው› ሲሉ የሚኖሩ ነበሩ! »

«ሲያብሉነው! ‹ሞቴን ላንቺ ያርገው› ማለታቸው ነው! ወዲያውም ተለምኖ የተገኘ የዘመድ ርዳታ እጅግ ቢበዛ ያሻከረውን ልብ ሊያለዝብ ይችል እንደ ሆነ ነው እንጂ፥ ከዚያ አያልፍም።»

«እንዴት? »

«ዘመዶች፥ ካንድ ቤተሰብ ተወልደው ከመሀከላቸው በሀብትም ይሁን በውቀት ወይም፥ በሌላ የሚበልጡዋቸውን የነሱን ድርሻ ቀምተው እንደ በለጥዋቸው ሁሉ ይጠልዋቸዋል፤ ይቀኑባቸዋል። ሲቸገሩ ከሚበልጡዋቸው ዘመዶቻቸው መለመናቸው እንኳዋ ባይቀር ለምነው የሚያገኙት በቅናትና በጥላቻ የተመረዘ ልባቸውን ሊያጠራ አይችልም። ወይዘሮ ማረከሻቸው እንዳጋጣሚ ከዘመዶቻቸው ሁሉ ድህነት የባሰባቸው ስለሆኑ በዘመዶቻቸው ላይ የጭዋ ልጆች አስተዳደግ በሚያስተምረው ያልሆኑንት መምሰል የተሸፈነ ብርቱ ቅናትና ጥላቻ ያላቸው ሴት ናቸው። ታውቂያለሽ? የሌቦቹ መሪ እንደ ነገረኝ፥ የወይዘሮ ጽጌን ወርቅ አሽጠው ካገኙት ብዙ ገንዝብ ይልቅ በጣም ደስ ያሰኛቸው፥ ወይዘሮ ጽጌና ‹ጥቁር ፋሽስት› ተጣልተው መለያየታቸው ነው! »

«እግዚኦ.....! በውነት ሰው አደሉም፣ ከሀዲ ናቸው! ታዲያ ለመሆኑ ይህን..... ሁሉ አይሰሩ ጉድ ሰርተው ምን አግኝተው ይሆን? »

«አስራ አምስት ሽህ ብር ያክል አግኝተዋል፤ አነሳቸው? »

«አስራ አስምት ሽህ ብር? ምን ያንሳቸዋል! መጦሪያቸውን አግኝተዋል እንጂ! ታዲያ ይህን ሁሉ ገንዘብ ይዘው የት ተሸሽገው ይሆን? »

«ወቄ የተሸጠ ጅቡቲ ስለሆነ እዚያ ነበሩ።»

«አሀ......! ለካ እዚያ ለመሄድ ነው፥ ጌቶች ከሀረር እንደ ተመለሱ ‹ጉንፋን አሞኛልና ድሬዳዋ እሄዳለሁ› ብለው መሄጃና መመለሻም ስንቅም፥ ተቀብለው የሄዱ! እውነትም ሰይጣን ናቸው! » አለች ደመቀች በመገረም ራስዋን እያወዛወዘች። ከዚያ ሁለቱም ዝም ብለው በዩበኩላቸው የሚያስቡትን ሲያስቡ ትንሽ እንደ ቆዩ «ለመሆኑ አንተ ጅቡቲ ምን ልታደርግ ሄድህ? » አለች ካነጋገሩ ሁሉ ለተሰራው ወንጀል ሙሉ ተካፋይ መስሎ ስለ ተሰማት ለማጣራት።

«ይህን ጥያቄ እንደምትጠይቂኝ አስቀድሜ አውቄያለሁ፤ የማላውቀው የምነግርሽን ማመን አለማመንሽን ነው! ብቻ፥ ‹አታምኝ ይሆናል› ብዬ መቸስ መናገሬን አልተውም። በዚህ ስራ ጭራሽ አልገባሁም። ልገባ የነበረ ቅድም ያልሁሽን ያክል፥ ማለት ሌቦችን አደፋፍሬ እኒያን ግፈኛ ሴት እንዲቀጥዋቸው ለማድረግ ነበር። ነገር ግን፥ ቀድመው ከወይዘሮ ማረከሻቸው ጋር መስማማታቸውን ስለ ነገሩኝ ‹መቀጣታቸው ከተረጋገጠ፥ በማናቸውም መንገድ ይቀጡ ብዬ ዝም አልሁ›። ጅቡቲ የሄድሁ፤...... ለሌላ ነገር ነው።»

«ምስጢር እንደሁ ግድ የለም አትንገረኝ።»

«ልነግርሽ አስቤ የመጣሁለት ምስጢር ነው! » አለ በሻህ የቅርታ ፈገግታ በፊቱ እዩታዩ።

«ምን? »

«የዱሮ እመቤትሽን ወርቅ ለመሸጥ፥ የሰረቁትና ያሰረቁት ተቃጥረው ወደ ጅቡቲ መሄዳቸውን በጎን ስሰማ ዱሮ ያላሰብሁበት አሳብ መጣብኝ። ያንጊዜ አንቺ ስራ አልነበረሽም! » ሲል ደመቀች ደንግጣ አፍዋንም አይኖችዋንም በሰፊው ከፍታ ታየው ጀመር።

«ያን ሀብት ምንም እንኳዋ የወይዘሮ ጽጌ የግፍ መሳሪያ ሆኖ እንዳይኖር ከሳቸው እጅ ማውጣቱ የሚያስፈልግ ቢሆን የሰረቁትም ቢሆኑ ያሰረቁት በሱ ለመጠቀም ከሳቸው የተሻለ መብት የላቸውም። በዚያ ሀብት ላይ መብት ሊኖረው የሚገባው ስለሱ

የደከመ የተቸገረ የተሰቀዩ ሰው ነው። ስለዚያ ሀብት የተቸገረ የተሰቀዩ በኔ አስተያየት አንድ ሰው ብቻ ነው። ታውቂያለሽ? »

«አላውቅም።»

«አንቺ ነሽ! »

«ውይ ጋሼ! ምን ማለትህ ነው? »

«አዎ አንቺ ነሽ! መኖሩን እንኩዋ ሳታውቂ በሱ ምክንያት የታሰርሽ የተደበደብሽ የገዛ ሰውነትሽን በልተሽ እስክትጨርሺ የተራብሽ አንቺ ብቻ ነሽ! ስለዚህ ሙብት የሌላቸው ሰዎች ሲከፋፈሉት ለማገገምያ ትንሽ ፍርፋሪ እንኩዋ ቢያስተርፉልሽ ልለምናቸው ነበር የሄድኩ። ብቻ ተስፋ ያደረግሁትን ያክል አልቀናኝም። ይሁን እንጂ፥ በመለመንም በማስፈራራትም ይህን - ሶስት ሸህ ብር አገኘሁ፤ ያንቺ ነው! » አለ ሶስት ሺብር በንቬሎፕ እንደ ተከተተ ከኪሱ አውጥቶ ለደመቀች ለመስጠት እጁን ዘርግቶ።

«ኧረ እናቴ ይደንግላይቱ! ምነው ጋሼ ምን አልሁህ? ደግሞ ብዬ ብዬ፥ ልስረቅ? » አለች ደመቀች እዬተንቀጠቀጠች።

«ባይበቃም በትንሹ ካሳ ነው፥ እንጂ ስርቆት አደለምኮ! »

«በጭራሽ አልነካውም ጋሼ! ማላ ይሁንብኝ አልነካውም! » አለች ሳታስበ ተንስታ ቆማ። አደነጋገጥዋና ጠቅላላ ሁኔታዋ ሁሉ ስትሰርቅ የተያዘች እንጂ፥ የተሰረቀ ገንዘብ ተጸይፋ ‹አልነካም› የምትል አትመስልም ነበር።

«ግፍ የተሰራብሽ መሆንሽን አይቼ፥ በመጠኑ እንኩዋ ካሳ ቢሆንሽ ብዬ ነበር። ትንሽ - የደከምሁ! ነገር ግን ይህን ያክል የሚያሳቅቅሽ ከሆነ ግዴለም ተይው እመልስላቸዋለሁ» አለ በሻህ ያወጣውን ገንዘብ መልሶ በኪሱ እዬከተተ።

«እባክህ አትቀየመኝ ጋሼ! የምጠላው እንዲያው - ከሞት የበለጠ የምፈራው ነገር ሆኖብኝ ነው! »

«ግዴለም፤ ምንም እንኩዋ ያሰብሁት ሳይፈጸምልኝ በመቅረቱ ግንሽ ቅር ቢለኝም ቅርታየ አድንቆቴን አይቀንሰውም። ይህ የችግር ጊዜ ባህሪሽ በምቾት ጊዜም እንዳይለሽ እግዜአብሄር ይርዳሽ! በይ አሁን ተቀመጭ» አለ በሻህ፥ እጅዋን ይዞ፥ ከቅርታ ፈገግታ

ጋር ሽቅብ አይኖችዋን እያዩ። እጅዋን እንደ ያዛት ስትቀመጥ ሽቅብ፣ ከሚያዩዋት አይኖች ጋር አይኖችዋ ተጋጩና እንደ መደንገጥ ብላ ቶሎ አይኖችዋን አሸሸች።

«አባባ አዛዥ ምን ጊዜ ነው የሚመለሱ? » አለ በሻህ እጅዋን፥ ለቆዋት ትንሽ ዝም ብለው ከቆዩ በሁዋላ።

«በምሳ ጊዜ ነው» አለች ደመቀች አንገትዋን ደፍታ እንደ ተቀመጠች።

«ወይዘሮ ጌጤ ወዴት ሄደዋል? »

«ገብያ እንደ ሄዱ አልተመለሱም፥ አሁን መምጫቸው ነው።»

«እንግዲህ ልሂድ መጥቸ አያችሁዋለሁ» ብሎ ሲነሳ፥ ልትሸኘው አብራው ተነሳች።

«ቅድም የነገርሁሽን ላባባ አዛዥ ስትነግሪ፣ ካፋቸው እንዳይወጣ ‹አስጠንቅቂያቸው› ያልሹን እንዳትረሺ፤ ደህና ሁኚ» አለ፥ እንደ ገና እጅዋን ይዞ፥ አይኖችዋን ጠልቆ እያዬ።

«አልረሳም» አለች። የስዋም አይኖች እንደ ልማዳቸው በመሸሽ፥ ፈንታ፥ የሱን አይኖች ሳይረግቡ፥ እያዩ። ከዚያ የጨበጠውን እጅዋን ስሞ ቀን አለና፥ ትንሽ አየት አድርጎዋት ሄደ። እስከዚያ ቀን ድረስ ከልጅዋ በቀር ሌላ ሰው ከንፈር ገላዋን ነክቶት አያውቅም። ከሞከሩት ሁሉ ጋር ስትጣላ ስትደባደብ፥ ነበር የኖረች። ያነለት ግን በሻህ እጅዋን ሲስም እንኩዋንስ ልትጣላው እጅዋን ለማሸሽ አልሞከረችም፤ ቁልቁል እያዬች ዝም ብላ አሳመችው። እንዲያውም እጅዋን ስሞ ሲሄድ ልብዋ ተከትሎ ሊሄድ እንደ ፈለገ ሁሉ ከደረትዋ ውስጥ ‹ምንጥቅ› ብሎ የወጣ መሰላትና ሳታስበው ደመነፍስዋን ‹ጋሼ፥ ጋሼ› አለች ሁለት ሶስት ርምጃዎች ወደ ፊት ተራምዳ።

«የኔ እመቤት» አለ በሻህ፥ ያጥሩን በር ከወጣ በሁዋላ መለስ ብሎ። ልትነግረው ያሰበችው ነገር ምንም አልነበራትም።

«ምንም አዶለም፤ እንዲያው እንዳትቀዬመኝ ‹አደራ› ልልህ ብቻ ነው» አለች፥ የምትናገረው ስላጣች።

« ‹ይቀዬማል› ብለሽ እንዳታስቢ። ሙች፥ እኔ ልሙት አልቀዬምም! » ብሎዋት ሄደ።

በሻህ ተሰናብቶዋት ከወጣ በሁዋላ ዘወር ብሎ ሳያያት፥ ዝም ብሎ መንገዱን ይዞ ወደሚሄድበ ሲሄድ፥ እስዋ ከቆመችበት ሳትነቃነቅ ካይንዋ እስኪጠፋ፥ ስትመለከተው ቆዬች። ካይንዋ ሲጠፋ ተቀምጠውበት ወደ ነበረው ቦታ ተመለሰችና እዚያ ተቀምጣ፥ እሱንም ባይነህሊናዋ መልሳ አምጥታ እፊትዋ አስቀምጣ እዬተመለከተች ያነለት መጥቶ እስከ ሄደ ድረስ የተናገረውንና ያደረገውን ሁሉ ታሰላስል ጀመር።

‹ለምነው እጄን የሳመኝ?› አለች ድምስዋን አሰምታ። ያስበች እንጂ የተናገረች አልመሰላምት ነበር። እጅዋን ከመሳሙ ጋር ተያይዘው፥ የደጃዝማች አሰፋ ቤት ጎረምሶች እነ ደጀኔ፥ አግደው ያስቸግሩዋት የነበረውና ባልዋ ያሳያት ስቃይ ስለ ታሰቡዋት ጊዜያዊ የቁጣ ትኩሳት ሰውነትዋን ሲወረው ተሰማትና ልብዋን እንደ ማቃር አፍዋን እንደ መምረር አላት። ብቻ ጊዜያዊ ስሜት ነበር። ወዲያው እስከ ጅቡቲ ድረስ ተጉዞ የድሮ እመቤትዋን ወርቅ ከሸጡት ሰዎች ጋር ተከራክሮ እስዋ አትቀበለው እንጂ ሶስት ሽህ ብር አምጥቶ እንድትቀበለው አጥብቆ መለመኑን ያን ደግነቱን ስታስብ ሻክሮ የነበረው ልብዋ እንደ መለዘብ አለና ‹የለም ደግ ነው! በደግነቱ ነው እንጂ - ሌላ አስቦ አደለም እጄን የሳመኝ› አለች፥ አሁንም ያሰበች እንጂ የተናገረች ሳይመስላት ድምጽዋን አሰምታ።

ከዚያ የፋሽቶች ወረራ ጊዜ ውስጥ አርበኛም የጫካ፥ አርበኛም ሆኖ ስለ ሰራው የጀግንነት ስራና ‹የጨለማው ንጉስ› እዬተባለ ያዲስ አበባን ህዝብ ያስጨንቅ እንደ ነበረ አዝማሪው ውቤ ሲተርክ የሰማችው እጹብ ድንቅ ታሪክ ታሰባት። ያን፥ አዝማሪው ውቤ ስለ በሻህ ሲተርክ የሰማችውን እጹብ ድንቅ ታሪክ፥ ያነለት ለስዋ ካደረገው ጋር አንድ ላይ አድርጋ ባሰበች መጠን በሻህን ሌላ አድርጎ እጹብ ድንቅ አድርጎ ያሳያት! ያ ሁሉ ጀግንነቱ፥ ያ ሁሉ ድግነቱ ያ ሁሉ ትልቅነቱ፥ ያን ጥንቃቄ የጎደለው ግዴለሽ፥ ሰውነቱን ሌላ አድርጎ አሳምሮ፣ እጹብ ድንቅ አድርጎ አሳያትና የማያዩ አካልውያን አይኖችዋን ስታረግብ ፊት ለፊት እንደ ተከለች ባይነ ህሊናዋ እሱን እያዬች ዝም ብላ ቆይታ፥ «ምን አይነት ሰው ነው! » አለች ፈገግ ብላ ራስዋን እዬወዘወዘች። ወዲያው እጅዋን ሲስማት የተስማት እንግዳ ስሜትና እስዋም ያን እንግዳ ስሜት ስታዳምጥ፣ ረስታ፥ እጅዋን ሳትነጥቅ ዝም ብላ ዘቅዘቃ እያዬች ማስምዋ ታሰባትና ተገረመች። «ወይ ግሩ - ም! ምን ሆኘ ነው? ምን አስነከቶኝ ነው?› አለች፥ የመገረም ብቻ ሳይሆን የማፈር ስሜት ጭምር ስለ ተሰማት ፊትዋ በቅርታ ፈገግታ እንደ ተዋበ በሻህ የሳመውን እጅዋን እንደ መስታዋት በፊትዋ ዘርግታ እያዬች። መሰንበቻውን በሻህ ካሳብዋ አልተለዬም። እሱ ግን ብቅ አላለም፥ ለብዙ ጊዜ ጠፍቶ ቆዬ።

# ምእራፍ ሀያ ሶስት

# ፍኖተ ድህነት

«የሚጠጣ ነገር አለሽ ጌጤ? » አሉ አዛዥ ተካልኝ አንድ ቅዳሜ፥ አዝማሪው ውቤንና በሻህ ዘለሌን አስከትለው እቤታቸው ሲገቡ።

«ጠጅ አለ ተቀመጡ» አሉ ባልተቤታቸው ወይዘሮ ጌጤ ለንግዶቹ ሰላምታ ሰጥተው። ደመቀችም ፍል ውሀ ሀኪም ቤት ቅዳሜ ስራ ስለሌለ፥ እዚያ ነበረች። በሻህን ስታይ እጅዋን፥ ሰምዋት የሄደች እለት ያዬችው፥ ያ እጹብ ድንቅ በሻህ እንጂ፥ ከዚያ በፊት የምታውቀው በሻህ መስሎ አልታያትም። እሱ ግን በሰውነቱም ሆነ በስሜቱ ያው የፊቱ በሻህ ነበር። እጅ ሰላምታ ሲሰጣት፥ እንደ ሁልጊዜው፥ ባይኖቹ የጎድን ገረፍ አድርጎዋት ብቻ አልቶፎ ተቀመጠ። የሱን ሁኔታ ስታይ ስሜትዋን እንዳያውቅባት አጥብቃ ትጠነቀቅ ጀመር።

«ሰው እወዳጁ ቤት ጠጅ አምሮት ሲመጣ፥

ጠላ ከጋበዘው ጠጅ ከቤት ሳያጣ፥

ከጠላው በሁዋላ ጠጅ ጠጣልኝ ቢለው አይችልም ሊጠጣ» ብሎ አዝማሪው ውቤ እንደ አንዷር በሚዝገመገም ውብ ድምጹ ዘፈነና፥ «እኔን ዛሬ ጠጅ ስላላሰኘኝ፥ ጠላ እንዳስገዛ ይፍቀዱልኝ» አለ አዝማሪው።

«ስሙልኝ፥ ይህን ውሸታ፥ ከይሲ ሲያሳጣኝ! መቸ አባትህ ነው ጠጅ እያለኝ በጠላ ሸኘቸህ የማውቅ? በል ግዴለም፥ መቸም አሁን ስምህ እንግዳ ስለሆነና፣ እንግዳም እሰው ቤት ገብቶ ‹ጠላ ላምጣ፥ ወጥ ላውጣ› ማለት ያባት ስላልሆነ፥ አርፈህ ተቀመጥ፤ እንካ አንተ ሩጥና ጥሩ ጠላ ካለበት ገዝተህ አምጣ» አሉ አዛዥ ብር አውጥተው እዚያ ቆሞ ለነበረ ልጅ። ያዝማሪው ውቤ ወቀሳ ለጭዋታ ያክልና አዛዥን ለማናገር ብሎ እንጂ የምሩን አልነበረም።

«ዱሮውንስ እርስዎን ለማስገዛት ነው እንጂ፥ እውነት እሱ የሚገዛ መሰለዎ? አዝማሪ ‹አጠጡኝ› እንጂ ‹ላስጠጣችሁ› ሲል ታይቶ ተሰምቶ ያውቃል? » አለ በሻህ ጉዋደኛውን በቀልድ አይን የጎድን አያዬ።

«እንግዲያውስ ሌባ ነው የራሱን ሰው ከመስጠት በቀር የሰው የማይነካ! » አለ አዝማሪውም የጉዋደኛውን የቀልድ አስተያየት ባሽሙር አስተያየት መልሶ። መቸም በሻህና አዝማሪው ሲነታረኩ ማየት አስቂኝ ትያትር እንደ ማየት ነው።

ባንድ ብር ትልቅ ማንቆርቆሪያ፥ ማለፊያ ጠላ ተገዝቶ መጥጦ ለሁሉም ተቀድቶላቸው እዬጠጡ ሲጫወቱ፥

«ራስሽ ተስማማሽ ደመቄ? ሁልጊዜ ‹እጠይቅሻለሁ› ብዬ አስብና ረሳዋለሁ» አለ አዝማሪው ውቤ።

«ስራውስ - ጥሩ ነው» አለች ደመቀች የማመንታት ምልክት ባነጋገርዋም በፊትዋም እዬታዬ።

«ታዲያ ምኑ ነው ክፉ? »

«ክፉ? ምንም ክፉ የለ! »

«ጽኑ ራብ የዘጋውን ሆድ ቀላል ቅምሻ ይከፍተዋል የሚባለውን ተረት ሰምታችሁዋል? » ሲሉ አዛዥ አቁዋርጠው ሁሉም አይናቸውን ወደሳቸው መልሰው፥ የተረቱን ትርጉዋሜ መፈለጋቸውን በሚገልጽ ፊት ተመለከቱዋቸው።

«ራብ ሲጸና» አሉ ቀጠሉና አዛዥ። «ራብ ሲጸና ራብ መሆኑ ቀርቶ ወደ ድካም ይለወጣል። ተመልሶ ራብ የሚሆን ትንሽ ነገር ከተቀመሰ በሁዋላ ነው። ይህን አታውቁም? እኔ ደህና አድርጌ አውቀዋለሁ። ደመቁም ከኔ እመቤት ጋር በጽኑ ችግር ትኖር በነበረችበት ጊዜ አሳብዋ ሁሉ እስዋና ልጅዋ ያኑ የችግር ኑሮዋቸውን እንዳያጡ ነበር እንጂ የገንዘብ ነገር አንስታ ሰምቸ አላውቅም። አሁን፥ ያን ችግር አለፈና፥ ሀያ አምስት ብር የወር ደመወዝ ስታገኝ አልበቃ ብሎ ራባት! መጀመሪያ ወሬውን እንደ ሰማች ገና፥ እጅዋ ሳይገባ ሀያ አምስቱ ብር ቢዝቁት የማያልቅ መስሎዋት እንዲሁ በገዛ እጁ እየወጣ የሚፈስበት ሀያ አምስት መንገድ ለመስራት አቅዳ ነበር። አሁን በጅዋ ገብቶ ብታየው፥ ለችግርዋ እንኩዋ የማይበቃ ሆኖ ተገኘ። ልግርዋ ጫማ እንኩዋ መግዛት አቅቶዋት አዩዋት ባዶ እግርዋን ናት» አሉ አፋቸውን እንደ ሁልጊዜው በሰፊው ከፍተው አንድ ጊዜ ደመቀችን አንድ ጊዜ፥ ባለቤታቸውን እያለዋወጡ እያዩ። አዛዥ፥

ደመቀችን ‹ሀያ አምስት ብር የምታወጣበት ሀያ አስምት መንገድ ለመስራት አቀደች› ያሉት ወዲያው ስራ እንደ ያዘች ቤት ተከራይታ ለመውጣት ወይም እዚያው ለመኖሪያዋ ለመክፈል ስለ ለመነቻቸው ተነስቶ የነበረው፥ ጥል መሆኑ ገባቸውና ወይዘሮ፥ ጌጤና ደመቀች እስበሳቸው ተያይተው ይስቁ ጀመር። አዝማሪውና በሻህ ሁለቱ ሴቶች የሳቁበት ስላልገባቸው ቀጥሎ የሚገልጽ መስሎዋቸው ቢጠባበቁ አዛዥም ሴቶቹም ሲስቁ ቆይተው ዝም ስላሉ ለውጭ ሰው የሚያካፍሉት የቤተሰብ ምስጢር መሆኑ ተስማምቶዋቸው እነሱም እስበሳቸው ተያይተው ዝም አሉ።

«ታዲያ……» አሉ አዛዥ አሁንም ቀጠሉና «ታዲያ እዩትላችሁ፥ ምንም ያልነበራት አሁን ትንሽ ስትቀምስ ጊዜ፥ ብዙ አማራትና ‹ደመወዝ ካልተጨመረልኝ መኖር አልችልም› ታልለች።»

ትንሽስ ድሮም ነበረኝ አባባ። እመይቴኮ ሰባት ብር ይሰጡኝ ነበር።

«አይ እሱን እንኩዋ ተይው! እሱ ደመወዝ አይባልይም።»

«ኧረ ለመሆኑ! አመት እንኩዋ ሳትሰሪ ነው የደመወዝ ጭማሪ የምትፈልጊ? » አለ አዝማሪው ውቤ።

«ካመትስ እንዲያውም አመት ከስድስት ወር ሆኖኛል! ብቻ ‹አሁን ያለሁበት ስራ ወደፊትም ቢሆን ደህና ደመወዝ የሚገኝበት አደለም› አልሁ እንጂ ‹ካሁን ቀደም የደመወዝ ጭማሪ አልተደረገልኝም› ብዬ እንኩዋ ይህን ያክል አልተቆረቆርሁም» አለች ደመቀች።

«ስራሽ ካማረና ጠባይሽ ከተስማማ፥ በዚያ ላይ ያገልግሎትሽ ጊዜ ለደመወዝ ጭማሪ የሚያበቃሽ ከሆነ፥ ወደ ፊት ደህና ደመወዝ የማታገኝበት ምን ምክንያት አለ? » አለ አዝማሪዉ።

«እኔ የምሰራ የጽዳት ስራ ነው ጋሼ። የጽዳት ሰራተኞች ምን ስራቸው ቢያምርም ቢስማማ፥ ያገልግሎታቸውም ዘመን ቢበዛ ደመወዛቸው ከሰላሳ ብር ሊያልፍ አይችልም። ለተራ የጽዳት ሰራተኛ የተወሰነው ከፍተኛ ደመወዝ ሰላሳ ብር ነው። የጻዳት ሰራተኞች አለቃ ብቻ አርባ ብር ያገኛሉ።»

«እኔ መቸም ውስጡን አላውቀውም። ብቻ እዚያ ሀኪም ቤት የሚሰሩ አንዳድ ወንዳጆቼ በጣም ሲያመሰግኑት እሰማለሁ» አለ አዝማሪው።

«እኔም ስራውን በጣም እወደዋለሁ። ጥዋት ገብተው የሚሰሩ የጽዳት ሰራተኞች ከቀትር በሁዋላ ነሳ ስለሆኑ እንዲሁም ከቀትር በሁዋላ የሚሰሩት ጥዋት ሰለማይገቡ፥ በነጻ ጊዜያቸው ሌላ ስራ ሰርተው ደመወዝ ሊያገኙ ይችላሉ። ስለዚህ እዚያ ብቻ ሰርቶ ከዚያ የሚያገኘው፥ ደመወዝ ብቻ ለሚኖር ነው እንጂ ደመወዙ የማይበቃ፥ በትርፍ ጊዜው ተቀጥሮ፣ የሚሰራበት ቦታ ለሚያገኝ ጊዜ ይሰጣል፤ ጥሩ ነው። እንዲያውም ትንሽ እንግሊዝኛ አውቀው የሀኪሞችና ያስታማሚዎች ረዳቶች እዬሆኑ ቁስል የሚያስሩና መድሀኒት የሚያድሉማ የደመወዝ፥ ጭማሪ በዬጊዜ ያገኛሉ። ይልቁንም ትምርት ጭምር ስለሚያገኙ የደመወዝ ጭማሪያቸውንም ሆነ የደረጃ እድገታቸውን ትጋታቸውና ችሎታቸው ካልሆነ ሌላ፥ የሚወስንባቸው ነገር የለም። እነሱ - ጥሩ እድል አላቸው።»

«ታዲያ ትንሽ እንግሊዝኛ ማወቅ፥ ለደረጃ እድገትና ደህና ደመወዝ ለማግኘት ይህን ያክል የሚረዳ ከሆነ ለምን በትርፍ ጊዜሽ አትማሪ? » አለ በሻህ፥ አዝማሪው ውቤና ደመቀች የተነጋገሩትን ዝም ብሎ ሲሰማ ቆይቶ።

«ትምህርት ቤት የት አገኛለሁ? ባገኝስ ከንግዲህ ተምሬ የት እደርሳለሁ? »

«ያለሽበት ሀኪም ቤት ቁስል አሳሪዎችና መድሀኒት አዳዮች ከሚያውቁት ባይበልጥ የማያንስ እንግሊዝኛ ካንድ አመት ባለበለጠ ጊዜ ተምረሽ የምትወጭበት ትምህርት ቤት እኔ አገኝልሻለሁ።»

«እሱ እንዲህ መቃዠት ልማዱ ነው፤ አትስሚው! ይልቅ አሁን እንዳልሽው ትርፍ ጊዜ ካለሽ በትርፍ ጊዜሽ እዬሰራሽ ትንሽ ገንዘብ የምታገኝበት ቦታ እንፈልግ። ለተወሰነ ጊዜ የጽዳት ስራ አሰርተው በመጠኑ የሚከፍሉ ሰዎች አይጠፉም» አለ አዝማሪው የበሻህ አሳብ ከንቱ መሆኑን በቃል ብቻ ሳይሆን በፊቱና ባስተያየቱ ጭምር እዬገለጸ።

« ‹ስሙን ለሰው›! የቅዠት ልማድ ያለህ አንተ ነህ፥ አልቃሾ እኔ አደለሁም» አለ በሻህ ንዴቱንና ንቀቱን ባንድ ላይ የሚገልጽ ፊቱ ጨምደድ የታች ከንፈሩ ወደ ፊት ረዘም እንዳለ ጠቋዋሚ ጣቱን ወደ አዝማሪው ቀስሮ። የበሻህን ሁኔታ ሲያዩ ሁሉም ይስቁ ጀመር።

«እስቲ እባካሁ ፍረዱ!? » አለ አዝማሪው ውቤም አብሮ ሲስቅ ቆይቶ። ‹ባንድ አመት ውስጥ እንግሊዝኛ አስጨርሶ ስራ የሚያስይዝ ትምህርት ቤት አለ› የሚል ሰው ‹ቅዠታም፥ ወይም ውሸታም› አይባል እንደሆነ እናንተ ፍረዱ።»

«ቅዠትህ ሜዳውን ገደል፥ ብርሃኑን ጨለማ፣ አስመስሎ እያላዬህ ስታለቅስ የምትኖር በውሸት ንፉጉን ለጋስ፣ ፈሪውን ጀግና፥ መጥፎውን ሸጋ አስመስለህ እያቆላመጥህ የምታድር አንተ ለመሆንህ ስራህ ምስክር ስለሆነ አሁን ‹መስክሩልኝ ፍረዱልኝ› አልልም። ብቻ እኔም እንዳንተ ውሸታምና ቅዠታምነቴን ‹አሜን› ብዬ የምቀበለው ደመቀች በምስተራበት ሀኪም ቤት ቁስል የሚያስሩትና መድሀኒት የሚያድሉት ከሚያውቁት የተሻለ እንግሊዝኛ ባንድ አመት ውስጥ ተምራ የምትወጣበት ትምህርት ቤት ሳላገኝላት የቀረሁ እንደሆነ ነው! »

«እስቲ ለመሆኑ! እንዲህ ያለውን ታምር የሚሰራ ትምህርት ቤት እስከ ዛሬ ሁላችን ሳናውቀው የት እንው ተሸሽጎ የሚኖር? እባክህ! » አለ አዝማሪው በቀልድ መልክ።

«አንተ ጥሩ ጠጅ ያለበትን ካልሆነ ጥሩ ትምህርት ቤት ያለበትን ማወቅ የማትፈልግ በመሆንህ ነው እንጂ፥ እሱስ አልተሸሸገም። እዚሁ አጠገብህ ገዳም ሰፈር ያለው፤ ስሙም ፍኖተ ድህነት ይባላል።»

«እ -! እሱን ነው? ሀ - ሀ - ሀ! »

«እኔኮ ቁም ነገር የሚናገር መስሎኛል! ለካ ቀልዱን ነው! የሴተኛ አዳሪዎችን ትምህርት ቤትኮ ነው! » አለ አዝማሪው ንግሩን ሳቁ እያቋዋረጠው።

«እንዴት? ደግሞ በንግሊዝኛ - የሴትኛ አዳሪ ተመሪ ቤት ተከፈተ? ዛሬ ዘበንኮ የማይመጣ ነገር የለም! » አሉ አዛዥ ግራ ገብቶዋቸው።

«የለም አባቴ» አለ በሻህ፥ አዛዥ በተናገሩት ከሌሎች ጋር ሲስቅ ቆይቶ፥ «የለም፤ ሴተኛ አዳሪዎችን ሌላ ልዩ ልዩ ትምህርት አስተምሮ፥ ሴተኛ አዳሪነታቸውን ለማስትው የተቋዋቋመ ትምህርት ቤት ነው። እንግሊዝኛ አንዱ ትምህርት ነው።»

«ማን እንዳቆቁዋመው ታውቃለህ? » አለ አዝማሪው ጉዋደኛውን ፍጥጥ አድርጎ እያዬ።

«አንተ እንኩዋ ‹አውቃለሁ› ትላለህ እንኩዋን እኔ! »

«ይህን ‹ትምህርት ቤት› የሚለውን ማን እንዳቆቁዋመው ልንገራችሁ፥ አባባ አዛዥ። ከዚያ በሁዋላ ምን አይነት ትምህርት ቤት እንደ ሆነ ልትገምቱ ትችላላችሁ። ትምህርት ቤቱን የከፈተችው አንዲት ሴተኛ አዳሪ ሆና ያረጀች ሴት ናት። ያች ሴት በጠላት ጊዜ፥ ላዲስ አበባ ሴትኛ አዳሪ ሁሉ አለቃ ሆና ተሹማ ያገኘችው ገንዘብ መጠኑ ‹ይህ ነው› ሊባል አይችልም። አሁን ስታረጅ ጊዜ ያን ገንዘብ የምታደርስበት አጣች። ለልጅ እንዳታወርሰው የመጣችበትን አገር የምታውቀው አይመስለኝም። ስለዚህ - ለግብራበሮችዋ ማውረስዋ ነው መሰለኝ ቀለባቸውንም መኖርያቸውንም ችላ አስቀምጣቸዋለች ይባላል።»

«ለመሆኑ ይችን ሴት ታውቃታለህ? » አለ በሻህ አዝማሪው ውቤ የፍኖተ ድህነትን መስራች እያጎሳቆለ ሲያወራ ከንፈሩን አበላልጦ በመጸየፍ ሲመለከተው ቆይቶ።

«ብዙ የሚያውቁዋት ሰዎች ነገሩኝ እንጂ፥ እኔስ አላውቃትም።»

«ታዲያ የማታውቃትን ሴት እንዲህ ከመጠን ያለፈ አበለሻሸተህ ስታወራ ሌላው እንኩዋ ቢቀር ድንገት የሚያውቃት ሰው ቢኖር ‹ውሸቴን ይገልጥብኛል› ብለህ አታስብም? አዝማሪ የሰጡትን በውሸት ማወደሱ ያልሰጡትን በወሸት ማኰሰሱ እንኩዋ መቸም በሰው ገንዘብ የሚኖሩት ሁሉ እንደ ፈጠሩት ልዩ ልዩ የሙብያ ዘዴ እሱም የሰው ገንዘብ የሚዘርፍበት የታወቀለት ዘዴው ስለሆነ የሚያስገርም መሆኑ ቀርቶዋል። ነገር ግን የማታውቃትን አንድ ቀን እንኩዋ ፊትዋን ያላዬኸውን ሴት እንዲህ አርገህ ስታጎሳቁል ላዝማሪም ከተፈቀደው ወሰን አልፈህ እባለጌዎች ሰፈር ገባህ ማለት ነውኮ! አዬህ? ስለስዋ እኔን ጠይቀኝ፤ ጥሩ አድርጌ አውቃለሁ። ከሁሉ በፊት አንተ እንዳልኸው ‹አሮጊት› አይደለችም ወጥት ናት። ከኔ ባታንስ አትበልጥም። ስለዚህ ባትፈልግ ነው እንጂ ከፈለገች በድሜም ይሁን በመልክ ከብዙዎቹ ሴትኛ አዳሪዎች ስለምታምርና ልጅነት ስላላት ወደ ፊት ብዙ አመታት በሴትኛ አዳሪነት ልትቀጥል ትችል ነበር።እ ኔ ያሁኑን ብቻ ሳይሆን የልጅነት ታሪክዋን ችምር አውቀዋለሁ። አንተ እንዳልኸው ሴተኛ አዳሪ ሆና ተወልዳ ሴትኛ አዳሪ ሆና ያረጀችም አይደለች። በልጅነትዋ ወላጆችዋ ስለ ሞቱባት ዘመዶችዋ አዲስ አበባ አምጥተዋት ከነሱ ጋር ተቀምጣ ካቶሊክ ሚሲዮን ትምርት ቤት እዬተመላለሰች ትማር ነበር። እኔም እዚያው እማር ነበር። መቸም በመልክዋ ማማርና በጠባይዋ እርምነት የማይደነቅ አልነበረም።

ነገር ግን ባፈና - ስምዋ ነው - ያ ሁሉ የሰው አድንቆትና ከንቱ ውዳሴ ልብዋን የማይማርከው ሁልጊዜ አንገትዋን ደፍታ የምትሄድና ለመመንኮስ የምትሰናዳ ልጅ ነበረች። አንድ ጎደሎ ቀን ከትምህርት ቤት ወደ ቤትዋ ስትመለስ፥ አንድ ሲያደባ የቆየ ርጉም ታከሲ ነጂ ጠልፎ ጫካ ወስዶ ህግዋን ገሰሰና እዚያው ጥልዋት ሄደ። ያን ጊዜ አስራ አምስት፥ ቢበዛ አስራ ስድስት ቢሆናት ነው። ከዚያ እያለቀሰች ወደ ዘመዶችዋ ብትሄድ የሆነችውን ሲያዩ በማዘን ፈንታ እንደ በሽተኛ ውሻ ሊገድልዋት ፈለጉ። ከዚያ ወደ ተማሪ ቤት ሄዳ የደረሰባትን አደጋ ለሹሞች ብትነግር እንዲያ ያለ ነውር ተሸክማ እፊታቸው መቅረብዋ ብቻ እነሱን፥ እንዳረከሳቸው ቆጥረውት፥ ዘበኛቸውን ጠርተው ወዲያ እንዲያባርራት አደረጉ። ይች ልጅ እንዲያ ያለ ጨካኝ አደጋ በደረሰባት ጊዜ እድሜዋም ሆነ ትምህርትዋ ለስራ የሚያበቁት አልነበሩም። ለለት እንኩዋን የሚስጠጋትና ቁራሽ እንጀራ የሚያስቀምሳት አጥታ ተጨነቀች! ከዚያ በሁዋላ ነው፥ መድረሻ ስታጣ ሴትኛ አዳሪ የሆነች። ቅድም እንዳልከው በጠላት ጊዜ የሴትኛ አዳሪዎች አለቃ ሆና መሾምዋ እውነት ነው። ብቻ ፈልጋው ወይም ደጅ ጠንታ አደለም፤ ታዝዛ ነው። ወራሪዎቻችን የሴትኛ አዳሪዎችን ቤት ሲፈትሹ፥ በልጅነትዋ የተማረችው ትምህርት ረድተዋት ራስዋን ብቻ ሳይሆን ቤትዋንና አሻሻጭዎችዋን የያዘችበትን የጽዳት አያያዝ ከሁሉም የበለጠ ሆኖ ስላገኙት አላፊ አደረጉዋት። ሴትኛ አዳሪነት ምንም እንኩዋ መድረሻ ስላጣች እንጂ መርጣው የገባችበት ባይሆን ከማነኛውም ጊዜ የበለጠ የሚያሰቅቅ መሆኑን የተረዳች በጠላት ጊዜ አላፊ ሆና ታስረዳድቸው በነበሩ ሴቶች ሲደርስ ያዬችው ስቃይ ነው። ወዲያው ጠላት እንደ ለቀቀ በዬጊዜው የገዛችውን የከተማ ሆነ የባላገር ርስት ሁሉ ጌጥዋን ሳይቀር ሽጣ፥ በዚያ ላይ እዬዞረች ለምና ሴትኛ አዳሪነታቸውን ትተው ልዩ ልዩ ስራ እዬተማሩ ሰርተው ለማደር ለሚፈልጉ ሁሉ ይህን ‹ፍኖተ ድህነት› ተብሎ የተሰዬመውን ትምርት ቤት ከፈተች። ዛሬ እዚያ እዬኖሩ የሚማሩትን የጥንት ሴትኛ አዳሪዎች ብዛት ብታዩ ይገርማችሁዋል። ይች ናት ባፈና የፍኖተ ድህነት መስራች አልቃሾ! አንተ አጎሳቁለህ አጨማልቀህ ስለህ ያሳዬኸን አደለችም! እንደውነቱ ከሆነ ሀውልት ሊቆምላቸው ወይም ታቦት ሊቀረጽላቸው የሚገባቸው በጎ አድራጊዎች ቢኖሩ በኔ አስተያየት አንድዋ ባፈና ናት! » አለች በሻህ።

«እኔ ስለዚህ ሴት የሰማሁት፥ ከሞላ ጎደል ቅድም ያልሁት ነው። ነገር ግን አሁን እንደ ነገርኸን ያለች ከሆነች አንተ እንዳልኸው ‹ታቦት ሊቀረጽላት የሚገባ ናት› ባልልም የሚያከብሩዋት እጅ ሊነስዋት የሚገባ ስለ ሆነች ይሄው እጅ ነስቻለሁ! » አለ አዝማሪው እዬሳቀ ተነስቶ ፊቱን ወደ ባፈና ሰፈር ዞሮ እጅ እዬነሳ።

«ያም ሆነ ይህ እንደኔ፥ ይች የምትልዋት ሴት እብድ የመከራት ሞኝ ወይም ራስዋ ልትታሰር የሚገባት እብድ ሳትሆን አትቀርም» አሉ አዛዥ ስለ ወይዘሮ ባፈና በሻህም አዝማሪውም ያሉትን ዝም ብለው ሲሰሙት ቆይተው።

«እንዴት አባባ? » አለ በሻህ።

«ተማሪዎች ከተማሪ ቤታቸው እዬወጡ ሴትኛ አዳሪዎች ሲሆኑ እያዬን ‹ሴትኛ አዳሪዎች የሚኖሩበትን ስራ ትተው እንደገና ‹ትምህርት ቤት ይገቡልኛል› ብላ ይህን ያክል ሀብት አውጥታ የምትበትን ሴት ጤነኛ ትባላለች? ደግሞስ - ዛሬ ጠጅና ረቂ እንደ ውሃ የሚጠጣእብት ስጋ እንደ ጎመን የሚበላበት የሴተኛ አዳሪዎች ቤት ሆኖዋል። ታዲያ እንዲያ ካለው ጌትነት ወጥተው ወደ ተማሪ ቤት የሚሄዱት ሴቶች ምን ሊያገኙ ነው? መቸስ - ትምህርት ሀብትና ምቾት ለማግኘት አደለም? ታዲያ - ሀብትና ምቾት እንዲህ፥ ያለ ድካም ‹እባካችሁ ተቀበሉን› ብለው እዬለመኑዋቸው ‹የለም፥ አክልደከምን አንቀበላችሁም› ይባላል? ይህማ - ‹ሳትዋጋ ንገስ› ቢሉት እንዳጣው ጥጋበኛ ሰው መሆን ነው! » ሲሉ አዛዥ ሁሉም ባንድነት ሳቁ።

«አደለም አባባ አዛዥ» አለ በሻህ ሲስቅ ቆይቶ። ‹አደለም እርስዎ እንደሚሉት ስጋ እንደ ጎመን የሚያበሉትና ጠጅ እንደ ውሀ የሚያጠጡትማ እንዲያው ባፍ ልማድ ‹ሴትኛ አዳሪዎች› ይባላሉ እንጂ፥ የሴትኛ አዳሪነት ፈተናቸውን አልፈው ከሴትኛ አዳሪዎች ተራ የወጡ በሌላ መንገድ የሚኖሩ እመቤቶች ናቸው። ብቻ እንደነሱ ያሉት ስንት ይመስሉዎታል? በጣም ጥቂት ናቸውኮ! እነሱ ጌትነታቸውን ትተው ትምህርት ቤት እንደማይገቡ የታወቀ ነው። ትምህርት ቤት የተከፈተ ለብዙዎቹ በፈተናው ውስጥ ለሚገኙት ነው። ከነዚህ ከብዙዎቹ መሀከል ቦታ ስለ ጠበበ፥ በመጠባበቅ ላይ ያሉትንና በዬቀኑ እየመጡ የሚመለሱትን ሳይቆጥሩ ገብተው የሚማሩትን ብዛት ቢያዩ ‹ይህን ያክል ሴትኛ አዳሪን ባዲስ አበባ ኖሮዋል ወይ!› ብለው ይገረማሉ።»

«ይሆናል፤ ብቻ እንጃ! » አሉ አዛዥ በሻህ የተናገረው ሁሉ ስላላጠገባቸው ራሳቸውን በዝግታ እዬወዘወዙ።

«የሴትኛ አዳሪዎች ትምህርት ቤት መሆኑን አላውቅም ነበር እንጂ ‹ፍኖተ ድህነት› የሚባል ጥሩ ትምህርት ቤት አለ› ሲባል እኔም ሰምቻለሁ። ታዲያ ሲያመሰግኑት ስለ ሰማሁ እንዲህ ያሉት የሚማሩበት አለመሰልኝም ነበር» አለች ደመቀች ደስ ያላላት መሆንዋን በግልስ እዬታዬ።

ደመቀች ያገርዋ፥ የንዶዳሞ ኪዳነ ምህረት ባላገርና የወላጆች የንስሀ አባት ቄስ መንግስቱ ስለ ሴትኛ አዳሪዎች በክፉ ሲናገሩ እዬሰማች አምናበት ስላደገች፥ ከስድስት አመታት በላይ አዲስ አበባ ትኖር ያን እምነትዋንና ስሜትዋን ምንም ያክል አልለወጠችም ነበር። መቸም እንደ ባላገር ቄሶችና በነሱ፥ ስብከት በባላገር ዘንድ እንዳደረው ኦሪታዊ እምነት ሴትኛ አዳሪዎች የእግዚአብሄርን መንገድ ትተው የሰይጣንን መንገድ የመረጡ፥ የሰይጣን ተከታዮች ስለሆኑ በድንጋይ ተወግረው መሞት የሚገባቸው ናቸው! እንደ ባላገር ቄሶችና እነሱ እንደ ሰበኩት ባላገር ኦሪታዊ እምነት ሴትኛ አዳሪዎች የእግዚአብሄርን ህግና የሰውን የበጎ ምግባር ስራት ሁሉ የናቁ በጠባያቸው ባነጋገራቸውና በስራቸው ሁሉ ጋጠ - ወጦች የሆኑ ባለጌዎች ስለሆኑ፥ ከነሱ መሸሽ እንጂ ከነሱ መቀራረብ ሀጢያት ነው! ስለዚህ ደመቀች እኒያን ሀጢያተኞች መጥላት ብቻ ሳይሆን ትፈራቸው ነበር። ፍል ውሀ ሀኪም ቤት ከተቀጠረች በሁዋላ፥ በሰፈርዋና በሀኪም ቤቱ መሀከል ስትመላለስ መሸት ሲል ወደ ቤትዋ በምትመለስበት ጊዜ በመንገዱ ዳር ዳር ቀይ መብራት በርቶ ሙዚቃውና ዘፈኑ ደርቶ ‹አሰረሽ ምቺው!› እዬተባለ አለም የሚያልፍባቸውን የሴትኛ አዳሪዎች ቤቶች ስታይ እዚያ ውስጥ ያሉት ሁሉ የሰይጣን ጭፍሮች ያ ቀይ መብራት የገሀነመ እሳት ምሳሌ ‹ገሀነመ እሳት በምድር› መስለው ይታዩዋትና እንዲያ ያሉ ቤቶች አጠገብ በደረሰች ቁጥር ‹በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ› እያለች እያማተበች እስኪታልፋቸው ትቸኩል ነበር! ስለዚህ ይህ ስለ ሴትኛ አዳሪዎች አብሮዋት ያደገ እምነትዋ ይህ እነሱን የመጥላትና የመፍራት ስሜትዋ ነበር፥ በሻህ ‹ፍኖተ ድህነት ትምርት ቤት ግቢ› ባላት ጊዜ ‹እንዲህ ያሉት - የሚማሩበት› ስትል ባፍዋ አትናገረው እንጂ ደስ ባላለው ፊትዋ በግልጽ ይታይ የነበረ።

«ፍኖተ ድህነትን ካልፈልገሽ ትምህርቱ እንደሱ አይሆንም እንጂ ሌላ ‹ንጋት› የሚባል የማታ ትምርት ቤትም እዚህ ቅርብ አለ እንዲያውም ያቆቁዋመው የድሮ ጉዋደኛዬ ስለሆነ፥ እዚያ እጠይቅልሻለሁ» አለ በሻህ ደመቀችን ደስ እንዳላላት ሲያይ። «ብቻ - እስቲ ቀድመሽ ፍኖተ ድህነትን እይው» አለ ቀጠል አድርጎ።

«እዚያ - ተማሪ ሆኘ ገብቸ ነው የማየው? »

«የለም፤ ዛሬ እንዲህ ወስጄ ‹ፍኖተ ድህነትን› አሳይቼ እመልስሻለሁ። እንደ ዛሬው ስራ በሌለሽ ቀን ብትፈልጊ ሳምንት ቅዳሜ ደግሞ ‹ንጋትን› አሳይሽና እንዳቸውን ስትመርጪ የመረጥሺውን ትምርት ቤት ባለቤት እጠይቅልሻለሁ።»

ደመቀች ምንም እንኳዋ እኒያ የምትጠላቸውና የምትፈራቸው ሴትኛ አዳሪዎች አንድ ላይ በተሰበሰቡብት መሄዱን እንደ ጦር ብትፈራው በሻህ እንዳይቀዬማት በሻህን ደስ ለማሰኘት ብቻ አብራው ወደ ፍኖተ ድህነት ትምርት ቤት ሄደች።

ቅዳሜ በሌሎች ትምርት ቤቶች ትምርት ባይኖርም ፍኖተ ድህነት እንኳዋንስ ቀን ማታም እስከ አምስት ሰአት አለ። በሻህና ደመቀች እዚያ ሲደርሱ የሀያ ደቂቃ እረፍታቸው ስለ ነበረ፥ ተማሪዎች ሁሉ ወጥተው ብቻ ብቻቸውንም ሁለትና ሶስት በዬጉዋዳቸው እዬሆኑም ግቢውን ሞልተውት ነበር። እንደ ብዛታቸው በሌሎች ትምርት ቤቶች የሚታዬው መሮሩዋጥና መላፋት የለ፤ በሌሎች ትምርት ቤቶች የሚሰማው መጠራራትና ጩኸት የለ፤ ግቢው ጸት ሰጥ ያለ ሰላም ነበር። እኒያ ውብ ውብ አበቦች ለዚያ ግቢ ውበትና ድምቀት ሰጥተውት፥ ጸጥታ ፍለጋ ሰላም ፍለጋ የሚሄዱበት ውብ ያትክልት ቦታ አስመስለውት ነበር! እኒያ ውብ ውብ ቆነጃጅት ደመና በሌለው የሰማይ ሜዳ እንደሚፍለቀለቁ ከዋክብት ያን ግቢ አሳምረውት ነበር!

ደመቀች ካጥሩ ውጭ ሳለች ግቢውን ሞልተውት ስታያቸው ‹መቸም ባለጌዎች ናቸውና ሳይሰድቡኝ አይቀሩም› ብላ ፈርታ ነበር። ነገር ግን በሻህን ተከትላ ጉልበቶችዋ እዬተብረከረኩ ያን ግቢ አቁዋርጠው ወደ ወይዘሮ ባፈና ጽህፈት ቤት ሲሄዱ፥ ከተማሪዎች መሀከል ዘወር ብለው ያዩዋቸው እንኳዋ አልነበሩም። ጽሕፈት ቤቱ ደርሰው በሻህ መዝጊያውን ቀስ አድርጎ ሲመታ፥

«ግ - ቡ» አለ አንድ እንደ ውብ መረዋ ደስ የሚል ድምጽ።

«ውይ! በሻህ ከምን ሰማይ ‹ዱብ› አልህ ዛሬ? » አሉ ወይዘሮ ባፈና በሻህ ደመቀችን አስከትሎ ሲገባ ፊታቸው ሁሉ በደስታ እየሳቀ የሚጽፉትን ትተው ተነስተው ወደሱ እያመሩ። በፊታቸው የሚታዬው የደስታ ፈገግታ ደስ ማሰኘቱ! ይልቁንም ከት ብለው የሚስቁት ሳቅ ወፈርና ቀጠን ያሉ ድምጾች ባንድ ላይ የተዋሀዱበት ሆኖ ሌት ሁሉም ጸጥ ሲል እንደሚሰሙት አርጋኖን ልብ ሰርቆ ይሄዳል!

«እይውልሽ ከላይ ከሰባተኛው ሰማይ ‹ዱብ› አልሁ» አለ በሻህ የቀልድ ፈገግታ ፈገግ ብሎ ጉንጮቹን አገላብጠው ስመውት እሱም፥ ደመቀችም ከተቀመጡ በሁዋላ።

«ከሜቴ ጋር ከዛሬ ቀደም ተያይተን የምናውቅ አይመስለኝም፥ ማን ልበል? » አሉ ወይዘሮ ባፈና፥ ‹ከሜቴ ጋር› ሲሉ ደመቀችን አመልክተው።

«አትተዋወቁም፤ ፍል ውሀ ሀኪም ቤት የምትሰራ የኔ እት ናት። ዛሬ ረፍታቸው ስለ ሆነ ትምህርት ቤትሽን ላሳያትና ካንቺ ጋር ላስተዋውቃት ነው ያመጣሁዋት።»

«እግዚአብሄር ይስጥልኝ በሻህ እንግዲህ እንተዋወውቅ፥ እሜቴ ስሜ ባፈና ይባላል፥ ባፈና ወልደየስ።»

«ደመቀች ጸሀይ ናት። ባልለመደቻቸው ሰዎች ፊት መናገር አትፈልግም፤ ከለመደች በሁዋላ ደግሞ - ‹እኔን ስሙ እንጂ አትናገሩ› ባይ ናት» አለ በሻህ ሲቀልድ፥ ደመቀች መላስዋን እንደ ታሰረች አንገትዋን ደፍታ ዝም ስላለች።

ጥሩ ባህሪ ነው፤ የጭዋ ባህሪ። በሉ እንግዲህ ፍቀዱልኝና ቡና ልጋብዛችሁ። ከዚያ በሁዋላ፥ ላይነት ያክል አንድ ክፍል አሳይቻችሁ ወደ ስራየ እመለሳለሁ። ብዙ ስራ አለብኝ» አሉ ወይዘሮ ባፈና። ቡና መጥቶላቸው ሲጠጡ፥ ‹ይገርምሀል፥ ‹ሰዎች ይፈልጉሻል› ሲሉኝ እሰቀቅ ጀመር! በተለይ ከወጣት ሴቶች ጋር ሲመጡ ሳያቸውማ - ምን ልበልህ ብሽሽግ እወዳለሁ! አንተም ብቅ ሳትል ስለ ሰነበትህ ‹ደህና አይደል ይሆን?› እያልሁ ሳስብ ሰንብቼ፥ ዛሬ ከሜቴ ጋር ድንገት ስትገባ ሳይህ፥ ሳስብ የሰነበትሁትን ረስቼ ‹ለምን መጣብኝ?› አልሁ» አሉ ወይዘሮ ባፈና፥ ከት ብለው፥ ያን እንዳርጋኖን ወፍራምና ቀጭን ድምጾች ባንድ የተዋሀዱበት ውብ ሳቃቸውን ስቀው።

«ለምን እባክሽ? » አለ በሻህ።

«ብዙዎች ራሳቸው መጥተው፥ ሌሎች መላከተኞቻቸውን ልከው፥ ሁሉም ‹ልጆቻችነን፥ እቶቻችነን፥ ዘመዶቻችነን ትምርት ቤት አስገቢልን› የሚሉ ናቸው። ይህን ያክል ስራና ደጃዝማች፥ ፊታውራሪ፥ ባገሩ መኖሩን አላውቅም ነበር! ምናልባት ብዙዎቹ እኔን በስማቸው አባብለው፥ ወይም አስፈራርተው የሚፈልጉትን ለማስደረግ ራሳቸውን ራስ፥ ደጃዝማች፥ ብለው ሾመው እንደሆነ አላውቅም! » ብለው፥ ውብ ሳቃቸውን እንደገና ከት አሉ ሳቁና፥ «እሱ እንኩዋ ግድ የለኝም» አሉ ቀጥለው። «እኔን ያስቸገረኝ የጠዬቀኝን እንዳልቀበል፥ ቤት እስክሰራ ለጊዜው ምንም ቦታ ስለሌለኝ ከሌላ ወገን ደግም ምንም ይሁን፥ መቸም ካልተቸገሩ ልመና አይመጡምና ተቸግረው ልመና ሲመጡ፥ መግፋቱ ስለ ከበደኝ ነው። ስለዚህ ከሁሉም የሚያዋጣው መሸሽግ ሆኖ አገኘሁት እና - አንተም ከሜቴ ጋር ድንገት ስትገቡ፥ የመጣችሁለትን ሳላውቅ ለሜቴ ትምህርት ቤት ፍለጋ የመጣችሁ መስሎኝ ነበር፥ እንደምጠላህ ሁሉ ‹ምነው ባልመጣ› ያልሁ» ሲሉ ደመቀችና በሻህ ሳያስቡት እስበሳቸው ተያዩ።

«ታዲያ አሁን ሴትኛ አዳሪዎች ከነበሩት በቀር እዚህ የሚማሩ የሉም? » አለ በሻህ።

«ሴትኛ አዳሪዎች ከነበሩት በቀር እዚህ እያደሩ የሚማሩ የሉም እንጂ እዬተመላለሱ የሚማሩማ አንድ ሀያ ያክል አሉ። ብቻ ቦታ ስለ ጠበበኝ ከዚህ በላይ መቀበል አልቻልሁም።»

ከዚያ ከመማሪያ ክፍሎች አንዱን ለማየት ሄዱ። ከገቡ ሶስት ወራት የሆናቸው ልጆች የሚማሩበት ክፍል ነበር። ወይዘሮ ባፈና መዝጊያውን ቀስ ብለው መትተው እንግዶቻቸውን፥ አስከትለው ሲገቡ ልጆች ሁሉ ተነስተው ቆሙ። አስተማሪው ፊቱንም ቆሞ ነበር። «በእግዚሀር ቁጭ በሉ» አሉ ወይዘሮ ባፈና። ነገር ግን አስተማሪው እንዲቀመጡ እስኪያዝ ድረስ አልተቀመጡም። ልጆች ያስተማሪያቸውን ትእዛዝ ተቀብለው እንደ ተቀመጡ፥ ወይዘሮ ባፈና እንግዶቻቸውንና የመጡበትን ምክንያት ገልጸው ከአስተማሪውም ከተማሮችም ጋር አተዋወቁ።

እዚያ ክፍል ውስጥ የሚታዩት እቃዎች ከጀርባ ይሁን ከጎን መደገፊያ የሌላቸው ሞላላ መቀመጫዎች ለያንዳንድዋ መሳቢያ ያላቸው ተራ ጠረጴዛዎች ያስተማሪው አንድ ጠረጴዛና አንድ ወንበር፥ በግንቡ ላይ የተሰቀለ አንድ የኢትዮጵያ ካርታና በጠመኔ የሚጻፍበት ጥቁር ሰሌዳ፥ ሁሉም ተራ ሁሉም ጌጣጌጥ የሌለው፥ ሌጣ ነው። ክፍሉን ያስጌጡት ያዋቡት እኒያ ውብ አበቦች፥ እኒያ ውብ ቆነጃጅት ነበሩ። የሰውነታቸውና የልብሳቸው ጽዳት እንከን የለውም። ብዛታቸው ካምሳ አያንስም። ታዲያ ክፍሉ፥ ‹ሰፊ› የሚባል ስላልነበረ በዝተው ተጨናንቀው ነበር።

«እስቲ - ከሶስት መሰመሮች ያላነሰ፥ አንድ አረፍተ ነገር ባማርኛ አሳክተሽ በጥቁር ሰሌዳ ላይ ጻፊ» አለ አስተማሪው፥ አንድዋን ልጅ ጠርቶ። የተጠራዋ ልጅ፥ ተነስታ ከሰሌዳው አጠገብ ቆማ ካንድ ደቂቃ ያልበለጠ ጊዜ ስታስብ ቆዬችና እንደ ታዘዘችው ጻፈች።

«ጥሩ ነው፤ እግዜር ይስጥልኝ፥ ተቀመጪ» አለ አስተማሪው። እውነትም ጥሩ ነበር። ልጅቱ እጅ ነስታ ስትመለስ፥ ሌላ ልጅ ጠርቶ፥

«ሶስት ሶስት ቤቶች ያሉዋት ሁለት ቁጥሮች በሁለት ረድፍ ጽፈሽ ድምራቸውን አሳይን። እንዲሁም ሁለት ባለ ሶስት ቤት ቁጥሮች ጽፈሽ አቀናንሽና ቀሪውን አሳይን» አለ። ሁለተኛዋ ልጅ ተነስታ ሄዳ፥ ቆማ ለማሰብ ለጀመሪያዋ ልጅ የወሰደባትን ያክል ጊዜ እንኳዋ ሳያስፈልጋት ቶሎ ሁለቱንም ቁጥሮች ሰርታ አሳዬች።

«በጣም ጥሩ ነው፤ እግዜሀር ይስጥልኝ፥ ተቀመጪ» ሲል አስተማሪው፥ ሁለተኛዋም እንደ መጀመሪያዋ እጅ ነስታ ወደ መቀመጫዋ ተመለሰች። ሶስተኛዋ የተጠዬቀችው እንግሊዝኛ ነበር። በቃል ካጠናችው የንግሊዝኛ ቃላት አምስት በሰሌዳው ላይ ጽፉ፥ ያማርኛ ትርጉማቸውን እንድትናገር ሲጠይቃት አምስቱን ቃላት በጅዋ ይዛቸው እንደ ነበረ ሁሉ፥ እንደ ደረሰች በሚያስደንቅ ፍጥነት በሰሌዳው ላይ ቁጭ አደረገቻቸውና፥ ያማርኛ ትርጉማቸውን ያላንድ ስህተት ተናገረች።

«እግዜር ይስጥል፥ ማለፊያ ነው» አለ አስተማሪው ልጅትዋ እጅ ነስታ፥ ወደ መቀመጫዋ ተመልሳ ከተቀመጠች በሁዋላ።

«የዚህ ክፍል ተማሪዎች ትምህርት ከጀመሩ ሶስት ወራቸው ነው። ነገር ግን፥ በሶስት ወር ውስጥ የዘጠኝ ወር ትምርት ተምረዋል። ስለዚህ እንግዶች ቢፈልጉ፥ ‹የዘጠኝ ወር ተማሪዎች ሊያውቁ ይገባል› ብለው የሚገምቱትን ጠቅላይ ግዛት የታወቀ ተራራ፥ ወይም ወንዝ በካርታው ላይ እንድታሳይ አንድዋን፥ ልጅ ሊጠይቁ ይችላሉ» አለ አስተማሪው እግንቡላይ ወደ ተሰቀለው ካርታ እዬተመለከተ።

«አንቺ እሜቴ፥ እስቲ አባይ የሚመነጭበትንና አልፎ መጨረሻ የሚገባበትን አሳይን» አለ በሻህ እፊቱ የተቀመጠችውን ልጅ። ልጅቱ፥ እርሳስዋን ይዛ ተነስታ ወደ ተሰቀለው ካርታ ሄደችና ትንሽ እንኳዋ ሳታመነታ፥ አባይ ጎጃም ውስጥ፥ ከሰከላ ተነስቶ፥ ጣና ሀይቅ ከገባ በሁዋላ ከዚያ እንደገና ወጥቶ፥ ጎጃምን በከፊል እዬከበበ ሄዶ፥ ሱዳን ሲደርስ እዚያ ካርቱም ላይ ከነጭ አባይ ጋር ተገናኝቶ መሀከለኛ ባህር የሚገባ መሆኑን በርሳስዋ እያሳዬች በቃልዋ ስትናገር፥

‹ብራቦ! ግሩም ነው!› አለ በሻህ። አድናቆቱ ከልቡ ነበር። ልጅቱ ‹ብራቦ› ምን ማለት መሆኑን ባታውቅም፥ ከ ‹ግሩም ነው› ጋር የተነገረ ስለ ሆነ ‹ምስጋና መሆን አለበት› ብላ ገምታ ከፈገግታ ጋር እጅ ነስታ ተቀመጠች። ከዚያ ወይዘሮ ባፈና፥ በራሳቸውና በንግዶቻቸው ስም አስተማሪውንና ተማሮችን አመስግነው እንደ ወጡ፥ እንግዶችን ይዘው ወደ ጽህፈት ቤታቸው አልተመለሱም። የሚጨርሱት ስራ ስለ ነበራቸው በውጪ ተሰነባብተው ተለያዩ።

ደመቀች ስለ ሴትኛ አዳሪዎች የነበራት እምነትና ስሜት ያነለት ፈጽመው ተለወጡ። ይገርማል! ሰው እምነቱንና ስሜቱን እንዲህ በአንድ ጊዜ ይለውጣል? እንኳዋንስ ሌላ ራስዋን አስገረማት! የፍኖተ ድህነት ትምርት ቤት ቅጽር ከገባች ጀምራ ያዬችው ሁሉ ስለ ትምርት ቤቱም ስለ ወይዘሮ ባፈናና - እዚያ ስለሚማሩት

ተማሪዎችና እስከዚያ ቀን ድረስ የነበራትን እምነትና ስሜት የሚያስለውጥ ነበር። ትምርት ቤት ግርግር የሌለበት ሰላም የሰፈነበት ነበር። የሴትኛ አዳሪዎች አለቃ፥ ወይዘሮ ባፈናና ጭፍሮቻቸው ሴትኛ አዳሪዎች አሪታዊው ሰባኪ፥ ቄስ መንግሥቱ እንዳሳመኑዋት በደንጋይ ተወግረው ሊገደሉ የሚገባቸው ሀጢያተኞች፥ ጋጠወጦች ሳይሆኑ፥ እርሞች ትሁቶች፥ አዋቂዎች፥ ሆነው ታዩዋት! እኒያን ሴትኛ አዳሪዎች የነበሩ ተማሪዎች በመጥላትና በመፍራት ፈንታ ወደደቻቸው፤ አከበረቻቸው። ራስዋን ከነሱ ጋር ስታነጻጽር እስዋ ዝቅ እነሱ ከፍ ብለው ታዩዋት። ወይዘሮ ባፈና ቦታ እንደሌላቸው አምርረው ሲናገሩ ባትሰማ ኖሮ፥ ምንም ቢሆን ፍኖተ ድህነትን በሌላ ትምርት ቤት ባልለወጠችው ነበር! ያነሉቱን እዚያ በገባች ነበር። ነገር ግን፥ ያን ያክል የወደደችው መሆንዋን ያነለት ለእብሻህ አልነገረችውም።

«ታዲያ - ፍኖተ ድህነት እንዴት ነው? ጥሩ ትምርት ቤት አይመስልሽም? » አለ በሻህ የትምርት ቤቱን አጥር ወጥተው ወደ ደመቀች ቤት መንገድ እንደ ጀመሩ።»

«ጥሩ ነው» አለች ደመቀች ባጭሩ፥ ስለ ትምርት ቤቱም ሆነ ስለ ወይዘሮ ባፈናና ስለ ተማሪዎች የተሰማትን ሁሉ ቆጥባ።

«ወይዘሮ ባፈናስ ምን መሰለችሽ? »

«በጣም ትሁትና ደግ ሴት መስለው ታዩኝ። ደግሞ አንተ እንዳልኸው ልጅ ናቸው።»

«ያ አልቃሻም - ስለ ትምርት ቤቱም፥ ስለስዋም እንዲያው በማያውቀው ጉዳይ ገብቶ ይወላፍታል እንጂ፥ እስዋ ያው እንዳዬሻት ልጅ ናት። ትምርት ቤቱም በጣም ጥሩ ነው። እዚያ እገባንበት ክፍል የሚማሩ ልጆች ባፈናም አስተማሪውም እንደ እንገሩን - ትምርት ከጀመሩ ሶስት ወር ብቻ ነው። ነገር ግን ቅድም፥ እዬተጠዬቁ የመለሱትን በሌሎች ትምርት ቤቶች አንድ አመት የተማሩ ሊመልሱት አይችሉም።»

«በምን ምክንያት ነው? »

«እዚህ ትምርት ቤት በበጎ ፈቃደኝነት ያለ ደመወዝ የሚያስተምሩ አስተማሪዎች ብዙ ናቸው። የሚሰጡት ትምርቶች ግን ለጊዜው የተወሰኑ ናቸው። ያማርኛ ንባብና ጽሕፈት፥ ሂሳብ እንግሊዝኛ፥ የቤት አስተዳደር፥ ልዩ ልዩ የጅ ስራ እንዲሁም በመጠኑ ታሪክና መልክአ ምድር ብቻ ናቸው። ስለዚህ - ካስተማሪዎቹ መብዛት የተነሳ፥ የሌላ ትምርት ቤቶች ተማሪዎች በቀን አንድ ጊዜ የሚማሩት ትምርት እዚህ አስተማሪዎች

እዬተፈራረቁ ሶስት ጊዜ ከቀትር በፊትና በሁዋላ፥ ማታ እስከ ሶስት ሰአት ሰለሚያስተምርዋቸው በቀደም ‹የሶስት አመት ትምርት ባንድ አመት ያስጨርሱዋቸዋል› ያልሁዋቸው ለዚህ ነው።»

«እ - ገባኝ! ግንኮ - አሁን እኔ እዚህ መግባት ብፈልግ - ሴትዬዋ ‹ቦታ የለም› ስላሉ - መግባት አልችልም ማለት ነው? »

«አዎ ቦታስ የላትም፤ ነገር ግን ከፈለግሽ መቀመጫው ቢጠብ እንኩዋ በአንዱ ማዕዘን ወንበር ሽጉጣም ቢሆን እንድትቀበልሽ እለምናታለሁ። ብቻ ሁዋላ እንዳትጸጸቺ፥ ቀድመሽ ‹ንጋት› የሚባለውን ትምርት ቤት እይው።»

‹ንጋት› የማታ ትምርት ቤት ስለ ነበረ፥ በሳልቱ ሰኞ ማታ ከስራዋ ስትመለስ ወስዶ አሳያት። ባለቤቱ በሻህ እንዳለው የድሮ ጉዋደኛው ስለ ነበረ በደስታ ተቀብሎ፥ ትምርት ቤቱን እያዞረ አስጎበኛቸው። ሴቶችና ወንዶች አንድ ላይ ባንድ ክፍል የሚማሩበት ትምርት ቤት ነበር። ስለዚህ አስተማሪው ቆሞ ሲያስተምር ተጠንቅቀው ከሚያዳምጡት ከዬጎረቤታቸው ጋር ቀስ ብለው የሚያወሩት ይበዙ ነበር። በጥያቄም ጊዜ ሶስት ተማሪዎች በተራ - አማርኛ እንግሊዝኛና፥ ታሪክ - ተጠይቀው፥ እንግሊዝኛ የተጠዬቀችዋ ተማሪ ትክክለኛ መስል ስትሰጥ የሁለቱ መልሶች ስህተት ነበሩ።

በሻህና ደመቀች ከዚያ እንደ ወጡ የትምርት ቤቱን ባለቤት አመስግነው ወዲያውም ተሰናብተውት ወደ ደመቀች ቤት ሲሄዱ፥

«ጋሼ፥ ግልጥ አድርጌ አልነገርሁህም እንጂ እኔኮ በቀደም ያዬነውን ትምርት ቤት ፍኖተ ድህነትን በጣም ወድጀዋለሁ። ሴትዬዋ የሚቀበሉኝ ከሆነ እዚያ ልግባ» አለች ደመቀች።

«ከወደድሽው ግዴለም፥ እንደ ምንም ተቻጋግራ ቦታ እንድታገኝልሽ እለምናታለሁ። እኛም ያን ትምርት ቤት ስታቋቁም አብረናት ሳንቸር አልቀረን! አቶ ማንደፍሮ ባሳብ እኔ በስራ ረድተናል። እንዲያውም፥ ሀብትዋን ሁሉ ለዚህ በጎ ስራ ለመስጠት መወሰንዋን ስትነግረኝ፥ ላቶ ማንደፍሮ ነግሬ፥ ትምርት ቤቱ ያጭርና የረዥም ጊዜ ትምርት እንዲኖረውና ትምርቱን ከስራ ጋር ያጣመረ እንዲሆን እንዲሁም ዘላቂነት እንዲኖረው ከውጭ አገር የበጎ አድርጎት ድርጅት ጋር ግንኙነት እንዲኖረው አድርገው እቅዱን የሰሩላት፥ ከጉዋደኞቻቸው ጋር እዬተመካከሩ እሳቸው ናቸው። ስለዚህ ችግራችን ችግርዋ ስለሆነ፥ እንደ ምንም ብላ ቦታ አታጣልሽም» አለ በሻህ።

እውነትም በሻህ ወይዘሮ ባፈናን ለምኖላት ባንድ ሳምንት ውስጥ ቦታ አገኙላትና የማታ ትምርት ጀመረች።

ፍኖተ ድህነት ባጭር እስኪቀጭ ድረስ በዚያ አጭር ህይወቱ የሰጠው የምስራች ፍሬ የረዥም፥ አላማው አድርጎ የተለመው ትልም በተስፋው ድርጅቱ፥ በወጣ መምህራንና ባስተዳደር ሰራተኞች ልብ ወገኖቻቸውን ለመርዳት የቀሰቀሰው የሀዋርያነት መንፈስ መስል የሌለው ብቻውን የቆመ ነበር።

ወይዘሮ ባፈና፥ ሴትኛ አዳሪነትን ለመቃወም ትምርት ቤት ሲመሰርቱ «ሀብት አግኝተው የኖሩበትን የኑሮ ዘዴ ለመቃወም ትምርት ቤት የሚከፍቱ ለምነው? » ተብለው ሲጠየቁ፥ «ሴትኛ አዳሪነት ምን መሆኑን ስለማውቅ» ይሉ ነበር። እውነትም ከታች፣ አሻሻጭ ሆኖ ከመስራት እስከ ላይ አሻሻጮችን ቀጥሮ እስከማሰራት ድረስ ያለፉበት ከመሆናቸው ሌላ፥ ጠላት ኢትዮጵያን ይዞ በቆየበት ጊዜ በሰፈራቸው የሴትኛ አዳሪዎች ሁሉ አለቃ ሆነው በተሹመው አዲስ መጪዎችን እዬመለመሉ ቦታ ሰጥተው የሚያስቀምጡና ተመልምለው የሚቀመጡትን እዬተቆጣጠሩ የሚያስተዳድሩ ስለ ነበሩ፥ ሴትኛ አዳሪነት ህይወት ምን መሆኑን ከማንም የበለጠ የሚያውቁ ነበሩ። በጠላት ይዞታ ጊዜ እያንዳንድዋ፥ ሴትኛ አዳሪ ስትመለመል፥ ስምዋ ከነወላጆችዋ እድሜዋ፥ የተወለደችበት አገር፥ ሴትኛ አዳሪ ለመሆን የፈለገችበት ምክንያትና ሌላም እነዚህን የመሳሰሉ ዝርዝሮች ይጻፉ ስለ ነበረ፥ ይህ ለረዥም ጊዜ እቅዳቸ ጠቀማቸው። የረዥም ጊዜ አላማቸው በግዜው የነበሩን ሴትኛ አዳሪዎች ሌላ ትምርትና ስራ አስተምሮ ሴትኛ አዳሪነትን ማስተው ብቻ ሳይሆን የሴትኛ አዳሪነትን በሽታ የሚፈጥሩን ምክንያቶች አውቆ ማጥፋት ጭምር ነበር።

ከዚያ፥ አዲስ ምልምሎች ከሚያስፋት ዝርዝር እንደ ተመለከቱት አብዛኞቹ፥ ምናልባት ከሙቶ ዘጠና አምስት በላይ የሚሆኑት ሴትኛ አዳሪዎች መሆን የሚፈልጉበት መከንያት፥ በጥቃቅን ዝርዝር ቢለያይም አይነተኛው አንድ መሆኑን ተረዱት። የሴትኛ አዳሪነት መነሻው ምንጬ አንድ መህኑን አወቁ።

በጠቅላላው አነጋገር፥ ሴትኛ አዳሪዎች የሚሆኑ ሴቶች ተወልደው ባደጉበት አገር ባል አግብተው ቤት ንብረት ይዘው፥ ልጅ ወልደው የቤት እናትነት ለሚሰተው መብትና ለሚያስከትለው አላፊነት እንደሚበቁ አድርገው ወላጆቻቸውም ይሁኑ ማህበራቸው ሳያሰናዱዋቸው ይቀሩና፥ ባል ሲተዋቸው ሌላ የሚይዙት፥ የሚጨብጡት ለመኖር፥ ተስፋቸውን የሚያሳርፉበት ያጣሉ። መኖር እንደማይችሉ ተስፋ ይቆርጣሉ። ከዚያ፥ ያ የጥንቱ ሳያሰናዳ መሳሪያ ሳያስይዝ፥ ከአለም ልዩ ልዩ ችግር ጋር ታግለው ድል

እንዲሆኑ፥ ያጋፈጣቸው ማህበር ሁዋላ ደግሞ ድል በመሆናቸው ከሰወንት ተራ ያወጣቸዋል! በውስጡ ቦታ የሌላቸው ትርፎች ያደርጋቸዋል! በማህበር ውስጥ ቦታ የሌለው መኖርም የለ! እያሉ አለመኖር የማይቻል እጅግ ከባድ ነገር ነው። ስለዚህ እያሉ እንዳይኖሩ በፈረደባቸው ግፈኛ ማህበር ላይ ሸፍተው መስሪያ ሁሉ ቆርጠው ስም፣ ክብር ጸያፍ፥ ነውር የሚባለውን ማህበር ዝባዝንኬ ሁሉ እዚያው አውልቀው ጥለው በማይታወቁበት የከተማ ጫካ በማይታወቁበት የከተማ ዱር ተሸሽገው ሌላ ስለሌላቸው ሰውነታቸውን እዬሸጡ ለመኖር ይሰደዳሉ! ተወልደው ያደጉበትን አገር ትተው መሰደዳችው መኖር ተነፍገው መኖር ፍለጋ፥ ስለሆነ ከዚያ ወዲያ ትግላቸው ሁሉ ለመኖር ብቻ ይሆናል! መብት፥ ግዴታ፥ ተስፋ፥ የህይወት፥ አላማ ሁሉ እዚያው ከማህበሩ ጋር የቀረ ስለሆነ አላማቸው መኖር ብቻ ይሆናል ለመኖር ሁለመናቸውን መስዋእት አድርገው ይሰጣሉ! ለመኖር መንፈሳቸው ኩራትን ልባቸው መውደድ መጥላትን አካላቸው ስሜትን ይተዋል! በዝሙት ስራ እንኩዋ ሌሎችን ደስ አሰኝተው መኖሪያ ማግኘት እንጂ ራሳቸውን ደስ ማሰኘቱ ይቀራል! ለሌሎች ደስታ የሚኖሩ ይሆናሉ!

ወይዘሮ ባፈና ላቆቁዋሙት፥ ትምርት ቤት የገንዘብ የቃ፥ ወይም ያስተማሪዎች ርዳታ ለማግኘት እዬዞሩ በሚለምኑበት ጊዜ የሴትኛ አዳሪዎችን ህይወት ሲያነሱ አይኖቻቸው እንባ ይሞሉና መሀረባቸውን ከቦርሳቸው አውጥተው አይኖቻቸውንም አፍንጫቸውን እዬጠራረጉ፥ «የሚኖሩበትን ስቃይ ባታውቁትኮ ነው! » ይላሉ።

«ሆ ሆ! ሴትኛ አዳሪዎች ደግሞ ምን ስቃይ አለባቸው እባክዎን! አጊጠው ቁጭ ብለው ደስታና ገንዘብ ይዘውላቸው ከሚመጡት ሁሉ ጋር አብሮ እዬተኙ ገንዘብ መሰብሰብ ነው ስቃዩ? » አለ አንድ ቀን እንዲያስተምሩላቸው ለመለመን በቀጠሮ ተሰብስበው ከተቀበሉዋቸው ወጣት አስተማሪዎች አንዱ።

«እሱም ቢሆንኮ በመጠኑ አንድ ስቃይ ነው! »

«እንዴት? ምኑ? »

«ውስጥ ውስጡን እዬተሰቀዩ ውጪን ደስተኛ መስሎ ለመታየት መጣጣሩ፥ የሰውነትን ጉስቁልና በንጹህ ልብስና ጌጥ የልብን ልቅሶ በጥርስ ሳቅ ለመሸፈን መታገሉ! ይህም በመጠኑ አንድ ስቃይ ነው። ዋናው ስቃይ ግን ሌላ ነው። ዋናው ስቃይ ልብ

ከማይፈቅደው እንዲሁ አልፎ ሲሄድ ባይን ለማየት እንኩዋ ከሚጸየፉት ጋር ሰውነትን አሰራቁቶ እንዲተቃቀፉ መገደዱ ነው! እንኳን ለሁልጊዜ ላንድ አፍታስ ቢሆን ልብስን አልቆ የሚጠላትና የሚጸየፉትን አቅፎ ከመተኛት የከበደ ነገር አለ? እንደኔ እንደኔ እንዲያ ካለ ስቃይ የሚበልጥ ስቃይ የለም፤ ከሱ የማይመረጥ ነገር የለም! »

«እሱስ እውነትዎ ነው፤ የሚጠሉትንና የሚጸዩፉትን ነገር እንኩዋንስ ማቀፍ በጥፍር መንካቱም ይቀፋል። ብቻ እሱ ወደው የገቡበት አደለም? ማን አስገደዳቸው? »

«አይ ወንድሜ! ግድ ካልሆነ የሚጠላውን ወዶ የሚያደርግ አለ? »

«እኮ ታዲያ ማን አስገደዳቸው? »

«በመጀመሪያ የመኖር ፍላጐት አስገድዶዋቸው ወዲያውም እንዲህ ያለ ስቃይ ያለበት ስለማይመስላቸው ይገቡበታል። ከገቡበት በሁዋላ ግን ቢጠሉትም ከሱ በቀር ሌላ የሚኖሩበት መንገድ ስለሌላቸው ይገፉበታል። የመኖር ፍላጎት እጅግ ብርቱ ነውኮ የማያስደርገው የለም። «ውሀ ውስጥ የገባ የዋና ተማሪ፥ ማእበል ቢደርስበው የሚይዘው ሌላ ካጣ እሾህ ይጨብጣል» የሚሉትን ተረት አልሰማችሁም? እሾህ የሚያስጨብጥ የመኖር ፍላጎ ነውኮ! ብቻ ዋና አዋቂዎች እዳር ቆመው ጭንቀቱ ስለማይሰማቸው በሾህ ጨባጩ ይስቁበታል። የኒያን ልጆች ስቃይ የማያውቅም እንደዚያው ነው። የህይወት ማእበል የኑሮ ማእበል ክፉ ነው። አያደርጉትን ያስደርጋል! በተለይ በጠላት ይዞታ ጊዜ የነበረውንማ እንዲያውም አለማንሳት ነው! ከጠላት ወረራ በፊት የነበረው እንኩዋን፥ ምንም ክፉ ቢሆን በጠላት ጊዜ የነበረውን ያክል አይከፋም። ከጠላት በፊት እንደ ሸቀጥ እቃ ዋጋዋን በውበትዋ መጠን ተምነው ለሽያጭ የሚያስቀምጡዋት ሴት አልነበረችም። ከዚያ በፊት የነበሩት ሴቶች መሸታ ቤት ከፍተው ለመጠጥ ከሚመጡት ወንዶች ጋር ሲፈቃቀዱ የዝሙት ስራ የሚፈጽሙ ነበር። ወንዱ ደስ ሲለው ስጦታ ሰጥቶ ይሄዳል እንጂ ዋጋ የሚባል ነገርም አልነበረም። እና እዩትላችሁ፤ በዚያን በጠላት ጊዜ ያዩሁትንና፥ ያ ልማድ ሆኖ ከዚያ በሁዋላ የቀጠለው ስቃያቸው ነው ዛሬ እረፍት አሳጥቶ እንዲህ የሚያንከራትተኝ።»

«እንዴት? »

«በጠላት ይዞታ ጊዜ ሴትኛ አዳሪ እንዲሆኑ እዩተመለመሉ የተቀመጡ ሴቶች ለመብል እንደ ቀረቡ ከብቶ የራበው ወንድ ሁሉ የሚቀራመታቸው ፍጡሮች እንጂ

‹ስዎች ነበሩ› ለማለት ያስቸግራል። ሴት ሲርበው ኖኦር ከጦር ግንባር የተመለሰው የሰከረው፥ የታመመው ሁሉ ገንዘብ ይዞ ከመጣ ልጆቹ እንደ ማናቸውም ሸቀጥ ዋጋቸው በውበታቸው ደረጃ የተቆረጠ ስለ ነበረ ገንዘቡ ሊገዛት የቻለውን እንደ ፈለገው ማድረግ የተመረቀለት መብቱ ነበር! ሴትዋ ግን እንዲያ ተጎሳቁሎ የመጣውን ሁሉ ተቀብላ ፈቃዱን መፈጸም ነበረባት። የመጥላትና የመጸየፍ ይቅርና፥ የመድከም እንኩዋ መብት አልነበራትም! »

«በሽተኛ ቢሆንም? »

«አዎ በሽታው በውጭ ጎልቶ የማይታይበት ከሆነ፥ በሽተኛ ቢሆንም ተቀብላ ፈቃዱን ለመፈጸም አለባት። ካንዱ የተቀበለችውን በሽታ ለሌላ እንዳታስተላልፍ በዩጊዜው የመመርመር ግዴታ ያለባት ሴትዋ ናት እንጂ፥ ወንዱ ጠያቂ አልነበረውም። ከዚያ ደግሞ የበለጠ የሚያስገርመው እኒያ ልጆች፥ እንዲያ ያለውን ስቃይ ሁሉ አልፈው የሚያስገኙት ገንዘብ፥ ለነሱ የሚደርሳቸው ጥቂቱ ክፍል ነው። አብዛኛው ለመንግሥት ግብርና ላስተዳዳሪዋ ይሄዳል! »

«ይገርማል! አዩ? እሜቴ፥ መቸም እኛ ሴትኛ አዳሪዎች ያለ ከባድ ስራና ኣላፊነት ደስ ብሎዋቸው የሚኖሩ እንጂ፥ እንዲህ እርስዎ እንዳሳዩን ባለ ክፉ ህይወት ውስጥ የሚኖሩ አይመለንም ነበር። መቸም እርስዎ የነሱን ኑሮ የገሀነም ኑሮ አስመስለው ነው የተረኩልን። ለመሆኑ እርስዎ እንዴት አወቁት? » አለ ጥያቄው የሚገባ መሆን አለመሆኑን በመጠራጠር ከጠየቀ በሁዋላ የጉዋደኞቹን አይን እያለዋወጠ አንድ ባንድ አይቶ። ሁሉን እንደ ማፈር ብለው አንገታቸውን ደፉ።

«ህም -! እኔም አንድ ጊዜ ሴትኛ አዳሪ ነበርሁ! » ሲሉ፥ እዚያ የተሰበሰቡት መምህራን ሁሉ ደንግጠው አይናቸው በጥፍ ወጣ።

«አዎ፥ እንዲያውም በጠላት ይዞታ ጊዜማ፥ በሰፈሬ፥ የሴትኛ አዳሪዎች ሁሉ አለቃ ነበርሁ። በጠላት ይዞታ ጊዜ፥ የሴትኛ አዳሪዎች አስተዳዳሪ ሆኘ፥ አሁን እንደ ነገርሁዋችሁ ከነሱ የስቃይ ዋጋ አብዛኛው እዬወሰድሁ፥ ባለ ብዙ ገንዘብ ባለ ብዙ ርስት ባለ ትልቅ ፎቅ ቤት፥ ባለ ማለፊያ ኦቶሞቢል ሆንሁ! ስለዚህ እንዲያው ግምት ሳይሆን፥ ራሴ ያለፍሁበትን በሁዋላም ምስክር ሆኘ በቅርብ የተመለስሁትን ስቃይ ነው የምነግራችሁ» አሉና ወይዘሮ ባፈና በፈንታቸው አይናቸውን በጥፍ አውጥተው መምህራኑን እያለዋወጡ ሲያዩ እነሱ፥ አይናቸውን ወደ መሬት መለሱ።

«የሚያስገርም ነው! » አለ አንዱ ሁሉም ዝም ብለው ከቆዩ በሁዋላ። «ታዲያ አሁን - ሴትኛ አዳሪዎች ‹ገና ተምራችሁ ሌላ ስራ ታገኛላችሁ› ቢሉዋቸው የሩቅ ተስፋ፥ አምነው ለለት የሚያኖራቸውን ስራ እዬተዉ ትምርት ቤት ለመግባት የሚፈቅዱ ይመስልዎታል? የሚፈቅዱ ቢሆኑስ - እንዴት ሆነው እዬኖሩ ይማራሉ? »

«ይገርማችሁዋል! ምንም እንኩዋ ይህ ትምርት ቤት የሚከፈት መሆኑ ከተገለጸ ጊዜው በጣም አጭር ቢሆን ባንድ ወር ውስጥ ብቻ ከሶስት መቶ በላይ መዝግበናል። ከዚያ በሁዋላ ያሰናዳሁት ምኝታ ቤት የማይበቃ ስለሆነ፥ ተጨማሪ ምኝታ ቤት እስካዘጋጅ የሚመጡትን ሁሉ መመለስ ግድ ሆነብኝ። ስለዚህ የኛ አቅም ካልወሰነን ሴትኛ አዳሪዎች ሁሉ መማር እንደሚፈልጉ እርግጠኛ ነኝ።

‹እንዴት ሆነው እዬኖሩ ይማራሉ?› ብላችሁ ለጠዬቃችሁኝ - ህም - ! ቅድም ጫፉን እንደ ነካሁላችሁ ርስትና ጌጥ የገዛሁበትም ሆነ ፎቅ ቤት የሰራሁበት፥ እንዲሁም በባንክ ያጠራቀምሁት ገንዘብ የኔ አይደለም። አስተዳደራቸው የነበሩ የብዙ ሴተኛ አዳሪዎች አይታወቅ፥ ስሜት ያደነዝዛል መስለኝ! በውስጡ ላሉ መጥፎነቱ አይታወቅም ስሜት ያደነዝዛል መሰለኝ! የሚታየው ካለፈ በሁዋላ ነው። እኔም ጊዜ ጥፋቴ ጎልቶ የታዬኝ ቀን እረፍት፥ ሌት እንቅልፍ የከለከለኝ አሁን ነው። ስለዚህ ምንም እንኩዋ ዛሬ ከነሱ የሚበዙት ባይኖሩ በነሱ እግር ተተክተው ለዚያ አሳዛኝ ኑሮዋቸው ወራሾች የሆኑ ሁሉ እንዲያ ካለው ኑሮ መውጫ እንዲሆናቸው ለኔ መጠነኛ ኑሮ የሚበቃኝን አስቀርቸ ለነሱ ሰጠሁት። ካስተማሪ በቀር ምንም የሚጎድለኝ ነገር የለም።

«ባንክ ከነበረኝ ገንዘብ ሌላ፥ ከተማና የባላገር ርስቴን፥ እንዲሁም ጌጤን ሸጨ በርከት ያለ ገንዘብ አግኝቻለሁ። በዚህ ላይ የወር ገቢ የሚሰጠው በመሀል ከተማ ሱቆች አሉኝ። ይህ እንግዲህ ለመነሻ ያክል ለጊዜው ነው እንጂ ለወደፊቱ ለዘለቃው፥ ድርጅቴንን ከትልልቅ የበጎ አድርጎት ድርጅት ጋር አዛምጀ እነሱ ተባብረው የሚረዱት የነሱ ክፍል እንዲሆን ነው የታሰበው። ነጻ አገልግሎት የሚሰጡ አስተማሪዎች የምፈልግም ለጊዜው ነው። ለወደፊቱ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን መንፈሳዊ ጉባኤ የስዊድን ያሜሪካ የንግሊዝ፥ የካቶሊክና ሌሎች ሚሲዮኖች በነሱም አማካይነት ልዩ ልዩ የውጭ አገር የበጎ አድራጎት ማህበሮች ለዚህ ድርጅት የገንዘብና ሌላም ድጋፍ እንደሚያደርጉ በጽሁፍ ቃል ገብተዋል። እንዲያውም ሁለት የውጭ አገር የበጎ አድርጎት ድርጅቶች ለዚህ ትምርት ቤት፥ ባመት ደንበኛ ወጫቸው ውስጥ የተወሰነ ገንዘብ የሚመድቡለት መሆናቸውን በጽህፈት አስታውቀውኛል። አሁን

የቆተርሁዋቸው የኢትዮጵያ ቤተክሲያን መንፈሳዊ ጉባኤና ባገራችን የተቋቋዋሙት ሚሲዮኖች እግዚአብሄር ይስጣቸውና ለምቆቁዋሚያ የሚሆን ገንዘብ ረድተውኛል። ስለዚህ ምንም እንኩዋ ቀለብ ልብስና መኖሪያ ችለን የምናስተምር መሆናችን ተስፋፍቶ ሲታወቅ፥ ካዲስ አበባም ሆነ ከሌሎች ከተሞች የሚሰበሰቡ ሴትኛ አዳሪዎች እጅግ ብዙ መሆናቸው የማይጠረጠር ቢሆን እስካሁን ካገኘሁትና ወደፊት እንዳገኝ ከተሰጠኝ የተረጋገጠ ተስፋ ስመለከተው ለመኖሪያ ለቀለብና ለልብስ የሚሆን ገንዝብ አልቸገረም። ለጊዜው ያውም ለጊዜው የሚቸግረኝ አስተማሪ ነው። በዚህ እናንተ ብትረዱኝ ድርጅቱ፥ ድርጅታችን ተሙዋልቶ ስራ ሊጀምር ይችላል። እባካችሁ ርዱኝ። እባካችሁ ተረዳድተን እቶቻችሁን ወደ ሰውነት ማእረጋቸው እንመልሳቸው። ያለዚያ እንዲሁ ከተተዉ እነሱም መበቀላቸውን ይቀጥላሉ! »

«እንዴት? ማነን ነው የሚበሉ? » አለ አንዱ ወጣት።

«የበደላቸውን፣ ማህበራቸውን።»

«እኮ - እንዴት? » አለ ወጣቱ ሴትኛ አዳሪዎች ማህበሩን ሊበቀሉ የሚችሉበት መንገድ አልታዬው ስላል፥ ግር ያለው መሆኑ ከፊቱ እዬታዬ።

«በል አግብተው ልጆች ወልደው ቤተሰባቸውን ስራ፥ ይዘው አገራቸውን በመርዳት ፈንታ የተጋቡትን እያፋቱ፥ ባለስራዎችን ስራ እያስፈቱ በልጅ ፈንታ በሽታን እዬወለዱ ላገር እዬሰጡ መበቀላቸውን ይቀጥላሉ! »

«ህም -! ‹በልጅ ፈንታ በሽታን እዬወለዱ ላገር እዬሰጡ!› ትሰማላችሁ? » አለ ወጣቱ፥ ዝም ብለው ወደሚያዳምጡት ጉዋደኞች ዘወር ብሎ።

«አዎ፥ ሰማን» አለሌላው ባዘነ ድምጽ በጉዋደኞቹ ስም ለመመለስ ፈቃድ እንደሚጠይቅ አንገቱን ከደፋበት ቀና አድርጎ ሁሉንም አንድ ባንድ ከተመለከተ በሁዋላ።

«ታዲያ ምን ይዤ ልመለስ? እሺታችሁን? ወይስ -» አሉ ወይዘሮ ባፈና፥ በጣም በሚያሳዝን ፊት። ወጣቶቹ የወይዘሮ ባፈናን የቃል ብቻ ሳይሆን ያይኖቻቸውንና፥ የፊታቸውን ልመና አይተው እስበሳቸው ሲተያዩ ሁሉም ለመርዳት ፈቃደኞች መሆናቸው በዬፊታቸውስ በጉልህ ተጽፎ ይነበብ ነበር።

«እንግዲህ ባለ በጎ ስራ እርስዎ ገንዘብዎን በሙሉ ሲሰጡ፥ ትርፍ ጊዜያችነን ብንሰጥ ያንስ እንደሆነ እንጂ መች ይበዛል እሜቴ? » አለ አንዱ።

«እንዲህ ጎልቶ ለሚታይ ጥሩ አላማ ‹ርዳ› ሲሉት ‹አልረዳም› የሚል የሚኖር ይመስልዎታል? » አለ ሌላው።

«እውነት ተማሪዎች ለመማር ፈቃደኞች ከሆኑና ሌላ ድርጅትዎ ከተሙዋላልዎ፥ ባስተማሪዎች በኩል ላለብዎ ችግር ዘላቂ መፍትሄ እስኪያገኙ ድረስ ግዴለም፥ እኛ አለንልዎ፣ እሜቴ። ከኛም ሌላ የሚያስፈጉዎትን ያክል ወንድም ሴትም አስተማሪዎች ለማምጣት እኛ አላፊዎች ነን። ብቻ ለመጀመሪያ እዚህ ያለነውን ይጻፉ። በነጻ ተቀጥረናል! » አለች ደግሞ አንድዋ ወጣት።

«በነጻ ተቀጥረናል! » አሉ ሁሉም እዬተቀባበሉ።

«ወይዘሮ ባፈና ያነለት ደስ ያላቸውን ያክል መቸም ደስ ብሎዋቸው አያውቅ! ያነለት ድርጅታቸው ሁሉ ተሙዋልቶ ስራቸው ሁሉ ተፈርሞ ሴትኛ አዳሪዎች ሁሉ ትምህርታቸውን ጨርሰው በልዩ ልዩ የክብር ስራ ሲቀጠሩ ያዩዋቸው መሰላቸውና እመጨረሻ ግባቸው የደረሱ መስሎ ታያቸውና፥ ነፍሳቸው በሙሉ ብጻት ከውስጣቸው መጥቃ ሰማየ ሰማያት ያረገች መስሎ ተሰማቸው! እንዲያ ያለ ስሜት የሚፈጥር ደስታ እንዴት አድርጎ ይገለጻል? እንዲያ የተሰማቸውን ደስታ ለወጣቶቹ የሚገልጹበት ቃል ስላጡ አይኖቻቸው እንባ እንደ መሉ ሲርገበገቡ ፊታቸው በውብ ፈገግታ እንዳጌጠ ጥርሳቸው ተገልጦ ከንፈሮቻቸው ሲንቀጠቀጡ፥ እንዲሁ ጠቅላላ ሁኔታቸውን ተመልከተው የደስታቸውን ሀያልነት እንዲረዱ ዝም ብለው እፊታቸው ቆመ ያዩዋቸው ነበር። ወጣቶችም ለወይዘሮ ባፈና የሰጡት የርዳታ ቃል ኪዳን ያን ያክል ከፍተኛ ዋጋ ያለው ያን ያክል ትልቅ መሆኑን አውቀው ደስ ያላቸው የሳቸውን ደስታ ሲያዩ ነበር።

ወይዘሮ ባፈና ከዚያ ወጥተው ከደስታቸው ጋር እዬተጫወቱ በመንገድ ከሚተራመሰው አቶሞቢል ጋሪ፥ አህያና፥ ሰው እንዳይጋጩ፥ አእምሮዋቸው ሳይሆን ደመነፍሳቸው ብቻ እዬመራቸው እግራቸው መሬት መንካቱ ሳይሰማቸው እንዲሁ ላይ ላዩን እያንዣበቡ እቤታቸው ደረሱ።

«ቀናኝኮ፥ እሁ - ቀናኝ! አስተማሪዎች በነጻ አገኘሁ! እንግዲህ እግዜር ይመስገን ተያያዘ፤ ሁሉም ተከናወነ» አሉ የግቢያቸውን በር እንደ ገቡ፣ መጀመሪያ ላገኙዋቸው አነጋግረዋቸው ለማያውቁ ደንጋይ የሚያግዙ ኩሊዎች።

«ሴትዮዋ ምን ሆኑ እባክህ? ብቻቸውን ይነጋገራሉ» አለ ከኩሊዎቹ አንዱ፥ በዝቅተኛ ድምጽ፣ እንዳያዩት፥ ፊቱን ከሳቸው ወደ ጉዋደኛው አዞሮ እዬሳቀ።

«ኧረ ካልሀስ አካሄዳቸውም የጤነኞችን አይመስል! ‹ፉት› የሚባለውን ‹ስምጥጥ› አድርገውታል መሰለኝ» አለ ሁለተኛው እሱም እንዳይሰሙት እንደ ጉዋደኛው ድምጹን ዝቅ አድርጎ።

ባጭር ጊዜ ውስጥ ለቀለምና ለጅ ስራ አስተማሪነት የተመዘገቡት ሴቶችና ወንዶች አስተማሪዎች ብዙ ነበሩ። ስለዚህ አስተማሪዎች በተማሪዎች ላይ እዬተለዋወጡእ እንደዬ ነጻ ጊዜያቸው ጥቃት ከቀትር በሁዋላና ማታ እስከ ሶስት ሰአት እንዲያስተምሩ ተደረገ። መቸም ያስተማሪዎችም ሆነ የተማሪዎች ትጋት የሚያስገርም ነበር!

አስተማሪዎች ለጥዋት የተመደቡት ጥዋት፥ ለቀትር በሁዋላ የተመደቡት ከቀትር በሁዋላ ለማታ የተመደቡት ማታ ወደ ፍኖተ ድህነት ሄደው ለማስተማር ፊታቸውን ሲያዞሩ ወደሚወዱት የጭዋታ ቦታ እንደሚሄዱ ልባቸው አስቀድሞ በደስታ ይጨፍር ነበር። ያላንድ ቀይ ስናቲም በነጻ፣ ያገልግሉ ለነበሩ ሁሉ ለመጀመሪያ ጊዜ፥ ጊዜያቸውን ምቾታቸውን መስዋእት አድርገው ርዳታ የሚፈልጉ ወገኖቻቸውን ለመርዳት መቻላቸው አገልግሎት የሚፈልጉ ወገኖቻቸውን ለማገልገል መቻላቸው የልብ ደስታን፥ ከመንፈስ ኩራት ጋር ይሰጣቸው ነበር።

የወይዘሮ ባፈና ትምርት ቤት ፍኖተ ድህነት ያጭርና የረዥም ጊዜ ትምርት ለመስጠት የታቀደ ነበር። የመጀመሪያ በድሜ ትንሽ ጸና ያሉትን ተማሪዎች እንደ እድሜያቸው ደረጃ ሁለትና ሶስት አመት ያማርኛ ንባብና ጽህፈት በመጠኑ፥ እንግሊዝኛ ንባብና ጽህፈት እንዲሁም በመጠኑ ሂሳብ የመዝገብ አያያዝ ጭምር፥ የቤት አስተዳደርና ልዩ ልዩ የጅ ስራ አስተምሮ በዬተማሩት ትምህርት ስራ እንዲይዙ ማድርግ ነበር። ሁለተኛው የረዥም ጊዜ እቅዱ፣ ወጣትነት ያላቸውን ተማሪዎች ጠለቅ ያለ ትምርት በተለይ ማህበራዊ ኑሮ ነክ የሆኑትን ትምርቶች አስተምሮ፥ ለሴትኛ አዳሪነት በሽታ መነሻ ወይም ጠንቅ፥ የሆኑትንና፥ ሊሆኑ የሚችሉትን ነገሮች ሁሉ ከማህበሩ ውስጥ ለማጥፋት ሰራተኞች፥ አስተማሪዎችና፥ አማካሪዎች ሆነው እንዲሰሩ ማድረግ ነበር። ፍኖተ ድህነት ከሌልቾ ትምህርት ቤቶች የሚለይበት አይነተኛው ነገር፥ ወይዘሮ ባፈና «ሞግዚት» ብለው በሰዬሙት ክፍሉ ነበር። ያ ክፍል ስራው - ትምርታቸውን ጨርሰው የወጡ ተማሪዎች ስራ ሲያጡ ወደ ሴትኛ አዳሪነት እንዳይመለሱ ካንድ ወገን፥ ከመንግሥትና ከግል መስሪያ ቤቶች ጋር የተቀራረበ ግንኙነት መስርቶ ስራ በሚገኝበት ማስቀጠር ሲሆን ከሌላ ወገን በመንግሥትና በግል ድርጅቶች ውስጥ ቦታ ላልተገኘላቸው ልጆች ብድር መሪና ተቆጣጣሪ እዬሰጠ፥ በዬተማሩት ትምርት ራሳቸውን ችለው የግል ስራቸውን እንዲከፍቱና እዬተቆጣጠሩ ብድራቸውን በዬጊዜው እንዲመልሱ ማድረግ፥ ነበር። ትምርት ቤቱን ከሁሉም ያስደነቀው፥ ይህ ትምርት ከስራ

ጋር አያይዞ መስራቱ ያሳዬው እጅግ ደስ የሚያሰኝ ውጤት ነበር። ፍኖተ ድህነት ትምርት መስጠር ከጀመረ በሁለተኛው አመት መጨረሻ ላይ የተመደበላቸውን ትምርት ጨርሰው የወጡት ሁለት መቶ ያክል ተማሪዎች ጥቂቱ ባል አግብተው ትዳር ሲይዙ የሚበዙትን የመንግሥትና የግል ድርጅቶች ቀጠሩዋቸው። በመንግሥትና በግል መስሪያ ቤቶች ቦታ ያልተገኘላቸው በ «ሞግዚት» በኩል ትምርት ቤቱ ሰርተው የሚመልሱት ብድር ሰጥቶዋቸው የግላቸውን የጅ ስራ ድርጅት እዬከፈቱ በመስራትም በማስተማርም፥ ራሳቸውን መቻል ብቻ ሳይሆን፥ ለሌሎችም ስራ ለመስጠት በቁ።

ደመቀች ምንም እንኩዋ ትምርት የጀመረች ትንሽ ዘግየት ብላ ቢሆን አስቀድማ ዳዊት የደገመች ስለ ነበረችና ያማርኛ ጽህፈት እንጂ ንባብ መማር ስላልነበረባት አሳብዋንና ጊዜዋን በሌሎች ትምርቶች ላይ አተኩራ በርትታ በማጥናትዋ ከሁለት አመት ተማሪዎች ጋር የተመደበውን ትምርት ጨርሳ ወጣች።

ለሁለት አመት የተመደበው ትምርት ጨርሰው የወጡት የጥንት ሴትኛ አዳሪዎች ተቀጥረውም፥ የዬራሳቸውን ስራ ከፍተኛውም የክብር ኑሮ በመመስረት ላይ መሆናቸውን የሶስተኛ አመት ተማሪዎች ሲያዩ ትምርታቸውን ሲጨርሱ የክብር ስራ ይዘው የክብር ኑሮ እንደሚኖሩ ሰዎች የነገሩዋቸውም ራሳቸው ተስፋ ያደረጉትም እድኒሁ ወሬና ተስፋ ብቻ አለመሆኑን፥ እውነት መሆኑን፥ ባይናቸው አይተው ስለ ተረዱ፥ እነሱም ቶሎ ጨርሰው የሚጠብቃቸውን የተሻለና የተረጋገጠ ስራ ለመያዝ ይናፍቁ ነበር። መቸም የወይዘሮ ባፈና ደስታ ዳር ድንበር አልነበረውም! ወይዘሮ ባፈና የትምርት ቤታቸውን የመጀመሪያ ፍሬ፥ የምስራቹን ሲያዩ እሱ ራሱን ብቻ ሳይሆን ከሱ ባሻገር የመጨረሻ ግባቸውን መልካም ፍጻሜ ጭምር አሳያቸውና ደስታቸው የደስታ ወሰን ሁሉ ያለፈ ሆነ! ልባቸው ከደም ጋር ደስታ ጭምር በህዋሳታቸው ሁሉ ይነዛ ይመስል ልባቸውን ብቻ ሳይሆን ህዋሳታቸውን ሁሉ ደስታ ተሰማቸው!

የፍኖተ ድህነት ተማሪዎች ተመርቀው በሚወጡበት ቀን በአሉን እንዲያከብሩ ከተጋበዙት ብዙ እንግዶች ጋር ለትምርት ቤቱ የገንዘብ ርዳታ ያደርጉ የነበሩት አብያተ ክርስቲያንና የበጎ አድራጎት ድርጅቶች ተጋብዘው፥ ሁሉም እንደራሴዎቻቸውን ልከው ነበር።

እኒያ የልዩ ልዩ መልክተኞች፥ የሁለት አመት ትምርታቸውን ጨርሰው የተመረቁትን ተማሪዎች፥ ተሰልፈው እያንዳንዳቸው በተራ እዬቀረቡ ገና ትምርት ቤት እንዳሉ በ «ሞግዚት» አማካይነት የተሰናዳላቸው ስራ እዬተነገራቸው የምስርክ ወረቀታቸውን ከወይዘሮ ባፈና እጅ ሲቀበሉ ሲያዩ እጅግ ደስ አላቸው። ይልቁንም

ምረቃው ስነ ስራት በፊት የትምርት ቤቱ ትምርት አሰጣጥ ላጭርና ለረዥም ጊዜ የታቀደ ሆኖ ያጭር ጊዘ አላማው ሴትኛ አዳሪነትን ማጥፋት የረዥም ጊዜ አላማው ለሴተኛ አዳሪነት መፈተር ምክንያት የሆኑትን ጠንቆች ከማህበሩ ውስጥ ማስወገድ መሆኑን እንዲሁም ትምህርታቸውን ጨርሰው የወጡ ተማሪዎች ስራ ሲያጡ እንደገና ወደ ሴተኛ አደሪነት እንዳይመለሱ፥ ወደ ስራ መስክ የሚሰማሩበትን መንገድ የሚያሰናዳ አንድ ሌላ አካል በውስጡ ያለው መሆኑን ይህን ሁሉ የሚያመለክት የድርጅቱ ስእል በሰሌዳ ላይ ከአጫጭር የጽሁፍ መግለጫ ጋር ተስሎ ሲያዩና በያንዳንዱ ርእስ ላይ የተሰጠውን ዝርዝር መግለጫ ሲሰሙ ከመደሰትም አልፈው በጣም ነበር የተደነቁ። ስለዚህ ድርጅቶቻቸውን ለፍኖተ ድህነት እስከዚያ ድረስ ያደርጉት የነበረውን የገንዘብ ርዳታ ከፍ ማድረግ ብቻ ሳይሆን በተለይ ለረዥም ጊዜ እቅዱ ከፍተኛ ትምርትና፥ የረዥም ጊዜ ልምድ ያላቸው አስተማሪዎችና አስተዳዳሪዎች ጭምር ቀጥረው እንዲሰጡ ባንድነት አሳብ ለማቅረብ ተስማሙ። መልክተኞቹ ሁሉ ባንድነት ፈርመውበት ለአብያተ ክርስቲያንና ለበጎ አድርጎት ድርጅቶች የቀረበው ዝርዝር መግለጫ ወደ መጨረሻው እንዲህ የሚል ክፍል ያለበት ነበር።

«እስመ ስሙ ይመርህ ሀበ ግብሩ› እንዲል እውነትም ፍኖተ ድህነት የሙሉ ደህንነት የስጋዊና የመንፈሳዊ ድህንነት መንገድ ነው! እንዲህ ያለ፥ ሴተኛ አዳሪነት ብቻ ሳይሆን ለሴተኛ አዳሪነት መነሻ የሚሆኑትን ጠንቆች ጭምር ከማህበሩ ውስጥ ለማጥፋት ታጥቆ የሚሆኑትን ጠንቆች ጭምር ከማህበሩ ውስጥ ለማጥፋት ታጥቆ የተነሳ ትምርት ቤት እንዲህ ያለ ለተማሮቹ ትምርትን መስጠት ብቻ ሳይሆን፥ እንዲህ ያለ ለተማሮቹ ትምርትን መስጠት ብቻ ሳይሆን፥ በተማሩት ትምርት ሰርተው ለመኖር የታመነ ዋስትና ጭምር የሚሰጥ ትምርት ቤት፥ በየትም አገር ምንጊዜም ቢሆን ታይቶ ስለማያውቅና፥ ‹የሴትኛ አዳሪነት በሽታ ከውስጣቸው ማጥፋት የሚፈልጉ አገሮች ሁሉ አራያ አድርገው ሊከተሉት የሚገባ ነው› ብለው ስለምናምን ያጭርና የረዥም ጊዜ እቅዱን ወደ ፍጻሜ ለማድረስ እንዲበቃ የሚቻለውን፥ ያክል በገንዘብ ባስተማሪና በትምርት መሳሪያ የሚያስፈልገው ርዳታ ሁሉ እንዲደረግለት ይህን ባንድነት ተስማምተን የፈረምንበትን አሳብ አቅርበናል።»

«ባጭር ጊዜ ውስጥ ካብያተ፥ ክርስቲያንና ከበጎ አድርጎት ድርጅቶች ላንድ ጊዜ የተወሰነ ገንዘብ የሰጡት ተጨማሪ ገንዘብ የሚሰጡ መሆናቸውን፥ በያመቱ የበጀቱ መዋጮ ያደርጉ የነበሩት መዋጮዋቸውን ከፍ የሚያደርጉ መሆናቸውን በጽሁፍ አስታወቁ። ሌሎች ለረዥም ጊዜ እቅዳቸው የተመደበው ትምርት ሲጀምር፥ ለልዩ ልዩ

ማህበራዊ ኑሮ - ነክ ትምርቶች አስፈላጊ የሆኑትን መምራን ያስፈልጉትን የትምርት መሳሪያዎች የሚሰጡ መሆናቸውን ለወይዘሮ ባፈና የምነት ቃላቸውን በጽሁፍ ሰጡ።

ወይዘሮ ባፈናና የትምርት ቤታቸው ሰራ፥ በውጭ የበጎ አድርጎት ድርጅቶች አማካይነት በውጭ፥ አገር የታወቁትንና የተደነቁትን ያክል፣ በኢትዮጵያ እምብዛም አይታወቁ ነበር። የሚያውቋቸው በየምክንያቱ ግንኙነት የነበራቸውና ከሰፈሩ ነዋሪ ህዝብ ሌላ ጥቂት ሌሎች ቢኖሩ ነው። የውጭ የበጎ አድርጎት ድርጅቶች ተጨማሪ ርዳታ ሰጪዎችን ለመጋበዝ ሲሉ ጭምር ወይዘሮ፥ ባፈናንና የትምርት ቤታቸውን ስራ እያሞገሱ ወደያገራቸው ይጽፉ ስለ ነበረ ያን ጋዜጠኞች እዬጻፉ በያገራቸው ህዝብ ዘንድ እንዲታወቁና እንዲደነቁ አድርገዋቸው ነበር። በኢትዮጵያ ግን፥ ‹ኢይከብር ነቢይ በሀገሩ› እንዲል እንዲያውም አንዳንድ የሚያሽሙዋጥጡ፥ አልጠፉ! ለምሳሌ ባንድ የውጭ አገር ጋዜጣ ተጽፎ የወጣው እንዲህ የሚል ነበር። «ሴተኛ አዳሪነት ከከበቡት ልዩ ልዩ የማህበራዊ ኑሮ መቅሰፍቶች ጋር የሌለበት አገር መቸም አይገኝ! ሴትኛ አዳሪነት ባንዳንድ አገሮች በህግ የታወቀ ሆኖ በሌሎች በህግ ያልታወቀ ይሆናል። ባንዳንድ አገሮች ገሀድ ሆኖ በሌሎች ምስጢር ይሆን ይሆናል። ባንዳንድ አገሮች ቁጥጥሩ ጥብቅ ሆኖ በሌሎች ልል ይሆናል። ነገር ግን በሽታው መቅሰፍቱ፥ በቀደሙትም ሆነ ወደ ሁዋላ በቀሩት በሀብታሞችም ሆነ በድሆች አገሮች ሁሉ ሁልጊዜ የነበረም ያለም ነው። ስለዚህ የሀይማኖትና የማህበራዊ ኑሮ መምህራን ሁሉ ‹ዛሬ ሰው በአእምሮው እጅግ ተራቅቆ፥ የፍጥረት ውስጣዊ ምስጢር እንደ መጽሀፍ ተገልጦ እንዲነበብ ባደረገበት ጊዜ ዛሬው፥ ሰው በመንፈሱ ነጻነት የፍጥረትን ህግና ስራት ለመለወጥ ከፈጣሪው ጋር በሚከራከርበት ጊዜ ዛሬ የሰው ክብር የመሬትን ወሰን ተሻግሮ በሰማያት ነዋሪዎች ዘንድ በታወቀበት ጊዜ፥ ዛሬ ይህ ሁሉ በሆነበት ጊዜ እንደ ሴትኛ አዳሪነት ያለ ከክብሩ የማይስማማ እንዲህ ያለ ከደረሰበት ከፍተኛ የክብር ቦታ አውርዶ በንግድ እቃ ተራ የሚያስቀምጥ እንዲህ ያለ የባርነት ቁራጭ በውስጡ ሊኖር ጨርሶ የማይገባ ነው› እያሉ ድምጻቸውን ከፍ አድርገው ያለ ማቋዋረጥ ሲጮሁ ሲሰብኩ እንደሚኖሩ እውቅ ነው። ነገር ግን በዚህ የማህበራዊ ኑሮ መቅሰፍት ተይዘው የወደቁት ድነው ከሽቀጥነት ወደ ሰውነት የክብር ቦታ ተመልሰው ከባርርት ቀንበር ነጻ ወጥተው እንደገና ሌሎችን ከችግር ነጻ እንዲወጡ ለማድረግ እንደገና ለሌሎች ቤአ እንዲሆኑ ለማድረግ የሚቻል መሆኑን በተግባር ሞክረው ያሳዩ አንድ ሴት ብቻ ናቸው! ያ መምህራኑና ሰባክያኑ በመጻፍም በቃልም፥ ያለ ተቀባይ ዘላለም ሲያስተምሩት የኖሩት፥ ያለ ብዙ ችግር ሊፈጸም የሚችል መሆኑን ባሰራር ሞክረው ያሳዩ አንድ ያልተማሩ አንድ በአእምሮዋቸ የመምህራኑን ያክል ጠልቀ መመርመር አንድ

አንደበታቸው የሰባኪያኑን ያክል አሳምሮ መናገር የማይችሉ ስለ ኖሩት የሴትኛ አዳሪነት ህይወት ከፉነቱን ደህና አድርገው ያወቁት ስላወቁት መናገሩ እንኩዋ የሚያስፈራቸው ሴት ወይዘሮ ባፈና ወልደዬስ ብቻ ናቸው! »

«እንዲህ እንዲህ ያለ አድንቆትና ምስጋና የተጻፉባቸው ጋዜጦች ደርስዋቸው ሲያዩ ወይም ጋዜጦችን ያነበቡ ሰዎች መጥተው እያደነቁ ሲነግሩዋቸው ወይዘሮ ባፈና የስራቸው ትልቅነት እሳቸው ካሰቡት የበለጠ ትልቅ መሆኑ ይሰማቸውና፥ ለሳቸው ከመሰላቸው የበልጠ ትልቅ ሆኖ ይታያቸውና፥ «ለካስ የሰራሁት ስራ ይህን ያክል ትልቅ ነው! » ብለው ልባቸው ይነካና አይኖቻቸውን የደስታ እንባ ሞላቸው ነበር።

መቸም መልካም ስራ ሰርቶ ያገኙት አድንቆት የሚሰጠው የልብ ደስታና የመንፈስ ርካታ ብርታትን እንደሚሰጡ የታወቁ ነው! የቀን እረፍትም ሆነ የሌሊት እንቅልፍ ከሚሰጡት ብርታት ከመልካም ስራ አድንቆት የሚያገኙት የልብ ደስታና የመንፈስ ርካታ የበለጠ ያበረታሉ! ስለዚህ ወይዘሮ ባፈና፥ ስላሳሰባቸውና ስለ ስራቸው ከጋዜጦች የሚያዩትና ጋዜጦችን ካነበቡ ሰዎች የሚሰሙት አድንቆት ያካልና የመንፈስ ብርታትን ሰጥቶ፥ ሀይላቸን እጥፍ ድርብ አድርጎ ከቀድሞው እጥፍ ድርብ አድርጎ፥ ከቀድሞው እጥፍ ድርብ ጊዜ እንዲሰሩ ስላደረጋቸው ላጭርና ለረዥም ጊዜ መድበዋቸው ከነበሩት የስራ እቅዶቻቸው ብዙዎቹን ካሰቡት ጊዜ በፊት ጨረሱ። ለትምርት ቤቱ ልዩ ልዩ አገልግሎት የሚያስፈልጉት ቤቶች ተሰርተው አልቀው፥ እቃዎቻቸው እዬተገዙ ገብተው፥ ሁሉም ተሙዋልተው አገልግሎት መስጠት ስለ ጀመሩ፥ የነበረባቸው የቤት እጥረት ተወገደ። በበጎ ፈቃደኝነት ነጻ አገልግሎት ይሰጡ በነበሩት አስተማሪዎችና ልዩ ልዩ ሰራተኞች ፈንታ፥ መደበኛ ደመወዝ የሚከፈላቸው አስተማሪዎችና ሰራተኞች ተተኩ። የሶስት አመት ተማሪዎች ተመርቀው የሚወጡበት ጊዜ ደርሶ በአሉን ለማክበር የሚደረገው ዝግጅት ተጠናቀቀ። ለረዥም ጊዜ የተመደበውን ትምርት ለመጀመር የሚያስፈልገው መሰናዶ አልቆ ስራው የሚጀመርበት ጊዜ ተቃረበ።

ወይዘሮ ባፈና፥ ሁዋላ ሁዋላ ባስተዳደሩ ክፍል ረዳቶች ቢኖሩዋቸውም ራሳቸው እዬዞሩ ሁሉንም ካላዩ የተሙዋላ ስለማይመስላቸው ሁልጊዜ ወዲያ - ወዲህ ሲባክኑ እንጂ፥ ‹አርፈው አዬሁ› ለሚል አልነበረም! የደስታ ሲቃ እዬኮለኮላቸው ማረፍ አይችሉም ነበር። ብቻ ባያርፉ አይደክሙም!

እንዲህ ባለ የደስታ ሲቃ እንዲህ ባለ የደስታ ትኩሳት ውስት እንዳሉ አንድ ቀን ጥዋት ሁለት ሰዎች «ንገሩልን» ብለው እቢሮዋቸው ገቡ። አንዱ በሰል ያለ ሁለተኛው ወጣት ነበሩ። ሁለቱም እንደ ሰላማውያን መኩዋንት የለብሱ ነበሩ። ወይዘሮ ባፈና

ውብ ፊታቸው በውብ ፈገግታ የበለጠ ተውቦ እበር ድረስ ሄደው ለሁለቱም እጅ ሰላምታ ከሰጡዋቸ በሁዋላ ከጠረጴዛቸው ፊት አስቀመጡዋቸውና፥ «ቡና፥ ይሻላል ወይስ ሻይ? » አሉ ውብ ፊታቸው በውብ ፈገግታው እንዳጌጠ እወንበራቸው ላይ ሲቀመጡ።

«ሌላ ጊዜ መጥተን ብንጠጣ ይሻላል፤ አሁን ብዙ ስራ እንዳለብዎ ስምተናል። እኛም - ሌላ ስራ አለን» አለና በድሜ በሰል ያለው ሰውም መታወቂያውን ከኪሱ አውጥቶ ሰጣቸው። «ባገር ግዛት ሚኒስቴር የጸጥታ ጥበቃ ክፍል ዲሬክተር» ይላል መታወቂያው። የሰው ፊት እንዲህ በቅጽበት ይለወጣል? ወይዘሮ ባፈና የሰውዬውን መታወቂያ ሲያዩ ያ፥ በውብ ፈገግታ አጊጦ የነበረ ውብ ፊታቸው ድንገት ጠል እንዳጣ ቡቃያ ጥውልግልግ ብሎ ይንቀጠቀጡ ጀመር። የጸጥታ ጥበቃ ስም ልክ እንደ ገሀነም ስም ያላዩትን ሁሉ ከሩቅ ሲሰሙት ያንቀጠቅጣቸዋል!

«ጸ - ጸጥታ እሚያውክ ም - ምን ጥፋት አጠፋሁ? » አሉ ወይዘሮ ባፈና እንዲያ ከንፈሮቻቸው ጉንጮቻቸውና እጆቻቸው እዬተንቀጠቀጡ።

«ከመልካም በቀር እርስዎ ምን ክፉ ይሰራሉ እሜቴ? የጸጥታ ጥበቃ ምልከት ሚኒስቴር ሊያነጋግሩዎ ስለ ፈለጉ፥ ይህን ልንነግርዎ ብቻ ነው ልከውን የመጣን። ምንም የሚያሰጋ ነገር የለም አይዞዎ! ስለዚህ ነገ ጥዋት ልክ በሶስት ሰአት አገር ግዛት ሚኒስቴር፥ እጸጥታ ጥበቃ ምክትል ሚኒስቴር ጽህፈት ቤት ቢደርሱ ሚኒስትሩ ሌላ ስራ ከመጀመሩ በፊት አነጋግረዎት ትሎ ወደ ስራዎ ይመለሳሉ። ጤና ይስጥልኝ በሶስት ሰአት ይጠብቁዎታል» አለና ዲረክተሩ ከተከታዩ ጋር ያንገት ሰላምታ ሰጥተው ወጡ።

በማግስቱ ጠዋት በሶስት ሰአት ወይዘሮ ባፈና አገር፣ ግዛት ሚኒስቴር እጸጥታ ጥበቃ ምክትል ሚኒስትር ጽህፈት ቤት ሲደርሱ ምክትል ሚኒስትሩ ቀድመው ገብተው ቆዩዋቸው።

«እሜቴ ወይዘሮ ባፈና ወልደየስ ነዎት? » አለች ጸሀፊዋ፥ እንግዳ ማረፊያው አዳራሽ ሲገቡ። በርከት ያሉ እንግዶች ምክትል ሚኒስትሩን ለማግኘት እዚያ ተቀምጠው ተራቸውን ይጠብቁ ነበር። ጸሀፊዋም እዚያው እንግዳ ማረፊያው ውስጥ ነበር ስራዋን የምትሰራ።

«አዎን» አሉ ወይዘሮ ባፈና።

«ይቀመጡ እሜቴ፥ ሚኒስትሩ ይጠብቁዎታል» አለችና፥ ቶሎ ተነስታ ውደ አለቃዋ ገብታ ወይዘሮ ባፈና ከመቀመጣቸው ተመልሳ እንዲገቡ በጅዋ ምልክት ሰጠቻቸው። ሲገቡ ምክትል ሚኒስትሩ ጠረጴዛውን ወደ ሁዋላ አድርገው እክፍሉ መሀከል ቆመው ነበር። ወይዘሮ ባፈና ከያነሉት በፊት አይተዋቸው ባያውቁም እዚያ ክፍል ውስጥ ብቻቸውን ስለ ነበሩ፥ «ምክትል ሚኒስትሩ እሳቸው ሳይሆኑ አይቀሩም» ብለው በመገመት ለጥ ብለው እጅ ነሱ። ምክትል ሚኒስትሩ ጠይም መልክ ቀና መጠነኛ ቁመትና ውፍረት ያላቸው እድሜያቸው ባምሳ በስድሳ መሀከል የሚሆን ነበሩ። ቡላ ገበርዴን ሙሉ ልብስ ለብሰው ቀይ ክራባት አስረዋል። ባለባበሳቸውና በጠቅላላ ሁኔታቸው በሳቸው ደረጃ ያሉትን ትልልቅ ሹማምንት አይመስሉም። የያዙት ጉዳይ የሚያሳዝን ከመሆኑ የተነሳ ይሁን፣ ወይም ከፍጥረታችው ፊታቸው የፈገግታ ምልክት አይታይበትም፤ የተኮሳተረም አይደለም። ከያዙት ጉዳይ ጋር ያልተዛመደ ባእድ ነገ አይናገሩም።

«ፈረንጅ ቁዋንቁዋ ያውቃሉ እሜቴ? » አሉ እፊታቸው በጠረጴዛቸው ላይ ላስቀመጡት አንድ ጋዜጣ እንደሚናገሩ ሁሉ አይኖቻቸውን ከወይዘሮ ባፈና ላይ አንስተው ያን ጋዜጣ እዬተመለከቱ።

«ትንሽ ፈረንሳይኛ ይገባኛል፤ ብቻ ማወቅ አይባልም።»

«ይህ ጋዜጣ ስለ ርስዎና ስላቁዋቁዋሙት ትምርት ቤት የተጻፈበት ነው፤ ብቻ በእንግሊዝኛ ነው የተጻፈው። ያስጠራሁዎም ስለሁ ላነጋግርዎ ነው።»

«ከቶ ምን ክፉ ሰርቼ ይሆን»

«ምንም የሰሩት ክፉ የለ። የሰሩት ሁሉ የሚያስመሰግን የሚያስደንቅ ነው። እኛም ስራዎን ከመጀመርዎ በፊት ገና በመሰናዳት ላይ ሳሉ በዬቀኑ ያደርጉት የነበረውን ሁሉ እያወቅን በማገድ ፈንታ እንዲያውም ችግር እንዳይገጥምዎ ከሩቅ እንጠብቅዎ የነበረ ከመጀመሪያ አሳቡም፥ ያ አሳብ በስራ ላይ ውሎ የሰጥው ፍሬም እኛ ራሳችን እንመኘው የነበረ በጣም ደስ ያሰኘን ስለሆነ ነበር። በውነት እኔም እንደኔ ብዙ ሰዎችም እርስዎ የሰሩትን በጣም ነው የምናደንቀው። ነገር ግን - ‹ጠላት ይቀባል ጥላት› እንደሚባለው ሰውም፥ ሆነ አገር ምንጊዜም ቢሆን ጠላት ስለማያጣና ጠላት ለመጉዳት መልካሙን ነገር አስከፊ ቀለም ቀብቶ ለማሳየት መፈለጉ የታወቀ በመሆኑ ያገራችን ጠላቶች የሚጠቅሙ መስለው አገራችንን ለመጉዳት የርስዎን መልካም ስራ መሳሪያ አድርገው ሊጠቀሙበት ነው የሚፈልጉ።»

«እንዴ - እንዴት አድርገው? »

«በዚህና በሌሎች ጋዜጦች በዬጊዜው እዬተጻፈው የሚወጣው ኢትዮጵያ ብዙ ድሆች አገሮች የባሰች ድሀ ናት። በከተሞች ከሚኖሩት ሴቶች የሚበዙት በሽርሙጥና ስራ ብቻ የሚኖሩ ናቸው። አንድ ሴት ናቸው ይህን ነውር ስራ ካገሪቱ ለማጥፋት ትምህርት ቤት ከፍተው ስለሚደክሙ ተባብረን እሳቸውን ረድተን ኢትዮጵያን ከዚህ ከፉ ስራ ነጻ እናውጣ» የሚል ነው። ታዲያ፥ እኒህ ቅዱሳን መስለው «ኢትዮጵያን ከዚህ ከፉ ስራ ነጻ ለማውጣት እንተባበር» እያሉ የሚንጫጩ ሁሉ በያገራቸው ሽርሙጥና ከኛ አገር ብዙ ጊዜ በከፉ መልኩ መኖሩን ያውቃሉ። ነገር ግን ስለነሱ አገር ጋዜጦቻችው አንድ መስመር አይስፉም። የኛን አገር ስምና መልክ አክፍቶ ለማሳዬት ሲሆን ንው - ሁሉም ባንድነት ሰፊ አፋቸውን፥ ከፍተ ያለም ጀሮ እስኪደነቁር የሚጮሁ። ብቻ ከነሱ ጋር የፕሮፓጋንዳ ጦርነት ለመግጠም አቅም የለንም። ማድረግ የምንችለው ያገራችነን ስም ለማከፋት ለሚያደርጉት ፕሮፓጋንዳ ምክንያት የሚሆን ነገር ከማድረግ መቆጠብ እንዲያ ያለ እንገር አለማድረግ ነው። ስለዚህ - መቸም ያገርን ጥቅምና ክብር ከመጠበቅ የሚቀድም ነገር የለምና ያገራችን ጠላቶች የስዎን ትምርት ቤት ምክንያት አድርገው ስምዋን ማከፋት ክብርዋን መንካት ስለ ጀመሩ ትምርት ቤትዎ እንዲዘጋ ተወስኖዋል። ደክመው ያቆቁዋሙትና ‹ወደ መልካም ግብ ያደርሳል› ብለው ያመኑበት ስራ በግማሽ መንገድ ላይ ተቁዋርጦ ሲቀርብዎ እንደሚያዝኑ አውቃለሁ፤ እንኩዋን እስዎ እኔም አዝናለሁ። ነገር ግን ያገር ነገር ስለሆነ ምንም ማድረግ አይቻልም። ለርስዎ - እዚህ እኛ መስሪያ ቤት ወይም እሌላ መስሪያ ቤት በመረጡት ስራ ይሰጥዎታል» ብለው ምክትል ሚኒስትሩ ከተቀመጡበት ተነሱ። እንግዳቸውን ማሰናበታችው ነበር። ነገር ግን፥ ወይዘሮ ባፈና አንገታቸውን ደፍተው እንደ ተቀመጡ ዝም ብለው ቀሩ። ምክትል ሚኒስትሩ «ትምህርት ቤትዎ እንዲዘጋ ተወስኖዋል» ያሉትን አረፍተ ነገር ሲሰሙ ለጊዜው ራሳቸውን በከባድ ዱላ የተመቱ መስሎ ተስማቸውና ሰውነታቸው፥ ሁሉ ደንዝዞ፥ ከዚያ በሁዋላ የጸጥታ ጥበቃው ሹም ሲናገሩ ድምጻቸውን ከመስማት በቀር ምን እንዳሉ አያውቁም ነበር። ተነስተው መቆማቸውን እንኩዋ ቢያዩም አያስተውሉም ነበር። ምክትል ሚኒስትሩ እንደ ቆሙ ወይዘሮ ባፈና የሚሉትን ለመስማት ቢጠብቁ ካፋቸው የሚወጣ አንድ ቃል አልነበረም። መቸስ ቃል ውስጥ ምንም አሳብ ስላልነበረ ካፋቸው የሚወጣ አንድም ቃል አልነበረ!

«ምነ ደህና አደሉም እሜቴ? » አሉ ምክትል ሚኒስትሩ ቆመው፥ ሲጠብቁ ቆይተው፥ ወይዘሮ ባፈና አንገታቸውን ደፍተው እንደ ትቀመጡ፥ ዝም ብለው ስለ ቀሩ።

«እ? ደ - ደህና ነኝ» አሉና ወይዘሮ ባፈና ለመነሳት ቢሞክሩ ጉለበቶቻቸው፥ እዬተብረከረኩ፥ ሰውነታቸውን መሸከም ስላቃታቸው፥ እንደገና ተመልሰው ተቀመጡ። ከዚያ ምክትል ሚኒስትሩ መጥሪያውን ደውለው ጸሀፊዋ ስትገባ፥

«እባክሽ እሜቴን ጤንነት ስላልተሰማቸው፥ ከዚህ ርጃቸውና በኔ ኦቶሞቢል እቤታቸው እንዲያደርስልኝ ለሾፌሩ ንገሪልኝ» አሉ። ወይዘሮ ባፈና ጸሀፊዋ እዬረዳቻቸው ተነስተው ሲወጡ፥ ሰውነታቸው ሁሉ እንደ ደነዘዘ ስለ ነበረ፥ እንኩዋንስ ልታዘዘላቸው ርዳታ ‹እግዜር ይስጥል› ማለት የስንብት ሰላምታ መስጠት የተለመደም የሚገባም መሆኑ ስላልተሰማቸው ዝም ብለው ወጡ። ከዚያ ወደ በኢታቸው ሄደው እንደ ተኙ አልተንሱም። ሀኪሞች፥ እዬተመላለሱ ሲያዩዋቸው ሰነበቱ። ብቻ ያዩዋቸው ሀኪሞች በሽታችውን ስላላወቁላቸው እንዲያርፉ ከመምከር በቀር ምንም መድሀኒት አልሰጡዋቸውም። በሽታቸው የጸጥታ ጥበቃ ምክትል ሚኒስትር ‹ትምህርት ቤትዎ እንዲዘጋ ተወስኖዋል› ያሉት አረፍተ ነገር መሆኑን ራሳችው ያውቃሉ። የማያውቁ መድሀኒቱ ምን መሆኑን ነበር። ሀኪሞች እንደ መከሩዋቸው ካልጋቸው ሳይነሱ ያን የሚያውቁትን በሽታቸውን በልባቸው ሲያስታምሙ እህል አልበላላቸው ብሎ ሰውነታቸው ራስኑ እዬበላ በዬቀኑ እያለቀ ይሄድ ነበር።

አንድ እሁድ ቀን ሁለት ጉዋደኞች አዳማ፥ ካረፉበት ሆቴል ጥግ ተቀምጠው ሲነጋገሩ ቆይተው ዝም እንዳሉ፥ አንድ ልጅ የለቱን ጋዜጣ በብዛት በግራ እቅፉ አቅፎ ከዚያ አንዱን በቀኙ ይዞ ላይና ታች ግራና ቀኝ ግራ እያራገበ» ጋዜጣ፥ ጋዜጣ፥ ጋዜጣ፥ ጋዜጣ፥ ጋዜጣ፥» ሲል፥

«እስቲ አንጣ ወዲህ ባለ ጋዜጣ፥» አሉ ከተቀመጡበት ጉዋደኞች አንዱ።

«አሁን ‹ምን አገኝበታለሁ› ብለህ ነው? » አሉ ሁለተኛው። ጋዜጣውን የገዙት ሰው በመጀመሪያው ገጽ በጉልህ የተጻፉትን አርስቶች ብቻ አየት አየት፥ አድርገው አልፈው ሁለተኛውንና ሶስተኛውን ገጾች ለመመልከት ገለጥ ሲያደርጉ እሶስተኛው ገጽ ላይ ያንድ ባለካባ ወይዘሮ ስእል በከባድ ጥቁር ቀለም ዙሪያውን ተከቦ ታትሞዋል፡ ከስእሉ ራስጌ «ሴተኛ አዳሪነትን ለማጥፋት ቃል ኪዳን የገቡት የጥንትዋ ሴተኛ አዳሪ አረፉ! » የሚል ጽሁፍ በጉልህ ታትሞዋል።

«እግዚኦ! እግዚኦ! ሞቱ? ወይዘሮ ባፈና? » አለ ሰውዬው ጋዜጣውን እጠረጴዛው ላይ ጥለው፥ ራሳቸውን በሁለት እጆቻቸው ደግፈው።

«ወይዘሮ ባፈና ማናቸው? » አሉ ጉዋደኛቸው እንደ መደንገጥ ብለው።

«ፍኖተ ድህነት የሚባለውን ትምርት ቤት የመሰረቱት» አሉ ሰውዬው ራሳቸውን በሁለት እጆቻቸው እንደ ደገፉ ዘለግ ላለ ጊዜ ዝም ብለው ቆይተው።

«ያን - የሴትኛ አዳሪዎችን ትምህርት ቤት የከፈቱት? »

«አዎ እሳቸው» አሉ ሰውዬው፥ አሁንም እንደ ፊተኛው ዝም ብለው ቆይተው።

«እኔ ወሬያቸውን ካልሆነ እሳቸውንም አላውቃቸውም፤ በወሬ፥ ግን ስራቸውን ሲያደንቁላቸው ስምቻለሁ።»

«እኔ አውቃቸዋለሁ፤ እንዲያውም ወዳጄ ነበሩ። ከስራቸው ትልቅነት ሌላ በጣም ደግ የወዳጅ ፍቅር አክባሪ ፍሬ ሴት ነበሩ፤ ሄዱ! »

«መቸም ይህ - የታወቀ ነው።»

«ምኑ? » አሉ ሰውዬው እንባ ያቀረሩ አይኖቻቸውን ወደ ጉዋደኛቸው መልሰው።

«ጥሩ ፍሬ ባለበት የማይቆይ መሆኑ! ጥሩ የበሰለ ፍሬ ወይ ተለቅሞ ይባላል፤ ያለዚያም እመሬት ይወድቃል! ይረግፋል! »

«እውነት ነው፤ ጥሩ ፍሬ ነበሩ፤ ረገፉ! አየ ጉ - ድ! መቸም የጀመሩት ስራ ግሩም ነበር! እውነት የማይመስል የልምእዣት! »

## ምእራፍ ሀያ አራት

# ወይዘሮ እሁድ

ደመቀች፥ ፍኖተ ድህነት ሁለት አመት የሚሰጡትን እንግሊዝኛ፥ ሂሳብና ያማርኛ ጽህፈት፥ ሌሎችንም ትምርቶች ከጨረሰች በሁዋላ የምትሰራበት ሀኪም ቤት እንደስዋ

መጠነኛ እንግሊዝኛ ለሚያውቁ የሀኪም ቤቱ ሰራተኞች የሚያስተምረውን ትምርት እዬቀጠለች፥ ደመወዝዋ ከሀያ አምስት ብር በዬጊዜው እዬተጨመረ ወደ ሰማንያ ብር ደረሰ። ይሁን እንጂ፥ በደመወዝዋ እድገት መጠን ኑሮዋ ምንም ያክል አልተሻሻለም። ሀኪሙ በሽተኞችን ሲጎእብኝ ለምትከተለው አስታማሚ ረዳት ሆና አብራ መዞር ስትጀምር ጫማ ማድረግና ከድሮው የተሻለ ልብስ መልበስ ግዴታ ስለሆነ፥ የሸራ ጫማና ጥቂት መለወጫ ልብሶች መግዛትዋ በቀር፥ ከዚያ አልፋ፥ በድሜም ሆነ በስራ ጉዋደኞችዋ ላይ የምታየው፥ ልብስና ጌጣጌጥ አዛዥ ተካልኝ ቤት ለምትኖርበት አስር ብር እንድትከፍል ከወይዘሮ ጌጤ ጋር የተስማምሙ ደመወዝዋ ሀያ አምስት ብር በነበረበት ጊዜ ስለ ነበረ፥ እሱን እንኩዋ ለመጨመር እዬፈለገች ስላቃታት አንዳንድ ጊዜ በጭዋታ መሀከል የኑሮ ውድነት ወይም የገንዘብ ማጠር ነገር ሲነሳ ታፍርና ትሰቀቅ ነበር። አዛዥም ሆኑ ባልተቤታቸው ትከፍለው የነእብረው በላይ ‹አልከፈለችም› ብለው ቅር እንደማይላቸው ታውቃለች። ብቻ እነሱ ‹አይሆንም› ሲሉ ይቅር እንጂ እስዋ ደመወዝዋ ሲያድግ ላዛዥና ለወይዘሮ ጌጤ ‹አንዳንድ ልብስ ወይም ሌላ ስጦታ› ማለትዋ ቢቀር ለመኖሪያዋ እንኩዋ ትንሽ መጨመር አድርጋ ለመርዳት መጠዬቅ በተገባ ነበር። ነገር ግን የማትችል መሆንዋን ስለምታውቅ እስከ ማንሳቱም ፈራች።

ከደመወዝዋ በጣም የሚበዛውን ክፍል የምታጠፋው በተከስተ ላይ ነበር። በዬሳምንቱ እሁድ፥ ተከስተ ትምርት ቤት ከገባ ጀምሮ አንድ ቀን እንኩዋ ታጉሎ የማያውቅ ምሳ ትወስዳለች። ቅዳሜ እስከ ቀትር ድረስ የስዋንም ያዛዥንም የባልተቤታቸውንም ልብስ አጥባ የሚተኮሰውን ተኩሳ፥ ቤት አጽድታ ትጨርስና፥ ከቀትር በሁዋላ ለተከስተ የሁድ ምሳ የሚያስፈልገውን ስትገዛ ታመሻለች። ከዚያ ራት ተበልቶ አዛዥና ባልተቤታቸው ወደ ምኝታቸው ሲሄዱ እስዋ፥ ድግስዋን መደገስ ትጀምራለች። የተከስተ እንጀራ ልዩ ነው። ጤፉ በውቅ ተገዝቶ በጥንቃቄ ተበጥሮ ተፈትጎ ከነጭም ነጭ፥ ከጥሩም ጥሩ፥ ከሆነ በሁዋላ ተፈጭቶና ተቦክቶ፥ የሚጋገር ባፍ ገብቶ ሳይቆም ጉሮሮ የሚሰርቀው ነው። የዶሮ ወጥ የበግ አልጫ ጎመን የተለመዱ ናቸው። በዚያ ላይ ተከስተ ጣፋጭ በጣም ስለሚወድ ቢያደርሳት ሰርታ ያለዚያም ገዝታ ትጨምርበታለች። ይህ እሁድ፥ ልክ እንደ ቅዳሴው የማይታጐል ሲሆን፥ ከሁ ጋር አንድ ቀን የውስጥ ሹራብ አንድ ቀን የላይ ሹራብ አንድ ቀን ሸሚዝ አልፎ አልፎ ኩታና ጫማ፥ ቢያንስ ቢያንስ መሀረብ ሳትይዝ የምትሄድበት እሁድ ቢኖር ያለ ጥርጥር በጣም ያንሳል።

እሁድ ባምስት ሰአት ግድም ደመቀች፥ ድግስዋን ተሸክማ ተፈሪ መኮንን ትምርት ቤት በምእራብ በር ገና ብቅ ከማለትዋ ተከስተ የምትመጣበትን ሰአት ስለሚያውቅ

ቀድሞ እዚያ ደርሶ ሲጠባበቅ ይቆይና ‹እመዬ› እያለ በሩን ከፍቶ ወደስዋ ሲሮጥ ስታይ እስዋም ሽክምዋን አውርዳ አስቀምጣ ‹አብዬ› እያለች አጆችዋን እንደ ክንፍ ግራ - ቀኝ ዘርግታ ትቀበለውና፥ ሁለቱም ከሞት አገር እንደ ተመለሱ ተቃቅፈው ትንፋሽ እስኪያጥራቸው ሲሳሳሙ ይቆያሉ። ከዚያ ተከስተ ሽክሙን እናቱ ካስቀመጠችበት አንስቶ ይዞ፥ እሱና እናቱ ዘወትር እሁድ ምሳ ይበሉባት ስለነበረ - ‹የተከስተ ሾላ› የሚባል ስም ወደ ወጣላት፥ በሩን ሲገቡ ወደ ግራ የምትገኝ ሾላ ይሄዳሉ። እዚያች ሾላ ስር ተቀምጠው ምሳቸውን እሱ በስዋ እጅ በስዋ በሱ እጅ በልተው ልክ፥ ከደጃዝማች አሰፋ ተጫኔ ግቢ ውስጥ በነበረችዋ ቤታቸው ሳሉ ያደርጉት እንደ ነበረው ከወሬ፥ ከቃል ጭዋታ ይጀምሩና፥ ከዚያ እዬሳቁ፥ እዬቦረቁ ወደ መላፋቱ ወደ ትግሉ ይሄዳሉ!

ወሬው ጭዋታው፥ ትግሉ፥ ልፊያው፥ እንዲሁ ገለል ብሎ ለሚያየውና ለሚሰማው እነሱን ላልሆነ ያን ያክል የሚያስቅ ያን ያክል ብርቅ ድንቅ ያን ያክል የሚናፈቅ ሆኖ አደለም። ብቻ ለነሱ ብርቅ ድንቅ ነው! እሱ ለስዋ እስዋ ለሱ የሚያወሩት የሚያደርጉት ስለሆነ በጣም ልዩ በጣም የሚያስቅ እሁድ ደርሶ እስኪያወጉት እስኪሰሙት እስኪያደርጉት እስኪያዩት በጣም የሚናፍቁት ነበር! እንዲያውም ተከስተማ ወሬውን ጭዋታውና እናቱ እሁድ እሁድ ይዛለት የምትመጣውን ነገር ሁሉ በልዩ መልክና በልዩ ስሜት ያያቸው የነበረ እሁድን ራስዋን ከቀኖች ተራ አውጥጦ፥ ሰዎች ተራ አግብቶ ማየት ጀምሮ ነበር! ለተከስተ እሁድ ሰው ሆና ጥሩ ወይዘሮ ሆና ትታየው ነበር!

«እመዬ፥ እሁድን ትወጃታለሽ? » አለ፥ አንድ እሁድ እንደ ልማዳቸው ምሳቸውን በልተው በሚያወሩበት ጊዜ።

«በጣም እወዳታለሁ» አለች እናቱ።

« ለምን? »

«አንተን የማይባት ቀን ስለ ሆነች»

«መልክዋ እንዴት ያለ ነው? እንዴት ያለች ሆና ትታይሻለች? »

«እንዴ! እሁድ ሰው ናት? ቀን አይደለችም? » አለች ደመቀች፥ ከልብዋ እዬሳቀች።

«ቀን መሆንዋንማ አውቃለሁ» አለ ተከስተም እዬሳቀ «ብቻ እኔ ሳስባት - በቀይና በጠይም መሀከል ያለ መልክ ምን ይባላል? »

«ዳማ! »

«አዎ፥ ዳማ ወይዘሮ መስላ ትታያኛለች። ጥርስዋ ከንቅሳቱ ጋር በጣም የሚያምር አይንዋን የተኩዋለች ጠጉርዋ በጣም፥ የሚያምር ሆኖ በትንሹ ሽበት ያሰረገው ነው። ብቻ ፊትዋ የልጅ ፊት ስለሆነ ሽበቱ አውቃ ለጌጥ ያደረገችው ይመስላል። ሁልጊዜ ከንፈርዋን ሳትከድን ፈገግ ብላ ፊትዋን፥ ደስ ብሎት በጥልፍ ቀሚስ ዋና በጥበብ ኩታዋ ላይ ካባ ደርባ፥ ረጋ ብላ ካንቺ ፊት ፊት በዚህ በምዕራብ በር ስትገባ አያታለሁ። ታዲያ እስዋን ሳይ ሁልጊዜም አንቺን በሁዋላዋ አይሻለሁ። ስለዚህ - አንቺን ይዛልኝ ስለምትመጣ ነው መሰለኝ በጣም እወዳታለሁ’ ትናፍቀኛለች።»

«በቃ! እንግዲህ ያችን እሁድን አልወዳትም! » አለች ደመቀች፥ ግንባርዋን በውሸት ኮስተር አድርጋ።

«ለምን? »

«አንተ ስለምትወዳት! እንዲህ አስጊጠህ አሳምረህ፥ የምታያት ከኔ የበለጠ ብትወዳት አደል? »

«ይህን የተናገረ አፍሽ መቀጣት አለበት! » አለና ተከስተ የናቱን አፍ ለመምታት እስዋ ለመከላከል ትንፋሻቸው እስኪቆረጥ እዬሳቁ ሲታገሉ ቆይተው በሁዋላ፥ ሲደክማቸው ትግሉን ትተው እንደገና ወሬያቸውን ቀጠሉ።

« ‹እስዋ እንዲህ አጊጣ አምራ አያታለሁ› አልሁ እንጂ የማስጌጣትና የማሳምራት እኔ አደለሁም። የምወዳትም፥ የምወዳትን እመዬን ስለምታመጣልኝ ነው» ሲል ተከስተ ድንገት ሳያስበው አንገቱን እቅፍ ጭንቅ አድርጋ ይዛ ስማእችው እናቱ።

« ‹ታዲያ እሁድ፥ እንዲህ ሆና ትታዬኛለች› ብዬ ለዚያ ‹ወይደኛል› ላልሁሽ አስተማሪ ሊጋሼ፥ ሀይሉ ስነግረው ያለኝን ልንገርሽ? » አለ ተከስተ ቀጥሎ፡

«ምን አለህ? »

«እሁድ ሁልጊዜ አጊጣ፥ አምራ፥ ፈገግ ብላ ፊትዋ በደስታ በርቶ ረጋ ኮራ ብላ፥ የወይዘሮ አካሄድ እዬሄደች እናትህን ይዛ ስትመጣ እሁድ፥ የእረፍት፥ የደስታ፥

የጨዋታ፥ የጌጥ ቀን ስለ ሆነችና የምትወዳትን እናትህን የምታይባት ቀን ስለ ሆነች ‹ህቡእ› አእምሮህ ላንተ ሳይሰማህ፥ ይህን ሁሉ አሳብ ባንድ ላይ አስምማቶ፥ ይህ ሁሉ አሳብ ባንድ ላይ የሚታይባት ወይዘሮ አሳምሮ ስሎ ለ ‹ክሱት› አእምሮህ ስላቀበለው ‹ክሱት› አእምሮህ ያችን ከ ‹ህቡእ› አእምሮህ የተቀበላትን ከረፍት ከደስታ፥ ከጭዋታ፥ ከጌጥ ቀለም የተሳለች እሁድ የዚያችን ጥሩ ወይዘሮ ስእል እያሳዬህ ነው› አለኝ።»

«ጥሩ ነው፤ እንግዲህ ስእል መሳል ተማርና እሁድን ብቻ ሳይሆን፥ ከሰኞ እስከ ቅዳሜ ያሉትን ቀኖች ሁሉ ወይዛዝርትና መኳዋንንት እያደረግህ፥ በዚያ - ምንድነው? ‹ህቡእ - ክሱት? አእምሮ ባልኸው ቀለም እንደ እሁድ እያሳመርህ እዬሳልህ ታሳይዬኛለህ! » ስትል ደመቀች በልጅዋ ለመቀለድ ተከስተ በፈንታው እናቱ ‹ህቡእና ክሱት› አእምሮ የስእል ቀለም መስሎዋት በተናገረችው በጣም ሲስቅ ቆዬና፥

«ህቡእና ክሱት አእምሮ› ቀለም አደለምኮ እመዬ፥» አለ።

«አንተኮ ነህ - ከ ‹እቡእ› - ከ ‹ክሱት አእምሮ የተሳለች ወይዘሮ ያልህ!› አላልህም! »

«እንደሱ አላልሁም።»

«እሺ መቸም ‹ህቡእና ክሱት አእምሮ› ያልኸውን ከስእል ጋር አያይዘህ ነው የተናገርኸው፤ ታዲያ እንግዲያ - የስእል መሳያ ወርቀት ነው? »

ተከስተ አሁንም እዬሳቀ የናቱን አንገት አቅፎ ራስዋን፥ ግንባርዋንና ፊትዋን ሁሉ ሲስም ቆዬና፥

«አእምሮ አታውቂም እመዬ? » አለ።

«አእምሮማ አውቃለሁ፤ እእምሮ የምናስብበት ነው። የማላውቀው - እሁድን ባለካባ ወይዘሮ የሚያደርገውን ያን፥ ያንተን - ‹ህቡእ - ክሱት› የሚባለውን አዲስ አይነት አእምሮ ነው» ደመቀችም እዬሳቀች።

ተከስተ ተፈሪ፥ መኮንን ትምህርት ቤት ከገባ በሁዋላ እስከ ብዙ ጊዜ ድረስ ምናልባት እድሜው፥ አስራ አምስት አመት ያክል እስኪሆነው ድረስ፥ ለናቱ የነበረው ስሜት ፍቅሩ፥ እደጃዝማች አሰፋ ግቢ አብሮዋት በነበረበት ጊዜ ከነበረው ምንም አልተለወጠም፤ ያው ነበር። እንዲያውም ሳምንት ሙሉ ሳይተያዩ፥ በመሰንበቻው፥

ናፍቆትን ጨምሮ እሁድ እስኪገናኙ ድረስ ሳምንቱ አመት ሆኖ ይታየው ነበር! ያች እናትና ልጅን የምታገናኝ እሁድ ያች ተከስተ አስጊጦ አሳምሮ ስሎ ያያት፥ የነበረች እሁድ፥ በጣም ጥሩ እሁድ ነበረች! ያች ሁለቱ ብቻ - እያወሩ እዬተሳሳቁ፥ እዬተላፉ፥ እዬታገሉ፥ እዬተሳሳሙ - አብረው ሳሉባት ደስታን አልፋ፥ ሲያስቡዋት ትዝታን ውለታን እንደገና ተመልሳ እስክትመታ ናፍቆትን እያፈራረቀች እዬሰጠች፥ ልባቸው ሁልጊዜ እንደ ሞቀ ህይወታቸው ሁልጊዜ ሙሉ ጊዜ እንደሆነች ታኖራቸው የነበረች እሁድ በውነት ጥሩ እሁድ ነበረች! ተከስተ ያንጊዜ ከናቱ ጋር ሳለ እንኩዋንስ ራሱ ጠርቶ፥ ሊያመጣ ባጠገባቸው እግረ - መንገዱን የሚያልፍ ሰው ወደሱ ዘወር ብሎ ያዬ እንደሆነ እናቱን፥ ‹ቀምቼ ልውሰድብህ› እንዳለው ሁሉ ተቆጥቶ ቀንቶ አይኑ ደም ይለብስ ነበረ! ያንጊዜ አስራ አምስት አመት ያክል እስኪሆነው ተከስተ እናቱን የሚወቅሳት ‹ለኔ ብቻ እያሰብሽ ራስሽን ፈጽመሽ ረሳሽ› እያለ ነበር! ከምሳው ጋር ልብስ ወይም አንዳንድ ሌላ እቃ የወሰደችለት እንደ ሆነ ለራስዋ ልብስ ጫማ፥ ወይም ያንገት ይሁን የጆሮ ጌጥ ሳትገዛ ሁልጊዜ ለሱ ብቻ በመግዛትዋ ያኮርፍና አላነጋግራት ስትመጣ ለራስዋ ሁሉ እዬሳመች አባብላ፥ ከተከታዩ፥ እሁድ ስትመጣ ለራስዋ፥ የገዛችውን ጌጥ ወይም ሌላ ነገር ልታሳዬው ምላ ይታረቃሉ። ወዲያው በተከታዩ እሁድ ከጎረቤት ወይም ከጉዋደኛ የተዋሰችውን ጌጥ ወይም ልብስ ‹ገዛሁት› ብላ ስታሳዬው እውነት መስሎት ደስታው ቅጥ መጠን ያጣ ይሆናል! እስዋም እሁድ እሁድ፥ በተለመደው ሰአት በምእራብ በር አገልግልዋን ታቅፋ ወይም አንጠልጥላ ገና ብቅ ስትል ሲያያት ከሚጠባበቅበት ቦታ፥ ‹እመዬ› እያለ የሚሮጠው ሩጫ ደስታው ቡረቃው ልብዋን በደስታ የሚሞላውን ያክል፥ የሚለያዩበት ጊዜ ደርሶ ስትጀምር ቅርታዋ በፊቱ እንባው ባይኖቹ ሲመጡ ታይና ልብዋ መሸበር ይጀምራል። የምታጽናናበት መላ እዬፈለገች መጨነቅ ትጀምራለች። ከዚያ እንባ የሞሉ አይኖቹን ቅርታ ያጠለለው ፊቱን ሁሉ ስማ ከተለያዩ በሁዋላ አጥሩ እስኪከለክላት እዬዞረች እያዬች የቤትዋን መንገድ ትጀምራለች። ተከስተ ካይንዋ ሲጠፋ፥ በፊቱ ቅርታው ባይኖቹ፥ የተንቸፈረረ እንባው በጠቅላላ ሁኔታው ለዬብቻም ባንድነትም መጥተው በፊትዋ፥ እዬተደቀኑ እዬተንጋጉ መንገድዋን እንዳታይ ይጋርዱባትና ለጊዜው የልብዋ መሸበር ጭንቀትዋ እጥፍ ይሆናል! ነገር ግን ቆም እያለችም ትንሽ እዬተራመደችም ባሰላሰለች መጠን ያ ሁል ቅርታው ያ ሁል እንባው ለስዋ ያለውን ፍቅር ጽኑነት የሚስታውስ የሚመስክር ለስዋ ያለውን ፍቅር ሀያልነት የሚያረጋግጥ መሆኑን ስታስታውስ ያ ቅድም ይሸበር ይጨነቅ የነበረ ልብዋ አሁን በደስታ መጨፈር በደስታ መዝለል ይጀምራል። የወደደ ልብ በወዳጆቹ ጭንቀት የሚደሰት፥ ጨካኝ ፍጥረት አደል? ለዚህ ነው። ከዚያ ልብዋ

እንዲያ በደስታ ሲጨፍር እንዲያ በደስታ ሲዘል እያዬችና እዬሰማች ተመስጣ፥ ስንዝር መንገድ የሄደች ሳይመስላት እቤትዋ ትደርሳለች።

አዎ፥ ያች ተከስተ አስራ አምስት አመት ያክል እስኪሆነው እናቱና እሱ ብቻቸውን ማነንም ሳይጨምሩ ከጥላማ ዛፋቸው ስር ያሳልፉዋት የነበረች እሁድ በውነት ግሩም ነበረች! ከዚያ በሁዋላ ግን፥ ካስራ አምስት አመት ያክል በሁዋላ ተከታትሎ፥ የመጣው፥ እያንዳንዱ አመት ተከስተን ሌላ የሚደረግ ብዙ ነገር እዬያዘ እዬመጣ ቀስ እያለ ሌላ ስላደረገው፥ እሁድም ሌላ እሁድ፥ ሆነች።

መቸም ልጅ፥ ከህጻንነት ወደ ጐማስነት ሲሸጋገርና ባካልም ሆነ ባእምሮ ሲያድግ አለሙ፥ ማለት የሚያየው የሚሰማው ባጠቃላይ የሚያውቀው ሲሰፋ፥ አሳቡ እውቀቱ፥ እምነቱ ምኞቱ ፍቅሩ ስሜቱ ሁሉ መለወጡ የማይቀር ነው፤ ለውጡም ወደ በጎ ወይም ወደ ክፉ የሚሆን እንደሚኖርበት አካባቢና ከዚያ እንደሚቀስመው ትምርት መሆኑ እውቅ ነው።

ተከስተ እያደገና አለሙን እያሰፋ በሄደ መጠን ያን ተከትሎ አሳቡ፥ እውቀቱ ምኞቱ፥ ፍቅሩ ስሜቱ፥ በመለወጡ፥ ደመቀች፥ እሁድ እሁድ ከልጅዋ ጋር ብቻ ትካፈለው የነበረውን ምሳ ጊዜ ፍቅር ደስታ ጨዋታ ሁሉ ለውጡ ካመጣቸው ብዙ ጉዋደኞቹና ወዳጆቹ ጋር መካፈል ስለ ተገደደች ድርሻዋ እዬተቀነሰ እዬተቀነሰ ሄዶ በመጨረሻ እነሱ ሲበዙ እንዲያውም ከማህበረተኛነት ወጥታ ተመልካች ብቻ ሆነች! ከዚያ በሁዋላ ልጅዋም የሚወቅሳት፥ ‹ለምን ራስሽን ረስተሽ ለኔ ብቻ ታስቢያለሽ?› በማለት መሆኑ ቀርቶ ‹ለኔ ብቻ ሳይሆን ለምን እኔን ለከበበው ሁሉ አታስቢ?› በማለት ሆነ የሚያኮርፈው። ‹ለምን ለራስሽ ልብስ ሳትገዥ፥ ለኔ ብቻ ትገዢለሽ?› በማለት መሆኑ ቀርቶ ‹ለምን እዳ ገብተሽ ለኔ ብቻ ሳይሆን ለሌሎች የምሰጠው ልብስ ወይም ሌላ እቃ አልገዛሽም?› በማለት ሆነ፥ ንግግር የሚከለክላት! ‹ለምን ሳትበይ እኔን ብቻ ማብላት ትፈልጊያለሽ?› በማለት መህኑ ቀርቶ ‹ለምን ሰርተሽ ተሸመሽ ያመጣሽው ድግስ ለጉዋደኞቼና ለወዳጆቼ እንዲያውም ሁዋላ ሁዋላ ለዘበኖች ጭምር አነሰ› በማለት ሆነ!

ተከስተ ጨዋታ አጥብቆ የሚወድና ችሎታ፥ የነበረው ስለሆነ፥ በትምርት ቤት ውስጥም ከትምርት ቤት ውጭም፥ በልዩ ልዩ ጭዋታ ሙሉ ተካፋይነቱን ሳይቀንስ በክፍል ትምርት ያለብዙ ችግር፥ ብዙ ሳያጠና፥ ሁልጊዜ ቀዳሚዎች ከሚሆኑት መሀከል ቆሞ የሚገኝ በመሆኑ አስተማሪዎችም ሆኑ የትምርት ቤት ሹሞች የሚወዱት ተማሮች፥ የሚያከብሩትና የሚያደንቁት ነበር። በዚያ ላይ ፈጣሪ ላንዳንድ የመረጣቸው ፍጡሮች

የሚያድለው ተቀብአ ስለ ነበረው በድሜ የሚበልጣቸውና የድሜ ጉዋደኞቹ ብቻ ሳይሆኑ በድሜ ከሚበልጡት መሀከልም ከባቢዎቹ፥ አድናቂዎቹና አጃቢዎቹ ብዙ ነበሩ። ታዲያ ይህ ከያፉ መደነቁ ይህ በብዙ መከበቡና መታጀቡ፥ ይህ በብዙ አይን ከፍ ብሎ መታየቱ፥ ይህ በብዙ ነገር ቀድሞና በልጦ መታየቱ፥ በትንሽ ነገር እንኩዋ ያነሰ መስሎ መታየቱን በሁሉም ነገር በልጦ አለመታየትን ብርቱ ውርደት አስመስሎ ያሳዬው ጀመር! ስለዚህ ባለባበስ፥ በስጦታ፥ በድግስና እነሱን በመሳሰሉት የገንዘብ ወጪ፥ በሚያስፈልጋቸው ነገሮች ሁሉ ከጉዋደኞቹ በልጦ እንጂ አንሶ አይገኝም በጥንቃቄ የመጠበቁ ሙሉ አላፊነት የደመቀች ስለሆነ፥ ተግንባርዋን ባትፈጽም የሰናፍጭ ቅንጣት ታክል ጉድለት ብትገኝባት ወዮላት!

ይህ አላፊነት ለደመቀች ከብዶ አይታያትም። ሰርታ የምታገኘው የወር ደመወዝዋ አንዳንድ ጊዜም የማይበቃ ሲሆን፥ የቅድሞሽ ወስዳ ጨምራ ፍላጎቱን ሊያረካት እስከ ቻለ ድረስ ልጅዋ ለሚፈልገው ጉዳይ እንዲከፋፍለው መስጠቱ፥ ምንም አይከብዳት። እንዲያውም ተቸግሮ፣ የሚወዱትን ደስ ማሰኘት የሚሰጠው ደስታ ትልቅ ስለሆነ በጣም ደስ ይላታል። ከብዶ የማትችለው ሆኖ የሚታያት፥ ለስዋ ይሰጣት የነበረውን ጉዋደኝነቱን ጭዋታውን ፍቅሩን ሁሉ የሚያከፋፍልበት እዬበዛ በሄደ መጠን ለስዋ የሚደርሳት እዬተቀነሰ እያነሰ መሄዱ ስለ ተሰማት፥ እስከዚያውም የምታጣበት ጊዜ የደረሰ እንደሆነ ነው! ይህን ስታስብ ብቻ ፍራት ይይዛታል፤ ትርዳለች! ወዲያው ከዚህ ጋር ተያይዞ መጀመሪያ ትምርት ቤት እንዲገባ የተፈቀደለት እለት ሌሊቱን እንጋት ላይ አጊጦ አምሮ አዬችው አጥብቃ የያዘችው ያቀፈችው ሲመስላት በመሀከላቸው የማይታይ አጥር እንደ ታጠረ፥ ሁሉ ልትነካው አለመቻልዋ ሲናገር የምታየው ሲመስላት፥ ልትሰማው አለመቻልዋ የሳመችው ሲመስላት ጉም እንደ ሳመች የገዛ ከንፈርዋ ጨኸት ብቻ መስማትዋ ያ ሳትተኛ ያዬችው የሚያስፈራራ ቅዠት ትዝ ሲላት ፍራትዋ ብዙ ጊዜ እጥፍ ይሆንና፥ ለሰው ያወራችው እንደሆነ ስታስበው የቆዬችው እንደሆን እንኩዋ እውነት የሚሆን ይመስላትና ቶሎ እሱን የምትረሳበትን ቶሎ እሱን ካሳብዋ የምታጠፋበትን መላ ወደ መፈለጉ ትሄዳለች።

የተከስተን የሁድ ምሳ የሚካፈሉት ጉዋደኞቹና ወዳጆቹ ሲበዙ እንጀራውና ወጡ በርከት አገልግሉ ከፍ ሸከሙ ከበድ ስላሉ፣ አግልግሉን በቅፍ መያዝ ወይም ማንጠልጠል የማይቻል ሆነና ደመቀች በራስዋ እዬተሸከመች ትመላለስ ጀመር። የምሳ መብያው ቦታም ‹ተከስተ ሾላ› ስር ያጥሩን በር ሲገቡ በስተቀኝ ወደሚገኘው የዘበኞች ቤት ተዛወረ። ተከስተ እሁድ እሁድ ባምስት ሰአት ግድም እንደ ተለመደው በምእራብ በር አቅራቢያ ወዲያ - ወዲህ እዬተንሸረሸረ እናንቱን ሲጠብቅ ይቆይና ብቅ ስትል

እንደ ህጻንነት ‹እመዬ› እያለ መሮጡ ቢቀር እንዳደጉ ልጆች ቀስ ብሎ ሄዶ እስዋንም ያመጣችውን ምሳና አስቀምጦ ቶሎ ሄዶ ጉዋደኞቹን ከያሉበት ጠርቶ ሲመጣ፥ ዘበኞች ጭምር፥ የደመቀች ድግስ እዬተበላ ጫጫታ ይሆናል! ተማሮችም ሆኑ ዘበኞች ምንም እንኩዋ ሰርታ ተሸክማ ካመጣችው እልህ ‹ትንሽ ቅመሽ› ማለት የሚገባ መሆኑን የሚወዱዋት። እስከ መጨረሻው ድረስ፥ ስምዋን የሚያውቅ ከመሀከላቸው አንድ እንኩዋ አልነበረም። ሁሉም እንደ እንደ ተከስተ ‹እመዬ ነበር የሚሉዋት። አገልግሉን አቅርባላቸው ገለል ብላ ስትቀመጥ፥

‹እመዬ ሁሉም ከፊቱ አልፎ ከሌላ ፊት እንዳይበላ ዳኛ ሁኚና አግጅልን› ይላል አንዱ።

‹እመዬ እይው፥ ያ የሱን ፊት ቆጥቦ ከኔ ፊት ሲበላ› ይላል ሌላዉ።

‹እሱ ካንተ ፊት ከበላ አንተም ከሱ ፊት ብላ› ትላለች ደመቀች እዬሳቀች።

‹እመዬ እስቲ፥ እባክሽ ያን ተመልከችው፥ የሚጎርሰውን ሳያላምጥ እዬዋጠ፥ ሁላችንም አንዳንድ ጊዜ ሳንጎርስ እሱ ሶስት ጊዜ ይጎርሳል› ይላሉ ደግሞ ሌላዉ።

«እመዬ ወድጄ፥ አደለምኮ! እንዲያውም ስለሚጥመኝ እንደ ጣመኝ እንድቆይ፥ ቶሎ መዋጥ አልፈልግም ነበር። ብቻ ጉሮሮየ በግድ ቀምቶ ይወስድብኛል! ላቆዬው ስሞክር ደግሞ ትንታ ይመጣብኛል! » ይላል፥ «ሳያላምጥ ይውጣል» የተባለው።

መቸም ይህን የመሳሰለው ቀልድ ሁሉ ተማሮችም በዘበኞችም የደመቀችን መሰናዶ በጭዋታ መልክ ለማመስገን የሚፈጥሩት ስለ ሆነ ምንም እንኩዋ፥ አሰናጂዋ እስዋ ብትሆን በተከስተ ስም የሚቀርብ፥ የተከስተ ድግስ በመሆኑ ልጅዋን ደስ የሚያሰኘው ልጅዋን የሚያኮራው እዬመሰላት በጣም ደስ ይላት ነበር። ተከስተ ግን የጌቶች ልጆች ጉዋደኞቹ በሚያደርጉት የድግስ ውድድር እዬተጋበዘ ሲሄድ መብል መጠጡ ሳይሆን እዚያ የሚያየው ቤቱ፥ እቃው አሳላፊውና ሌላ ሌላው በጌቶች ቤት ያለው ስነስራት ሁሉ አይኑን ብቻ ሳይሆን አእምሮውን ጭምር ስለሚያጥበረብረው እናቱ እሁድ እሁድ በሌጣ አገልግል እዬተሸከመች የምትወስድለት ተበልቶ የማይጠገብ ምግብ ባይኑ አይሞላም፤ የምትወስድለት፥ ተበልቶ፥ የማይጠገብ ምግብ ባይኑ አይሞላም፤ የልቡን አያደርሰውም። ጉዋደኞቹ ከልባቸው ሲያመሰግኑ የሚያሽሙዋጥጡ እዬመሰለው ስለሚጠርጥር ሙሉ ደስታ ሳይሰማው ይቀርና ይቅበጠበጣል። ብቻ እንደ እውነቱ የሆነ እንደሆነ የደመቀች ድግስ የጌቶችን ቤት ድግስ

የከበበው ያቀራረብ ሽርና ስነስራት አይኑረው እንጂ ባለመለዮ አሳላፊ ልዩ ልዩ እቃ ባስጌጠው ጠረጴዛ አያቅርበው እንጂ በጣሙም ሆነ በጽዳቱ፥ በማነኛውም የጌታ ቤት ከሚቀርበው ድግስ ይበልጥ እንደ ሆነ እንጂ የማያንስ ስለ ሆነ ተማሮችና ዘበኖች እዬተሻሙ ሙጥጥ አድርገው በልተው ይጨርሱታል። ለዘበኞች ውሻ፥ ‹ለመቻል ደጉ› እንኩዋ ትንሽ ፍርፋሪ አይተርፈውም! መቻል ደእጉ ድግሱ ሲበላ እዚያ ቁጭ ብሎ አይኑ የያንዳንዱን እጅ እዬተከተለ ወዳግልግሉ ሲሄድ ከዚያ እጅ ፍትፍት ተሸክሞ ሲመለስ አጅቦ እስካፉ ሲያደርስ እንዲሁ አንድ ጊዜ ያንዱን ሌላ ጊዜ የሌላውን እጅ እያጀበ ካገልግሉ ወዳፉ ካፉ ወዳገልግሉ ሲመላለስ ከንጀራው ትንሽ ቁራሽ ከፍትፍቱ ትንሽ ፍርፋሪ ሳይተርፍ ሁሉም ሙጥጥ ብሎ አልቆ አገልግሉ ሲከደን ያይና ተስፋ ቆርጦና ‹ታዘብሁዋችሁ!› እንደሚል ሁሉ አፉን በሰፊው እዬከፈተ ‹አ - ው አ - ው!› ብሎ ደጋግሞ ያፋሽከውና ወጥጦ ሄዶ እውጭ ተጣጥፎ ይተኛል።

ወዲያው የትምርት ቤቱ የምሳ ጊዜ ደርሶ የተከስተ ጉዋደኞች ምንም እንኩዋ ከደመቀች ድግስ በሁዋላ የትምርት ቤቱን ምሳ መብላት ቀርቶ ማየት ባይፈልጉ በግብር ጊዜ ሁሉም በቦታቸው እንዲገኙ ጥብቅ ትዛዝ ስለ ነበረ፥ የደመቀችን እያመሰገኑ ተሰናብተዋት ይሄዳሉ። ተከስተ ብቻ እሁድ እሁድ ቀዋሚ ስንብት ስለ ነበረው እናቱ ደመወዝዋን ስትቀበል እንድትገዛለት የጻፈውን የልብስና የቃ ዝርዝር ሊሰጣት ወደ ሁዋላ ይቆያል።

ደመቀች እሁድ እሁድ፥ ልጅዋንና ጉዋደኖቹን ምሳ አብልታ ስትመልስ ደመወዝዋን ስትቀበል የምትገዛው፥ ይብዛም ይነስ የልብስና የቃ ዝርዝር ሳትይዝ የምትመለስበት ጊዜ በቁጥር ይሆናል። ይልቁንም ተከስተ በዬጊዜው እንድትገዛለት እዬጻፈ ለናቱ የሚሰጣት የልብስና የቃ ዝርዝር ብዙ ጊዜ የማይለያይ አንድ አይነት ስለሆነ በመጀመሪያ እንዲያ ባጫጭር ጊዜ ውስጥ የምትገዛለትን ልብስና እቃ ምን እንደሚያደርገው አልገባት እያለ እንዳትጠይቀው ‹ይቆጣ ይሆናል› ብላ እዬፈራች ትቸገር ነበር። በሁዋላ ግን ለጉዋደኞቹ የሚሰጥ መሆኑን አወቀች።

አንድ ቀን ከብዙ ጊዜ በሁዋላ እንድትገዛለት ጽፎ ለሰጣት ልብስና እቃ ደመወዝዋ እንደማይበቃ ስታይና ይልቁንም ከዚያ ወር ደመወዝዋ የሚበልጠውን ባለፈው ወር የቅድሞሽ ወስዳ ስለ ነበር፥ ያ ሲቀነስ፥ ቀሪው ከጠዬቃት ለግማሹ ያክል ብቻ የሚበቃ መሆኑን ገምታ፥

«ግማሹ ያክል - የሚመጣው ወር መጨረሻ ሊሆን አይችልም አብዬ? » አለች ስትፈር - ስትቸር።

«ሁሉም ለሚመጣው እሁድ ያስፈልገኛል በሚመጣው እሁድ እተፈራ ሉልሰገድ ቤት ፓርቲ - ባማርኛ ምን ይባላል! እ - ግብዣ አደለም? አዎ ግብዣ፥ አለብኝ ስለዚህ ሁሉም ያስፈልገኛል?? አለ ተከስተ።

«ባይሆን እንኳዋ ነጩ ሸሚዝና ጥቁሩ ጫማ በሚመጣው ወር ቢገዙ እነሱን - በቅርቡ ነበር፥ የገዛሁልህ ጠፍተውብህ ነው? » አለች ደመቀች፣ ቀና ብላ የልጅዋን አይን ማየት ስለ ፈራች አይኖችዋን የቃ ዝርዝር ከተጻፈበት ወረቀት ሳታነሳ።

«ሸሚዙ ጠቦ፥ ጫማው - እሱም ጠቦ - ሁለቱም አልሆኑኝም» ካለ በሁዋላ እሱ በሰጣት፥ ቁጥሮች ልክ የተገዙ መሆናቸውን ሊያስታውስ አፍሮ እፍረቱን እንደ ልማዱ በመቅበጥበጥ በቁጣ መግለጽ ፈልገና፥

«ለመሆኑ አንቺ - ለምንድነው በትንናንሹ ነገር ሁሉ እንዲህ መቆጣጠር የምትፈልጊ? ዱሮ እንዲህ አልነበርሽም። አሁን እንደ ገና ብዙ ደመወዝ ስታገኝ ጊዜ ነው ገንዘብ እንዲህ መውደድ ያመጣሽ? ገንዘብ መቆጠብ - ያማረሽ? »

«ገንዘቡን ቆጥቤ ለማን ላደርገው? ቀዳሚ የለህ ተከታይ! በዚህ አለም ያለኸኝ አንተ ብቻ ነህኮ አብዬ! ልብስህ ጠፍቶብህ እንደሆነ ብዬ ጠዬቅሁህ እንጂ - ለመቆጣጠር አልነበረም። ተወው መጠዬቄ የሚያስቀይምህ ከሆነ ከንግዲህ ወዲያ አልጠይቅህም! »

«የለም ዛሬ ‹ምን ቸገረኝ› እያልሁ ብችልሽ ነው እንጂ - አንቺኮ ዛሬ ብቻ አደለም፤ ብዙ ጊዜሽ ነው ‹ጫማህ የት ሄደ? ሸሚዝህን ለማን ሰጠህ? ሹራብህን እገሌ ለብሶ አዬሁ› እያልሽ መጨቅጨቅና መቆጣጠር ካመጣሽ! ህ! የሌሎች እናት አባቶች ለልጆቻቸው የሚያደርጉትን ባዬሽ! ጉዋደኞቻቸውን ይዘው ሲሄዱ የሚያደርጉላቸውን ፓርቲ - ምንድነው - ግብዣ ለጉዋደኞቻቸውም ሆነ ላስተማሪዎችና ለሹሞች ‹ጊፍት› ባማርኛ ምን ይባላል - እ - ስጦታ ነው መሰለኝ - አዎ ስጦታ እንዲያደርጉ የሚሰጡዋቸውን ገንዘብ ብታይ - እንዲህ በትናንሹ ነገር ሁሉ አትጨቀጭቂኝም ነበር! ከንግዲህ ወዲያ አንድ ነገር ‹ግዥልኝ› ብዬ አልጠይቅሽም በትምርት ቤት እንደ ተለመደው ከንግሊዝኛ ጋር በተደባለቀ አማርኛ።

«ተው እንዲህ አትበል አብዬ፤ ሆድ ይብሰኛል! »

«ከጕዋደኞቼ ሳንስ እኔን ሆድ ይባሰኝ እንጂ፥ አንቺን በምን ምክንያት ሆድ ይብሰሻል? »

« ‹ካንቺ ምንም አልፈልግ› ማለትህ ብትቀዬመኝ አደል? ስትቀዬመኝ ሆድ ይብሰኛል! »

«ዱሮ ያልነበረብሽን - እንደገና አሁን የተሻለ፥ ደመወዝ ስታገኝ ‹ግዥልኝ ብዬ› የምጠይቅሽን ሁሉ ‹ለምን› እያልሽ መቆጣጠርና ገንዘብ የመቆጠብ አመል ስታመጪ ምን ላርግ? »

«በዚህ ወር መክፈል የምገደድበት እዳ ስላለብኝ ከዚያ የሚተርፈው የጠዬቅሽኝን በሙሉ ለመግዛት አይበቃምና፥ ግማሹን በሚመጣው ወር መጨረሻ፥ ‹ልግዛልህ› አልሁህ እንጂ ‹አልገዛልህም› አላልሁምኮ! ገንዘብ ለመቆጠብ የምፈልግ መስሎ ከተሰማህ አንድ ነገር ልለምንህ» አለች ደመቀች።

«ምንድነው የምትለምኚኝ? »

«ደመወዜን ስቀበል ሁሉንም እያመጣሁ ላንተ ልስጥህና ላባባ አዛዥ የምከፍለውን ብቻ እዬሰጠኸኝ የተረፈውን ለምትፈልገው አውለው፤ እኔም አንዳንድ ነገር ስፈልግ አንተ ትሰጠኛለህ! »

«አልፈልግም ከንግዲህ ወዲያ ካንቺ ምንም የምፈልገው ነገር የለ! »

«ተው እባክህ እንዲህ አትበለኝ አብዬ፥ ያላንተ ማን አለኝ? » ብላ አንድ እጁን በሁለት እጆችዋ እንደ ያዘች የልብዋን ጭንቀት በሚያሳዩ እንባ የሞሉ አይኖችዋ ሽቅብ ስታየው ያ አስተያየት ለጊዜው ቁጣውን ሁሉ ዘልቆ ልቡን ነካውና ልቡ ወራሪ እንደ ገባው ተሸበረ። ወዲያው ፊቱን አጥልሞት የነበረው ቁጣ ከጸሀይ ፊት እንደሚሸሽ ደመና የጋረደውን ፊት ገልጦ ተበተነ! ተከስተ እኒያን እንባ ያዘሉ የናቱን አይኖች፥ በነሱም በኩል አልፎ የናቱን የተጨነቀ ልብ ዘቅዝቆ ሲመለከት ትንሽ ቆዬና «ቬሪ ሶሪ ስላሳዘንሁሽ በጣም አዝናለሁ እመዬ» አለ ቁጣው ቀርቶ ጸጸት ባሰለሰለው ድምጽ።

«እኔንስ ምንም አላሳዘንኸኝ ይልቅ አንተን አሳዘንሁህ፥ አልሞላልኝ ብሎ - አሳዘንሁህ› አለች ደመቀች አይኖችዋን ሞልቶ የነበረው እንባዋ ተርፎ መፍሰስ ሲጀምር እንዳያይባት አንገትዋን ወደ ላይ ካቀናችበት ወደ መሬት መልሳ ከዚያ ተከስተ

አንገትዋን አቅፎ ራሱን በራስዋ ላይ ጥሎ ሁለቱንም ሳይናገሩ ዝም ብለው በዬልባቸው ራሳቸውን ሲወቅሱ ከቆዩ በሁዋላ፥

«እባክህ አትዘን፥ ‹ብድር ያላገኘሁ እንደሆነ› ብዬ ፈርቸ ነው እንጂ ገንዘብ መቆጠብ ፈልጌ አደለም» አለች በሹክሹክታ የሰይጣን ጆሮ ሰምቶ እርቁ እንዳይፈርስ።

«ሸሚዙና ጫማው ብቻ ለዛሬ ሳምንት፥ እሁድ የሚደርሱልኝ ከሆነ ሌላው ቢቆይ ግዴለም፤ ሲመችሽ ትገዥልኛለሽ፤ ካልተመቸሽ ይቅር» አለ ልጅዋም እንደናቱ በሹክሹክታ። ለጊዜው በናትና ልጅ መሀከል እርቅ ሰላም ወረደ።

## ምእራፍ ሀያ አምስት

# በሻህ ደማሙ

ደመቀች፥ ወደ ቤትዋ ስትመልስ ምሳ ተበልቶ ሲያልቅ ደረሰች። ወይዘሮ ላቀች ተገኔ የሚባሉት የወይዘሮ፥ ጌጤ ዘመድና አቶ በላቸው ይፍሩም እዚያ ነበሩ። ወይዘሮ ላቀች የደጃዝማች ሉልሰገድ ክንፌ ሚስት፥ በድሮ ባህልና ልማድ አድገው የበለተቱ፥ የዘመኑን ስልጣኔ እንደ እብደት የሚቆጥሩ እጅግ፥ የተከበሩ ወይዘሮ ነበሩ። ዘምዳቸው ወይዘሮ ጌጤ ታመው ሰንብተው በጎ ከሆነ በሁዋላ ስለሰሙ፥ ሊጠይቅዋቸው መጥተው ነበር። አቶ በላቸው ይፍሩ - በትምርት ሚኒስቴር የትምርት አመራር ክፍል ሹም - የወይዘሮ ላቀችን ዘመድ ያገባ ወጣት ነበር። የወይዘሮ ላቀችን አቶሞቢል ባለቤታቸው ደጃዝማች ሉልሰገድ ይዘውባቸው ወደ ግቢ ስለ ሄዱ፥ ሊያደርሳቸው መጥቶ ነበር። ደመቀች ከመድረስዋ ትንሽ ቀደም ብሎ በሻህ ዘለሌም አዝማሪው ውቤን ፍለጋ መጥቶ ስላጣው ሊሄድ ከበሩ አጠገብ ቆሞ ነበር።

«ዛሬ እንኩዋን አገኘሁ ጋሼ፤ ለልጄ እቃ ትገዛልኛለህ፥ ተቀመጥና ምን ምን እንደምትገዛልኝ ልንገርህ» አለች ደመቀች ለወይዘሮ ላቀች ለጥ ብላ እጅ ነስታ፥ ለሌሎች ሰላምታ ሰጥታ ስትቀመጥ።

«ምን - እቃ ነው የምገዛልሽ? » አለ በሻህ እያመነታ ተመልሶ አጠገብዋ ሲቀመጥ።

«አንድ ነጭ ሸሚዝና አንድ ጥቁር የሁለቱም ቁጥር ይሄው፤ ብቻ ሁለቱንም ከዛሬ ሳምንት እሁድ አፊት እንድታደርስልኝ አደራ! »

«የዛሬ ሳምንት እሁድ ምንድነው? አለም የሚያልፍበት ነው? ከዚያ በሁዋላ አለም የለም? » አለ በሻህ ትንሽ ፍርጥም ብሎ።

«የዛሬ ሳምንት እሁድ፥ ግብዣ ስላለበት ከዚያ በፊት እንዲደርስለት አደራ ብሎኝ ቃል ገብቻለሁ፥ ጋሼ።»

«ከተፈጠርሁ ሁለት.... ኧረ ሶስት እንጂ! ሶስት የማያልቁ ነገሮች አዬሁ! » አሉ አዛዥ አቁዋርጠው። «አንዱ የደመቀች ልጅ ምክንያት ሁለተኛዉ የስዋ ትግስት መብዛት፤ ሶስተኛው የገንዘብዋ አለማለቅ ናቸው። ይገርማችሁዋል! ይህ ልጅ ትምርት ቤት ከገባ ጀምሮ አሁን ይኸው..... እንጃ፥ ስንት አመት ሆነው? ብዙ አመት ሆኖታል፤ እሁድ እሁድ ምሳውን ይዛለት በሄደች ቁጥር ምክንያት እዬፈጠረ ‹ይህን ግዢልኝ፤ ያን ግዢልኝ› ሲል እስዋ እዬገዛች ስታግዝ የሱ ምክንያትም ሆነ የስዋ ትግስትና ገንዘብ ሳያልቅ እኛን እዚህ ማየት መስማቱ አሰለቸን! እኔማ አንዳንድ ጊዜ ‹ከቶ ይህ ልጅ..... እንዲህ በዬሳምንቱ የምታግዝለትን እቃ እዬተቀበለ የሚሸጥበት እዚያ ሱቅ ከፍቶ ይሆን?› እላለሁ» ሲሉ አዛዥ ትንሽ እንደ መሳቅ ብለው ሁሉም ሳቁ።

«አይ - ! ምነው አባባ? » አለች ደመቀችም ከሌሎች ጋር፥ ስትስቅ ቆይታ።

«ምን ልበል? በዬሳምንቱ ልብስና ጫማ...... ሌላውንም ሁሉ ከምሳው ጋር እዬተሸከምሽ ስታግዢ አያለሁ! ታዲያ.... ካልተሸጠ፥ ወይ ካልተሸጠ ልብስና ጫማ ሹራብና እንዲህ እንዲህ ያለው እቃ ሁሉ እንድ እንጀራ በለት ተበልቶ የሚያልቅ ነገር አይደለ! »

«ምናልባት ለጉዋደኞቹ ይሰጥ ይሆናል፥ ተማሪዎች ልብስ ይለዋወጣሉ» አለ በሻህ።

«ታዲያ እስዋ እዚያ ተማሪ ቤት ያለውን ተማሪ ሁሉ እቃ ገዝታ ትገፋዋለች? »

«አይ እምቸም....... ልብስ የሚለዋወጡት በቁጥር ይሆናሉዋ! »

«የጌቶች ልጆች እንዲህ ቢያደርጉ ግዴለም! መቸም ጌታ ማለት፥ እንዲያው የተገኘ ገንዘቡን እንዲያው ‹ለይዩልኝና ለይስሙልኝ› ብቻ የሚበትን ነው! ታዲያ...... ደመቀች ገንዘብ በመበተን ከጌቶች ጋር መወዳደር ይሆንለታል? »

«ስሙልኝ ይህን ተሳዳቢ» አሉ ወ/ላቀች እዩሳቁ።»

«የለምኮ አባባ! ቅድም ጋሼ እንዳለው ብዙ ጊዜ የጉዋደኞቹን ልብስ ለብሶ፥ የጉዋደኞቹን ጫማ አድርጎ ስለማይ፣ ‹የነሱን ያክል እንኩዋ ባይሆን በትንሹ ስጦታውን ሲመልስ ደስ ይለው ይሆናል› ብዬ ራሴ ገምቸ አንዳንድ ነገር እገዛታለሁ እንጂ፥ እሱ ‹ካልገዛሽልኝ› ብሎ አስቸግሮኝ....... አያውቅም። ‹ምንም ባይናገር ከጉዋደኞቹ ያነሰ መስሎ የተሰማው እንደሆነ ሳያዝን አይቀርምና አቅሜ እስኪወስነኝ የምችለውን ላድርግ› ብዬ...... እኔ የማደርገው ነው» አለች ደመቀች ልጅዋን ላለማስወቀስ አሰት ስትናገር ከህሊናዋ ጋር የነበራት ሙግት በፊትዋ እዩታዩ።

«የለም! » አሉ አዛዥ ራሳቸውን እዩወዘወዙ። «የለም ያቅምሽን ወሰን አለማወቅሽማ......ይሄው እዩተበደርሽ ለጌቶች ልጆች ልብስ ስትገዥ ይታያል! ደግሞ» አሉ አዛዥ ቀጠሉና። «ደግሞ እኔ የምሰጋው ይህ ሁሉ ከሆነ በሁዋላ፥ ‹እንዳይከፋው ደስ እንዲለው› ብለሽ ደመወዝሽን የቅድሞሽ እዩወሰድሽ ለማታውቂያቸው ሁሉ ልብስ ስትገዥ ከኖርሽ በሁዋላ በመጨረሻ የፈራሽው እንዳይደርስ እንዳይቀዩምሽ ነው! »

«እንዴት! ለምን? » አለች ደመቀች እንደ መገረምም እንደ መደንገጥም ብላ።

«አሁን» አሉ አዛዥ ደመቀች የጠዩቀቻቸውን ለሌሎቹ እዩመለሱ። «መቸም አሁን የሚጠይቃትን ሁሉ ያለ ቅርታ ስለምትፈጽምለት የሚቸግራት ነገር ያለ አይመስለውም። ድህ እስከ መሆንዋም ጨርሶ ሳይረሳው አይቀርም! ነገር ግን መቸም ሁልጊዜ አይሞላ፥ አንድ ቀን ማድረግ የማትችለውን ነገር ይጠቃይቃትና ‹አልችልም› ያለችው እንደሆነ አያምናትም፤ አይቀዩምም? ይቀዩማል፤ የፈራችው ይደርሳል! እንደኔ እንደ ሞኙ የሆነ እንደሆነ ለሁሉም ነገር አስቀድሞ ወሰን ማድረጉ ነው የሚጠቅመው! ደግሞ ከዚህ ሌላ» አሉ አዛዥ እንደገና ወደ ደመቀች አይናቸውን መልሰው። «ደግሞ ከዚህ ሌላ ልትረሽው የማይገባ አቢይ ነገር ለጊዜው ‹እንዳይከፋው› ብለሽ አቅሙን

አውቆ እንዳይኖር ማድረግሽ ለሁዋላ ራሱን የሚጎዳው መሆኑን ነው። ‹ሲጎርስ ያደገ በመላስ ዘመን ራብ ይገለዋል› የሚሉት እንዳይደርስበት ማሰብ አለብሽ።»

«የሚፈልገውንና የሚጠይቀውን ለማድረግ የምትችልበት ጊዜ አይምጣ እንጂ፥ ከመጣማ፥ እናትና ልጅነታቸው ቀረ ማለት ነው! » አለ በሻህ።

«እንዴት? ምን ማለትህ ነው? » አለች ደመቀች፥ በመገረም ፊት።

«ይቅርታሽን! ‹ያንቺ ልጅ ከሌሎች ልጆች ቢለይም ልዩነቱ ብዙ ሊሆን አይችልም› ብዬ ነው እንጂ ጠባዩን ይህን ያክል አውቄው አደለም። እንደ ሌሎች ልጆች ከሆነ ግን……. የዛሬ ልጆች ወላጆቻቸውንና ዘመዶቻቸውን የሚቀርቡ ጥቅም እስካዩ ድረስ ነው እንጂ ጥቅም ካላዩ መራቅ ብቻ ሳይሆን ይንቁዋቸዋል፤ ይጸዩፋቸዋል! የዛሬን ልጆች ጥቅም እንጂ የወላጆችና የዘመድ ፍቅር አይስባቸውም።»

«የኔ ልጅ እንዲህ አደለም፤ ባታውቀው ነው» አለች ደመቀች።

«ያንቺ ልጅ አንቺ እንደምትይው ይሆናል፤ እኔ የማውቃቸው ግን፥ እኔ እንደምለው ናቸው። አንድ ማስረጃ የሚሆን ምሳሌ ልስጥሽ። መንግስት እዬከፈላቸው ባዳሪነት የሚማሩት ልጆች ሁሉ፥ ትምርት ቤት ሲዘጋ የረፍቱን ጊዜ ከዬዘመዶቻቸው ጋር ለማሳለፍ እዚህ ከተማ የሚኖሩት እዚህ ከዬጠቅላይ ግዛቱ የመጡት ወደያገራቸው ሲሄዱ በዬወሩ ለትምርት ቤት የሚከፍልላቸው ታስቦ ሄደው ለሚቆዩበት ጊዜ ገንዘቡን ይዘው ይሄዳሉ። ያን ገንዘብ ይዘው እውነት ወደ ዘመዶቻቸው የሚሄዱ ይመስልሻል? ምን ቸገረን ብለው! ያን ገንዘብ ከድሆች ወላጆቻቸው ወይም ዘመዶቻቸው ጋር እዬተካፈሉ አብረው በመቆዬት ፈንታ እዚህ፥ ያሉት እዚህ ወደዬጠቅላይ ግዛቱ የሄዱት እዚያ በሚገኙ ከተሞች ጉዋድ ጉዋድ እዬሆኑ ከዘመዶቻቸው ርቀው ቤት ተከራይተው፥ የራሳቸውን ደስታ ሲከታተሉ ቆይተው ‹ከመሀከላቸው ወላጆቻቸውን አንድ ቀን እንኩዋ ሳያዩ የሚመለሱ አሉ› ብልሽ ታምኛለሽ? በምቹ አልጋና ፍራሽ የሚያስተኙ ለከንቱ ውዳሴ እዬደገሱ የሚያመጡዋቸውን ሁሉ ሊጋብዙላቸው የሚችሉ ወላጆችና ዘመዶች ያሉዋቸው እያዋሉ፥ ከጎን አዳሪ ወላጆቻቸውና ዘመዶቻቸው ጋር ቆይትው ይመለሳሉ። ይህ አንድ ጊዜ ትምርት ሚኒስቴር ሰራተኛ ስለ ነበርሁ እኔ የማውቀው ነው።»

«ይህ የሚለው ሁሉ እውነትኮ ነው! » አሉ ወይዘሮ ላቀች ባይናቻቸው መጀመሪያ አዛዥን ከዚያ ደመቀችን ገረፍ አድርገው እንደገና በሻህን ፊት ለፊት እያዩ።

«የምትለው ሁሉ እውነት ነው። የኛ የቅርብ ብቻ ሳይሆን የሩቅ ዘመዶቻችን ልጆች እንኩዋ የወላጆቻቸውን ቤት አያውቁትም። ወላጆቻቸው እንደኛ የተመቻቸው ስላልሆኑና የሚፈልጉትን ቅጥ መጠን የሌለው ነገር ሁሉ ሊያደርጉላቸው ስለማይችሉ ጭራሽ ዘወር ብለው አያይዋቸውም። «ጉዋደኞቻችነን ልንጋብዝ ነው ድግስ ደግሱ ስጦታ ልንገዛ ነው ገንዘብ አምጡ «የምንባል እኛ ዘመዶች ነን! እንጃ! እንዲያውም አሁንስ ከነሱ መወለዳቸውን እንኩዋ ሳይረሱት የቀሩ አይመስለኝም! ወላጅ አባታችን ናቸው እያሉ ለሰው የሚያወሩም፣ የሚምሉባቸውም፥ ከሩቅ ተፈልገው ሄደው ደጃዝማች ሉልሰገድ ሆነዋል! መቸስ...... አንዳንድ ባለጌ ልጅ አንዳንድ፥ ወላጆቹን የሚንቅና ከነሱ የሚኮበልል የተረገመ ልጅ ድሮም ቢሆን አልፎ አልፎ ጠፍቶ አያውቅ። ነገር ግን የዛሬ ልጅ ሌላ ነው፥ ዛሬ...... ልጁ ሁሉ እንደ ተማከረ ሁሉ ያው አንድ አይነት ነው። ታዲያ ይህ ሁሉ አይና፥ ችግር ሲለኝ ጊዜ «ከቶ ይህ የፈረንጁ ትምህርት እንደ ሰይጣን ትምርት ልጆችን ከድሆች ወላጆቻቸውና ወገኖቻቸው አጣልቶ ትምርት ልጆችን ከድሆች ወላጆቻቸውና ወገኖቻቸው አጣልቶ፥ የሚለያይ ይሆን? ወይስ - ያ ልጅ ከናት ካባቱ ባል ከሚስቱ ወንድም ከህቱ ወገን ከወገኑ የማይስማማበትና የዚህ አለም ስራቱም ህግጋቱም ሁሉ የላዩ ታች የፊቱ ሁዋላ ግልብጦሽ የሚሆንበት ጊዜ፥ ያ ስምንተኛው ሺ የሚባለው ጎግ - ማጎግ ደርሶ ይሆን? » ስል እነሱ ይስቁብልኛል! » አሉ በላቸውን ባገጫቸው እያሳዩ። በላቸው እንደ መሳቅ ብሎ አንገቱ ደፋ።

«እውነትዎ ነው እመቤቴ የሚያሰኝ ነው፤ ከሁለቱ አንዱ መሆን አለበት! » አለ በሻህ ከሌሎች ጋር ሲስቅ ቆይቶ። በላቸው ከንፈሮቹን ሞጥሞጥ አድርጎ ራሱን ወዘወዘና አሁንም አንገቱን ደፋ። «ሊቁ ለሊቅዋ መሰከረ» ማለቱ ነው።

«ተባረክ ልጄ! » አሉ ወይዘሮ ላቀች፥ በሻህ አሳባችወን የተቀበለ ስለ መሰላቸው ፊታቸው በደስታ በርቶ። «ተባረክ! የሰው አስባ የሚገባው የሰው አሳብ የሚያስተውል ሰው እወዳለሁ! አንተ በጣም አስተዋይ ነህ። አሁን ስለዛሬ ልጆች የተናገርኸው ልክ ቅቤ እንደ ጠጣሁ አንጀቴን ገብቶ ሲያርሰው ተሰማኝ! አንተ አስተአይ ብትሆን ነው እንጂ - ሌሎችማ እኒህ እኒህማ አሁን፥ የተናገርሁትን ስናገር እንዳላዋቂ ቆጥርውኝ ይስቁብኛል» አሉ አሁንም በላቸውን ባገጫቸው እያሳዩ። በሻህ ለወይዘሮ ላቀች እድነ መሰላቸው ባሳባቸው ተስማምቶ ሳይሆን ገና ያንለት የተዋወቅናቸውን ትልቅ ወይዘሮ ማስተሀቀር ከብልግና እንዳይቆጠርበት፥ ‹አዎን› ብሎ ለማሳለፍ ፈልጎ ነበር። ነገር ግን ወይዘሮ ላቀች በሳቸው እድሜ ያሉት ሰዎች እንኩዋ ዋጋ እንደሌለው አሮጌ ቡትት

እዬቆጠሩት የሚንቁት አሳባቸው ለመጀመሪያ ጊዜ ይልቁንም ከወጣቶች መሀከል ደጋፊ ስላገኙ፥ ደስታው ገፋፍቶዋቸው፥ ከሊቃውንቱ ከቄሶች የተረዱትን ለበሻህና እዚያ ለነበሩት ሁሉ አስፋፍተው ለማስተማር ፈልጉ።

«እኔ አልተማርሁም» አሉ፤ «ነገር ግን የተማሩት ቄሶች እንዳስረዱኝ» ብለው ሊቃውንቱ ቄሶች፥ ያስረዱዋቸውን ሊቀጥሉ ሲሉ፡-

«ዳይት ይደግሙ የለ፥ ከዚህ ወዲያ ትምርት ቄስና ደብተራ ይሆኑ ይመስል ምን ያረጋል! » አሉ አዛዥ አቁዋርጠው።

«አ - ይ ለዚያስ ውዳሴ ማርያምና መልከ ማርያም፥ መልከ ዬሱስም አውቃለሁ! » አሉ ወይዘሮ ላቀች፤ በኩራት ትንሽ እንደ መንጠራራት ብለው። «ቄሶች ብዙ ጊዜ ሲሉ እንደ ሰማሁ» አሉ ቀጠሉና። «ዛሬ የሚሆነውን ሁሉ ስመለከተው ያ ክፉ ጊዜ ያ ‹ስምንተኛው ሽ› የደረሰ ይመስለኛል! መቸም በወዳጆች መሀከል ፍቅር መተሳሰብ መተዛዘን የሚጠፋ፥ መጣላትና መጨካከን የሚስፋፋ ስራቱና ህግጋቱ ሁሉ ግልብጦሽ የሚሆን ‹ስምንተኛው ሺ ሲደርስ› ነው ይባላል። ታዲያ ዛሬ የምናየው ሁሉ ይህ አደለም? ይህኮ ነው! እስቲ - ልጅ - ፈጥረው ብርሃን አሳይተው ከነለሀጩ እየሳሙ ከነሽንቱና ከነ - እያቀፉ ሳይጸዬፉ ያሳደጉትን የፈጠሩትን ወላጆቹን አክብሮ በመታዘዝ ፈንታ እንዳሳደራቸው ሎሌዎቹ ከፍ ዝቅ አርጎ እያዬ የግልብጦሽ ‹ልዘዛችሁ› የሚልበት ጊዜ በራስ ስራትና ህግጋት እዬሳቁ እየተሳለቁ ለባእድ ለተውሶ ስራትና ህግጋት ‹አንሙት› የሚባልበት ጊዜ የበላይን ማፈርና ማክበር እንደ ገልቱነት መባለግና አይነ ደረቅ መሆን እንደ ስልጡንነት የሚቆጠርበት ጊዜ፥ ወንድ ሴትን ማባበሉን ቀርቶ ሴት ወንድን የምታባብልበት ጊዜ እስቲ እንዲህ ያለውን ጊዜ ቀርቶ ጊዜ ይባላል? ጤነኛ አደለም! የዚያ የክፉው ጊዜ የዚያ የጎግ - ማጎጉ መንገድ ጠራጊ ነው! የሴቶችን ልጆች ነገርማ እንዲያው ትተውታል። ከፍረት ታጥበው ጠርተዋል! እስቲ..... ሴት እፍረትን ከተወች ምን ይቀራታል? ሴት በፍረትዋ በደካማነትዋ በኩራትዋ ነበር ደፋሩን ብርቱውን ጀግናውን ወንድ ማርካ፥ እስረኛዋ አድርጋ ሁዋላ ሁዋላዋን ስታስከትለው የምትኖር። ሴት ሳያይዋት ሰረቅ አርጋ አይታ ሲያይዋት አይንዋን መለስ፥ አንገትዋን ቀለስ አድርጋ ዘወር ያለች እንደሆነ ወንድ ልቡ እየሮጠ፥ የሚሸሽ አይንዋን እንደገና ለመያዝ መከታተል መጨነቅ፥ መቸገር ይጀምራል! ያንጊዜ ተስፋ ቆርጦ እንዳይቀር እዬሰረቀች እያዬች አገኘሁዋት ብሎ ደስ ሲለው እዬሸሸች እያመለጠች ወዳው ልብዋ እሺ ሲል አፍዋ እምቢ እያለ ልብዋ ከሱ ጋር ወደ ሁዋላ ሲቀር እግርዋ ወደ ፊት እየሄደ

እንዲህ ደጅ አስጠንታ፥ እንዲህ ጉልበቱን አድክማና ልቡን አሳምማ፥ በመጨረሻ ‹እሺ› ስተልው ያለው ደስታ! የፍቅር ጉዞ እንዲህ ጎትቶ፥ ጎትቶ አስረዝሞ በመጨረሻ ሲደርሱበት ደስታውም ያን ያክል ነው! ፍቅር የሴትዋም የወንዱም ልብ እስኪያለቅስ ተርቦ ተርቦ ሲገኝ አይጠገብም! የዛሬ ሴት ልጆች የሚያደርጉት ግን ‹ሴት ባልሆንሁ› የሚያሰኝ ነው! አንድ ቀን ሴቶችም ወንዶችም ተማሪዎች እኛ ቤት ተሰብስበው ያን - ድስ ነው? ‹ድንስ› የሚሉትን ነገራቸውን ካዬሁ በሁዋላ እነሱ ሲመጡ ቤቱን እዬተውሁላቸው እሄድ ጀመር! ወንዱ ተነስቶ ገና ወደስዋ ለመሄድ መንገድ ሳይጀመር ወደስዋ ለመሄድ ማሰቡን እንኳዋ ሳታረጋግጥ ከተቀመጠችበት ብር ብላ ሄዳ ትጣበቅበታለች። ከዚያ እንዳልመጣት ወገቡን አንቃ ይዛ እሱ ወንገር ወንገር ሲል እስዋ ውጥን ውጥን እሱ ወንገር ወንገር እስዋ ውንጥ ውንጥ እያሉ ሁሉም ወንድና ሴት እዬሆኑ መተራመስ ነው! ውይ! አበስኩ ገበርኩ! ታዲያ እንድነህ ያለው ጊዜ ምን ነው? እድነህ ያሉት ልጆችስ ምንድናቸው? ሴቶች እናቶቻቸውን ወንዶች አባቶቻቸውን የማይመስሉ ልጆች የማናቸው ይባላል! »

«የማንም! » አለ በሻህ፥ ሌሎች ሲስቁ አንገሩን ደፍቶ ከቆዬበትና ቀና ሲል ማዘኑ ከፊቱ እዬታዬ።

«ታዲያ - የማንም ያልሆኑ ልጆች የሚወለዱበት ጊዜ ጤነኛ ነው ይባላል? »

«ሲወለዱኮ የማንም ያልሆኑ ልጆች የሉም፥ እመቤቴ። ልጆች ሁሉ ወላጆች እንዳሉዋቸው መቸም ግልጽ ነው። ነገር ግን የስጋ መወለድ ብቻ ልጆችን ሙሉ በሙሉ የወላጆቻቸው ልጆች አያደርጋቸውም። ልጆች ሙሉ በሙሉ የወላጆቻቸው ልጆች እንዲሆኑ፥ ወላጆች ለልጆች ስጋና ደማቸውን አጥንትና ጅማታአቸውን ቆዳቸውን ብቻ ማካፈላቸው አይበቃም። ልጆች ሙሉ በሙሉ የወላጆቻቸው ልጆች እንዲሆኑ ወላጆች ለልጆቻቸው ታሪካቸውን ስልጣኔያቸውን ባህላቸውን ህገ - ወጋቸውን የኑሮ ስራታቸውንና ይህ ሁሉ የሚሰጠውን የመንፈስ የምነትና የስሜት ጸጋ ጭምር ማካፈል ይገባቸዋል። ወላጆች ልጆቻቸውን ወልደው ማን መሆኑን የማያውቁት ባእድ እንዲያሳድጋቸው የተዋቸው እንደሆነ በስጋ ወላጆቻቸው በመንፈስ በምነትና በስሜት አሳዳጊያቸው የሚካፈሉዋቸው ይሆኑና በመሀል ቤት የማንም አይሆኑም።»

«አሁን ያለውን ጭራሽ አላስተዋልሁትም እናንተ አስተውላችሁታለሁ? » አሉ ወይዘሮ ላቀች፥ ወደናዛዥ ዘወር ብለው።

«በሻህ አንዳንድ ጊዜ የሚናገረው ፍቺ የሌለው እንቆቅልሽ ነው፥ ለማንም አይገባ! » አሉ አዛዥ እዮሳቀ።

«የተናገርሁት እንቆቅልሽ አደለም፥ ግልጽ ነው» አለ በሻህ። «አዩ! » አለ ቀጠለና፥ መጀመሪያ አዛዥን ከዚያ ሌሎችን ባይኑ ገረፍ አድርጎ። «አዩ? አያችሁ? የኢትዮጵያን ልጆች ኢትዮጵያውያን ወለዱዋቸው፤ በቃ። የኢትዮጵያ ልጆች ኢትዮጵያውያንነታቸው እዚያ ላይ ቆመ። ከዚያ ፈረንጅ ተቀብሎ ታሪኩን ስልጣኔውን ህገ - ወጉን ባህሉን የኑሮ ስራቱንና የዚህ ሁሉ ስሜት የሚገልጽበትን ልዩ ልዩ ዘዴ እያስተማረ አሳደጋቸው። በመንፈስ በምነትና በስሜት የፈረንጅ ልጆች ሆኑ። እንግዲህ እንዲህ ያሉት ልጆች በሙሉ ኢትዮጵያውያን አይደሉም፤ በሙሉ ፈረንጆች አደሉም፤ ስለዚህ ማንም አደሉም ነው ያልሁ። ታዲያ ይህ ግልጽ አደለም? ይህ እንቆቅልሽ ነው? »

«እውነትም በሻህ የተናገረው ለወይዘሮ ላቀችና ላናዛዥ ፍቺ የሌለው እንቆቅልሽ ነበር። ለኢትዮጵያ ትምርት አመራርና ያላፊነት ተካፋይ ለሆነው ለበላቸው ይፍሩ ግን እንቆቅልሽ አልነበረም። በሻህ የተናገረው የኢትዮጵያን የትምህርት አመራር መሰረት እንደሌለውና ለሱ አላፊ የሆኑትን ባለስልጣኖች በላቸውን ራሱን ጭምር የሚያደርጉትን ሳያውቁ እንዲሁ እውር ድንበሩን የሚዳብሱ አላማ ቢሶች አድርጎ የሚነቅፍ የሚዘልፍ ስለ መሰለው ዝም ብሎ ማሳለፉ ዘለፋውን ስድቡን ለብሶ መሄድ መስሎ ታይቶት ባላቸው ሊከላከል አሰበ። ነገር ግን ውስጥ ውስጡን የበሻህ ነቀፋና ዘለፋ መሰረት የያዘና የትምርቱን ባለስልጣኖች አጥብቆ የሚያሳስብ መሆንኑ ሳይሰማው አልቀረም።

በላቸው ይፍሩ በትምርት ሚኒስቴር ውስጥ የትምርት አመራር ክፍል የዋናው ሹም ምክትል ነበር። በላቸው በትምርቱና በችሎታው ከፍተኛነት ላይ ቀድሞ ገብቶ፥ ዘግይቶ ወጥቶ፥ ጊዜውን ሳይቆጥብ በሙሉ ልብ የሚሰራ ትጉ ሰራተኛ ስለሆነ በትምርት ሚኒስቴር አካባቢ ከሚመሰገኑትና ባለ ብርቱ ተስፋ ከሆኑት ሹማምንት አንዱ ነው። ይልቁንም በላቸው ኢትዮጵያ፥ የተፈጥሮ ሀብትዋ ገና ያልለማ፥ ህዝብዋ ገና ያልተማረ አገር መሆንዋን ሀብትዋን ማልማቱም ሆነ ሕዝብዋን ማስተማሩ አዲሱን ወይም የተማረውን ትውልድ የሚጠብቅ የተማረው ትውልድ የተቀደሰ ተግባር በተማረው ትውልድ ላይ የተጣለ አደራ መሆኑን እየገለጸ ሁሉም፥ ከሚኒስትሩ ጀምሮ እስከ ተራው ሰራተኛ ይህ አላፊነት ተሰምቶ፥ ይህ ጥብቅ አደራ፥ ከብዶት የሀዋርያነት

ተግባሩን ባለመፈጸሙ ነቅፎ ወቅሶ ሲናገር የሚሰሙት ሁሉ ራሱ በሚያርሰው ብቻ ሳይሆን ሌሎች ጭምር እንዲሰሩ ለማነቃቃት በሚያደርገው ጥረት ይደነቃሉ።

በላቸው ይፍሩ የተማረውን ክፍል የሀዋርያነት ተግባሩን ባለመፈጸሙ ‹አደራበላ› በመሆኑ የሚነቅፈውን ያክል ላልተማረው ክፍል አዛዥና ተቆርቋሪነቱ በሰፊው የታወቀለት፥ ነበር። ገንዘብ በጁ ካለ ለድሀ መስጠት፥ ደካማ ካዬ ከመንገዱ ወጥቶ መርዳት መውደዱ፥ በቃል የሚናገረውን በግብር የሚፈጽም ለመሆኑ አንድ ምስክር ነው። ያልተማሩት ሁሉ ይልቁንም ባጠቃላይ ስም «አዲስ ትውልድ» እዬተባለ ከሚጠራው ቀደም ያሉት ርዳታ የሚገባቸው የሚታዘንላቸው መሆናቸውን ከልቡ አምኖ፥ «ፑር ቲንግስ» እያለ ያዝንላቸዋል። የሚችለውን ያክልም ሊረዳቸው ይጥራል። ነገር ግን ከነሱ ጋር ካዲሱ ትውልድ ቀደም ካሉት ጋር ከቀልድና እንዲሁ በተራ ወሬ በቀር ስለ ጠቅላላ ያገር አስተዳደር ወይም ሌላ ከፍተኛ ጉዳይ መነጋገር መቻም የማይታሰብ ነው። ዘመናዊ ትምርት ተምረው በላቸው ባለፈበት ወይም ከሱ ተመሳሳይ በሆነ መንገድ ያላለፉ ሁሉ ‹ስለ ሀገራቸው የፖለቲካ ይሁን የኢኮኖሚ ወይም የማህበራዊ ኑሮ ጉዳይ ቢነግሩዋቸው ይገባቸው ይሆናል፥ ወይም እነሱ ከሚናገሩት አንዳንድ የሚያዝ ነገር ይኖርበት ይሆናል› ብሎ እንኩዋንስ ሊያምን ስለማይጠረጥር እንዲያ ባሉ ከፍተኛ ጉዳዮች ላይ ካዲሱ ትውልድ ቅደም ካሉት ጋር አሳብ መለዋወጥን በከንቱ ጊዜ እንደ ማባከን እዬቆጠረው በነሱ መሀከል የሚያሳስብ ያገር ጉዳይ አያነሳም። የሚያነሳም ቢኖር የሚያዳምጥ ለመምሰል የውሸት ፈገግታ እያሳዬ፥ ከመቀመጥ በቀር ተካፋይ አይሆንም።

ያንለትም ወይዘሮ፥ ላቀችን አዛዥ ቤት እንደደረሰ እሳቸው፥ ሲገቡ እሱ አውቶመቢሉ ውስጥ ለመቆዬት ፈልጎ ነበር። ነገር ግን ወይዘሮ ላቀችም አዛዥም እንዲገባ ስላስገደዱት ገብቶ ለወይዘሮ ጌጤ ሰላምታ ከሰጠ በሁዋላ አንድ ወንበር ላይ እግሮቹን አደራርቦ እንደ ተቀመጠ ከዝምታው የተነሳ እስከ መኖሩም ረስተውት ሌሎች እስበሳቸው ይጫወቱ ጀመር። በምሳ ጊዜም አዛዥና ባልተቤታቸው ከንግዳዋ ጋር ሲበሉ ወደ መሶቡ ለመቅረብ እንኩዋ አልፈለገም። ባለቤቶቹ ለመና ሲያበዙ «እሱ ይህን - የኛውን አይበላም ተዉት» አሉ ወይዘሮ ላቀች። እሱም፥ «ኧረ - አሁን በልቼ ስለ መጣሁ ነው» ብሎ ትንሽ እንደ መሳቅ አለና አንገቱን ደፍቶ ዝም አለ።

ከዚያ በሻህ ገብቶ እጅ ነሳ። ተጠርጎም ተተኩሶም የማያውቅ ጠቆር ያለ ሱሪና ባለቀበቶ ካኪ ኮት ለብሶ ሁለቱም ባንድነት በቀበቶው ከርፈፍ አድርጎ ታጥቆ ከንጹህነቱ በቀር መተኮሻ ያልነካው ጨምዳዳ ሸሚዙን ለብሶ፥ ቀለምና ቡርሽ ነክቶት የሚያውቅ

የሚመስል ከባድ ጫማ አድርጎ እንደ ወጣቶች ፈጠን ፈጠን ሳይል፥ ከባድ ጫማውን እዬጎተተ ቀስ ብሎ ስለ ነበረ ገብቶ እጅ የነሳ፥ በላቸው በድሜ ባይሆን በሌለው ሁሉ የናዛዥ ወይም የቀድሞው ትውልድ ውገን አድርጎ ቆጥሮት፥ ትንሽ ቀና ብሎ ተመለከተውና አይኖቹን ወደ ነበሩበት መለሰ። እንዲያውም መጀመርያስ ካለባበሱና ከጠቅላላ ሁኔታው እዚያው ያዛዥ ዘበኛ ወይም አታክልተኛ ወይም ባልተቤታቸው ተነስተው የጅ ሰላምታ ሲሰጡና፥ ከዚያም ደመቀች እንዲቆይ ስለ ለመነችው ቅር እያለው መቀመጡን ሲያይ አሽከርም ቀላዋጭም አለመሆኑን ገመተ። ነገር ግን እንኳዋንስ እንደ ትምህርት አሰጣጥ፥ ባለ ከፍተኛ ፍልስፍና ላይ አሳብ ለመስጠት የሚንጠራራ፥ ‹ንባብና ጽህፈት በቅጡ የሚያውቅ ይሆናል› ብሎ አልጠረጠረም። በሻህ መጀመሪያ ካዛዥ ጋር ተማሮችን እዬነቀፈ ሁዋላም ወይዘሮ ላቀች ‹ተማሮች ከወገኖቻቸውና ከባህላቸው እዬራቁ ወደ ባእድና ወደ ባእድ ባህል እዬተጠጉ የሚሄዱ የሚማሩት የፈረንጅ ትምርት የሰይጣን ትምርት ስለሆነ ወይም ስምንተኛው ሺህ ስለ ደረሰ ነው› ሲሉ እሳቸውን እዬደገፈ መናገሩ ያው የነሱ ቢጤ ያው እንደነሱ ‹ከጥንቱ ዝባዝንኪ አንድ ነቁት ከሚወድቅ ሰማይና ምድር ቢያልፍ› የሚመርጥ ያው እንደነሱ የዘመናዊን ትምርት ከፍተኛ ዋጋ የማያውቅ ስለሆነ መሆኑን አምኖ ይህ ሁሉ መጀመሪያ ስለሱ የገመተው ያልተሳሳተ መሆኑን አምኖ ይህ ሁሉ መጀመሪያ ስለሱ የገመተው ያልተሳሳተ ሆኖ ታዬው። ስለዚህ መጀመሪያ ባላቸው እዚያ ያሉትን ሁሉ በሻህን ጭምር እንዳላዋቆች በድሜ ባይሆን በአእምሮ እንደ ህጻናት ስለ ዘመኑ ትምርትና ስለ ተማሮች እዬተከራከሩም እያተቱም ሲለፈልፉና ሲንጫጩ ጫጫታው እያጫወተው እያተቱም ሲለፈልፉና አንገቱን ደፍቶ ራስን እዬወዘወዘ አንዳንድ ጊዜም ከንፈሮቹን እያሞጠሞጠ ከመስማት በቀር አንድ ጊዜ እንኳዋ አፉን አልከፈተም። በሁዋላ ግን በሻህ በቀጥታ ባይሆን በትርጉም የትምህርቱን አመራርና ለትምርቱ አመራርና ለትምርቱ አመራር አላፊ የሆኑትን ባለስልጣኖች እዬነቀፈ ከሞቅታ ጋር መናገር ሲጀምር የተናገረው ቃል እያንዳንዱ እዬሄደ በላቸውን ከተኛበት እንደ ቀሰቀሰው ሁሉ ወንበሩን ወደ ሁዋላ ተደግፎ ከተንጋለለበት ፊት ራሱን ከዚያ ወገቡን ቀስ አድርጎ አቃናና ቀጥ ብሎ ተቀምጦ ይሰማ ጀመር።

«ይቅርታ የኔ ወንድም» አለ በላቸው፥ በሻህ የተናገረው እንቆቅልሽ አለመሆኑን ለማስረዳት ተናግሮ ከጨረሰ በሁዋላ። በላቸው ከገባ ጀምሮ፥ ያን ያክል ጊዜ አልብሰው እንዳስቀመጡት ምስል አንድ ቃል ሳይተነፍስ ሳይላወስ ቆይቶ ድንገት ሲናገር እዚያ፥ እንግዳ ነገር እንደ ሆነ ሁሉ ሁሉም፥ ባንድነት አይናቸውን ወደሱ መልሰው አፈጠጡ።

«ይቅርታህን የኔ ወንድም! ስምህን አልያዝሁትም። የኔ ስም በላቸው ይፍሩ ይባላል፤ ስራየ በትምርት ሚኒስቴር ውስጥ ነው።»

«በሻህ ዘለሌ እባላለሁ ስራየ - ስራ የለኝም» አለ በሻህ፥ ለስራው ስም ሲፈልግ ትንሽ ቆይቶ ካጣ በሁዋላ።

«ያ ውቤ እዚህ ቢኖር ስራህ ምን መሆኑን ይነግርልህ ነበር» አሉ አዛዥ አቋዋርጠው እዬሳቁ።

«አባባ! » አለች ደመቀች ግንባርዋን ኮስተር አድርጋ። አዛዥ አዙረው ሳያዩ፥ ስለ በሻህ ስራ የጀመሩትን በንግዶች ፊት ቀጥለው እንዳያሳፍሩት ማስጠንቀቅዋ ነው።

«አዝማሪው ውቤ እዚህ ቢኖርማ ‹ወሮበላ ነው› ብሎ ያስተዋውቁኝ ነበር። ታዲያ እኔም ለሰው ጀሮ እንዳይከብድ ‹ስራ የለኝም› ያልሁት ከዚያ የተለዬ አይደለምኮ! መቸም ስራ የሌለው ሰው ‹ወሮበላ› ነው የሚባል አለ በሻህ እንደ መሳቅ ብሎ።

«አየ - እሱ እንኩዋ እንጂ! አሁን ስለ ዘመኑ ትምርትና ስለ ተማሮች የተናገርኸው እኔና ከኔ በላይ ለትምርቱ አላማም ወዳላማው ለሚደርስበት ጠቅላላ አመራርም አላፊ የሆኑት ባለስልጣኖች እንስማማበት እንጂ በወሮበሎች ደረጃ የሚነገር ተራ አነጋገር አደለምኮ! ብቻ እነሱ እንተወው፤ የስራህ ነገር እኔን አያገባኝም። እኔን የሚያገባኝ ስለ ዘመኑ ትምርትና ስለ ተማሮች የተናገርኸው ነው። አሁን ስትናገር የዘመኑ ትምርት እንደሚጎዳ? የዘመኑን ትምርት የተማሩት ሁሉ እንደማይጠቅሙ ትምርቱንም ተማሮችንም ዋጋ እንደሌላቸው አድርገህ ለማሳዬት ስትሞክር ስለ ተመለከትሁ በዚህ ላይ ያለህን አሳብ አጥርቶ ማወቁ ለስራየ እንደሚጠቅመኝ ስላመንሁ ነው....... አሁን ጣልቃ የገባሁ» አለ በላቸው።

«ስለ ትምርቱና ስለ ተማሮች አሳቤን ቅድም ተናገርሁኮ! ቅድም ያልተናገርሁት አሁን ካንተ አፍ ስስማ ያስታወስሁት ‹የትምርት አላማና ወደ አላማው የሚደረስበት ጠቅላላ አመራር› ያልኸው ነው። ለመሆኑ እንዲህ ያለ የትምርት አላማና ወደዚያ አላማ በቀጥታ የሚያደርስ ጠቅላላ መምሪያ አላችሁ? እንዲያ ያለ አላማ ካለስ ምን አይነት ትውልድ ምን አይነት ኢትዮጵያውያን አስተምራችሁ ማውጣት ነው አላማችሁ? ታሪኩን ስልጣኔውንና ሌላውን በተፈጥሮ ይሁን በጸጋ የኢትዮጵያ የሆነውን ሁሉ ወይም ባጭሩ ስር መሰረቱ ማንነቱን ተምሮ አውቆ በባህል በወግና፥ በኑሮ ስራት

የባእድ ቅኝ የባእድ ጥገኛ ከመሆን ይልቅ የራሱን ተምሮ መርምሮ የሚሻሻለውን እያሻሻለ እያደሰ እያሳመረ የዚያ ባለቤትን በመሆን የሚኮራ የሚመካ፥ ራሱ ተከብሮ አገሩን የሚያስከብር ትውልድ አስተምሮ ማውጣት ነው አላማችሁ? ወይስ እንዲሁ ትምርት ቤት ከፍቶ ልጆችን ሰብስቦ «ሂዱ እዚያ፥ የምታገኙትን ሁሉ ተማሩና የተማራችሁንት የሚያደርጋሁን ሁሉ ሁኑ ማለት ነው? በውነት እንነጋገር ካልነ አሁን፥ ሲሆን የምናየው መጨረሻ ያልሁት ነው» ታዲያ ይህ አላማ ይባላል? አላማ አይባልምኮ! ስለዚህ አላማ የላችሁም! ቅድም ባልሁት ላይ የምጨምረው ይህ ነው አቶ በላቸው» አለ በሻህ የተቆጣ ይመስል አይኖቹን በበላቸው ላይ ፍጦ።

በላቸው አይኖቹን ቦዘዝ አድርጎ ሽቅብ ጣራ ጣራውን እየተመለከተ ሲሰማ ቆይቶ «መንቀፍ አያስቸግርም መንቀፍ ቀላል ነው» አለ።

«ይልቁንም» አለ ቀጠለና። «ይልቁንም በሁለት ተቃራኒ ክፍሎች መሀከል አንዱ ሌላውን ለመንቀፍና ለመወንጀል ሁለቱም ለየራሳቸው የሚያጠግብ ምክንያት አያጡም። ዛሬ ባገራችን ሁለት ተቃራኒ ክፍሎች አሉ አቶ በሻህ። እነሱም አሮጌው የሚወጣው የኑሮ ስራትና አዲሱ አሮጌውን አስወጥቶ የሚገባበት የኑሮ ስራት ናቸው። ታዲያ አሮጌው መውጣቱ አዲሱ መግባቱ ላይቀር መነቃቀፋቸው መወነጃጀላቸው መታገላቸው መጋደላቸው አይቀርም። ብቻ ምንም ቢሆን ዞሮ ዞሮ አሮጌው ድል መሆኑ አዲሱ አሮጌውን ድል አድርጎ ቦታውን መያዙ ስለማይቀር በዚያ ጊዜ አሮጌው አልፎ ሞቶ አዲሱ ሲተካ የለት ጥቅማቸና የወደፊት ተስፋችው ካሮጌው የሚነቅፉና የሚረግሙ የሚያለቅሱ መሆናቸው የማይቀር ነው። ይህ ሆኖ ነው እንጂ አቶ በሻህ አዲሱ ትምህርት ወይም ‹ስራት› ልበለው አዲስ እንደ መሆኑ አንዳንድ ጥቃቅን ስህተት ሊንኖርበት ቢችልም አንተ እንዳልኸው ይህን ያክል ጥቃቅን ሆኖ የኢትዮጵያን ልጆች ከንቱ የሚያደርግ አደለም። ‹አላማ የላችሁም› ያልኸውም ይቅርታ አድርግልኝና እውነት አደለም። አላማ አለን ጥሩ አላማ! አላማችን የኢትዮጵያን ልጆች ዘመናዊ ትምርትን አስተምረን ኢትዮጵያን ዘመናዊት አገር ማድረግ ነው።

«ዘመናዊ ትምርት በኢትዮጵያ የተጀመረ ከኔና፥ ምናልባትም ካንተ እድሜ ትንሽ ቀደም ቢል ነው። በጣም አጭር ጊዜ ነው። ነገር ግን በዚህ አጭር ጊዜ የሰጠውን ጥቅም የሰጠውን አገልግሎት ለመረዳት ዛሬ፥ ባገራችን በያይነቱ የሚሰራውን ዘመናዊ ስራና እንዲያ ያለውን ዘመናዊ ስራ ማለት፥ ያስተዳዳሪነቱን ያስተማሪነቱን፥ የሀኪምነቱን፥ የመሀንዲስነቱን፥ እኒህን የመሳሰሉትን ሁሉ የሚሰሩትን የኢትዮጵያውያን ቁጥር ማየት ብቻ ይበቃል። ስለዚህ አቶ በሻህ ምንም እንኩዋ መንቀፍ ቀላል ስለሆነ የትምህርት

አመራራችነን መንቀፍ ለሚፈልግ አንዳንድ ጥቃቅን ጉድለት ባይታጣ እንዲያ ያለው ጉድለ አንተ እንዳልኸው ይህን ያክል መሰረት የሚገድ ሊሆን አይችልም፤ ኢትዮጵያውያንም የፈረንንጅ ትምርት ስለ ተማሩ ኢትዮጵያውያንነታቸው አይቀርም፣ ብቻ እስቲ ፍቀድልኝና አንድ ነገር ልጠይቅህ አቶ በሻህ። የትምርት አመራራችንነ እንዲህ ገብያ ወጥቶ ዋጋ እንዳያወጣ አድርገህ ስትነቅፍ መለወጫው ምን ይሁን ትላለህ? እንዲሁ የጠቃላላ ነቀፋህ መስመር የምንከተል ብንሆን ወዴት እንደሚያመራን የት እንደሚያደርሰን አይተኸው ይሆን? ያዬኸውኮ አይመስለኝም! አልተሳሳትሁ እድነሆነ አንተ ያልኸው ‹የኢትዮጵያ ልጆች የፈረንጅ ትምርት ስለ ተማሩ ከኢትዮጵያውያንም ከፈረንጆችም፥ ሳይሆኑ በመሀል ቤት ከንቱ ሆነው ቀሩ› ነው። መቸም በዚህ አሳብ እንደማልስማማ ከነምክንያቱ አሁን ገልጨልሀለሁ። ነገር ግን እስቲ ለክርክር ያክል፥ ያንተን አሳብ የተቀበልሁ ልምሰልና ‹ያልኸው ሁሉ እውነት ነው› ልበል! ታዲያ  ምን ይሻላል? መለዋወጫው ምን ይሁን? ያለ ጥርጥር ይህ የፈረንጅ ትምርት የኢትዮጵያ ልጆች ወገኖቻቸውንና የነሱ የሆነውን ሁሉ እንዲሰጡ እንዲንቁ እንዲጸዬፉ የሚያደርግ ከሆነ የኢትዮጵያ፥ ልጆች ከስራቸው ተእንቅለው ከላያቸው፥ የሚጨብጡት አጥተው፥ እንዲሁ ከመሀል ቤት እውር ድንበቱን የሚዋልሉ እንዲሆኑ የሚያደርጋቸው ከሆነ እንዲህ ያለውን የሰይጣን ትምርት ባንድ ላይ ጥቅልል አድርጎ ሰብስቦ አስሮ ጠፍሮ ወዲያ ወደ፥ መጣበት መጣልና እንደ ጥንታችን ብዙ ሽህ አመት እንደ ኖርነው መኖር ነው። እንዲህ አንተ ያልኸውን ብንከተል መለወጫው ይህ ነው! አቶ በሻህ አይደለም? »

«አይደለም» አለ በሻህ በለዘብታ።

«ታዲያ ምንድን ነው? »

«መለወጫው፥ የኢትዮጵያ ልጆች ኢትዮጵያውያንነታቸውን ሳይለቁ፥ ኢትዮጵያውያን እንደሆኑ የፈረንጅ ጥበብ እንዲማሩ ማድረግ ነው።

«የፈረንጅ ትምርትማ፥ የፈረንጅ ጥበብማ፥ ‹ወገኖቻቸው ገና የነሱ የሆነውን ሁሉ የሚያስጠላ የሚያስንቅ የሚያስጸይፍ ነው አልህኮ! »

«አስቀድሞ ራሳቸውን ደህና አድርገው እንዲያውቁ አለመደረጉ ነው እንጂ፥ ራሳቸውን አውቀው በዚያ ላይ የፈረንጅ ጥበብ እንዲማሩ መደረጉ፥ የራሳቸው የሆነውን ሁሉ እንዲጠሉ፥ እንዲንቁ እንዲጸየፉ አደረጋቸው አላልሁም።

«እንግዲያስ ያልኸው ሁሉ አልገባኝም ማለት ነው፥ እንቆቅልሽ - ሆነብኝ መሰለኝ! » አለ በላቸው፥ ትንሽ እንደ መሳቅ ብሎ።

«ካገላልጽ ጉድለት እንቆቅልሽ አስመስዬው ይሆናል እንጂ ነገሩስ እንቆቅልሽ አደለም፥ ግልጽ ነው» አለና አንገቱን ደፍቶ ትንሽ ሲያስብ ቆይቶ «ምናልባት» አለ በሻህ፥ ቀና ብሎ በላቸውን እያዬ። «ምናልባት፥ የኢትዮጵያን ልጆች የፈረንጅ ትምርት የራሳቸው የሆነው ሁሉ እንዲንቁ አደረጋቸው እያልሁ እዬነቀፍሁ ወዲያው ደግሞ፥ የፈረንጅ ጥበብ መማራቸው አስፈላጊ ነው ማለቴ ትምርትን ከጥበብ ለይቼ፥ አንዱን ስነቅፍ ሌላውን መደገፌ ይሆናል፥ የተናገርሁትን እንቆቅልሽ ያስመሰለው። በኔ አስተያየት ትምርትና ጥበብ የተለያዩ ናቸው፥ አቶ በላቸው። ትምርት ሰፊ ነው በሱ መጠን ጥበብ ጠባብ ነው። ትምርት ለስው ሁለተኛ ፈጣሪው፤ ጥበብ መሳሪያው ናቸው። ይህን ልዩነት ያዝልኝ፣ አቶ በላቸው! ሰው በትምርት ያደረጉትን ሁሉ ይሆናል። በጥበብ መሳሪያነት እሱነቱን ሳይተው ኑሮውን፥ ህይወቱን፥ ያሻሽላል፤ ያሳምራል! ስለዚህ የዛሬው ትውልድ ትምርት ቤት ተከፍቶለት እዚያ ያገኘውን እንዲማርና የተማረውን ያደረገውን ሁሉ እንዲሆን ስለ ተፈረደበት፥ የተማረው ያደረገው ሆነ አቶ በላቸው! የተማረው ምንድን ነው? የፈረንጅ የሆነው ሁሉ የሚያስመኝ! ዛሬ የፈረንጅ ትምርት ቤት በተማርውም ሆነ ከተማርው በቀላወጠው ጥራዝ ነጠቅ መሀከል፥ ኢትዮጵያዊ ላለመምስልና ፈረንጅ ለመምሰል ልብ እስኪወልቅ፥ ትንፋሽ እስኪርቅ ያለውን ሩቻ ያለውን ቅድድም እናውቃለን። መቸም በምግብ በልብስ፥ በኑሮ፥ በባህል፥ በወግ፥ በስራት በምነት በስሜት፥ በመልክ፥ እንኩዋ ሳይቀር፥ ኢትዮጵያዊ ላለመምሰልና ፈረንጅ ለመምሰል ሁሉም ከፈረንጅ የበለጠ የሚጨነቅ የሚጣጣር መሆኑ የማይካድ ነው። መቸም እንደ ፈረንጅ በመኖር ፈረንጅ ለመምሰል ያለው ጽኑ ጉጉት የፈረንጅ ትምርት የተማረውንና ከሱ የቀላወጠውን ጥራዝ ነጠቁን ሁሉ የሚያደርገውን እንዳሳጥው፥ እንዳስከረው የታወቀ ነው። ዛሬ ባገራችን በጠቅላላው የመምሰል በተለይ፥ ፈረንጅ የመምሰል ጽኑ ጉጉት፥ ማህበራዊ ስካር ብሄራዊ ስካር፥ ፈጥሮ የሁሉንም ያስተሳሰብና ያስተያየት ሚዛን፥ አቃውሶት ሁሉም፥ የፊቱ ሁዋላ የሁዋላው ፊት የታቹ ላይ የላዩ ታች እዬሆነ ተወነጋግሮ ተጠነጋግሮ ስለሚታዬው፥ ከስራ በፊት ሀብትን ከሀብት በፊት ምቾችን ለማግኘት የሚቀዳደም በመሆኑ ሁሉም መነሻ ሳይኖርው ወደ መድረሻው ወደ መጨረሻው ለመድረስ ያላቅሙ የሚንጠራራ በመሆኑ ሁሉም እንደ ፈረንጅ በመኖር ፈረንጅ ለመምሰል፥ እረፍትን ትቶ ይሉኝታን ረስቶ፥ ነውርን ንቆ ክብርን ደቅድቆ እያደርጉት የሚያደርግ በመሆኑ በጠቅላላው፥ ትውልዱ የሀብትና የመንፈስ ቅርስ የሌለው የሀብትና የመንፈስ ድሀ በሀብትና በመንፈስ

ከስሮ፥ ለተከታዩ ትውልድ ባለዳ የሆነ ትውልድ መሆኑ የታወቀ ነው። ይህ ሁሉ እንዲህ እንዲሆን አያደረገም የፈረንጅ፥ ትምርት መሆኑ አይጠረጠርም። ስለዚህ አቶ በላቸው በምን ምክንያት? ብለህ ትጠይቀኝ እንደሆነ እንጂ፥ የፈረንጅ ትምርት የተማረውና እሱን የሚከተለው ጥራዝ ነጠቁ ትውልድ በጠቅላላው ፈረንጅ ለመምሰል ባለው ጉጉት አሁን እንዳልሁት ለመሆኑ ማስረጃ የምትጠይቀኝ አይመስለኝም።»

«እንዲያው ተገኔ ይሙት ልክ፥ ነው! » አሉ ወይዘሮ ላቀች፥ በሻህ ሲናገር አፋቸውንም አይኖቻቸውንም፥ ሰፋ አድርገው ከፍተው ሲሰሙ ቆይተው። «አሁን ያለው ሁሉ እክዚህ በቀር ያማይባል አንድ የሚወድቅለት የሌለው ሁሉም ልክ ነው! ዛሬ እንኩዋንስ ያን የፈረንጁን የተማረው ወጣቱና ያልተማረው ሽማግሌውም ‹ፈረንጅ ያደርገዋል› ካሉት ያማያደርገው የለም። ማናቸውንም ነገር ለማድረግ ‹ያምር ሆይን? ይከፋ፥ ይጠቅም፥ ይሆን? ይጎዳ› ብሎ መጠዬቅ ቀርቶዋል። ‹ያጸድቅ ይሆን? ያስኮንን ተብሎ እንኩዋ አይጠዬቅም። ጥያቄው ‹ፈረንጆች ያደርጉታል ወይ? ነው። ፈረንጆች ካደረጉት ማድረግና ከነሱ ጋር እዚያው እነሱ ወደሚሄዱበት ወደ ገሀነም እሳቱ መሄድ ነው› ሲሉ ሁሉም ባንድ ላይ ሳቁ። ‹እውነቴኮ ነው› አሉ ወይዘሮ ላቀች፥ ቀጠሉና። ‹እውነቴን ነው። እስቲ እግዚአብሄር ያሳያችሁ! ጾም ቀረ ባል፥ ማክበር ቀረ። ለምን? ፈረንጅ ለመምሰል! በጥልፍ መሶብ ከመብላት እንደ ድመት በገል መብላት ተመረጠ። ፈጣሪ አሳምሮ የሰራው እጅ እያለ በመንካና በሹኬ፥ መብላት ተመረጠ። ሹኬ ድሮ የጠጉር መንቀሻችን መንካ የወጥ ማማሰያችን ነበሩ። ኧረ ስንቱን? ስንቱን! ከሸማ ከቀጭን ኩታና ከካባ እንደ እረኛ ጥብቆ መልበስ ተመረጠ። ታዲያ ይህ ሁሉ የሚያምር የሚያስከብር ሆኖ ነው? አደለም፥ «ፈረንጅ ያደረገው አይቅርብን» ተብሎ ነው! አሁን የቀረው ቆዳን ገልብጦ ወይም ልጦ ያው ባንድ ፊቱ እሱን - ያን ፈረንጁን መሆኑ ነው። ያውም የማይቻል ቢሆን ነው እንጂ፥ የሚቻል ቢሆን ኖሮማ - እስከ ዛሬ ድረስ ሁሉም ተልጦ ተልጦ ሁሉም እንደ ሽንኩርት ተገሽልጦ የውስጥ ገላው በላይ ሆኖ አልቆ ነበር! ውይ አበስኩ ገበርኩ! » ሲሉ ወይዘሮ ላቀች የተላጠው፥ የተገሸለጠው ሁሉ ሊያስፈራቸው ተሰልፎ እንደ መጣባቸው ሁሉ አይኖቻቸውን በሁለት እጆቻቸው ሸፍነው እዚያ ያሉት ሁሉ በሳቅ አወኩ።

«በውነቱ» አለ በላቸው ወይዘሮ፥ ላቀች ከተናገሩት ከሌሎች ጋር ሲስቅ ቆይቶ። «በውነቱ አቶ በሻህ፥ የዛሬው ትውልድ ወይም በጠቅላላው የዛሬው መህበር፥ ፈረንጅ ለመምሰል ካቅሙ ጋር የማይመዛዘን ኑሮ መኖር ስለሚፈልግ የሀብትና፥ የመንፈስ ድህ

የሚያደርገውን መንገድ ተከትሎዋል፤ ያልኸውን ምንም እንኩዋ አንተ ያልኸውን ያክል ባይሆን ጨርሶ ‹የማያሳስብ ነው› አልልም። ነገር ግን፥ ትውልዳችን ማህበራችን፥ ያላቅሙ መኖር በመፈለጉ የሀብትና የመንፈስ ድሀ እንዳሆይን የሚያሰጋው፥ ‹የፈረንጅ ትምርት ስለ ተማረ ነው› ያልኸው ጭራሽ የተሳሳተ ከመሆኑም ሌላ አደገኛ ነው። ወዲያውምኮ አቶ በሻህ የመልካምን አራያ መከተል መልካም አራያን መምሰል መልካም ነው። ዛሬ የፈረንጆችን አራያ የማይከተል ማነው? »

«ራሳችነን አስንቆ እኛነታችነን፥ አስትቶ ከንቱ፥ እነሱን ላንሆን እነሱን ለመምሰል እንድንባክን የሚያደርገንን ትምርት ነቀፍሁ እንጂ ጥበባቸውን መማር እንደሚያስፈልገንማ መላልሽ ተናገሪያለሁኮ አቶ በላቸው! የነቀፍሁት የጠላሁት፥ እነሱን ላንሆን እነሱን ለመምሰል የሀብትና የመንፈስ ባካናዎች ያደረገንን ትምርት ነው፡ «መሆን በድል፥ መምሰል በትግል ያውም በከፊል?› የሚባለውን ተረት ሳትሰማው እንዳልቀረህ አምናለሁ፥ አቶ በላቸው። መምሰል በጣም አድክሞ በጣም አስክሮ ለመምሰል የሚፈልገውን በሙሉ ለመምሰል ምንም ቢሆን የማይቻል ነው። ጥበብ ግን አንድ ጊዜ ባንድ አገር ይፈጠር እንጂ፥ በዘር በባህል፥ በወግ፥ በስራት በምነት በስሜት፥ የማንም ያልሆነ የሁሉ የሆነ በመሆኑ፥ ‹ጥበባቸውን አንቅዳ› አላልሁም። ፈረንጆች ራሳቸው፥ እያንዳንዳቸው የሚፈጥሩትን አዳዲስ ጥበብ እስበሳቸው እንደሚቀዳዱ የታወቀ ነው። ብቻ ሁሉም የየራሳቸውን የተፈጥሮና የጸጋ መለያ እንደያዙ ሁሉም የዬራሳቸውን እነሱነት ሳይለቁ ነው! » አለ በሻህ።

«እስቲ ሌላ ነገር ልጠይቅህ አቶ በሻህ፥ ቅድም ‹የዛሬውን ትውልድ፥ ወይም ማህበር የመንፈስና የሀብት ድሀ ያደረገው የፈረንጅ ትምርት ነው ያልሁበትን ምክንያት ብትጠይቀኝ እነግርሀለሁ› ያልህ መሰለኝ፣ እንዲያው ያለውን ምክንያት ልትገልጽልኝ..... ትፈቅዳለህ? » አለ በላቸው።

«ደስ እያለኝ! » አለና በሻህ፥ አይኖቹን ሳያረግብ ፊት ለፊት ቦዘዝ አድርጎ አገጩን በግራ ጣቶቹ ሲያሻሽ ትንሽ ቆይቶ «መቸም እንደምታውቀው አቶ በላቸው ልጅ ሲባል በጠቅላላው ልጅ ሁሉ ያስተማሩትን እዬተማረ ተምሮ ያወቀው እዬተከተለ የሚያድግ ነው። ያላተማሩትን የሚማር፥ ተምሮ ያላወቀውን የሚከተል ልጅ የለም። በዚህ ረገድ የኛ ልጆችም እንደ ልጆች ሁሉ ናቸው። ማለት ያስተማሩዋቸውን እንጂ፥ ያላተማሩዋቸውን እንዲህ አውቀው ሊከተሉ አይችሉም።

«ኢትዮጵያ ገናና ታሪክ፥ አስደናቂ ጥንታዊ ስልጣኔ ህብረተሰብዋ በዬድሜው ደረጃና በዬስራ መስመሩ ሁሉም መብቱን እያስረከበና ተግባሩን እዬፈጸመ ህይወቱን የሚመራባቸው ድንቅ የሆኑ ህግጋት ወጋትና ስራታት የነበሩዋት አገር ናት።

«ኢትዮጵያውያን እንደ ህጻናት ሲጫወቱ እንደ ጐማሶች ሲጋቡና ትዳር ሲመሰርቱ እንደ ወላጆች አሰርገው ሲድሩ በስራ፥ ቀናት ስራቸውን ሲሰሩ፥ በበአል ቀናት በአላታቸውን ሲያከብሩ ሙታናቸውን አዝነው ሲቀብሩ እንደ ሽማግሎች፥ እንድበር ተቀምጠው ለወጣቶች ወራሾቻቸውን ታሪክ ሲነግሩ የተጣሉትን ተቀምጠው ለወጣቶች ወራሶቻቸው ታሪክ ሲነግሩ የተጣሉትን ገስጠው ሲያስታርቁና ለተበደሉት ፈርደው ሲያስክሉ የሚከተሉዋቸውና የሚመሩባቸ የኢትዮጵያ ብቻ የሆኑ ህግጋት ወጋትና ስራታት የነበሩዋት አገር ናት። ጉዛሞች - እንደ ወራቱ - አርሰው ዘርተውና አዝምረው ምርት ሲያፍሱ፥ ጀግኖች አገራቸውን ከወራሪ ጠላት ለማዳን ዘምተው በጦር ሜዳ ደማቸውን በልግስና ሲያፈሱ ሌሎች ጠላታቸውን ድል እዬመቱ ወደ መጣበት አባረው ሲመለሱ እነኒህን ሁሉ፥ እንዲህ ያሉትን መልካምና ትልልቅ ነገሮች ሁሉ ለማስታወስ ወይም ልብ የሚፈጥሩት ውስጣዊ የጋራ ስሜት የሚገለጽባቸው የኢትዮጵያ ብቻ የሆኑ የስሜት መግለጫዎች የነበሩዋት አገር ናት።

«ለሰርግና ላመትባል ዘፈኑ፥ በጦር ሜዳ ለሚሰራ አስደናቂ ጀብድ ቀረርቶው፥ ፍከራው፥ ሰንጎመገኑ በማህበር ወይም በሌላ፥ ድግስ ተሰብስቦ እዬተበላና እዬተጠጣ ለመዝናናት እሽረረው፥ የግጥም ውድድሩ፥ ተረቱና ስለምኑ፥ ለሀዘን ወዬታውና እንጉርጉሮዉ እኒህ ሁሉ ማንም የማይጋራት የስዋ ብቻ ሀብት ነበሩ። እኒህ የጋራ ስሜት መግለጫዎች ከመሳሪያዎቻቸው ጋር የኢትዮጵያ ብቻ የሆኑ የኢትዮጵያ ውበትና የኢትዮጵያውያን ትልቅነት ደግነት፥ ለጋስነት፥ ርህሩህነት፥ ጭዋነት፥ ቆራጥነት፥ ጀግንነት፥ የሚገለጽባቸው ነበሩ። ይህ ሁሉ ባንድነት ይህ በጋራ የስሜት መግለጫዎች የሚገልጸው የጋራ ህይወት ከመገለጫዎቹ ጋር ነበር፥ ኢትዮጵያውያንን በውስጡ ተካፋዮች ሆነው ሲኖሩት የሚያስደስታቸውና ርቀው ሲሄዱ ትዝታው እስኪመለሱ የሚያስቸኩላቸው የትም ቢሆን ካገራቸው ጋር አቆራኝቶ የሚያኖራቸው! ይህ ሁሉ ባንድነት ነበር ኢትዮጵያውያንን በመልካቸው ብቻ ሳይሆን ሳስባቸው በምነታቸው በስሜታቸው፥ በጠባያቸው፥ ባስተሳሰባቸው፥ ባሰራራቸው ከሌሎች ሁሉ ለይቶ ኢትዮጵያውያን አሰኝቶ ያኖራቸው።

«በኢትዮጵያ መሬት፥ ከኢትዮጵያ ወላጆች መወለድ ብቻ ኢትዮጵያውያንን ሙሉ በሙሉ ኢትዮጵያውያን አያደርጋቸውም። ሙሉ በሙሉ ኢትዮጵያውያንን

የሚያደርጋቸው በኢትዮጵያ፥ መሬት ከኢትዮጵያ ወላጆች ከመወለድ ጋር ከጥንት ጀምሮ ትውልድ እያለፈ ትውልድ ሲተካ ከቀደመው ወደሚከተለው እዬተወራረሰ ሲወርድ ለመጣው ለዚያ አሁን ለቆጠርሁት ሁሉ፥ የኢትዮጵያ ባህላዊ ሀብት ባህላዊ ጸጋ ወራሾች ሆኖ መገኘት ነው!

«ከጥንት ጀምሮ፥ ትውልድ እያለፈ ትውልድ ሲተካ፣ እዬተከታተሉ የመጡት ኢትዮጵያውያን ሁሉ ጉርሱን፥ ልብሱንና ሌላውን ስጋዊ ፍላጎታቸውን አሙዋልቶ የሚያኖራቸውን የኢትዮጵያን መሬትና ባስተሳሰብ ባሰራር በምነት በስሜት ውስጣዊ የመንፈስ ፍላጎታቸውን አሙዋልቶ አርክቶ፥ የሚያኖራቸውን የኢትዮጵያን ባህል እጅግ ይወዱዋቸው ያከብሩዋቸው ይኮሩባችወ ይቀኑላቸው ነበር። ለነሀ ስጋዊና መንፈሳዊ ሀብቶች ለነሀ የተፈጥሮና የሰጋ ብሄራዊ ሀብቶች፥ ጀግኖች በዬጦር ሜዳዉ፥ የጀብድ ታምር እዬተሰሩ ህይወታቸውን ሲሰዉ የጀግኖች ምሽቶች ባገር ቤት በቤት እናትነታቸው ላይ የቤት አባትነቱን ተግባር ደርበው፥ ለቤተሰብ ክብርና ለልጆቹ ደህንነት የሚገጥማቸው ልዩ ልዩ ጨካኝ አደጋ ጋር የሚያደርጉት ተጋድሎና የሚሰሩት የጀግንነት ስራ ‹እጹብ ድንቅ› እዬተባለ አእሩግ እዬተቀባበሉ ሲተርኩት፣ አዝማሪዎች እንደ ሁኔታው - ሲገጥሙበት እረኞች ሜዳ ለሜዳ ሲዘፍኑበት አልቃሾች ‹ወዬ› ሲሉበት የሚኖሩ ግሩም ነው!

«ታዲያስ! ልጆቻችን ይህን ሁሉ ያገራቸውን ገናና ታሪክ፥ አስደናቂ ጥንታዊ ስልጣኔዋን ህግ ወግዋንና የኑሮ ስራትዋን በልዩ ልዩ መልኩ ከባህላዊ የምነትና የስሜት መግለጫዎችዋ ጋር እያዛመዱ አሰናድቶ በትምርት ቤት እዬተማሩት ቢያድጉና ቢያውቁት ኖሮ እንድኩዋንስ ሊጠሉት የሚጣላባቸውን አይጠሉም? እንኩዋንስ ለጸዬፉት የሚጸዬፋቸውን አይጸዬፉም? እንኩዋንስ ሊንቁት የሚንቅባቸውን አይፋለሙትም ኖሮዋል? አቶ በላቸው! ይህን ሁሉ ስጋዊና መንፈሳዊ የተፈጥሮና የጸጋ ብሄራዊ ሀብታቸውን እንዲያውቁት ብናደርግ ኖሮ፥ ላስተሳሰባቸው ላሰራራቸው ላኖኑዋራቸው ለምነታቸውና ለስሜታቸው መሪ ሆኖ ይከተሉት ነበር! ነገር ግን አስተምረን እንዲያውቁት ስላላደረግን አልተከተሉትም። በዚያ ፈንታ ምን አደረግን? የዚያን ሁሉ ብሄራዊ ሀብት ጌቶች የዚያን ሁሉ የተፈጥሮና የጸጋ ሀብት ወራሾች ያ ሁሉ እንደማይገባቸው ከደን ከዚያ ሁሉ ውጹአን አድርገን ያን ሁሉ ሸሽገን ነፍገን ትምርት ቤት ከፈትንና ምንም እንደሌላቸው ባዶ እጃቸውን እዚያ ሄደው ከባእዳን የባህል የወግ የኑሮ ስራት ፍርፋሪ እንዲቀላውጡ አደረግን! ይህ ሁሉ ለጠየቅሽኝ ቀጥተኛ መልስ አለመሆኑን አውቃለሁ፤ ወደ መልሱ መግቢያ እንዲሆነን ነው። ጥያቄው ‹የፈረንጅ

ትምርት የዛሬውን ትውልድ ወይም ማህበር የኢትዮጵያ ከሆነው ሁሉ እንዲርቅና የሀብትም የመንፈስም ድሀ እንዲሆን ያደረገው እንዴት ነው?› ነው አደለም? »

«ጥያቄው እንዲያ ነበር፤ የሰጠኸኝ መልሱም - ከጠዬቅሁህ ጥያቄ ጋር ያልተዛመደ መሆኑን አንተ አስቀድመህ ተናገርኸው፤ እንግዲህ እኔ ምን ልበል? ብቻ የተናገርኸው ሁሉ ተናገርሁህ መልስ ባይሆንም የጠላሁት አይምሰልህ፣ አቶ - በሻህ። ይልቁን፣ - ግጥማ ግጥም መሳይ ስላለበት፥ መስማቱ ደስ ይላል፤ ያጫውታል» አለ በላቸው ምንም እንኳዋ በሻህ የተናገረው ከባድ መሆኑ ቢሰማው ከቁም ነገር ያልቆጠረው ለመምሰል የፌዝ ሳቅ ለመሳቅ እየሞከረ።

«አትቀልድ፤ ግዴለህም አትቀልድ፥ አቶ በላቸው! » አለ በሻህ ቆጣ ብሎ። «የተናገርሁት ላገራቸው የሚቆረቆሩ ብዙ አዋቆች ተከራክረው የተስማሙበት ቁም ነገር ነው እንጂ አንተ እንዳልኸው፥ ለግጥማ - ግጥም ጭዋታ አደለም። ስለዚህ አንተን የሆነ አንተ የተሸከምኸውን ከባድ አላፊነት የተሸከእም እንዲህ ባለ አሳሳቢ ነገር ላይ ሲቀልድ አላፊነቱ አይከብደው ያላፊነነት ተግባር የማያውቅ መስሎ ስለሚገመት ባትቀልድ ይሻላል። ‹በተናገርሁት ተስማማ› አልልህም እንድታፌዝብኝ ግን አልፈቅድልህም! ገባህ? »

«ይቅርታህን! » አለ በላቸው የበሻህን መቆጣት፥ ሲያይ ደንግጦ። «ይቅርታህን፥ መልስህ ከጥያቄየ ጋር የተዛመደ ባይሆንም ቁም ነገርነቱን ሳይለቅ፥ ደስ ደስ እያለ የሚሰሙት ነው፥ ማለቴ፥ ነው - በጣም - ደስ ስላለኝ ነው። በውነት በጣም ቁም ነገር ያለው ነው። ከጥያቄየ ጋር - አንተ እንዳልኸው ባይዛመድም በጣም ደስ ነው ያለኝ። ግጥም ያልሁት - እንደ ግጥም ደስ ይላል ማለቴ ነው። ግጥም እወዳለሁ። ለዚህ ነው፥ ስለዚህ - ይቅርታ ህን አትቆጣ።

«በሻህ ይቆጣል መስሎህ አይዞህ አትስጋ» አሉ አዛዥ አቁዋርጠው። «በሻህ የተቆጣ እለት፥ ውሀ እንጨት ሆኖ የነደደ እለት - » በቃ፥ አለም ህግጋትዋን ለወጠች ማለት ነው! በሻህ የሚቆጣ ቢሆን፥ ውቤ ያን ያክል አህያ ቢጭኑዋት የማትችለው ከባድ ስድብ እዬፈለገ ሲያሸክመው በተቆጣ ነበር! ብቻ እሱና ቁጣ አይተዋወቁም ግዴለህም። መጀመርያ ውቤ የስድብ መአት ሲያወርድበት የሰማሁ እለት፥ ዳግመኛ የሚነጋግረው አልመሰለኝም ነበር። ታዲያ በነጋው ‹ውቤን እያችሁልኝ ወይ› እያለ ፈልጋ ሲመጣ ገረመኝ! ስለዚህ አቶ በላቸው በሻህ በጣም እንዲወድህ የፈለግህ

እንደሆነ እዚያ እናንተ ዘንድ እንደ ህጉ እንደ አኪምነቱና እንደ ሌላው ነገር ሁሉ የስድብ ሊቃውንቶች አሉዋችሁ እንደ ሆነከነሱ አስቀያሚ አስቀያሚውን ስድብ እዬመረጥህ እያመጣህ ብትለድፍበት አዬ ተዚያ ወዲያ፥ ካንተ በቀር ሌላ ወዳጅ ይኖረዋል ብለህ አታስብ! ‹በላቸው በየት ሄደ› እያለ በሄድህበት ሲከተልህ ይኖራል! » ሲሉ አዛዥ እዬሳቁ እዚያ ያሉት ሁሉ በሻህና በላቸው ጭምር ከልባቸው ሳቁና በሁለቱ ተከራካሪዎች መሀከል የተፈጠረው መሸካከር ወዲያው ለዘበ። ያዛዥ አላማም ይህ ነበር። ያዛዥ አላማም ይህ ነበር። ከዚያ በላቸው በሻህን እንደገና ይቅርታ ስለ ለመነው ንግግሩን ቀጠለ።

«አቶ በሻህ አንተ ራስህ እንዳልኸው የትምርታችነን አመሰራረትና አመራር እዬነቀፍህ በተናገርኸው ሁሉ አልስማማ ይሆናል። በርግጥ አልስማማም፤ ነገር ግን አልስማማበት እንጂ ስለ ትምርትና ስላሰጣጡ ባለህ ጠቅላላ ፍልስፍና ባቀራረብህ ጭምር በጣም ነው የተነካሁ። ስለዚህ ባነጋገሬም ሆነ በጠቅላላ ሁኔታየ የምቀልድ መስዬ ታይቸህ እንደሆነ ይቅርታ አድርግልኝ። በውነቱ የትምርት ጉዳይ ጉዳያቸው አድርገው እንዲህ ጠልቀው የሚመረምሩ፥ እንዲህ የሚቆረቆሩ ሰዎች ለትምርቱ ስራ አላፊዎች ሆነን ከተቀመጥነ ሰዎች ሌላ ‹ይኖራሉ› ብዬ አልጠራጠርም ነበር። ዛሬ ካንተ የሰማሁት ማለት፥ የትምርት አመሰራረታችነን የሚመረምሩና በጉድለቱ የሚቆረቆሩ ብዙ አዋቆች መኖራቸው ለኔ እንግዳ ነገር ነው፤ አዲስ ትምርት ነው። በል አሁን ፈቃድህ ቢሆን የጀመርኸውን ጨርስልን» አለ በላቸው በሻህ የተናገረውን ሁሉ አውቆ የተወው አይቶ የጣለው የማይረባ ነገር አስመስሎ ለማሳዬት ጭራሽ ያላሳሰበው መስሎ ለመታየት የለበሰውን የውሸት ልብስ አውልቆ ወዲያ ጥሎ የውነተኛ ስሜቱን በመናዘዝ። አንዳንድ ግጭት መልካም ነው። ይልቁንም በውሸት መሸፈኛ በግብዝ መሸፈኛ ተሸፍነው፥ ያልሆኑትን መስለው መታየት የሚፈልጉትን ድንገት የገጭዋቸው እንደሆነ የግጭቱ ሀይል ሲነቀንቃቸው ሲያናውጣቸው ያ ግብዝ መሸፈኛቸው ከላያቸው ይወድቅና ራቁታቸውን በውነተኛ መልካቸው ይታያሉ!

«አንዳንድ ጊዜ ከስሜት ጋር ስናገር የተቆጣሁ እመስል እንደሆነ እንጂ አባባ አዛዥ እንዳሉት መቆጣት አላውቅም። ብቻ ላንተ የተቆጣሁ መስዬ ታይቸህ እንደሆነ ይቅርታ አድርግልኝ» አለ በሻህም ምንም ቢቆጣ ያልተቆጣ ለመምሰል ፈገግ እንዳለ ራሱን ትንሽ ዝቅ አድርጎ። «እንግዲህ የጀመርሁትን ለመጨረስ» አለ ቀጠለና። «ቅድም የዛሬው ትውልድ ራሱን ማንነቱን ስላለማወቁ የተናገርሁት ሁሉ፥ ‹ለጥያቄህ መልስ ለመስጠት መግቢያ ነው እንጂ ቀጥታ መልስ አደለም› ስላልሁ እኔ የተናገርሁት

አንተ ከጠዬቅኸኝ ጋር የማይዛመድ መሆኑን እዬመላለስህ ስትናገር ሰማሁህ። ይቅርታ አድርግልኝና፥ የተናገርሁት ለጠዬቅኸኝ ቀጥታ መልስ አይሁን እንጂ በጣም የተዛመደ ነው፤ ባይዛመድ አልናገረውም ነበር። የተናገርሁት ሁሉ፥ የዛሬው ትውልድ የባልህ፥ የወግ የኑሮ ስራት፥ ጌታ መሆኑን አሳይቼ፥ የዚህ ሁሉ ጌታ የዚህ ሁሉ ወራሽ ይህን ህጋዊ ሀብቱን ይህን ብሄራዊ ጥሪቱን ስለነፈግነው ስለ ሸሸግነው ስለ ከለከልነው የባእድ ባህል የባእድ ህገ ወግ የባእድ የኑሮ ስራት ለመልቀም መገደዱንና ያም ያም እንዳስከተለ ለማሳዬት ነው። ስለዚህ የተናገርሁት ከጥያቄ ጋር ያልተዛመደ አደለም፤ በጣም የተዛመደ በጣም የተያያዘ ነው። አዬህ? አእምሮና ልብ ልክ እንደ ሆድ ጦም መኖር ስለማይችሉ አእምሮ የሚማረው የሚመራው የሚያውቀው የሚያሰላስለው የሚሳለው የሚመስለው ስለሚፈልግ ልብ የሚወደው የሚጠላው፥ የሚያከብረው የሚያንደንቀው የሚንቀው ስለሚፈልግ ልክ እንደ ሆድ አእምሮና ልብ እንዲህ እንዲህ ያለ ምግብ ስለሚፈልጉ የዛሬው ትውልድ አእምሮና ልብ የንሱን የራሳቸውን የሚሰጣቸው ቢያጡ ከባእድ የባህል የወግና የኑሮ ስራት ፍርፋሪ እንዲቀላውጡ የተገደዱ መሆናቸውን ለማሳዬት ነው የተናገርሁት አቶ በላቸው! አሁን ከዚህ ወደ ቀጥታ መልሴ ልራመድ። አሁን ‹የፈረንጁ ትምርት፥ የዛሬውን ትውልድ የኢትዮጵያ ከሆነው ሁሉ እንዲቀርና ፈረንጅ ለመምሰል ባለው ጽኑ ጉጉት የመንፈስም የሀብትም ድሀ እንዲሆን አደረገው› ወዳልሁበት ምክንያት ልለፍ። ፈረንጆች በውቀት ይሁን በስተት በየትኛው መሆኑን እግዜር ይወቀው - የሚጽፉት ሆነ የሚያስተምሩት ፈረንጅንና የፈረንጅ የሆነውን ሁሉ በተለይ አፍሪቃውያንና የአፍሪቃውያን የሆነውን እናንና የኛ የሆነው ጭምር አዋርዶ፥ አጎሳቁሎ የሚያሳይና የሚያስንቅ የሚያስጠላ የሚያስጸይፍ ነው። ታዲያ እንግዲህ ከህጻንነታቸው ጀምረው እንዲያ ያለውን ትምርት ብቻ በትምርት ቤት እዬተማሩ የሚያድጉ ልጆች እንዲያ ያለው ትምርት እውነት አለመሆኑ የሚያስረዳ ማረምያ፥ እዬሰጠን እሱን ብቻ እዬተማሩ፥ የተማሩትን አምነው በሱ እንዲመሩ እያደፋፈርን የምናሳድጋቸው ልጆች በግድ ያን የሚጠላውን የሚናቀውን ወይም፣ በጠቅላላው የራሳቸው የሆነውን ሁሉ የሚንቁና የሚጠሉ ያን የሚወደደውን የሚደነቀውን ወይም በጠቅላላው የፈረንጅ የሆነውን ሁሉ የሚወዱ የሚያደንቁና የሚመኙ መሆናቸው የማይቀር ነው። ብቻ እዚህ ላይ አንድ አይነተኛ ነገር አለ። ማንም ቢሆን የራሱ የሆነውን ራሱ ውስጥ ውስጡን ንቆ፥ ጠልቶ የሌሎች የሆነውን ያድርንቅ ይወደድ ይመኝ እንጂ ሌሎች ‹እንናቅህ› ሲሉት ሌሎች የሚያስከብርና የሚያኮራ መሰረት የሌለህ ነህ› ሲሉት ‹በዝቅተኛው የሰውነት ደረጃ ያሉትና የሚናቁት ክፍሎች ወገን ነህ› ሲሉት ይህን አምኖ የሚቀበል የለም። ስለዚህ ይህ የተባለው ሁሉ እውነት አለመሆኑን አስመስክሮ የሚረታበት እሱና ወገኖቹን የሚያስከብርና የሚያኮራ መሰረት ያላቸው

መሆናቸውን የሚያስረዳበት ሌላ መንገድ ካጣ እንዲያ ካለው ችግር መውጫው እምሽሽ ብቻ ነው። ተዋርደው ከሚያዋርዱት ተንቀው ከሚያስንቁት መሰረተ ቢሶች ሆነው መሰረተ ቢስ ከሚያደርጉት ወገኖቹ መሸሽ! በነሱ አይን እንዳይታይ እነሱን ለመምሰል ከነሱ መራቅ ከነሱ አለመነካካትና የዝቅተኛነት ስሜት እንዳደረባቸው ሰዎች ሁሉ የሚደነቅ የሚወደድ የሚያስመኝ ነገር ያላቸውን ከፍተኞችን እዬፈለገ እነሱን ለመምሰል መታገል፥ መጋደል፣ ነው! ሽሽት ከሚፈሩት ከሚጠሉት ከሚጠየፉት ሁሉ ለመራቅና ለመዳን አንድ አይነት መከላከያ ስለሆነ ሰው አንድ ጊዜ ከጠላ አንድ ጊዜ ከተጠዬፈ ሆነ ብሎ እንኩዋ ሳይሆን ሳያስበው ከሚጠላውና ከሚጠዬፈው ሁሉ እንዲሸሽ ደመ ነፍሱ ይገፋዋል። በዛሬው ትውልዳችን ከዚያ ተያይዞ በዛሬው ማህበራችን በሁላችን መሸሽ! ታሪካችነን በጠቃላላው ኢትዮጵያውያንነታችንን ወደ ሁዋላ ጥለን መሸሽ! ከዚህ ሁሉ ጋር የሚያገናኝ ድልድያችነን አፍርሰን ከዚህ ሁሉ ጋር የሚያያይዝ ማሰሪያችን ከኛነታችን ተለይተን መሸሽ! እንግዲህ መልሴን አጠቃልዬ ለመስጠት አቶ በላቸው የዛሬው ትውልድ ኢትዮጵያውያን ወገኖቹ ክብራቸውን ኩራታቸውን ጀግንነታቸውን ቆራጥነታቸውን ልግስናቸውን፥ ርህራሄያቸውን አድንቆታቸውን ንቀታቸውን ፍቅራቸውን ርህራሄያቸውን የመሳሰለውን፥ አሁን ቆጥሬ ልገፋው የማልችል ላፋዊ መልካቸው ሆነ ለውስጣዊ እምነታቸውና ስሜታቸው መግለጫ የሆነ አፋዊነቱ እይሚገልጹበት ባልህ ወግ የኑሮ ስራት ያላቸው መሆናቸውን ሳያው ራሱ የዚህ ሁሉ ወራሽና በዚህ ሁሉ የተረፈው ባለ ጸጋ መሆኑን ሳያውቅ ምንም እንደሌለው ባዶውን ትምርት ቤት ገብቶ የተማረው የፈረንጅ ትምርት የሱ የራሱ የሆነው ሁሉ የሚናቅ የሚጠላ የፈረንጅ የሆነው ሁሉ የሚወደድ የሚደነቅ የሚያስመኝ መሆኑን ስላሳመነው የዝቅተኛነት ስሜት ስላሳደረበት ወገኑን ላለመምሰልና ፈረንጅ ለመምሰል የሚያደርገው የለም! ወገኑን ላለመምሰልና ፈረንጅ ለመምሰል የሀብትና የመንፈስ ድህ እስኪሆን ድረስ የማይከፍለው ዋጋ የለም! ፈረንጅ መሆን ስለማይቻል ፈረንጅ ለመምሰል በትውልዱ መሀከል ‹እኔ እበልጥ እኔ እበልጥ› ያለው ቅድድም ያለው ውድድር መመሰያ ማመዛዘኛ የለውም! የፈረንጅ ትምርት በተማሪውና ጥራዝ ነጠቅ በሆነው ትውልዳችን ዘንድ እንደ ፈረንጅ መብላት እንደ ፈረንጅ መልበስ እንደ ፈረንጅ መናገር እንደ ፈረንጅ መጫወትና እንዲያው በጠቅላላው እንደ ፈረንጅ ለመምሰል ያለው ጉጉት ምን ያክል ጽኑ መሆኑን የሚያሳይ ነው! እንግዲህ ያጥግብህም አያጥግብህ ለጠዬቅሽኝ የምሰጥህ መልስ ይህ ነው አቶ በላቸው» አለ በሻህ በላቸውን ፍጥጥ አድርጎ እያዩ። «ከዚህ ተነስተን» አለ አይኖቹን ከበላቸው አንስቶ እጣራው ላይ ሳያረግብ ተከሎ። «ከዚህ ተነስተን ወደ እያንዳንዱ ቤተሰብ ስንገባ ፈረንጅ ለመምሰል

ባለው ውድድር ፈረንጅ ለመምሰል ባለው ቅድድም መርዳት የሚችሉ ወላጆችና ዘመዶች ከተገኙ መቸም ለሌላ ሳይሆን ለርዳታቸው ሲባል እንደ ሚፈልጉት የታወቀ ነው። የማይችሉት ግን በመምሰሉ ውድድር እንዳያሳድፉ እንዳያጎድፉ፥ የሚሸሹዋቸው እንጂ የሚጠጉዋቸው አይደሉም! » ሲል ያሽሙር ፈገግታ ፈገግ እንዳለ እዚያ ያሉትን ሁሉ ባይኖቹ አዙሮ ገርፎ ሁሉም ይስቁ ጀመር።

«እግዚአብሄር ይስጥልኝ አቶ በሻህ! ከተነጋገርኸው ብዙ የማስማማበት ቢኖርም በጠቅላላው በጣም ጠቃሚ ነው። ነገር ግን የማልስማማበትን ሁሉ ለመግለጽ አሁን ጊዜ ስለሚያጥረን በሌላ ቀን ሰፋ አድርገን ብንነጋገር ይሻል ይመስለኛል፤ አይመስልህም? » አለ በላቸው፤ ፈገግ ብሎ አንድ ጊዜ ሰአቱን አንድ ጊዜ በሻህን እያየ።

«ሳላስበው ነገሩ እዬሳበኝ ብዙ ተናግሬ፥ ስላሰለቸሁህ ይቅርታ አድርግልኝ። እንደገና የተገናኘን እንደሆነ ካንተ ከመስማት በቀር ላልናገር ማንቀርቀሪያ ጠጅ ግይድ ይሁንብኝ! » አለ በሻህ ለመሄድ ሲነሳ ትንሽ እንደ መሳቅ ብሎ።

«እንዲያው ተገኜ ይ - ሙት፥ ይህ ሰው በጣም ደማም ነው፥ እባክህ እዬመጣህ ጠይቀን» አሉ ወይዘሮ ላቀች።

## ምእራፍ ሀያ ስድስት

## ‹እስመ ነፍስ ተአምር ቀታሊሁ›

በሻህ የደመቀችን ልጅ ተከስተን አይወደውም ነበር። ስለዚህ ደመቀች፥ ለሹ ሸሚዝና ጫማ እንዲገዛለት ስትለምነው ‹አልችልም› ሊል ፈልጎ ነበር። ነገር ግን የሚያጠግብ ምክንያት ሳያሰናዳ ድንገት ስለ ነበረ የለመነችው ቅር እያለው እያመነታ የሸሚዙንን ቁጥሮች ከሚገዙበት ገንዘብ ጋር ተቀበለ።

ተከስተን መጀመሪያ ያየው ትምርት ቤት ከመግባቱ በፊት እናቱና አዛዥ ተካልኝ እቃ ሊገዙለት ገብያ ይዘውት ሄዶ ነው። ከዚያ በፊት ሆነ፥ ከዚያ በሁዋላ አይቶት አያውቅም። ያነለት ሲያየው ገና የሰባት አመት ልጅ ነበር። ታዲያ እሱ አዛዥና፥ እናቱ፥ ስለ ሚገዙዋቸው እቃዎች አይነት ወይም ዋጋ ከሻጮች ጋር ሲከራከሩ፥ ተከስተ ጣልቃ እዬገባ ‹ይህ አይሆንም፥ ያ ይሆናል› ማለት ስላበዛ በሻህ በሽቆ ‹ራሱን በኩርኩም

ግጨው› የሚል ሰይጣን መጥቶበት ነበር። ብቻ ‹ምን አገባህ ቢሉኝ ምን እላለሁ?› እንኩዋንስ ትእግስቱን አጠራቅሞ ንዴቱን፥ ውጦ ዝም አለ። ልጆች እንኩዋንስ ስለ ራሳቸው የነሱ ባልሆነ ጉዳይም አዋቆች ሲነጋገሩ ጣልቃ ገብተው ‹እኛን ስሙን› ማለታቸው አዲስ አደለም፤ የሚበዙት እንዲያ ናቸው። ልጆች አዋቆች ቁም ነገር ሲጫወቱ ጣልቃ ገብተው ‹ብስል ከጥሬ› ወሬያቸውን ሲያወሩ ሲዘባርቁ እንኩዋንስ ሊያናድዱ እንዲያውም ደስ ያሰኛሉ፤ ያስቃሉ። በሻህ ራሱ ልጆችን ይወድ ነበር። ‹ብስል ከጥሬ› ወሬያቸው እየጣመው ግን ገና ሲያየው ‹ውቃቤ አምላኩ› አስጠልቶት በሌሎች ልጆች ላይ የሚወደው ጣልቃ ገብቶ መዘባረቅ በሱ ላይ ከፍቶ፥ ታዬው። ከዚያ ቀን ጀምሮ የተከስተ ነገር አልዋጥለት እንዳለ ቀረ። ደመቀች ወደምትኖርበት ወደ አዛዥ ተካልኝ ቤት መሄዱን ካዘወተረ በኋላ እስዋ ተከስተን ስታመሰግን ይልቁንም ከመጠን ያለፈ እንደምትወደውና ከሱ ተለይታ መኖር እንደማታችል መስሎ እንደሚታያት ስትናገር ሲሰማ ትእግስቱ ያልቅና ተነስቶ መሄድ አምሮት መንቆራጠጥ ይጀምራል። ለተከስተ አንድ ነገር - ትልቅ ይሁን ትንሽ - ‹ላድርግ› ትልት የሰማ እንደሆነ ወይም ስታደርግ ያዬ እንደሆነ እንኩዋንስ በቂ ምክንያት ኖሮት ባይኖረውም ሳያስበው ተቃዋሚ ሆኖ ይገኛል። ርግጥ ተቃውሞውን በተዘዋዋሪ መንገድ እንጂ የተቻለውን ያክል በቀጥታ ለማድረግ ይሞክራል። ተከስተን የማይወድ መሆኑንም ካፉ አውጥቶ ለማንም ተንፍሶ አያውቅ። ‹የዛሬ ልጆች› እያለ ጠቅላላ አስመስሎ ቢናገር፥ ለደመቀች ከግዚኤ ብዛት በሻህ ልጅዋን እንደማይወድ እዬተሰማት ሄደ። ብቻ ምክንያቱን ፈልጋ ልታገኘው አልቻለችም። ምክንያቱ እንኩዋንስ ለስዋ ለሱም ግልጽ አልነበረ።

በሻህ ተከስተን የማይወድ መሆኑን ለማንም ተንፍሶ እንደማያውቅ ደመቀችን እንደሚወድም ሊገልጽ የማይፈልግባቸው ምክንያቶች ስለ ነበሩት፥ ለስዋ ይሁን ለሌላ ገልጾ አያውቅ። እንዲሁ ልቡ በምስጢር የስዋ እስረኛ ሆኖ ከስዋ ጋር ተቆራኝቶ እስዋ ወዳለችበት ይጎትተዋል። ብዙ ግዚኤ ሳያስበው በስሜቱ ተገፍቶ ምስጢሩን የሚያወጣበት የሚያጋልጠው ነገር ይናገርና ወይም ያደርግና ደንግጦ ያን ለማረም የሚናገረው ሆኖ የሚያደርገው ከፊቱ የወጣ ደንቃራ ነገር ይብሱን ያጋልጠዋል። መቸም ፍቅርንና ጥላቻን ሸሽጎ ማስቀመጥ አይቻል። ባፍ ባይናገሩዋቸው አካላት ሁሉ ሁኔታ ሁሉ አሳባቂዎቻቸው አጋላጮቻቸው ናቸው! በሻህ ደመቀችን የሚወድና ልጅዋን የማይወድ መሆኑ እንዳይታወቅበት ምንም ያክል ቢሞክር አልተሳካለትም። አነጋገሩ አድርጎቱ ሁኔታው ሁሉ የውነተኛ ውስጣዊ ስሜቱን ገልጾ የሚያሳይ የሚያጋልጠው ነበር። ተከስተን ገና ሲያየው ውቃቤ አምላኩ ያስጠላው፥ ደመቀችን

መውደድ ከመጀመሩ በፊት ነው። ምናልባት ‹እስመ ነፍስ ተአምር መቀታሊሀ› የሚሉት በሰፊ ትርጉሙ ‹ነፍስ ገዳይዋን ብቻ ሳይሆን - ጠላትዋን ተወዳዳሪውና ተፋላሚዋን፥ አስቀድማ ታውቃለች› ማለት ነውና፥ ደመቀች ልጅዋን ተከስተን አጥብቃ ትወድ ስለ ነበረ ከሱ በቀር፥ የምትወደው ስላልነበረ የስዋን ፍቅር የሚካፈለው ለስዋ ፍቅር ተፋላሚው እሱ ብቻ መሆኑ አስቀድሞ ታይቶት ይሆን?

ለልጅዋ አንድ ነጭ ሸሚዝና አንድ ጥቁር ቻማ እንዲገዛለት በሰጠችው ገንዘብ ገዝቶ አሰንብቶ፥ እንደ ለመነችው ለሁድ ግብዣ እንዲደርስላት ቅዳሜ ጥዋት እቤትዋ ወስዶ ሲሰጣት፥

«እግዚአብሄር ይስጥልኝ ጋሼ። እንግዲህ ልውሰድለትና እስቲ - የሚለውን ልስማ» አለች ደመቀች፥ ሸሚዙንም ጫማውንም ከተጠቀለሉበት እያወጣች ካዬች በሁዋላ።

«የፈለጋቸውን ካገኘ በሁዋላ ደግሞ - ሌላ ‹ምን ፍጠሩ› ሊል ነው? ወይስ - የፈለጋቸውን አደለም የገዛሁ? » አለ ባሻህ ሳያስበው ግልፍ ስላለው ግንባሩን ኰስተር አድርጎ።

«አንተስ - ልክ እንድትገዛልኝ የለመንሁህን ነው የገዛልኝ ጋሼ። ብቻ - እንድትገዛልኝ የለመንሁህ እሱ እንዲገዙለት የፈለጋቸው መሆናቸውን ተ - ተጠራጠርሁ እንጂ» አለች፤ ድንገተኛ ግልፍታቸውን የግንባሩን መኮስተር ስታይ፣ እንደ መፍራት ብላ፥ ንግግርዋ እዬተደናቀፈ፥ አይኖችዋን ቶሎ በጅዋ ወደ ያዘችው ሸሚዝ መለሰችና። «ከዛሬ ቀደም በኒህ ቁጥሮች የገዛልሽልኝ ሸሚዝና ጫማ ጠበቡኝ ብዬ ነግሬሽ እንዴት እንደገና በኒያው ቁጥሮች ገዝተሽ ታመጪልኛለሽ? ብሎ ይቆጣ ይሆን? ብዬ ሰግቼ ስቸገር ነው የሰነበትሁ» አለች ቀጥላ አይኖችዋን ከሸሚዙ ላይ ሳታነሳ።

«ታስገርሚኛለሽ! ለመሆኑ እንዲገዛለት የፈለጋቸውን የሸሚዙንና የጫማውን ቁጥሮች እሱ አደለም የሰጠሽ? »

«መስጠቱንስ - የሁለቱንም ቁጥሮች የሰጠኝ እሱ ነው። ነገር ግን - ‹በኒህ ቁጥሮች ነጭ ሸሚዝና ጥቁር ጫማ በቅርቡ አልገዛሁልህም ኖሮዋል ወይ?› ስለው ‹ልኬ አልሆኑም ጠበበኝ› ብሎኝ ነበር። ታዲያ ‹የፊተኞኖች ከጠበቡህ ለምን በኒያ በጠበቡህ ልክ እንድገዛልህ ትፈልጋለህ?› ብዬ ያኔውኑ ማጣራት ይገባኝ ነበር። ነገር ግን - ትንሽ

አዝኖ ነበርና ወደ ማባበሉ ገብቼ ይህን ስለረሳሁት የሰጠኻኝን ቁጥሮች ዝም ብዬ ተቀብዬ መጣሁ።»

«ታዲያ - ፊት የገዛሽለት ‹ጠበቡኝ› ካለ ልኩን መስጠት የሱ ፈንታ ነው እንጂ ያንቺ ነው? እንዲያው - ከራስሽ አብልጠሽ ስትወጂው ጊዜ የሱን ጥፋት አድርገሽ ራስሽን ትወቅሻለሽ። እንዲያውም - አንቺን አልገባሽም እንጂ ነገሩ ሌላ ነው። ብቻ እሱን እንተወው ግዴለም። ለመሆኑ ‹ሲያዝን አይቼ ወደ ማባበሉ ገባሁ› ያልሽ ምን አሳዘነው? »

«ኦ - ልጅ አደል? መቸም ልጅ ሲባል እንደምታውቀው ወላጆቹን የሚቸግራቸው አይመስለውም። ከሽሚዝና ከጫማው ጋር አንዳንድ ጥቃቅን ነገሮች እንድትገዛለት ፈልጎ፥ ለግዜው ገንዘብ አጥሮኝ የማልችል መሆኑን ስነግረው - ትንሽ አዘነ።

«የወላጆቻቸው ችግር የማይሰማቸው ‹ወላጆቻችን ይቸገሩ ይሆናል› ብለው የሚያስቡ ልጆች፥ ወላጆቻቸውን የማይወዱ መሆናቸው የታወቀ ነው። ይቅርታሽን ያቺን ልጅ ማለቴ እንዳይመስልሽ፤ ያንቺ ልጅማ - ከራሱ የበለጠ፥ ላንቺ እንደሚያስብ - ብዙ ጊዜ ስትናገሪ ሰምቻለሁ» አለ በሻህ ባሽሙር። ደመቀች አልመሰለሽም። ጠቅላላ አስመስሎ በተለይ ስለስዋ ልጅ የተናገረው አሽሙር እንደሆነ ስላወቀች አንገትዋን ደፍታ ዝም አለች።

«በቀደም - እነኒህን እቃዎችን እንድገዛልሽ ስትጠይቂኝ አባባ አዛዥ ያሉት ትዝ ይልሻል? » አለ በሻህ ሁለቱም ዝም ብለው ከቆዩ በሁዋላ።

«አባባ አዛዥ ምን አሉ? » አለች እንደገና ቀና ብላ አይኖቹን እያየች።

«እንዲህ - እዬተበደርሽ እዬተቀደምሽ፥ የጠዬቀሽን ሁሉ ስታደርጊለት ኖረሽ አንድ ቀን ተበድረሽም ተቀድመሽም ልታደርጊለት የማትችይው ነገር ይጠይቅሽና ሳታደርጊለት የቀረሽ እንደሆነ ባትፈቅጅ እንጂ ባትችይ ስለማይመስለው ‹ተጣልታችሁ እንዳትለያዩ አስቀድመሽ ብትጠነቀቂ ይሻላል› አላሉሽም? እይው እሳቸው ያሉት ደረሰኮ! ደግሞ አንቺና ልጅሽ ተጣልታችሁ እንዳትለያዩ የሚያሰጋ ሌላ ነገር እኔ ልንገርሽ። ልጅሽ ህጻን ሳለ አንቺ ለሱ ላንቺ ከናትና ልጅነታችሁ ሌላ የጭዋታ የምግብ፥ የምኝታ የሌላም ብዙ ነገር ጉዋደኞች ነበራችሁ። አሁን ካደገ በሁላ ግን አንቺን በናትነሽ እንደ እናት እንጂ ከናትነትሽ ሌላ የምንም ነገር ጉዋደኛአው እንደ ሆንሽ አድርጎ

አያይሽም። አሁን ባለበት እድሜና ባለበት ቦታ፥ ካንቺ ማግኘት የማይችለውን የጣንት የጭዋታ፥ የፍቅር፥ ጉዋደኝነት የሚሰጡት ብዙ የወንድና የሴት ጉዋደኞች ስለሚኖሩት አሳቡንና ጊዜውን ለነሱ ጉዋደኝነት ሊሰጥ ይመርጣል። ይህ በሱ እድሜና በሱ ቦታ የሚገኙ ወጣቶች ሁሉ የሚያልፉበት መንገድ መሆኑን ተረድተሽ እናንትነሽ ብቻ በቅቶሽ ጉዋደኝነቱን እሱ ለመረጣቸው መልቀቅ አለብሽ። ያለዚያ - ከዚያ ‹ልለፍ› ካልሽ በግል ጉዳዩ ጣልቃ እንደ ገባሽ ይቆጥረውና ይጠላሻል። ላንቺም ቢሆን -» አለ ትንሽ ዝም ብሎ ቆይቶ። «ላንቺም ቢሆን መቸም አሁን እንዳልሁሽ ልጅ ከልጅነቱ አልፎ ሊሰጥ የሚገባውን ለሱ እዬሰጠሽ ሌላውን - ለሌላ ብትቆጥቢው የሚሻል ይመስለኛል።»

«ከሱ ቀንሼ - የምቆጥበው ለማነው? »

«ጉዋደኝነትሽ፥ ፍቅርሽ ጎትቶ ለሚያመጣው» አለ አይኖቹን ገደም አድርጎ ወደስዋ እያዬ።

ደመቀች ልብዋ እንደ መሸበር ሲል ቀይ ፊትዋ፥ ይበልጡን እንደ መቅላት ብሎ፥ ላንድ አፍታ ቀና ብላ አዬችውና መልሳ አንገትዋን ደፍታ ዝም አለች። ከዚያ ሁለቱም ዝም ብለው ቆይተው፥

«ለማናቸው - አባባ አዛዥ የመከሩሽ ጥሩ የሽማግሌ ምክር ነውና፥ ካሳብሽ ባታጠፊው መልካም ነው። የዛሬ ልጆች - የሚፈልጉት ነገር መሙላቱን እንጂ ያን ለማሙዋላት ወላጆቻቸው አይደርስ ችግር ቢደርስባቸው ከመ - ጤፍ አይቆጥሩትም፥ ግዴላቸውም» አለ፤ ነገሩን ከያዘው መንገድ ወደሌላ መምራት ስለ ፈለገ።

« ‹ልጆች - የዛሬ ሆኑ የድሮ ምንግዜስ ቢሆን ያው ልጆች አደሉም? » አለች ደመቀች ጠቅላላ አስመስሎት የተናገረው ስለስዋ ልጅ መሆኑን ስለምታውቅ፥ ቅር ያለው ፊትዋ ባሽሙር ፈገግታ አጊጦ።

« ‹ልጆች› ከሚባለው ስም በቀር የዛሬ ልጆች ከድሮ ልጆች የሚነገሩት አንድ ነገር የለም። ‹ሽሚዙና ጫማው ልኩ አይሆኑ ይሆናል ብዬ ፈራሁ› ስላልሽው ልነግርሽ ያሰብሁትን ሳልረሳው ልንገርሽ። ‹የዛሬና የድሮ ልጆች ከስም በቀር የሚነጋገሩት የለም› ስላልሁት፥ ሁዋላ ትንሽ ሰፋ አድርገን ብንነጋገር እንዲያውም - ጥሩ አጋጣሚ ነው።

«ለኔ እንደ መሰለኝ ሽሚዙም ሆነ ጫማው ልኩ ስላሆኑ አደለም ልጅሽ ሁለቱም እንደገና እንድትገዥለት የፈለገ። ወደ ፊት የገዛሽለትን ለጓደኞቹ ሰጥቱዋል፤ ያለዚያም አሁን እነዚህን ሊሰጥ ነው። ፊት የገዛሽለት ልኩ ባይሆኑ ኖሮ እንደገና እንድትገዥለት ሲፈልግ የነሱን ቁጥሮች መልሶ አይሰጥሽም ነበር። ስለዚህ አሁን የተገዙለትን ‹ልኬ አልሆኑም ብሎ ያዝናል› ብለሽ ምንም አትስጊ በኔ ይሁንብሽ» አለ። ከዚያ አይኖቹን በአንጻሩ ባለው የቤት ግድግዳ ተክሎ ከቆየበት መለስ አደረገና «አሁን እንግዲህ ጊዜና ትግስት ካሉሽ ‹የዛሬና የድሮ ልጆች ከስም በቀር የሚነጋገሩት ነገር የላቸውም› ስላልሁት እንነጋገር» አለ።

«ዛሬ ጊዜም፥ ትእግስትም ከኔ የተረፉኝን ለሌሉዋቸው ላበድር እችላለሁ! » አለች ደመቀች እንደ መሳቅ ብላ።

«መልካም እንግዲያ! አዬሽ? በዘመናዊ ትምርት ቤት እዬተማሩ የሚያደርጉት የዛሬ ልጆች የኢትዮጵያ ከዘመናዊ ስልጣኔ ወደ ሁዋላ የቀረች አገር ስለ ሆነች ‹ወደ ሁዋላ ያስቀሩዋት ባህልዋ ልማድዋ፥ ወግዋ፥ እምነትዋና በጠቅላላው፥ የኑሮ ስራትዋ ናቸው› ብለው አምነው እነዚህን ሁሉ ባንድ ላይ ጥቅልል አድርጎ ወዲያ ጥሎ በነሱ ፈንታ የፈረንጆችን ባህል ልማድ ወግ እምነትና የኑሮ ስራት መተካት እንደሚያስፈልግ የሚያምኑ ናቸው።

«በድሮ ወግና ስራት፥ ወላጆች ልጆቻቸውን ከደማቸው ቀንሰው፥ ከስጋቸው፥ ቆርሰው ካለመኖር ወደ መኖር ካመጡዋቸው በሁዋላ ክፉ እንዳይደርስባችው መልካሙ እንዳይቀርባቸው ከራሳቸው አስቀድመው ለልጆቻቸው እያሰቡ ተጠንቅቀው ጠብቀው በበጎ ምግባር እዬመሩ አሳድገው ለአካለ መጠን ሲበቁ ጥማድ ለሽትና ለምርት ጥገት ለወተት ሰጥተው ይድሩና ራሳቸውን አስችለው ያቆሙዋቸዋል። ስለዚህ ልጆች ወላጆቻቸውን ማፍቀር ብቻ ሳይሆን ከእግዚአብሄር በታች ሁለተኛ ፈጣሪያዎቻቸው በመሆናቸው ሊያከብሩዋቸው ይገባል!› ተብሎ ይታመን ስለ ነበረ እንዲህ ባለ እምነት እዬተመሩ የሚያድጉ የድሮ ልጆች ወላጆቻቸውን ያፈቅሩና ያከብሩ ነበር።

«ነገር ግን በዛሬ ዘመን ልጆች ዘንድ ስለ ወላጆችና ስለ ልጆች ግንኙነት ያለው ትምርትና እምነት ጨርሶ ሌላ ነው። እንደ ዘመኑ ልጆች ትምርትና እምነት ‹ወላጆች ራባቸውን በምግብ ጥማቸውን በመጠጥ ማርካት በፍጥረት ህግ እንደ ተደነገገላቸው ፍትወተ - ስጋቸውን በሩካቤ - ስጋ እንዲረኩ በፍጥረት ሕግ የተደነገገላቸው ስለሆነ

እንዲያ ፍትወተ - ስጋቸውን በሩካቤ - ስጋ በሚያረኩበት ጊዜ ልጆች ፈልገው ሳይሆን ባጋጣሚ ወላጆች ለራሳቸው ደስታ ሲሉ በሚፈጽሙት ግብር ይፈጠራሉ። ከተፈጠሩ በሁዋላ ደስታ ሲሉ በሚፈጽሙበት ግብር ይፈጠራሉ። ከተፈጠሩ በሁዋላ ርግጥ፥ ልጆች የወላጆች የደማቸው ቅናሽ የስጋቸው ቁራሽ እንደ መሆናቸው ወላጆች የራሳቸውን ህያው ምስል ከሞላ ጎደል በልጆቻቸው ስለሚያዩ ይወዱዋቸውና ደስ ያሰኙዋቸውና እዬተጠነቀቁ እዬጠበቁ ያሳድጉዋቸዋል። ከዚያም የራሳቸውን ደስታ ሲፈልጉ ፍትወተ - ስጋችወን ሲያረኩ ያፈሩዋቸውን የፈጠሩዋቸውን ፍጥረቶች ካደጉ በሁዋላ ተሸክሞ ከመኖር ከብት ገልጦ ድሮ ከትከሻቸው ማውረድና ራሳቸውን ማስቻል የሚቀል በመሆኑ አቁዋቁመው ራሳቸውን እንዲችሉ ያደርጉዋቸዋል። ስለዚህ ልጆች ከመፈጠራቸው በፊት ጀምሮ ተወልደው አድገው ራሳቸውን እስከሚችሉበት ጊዜ ድረስ በሚጉዋዙበት የሕይወት ጎዳና የሚደረገው ሁሉ በመጀመርያ ደረጃ፥ ለወላጆች ተድላ፥ ደስታና ምቾት ተብሎ የሚደረግ እንጂ፥ ለልጆች ድሎት ወይም ደስታ ተብሎ የሚደረግ አደለም። ስለዚህ ልጆች ወላጆቻቸውን እንደ ባለ ውለታ የሚቆጥሩበት ምንም ምክንያት የለም። ልጆች ከተወለዱ በሁዋላ፥ የሚደረገው ሁሉ እንዲደረግ የልጆች መብት የወላጆች ግዴታ ስለሆነ የሚደረግ ነው! »

«እይውልሽ እንግዲህ የዛሬ ልጆች ስለ ወላጆችና ስለ ልጆች ያላቸው አስተያየት ይህን የመስለ ነው። ታዲያ እንግዲህ እንዲህ ያለ ትምርት እዬተማሩ እንዲህ ባለ እምነት እዬተመሩ የሚያድጉ ልጆች ወላጆቻቸውን እንደ ባለውለታዎቻቸው ሊያፈቅሩና ከእግዚአብሔር በታች እንደ ፈጣሪያዎቻቸው አድርገው ሊያከብሩ ይችላሉ? አይችሉም! » አለ በሻህ ጥያቄውን ራሱ መልሶ ደመቀችን ፍጥጥ አድርጎ እያዬ።

«ኡም -፥ እንጃ! ይህን አሁን ያልኸውን እንኩዋንስ ከልጅ፥ ካዋቂም ከማንም ሰምቸው አላውቅ! ስለዚህ - ምናልባት አንዳንድ ‹እንወቅ ተራርቀን› የሚሉ ልጆች እንዲህ ያስቡ እንደሆን እንጂ በጠቅላላው የዘመኑ ልጆች ሁሉ በነሱና በወላጆቻቸው መሀከል ያለውን ግንኙነት እንዲህ አሁን እንዳልኸው - ዛሬ ሲርብ ተበልቶ፥ ነገ ሲጎረብጥ አውጥቶ እንደሚጥሉት የህል አተላ፥ የሚቆጥሩ አይመስለኝም! » አለች ደመቀች ትንሽ እንደ መሳቅ ብላ። በሻህ ደመቀች በሰጠችው ምሳሌ አብሮዋት ሲስቅ ቆዬና «እስቲ ስላንቺ ስለ ራስሽ ልጅ ልጠይቅሽ» አለ።

«ምን? » አለች ደመቀች።

«ያንቺ ልጅ ገና በህጻንነቱ ጡት አጥብተሽ ሁዋላም የድሀ አቅምሽ በሚፈቅድልሽ መጠን የተወሰነ የህጻን ፍላጎቱ ሁሉ እዬፈጸምሽ የናትነት ፍቅርሽንና ጉዋደኝነትሽን እዬሰጠሽ ስታሳድጊው ይህን ሁሉ ካንቺ፥ ከሌላ ሊያገኝ ስለማይችል በጣም፥ ይወድሽ ነበር። ከዚያ ምንም እንኩዋ አሁን እሱ አድጎ ጎምሶ በዚያው መጠን የሚፈልጋቸውና የሚወዳቸው ነገሮች ጉዋደኞቹ ጭምር እዬብዙ ቢሄዱ አንቺ ለሱ ያለሽ ፍቅር እያደገ እንጂ እያነሰ እንዳልሄደ በምታደርጊው ሁሉ ያይን ምስክሮች ሆነን ስለምናይ እናውቃለን። ነገር ግን - እሱ ላንቺ ያለውን ፍቅር አንቺ እንጂ እኛ አናውቅም። አሁን ካደገ በሁዋላ እሱ ላንቺ ያለው ፍቅር - እንደ ድሮው ነው? እንዳንቺው እዬጨመረ እያደገ ነው፥ የሄደ? ወይስ እዬቀነሰ እያነሰ! » ብሎ ጠይቆ፥ የተቸገሩ አይኖችዋ ለጠዬቃት መልስ እንደሚፈልጉ ወዲያ - ወዲህ ሲቃብዙ ዝም ብሎ ይመለከታት ጀመር። የበሻህ ጨካኝ ጥያቄዎች፥ ልክ እንደ ሹል ጦር እንደ ፍላጻ የቀሰለ ልብዋን ሲወጉት የተስማት እመም የተሰማት ስቃይ በፊትዋ ይታይ ነበር።

ልጅዋ ፍቅሩንና ጉዋደኝነቱን ከስዋ እዬቀነሰ እዬቀነሰ በዬጊዜው ለሚያበጃቸው ወዳጆቹና ጉዋደኞቹ ሲያካፍል እዬተመለከተች እስዋ፥ እንዲያ በዬጊዜው እዬበዙ ለሚሄዱት አዳዲስ ጉዋደኞቹና ወዳጆቹ ድግስ ደጋሽና ስጦታ አመላላሽ ብቻ ከመሆንዋ በቀር፥ በልቡ ውስጥ የነበራትን የፍቅር ቦታ ትንሽ በትንሽ እዬለቀቀች እያጣች፥ መሄድዋ እዬተሰማት ልብዋ ባዘን ቆስሎ፥ ለሰው እንዳትገልጸው እያፈረች፥ እዬፈራች ሸሽታ ያስቀመጠችውን የምስጢር ቁስልዋን ነውረኛ ቁስልዋን እኒያ የበሻህ ጨካኝ ጥያቄዎች ሲነኩባት፥ ሲወጉባት የተሰማት እመም በፊትዋ ግልጽ ሆኖ ይታይ ነበረ! ብቻ ቢሆንም እንዲያ ያለ የምስጢር ቁስል እንዲያ ያለ ነውረኛ ቁስል ምንም ያክል ቢያም ምንም ያክል ቢያሰቃይ በፊትዋ እንኩዋ ግልስ ሆኖ ቢታይ ጥርስን ነክሶ መቻል ነው እንጂ፥ አፍን ከፍቶ አይነገርም! ስለዚህ ደመቀች የልጅዋ ልብ ከስዋ ልብ እዬሸሸ የሚሄድ መሆኑ ቢሰማትም መናገሩን ከማፈርዋም ሌላ የተናገረችው እንደሆነ ከስሜት ደረጃ አልፎ እውነት እንዳይሆን ባፍዋ እዬፈራች መናገር አትፈልግም አትችልም ነበር!

«ፍቅሩን - ለኔ ያለውን ፍቅር ከድሮው መቀነስ? ኧረ በስማብ! ምን አልሁህ አያ! ፍቅሩን ጭራሽ አልቀነሰም! » አለች ደመቀች። የውነተኛ ስሜትዋን ልብዋ አልቀበል ብሎ፥ እምቢ ብሎ ሲታገል በውስጥዋ የተነሳው ሁከት በሁለመናዋ ወለል ብሎ ይታይባት ነበር።

«ጭራሽ አልቀነሰም! እ? » አለ በሻህ ከቅርታ ፈገግታ ጋር፥ ጭንቀትዋን ከሁኔታዋ ሁሉ ሲያይ አሳዝናው።

«ጭራሽ አልቀነሰም ያው ነው» አለች ደገመችና።

«አንቺ ለሱ ያለሽ ፍቅር ግን - እየጨመረ ነውኮ የሄደ! »

«የሱም እንደዚያው - እየጨመረ ነው የሄደ» አለች፤ የማያዩ አይኖችዋ ቦዘዝ ብለው እንዲሁ በባዶ ላይ እንደ ተከፈቱ አይነ - ህሊናዋ ከስዋ የሚሸሸውን የልጅዋን ፍቅር እዬተመለከተ።

«ጥሩ ነው፥ እስቲ እንዳፍሽ ያድርግልሽ! » አለ በሻህ፤ ቅርታው ከፊቱ ሳይጠፋ አይኖቹን ከስዋ አንስቶ ሳያረግብ ፊት ለፊት ተክሎ። ደመቀች አሳብዋ አይነ - ህሊናዋን ተከትሎ ሄዶ ከስዋ የሚሸሸውን የልጅዋን ፍቅር ሲመለከት በሻህ በመጨረሻ ያለውን አልሰማችም።

«ለመሆኑ ለምነው እንዲህ ያለ ጥያቄ የጠዬቅኸኝ? የሰማኸው ነገር አለ? » አለች አሳብዋ ከሄደበት ሲመለስ። ልጅዋ ለስዋ ያለውን ፍቅር መቀነሱን የሚያረጋግጥ ማስረጃ ያመጣብኛል ብላ ፈርታ ነበር።

«በተለይ ስላንቺ ልጅ የሰማሁት ምንም የለ፤ በጠቅላላው የዛሬን ልጆች ጠባይ ስለማውቅ ያንቺ ልጅም ቢሆን - ከመንጋው ምንም ያክል ልዩ ልሆን አይችልም በማለት ብቻ ነው።»

«እሺ ይሁን፥ እስቲ - እግዚአብሄር እንዲሁ ያዝልቅለት» አለና በሻህ ትንሽ ዝም ብሎ ሲያስብ ቆይቶ፥ «እስቲ አሁን አንዳንድ አሳቦች ላካፍልሽና ከውስጣቸው ‹ይጠቅሙኛል የምትያቸው ቢኖሩ› ትይዣቸዋለሽ፤ ያለዚያም - መስማቱ ይህን ያክል ጎድቶ አይጎዳሽ! » አለ አሁንም ከቅርታ ፈገግታ ጋር።

«ያንተን አሳብና ምክር ካልሰማሁ የማነን እሰማለሁ? ካባባ አዛዥ ሌላ እዚህ አገር አንተና ጋሼ ውቤ አደላችሁ ያላችሁኝ? »

«እግዚአብሄር ይስጥልኝ» አለና ፈገግ እድናለ ትንሽ እንደ መስገድ ብሎ፥ ‹ይኸው ከተዋወቅን - » አለ አይኖቹን ሳይረግብ ማዶውን እዬተመለከተ፥ «ከተዋወቅን አስር፥ ወይም አስራንድ አመት መሆኑ ነው መሰለኝ አደለም? »

«ይሆናል» አለች ደመቀች አዎታዋን ራስዋን ወደ ላይ በመግፋት ጭምር እዬገለጸች።

«አዎ ታዲያ ያንጊዜ መጀመሪያ ስንገናኝ ልጅሽ ሰባት አመቱ እንደ ነበረ ስትነጋገሩ መስማቴ ትዝ ስለሚለኝ እንግዲህ ዛሬ ያስራ ሰባት ወይም ያስራ ስምንት አመት ጐበዝ ነው ማለት ነው» ሲል በሻህ፥ «እንዲያውም አሁን አስራ ዘጠኝ ሆኖታል» አለች ደመቀች።

«እሺ አስራ ዘጠኝ። ታዲያ ያ የተገናኘንበት ቀን እሱን ትምርት ቤት ለማስገባት አባባ አዛዥና አንቺ እቃ ልትገዙለት ገበያ ወጥታለችሁ ነው። ያነለት፥ ገንዘብሽ የማይበቃ ሆኖ፥ ልትገዥለት ከፈለግሻቸው እቃዎች ዳንዳንዶቹ እንዲቀሩ ስንነጋገር ከልጁ ይልቅ አንቺ ልቅሶ መጥቶብሽ አይኖችሽን የሞላው እንባ እንዳናይብሽ ስትቸገሪ እንዳላዬሁ አይቼ፥ በጣም አዘንሁና፥ አንጀቴ በሆዴ ውስጥ ሲላወስ ተሰማኝ። ስለዚህ ነበር፥ በማናቸውም መንገድ የፈለግሻቸውን እቃዎች ሳታገኚ እንዳትቀሪ ህግ አክብረው በሚሰሩት ነጋዴዎች ዘንድ የተፈለጉት እቃዎች ልትከፍይ በምትችይው ዋጋ ሳይገኙ ስለቀሩ በር እዬሰበሩ አጉራ ዘለል እቃዎች ወደሚያስገቡ ነጋዴዎች ይዣችሁ የሄድሁ። ያነለት ያን ያክል የምትወደው እናት ስላለችው በልጅሽ እንዴት ቀናሁ መሰለሽ! የኔን እናት የዚያን አስረኛ እጅ እንኩዋ ትወደኝ ስላልነበረ እንዴት ጠላሁዋት መሰለሽ! ከመቃብርዋ ቀስቅሽ ረገምሁዋት! በህጻንነታቸው ራሳቸውን በማይችሉበት ጊዜ እንዲያ የሚወዱዋቸውና የሚጠነቀቁላቸው የሚረዱዋቸው ወላጆች ያሉዋቸው ልጆች በውነት እድላሞች ናቸው! ብቻ የወላጆች ፍቅር እንኩዋ ቢቀጥል ርዳታቸውና ጥንቃቄያቸው ልጆች ራሳቸውን መርዳትና ለራሳቸው መጠንቀቅ እስኪችሉ ድረስ መሆን አለበት፤ የጊዜ ወሰን ሊኖረው ይገባል። ያለዚያ የወላጆች ርዳታና ጥንቃቄ የጊዜ ወሰኑን አልፎ የቀጠለ እንደሆነ እነሱን ብቻ ሳይሆን ልጆችን ጭምር ሊጎዳ ይችላል። በዚህ በተዋወቅንበት አስር ይሁን አስራንድ አመት ውስጥ እኔ እንደ ተመለከትሁት ልጅሽ ባደገ መጠን የሚፈልገው እየበዛ ሲሄድ ያን ሁሉ ብዙ እጥፍ ጊዜ እዬበዛ እዬበዛ ሲሄድ አሁን በጣም ከብዶ ለመሸከም በማትችይበት ደረጃ ደርሶዋል። ይህ ታዲያ አንቺን ብቻ ሳይሆን ለጊዜው ባይታወቅም እሱን ጭምር ይጎዳዋል። ‹እንዴት?› ብትይኝ አንቺ ማወቅ አለማወቅሽን አላውቅም እንጂ የተፈሪ መኰንን ትምርት ቤት ብዙ የሀብታሞች ልጆች ብዙ በመሀከለኛ ኑሮ የሚኖሩ ቤተ - ሰቦች ልጆችና ብዙ የድሆች ልጆች ባንድነት እዬኖሩ የሚማሩበት ትምርት ቤት ነው። ታዲያ የድሆች ልጆች ትምርት ቤቱ የሚያቀርብላቸው ምግብ ልብስና፥ ሌላውም ለኑሮ የሚያስፈልገው ነገር በቅቶዋቸው ደስ ብሎዋቸው ይኖራሉ። በመሀከለኛ ኑሮ የሚኖሩ ቤተሰቦች ልጆችም ቢሆኑ እዚያ ከሚያገኙት በላይ ነው የፈለጉ እንደሆነ የፈለጉትን፥ ሁሉ አያገኙም። እኔ የማውቀውን ነው የምነግርሽ። ሀብታሞች ግን ልጆቻቸውን ደስ ለማሰኘት ብቻ ሳይሆን ከተራ ሰዎች

ልጆች በላይ መሆናቸው ለነሱም ለታች ቤት አካባቢ የጌትነት የቸርነትና የዘመናይነት ዝናን ለማግኘት ሲሉ ሞልቶ ከተትረፈረፈው ሀብታቸው እንኩዋንስ ተጠይቀው ሳይጠየቁ፥ ራሳቸውን ለምነው ለልጆቻቸው በዬለቱ ልስብ መግዛት ለልጆቻቸው ጉዋደኞች ላስተማሪዎችና ለሹሞች ስጦታ መስጠት ድግስ መደገስ ደስ ይላቸዋል» አለና በሻህ ትንሽ ዝም ብሎ ሲያስብ ቆይት፥ «አሁን» አለ አይኖቹን ወደ ማዶ ከሚመለከቱበት መልሶ ደመቀችን ፊት ለፊት እያዬ፥ «አሁን፥ ‹ከነዚህ ከተመለከቱት ሶስት አይነት ቤተሰቦችና ልጆቻቸው አንቺና ልጅሽ በየትኛው ተራ ናችሁ?› ብሎ የሚጠይቅሽ ቢኖር ‹ይት ነን› ትያለሽ? »

«ከቶ በየትኛው ተራ ልታስቀምጠኝ አምሮህ ይሆን? » አለች ደመቀች እዬሳቀች።

«አንቺ ሀብት ሞልቶ ከተትረፈረፋቸው ጌቶች፥ ልጅሽ የድሆችንና በመሀከለኛ ኑሮ የሚኖሩ ቤተሰቦችን ልጆች ዘሎ አልፎ ሌሎችን ዘቅዝቀው ከሚመለከቱ የጌቶች ልጆች ተራ ናችሁ! »

«እንዲያ እንጂ! ምነ ከለገሰህ አይቀር ትንሽ ከፍ ብታደርገን? ትንሽ ከፍ አድርገንና እኔን አንግሰህ በንጉሱ ልጄን ባልጋ ወራሹ ቦታ አስቀምጠን! » አለች ደመቀች እዬሳቀች።

«ተይ አትሳቂ፥ እኔ ቁም ነገር ነው የምነግርሽ! » አለ በሻህ በተናገረችው ሳይሆን ሳቅዋ ተጋብቶበት አብሮዋት ሲስቅ ቆይቶ። «አሁን ቢያስቅሽም ቢያስለቅስሽ፥ የጀመርሁትን እስክጨርስ - ትንሽ ታገሽኝ።»

«እሺ በል ጨርሲ ይቅርታ አድርግልኝ።»

«አዎ፥ አንቺ የጌቶች ሀብት ሳይኖርሽ በጌቶች ተራ ገብተሽ ጌቶች ለልጆቻቸው የሚያደርጉት ሁሉ ላንቺ ልጅ እንዳይቀርበት እሱን ደስ ለማሰኘት እዬተበደርሽ እዬተቀደምሽ ልትከፍይው በማትችይ እዳ ውስጥ ገብተሽ ትዋኛለሽ! ልጅሽ እዳ እዬገባሽ በምታደርጊለት ርዳታ ጉዋደኝነቱን ከጌቶች ልጆች ጋር አድርጎ ከዚያ ከፍተኛ ቦታ የድሆችንም የመሀከለኛ ቤተሰቦችንም ልጆች ማለት በዙሀኑን የሚንቅና ብዙሀኑ የሚጠሉት ይሆንንሻል! ይህን ክፉ ሁኔታ እንዲፈጠር የሚያደርግ ይህን ልጅሽ በሚኖርበት ትምርት ቤት ብዙሀኑን እንዲንቅንና ብዙሀኑ እንዲጠሉት የሚያደርግ አንቺ እዳ እዬገባሽ የምታደርጊለት ወሰን የሌለው ርድታ መሆኑን መገንዘብ አለብሽ።

ለመሆኑ አንቺ እንዲያ ያለ ወሰን የሌለው ርዳታ ባታደርጊለት ምን ይሆን ኖሮዋል? ይሞት ኖሮዋል? የለም አንቺ እዳ እዬገባሽ ባትረጂው አስቀድሞ ቦታውን አውቆ፥ ቦታው ወዴት እንደሆነ ተረድቶ እንደ ድሆችና መሀከለኛ ኑሮ እንደሚኖሩ ቤተሰቦች ልጆች ሁሉ ትምርት፥ ቤቱ የሚያቀርብለት ምግብ ልብስና ሌላው ለኑሮ አስፈላጊ የሆነ ነገር በቅቶት ደስ ብሎት ይኖር ነበር። አሁን - እግዚአብሄር አይበለውና አንቺ፥ ባትኖሪስ? ከንግዲህ አንቺ ባትኖሪ ይህ ልጅ ከሁለት ነገሮች አንዱን መምረጥ ግድ ይሆንበታል። መጀመሪያው አንድ፥ ጌቶች ልጆች ያንኖረው የነበረው ያንቺን ርዳታ ሲያጣ፥ ከከፍተኛ ቦታው ወርዶ ጉዋደኝነቱ ከድሆች ልጆች ጋር አድርጎ፥ እንደነሱ መኖር ነው። ብቻ ንቆ ደቅድቆ ወደ ተዉት መመለስ ለማንም ቢሆን ቀላል አደለም፣ ከባድ ነው። ስለዚህ ሁለተኛው ማማረጫ ይቀለዋል። ሁለተኛው ማማረጫ ጉዋደኝነቱን ከጌቶች ልጆች ጋር እንዳደረገ እዚያው እከፍተኛው ቦታው ሊያቆዬው የሚችል መንገድ ፍለጋ፥ - አንዳንድ የጨነቃቸው ሰዎች የሚሰሩዋቸውን ስራዎች እንኩዋ - ያንቺ ልጅ ይሰራል ብዬ ሳይሆን - እንዲህ ያለ ሁኔታ አይፈጠር እንጂ ከተፈጠረ, ወደዚያ ይመራል ለማለት ያክል ብቻ ነው» አለ በሻህ የፊትዋን መለወጥ ሲያይ አሳዝናው ያስበውን በእምቀበልና ባለመቀጠል መሀከል እያመነታ።

«ለመሆኑ ምን አይነት ስራዎች ናቸው? » አለች ደመቀች፤ ፊቱን ኮስተር ፈካ፥ እያደረገ የስዋም ስሜት የሱን ፊት ተከትሎ እዬተዋወጠ ዝም ብላ ስታዳምጥ ቆይታ።

«አ - ፥ - መስረቅ መቀማት ማጅራት መምታት! » አለ፥

«ኧረ በስማብ! ምነ ምን አለህ? ምን አልሁህ ጋሼ? »

«አንቺም፥ እሱም አሁን የተከተላችሁት መንገድ በጠቅላላው የሚያደርሰው ወደዚያ ነው» ለማለት ያክል ነው እንጂ - ‹ያንቺ ልጅ እንዲያ ያልቱን ስራዎች ይሰራል ብዬ አደለም› አልሁኮ» አለ በሻህ፤ አሁንም የተናገረውን በጠቅላላ ስለ ወላጆችና ስለ ልጆች በተለይ ስለስዋና ስለ ልጅዋ የተናገረ ላለማስመሰል ቀደም ብሎ የተናገረውን ደግሞ። ነገር ግን እንዳታዝን የፈጠረው መላ፥ ከመላነቱ ሊያስረዳት አልቻለም፤ ማዘንዋ በፊትዋ ጎልቶ ይታይ ነበር።

«እኔ መቸም» አለ ሁለቱም ትንሽ ዝም ብለው ከቆዩ በሁዋላ። «እኔ መቸም በጊዜ ካልተጠነቀቅሽ ሁለታችሁም ወደምትጎዱበት ሁኔታ ትደርሱና መመለሻ እንዳታጡ ነው እንጂ በተለይ ስለስዋና ስለ ልጅዋ የተናገረ ላለማመስመሰል ቀደም

ብሎ የተናገረውን ደግሞ። እንገር ግን እንዳታዝን የፈጠረው መላ ከመላነቱ አልፎ ሊያስረዳት አልቻለም፤ ማዘንዋ በፊትዋ ጎልቶ ይታይ ነበር።

«እኔ መቸም» አለ ሁለቱም ትንሽ ዝም ብለው ከቆዩ በሁዋላ። «እኔ መቸም በጊዜ ካልተጠነቀቅሽ ሁለታችሁም ወደምትጎዱበት ሁኔታ ትደርሱና መመለሻ እንዳታጡ ነው እንጂ - ሌላ አላማ እንደሌለኝ ታውቂያለሽ።»

«ይገባኛልኮ! አንተ መቸም - እኔ ከመጠን ያለፈ ነገር የማደርግለት መስሎህ ሁለታችንም እንዳንጎዳ ለኛ አስበህ ነው። ደግሞ ልጁን ደህና አድርገህ ባታውቀው ጭምር ነው።»

«በጠቅላላው ‹የጆችን ጠባይ አውቃለሁ› አልሁ እንጂ፥ ርግጥ ያንቺን ልጅ ደህና አድርጌ እንደማላውቀውማ ነግሬሻለሁኮ! አንቺ ለሱ የምታደርጊውን ግን ደህና አድርጌ አውቃለሁ» አለና በሻህ አይኖቹን ከራስዋ በላይ አሻግሮ ማዶውን እዬተመለከተ ትንሽ ዝም ብሎ ቆይቶ፣ «ለመሆኑ» አለ፤ መቀየምዋ ካልቀረ ያሰበውን ሁሉ እንድያውን ማውጣቱ የሚሻል አለ መሰለው። «ለመሆኑ እስቲ - ይህን ዳር ዳር፥ መነካካቱን ትተን ፍርጥርጥ አድርገን እንነጋገር። ዳር ዳር መነካካቱ፣ ማሳመሙ ሳይቀር በሽታ አያወጣም! ለመሆኑ እግዚአብሔር አያርገው እንጂ፥ ያንቺ ልጅስ ቢሆን አንቺን ቢያጣ ባንቺ ርዳታ እንደሚኖርወ ለመኖር የሚችልበት ሌላ መንገድ አለው? ሌሎችምኮ የሚበዛውን ጊዜ፥ ካንዳንድ ጤነኛ አእምሮ ከሌላቸው በቀር የለመዱትን አጥተው ሲጨንቃቸው ነው እንዲያ ያሉትን ስራዎች ወደ መስራቱ የሚሄዱ እንጂ ወደው አይደለም። ስለዚህ ያንቺ ልጅም አጥቶ ከተቸገረ ወንጀል ለመስራት - እንደሚገደድ አትጠርጥሪ! »

«አይምስልህ ጋሽ! እኔን ቢያጣ - እናት ብቻ ትቀርበታለች እንጂ መኖር አይቀርበትም። እዚያ ትምርት ቤት እናት የሌላቸው ልጆች እንደሚኖሩት ይኖራል! »

«እንደ ድሆች? »

«አዎ እንደ ድሆች፤ አሁንም ቢሆን ላንተ እንደ ጌቶች ልጆች የሚኖር መሰለህ እንጂ እንደ ድሆች ልጆች ነው የሚኖር። ደግሞ - የሀብታሞች ልጆች የድሆችን ልጆች ዘቅዝቀው እንደሚመለከቱ የድሆች ልጆች የሀብታሞችን ልጆች እንደሚጠሉ፥ ዛሬ ካንተ ሰማሁ እንጂ፥ እዚያ ትምርት ቤት ያሉት ልጆች ሁሉ «ሀብታም ድሀ» ሳይባባሉ ሁሉም እስበሳቸው እንደ ማር ሲላላሱ ነው የሚታዩ! »

«አይ እሱን እንኳዋ ተይው! ብቻ ‹እኔን ቢያጣ እንደ ድሆች ልጆች ይኖራል› ላልሽው ምንጊዜም ቢሆን በከፍተኛ ደረጃ መኖር ለለመደ ሰው ከዚያ ወርዶ በዝቅተኛ ደረጃ እንደ መኖር ከብዶ የሚታዬው ነገር ስለሌለ ከዚያ ለመዳን ‹የማይሰራው ክፉ ስራ ይኖራል› ብለሽ አታስቢ። መቸም - እንዳሳዘንሁሽ ይሰማኛል፤ ነገር ግን ለጊዜው እንዳታዝኝ ብዬ እንደሚጎዳሽ ከማውቀው ነገር ንድትጠነቀቂ አለመምከር ‹የወዳጅነት ተግባርን አለመፈጸም ነው› ብዬ ስለማምን ነው እንዲህ ጨክኘ የነገርሁሽና፥ ይቅርታ አድርጊልኝ» አለ በሻህ ይቅርታ ለመናውን በቃል ብቻ ሳይሆን ራሱን ትንሽ ዝቅ በማድረግ ጭምር ገልጾ።

«ለኔና ለልጄ የሚጠቅመን የመሰለህን መከርኸኝ እንጂ፥ ምን አደረግኸኝ ብዬ አዝናለሁ? ስለ መከርኸኝ አመሰግናለሁ እንጂ ጭራሽ አላዝንም» አለች ደመቀች። ነገር ግን ‹አላዘንሁም› ያለች ስታብል ካንገት በላይ ነው እንጂ እውነት አደለም። እንደ እውነቱስ ‹ልጅሽን ካቅሙ በላይ መኖር አስለምደሽው የለመደውን ሲያጣ ወደ ወንጀል ስራ እንዳያመራ ተጠነቀቂ› ሲላት ልክ፥ ‹ወንጀል ሲሰራ አዬሁት› እንዳላት ነበር እጅግ ጥልቅ አዘን የተሰማት።

ብቻ ያን በሻህ ያነለት በረዥሙ የነገራትን እንዲያ አያስረዝሙት እንጂ አዛዥ ተካልኝ በዬጊዜው ይነግሩዋት ስለ ነበረ እንደ አዲስ ነገር ምንም ያክል ባስብዋ አላቆየችውም፤ በሻህ ትቶዋት እንደ ሄደ አሳብዋ እሱን ሸኝቶ፥ ስትቸገርበት ወደ ቆዬችው ወደ ጫማውና ወደ ሸሚዙ ልክ መሆን አለመሆን ተመለሰ።

ከግብዣው ቀን በፊት ቅዳሜ ከቀትር በሁዋላ ሸሚዙንና ጫማውን ወስዳ ለልጅዋ ስትሰጠው እስዋ ሆነ ብላ እሱ ፊት በኒያ ቁጥሮች የተገዙት፥ ‹ልኬ አልሆኑም› ማለቱን ረስቶ የልክ መሆኑ አለመሆናቸው ነገር ጨርሶ አልተሳም። ከግብዣው በሁዋላም ተከስተ አንዳንድ እናቱ ‹አጎደለች› የሚለው ነገር ኖሮ እሁድ እስኪገናኙ ሲቸኩል እንደሚያደርገው ወደ ደጃዝማች አሰፋ ቤት ስልክ ደውሎ ባዛዥ በኩል እንዲያደርሳት ያስተላለፈው መልእክት አልነበረም። ስለዚህ እነዚህ ሁሉ የተገዙት እቃዎች ልኩ መሆናቸውን የሚያመለክቱ ናቸው። ይሁን እንጂ ይህ የስዋ ግምት ስለሆነ፥ ግምትዋን የሚያረጋግጥ ቃል ከሱ አፍ እስክትሰማ ልብዋን ማሳረፍ ባለመቻልዋ ከግብዣው በሁዋላ የሚመጣውን እሁድ በናፍቆት ስትጠባበቅ ሰነበተች።

በሻህ ዘለሌም ሆነ አዛዥ ተካልኝና ሌሎች ደመቀች ለልጅዋ የምታደርገውንም፥ የምትሆነውንም የሚያውቁ ሁሉ ልጆቻቸውን የሚወዱ እናቶች ለልጆቻቸው

ከሚያደርጉትና ከሚሆኑት ፍጹም የተለዩ ሆኖ እዬታያቸው ‹መልካም አደለም› በማለት ከመምከርም አልፈው ይፈርዱባት ነበር። እንገር ግን እንዲያ የሚፈርዱባት ተከስተ ለስዋ ምን መሆኑን በስዋ ቦታ ቆመው እስዋን ሆነው ባያዩት ነው!

ደመቀች ተከስተን የልጅነት ልጅዋ ስለሆነ ብቻ አልነበረም እንዲያ ስቅቅ ብላ ትወደው የነበር፤ ይህ ከሌሎች፥ የልጅ እናቶች ሁሉ ጋር የምትጋራው የልጅ እናቶች ሁሉ ባህሪ ነው። ከሱ ሌላ እንደ ጣእረ ሞት ከምትጠላውና ከምትፈራው ባልዋ ሽሽታ ስትሰደድ አብሮዋት የተሰደደ የስደት ጉዋደኛዋ ስለ ነበረ እወይዘሮ ጽጌ ቤት ግርድና ተቀጥራ ክፉ ተናግረው ሲያስከፉዋት አብሮዋት እዬተከፋ ሲመቱዋት አብሮዋት እዬታመመ የመከራዋ ሁሉ ተካፋይ ስለ ነበረ፥ ከሁሉም ይልቅ አገርዋ ለተወችው በታም ለምትወደው ነገር ሁሉ፥ ለዚያ ሳትጠግበው ለተቀማችው የህጻንነት ህይወትዋ መታሰቢያ ያን ሁሉ የምታይበት ህይወታዊ መስታወትዋ ስለ ነበረ፥ የወደእፊት ተስፋዋን ያሳረፈችበት ቀዳሚ ወይ ተከታይ የሌለው አለኝታዋ፥ ይህ ሁሉ ስለ ነበረ እንዲያ ስቅቅ ብላ የምትወደው!

አገርዋ ከህጻናት ጉዋደኞችዋ ጋር አፈር እየፈጨች ውሀ፥ እየተራጨች ብራብሮዎችን ወይ ወፎችን መስከ ለመስከ እያባረረች በጻገይ ወራት ላዲስ አመት፥ ራስዋን ጋሜ ከቁንጮ ተላጭታ፥ አንገትዋን ባሽክት ክንዶችዋን ባጨንቢላ እያጌጠች የንግጫና ያደይ አበባ ጉንጉንዋን ይዛ በየቤቱ እዬዞረች እዬዘፈነች ለመስቀል የደመራ ርምጦ እዬበላች የፍራጅ ወተት እዬጠጣች ይህን ሁሉ ኧረ ስንቱን ባገርዋ የህጻንቱን ህይወት የሚያስወድደውን ሁሉ እያደረገች በጣም ደስ ይላት የነበረውን ኑሮ፥ በትዝታ መልሳ አምጥታ ለተከስተ ብዙ ጊዜ እዬደጋገመች ስታወራው፥ ያን ግሩም የሆነ ህይወት ያን ገና ትንሽ ከመቅመስዋ ሳትጠግበው የተቀማችውን የህጻንነት ህይወት ያንጊዜ ከሱ ጋር እብውን የሚኖሩት ይመስላትና ደስታዋ ቅጥ መጠን ያጣ ይሆን ነበር! ያን በጣም ትወደው የነበረውንና ያጣችውን የተቀማችውን የህጻንነት ሕይወት ለተከስተ ብዙ ጊዜ፥ ሁልጊዜ፥ እዬደጋገመች ስታወራው ያንጊዜ እሱ እንደገና መልሳ እንድትኖረው ያደረጋት ይመስላትና እሱ ከቀሙዋት ቀምቶ አምጥቶ የሰጣት ይመስላትና ስቅቅ ብላ ትወደው ነበር! ተከስተ ለደመቀች የልጀንት ልጅዋ ብቻ ሳይሆን፥ የናት አባትዋና የጉዋደኞችዋን ያገርዋን፥ የህጻንነት ህይወትዋን የዚያን ሁሉ ፍቅር ሰብስቦ የያዘ የዚያ ሁሉ ማህደር የዚያ ሁሉ መንበር ስለሆነ ነበር፥ ፍቅርዋና ጭንቀትዋ ሌሎች የልጅ እናቶች ለልጆቻችወ ካላቸው ፍቅርና ጭንቀት ፍጹም ልዩ ሆኖ ሊታይ የነበረ!

## ምእራፍ ሀያ ሰባት

# ፍቅር እውር ነው አይናማ?

በተለምዶ አነጋገር፥ «ፍቅር እውር ነው» ይባላል። አንድ መልከ መልካም ሴት መልከ መጥፎነት ወንድ ወድዳ «አበድሁ» ያለች እንደሆነ «አሁን እገሊትን የመሰለች ውብ ሴት ያን - ውሻ በጨው የማይለክፈውን እገሌን ወድዳ ‹ልብሴን ልጣል› ያለች ምኑ አምሮዋት ነው? » ተብሎ የተጠዬቀ እንደ ሆነ፥ መልሱ «አ - ፍቅር እውር አደል? ያ ሆኖ ነው! » ማለት ነው። መልከ መልካም ወንድ መልከ ጥፉን ሴት የወደደ እንደሆነም ጥያቄውና መልሱ እኒያኑ የመሰሉ ናቸው። ነገር ግን ፍቅር እውር አደለም። ፍቅር አካላዊ አይን ማየት የማይችለውን ውስጣዊ ውበት፥ ውስጣዊ ጀግንነት ውስጣዊ ትልቅነት የሚያይ አይናማ ነው!

ደመቀች ጸሀይ በቁጥር መልክዋ በደም ግባትዋና በጠባይዋ ስሀ የማይወጣላት፥ ሁሉን አሙዋልቶ ያደላት፥ ውብ ወይዘሮ ነበረ። ያ ሁሉ ውበትዋ ብርቱ ችግር አድርሶባታል። ውብ ሆና የተፈጠረችበን ሌሊት እስክትረግም ድረስ አስመርሮዋአል! እደጃዝማች አሰፋ ተጫኔ በኤት አምስት አመት ስትኖር ከዚያ የሚበዛው ሰላም ሳታገኝ በብርቱ ጦርነት ያለፈችው ነበር። የዚያ ቤት ጎረምሶች አንዳንድ አዋቆች ጭምር ውበትዋ ይሉኝታን ሁሉ አስረስቶዋቸው ነውርን ሁሉ አስንቆዋቸው በውድ ባይሆንላቸው በግድ አሸነፍው ሊደፍሩዋት ያላደረጉት ጥረት ያላደረጉት ተጋድሎ አልነበረም። ከነሱ መሀከል የሚደነቁ ሽጋዎች ሎጋዎች፥ ጀግናዎች፥ ነበሩባቸው። ነገር ግን ደመቀች ሁሉንም ‹እንቢ› ብላ ሁሉም አሸንፋ እጅዋን ለማንም ባለመስጠትዋ ሴቶች ‹ወንድ የሚያስጠላ ክፉ ተያዥ ተቆራኝቶዋታል› እያሉ ሲያሙ፣ ወንዶች በፈንታቸው ‹መልክዋ ስላማረ፥ የቀኑባት ሴቶች ወንድ የሚያስጠላ አስማት አዙረውባት ነው!› እስከ ማለት ደርሰው ነበር።

ከደጃዝማች አሰፋ ቤት ጎረምሶች ጋር የነበረው ጦርነትም የክፉው መንፈስ ቁራኛና ያስማቱ አሜትም፥ በረድ እያሉ ከሄዱ በሁዋላ አንድ ቀን ባጋጣሚ ደመቀች፥ ከበሻህ ዘለሌ ጋር ተገናኘች። በሻህ ሽጋም፥ ሎጋም አልነበር፤ ጀግናም አይመስል!

በሻህ፣ ምንጊዜም ቢሆን፥ በቁጥር መልክ ከጥርሱና ከጠጉሩ በቀር «ምን ያምር! » የሚባል ነገር ነግሮት አያውቅ። ከንፈሮቹ ትንሽ ወፈር አፍንጫው ሰፋና አጠር

በለው፥ ክብብ ካለ ፊቱ በላይ ጎልተው ከሚታዩት የጉንጮቹ አጥንቶችና ከቅንድቦቹ መሀከል ጎድጎድ ባለ ቦታ እንደ ተቀመጡ ፈርጦች የሚፍለቀለቁ ትናንሽ አይኖቹ የተፈጥሮ ብልህነቱን ያሳያሉ። ተከክለው የተሰኩ ነጫጭ ፈርጦች የመሰሉ ጥርሶቹ እህል አስነክቶዋቸው እንደማያውቅ ሁሉ ንጣታቸው ያዩዋቸውን ሁሉ የሚያስደንቁ ናቸው! ዞማ ጠጉሩ ሰብስበው በራስ እንዳሸከሙት የጥቁር ሀር ነዶ ብዛቱና አለሳለሱ፥ ‹እስቲ እንየው እስቲ እንካው!› የሚሉት ግሩም ነበር! እሱም ከጥርሱ ሌላ ያለው መልክ ጠጉሩ መሆኑን አውቆ፣ ባጫጭር ጊዜ እያስከረከመ ይበልጥ፥ እያሳመረ ተጨንቆ፥ ተጠቦ ነበር የሚይዘው። ከወገቡ በላይ ደረቱና ትከሻዎቹ ሰፋ ሰፋ በለው ከወገቡ በታች እንደ ዳሌው ያሉ አካላቱ ሽብልል ብለው ያንበሳን ቅጥና ግርማ ይሰጡት ነበር! በኒያ አንሳር እንዳጠሩዋቸው ጥምድ ገንበዛን አረጎች የተጠማዘዙና የተወላገዱ እግሮቹ ‹እድሜ፥ ለቦልቦሌ ሱሪ እንጂ› እሱ ባይሸፍናቸው ለማየት እንዴት ባስጠሉ ነበር! ቢሆንም ታዲያ፥ ሁሉንም ባንድነት አጠቃሎ ሲያዩት ጉርድርድ ያለ፥ ‹ወንዳወንድ› የሚሉትና ደስ የሚል እንጂ ‹መጥፎ› የሚባል አልነበረም። በዚያ ላይ ልብስ መርጦ የሚለብስና ለሰውነቱ አጥብቆ የሚጠነቀቅ ጌጥ ወዳጅ ነበር። እንዲያውም ከጣሊያኑ ጌታው ጋር ተጣልቶ ስራውን የለቀቀ ጌጥ በመውደዱ ነበር። ብቻ ያ ሁሉ፥ ከደመቀች ጋር ከመገናኘታቸው በፊት የውስጥና የጫካ አርበኛ ከመሆኑ በፊት፥ ‹የጨለማው ንጉስ› እዬተባለ አዲስ አበባን ያስጨንቅ የነበረ ከመሆኑም በፊት ከዚያ ሁሉ በፊት ያስራ ስምንትና ያስራ ዘጠኝ አመት ጎረምሳ እስከ ነበረበት ጊዘ ድረስ ነው።

ከዚያ በሁዋላ ይልቁንም በከተማ ሽፍታነቱ ድል ሆኖ ፖሊስ ጣቢያ ታስሮ ከወጣ በሁዋላ ሌላ በሻህ ሆነ! ተስፋ ባደረገው ነጻ ስራተ ማህበር ፈንታ ሌላ ስራተ - ማህበር ለዚያ ፍጹም ተጻራሪ የሆነ ስራተ - ማህበር በመመስረቱ ያልመው የነበረው ነጻ ስራተ - ማህበር እውን ሳይሆን በመቅረቱና እንዲያ ያደረጉትን ባለስልጣኖች ከተባባሪዎቻችወ ጋር ለመቅጣት በጀመረው ጦርነት ድል በመመታቱ ይህ፥ ሁሉ በመሆኑ አዝኖ ተበሳጭቶ፥ ለሰውነቱ ሆነ ለልብሱ ጥንቃቄ ማድረግን ርግፍ አድርጎ የተወ ጌጥ የሚሉትን ነገር እንኩዋንስ በራሱ፥ በሌሎች ላይ ሲያይ የሚጠላ በሻህ ሆነ። ራሱን ገና በንሱ ስለሚላጨው ያ የተላጨው ራሱ በጢም በጎፈር ፊቱ ተውጦ ሲታይ አንገቱ ራስ የሌለው ፊት የተሸከመ ይመስል ነበር። ከተለያዩ ሰዎች እንደ ተዋሳቸው ወይም፣ እንደ ለመናቸው ሁሉ የተለያዩ፥ መጠንና ቀለም ያላቸው በስልቻ ታስረው ካደሩበት የወጣ፥ እንደሚለብሳቸው ሁሉ የተጨማደዱ ሱሪ፥ ሸሚዝና፥ ባለቀበቱ ካኪ ኮቱን ለብሶ፥ ሁሉንም በኮቱ ቀበቱ ከርፈፍ አድርጎ ታጥቆ፥ እንኩዋንስ ቀለም ቡርሽ ነክቶት የሚያውቅ ከብዳድ ጫማውን አድርጎ፥ ያን እዬጎተተ ሲሄድ፥ ለማያውቁት ሁሉ

ሞኝ ያለዚያም የመጨረሻው ሰነፍ ይመስል ነበር። ባጠቃላይ አለባበሱንና የሰውነት ሁኔታ ሲያዩት እንኳዋንስ ስቦ ሊያቀርብ ገፍትሮ የሚያርቅ ነበር! ነገር ግን ለደመቀች እንዲያ አልነበረም። ለደመቀች ገፍትሮ የሚያርቅ ሳይሆን ስቦ የሚያቀርብ ብቻም ሳይሆን ስቦ ከሱ ጋር የሚያዋህድ ብርቱ ምህስብ ያለው ነበር! ለደመቀች የሚታያት፥ በዚያ የጢም ጫካ በዋጠው ፊትና የተጨማደደ ውጥንቅጥ ልብስ በለበሰ ሰውነት ውስጥ የተሸሸገ ሌላ በሻህ ነበር! ፍቅር አይናማ አይደል? ስለዚህ ያን፥ የጢም ጫካ የዋጠውን ፊትና የተጨማደደ ውጥንቅጥ ልብስ የለበሰውን ሰውነት ዘልቆ እዚያ ውስጥ የተሸሸገውን በሻህ ሽጋውን ሎጋውን፥ ደማሙን፥ ጀግናውን፥ አዋቂውን፥ ደጉን በሻህ ነበር የሚያሳያት!

ደመቀች፥ በበሻህ ፍቅር የታሰረችበት መንገድ ሌሎች ሴቶች ከወንዶች ጋር በፍቅር ከሚተሳሰሩበት መንገድ ፍጹም የተለዩ ነበር። ሴቶችና ወንዶች ገና ሲተያዩ በመልካቸው በቁመናቸው ወይ፣ በሌላ ሁኔታቸው የተፈቃቀዱ እንደ ሆነ፥ ሁለቱም ወገኖች መፈቃቀዳቸውን ሲያውቁ የተሻለ - አቀራርበው የሚያስተዋውቁዋቸው ተከታይ ርምጃዎች እያደረጉ መጨረሻ የፍቅር ጉዋደኞች እስኪሆኑ ወይም፥ በፍቅር እስኪተሳሰሩ ይብዛም ይነስ ጊዜ መውሰዱ አይቀርም። ደመቀች ለበሻህ የነበራት ፍቅር ግን ተፈጥሮ ተወልዶ አድጎ፥ ልብዋን ማርኮ እስረኛው ለማድረግ የፈቃድዋም ያሳብዋም ገዥ ለመሆን የበቃው ባንድ ቀን ነበር!

ደመቀች፥ በበሻህ ፍቅር የታሰረችበትን መንገድ ሌሎች ሴቶች ወንዶችን ከሚወዱበት የተለዩ የሚያደርገው ሌላው መንገድ፥ እንደ ሌሎች ሴቶች መልኩን ቁመናውን ወይም ሌላ ሁኔታውን በማየት ሳይሆን ታሪኩን በመስማት ብቻ መውደድዋ፥ ታሪኩን በመስማት ብቻ ተማርካ የፍቅር እስረኛው መሆንዋ ነው!

አንድ ቀን አዝማሪው ውቤ ወደ አዛዥ ተካልኝ ቤት ሄዶ ደመቀችም በነበረችበ ሲጫወት በጭዋታው ሳቢያ የበሻህን ታሪክ፥ በረዥሙ ተረከላቸው። መቸም በሻህን አይተው ታሪኩን ለሚሰሙ ሁሉ፥ ‹ያ ሰው ለዚያ ታሪክ ባለቤት ይሆናል› ብሎ ለማመን የሚያዳግት ነው። ነገር ግን ፋሽስቶች ኢትዮጵያን ወርረው በያዙ ጊዜ የውስጥ አርበኛም የጫካ አርበኛም እዬሆነ ይሰራው፥ ስለ ነበረው የሚያስደንቅ የጀግንነት ስራ የገጠሙለት የነበሩት የውዳሴ ግጥሞች በሻህ የታሪኩ ባለቤት ለመሆን ለጥርጥር ቦታ ይሰጡ፥ አይነተኛ ምስክሮቹ ነበሩ። ስለዚህ አዝማሪው ውቤ፥ በሻህ የውስጥ አርበኛ ሆኖ ፋሽስቶችን የሚያደርጉትን አሳቶ፥ ያስጨንቃቸው የነበረ ከመሆኑ ሌላ በተለይ የጫካ አርበኛ በነበረ ጊዜ በዬቦታውና በዬጊዜው ይሰራው የነበረውን አስደናቂ

የጀግንነት ስራ ይገጠሙለት ከነበሩት የውዳሴ ግጥሞች ጋር እያዛመደ እያዋደደ፥ ሲተርክላቸው፥ ያ ታሪክ እያንዳንዱ የጀግንነት ስራ ከሰሪው ጋር መልሶ አምጥቶ ያን ጊዜ፥ እዚያ እፊታቸው በገሀድ የሚሰራ አስመስሎ አሳይቶዋቸው፥ ምንም እንኳዋ አዛዥ ሽማግሌ ደመቀች ሴት ቢሆኑ፥ ሁለቱንም ሲቃ ይዞዋቸው ነሸጦዋቸው ይንቆራጠጡ ጀመር!

ከዚያ ፋሽስቶች ድል ተመትተው ሄደው የኢትዮጵያ፥ መንግሥት ወደ ስልጣኑ እንደ ተመለሰ የመንግስት ሹሞችና ሰራተኞች ህዝብ ሊያገለግሉበት ባደራ የተቀበሉትን ስልጣን ለራሳቸው መገልገያና ግል ጥቅማቸው ማዳበሪያ እንዳደረጉት ሲመለከት ተበሳጭቶ፥ ተቆጥቶ እነሱን ለመቅጣት ስራውንም ቤት ንብረቱንም ጣጥሎ ንጉሱ ከነሰራዊታቸው ባሉበት ባዲስ አበባ ከተማ ሸፍቶ፥ ‹የጨለማው ንጉስ› እዬተባለ ያደርገው የነበረውን ምትሀታዊ ስራ ተረከላቸው። ያንግዜ ‹የጨለማው ንጉስ› ተብሎ የከተማውን ህዝብ ሲያንቀጠቅጥና የፖሊሱን ሰራዊት ይይዘውን አሳጥቶ ሲያስጨንቅ እንደ ነበረ ሲተርክላቸው ሁለቱም ያን ታሪክ በተመስጦ እያዳመጡ፥ ስለ ልበ ሙሉ ወንድነቱና ስለ ቆራጥነቱ የተሰማቸውን ጥልቅ አድናቆት የሚገልጹባቸው ቃላት አጥተው የተሰማቸውን ጥልቅ አድናቆት የሚገልጹባቸው ቃላት አጥተው ሲቸገሩ ከፊታቸው፥ ከሁለመናቸው፥ እንዲያው ከሁኔታቸው ሁሉ ይታይ ነበር!

ከዚያ፥ ላላማው ተባባሪ ሊሆኑ ምለው የተጠጉት ሰዎች ማላቸውን አፍርሰው እቅዱን ስላሰናከሉበት አሳቡ ሳይሳካለት መቅረቱንና ድል መሆኑን ሲያይ፣ ኩሩ ልቡ ቆስሎ አንጀቱ ተቆርጦ፥ ጌጥ ከሚባል ነገር ሁሉ ተለይቶ እንደሚያዩት ራሱን እንደ ተላጨና የሸፍታነት ልብሱን እንደ ለበሰ፥ አዘነተኛ ሆኖ የሚኖር መሆኑን እየተከዘ ባዘንተኛ ድምጽ ሲተርክላቸው ደመቀች ልብዋ ተመትቶ ወዲያው አይኖችዋን የሞላው እንባ በፊትዋ ይፈስ ጀመር!

ከዚያ በሻህ ከዚያ ሁሉ ጀግንነት ጋር ደግሞ፥ በዚያ ሁሉ ጀግንነቱ ላይ የተራራቀ አዋቂ ቸር፥ ሩህሩህ መሆኑን ያን ሁሉ ተረት እንጂ እውነት የማይመስለውን የበሻህን ጌጠኛ ታሪክ የባለቅኔዎች የግል ሀብት በሆነ የሚያምር ቁዋንቁዋቸው ይበልጥ እያስጌጠ፥ ሲተርክላቸው አዛዥ ተካልኝ ‹የጨለማው ንጉስ› ያንቀጠቅጣቸው ከነበሩት ያዲስ አበባ ከተማ ነዋሪዎች አንዱ ስለ ነበሩ፥ ያ ስሙ ከሩቅ በወሬ፥ የሚያንቀጠቅጠው፣ ‹የጨለማው ንጉስ› እሱ በሻህ መሆኑን ባወቁ ጊዜ ተገርመው ተደምመው አላበቃ አሉ! ደመቀችን፥ ያ የነለት የሰማችው የበሻህ ታሪክ ከማስደነቅም

አልፎ ልብዋን ማረከው! ከዚያ ቀን ጀምሮ፥ እስከዚያ ጊዜ ድረስ ገዥ አጥቶ፥ ባዶውን ይኖር በነበረ ልብዋ ውስጥ ባሻህ ሲገዛ እንዲኖር አደረገው።

መቸም ሴት ጀግና መውደድዋ የታወቀ ነው። ሴት ከፈሪ ሽጋ ጀግና ፉንጋ ትወዳለች። የጦር ሜዳ ጀግና ብቻ ሳይሆን በማናቸው፥ እንዶች በሚስለፉበት ነገር፥ ከሁሉ በላይ የሆነ ሁሉን አሸናፊ የሆነ ጀግና፥ ትወዳለች። በዘይቤ፥ አነጋገር ‹እገሌ ወንድ ነው!› ሲባል ‹ጀግና ነው› ማለት ስለሆነና እንዲያም ማለት ‹ጀግና ያልሆነ ወንድ አዶለም!› ማለት ስለሚመስል የወንድነት መለኪያው የወንድነት መስፈሪያ ቁናው ጀግንነት ሆኖ በመታየቱ ሴት ከመልከ መልካም ወንድ ይልቅ ጀግና ትወዳለች። ደመቀች ደግሞ፥ ለበሻህ የነበራት ፍቅር ከዚያም የላቀ ከዚያም የጠለቀ ነበር።

ደመቀች ባልዋን ጠልታ፥ ከባልዋ ሸሽታ ከጎጃም ወደ አዲስ አበባ በተሰደደችበት የደጃዝማች አሰፋ ቤት ወንዶች ከበው ሲያባርሩዋት መድረሻ ሲያሳጥዋት እንዳመትባል ፍሪዳ፥ ተቀራምተው ሊበሉዋት የፈልጉ መስለው ታዩዋትና ወንድ መጥላት ብቻ ሳይሆን ወንድ ትፈራ ጀመር። እደጃዝማች አሰፋ በኢት የመቤትዋን ክፉ አመልና የጊዜ ወሰን የሌለው ከባድ ስራችውን ጥርስዋን ነክሳና ችላ ትኖር የነበረ ከዚያ የወጣች እንደሆነ ባልዋ ወይም ሌሎች ወንዶች እንደማይለቁዋት ስላወቀች ወንድ በመፍራት ነእብር። ሁዋላ የፈራችው ደረሰ። ከደጃዝማች አሰፋ ቤት ወጣች። የያዘችው አዲስ ስራ ፍልውሀ ህክምና ቤት ስለ ነበረ፥ በፍልውሀና በገዳም ሰፈር መሀከል በቀን ሁለት ጊዜ ጥዋትና ማታ - ትመለሳለች። ታዲያ መቼስ፥ ሁልጊዜ ቀን ሙሉ አይሆን! አንድ ጎደሎ ቀን፥ ይልቁንም ማታ ወደ ቤት ቤትዋ ስትመለስ፥ ባልዋ ወይም አንዱ ቤት አዳኝ ወንድ አድብቶ፣ ቢያንቃትስ? ያ አገርዋን አስለቅቆ ያሰደዳት፥ ያ ስትፈራው የኖረች ቢደርስባትስ? ይህ አሳብ ተለይቶዋት፥ የማያውቅ አብሮዋት የሚኖር ሆነና ልብዋ ረግቶ፥ መንፈስዋ ጸጥታ አግኝቶ የማትኖር ሁልጊዜ በፍራት የምትኖር አደረጋት! በኑሮዋ የምትተማመንበት የሌላት ነፍስዋ የምትተማመንበት አጥታ እንደ ፈራች እንደ ተጨነቀች የምትኖር አደረጋት። ስለዚህ አዝማሪው ውቤ ስለ በሻህ ጀግንነት፥ ስለ ትልቅነቱ፥ ስለ ደግነቱና፥ ስለ ሌላው አስደናቂ ምግባሩ ሁሉ የተረከውን ስትሰማና ባልሰራችው ወንጀል ፖሊስ ጣቢያ ታስራ ለተሰቃዩችበት ካሳ እንዲሆናት ጅቡቲ ድረስ ተጉዞ የመቤትዋን ወርቅ ከዘረፉት ሰዎች ጋር ተከራክሮ ሶስት ሽህ ብር አምጥቶ እንድትቀበለው አጥብቆ መለመኑ አዝማሪው ውቤ የተረከውን ሁሉ ስላረጋገጠላት፥ ያ ጀግና ያ ትልቅ፥ ያ ደግ፥ በሻህ ‹ከምትኖሪበት ፍራት ነጻ አወጣሻለሁ› እንዳላት ሁሉ፥ ‹ነፍስሽ ስትፈልገው የኖረውችው መተማመኛ ያውልሽ!› እንደ ተባለች ሁሉ ለሱ

በፈቃድዋ ባሳብዋ በሁለመናዋ ላይ ገዥ እንዲሆን አደረገች! ወንድ ጠልታ ከወንድ ስትሸሽ የኖረችዋ እሱ ወንድ እንዳደለ ሁሉ እሱን ወደደች! ብዙ ዘጋዎችና ሎጋዎች ሲያባርሩዋት ሁሉንም ጠልታ፥ ሁሉንም፣ ፈርታ፥ ስትሸሽ የኖረችዋ ሰውነቱን አጎሳቁሎ ባለባበሱም ሆነ በሌላ ሁኔታው ሁሉ አልባሌ መስሎ የሚታየውን እንደ ሌሎች በማባረር ፈንታ ስትከተለው መሸሽ የሚፈልገውን በሻህን» እጉም! የሙጥኝ! » አለች!

‹ጀግና ስለሆነ ከምፈራው ሁሉ ያድነኛል፥ ትልቅ ስለሆነ እሱን መውደዴ ያኮራኛል ደግ፥ ስለሆነ ስቸገር ይረዳኛል ቸር ስለሆነ ሳጣ፥ ይሰጠኛል› ብላ አስባ አሰላስላ አደለም የወደደችው። እንዲያው ታሪኩን ስትሰማና ለስዋ ሲል ጅቡቲ ድረስ ደክሞ ያደረገውን ስታይ ልብዋ ተማርኮ ወንድ ስትጠላ፥ ወንድ ስትፈራ የኖረችዋ የፍቅርዋ ሀያልነት በሌሎች ወንዶች ዘንድ ስትጠላውና ስትፈራው የኖረችው ሁሉ እሱ ዘንድ የሌለ አስመስሎ አሳያትና እሱን ወደደች!

እሱም ይወዳታል። እስዋን እንደሚወድ፥ በህይወቱ ሌላ ሴት ወዶ አያውቅም። ስለሚወዳት ሴት ውበት ደም ግባትና፥ ጠባይ ባሳቡ ስሎ፥ መስሎ ያስቀመጠውን ሁሉ በስዋ ብቻ ስለሚያይ ከመጠን ያለፈ ይወዳታል። ነገር ግን አስቀድሞ ያሰረው ቃልኪዳን የማለው ማላ ስለ ነበረው፥ በቃል ኪዳኑና በስዋ ፍቅር መሀከል ተወጥሮ ይጨነቅ ነበር። እንደ መናኝ ሰውነቱን አጎሳቁሎ ምቾትን ድሎትን፥ ጌጥን ሁሉ «ወዲያ» ብሎ ለቆመለት አላማ በገባው ቃል ኪዳንና ለስዋ ነበረው ጽኑ ፍቅር መሀከል ከቀኝ ከግራ ተወጥሮ ይጨነቅ ነበር። ፍቅሩን ገልጾ የግብረ - ዝሙት ጉዋደኛዋ እንዳያደርጋት ክብሩን ቢነኩበት የማይወደውን ያክል የሌሎችን ክብር ይልቁንም ለስዋ ክብር አጥብቆ ስለሚጠነቀቅ ያ መቸም፥ የማይከጅለው ባሳቡ ውስጥ ቦታ የሌለው ነው። ለጋብቻ እንዳይጠይቃት ቃል ኪዳኑን ማፍረስ ሞት መስሎ ታዬው። ቃል ኪዳኑን አክብሮ ትቶዋት እንዳይሂድ ከስዋ ጋር ያስተሳሰረው የፍቅር ማሰሪያ ሊፈታው የማይችል ውትብትብ ሊቆርጠው የማይችል ብርቱ ሆነበት። ስለዚህ ከስዋ፥ መራቅ አይችል፥ ወይ እንድያውን ተጠግቶ፣ የሱም የስዋም ልቦች ያን ያክል ታመው ሲያለቅሱ እንባቸውን አያደርቅ የሚያደርገው ቅጡ ጠፍቶት ሲጨነቅ ነበር።

በሻህ ምንም እንኩዋ አቶ ማንደፍሮ፥ ‹የልጅ አሳብ፥ ወይም የጨነቀው አዋቂ ሰው ምኞት› ያሉት እቅዱ ሳይሳካለት ቀርቶ ድል ቢሆን ድል መሆኑን አምኖ ስላልተቀበለው ልቡ እንደ ተንጠለጠለ እንዲሁ በቁዋፍ ላይ ነበር የሚኖር። ያ የውስጥ አርበኛ የጫካ አርበኛ የከተማ ሽፍታ ሆኖ የተዋጋለት ነጻነት ባለመገኘቱ ልቡ ሹሞችና ሰራተኞች ጥቅም በመዋል ፈንታ ለልማትዋና ለህዝብዋ የኑሮ እድገት የሚውልበት

ነሳነት እስኪያገኝ ልቡ ሰላም ሳያገኝ እንዲሁ እንደ ተንጠለጠለ በቁዋፍ ላይ ነበር የሚኖር። እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ የዘር አረግ ስቦና ልዩ ጥቅም ይዞ ስለ ቀረበ ሳይሆን ችሎታው የሚፈቅድለትን ስራ ሰርቶ የመኖር ብሄራዊ መብቱ የሚጠብቅበት ‹ይጠቅማል› ብሎ ያሰበውን በቃል ይሁን በጽሑፍ ለሌሎች የማካፈልና የሌሎችን የመካፈል ነጻእንቱ የሚከበርበት ፍትርት በዋጋ ሳይሆን በነጻ የሚገኝበት ስራተ - ማህበር እንዲመሰረት በጀመረው ጥርነት ድል መሆኑን አምኖ ስላልተቀበለው ልቡ እንደ ተንጠለጠለ በቁዋፍ ላይ ነበር የሚኖር። የስም ብቻ ሳይሆን በግብር ተተርጉሞ የሚታይ የውነተኛ ነጻነት ያለበት ስራተ - ማህበር እስኪመሰረት ድረ በጀመረው ጦርነት መሸነፉን የተመቸ ጊዜ እስኪገኝ ሀይል እስኪገኝ ድረስ እንደ ጊዜያዊ ማፈግፈግ እንደ ጊዜያዊ መሸሽ፥ አድርጎ ማየት እንጂ እንደ መጨረሻ ድል አድርጎ አምኖ ስላልተቀበለው ልቡ እንደ ተንጠለጠለ በቁዋፍ ላይ ነበር የሚኖር። ባእምሮው አስቦ፥ አሰላስሎ፥ ያ የተመቸ ጊዜ ወይም ሀይል እንዴት ከየት መቸ፥ እንደሚገኝ አያውቅም። ነገር ግን ትክክል በሆነ መሰረት ላይ ያልተገነባን ሁሉ ገፍቶ፥ ለመጣል ትንሽ ሀይል ብቻ የሚበቃ መሆኑ የታወቀ ስለሆነና ይዋል ይደር እንጂ፥ እንዲያ ያለ ሀይል አንድ ቀን መፈጠሩ የማይቀር መሆኑን ደመ ነፍሱ እዬነገረው ያ፥ የነጻነትን ስም ብቻ የያዘ ስራተ - ማህበር በውነተኛ ነጻ ስራተ - ማህበር እስኪለወጥ ድረስ፥ ለዚያ አንድ ቀን ለሚፈጠረው ሀይል መሪ ባይሆን ተባባሪ ሆኖ መታገልን መጋደልን በዚች ምድር ምንም ነገር የማይለውጠው፥ የህይወቱ የህልውናው አይነተኛ አላማ አድርጎ የቆመለት ነበር! ስለዚህ፥ ምሽት አግብቶ፥ ትዳር መስርቶ መኖር ቀዋሚ ስራ፥ እንኩዋ መያዝ ያን አላማውን የሚያሰናክሉበት ላላማው ተጻራሪዎች ሆነው ታይተውት በምሽት በልጅ፥ በንብረትና በምቾት ሳይታሰር ለሚጠብቀው ትልግ ለተጋድሎው ነጻ ሆኖ ደረቅ ጦር ሆኖ ለመቀመጥ ወስኖ ለምግብ ይሁን ለመኖሪያ ሳያስብ ካቶ ማንደፍሮ ጋር በነጻ እዬኖረ በዬወሩ ከሚከፍሉት አንድ መቶ አምሳ ብር - የሚረባ ልብስ እንኩዋ ‹ልልበስ› ሳይል - የሚበዛውን ለችግረኞች እያካፈለ እንዲሁ የመሽ - አዳሪ ያድሮ ሂያጅ መንገደኛ ኑሮ ይኖር ነበር!

የሰው ህይወት፥ የሰው ኑሮ ባለቤት ብቻ ባሰበውና በመራው መንገድ የሚሄድ ቢሆን እንዴት መልካም እንዴትስ ቀላል በሆነ ነበር! ብቻ እንዲያ ሆኖ አያውቅም። ሰው በሚኖርበት አለም የሚኖር ሰው ሁሉ ህይወቱ ወይም ኑሮው በውድም በግድም ከሌሎች ይህወት ወይም ኑሮ ጋር ተገናኝቶ እዬተጋጨ እዬተፋጨ፥ ከዚያ የሚፈጠረውን አዳዲስ ኑሮ፥ አዳዲስ ህይወት እዬኖረ እስከ ጉዞው መጨረሻ መሄድ አለበት! በሻህ ለህይወቱ የቀዬሰው መንገድ፥ ያ ለውነተኛ ነጻነት ታግሎ ተጋድሎ፥

ቢቀናው ድል ተቀዳጅቶ ለቆመለት አላማ መብቃት ባይቀናው መሞት እንዴት ቀላል ነበር! ነገር ግን ሳያስበው፥ ባጋጣሚ ከደመቀች ጋር ተገናኘና፥ ህይወቱ ከህይወትዋ ጋር እንደማይፈታ ሆኖ ተሳስሮ ተቆራኝቶ የሚያደርገው ቅጡ ጠፍቶት ይቸገር ነበር።

አንድ ቀን፥ ከረዥም ጊዜ በሁዋላ ከነበረበት ጭንቅ መውጫ መንገድ የሚያሳዬው ስለ መሰለው ወዳጁን፥ አዝማሪው ውቤን ጋብዞ ወዳንድ የመጠጥ ቤት ወሰደና ገልል ባለ ቦታ ለብቻ ተቀምጠው እዬጠጡ ምስጢሩን አካፈለው።

«አየ ጉድ፥ አያ! አላምጨ፥ መጥጨ የጣልሁትን ምጣጭ ነው - እንደገና አዲስ አድርገህ የምታጎርሰኝ? » አለ አዝማሪው ውቤ፥ እንደ መሳቅ ብሎ ጉዋደኛውን በቀልድ አይን እያዬ።

«እንዴት? ምን ማለትህ ነው? »

«ካወቅሁት ዘመን የለውማ! »

«ለሌላ ሰው ቀርቶ ለስዋ እንኩዋ ተንፍሸው የማላውቀውን አንተ እንዴት አወቅኸው? »

«ደብተራነቴን አትርሳ! » አለ አዝማሪዉ፥ ካሽሙር ፈገግታ ጋር።

«ጥንቆላ ነው? »

«አ - ይ! ጥንቆላ እንኩዋ ከኛ በታች ላሉ፥ ተራ ደብተሮች ነው። የኛ፥ የሊቃውንቱ ስምር፥ ከዚያ በላይ ወደ ንባቡና እደ ትርጉዋሜው ነው።»

«እኮ እንዴት ያለ ንባብና ትርጉዋሜ ነው - ማንም ያልነገረህን የሰው ምስጢር አውቀህ እንድትገኝ ያደረገህ? »

« - እስዋ ጭምር አብረን በምንገኝበት ጊዜ ሁሉ፥ እንደ ተመለከትሁት በጣም፥ የምትወዳት መሆንህ፥ ባይሆን በፊትህ፥ በከንፈርህ በሁለመናህ ተጽፎ ይታያል። ታዲያ፥ ሊቅ እንደ መሆኔ ያን አንብቦ መተርጎም የተሰማራሁበት ሙያየ ነው» አለ አዝማሪው አሁንም ባሽሙር አስተያየት በሻህን የጎድን እያዬ።

«እሺ፥ ያንተ ሊቅነት እንዲህ እንደምትነፋው ጉራህ ያላዬኸውንና ያልሰማኸውን እስከ ማወቅ የሚያደርስ ከሆነ ጥሩ ነው። ያለዚያም ይኸው አሁን ነገርሁህ። አሁን ቀልዱ ይብቃህና ምን ማድረግ እንደሚሻለኝ እስቲ - ምከረኝ። አዬህ? ደመቀችን

መውደድ ከጀመርሁ ብዙ ጊዜ ሆኖዋል። መጀመሪያ ከመልከ ቀና ሴቶች ጋር እዬተጨዋወትሁ ጊዜ ማሳለፍ ደስ ስለሚለኝ ባጋጣሚ ከስዋ ጋር ከተዋወቅን በሁዋላ በዚያው አይነት ነበር የቀረብሁዋት። ነገር ግን ግንኙነታችነን ስናዘወትር ስለስዋ እዬተሰማኝ የሄደው ስሜት እዬተጨዋወትሁ ጊዜ የማሳልፍበት መሆኑ ቀረና እያደር ሌላ ሆነ። እያደር ወደ ጽኑ ፍቅር እዬተለወጠ ሄደ! እያደር ታምሜ የማልድነው በሽታ እዬሆነ ሄደ! » አለ፥ አካላውያን አይኖቹን ሳያረግብ አሻግሮ እማዶው ጣራ ላይ ተክሎ ባይነ - ህሊናው ደመቀችን እያዬ።

«አባባ አዛዥ ቤት አንዳንድ ጊዜ አብረን አንዳንድ ጊዜም ለብቻዬ ከምንገናኘው ሌላ ሁለታችሁ ብቻ አዘውትራችሁ የምትገናኙ መሆናችሁን አላውቅም ነበርኮ! »

«ሁለት አመት ‹ፍኖተ ድህነት› ትምርት ቤት የማታ ትምርትዋን ተምራ እስክትወጣ አንድ ማታ እንኩዋ ተለይቻት አላውቅም ነበር። ‹ማታ ብቻየን ወደ ቤቴ መመለስ እፈራለሁ› ስላለች፥ ሁልጊዜ እቤትዋ የማደርሳት እኔ ነበርሁ። ከክፍል በምትወጣበት ጊዜ ያልደረስሁላት እንደ ሆነ አጥሩን ሳትወጣ፥ እውስጥ እንዳለች ነበር የምትጠብቀኝ። ያንጊዜ ነው ተጠግቼ ያወቅሁትና - እንዲህ ባለ ጣጣ ውስጥ የገባሁ! »

«እንደስዋ ያለች፥ ጎበዙን ሁሉ ያሸነፈች ጀግና ድል አድርጎ መማረክ መታደል ይባላል እንጂ እጣጣ ውስጥ መግባት ይባላል? »

«እውነት ነው፣ ለሚፈልጉት መታደል ነው። ለኔ ግን አደለም። ለኔ - እንጃ፥ ከጣጣም የበሳ ነው። እኔ ከስዋ ጋር ከፉ አጋጣሚ እንዲህ አድርጎ እስኪያቆራኘኝ ድረስ ለሴት እምብዛም ተጨንቄ አላውቅም። ርግጥ አንድ እንደ መሆኔ፥ «ወደ ሴት ሄጄ አላውቅም፥ ወይም ከሴት ጋር ጉዋደኝነት ኖሮኝ አያውቅም» ብዬ አልምልም። ቅድም እንዳልሁህ የመልከ ቀና ሴቶችን ጉዋደኝነትና ጭዋታ እወዳለሁ። ብቻ ጉዋደኝነታቸውን የምፈልገው ለጭዋታ ያክል ነው። ከጭዋታ ደረጃ አልፌ የግብረ ስጋ ጉዋደኞቼ የማደርጋቸው አልፎ አልፎ ከስንት አንድ ናቸው! በዚህ - ‹ራስህን አሞገስህ› አትበለኝና ባጣም ቁጥብ ነበርሁ። አሁን ግን በስዋ ምክንያት - አመንዝራ ልሆን ነው፥ ጋሽ ውቤ! »

«እንዴት! እባክህ? »

«ደመቀች ግሩም የሆነች ልጅ ናት። ብቻዋን አግኝተህ አነጋግረሀት ታውቃለህ? » አለ በሻህ ለተጠዬቀው መልስ በመስጠት ፈንታ።

«እንዴታ! ደመቀች እንደ እቴ በጣም የማውቃትና የምወዳት ልጅ ናት። አሁን አንተ አንዳልኸው ያለ እውቀት ግን የለኝም። መቸም የሚበዛውን ጊዜ የምንገናኝ እናባባ አዛዥ ባሉበት ነው።»

«እንኩዋንስ ‹በምትፈራቸውና በምታከብራቸው›፥ በናባባ አዛዥ ፊት በርከት ካሉ፥ በሌሎችም ፊት ቢሆን ብዙ አትናገርም። ከመናገር ይልቅ ሌሎች የሚናገሩትን መስማት ትወዳለች። ብቻችሁን ሆናችሁ ተዝናንታች ስታጭውትህ ግን ሌላ ናት። ለዛ ብቻ ናት! ከውበትና ከጭዋታ አሳማሪነትዋ ሌላ ደግሞ እያደር ብልህነትውና ስታይ፥ መውደድ ብቻ ሳይሆን ከብልህ ታከብራታለህ! ተምራ አንብባ ወይም ካዋቂዎች ጋር የምትኖር በመሆንዋ ከነሱ ሰምታ ሳይሆን እንዲሁ ፈጣሪ እንደ መልከዋ የአእምሮ ብልህነትን ጭምር ስላደላት ነው! ደመቀች ያካልና የመንፈስ ውበትን ከፈጣሪ የታደለች ከመሆንዋ ሌላ ደግሞ ካጠገብዋ የማትለይ እስረኛዋ የሚያደርግ የዘወትር ደጀጠኝዋ የሚያደርግ ተወዳጅ የሴት ጠባይ ያላት እመቤት ናት! ታዲያ በዚህ ሁሉ ያካልና የመንፈስ ውበት በዚህ ሁሉ የተወዳጅ ሴት ጠባይና ለዛ እንዳጌጠች ብቻችሁን ሆናችሁ ፍራትና ‹ምን ይሉኝ?› ማለት በሌሉበት ተዝናንታ፥ በሚያባብሉ አይኖችዋ ያንተን አይኖች ጠልቃ እያዬች ስታጫውትህ ምንም ፈቃድህን ገዝተህ የምትኖር ‹ቆራጥ ጎበዝ ብትሆን ትሸነፋለህ። እፈተና ውስጥ ትወድቃለህ፥ እየውልህ ጋሼ፥ ካንተ የምሸሽገው ምስጢር ስለሌለኝ ጉዴን ልንገርህ።

«ብቻችነን በሆነን ቁጥር እንዲህ ባለ ፈተና ውስጥ ስገኝ ፍትወት ራሴን መግዛት እስኪሳነኝ ድረስ ያቃጥለኝና የምሆነውን ያሳጣኝና እስዋን እንደ ታቦት የማከብራትን ቅዱስዋን መድፈር ታቦት ማርከስ ቅድስናዋን ማርከስ መስሎ ስለሚታዬኝ ወዲያወኑም - ለምን እንደሆነ አላውቅም - ስለምፈራት እስዋን ቶሎ እቤትዋ አድርሼ የግብረ ዝሙትን ስራ መተዳደሪያ አድርገው ወደ ሚኖሩት ሴቶች ሮጣለሁ! እዚያ እስዋን እያሰብሁ እስዋን ካሳቤ ላላጠፉ ከነሱ ጋር - ስቆይ፥ ከስዋ ጋር ያለህ እዬመሰለኝ ከዚያ በፊት አግኝቸው የማላውቀውን ደስታ አገኛለሁ! ታዲያ እንዲህ ያለው ወራዳ ስራ ከስዋ ጋር ብቻችነን በተገናኘን ቁጥር የማይቀር የማይታሎል ተግባር ሆነና ራሴን፥ መግዛት የማልችል አመንዝራ ሊያደርገኝ ምንም አልቀረው! ስለዚህ - እስዋን ወደማላይበት አገር መሄድ፥ ከዚህ መጥፋት አሰብሁ! ‹ምናልባት ወደ ባላገር ሄጅጄ

እዚያ የጉዞሞችና የገበሬዎች የስራቸውም የኑሮዋቸውም ተካፋይ ሆኘ፥ እርሻውን ዘሩን ቡቃያውን አበባውን ፍሬውን፥ ውበት እያዩሁ አንድ አመት ያክል ብቆይ እስዋን ያሰረሳኝ ይሆን?› ብዬ አሰብሁ! እና - እንዲህ ካለ በሌሎች ላይ ስጸዬፊው ከኖርሁት ስራ የምወጣበትን ዘዴ እስቲ እባክህ ምከረኝ» አለ በሻህ የገዛ ስራውን መጸየፉን በሚገልጽ ፊት ጉዋደኛውን እያዬ።

አዝማሪው ውቤ፥ በሻህ ውስጠ ምስጢሩን አውጥቶ እንደ ንስሀ አባት ሲናዘዝለት ፊቱ ታሪኩ በውስጡ የፈጠረውን ልዩ ልዩ ስሜት ተከትሎ እዬተለዋወጠ ዝም ብሎ ሲሰማ ቆይቶ፥ ጠጅ የሞላ ብርሌውን አስንቶ እስኪጋመስ አንደቅድቆ አስቀመጠና፥

«ምከረኝ ካልኸኝ፥ ወደ ባላገርም ይሁን ወደ ሌላ እንድትጠፋ አልመክርህም» አለ ፈገግ ብሎ።

«እንግዲያ ምንድነው የምትመክረኝ? »

«ስማ በሻህ! ቅድም ‹ደመቀችን እንደምትወድ ስታያት የምትሆነውን ተመልክቸ አወቅሁ› እንዳልሁህ እስዋም አንተን እንደምትወድህ ደህና አድርጌ ተመልክቻለሁ። እንዲያውም - ይህ አንኩዋ ግምት ነው - ለኔ እንደሚመስለኝ አንተ እስዋን ከምትወዳት አብልጣ ነው የምትወድህ! ስለዚህ እንዲህ ያለች ፈጣሪ ለውብ ሴቶች መርጦ ያስቀመጠውን ጥሩ ጥሩ ነገር ሁሉ ማለት ውበቱን ደም ግባቱን፥ ጠባዩንና ሌላዉን የታደለች ልጅ ልብዋን ከፍታ እጆችዋን ዘርግታ ስለምትጠብቅህና እንዲሁም የመንግስት መስሪያ ቤቶች ሁሉ በሮቻቸውን ክፍት አድርገው በፈልግህ ጊዜ ገብተህ እንድትሰራ ቀዋሚ ግብዣ ያለህ ሰው መሆንህን ስለማውቅ በምትፈቅደው መስሪያ ቤት ስራ ይዘህ እስዋን አግብተህ ወንድሜ ደስ ብሎህ እንድትኖር ነው የምመክርህ! መጽሀፉ ‹ብዙህ ተባዝሁ ወምልእዋ ለምድር› እንደሚለው ያችን የውቦች ውብ ደመቀችን አግብተህ ውብ ውብ እዬወለዳችሁ በልጆቻችሁ በልጅ ልጆቻችሁ በልጅ ልጅ ልጆቻችሁ ምድርን እንድትሞሉ ነው አንተንም እስዋንም የምመክራችሁ! » አለ አዝማሪው እንደ ልማዱ ቁም ነገሩን የቀልድ መደረቢያ አልብሶ።

«የቆምሁለትን አላማ ትቼ፥ የገባሁለትን ቃል ኪዳን አፍርሼ፥ አምኘበት የኖርሁትን ሀይማኖቴን ክጄ፥ ነው ምሽት የማገባ? »

«ይህን - ‹የቆምክለትን አላማ ቃል ኪዳን የገባሁለት አላማ› የምትለው የስራተ - ማህበር ለውጥ ከልም ደረጃ አውጥቶ እውን ለማድረግ የሚቻለው ደህና ሆኖ

የተደራጀ ሀይል ሲኖር ነው እንጂ እንዲህ እንዳንተ አንድ ሰው ከምቾትና ከመልካም ነገር ሁሉ ተከልክሎ ራሱን በድሎ ቢኖር ያን ጥሩ እልም እውን ለማድረግ አይችልም› እያልሁ ብዙ ጊዜ ነግሬሀለሁ፤ እንዲያ ያለ የተደራጀ ሀይል እስካልተፈጠረ ድረስ ደግሞ አንተ ብቻህን እንዲህ የመናኝ ኑሮ እዬኖርህ ምን ያክል ከመልካም ነገር ሁሉ እዬጾምሁ ብትጸልይ የቆምህለትን አላማ መድረሱን ይቅርና የመቅረቡን እንኳዋን ምልክት ሳታይ አርጅተህ ትሞታለህ! »

«ታዲያ ብሞት ምናለ! ለመልካም አላማ ለከፍተኛ አላማ መሞትኮ ህይወት ነው ጋሼ ውቤ፥ ለዘላለም ይህወት! »

«እ! ለጽድቅ ከሆነ እንዲህ - ከመልካም ነገር ሁሉ እዬጾምህ ተንሳቁሎ መኖሩን የመረጥኸው እሱ ሌላ ነገር ነው! ለዚያ ከሆነ ባንድ ፊቱ ገዳም ገብተህ መቀመጥ ነው! ነገር ግን ሁልጊዜ ስትናገር እንደምሰማህ፥ ‹የምንኖርበትን ፍት ርት የሌለበት ስራተ - ማህበር እንዲለወጥ ለማድረግ ከሆነ› እሱ አንድ ሰው የሚያደርገው አደለም። ለሱ፥ ባንድ አላማ አምኖ የተደራጀ ላንድ አላማ የተሰለፈ ብርቱ ሀያል ያስፈልጋል። ነገር ግን ከዛሬው ትውልድ እንኳዋንስ ባላማህ አምነው አብረውህ የሚሰለፉ አላምህ ምን መሆኑን ብትነግራቸው በጥሞና ሰምተው የሚረዱልህ ያሉ አይመስለኝም፤ ቢኖሩም በጣም ጥቂት ይሆናሉ። ትውልዳችን የተራበ ገና ሀብት ያልጠገበ ቢሆን እንደሆነ አላውቅም፥ ሀብትን ወይም የግል ጥቅምን ንቀው ከዚያ በላይ ለሆነው ከፍተኛ አላማ የሚያስቡ አይገኙበትም። ሁሉም ያለውን ስራተ - ማህበር ከመለወጥ ይልቅ በሱ ውስጥ ሀብትና የግል ጥቅም የሚያስገኝ ቦታ ለመያዝ የሚቀዳደሙ ናቸው። ስለዚህ ነው - ‹ቃል ኪዳን የገባህለት ከፍተኛ አላማ እንኳዋንስ ሊደርስ የመቅረቡን ምልክት ሳታይ አርጅተህ ትሞታለህ› ያልሁህ።

«ርግጥ ነው፥ የዛሬው ትውልድ፥ ትውልዳችን፣ ከጊዜያዊ የግል ጥቅም አሻግረው፥ ዘላቂ የጋራ ጥቅም የሚያዩ አይኖሩበት ይሆናል። ግንኮ የዛሬው ትውልድ እንዲህ ቢሆን የነገው እንዲህ አይሆንም። እኔ የቆምሁለት ከፍተኛ አላማ ደግሞ - ለዛሬው ብቻ ሳይሆን ለነገው፥ ለተነገወዲያውም ለከዚያ ወዲያውም ጥቅም ነው።»

«የነገውን የከነገ ወዲያውንና የከዚያ ወዲያውን ተወው። አሁን የምንነጋገረው ስለ ዛሬው ነው።»

«እንዴ! ለምን! አገሪቱኮ የዛሬው ትውልድ ብቻ የሚኖርባት አደለችም። የነገውም የከነገ ወዲያውም የከዚያውም ትውልድ የሚኖርባት ናት! »

«እሱ ሌላ ነው አልሁህኮ! »

«እኮ ለምን? »

« ‹ኢትበሉ ለጌሰም፥ ጌሰምስ ትሄሊ ለርእሳ› ብሎዋላ - መጽሀፉ! »

«አ - ህ! እባክህ፥ ይህን - ‹ሀሌ ሀሌህን› እዚያ - ከደብተሮችህ ጋር አድርግና እኔ በማውቀው ቋዋንቋዋ ተናገር! » አለ በሻህ በስጨት ብሎ።

«እሺ ተወው፣ አትበሳጭ ስምሬ ከሊቃውንቱ ጋር ሆነና ከመሀይም ጋር የምነጋገር መሆኔን እዬረሳሁኮ ነው! » አለ አዝማሪው እዬሳቀ። በሻህም መበሳጨቱን ረስቶ አብሮት ይስቅ ጀመር።

« ‹ኢትብሉ ለጌሰም ቴሄሊ ለርእሳ› ማለት፥ ነጠላ ወይም ቃል በቃል ትርጉዋሜው ‹ለነገ አታስቡ፥ ነገ ለራስዋ ታስባለችና!› ሲል ነው። ይህ ነጠላ ትርጉዋሜ ‹አንድም› ተብሎ በሰፊው ሲተረጎምን ወይም ውስጣዊ ምስጢሩ ተዘርዝሮ ሲተነተን ደግሞ ‹ዛሬ ትናንት አደለም፤ ነገም አደለም፤ ዛሬ በውስጡ ከሚኖርበት ሁኔታ ጋር ለብቻው ራሱን የቻለ ዛሬ ነው እንጂ! የዛሬው ትውልድም የትናንት አደለም የነገም አደለም፤ እንደ ዛሬው ሁኔታ ለዛሬ የሚያስብና የሚሰራ የዛሬ ትውልድ ነው እንጂ። ነገ ዛሬ አይሆንም፣ ከነገ ወዲያም አይሆንም። ነገ ከሚኖርበት የተለዩ ሁኔታ ጋር ለብቻው ራስኑ የቻለ ነገ ይሆናል እንጂ! የነገው ትውልድም የዛሬው አይሆንም ከነገ ወዲያውም አይሆንም። እንደ ነገው የተለዩ ሁኔታ ለነገ የሚያስብና የሚሰራ የነገ ትውልድ ይሆናል እንጂ! ስራት - ማህበርና ትውልድ አይደጋገሙም፤ አይተላለፉም፤ ተራቸውን ጠብቀው ከወደ ሁዋላ ወደፊት ከአለም መጀመሪያ እስከ መጨረሻ ሲሄዱ ይኖራሉ እንጂ› ማለት ነው! » አለ አዝማሪው ፈገግ ብሎ በሻህን በቀልድ አይን እያዬ።

«አቤ - ት! የውትብትቡ የውስብስቡ ያለህ! የምን ውትብትብ ነው ይሄ!? » አለ በሻህ እዬሳቀ። አዝማሪውም መልስ መስጡትን ትቶ አብሮት ይስቅ ጀመር።

«ይህ ሁሉ የናንተ የሊቃውንቱ ውትብትብ በኛ በመሀይማኑ አማርኛ ሲተረጎም ‹የዛሬው ትውልድ ለዛሬ ብቻ እንጂ ለነገ ማሰብ የለበትም። ለነገ የሚያስብ የነገው ትውልድ ነው› ለማለት መሰለኝ አደለም?›

«ልክ ነው፥ ማለፊያ ነው እግዚአብሄር ይባርክህ! » አለ አዝማሪው አሁንም ፈገግ እንዳለ ጉዋደኛውን በቀልድ አይን እያዩ።

«ይቅርታ አድርግልኝና እንዲህ ያአልው - ‹ለዛሬ ብቻ እንጂ ለነገ ማሰብ አያስፈልግም። ዛሬ የተገኘውን ሁሉ በላይ እስኪያስገሳ፥ በታች እስኪያስፈሳ እያግበሰበሱ እዮጎረሱ ጨርሶ መሞት ነው። ነገ ቢፈልግ ገደል ይግባ፥ የራሱ ጉዳይ ነው!› የሚል ፍልስፍስና ያህያ ፍልስፍና ነው! »

«ፍልስፍናው ‹የዛሬው ትውልድ ለዛሬ እንጂ ለነገ ማሰብ የሱ ፈንታ አደለም፤ ለነገ ማሰቡ የነገ ትውልድ ፈንታ ነው› ነው። በዚህ ላይ ‹እስኪያስገሳ ምን እስኪል ገደል ይግባ የራሱ ጉዳይ› ብለህ የጨመርኸው ሁሉ መቾም ያው - ያልታረሙ መሀይማን የሚናገሩት ብልግና ነው። በነገራችን ላይ እንዲህ ያለው አነጋገር በኛ፥ በሊቃውንቱ ዘንድ ‹ጸያፍ› ይባላል። ጸያፍ ቢደረግም የማይነገር ማለት ነው። በቻ እንተወውና፥ ‹ፍልስፍናው ያህያ ፍልስፍና ነው› ያልኸው እንዴት ነው? »

‹አህያ እኔ ከሞትኩ ሰርሶ አይብቀል› አለ ይባላል። ‹እኔ እስካለሁ እኔ እስክሞት ጠግቤ ከበላሁ ከዚያ በሁዋላ ሳር ቢበቅል ባይበቅል ጉዳየ አደለም፤ ባለጉዳይ የሆነ ወይም ከኔ በሁዋላ የሚመጣ አህያ ይጨነቅበት› ማለት ነው። ይህ ታዲያ ከናንተ ፍልስፍና ከዚያ - ‹ከሄሌ፥ ሄሊው› ጋር አንድኮ ነው! አደለም? » አለ በሻህ አዝማሪው ውቤን ባሽሙር የጎድን እያዩ።

«አንድ ነው፤ ታዲያኮ እውነት አህያ እንዲህ ብሎ እንደሆነ፥ ይህን ያለው አህያ ማለፊያ ፈላስፋ ኖሮዋል ማለት ነው። እንዲያ ያለ ፈላስፋ ያወጡ የነበሩ፥ የድሮ አህዮችም ከዛሬ መሀይማን የተሻሉ ኖረዋል ማለት ነው? አይመስልህም? » አለ አዝማሪው እንደ መሳቅ ብሎ።

«እንዴት? » አለ በሻህም እዮሳቀ።

«አዮህ? ይህ አሁን በምንኖርበት ዙሪያ የምናየው ሁሉ ማለት ዘመናዊ ትምርት ቤት የህክምና ቤቱ፥ የመሬትና ተሰማይ መጎጉዋዣው፥ ዘመናዊ የጦርና የፖሊስ ሰራዊት፥ ህግ አውጭው ፓርላና ፍርድ ሰጪው፥ ዘመናዊ ፍርድ ቤት ፋብሪካውና ስንቱ ጊዜው የወለደው አዳዲስ ነገር ሁሉ ከዚያ በፊት ይቅርና እኔ ልጅ በነበርሁበት ጊዜ እንኩዋ ያልነበረ አዲስ የመጣ ነው። እሱን ተከተለውም ሁሉም በዩበኩሉ እንደዩሁኔታው የሚተዳደርበትና የሚመራበት ህግ ስራትና፥ ድርጅት ተሰሩለት፥ ነገር

ግን፥ እንዲያ ያሉትን ህገ ስርአትና ድርጅት መስራት የቻእልው ትውልድ እንኩዋንስ መልኩንና ስራውን ወሬውን ለማያውቀው አሁን ለቆጠርሁልህ እንግዳ ነገር ሁሉ መተዳደሪያ የሚሆን ህግ፥ ስራትና ድርጅት ሊሰራ አይችልም ነበር። እንዲሁም ይህ ዛሬ የወለደው አዳዲስ ነገርና ለሱ መተዳደሪያ ህግ ስራትና ድርጅት የሰራው የዛሬው ትውልድ አርጅተው ያልፋሉ። ነገ ለሚወለደው አይነቱ ሆነ ብዛቱ እንኩዋንስ ሊታወቅ ሊገመት የማይችል አዳዲስ ነገር መተዳደሪያ የሚሆን ህግ ስራትና ድርጅት እንደ ሁኔታው መስራት የሚችል የነገው ትውልድ ነው እንጂ የዛሬው አደለም። የዛሬው ትውልድ በማያውቀው ገብቶ ህግና ስራት ልስራ ቢል እንኩዋ የነገው ትውልድ አይቀበለውም። ርግጥ ለዛሬው ትውልድ የሚስማሙ መልካም ህጎች ስራቶችና፥ ድርጅቶ ለነገው ትውልድም የሚስማሙ ነዋሪ ዋጋ ያላቸው ከሆኑ የዛሬው ትውልድ ስለ ሰራቸው ብቻ አይወድቁም። መጪው ትውልድም ወርሶ ይይዛቸዋል። ነገር ግን እነሱንም ቢሆን እንዳሉ ወይም ላዲሱ ሁኔታ እንዲስማሙ አሻሽሎ ለመያዝም ሆነ ለመጣል ወሳኙ አዲሱ ትውልድ ነው። እንግዲህ እንደ ‹ኢትበሉ ለጌሰም ጌሰምስ ትሄሊ ለርእሳ› ፍልስፍና ሰራተ - ማህበርና ትውልድ ከቀደመው ወደሚከተለው እዬተላለፉ በሄዱ መጠን እዬታደሱ እዬተሻሻሉ ሄደው በመጨረሻ ሰው ባካሉና በመንፈሱ አድጎ ለሙሉ ሰውነት በቅቶ ከጉስቁልና ሁሉ ጠርቶ በእለተ ምጻት ከፈጣሪው ፊት የሚቀርብበት መንገድ ይህ ነው። ፈላስፋው አህያ ያለውም ከዚህ እምብዛ የተለየ አደል» አለ አዝማሪው እንደ ልማዱ ቁም ነገሩን የቀልድ ቀለም ቀባ አድርጎ።

«እውነትም ይህ ‹ሄሉ ሄሉያችሁ› እንዲያው ውትብትብ ብቻ አደለምና! አንዳንድ ቁም ነገርም ያለበት ይመስላል» አለ በሻ።

«አንተ አስቀድመህ እንዳህያው ንቀኸው ምስጢሩን ለመመርመር ባትፈልግ ነው እንጂ እሱስ ሁሉም ቁም ነገር ነው። ብቻ አሁን እሱን እናቆይና ወደ ተነሳንበት አይነተኛ ጉዳይ እንመለስ። እኔ እንደ ትልቅ ወንድም የምመክርህ መደበኛ የመንግስት ስራ ይዘህ ደመቀችን እንድታገባ ነው። ለዚያ - ‹የቆምሁለት የማልሁለት ከፍተኛ አልማ› ለምትለው የዛሬ ትውልዳችን ከግል ጥቅም አልፈው ለጋራ ጥቅም ለማሰብ የደረሱ ስለሌሉበት አብሮህ የሚሰልፍ አታገኝም። ብቻህን ስራተ - ማህበር ልትለውጥ አትችልም። የነገው አዲስ ትውልድ እንደ ነገው አዲስ ሁኔታ የሚኖርበትን ስራተ - ማህበር የሚሰራ እሱ ነው እንጂ አንተ ዛሬ አትሰራለትም። የነገው አለም ሌላ ስለሚሆን ትውልዱና ስራቱም ሌሎች ናቸው የሚሆኑ። ስለዚህ እባክህ ይህን ሁሉ ከንቱ

ምኞትህን ተውና ጠቃሚ ህይወትህን በከንቱ አታሳልፍ፤ መደበኛ የመንግስት ስራ ይዘህ፥ ደመቀችን አግባ።»

«የኔ ህይወትማ - ለዛሬው ትውልድም ለነገውም፥ ‹ለማንም አይጠቅምም» አልህኮ! ታዲያ እንዴት ነው እኔ ህይወት የማይጠቅምም የሚጠቅምም የሚሆነው? »

«ህይወትህ ለማንም አይጠቅምም አላልሁም፤ በጣም ይጠቅማል። ብቻህን ባዶ እጅህን ‹ያንድ አገር ስራተ - ማህበር አስለውጣለሁ› ብለህ ማሰብህን ነው - ‹ራስህን ከመደበል በቀር ማነንም የማይጠቅም ከንቱ አሳብ ነው› ያልሁ። ከግል ጥቅም አልፎ የጋራ ጥቅም ማየት ከማይችል የግል ጥቅም ካወረው ህዝብ ጋር ሆኖ የጋራ ጥቅም ባለበት መድረስ አይቻልም። የግል ጥቅም ካወረው ህዝብ ጋር ሆኖ ‹የጋራ ጥቅም ባለበት እደርሳለሁ› ብሎ ተስፋ ማድረግና መጨነቅ አባቶቻችን እንደሚሉት ‹ከንቱ የጋን መብራት› ሆኖ መቅረት ነው! በተከደነ ጋን ውስጥ የበራ የሻማ ወይም የጡዋፍ መብራት ለመንም ብርሃን ሳያሳይ ብቻውን ተቃጥሎ ያልቃል! እና - ብቻህን ብዙ መልካም ነገር ለማድረግ የምትችልበት መንገድ እያለ ብቻህን ለማድረግ የማትችለውን ‹አደርጋለሁ› ብለህ፥ ‹እንደ ጋን መብራት ብቻህን ተቃጥለህ አትለ - ቅ› ነው የምልህ! »

«ብቻየን ላደርገው የምችለው መልካም ነገር እስቲ እንዴት ያለ ነው? »

«አሁን እንዳልሁህ የመንግስት ስራ ይዘህ ደመቀችን አግብተህ መቀመጥ፥

«1ኛ. በዬለቱ ወደ መንግስት መስሪያ ቤቶች የሚመጡ ባለጉዳዮች ጉዳያቸውን በለት አልቆ ወደዬስራቸው መመለስ ሲችሉ ሳምንት ወር፥ ከዚያም በላይ ስራ ፈትተው በደጅ ጥናት ሲጉላሉ እንደሚኖሩ ታውቃለህ። ታዲያ፥ ምንም እንኩዋ ከኒያ ሁሉ መሀከል ወዳንተ ክፍል የሚመጡት ጥቂት ቢሆኑ እነሱን በደህና ፊት ተቀብለህ፥ ሳይጉላሉ፥ ‹ጉቦ አምጡ› ሳይባሉ በዬለቱ ጉዳያቸውን እዬፈጸምህ ወደዬሰራቸው እንዲመለሱ ብታደርግ ባመቱ ብዙ ድህ ስራ ከመፍታት ከመጉላላትና ከጉቦ ታድናለህ ማለት ነው። እንዲህ ያለው ቅን አገልግሎት ከብዙዎች የመንግስት ሰራተኞች ስለማይገኝ ለባለጉዳዮች ትልቅ ርዳታ ትልቅ ጥቅም ነው።

«2ኛ. ደመቀች ልጅዋ አንድ በመሆኑ ከሱ የሚለይ ወይም በሱ ላይ አንድ ክፉ ነገር ቢደርስ የህወትዋ መጨረሻ የሚሆን እዬመሰላት ዘወትር እንደ ፈራችና ልብዋ እንደ ተንጠለጠለ ነው የምትኖር። ታዲያ እድላችሁ አምሮ አንድም ይሁን ካንድ በላይ

ብትወልዱ፥ አሳብዋንና ፍቅርዋን ከሱ ሌላ የምታሳርፍበት ታገኝና እንዲያ ካለ የዘወትር ፍራት ምናልባትም ከክፉ አደጋ ትድናለች። ያችን ውብና ደግ ልጅ ሊደርስባት ከሚችል ክፉ አደጋ መጠበቅ ከማይወጣ ጸጸት የሚያድንና አይከፈል ዋጋ የሚከፈልበት ነው» ሰምቶት ልቡ እንደ መታወቅ አለበትና ቀና ብሎ እንባ ባቀረሩ አይኖቹ ላንድ አፍታ፥ አየት አድርጎ መልሶ ራሱን ሰፋ።

«3ኛ. የሚወዳትንና የምትወደውን ሴት አግብቶ የሚኖር ሰው ደስታው መልስ የሌለው የደስታ ሁሉ ቁንጮ ለመሆኑ እኔ አንድ ምስክር ነኝ። ባሳለፍሁትና በምኖረው የችግር ኑሮ የምሽቴን የውባዬሁን ፍቅር ባያድለኝ ኖሮ፥ ምን ይውጠኝ እንደ ነበር አላውቅም! ከስዋ ጋር አብረን መንገላታቱን ወደ ምቾት እዬለወጠ፣ ከስዋ ጋር አብረን የምንካፈለውን ማናቸውንም መራራ ጽዋ እያጣፈጠ ቀን እያለፈ ቀን በተተካ ቁጥር ወደ ፊት እስዋና እኔ አብረን አለምን የናቅን ጌቶች እንደምሆን የማያቁዋርጥ ተስፋ እዬሰጠ ሁልጊዜ፥ በጥሩ እልም ውስጥ የሚያኖረኝ የውባዬሁ ፍቅር ነው! አንተም የምትወዳትንና የምትወድህን ደመቀችን አግብተህ ብትኖር አለም አሁን የምታሳይህን አስከፊ ፊትዋን ወዲያ አዙራ በፈገግታ፥ ያጌጠ፥ ውብ ፊትዋን፥ ስታሳይህ፥ አዘንህና ብስጭትህን ረስተህ በደስታ የምትኖር ሌላ፥ በሻህ እንደምትሆን፥ - አይጠረጠርም! ከምትወዳትና ከምትወድህ ምሽትህ ጋር እዬኖርህ ፍቅርዋ ተካፋይ የሌለበት ያንተ ብቻ መሆኑን ስታውቅ ሁልጊዜ ደስታ ብቻ እንጂ፥ አዘንና ብስጭት ባጠገብህ አይዞሩም! ከምትወዳትና ከምትወድህ ምሽትህ ጋር ደስ ብሎህ ስትኖር ክፉ ነገር አይታይህም! ያንጊዜ ክፉ ሁሉ ደግ መጥፎው ሁሉ ውብ፥ ችግረኛው ሁሉ የተመቸው መስሎ ይታይሃል! ይህ የምትጠላው ስራተ - ማህበራችን እንኩዋ አሁን የሚታይህን ያክል አይታህም! ከምትወዳትና ከምትወድህ ምሽትህ ጋር መኖር እንጂ መሞት አትፈልግም!

«ከዚህ ሁሉ በላይ ደግሞ ምናልባት፥ ትውልዳችን እዬበሰለ እያስተዋለ ሲሄድ፥ ይህ አሁን የምናየው የግልጥ ጥቅምን ማባረር፥ ይህ የግል ጥቅም ስካር፥ እዬበረደ ሄዶ፥ የጋራ፥ ጥቅም ማሰብ ይከተልና፥ ስራተ - ማህበራችን የምንመኘውን ያክል እንኩዋ ባይሆን፥ በመጠኑ ይሻሻል ይሆና። ‹እንቁላል ከቆዬ ዶሮ ሆኖ በግሩ ይሄዳል› ይባል የለ? » ሲል አዝማሪው፥

«እንቁላል ዶሮ ሆኖ በግሩ ለመሄድ የሚችልኮ አፍኖ የያዘውን ቀፎ፥ ሰብሮ ከላዩ ሲያነሱለት ነው! » አለ በሻህ ባሽሙር አስተያየት ጉዋደኛውን እያዬ።

«እ እ! መስበር አደለም፤ ቀስ ብሎ በጥንቃቄ ሲቀረፍቱት ነው። ሲሰብሩትማ፥ እንቁላሉም እዚያ ይፈርጥና ይጨፈለቅና፥ ዶሮ ሆኖ በግሩ መሄዱ ይቀራል! » አለ አዝማሪው ላሽሙሩ አስተያየት አጠፋውን መልሶ፥ ከዚያ ሁለቱም ሲስቁ ቆይተው።

«እንግዲህ ምከረኝ ካልከኝ» አለ አዝማሪው ውቤ። «ምከረኝ ካልከኝ ምክሬ ይህ ነው። ‹የምትቀበልው መሆን አለመሆንህን አሁን ንገረኝ› አልልህም። አደራ የምልህ እንድታስብበት ነው። የሰማነውን በልቡናችን ያሳድረው አሜን አቡነ ዘበሰማያት! »

«በሻህ ተጋምሶ የቆዬ ብርሌውን አንስቶ ጨልጦ አስቀመጠና፥ «አልቃሻም! » አለ አፉ ሲሳደብ ልቡ የሚያመሰግን መሆኑን በሚገልጽ ፊት ወዳጁን እያዬ።

« ‹ምክሬን ከንቱ አድርገህ ታስቀርብኛለህ› ብዬ ባልፈራ ‹ሌባ› እልህ ነበር! » አለ አዝማሪውም።

## ምእራፍ ሀያ ስምንት

# የተፈራ ሉልሰገድ ግብዣ

ተፈራ ሉልሰገድ፥ የደጃዝማች ሉልሰገድ ክንፌ ያክስታቸው የልጅ ልጅ ነበር። አባቱ ሜጫ ውስት አቶ ገለታ የሚባሉ የጋላ ባላባት ነበሩ። እሱም እንደ ተወለደ ስሙ ዳባ ነበር። ሁዋላ ግን ለትምህርት አዲስ አበባ እንደ መጣ ‹ዳባ› መባሉን ትቶ ‹ተፈራ› ተባለ። እንደ ደጃዝማች የልጅ ልጆችና የቅርብም የሩቅም ዘመዶቻቸው ልጆች ሁሉ መጠሪያውም መማሪያውም ደጃዝማች ሉልሰገድ ሆኑ።

ደጃዝማች ‹ዘመናዊ› መባልን በጣም ስለሚወዱና ተማሮችን መርዳት ወይም፥ ፈቃዳቸውን ሁሉ ለመፈጸም ‹ዘመናዊ› ከሚያሰኙት ነገሮች አንዱ ምናልባትም አይነተኛው መሆኑን ስለሚያውቁ የልጅ ልጆቻቸውንና የቅርብም የሩቅም፥ ዘመዶቻቸውን ልጆች ሲረዱ ወይም ፈቃዳቸውን ሲፈጽሙ ልክ የራሳቸው ፈቃድ እንደ ተፈጸመ ሁሉ ደስ ይላቸው ነበር።

ወንዶች ተማሮች መጥተው ለጢም ማስላጫና ለጠጉር ማስተካከያ ወይም ለትምህርትና ለልዩ ልዩ የጨዋታ መሳሪያ መግዣ ሲጠይቁዋቸው ሴቶች ተማሮች በፊንታቸው መጥተው ለጠጉር ማሰሪያ፥ ለፊትና ለጠጉር ቅባት ለሲኒማና እንዲሁም ለልዩ ልዩ ስም - አይጠሩ ነገር ሁሉ የሚሆን ገንዘብ ሲጠይቁዋቸው ከዚህም ሌላ ተማሮች መዋጮ የሚያደርጉበት ምክንያት ኖሮ ወይም ስጦታ ማድረግ ፈልገው ገንዘብ እንዲሰጡዋቸውና ግብዣ ማድረግ፥ ፈልገው፥ ድግስ እንዲያስደግሱላቸው ሲጠይቁዋቸው ስለሚፈጽሙ ልጆች ደስ ይላቸውና ‹አባባ እስዎንኮ እንደ ዱሮ ስዎች አንቆጥሮዎትም! አሳብዎ ሁሉ ከአዲሱ ትውልድ አሳብ ስለሚስማማ ከወጣቶች እንዳንዱ እንደ ዘመናዊ መሪያችን ነው የምናይዎ› ይሉዋቸዋል። ይህ ለደጃች ሉልሰገድ ብዙ አመት ደጅ ጠንቶ የሚያገኙት ትልቅ ሹመት ምንም ያክል ዋጋ ቢከፈልበት የሚያስጎዳ ውድ ነገር ነው። ስለዚህ እንኩዋንስ ተጠይቀው ጠይቀው ተማሮችን ደስ ማሰኘት በጣም ደስ ይላቸው ነበር። አንዳንድ ጊዜ፥ አንድ ነገር ሳይጠይቁ ወር ያሳለፉ ተማሮች እንዳሉ ወንዱን ‹ጠጉርህ ያላስተካከልኸው - ገንዘብ ጠፍቶ ነው?› ይሉና ባጠገቡ ሲያልፉ እንደ ዋዛ፥ አምስት ወይም አስር ብር በኪሱ ሽጉጥ፣ ሴትዋን ‹ምነው? ፊትሽም ጠጉርሽም ‹ቅባት ከለከለኝ» እያሉ አቤት ይሉብሻል› ይሉና አስር ወይም አስራ አምስት ብር በጉንፍዋ ክትት ሲያደርጉ ከስጦታቸው የበለጠ ያሰጣጥ ዘዴ ማወቃቸው በጣም ያስወድዳቸዋል። እንኩዋንስ የሚረድዋቸው፥ የዘመዶቻቸው ልጆች ሌሎችም የሚያውቁዋቸውና ወሬያቸውን የሰሙ ተማሮች ሁሉ የመልካም አባት የዘመናዊ አባት ምሳሌ አድርገው ወላጆቻቸውንና ዘመዶቻቸውን ይሰብኩባቸዋል።

እውነትም፥ ደጃዝማ በቅርብ ለማያውቃቸው ካለባበሳቸው ሆነ ከጠቅላላ ሁኔታቸው ዘመናዊ አስተያየታቸው ያላቸውን አዋቂ መስለው ይታያሉ። መቸም በሽማግሎች ጉዋደኞቻቸው ዘንድማ ፈረንጅ ናቸው። ያውም ተራው አደለም፤ ሊቁ ፈረንጅ! ከተማሮችም ከረጅንጆች ወዳጆቻቸውም ትርጉማቸውን አስተካክለው ሳያውቁ የሰበሰቡዋቸውን ብዙ የፈረንሳይ የንግሊዝና ይልቁንም የጣልያን ቃሎች ካማርኛ ጋር ጣልቃ እያገቡ መናገር ስለሚወዱ ይህ በሽማልጎች ጉዋደኞቻችው ዘንድ ላዋቂነታቸው ለጥርጥር ቦታ የማይሰጥ አይነተኛ ምስርክ ነው።

ከነዚህ የዘመኑ ስልጣኔ ያመጣው አዲስ የኑሮ ስራት ተወልደው አድገው ላረጁበት አገራቸው እንግዶች ካደረጋቸውና ግራ ካገባቸው ጉዋደኞቻቸው ጋር በድግስ፥ በግቢ፥ ወይም በሌላ ቦታ ተገናኝተው ባንድ ቁጭ ሲሉ ለሁሉም መምህሩ ደጃች ሉልሰገድ ናቸው። የፈረንጅ አገር ሕዝብ ስለሚኖርበት የደስታና የጽድቅ ኑሮ የሰሙት እያጋነኑ ያልሰሙትን ራሳቸው እየፈጠሩ ካወሩ በሁዋላ ‹እኛኮ› ይላሉ

ደጃዝማች ሉልሰገድ ‹እኛኮ› ሲስተሙን ስላተረዳነው፥ በከንቱ እንደከማለን እንጂ ሲስተን ብንረዳው ኖሮ ፈረንጆች በደረሱበት ባጭር ጊዜ እንዲያውም እነሱ ከደረሱበት በጣም ባጠረ ጊዜ እንደርስ ነእብር። ፈረንጆች ምቀኝነትና ተንኮል የሌላቸው ቅኖች በመሆናቸው ያገኙትን «ሲቭላዛሲዮን» ሁሉ ማለት - ፋብሪካውን ሌትሪኩን፥ ራዲዮን አውሮፕላኑንና ሌላውን በየጊዜው የሚፈጥሩትን አዳዲስ ነገር ሁሉ አንድ ሳይቀር እንዴት እንደሚሰራ ከነስእሉ «ዲክሲዬኔር ላሩስ» በሚባል መጽሐፋቸው ስለሚጽፉ ቁንዋንቁዋችውን ደህና ድርገን ካወቅን እነሱ ረዥም ዘመን የደከሙበትን ባጭር ጊዜና ባቁዋራጭ መንገድ ከዚያ መጽሐፍ መቅዳት ብቻ ነው! ለዚህ የሚያስፈልገው ሁሉንም ባንድ ላይ «አድሞንስትሬሽንና ወርጋንዜሽን» አድርጎ በዬከተማም በዬገጠሩም ሁሉ «አስኮላ» በብዛት መክፈትና ቁዋንቁዋቸውን «እስቴዲያሪ» ማድረግ ነው፤ የምስጢራቸው ቁልፍ መክፈቻው ቁዋንቁዋቸው ብቻ ነው! » ሲሉ ጉዋደኞቻቸው መንግስት ለምን ደጃች ሉልሰገድ እድናሉት ባቁዋራጭ የኢትዮጵያን ሕዝብ እንደሚያሰለጥን አልገባቸው ብሎ ግራ ይገባቸውና በዚያው መጠን የደጃዝማችን አዋቂነት ያደንቃሉ።

በሀብትም ቢሆን፥ ደጃዝማች ሉልሰገድ ክንፌ፥ ሀብታሞች ተብለው መጀመሪያ ከሚቆጠሩት ጥቂት መኩዋንንት አንዱ ናቸው። በ1928 ዓ.ም ኢጣልያን ኢትዮጵያን ስትወር በኦጋዴን ግንባር ዘምተው ከተመለሱ በሁዋላ ኢጣልያኖችና አርበኞች በሚለያዩበት መንታ መንገድ ቆመው አርበኞቹን ሲያገኙ ተቀበለው የእከተማ ወሬና ስንቅ ቢገኝ ጥይትም ሰጥተው እዬሸኙ በዚያ ካርበኞች የሸመቱት ወሬ ከራሳቸው ጨማምረው ለጣሊያኖች እዬሰጡ በሁለቱም ወገኖች ዘንድ ፍጹም የታመኑና ሁለቱንም ወገኖች ፍጹም የካዱ መሆናቸውን ማንም ሳያውቅባቸው ክፉውን ቀን ወደ መልካም ለውጠው ለማሳለፍ የቻሉ ትልቅ ዘዴኛ ናቸው። ጣሊያኖች ሄደው ኢትዮጵያ መንግስት ወደ ስልጣኑ ሲመለስ የውስጥ አርበኝነታችውን አርበኞች ራሳችው መስክረውላቸው ኒሻንና ብዙ ምርጥ የከተማም የገጠርም ርስትና ንብረት አግኝተዋል። ከጣሊያኖች በቅርብ ጊዜ ለመመለስ ተስፋ ስለ ነበራቸው በባላደራነት የሚጠብቁት አይነቱም ሆነ ብዛቱ ለግምት የሚያስቸግር እቃ ስላገኙ፥ ከዚያ ካደራው እቃ የሚበዛውን ብር እስኪጠግቡ ሸጠው በተረፈው ያርበኞችንና የስደተኞችን ወዳጅነትና ወገንነት ገዝተው የትም ቢሆን እንደ ልባቸው ተናግረው የፈለጉትን አድርገው ኮርተው ምንም ሳይሰጉ ተዝናንተው የሚኖሩ ነበሩ ፡

ደጃዝማአች ሀብታም እንደ መሆናቸው ዛሬ፥ ባይሆን ነገር፥ ‹ትርፍ አገኝበታለሁ› ለማይሉት ገንዘብ ማውጣት አይወዱም፤ የሚነግድ ለመሰላቸው ግን ሲያወጡ አይን

የላቸውም። ‹መስራት ለማይችል ድህ መስጠት ወልዶ ተዋልዶ የሰውን ሀብት ሊያበዛ የሚችለውን ገንዘብ ማምከን ነው› ይላሉ። በዚህ ከምሽታቸው ከወይዘሮ ላቀች ተገኔ የሚለያዩበት ሰማይና ምድር የሚለይበትን ያክል ሰፊ ነው። ‹ድሮ እንዲህ አልነበሩም! ይህ ሁሉ አሁን ከኒያ ከፈረንጆች የተማሩት አዲስ ፈሊጥ ነው። ይልቅ፥ ያለምስክር ዝምድና እዬቆጠረ ለሚመጣው ተማሪ ሁሉ ከሚያባክኑት ገንዘባችን ቀንሰው አይናቸውንና እጅ እግራቸውን ላጡ ደካሞች ቢሰጡ በመንግሥተ ሰማያት፥ ከኛ ተርፎ ለዘመድ ሁሉ የሚያበቃ ርስት ይኖረን ነበር› ሲሉ ወይዘሮ ላቀች፥ ‹እ እ› ይላሉ ደጃዝማች፥ ‹እ እ ተሳስተሻል ላቁ፥ ጊዜው ዛሬ የኛ ቢሆን፥ ነገ የነሱ ስለሆነ ለተማሮች፥ የሚወጣ ገንዘብ ባከነ አይባልም። ነገር የሚከፈል ብድር ነው! ስለ መንግሥተ ሰማያት - ሀ ሀ ሀ ሀ› ይላሉ፥ ሊናገሩ ያሰቡት ቀልድ ከመናገራቸው በፊት ራሳቸውን ያስቃቸውና። ‹ስለ መንግሥተ ሰማያት የሆነ እንደሆነ አለም ከተፈጠረ ጀምሮ ከዚህ ወደ ሰማይ የሄደውን ስንት እውቀትና ችሎታ ያለው መሀንዲስ ሁሉ ስራ አስፈትቶ አስቀምጦ፥ እግዚአብሄር ርስት ማካፈልን ያክል ነገር «አይንና እጅ እግር ደካሞች ይሰጣል» ብዬ እንኩዋን ላምን አልጠርጥርም። አንቺ እንደ ምትይው በሰማይ ርስት አከፋፋዮች አይንና እጅ እግር የሌላቸው ደካሞች ከሆኑ ግን መቸም ደካማ ባለሥልጣን ለሀይለኞች፥ መሳሪያ ሊሆን የተፈጠረ ስለሆነ፥ ሀ ሀ ሀ ሀ፥ እዚያም ባለርስቶች የሚሆኑ ሀይለኞች ብቻ አርበኞች፣ ብቻ እንደሚሆኑ አትጠርጥሪ! ስለዚህ ሀ ሀ ሀ ሀ ሀ ሀ! ስለዚህ ላቁ፥ እንደምታውቂው አርበኞች እጣዎቻችን ናቸውና ለዘመድ የሚተርፍ ባይሆን ለኔና ላንቺ የሚበቃ ያክል ምንም ቢሆን «የንፍጉናል› ብለሽ አትስጊ።

ወይዘሮ ላቀች ባላቸው እንዲያ ያለ ከመንገድ የወጣ ፌዝ ስለ መንግሥተ ሰማያት ወይም እሱን፥ ስለሚመስል ሀይማኖት ነክ የሆነ ነገር በድፍረት ሲናገሩ ሲሰሙ እግዚአብሔር ያኔውኑ መአት እንዳያወርድ ፍራት ይዞዋቸው፥ አይኖቻቸውንም እጆቻቸውንም ወደላይ አቅንተው እያርገበገቡ፥ ‹እግዚኦ መሀረነ ክርስቶስ እግዚኦ መሀረነ ክርስቶስ እባክህ ጌታየ የሚሉትን ባያውቁ ነው፥ አትስማቸው!› ይሉና ከዚያ እጃቸው እያማተቡ፥ ‹በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅድሱ አበስኩ ገበርኩ፥ አበስኩ ገበርኩ› ብለው ከደጃዝማች ጋር እንኩዋንስ መነጋገር አብረዋቸው መቆዬቱ የሀጢያታቸው ተካፋይ የሚያደርጋቸው ስለሚመስላቸው ለጊዜው ትተዋቸው ሸሽተው ይሄዳሉ።

ደጃዝማች ሉልሰገድ፥ ስለ ሃይማኖት ሆነ በጠቅላላው ስለ ኢትዮጵያ ልማድና የኑሮ ስራት ይህን የመሳሰለ ጸያፍ ይናገሩ የነበረ የጫማ ሰፊዎችን፥ የልብስ ሻጮችንና

ሌላ ሌላም የንግድ ስራ የሚሰሩትን የፈረንጅ ሱቆች ማዘውተርና፥ እዚያ የሚሰበሰበው ስራ ፈት የሚያወራውን ሁሉ እዬለቃቀሙ አዲስ የፈረንጅ ደቀመዝሙር አዲስ አማኝ መሆን በጀመሩበት ጊዜ ነው። ሁዋላ ሁዋላ እንዲህ ያለ ጻያፍ አነጋገር በሳቸው ደረጃ ያለ ሰው ሊናገርው የማይገባና በከፍተኛ ቦታ የሚያስነቅፍ መሆኑን፥ አንዳንድ ባለቁርጥ ወዳጆቻቸው ስለ መከሩዋቸው የሚያስፈልግ ጻያፍ ከመናገሩ እዬቆጠቡ ፈረንጆችንና ዘመናውያን መሆናቸውን የታወቀላቸውን ኢትዮጵያን ለመምሰል በመጣጣር ወሰኑ። ይኸውም ቢሆን በሃይማኖታቸው ጽኑ ስለሆኑትና ፈረንጆችም ሆኑ የዘመኑ ወጣቶች የሚያደርጉት ሁሉ የሃይማኖት ተጻራሪ ለሚመስላቸው ለወይዘሮ ላቀች አልጥማቸው አልዋጣቸው፥ ብሎ ባልና ሚስት እንደ ዱሮዋቸው ተጫውተው ተሳስቀው በስምምነት ውለው ከሚያድሩበት ተጋጭተው የሚኮራረፉበት ጊዜ ይበልጥ ነበር። በሁዋላ ግን፥ ወይዘሮ ላቀች ባላቸውን መክረው አኩርፈው ‹እፋታለሁ› ብለው አልፎ አልፎ ደጃዝማች በሃይማኖት ‹ለቀልድ› ሲሉ ብቻ አላስቻላቸው እያለ ተቆጠው ይሄዳሉ እንጂ፥ በሌላው ሁሉ እንደ ፈቀዱት እንዲሆኑ ተዋቸው። እንዲያውም የራሳቸውን እምነትና ስሜት ለራሳቸው አድርገው ከምነታቸውና ከኑሮ ልማዳቸው አንድ ጋት እንኩዋ ዘባ ሳይሉ ባላቸው ከሚፈልጉት ምንም እንዳይጎድል ሲጠነቀቁ ያን ያክል የምነትና የስሜት ልዩነት በመሀከላቸው ያለ አያስመስሉትም። ‹እኔ ምን ቸገረኝ! «ሁሉ በከመ ምግባሩ» እንደ ተባለው እግዜር ለሁላችንም እንደዬስራችን ሊከፍለን በሳቸው ነፍስ ምን አገባኝ? ህእ! እዚያ ላይ - የምትጠትዬቀው የሳቸው ነፍስ!› ይላሉ የደጃዝማች ነፍስ የምትጠዬቅበትን ቦታ ላንድ አፍታ ቀና ብለው አየት ያደርጉና።

«ላቁ፥ የዚያ ልጅ፥ የዚያ የተፈራ ግብዣ እንገር መሆኑን ነግሬሻለሁ። የጋበዛቸ ልጆች ሴቶችና ወንዶች ባንድ ላይ ሰላሳ ናቸው። ስለዚህ፥ አንዳንድ የጎደለ ነገር እንዳለ ለመግዛት የመጨረሻ ቀን ዛሬ ቅዳሜ ስለሆነ አዳራሽ እንዳይረሳና ልጁ እንዳያዝን» አሉ ደጃዝማች አንድ ቅዳሜ ወደ ውጪ ለመሄድ ሲሰናዱ።

«እግዚአ መሀረነ ክርስቶስ! ‹የተፈራ ግብዣ የተፈራ ግብዣ፥ የተፈራ ግብዣ› ሲሉ ከነጋ ይህ ሶስተኛ ጊዜዎ ነው! ለመሆኑ እዚህ ቤት የተማሪ ግብዣ ማድረግ የምንጀምረው ገና ዛሬ የተፈራ ግብዣ ነው? እዚህ ቤት ለተማሪ ከመደገስ በቀር ሌላ ስራ አለ? ወይስ እስከ አሁን በተደረገው ግብዛ፥ ተረስቶ የጎደለና በዚያ ምክንያት ያዘነ ተማሪ አለ? »

«ምንም! ሁሉም እዚህ ስለሚደረገው ግብዣ፥ ከማመስገንና ደስታቸውን ከመግለጽ በቀር ‹ይህ ጎደለ› የሚል ሰምቼ አላውቅም።»

«ታዲያ ለተፈራ ሲሆን በምን ምክንያት የሚጎድል መሰለዎ? እንዲያውም እዚህ ከሚሰበሰበው ሁሉ ተፈራ ይሻላለኛ! »

«አዎ፥ ተፈራ ጥሩ ልጅ ነው፤ ደህና አድርገሽ ባታውቂያቸው ይሆናል እንጂ፥ ሁሉም ጥሩዎች ናቸው። አሁን እንኩዋ ሳላስብ የተናገርሁትን ደገምሁት እንጂ ልነግርሽ የፈለግሁ ቀድሞ ረስቼ ያልነገርሁሽን ነው።»

«ምንድነው? »

«ራቱ እንድ ሁልጊዜ አደለም፥ ‹ቡፌ ይሁንልኝ› ብሎዋል።»

«አይመጣ ነገር የለ! ደሞ ‹ቡፍ› ምንድነው? »

«ሀ ሀ ሀ ሀ! ‹ቡፍ› አደለም ላቂ፤ ‹ቡፌ› ነው! ቡፌ አታውቂም? »

«እናቴ አላስተማረችኝ፥ አክስቴ! ከየት አምጥቼ ልወቀው? »

«ዛሬ ካንቺ በቀር፥ ቡፌ የማያውቅ የለምኮ ላቂ፤ በጣም የተለመደ ነው።»

«እንዲያውስ ይህን የፈረንጁን ምግብ፥ ለዚህ ለግብዣችሁ ስል ነው እንጂ ካጠገቤ ቢዞር እወዳለሁ? ባላውቀው ምን ቸገረኝ! ከፈረንጆች ምግብ ያ፥ ጣፋጫቸው ብቻ ይምጣብኝ፥ ሌላ ሌላውንስ - ወዲያ፥ በጠበል ያርቀው! የመልኩ ቅጥ መላ ማጣትና የጣሙ ‹ውሀ ውሀ› ማለት ሲገርመኝ፥ ከሁሉም የባሰ፥ ስሙ፥ ደግሞ...... ቡፊ! » አሉ ወይዘሮ ላቀች እዬሳቁ።

« ‹ቡፍ› አደለም፥ ‹ቡፊም› አደለም፥ ‹ቡፌ› በይ፥ ላቂ።»

«እሺ ቡፌ! ለመሆኑ ቡፌ ምን አይነት ወጥ ነው? የስጋ ነው? ወይስ የህል ወጥ? » ሲሉ ወይዘሮ ላቀች፥ ደጃዝማችን ሊገቱት የማይችሉ ሳቅ፥ ከሳል ጋር ባንድ ላይ ይዞ ያንፈራፍራቸው ጀመር። ሳቁና ሳሉ ታገስ ሲሉላቸው፥ መሀረማቸውን አውጥተው ላባቸውንም እንባቸውንም እየጠራረጉ፥

«ቡፌ የወጥ አይነት አደለም፥ ያቀራረብ አይነት ነው፣ ላቂ። ቡፌ የስጋ የህል፥ ያታክልት፥ ይወጥና ሌላውም ለግብዛ የተሰናዳው ምግብ ሁሉ፥ በዬቃው ሆኖ በትልቅ ጠረጴዛ በተራ ይቀመጥና ተጋባዦቹ ሳህናቸውን እዬያዙ ሄደው የሚፈልጉትን እያነሱ ወደዬመቀመጫቸው ተመልሰው የሚጋበዙበት ያቀራረብ አይነት ነው» አሉ።

«ውይ! ቡፌ እሱ ነው? እሱንማ አውቀው የል! » አሉ ወይዘሮ ላቀች በፈንታቸው እዬሳቁ። «ስሙን አላውቀውም እንጂ፥ ነገሩንስ አውቀዋለሁ። ባንዳንድ ቦታ ስንጠራ፥ ትልልቆች መኩዋንንትና ወይዛዝር ሁሉ ሳይቀር ቁና ቁናቸውን እዬያዙ ተኮልኩለው ሲተራመሱ ተመልክቼ ‹መኖር አያሳዬው የለ!› እያልሁ ይገርመኝ ነበር! መቼም እኔ፥ እዚያው በተቀመጥሁበት አመጥተው ሲሰጡኝ አበላለሁ እንጂ ቁና ተሸክሜ፥ ‹እባካችሁ ሙብል ያለበትን አሳዩኝ እያልሁ ፍለጋ አላውቅም! ወደ ፊትም አላደርገውም! »

«የለም፥ አልገባሽም» አሉ ደጃዝማች። «ባይገባሽ ነው እንጂ፥ ሁሉም ለዬራሱ ባይነት የሚፈልገውን መርጦ በመጠን የሚበቃውን ገምቶ፥ እንዲያነሳ ታስቦ የተደረገ ‹ሲስተም› ማለት - ነገር ነውኮ! ወዲያውም ያሳላፊን ችግር ስለሚያቃልል በጣም ጥሩ ነገር ነው።»

«ለርስዎ የፈረንጅ ነገር ሁሉ ጥሩ ነው! እኔ ግን እግዚአብሔር የሚበላ እህልና የሚያገለግል ሎሌ ሳያጣ፣ እግዚአብሔር የሰጠን ሳይነሳ፥ በወግ በማእረግ ተቀምጦ፥ እሱን እያመሰገኑ በሙብላት ፈንታ እንደ ክፉ ቀን እንደ ችጋር ቀን ቁና እዬነጠቁ ሄዶ፥ እዚያ እዬታገሉና እዬተጋፉ በህል ላይ ሸማ መግጠም እግዚአብሄር የሚወደው አደለም፤ እግዚአብሔርን አሳዝኖ ክፉ ቀን እንዲመጣ የሚያደርገው ነው።»

«በይ እንግዲህ፥ ቡፌ እግዚአብሔርን የሚያሳዝን መሆን አለመሆኑን ሊቃውንቱ ተከራክረው እንዲወስኑ እንተውላቸውና ግብዛዉ የተፈራ ስለሆነ እሱ እንደሚፈልገው ይሁንለት። ግብዣው ያንቺና የኔ ሲሆን እንዴት እንደምናደርገው እንመካከራለን» አሉ ደጃዝማች በቀልድ መልክ።

«እኔ ምን ቸገረኝ ይህን ለመሰለው ነገር ሁሉ፥ ልቤ ተባባሪ አለ መሆኑን እግዜር ያውቃል! ያዘዙ እርስዎ የሚሰሩት አሽከሮች ናቸው። እኔ እርስዎ ያዘዙት ምን እንደሆነ ላሽከሮች ነግሬ፥ ሁሉም በጊዜው ተሰናድቶ እዚያ ይመጣላችሁዋል፤ ከዚያ ወዲያ፥ ቢሻችሁ ተሻሙት፤ ያለዚያም - እንደ ፈለጋችሁ አርጉት! »

እሁድ አመሻሽ ላይ እንግዶች፥ ከመድረሳቸው በፊት ለተፈራ ሉልሰገድ ግብዣ የተሰናዳው ምግብ ሁሉ ስራው፥ ተጠናቆ መብል ቤት በተዘረጋው ትልቅ ጠረጴዛ ላይ ዙሪያውን በድርብ ተራ ተደረደረ። ከምግቡ በጣም የሚበዛው ደጃዝማች ኢጣልያኖች ቤት እንዲሰለጥንላቸው አድርገው ቀለብ ከቤት በወር ሰላሳ ብር የሚከፍሉት ወጥቤታቸው፥ ስጋውንና አታክልቱን፥ ፓስታውን ባንድ ላይም ለዬብቻም

‹በአልፉርኖ› በአሮስቶ፥ ‹በቡሌቶ› ‹በሳልታቶ› ‹በሶኮንድ ሚስቶ› ‹በአለካቻቶሬና› በሌላም ልዩ ልዩ የጣልያኖች ያሰራር ዘዴ ያሰናዳው ነው። በዚህ ላይ፥ እንዲያውም ለመጠባበቂያ ያክል ወይዘሮ ላቀች፥ ቀይና አልጫ ወጥ ከንጀራ ጋር እንዲሁም ቁዋንጣና አንዳንድ እንደ ኢትዮጵያ ያሰራር ዘዴ የተሰናዱ ነገሮች እንዲጨመሩ አደረጉ። በመጠጥ በኩል ልዩ ልዩ ለስላሳ መጠጥና ቢራ በብዛት ተገዝቶ ነበር። መቸም የቃ እንገር አይወራም፤ ሞልቶ የተረፈ ነው። ደጃዝማች ሉልሰገድ አንድ ጊዜ እቃ ከገዙ በሁዋላ እቤት መቆጣጠሩ ካቅማቸው በላይ ሆኖባቸው እዬተሰበረም፥ እዬጠፋም ሙሉ ሆኖ የሚገኝ እቃ አይገኝም እንጂ ሰው ሲያደንቀው ከሰሙ የማይገዙት እቃ ስለ ሌለ፥ እንኩዋንስ ሰላሳና አርባ መቶ ሰው ለመጋበዝ ቢሆን፥ እቤታቸው «የቃ ችግር ይኖራል» ተብሎ አይታሰብም።

ደጃዝማች «ሳሎኔ» የሚሉት ሰፊ አዳራሻቸው ከውስጡ፥ ምንጣፎችና ከባድ የሆኑት መቀመጫዎችም ሌሎች እቃዎችም ተነስተው መሀሉ ለዳንስ ዙሪያው፥ ነጭ እየለበሱ የመጠጥ፥ ጠርሙስ፥ ሳህን፥ ብርጭቆ፥ ቢልዋና፥ ሹካ እስኪከብዳቸው የተሸከሙ ጠረጴዛዎች ከከበቡዋቸው ወንበሮች ጋር ተደርገውበት ለራቱ መጋበዣ ተሰናዳ።

ተፈራና ሁለት ጉዋደኞቹ የግብዣውን ድርጅት ለመቆጣጠር፥ እዚያው ምሳቸውን በልተው ስለዋሉ ወዲያው ከራት በሁዋላ ለሚሆነው ዳንስ የሚስማሙትን የሙዚቃ ሸክላዎች መርጠው ከሸክላ መጫወቻው አጠገብ አስቀመጡ። የተመረጡት ሙዚቃዎች ሁሉ - ከመከፈቻው በቀር - የወጣትነት ፍጥነት ለግልቢያ የሚኮለኩሉ የወጣትን ሙቀፍ አናፍተው የሚያግሉ አርገብግበው የሚያቃጥሉ ነበሩ።

ካስራ ሁለት ሰአት እስከ አስራ ሁለት ተኩል፥ ከቴዬ መነንና ከናዝሬት ትምርት ቤቶች፥ አስራ ራት ሴቶች ልጆች፥ ሁለትም ሶስትም ሆነው እዬተንጠባጠቡ፥ ተማሮች ‹የተፈራ ሉልሰገድ ቤት› በሚሉት እደጃዝማች ሉልሰገድ ቤት ደረሱ። ከዚያ እንዲገቡ ቢለምኑ ጉዋደኞቻቸው እስኪመጡ እውጭ መቆዬት ስለ ፈለጉ፥ እግቢው ውስጥ ሰፍረው ሲጠባበቁ ወዲያው፥ ከተፈሪ መኮንን ትምህርት ቤት ወንዶች ልጆች ተከታትለው ደረሱ። ከሁለት ሴቶችና ወንዶች ልጆች በቀር እዚያ የነበሩት ሁሉ ቀደም ብለው የሚተዋወቁና በጉዋደኝነት የቆዩ ስለ ነበሩ እንግዶችን ማካዮቻቸው አስተዋወቁዋቸው። በመጨረሻ ከሁሉም ወደ ሁዋላ ቀርቶ የነበረው ተማሪ ካንድ ሴት ልጅ ጋር መጣ። ልጅቱ ባለባበስዋ ሆነ በጠቅላላ ሁኔታዋ እዚያ ከነበሩት ልጆች ለየት ያለች ስለ ነበረች ሁሉም ያይን ሩምታ ወርውረ፥ ከግር እስከ ራስዋ አስፈሩባት። ደግነቱ

አይን ሹል አደለም! አይን ሹል ቢሆን ኖሮ፥ ያ ሁሉ አይን የወጋው ገላዋ ገላ አይሆናትም ነበር! ወይም አይን አፍር ብትሆን ኖሮ፥ ያ ሁሉ ጣምራ ጣምራ እየሆነ እየተወረወረባት አይን አይንዋን ሸፍኖት ልብዋን አሽብሮ የምትቆምበትን ትስትና ትወድቅ ነበር! እስዋ ግን ‹ሶስና› ግን አይን ፈላጊ እንጂ አይን ፈሪ ስላልነበረች፥ ያን ሁሉ ያይን ሩምታ ከምንም አልቆጠረችው። ከያቅጣጫው የመርጣውን ፍጥጫና ግልምጫ ሁሉ ንቅሳት ያስጌጣቸው የሚያማምሩ ጥርሶችዋን በከፊል ገለጥ አድርጋ የደስ ደስ ባለው፥ ፈገግታ እዬመለሰች ወዳፈጠጡባትና ወደ ገላመጥዋት ለመጨመር ቀጥ ብላ ስለ ሄደችባቸው ሁሉም እንደ ገና እንደ ማፈር እያሉ፥ በስዋ ላይ ሊወረውሩ የቃጡትን አይን የሚያሳርፉበት ይፈልጉ ጀመር።

ጉዋደኝዋ ከማን፥ ሳያስተዋውቃት ራሱ መጀመሪያ ካገኛቸው ጉዋደኞቹ ጋር ሰላምታ ተሰጣጥቶ ወሬ ሲጀምር ሶስና ከተሰበሰቡት ልጆች መሀከል ፈገግ እንዳለች ቆማ የያንዳንዳቸውን አይን ለመያዝ ብትፈልግ ሁሉም አይናቸውን አሾሹ።

«ባይ ጆቭ! ይህ ወንድማችን አድጎልናልና! ማንን ይዞ፥ እንደ መጣ ታውቃለህ? » አለ አንዱ ተማሪ አብሮት ላለው ጉዋደኛው ሶስናን ወዳመጣው ተማሪ ባገጩ እያመለከተ።

«ማናት? የየት ትምህርት ቤት ተማሪ ናት? »

«ምን ተማሪ! አስተማሪ እንጂ! »

«እውነትህ ነው? ታውቃታለህ? »

«አዎ አውቃታለሁ። ነገር ግን - እንዲሁ ባይን ብቻ።»

«የምን ትምህርት ቤት አስተማሪ ናት ታዲያ? »

«ደጃች ውቤ ሰፈር፥ ወይም ‹ከዶሮ ማነቂያ› ኮሌጆች ያንዱ! » አለ ሲያሽሙዋጥጥ።

«ምን? እምፖሲብል! »

«እሽሽ -! » አለ አሚተኛዉ የፊት ጣቱን አፉ ላይ አድርጎ።

ወዲያው ተፈራ፥ ሉልሰገድ መጥቶ ጠራቸውና ገብተው አዳራሽ ውስጥ የተሰናዳላቸውን ጠረጴዛዎች በዩጉዋዳቸው እዬከበቡ ተቀመጡ። ደጃዝማች ሉልሰገድ

ተፈራን፥ አስፈቅደውና ጉዋደኞቹን ይቅርታ እንዲለምንላቸው ነግረው የልጆችን ጨዋታ ለማሳዬት፥ ሶስት ወዳጆቻቸውን ከነምሽቶቻቸው ጋብዘው ስለ ነበረ እነሱም ከደጃዝማች ጋር በተለይ አንድ ጠረጴዛ ከበው ተቀመጡ።

ልጆች፥ ቦታ ቦታቸውን ይዘው እንደ ተቀመጡ ደጃዝማች ባጠገባቸው ወዳለው ጠረጴዛ ሄደው አንዱ ተማሪ የተቀመጠበትን ወንበር ባንድ እጃቸው አንድዋ ተማሪ የተቀመጠችበትን በሌላ እጃቸው ይዘው ጎንበስ አሉና ሁለት ሶስት የቀልድ ቃሎች እየሳቁ ጣል ካደረጉ በኋላ በጣም ደግና ዘመናዊ አባትነታቸውን ለመግለጽ ወንዱን ትከሻውን ሴትዋን ጉንጭዋን ደበስበስ አድርገው ወደ ሁለተኛው ጠረጴዛ ከዚያ ወደ ሶስተኛው ከዚያ እስከ መጨረሻው እንዲህ እያደረጉ ሁሉንም አዳርሰው ተመልሰው ከጉዋደኞቻችው ጋር ሲቀመጡ ራቱ ተጀመረ። ከደጃዝማች በቀር ጉዋደኞቻቸውና ምሽቶቻቸው ያለውን እዬጠየቁ ወይም በዙሪያቸው የሚበላውን እያዩ፥ እዚያው በተቀመጡበት አሳላፊ እያመጣላቸው ነበር የሚበሉ።

ምንም እንኩዋ፥ ደጃዝማች አስቀድመው ተፈራን ቢያስፈቅዱና ጉዋደኞቹንም ይቅርታ እንዲጠይቅላቸው ቢነግሩት የነዚህ ጥንታውያን እዚያ፥ ያለቦታቸው ያለጎሳቸው፥ በወጣቶች መሀከል መገኘት፥ በተማሮች፥ ዘንድ በተለይ በሴቶች ተማሮች ዘንድ ልክ የጠላት ሰላይ በመሀከላቸው እንደገባ የስጋትና የጥርጥር ስሜት መፍጠሩ ስላልቀረ በመጀመሪያ በሚያደርጉት ሁሉ ስብስብ ለማለትና ለመቆጠብ ሲሞክሩ ይታዩ ነበር። በሁዋላ ግን ራስ ላይ፥ ወሬ መድራት ሲጀምርና ከዚያ ራቱ አልቆ ወደ ዳንስ ሲያልፉ ጥንታውያኑን እስከ መኖራቸው እንኩዋ ረሱዋቸው።

ምግቡ ባይነትም፥ በቁጥርም ብዙ ስለሆኑ ተማሮችን ደስ አላቸው። ያበሻውን ወጥ ግን፥ በተለይ የበርበሬውን ትንሽም ወንዶች እንደሆኑ እንጂ፥ ሴቶች እምብዛም አልተጠጉትም። እነ ደጃዝማች ከተቀመጡበት ጠረጴዛ አጠገብ ከተቀመጡት ልጆች አንዱ ካመጣው ልዩ ልዩ የፈረንጅ ምግብ ጋር፥ የበርበሬ ወጥና እንጀራ በጎን አድርጎ አምጥቶ ሲበላ ጉዋደኛው ለቅንጦት ያክል ከፊቱ ተሻምታ የጎረሰችውን ትንሽ ጉርሻ በቅጡ ሳታላምጥ እንደ ምንም አድርጋ ዋጠችና፥ ከልብዋ ይሁን ወይም በርበሬ መብላት የማትችል ለመምሰል ምላስዋን አውጥታ እግዚኦ ትል ጀመር። ከዚያ ጉዋደኞችዋ እንደ መከርዋት ዳቦ በርከት አድርጋ በመጉረስም ኮካ ኮላ በጉንጭዋ ይዛ በመቆየትም አፍዋ በረድ ያለላት ሲመስል፥

«ይህን ያህል ‹እስትሮንግ› ነው? » አለች ሲስቁባት ከነበሩት ጉዋደኞችዋ አንድዋ።

«አዬሽ! እኔ እምልሽ - በርበሬ ጭራሽ አልችልም፥ ‹ታንጌንበርን› ያድርገኛል።

«እኔም አልችልም፤ ‹ባት - እስቶማኬን ነው እንጂ፣ ታንጌን በርን አያደገኝም» አለች ሌላዋ።

«ይገርማል የሰው ‹ኔቸር› ልዩ ልዩ ነው፤ ደግሞ ‹ታንጌንም እስቶማኬንም በርን አያደርገኝም› በርን የሚያደርገኝ፥ በማግስቱ ‹ሞርኔንግ› ወደ ‹ደብልዩሲ› ስሄድ ነው፣ ብቻ ቢሆንም ስለሚጣፍጠኝ፥ በርበሬ ካዬሁ መብላቴ አይቀርም» አለች በርበሬ ወጥ አቃጥልዋት ምላስዋን ያወጣችዋ ልጅ ጉዋደኛ።

ልጆቹ እዬተሳሳቁ፥ የበርበሬን ወጥ ጉድ ሲያወሩ፥ በነደጃዝማች ጠረጴዛ ከተቀመጡት፥ በልጆቹ በኩል የነበሩት ባልቴት ወይዘሮ «በርን» የሚባለውን ቃል ብዙ ጊዜ ሲደጋገም ጆሮዋቸው ሰምቶ፥

«እኒህ ልጆች ‹በርን በርን› ይላሉ ‹በርን› ከቶ ምን ማለት ይሆን? » አሉ፥ በዝቅተኛ ድምጽ ወደ ባላቸው ቀና ብለው።

«እንዲህ ያለውን የደጃዝማች፥ ሉልሰገድን ጠይቂ፥ እኔን አደለም» ሲሉ ባልዬው ደጃዝማች ሉልሰገድ ሰሙና ‹ምንድን ነው?› አሉ ቶሎ እንደ ተቀመጡ ወደ ፊት ቀረብ ብለው።

«ምን ነበር ያልሽው? » አሉ ሰውዬው፥ ወደ ሚስታቸው ዘወር ብለው።

«በርን» አሉ ወይዘሮዋ አሁንም በዝቅተኛ ድምጽ።

«አዎ ‹በርን።› አጠገብዋ ያሉት ልጆች እየተቀባበሉ ‹በርን› ሲሉ ሰምታ ፍቹን ማወቅ አማራት፤ ዛሬ የፈረንጅ አፍ ተምራ ሊቅ ሆናልኝ ሳትሄድ የምትቀር አይመስለኝም! » አሉ ሰውዬው ባለቤታቸውን ባሽሙር አስተያየት የጎድን እያዩ።

«እህ -! ‹በርን› አሉ? ‹በርን› አንድ አይነት የፈረንጅ ወጥ ነው «አሉ ደጃዝማች ሉልሰገድ ተማሮች እንዳይሰሙ ቀስ ብለው።

«አየ ጉ - ድ! ‹በርን፥ በርን› አሉ? ‹በርን› በፈረንጅ በጣም የተወደደና የተለመደ ወጥ ነው፤ ታዲያ - ተረስቶ ሳይሰራላቸው ቀርቶዋል» አሉ ቀጠሉና።

ተማሪዎች በመጀመሪያ በያይነቱ ከተደረደረው ምግብ እንደ ምርጫቸው እዬያዙ ተቀምጠው ሲበሉ ከቆዩ በኋላ በርከት ያሉ አሳላፊዎች ምግብ፥ ከያይነቱ ይዘው

በዬጠረጴዛው እዬዞሩ ይጋብዙ ጀመር። ነገር ግን ከተማሪዎች በጣም የሚበዙት ወንዶችም ሆኑ ሴቶች አሳላፊዎች በየጠረጴዛው እያዞሩ ያቀረቡላቸውን ችላ እያሉ ተነስተው ምግብ ባንድነት ከተደረደረበት ከቡፌው እያመጡ ነበር የሚበሉ። ስለዚህ በነደጃዝማች ጠረጴዛ ከተቀመጡት ባልቴት ወይዘሮዎች አንድዋ እመት አልጣሽ ዝም ብለው ሲመለከቱ ቆይተው ገረማቸውና፥

«ወይ መቆየት! ወይ እድሜ፥ እህ - ሀ - ህም! እንዲያውኮ - እድሜ ከቆዩ ብዙ ነገር ያሳያል! እስቲ እሰው ቤት እንግዳ ሆኖ ገብቶ ባለቤት ያቀረበለትን በልቶ አመስግኖ በመሄድ ፈንታ - ‹እንጀራውና ወጡ፥ ካለበት ቦታ ሄጄ ካልዘረፍሁ አልበላም› የሚል አለ? » ብለው ሲስቁ ያን ጠረጴዛ ከበው የተቀመጡት ወይዛዝርም መኳዋንንትም ሁሉ ባንድነት ሳቁ።

«እሜቴ ባይለምዱት ይሆናል እንጂ ማለፊያኮ ነው፤ ዛሬ እንኳዋንስ በሌላው - በቤተ መንግሥትም ቢሆን፥ እዳ ግብር ካልሆነ፥ ከዚያ ዝቅ ያለው ግብር ሁሉ - ቡፌ ነው» አሉ ደጃዝማች ሉልሰገድ፥ ከሌሎች ጋር ሲስቁ ቆይተው።

«አይ ወዲያ! ያ ፈረንጁ ስላደረገው፥ ‹እሱ ያደረገው አይቅርብን› ተብሎ ነው እንጂ - ምኑ አምሮ ነው? » አሉ ወይዘሮዋ።

«አደለም እሜቴ ‹ፈረንጅ ያደረገው አይቅርብን› ለማለት ሳይሆን ጥቅሙ ታይቶ ነው። መቸም ፈረንጅ ጥቅም የሌለው ነገር አይሰራም። አንደኛ - እያንዳንዱ እንግዳ፥ ተሰናድቶ ከቀረበው ምግብ፥ ሆዱ የሚወደውን እዬመረጠ እንዲበላ ሁለተኛ፣ ያሳላፊ ችግር ለማቃለል ታስቦ የተደረገ ነው፤ ስለዚህ በጣም ማለፊያ ነው።»

« ‹አሳላፊ ይቸግራል› እንዳይባልማ፥ እንኳዋንስ በቤተ መንግስት፥ እዚህም ይኸው - አንድ መንጋ አሳላፊ ምግቡን በያይነቱ ተሸክሞ ‹ምንተ ማርያም ብሉልኝ› እያለ ይለምናል! እንዲያው - ባለቤት ባሳላፊ እጅ የሚያቀርብልን አይጥመንም፤ አያጠግበንም፤ ወይም ደግሞ ‹ተደብቆ የተቀመጠ ምግብ መኖር አለመኖሩን እዚያው እቦታው ድረስ ሄደን፥ በዬስርቻው ፈልገን፥ በርብረን ካላረጋገጥን የልባችን አይደርስም› በማለት ይሆናል እንጂ፥ እንዲህ ሁሉም በዬፊናው ሰሀኑን እዬነጠቀ ምግቡ ተሰናድቶ ወደ ተቀመጠበት የሚቀዳደመው! ኧረ እንዲያው ለሰሚው ግራ ነው! እኔ መቸም እቤት እንግዳ ሆኖ የመጣ ሰው ያቀረብሁለትን በሙብላት ፈንታ፥ ‹እማጀትሽ ገብቼ እዚያ ያስቀመጥሽውን ሳላይ አልበላም› ብሎ እዚህ እንደማያቸው

እንግዶች እማጀቴ ሊገባ ቢነሳ፥ እንዲያው - ማሪያምን ተጣልተን እንደባደብ እንደሆነ እንጂ፥ ማጀቴን አላስገባው! » ሲሉ እመት አልጣሽ እዬሳቁ፥ እዚያ ጠረጴዛ ዙሪያ የተቀመጡት ሁሉ አብረዋቸው ይስቁ ጀመር።

«የቡፌ እንግዶች እንደማያዩዋቸው ለመምረጥ የሚነሱ ተሰናድቶ ከማጀት ወጥቶ፣ ባጠገባቸው ከቀረበላቸው ነው እንጂ፥ እንደርስዎ እንግዳ ‹እማጀት እንግባ› አይሉምኮ» አሉ ደጃዝማች ሉልሰገድ እዬሳቁ።

«አይ ሁሉም ያው ነው! »

ከዚያ፥ እዚያ ጠረጴዛ፥ ስለ ቡፌ ስራት የደጃዝማች ሉልሰገድንም የባልቴትዋን ወይዘሮም አስተያየት ደጋፊዎችና ነቃፊዎች አንዱን ደግፈው ሌላውን የሚነቅፉበትን ምክንያት በዬበኩላቸው እያቀረቡ ሲከራከሩ መብሉም መጠጡም እንደ መገባደድ ስላለ፥ ተፈራ ሉልሰገድ ተነስቶ ከተመረጡ ሸክላዎች ሁሉ መጀመሪያ ለመክፈቻ ለዘብ ያለውን በግራማፎኑ ጠምዶ ያ ሸክላ ከተመረጠ ጥሩ ምንጭ የቀዳውን ጥኡም ዜማ እያንቆረቆረ ተቀባይ መጥራት ተቀባይ መጋበዝ ሲጀምር ተፈራ፥ ወደ መቀመጫው ተመልሶ ጉዋደኛውን አስነሳና ዳንሱን ከፈተ። ወዲያው ሌሎች ተማሪዎች እዬተከታተሉ ከዬተቀመጡበት ጠረጴዛ ተነስተው በዬጉዋዳቸው ጥንድ ጥንድ እዬሆኑ ያን ሰፊ ጠረጴዛ ሞልተው መዝመማቸውን መወረባቸውን ጀመሩ! ተፈራ እዚያ ወረብ፥ እዚያ ዝማሜ ውስጥ መቆየት እንዴት በወደደ ነበር! ብቻ ጋባዥ እንደ መሆኑ የተመረጡትን ሸክላዎች እዬለዋወጠ ማጫወት ስለ ነበረበት እያዘነ ወደዚያ ሄደ። ለዘብ ካለው የመክፈቻ ሙዚቃ በኋላ ተከታትሎ የመጣው እያንዳንዱ ሙዚቃ የሁዋለኛው ከፊተኛው እዬፈጠነ እዬፈጠነ የሚሄድ ስለ ነበረ፥ እኒያ ወጣት ዘፋኞች አካላትም፥ ያን ፈጣን ሙዚቃ ተከትሎ በሄደበት ሁሉ ሲሄድ ከዚያ ፈጣን ሙዚቃ ጋር አብሮ ሲነጉድ የዜማ ሰሚ ተመልካችም አሳብ ጭምር አብሮ ይወድ ይዞ የንጉድ ነበር! በዚያ መሀከል ያ ፈጣን ሙዚቃ የልብዋን አላደርሰው ያለ ልጅ፥ ከዚያ ፍጥነት አልፋ መሄድ ያማራት ልጅ፥ ዘፈኑን አቁዋርጣ ቆማ እዬደጋገመች፥ አጨበጨበችና፥ ሙዚቃው ዝም ሲል «ቻ - ቻ - ቻ! » አለች ድምጽዋን ከፍ አድርጋ። «እንዲያ እንጂ! ቻ - ቻ - ቻ ደግሞ ምንድነዋ! ፈረስ ልትጋልብ አምሮዋት ነው? እህ - ህ - ህ - ህም! » አሉ እመት አልጣሽ። እወንትም፥ ቻ - ቻ - ቻ የሩጫ፥ የግልቢያ ሙዚቃ መሆኑ ነው! ከዚያ ወንድና ሴት ወንድና ሴት እየሆኑ የተጣመሩት ወጣቶች እንደ ተቃቀፉ፥ ወገባቸውን ገዳይ ፈካሪ እንደሚያደራው ጨሬ እዬሰበቁ፥ አዳራሹን በቁሙም በወርዱም እዬዞሩ ሲያረበርቡ ሲያሸበሽቡ አንዳንዶቹ፥ ሴትዋ ራስዋን በወንዱ ትከሻ አረፍ፥ ወንዱ ራሱን በሴትዋ

ራስ ደገፍ አድርገው፥ ሌሎች ወገብ ለወገብ ብቻ ሳይሆን ጉንጭ ለጉንጭ ጭምር እዬተቃቀፉ የተኙ ይመስል አይናቸውን ለበስ አድርገው ከነሱ የተለዬ ሌላ ሀይል ምስጢራዊ ሀይል፥ መሬት አስለቅቶ እንደሚነዳቸው ሁሉ ሲከንፉ ሲሰፍፉ፥ ደጃዝማች ሉልሰገድ የጋበዙዋቸው መኳዋንንትና ወይዛዝር ገርሞዋቸው ሁሉም አፍ አፋቸውን እዬያዙ ዝም ብለው ይመለከቱ ነበር። ከመሀከላቸው እስከዚያ ማታ ድረስ የዳንስን ስም የሰማ ይኖር እንደሆነ እንጂ፥ አይቶ የሚያውቅ አልነበረም።

«ታዲያስ ጨዋታውን ወደዳችሁት? ማለፊያ አደለም? » አሉ ደጃዝማች ሉልሰገድ እሳቸውም ዝም ብለው ሲመለከቱ ቆይተው።

«መቸም - ከኛ እምነትና ከኛ ስራት ጋር አይስማማም። በኛ ስራት ይህ አሁን እዚህ ሲደረግ የምናእየው ሁሉ እጅግ ነውር ነው፤ ወደ ክፉ ሃሳብ ወደ - ውልስትና የሚመራ ነው» አሉ ከመኳዋንንቱ አንዱ፥ ደጃዝማች ኑርልኝ ተገኜ፤ ምንም እንኳዋ «ግብዣህ መጥፎ ነው» ብሎ ለጋባዥ መንገር የማይገባ መሆኑን ቢያውቁ ዳንሱን መጥላታቸው ይሉኝታቸውን አሸንፎ።

«እኔ ፊቱንም ደጃዝማች ስለ ጋበዙኝ የሳቸውን ግብዣ፥ መግፋቱ ከብዶኝ ነው እንጂ፥ አሁን በስተርጅና ዘፈንና ጨዋታ ማየት አምሮኝ አደለም የመጣሁ። የፈረንጆቹን ስራቸውን ነበር እንጂ ቀድሞ መማር፥ ጨዋታና ዘፈንማ እኛስ መች ገደደን። የቸገረን ስራው ነበረ! ታዲያ - ከስራ በፊት ጨዋታ መማር ደግ አደለም ጨዋታ ወዳጅ አድርጎ ያስቀራል! » አሉ ሁለተኛ የደጃዝማች ሉልሰገድ እንግዳ ፊታውራሪ አሸብር በሀይሉ።

«ጭዋታስ ቢባል እንዲህ ነው? እኔማ እሜቴ ወይዘሮ ላቀች፥ ‹ያን - ድስ ነው? ድንስ የሚባለውን ነገር፥ እንኳዋንስ ባይኔ ማየት ስሙን መስማት አልፈልግም!› ሲሉ ‹ከቶ እንዴት ያለ ቢሆን ይሆን እንዲህ የጠሉት?› ስል ነበር! አሁን ሳየው እውነትም ሊጠሉት የሚገባ ነገር ነው!› እውነቱን ልንገራችሁ፤ እኔም አሁን - ህ - ህ - ሞ -! ወይን አንተ እግዚኦ - ር! እስቲ እባካችሁ የሚሆኑትን እዩልኝ፤ እንዲያውኮ - ሰው ጨለማ ለብሶ የሚያደርገውን ሁሉ፣ እዚህ ባደባባይ እንዲያው እንደ ከብቶች ‹በሜዳ ካላደረግነው› ብለው ነው - እንዲህ መከራቸውን የሚያዩ! እስቲ ምን ቀራቸው? እህ - ህ - ህ - ም! ግሩምኮ ነው! » ብለው እመት አልጣሽ የመገረም ሳቅ ሲስቁ ጠረጴዛውን ከበው የተቀመጡት ሁሉ ባንድ ላይ በሳቅ ያወኩ ጀመር። ‹ደጃዝማች ሉልሰገድ እንኳዋ ከመኳዋንንቱና ከወይዛዝሩ ተጨማሪ ዝናና ምስጋና ያስገኝልኛል› ያሉት ግብዛ

እንዳሰቡት ሳይሆን በመቅረቱ ለጊዜው ቅር ቢላቸው የመት አልጣሽ አነጋገርና ሁኔታቸው ሁሉ ያለውዳቸው ከልባቸው አሳቃቸው።

በነደጃዝማች ጠረጴዛ እመት አልጣሽ የተናገሩት ያስነሳው ሳቅ ገና እንደ ደመቀ ሳለ፥ እንደገና ተደጋግሞ ተጨበጨበና ሙዚቃው ጸጥ ሲል «አንቺ ልጅ አንቺማ! » አለች ሶስና በከፍተኛ፥ ድምጽ። ‹አንቺ ልጅ አንቺማ› ከኢጣልያና ከኢትዮጵያ ጦርነት በሁዋላ፥ ባዲስ አበባ ለብዙ ጊዜ ባላፍላ ሆኖ የቆዬ ሙዚቃ ነው። ሙዚቃውን ተከትሎ ዳንስ ሲደረግ ያረማመዱ ስልት ‹ዳንግላሳ› ሆኖ ተጫዋቾቹ ወገባቸውን ባንድ ላይ አስተባብረው ወደ ሁዋላ፥ ሳብ ወደ ፊት ገፋ እያደረጉ የሚጋልቡበት ነው። ‹አንቺ ልጅ አንቺማ› ደጃች ውቤ ሰፈር ገዳም ሰፈርና ዶሮ ማነቂያ ሲገባ፥ በወገብ ‹ሳብ ገፋው› ላይ ያንገት ዘፈን ተጨምሮበት የወገብ ‹ሳብ - ገፋና› ያንገት ዘፈን ባንድ ላይ ተዋህደውበት መልኩ ለወጥ ብሎ ሌላ ሆኖዋል፤ ግሩም ሆኖዋል! ታዲያ ይህን የወገብ ‹ሳብ - ገፋና› ያንገት ዘፈን የተዋሀዱበት ዳንስ አንዳንድ ሰዎች ‹የፈረንጅ ያበሻ ክልስ ዳንስ› ይሉት ነበር።

«አንቺ ልጅ አንቺማ «ሙዚቃ ሲጀምር፥ ፈረንጅኛውን ተማሪዎቹ ሁሉ ግሩም አድርገው ስለሚያውቁት፥ ወንድና ሴት እየሆኑ እንደ ተጣመሩ በዚያ ሰፊ ሜዳ «ዳንግላሳ» ግልቢያቸውን ይጋልቡ ጀመር። ነገር ግን፥ ካበሻ ያንገት ዘፈን ጋር የተዋሀዱትን ክልሱን «አንቺ ልጅ አንቺማ» ከሶስና በቀር አንድ እንኳዋ የሚያውቀው አልነበረም። ስለዚህ ሶስና ጉዋደኛዋን እዬመራች «አንቺ ልጅ አንቺማ» ን፥ እሱዋ በምትኖርበት በደጃች ውቤ ሰፈር በሚደነስበት ስልት ስትደንስ መጀመሪያ ባጠገብዋ የነበሩት ከዚያ በነሱ ሳቢያ፥ የነሱን አይን እዬተከተሉ፥ ራቅ ያሉት ሲያዩ ትንሽ በትንሽ ጨዋታቸውን ትተተው እዬቆሙ እስዋንና ጉዋደኛዋን ይመለከቱ ጀመር። ጉዋደኛዋ ተከስተ ታምራት ነበር። ተከስተ፥ ያነለት ሶስና እዬመራችው ከስዋ ቀድቶት ይሆን ወይም ቀደም ብሎ እሌላ ቦታ አይቶት ‹ክልሱን ዳንስ› ሲደንስ በመጠኑ ደህና ነበር። መቼም እዚያ ለነበሩት ተማሪዎች ሁሉ አስተማሪ ሊሆን ይቻላል። በመጨረሻም፥ ተማሪዎች ሁሉ ደከሞዋቸው ስለ ነበረ፥ ሜዳውን ለሶስናና ለተከስተ ትተው ወደ ጠረጴዛቸው እየተመለሱ ተቀመጡ እነሱን ይመለከቱ ጀመር። ተከስተ ምን ጊዜም ቢሆን በግብዣ ልብስ መርጦ የመለበስ ልማዱ የታወቀለት ስለ ነበረ ያነለትም የለበሰው እዚያ ከጉዋደኞቹ መሀከል ተወዳዳሪ አልነበረውም። ግራማፎኑ «አንቺ ልጅ አንቺማ» ን አንድ ዙር ተጫውቶ ሲጨርስ ብዙ ልጆች «ቢስ ቢስ ይደገም! ይደገም! » ብለው

ስለጮሁ እንደገና እንዲደገም ተደረገና ሶስናና ተከስተ ያን ሰፊ አዳራሽ ብቻቸውን ይዘው ዳንሳቸውን ቀጠሉ።

መቸም መመስገን ከያፉ መወደስና፥ መሞገስ ደስታና ኩራትን፥ ትቢትን ብቻ ሳይሆን፥ እውቀትንና ብርታትን ጭምር እንደሚሰጥ የታወቀ ስለሆነ፥ ሶስናና ተከስተ ያዳራሹ ሰው ሁሉ አይን በዬሄዱበት ተከትሎዋቸው ሲዞር ያዳራሹ ሰው ሁሉ አፍ እነሱን እያደነቀ ሲነጋገር ስርቅ አድርገው እዬተመለከቱ ዳንሳቸውን በቀጠሉ መጠን በመድከም ፈንታ እዬጠነከሩ ባረማመዳቸውና ባካላት ንቅናቄያቸው ላይ አዳዲስ ስልት በመጨመር ዳንሱን እያራቁና ይሄዱ ነበር።

«ይህ ሰይጣን ይህ ተከስተ አይገባበት የለው! የት ገብቶ ነው ይቺን ደግሞ - አውጥቶ ይዞ የመጣ እባክህ? » አለ ከተማሪዎች አንዱ፥ ባጠገቡ ወደ ተቀመጠ ጉዋደኛው ጠጋ ብሎ።

«እሱኮ አደለም ያመጣት፥ የሱ ጉዋደኛ ሌላ ናት። ይቺንስ ያመጣ - ተኮላ ነው፥ የተኮላ ዘመድ ናት» አለ ጉዋደኛው።

«ናይስ ቸክ! እ? አደለችም? » አለ ጠያቂው በተማሪዎች መሀከል እንደ ተለመደው እንግሊዝኛና አማርኛ አደባልቆ።

«ያ፥ ናይስ ቸክ! » አለ ጉዋደኛው።

ተማሪዎች የሶስናንና የተከስተን ዳንስ እያዩ ስለነሱ በዬገዋዳቸው ሲያወሩ «ይህን - በወገባቸው ‹ሱክ - ሱክ› ማለቱን ወዲያው ትተው ያንገት ከትከሻውን ዘፈን ብቻ ቢዘፍኑ እንዴት ባማረባቸው! » አሉ እመት አልጣሽ፥ ከነደጃች ጠረጴዛ።

«አንቺ ደግሞ ምን ማለትሽ ነው? ‹ሱክ - ሱክ› ማለቱን ትተው ያንገት ከትከሻውን ዘፈን ብቻ ከዘፈኑማ ፈረንጅ መሆናቸው ቀርቶ እኛን ሊመስሉ አደል? እኛን ትቶ ፈረንጅ መሆንኮ ነው የሚፈለገው! » አሉ ደጃዝማች ኑርል እዬሳቁ። «ይልቅስ» አሉ ደጃዝማች ቀጥለው «ይልቅስ ያ እንዱ ባለባበሱና - በሁኔታው ሁሉ ተማሪ አይመስልም፥ ተማሪ ነው? »

«ተማሪ ነው፤ ሁልጊዜ ከኛ ልጆች ጋር እዚህ እዬመታ አውቀዋለሁ። እዚህ ያሉት ሁሉም ተማሪዎች ናቸው» አሉ ደጃዝማች ሉልሰገድ።

«ማለፊያ ልጅ ይመስላል የማን ልጅ ነው? »

«የማን ልጅ እንደሆነ አላውቅም፤ አልጠዬቅሁም ይቆዩ፤ ተፈራ የነግረናል።»

ወዲያው ግራማፎኑ የ «አንቺ ልጅ አንቺማ» ን ሁለተኛ ዙር ተጫውቶ ሲጨርስ ሙዚቃው ቆመና ተከስተ ሶስናን አጅቦ ተኮላ ወደ ተቀመጠበት ወስዶ ተኮላንም እሱዋንም አመስግኖ ጉዋደኛው ወደ ተቀመጠበት ሂዶ ሲቀመጥ፥ ብዙ ሴቶችም ወንዶችም ተማሪዎች ከዬጠረጴዛቸው እዬተነሱ ሄደው ከበው፥

«አብራህ ዳንስ ያደረገችው ልጅ ማን ትባላለች? »

«የምን ትምህርት ቤት ልጅ ነች? »

«ይህን ዳንስ መች ተማርኸው? »

«ማን አስተማረህ? » እያሉ ላንዳቸውም መልስ ለመስጠት ፋታ ሳይሰጡ ብዙ ጥያቄዎች ባንድ ላይ ስላደራረቡበትና ከደስታውም ብዛት የተነሳ ጭምር፥ ለጥያቄዎች ሁሉ በመመለስ ፈንታ ዝም ብሎ የደስታ ሳቅና የጅ ሰላምታ ብቻ ይሰጣቸው ጀመር። ለሶስናም መጀመሪያ ስትመጣ ካፈጠጡባትና ከገላመጡዋት ሴት ልጆች መሀከል ብዙዎቹ ወደ ጠረጴዛዋ ሄደው ዳንስ በተለይ «አንቺ ልጅ አንቺማ» ን ግሩም አድርጋ የምታውቅ በመሆንዋ አድንቆታቸውን እየገለጹ እንዲሁ ሁሉም ለጠዬቁት መልስ ሳይጠብቁ በላይ በላዩ አዳዲስ ጥያቄ እየደራረቡ ባንድ ላይ ይንጫጩ ጀመር።

በተማሪዎች መሀከል እንዲያ ጭዋታውና ጫጫታው እንደ ደራ፥ ደጃዝማች ሉልሰገድ ተፈራን በጥቅሻ ጠርተው ሶስናና ተከስተ የማን ልጆች እንደሆኑ ጠዬቁት።

«ሶስና፣ የተኮላ ወንዳዬን ያክስት ልጅ ናት፤ ተከስተን ግን ያውቅታልኮ? ብዙ ጊዜ - እኛን ፍለጋ እዚህ ይመጣል» አለ ተፈራ።

«ስሙንና መልኩንማ ብዙ ጊዜ እዬጋበዛችሁት ሲመጣ አውቀዋለሁ፤ ያባቱን ስም አላውቅም እንጂ፥ አሁን የጠዬቅሁህ ያባቱን ስም ነው።»

«እ - አባቱ፥ ጎጃም፥ ደጃዝማች ታምራት ይባላሉ።»

«ጎጃም ደጃዝማች ታምራት? ይህን ስም ሰምተሽ ታውቂያለሽ? » አሉ ደጃዝማች ኑርልኝ ወደ ባልተቤታቸው ወደ እመት አልጣሽ፥ ዘወር ብለው። ደጃዝማች ኑርልኝና ባልተቤታቸው ጎጃሞች ናቸው። እዚያ ከንደራሴዎች ጋር ባለመስማማታቸው እነሱን እንደ ሚመሳሰሉ ብዙ ታላላቅ ሰዎች አዲስ አበባ ደጅ እዬጠኑ በትንሽ ቀለብና አልፎ አልፎ በያመትባሉ በሚያገኙት ጉርሻ ይኖራሉ።

«እንጃ! ትዝ አይለኝም ታምራት ማን? » አሉ እመት አልጣሽ እሳቸውም፥ በበኩላቸው ተፈራን ቀና ብለው እያዩ።

«ያባቱን ስም ነው እንጂ ያባቱን አባት ስምስ አላውቅም። ያባቱን ስምና እናቱን ነው የማውቅ፡ እናቱ እንዲያውም እዚህ ናት። እዚህ እፍል ውሀ ሀኪም ቤት ተቀጥራ ሰራተኛ ነች» አለ ተፈራ የተጠዬቀውን ትቶ ያልተጠዬቀውን።

«እንዲያ እንጂ! እና - የደጃዝማች ምሽት ናቸው፥ አኪም ቤት ተቀጥረው ሰራተኛ የሆኑ? ጆሮ ጉድ አልሰማ አይልምኮ እናንተ! እህ - ህ - ህ - ም! » አሉ እመት አልጣሽ ገርሞዋቸው፡

«እሱ እንኩዋ ምንም አደለም፤ ስለ ተቸገሩ ይሆናል። መቸም ከችግር የማይሻል የለም። ይልቅስ» በለው ደጃች ኑርልኝ ሊናገሩ ያሰቡትን ሳይናገሩ፥

«እኔስ ባንድ ፊቱ - ያው ችግሩ ይሻለኛል፤ ኩራት ራት ነው! አኪም ቤት ሰራተኛ ሆኘ ከምቀጠር ‹ምንተ ማርያም!› ብዬ ለምኘ አልበላም? » ሲሉ እመት አልጣሽ ባላቸውን አቋዋርጠው እዚያ ያሉት ሁሉ ባንድነት ይስቁ ጀመር።

«እኔ እንኩዋ እስዋ አቋዋረጠችኝ እንጂ አሁን ልጠይቅ የነበር የልጁ አባት ጎጃም የት ክፍል እንደሆነ ነው» አሉ ደጃች ኑርልኝ በምሽታቸው አነጋገር ከሌሎች ጋር ሲስቁ ቆይተው።

«ቆዩ ልጥራውና ሁሉንም እሱ የንግርዎታል» ብሎ ተፈራ ሄዶ እነደጃዝማች ሉልሰገድ ጠረጴዛ ያሉት መኩዋንንትና ወይዛዝርት ሊያነገግሩት መፈለጋቸውን ለተከስተ ነገረው። ተከስተ፥ ተማሪዎች ባሸከሙት አድንቆት ላይ ወይዛዝርቱና መኩዋንንቱ የሚጨምሩለት መስሎት ደስታ ልቡን ፈንቅሎ ወጥቶ በፊቱ ላይ መታየት ሲፈልግ እሱ፥ ለመሸሸግ እዬተጣጣረ መኩዋንንቱና ወይዛዝሩ ባሉበት ደረሰ።

«ያገራችን ልጅ መሆንህን ስለ ሰማን፥ መቸም - ሰው አረገ - ብዙ ነውና ምናልባት ዝምድና ይኖረን እንደሁ ጎጃም የወላጆችህን ስምና የሚኖሩበትን አገር ልንጠይቅህ ፈልገን ነበር - ጨዋታህን አስትተን ያስጠራንህ» አሉ ደጃች ኑርልኝ፤ ተከስተ ‹እንዴት ደፍረው አስጠሩ› እንዳይላቸው እዬሰጉ።

«አባቴ ኤልያስ በሚባል አገር ነው የሚኖሩ። ደጃች - ደጃዝማች ታምራት ይባላሉ» አለ ተከስተ ደስታ አግሎት የነበረ ፊቱ በረድ እያለ ሲሄድ በገሀድ እዬታየ።

«ታምራት ማን? »

«ታም - ታምራት - ተገኘ? »

«ይገርማል! እኛም አገራችን - አበሸባ የሚባል እዚያው የኤልያስ ጎረቤት ነው። ኤልያሶችና አበሸቦች ከጉርብትናቸው የተነሳ የጥዋት ቡና እዬተጠራሩ የሚጠጡ አሉ። ስለዚህ ኤልያስ ሕጻንቱን አናውቅ እንደሆነ እንጂ ካዋቂዎቹ እንኩዋንስ ደጃዝማቾችን ተራውን ሰውም ቢሆን ስም ከናባቱ የማናውቀው አይገኝም። ታዲያ እንዴት ካንተ አባት ጋር ሳንተዋወቅ እንደ ቀረን አልገባኝም» አሉ ደጃዝማች አፋቸው ለተከስተ ሲናገር ከሚስታቸው ጋር ያሸሙር አስተያዬት ተለዋውጠው። ደጃች ኑርልኝና ባልተቤታቸው የጥንቱን የነጋዴ ጎረደማን፥ የሁዋላውን ከበርቴ፣ ታምራት ተገኘን ደህና አድርገው ያውቁታል!

«እኔ እንጃ! በትንሽነቴ ነው - ወዲህ የመጣሁ» አለ ተከስተ ከመደንገጡ ብዛት ግንባሩን ላብ አውስቶት።

«የናትህን ወገኖችሽ ታውቃቸዋለህ? »

«እንጃ! የናቴ አባት - ባሻ ጸሀይ አበራ ነው መሰለኝ የሚባሉት የሚኖሩበት አገር ደግሞ - እንዶዳሞ ኪዳነ ምህረት ነው? ማን ይባላል መሰለኝ።»

«አዎ እሳቸው እርግጥ እሳቸው፥ እጅግ ትልቅ ሰው መሰረተ ጌታ መሆናቸውን እኛ ብቻ ሳንሆን፥ ሁሉም የሚያውቀው ነው» አሉ ደጃዝማች ኑርልኝ ተከስተን ፍጥጥ አድርገው እያዩ። ካነጋገራቸውና ካስተያየታቸው ‹ደጃዝማች ታምራት ተገኘ የሚባሉ ትልቅ መኩዋንን ግን ካንተ ራስ ውጪ በኤልያስ ኖረው አያውቁም!› ለማለት እንደ ፈለጉ ለተከስተ ግልጽ ስለ ነበረ ማፈሩ ከሁኔታው ሁሉ እዬታዬ አንገቱን ደፍቶ አይኖቹን ወዲያ - ወዲህ አያባከነ ዝም አለ።

ተፈራ ሉልሰገድ የጉዋደኛውን አፍሮ መድረሻ ማጣት ከሁኔታው ሁሉ ሲመለከት በህጻንነቱ ወዳዲስ አበባ ስለመጣ ዘመዶቹንና የተወለደበትን አገር ደህና አድርጎ አጣርቶ፥ አለማወቁ ያሳፈረው መስሎት፥

«ማንም ቢሆንኮ አገሩን እንደሱ በህጻንነቱ ከለቀቀ - ዘመዶችህንም ሆነ አገሩን ደህና አድርጎ ሊያውቅ አይችልም» አለ ጉዋደኛውን ለመርዳት። «እመዬ እንደ ነገረችኝ» አለ፥ ወዲያው ከተል አድርጎ። «እመዬ እንደ ነገረችን ተከስተ ከጎጃም ወዲህ

የመጣ ገና ትንሽ ህጻን ሳለ በጐልት ዓመቱ ነው። ታድያ በጐልት አመት ማንስ ቢሆን፥ ምን ማወቅ ይችላል? »

«እመዬ? የትኛዋ እመዬ? » አሉ ደጃች ሉልሰገድ ተፈሪን ቀና ብለው በጥያቄ አይን እያዩ ‹እመዬ ነገረችን› ሲል የገዛ እናቱን ያለ መስሎዋቸው።

«የተከስተ እናት። ቅድም ሀኪም ቤት ተቀጥራ ትሰራለች ያልሁዋችሁ። እስዋ ነች ያሳደገችው። ትምህርት ቤት ከገባ በሁዋላ እንኳዋ፥ ምንም ቢሆን እሁድ እሁድ ተለይታው አታውቅም። እሁድ እሁድ ሁልጊዜ ምሳ ግሩም እያደረገች እያሰናዳች፥ ራስዋ ተሸክማ አምጥታ፥ እሱን ብቻ ሳይሆን እኛን ጉዋደኞቹን ጭምር ታበላናለች። ስለዚህ ነው እኛም እንደሱ ‹እመዬ› የምንላት» አለ ተፈራ ጉዋደኛውን ለምደገፍ በጀመረው ንግግር ወዲያው እገረመንገዱን የደመቀችን ጥሩ እናትነት ለመግለጽ።

«የደጃዝምች ምሽት ሆነው - እንዲያው ሙላቱስ ቢጎድል በንጥፍጣፊው አንድ አሽከር ማሳደር ተስኖዋቸው ነው - እንጀራ በራሳቸው ተሸክመው ተማሪ ቤት የሚመላለሱ? እህ - ህ - ህ - ህም» አሉ ወይዘሮ አልጣሽ።

«እስዋኮ፣ ሞ - ሞግዚቴ ናት እንጂ እናቴ አደለችም» ሲል ተከስተ አንገቱን ከደፋትበት ቀና አድርጎ የተናገረውን ከተናገረ በሁዋላ ብቻ ጆሮው የሰማው እንጂ እሱ አስቦ እንዳልተናገረው ሁሉ በፊቱ ላይ ይታይ የነበረውን ድንጋጤ በቃላት ለመግለጽ ያስቸግራል። መቸም አእምሮው አስተካክሎ በሚያስብበትና በሚያመዛዝንበት ጊዜ ቢሆን ኖሮ እንዲያ ያለ ጉድ እንዲያ ያለ የጉድ ጉድ ባልተናገረ! እንዲያ ያለ ከጴጥሮስ ክህደት የከፋ የክህደት ክህደት ባልከዳ! ነገር ግን አእምሮው በትክል የሚሰራበት ጊዜ አልነበረም። በብዙ የታላላቅ መኩዋንንት ልጆች መሀከል የመሰረተ ጌታ ደጃዝማች ልጅ መሆኑን ጉዋደኞቹንም ሆነ ሌሎቹን ለማሳመን በዬምክንያቱ ሲናገር ሲናገር ኖረና በመጨረሻ፥ ያን አፉ ሁልጊዜ ሲናገር ጆሮው እዬሰማ የኖረውን እሱም እንዳመነበት ሁሉ ኮርቶ ተቀምጦ፥ ነበር። ታዲያ፥ ድንገት እኒያ ደጃዝማች ኑርልኝና ሚስታቸው የሰይጣን መላክተኞች ሆነው ያባቱን ትንሽነትና የሱን ውሸታምነት ሲያገልጡ በትምህርት ቤት በነበረበት እድሜው ሁሉ ሲገነባው የኖረውን የክብር ቦታ ከሁሉ ከፍ አድርጎ አቁሞ ሽቅብ የሚያሳየውን የበላይነት ቦታ ሊንዱበት ታጥቀው የተነሱ መስሎ ስለ ተሰማው ልቡ ተሸብሮ አእምሮው ታውኮ በትክክል ማሰብ አቅቶት ነበር። ስለዚህ ያ ጊዜ የሚያደርገው ቅጡ ጠፍቶት እንዲያው እንዲሁ ደመነፍሱን እኒያን ከፉ ጠላቶች ተከላክሎ የሚመልስበት ማናቸውንም አይነት መከላከያ እነሱን መቶ የሚያሸንፍበት

ማናቸውንም አይነት መሳሪያ የሚፈልግበት ነበር! አባቱ መሰረተ ጌታ ደጃዝማች እንደሆኑ እሱም ለሳቸው ሲናገረው የኖረው እውነት እንደሆነ የሚቆይበትን መላ ፈጥሮ እኒያን እሱን ለማሳፈርና ለማዋረድ ከሰይጣን ተልከው ያለቦታቸው የተገኙ ባልና ሚስት አሳፍሮ አዋርዶ ወደ መጡበት ለመመለስ የሚችልበት ዘዴ አጥቶ አሳቡ ወዲያ ወዲህ እዬባከነ የሚፈልግበት ጊዜ ነበር! በዚህ የሚረዳው ዘመድ የሚረዳው ጉዋደኛ ቢያገኝ እንዴታ ከሞት መንጋጋ ፈልቅቆ እንዳወጣ ቆጥሮ የድሜ ልክ ባለ ውለታ የድሜ ልክ ባለዳው ሆኖ በኖረ! ታዲያ እንዲህ ባለ ጭንቅ ውስጥ ሳለ ያባቱን መሰረተ ጌትነትና ደጃዝማችነት የሚያስመሰክርበት ትንሽ ማስረጃ አጥቶ ሲጨነቅ ከኒያ ሊያዋርዱት ታጥቀው ከተነሱ ጠላቶች የሚከላከልበት መሳሪያ የሚያቀብለው ዘመድ አጥጦ ሲጨነቅ ከዚያ ጭንቅ የሚያመልጥበት ትንሽ መውጫ ቀዳዳ አጥቶ ሲቸገር ያ የዋህ ጉዋደኛው ተፈራ እንዲያውም ይግረምህ ብሎ ‹በንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ› እናቱ ሀኪም ቤት ተቀጥራ እዬተሸከመች እያመላለሰች እሱንና የትምህርት ቤት ጉዋደኞቹን የምትመግብ ተራ ሴት መሆንዋን እዚያ በጠላቶቹ ፊት ተናገረበት! ያን ጊዜ ነው ተከስተ ታውኮ የነበረ አእምሮው ጭራሹን አፉን መዝጋት በማይችልበት ደረጃ ደርሶ፥ እንዲሁ ልጉዋም የተለቀቀለት አፉ እንዳመጣው ‹እስዋኮ ሞግዚቴ ነች እንጂ፥ እናቴ አደለችም!› ያለ እንዲያው እንዲሁ አፉ እንዳመጣ የዘላበደ! የተከስተን መዘላበድ ሲሰሙ፥

«እ - እሱ፥ እንኩዋ ይሻላል! እህ - ህ - ህ - ህም! » አሉ እመት አልጣሽ።

«እመዬ እናትህ አደለችም? ይገርማል! እኛ ሁላችንምኮ እናቱ ትመስለን ነበር! እንኩዋንስ ሞግዚት - ከናቶቹም መሀከል እንደስዋ ለልጆቻቸው የሚጨነቁ ቢኖሩ፥ በጣም ጥቂት ይሆናሉ! » አለ ተፈራ ገርሞት፥ ተከተንም፥ እዚያ የተቀመጡትን ወይዛዝርና መኩዋንንትም እያለዋወጠ እያዬ።

## ምእራፍ ሀያ ዘጠኝ

## የጭንቅ ሳምንት

ተከስተና ተፈራ፥ ከነደጃዝማች ሉልሰገድ ጠረጴዛ ተመልሰው፥ ተፈራ ዳንሱን እንደገና ለማስጀመር ወደ ሙዚቃ ማጫወቻ ተከስተ ወደ ጉዋደኛው ሂዱ። ከዚያ

ሙዚቃው ተጫዋቾቹን ለዳንስ መጥራት ሲጀምር ልጆቹ ተነስተ ወንድና ሴት ወንድና ሴት ባንድ እዬተጣጣሩ አዳራሹን ሞልተው ይዘው፥ ይተሙ ጀመር።

ያ ሙዚቃ ለሁለተኛው ዙር ዳንስ መጀመሪያ፥ እንደ መሆኑ ቀስተኛ ለዘብተኛ ነበር። ልክ እንደ ሜዳ ላይ ውሀ ሙላት ብሎ ሲሄድ ስሜትን እንዲያ በጸጥታ እያባበለ ይዞ የሚሄድ እንደ ሰመመን እያዋዛ ይዞ የሚነጉድ ነበር! ለተከስተ ብቻ እንዲያ አልነበረም። ለተከስተ የሚሰማው የሪታ የዋይታ፥ የግዚኦታ ድብልቅልቅ ነበር! ልክ ሰው ሲሞት ባፍላ ልቅሶ እንደሚሰማው ጆሮ የሚያደነቁርና ራስ የሚያዞር የጩኸት ድብልቅልቅ! ስለዚህ እግሮቹ የሙዚቃውን ጸጥተኛ ጉዞ መከተል ትተው፥ በራሱ ውስጥ የሚሰማውን የጩኸት ድብልቅልቅ እዬተከተሉ ሲደናገሩና ሲደናበሩ፥

«ተከስተ ዛሬ ምን ሆነሀል? ደህና አደለህም? » አለች ጉዋደኛው አልማዝ፥ በላይህን ርግጫው ስለ ባሰባት ዳንሱን አቋዋርጣ ቆማ።

«ምነ ምን ሆንሁ? ደህና ነኝ» አለ ፈገግ ለማለት እዬሞከረ። ነገር ግን ደህና አለመሆኑን ሁኔታው ሁሉ ይናገርበት ነበር።

«የለም ደህና አደለህም መሬቱን ትተህ በግሬ ላይ ነውኮ የምትጨፍረው! »

«ረገጥሁሽ? ‹ሶሪ› ይቅርታ፥ አድርጊልኝ አልታወቀኝም።»

«እስቲ ና ወደ ዳር እንውጣ» ብላ ይዛው ዳር ወጥተው እንደ ቆሙ፥

«ቅድም ከዚያች - ማነው ስምዋ? ሶስና ከምትሉዋት ጋር ስትደንሱ ግሩም ነበራችሁ፤ እና ምናልባት - አይን በልቶህ ወይም አሁን እሱዋ ከሌላ ጋር ስትደንስ አይተህ፥ ቀንተህ እንደሆነ! እ? » አለች አልማዝ አፍዋን ስለሱ ቅናት ሲናገር የራስዋን ቅናት በሚገልጽ ያሽሙር አስተያየትና ያነጋገር ስልት። ተከስተ እንኩዋንስ፥ ሊመልስላት የተናገረችውን አስተካክሎ የሰማ አይመስልም ነበር። አይኖቹ ሳይረግቡ ቦዘዝ እንዳሉ በሶስና ላይ ተተክለው ከጉዋደኛዋ ጋር ስትደንስ በሄደችበት ሁሉ እየተከተሉ የሚያዩ መስለው አይነ - ህሊናዋ የሚመለከተው ከነደጃዝማች ኑርልኝ ጋር ክርክር ገጥሞ እናቱን የካደበት ስእል ነበር።

አልማዝ አብራው ቆማ እያነጋገረችው ለመልስ እንኩዋ እንደማትበቃ እሱዋን ዝም ብሎ አይኖቹ ሶስና በሄደችበት እዬተከተሉ በተመስጦ ሲመለከቱ ስታይ እንዲያ ያቦዘው እንዲያ ይሉኝታውን እስኪያጣ ያደነዘዘው ‹የሶስና ፍቅር ነው› ብላ አምና እንዲህ ያለውን ስድብ እንዲያ ያለውን ውርደት መታገስ አቅቶዋት ልታግደው

የማትችል የቁጣ፥ ፍላት ገንፍሎ ፊትዋን ሁሉ ሲያኮማትረው ይታ ነበር። ወዲያው እዚያው ባለበት እንደ ቆመ ትታው ወደ ጠረጴዛዋ ሄዳ ተቀመጠች። እሱም ስትሄድ ሲያያት ከስዋ ጋር እንደ ተቆራኘ ሁሉ አስቦ ሳይሆን እንዲሁ በንቅልፍ ልቡ እንደሚሄድ ግብኑን ተከትሎዋት ሄዶ አጠገብዋ ተቀመጠ።

«ምን ትፈልጋለህ? » አለችው፣ እንደ ተቆጣች።

«ምን እፈልጋለሁ? እ - ምንም አልፈግም። ብቻ አሞኛል አልማዜ» አለ ተከስተ በጥሞና። ምንም እንኳዋ ቁጣዋ በፊትዋ ሲነድ በግልጽ ቢታይ ለተከስተ አይኑ እንጂ አሳቡ ከሱ ጋር ስላልነበረ የታዬው አይመስልም።

«የታመመ እቤቱ ሄዶ ይተኛል እንጂ ሰው እዬተከተለ ‹ቦዘር› አያረግም ካመመህ - እቤትህ ሄደህ መተኛት ነው! ኦኬ? » አለች አልማዝ።

«አንቺስ? አንቺን ሳላደርስ? »

«ሀ! የኔ አሳቢ! ‹ኒቨር ማይንድ› እኔ ከልጆች ጋር እሄዳለሁ! »

«ኦኬ እንግዲያ ‹ቬሪ ሶሪ› አልማዜ! ስላመመኝ ነው፤ ባይ ባይ» ብሎዋት ነፋስ ተቀብሎ እንደሚመለስ ቀስ ብሎ ወጥቶ ወደ ትምህርት ቤቱ ሄደ። ሁለተኛዉ ዙር ዳንስ ተፈጽሞ ልጆቹ ሁሉ ወደ ዬጠረጴዛቸው እዬተመለሱ እንደ ተቀመጡ ተፈራ ሉልሰገድ ተከስተን ባይኑ ፈልጎ ስላጣው፥ ወደ አልማዝ ጠረጴዛ ሄዶ ጠየቃት።

«እኔ እንጃለት! ‹አመመኝ› ሲል ነበር፤ ወደ ትምህርት ቤቱ ሄዶ ይሆናል» አለች አልማዝ። ቁጣዋ ገና ስላልበረደ ስለ ተከስተ መነጋገር የማትፈልግ መሆንዋን ሁለመናዋ ያሳይ ነበር።

«ቅድም ደህና አልነበር? » አለ ተፈራ።

«ያቺ - ከዶሮ ማነቂያ ይሁን ከ - ውቤ በርሀ ፈልጋችሁ ያመጣሁዋት ምናቃለሁ! ምናም አዙራበት ይሆናላ! ህእ! እስዋ ገና - ብዙ ሰው ሳታሳምም ብትቀር ምን አለች ትለኛለህ! »

«ኡስ - ! ኧረ በናትሽ ዝም በይ! » አለ ተፈራ ጠቁዋሚ ጣቱን ባፉ ፊት ደቅኖ። ብቻ ደግነቱ ጫጫታው በዝቶ ስለ ነበረ፥ ምንም እንኳዋ አልማዝ ድምጽዋን ከፍ አድርጋ ብትናገር ከተፈራ በቀር ሌሎች የሰሙዋት አይመስልም።

ያን ሌሊት ተከስተ፥ እንቅልፍ የሚሉት ባይኖቹ አልዞረም። ያን ሌሊት አይኖቹን በጨለማው አፍጦ፥ አልጋው ላይ በጀርባው እንደ ተንጋለለ ደጃች ኑርልኝና ምሽታቸው ወይዘሮ አልጣሽ እንደ ወንጀለኛ እፊታቸው አቁመው የተወለደበትን አገርና የወላጆቹን ስም እስከ አያት ቅማቶቹ እያስቆጠሩ ሲመረምሩት የነበረበት የቁም ስቃይ ይታዬዋል! ‹የደጃዝማች ልጅ ነኝ› በማለቱ ደጃች ኑርልኝና ምሽታቸው ባሽሙር አይን እየተያዩ ሲቀልዱበት ሲላገዱበት የተሰማው እፍረት የተሰማው ውርደት ይታዬዋል! ከዚያ ተፈራ ሉልሰገድ እናቱ ሀኪም ቤት ተቀጥራ የምትሰራ ለሱና ለጉዋደኖቹ እንጀራ በራስዋ እየተሸከመች የምታመላልስ ተራ ሴት መሆንዋን ሲናገርበትና እሱ ተጨንቆ የሚጨብጠው የሚረግጠው የሚሾልክበት ትንሽ ቀዳዳ አጥቶ እናቱን ‹ሞግዚቴ ናት እንጂ እናቴ አደለችም› ብሎ ሲሙዋገት እናቱን ሲክድ እዬተለዋወጠች ትታየዋለች! ደመቀች እፊቱ ቁጭ ብላ ስላገርዋ ስታጫውተው ደመቀች እቸምቢላ አስራ ወይም ካንዱራ ጭዋታ ስታስተምረው ደመቀች ወይዘሮ ጽጌ መተዋት ወይም እሱን ረግመውት ስታለቅ ደመቀች ዝፈኝልኝ ብለዋት ስትዘፍን ደመቀች ‹አልበላም› ብሎኝ ሲቅበጠበጥ በታቦቶች ሁሉ እያማጠነች ስታጎርሰው ደመቀች የሁድ ድግስዋን ይዛ ትምህርት ቤት መጥታ እሱና ጉዋደኞቹን ዘበኞች ጭምር እየተሻሙ ሲበሉ ገለል ብላ ተቀምጣ እዬሳቀች ስትመለከታቸ ትታዬዋለች! ከዚያ ‹ሞግዚቴ ናት እንጂ እናቴ አደለችም› ማለቱን እናትነትዋን መካዱን ስምታ ከፍ፥ ሌላውን ዝቅ አድርጋ አጣማ በትዝብት አይን ዘቅዝቃ እያዬች ‹አየ ጉድ! እንዲያ ራሴን ክጄ ሳምንህ ካድሽኝ? ታዘብሁህ!› ስትለው ያንጊዜውኑ እዚያ፥ በግዘፈ - ስጋ እዚያ በውን ቆማ የምትዘልፈው መስሎት ይደነግጥና ከተንጋለለበት በርግጎ ተነስቶ ቁጭ ሲል ያ ሲያስቸግረው የነበረ ነፍስ ያለው ስእል ሁሉ ያ፥ የስእል ሰራዊት ሁሉ ከፊቱ ይጠፋል! ከዚያ እንዲያ ቁጭ እንዳለ የተቀመጠበትን አልጋ በጐልት እጆቹ ጥፊ እየመታ ‹ውሻ ርኩስ፥ አሳማ ነኝ፤ አዎ ሰው አደለሁም። አሳማ ነኝ! እስቲ ምን - ማን አስገድዶኝ ነው እንዲያ ያለ - ርኩስ ነገር የተናገርሁ?› እያለ ራሱን ሲወቅስ ቆይቶ እንደገና በጀርባው ሲንጋለል እንደገና ያ ሲያየው የቆዬው የስእል ሰራዊት ስእሉን እየተነባበረ ወይም እግር በራስ እዬተመሳቀለ ይመጣበትና ደግሞ ተነስቶ ቁጭ ይላል! እንዲህ በተፈራ ሉልሰገድ ግብዛ ያመሸበት ፈተና በክፉ መልኩ ተስሎ ተስሎ መጥጦ እያስፈራራው አንድ ጊዜ በሆዱ ሲንበለበል አንዳንድ ጊዜ በጀርባው ሲንጋለል ሌላ ጊዜ በጎኑ ሲጋደም ከዚያ በርግጎ ሲነሳ፥ ላንድ ትንሽ ቅጥበት፥ እንኳዋ እረፍት ሳያገኝ መንጋት አይቀርም ነጋ። ጥዋት ተፈራ፥ ሉልሰገድ እግብዣው ካደረበት መጥቶ፥ ተከስተን እንቅልፍ ያልዞረባቸው አይኖቹ አባብጠው ፊቱ ሁሉ ተጎሳቁሎ ስላገኘው፥ እውነት የታመመ መስሎት ደነገጠ።

«ትናንት ማታ ከጭዋታው ታመህ መውጣትህን አልማዝ ነግራኝ አዘንሁ፤ ዛሬስ አልተሻለህም? » አለ ተፈራ።

«አሞኛል፤ አሁንም በግድ ነው ተነስቸ የመጣሁ» አለ ተከስተ።

«ታዲያ እያመመህ ለምን ተነሳህ? አሁንም ሂድና ተኛ፤ ላስተማሪው እኔ እነግርልሀለሁ።»

«ስነሳ የሚሻለኝ መስሎኝ ነበር አልተሻለኝም። ስለዚህ - እውነትህ ነው፥ ሄጄ ልተኛ መሰለኝ። ብቻ ላስተማሪው እንድትነግርልኝ አደራህን እንዳትረሳ! » ብሎ ወደ መኝታ ክፍሉ ለመሄድ የቃጣ ከመሰለ በሁዋላ፥

«ደግሞ አንድ ሌላ ነገር» አለ መለስ ብሎ።

«ምን? » አለ ተፈራ።

«ትናንት ማታ ስለ እመዬ የተናገርሁትን እስዋም ሆነች ሌላ ሰው እንዲሰማው አልፈልግምና ለማንም እንዳትናገር አደራ! »

«ምንድነው እሱ? »

«ሞግዚቴ ናት እንጂ - እናቴ አደለችም» ያልሁትን አለ ተከስተ እኒያን የተረገሙ ቃሎች መድገሙ አፉ እየፈራ።

«እ - የላከኸኝ ይመስል ለምን እናገራለሁ? አልናገርም» አለ ተፈራ ፈገግ ብሎ።

«አይ እንዲያው በጭዋታ ላይ ‹ተራ ነገር ነው› ብለህ እንዳትናገር ላስጠነቅቅህ ብዬ ነው። አዬህ? እስዋ ልክ እንደ ልጅዋ ስለምታየኝና - ለሚጠይቃት ሁሉ ‹ልጄ ነው› እያለች ሰለምትናገር እኔ - ‹እናቴ አደለምች› ማለቴን ብትሰማ - በጣም ነው ‹ሶሪ› የምትሆን፤ አይመስልህም? »

«እውነት ነው ‹ሶሪ› ትሆናለች።»

«እንደምታውቃት ለኔ በጣም - ‹ካይንድ› ስለሆነች ‹ሶሪ› እንድትሆን አልፈልግም ‹ዩ አንደርስታንድ?›

« ‹ያ አንደርስታንድ› በኔ በኩል ይወጣል ብለህ - ‹ኔቨር ማይንድ› አትስጋ ይልቅ እሁን ሂድና ተኛ» አለ ተፈራ የክፍል መግቢያው ጊዜ ደርሶ ስለ ነበረ ወደዚያ እዬቸኮለ።

ተከስተ ካንድ ወር ያክል በፊት ብርቱ ጉንፋን ታሞ ስለ ነበረ፥ እንዲያ ያለ ተላላፊ በሽታ የታመሙ ተማሪዎች እስኪድኑ ድረስ በህብረት ከሚተኙበት መኝታ ቤት ወደ ብቻኛ ክፍል ተዛዋረው ሲተኙ እንዲቆዩ ቀዋሚ ትእዛዝ ሰነበተ ኪዳነ በሁዋላም ‹ዛሬ ነገ› ሲል ወደ ህብረቱ መኝታ ቤት ገና አልተመለሰም ነበር። ስለዚህ ወደዚያ ብቻኛ መኝታ ቤቱ ተመልሶ የቀን ልብሱን አውልቆ፥ የሌሊቱን ለብሶ፥ ለመተኛት ቢሞክር ያካላቱ እያንዳንዱ ህዋስ ሁሉ በያለበት ቆሞ እንኩዋንስ እንቅልፍ ያስብ እረፍት ማግኘት ስላልቻለ ‹መንፈስ አሳርፎ እንቅልፍ እንዲመጣ ያደርጋል› ሲባል የሰማውን ዘዴ ሁሉ መሞከር ጀመረ። ‹በጀርባ ተኝቶ አይንን እጣራ ላይ ባንድ ቦታ አሳርፎ ወደ ውስጥ አጥልቆ እዬተነፈሱ እንደገና ወደ ውጭ አስረዝሞ ሲተነፍሱ ትንሽ ጊዜ መቆዬት! ባሳብ ሰፊ ባህር ፈጥሮ፥ እዚያ ባህር ውስጥ እጅንና እግርን አዝናንቶ እዬቀዘፉ መዋኘት! ክንፍ አውጥቶ ጸጥ፥ ሰጥ ባለ አዬር ውስጥ መንሳፈፍ! የሻከረን ስሜት የሚያለዝቡ ውብ ውብ ግጥሞች እዬመረጡ መድገም!› ነገር ግን ሁሉ አላገለገሉትም። ግጥሞች ፈልጎ ሊደግም ሲጀምር ‹ሞግዚቴ ናት እንጂ እናቴ አደለችም› ያላቸው ቃሎች እመሀከል ገብተው ድንቅር! ባህር ገብቶ ሊዋኝ ወይም ክንፍ አውጥቶ ባዬር ሲንሳፈፍ ሲሞክር የናቱ ስእል መጥቶ በፊቱ ድቅን! እያሉ ስላስቸገሩት ሁሉንም ጣጥሎ ተነስቶ ቁጭ አለ። ከዚያ እንዲያውም ተነስቶ በክፍሉ ውስጥ ወዲያ - ወዲህ ይል ጀመር። ነገር ግን የልቡን ጭንቀትና ያእምሮውን ሁከት የሚያስታግስለት መስሎት የፈጠረው ዘዴ ላንድ አፍታ ያገለገለው ቢመስልም፥ ተመልሶ እዚያው ከጭንቀቱና ከሁከቱ ጋር ይገኛል። ያነለት ቁርስም ምሳም አፉ አልነካም። ትኩሳት ስለ ነበረው ውሀ ብቻ ሲጠጣ ውሎ አመሻሽ ላይ እንዲያ ከያቅጣቸው ሲያጠናፍረው አድሮ የዋለው ያሳብ ውሽንፍር ትንሽ በትንሽ እዬተቀነሰ ሄደና ትኩሳቱም በዚያው መጠን በረድ በማለቱ ማታ ትንሽ እህል ቀመሰ። ሌሊቱን እንቅልፍም ትንሽ ተኛ።

በተከታዩ ቀን በራሱ ውስት ይንጋጋ የነእብረው ያሳብ መንጋ፥ ያ በራሱ ውስጥ ይንጫጫ የነበረው ስራተ - ቢስ ያሳብ ሰራዊት ወደይመጣበት ርጥ ብሎ ሄዶ አእምሮው መጥራትና አሳቡን በተራ ስነ - ስራት አስይዞ ማሰብ ሲጀምር ማሰብ ሲጀምር እናቱን የካደበትን ምክንያት ቢፈልግ፥ ያባቱን ደጃዝማችነት የሚያስተባብሉ ሰዎች ድንገት ስለገጠሙት በድንጋጤ የናቱ ተራ ሴት መሆን ያባቱን ደጃዝማች

አለመሆን የሚመሰክርበት መስሎት የራሱን ከንቱነት ግብዝነቱን ለመሸፈን የዘላበደው ከመሆኑ በቀር ሌላ ምንም ምክንያት ሊያገኝ አልቻለም። ከንቱነቱን ለመሸፈን አባቱን ታምራት ተገኘን ከነጋዴ ጎረደማንነት አውጥቶ በደጃዝማችነት የክብር ቦታ ባስቀመጠበት ለማቆየት እናቱን ከእናትነት ወደ ሞግዚትነት ደረጃ ማውረድ የሚረዳው ስለ መሰለው ብቻ ያደረገው ከመሆኑ በቀር ሌላ ምንም ምክንያት አልነበረው!

‹ከንቱነቱ ብቻ ግብዝነት ብቻ ነው፤ ሌላ ምንም ምክንያት የለ!› አለ አልጋው፥ ጠርዝ ላይ እንደ ተቀመጠ፥ የማያዩ አይኖቹን ፊት ለፊት ተክሎ እንደ ተቀመጠ የናቱ ስእል ባይነ - ህሊናው ፍት ብቅ አለ። ያ ስእል ያዘነ የተከዘ የፊቱ ቀለም ተፈግፍጎ እንደ ተጠረገ የደበዘዘ ነበር!

«እመዬ! » አለ በሻከረ ዝቅተኛ ድምጽ ስእሉን እዬተመለከተ።

«ለምን እመዬ ትለኛለህ፥ እናትህ ሳልሆን? እኔኮ ሞግዚትህ ነኝ እንጂ እናትህ አደለሁም! » አለ ስእሉ፤ አንገቱን በትካዜ ከደፋበት ወደ ተከስተ ቀና ሲያደርግ ቅርታና አሽሙር ባንድነት የተዋሀዱበት ፈገግታ የሚመስል ነገር፥ በደበዘዘ ፊቱ ላይ እዬታዬ። ተከስተ፥ እውነት እናቱ እዚያ በግዘፈ ስጋ ቆማ የምትወቅሰው መስሎት እፍረት ተሰማውና ሳያስበው አይኖቹን ፊት ለፊት ከተከለበት መልሶ መሬቱን እዬተመለከተ ዝም አለ።

«አይዞህ ቀልዴን ነው» አለ ስእሉ ወዲያው ከተል አድርጎ። «ርሳው ግዴለም፥ አልቀዬምም። ደንግጠህ ድንገት የተናገርኸው እንጂ አስበህ የተናገርኸው አለመሆኑ ይገባኛል። ስለዚህ አይዞህ› ....... ብሎ ማጽናኛውን ሊቀጥል ሲል፥

«ተኩ ምን ሆንክ? » አለ ከተከስተ ጉዋዋደኞች አንዱ ተሾመ ወልደዬስ፥ ድንገት ገብቶ። ተከስተ ከንቅልፉ እንደ ተቀሰቀሰ አይኖቹን መላልሶ አርገበገበና፥

«እ? ደህና ነኝ ተሸሎኛል» አለ።

«ምንድነው ያመመህ? »

«ምን እንደሆነ እንጃ ራሴን ያመኛል፥ ‹ፊቨርም› - ነበረኝ። አንተ ለምን ‹ክላስ› አልገባህም? »

«ትናንት ማታ ‹እትፉ› ግብዣ ሲያቀብጠኝ በርበሬ በርከት አድርጌ በልቼ ‹እስቶማኬን በርን› ስላደረገኝ፥ ብዙ ውሀ ስጠጣ ጊዜ መሰለኝ በያምስቱና - በያስሩ

ደቂቃ ወደ ‹ደብልዩሲ› መሄድ አስፈለገኝና ስወታ ስገባ ‹ቲቸሩ› አይቶ ‹ምን ሆነህል?› ቢለኝ ነገርሁት። ከዚያ ‹እውጭ ቆይ› አለኝ።

«ማች በርበሬ እስቶማከም ሌላም ነገር ሁሉ ያሳምምማል።»

«ለመሆኑ ሌላ የታመመ ልጅ አለ? ወይስ አንተ ብቻ ነህ? » ሌላ የታመመ እንኩዋ የለም፤ ሌሊቱን ሙሉ ስንጨፍር ስላደርን እዚያ ያደሩት የኛ ‹ክላስ› ልጆች ሁሉ እንዲያው ለስሙ ነው እንጂ ገብተው የተቀመጡ ምንም አይሰሙ። ሁሉም በ ‹ዴክሳቸው› ላይ ‹ሄዳቸውን› እዬደፉ ‹ስሊፕ› ነው የሚያደርጉ።

«ታዲያ - ‹ቲቸሩ› ዝም ይላል? ማለቴ - ‹አንግሪ› አይሆንም? »

« ‹አንግሪ› ቢሆን ማን ሰምቶት! »

«እና - ሌሊቱን ሙሉ ስትጨፍሩ ነዋ ያደራችሁ! » አለ ተከስተ የጭፈራው ወሬ ለልቡ ጊዜያዊ ሙቀት የሰጠው መሆኑ ከፊቱ እዬታዬ።

«እንዲሁ አነጋነው! ያች የተኮላ ዘመድ ሶሳና - እሱዋን አይደክማት! ልጁን ሁሉ በየተራ ስታሳብደው አደረች! »

«ታዲያ - ልጁ ሁሉ ከስዋ ጋር ሲጨፍር - ሌሎች ‹ገርሎች› ምንም አላሉም? ማለቴ አልቀኑም? »

« ‹አልቀኑም ወይ› ትላለህ? ሊበሉዋት ምንም አልቀራቸው።»

«አንተን ብዙ ጊዜ አስጨፈረችህ? »

«እኔ ሁለት ጊዜ ብቻ ነው ከስዋ ጋር የጨፈርሁ፤ መቸስ - ይዛህ ስትሄድ መሬት የምትነካ አይመስልህምኮ! ምን ልንገርህ፤ አንተማ አይተህት የል? እንዲያው - ባዬር ላይ ‹ፍላይ› የታደርግ ነው የሚመስልህ! ከዚያ በሁዋላ፥ ፍቅርተ አፍዋን አውጥታ ‹እንደገና ከስዋ ጋር ልጨፍር ያልህ እንደሆነ በጨለማ ወጥቼ ነው የምሄድ› ስትለኝ ጊዜ - ‹ኦኬ› ብዬ እንደገና ወደስዋ አልሄድሁም። ፍቅርተ - ‹ማድ› እንዳትሆን ብዬ፥ ‹ይኖው ዋት አይ ሚን?› »

«ያ፥ አይ ኖው ዋት ዩሚን።»

«ተሾመ ሲያጫውተው ቆይቶ ከሄደ በሁዋላ ተከስተ ላጭር ጊዜ ባለፈው ሌሊት እግብዣው ላይ ወንዶች ጉዋደኞቹ እየተፈራረቁ ከሶስና ጋር ሲያብዱ ሴቶች ልጆች ከስዋ ቀንተው ሲናደዱ ሲሄድ ዝም ብሎ ሲመለከት ስእሉን ስሎ ባይነ - ህሊናው ፊት ሲሄድ ዝም ብሎ ሲመለከት ቆዬ። ብቻ ያ ተሾመ ያወራው አብሮት የቆዬ ላጭር ጊዜ ነው። ወዲያው አሳቡ ወደናቱ ተመለሰ። መሰንበቻውን በመም አመካኝቶ ከመኝታ ክፍሉ አልወጣም። ምንም አንኩዋ ባእምሮው ተነስቶ የነበረው ሁከት ጸጥ ቢልና አሳቡን ተራ አስይዞ ማሰብ ቢችል ስለናቱ የተናገርውን የሚያምርበትና ከገባበት ማጥ የሚወጣበት መንገድ አስቦ ሲያገኝ ባለመቻሉ የሚያደርገው ቅጡ ጠፍቶት ይጨነቅ ጀመር።

‹እንዴት አድርጌ ነው አይንዋን የማየው?› አለ ባሳቡ አልጋው ጠርዝ ላይ እንደ ተቀመጠ፥ አይኖቹን ሳያረግብ ፊት ለፊት ተክሎ ፡

‹ማን ይነግራታል? ተፈራ ለስዋም ሆነ ለሌላ ሰው እንዳይናገር አስጠንቅቄዋለሁ፤ ደጃች ሉልሰገድና እኒያ ጎጃሞችም አያውቁዋት› አለ እንዲያ እንደ ተቀመጠ ትንሽ ሲያስብ ቆየና። ‹ነገር ግን ደጃች ሉልሰገድ - እስዋን ባያውቁዋትም ለልጆች ሊያወሩ ይቻላሉ› አለ አሁንም ሲያስብ ቆይቶ። ‹አዎ እሳቸው ናቸው ወሬውን የሚያዛምቱት፤ ከዚያ እስዋም ትሰማለች። እንዲያውም ደጃች ሉልሰገድ እንኩዋንስ የማያውቁትን የሚያውቁትን ሰውም ቢሆን በስሙ ከመጥራት በስራው መጥራት የሚቀናቸው እንዳሻ ተናጋሪ ናቸው። «ያ የገሌ አሽከር ያ የገሌ ሾፌር፥ ያች የወይዘሮ እገሊት ወጥ ቤት፥ ያች የወይዘሮ እገሊት ገረድ» ማለት ይወዳሉ። ስለዚህ - ያች «የተከስተ ሞግዚ» እያሉ እዚህ እሳቸው ዘንድ ለሚሰበሰበው ተማሪ ሁሉ መናገራቸው ስለማይቀር ትሰማለች! ታዲያ ምን ማድረግ ይሻለኛል? መድህኒቱ - ያ ነገር ማለቂያ አጣ እንጂ እሱ ቶሎ ቢያልቅ ኖኦር አይንዋን ሳላይ ዝም ብዬ መሄዱ ነበር! ብቻ አላልቅ ማለቱ ነው የከፋ።

ለተከስተና እንደሱ ከመጨረሻ ክፍል በትምርታቸው ለበረቱ አራት ልጆች ካናዳ ነጻ ትምርት (ስኮላሽፕ) ተገኝቶላቸው ወደዚያ እንደሚሄዱ ከተነገራቸውና ለጉዞ የሚያስፈልገውን መሰናዶ ከተጀመረ ወራት አልፈዋል። ብቻ ባንዳንድ ጥቃቅን ምክንያት የሚነሱበት ቀን ሲጎተት ቆይቶዋል። ተከስተ ነሳ ትምርት የማግኘቱን የምሥራች የሰማ እለት ለናቱ ሊነግራት ካሰበ በሁዋላ የሱ የምስራች ለሱዋ ከፉ መርዶ እንደሚሆንባትና አጥብቃ እንደምታዝን ስላወቀ ልቅሶውና የሚያይበት ጊዜ አጭር እንዲሆን የሚነሳበትን ርግጠኛ ቀን ሲያውቅ አንድ ቢበዛ ሁለት ቀን ቀደም ብሎ

ሊነግራት ወስኖ ሸሽጎዋት ነበር። አሁን መሄዱን ነበር የሚፈልገው ብቻ - መቸ ወይም እንዴት እንደሚያልቅ እግዜር ይወቀው።

መቸም፥ ነፍስ ካወቀ ጀምሮ በመም አመካኝቶ፥ እዚያ እመኝታ ክፍሉ እስከ ሰነበተበት ጊዜ ድረስ እናቱ ለሱ ያላት ፍቅር ሀያልነት ለሱ፥ ከናትነትዋ ሌላ ጥሩ ጉዋደኛ ጥሩ አስተማሪ መሆንዋ እያንዳንዱ እንዲያ ጎልቶ እንዲያ ጠርቶ ታይቶት አያውቅም! ብርቱ ያእምሮ መናወጥ እሱ የሚያስከትለው ብርቱ የህዋሳት ሁሉ መናጋት ከከባድ እንቅልፍ ማንቃት አልፎ ከበሽታም ያድናል! ተከስተ ከዚያ ብርቱ ያእምሮ መናወጥ በሁዋላ ከረዥም ጊዜ እንቅልፉ ነቃና የናቱን ታላቅነት እንዳያይ አውሮት የናትነት ፍቅርዋ እንዳይሰማው አፍዝዞት አደንዝዞት ከኖረው የከንቱነት በሽታ ዳነና፥ መሰንበቻውን ወደ ሁዋላ ተመልሶ እናቱና እሱ እደጃዝማች አሰፋ ተጫኔ ግቢ ሳሉ እዚያች እትንሽ ክፍላቸው ተቀምተው ያወሩት ያደርጉት የነበረው ሁሉ ተፈሪ መኮንን ትምርት ቤት ከገባ በሁዋላም እስኪያድግና ወጣትነት አጅቦ የሚመጣው የሴትና የወንድ ጉዋደኝነት የጭዋታ የጉራው፥ የከማን አንሽ የከንቱ ውዳሴው፥ ሰራዊት አሳቡን ሆነ ስሜቱን እስኪለውጠው ስረስ እናቱ የሁድ ምሳውን ይዛለት ስትመጣ ‹የተከስተ ሾላ› የተባለችዋ ጥላማ ዛፍ ስር ብቻቸውን ተቀምጠው እዬተጎራረሱ ሲበሉ ወይም በልተው ሲጨርሱ ይጫወቱት ይደሰቱት ይስቁት፥ ይቦርቁት የነበረው ሁሉ እንደገና በተራ ሰልፉን እያሳመረ መጥቶ በፊቱ ሲያልፍ ታዬው!

እደጃች አሰፋ ተጫኔ ግቢ ስላሉና እሁድን እሾላዋ ስር ብቻቸውን ሲያሳልፉ እስዋ መብላት መጠጣት ቀርቶባት እሱ እንዲበላላት እሱ እንዲጠጣላት እስዋ ለብሳ ማጌጥ ቀርቶባት እሱ ለብሶ እንዲያጌጥላት መውደድዋን ቢያውቅም ያ አልበቃው ይልና መውደድዋ ብቻ አላጠግበው ይልና ከመውደድ አልፋ እንድታመልከው እንድትለማመነው፥ እንድትማጠነው፥ ይፈልግና፥ ራስዋን ነፍጋ ያቀረበችለትን መብል መጠጥ ልብስና ሌላ ሌላም ስጦታዋን ሁሉ መስዋእትዋን ሁሉ ‹አልቀበልም› ይላል! ያንጊዜ እፊቱ ተንበርክካ ግርናብሩን ፊቱን ዝቅ ብላ ጉልበቱን ከዚያ ወርዳ እግሩን እዬሳመች ስጦታዋን መስዋእትዋን እንዲቀበላት ስትለምነው ስትማጠነው፥ ባይኖችዋ በፊትዋ በሰራ አካላትዋ ገብቶ ውስጣዊ ስሜትዋን ውስጣዊ ጭንቀትዋን ስለሚያይ መውደድ ብቻ ሳትይሆን እንደምታመልከው አረጋግጦ ባንገትዋ ይጠመጠምና ትንፋሽ እስኪያጥረው ምጥጥ፥ ስምጥጥ አድርጎ ከሳማት በሁዋላ ይጠባል፤ ይረካል፤ ደስታው ፍጹም ይሆናል!

ከዚያ በሁዋላ ያቀረበችለትን መስዋእትን ይቀበላል! ወዲያው ያ ዘወትር፥ ከተደገመ ከተደጋገመ መጠን አዲስ እዬሆነ ደስ ደስ ከማለትና ከመጣም በቀር የማይቸከ፣ የማይመነችከው የንዶዳሞ ኪዳነ ምህረት ወሬ መወራት ይጀምራል! እንዶዳሞ ኪዳነ ምህረት የናባባ የነማማ የናያ ድንቁ የናያ ገብሬ የነቴቴ ጣይቱ፥ የነቴቴ እሙቴ፥ የወንዶችና የሴቶች ልጆች የብቶች ሳይቀር ወሬ ከነስማቸው ከነመልካቸው ከናመላቸው ይወራል! ከዚያ ከሁሉም የበለጠ ባለበት እንዳለ በደስታ በሲቃ የሚያስጨፍረው የልጆች ጭዋታ የመጣል! ከልጆች በተለይ የወንዶችን ልጆች ጭዋታ ብታሜውታቸው ስለሚወድ የገና ጭዋታውን የኩዋስ በተራ ችዋታውን የኩዋሴ አበዶቹን የሸመለ - ቀንድዬሹን ያካንዱራውን የዶቃ ጭዋታውን እረ የስንቱ ወሬ የያንዳንዱን ልጅ ስም ከነ መልኩ ከናመሉ ሳይቀር ብዙ ጊዜ ሁልጊዜ እዬመላለሰች ስታወራው፥ ጭዋታውን ሁሉ ብቻ ሳይሆን ተጫዋቾን ጭምር በዬስማቸው በዬመልካቸው በያመላቸው ልክ አብረውት እንደሚኖሩ ጉዋደኞቹ ያውቃቸው ነበር! አዲስ አበባ እዬኖረ በናቱ አስተማሪነት በናቱ አስተዋዋቂነት ከንዶዳም ኪዳነ ምህረት ከሰው ከህጻናቱ ከጭዋታው በያመትባሉና በዬወራቱ አዋቂዎችም እንዶዳሞ ኪዳነ ምህረት ሊለያይ የማይችል አንድ አካል እንደሆነ የንዶዳሞ ኪዳነ ምህረት ህጻነት ማህበረተኛ እንደሆነ ለጭዋታቸው ለደስታቸው ላዘናቸው ለተንኮላቸው ለሁለመናቸው አባል እንደሆነ ይሰማውና ደስታው ቅጥ መጠን ያጣ ይሆን ነበር! ተፈሪ መኮንን ትምርት ቤት ከገባ በሁዋላ እዚያ ተማሪዎች ለሚጫወቱዋቸው እንደ - የግር ኩዋስ የጅ ኩሳ የቅርጫት ኩዋስ ቴኒስ ላሉና ለሌሎች ዘመናውያን የጭዋታዎች መሪ ለመሆን ወደ ፊት የገፋት ወይም የረዱት እናቱ ያስተማረችው የንዶዳሞ ኪዳነ ምህረት ልጆች ልዩ ልዩ ጭዋታዎች ነበሩ። ትምርት ቤት ገብቶ ቆይቶ ከልጆችም ካካባቢውም ሁሉ ከተላመደና ከተዋወቀ በሁዋላ አክርማ እዬቀጨ፥ አጨምቢላ ስራ ልት፥ ወይም ቄልቄዋል እዬቆረጠና ለጦር እንጨት ጠርቦ እያሾለ አካንዱራ ጭዋታ ሸመለ - ቀንድዬሽ ሽመል ግራፊያ (መከታ) ጭዋታ ሌሎችንም የባላገር ልጆች የሚጫወቱዋቸውን ጭዋታዎች ለተማሪዎች አሳይቶ ተማሪዎች ሲለምዱዋቸው ስለወደዱዋቸው ተከስተ አዲስ ነገር ፈጥሮ እንዳበረከተ ሁሉ የድሜ ጉዋደኞቹ ‹ተከስተ ተከስተ› የሚሉት ሆነ! ይህ ነበር ከተፈጥሮ ችሎታው ጋር ለዘመናውያን ጭዋታዎች መሪ ለመሆን መረማመጃ የሆነው። ታዲያ ይህ ሁሉ እንዲያ ጠርቶ እንዲያ ጎልቶ፥ የታዬው እዚያ የመኝታ ክፍሉን ዘግቶ ወደ ሁዋላ ተመልሶ የህይወት ታሪኩን ሲመለከት በሰነበተበት ጊዜ ነው። ይህ ሁሉ ግብዝና ከንቱ ውዳሴ ከማን - አንሼና እነሱን የመሳሰሉት በጊዜው ወጣቶች ላይ ብርቱ ተጽእኖ ብርቱ ሀይል የነበራቸው ልማዶች

ሸፍነውት ሸሽገውት ለብዙ ጊዜ ሳይታዬው ኖሮ፥ አሁን መጥቶ ሲታዬው ይህ ሁሉ ከየተሸሸገበት እዬወጣ በሰልፍ መጥቶ ሲታዬው ይህ ሁሉ ከየተሸሸገበት እዬወጣ ምስጋና - ቢስ ይሉኝ አይል አጉራሹን - ነካሽ በመሆኑ ሲወቅሰው ሲከሰው ሲመሰክርበት ሲፈርድበት እውነት ይቅርታ የማይገባው በደለኛ ወንጀለኛ መሆኑን አመነ!

‹አዎ ምስጋና ቢስ ይሉኝ - አይል አጉራሹን - ነካሽ ወንጀለኛ ነኝ! ስለዚህ በቀጥታ አለችበት ድረስ ሄጄ የተናገርሁትን መናዘዝና በግርዋ ወድቄ ይቅርታ እንድታደርግልኝ መለመን አለብኝ! ምንም እንኳዋ የተናገርሁት ይቅርታ የሚያደርግ ባይሆን እስዋ ደግ ናትና ይቅርታ ታደርግልኛለች፤ አስቤ የተናገርሁት አለመሆኑን እኒያ ጎጃሞች ስለናት አባቴና ስላያቶቼ እዬተቀባበሉ በጥያቄ ሲያጣድፉኝ በድንጋጤ ድንገት ካፌ በሮ የወጣ መሆኑን ላስረዳት ይቅር ትላለች!› አለ። ወዲያው ይህ በደለኛነቱን አምኖ ለናቱ ለመናዘዝና በግርዋ ወድቆ ምህረት ለመለማመን መወሰኑ ያኔውኑ ከበደሉ አጥቦ እንዳጠራው ሁሉ የደስታ ስሜት ተሰማው! የተጫነውን ከባድ ሸክም ከትከሻው አንስቶ ወዲያ እንደ ጣለለት ሁሉ የቀለለው መስሎ ተሰማው! ነገር ግን እንዲያ ደስ እንዳለው እንዲያ እንደ ቀለለው ምንም ያክል አልቆዬ። እናቱን የካደበትን ምክንያት መግለጽ ስላባቱ ደጃዝማችነት ሲያወራው የኖረውን ውሸት ጭምር መግለጽ መሆኑ ስታሰበው ጥፍተኛነቱን መናዘዙንም ሆነ ይቅርታ መለመኑ ከሰነበተበት ጭንቅ በማውጣት ፈንታ እንዲያውም ወደ ባሰ ችግር እንደሚመሩት ታዬው። ያን ሁሉ ጊዜ ‹የደጃዝማች ልጅ ነኝ› እያለ ሲዋሽ መኖሩን እናቱ አታውቅም ነበር። አሁን የስዋን እናትነት መካዱን ብቻ ሳይሆን ውሸታምነቱን ጭምር ልታውቅ ነው! ከሀዲ ውሸታም አጭበርባሪ ግብዝ፥ ይህን ሁሉ መሆኑን ልታውቅ ነው! ታዲያ እንዲህ - መሆኑን ስታውቅ አፉዋ ‹ይቅር› የሚል ቢሆንስ ልቡዋ መናቁ መሆኑን ሲያይ ራሱ ታዘበው! የውሸት የከንቱ ውዳሴና የግብዝና መሸፈኛውን አውልቆ ጥሎ ርቃኑን ሲያይ አስፈራራው። አስጸዬፈው አፈረ! ‹ያፈረ እንደ ሄደ ቀረ› እንደሚባለው ያፈረሰው ወደ ሁዋላ ከመመለስ ወደ ፊት ሲሄድ መሞትን ይመርጣል!

ተከስተ ጥፉቱን ተናዞ እናቱን ይቅርታ ለመለመን ከቆረጠው በሁዋላ እፍረቱ ሊወጡት እንደማይቻል ገደል በፊቱ ተደቅኖ ስላገደው፥ ለጊዜው እስዋን ማየቱን አቆይቶ ምናልባት ከዚያ አስቸጋሪ ሁኔታ የሚወጣበትን መንገድ ቢያገኝ ለመፈለግ ወሰነ። ስለዚህ ከመኝታ ክፍሉ እንደ ወጣ ትምርት እንኳዋ ከጀመሩ በፊት ወደ ዘበኞች ሄዶ እንደ ተለመደው እሁድ እናቱ ምሳ ይዛ ስትመጣ፥ አስተማሪውና ከጉዋደኞቹ ጋር

ወደ ‹ጥናት ጉዞ› መሄዱንና መቸ እንደሚመለስ የማያውቁ መሆናቸውን እንዲነግሩዋት ነግሮዋቸው ተመለሰ። ‹የጥናት ጉዞ› የሚሉት ከላይኞች ክፍሎች ተማሪዎች በዬተራ ባንዳንድ አስተማሪ መሪነት በዬክላተ - ሀገሩ በታሪካቸውና በውበታቸው ስመ - ጥሮች የሆኑትን ቦታዎች እዬጎበኙ ሲያጠኑ የሚሰነብቱበት መሆኑን ደመቀችም ከዚያ በፊት ልጅዋ ይነግራት ስለ ነበረ ታውቃለች።

መቸም ህሊና ላለው፥ ህሊናው ጭራሽ ላልሞተ ሰው ከፍረት የከፋ ብርቱ ጠላት የለውም። በኢትዮጵያ ስለፍረት ሀይል ብርቱነት የሚገልጹ ልዩ ልዩ ዘይቤዎች አሉ። ለምሳሌ ከነሱ አንዳንዶቹ እንደ «ያፈረ እንደ ሄደ ቀረ! »

«የጭዋ ልጅ ካፈረ በግ ከበረገገ አይመለስም! »

«ጳጳስ ካወገዘው እፍረት ያዘዘው! ወ.ዘ.ተ.» ያሉ ናቸው።

እንዲሁም፥ አጼ ቴዎድሮስ ገና ሳይነግሱ፥ ደጃዝማች ካሳ ሲባሉ ስለፍረት ሀይል ‹ተናገሩ› እዬተባለ የሚወራላቸው ምሳሌንቱ ያገለግላል።

አጼ ቴዎድሮስ ደጃች ካሳ ሲባሉ ካደረጉዋቸው ብዙ ጦርነቶች ባንዱ መኩዋንንታቸውን ቦታ ቦታ አስይዛእው አሰልፈው፥ እሳቸው አንድ ከፍተኛ ቦታ ላይ ቆመው እዬተመለከቱ ጦርነቱን ሲመሩ ጠላት እያዬለ እያባባተ ሄዶ፥ ሁዋላ እንዲያውም፥ የሰፍል መስመራቸውን በብዙ ቦታ እዬሰበረ ስለ ገባ መኩዋንንቱ ፊታቸውን እያዞሩ መሸሽ ጀመሩ። አንድ መኮንን ብቻ የሚወዳት የጭን ገረዱ ጥይት በኮረጆ ውሀ በቀንድ ይዛ በሁዋላ ነበረችና ጥይት ሲያልቅበት ጥይት ውሀ ሲጠማው ውሀ እያቀበለች ስትረዳው ጉዋደኞቹ ፊታቸውን ሲያዞሩ አይቶ እሱም ለመመለስ መቃጣቱን አይታ ‹አይዞህ! እንካ!› አለችው ጥይት የያዘ እጅዋን ወደሱ ዘርግታ። ያንጊዜ ከብርቱ ጠላቱ አደጋ የበለጠ የስዋን ትዝብት ስለ ፈራ፥ ‹ወደ ፊት ሂድ ልከተልህ› ስትለው ‹አልሄድም› እንዳይል ስለ ፈራ ሰዎቹን እዬመራ ወደፊት ገፍቶ በግንባሩ የጠላትን መስመር መስበርና ባጥቂው የጠላት ጦር ጀርባ መግባት ቻለ። ወዲያው ድል ለካሳ ሆነ! ከዚያ ግዳይ ተጥሎ ምርኮ ተበርክቶ ካሳ እንደ ተለመደው ጀግኖቻቸውን ስለ ሰሩት ጀብድ ካመሰገኑ በሁዋላ ‹ከሁሉ ሞትን አስንቆ እጦርነት እሳት ውስጥየሚማግድና አስደናቂ ጀብድ አሰርቶ ብዙ ጊዜ ለድል የሚያበቃ ምን የምስላችሁዋል?› ብለው ጠዬቁ። መኩዋንንቱ በዬተራ እዬተነሱ አንዱ ‹የተፈጥሮ ደፋርነት› ሁለተኛው ‹የሹመትና የሽላምት ፍላጎት› ሶስተኛው ‹ከሁሉ የበላይ ሆኖ

መታየት› እያሉ መልስ ሰጡ። ሌሎችም እንዲሁ የመሰላቸውን አሳብ አቀረቡ። ከዚያ በመጨረሻ ‹የለም› ! አሉ ካሳ። ‹የለም ከሁሉም ሞትን የሚያስንቅ እፍረት ነው!› ብለው ለማስረጃ በከፍተኛ ቦታቸው ሆነው የተመለከቱትን ለለቱ ድል ምክንያት የሆነውን የመኮንኑንና የጭን ገረዱን ታሪክ በሰራዊቱ ፊት ተናገሩ ይባላል።

## ምእራፍ ሰላሳ

# ምሾ የሚያስጠራ የምስራች

ለደመቀች፥ ያ ከልጅዋ ተገናኝታ የገዛችለት እቃዎች ልኩ መሆን አለመሆናቸውን ከቃሉ ለመስማት ሲናፍቃት የሰነበተው እሁድ ደረሰ። ስለሲህ እንደ ተለመደው ድግስዋን አሰናድታ ያን ተከስተና ጉዋደኞቹ ‹ምላሳችንን ጨጉዋራችንን ወይም በማግስቱ ጥዋት ወደ ጉዋሮ ስንዞር አንጀታችንን ያቃጥለናል› የሚሉትን የመምሰል ውድድር ረስተው እዬተሻሙ ትንሽ ፍርፋሪ እንኩዋ ሳይቀሩ ሙጥጥ አድርገው የሚበሉትን የዶሮ ወጥ የበግ አልጫና የልዩ ልዩ አትክልት ወጥ ከለስላሳ ነጭ እንጀራ ጋር በትልቅ አገልግልዋ ሞልታ ተሸክማ ወደ አምስት ሰአት ግድም ተፊሪ መኮንን ትምርት ቤት ደረሰች። ነገር ግን ተከስተ እንደ ሁልጊዜው እስዋን በሚጠብቅበት ቦታ አልነበረም። ደመቀች አገልግዋን በራስዋ እንደ ተሸከመች የበሩን መዝጊያ ተደግፋ ከተማሪዎች ወይም ከዘበኞች አይንዋ ቢፈልግ በሩቅ እቴኒስ ሜዳው ውስጥ የቅርጫት ኩዋስ ከሚጫወቱት ጥቂት ልጆች በቀር ሌላ ሰው ስላጣች ሸክምዋን አውርዳ፥ እስዋ አድን ደንጋይ ላይ ተቀምታ ትጠብቅ ጀመር። ከዚያ መቀመጡ ስላሰለቻት፥ እንደገና ተነስታ፥ የበሩን መዝጊያ ይዛ ስትመለከት ዘለግ ያለ እንደ ገና ተነስታ የበሩን መዝጊያ ይዛ ስትመለከት ዘለግ ያለ ጊዜ ከቆዬች በሁዋላ ከዘበኞቹ አንዱን ከትምርት ቤቱ ጽህፈት ቤት አቅጣጫ ሲመጣ አየች። ዘበኛው ገና በሩቅ ሳለ እዚያ ቆማ ሲያያት እንደ መደንገጥ ብሎ እዬሮጠ መጣና፥

«እንዴት አደርሽ እመዬ፤ ያን - የኔን ጉዋደኛ ሽመልስን አላገኘሽውም? » አለ።

«ኧረ ማንንም አላገኘሁ፤ አብዬንም አላገኘሁት፤ የ - ለም? » አለች አፍዋ እዬፈራ።

«ያ፥ ሽመልስ የታባቱ ሄዶ፥ ‹እዚህ ሆነበት ጠብቀህ፥ ስትመጣ እንድትነግራት አደራ!› ብዬ ነግሬውኮ ነው - ሁሉንም ትቶ የጠፋ! » አለ ዘበኛው በጉዋደኛው ላይ እዬተቆጣ።

«ምን ኖሮዋል እንዲነግረኝ - የነገርኸው? » አለች፤ ‹ክፉ ነገር ደርሶ ይሆናል› ብላ ልብዋ እዬፈራ።

«እኔን አስተዳዳሪው አስጠርተውኝ ስሄድ - የምተምጭበትን ጊዜ ስለማውቅ ‹እበር እንዳትቆም አደራህ ጠብቀህ ንገራት› ብዬው እይውልሽ - እሱ አደራ በላ ሆኖ ሰው ጭምር አደራ በላ ያደርጋል! » አለ ዘበኛው ጕዋደኛው አጥብቆ አደራ ያእልውን መልእክት ጠብቆ ባለማድረሱ የተሰማው ንዴት አልወጣለት ብሎ።

«እኮ ምን ኖሮዋል የነገርኸው? የሱን ትተህ - አሁን አንተ አትነግረኝም? » አለች ደመቀች ትግስት አጥታ።

«እንዲያው እይሱ ነገር ያናድዳል እንጂ! አያናድድም? ቆይ ግዴለም እኔም እሰራለታለሁ፤ የታባቱ! እንዲህ - እንዳዋረደኝ አይቀር! » ሲል ዘበኛው ደመቀች የምትለው ቅጡ ጠፍቶዋት፥ ዝም ብላ ትመለከተው ጀመር። ከዚያ እሱም ትንሽ ዝም ብሎ ጉዋደኛው ሲመጣ የሚለውን ሲያስብ ከቆዬ በሁዋላ መልእክቱን አለማድረሱ ትዝ ሳለለው፥ «እ አዎ ተከስተ - አርብለት መጥጦ ‹ወደ ጥናት ጉዞ ካስተማሪያችን ጋር ሄደን እንሰነብታለንና መመለሳችነን በስልክ እስካስታወቅሽ ድረስ እንዳትመላለሺ› ብለህ እንድትነግርልኝ ነበር ያለኝ» አለ።

«መቸ ሄደ? » አለች፤ ወሬው የፈራችውን ያክል ክፉ ባለመሆኑ ልብዋን ተጭኖት የነበረው ጭንቀት ገለል ሲልላት በረዥሙ ተንፍሳ።

«እንጃ፤ ያነለት ወይም ትናንት ይሆናል»።

«ካስተማሪው ሌላ አብረውት የሄዱትን ታውቃለህ? »

«አልጠዬቅሁትም፤ እሱም አልነገረኝም።»

«መቸ እንደሚመለሱም አልነገረህ? »

« ‹እንሰነብታለንና መመለሳችነን እስካስታወቃት ድረስ እንዳትመላለስ ንገራት› አለኝ እንጂ ሌላስ - የነገረኝ ነገር የለም።»

ደመቀች በቆመችበት እንዳለች ዝም ብላ ስታስብ ቆይታ ለልጅዋ የወሰደችውን ምሳ ከመመለስ ይልቅ እዚያው ለዘበኞችና ሁልጊዜ ከሚጋብዙት ተማሪዎች ወደ ጥናቱ ጉዞ ያልሄዱ እንድላኡ ለነሱ ለመተው ስለ ወሰነች፥

«እባክህ የኔ ወንድም፤ አብዬ፣ ቢኖር - አብራችሁ ትጋበዙት የነበረው ዛሬ እሱ ስለሌለ መልሼ አልወስደውምና ከጉዋደኞቹ አብረውት ያልሄዱ አሉ እንደሆነ፥ ዛሬ እነሱንም ጠርታችሁ ተጋበዙልኝ እቃውን - እቃውን አርብ መጥቼ እወስደዋለሁ። እስከዚያ ድረስ - እናብዬ ያልመጡ እንደሆነ መቸ እንደሚመለሱ ወሬ ብታገኝ ተጠያይቀህ ቆዬኝ» ብላ አገልግሉን ለዘበኛው ሰጥታ ተመለሰች። በተከታዩ አርብ ከምሳ በሁዋላ ሀኪም ቤት ስራ ስላልነበራት ወደ ትምርት ቤት ተመልሳ አገልግልዋ ከሰጠችው ዘበኛ ስትወስድ ወደ ‹ጥናት ጉዞ› ስለ ሄዱት ተማሪዎች የሰማው ወሬ እንድላእ ብትጠይቀው ምንም የሰማው ነገር አለመኖሩ ነገራት።

«ከዚያ ወዲህ ምንም የሰማሁት ወሬ የለ፥ እመዬ። እንዲያውም - ትንሽ አሞኝ ስለ ሰነበትሁ ከዛሬ በቀር እዚያ ወደ ተማሪዎች ሰፈር አልሄድሁ። ያነለት ግን፥ ‹ስመለስ እኔ በስልክ አስታውቃታለሁና - ስልክ እስክደውልላት ድረስ እንዳትመላለስ› ማለቱን ነገሬሻለሁ። ስለዚህ መመለሱን እስኪያስታውቅሽ ባትደክሚ ይሻላል። ሲመለስ እሱ እንኩዋ ቢረሳ እኔ አስታውሼ እንዲውልልሽ አደርጋለሁ» አለ ዘበኛው አገልግሉን ይዞላት በሩን እስክትወጣ ሲሸኛት።

ደመቀች ከትምርት ቤት ምሳ የወሰደችበትን አገልግል ይዛ ከተመለሰች ሁለት ሳምንት አለፈ። ተከስተ ‹ወደ ጥናት ጉዞ ሄደ› ከተባለ ጀምሮ ሶስት ሳምንት መሆኑ ነው። ነገር ግን በስልክ ሆነ ወይም በሌላ መንገድ ስለሱ የሰማችው ወሬ የለም። ከዚያ በፊት ወደ ጥናት ጉዞ ሄዶ ካንድ ሳምንት ግፋ ቢል ካስር ቀን የበለጠ ቆይቶ ስለማያቅ ‹ከፉ ነገር ቢደርስ ነው እንጂ በደህንነት ሶስት ሳምንት ሙሉ በሄደበት አይቆይም ነበር› እያለች ስትጨነቅ ጭንቅትዋ ከስዋ አልፎ አዛዥ ተካልኝንና ባልተቤታቸውን ሰላም አሳጥቶዋቸው ሰነበተ። በሶስተኛው ሳምንት መጨረሻ እሁድ መታገስ ስላቃታት ግፋኙን ወደ ተፈሪ መኮንን ትምርት ቤት ሄደች። በሁለቱ የምእራብ በር ዘበኞች አንድ የፊት በር ዘበኛ ጭምር እደጃቸው ተቀምጠው ገበጣ ይጫወቱ ነበር። ሁለቱ ዘበኞች ደመቀችን እበር ቆማ ሲያዩ ‹ገና ስላልተመለሰኮ ነው - ስልክ ያልተደወለልሽ እመዬ› አለ ወሬ ተጠያይቆ እንዲያቆያት ‹አደራ› ያለችው ዘበኛ እንዳትወቅሰው አስቀድሞ ለመከላከል።

«እስከ ዛሬ የቆዩበት - ምክንያቱም አልታወቀ? » አለች ደመቀች ከሁለቱ ዘበኞች አንዱ ወንበር አቅርቦለት ስትቀመጥ።

« ‹አደራ› እንዳልሽኝ መሰንበቻዬን እዬተመላለስሁ ስጠይቅ ነው የሰነበትሁ፤ ምንም ወሬ አላገኘሁ። የጠዬቅሁዋቸው ሁሉ እንዲያውም፥ ‹አሁን ወደ ጥናት ጉዞ የሄደ ሰው እስከ መኖሩም አናውቅ› አሉኝ» አለ ዘበኛው። ከፊት በር የመጣው ዘበኛ ጉዋደኞቹ የሚነጋገሩትን ይሰማ ነበር።

«ምናልባት - ስለ ጉዞው የሚያውቁ ሰዎች ባያጋጥምህ ይሆናል» አለች፤ የመጣባትን ልቅሶ ውጣ ለማስቀረት ስትጣጣር ከፊትዋ እንዳይታወቅባት ሰዎችን ትታ አንድ ጊዜ ወደ መሬት አንድ ጊዜ ወደ ጎንና ጎን እዬተመለከተች።

«ምን - እዚህ የሚኖረው ያንድ አለም ህዝብ የሚያክል ነው! ታዲያ - አንዱ የሚያደርገውን ሌላው እንዴት ሊያውቅ ይችላል» አለ ሁለተኛው ዘበኛ።

ከዛሬ - ከዛሬ ቀደም ‹ወደ ጥናት ጉዞ እሄዳለሁ› ሲለኝ በሄደበት ይህን ያክል ቆይቶ አያውቅም። ታዲያ አሁን - በደህንነት ይህን ያክል ይቆይ - ይቆይ የመሰላችሁዋል? » አለች ደመቀች በተሰበረ ድምጽ እንባዋ አሸንፎዋት እዬወረወረች።

ሁለቱ የምእራብ በር ዘበኞች ደመቀች ስታለቅስ ሲያዩ አዝነው አንገታቸውን ደፍተው ቆዩና «አይዞሽ ምንም አይሆን፣ መቸም - ሰው በሌለበት አገር አልሄዱ፤ ክፉ ነገር ቢደርስ እስከ ዛሬ ሳይሰማ አይቀርም ነበር። የክፉ ነገር ወሬ አይደበቅም» አለ አንዱ ለማጽናናት ያክል።

«ለመሆኑ ማነው ወደ ጥናት ጉዞ ሄዶ የጠፋው? » አለ ከፊት በር የመጣው ዘበኛ ከጉዋደኞቹ ወዳንዱ ጠጋ ብሎ በሹክሹክታ።

«አንዱ ተከስተ ነው፤ ሌሎችን ግን አላወቅናቸውም» አለ ተከስተ ወደ ጥናቱ ጉዞ የሚሄድ መሆኑን የተናገረው ዘበኛ።

«የቱ ተከስተ? ተከስተ ሻምፓኝ? » አለ የፊት በሩ ዘበኛ።

«አዎ ተከስተ ሻምፓኝ! »

«አደለም ተከስተ ታምራት» አለች ደመቀች ያባቱን ስም አርማ።

«ያው ነው እመዬ፤ ‹ተከስተ ሻምፓኝ› እዚህ የሚጠራበት ነው። ብቻ - ‹ሻምፓኝ› የስድብ ስም እንዳይመስልሽ፤ የጉብዝና ስም ነው፥ ‹መሪ (ቻምፒዮን) ማለት ነው» አለ ከምእራብ በር ዘበኞች አንዱ ትንሽ እንደ መሳቅ ብሎ።

«ታዲያ - ተከስተ ሻምፓኝ መቼ ነው ወደ ጥናት ጉዞ የሄደ? » አለ የፊት በሩ ዘበኛ።

«አ - አሁንማ ሶስት ሳምንት መሆኑ አደለም? » አለ የተከስተን ጉዞ ያወራው ዘበኛ በጥያቄ አይን ደመቀችን እየተመለከተ። ደመቀች ‹አዎንታዋን› ራስዋን ወደ ላይ በመግፋት ገለጸች።

«ምነው - ከሶስት ይሁን ካራት ቀን በፊት - እዚህ አይቼው የለም እንዴ? »

«አ - ይ፥ እሱን የሚመስል ልጅ አይተህ ይሆናል፥ እንጂ እሱስ ከሄደ - ሶስት ሳምንቱ ነው። ራሱ መጥቶ ነው መሄዱን የነገረኝ።»

«እንዲያ እንጂ! ደግሞ ተከስተ ሻምፓኝ ይጥፋኝ? ተከስተ ሻምፓኝ ደህና አድርጌ ሳላውቀው ቀርቼ ነው - እሱን የሚመስል ልጅ የሚያሳስተኝ? እንኳዋንስ ሌላ ልጅ መንትያ ቢኖረው አያሳስተኝም! »

«ሆነ ብለህ ከተመለትኸውማ እንደማያሳስትህ የታወቀ ነው፣ ብቻ - አንዳንድ ጊዜ ቅድም አንዱ ለብሶት ያየኸውን ልብስ ትንሽ ቆይቶ ሌላው ለብሶ በሩቅ ሲሄድ ስታይ ያ - ቅድም ያያኸው ሊመስልህ ይችላል ማለቴ ነው።»

«በሩቅኮ አደለም ‹አዪሁት› ያልሁ። እሱና ሌሎች ልጆች የኔ ጉዋደኞች ጭምር አብረን ቁጭ ብለን በቅርቡ የምኒልክ ትምህርት ቤት የግር ኩዋስ እዚህ መጥቶ ከኛ ትምርት ቤት ቡድን ጋር ስላደረገው ግጥሚያ ስናወራ ብዙ ቆይተናል። እንዲያውም ይህ ብቻ አደለም፤ አላነጋገርሁዋቸውም እንጂ ዛሬ ጥዋትም ተከስተ ሻምፓኝና ተፈራ ‹ደከር› ተፈራ ሎልሰገድ በትምርት ቤት አካባቢ የሚጠራበት ስም ነው። ተፈራ በግር ኩዋስጭምር ኩዋስን ሲያገኝ በፍጥነት በመምታት ፈንታ ሲቃ ይይዘውና በቆመበት እንዳለ ዳንኪራ ሲመታ ብዙ ጊዜ ተቃዋሚ ነጥቆ ስለሚወስድበት ‹ደከር› ተብሎ ቀረ።

የፊት በሩ ዘበኛ ተከስተን ማየቱን ሲናገር ደመቀችንና ሁለቱ የምእራብ በር ዘበኞች የሚሉት ጠፍቶባቸው ዝም ብለው እስበሳቸው ሲተያዩ ቆዩ። ከዚያ ደመቀች እንደ ምንም የተበተነ አሳብዋን ለመሰብሰብ ቻለችና፥

«እንግዲያ - እሱ ወንድሜ እንዳለው ከሶስት ወይም ካራት ቀን በፊት ያየው ለመሆኑ ርግጠኛ ከሆነማ - ተመልሰዋል ማለት ነዋ» እያለች፥ ‹እሱ ወንድሜ› ስትል የፊት በሩን ዘበኛ ባገጭዋ እያመለከተች።

«ቢመለስ ነው እንጂ ቢመለስ ነው ነው» አሉ ሁለቱ የምእራብ በር ዘበኞች እዬተቀባበሉ።

«አላመናችሁኝም መሰለኝ፤ የጥርጣሬ መልክ አዬሁባችሁ። እንዴት አባቴ አድርጌ ብነግራችሁ ነው ላሳምናችሁ የምችል? » አለ የፊት በሩ ዘበኛ በተለይ በደመቀች ላይ የጥርጣሬ መልክ ስላዬባት።

«እይው የኔ እህት ማየት ብቻኮ አደለም» አለ ቀጠለና። «ማየት ብቻ አደለም። እዚያ ታች ያን ዛፍ ታያለች? » አለ ወደ አንድ ዛፍ እያመለከተ።

«አዎ» አለች ደመቀች።

« ‹እሱ ስር አብረን ጎን ለጎን ተቀምጠን ስንጫወት ረዥም ጊዜ አሳልፈናል› ነው ያልሁ። አብረውን የነበሩት ልጆችም ዘበኞችም አሁን ቢኖሩ ይነግሩዋችሁ ነበር፤ ወይ - ዛፉ አፍ የለውም እንጂ፥ ቢኖረው ጠርቼ አስመሰክረው ነበር! » አለ ዘበኛው ትንሽ እንደ መሳቅ ብሎ።

«የለም አንተን አለማመንኮ አደለም» አለ ተከስተ ወደ ጣንት ጉዞ የሚሄድ መሆኑን የነገረው ዘበኛ። «አንተን አለማመን ሳይሆን እኛን ግራ ያጋባን ከተመለሰ - አራት ቀን ሲሆነው ለመዬ ስልክ አለመደወሉና እኔም በየቀኑ እዬሄድሁ ስጠይቅ መመለስ አለመመለሱን አንድ እንኳዋ ‹አውቃለሁ› የሚል መጥፋቱ ነው። ከሁሉም ደግሞ ይብሱን ግራ የሚያጋባው ተከስተ ራሱ የሚሄድ መሆኑን እዚህ ድረስ መጥቶ ነግሮኝ የጠዬቅሁዋቸው ሁሉ ‹እንኳዋንስ እሱ ማንም አሁን ወደ ጥናት ጉዞ የሄደ መኖሩን አናውቅም› ሲሉኝ ‹ባያውቁ ይሆናል› ብዬ ሳለሁ ደግሞ አሁን አንተ ‹ካራት ቀን በፊት አግኝቸዋለሁ› ስትለን ጊዜ ነገሩ ሁሉ የተምታታ ሆነብንና ‹ግር› ስላለን ነው እንጂ አንተን ባለማመን አደለም።»

«የጉዞው ነገርስ እኔንም ግራ አጋብቶኛል። ሌላ ጊዜ ተማሪዎች ካስተማሪያቸው ጋር ‹የጥናት ጉዞ› ወደሚሉት ሲሄዱ እንደምታውቁበት እቃቸውን ለመጫን የምንረዳቸው እኛ የፊት በር ዘበኞች ስለሆን አንዱ ‹ሻንጣየን ሌላው ደብተሬን ደግሞ

ሌላው እርሳሴን ረሳን› እያሉ አንድያቸውን ነገር ጥለው ይሄዱ ይመለስ ሲወጡ ሲወርዱና ሲረበሹ እኛንም ‹ያን አምጡልን ይህን መልሱልን› እያሉ ሲያስቸግሩን ስልችት ይለንና ወዲያ ሂደውልን እስክንገላገል ደቂቃው ቀን መስሎ ይታዩን ነበር! አሁን - ይህ ሁሉ ቀርቶ ወሬውን እንኩዋ ሳንሰማ ‹ተከስተ ሻምፓኝና ሌሎች ወደ ጥናት ጉዞ ሄዱ› ስትሉም - ጭራሽ እንግዳ ነገር ሆነብኝ! ብቻ ግዴለም ሁሉም ነገ ይጣራል» አለ የፊት በሩ ዘበኛ።

«ዛሬ ማጣራት አይቻል ይሆን የኔ ወንድም? » አለች ደመቀች።

«ተከስተ አሁን እዚህ አዲስ አበባ መኖሩን እንደ ሆነ ማወቅ የምትፈልጊው፥ እዚ አትጠርጥሪ የኒ እህት። ወደ ጉዞው መሄድ አለመሄዱንና ሄዶ እንደሆነ መቸ እንደ ተመለሰ ለማጣራት ግን ዛሬ የምንችል አይመስለኝም። ዛሬ እሁድ ስለሆነ እዚህ የሚቀሩት ጥቂት ናቸው። መቸም ተከስተና ተፈሪ ተያይዘው ሲወጡ ያዩሁዋቸው መሆኔን ቅድም ነግሬያችሁዋለሁ። ሌሎች የሚበዙት ተማሪዎች እዚህ ዘመዶች ያሉዋችው በየዘመዶቻቸው ቤት የሌሉዋቸው ካሉዋቸው ጉዋደኞቻቸው ጋር ምሳቸውን በልተው፥ ከዚያም - በዬስኒማውና በዬጭዋታው ቦታ ምሳቸውን በልተው በሁዋላ ነው የሚገቡ። ስለዚህ - ከነገ በፊት ሁሉንም ማወቅ አንችልም» አለ የፊት በሩ ዘበኛ።

«እንግዲህ ግዴለም እመዬ ነገ ወይም ከነገ ወዲያ እኛና ይህ ጉዋደኛችን ተከስተን እንደ ምንም ፈልገን ሳናገኘው አንቀርምና ደህንነቱን እሱ ራሱ በስልክ እንዲያስታውቅሽ እናደርጋለን» አለ ከምእራብ በር ዘበኞች አንዱ።

ደመቀች ምንም እንኩዋ ከፊት በሩ ዘበኛ ስለ ልጅዋ የሰማችው ሁሉ በራስዋ ውስጥ ልዩ ልዩ ተቃራኒ አሳቦች አለ ፈጠረ ሙሉ ሰላም ማግኘት ባትችል ‹ያን ያክል ጊዜ ወሬው የጠፋ፥ ያለ ጥርጥር ክፉ አደጋ ቢደርስበት ነው› ብላ ተጨንቃ ስለ ነበረ ከዚያ ተጭኖዋት ከነበረው ከባድ ጭንቀት ቀለል ብሎዋት ተመለሰች።

ብቻ የምእራብ በር ዘበኞች እንዳሉትና ደመቀችም ወደ ቤትዋ ስትመለስ ተስፋ እንዳደረገችው ተከስተ እንኩዋንስ በማግስቱና በሳልስቱ በሳምንትም ሆነ ባስራ ምስት ቀን ውስጥ ለናቱ ስልክ አልደወለም።

‹አውቆ የተሸሸገ ቢጠሩት አይሰማም› እንደሚሉት የምእራብ በር ዘበኞች ገና በሩቅ ሲያያቸው እዬተሰወረ እስከ ብዙ ቀን ድረስ ፈልገው ሊያገኙት አልቻሉም። እንደ

ምንም ፈልገው አግኝተውት የናቱን መጨነቅና በስልክ እንዲያነጋግራት ‹አደራ› ማለትዋን ከነገሩት በሁዋላ እንኩዋ አንዳንድ ጊዜ «ስልክ ደውዬ የሚያነሳ አጣሁ› እያለ አንዳንድ ጊዜም ‹እስዋን ላገኛት ስላልቻልሁ ደህንነቴን እንዲነግርልኝ ለደጃዝማች አሰፋ ስልከኛ ነግሬ ነበር› እያለ ውሸት ሲነገራቸው ሰነበተ። እስዋም እሁድ እሁድ ስትሄድ አታገኘውም፤ ይሸሸጋል።

አንድ ቅዳሜ አናዛዥ ተካልኝ ቤት ምሳ ከተበላ በሁዋላ እሳቸው ወደ ስራቸው ሊሄዱ ሲነሱ፥ በሻህ ዘለሌ ደረሰ።

«የምንጠላህ ይመስል ምሳችነን በልተን ስንነሳ የመጣህ ስም ነው? እንድናባላህ ቀደም ብለህ አትመጣም ኖሮዋል? » አሉ አዛዥ የጅ ሰላምታ ሰጥተውት ተመልሰው ሲቀመጡ።

« ‹ከልብ ከታዘነ እንባ አይገድም› እንደሚባለው ካዘናችሁልኝ ልትነፍጉኝ ካልፈለጋችሁ ምንጊዜም ብመጣ ለኔ ያክል አታጡልኝም ብዬ ነው» አለ በሻህ ለወይዘሮ ጌጤም ለደመቀችም ሰላምታ ሰጥቶ ሲቀመጥ። አዲስ ዘመን ጋዜጣ በጁ ይዞ ነበር።

«የምን ጋዜጣ ነው የያዝከው? ግብር የሚያምር አዋጅ ጣፈበት እንደ ሆነ የምስራቹን አንድ ጠርሙስ አረቄ እገዛልሃለሁ» አሉ አዛዥ ቀልዳቸውን። እዳ ላለው አንድ ጋሻ መሬታቸው የሁለት አመት የግብር እላፊ ስለ ነበረባቸው ‹ውዝፉ ግብር ሳይከፈል ባለርስቱ እህል እንዳትጭኑ ተብለን ተከለከልን› ብሎ ጢሰኛቸው ባድ እጁን መጥቶ ነግሮዋቸው ሲበሳጩ ሰንብተው ነበር።

«የግብር ምህረት የምስራች ያለበት አደለም፥ ሌላ ምስራችን ያለበት ነው» አለና በሻህ አጥፎ የያዘውን ጋዜጣ ሶስተኛውን ገጽ ገልጦ፥ ለደመቀች ሰጣት። እዚያ በሶስተኛው ገጽ ላይ ያምስት ወጣቶች ስእል ነበረ። ከስእሉ ራስጌ ‹ከተፈሪ መኮንን ትምርት ቤት በትምርታቸው ሄዱ› የሚል በጉልህ ተጽፎዋል። በተራ ቁመው ከሚታዩት አምት ወጣቶች በስተቀኝ የመጀመሪያው ስእል ስር ‹ተከስተ ታምራት› የሚባእልውን ጽሁፍ ከማየትዋ ያ፥ ጽሁፍ ‹ተከስተ ታምራት ሞተ› የሚል እንደ ሆነ ሁሉ «ዋ - ይ! » ብላ ጮህ ስትነሳ፣ ጋዜጣው ከጅዋ ኩታዋ ከተከሻዋ ወደቁ። ወይዘሮ ጌጤ ደንግጠው ደመነፍሳቸውን ሁለት እጆቻቸውን ዘርግተው አብረዋት ተነሱ።

«ልጄን! » አሉ አዛዥም በተቀመጡበት እንዳሉ እንዲሁ ደንግጠው።

ሰውመትዋ ሁሉ እዬተንቀጠቀጠ ጋዜጣውን ከጣለችበት አንስታ እንደገና ላንድ አፍታ አየት አደረገችና፥

«የለም፤ እሱ አደለም! ልጄ አደለም! አብዬ አደለም! ሌላ ነው! ልጄ እንዲህ ጨክኖ እዚህ ብቻየን ጥሎኝ አይኔን እንኩዋ ላንድ አፍታ ሳያየኝ ‹ደህና ሁኝ› እንኩዋ ሳይለኝ አይሄድም! አያደርገውም! ‹ማን አላት› ብሎ? ለማን ጥሎኝ? ምን አልሁትና? ምን በደልሁትና እንዲህ ይጨክንብኛል? » እያለች ፊትዋ በንባ ውሀ እዬታጠበ እንዲሁ ግብንዋን እንዲሁ ደመነፍስዋን ስትለፈልፍ በሻህ አስቀምጦ የሆነውን በጥሞና ሲገልጽላት ቢሞክር ገፍትራው ወጥታ ሮጠች። ከዚያ ኩታዋን ከጣለችበት አንስቶ፥ እሱም እየሮጠ ተከተላትና አጥሩን እንደ ወጣች ደረሰባት።

«አሁን ወዴት ልትሄጂ ነው እንዲህ ልብስሽን ጥለሽ የምትሮጪ? » አለ እንዳትንቀሳቀስ እጅዋን አጥብቆ ይዞ።

«ልቀ - ልቀቀኝ እባክህ፤ ተፈሪ መኮንን ትምህርት ቤት እሄዳለሁ! » አለች ባንድ ወገን ከሱ ባንድ ወገን ከልቅሶ ጋር እዬታገለች።

«እሺ እንኪ ኩታሽን ደርቢና አርበን እንሂድ።»

ከዚያ ኩታዋን ተቀብላ በቅጡ ሳትለብስ እንደ ተጠቀለእል ባንገትዋ ጠምጥማ ትናንት የሄደው ልጅዋ ‹ገና ሊሄድ ነውና ሳይሄድ ድረሽበት› እንደ ተባለች ሁሉ እየሮጠች ተፈሪ መኮንን ትምህርት ቤት ደረሰች። በሻህ ሁዋል ሁዋልዋን ተከትሎ እየሮጠ «ኧረ እባክሽ ቀስ ብለን እንሂድ የሚያየን ሰው ሁሉ «ጉድ» ይላል! እባክሽ እንድትወድቂ የምትረግጪውን እያየሽ ርገጪ› እያለ እንደ ለፈለፈ ነበር ትምህርት ቤት የደረሱ።

እውነትም እዬሮጡ ትምህርት ቤት እስኪደርሱ ካለፉት ሰው ሁሉ አንድ እንደ ሆነ ቆሞ ወይም ዘወር ብሎ እነሱን የማይመለከት ካንድ የሚበዙ እንደ ሆኑ፥ እንዲሁ ቆሞ ወይሞ ዘወር እያሉ ስለነሱ የማይነጋገሩ አልነበሩም! ነገር ግን ደመቀች አላፊ አግዳሚው እንድ ጉድ መመልከቱን ሆነ፥ በሻህ ሁዋል ሁዋላዋን እየሮጠ ይለፍልፍ የነበረውን አይታም አትሰማም ነበር!

በትምርት ቤቱ የምእራብ በር፥ ከዘበኞች ቤት ደጅ ቆሞ የነበረ አንድ ዘበኛ ደመቀችና በሻህ እየሮጡ መጥተው፥ ወደ በሩ መጠጋታቸውን ከቆመበት ከፍተኛ ቦታ

ገና በሩቁ ሲያይ፥ ቶሎ ከፍቶ ለማስገባትና የምስራቹን ለደመቀች ለመንገር ቸኩሎ፥ እሱም ወደ በር እዬሮጠ፥

«የምስራች እመዬ! » አለ በሩን እስኪከፍትና፥ ሰላምታ እስኪሰጥ እንኩዋ መቆየት አላስችለው ብሎ፥ ገና በመንገድ ሳለ። «የምስራች! ያንቺ ልጅ እዚህ ካለው ተማሪ ሁሉ በትምህርር በልጦ እሱና ሌሎች አራት ልጆች ትናንት ወደ ፈረንጅ አገር ሄዱ! » ሲል፥

«በቃ በቃ፥ በቃ፥ እንግዲህ! በቃ እንግዲህ ልጄ አንገናኝም! » አለች ደመቀች ሁለት እጆችዋን ወደ ላይ አንስታ እያርገበገበች። ከዚያ የምስራቹ መርዶ ጽኑ የሆድ ቁርጠት እንዳስነሳባት ሁሉ በሁለት እጆችዋ ሆድዋን ይዛ አጎንብሳ እዬተቅመደመደች ስታለቅስ፥ በሻህና ዘበኛው እንዳትወድቅ ደግፈው ብዙ ጊዜ፥ ለልጅዋ ምሳ እዬያዘች ስትሄድ በር እስኪከፈትላት ተቀምጣ ትቆይበት ወደ ነበረው ድንጋይ ወስደው አስቀመጡዋት። እዚያ ‹ልጅሽ ሞተ› እንደ ተባለች ሁሉ «ልጄ፥ ልጄ፥ ልጄ! » እያለች ምሾ ስትጠራ ዘበኛው ደንግጦ ደስ የሚያሰኝ የምስራች መስሎት የሚያስለቅስ መርዶ የተናገረበትን አፉን እንደሚቀጣ ልጅ ባንድ እጁ እፍን አድርጎ ይዞ፥ አይኖቹን በጥፍ አውጥጦ በላይዋ አፍጥጦ ዝም ብሎ ያያት ጀመር። በሻህም ምንም እንኩዋ ታለቅስበት የነበረው ምክንያት የሚያሳዝን ባይሆን፥ እንዲያው እስዋን ስታለቅስ ማየቱ ብቻ እንዲያው የስዋን ምጥ ማየቱ ብቻ አሳዝኖት አይኖቹ እንባ ሞልተው ነበር።

«ከድንጋይኮ ወንበር ይሻላል፥ ጋሼ። እውስጥ ወንበር ስላለ.፥ ገብተን ወንበር እንድትቀመጥ ንገራት» አለ ዘበኛው ወደ በሻህ ጠጋ ብሎ በሹክሹክታ። ከዚያ፥ በሻህ ደመቀችን ሲያስነሳ ዘበኛው ወደ ቤቱ እዬሮጠ ሄዶ ወንበሮችን አወጣና ሶስቱም እደጅ ተቀምጠው ስታለቅስ ብዙ ቆይታ ሲደከማት ኩታዋን ነጥላ አይኖችዋንም አፍንጫዋንም ትጠራርግ ጀመር። ሳግ ባይተዋትም «ልጄ ልጄ! » እያለች ማልቀሱን አቆመች። በሻህና ዘበኛውም እንደ አስተዛዛኞች አንገታአቸውን ደፍተው ዝም ብለው ከቆዩ በሁዋላ፥

«ይቅርታ አድርጊልኝ፥ እመዬ» አለ ዘበኛው ሲፈር ሲቸር፥ «እኔኮ ከነተከስተ ጋር ለመሄድ ሳይመረጡ የቀሩት የላይኛው ክፍል ተማሪዎች ሁሉ ተናደው ጠጉራቸውን ሲነጩ ወላጆቻቸው ደግሞ - ‹እናንተ ትምህርት የማይገባችሁ ደደቦች ወይም፥ ጊዜያችሁን ሁሉ ለጭፈራ የሰጣጭሁ ፍሬ - ቢሶች ብትሆኑ ነው ከጉዋደኞቻችሁ ጋር ፈረንጅ አገር ለመሄድ ሳትመረጡ የቀራችሁ› እያሉ ልጆቻቸውን

ሲሰድቡና ሲበሳጩ አይቼ፥ ልጅሽ ከዚያ ሁሉ ተማሪ መሀከል በትምህርት በልጦ ወደ ፈረንጅ አገር ለመሄድ መመረጡ፥ ደስ የሚያሰኝና የሚያኮራሽ መስሎኝ ነበር እንጂ፥ እንዲያ ደስ ብሎኝ እየጨፈርሁ - ‹የምስራች› ያልሁሽ ያን ያክል የሚያስለቅስሽ መሆኑን ባውቅ ኖሮ ጭራሽ ትንፍሽ አልልም ነበር! ግን አሁን - ይቅርታሽን ከመለመን በቀር - መቸስ ምን አደርጋለሁ! አንድ ጊዜ ካፍ የወጣ ነገር ተመልሶ አይዋጥ! »

«አንተማ ምን ታደርግ! መቸም ደስ የሚያሰኝ ወሬ የያዘ ወዳጅ፥ ደስ ብሎት የምስራች ማለቱ የተለመደም የሚገባም ነውኮ» አለ! በሻህ።

«ፊትማ እንኔም እንደሱ መስሎኝ ነበር - የግዜርን ሰላምታ ከመስጠቴ በፊት በሩን እንኩዋ ከፍቸ ሳላስገባችሁ እንዚያ እዬዘለልሁ ‹የምስራች› ያልሁ! ያን እድል ያላገኙት ተማሪዎችና ወላጆቻቸው ቀንተው አንዳንድ ጊዜ እስበሳቸው ሲወዘጋገቡ እንዳንድ ጊዜም አስተማሪዎችን፥ ‹አድላዊዎች› እያሉ ሲሳደቡ አይቼ፥ በጣም ደስ የሚላት መስሎኝ ነበር። ሁዋላ ግን እንዲያ - እያማጠች ስታለቅስ ሳይ፥ ምነ ባልተናገርሁ! ምነ ቅድስ ገብሬል ጉሮሮየን በዘጋው አልሁ! »

«ኧረ ለምን? አይዞህ አትዘን፥ አንተ ምንም አላጠፋህ። መቸም የወለደች እናት ስለ ሆነች፥ ለጊዜው ከልጅዋ መለየቱ እንጂ ጥቅሙ ባይታያት ነው። እንኩዋንስ የናት ልብ፥ ሌላም የሚወድ ልብ ከሆነ የሚወደውን እንጂ የሚጠቅመውን አያይ! እንዲያ ስለ ሆነ ነው። ነገር ግን ውላ አድራ ስትረጋጋና ይህ ያሁኑ ብርቱ የሀዘን ስሜት በረድ እያለ በጥሞና ጥቅሙን ማሰብ ስትችል ደስ እንደሚላት የታወቀ ነው» አለና በሻህ ደመቀችን ላለማጋለጥ ያክል «ለመሆኑ» አለ ወዲያው፥ ከተል አድርጎ «ለመሆኑ ተከስተ ጊዜ አጥቶ ይሆን? ወይስ - ለምን ይሆን ብቅ ብሎ ላንድ አፍታ ሳያያትና ሳይሰናበታት የሄደ? » ይህን ጥያቄ ለመጠየቅ ነበር ደመቀች እየሮጠች ወደ ተፈሪ መኮንን ትምህርት ቤት የሄደች። ነገር ግን እዚያ ከደረሰች በሁዋላ ልጅዋ በውነት የሄደ መሆኑንና ሳያያት የሄደበትን ምክንያት ለማጣራት ኩታዋን በቅጥ ሳትለብስ ባንገትዋ ጠምጥማ የምትቆምበት ጉድባ ይሁን ጋሬጣ ሳታስተውል እዬሮተች እንዳልሄደች ሁሉ ለማልቀስ ብቻ እንደ ሄደች ሁሉ፥ ‹ልጄ፥ ልጄ› እያለች ከማልቀስ በቀር፥ ሌላው አሳብና ሌላው ቃል ሁሉ ጠፋት!

«ጊዜስ አልነበራቸውም። የሚሄዱ መሆናቸው ከታወቀ አንኩዋ ሰንብቶዋል፤ ሶስት ወይም አራት ወር ሆኖታል፥ አሉ። ብቻ በመሀከሉ ምክንያቱን እኔ እንጃ - ነገሩን

አስተኝተውት ቆይተው በመጨረሻ - ፓሳፓርቶ ቪዚ፥ ምን የሚሉትን ነገር ሁሉ ለማስወጣት ላይና ታች ሲሮሩዋጡ ሰንብተው ልብስ ለማሰፋት እንኩዋ ጊዜ ስላጡ እንዲሁ የተሰፋውን ይስማማቸው አይስማማቸው እዬገዙ፥ እያጠለቁ ነው አሉ የሄዱ። ትናንት ሊሄዱ ከትናንት ወዲያ ማታ ራት ከተበላ በሁዋላ ከዋሉበት ስለ ተመለሱ እንዲያውም ጦማቸውን ሳያድሩ አልቀሩም። ከዋሉበት ሲመለሱ ተከስተ በቀጥታ እዚህ መጥቶ ይህን ሁሉ ነገረንና ‹አሁን ለመዬ ስልክ እንደውልላታለን ለጌው በማለፉ ስልከኛው ስለማይኖርና ነገርም የምሄድ ሳይነጋ በመሆኑ ልትደርስብን ስለማትችል ሳላያት በመሄዴ በጣም ማዘኔን ንገሩልኝ አደራ» ብሎን ሄደ። ‹እዚያ እንደ ደረስሁ ሁሉንም እጽፍላታለሁ› ብሎዋል» ሲል ዘበኛው፥

«እንዲያ ቢሆን ነው! ቢቸግረው ነው! ሳይችል ቀርቶ ነው ልጄ ሳያየኝ የሄደ! ባይቸግረው ኖሮ ቢችል ኖሮ ልጄ ጨክኖ ሳያየኝ እንደማይሄድ አውቃለሁ! እኔን ይቸግረኝ! እኔን ይጭነቀኝና ልጄ ልጄ ልጄ! » እያለች እንደገና ምሾዋን መጥራት ጀእምረች። መቸም የሚወዱት ሲበደል እንኩዋንስ ምክንያት ተገኝቶ ባይገኝ ፈጥኖ ለተወዳጁ በደለኛ ይቅርታ ማድረግ ቀላል ስለሆነ፥ ዘበኛው የነገራት የማይበቃ ምክንያት ልጅዋን ከበደሉ አጥቦ አጥርቶ አሳያትና ‹ልጄ ልጄ› ማለትዋን ቀጠለች። ከዚያ በሻህ ከተቀመጠበት ተነስቶ ትከሻዋን ይዞ፥

«እባክሽ ይብቃሽ የኔ እመቤት አሁን እሱ ወንድሜ እንደ ነገረን ተከስተ እዚያ እንደ ደረሰ ስለሚኖርበት መልካም ሁኔታም ከዚህ ሳይሰናበትሽ ስለ ሄደበት ምክንያት ትክክለኛውን በዝርዝር ሲስፍልሽ ነገሩ ሁሉ እንዲህ አሁን ከፍቶ እንደሚታይሽ አለመሆኑን ትረጃለሽ። አሁን ተነሺ እንሂድ» ብሎ አሰንሳትና፥ ዘበኛውን እሱም እስዋም አመስግነው ተመለሱ። አዛዥ ቤት እንደ ደረሱ፥

«ሂድ እንግዲህ ጋሽ እግዚአብሄር ይስጥልኝ» አለች ደመቀች፥ በግድ ፈገግ ለማለት እዬሞከረች። ነገር ግን ፈገግ እንዲል የተገደደው ፊትዋ የሚያሳዬው ቢኖር፥ ጭንቀትዋን ብቻ ነበር። ያነለት አዛዥና ወይዘሮ ጌጤ ቢያባብሉዋትም፥ ቢቆጡዋትም ሰውነትዋ ከመታወኩ የተነሳ ትኩሳት ስለ ነበረባት ውሀ ደጋግማ ከመጠጣት በቀር ራት አልበላችም።

## ምእራፍ ሰላሳ አንድ

# በፍቅር ፊት የሚቆም ቆራጥ ጀግና አለ?

ደመቀች፥ የምስራች መርሶዋን ከተፈሪ መኮንን ትምህርት ቤት አረጋግጣ ወደ ቤትዋ እንደ ተመለሰች፥ በሻህ አድርሶዋት፥ እስዋ ወደ መኝታ ቤትዋ ስትገባ እሱም፥ በቀጥታ፥ ወደ ቤቱ ሂዶ፥ ራሱን ከበላ በሁዋላ ሌሊቱን ሙሉ እንቅልፍ ባይኑ ሳይዞር አደረ። ካንድ ወገን የደመቀች ጭንቅ፥ ምጥዋ እንዲያው ሁኔታው ሁሉ ባይነ - ህሊናው መጥቶ እዬታየው አንድ የሚያጽናናት ነገር ቶሎ ካላገኘች ‹ከፉ አደጋ ሊደርስባት ይችላል› ብሎ ስለ ሰጋ፥ ከሌላ ወገን ስለሱና ስለስዋ ጋብቻ ያሰበው አሳብ የሚፈጸም ቢሆን እንኳዋ ገና ጊዜ ስለሚወስድ ስለ መሰለው እነኝህን ሁለት ተቃራኒ ነገሮች ለማስታረቅ ነበር እንቅልፍ አጥቶ ሲታገል ያደረ።

በሻህ በኢትዮጵያ «ነጻነት» የሚባለው ቃል የውነተኛ ትርጉሙን እንዲያገኝና፥ የኢትዮጵያ ህዝብ ለዜግነት ግዴታው ተገዥ ብቻ ሳይሆን ለሙብቱ ባለቤት ጭምር እንዲሆን የሚያደርግ ስራተ መንግሥት ተቋቁሞ እስኪያይ ድረስ ምሽት አግብቶ ንብረት መስርቶ ላይኖር፥ ሁልጊዜ ለትግል ታጥቆና ተጠንቅቆ ሊኖር ቃል ኪዳን የገባ ሰው ነበር። ነገር ግን አንድ ቀን አዝማሪው ውቤን ጋብዞ አንድ መጠጥ ቤት ተቀምጠው እዬጠጡ በረዥሙ ከተነጋገሩ በሁዋላ የጊዜው ትውልድ ያስተሳሰብም ሆነ ያሰራር መንፈስና ባገሩ የነበረው ጠቅላላ ሁኔታ ሁሉ እንዳለ እስከ ቆዬ ድረስ ብቻውን ምንም ያክል ራሱን በድሎ ቢኖር ያ ቃል ኪዳን የተገባለት የተቀደሰ ተግባር ፍጻሜ ሊያገኝ የማይችል መሆኑን ተረድቶ ኑሮውን አዝማሪው ውቤ በመከረው መንገድ ለመምራት ስለ ወሰነ ራሱን አስችሎ የሚያኖረው ስራ ይዞ፥ ደመቀችን አግብቶ ለመኖር የሚችልበትን መንገድ በማሰብና በማጥናት ላይ ነበር። ስራ የማግኘቱ ነገር እንኳዋ እምብዛም አላሰበውው። ስራ በፈለገው የመንግስት መስሪያ ቤት ቢጠይቅ እንደማያጣ እርግጠኛ ነበር። እርግጥ በመጀመሪያ ሰውነቱ እንደ ተጎሳቆለ፥ ጎስቋዋላ ልብሱን ለብሶ ስራ ፍለጋ ከሄደ ምንም ያክል አዋቂ ቢሆን፥ ከተላላኪነት በላይ፥ ላለ ስራ የሚከጅለው መስሪያ ቤት እንደሌለ ስለሚያውቅ፥ ለሰውነቱና ለልብሱ ግሩም አድርጎ መጠንቀቅ ጀምሮዋል። ሌላ በስራ በኩል የሚያሳስበው ነገር ቢኖር፥ የሚሰራው ስራ በመጠኑም ቢሆን ለሱ ደስታን ለሚያገልግላቸው - ለመስሪያ ቤቱም፥ ወደሱ ክፍል ለሚመሩት ባለ ጉዳዮችም - ጥቅምን የሚሰጥ እንዲሆንና ወዲያው ምሽት ማግባት አስከትሎ ለሚመታው ጉዋዝና መዘዝ የሚበቃ ደመወዝ የሚያስገኝ እንዲሆን ነው።

ለብዙ ሴቶች - ባሎቻቸውን ለሚወዱት እንኳዋ - በጥሩ እቃ ያጌጠ ጥሩ ቤት ኖሮዋቸው ያን ለማሳየት ሲጋብዙ በጉዋደኞቻቸው ፊት መቶ ብር እንደ ትንሽዋ መሀረባቸው ከቦርሳቸው ሲመዘዙ መታየቱ የሚሰጣቸው ደስታ የባሎቻቸው ፍቅር ከሚሰጣቸው ደስታ ባይበልጥ አያንስም። ስለዚህ በጋብቻ ኑሮ እቤት ውስጥ ሰላም አግኝቶ ለመኖር ያን ያክል ባይሆን እንኳዋ ምሽት በጉዋደኞችዋ ዘንድ የማታፍርበት ቤት እንዲኖራትና በገንዘብ ተቸግራ ከጉዋደኞችዋ ያነሰች መስሎ እንዳይሰማት ራስን የሚያስችል ደመወዝ የሚያስገኝ ስራ መያዝ አስፈላጊ ነው። ብቻ ይህ አስቸጋሪ ሆኖ አልታዬውም። የሚያስቸግርና ያን ችግር ለማለፍ በጥንቃቄ የተጠና ዘዴ ለማግኘት ጊዜ የሚያስፈልገው መስሎ የታዬው ደመቀችን የማግባቱ ጉዳይ ነበር።

ደመቀች ከረዥም ጊዜ ጀምራ እንደምትወደው ቢያውቅም ልታገባው ፈቃደኛ ስለ መሆንዋ አለመሆንዋ እርግጠኛ አልነበረም። እደጃዝማች አሰፋ ተጫኔ ቤት አምስት አመት ስትኖር ከዚያ ቤት፥ ወንዶች ጋር ስለ ነበራት ጦርነት ሲተርክ የሰማው ሁሉ በጠቅላላው ከወንዶች ጋር እንዲኖራት የምትፈልገው ግንኙነት ምን አይነት እንደሆነ ለመገመት የሚያስቸግርና መስላ እንደምትታዬው አለመሆንዋን የሚያመለክት ነው።

በዬጊዜው እዬተከታተሉ የቀረቡት ወንዶች ሁሉ እንደ ልማድዋ በንጹህ ህሊና ገደም አድርጋ እያዩች፥ ስታጫውታቸውና ስትስቅላቸው፥ እያንዳንዱ ወንድ ያን አይነት ጭዋታና ሳቅ ከዚያ ገደም ያለ፥ አስተያየት ጋር በተለይ ለሱ፥ ብቻ ያሳዬችው የፍቅር ምልክት አድርጎ ይቆጥረውና የንጽህና ጉዋደኝነቱን ድንበር አልፎ በውድ ሳይሆንለት በግድ የግብረ - ስጋ ጉዋደኛ ሊያደርጋት ሲሞክር፥ ጭዋታውና ሳቁ ወደ ብርቱ ቁጣ ተለውጦ መጨረሻው ተጣልቶ መደባደብ ይሆናል።

መስላ የምትታዬውን ላለመሆንዋ፥ ደጀኔ አግደው ስለሚባለው ሰውና ስለስዋ የሰማው ታሪክ ካይነተኞች ምሳሌዎች አንዱ ነበር። ከደጀኔ አግደው ጋር ጎን ለጎን፥ ተቀምጠው፥ እዬተቀላለዱና እዬተሳሳቁ የሚጫወቱበትን ወይም አንዳንድ ጊዜ እጅ ለጅ አንዳንድ ጊዜ ትከሻ ለትከሻ ተያይዘው የሚሄዱበትን ሁኔታ፥ የማያውቁዋቸው ሰዎች ቢያዩ፥ ‹የግብረ - ስጋ ጉዋደኞች ናቸው› ብለው ሳያመነቱ በማሉ ነበር! ነገር ግን በመጨረሻ ደጀኔ እንዲያ ‹ሰው ምን ይለኝ› ሳትል በንጹህ ህሊና የጣለችበትን እምነት አጉድሎ የሌሊት ጨለማ ለብሶ ክፉ መንፈስ የተጠጋው ከሀዲ ብቻ የሚሰራውን ተንኮል ሊሰራ በመሞከሩ በበርበሬ ወጥ አጥምቃ እያስለፈለፈች ካጠገብዋ አባረረችው!

በሻህ ይህን ሁሉ ደመቀች መጀመሪያ ወንዶችን የምትወድ እምስላ ካንዳንዶችም ጋር በተቀራረበ ጉዋደኝነት ረዥም ጊዜ ኖራ፥ መጨረሻ ለጋብቻም ይሆን ለውሽምነት

ሲጠይቁዋት በብርቱ እዮተጣላች ስለ መለያየትዋ የሰማውን ሲያስታውስ እሱንም እንደ ሌሎች የማታደርገው ለመሆንዋ መተማመኛ ስላልነእብረው እንደ ምትወደው ቢያውቅም ፍቅርዋ ልታገባው ፈቃደኛ እስከ መሆን ድረስ የሚዘልቅ እንደ ሆነ የሚያረጋግጥበት ዘዴ ይፈልግ ነእብር። መቸም እንድታገባው ጠይቆዋት ‹እንቢ› ያለችው እንደሆነ እንዲያ ያለውን ስድብ እንዲያ ያለውን ውርደት ኩሩ ልብ የማይቀበለው ሊሸከመው የማይችል ከባድ ነገር ነው! ታዲያ እንዲህ ያለ ሁኔታ ደርሶ ለሱም ለስዋም፥ የማይበጅ ነገር ከማድረግ የሚያድን ዘዴ ማግኘት ይቻል እንደ ሆነ ለማሰብና ለማጥናት ነበር ዘለግ ያለ ጊዜ ያስፈለገው። ነገር ግን ያን ለት እንዳያት ሁኔታዋ ሁሉ ያን የፈልገውን ዘዴ እስኪያገኝ የሚሰጥ አልነበረም። ልጅዋ ፍቅርዋን አለኝታዋን ተስፋዋን፥ ሁሉ ይዞባት፥ በመሄዱ በዚህ አለም ምንም ያልቀራት ፍጹም ባዶ የሆነችና መኖር የማትችል ስለ መሰላት ፍቅር አለኝታና ተስፋ የሚሰጣት ቶሎ ካላገኘች ክፉ ነገር ሳይደርስባት እንደማይቀር እርግጠኛ ሆኖ የሚያደርገው ጠፋው። አንዳንድ ጊዜ እስከዚያ ድረስ፥ ባል ለማግባት የምትመኝ መሆንዋንና ለማግባት የምትመኘው ባል እንዴት ያለ እንደ ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ለማዋቅ እቅድ እየነበረው ሳይጠይቃት በመቅረቱ ራሱን ይወቅሳል። ብቻቸውን በተገናኙ ቁጥር፥ ስለ ራሳቸው አይሁን እንጂ፥ ስለ ሌሎች ወይም በጠቅላላ ስለ ጋብቻና ስለ ፍቅር ሳይጫወቱ ቀርተው አያውቁም። ታዲያ ያን ጊዜ ስለ ራስዋ ጠይቆ ማወቅ ይችል ነበር።

የስበሳቸውን ፍቅር ለዩብቻ በዩልባቸው አቅፈው እዮተጨነቁ መኖር ከጀመሩበት ጊዜ ጀምረው መቸም፥ ፍቅር ባያደርጉት ሲናገሩት ደስታ ስለሚሰጥ ብቻቸውን ከተገናኙ ሁልጊዜም ስለ ፍቅርና ጋብቻ ይጫወታሉ። ብቻ፥ እሱ ምሽት የማያገባበት ምክንያት ስለ ነበረው፥ እስዋ አድቀድሞ ከሱ ካልመጣ ለሱ ያላትን ፍቅርና ብታገባው የምትወድ መሆንዋን እንዳትገልጽለት የሴትነት ኩራትዋ አጥር ሆኖ እያገዳት ስለ ራሳቸው ፍቅርና ጋብቻ ስሜታቸውን ሳይገላለጹ ባመት የሚቆጠር ጊዜ በማለፉ፥ ምናልባት መንገድ ብትከፍትለት ስሜቱን የሚገልጽ ስለ መሰላት ስለ ሌሎች ወይም በጠቅላላ ስለ ፍቅርና ስለ ጋብቻ ማውራት ፈንታ ስለ ራሱ ፍቅርና ጋብቻ እንዲያጫውታት ልትጠይቀው አሰበች።

ለምሳሌ አንድ ማታ ከፍኖተ - ድህነት ትምህርት ቤት የማታ ትምህርትዋን ተምራ ወጥታ እንደ ተለመደው እስከ ቤትዋ ሲሸኛት፥ ዝናብና ዳጥ ስለ ነበረ በሻህ ለሁለቱም ጠለላ አንድ ጃንጥላ ይዞ ሲሄዱ ያለ ጫማ፥ ባዶ እግርዋን፥ በመሆንዋ አድጦዋት እንዳትወድቅ የፈራች መስላ፥ መጀመሪያ ጃንጥላ የያዘበትን ክንዱን ትንሽ ቆይታ ክንዱት ትታ ከሁዋልው በኩል ወገቡን ይዛ ትሄድ ጀመር። ነገር ግን እንዳትወድቅ

ከመፍራት ይልቅ ወገቡን የማቀፍ አምሮትዋ ገፍቶዋት ነበር እንዲያ አድርጋ የያዘችው። እንዲያ እሱ ጃንጥላውን እስዋ ወገቡን ይዛው፥ ልበቻቸው ፈጥነው እዬመቱ እግሮቻቸው ቀስ ብለው እዬተራመዱ ትንሽ እንደ ሄዱ፥

«ጋሼ፥ እስቲ አንድ ነገር ልጠይቅህ» አለች ቀና ብላ።

«ምን? »

«ምሽትህ በጣም መልከ መልካም በዚያ ላይ የተማሩ ነበሩ አሉ፥ ለምን ፈታሀቸው? »

«ሚስት አግብቸ መፍታቴን ማን ነገረሽ? ሰላይ አለሽ? »

«በምስጢር ኖሮዋል አግብተህ የፈታሀቸው? » ስትለው ሳቀና፥

«አንቺ ባልሽን ለምን ፈታሻቸው? » አለ ለጠዬቀችው መልስ በመስጠት ፈንታ።

«የኔው የተለዬ ነው።»

«የሁለታችንስ ጋብቻ ፍቺ አደል? ምን ልዩነት አለው? »

«እኔማ - ገና ትንሽ ልጅ ሳለሁ አባቴ ለማላውቀው ሰው ሰጡኝና - ሳይሆነኝ ስለ ቀረ፥ ትቸው ወደዚህ መጣሁ። አንተ ግን - መቸም ካዲስ አበባ ቆነጃጅት ሁሉ እሳቸውን ‹ይሆኑኛል› ብለህ መርጠህ ሳይሆን አይቀርም ያገባሀቸው።»

«አዎን መጀመሪያ እስዋም እኔም የምሆሁዋን መስሎን ተጋብተን ነበር። በሁዋላ ሳንሆሁዋን ስለ ቀረ ተፋታን።»

«አሁን - የምታገባ ብትሆን እንዴት ያለች ሴት ነው ማግባት የምትፈልግ? »

«ሁለተኛ - ሚስት ላላገባ ወስኛለሁ» አለ ትንሽ ዝም ብሎ ቆይቶ እያመነታ፤

«አሁን ይወሰንኸውን ለውጠህ - እንደገና ለማግባት ብትወስንስ? »

«ለማግባት የምፈግ ብሆን - እኒያን ደማም እመቤት ወይዘሮ ላቀች ተገኜን ነበር የማገባ! » አለ እየሳቀ።

«እሳቸውማ - አያትህ አይሆኑም? ወዲያውስ ባለ ባል አደሉ? » አለች እስዋም እየሳቀች።

«እ - ! ለካስ ባለ ባል ናቸው! እንግዲያስ - ያነለት እሳቸው እንደ ተረኩልን ያለች ሲያዩዋት ስርቅ አድርጋ አይታ አይኖችዋን የምታሸሽ ሊይዙዋት ሲከተሉዋት ልብዋ ‹እሺ› ሲል፥ አፍዋ ‹እምቢ› እያለ፥ የፍቅርን ጎዳና ቶሎ እንዳያልቅ እዬጎተተች ማስረዘም የምታውቅ ጥሩ ልጅ ያገኙሁ እንደሆን ነው የማገባ! » አለ እንደ መሳቅ ብሎ። ከቤትዋ ያጥር በር ደርሰው ቆመው ነበር። እንዲያ እንደ ቆሙ ያ፥ ስሎ ያሳያት ስእል እስዋን የሚመስል ሆኖ ታይ ጀምር። እሱም እንደስዋ ዝም ብሎ አይን አይንዋን ያይ ጀመር። ያን ጊዜ በሁለቱም ውስት የፍትወት እሳት ነድዶ ያቃጥላቸው ስለ ጀመረ፥ እሱ ‹በይ እንግዲህ ግቢ፥ ነገ አይሻለሁ› ብሎዋት እንዲያ ያለ እሳት ሲያቃጥለው ወደሚያጠፋበት ቸኮለ። እስዋ ግን ያን እሳት ለማጥፋት የምትሄድበት ስላልነበራት፥ በውስጥዋ ነድዶ ነድዶ ልብዋን አንድዶ አክስሎ፥ በገዛ እጁ እስኪጠፋ ድረስ አፍና ይዛው ወደ ቤትዋ ገባች።

በሻህ መከዳውን ከፍ አድርጎ፥ በዚያ ላይ እጆቹን አመሳቅሎ ተንተርሶና በጀርባው እንደ ተንጋለለ ይህን ሁሉ፥ በመሀከላቸው ይደረግ የነበረውን የፍቅር የድብብቆሽ ጭዋታ በትዝታ መልሶ አምጥቶ ባይነ - ህሊናው እያሳለፈ ዝም ብሎ ሲያሰላስል ሲያብሰለስል ቆይቶ፥

«እ - ህ አሁን ያንጊዜ፥ ‹አንቺስ ባል ማግባት ታስቢ እንደሆነ እንዴት ያለ ባል ማግባት ነው የምትመኚ?› ብሎ አይጠይቅም ሰው? እድኒያ ብዬ ብጠይቃት ኖሮ ባል ማግባት የምታስብ መሆንዋን እንዴት ያለ ባል ማግባት እንደምትመኝ ትነግረኝ ነበር። ሊላ ቢቀር ባል ማግባት መፈለግ አለመፈግዋን አውቅ ነበር» አለ የሚያስብ እንጂ የሚናገር ሳይመስለው ድምጹን አሰምቶ። ‹እንዲህ ያለው መልካም እድል ስለፈ፤ እንግዲህ ተመሶ አይመጣ! የሚመጣ ቢሆንም እሱን ለመጠበቅ ጊዜ የለ! ተመልሶ አይመጣ! የሚመጣ ቢሆንም እሱን ለመጠበቅ ጊዜ የለ! ታዲያ አሁን ምናባቴን ላድርግ?› አለ ባሳቡ። ከዚያ አልጋው ላይ እንደ ተንጋለለ ስላለፈው ማሰቡን ትቶ አይኖቹን በዚያ ጥቁር ጨለማ ላይ አፍጥጦ ስለ የወደፊቱ ዘለግ ያለ ጊዜ ሲያስብ ቆዬና፥

«አሁን ሲነጋ ሄጄ እወንቱን እነግራታለሁ። ከመጠን ያለፈ የምወዳት መሆኔንና ያን ያክል ጊዜ ሳልገጽላት ስጨነቅ የኖርሁ ምሽት ላላገባ የማልሁት መሀላ የገባሁት ቃል ኪዳን ስለ ነበረብኝ መሀላየን ማስረሱ ጨንቆኝ መሆኑን ገልጨ ከንግዲህ ወዲያ ግን፥ እስከ ዛሬ የኖርሁትን የስቃይ ኑሮ መቀጠል እንደማልችል ስለ ተረዳሁ መሀላየን አፍርሼ ቃል ኪዳኔን ጥሼ የምትፈቅድልኝ ከሆነ እስዋን ላገባ የወሰንሁ መሆኔን

እነግራታለሁ። መቸም ይህን ሁሉ ስገልጽላት ለስዋ ፍቅር ብዬ መሀላየን ማፍረሴን ስነግራት ‹እንቢ› አትል!

«ግን - ‹እንቢ› ብልትስ? »

«እንዴት አርጋ ‹እንቢ› ትላለች? አምኘበት የኖርሁትን ሃይማኖቴን ከጀ በስዋ ፍቅር ማመንን መርጬ እንድትቀበልኝ፥ ስለምናት፥ ስማጠናት ‹እንቢ› ትለኛለች? አትለኝም! ይህን ሁሉ ገልጬላት ካወቀች በሁዋላ ‹እንቢ› ካለች ግን - እግዜር አያድርገው እንጂ የስዋም የኔም መጨረሻችን ይሆናል! እስዋም እኔም እናርፋለን! እስዋ በዚያ ርጉም ልጅዋ ምክንያት ስትሰቃይ ከመኖር ታርፋለች። እኔም በርካሽ የግብረ - ስጋ ተግባር ሊደፍሩዋት ፈልገው ውቃቢ እያራቀች እያዋረደች ካባረረቻቸው ጎረምሶች ተራ ገብቼ እንደነሱ መሳቂያ ሆኘ ከመኖር እድናለሁ! ይህ እንዳይደርስ እግዜር ቅን ያስመከራት እንጂ፥ ከደረሰ መጨረሻው ይህ ይሆናል! » አለና መብራት አብርቶ ሰአቱን ሲያይ ነግቶዋል።

በሻህ ‹መልካም፥ ወይም ክፉ› ሊባል የሚችል ባህሪ ይሁን ጣባይ ነበረው። እሱም አንድ ውሳኔ ለማድረግ ጊዜ ይወስድበት እንደሆነ እንጂ ከወሰነ በሁዋላ ውሳኔው አላማውን መትቶ ወይም ስቶ እስኪያይ ድረስ ማረስ የማያውቅ ማረፍ የማይችል መሆኑ ነው። ስለዚህ ያነለት ስለ ወሰነው ውሳኔ ከደመቀች ጋር ተገናኝቶ እስኪያናግራት ድረስ በመቸኮሉ በጥዋት ተነስቶ ተጸዳድቶ ጢሙን ተላጭቶ ተጣጥቦ ለባብሶ፥ ሲጠብቅ፥ የመገናኛ ሆቴል ሰራተኞችና ወጥ ቤቶች ቁርስ ሰርተው አሳላፊዎች ገበታ አሰናድተው እስኪያቀርቡ፥ ጊዜው ከተለመደው ብዙ እጥፍ መስሎ ታዬው። ከዚያ ሲተናነቀው በሻይ እያስወረደ በልቶ ሽጉጡን ስድስት አቅሞ በኪሱ አግብቶ፥ ደመቀች ወዳለችበት ወደ አዛዡ ተካልኝ ቤት ቸኮለ። ከዚያ ሲደርስ ሰአቱ በሁለትና በሶስት መሀከል ስለ ነበረ አዛዡ ወደ ጌታቸው ግቢ ሄደው ባልተቤታቸውን ወይዘሮ ጌጤን ብቻ አገኘና ሰላምታ ከተሰጣጡ በሁዋላ ደመቀች እንዴት እንዳደረች ጠዬቃቻቸው።

«የስዋ ነገር ያሳዝናል፥ እባክህ! ታንንት ማታ ራት ዛሬ ጥዋት ቁርስ እንድትቀምስ ብወስድላት ‹ትኩሳት ስላለብኝ፥ እህል እንኩዋንስ መብላቱ ሽታው ሆዴን አወከብኝ› ብላ ምንም አልቀመሰች፤ እንዲሁ እግዜርዋ እንደ ሰራት ናት። እስቲ አንተን ‹እሺ› ትልህ እንደሆነ ለምናት» አሉ ወይዘሮ ጌጤ።

«እስዎን ‹እሺ› ያላለች እኔን ‹እሺ› ትለኛለች? »

«ምን እኔ ብቻ ጌታም ለምነው አልሆነላቸው እንጂ! »

«አሁን ተንቀልፍታ ይሆን? » አለ ‹ተንቀልፍታለች› ቢሉት በመጣ፥ እግሩ ለመመለስ፥ አስቦ። በሻህ ከደመቀች ጋር ተገናኝቶ የሞተ - ሽረቱን ቁርጥ ለማወቅ እዬቸኮለ እንዳልመጣ ሁሉ እዚያ ከደረሰ በሁዋላ፣ ባለችበት ክፍል መግባቱን እንኩዋ ፈርቶ ‹ልግባ አልግባ?› እያለ ያመነታ ጀመር።

«ቅርብ ጊዜ ገብቼ ሳያታልተንቀለፋችም ነበር። እስቲ ግባና እያት አልተንቀለፋች ይሆናል» አሉ ወይዘሮ ጌጤ ሲያመነታ ስላዩት። ከዚያ በቀስታ ራመድም ቆምም እያለ ሄዶ፥ ደመቀች ባለችበት ክፍል ሲደርስ፥ መዝጊያው ከበሩ መቃን ጋር ገጥሞ ሳይዘጋ፥ እንዲሁ ገርበብ ብሎ አገኘው። ወይዘሮ ጌጤ፥ እንዳሉት ቀደም ብለው እስዋ ዘንድ ቆይተው ሲወጡ በቅጥ አልዘጉት ኖሮዋል።

ደመቀች ትራስዋን ባልጋዋ ራስጌ አስደግፋ፥ ያን ትራስ እንደ ተጠጋች ከወገብዋ በላይ ቀና ብላ በግማሽ ተቀምጣ፥ ትታያለች። በሻህ ፊት ለፊት የቆመ እንደሆነ እንዳታየው ጎድን ገብቶ፥ ግድ ግዳውን ተጠግቶ ሲመለከታት ከምን ጊዜም የበለተ ተውባ ታዬችው! ትኩሳት ስለ ነበረባትና ጭንቅ ጭንቅ ስላላት፥ ሌሊት ደራርባ የለበሰቻቸውን ኩታና ብርድ ልብስ ወደ ታች ገፍታ እንደ ሸንኮር አጥቅ አጥቅ ያሉ ውብ አንገትዋ እስከ የላይ ክፍል ደረትዋ ራቁትን ይታያል። ጥቁር ዞማ ጠጉርዋ ተመሰቃቅሎ ቅጡን አጥቶ ቀኝና ግራ እስከ ትከሻዎችዋ ወደ ፊት እስካይኖችዋ ወርዶ ተዘርግፎዋል! ከዚያ ውስጥ ሲያለቅሱ ውለው ያደሩ አይኖችዋ እንባ ያጠራ ይመስል ጥርት ብለው በሌሊት ጥቁር ጨላማ እንደሚያበሩ ከዋክብት ይፍለቀለቃሉ! ፊ - መልክዋ ከህልና ከውሀ መለየት የውበት አብነት እንደ ሆነ ሁሉ ምንጊዜም ይበልጥ ተውበዋል! ታዲያ እንዲያ ትራስዋን ተጠግታ በግማሽ እንደ ተቀመጠች ከታች ከራቁት አንገትዋ ደረትዋ እስከ ላይ እስከ ራስ ጠጉርዋ ባንድነት በሻህ በቆመበት ቆሞ እንደ በሻህ ለሚያያት እንዲያ መነሳቀልዋ መጉላላትዋ መንገላታትዋ ያ ሁሉ ሆነ ተብሎ ለማሳመር ለማስጌጥ የተደረገ ይመስል፥ እጅግ አሳምሮዋት ነበር! እንዴት ታምራለች! እንዴት ታሳዝናለች!

በሻህ ግድግዳውን ተጠግቶ እንደ ቆመ ያን የሚያሳዝን ውበት ዝም ብሎ ሲመለከተ ቆይት ሊያነጋግራት እዬቸኮለ የመጣለትን ሲያስብ አሳዘነችውና ልቡ በውስጡ ሲሽበር አንጀቱ ሲላወስ ተሰማው! ወዲያው አይኖቹ እንባ ሞሉ! በፍቅር ፊት የሚቆም ቆራጥ ጀግና ይኖር ይሆን! መውደድ እንዳይችል ሆኖ የተፈጠረ ይኖር

እንደሆን ነዋ! በሻህ ግን ቆራጥ ጀግና ቢሆንም ከወደደ አጥብቆ የሚወድ ልብ ያለው ሰው በመሆኑ፣ ቆራጥ ጀግናነቱ ለጠላቱ ነበር እንጂ፥ በሚወደው ፊት በፍቅር ፊት ወላዋይ ፈሪ ነበር። ስለዚህ፥ ያነለት ለማድረግ ወስኖ የመጣልት ነገር ለፍቅሩ መጨረሻ ወደሚሆነው መንገድ ሊመራ የሚችል ስለ ነበረ፥ ምንም እንኩዋ የስዋ ሁኔታ ረዥም ጊዜ የማይሰጥ ቢሆን ያነለት ስለ ጋብቻቸው ማንሳቱን አቆይቶ ካዝማራው ውቤ ጋር መመካከሩ የሚሻል መስሎ ታየው።

«አዎ ይሻላል። እስቲ ቀድሜ ከጋሽ ውቤ ጋር ልነጋገር» አለና ገርበብ ያለውን መዝጊያ ድምጽ እንዳይሰማ ቀስ ብሎ ገፋ አድርጎ አንገቱን ብቻ ገባ ሲያደርግ አይኖችዋን ቀና አድርጋ አይታ፥

«አንተ ነህ ጋሽ?። ግባ እማማ መስለውኝ ልቆጣ ቃጥቼ ነበር» አለች ደመቅች ፊትዋን በቅርታ ፈገግታ አስጊጣ።

«እንዴት አደርሽ? ለ - መሆኑ እማማ ጌጤ ቢሆኑ ለምን ኖሮዋል የምትቆጪ? » አለ ገብቶ በሩን ከዘጋ በሁዋላ፥ አጠገብዋ በነበረው ወንበር ሲቀመጥ።

«እሳቸው ‹ብይ› ከማለት በቀር ሌላ ነገር ካፋቸው አይወጣም። ትናንት ማታ ብርቱ ትኩሳት ተንሰቶብኝ እንደ ወባ ሲያራግፈኝ እያዩ፥ አባባም እሳቸውም ‹እንዲህ ያለው መብላት ነው መድህኒቱ ብይ› እያሉ ሲጨቀጭቁኝ እመሜን ልቻል? ወይስ ከነሱ ጋር ልሙዋገት? በመጨረሻ ‹ካልትዋችሁኝ ወጥቼ እሄዳለሁ› ስላቸው ጊዜ ሁለቱም አኩርፈው ወጡ። አባባ ኩፊያው አላለፈላቸውም መሰለኝ - ዛሬ ጥዋት ‹እንዴት አደርሽ› ሳይሉኝ ወደ ስራቸው ሄዱ። እማማ ግን ቁርስ ይዘውልኝ መጥተው ነበር። ብቻ ገና ከሩቅ ቡናው ሲሸተኝ ሆዴን ስለ ታወከብኝ ‹ትንሽ ልቆይ› ብዬ መልሻቸው ነበርና አሁን በሩን ስትከፍት እሳቸው ‹ብይ› ሊሉኝ የመጡብኝ መስሎኝ ነው - ልቆጣ ቃጥቶኝ የነበር።»

«እማማ ጌጤ በጣም አዝነዋል። የሙብል ፍላጐት ባይኖርሽም ሆድሽ የሚቀበልሽ ከሆነ ደስ እንዲላቸው ትንሽ እህል ብትቀምሺ መልካም ነውኮ! »

«አሁን ተሽሎኛል። አባባ ከስራ ሲመለሱ ምሳየን አብሬያቸው እበላለሁ። አሁን ይልቅስ - እኔ አለ መብላት እስኪርበኝ ነው እንጂ ከራበኝ እንኩዋንስ ለምነውኝ ለምኘኔ ስለምበላ - እሱን እንተውና ሲቆረቁረኝ ወዳደረው ነገር እንመለስ። ትናንት ስላሳዘንሁህ እባክህ ይቅር በለኝ፥ ጋሽ። ያን ያክል አብረኸኝ ስተንገላታ ውለህ ‹እግዜር ይስጥልኝ›

በማለት ፈንታ መከራየን አንተ ያመጣህብኝ ይመስል ተቆጥቼ ሰላምታ እንኳዋ ሳልሰጥህ አባረርሁህ። ከሄድህ በሁዋላ ጥፋቴ፥ ብልግናየ ትዝ ሲለኝ በጣም አዘንሁ፤ አፈርሁ።»

«እኔን ያሳዘነኝ ያንቺ ሁኔታ ነው እንጂ አሁን ያልሽውን ጭራሽ አላሰብሁትም። አንቺንም ፈጽሞ የሚያሳስብሽ አደለም። ብቻ የሚገባኝ፤ ‹መከራ› ያልሽው ነው! የምን መከራ? ልጅሽ በትምህርት ቤቱ ከጉዋደኞቹ በትምህርት በልጦ ተመርጦ ወደ ከፍተኛ ደረጃ ወደ ሹመት የሚያደስ ከፍተኛ ትምህርት ወደ ሚገኝበት አገር መሄዱ ደስ የሚያሰኝ የሚያኮራ ነው እንጂ - የሚያሳዝንና የሚያስለቅስ መከራ ነው? ይህ ነው የማይገባኝ ማነንም የማይገባው! »

«አዎን እውነትህ ነው። እኔ የማውቀውን የማያውቅ ሁሉ ማንም ቢሆን ሊገባው አይችል! »

«መልካሙን ወደ ክፉ ለውጦ እንዲህ የሚያሳዝንና የሚያስለቅስ ምን ነገር አለ? ምስጢር ካልሆነ፥ እስቲ - አትነግሪኝም? »

«እስኪደርስ ነበር ምስጢርነቱ! እንዲህ መድረሱ ላይቀር የተናገርሁት እንደሆነ ይደርስብኛል› ብዬ ፈርቼ በልቤ፥ ውስጥ ተደብቆ ሲያስፈራራኝና ሲያስጨንቀኝ ለማንም ላልተነፍሰው በምስጢር ይዤው እኖር ነበር። አሁን ደረሰ! እስከ ዛሬ ድረስ እንኩዋንስ ለሰው ልናገርው ብቻዬን ሆኘ ሳስበው እንኩዋ ‹በውነተኛ ስሙ የጠራሁት እንደሆነ እውነት ይሆናል› ብዬ ፈርቼ ‹ቅዠት› ስለው ነው የኖርሁ! አሁ - አሁን የፈ - የፈራሁት ስለ ደረሰ ብናገረውም ግ - ግዴለ! » አለችና ሳግ አላናግራት ስላለ ታሪኳን አቁዋርጣ ስቅ - ስቅ ብላ ታለቅስ ጀመር።

«እኮ ምንድነው የደረሰው? እባክሽ እንዲህ ሆድ አይባስሽ የኔ እመቤት! እስቲ ማልቀሱን ተይና የጀመርሽውን ጨርሽልኝ» አለ የሚያደርገው ግራ ገብቶት። ደመቀች ዝም ብላ ስታለቅስ ቆይታ፥ ትንሽ ጸጥ ስትል ከትራስዋ ግርጌ መሀረብዋን አውጥታ፥ አይኖችዋንም አፍንጫዋንም ለመጠራረግ ብትሞክር መሀረቧ ከመራስ አልፎ በስቦስ ስለ ነበረ በማድረቅ ፈንታ ካይኖችዋ የተቀበልውን እንባ ላካባቢው ፊትዋ አዳረሰው።

«እሱ ረጥቦአል፥ እኔ ትርፍ መሀረብ ስላለኝ እስቲ እንኪ አይንሽን በዚህ አድርቂው» አለ ከደረት ኪሱ መሀረቡን አውጥቶ።

«መነሳቱን ሰንፎ ነው እንጂ መሀረቦች እዚያ ሳጥን ውስጥ አሉኮ ጋሽ» አለች ትንሽ እንደ ማፈር ብላ።

«ቢኖሩም ያንቺ መሀረቦች ትንንሾች ይሆናሉ፤ ይህ ትልቁ ይሻላል» አለ መሀረብ የያዘ እጁን እንደ ዘረጋ። ከዚያ መሀረቡን ተቀብላ የረጠበ ፊትዋን ሁሉ አደራረቀችና ታሪክዋን ቀጠለች።

«አብዬ ትምህርት ቤት እንዲገባ የተፈቀደለት መሆኑን አባባ በስልክ ሲሰሙ ለኔ ሳይነግሩኝ እዬሮጡ እዚህ ቤት መጥተው ለማማ ነግረው፥ - ባንድ ቀን እንዲያ ያለ ድግስ ማሰናዳት እንዴት እድነ ተሳካላቸው አላውቅም - እዚህ አካባቢ የሚኖሩትን ጎረቤቶች ሁሉ ከነልጆቻቸው ጠርተው ማታ ግሩም የሆነ የደስደስ ግብዣ አድርገው ነበር። እኔንም ‹ጌጤና እኔ የተጋባንበትን አርባኛ አመት የምናከብርበት በአላችን ነውና፥ በጊዜ ተሰናብተሽ ከሌሎች ቀድመሽ እንትደርሺ› ብለው የውሽት ምክንያት ፈጥረው ጋብዘውኝ ነበር። ያነለት ሌሊቱን ሙሉ የነበረውን ዘፈንና የግጥም ጭዋታ ደስታውን ውካታውን ምን ብዬ፥ ልንገርህ? ግሩም ነበር! ጋሽ ውቤም ነበር። እንዲሁ ስናወካ አደርን፥ ሊነጋ ትንሽ ሲቀረው ተለያይተን ሁላችንም ትንሽ እንኩዋ ለማረፍ ያክል ወደ የምኝታችን ሄድን።

«ከዚያ ሁሉ ደስታና ጭዋታ በሁዋላ አብዬን ይገፎ፥ እንደ ተኛሁ፥ ትምህርት ቤት እንዲገባልኝ ለማውቀው ታቦት ሁሉ ስሳልን ስማጠን ያልኖርሁ ይመስል፤ ስእለቴ ደርሶ ወደ ትምህርት ቤት መሂዱ ቁርጥ ሲሆን ከሱ መለየቱ ሞት መስሎ ታይቶኝ፣ ጭንቅ ያዘኝ። በሄደበት በሰው ደርሶ የማያውቅ ችግር ሁሉ የሚደርስበት መስሎ ታይቶኝ ፍራት ያዘኝና ትምህርት ቤት እንዲያገቡልኝ ሚንስትሩን መለመኔ ለእግዚአብሄር መጸለዬ ለታቦት መሳሌ፥ ይህ ሁሉ አስጸጸተኝ! እንዲያ ፈርቼ አዬተጨነቅሁ ራሴን የማጽናናበት ነገር ስፈልግ ትንሽ ሽልብ ያደርገኛል። አልተንቀላፋሁም፤ አይኔ እንኩዋ በውል አልለበሰም ነበር! ወዲያው አብዬ ካኪ ኮትና ቁምጣ ሱሪ ለስቦ ቀይ ጫማ አድርጎ ጠጉሩን ተከርክሞ አምሮበት መጥቶ እፊቴ ይቆማል! እንዲያ አምሮበት ሳየው ደስታ ይውጠኝና እቅፍ አድርጌ ይገፎ ስስመው ምንም የነካሁ አይመስለኝም፤ ከንፈሬን ብቻውን ሲጮህ ብቻ ይሰማኛል! ከቀኝ እቅፎ ወደ ግራ ከግራ እቅፎ መልሼ ወደ ቀኝ እያገላበጥሁ አጥብቄ ይገፎ ስስመው አሁንም ባዶ ነገር አቅፎ እንደምስም ምንም አይሰማኝም! በመሀከሉ አቡ በሽር የሚባሉትን የጨርቅ ነጋዴ ታውቃቸዋለህ? እሳቸው ይመጡና ‹ልጄን አቅፈሽ የምትስሚው ልትወስጅብኝ አምሮሽ ነውይ› ብለው

ከቅሬ ነጥቀው ይዘውብኝ ሲሄዱ ‹እባክዎ የሚፈልጉትን ዋ ጋ እከፍላለሁ ልጄን መልሱል› እያልሁ እዬለመንሁ ተከትያቸው ሮጣለሁ ልጄን ይመሱልኝ› እያልሁ እዬለመንሁ ተከትያቸው ሮጣለሁ! ነገር ግን ሳልደርስባቸው በመሀከላችን አንድ ሰፊ ጉድባ ይከፈትና ያግደኛል! ከዚያ ጉድባ ዳር እንደ ቆምሁ አቡ በሽርን ስማጠን፥ አብዬ እጁን እያርገበገበ ‹እመዬ ተለያዬን ከንግዲህ አንገናኝም! » እያለ እሱም አቡ በሽርም እጉም ውስጥ ገብተው ይጠፉኛል» ስትል እጁን እያርገበገበ እጉም ውስጥ ገብቶ ጠፋባት ሁኔታ ታያትና እንደገና የምትተርከውን አቁዋርጣ «እኔ ልጥፋልህ ልጄ! አፈር ልብላልህ ልጄ! » እያለች ማልቀስ ጀመረች።

«እባክሽ ልቅሶው ይብቃሽ እኔ እንደዚህ ስታለቅሺ ማየት አልችልም፤ ይጨንቀኛል! ለመሆኑ ይህ ነው ‹ሲያስፈራራኝ ኖሮ አሁን ደረሰ› ብለሽ የምታለቅሽበት? » አለ እውነትም ስታለቅስ ማየቱ አሰቅቆት፤ አስጨንቆት።

«ይህ ብቻ አደለም ከዚህ የከፋው ገና አለ» አለችና፥ ትንሽ ዝም ብላ በሰጣት፥ መሀረብ አይኖችዋን ስትጠራርግ ቆይታ፥ ቀጠለች።

«ሀሙስለትምህርት ቤት የሚሆነውን ልብስና - አንዳንድ ነገር ልንገዛ አባባ ገብያ ይዘውን ወጡ። መጀመሪያ ልብሱን እንዲሰፉልን እጋሽ ታዬ ሱቅ በሄድንበት ካንተ ጋር ተገናኝንና ሌላውን ሁሉ ያው - አንተ ገዛህልን። በነጋው አርብም ፍል ውሀ ወስጄ ሳስታጥበው፥ ወደ ጠጉር አስተካካይ ወስጄ ሳስከረክመው እቤት የሚታጠበውን ልብስ ሳጥብ የሚተኮሰውን ስተኩስና ሌላ ሌውንም የሚያስፈልገውን መሰናዶ ሳሰናዳ ሀሙስና አርብ ጭራሽ ነፍስ አልነበረኝም። ስለዚህ ህልሙ ከራሴ ውስጥ ጠፍቶ ረስቸው ነበር። ቅዳሜ ጥዋት ካባባ ጋር ወደ ትምህርት ቤት ይዘነው ልንሄድ ቁርሱን አብልቼ አጥቤ ጠጉሩን አበጥሬ ልብሱን አልብሼ ሳየው፥ ‹ከዚህ በቀር› የማይባል ልክ ያ በህልሜ ያየሁት ሆነ! ያንጊዜ ድንጋጤየን ብታይ! በድን ሆንሁ! እንደዚህ ያነለቱ እንዳያመልጠኝ ፈርቼ በሁለት እጆቼ አጥብቄ ይዤ ስስመው ልክ እንደዚያነለቱ፥ እጄም አፌም እንዲያው ሰውነቴ ሁሉ የደነዘዘ ይመስል ምንም አይሰማኝም ነበር! እሱ የሚናገረውን እንኩዋ አልሰማው ብሎ ከንቅልፌ እንደሚቀሰቅሰኝ እዬነቀነቀ ‹ስናገር የሚትሰሚኝ ምን ሆነሽ ነው?› ሲሉኝ ነው - ነፍሴን አውቄ ለጠዬቀኝ መልስ መስጠት የጀመርሁ! ከዚያ ትምህርት ቤት ደርሰን ከተቀበሉን በሁዋላ ደግሞ ልንለያይ ስንል ባብቶ እኔን «አልለቅም» ብሎ ማልቀስ ስለ ጀመረ የተማሪዎች ሞግዚት - አቡ በሽር እንዳደረጉት - ከኔ ነጥቀው ሲወስዱት ልክ በህልሜ እንዳየሁት እጁን እያርገበገበ

‹እመዬ ተለያዬን እንግዲህ አንገናኝም› ብሎኝ ሄደ። ይህ ነው፥ እስከ ዛሬ በልቤ ውስጥ ተደብቆ ሲያስፈራራኝ የኖረ! እና - ‹ከልቤ አውጥቼ የተናገርሁት እንደሆነ፥ እውነት ይሆናል፥ ልጄ ይሞትብኛላ!› ብዬ ፈርቼ ለማንም ተንፍሸው አላውቅም ነበር! አሁን፥ ሄዶ ይሞታል ወይም በሄደበት ሳንገናኝ እዚያው ይቀራል - ! እንግዲህ ‹ማ - ማን አለኝ› እላለሁ? » ብላ እንደገና ያን የማያልቅ እንባዋን ታወርደው ጀመር።

«ይህ ብቻ ከሆነ ‹በልቤ ውስጥ ተደብቆ ሲያስፈራራኝ ኖረ› ያልሽውን አሁን ይህን ያክል ተስፋ አስቆርጦ የሚያስለቅስሽ በውነት ምንም አደል። ልጅሽ እንኩዋንስ ሞት፥ ምንም አይደርስበት፤ በሄደበትም አይቀር። ትምህርቱን ተምሮ በደህና ይመለሳል። ይልቅስ ባሁኑ ሁኔታሽ ከቀጠልሽ የሚያሳዝን ክፉ ነገር ሊደርስብሽ የሚችል ባንቺ ላይ ነው።»

«እንዴት ምንም አደል? ከዚህ የበለጠ የሚያስፈራ ነገር አለ? ከህልም እንኩዋ ራእይ አደለም? ገሀድ አደለም? » አለች፥ በንባ የሚታጠብ ፊትዋን ወደሱ ቀና አድርጋ።

«እኔ የህልምንና የራእይን ልዩነትም ትርጉማቸውንም አላውቅ። ብቻ የሚያውቁ ሰዎች ሲናገሩ የሰማሁትንና እኔም በራሴ የደረሰውን ስከታተል እውነት ሆኖአ ያገኘሁት ህልምም ይሁን ራእይ ሆኖ የሚታይ ቀን ወይም በማናቸውም ጊዜ እንቅልፍ ሳይዝ ያሰቡት ነገር ነው። አንድ ወይም ልዩ ልዩ የሚያሳስቡ ነገሮች ቀን የታሰቡ እንደ ሆነ እኒያ የታሰቡ ነገሮ በንቅልፍ ጎልተው አንዳንድ ጊዜም መልካቸውን ትንሽ ለወጥ አድርገው የሚያስፈራሩ ሆነው በህልም ይታያሉ። ለምሳሌ አንቺ ካኪ ኮትና ቁምጣ ሱሪ ጫማ ለልጅሽ ለመጋት ያሰብሽ ህልሙን ከማየትሽ በፊት ነው። በህልምሽ ለብሶ ያዬሽው ያኑ አስበሽ የገዛሽውን ነው እንጂ - ህልምሽ የፈጠረው አዲስ ነገር አደለም! እንዲሁም አሁን እንደ ነገርሽኝ ልጅሽ ተለይቶሽ ባዳሪነት ትምህርት ቤት የሚገባ መሆኑን ቁጥ ስታውቂ በሰው ደርሶ የማያውቅ ችግር የሚደርስበት መስሎ ታይቶሽ በጣም ፈርተሽ በጣም ተጨንቀሽ ስለ ነበረ አቡ በሽር ከቅፍሽ ነጥቀው ሲወስዱትና እጁን እያርገበገበ እያለቀሰ እጉም ውስጥ ገብቶ ሲጠፋ፥ ያዬሽው ያ ህልሙን ከማለምሽ በፊት ‹ምን ክፉ ይደስበት ይሆን?› እያልሽ ስታስቢ ስትጨነቂ የቆዬሽው መልኩን ለወጥ አድርጎ፥ የሚያስፈራራ ህልም ሆኖ ታይቶሽ ነው። እና - ይህ የነገርሽኝ ህልም ያሳዬሽ ስላልሆነ እንኩዋንስ ይህን ያክል እግዚአብሔር ከበሽታ ላይ ሊጥል ምንም የሚያሳስብ ባለመሆኑ በከንቱ ራስሽንም ሰውንም አታስቸግሪ በልጅሽም መአት አታውርጅበት! ለወደፊቱም የምመርክሽ በህልም ማመኑን እንደ ምንም ብለሽ

እንድትተይው ነው። ያለዚያ የህልም ባሪያ ሆነሽ ህልም ባዬሽ ቁጥር እንደ ፈራሽና እንደ ተጨነቅሽ ትኖሪያለሽ። ህልም የማያምኑ ሰዎች አይፈሩም። ስለዚህ በሰላም ይኖራሉ። ደግሞ» አለ ንግግሩን ቆም አድርጎ ትንሽ ዝም ብሎ ቆይቶ፥ «ደግሞ ይቅርታ አድርጊልኝና በዚህ አጋጣሚ ሌላ ነገር ልንገርሽ። ይህን ሁሉ ያመጣው የዚህ ሁሉ ጠንቅ አንቺ ለልጅሽ ያለሽ ፍቅር ከናትነት ፍቅር አልፎ እንጃ፥ ምን ልበለው? ሌላ ባህሪና ሌላ መልክ እስኪይዝ ድረስ ቅጥ ያጣ መሆኑ ነው! እንዲህ ያለው ጥቅ ያጣ እስኪይዝ ድረስ ቅጥ ያጣ መሆኑ ነው! እንዲህ ያለው ቅጥ ያጣ ፍቅር፥ ልጅሽ ትንሽ ካይንሽ ሲርቅ እንድያውን ጠፍቶ የሚቀር አስመስሎ እያሳዬ ያስጨንቅሻል! ሌሎች ወላጆች ለልጆቻቸው የሚመኙትን መልካም እድል አግኝቶ ለከፍተኛ ትምህርት ሲሄድ እንኩዋ ወደ ሞት አገር የሄደ አስመስሎ አሳይቶሽ ይኸው፥ - እበሽታ ላይ ለመውደቅ ደርሰሻል! እንዲህ ያለው ከመንገድ ሁሉ የወጣና ቅጥ ያጣ ፍቅር ላንቺም ለሱም መልካም ካለ መሆኑ ሌላ ሊዘልቅ ሊቆይ እንኩዋ የማይችል መሆኑን አስቀድመሽ ማወቅ አለብሽ። ከንግዲህ ወዲያ እሱ ትምርቱን አስቀድመሽ ማወቅ አለብሽ። ከንግዲህ ወዲያ እሱ ትምርቱን ሲጨርስ ካንቺ ቅርብም ይሁን ሩቅ - ባገኘው ቦታ - ስራውን ይዞ ሚስቱን አግብቶ፥ ትዳሩን መስርቶ የራሱን ኑሮ ይኖራል እንጂ፥ አንቺ ካጠገብሽ ቢርቅ ስለማትወጂ ብቻ ትዳሩን ትቶ ካንቺ ጋር ተቆራኝቶ አይኖርምና ይህን ተረድተሽ አንቺም ለራስሽ ትዳር ለራስሽ ኑሮ ማሰብ አለብሽ። ለመሆኑ ያን ሁሉ ብርታትሽን ያን ሁሉ ጉብዝናሽን ለመቸ ሊሆንሽ ነው የምትቆጥቢው? ይህስ ምንም አደልና ሌላ ክፉ ችግር ቢገጥምሽ እንኩዋ እንዲያ ያለውን ችግር ተቋቁሞ ለማሸነፍ አልነበረም ብርታትና ጉብዝና የሚያስፈልገው? እና - ይልቁንም ስለ ትዳር የነገርሁሽን አትርሺ እባክሽ በርቺ» አለ።

ስለ ህልም ውሸቱን ‹ከሚያውቁ ሰዎች የሰማሁት ነው› ብሎ የራሱን ግምት ከነገራት ስለ ልጅዋ ቅጥ ያጣ ፍቅር ከወቀሳት በሁዋላ ወዲያው እግረ - መንገዱን የትዳርን ጉዳይ ከጎን ጨረፍ አድርጎ ማንሳቱ በፊትዋ ላይ እንደ ምልክት የሚያሳዬው መስሎት ነበር። ነገር ግን ደመቀች በፊትዋ ምንም አይነት ምልክት ሳታሳይ፥ አንገትዋን እንደ ደፋች ዝም አለች። ለልጅዋ ስላላት ፍቅር የወቀሳትን ወቀሳ፥ ከዚያ በፊት ብዙ ጊዜ የሰማችው ስለሆነና በሻህ ልጅዋን እንደማይወድ ስለምታውቅ በንጹህ ህሊና በቅን ልብና እንደ ተሰጠ ምክር አድርጋ አልተቀበለችውም። ስለ ህልም የነገራት ግን እውነትም በህልምዋ ያዬችው ህሉ ከማለምዋ በፊት ስታስበው ስታሰላስለው የነበረ መሆኑ ትዝ አላትና ስለ ህልም የነበራት ጽኑ እምነት በውስጥዋ እንደ መነቃቃት እንደ

መናጋት ሲል ተሰማት! ከዚያ እስዋ ያ ሲያስፈራራት የኖረው ህልም እውነት ያልሆነ እንደሆነ ከልጅዋ ጋር እንደገና በደህና የመገናኘቱ ደብዛዛ የተስፋ ጮራ ብልጭ ድርግም እያለ እዬታያት እሱ ‹ስለ ትዳር ያነሳሁት በፊትዋ ላይ አንድ አይነት ምልክት አለ ማሳየቱ ነገሩ ባይገባት ይሆን ወይስ ባይጥማት?› ብሎ ምክንያቱን እዬፈለገ ሁለቱም ዝም ብለው ከቆዩ በሁዋላ፥

«መቸም - ካልተሻለሽ እንዲህ ሆነሽ ነገ ስራ ልትገቢ የምትችይ አይመስለኝም» አለ ያን ዝምታ አቁዋርጦ።

«ድካም ነው እንጂ የትኩሳቱ ስሜት እንኩዋ አሁን ጨርሶ ባይጠፋም ተሽሎኛል። ግን ትናንት አንተ እንደ ሄድህ የሺመቤት መጥታ ስለ ነበረ መታመሜን ላለቃችን እንድትነግርልኝ ለምኛታለሁ። ስለዚህ ነገ አርፌ እውል ይሆናል።»

«አዎ አርፈሽ ብትውይ ይሻላል። ለመሆኑ የሺመቤት ማናት? »

«እዚያው ሀኪም ቤት የምትሰራ ጉዋደናዬ ናት! »

«ነርስ ናት? »

«አዎ ነርስ ናት።»

«አሁን እናንተ - ስምንት ሆናችሁ ስትመረቁ አብራችሁ የተመረቀች ናት? ወይስ ከናንተ ቀደም ብላ የነበረች ናት? »

«ከኛ ጋር የተመረቀች ናት።»

«እንግዲህስ ነገ እዚህ ከዋልሽ፥ ከዚያ አልቃሻም ጋር መጥተን እናጫውትሻለን። አደራሽን፥ የነገርሁሽን አትርሺ። ነገ ስንመጣ በርትተሽ ደህና ሆነሽ እንድናገሽ እሺ? » አለ ለመሄድ ሲነሳ።

«እሺ እበረታለሁ» አለች፥ ከውብ ፈገግታ ጋር ከግንባርዋ አልፎ እስከ አይኖችዋ የተዘረገፈ ጠጉርዋን ወደ ላይ ገፍታ እጅዋን ለሰላምታ ስትዘረጋለት።

በሻህ፥ ያን የተዘረጋ እጅዋን በሁለት እጆቹ ጨብጦ፥ አይኖችዋን ትንሽ አየት አደረገና ሲፈር ሲቸር፥ ስምዋት፥ ዘወር ብሎ እንኩዋ ሳያይት ወጥቶ ሄደ። እጅዋን ስሞ ሲሄድ ልብዋ ተርተር ብሎ ደንጣ አፍዋን ከፍታ ቀረች! አይን ጊዜ ዘወር ብሎ ቢያይ ኖሮ በፊትዋ ላይ በቁጣ ፈንታ የደስታ ምልክት ባዬ ነበር! ነገር ግን ዘወር ብሎ አላዬም፤

ሰርቆ እንደሚሸሽ ልቡ እዬተሸበረ ሲወጣ ወይዘሮ ጌጤን እንደጅ አገኛቸው። «እንዴት ናት? እህል እንድትቀምስ - ለመንሃት? » አሉ ወይዘሮ ጌጤ።

«ተሽሎዋታል፥ ‹አባባ ሲመለሱ ምሳይነ አብሬ እባላለሁ› ብላለች» አለና ተሰናብቶዋቸው በቀጥታ ወዳዝማሪው ውቤ ቤት ሄደ

ደመቀች በሻህን እጅዋን ስምዋት ከወጣ በሁዋላ ያ፥ የጅዋን ጫፍ መሳሙ የትኩሳትና የጭንቀት መድህኒት እንደ ሆነ ሁሉ ትኩሳቱም ጭንቀቱም ባንድነት ጭራሽ ትተዋት ሄደው ሙሉ ጤንነት ብቻ ሳይሆን ብርታት ጭምር ስለ ተሰማት ተነስታ መውጣት አምሮዋት ነበር። ነገር ግን በሻህ ከመምጣቱ ትንሽ ቀደም ብለው ወይዘሮ፥ ጌጤ ቁርስ ይዘው መጥተው እንድትቀምስ ቢለምኑዋት፣ ‹ትኩሳት ስላለብኝ እንኩዋን እህል መብላት መነጋገር አልችም› ብላ ያባረረቻቸው መሆንዋ ትዝ ሲላት «ምን ይሉኛ? » ብላ ልትነሳ የቃጣችውን መልሳ ተወች። ከዚያ እዚያው በነበረበት እንዳለች በሻህ አብሮዋት ቆይቶ እስኪሄድ ድረስ የተናገረውንና ያደረገውን ከዚያም በፊት እሱን መውደድ ከጀመረችበት ጊዜ ጀምሮ በተገናኙ ቁጥር እስዋን አድርቶ አድርቶ፥ በውስጥዋ የፍትወት እሳት ቆስቁሶ አንድዶ መቃጠል ስትጀምር ትቶዋት የሚሮጠውን ለረዥም ጊዜ ለብዙ አመታት የማይሞት፥ ወይ የማይነድ እንዲሁም የሚሰቃይ ፍቅርዋን በልብዋ አስተኝታ ስታስታምም የምትኖር መሆንዋን ካጭር ጊዜ ወዲህ ወደስዋ ሲመጣ ስለ ሰውነቱና ስለ ልብሱ ከሚያደርገው ጥንቃቄ ሌላ በግልጽ አይናገር እንጂ ስለ ትዳር እያነሳ ዳር ዳር ማለቱ ከድሮ ሁኔታው ጋር ሲነጻጸር ትልቅ ለውጥ የሚያሳይ መሆኑን ይህን ሁሉ በትዝታ መልሳ አምጥታ ባይነ - ህሊናዋ ፊት በተራ አሰምጣ ከሱ ጋር ትጫወት ጀመር። በሻህ አብሮዋት ቆይቶ ከወጣ በሁዋላ ከሱና ከፍቅርዋ ታሪክ በቀር ሌላ አታይም፥ አትሰማም፥ ነበር! አሳብዋን በሙሉ ይዞት ውሎ ያደረው ልጅዋ እንኩዋ ለጊዜው ቦታውን ለብሻህ ትቶ ወጣ! ስለዚህ ያንጊዜ በሻህን እያዬችና የፍቅርዋን ታሪክ እያነበበች ተመስጣ ሌላ ማየትም መስማትም አትችል ስለ ነበረ አዛዥ በሩን ከፍተው ሲገቡ አላዬችም አልሰማችም ነበር!

«እንዴት አድረሽ ዋልሽ ልጄ? አሁንም አልተሻለሽ? » ሲሉ ብቻ ከንቅልፍዋ እንደ ቀሰቀስዋት ደንግጣ አይኖችዋን እያርገበገበችና ፊትዋን እዬጠራረገች፥

«እ? ተሽሎኛል አባባ፤ አሁን በጣም ተሽሎኛል! » አለች።

«ታዲያ ከተሻለሽ ለምን ‹ቁርስ አልበላም› አልሽ? ሰው ያል ህል ቆሞ መሄድ ይችላል? ትናንት ጦምሽን እንዳደርሽ ዛሬም ቁርስ አለመቅመስሽን ጌጤ ነገረችኝ።»

«ጥዋት እንዳመመኝ ነበርሁ፤ ከረፈደ በሁዋላ ነው የተሻለኝ፤ አሁን ከተሻለኝ በሁዋላ ግን ‹ቁርስ የበላሁ እንደሆነ ምሳየን ይከለክለኛል› ብዬ - ከናንተ ጋር እንድበላ ነው ቁርስ ያልበላሁ» አለች።

እውነትም እምሳ ላይ ሆድዋ ተቀብሎዋት እዬሳቀች እዬተጫወተች ደህና አድርጋ ስለ በላች አዛዥንና ወይዘሮ ጌጤን በጣም ደስ አላቸው። ማታ ጉዋደኛዋ የሽመቤት መጥታ ካልተሻላት በነጋው ሰኞ ወደ ሀኪም ቤት ሄዳ እንድትመረመረና መድሀኒት እንዲታዘዝላት ከተሻላት ግን ሳታርፍ ዘለግ ያለ ጊዜ በስራ ላይ ስለ ቆየች አስር ቀን ያክል አርፋ እንድትመለስ» የሀኪሙን መልእክት ነግራ ስታጫውታት አምሽታ ሄደች።

## ምእራፍ ሰላሳ ሁለት

# የተባረከ ሴራ

በሻህ ቀጨኔ አዝማሪው ውቤ ቤት ሲደርስ የምሳ ጊዜ ተቃርቦ ስለ ነበረ ያዝማሪው ምሽት ውባዬሁ ማድቤት ከሰራተኛዋ ጋር ምሳ ለማሰናዳት ደፋ - ቀና ትል ነበር። አዝማሪው ብቻውን ሲሆን የክራሩንና የገዛ ድምጹ እያጫወቱት እደጅ ተቀምጦ ነበር። መቸም ትልልቅ ሰዎችና ድርጅቶ ግብዣ አድርገው እንግዶቻቸውን እንዲያጫውትላቸው ተዋውለው ካልወሰዱት ወይም እወዳጆች ቤት ተለምኖም ይሁን ራሱ ፈልጎ ሲጫወት ካልሄደ ‹አዝማሬው ውቤ እንደ ተራ አዝማሪዎች ትንንሽ ገንዘብ ለመለቃቀም በዬቤቱና በዬመሸታ ቤቱ ይዞራል› አይባል! ስለዚህ የሚበዛውን ጊዜ፥ በተለይ በምሳና በራት ጊዜ ከቤቱ አይጠፋም። ምሽቱ ውባዬው እሱ ካላጎረሳት የበላች ሳይመስላት እስዋ ጭምር የምታውቀው አስገዳጅ ቀጠሮ ካልኖረ ባልና ምሽት ምሳና ራታቸውን አብረው መብላታቸውን በቅርብ ጎረቤቶቻችወ ብቻ ሳይሆን በሩቅ ወዳጆቻቸው ዘንድ ጭምር የታወቀላቸው ነበር። ውባዬሁ ባልዋ ለሌለ ምሳ ይሁን ራት በጠረጴዛ ላይ አቅርባ እስዋ ተቀምጣ በልታ አታውቅም። እንዲሁ ቁራሽ እንጀራና ውሀዋን ጠጥታ ‹ኤዲያ - ዲያ! ያለባል ለሚኖሩት መጥኔውን ይስጣቸው እቴ!› ትላለች። እሱ ሲኖር ግን መጀመሪያ ማእድ ሲቀርብ እንዲያው ለወጉ ከንጀራው ጥርፍት ከወጡ ጥንቁል አድርጋ ቅምስ ካደረገች በሁዋላ ወጥ እያወጣችና እንጀራ እዬቆረሰች እባልዋ ፊት ማድረግ እንግዳ ከኖረም እንግዳው ፊት ማድረግ ነው።

ከዚያም ባልዋ አንድ ጊዜ እስዋን እያጎረሰ አንድ ጊዜ ራሱ እዬጎረሱ በልተው ጠግበው ይነሳሉ። ‹ውባዬሁን ከባልዋ ጋር ለምግብ ተሰልፋ፥ ራስዋ እንጀራ ቆርሳ፥ ወጥ አድርጋ ስትበላ አዬሁ› የሚል አይገኝም።

‹ለምን በጅሽ አትበይ?› የተበላች እንደሆነ፥

‹የሱን እጅ ምን ቆርጦት? እኔ አገር ጎጃም «ባል ካላጎረሰ በሬ ካላረሰ ወዲያ ፈትቶ መልቀቅ ነው! » ይባላል› ትል ነበር።

ባገር ካለህ ‹ምንም ቢሆን በምሳ ጊዜ አላጣህ› ብዬ ነው አሁን የመጣሁ። ወዲያውም ምሳየን እዚህ እንድበላ ጭምር ነው» አለ በሻህ ገና አጥሩን ሲገባ፥ ስላምታ እንኩዋ ከመስጠቱ በፊት። ከዚያ አዝማሪው ውቤ ተነስቶ ሰላምታ ሰጥቶት ተያይዘው ወደ ቤት ገቡ።

ያዝማሪው ውቤ ቤት ከማድቤቱ ሌላ፥ አንድ የንግድና የመብል ቤት ባንድ ላይ አንድ ምኝታ ቤት አንድ መታጠቢያ ቤት ብቻ ያላት ካባቱ ከባላምባራስ አጎናፍር የወረሳት ትንሽ ቤት ነበረች። መታጠቢያ ቤቱን እንዲያውም ሁዋላ እሱ ያስቀጠለው ነበር። ያች ትንሽ ቤት እሱና ከሱ በሁዋላ ተከታትለው የተወለዱት ሁለት እህቶች የስበሳቸውንና የወላጆቻቸውን ፍቅር እንዲሁም ሌላውን ስጋዊና መንፈሳዊ ሀብት ሁሉ አንድ ላይ በማህበር እዬተካፈሉ፥ የልጅነትና የወጣትነት እድሜያቸውን ያሳለፉባት በውስጥና በዙሪያዋ ያለው እያንዳንዱ ጥቃቅን ነገር ሁሉ የዚያ ቤተሰብ የህይወት ታሪክ በዝርዝር እንደማይጠፋ ሆኖ ተቀርጾ የሚያይባት ያን ሁሉ የምታስታውሰው የዚህ ሁሉ የትዝታ ማህደር ስለ ነበረች ለምንም ትልቅ እንገር ሊለውጣት አይፈልግም ነበር።

«እሜቴ የት ትሄዳለች? » አለ በሻህ፥ ገብተህው እንደ ተቀመጡ።

«ማድ ቤት ናት ልጥራት? »

«ቆይ ግዴለም» አለ በሻህ፣ ሰአቱን አይቶ። «መጀመሪያ እስቲ ስለ መጣሁበት ጉዳይ ብቻችነን እንነጋገር። ደመቁን አሞዋታል። አሁን ከስዋ ዘንድ መምጣቴ ነው።»

«ምን አመማት? ጽኑ እመም ነው? » አለ አዝማሪው ፊቱ የስጋት ምልክት እያሳዬ።

«ዛሬ እንኩዋ ተሽሎዋታል የትናንትን ሁኔታዋ ግን - በጣም ያስፈራት ነበር። የልጅዋን ወደ ፈረንጅ አገር መሄድ በጋዜጣ ተጽፎ ከፎቶግራፉ ጋር ስታይ እንደ እብድ

ልብስዋን ጥላ ወደ ተፈሪ መኮንን ትምህርት ቤት በረረች። እኔም ድንገት በመንገድ የወደቀች እንደሆን ክፉ አደጋ እንዳይደርስባት ሰግቼ ተከትያት እዬሮጥሁ ትምህርት ቤት እንደ ደረስን በረኛው የልጅዋ መሄድ እውነት መሆኑን ሲያረጋግጥላት ጊዜ - ምን ልበልህ? ልክ ‹ሞተልሽ? እንዳላት ሁሉ እዬወደቀች እዬተነሳች አጎንብሳ መሬቱን እዬቡዋጠጠች ስታምጥ ስትጨነቅ ብታያት ኖሮ አልቅስህ ባልወጣልህ ነበር። ከዚያም እንደ ምንም አባብዬ ጸጥ እንድትል ካደረግሁዋት በሁዋላ ወደ ቤትዋ መልሻት እኔም ወደ ቤት ሄድሁ። ዛሬ ጥዋት ተመልሼ እስዋ ዘንድ ከመግባቴ በፊት እማማ ጌጤን አግኝቼ እንዴት እንዳደረች ብጠይቃቸው ‹ብርቱ ትኩሳት አለብኝ› ብላ ትናንት ማታም ዛሬ ጥዋትም እህል ውሀ አልቀመሰችም» አሉኝ። እኔ ገብቼ ሳነጋግራት ግን - በትናንቱ አንጻር በጣም ደህና የሆነች መሰለኝ፤ እንዲያውም አባባ አዛዥ ከስራቸው ሲመለሱ አብራቸው ምሳ እንደምትበላ አረጋገጠችልኝ። እየውልህ ታሪኩ ባጭሩ ይህ ነው። ታዲያ - አንድ ቀን አንተ የነገርኸኝ ትዝ አለኝና ትናንት ልክ እሱ የደረሰ መስሎ ታይቶኝ ሌሊቱን ሙሉ እንቅልፍ ባይኔ ሳይዞር እንዲሁ ተጨነቅሁ ነጋልኝ።»

«አንድ ቀን የነገርሁህ ምን ኖሮዋል? »

« ‹ከልጅዋ የሚለያያት ነገር ቢደርስ በሀዘን ብዛት አንድ ክፉ አደጋ ላይ እንዳትወድቅ - የምታሰጋ ናት› ያልሽኝ ትዝ ይልሃል? እየውልህ የትናንት ሁኔታዋ ያን አንተ ያልሽውን አስታውሶኝ ነው - እንቅልፍ አጥቼ ያደርሁ።»

«ታዲያኮ - እንዲያ እንዲያ ካለው አደጋ ላይ እንዳትወድቅ - የምታሰጋ ናት› ያልሽኝ ትዝ ይልሃል? እየውልህ የትናንት ሁኔታዋን ያን አንተ ያልሽውን አስታውሶኝ ነው - እንቅልፍ አጥቼ ያደርሁ።»

«ታዲያኮ - እንዲያ እንዲያ ካለው አደጋ መከላከያ የመሰለኝን ጭምር ነበር ያነለት የነገርሁህ።»

«ልክ ነው ነግረኸኛል፤ እኔም ተቀብያለሁ። ‹ለቆምህለት አላማ ለመስራት የሚመች ጊዜ እስኪያጋጥምና - ምቹ ሁኔታ እስኪፈጠር አንድ ሰው ሊሰጥ የሚችለውን ቅን አገልግሎት እዬሰጠህ፥ ደመቁንም ሊደርስባት ከሚችል አደጋ እዬጠበቅህ፣ ብትቆይ ይሻላል› ብለህ የሰጠኸኝን አሳብ በሙሉ ተቀብዬ፥ ስራ በማማረጥ ላይ መሆኔን መቸም ነግሬሀለሁ። ብቻ - የትናንት ሁኔታዋን ሳይ ‹ይሆነኛል› የምለውን ስራ አግኝቼ

እስክይዝና ስለ ጋብቻችንም - እስካነጋግራት ድረስ ጊዜ የማይሰጥ መስሎ ስለ ታዬኝ ነው የተቸገርሁ።»

«ስለ ጋብቻችሁ እስዋን ማነጋገሩም ጊዜ ይወስዳል? » አለ አዝማሪው እንደ መሳቅ ብሎ።

«እንዲውም እውነቱን ለመናገር ስለ ጋብቻችን እስዋን ማነጋገሩ ነው መውጫ የሌለው ገደል እምስሎ የታዬኝ።»

«እንዴት እባክህ? »

«ፈራሁዋት! »

«ቀልድህን ወዲያ እባክህ። ‹በሻህ› ብሎ ፈሪ አይቼም ሰምቼም አላውቅ! »

«አየው ዛሬ ነገርሁህ ቀልድ አደለም፤ በጣም ነው የፈራሁዋት! »

«እንዴትኮ? ከዛሬ ቀደም ከምታውቀው ሁሉ የበለጠ የሚያስፈራ የጦር መሳሪያ ይዛ ታዬችህ? »

«በጣም እንጂ! »

«እንዴት ያለ? »

« ‹እንቢ› ያለችኝ እንዲሁ ብዬ ፈራሁ! »

« ‹እንቢ› እንደማትልህ እኔ አውቃለሁ። ‹እንቢ› ብትልህ እኔ አላፊ እሆናለሁ! »

« ‹እኔ አላፊ እሆናለሁ› ብሎ ነገር አለ? አንተ አላፊ የምትሆን እንዴት ነው? እስዋ! ‹እምቢ› ብትል በስዋ ፈንታ አንተ ምሽት ልትሆነኝ አትችል! ለምኑ ነው አላፊ የምትሆን? » ሲል በሻህ በስጨት ብሎ፣ አዝማሪው ይስቅ ጀመር።

«እስዋ እንቢ ብትል ‹እኔ አላፊ እሆናለሁ› ማለት ‹በስዋ ፈንታ እኔ ምሽት እሆናለሁ› ማለት አደለም፤ የኔ መሀይም! እስዋ ‹እንቢ የማትል መሆንዋ እኔን ሴት ሆኘ ልታገባኝ እንደማትችል ሁሉ የተረጋገጠ ነው ማለት ነው» አለ አዝማሪው ቀጥሎ።

«አንተ እንደምትለው ቢሆንልኝ በማን እድሌ! ግን - ‹እንቢ አትልም› የምትል በግምት ነው እንጂ፥ ‹ቢጠይቀኝ እንቢ አልልም› ብላ አልነገረችህ! ስለዚህ ግምት እውነት ሊሆን እንደሚችል ስህተትም ሊሆን ስለሚችል አንተ እንደምትለው ሳይሆን ቢቀርና ‹እንቢ› ብትልስ? »

«አትል - ም አልሁህኮ! »

«አ - ህ! ‹ብትል - ስ?› አልሁህኮ! »

«አትልም እንጂ ካለችማ - ይቀራላ! ባልና ሚስት ሆናችሁ መኖራችሁ ይቀራል እንጂ መቸስ - እስከ ዛሬ ለዬብቻ እንደ ኖራችሁት መኖራችሁ አይቀር! »

«እየውልህ እሱን ነው የፈራሁት! እንድታገባኝ ለምኛት ‹እንቢ› ያለችኝ እንደሆነ በስዋም በኔም ከፉ ነገር ሊደርስ ይችላል። እስዋም እኔም እስከ ዛሬ ለዬብቻ እንደ ኖርነው መኖራችን እንኳዋ ሊቀር ይችል ይሆናል! እዬውልህ ይህን ነው የፈራሁት! ራሴን ነው የፈራሁት! » አለ በሻህ ያን የመሰለ መራራ ስሜት ሲገልጽ እንደሚያደርገው ግንባሩን ቁጥር አድርጎ።

«አንተኮ - እብድ አይሉህ ወይ ጭምት ምን እንደሚሉህ የምታስቸግር ሰው ነህ! » አለ አዝማሪው መጨረሻ አሳቡ ስለገባው እንደ መፍራት ብሎ።

«የፈለግኸውን በለኝ። ብቻ - ምንም ቢሆን፥ ‹አንዱን፥ ፊቱን ነብር የዋለበት አስመስላ ለቀቀችው! ሌላውን በበርበሬ ወጥ አጥምቃ እንደ ጋኔን ‹ለቀቅሁ! ለቀቅሁ!› እያሰኘች አስለፈለፈችው!› እዬተባሉ መሳቂያ ከሆኑት - ባለጌ ጎረምሶች ተራ ገብቼ ቡና እዬጠጡ ወሬ ለማፕኪ ለሚሰበሰቡ አሮጊቶች የቡና መጠጫ የቡና ቁርስ መሆን አልፈልግም! »

«በል ተወው ዝም በል፤ እንዲህ ያለው የሰይጣን ምክር ዳግመኛ ካፍህ እንዳይወጣ ሌላ ሰው እንዳይሰማው! »

«ለሱስ አትስጋ፤ ላንተም የተነፈስሁት ‹ምናልባት መውጫ መንገድ ታገኝ እንደሆነ› ብዬ ነው» አለ በሻህ ለትንሽ ጊዜ አዝማሪው ውቤ ምን ማድረግ እንደሚቻል ሲያስብ በሻህ ጉዋደኛው ምን ምክር እንደሚሰጠው ሲጠብቅ ሁለቱም አንገታቸውን ደፍተው ዝም ብለው ቆዩ።

«እስቲ - እንዲህ እናድርግ» አለ አዝማሪው ውቤ፥ አንገቱን ከደፋበት ቀና አድርጎ በሻህን እያዬ።

«ምናልባት - ተሽሎዋት፥ ከነገ ጀምራ ወደ ስራዋ የምትገባ የሆነች እንደሆነ መሰንበቻውን ማታ ማታ ከስራ ስትወጣ ውባዬሁን ጨምረን ወደ ስኒማ ቤት ትያትርም ይኖር እንደሁ ወደዚያና እንዲሁም ወደ ሌሎች የመዝናኛ ቦታዎች እዬያዝናት እንውጣ። እንዲሁ ብቻዋን ተቀምጣ የልጅዋን ነገር ማንሳት መጣሉና ማሰላሰሉ እስዋን ጎድቶ ለበሽታ የሚሰጣት ከመሆኑም በቀር ለልጅዋ አንዳች ጥቅም ጎድቶ ለበሽታ የሚሰጣት ከመሆኑም በቀር ለልጅዋ አንዳች ጥቅም የማይሰጠው መሆኑንና ባሳብና ባዘን ብዛት እክፉ በሽታ ላይ እንዳትወድቅ አዘንዋን፥ የሚያስረሳ ባይሆን እንኳዋ የሚያቃልል ዘዴ መፍጠር የሚያስፈልግ መሆኑን አስረድቼ አብራን እንድትወጣ እኔ ‹እሺ› አሰኛታለሁ። መቸም እንዲያ ባሉት ሴቶችና ወንዶች በብዛት እዬተጎራበቱ፥ እዬተቀራረቡ ተቀምጠው በሚገኙባቸው የመዝናኛ ቦታዎች፥ ሙዚቃው ጭዋታው እንዲያው አካባቢው ሁሉ ባንድነት ወንዶችና ሴቶች ባካል ከመጎራበታቸውና ከመቀራረባቸው የበለጠ፥ ነፍስ ለነፍስና ልብ ለልብ እንዲቀራረቡ እንዲተቃቀፉና እንዲዋሀዱ የሚገፋፉ መሆኑ የታወቀ ነው። ስለዚህ እስዋም እንደምትወድህ ስለማውቅ ልብዋ ያካባቢውን ቅኝት ተከትሎ እዬዘፈነ ዳንኪራ እዬመታ ካንተ ልብ ጋር ለመተቃቀፍና ለመዋሀድ ሲመጣ፥ እንደምታገኘው እርግጠኛ ነኝ። ታዲያ ያን ጊዜ፥ ያንተም ልብ የስዋን ተቀብሎ አጠፋውን ለመመለስ የተሰናዳ መሆን አለበት! ያንጊዜ አፎቻችሁ በአርምሞ ሲገናኙ መግለጫ ይለዋወጣሉ እንጂ ያንተ አፍ ‹ላግባሽ› የስዋ አፍ ‹እንቢ› ወይ ‹እሺ› ለማለት ጊዜ አይኖራቸውም። ነገሩ እንዲህ በአርምሞ ያልቃል! ከዚያ በሁዋላ ጥያቄው ‹መቸ እንጋባ?› ብቻ ይሆናል› ብቻ ይሆናል! እየውልህ እንግዲያ መጀመሪያ እንድንሞከረው የማቀርብልህ አሳብ ይህ ነው። ነገር ግን ይህን ሞከረን ያልተሳካ እንደሆነ አንተም እኔም የአልክናት ሳታስመስል ውባዬሁ ሴቶች እስበሳቸው በሚግባቡበት መገናኛቸው ተነጋግራ እንድትጨርስ አደርጋለሁ» ሲል አዝማሪው በሻህ አሳቡ ያኔውኑ እንደ ተፈጸመለት ሁሉ አፉን ከፈት አድርጎ ጥርሱ ብቻ ሳይሆን ፊቱ በሙሉ እዬሳቀ ሲሰማ ቆይቶ፥

«እየውልህ አልነገርሁህም? » አለ።

«ምን ብለህ? መቸ? »

«ቀኑን ረስቸዋለሁ፤ ግን አንድ ቀን ‹የትንኮሉ ሁሉ ቁልፍ መክፈቻው መፍቻው በደብተሮች እጅ ብቻ ነው የሚገኘው› ብዬሀለሁ! »

«እ - እሱ እንኩዋ እንዲያው ነው። ይህ - የረቀቀ ተንኮል መስሎ የታዬው ላንተ ብቻ ነው እንጂ ሰው ሁሉ የሚያውቀው ተራ ነገር ነው። አንተ ብቻ - ዛሬ እናንተ ‹ሰው ካውሬነት ወደ ሰውነት ቀስ እያለ የተለወጠ ነገር ነው› እንደምትሉት - ገና ካውሬነት ወደ ሰውነት ያልተለወጥህ ወይም አውሬ እንደ ሆንህ የቀረህ ስለ ሆንህ እንዳውሬዎች ሁሉ ከመስረቅ ከመቀማትና ከመግደል በቀር የሰው ስሜት ገና ያልተፈጠረብህ በመሆንህ የሰዎች ስሜት አይገባህም። ያውሬነት ስሜትህ በገፋህ ጊዜ የፈልኸውን ካላገኘህ፥ ተቆጥተህ በፊትህ ያገኘኸውን መግደል ትፈልጋል! እየው አሁን እንኩዋ የምትለው ለዚህ ጥሩ ማስረጃ አደለም! »

«ምኑ? » አለ በሻህ አዬሳቀ።

« ‹ደመቁን እንድታገባኝ ጠይቄያት ያልፈቀደች እንደሆነ እስዋም እኔም መኖራችን ይቀራል› ማለት ምን ማለት ነው? ‹እስዋንም ራሴንም እገድላለሁ› ማለት አደለም? እዬውልህ በሰዎች ዘንድ እንዲህ አይባልም፤ እንዲህም አይደረግ! »

«ታዲያ - ያስቆጣውን የሚገድል እንደሆን እንጂ ራሱን ጭምር የሚገድል አውሬ አይተህ ወይስ ሰምተህ ታውቃለህ? »

«ግስላ ነው? ምን የሚሉዋት እጅግ ቁጡ አውሬ፥ ከቁጣዋ ብዛት የተነሳ ምንም ያክል የሚያስፈራት ነገር በፊትዋ ብታይ አትመለስም፤ ‹ገድላ ትሞታለች!› ሲሉ ስምቻለሁ። ሌላው - እንደ ግስላ ‹ገድዬ ልሙት› የሚል አውሬ ይኸው አሁን አንተን ማየቴ ነው» ሲል አዝማሪው በሻህ ከልቡ ሳቀ። አዝማሪው ውቤም በገዛ ቀልዱ ከበሻህ ጋር ሲስቅ ቆይቶ፥

«በል እንግዲህ ለነገራችን እዚህ ላይ እልባት እናድርግለትና አሁን የምሳ ጊዜ ስላለፈ፥ ውባዬሁን ጠርቼ ምሳችነን ትስጠን» አለ ሰአቱን አይቶ ሲነሳ። ከዚያ፥

«አ - ገዳሜ ገዳሜ ገዳሜ፥ ገዳሜ፤

ብጠብቅ ከቀረሽ ሌሊቱ ሁሉ ቆሜ

እስቲ ገደም ለበል ትመጪ እንደሁ በልሜ»

እያለ በዜማ እያንጎራጎረ ወደ ማድ ቤት የሚያስወጣውን መንገድ ተከትሎ ሄዶ እበር ቆመና፥

«ውባዬሁ የኔ ውብ በሻህ ሰላም ይልሻል፤ ወዲያውም ‹እባክሽ ምሳየን አብይኝ› እያለ ይለምንሻል» አለ።

«ውይ! በሹን ነው ቅድም ሲመጣ በመስኮት ያዬሁት? እኔኮ ሌላ ሰው መስሎኝ! መጣሁ» አለች ውባዬሁ።

«በሻህ ነው የኔ ውብ እንዳይመስልሽ ሌላ፥

ለምኖ ‹እንቢ› ካሉት ቀምቶ እሚበላ።

«ከተወለድሁ እንኩዋ አያሌ ዘገዬሁ፤

«አሁን አንቺን ብቻ ውባዬሁ ውባዬሁ» እያለ በላሄያማ የሚዝገመገም ድምጹ ወደ በሻህ ተመለሰ።

«በሹ ለካስ፥ አንተ ኖረህል ቅድም ስትመታ፥ በመስኮት ያዬሁ! ሌላ ሰው መስሎኝ ነውኮ - እስኪሄድልኝ ስራየን ከጨረስሁ በሁዋላ እዚያው ዝም ብዬ የተቀመጥሁ! ኧረ! ኧረ! ኧረ! ለመሆኑ ልብስስ መቸም ገንዘብ ከተገኘ ከዚህ የሚያምር ይገዛል። መልክ የሚገዛበት ሱቅም ተከፈተ? ወይስ እንዴት ነው - እንዲህ ከግር እስከ ራስህ ውበት ብቻ የሆንህ? እስቲ እባክህን ና ሳመኝ» አለች ውባዬሁ ከማድ ቤት እዬተዥራገደች መጥታ። ውባዬሁ ዘለግ ያለ ውብ፥ ቅብጢ ወይዘሮ ናት። ውበትዋን ቅብጠትዋ የበለጠ ያሳምርላታል! ከበሻህ ጋር ተሳስመው ሁለቱም ከተቀመጡ በሁዋላ፥

«የራስ ጠጉሬን ትቼ የፊቴን ከመላጨቴ በቀር ምን አዲስ መልክ ገዝቼ የጨመርሁ መስዬ ታዬሁሽ? » አለ በሻህ።

«እኔ እንጃልህ! እንዲያው በጠቅላላው በጣም አምረህ ታዬኸኝ። ጥርሶችህና አይኖችህ ግን የድሮዎቹ ያምሩኛል? »

«ያሁኖቹ ሌሎች ናቸው? » አለ በሻህ እዬሳቀ።

«ሌሎች እንኩዋ አደሉም እኒያው ናቸው። ግን - ምን ልበልህ? ድሮ ፊትህ ሁሉ ዙሪያውን - ጠጉር ብቻ ውድማ ብቻ ሆኖ ከዚያ መሀከል እነሱ ፍልቅልቅ ሲሉ ያምሩኝ ነበር! ለመሆኑ አገባህ? ወይስ ልታገባ አስበህ ነው እንዲህ ማማር የጀመርህ? »

«ጋሼ ውቤ አልነገረሽም? አገባሁኮ! »

«ጎ - ሽ! አገባህ? በቃ እንግዲህ ሰው ልትሆን ነው! » ስትል ውባዬሁ አዝማሪውና በሻህ ትንሽ ቀደም ብለው ስለ ‹በሻህ አውሬነት› የተነጋገሩት ትዝ አላቸውና እስበሳቸው ተያይተው ይስቁ ጀመር፡

«በይ እንግዲህ የኔ ውብ ወሬ ምሳ አይሆንምና ምሳችነን አብይን» አለ አዝማሪው ከሳቁ በሁዋላ።

«እንግዲህ ደመቁን መቸ ታያት? ነገ ንደማትገባ ነግራኛለች፥ ምናልባት ከተሻላት ከማክሰኞች ጀምራ ይሆናል ወደ ስራዋ የምትሄድ» አለ በሻህ ውባዬሁ ምሳ ለማቅረብ ወደ ማድ ቤት እንደ ሄደች።

«ነገ እኔም ራጉኤል ቀጠሮ ስላለኝ እዚያ ነው የምውል። ማክሰኞ ስራ የምትገባ ከሆነች፥ ከዚያ ስትመለስ ወደ ማታ ሄጄ አያታለሁ።»

«እንግዲያስ ቀደም ብለህ ወደኔ ናና እዚያ ቆይተን አብረን እንሄዳለን።»

## ምእራፍ ሰላሳ ሶስት

# የልም እዣት

አዝማሪው ውቤ፥ እቤቱ ለበሻህ እንደ ነገረው ሰኞ ራጉኤል ቀጠሮ ስለ ነበረው፥ ወደዚያ ሄዶ ነበር። ነገር ግን የቀጠርወን ሰው ስላላገኘው እንዳሰበው ራጉኤል አልዋለም። ከዚያ ቶሎ ተመልሶ እቤቱ ምሳውን ከበላ በሁዋላ ወደ ከተማ ወጥቶ በስኒማ ቤቶች ስለሚታዩት ፊልሞች አገር ፍቅር ትያትር ስለሚታዬው ጭዋታና ካዲስ አበባ ውች ስላሉት የመዝናኛ ቦታዎች ሁኔታ ሲጠያዬቅ አመሸ። ማክሰኞ ካስር ሰአት በሁዋላ በቀጠሮ ወደ በሻህ ሲሄድ እሱም እሌላ ቦታ ቆይቶ ሲመለስ ከመገናኛ ሆቴል አጠገብ ተገናኙና ተያይዘው እበሻህ ክፍል ገቡ።

«ጠጅ ቤት ወስጄ ልጋብዝህ? ወይስ - እዚህ ሆቴል አንድ ነገር ልዘዝልህ? መቸም ዛሬ የኔ እንግዳ ነህ» አለ በሻህ ገብተው እንደ ተቀመጡ።

«እቤቴ ከምሳየ ጋር ጠላ ስለ ጠጣሁ አሁን መጠጣት እንኩዋን አልፈልግም ነበር። ነገር ግን ‹ልጋብዝህ› ካልኸኝ እስቲ - ኮኛክ እዘዝልኝ» አለ አዝማሪው። ከዚያ ለሁለቱም ኮኛክ መጥቶላቸው አንዳንድ ጊዜ እንደ ተጎነጩ፥

«ትናንት ራጉኤል እውላለሁ» ብለኸኝ ነበር፥ የሄድህለት ጉዳይ ቀንቶህ ተመለስህ? » አለ በሻህ።

«እንዲያውም እዚያ አልቆየሁ፤ የቀጠረኝን ሰው ስላጣሁት ቶሎ ተመለስሁ። እዩውልህ ትናንት - አምስተኛ ቀኑ መሆኑ ነው እየቀጠረኝ ሲጠፋ! ‹መሮጥ ቢያምርህ ለማዳ ዶሮህን ላውሬ ቆት ለውጥ› እንደሚሉት ተረት! ለማዳ ገንዘቤን ከኪሴ አውጥቼ አንድ ድሮ ጉዋደኛየ የነበረ ሰው ‹ተቸገርሁ› ብሎ በግሬ ወድቆ ስለ ለመነኝ አበድሬ አሁን እኔ ሲቸግረኝ ‹መልስልኝ› ብለው እዩቀጠረ ባዲስ አበባና በራጉኤል መሀከል ያመላልሰኛል።»

«ለመሆኑ - በግር ወድቆ ለሚለምን ሰው ገንዘብ ይሰጡታል እንጂ ያበድሩታል? በግር ወድቆ እስኪለምን ድረስ የተቸገረ ከሆነ ‹ከምን አምጥቶ ይሰጠኛል› ብለህ ኖሮዋል ያበደርኸው? ራሱ ከችግር ለመውጣት ባንተ እግር ወድቆ ‹መለመኑ አንሶት - ደግሞ አንተ ከችግር ለማውጣት በሌላ ሰው እግር ወድቆ እንዲለምን ነው የምትፈልገው? » አለ በሻህ እንደ መሳቅ ብሎ።

«ደግሞስ! እኔ በጄ የነበረኝን ብቻ መሰለህ? ውባዩሁ ለልብስ መግዣ ያስቀመጠችውን ለምኘ ጨምሬ ነውኮ የሰጠሁት! ደግነቱ ያን ይዞ ቶሎ መሄዱ ነው እንጂ ‹አይበቃኝም ተበደርልኝ› ቢለኝ ኖሮ በሹ ልሙትልህ ብድር ፍለጋ መሄዴ አይቀርም ነበር! » አለ አዝማሪው በገዛ የዋሀንቱ እዩሳቀ።

«ያንተስ ቢሻው ዱሮውንም ያንተ ገንዘብ ውባዩሁ እንደምትለው ‹በወንፊት እንዳስቀመጡት ጤፍ ባንድ በኩል ገብቶ በሌላ በኩል ፈስሶ የሚያልቅ› ነው። የሚያሳዝነው የስዋን ገንዘብ ጭምር ማስወሰድህ ነው። ለመሆኑ እስዋ ምን ትላለች? »

«እስዋስ ከምንም አልቆጠረችው። ‹ለሰው እንዳበደርኸው የነገርኸኝ እለት ነውና የጠፋ ገንዘብ መሆኑ የተረዳሁ፥ ከድካሙ ስለ ማይበልጥ ብትተወው ይሻላል? ነው የምትል። ብቻ - እዚህ አዲስ አበባ በተገናኘን ቁጥር በቀጠረኝ ቀን ሊገኝ ያልቻለበትን እዬማለ ከነገረኝ በሁዋላ ገንዘብ እቤቱ፥ ተቀምጦ የሚጠብቀኝ አስመስሎ እንደገና ሲቀጥረኝ እውነት እዬመሰለኝ ነበር የምመላለስ። ከንግዲህ ግን በቃኝ አልመላለስም። እውነትም ውባዬሁ እንዳለችው ከድካሙ ስለማይበልጥ ይቅርለት! » አለ አዝማሪው ኮኛኩን አንስቶ ጨልጦ።

«አንተም ገንዘብህን ላታገኝ ከንቱ መድከሙ ቀረልህ፥ በቃ! እንኩዋን ደስ ያለህ! » አለ በሻህ ኮኛክ በድጋሚ እንዲመጣላቸው ሊነግር ሲነሳ።

«በል እንግዲህ ይህን የኔን ጉድ ለሌላ ቀን መሳቂያ እንዲሆነን እናቆዬውና አሁን ዋና ጉዳያችነን እንነጋገር ወንድሜ» አለ አዝማሪው ሰአቱን አይቶ። «ትናንት ከራጉኤል ተመልሼ ምሳየን እቤት በልቼ ስለ መዝናኛ ቦታዎች ሳጠያይቅ ነው ያመሸሁ። ታዲያ፥ ‹አድዋ ሲኒማ ቤት ላንድ ሳምንት ሲታይ የሚቆይ ጥሩ ፊልም መኖሩን አረጋግጫለሁ። አገር ፍቅር ትያትርም ከተጀመረ አንድ ሳምንት የሆነውና ሶስት ሳምንት ያክል ሲታይ የሚቆይ ጭዋታ› አለ ብለውኛል። ብቻ ጭዋታውን ያዩት ሰዎች አላደነቁልኝም። ግን - ከሁሉም የሚሻል መስሎ የታዬኝ ደመቁ፥ መቸም ቅዳሜ ስለማትሰራ፥ እሁድን ጭምር ለማረፍ ብታስፈቅድ - ከዚህ ወደ አንቦ ወይም - ወደ ሌላ መዋኛ ያለበት የመዝናኛ ቦታ ውባዬሁን ጨምረን ሄደን ሁለት ቀን፥ ያክል አብረን ስንጫወትና ስንዝናና መቆዬቱን ነው። ሁለት ቀን እዚያ ሲዋኙ መቆዬቱ ዋናው፥ ቢቀር፥ ልብስን አውልቆ ጎን ለጎን ተኝቶ ጸሀይ እዬሞቁ ማውረቱ ይህ ሁሉ - ባካል ብቻ ሳይሆን በስሜት ጭምር ለማቀራረብና ብዙ ነገር ለማድረግ ምቹ አጋጣሚም የሚበቃ ጊዜም ይሰጣል። ከቤተ ክህነት መለያየቱ ሌላ ባይሆን እንዲህ እንዲህ ባሉ የመዝናኛ ቦታዎች እንደ ልብ እንጻነት ስለሚሰጥ ውባዬሁም እኔም ዋና ተምረን እስዋ ዋና በጣም ስለምትወድ ሴምቸን ብዙ ጊዜ አንቦ እዬሄድን ሁለትም ሶስትም ቀን ስንዋኝ ሰንብተን እንመለሳለን። እና - ይህ አሳብ ምንም ይመስልሃል? »

«ጥሩ አሳብ ነው። አሁን እንዳልኸው ለሁድ ጭምር ፈቃድ ካገኘችና ካዲስ አበባ ውጭ ለመሄድ ‹እሺ› ካለች ወዳንድ የመዝናኛ ቦታ ይዘናት እንሄዳለን። ነገር ግን እስከ ቅዳሜና እስከ እሁድ - ቀን ቀን እንኩዋ መቸም እስራዋ ትውላለች - ማታ ማታ ቤት

ዘግታ ልጅዋን እያሰበች ስታለቅስ እንዳትሰነብት ወደ ሲኒማ ቤቶች እዬያዝናት ስንወጣ ብንሰነብት ደህና ይመስለኛል።»

«እስማማለሁ እንሂድ እንግዲህ። የምትመለስበት ጊዜ እንኩዋ ገና ትንሽ ይቀረዋል፤ ግን እስዋና አባባ አዛዥ እስኪመለሱ ከማማ ጌጤ ጋር ስንጫወት እንቆያለን» አለ አዝማሪው። ሁለቱ አዛዥና ቤት ሲደርሱ ወይዘሮ ጌጤ እውጭ ተሰጥቶ የዋለ ልብስና አንዳንድ እቃ አሽከራቸው እዬሰበሰበች ስታነሳ እበረንዳቸው ቆመው ይመለከቱ ነበር።

«አባባ አዛዥ ገና አልተመለሱም? » አለ አዝማሪው ውቤ ሁለቱም ለወይዘሮ ጌጤ ሰላምታ ከሰጡ በሁዋላ።

«ምን እሳቸው - እዚያ ከስራ የቤት ጋር ሲጨቃጨቁ በጊዜያቸው አያዝዙበት! አንዳንድ ቀን ካሁን ቀደም ብለው ይመጣሉ? አንዳንድ ቀንም ያመሻሉ።»

«ደመቁም ገና አልተመለሰችም? »

«እስዋስ አለች እንዲያውም፥ ስራ አልገባች! »

«ለምን ስራ አልገባች? አሁንም እንደ ታመመች ነች? » አለ በሻህ።

«ትናንትም ዛሬም፥ ኧረ አንተ አይተሀት ከሄድ ወዲህ ሁሉ ደህና ናት! አኪሙ መታመሙዋን እሁድ ለት ሰምቶ ካልተሻላት አኪም ቤት ሄዳ እንድትታከም ከተሻላት፥ ግን እረፍት አግኝታ ስለማታውቅ አስር ቀን ያክል አርፋ ቆይታ ወደ ስራዋ እንድትመለስ ስለ ላከባት፥ ነው ስራ ያልገባች። ብቻ - እስዋ የማትድነው በሽታዋ ልጅዋ ነው! እኔም እግዜር ሳያድለኝ ቀርቶ በለጋው ተቀጠፈብኝ እንጂ የልጅ እናት ነበርሁ! ግን እንኩዋንስ ሩቅ አገር መሄድ ሲሞትም እንዲህ እንደስዋ ሰውን ሁሉ - ግራ አላገባሁ! የስዋ ሆድ - እንንጃ፥ ለብቻው ነው! »

«አሁን ተኝታ ይሆን? » አለ በሻህ።

«እምኝታ ቤትዋ እብታለች። ግን የተኛች አይመስለኝም፤ እሁድ እዚህ ነእብረች። እስቲ ግቡና አጫውቱዋት የሚያጫአውታት ዘመድ ያስፈልጋታል።»

«የዘመድ ጭዋታ የሚረዳ ከሆነማ፥ ከናንተ የተሻለ ዘመድ የት ታገኛለች? » አለ አዝማሪው ውቤ።

«የኛውማ - ሁልጊዜ ምክርና ተግሳጥ ሆነና፥ አልጥማት አለ፤ እጅ እጅ አላት! »

ደመቀች ወደ ራስዋ ካልሄደች እቤት ስትሆን፥ ያበሻ ቀሚስ ለብሳ ሳትደርብ፥ ባዶ አንዳንድ ጊዜም በነጠላ ጫማ መሄድ ትወድ ነበር። ያነለትም አዝማሪው ውቤና በሻህ መዝጊያ መትተው ከፍተው ሲገቡ እንደ ልማድዋ እጅጌ - የለሽ አንገትዬው እንደ ደረትዋ ክፍት የሆነ ያገርዋን፥ ቀሚስ ለብሳ፥ ያን አጠር አድርጋ ታጥቃ ኩታዋን ጠቅልላ አልጋዋ ላይ ካንድ ወገን ጥላ፥ ወንበር ተቀምጣ ጠረጴዛ ስላልነበራት ባልጋው አስደግፍፋ ትጽፍ ነእብር። እነሱን ስታይ የምትጽፈውን እንዳለ ትታ ቶሎ ተነስታ በደስታ፥ ፈገግ ብላ ለሁለቱም ሰላምታ ሰጠቻቸው። አጠር አድርጋ የታጠቀችው እጅጌ - የለሽ አንገተ - ሰፊ፥ ቀሚስዋ፣ ‹ከታች የባት የተረከዝዋን ከላይ ያንገት የደረትዋን ውበት ገልጠህ አሳይ!› ተብሎ እንደ ታዘዘ ሁሉ ገልጦ እያሳዬ ሳይበጠር የሰነበተ ዞማ ጠጉርዋ ማሰሪያው እንደ ተፍታ የጥቁር ሀር ነዶ ድብልቅልቅ ዝብርቅርቅ፥ ብሎ በራስዋም በፊትዋና በትከሻዎችዋ ዙሪያም ተረፍርፎ ከዚያ፥ መሀከል እንደ ንጋት ከዋክብት የሚያምሩ አይኖችዋ እንደ ጋመሩ እንኮዮች ንከሱን ጉረሱን፥ የሚሉ ጉንጮችዋና ከንፈሮችዋ ተካክለው እንደ ተሰኩ ነጫጭ ፈርጮች የሚፍለቀለቁ ጥርሶችዋ ያ ሁሉ ባገረሰብ ጌጣጌጥ ያልተበላሸ የተፈጥሮ ውበት ባንድነት በደመቀች ላይ ሲታይ ደመቀች እንዲህ ሆና ስትታይ፣ በውነት ‹የውበት አራያ› የሚሉዋት ነበረች! ሰላምታ ሰጥታቸው እንደ ቆሙ አዝማሪው ውቤ እጅዋን ይዞ ከግር እስከ ራስዋ መልሶ፥ ከራስዋ እስከ እግርዋ ሲያያት ቆይቶ፥

«እንዴ! ታዲያ እንዲህ አምሮባት እንዲህ ተሞሽራ እልፍኝዋ ውስጥ ቁጭ ብላ ‹መጥታችሁ ስገዱልኝ!› የምትለዋን ወይዘሮ ነው - ‹ታማለች ተጨንቃለች› እያልህ መአት የምታወራ? መታመም ማዘን እንዲህ ነው? » ብሎ በሻህን አየት አደረገና፥

«ምነ ሴቱ ሁሉ እንዲህ በታመመ፥ እንዲህ ባዘነ? »

«ደመቀች እንዳንቺ የሚያምድር ከሆነ! » ሲል በጥሩ ዜማ እጅዋን እንደ ያዘ እያንጎደጎደ፥

«ተው እባክህ አትቀልድብኝ ልቀቀኝ ጋሼ» አለች ደመቀች ፊትዋን በፍረት ይብሱን ቀልቶ። በሻህ ይስቅ ጀመር።

«እኔ ልሙት ቀልዴን አደለም፥ እውነቴን ነው፤ እንዲህ አድርጎ ማማርም የለ! እየውልህ በሹ» አለ አሁንም ወደ በሻህ እንድ ጊዜ ዘወር ብሎ። «እየውልህ እንዲህ

ያለችውን ውብ ልጅ እንዲህ ያለችውን - እንኩዋንስ አለማውያኑን መናንያኑ አከፋዮችን አስጎምዥታ የምታስገድፍ ያማረ፥ የጋመረች ፍሬ ነው

ባለቅኔው፣-

‹ያች የገነት ፍሬ አዳምን ያሳተች፥

እግዜር ከሰማይ አውርዳ ያስሞተች፥

ከዚያም እስከ ሲኦል፥ በፍቅር ሰንሰለት አስራ የጎተተች፥

ኸረ በየት መጥታ፥ እዚህ ተከሰተ?

ቀጥፌ በልቻት አምሮቴ፥ እስኪወጣ፥

ሞት ይፈረድብኝ የሚመጣው ይምጣ።

እንኩዋንስ በስጋየ፥ በነፍስም ልቀጣ›

ያላት» ብሎ ግጥሙን በማንበብ ሲጨርስ በሻህ ያን ግጥም አደነቀ። ደመቀች ፊትዋ በፍረት እንደ ጋመ፥ አይንዋን የምታሳርፍበት አጥታ ስትቸገር ቆዬችና፥

«ተው እባክህ እኔ እንዲህ ሲቀልዱብኝ አልችልም፤ አፍራለሁ። አሁን በቃ ልቀቀኝ አንድ ወንበር ልጨምርና ተቀምጠን እንጫወት» ብላ ዝማሪው እጅዋን ሲለቃት ወንበር ልታመጣ ወጣች። አዝማሪው ውቤ አልጋው አጠገብ እንደ ቆመ ሆነ ብሎ ሳይሆን ድንገት አይኖቹ ደመቀች በጻፈችው ላይ አረፉ። ከመስመሮቹ ቅጥ ግምጥ፥ መሆኑን ሲያይ ጎንበስ ብሎ ጥቂት መስመሮች ካነበበ በሁዋላ የተጻፈበትን ደብተር አንስቶ፥ ድምጹን ሳያሰማ ማንበብ ጀመረ።

«ኸረ ነውር ነው፥ ጋዜ ውቤ! ብልግና ነውኮ! ሰው የሚጽፈውን ሰርቀህ ታያለ? » አለ በሻህ።

«ተገልጾ የተቀመጠ ጽሁፍ የሚነበብ ነው፤ ምስጢር አደለም ዝም በል! » አለና አዝማሪው ማንበቡን ቀጠለ። ደመቀች እንግዶች ስለሚጋበዙት ነገር ከወይዘሮ ጌጤ ጋር ተነጋግራ ወንበሩን ይዛ ስትመለስ ንባቡን አጋምሶ ነበር።

«ምነው ምነው፥ ጋሼ ውቤ፥ እንዲያው - ነውር ነው! ስጠኝ እባክህ የኔኮ አደለም ሰው ‹ገልብጭልኝ› ብሎ የሰጠኝ ነው» አለች ደመቀች ወቀሳውንም ልመናውንና

ውሸቱንም አፍዋ እንዳመጣው ባንድ ላይ አደባልቃ እዬለፈለፈችና ደብተሩን ከጁ ለመንጠቅ እዬተንጠራራች። ግን አልሆነላትም። ባንድ እጁ ከስዋ እዬተከላከለ አንብቦ ከጨረሰ በሁዋላ ለስዋ በመመለስ ፈንታ ለበሻህ አሳልፎ ሰጠው።

«የልም እዣት» ከሚል ርእስ ግርጌ የሚከተሉት የናፍቆት ግጥሞት ተጽፈዋል።

«እይዝና ስራ ትምርቴን አብቅቼ፥

ትዳር እይዝና ጥሩ ምሽት አግብቼ፥

ከኔ ቤት አጠገብ ያንቺን ቤት ሰርቼ፥

ጌትነት ቢጠራኝ ወይም ደስታ ተድላ፥

አንቺን ትቼ ላልሄድ ይሁንብኝ ማላ።

‹ከስራ ብወጣ እንዴት እኖራለሁ?› ብለሽ እንዳትፈሪ፥

ቤት ሙሉ እንዲሆን እንዳትቸገሪ፥

አሽከሮች ቀጥሬ፥ ስራ እንዳትሰሪ፥

ጥሩ እመቤት ሆነሽ ደልቶሽ እንድትኖሪ፥

እንድትኖሪ ሞልቶሽ ምንም ሳትፈልጊ፥

ለዚህ ሁሉ ነገር፥ አይዞሽ አለሁልሽ፥ እመዬ እንዳትሰጊ»

ትለኝ አልነበረም ምሳ አብረን ስንበላ ‹ተከስተ ሾላ› ስር?

ይህ አሰት እንደሆን እስቲ እንጥራትና ያች ሾላ ትመስክር!

ያች ሾላ ትመስክር በል እንጥራትና!

መቸም አትዋሽ እስዋ ምንም ስለሌላት ከሰው ዘር ዝምድና፥

አየ ጉ -ድ! አብዬ እኔኮ ያ ሁሉ የምትነግረኝ ነገር።

በውን ተቀምጠን የምንጫወተው መስሎኝ እኖር ነበር!

ለካስ እልም ኖሮዋል ሲነቁ እማይገኝ ከንቱ ሆኖ እሚቀር!

ስትሰጠኝ የኖርኸው ያ ሁል ግሩም ተስፋ፥

የልም እዣት ሆነብኝ፥ ሲነቁ እሚጠፉ!

ግን ይቅር ግዴለም ግዴለም፥ ይሁና!

ቂም አልይዝብህም፤ እመኛለሁ እንጂ እንድትሆን ደህና።

የምወድህ ልጄ፥ ያካላቴ ክፍል አንጀቴ ነህና።

ስምህን እንዳልጠራው ይሰማል አጥማጄ፥

እንዲያው ልጄ ‹ሞረ -ሽ› እያልሁ ልጥራህ እንጂ!

ወላጆች ንገሩኝ ልምድ አላችሁና

እኔ ልጅ፥ ስለሆንሁ ብዙ አላውቅም ገና፥

የተወለደ ልጅ ደግሞ፥ ተመልሶ ይረገዛል ከቶ?

የኔው ያስምጠኛል በሆዴ ውስጥ ገብቶ!

ጎረቤቶች ሁሉ ቤተክሲያን ሊስሙ ሲሄዱ ባንድነት፥

እኔም እሁድ እሁድ በእለተ ሰነብት፥

ሄጄ እሳለማለሁ የነእብርህበትን ያነን ትምህርት ቤት!

የናት ልብ ሲታራ ድምጹን አሰምቶ፥

ምነው ‹አቤት› አይል የልጅ ልብ ተኝቶ?

እንደ መሳሳቱ እንደ መሰልሰሉ፥

የናት አንጀት መቁረጥ ምነ አለመቻሉ?

የተኛህበትን ማህጸኔን አቅፌ፥

‹እሽሩሩ› እላለሁ እስኪመጣ እንቅልፌ።

አደራህ እንቅልፌ እባክህ ቶሎና

ከልጄ እምገናኝ ልጄን እምስመው በህልሜ ነውና!

አለም እልም ቢሆን እወንነቱ ቀርቶ፥

ሌሊት ብቻ ቢሆን ቀን ጭራሹን ጠፍቶ

ከልጇ ላንድ አፍታ ባልተለዩሁ ከቶ! »

በሻህ አንብቦ ሲጨርስ እሱም አዝማሪው ውቤም አዝነው፥ አንገታቸውን ደፍተው ቆዩና፥

«እንዲህ ያለው ነገር ደህና እንዳይመስልሽ ደመቁ፤ በዚህ አሁን በያዝሽው ከቀጠልሽ - እጽኑ በሽታ ላይ ትወድቂና ራስሽን ብቻ ሳይሆን ልጅሽን ጭምር ትጎጃለሽ! » አለ አዝማሪው።

«የለምኮ ጋሼ፥ አሁን - በቀደም - ጋሼ በሻህ ከመከረኝ በሁዋላ ማዘኑን ትቻለሁ። ብቻ - እንዲያው - እንጃ አንዳንድ ጊዜ፥ ብቻየን ስሆን ይናፍቀኝና - አብረን ሳለን የምናደርገው የነበረው፥ እንጫወተው የነበረው ሁሉ እዬመጣብኝ - ነው» አለችና ወዲያው እንባ የሞሉ አይኖችዋን ትጠርግ ጀመር።

«ለምን ቤትሽን እዬዘጋሽ ብቻሽን ትቀመጫለሽ? ከሰዎች ጋር አትሆኝም? እንዲያውም አሁን ስንገባ እማማ ጌጤ እንደ ነገሩን ያስር ቀን እረፍት እንደተፈቀደልሽ በሻህና እኔ አንቺ ውባዬውሁን ጨምረን እዚህ አዲስ አባባ ወደ ስኒማ ቤቶች ካዲስ አበባ ውጭም ወንዳንድ የመዝናኛ ቦታዎች እዬሄድን ስንጭወት ብንሰነብት ብቻሽን ስትሂኚ የሚመጣብሽ የልጅሽን ናፍቆት አይመጣብሽም። በይ በዚህ እንስማማ። ዛሬ መቸም - ውባዬሁን እስክናመጣ ጊዜው ስለሚያልፍብን ከነገ ጀምረን እንዲህ እናድርግ። በይ እሺ» አለ አዝማሪው። ደመቀች ወደ አዲስ አበባ ሲኒማ ቤቶች ወይም ካዲስ አበባ ውጭ ወዳሉት የመዝናኛ ቦታዎች ሄዳ የምታውቅ በመሆንዋ ግብዣው እንግዳ ከመሆኑም ሌላ ድንገት ስለ ሆነባት ‹እሺም እንቢም› ለማለት ቸግሮዋት፥ ለጊዜው አንገትዋን ደፍታ ዝም አለች።

«በይኮ ያለዚያ እቀዬምሻለሁ! » አለ አዝማሪው። ጉዋደኛውን ተከትሎ።

«እ - ሺ» ስትል ደመቀች ከቅርታ፥ ፈገግታ ጋር፥ በሻህንና አዝማሪውን እያለዋወጠች እያዬች፥

«እንዴት ዋላችሁ? » አሉ አዛዥ በሩን ከፍተው ገቡና።

«እንኩዋን መጣችሁ እስቲ እባካችሁ - ይችን ልጅ አበረታቱዋት ሆደ - ባሻ ሆና አስቸግራናለች» አሉ ቀጥለው ሰላምታው ከተሰጣጡ በሁዋላ። ከዚያ ሁሉንም ወደ

እንግዳ ቤት ይዘዋቸው ሄደው ጠጅ ቀርቦ እዬጠጡ በሻህና አዝማሪው እንደ ልማዳቸው እይስበሳቸውን ነውር እዬተዘካዘኩ ዱላ - ቀረሽ የውሸት ጥል ሲጣሉ ሌሎች ደመቀች ጭምር - እነሱን እያዩና እዬለሙ በሳቅ ሲያወኩ አመሹ።

## ምእራፍ ሰላሳ አራት

# እድሜ ላምቦ ጠበል

ደመቀችን ወደ ሲኒማ ቤቶችና ወደ ሌሎች የመዝናኛ ቦታዎች ለመውሰድ በተስማሙ ማግስት ካስራ ሁለት ሰአት ቀደም ብለው በሻህና አዝማሪው ውቤ፥ ከባልተቤቱ ጋር እናዛዥ ተካልኝ ቤት ደረሱ። አዛዥ ከስራቸው ገና ስላልተመለሱ እቤት ያገኙዋቸው ወይዘሮ ጌጠንና ደመቀችን ብቻ ነበር።

«የምትጠጡት ምን እናምጣላችሁ? » አሉ ወይዘሮ ጌጤ ሁሉም ሰላምታ ተሰጣጥተው ከተቀመጡ በሁዋላ።

«ወደ ሲኒማ ቤት ለመሄድ ነው ውባዬሁን ጭምር ይዘናት የመጣን። ስለዚህ - ሌላ መጠጥ ጠጥተን የሄድን እንደሆነ እዚያ እንቅልፍ እንዳይዘን ቡና ብንጠጣ የሚሻል ይ - መስለኛል» ብሎ አዝማሪው ባሳቡ የሚስማሙ መሆናቸውን ለማረጋገጥ በጥያቄ አይን በሻህንና ውባዬሁን እያለዋወጠ ሲያይ፥ ሁለቱም መስማማታቸውን በዬራሳቸው ምልክት አሳዩ።

ውባዬሁ፥ አንዳንድ ጊዜ ድግስ ሆኖ ባንድነት ስትጠራ ካልሆነ፥ የናዛዥ ተካልኝን ቤት እንደ ባልዋ የምታዘወትር አልነበረችም። ስለዚህ ከወይዘሮ ጌጤም ከደመቀችም ጋር የባልዋን ያክል ስላልተላመደችና የቅርብ ወዳጅነት ስለልነበራት ከመዝናናትና ከቅብጠት ተቆጥባ እንደ እንግዶች ወይዛዝር ሁሉ ኮራ ረጋ ብላ ነበር ለሁለቱም ሰላምታ የሰጠቻቸው። ምንጊዜም ቢሆን የውባዬሁ ቅብጠት ከቤትዋ ወጥቶ አያውቅ! ከቤት ውጭ ይልቁንም በጣም ባልለመደቻቸው ሰዎች ፊት የረጋች የኮራች ወይዘሮ ናት! እቤትዋ ከባልዋ ከለመደቻቸው ሰዎች ጋር ስትሆን ግን አካሄድዋ አነጋገርዋ አሳሳቅዋ፥ እንዲያው ሁለመናዋ ቅብጠት ብቻ ነው። ታዲያ በጣም ያምርባታል!

ውባዬሁ ጌጥ ማብዛት አትወድም። ‹ለምን?› ሲሉዋት ‹እኔ ውቢት እኔ ራሴ የምታይ ነኝ እንጂ የጌጥ ማሳያ የጌጥ መደርደሪያ ነኝ እንዴ! የጌጥ መደርደሪያ አራዳ ሱቅ ይሂድ እዚያ ሞልቶለታል!› ትላለች። ያነለትም፥ ትናንሽ የወርቅ ጉትቻዎች በጆሮችዋ ከማድረግዋ በቀር የጅ አንባር ይሁን ያንገት ድሪያ እምስቀል፥ ወይም ሌላ ብልጭልጭ ጌጣጌጥ በላይዋ አይታይም ነበር። ባትምላሽ ጥልፍ ቀሚስና ጥበብ ኩታ ለብሳ፥ ከዚያ ላይ ቀላል ግራጫ ካባ ደርባ፥ ቀለሙ ከገላዋ ጋር ተመሳሳይ የሆነ ሀር የግር ሹራብና ባላጭር ተረከዝ ጥቁር ጫማ ከማድረግዋ በቀር ሌላ ጌጣ ጌጥ አልነበራትም፤ በውበትዋ ብቻ ነበር ያጌጠች። ‹ለምነው ባላጭር ተረከዝ ጫማ የምታደርጊ?› የተባለች እንደሆነ ‹ወንድ እንዳልመስል ነዋ! ረዥም ሆኘ በመፈጠሬ ሲቆጨኝ ደሞ በዚያ ላይ ረዥም ተረከዝ ያለው ጫማ ከስር የቀጠልሁበት እንደሆነማ - ከሴቶች ተራ ወጥቼ ቀውላላ ወንድ እመስል የለም እንዴ! እኔ ሴትነቴን በጣም ስለምወደው ወንድ መምሰል አልፈልግም!› ትል ነበር።

ቡና መጥቶላቸው ከጠጡ በሁዋላ፥ ደመቀች ወደ መኝታ ቤትዋ ሄዳ ልብስዋን ለውጣ እንደ ወባዬሁ ወርቅ ጉትቻዋና ካባ እንኩዋ ስላልነበሩዋት ቀሚስዋን አጠር አድርጋ ታጥቃ፥ በዚያ ላይ ጥበብ ኩታዋን ደርባ ባይኖችዋ የልቅሶ ምልክት እንዳይታይባቸው አባብሳ፥ ጠጉርዋን ከተመሰቃቀለበት በቅጥ በቅጥ አድርጋ፥ እንደ ውባዬሁ ባላጭር ተረከዝ ጫማ አድርጋ ተመለሰች። ታዲያ የማይደረግ ሆነና ነው እንጂ ለማስጌጡስ ለማሳመሩስ ቢሆን ጠጉርዋን በማስተካከል ፈንታ እንዲሁ እንደ ተመሰቃቀለ ትታ አሳጥራ በታጠቀችው ቀሚስ ላይ ጥበብ ኩታ መደረቡን ትታ፥ መውጣቱ የበለጠ ባሳመሩዋት የበለጠ ባስጌጡዋት ነበር! ነገር ግን እንዲያ ሆነው የማይወጡ ወይዛዝር በተመልካች ዘንድ ከብዶች እንጂ ከውቦች ስለማይቆጠሩ የበለጠ የሚያሳምሩዋትን ትታ የማያሳምሩዋትን አድርጋ ለመውጣት ተሰንድታ መጣች።

በሻህና አዝማሪው ውቤ ከሁለቱ ሴቶች ጋር አድዋ ሲኒማ ቤት መጀመሪያ ከደረሱ መሀከል ስለ ነበሩት የመግቢያ ትኬት ለመግዛት ሰልፍ ቦታ ለመያዝ የመጋፋት ችግር አልገጠማቸውም። አዝማሪው ለኊልቱም ቲኬት ሊገዛ ገንዘብ ሲያወጣ፥

«ነጻ መግቢያ ቲኪቶች እኒሁ» አለ በሻህ ቀደም ብሎ የገዛቸውን አራት ያንደኛ ማእረግ ቲኪቶች ከኪሱ አውጥቶ።

«ቀምተህ ነው? ወይስ ሰርቀህ? » አለ አዝማሪው መለስ ብሎ ቲኬቶችን ሲያ ትንሽ እንደ መሳቅ አለና።

«መቸም ካልተገዙ፥ አሁን ካልሀቸው አንዱ የተገኙ መሆን አለባቸው» አለ በሻህ አዝማሪው ውቤን ብቻውን ሲሆኑ ወይም በሌሎች ሰዎች ፊት የሚሰድበውን ያክል በምሽቱ በውባዬሁ ፊት አይሰድበውም። ስለዚህ ያነለትም ውባዬሁ በመኖርዋ አጠፋውን አልመለሰለትም።

አዳራሹ ውስጥ ገብቶ ሁለቱ ሴቶች እመሀል አዝማሪው በምሽቱ ጎን በሻህ በደመቀች ጎን እንደ ተቀመጡ፥ ተመልካቹ በድርብ መስመር እዬተጥመለመለ ገብቶ ቤቱን እስኪጨንቀው ሞላው። በልማዱ ቅዳሜና እሁድ ማታ ወይም በበአል ካልሆነ ባዘቦት ስኒማ ማየት የሚፈልጉ ብዙ ስላልነበሩ ከስኒማ ቤቶች ወንበሮች የሚበዙት ባዶዋቸውን ነበር የሚያመሹ። ሰሞኑን ግን፣ አድዋ ሲኒማ ቤት የሚታየው ፊልም ጥሩ መሆኑ ተስፋፍቶ ስለ ተወራ፥ እዚያ ማታ ማታ ሁልጊዜ ቦታ ይጠብ ነበር።

ፊልሙ የሁለት አሜሪካን ወጣቶች የተጨነቀ ፍቅር የሚያሳይ ነበር። ሴትዋ ያንድ ትልቅ ኩባንያ ባለቤት ልጅ ናት። ወንዱ እዚያ ሀብታም ሰው ቤት ባሽከርነት ተቀጥሮ የሚሰራ፥ መልከ መልካም ጥቁር ነው። ከመልኩ ማማር ሌላ ግሩም የሆነ ድምጽ ስለ ነበረው በትርፍ ጊዜው ዘፋኝ ለመሆን ይሰናዳ ነበር። እዚያ እንዳለ ከጌታው ልጅ ጋር በጽኑ ፍቅር ይጠመዳሉ። ወዲያው የልጅቱ ወላጆች ያውቁና አሽከራቸውን ከቤታቸው አባርረው እስዋን በራስዋና በቤተ ሰብዋ ብቻ ሳይሆን በጠቅላላው በነጭ ዘር ላይ ውርደት ለማምጣት የተነሳች በመሆንዋ ወቅሰው ዘልፈው ዳግመኛ ያን ጥቁር ፍቅረኛዋን እንዳታይ በጥብቅ ከመከልከላቸው በላይ በሁለቱም ላይ ጠባቂዎችና ሰላዮች ያደርጉባችዋል። ታዲያ መቸም የተጨነቀ ፍቅር መላ አያጣ! ያ የተጨነቀ ፍቅራቸው በሚያሳያቸው መላ ከተከበቡበት የጠባቂና የሰላይ አጥር እዬወጡ በተገናኙ ቁጥር ከደስታቸው ብዛት የተነሳ እዬሮጡ እስዋ በሱ እሱ በስዋ ላይ ወድቀው ሲሳሳሙ፥ ሲላላሱ ሲጉዋረሱ፥ የሆኑት ሲያጡ ተመልካቹን ሁሉ በውድም በግድም የደስታቸው ተካፋይ ያደርጉታል!

እኒያ ልጆች በፍቅራቸው፥ ሰክረው፥ የሚያደርጉትን ሲያዩ በዬልባቸው የተኛ ፍቅራቸው ተቀስቅሶ የሚሳሳሙና እዬተቃቀፉ የሚተሻሹ ተመልካቾች አልፎ አልፎ ይታዩ ጀመር። እኒያ ልጆች በፍቅራቸው ሰክረው የሚያደርጉትና የሚሆኑት ሁኔታ እንኩዋንስ የተኛ ፍቅር ለመቀስቀስ ያልነበረ አዲስ ይፈጥር ነበር!

ፊልሙ ሲታይ ይቆይና በዬምእራፉ፥ ላጫጭር ጊዜ መብራት በርቶ ቆይቶ እንደገና በቀጠለ ቁጥር የሚሳሳሙትም እዬተቃቀፉ የሚተሻሹትም ተመልካቾች ቁርጥ እዬጨመረ ሄደ። የፊልሙ ተጫዋቾች የሚያቀናቅኑትን ከተመልካቾች መሀከል

መጀመሪያ ተቀባዮች የሆኑ ፈረንጆች ብቻ ነበሩ። እዬቆዩ ግን አንዳድ ኢትዮጵያውያን ወጣቶችም ጎረቤቶቻቸው የሚያደርጉትን ያደርጉ ጀመር። ከዚያ እዚያ አዳራሽ ውስጥ በገባው የመሳሳምና የመተቃቀፍ ወረርሽኝ እንደ ተለከፈ ሁሉ አዝማሪው ውቤም ራሱን በውባዬሁ ትከሻ ላይ ጣል አድርጎ፥ እጁን ባንገትዋ በከፍነሮቹ ሲደባብስ ቆዬና ተጠንራርቶ አፍዋን ሊስም ወደሱ ሳባት።

«ኧረ! ኧረ ተው ስለ እግዜር ሰው ጉድ ይላል! እዚህ - ባደባባይ ውስጥ ነው እንዴ! » አለች ውባዬውሁ በጅዋ እዬተከላከለች።

«ጉድ የሚባል ሰው ሁሉ የሚያደርገውን የማያደርግ ነው! » አለ አዝማሪው።

«ከኒያ - ከፈረንጆችና ካንዳንድ - እፍረት - የለሽ ልጆች በቀር - ማን ደህና ሰው እንዲህ ሲያደርግ አዬህ? ተው እባክህ እቤት - ትደርስበታለህ» አለች ውቤቱ መከላከልዋን ሳትተው።

«እቤት አላደርስ ሲልሳ! » አለና እንደ ምንም ብሎ አንድ ጊዜ አፍዋን ሲስማት ድል ሆነች! ወዲያው ትከላከልበት በነበረው እጅዋ እንዳያመልጣት አንገቱን ጥምጥም አድርጋ ይዛ አጠፋውን ትመልስ ጀመር!

አዝማሪውና ውቢቱ ሲሳሳሙ ደመቀችን ስለ ተጫኑዋት፥ ለነሱ ቦታ ለማስፋት እዬፈራች ወደ በሻህ ጠጋ ስትል የሱ የሰውነት ሙቀት ለስዋ የስዋ ለሱ ልብሳቸውን ዘልቆ ተሰማቸው። ያንጊዜ የሁለቱም ልቦች በዬደረታቸው ውስጥ በሀይል ሲመቱ ከነሱ አልፎ ለጎረቤታቸው የሚሰማ ይመስል! ከዚያ በሻህ ‹ልበል ልተው?› እያለ እያመነታ ቀስ አድርጎ እጁን ከሁዋላዋ በኩል አንገትዋ ላይ ጫን አደረገ። ምንም አላለች፤ ዝም አለች! ብቻ የወባ መነሾ እንዳለበት ሁሉ ሰውነትዋ በሙሉ ይንቀጠቀጥ ነበር! ‹ተመስገን!› አለና እጁን ባንገትዋ ላይ እንደ ጫነ ፊልሙ ከሚታይበት መድረክ በሚመጣው ድንግዝግዝ ብርሃን አይን ላይን ተያዩ። ከዚያ ቀስ ብሎ አፉን ወዳፍዋ ሲያደርግ ነገር ግን አፍዋን ሳይነካ ገና በምገድ ሳለ መብራቱ በራ!

«እጭ ምናባቱ! » አለች ደመቀች በስጨት ብላ።

«ማነን ነው? » አለ በሻህ እሱን ያለችው መስሎት በጥፊ እንደ ተመታ ድንግጥ አለና። ወዲያውኑ አልመለሰችም። ትንሽ ቆየት ብላ፥

«እ? እ - መብራቱን ነው ‹ብልጭ ድርግም› ሲል - አይን ያሳምማል» አለች።

ያ መብራት የፊልሙ መጨረሻ ስለ ነበረ ሰው ሁሉ ተነስቶ እዬተንጫጫ ለመውጣት ሲተራመስ አዝማሪው ውቤና ጉዋደኞቹም አብረው እዬተጋፉ ወጡ።

«ወደ ቤታችን ከመሄዳችን በፊት አንድ ቡና ቤት ገብተን አንዳንድ ቀዝቃዛ ነገር እንድንጠጣ ጋብዣችሁዋለሁ» አለ አዝማሪው። ከዚያ እዚያው ከስኒማ ቤቱ አጠገብ ባለ ቡና ቤት ቤት ገብተው ለሱና ለበሻህ ቀዝቃዛ ቢራ፥ ለውባዬሁና ለደመቀች ቀዝቃዛ ሎሚ ናት ቀርቦላቸው ሲጠጡ፥

«እንግዲህ» አለ አዝማሪው ቢራውን አንድ ጊዜ ተጎንጭቶ አጣጣመና። «እንግዲህ የደመቁ ረዥም የረፍት ጊዜ በከንቱ እንዳያልፍ ነገ አምቦ ሄደን እስከ እሁድ ድረስ ስንዋኝ ሰንብተን ሰኞ እንመለስ እኔ ውብ፥ ‹ዋና ካልወሰድኸኝ› እያለች መጨቅጨቅ ከጀመረች ዘመናት አልፈው ዘመናት ተተክትዋል» አለ ከቀልዱ ጨመር አድርጎ።

«ሀ! ‹በልጅ አመካኝቶ ይበሉዋል አንጉቶ› እንደሚሉት ራስህ አንድ ነገር ስትፈልግ በኔ ማመካኘት ትወዳለህ! ‹ዋና መሄድ ፈልጌያለሁ› አትልም? ምን አሳፈረህ! » አለች ውባዬሁ ባልዋን የጎድን እያዩች።

«ፈቃድ ፈጻሚሽ ታዛዥሽ መሆኔን በምስክሮች ፊት ለማረጋገጥ ነዋ የኔ ውብ! » አለ አዝማሪው ጉንጭዋን እዬዳበሰ።

«አይ ወዲያ! ድንቄም ታዛዥ እቴ! ስትል ውቤቱ እጁን ከጉንጭዋ ላይ እዬገፈተረች ደመቀችና በሻህ የባልና ምሽቱን ወዘበሬታ አይተው ይስቁ ጀመር።

«ብቻ - ‹ዋና እንሂድ› ስላኸው እኔ ዋና አላቅምኮ፥ ጋሼ» አለች ደመቀች።

«ትማሪያለሻ! ሁላችንም ተምረን ነው እንጂ አውቀን አልትወለድንምኮ! የኔ ውብ በሁለት ቀን ትምርት ነው ጥሩ ዋናተኛ ያደረግሁዋት፤ አንቺንም ቅዳሜና እሁድ አስተምሬ አባይን በዋና መቁረጥ የምትችይ፣ ጥሩ ዋናተኛ ባላደርግሽ ‹ምን ብለኸኝ ነበር?› ትያለሽ» አለ አዝማሪው እንደ ልማዱ ንግግሩን የቀልድ ቀለም እዬቀባባ።

«አሳቡስ - መልካም ነበር። ብቻ - የዋና ልብስና - አንዳንድ የሚያስፈልግ ነገር አስቀድመውን ስላላሰናዳን ለሌላ ጊዜ ብናደርገው ይሻል እንደሆነ እንጂ» አለ በሻህ እያመነታ። ደመቀች መብራቱ ሲጠፋ ‹እጭ! ምናባቱ› ባለችው ስሜቱ እንደ ታወከ

ስለ ነበረ ያንጊዜ ቀደም በለው ካዝማሪው ጋር እንደ ተመካከሩ ደመቀችን ይዞ ወደ ሲኒማ ቤቶች ይሁን፥ ወደ ሌሎች የመዝናኛ ቦታዎች የመሄዱ ነገር አልጣመውም ነበር።

«የዋና ልብስ ችግር የለም። በግዢም ሆነ በኪራይ፥ እንደምንፈገው እዚያ እናገኛለን። ስለዚህ እንሄዳለን፤ አንቀርም። መሄዳችን የማይቀር ከሆነም ነገር ከምሳ በሁዋላ መዋኘት እንድንችል ያንድ ሰአቱን ኦቶብስ መያዝ ይኖርብናል። ስለዚህ የኔ ውብና እኔ መርካቶ ኦቶብስ መቆሚያ በቀጥታ እንሄዳለን፤ አንተና ደመቁ እዚያ ቅዩን፤ የቀደምናችሁ እንደሆነም ድረሱብን» አለ አዝማሪው፤ እንደ ወታደር አለቃ የማያጠያይቅ ትእዛዙን ሲስጥ በሻህንና ደመቀችን እያለዋወጠ እያዬ። በሻህ አምቦ የመሄዱ አሳብ ደስ ባይለውም አለመደሰቱን መግለጽ አልፈለገም። ከዚያ ሁሉም ባንድነት ሆነው ደመቀችን እቤትዋ ካደረሱ በሁዋላ ወደዬቤታቸው ሄዱ።

ያን ሌሊት ደመቀችና በሻህ፥ ስኒማ ቤት እነሱም ሌሎችም ሲያደርጉት ያመሹትን በዬበኩላቸው ባሳባቸው ጠርተው አምጥተው ሲያዩ እሱን እያነሱ እዬጣሉ እያገላበጡ ሲመረምሩ እንቅልፍ ሳይመጣባቸው ብዙ ቆዩ።

ደመቀች ለነውባዬውሁ ቦታ ለመስጠት በሻህን ስትጠጋው የሰውነቱ ሙቀት የሱንም የስዋንም ልብስ ዘልቆ የኤሌክትሪክ ሽቦ እንደ ያዘች ሁሉ በሰራ አካላትዋ የሚያንቀጠቅጥ ነገር ያሰራጨባት ታሰባትና እንዲያ ያለ ነገር ደርሶባት ስለማያውቅ እንዲያ ያለ ስሜት ተሰምቶዋት ስለማያውቅ ምክንያቱን ፈልጋ ማግኘት አቃታት። ‹የሚሞቅ የሰው ገላ መንካት እንዲያ ያንቀጠቅጣል? ብርቱ ትኩሳት ያላቸው በሽተኞች እጅ ስይዝ መች እንዲያ ተንቀጥቅጬ አውቃለሁ? እንግዲያ ፈርቼ ነው? ምን አስፈራኝ? አብሬው የኖርሁት አደል? እንጃ ዛሬ ምን እንደ ነካኝ አላውቅም እንጂ አንድ ነገር ሆኘ ኖሮዋል!› አለች። ከዚያ እጁን፥ አንገትዋ ላይ እንዳደረገ አይን አይንዋን አያዬ ቀስ ብሎ ወደስዋ ቀረብ ሲል ስታየው ሰውነትዋ አንድ አድርጎ የያዘው ሀይል እንደ ተለያት ሁሉ የሰራ አካላትዋን ጠቅላላ ድካም ጠቅላላ ዝለት ተሰምቶት የነበረው ታሰባት! ያን ጊዜ ከሱ ለመሸሽ አቅምም ፈቃድም፥ እንዳልነበራት፥ እንዲያውም ከሱ በመሸሽ ፈንታ አንድ የማታውቀው ስውር ሀይል ወደሱ ይገፋት እንደ ነበረ አንገቱን እቅፍ አድርጋ አፍዋን ፍለጋ በመንገድ ላይ የነበረውን አፉን እንድትሰምው አምሮት ለቆባት እንደ ነበረ ታሰባት? ‹እንዲህ ያለው ነገር ምንድነው? ፍቅር እንዲህ ያደርጋል? እም - ! እንጃ› አለች ለጥያቄዋ ሁሉ መስል ለመስጠት የሚችል በፍቅር የተነካ ሰው ባጠገብዋ ስላልነበረ።

የደመቀችና የበሻህ ፍቅር በቃል ወይ በግብር ተገላጸውት ባያውቁም ረዥም ጊዜ አብሮዋቸው የኖረ ነው። አዝማሪው ውቤ አዛዥ ተካልኝ ቤት የበሻህን የሚወደዱና የሚደነቁ ባህሪዎችም ስራዎምች በተለይ የጀግናነቱን ታሪክ በረጅም ሲተርክ ከሰማችበት ቀን ጀምራ ደመቀች ከሌሎች ወንዶች ስትሸሽ የኖረችውን ያክል እሱን ስትከትል የኖረች ነበረች። ነገር ግን በዚያ ረዥም ጊዜ ውስጥ በተገናኙ ቁጥር የሰላምታ እጁን ከመስጠቱና ሁለት ጊዜ ያክል እጅዋን ከመሳሙ በቀር እንደ ያነለት አንገትዋን አቅፎ ወደሱ አስጠግቶ ከገላው ሙቀት ኣካፍሎዋት አያውቅም። ስለዚህ ያ ሙቀት በገላዋ ሲሰራጭ እንደ ወባ በሽታ ያንቀጠቀጣት እጁን በንገትዋ ላይ ሲያደርግ አስማት እንዳስነካት ሁሉ የስዋ ፈቃድ ትቶዋት ሸሽቶ እንዲሁ ግብዝንዋን የሱ ፈቃድ ብቻ የምትከትል ያደረጋት ምን እንደሆነ ስም ልታገኝለት ስላልቻለች ‹እም - ! እኔ እንዲያው እንጃ!› አለች።

ከዚያ ውባዬሁ ባልዋ ሲስማት ትሆነው የነበረው ታሰባት። ውባዬው ባልዋ ሲስማት አፍዋን መሳሙ አላጠግበው ብሎት እንዲያውም የተኛ የፍቅር ራብዋን ቀስቅሶባት እስዋን ደመቀችን እንደ ተደገፈች ጉንጮቹን ራሱን ጆሮዎቹን አንገቱን ትከሻዎቹን ወገቡን እንዲያው በቅርቡ ልታገኝ የቻለችውን የሰውነት ክፍሉን ሁሉ በሁለት እጆችዋ ጥ - ብቅ እያደረገች እዬያዘች ስትወራጭ አንድ የፍቅር ጠብታ በሰውነቱ ውስጥ እንዳይቀር ሁሉንም እየጨመቀች ለመዋጥ የምትፈልግ ትመስል የነበረው ያ ሁኔትዋ ያንጊዜ እዚያ እፊትዋ እንደ ሆነው ሁሉ አንድ ደስ የሚያሰኝ ሙቀት በሰውነትዋ ውስጥ ስለ ተሰማት፥

«ወዬው ጉ -ድ! እኔንም እንደ መጣ ቢስመኝ ኖሮ እንደስዋ እሆን ኖሮዋል? እንጃ!› አለች፤ ያን የተዋረራትን ደስ የሚያሰኝ ሙቀት ዝም ብላ ስታዳምጥ ቆይታ ብቻዋን ፈገግ አለችና።

በሻህን እንቅልፍ ከልክሎ ሲያወራጨው ብዙ ጊዜ የቆዬ፥ ያነለት ደመቀች፥ በሁኔታዋም፥ ባድርጎትዋም ያሳደረችበት ጥርጣሬ ነበር። መጀመሪያ ሰውነትዋን ከሰውነቱ አስጠግቶ ተቀምጣ ትንሽ እንደ ቆዬች የሰራ አካላትዋ ሲንቀጠቀጥ ትንፋሽዋ ቁርጥ ቁርጥ እያለ ልብዋ ፈጥኖ ሲመታ፥ አንገትዋን አቅፎ በመድረኩ ድንግዝግዝ ብርሃን ሲያያት አይኖችዋ አፎታቸውን በሞላው ፍትወት ያሞቀው ውሀ እዬዋኘ ፊትዋን ወደሱ አቅንታ አፍዋን በከፊል ከፍታ ሁለመናዋን ረስታ ሊስማት በመንገዱ ላይ የነበረው አፉ ደርሶ እስኪስማት በናፍቆት የምትጠብቅ መስላ ታይታው ስጋቱ ሁሉ ያበቃ፥ ያከተመ መስሎ ታይቶት ደስታ ነሸጦት ነበር።

ነገር ግን ድንገት መብራት ሲበራ፥ ወዲያው ተለውጣ ተቆጥታ፥ ‹ምናባቱ› ብላ መሳደብዋ ለጊዜው ማስደንገጥ ብቻ ሳይሆን ሁዋላም ሞቆ የነበረ ስሜቱን ቀዝቃዛ ውሀ እንዳፈሰሱበት አቀዘቀዘው። እርግጥ ‹መብራቱን ነው የሰደብሁት› ብላዋለች። ብቻ አባባልዋ ራሱ የሚያጠራጥር ነበር። ‹ማነን ነው?› ብሎ ሲጠይቃት የምትመልሰው ጠፍቶዋት ስትፈልግ ቆይታ፥ እዬቀዘቀዘች ‹እ? እ -! መብራቱን ነው› ያለችው እውነትዋን ይሁን ወይም በተናገረችው ተጸጽታ፥ ወይም ደግሞ ፈርታ ሁዋላ የፈጠረችው ይሁን መቸም ከስዋና ከግዜር በቀር ማንም ሊያውቅ አይችል!

ታዲያ እስዋና እግዜር የሚያውቁት እውነት የተሳደበች እሱንም መብራቱንም መሆኑን ነው! መብራቱን ያንጊዜ በመብራቱ እሱን ሊስማት በመቃጣቱ ሁለቱንም ነበር የሰደበች! እሱ ሁለቱም እንዲያ እንደ ጋሉ ቶሎ በመሳም ፈንታ አንገትዋን አቅፎ አይን አይንዋን እያዬ ቀስ እያለ ወዳፍዋ ሲያዘግም ጊዜ በማጥፋቱ ሳመኝ» ብላ ልብዋ በደስታ እየጨፈረ ስጠበቅ፤ በዚያ መሀከል የሰይጣን መላከተኛ ሆኖ ደስታዋን ለማሰናከል ያን ጊዜ ስለ በራ ሁለቱንም ነበር የተሳደበች!

ታዲያ ምን ይሆናል? መቸስ የሰውን ልብ እንደ መጽሀፍ ገልጾ ማንበብ አይቻል! ልብዋን ገልጾ ማንበብ ቢችል ኖሮ ያ ስሜቱን እዬከነከነ ልቡን አሻክሮ ያመሸው ጥርጣሬ እስከ ቤቱ ተከትሎ ሄዶ የሌሊት እንቅልፉን ባልከለከለው ነበር! ልብዋን ገልጾ ማየት ቢችል ኖሮ ያንለት ብቻ ሳይሆን ከዚያም በፊት ለረዥም ጊዜ እሱ ሲርባት እሱን በልታ የምትጠግብበት ቀን ሲናፍቃት የኖረች መሆንዋን ባወቀ ነበር! ነገር ግን የምትወደው መስላ ፊት ስትሰጠው ኖራ በመጨረሻ ለጋብቻ ሲጠይቃት እንደ ሌሎች የገፋችውና ፊትዋን አዙራ ጀርባዋን የሰጠችው እንደሆነ እንዲያ ያለውን ውርደት መሸከም የማይችል መስሎ ታይቶት ለጋብቻ ሊጠይቃት ከወሰነበት እለት ጀምሮ ያካል ሆነ የመንፈስ እረፍት ሳያገኝ እንዲሁ እንደ ባከነ ነበር የሰነበተ! ሁለት የማይጣጣሙ ሁለት እይሚጻረሩ ተወዳዳሪዎች ፍቅርና ኩራት - በውስጡ እዬተሙዋገቱ ማስታረቅ ወይ ባንዱ ፈርዶ ፍርዱን ማስቀበል የማይችል አቅመ - ቢስ ሆኖ እንዲሁ እረፍት ሳያገኝ ሲጨነቅ ነበር የነበተ!

ያነለት ካደረበት ጥርጣሬ በመጠርጠሩም ምክንያት ከባድ ቅርታ የተጫነው ከመሆኑ የተነሳ አዝማሪው ውቤ፥ በማግስቱ ወደ አምቦ ሄደው እንዲሰነብቱ ያቀረበውን አሳብ ላለመቀበል አስቦ ነበር። ነገር ግን አዝማሪው፥ ውቤ የሁለቱን ወዳጆቹን በሻህንና የደመቀችን ጋብቻ አጥብቆ ይመኝ ስለ ነእብረ ያን ምኞቱን ተፈጽሞ

ለማየት አያደርጉትን የማያደርግ ወዳጅ መሆኑን ስለሚያውቅ የሱን ፈቃድ ላለመቃወም ሲል ብቻ አሳቡን ቅር እያለው የተቀበለ።

በሻህ ያነለት ብቻ አልነበረም ካዝማሪው ውቤና ከምሽቱ ጋር ስኒማ ቤት የሄደ። እዬጋበዙትም እዬጋበዛቸውም ደጋግሞ አብሮዋቸው ሄዶዋል። ነገር ግን እዚያ ሲሳሳሙ መጀመሪያ ማየቱ ነበር። መቸም አዝማሪው ጭዋታና ደስታ ወዳጅነቱ የታወቀለት ነበር። ብቻ ጭዋታና ደስታ ወዳጅነቱ ምሽቱን ስኒማ ቤት ባደባባይ መሀል እስከ መሳም የሚያደርሰው አልነበረም። እንዲያውም ፈረንጆችን አይተው አንዳንድ ኢትዮጵያውያን ወጣቶች እዚያ ሲሳሳሙ ያዬ እንደሆነ እንኩዋ ‹እኒህ - ዝንጀሮ ይመስል ያዬነው አይቅረን ባዮች› እያለ የሚነፍቅ ነበር። ውባዬሁም እስከትሸነፍ ድረስ መጀመሪያ እንዲያ አጥብቃ የተካላከለች አድርገውት የማያውቁ እንግዳ ነገር ስለሆነባት ነበር።

ስለዚህ አዝማሪው፥ ውቤ አድርጎት የማያውቀውንና እንዲያውም የሚነቅፈውን ነገር ያነለት ያደረገበት ልዩ ምክንያት እንደ ነበረው ለበሻህ ግልጽ ነበር። ምክንያቱም በደመቀችና በበሻህ ውስጥ ፍትወት ቀስቅሶ ሲሞቁ፥ ሲዳሩ፥ በመሀከላቸው የነበረውን የፍረት አጉራ ዘለው የጋብቻውን ጉዳይ በቃል ተገላልጸው ወደ ሚፈጸምበት መንገድ እንደሚመሩት አምኖ ነበር። ስለዚህ በሻህ ይህን ያዝማሪውን አሳብ ተረድቶ ልቡ ተነካና ‹አይ ጋሼ ውቤ -!› አለ አይኖቹን እጨለማው ውስጥ አፍጥጦ አልጋው ላይ እንደ ተንጋለለ ደግ ጉዋደኛውን እፊቱ አቁሞ ከቅርታ ፈገግታ ጋር ባይነ ህሊናው እዬተመለከተ።

በሻህ ከስኒማ እንደ ተመለሰ ዘግይቶ ራቱን ሲበላ ለማግስቱ ባስራ ሁለት ሰአት ዳቦና ሻይ ቁርስ እንዲያሰናዳለት የሆቴሉን ወጥ ቤት ለምኖት አድሮ ስለ ነበረ ያን ቁርስ አድርጎ በጥዋት ደመቀችን ሊቀሰቅስ ሄደ። እስዋም አዛዥዋንና ወይዘሮ ጌጤን ማታውን ተሰናብታቸው ስላደረች ቀደም ብላ ተነስታ እንደ ቤቱ ልማድ እንጀራ ባዋዜና ጥቁር ቡና ቁርስዋን አድርጋ ያንድ ጊዜ መለውወጫ የሚሆን ልብስና የሴት እቃዋን (መስትዋት፥ ሚዶና እነሱን የመሳሰሉ) በትንሽ ሻንጣ ከትታ ትጠብቀው ነበርና እንደ ደረሰ ወዳዲስ ከተማ ኦቶብስ መቆሚያ ለመሄድ ቸኮሉ። እዚያ ሲደርሱ አንድ ሰአት ሆኖ ነበር። ስለዚህ ባምቦ አልፎ ወደ ወሊጋ የሚሄደውን ኦቶብስ ሰው በሰው ላይ እየተደራረበ ሞልቶ በሩ ተዘግቶ አገኙት። ነገር ግን መቸም በበለኦቶብሶች ዘንድ የተሳፋሪ ገንዘቡ እንጂ ምቾቱም ሆነ ጤንነቱ ከቁጥር ስለማይገቡ በሻህና ደመቀች እንዲያ እስኪጨንቀው በሞላው ኦቶብስ ውስጥ ለመግባት ሲጠይቁ በር ተከፍቶላቸው ገቡ።

ያንጊዜ ደንበኛ ኦቶብሶች የሚያገልግሉ ባዲስ አበባ ከተማ ውስጥ ነበር። ባዲስ አበባና በጠቅላይ ግዛት ከተሞች መሀከል በኦቱብሱስ ስም እዬተመላለሱ የሚያገለግሉ ሽራ የተከደኑ ካሚዮኖች ነበሩ። እኒያ የኦቱቡስ ስም የተሰጣቸው ካሚዮኖች ከሁዋላ እስከ ፊት በቀኝና በግራ ሁለት አግዳሚ መቀመጫዎች ብቻ ነበሩዋቸው እነሱም እንዲያ ሰው ሲበዛ የሚቀመጡባቸው ቢኖሩ በጣም ጥቂት ይሆናሉ። የቆሙት በዝተው ሲጨናነቁ የተቀመጡትን ስለሚጫኑዋቸውና ብዙ ጊዜም ስለሚወድቁባቸው የሚበዙት ሰዎች ቆመው መጉዋዙን ይመርጣሉ። ስለዚህ መቀመጫዎች ተሳፋሪ በሚበዛበት ጊዜ ቦታ ከማጣበብ በቀር እምብዛም አገልግሎት አልነበራቸውም።

ደመቀችና በሻህ አዝማሪው ውቤና ምሽቱን እውጭ ሲያጡዋቸው ከኦቶብሱ ውስጥ ቀድመዋችው የገቡ መስሎዋቸው ነእብር። ነገር ግን መቸም እዚያ ሰው በሰው ላይ ተደራርቦ በሰፈረበት ሩቅ ማየት አይቻል። ገብተው እዳር እንደ ቆሙ ባቅራቢያቸው ተጨናንቆ ከቆመው ተሳፋሪ መሀከል ቢፈልጉ ሊያዩዋቸው አልቻሉም። ጭራሹን ኦቶብሱ ውስጥ አለመኖራቸው ያረጋገጡ ካምቦ በፊት ባሉት ከተሞች የሚቀሩት መንገደኞች የሰዉ ብዛት እዬተቀነሰ በመሄዱ እሁዋላ ከቆሙበት እስከ ፊት ማየት ሲችሉ ብቻ ነበር።

«ሀ፥ ያ አልቃሻምና ምሽቱ አልመጡም ማለት ነው! » አለ በሻ።

«የሉም። እኔም ከገባን እስካሁን አይኔ እነሱን ከመፈለግ አልቦዘነም፤ ግን ላያቸው አልቻልሁም። ምን አግኝቶዋቸው ይሆን? በጤናቸው አይቀሩም» አለች ደመቀች።

«እንጃባቱ! » አለ ፊቱ በቅርታ እንደ ከበደ ትከሻዎቹን ወደ ላይ ገፋ አድርጎ። ባለፈው ማታ ስኒማ ቤት ያሳደረችበት ጥርጣሬ ገና ካሳቡ ባለመጥፋቱ ቅርታው ከፊቱ ብቻ ሳይሆን ካነጋገሩም ከሌላ ሁኔታውም ሁሉ በግልጽ ይታወቅበት ስለ ነበረ ቅር ያለው ላለመምሰል ያደረው ሙከራም ሳይዋጠለት ስለ ቀረ ካዲስ አበባ ተነስተው አምቦ እስኪደርሱ የተለዋወጡዋቸው ቃሎች በቁጥር ነበሩ። ቆመው ሳሉም ሆነ ተሳፋሪዎቹ በዬከተማው ሲወርዱ መቀመጫ አግኝተው ከተቀመጡ በሁዋላ ሁለቱም የሚበዛውን ጊዜ ፊታቸውን ከስበሳቸው አዙረው ወደ ውጭ አገሩን እያዩ ነበር የሚጉዋዙ።

ደመቀች ከትናንቱ ማታ ጀምራ፥ መቀየሙንና የተቀየመበትን ምክንያት አውቃ ነበር። ብቻ ያስቀዬመውን ነገር የተናገረችው ለሱ እንደ መስለው አለመሆኑን ለማስረዳት እድል ስላልሰጣትና እስዋም አንስታ ያን የተናገረችውን ለምን እንደ

ተናገረች በዝርዝር እንዳትገልጽለት የሴትነት ኩራትዋ ስላገዳት እንዲሁ ልብ ልብዋን እንደ ፈጃት እንዳከመነመናት መድረስ አይበለው ከጉዞዋቸው መጨረሻ ደረሱ።

በሻህ ከዚያ በፊት እንዳዝማሪው ውቤ አምቦን የሚያዘወትር ስላልነበረ አልፎ አልፎ ሲሄድ የሚያርፍበት ‹ካብትይመር ሆቴል› በሚባለው ብቻ ነበር። የሌሎችን ሆቴሎች ብስም ካልሆነ በቀር ገብቶ አይቶዋቸው አያውቅም። ስለዚህ ከኦቶብሱ እንደ ወረዱ ደመቀችና እሱ ወደ ‹ካብትይመር ሆቴል› ሂደው ለዬራሳቸው አንዳንድ ክፍል መርጠው ያዙ። አምቦ ቅዳሜና እሁድ ወይም ዘለግ ባለ ያመትባል ጊዜ ካልሆነ ባዘቦት ቀን እንግዳ እምብዛም ስለማይኖር ክፍል መርጦ መያዝ ይቻላል። ባዘቦት እዚያ የሚገኙ ጠበል እዬጠጡና እዬተጠመቁ ዘለግ ያለ ጊዜ ለመሰንበት የሚሄዱት ስለሆኑ ዘመዶች ያሉዋቸው ከዘመዶቻቸው ጋር ዘመዶች የሌሉዋቸው በዝቅተኞች ሆቴሎች ይቆያሉ እንጂ ላልጋ ብቻ በቀን እስከ አራት ብር እዬከፈሉ በካብትይመር ሆቴልና በሱ ደረጃ ባሉት ውድ ሆቴሎች የሚቆዩ በጣም ጥቂት ናቸው።

በምሳ ጊዜ እመብል ቤት ውስጥ ከደመቀችና ከበሻህ ሌላ ሁለት ወንዶች ብቻ ነበሩ።

«እንግዲህ እነጋሼ ውቤ መቅረታችው ነው? » አለች ደመቀች ሁለቱም እንዳዘንተኞች አንገታቸውን ደፍተው ዝም ብለው ሲበሉ። አልፎ አልፎ በሚነጋገሩበት፥ ጊዜ እንኩዋ እዬተያዩ በመነጋገር ፈንታ ከጣራውና ከግድግዳው ጋር እንደሚነጋገሩ ሁሉ ሽቅብ ጣራውን ወይም ማዶ ግድግዳውን ወይም የሚበሉበትን ስሀን እያዩ ነበር የሚነጋገሩ! ያ በመሀከላቸው የነበረው ከፉ ቅርታ ‹ትተያዩና!› ብሎ እንዳስፈራራቸው ሁሉ የሱ አይኖች ከስዋ የስዋ አይኖች ከሱ ይሸሹ ነበር! አዝማሪው ውቤ ቢኖር ኖሮ ያ፥ ካዲስ አበባ የተከተላቸው ከባድ ቅርታ እንድኩዋንስ አንቦ ሊደርስ ካዲስ አበባ ባልወጣ ነበር! ስለዚህ ሁለቱም ያዝማሪው ውቤ ጉዋደኝነት የሱ በመሀከላቸው መገኘት እንደዚያን ጊዜ ናፍቆዋቸው አያውቅም።

«ምናልባት ከቀትር በሁዋላ የሚነሳውን ኦቶብስ የያዙ እንደሆነ አመሻሽ ላይ እዚህ ይደርሳሉ፤ ያለዚያ - አንዳይቸውን ካልቀሩ ነገ ባንድ ሰአት ቢነሱ እኛ ከደረስንበት ጊዜ እዚህ ይደርሳሉ» አለ ከራስዋ በላይ የማዶውን ግድግዳ እያዬ።

«ነገ ያልመጡ እንደሆነስ? » አለች ደመቀች ከረዢም ዝምታ በሁዋላ የምትበላው ከፊትዋ እንዳይጠፋ የምትጠብቅ ይመስል አይንዋን በሱ ላይ አተኩራ፡

«ነገ ካልመጡማ - እንድያቸውን መቅረታቸው መሆኑን አውቀን - እኛም ወደ መጣንበት መመለስ ነዋ! » አለ ጣራውን ሽቅብ እያዬ። ያንግዜ አንጀትዋን በስለት ቁር - ጥ ያደረገው መስሎ ተሰማትና፥

«ይ - ሻላል» አለች ልቅሶ መጥቶባት በሻከረ ድምጽ። ሳግዋ እዬተናነቃት ሊያጋልጣት ሲል ጥርስዋን ነከሳ፥ ጉሮሮዋን ደፍና፥ እንደ ምንም ወደ ውስጥ አስቀረችው። ጥርስን በመንከስና ጉሮሮን በመድፈን መዋጥ የማይቻለው እንባዋ ግን አይኖችዋን ሞልቶ ተንቸርፍፎ ነበር። ደግነቱ አይኖቹ ከስዋ ይሸሹ ስለ ነበረ እንባዋንም አላዬ።

«ነገ ጥዋት ካለመጡ ለምን ከቀትር በሁዋላ እንመለስ? » አለች አሁንም ዘለግ ካለ ዝምታ በሁዋላ ይተናነቃት የነበረ ሳግዋን መለስ እንዳለ።

«ምናልባት ከቀትር በሁዋላ የመጡ እንደሆነ - የሁላችንም ድካም ከንቱ ሆኖ እንዳይቀር - የነገን ቀን ብንጠብቃቸው ይሻል እንደሆነ ብዬ ነዋ! » አለና የሻከረ ድምጽዋ፥ የሚሸሹ አይኖቹን ወደስዋ እንዲያይ ስላስገደዳቸው የምትበላበትን ሰሀን እያዬች እንደ ተቀመጠች ላንድ አፍታ ጨረፍ አድርገዋት ሲያልፉ አይኖችዋ የደፈረሰ ፊትዋ የጋሙ መስለው ስለ ታዩት ገና ባልተረጋገጠ ነገር በጥርጣሬ ብቻ ተቀይሞ ስላስቀዬማት ጥፋተኛ መሆኑን ተረክቦ በውስጡ ራሱን እዬወቀሰ እሱም አንገቱን ደፍቶ የሚበላበትን ሰሀን ይመለከት ጀመር።

«ነገ ጥዋት ካልመጡ እኔ ከቀትር በሁዋላ ወዳዲስ አበባ እመለሳለሁ፤ አንተ ቆይተህ ጠብቃቸው» አለች። በሻህ ቀና ብሎ አይቶዋት እንደገና አንገቱን ደፋ። ፊትዋ ክርር ግንባርዋ ኩስትር ብለው ዞማ ጠጉርዋ ተነስቶ ቆሞ ተቆጥታ ያችው ‹አራስዋ ነብር› ሆኖ ታስፈራ ነበር! ወዲያው አሳላፊው ምሳ የበሉበትን ሂሳብ አምጥቶ በጠረጴዛው ላይ ሲያደርግላቸው በሻህ አንስቶ ትንሽ ተመለከተና መልሶ እጠረጴዛው ላይ አስቀምጦ ሊከፍል እጁን እኪሱ ውስጥ እንደ ገባ እስዋም በፈንታዋ አንስታ ተመለከተችው። ‹አንድ ምሳና አንድ ቢራ ሁለት ብር ካምሳ ሳንቲም (የሱ) አንድ ምሳ እና አንድ አምቦ (የስዋ) ሁለት ብር ካስር ሳንቲም ድምር አራት ብር ከስድሳ ሳንቲም› የሚል ነበር። በሻህ የሁለቱንም ለመክፈል አምስት ብር በጠረጴዛው ላይ ሲያስቀምጥ እስዋም ድርሻዋን አስር ሳንቲም ስላልነበራት ሁለት ብር ከሀያ አምስት ሳንቲም ከቦርሳዋ አውጥታ ሰጠች።

«ይንቺስ ሂሳብ ከዚህ ቢከፈል ምናለበት? » አለ በሻህ እጠረጴዛው ላይ ያስቀመጠውን አምስት ብር እያመለከተ።

«እግዚአብሄር ይስጥልኝ፤ ግብዣው አዲስ አበባ ለሌላ ጊዜ ይሁንልኝ። ለዚህ የሚበቃ ገንዘብ ይገፔ ስለ መጣሁ አንተን የሚያሳስብህ ነገር የለም» አለችና ያስራ አምስት ሳንቲም መልስዋንም ሳትጠብቅ ተነስታ ወደ ምኝታ ክፍልዋ ሄደች። እሱም ሂሳቡን ከጉርሻ ጋር ላሳላፊው ከሰጠ በሁዋላ ርሱን ደፍቶ በተቀመጠእብት ከትናንት ማታ ጀምሮ በመሀከላቸው የተፈጠረውን አለመግባባት ሲያሰላስልና ያ አለመግባባት ጭራሹን ወደ መለያየት ሊያደርሳቸው የሚችል ስለ መሰለው ሰግቶ ምን ማድረግ እንደሚሻለው ሲያስብ ቆይቶ በመጨረሻ ተንስቶ ወደ ክፍሉ ሄደ።

ወደዬክፍላችወ ከገቡ በሁዋላ ሁለቱም እንኩዋንስ እንቅልፍ ያሳብ እረፍት አላገኙም። ባልጋቸው ላይ እንደ ሆኑ እስዋ ያ ገደ - ቢስ ያምቦ መንገዳቸው ከበሻህ፥ ጋር የሚለያዩበት መሆኑን አረጋግጣ፥ ለጉዋደኛነቱም ከዚያ በላይ በተስፋ ትጠብቀው ለነበረ ደስታም መጨረሻ መሆኑ ቁርጥ አውቃ አንዳንድ ጊዜ ስታለቅስ አንዳንድ ጊዜ አዝማሪው ውቤ ወዳምቦ የመሄድ አሳብ በማምጣቱና እስዋም በመስማማትዋ እሱንም ራስዋንም ስትረግም በሻህ በበኩሉ ጭራሹን ተለያይተው እንዳይቀሩ ቁጣዋን የሚያበርድበት ዘዴ ሲፈልግ፥ ሁለቱም እንኩዋንስ እንቅልፍ ያሳብ ሆነ የልብ እረፍት አላገኙም።

መጨረሻ ለበሻህ የተሻለ መላ መስሎ የታዬው ያነለት፥ አመሻሽ ላይ ወደ ፍል ውሀው ጠበል አብራው እንድትሄድ ለማድረግ ቢችል እዚያም ሆነ ሲመለሱ ያልተቀዬመ መስሎ ፊቱን ሳይከብደው እንደ ድሮው በፈገግታ ሲያነጋግራት ማምሸት ያ ቁጣዋን በረድ አድርጎት ያደረ እንደሆነ በነጋው ወደ መዋኛው ቦታ መውሰድና ከዚያ ቀስ እያለ አባብሎ ወዳዲስ አበባ ለመመለስ ያሰበችውን ማስተው ነው። መላውን እንዲያ አድርጎ ከስራ በሁዋላ አስራ አንድ ሰአት እስኪደርስና ወደ ክፍልዋ ሂዶ ፍልውሀ ጠበል ለመጠጣትና ለመጠመቅ አብራው እንድትሄድ እስኪነግራት ቸኩሎ በያጫጭር ጊዜ ሰአቱን እያዩ ተነስቶ እክፍሉ ውስጥ ይንቆራጠር ጀመር።

አስራ አንድ ሰአት ግድም ወደ ክፍልዋ ሄዶ መዝጊያዋን ሲመታ፥

«ማነው? » አለች።

«እኔ - በሻህ ነኝ» አለ እያመነታ።

ደመቀች ለጊዜው ልብዋ እንደ መሸበር አለና ‹ለምን መጣ? ጥል ፍልጎ? እርቅ ፈልጎ? ወይስ ምን?› ብላ ራስዋን ጠይቃ መልሳ ስታጣ፥

«ምንድነው? » አለች ካልጋዋ ሳትወርድ የመጣበትን ክንያት ለማግኘት ፈልጋ እስክታጣ የወሰደባትን ያክል ጊዜ ዝም ብላ ቆይታ።

«ጠበል ጠጥተን ወዲያውም ታጥበን ለመመለስ - ወደ ፍልውሀ እንድንሄድ ልጠይቅሽ ነበር የመጣሁ? »

«እኔ - ፎጣም ሳሙናም ይገዬ ስላልመጣሁ ዛሬ አልታጠብም፤ አንተ ሂድ» አለች አሁንም አልጋዋ ላይ ትንሽ ዝም ብላ ቆይታ። የከፈተችለት እንደሆነ በመሀከላቸው በተፈጠረው ያለ መግባባት ጦርነት ተሸንፋ እጅዋን ለመስጠት የቸኮለች እንዳይመስለውና ወዲያውም ስታለቅስ የቆየች መሆንዋን አይኖችዋም የተጎሳቆለ ፊትዋም ይናገሩ ስለ ነበረ እንዳያውቅባት ልትከፍትለት አልፈለገችም።

«ፎጣና ሳሙና እናገኛለን። ስለዚህ - ነገ ወዳዲስ አበባ የተመለስን እንደሆነ እዚህ ደርሰን ጠበል ሳንጠጣና ሳንጠመቅ እንዳንሄድ ብዬ ነውኮ የኔ እመቤት! እና - እባክሽ እንሂድ! »

ያ አይነት አነጋገር የሰላም ጥሪ የድል መሆኑንምም መልእክት ነጋሪ ሆኖ ታይቶዋት አዘንተኛ፥ ልብዋ ደስ ብሎት በውስጥዋ ሲዘል ተሰማትና፥ ብችዋና አልጋዋ ጠርዝ ላይ እንደ ተቀመጠች ፈገግ አለች። ከዚያ በደረትዋ ውስጥ ደስ ብሎት የሚዘለው ልብዋ ንግግርዋን እንዳያደናቅፈው ጸጥ እስኪል ትንሽ ዝም ብላ ቆዬችና፥

«እሺ፤ ለብሼ እመጣለሁ አዳራሽ ቆዬኝ» አለች። እሱን ካሰናበተች በሁዋላ፥ ‹ለብሼ እመጣለሁ› ያለች ዋሽታ ነው እንጂ ፊቱንም ልብስዋን እንደ ለበሰች ስለ ነበረች ጭማዋን አድርጋ እንባ ያጎሳቆላቸው አይኖችዋንና ፊትዋን በመስትዋት እያዬች በውሀ ጠራርጋና አደራርቃ ጠጉርዋን በሻሽ አስራ ወደሚጠብቅበት ወዳዳራሹ ሄደች።

«ትንሽ የሚያሳፍር እንቅልፍ አገኘሽ? » አለ የልቡን ቅያሜ በውሸት የፊት ፈገግታ ለመሸፈን ከውነተኛ ስሜቱ ጋር እዬታገለ። ደግነቱ እርቀ - ሰላም መውረዱንና ገና ስላላረጋገጠች፥ ፊቱን አተኩራ ለማየት አለመድፈርዋን ነው እንጂ፥ ፈገግታው ከልቡ አለመሆኑን ታውቅበት ነበር።

«ጥሩ እንቅልፍ አገኘሁ» አለች፥ ውሸትዋን መሬት እያዬች ከዚያ ወደ ጠበሉ ሄዱ። ያዘቦት ቀን በመሆኑ ብዙ ሰው ስላልነበረ ካስተናባሪዎች አንዱ። ብዙ ሰው ሲኖር የማያሳዬውን የደስታ ፊት እያሳዬ ቶሎ ተቀብሎ ካርኔ ወደሚቆረጥበት ወሰዳቸው።

«አንድ ክፍል ወይስ፥ ሁለት? » አለ ካርኔ ቆራጩ፥ ቀለም እርሳሱን በካርኔው ላይ ደግኖ በሻህንና ደመቀችን እያለዋወጠ እያዬ።

«ሁለት አንደኛ ማእረግ» አለና በሻህ፥ ቶሎ አስር ብር አውጥቶ ሲሰጥ፥ ከቅርታ ፈገግታ ጋር ላንድ አፍታ ቀና ብላ አይታው፥ ምንም ሳትናገር አይኖችዋን ወደ ነበሩበት መለሰች።

ጠበል ጠጥተውና ታጥበው ተመልሰው በዬክፍላቸው አርፈው ከቆዩ በሁዋላ ራት ሲበሉ እሱ የጠረጠረው እውነት መሆን አለመሆኑን ሊያውቅ የሚችልበት ዘዴ አጥቶ እስዋም የጠረጠረው እውነት አለመሆኑ የምታስረዳበት እድል አጥታ ሁለቱም በዬራሳቸው እዬፈለጉ ሁለቱም ያን ለቅርታቸው ምክንያት የሆነውን ነገር ያነሱ እንደሆነ ቀን ወደ ዋሉበት ምናልባትም ከዚያ ወደ ባሰ ሁኔታ እንዳያደርሳቸው ፈርተው እንዲሁ ዳር ዳር ሲሉና፥ በሚናገሩትም በሚያደርጉትም ቅር ያላላቸው ለመምሰል ሲጠነቀቁ አመሹ።

ደመቀችና በሻህ የጋራ ፍቅር ካደረባቸው ጊዜ ጀምረው፥ ፍቅራቸውን በምስጢር ይዘው ያን በዬልባቸው ደብቀው የያዙትን ጽኑ ፍቅር ተጋላልጸው ደስታችወ ፍጹም የሚሆንበትን ቀን በናፍቆት የሚጠብቁ ነበሩ እንጂ እንዲያ ያለ ወደ መለያየት የሚያደርስ ከባድ ቅሬታ በመሀላቸው ተፈጥሮ አያውቅም፤ ‹ይፈጠራል› በለው አስበውም አያውቁ። ስለዚህ አምቦ ያቀያየማቸው ይመስል ሁለቱም አምቦን ጠሉት። ባንድ ቀን ሁለቱም አምቦ እጅ እጅ አላቸው! በሻህ ተከታዩን ቀን እዚያው ለማሳለፍ ያሳሰበ ምናልባት፥ አዝማሪው ውቤ የመጣ እንደሆነ ለዚያ በመሀከላቸው ለተፈጠረው ችግር (በሻህ ራሱ ለፈጠረው ችግር) መድሀኒት እንደሚያገኝለት በማመን ብቻ ነበር።

አሳላፊው ሂሳባቸውን ይዞ መጥቶ እጠረጴዛው ላይ ከማስቀመጡ በፊት በሻህ ቶሎ ከጁ ተቀብሎ ተመለከተና የሂሳብ፥ ወረቀት በጁ እንደ ያዘ አስር ብር አውጥቶ ሲሰጠው፥

«እስቲ እባክህ ሂሳቡን እኔም ልየው» አለች ደመቀች፥ ከጠረጴዛው ማዶ በአንጻሩ እንደ ተቀመጠች እጅዋን ዘርግታ።

«ሂሳብ ለማስወረድ ማስታወቂያ ያስፈልገኛል ጌታዬ» አለ አሳላፊው ከበሻህ ጋር ተመሳጥረው ስለ ነበረ፥ እሱም እጁን ዘርግቶ።

«ያው እንደ ቀኑ ነው» አለና በሻህ የሂሳቡን ማስታወቂያ ለስዋ በመስጠት ፈንታ ላሳላፊው ሰጠው። አሳላፊው አስሩን ብርና የሂሳቡን ማስታወቂያ ይዞ መልሱን ሊያመጣ ሲሄድ፥

«ይቅርታሽን በስራቱ ወንድና ሴት አብረው ሆቴል ሲበሉ፥ ወይም ስኒማና ትያትር ሲገቡ ወንዱ ገንዘብ ባይኖረው እንኳዋ ከሴትዋ ተበድሮም ቢሆን፥ መክፈል የሚገባው እሱ ነው። ቅድም ስራት ተላልፈሽ ስትከፍይ - ዝም ያልሁ ከከፈልሽ በሁዋላ ‹መልሺ› ማለቱን ፈርቼ ነው። ስለዚህ እባክሽ ገንዘብ ካነሰኝ እንድታበድሪኝ ስለምጠይቅሽ እዚህ ሆቴልም ወደ ጠበል የሄድን እንደሆነም ሰው እንዳይነቅፈን ‹ገንዘብ ልክፈል› አትበይ። ስላንቺ የማወጣን ሁሉ እነግርሻለሁና በማስታወሻ ይዘሽ፥ ለብቻችን ስንሆን ወይም አዲስ አበባ ስንመለስ ትከፍይኛለሽ» አለ፥

ራሱ በፈጠረው ስራት አስፈራርቶ ገንዘብ እንዳትከፍል ለማድረግ ስለ ፈለገ።

«እሺ ይቅርታህን ስራቱን፥ ባላውቅ ነው» አለች ካሽሙር ፈገግታ ጋር በተናገረው አምና ሳይሆን በመጠኑ ተሻሽሎ ያመሸው ግንኙነታቸው ደግሞ እንዳይበላሽ ፈርታ።

በነጋው ጥዋት መዝጊያዋ በሀይል ተመታ። በሻህ ምንጊዜም መዝጊያ እንዲያ አድርጎ መትቶ አያውቅ። ስለዚህ ሌላ ሰው መሆኑን ገምታ እንደ መፍራት አለችና፥

«ማነው? » አለች ለብሳ፥ አልጋዋ ጠርዝ ላይ እንደ ተቀመጠች።

«ሰራተኛ ነኝ፤ አምስት ቁር ለቁርስ ይጠብቅዎታል።»

«አምስት ቁጥር? ማነው አምስት ቁጥር? »

«ትናንት ምሳና ራት አብረውዎ የበሉት ጉዋደኛዎ» አለ አሳላፊው። ብዙ ጊዜ የሆቴል ሰራተኖች በስማቸው የሚያውቁዋቸውን እንግዶች በክፍላቸው ቁጥር መጥራታቸው የተለመደ ነው።

«እ -! ‹እሺ መጣሁ› ብላለች በላቸው» አለችና ተነስታ እክፍልዋ ውስጥ ወዳለው የፊት መታጠቢያ ቀረብ ብላ፥ መስታዋት እያዩች ሻሽዋን ከራስዋ ፈትታ ውሀ እዩነካች ፊትዋን አባብሳና ጠጉርዋን አስተካክላ ወደ መብል ቤት ስትሄድ በሻህን ተቀምጦ ሲጠብቃ አገኘችው። ትናንት በፊትዋ ይታይ የነበረው የከበደ ቅርታና የድካም

መልክ ያምቦ ጠበል ወዲያ እንዳስለቀቀው ሁሉ የድሮ ውበትዋም ንቃትዋም ተመልሰው አምሮባት ነበር።

«ጥሩ እረፍት አግኝተሽ ያደርሽ ትመስያለሽ፤ እሸት ሆነሻል» አለ፥ ገና ከሩቅ ሲያያት እንደ ድሮው ፊቱ ሙቀትና ድምቀት ባለው ፈገግታ በርቶ ሊቀበላት ከተቀመጠበት ተነስቶ ወደስዋ እያመራ።

«እባክህ አትቀልድብኝ» አለች ለሰላምታ የዘረጋላትን እጁን ስትጨብጥ ፊቱን ገደም አድርጋ እያዬች። ያን ከትናንት ወዲያ ማታ ጀምሮ ጠፍቶ የነበረውን ውብ ፈገግታውን እንደገና በፊቱ ብቅ ብሎ ስታይ በጣም ነበር ደስ ያላት።

በሻህ፥ ሌሊቱን አልጋው ላይ እንደ ተንጋለለ አይኖቹን በጨለማው ውስጥ አፍጥጦ አዲስ አበባ ስኒማ ቤት በሱና በደመቀች መሀከል የሆነውን ሁሉ ጠርቶ አምጥቶ አንድ ባንድ ባይነ - ህሊናው ፊት እያሳለፈ ሲያይ ጥርጣሬው ያን ያክል እስከ መቀየም የሚያደርስ አለመሆኑ ግልጽ እዬሆነለት በሄደ መጠን ተጸጽቶ ራሱን ይወቅስ ጀመር። ተጠጋግተወ እንደ ተቀመጡ፥ ግላ ደርታ ሰውነትዋ ሁሉ እዬተንቀጠቀጠ ከላይ ከላይ ትተነፍስ የነበረው አንገትዋ አቅፎ ሲስማት ቀረብ ሲል ፊትዋን ወደሱ አቅንታ አፍዋን ከፍታ ትጠብቀው የነበረው እንዲያ ከንፈሮቻቸው ሊገናኙ አንድ ጋት የማይሞላ ርቀት ሲቀራቸው መብራቱ ስለ በራ፣ ተበሳጭታ የሰደበችው መብራቱን መሆኑን የነገረችው ይህ ሁሉ ሲታሰበው እሱን የሰደበችው መስሎት የተቀዬመ እንዲያው ቆዳው ስስ ስለሆነ ብቻ እንጂ ያን ያክል ተቀይሞ እስዋን ጭምር የሚያስቀይምበት በቂ ምክንያት እንዳልነበረው ተገንዝቦ ጸጸት ገባውና ያልተቀየመ ለመምሰል ሳይሆን ያልተቀዬመ መሆኑን ለማስረዳት ይጥር ጀመር።

«ልሙትልሽ ቀልዴን አደለም። ከትናንት ትውት ጀምሮ ቀኑንም ማታውንም ፊትሽን ከብዶት ምን ልበልሽ? እንቅልፍ አጥተሽ እንዳደርሽ - የድካምና የመጠውለግ መልክ ይታይብሽ ነበር። ዛሬ የዚያ ሁሉ ምልክቱም የለ! ፍጹም ያረፈ መልክ ነው ያለሽ።»

«ትናንት የጠጣሁት ጠበ መድህኒት ሆኖኝ ይሆናል፤ ያምቦ ጠበል መድህኒት አደል? » አለችና ፈገግ እንዳለች ትንሽ ዝም ብላ ቆይታ «ታዲያኮ - ያንተን ፊት ብታየው ኖሮ የኔ ፊት መክበድ ባላስገረመህ ነበር! » አለች፤ ካሽሙር ፍርጥምታ ጋር አይኖቿን ገደም አድርጋ እያዬች።

«ባላየውም ከብዶኝ እንደ ነበረ ተሰምቶኛል። ዛሬ ግን ደህና ነኝ። ደህና አደለሁም! ዛሬም ፊቴ ከብዶ ይታያል? » አለ እሱም ካሽሙር ፈገግታ ጋር ገደም አድርገው የሚተያዩትን አይኖችዋን እያዬ።

«እንደገና ካልተመለሰበት አሁንስ - እድሜ ላምቦ ጠበል፥ ደህና ነው» ብላ ስትስቅ እሱም አብሮዋት ሲስቅ ቆይቶ፥

«ያሁኑን አልሁ እንጂ ለወደፊቱማ - ያንቺስ ቢሆን እንዳይመለስ ዋስ ጠርቶ አልሄደ! » አለ።

«ያንተው ከተመለሰማ የኔውም እንደሚመለስ ሳይነበብ የተተረጎመ ነው! »

«እንዴት? ለምን? »

«እኔ እንጃ! ይህ አይነቱ በሽታ ከማናቸውም፥ በሽታ የበለጠ ተላላፊ ነው መሰለኝ! »

እንዲህ እንዲህ ያሉ የዘይቤ ድብብቆሽ ጭዋታዎች እዬተጫወቱና እዬተሳሳቁ ቁርሳቸወን በልተው ሲጨርሱ አጠገቡ ባንድ ወንበር ላይ በጋዜጣ ወረቀት ሸፍኖ ያስቀመጠውን ጥቅል አንስቶ መሸፈኛውን ገለጠና ለሱም ለስዋም ጥዋት ወጥቶ የገዛቸውን የዋና ልብሶች ሲያሳያት፥

«ምንድነው እሱ? » አለች።

«የዋና ልብስ ነው። ጥዋት ከቁርሴ በፊት ትንሽ መንቀሳቀስ ስላስለመድሁ ዛሬም በጥዋት ወጥቼ ስዘዋወር እዚህ አጠገባችን ባለው የሱቅ መስታዋት የዋና ልብሶች ሳይ ጊዜ ገብቼ እነዚህን ገዛሁ» አለ የሱን መልሶ በወንበሩ ላይ አስቀምጦ የስዋን ዘርግቶ ፊቱንም ሁዋላውንም እያገላበጠ እያሳዬ። የዋና ልብሱ ጠቆር ያለ ሰማያዊ ሰለ ነበረ እንደ ደመቀች ቀይ መልክ ላላቸው በጣም የሚስማማ ነበር።

«እኔኮ ዋና አላውቅም ጋሼ! እኛ አገር ወንዶች፥ ናቸው እንጂ ሴቶች እንኩዋንስ ሊዋኙ ወንዶች ባሉበት ልብሳቸውን አውልቀ አይታዩም። ወንዝ ሲሻገሩ እንኩዋ ውሀው እስከ ባታቸው የሚደርስ ከሆነ ቀሚሳችውን ከባታቸው ከፍ የሚያደርጉት ውሀው ውስጥ ከገቡ በሁዋላ ነው። ስለዚህ - ያልለመድሁት ሆነና እንኩዋንስ ዋና የማላውቀውን ባውቅም በብዙ ሰው ፊት ልብሴን አውልቄ ይህን ለብሼ መታየት -

በጣም ነው የሚያሳፍረኝ» አለች ያኔውኑ በብዙ ሰው መሀከል ልብስዋን አውልቃ ራቁትዋን እንደ ቆመች ሁሉ አፍራ እዬሳቀች ፊትዋን በሁለት እጆችዋ ሸፈነችና፥

«ይህ እንኩዋ ምንም አደል! አሁን እንዳልሽው ሌሎች ሴቶች ሲያደርጉት ስላላዬሽ ነው። ሌሎች ሴቶች ልብሳቸውን አውልቀው እንዲህ ያለ የዋና ልብስ ለብሰው ሲዋኙ ስታይ ማፈርሽ ይቀራል። ‹ዋና አላውቅም› ላልሽው ያልቃሻሙን ያክል ባይሆን እኔም በመጠኑ ዋና ስለማውቅ ላስተምርሽ እችላለሁ። እሱ አሁን ደብተራነቱን ከተወ በሁዋላ እኔ ከልጅነቴ ጀምሬ ስለሆነ ከዋና ጋር አብረን የኖርን ውሀ ከኔ ከረዥም ጊዜ ጉዋደኛው እጅ ቀምቶ አይበላሽም አይዞሽ። ስለዚህ የዋና ልብስሽን እዚሁ እክፍልሽ ውስጥ ለብሸሽ በላይ ልብሽን ደርበሽ እንሂድና እዚያ ቁጭ ብለን የሚዋኙትን ሴቶች ስትመለከት ከቆዬሽ በሁዋላ ስትደፋፈሪ ቀስ ብለሽ ልብስሽን ከላይ አስንተሽ እግር በሚያስቆመው ጥልቅ ባልሆነው ክፍል አለምድሻለሁ።»

«ኡም - ! እንጃ ፈራሁ! »

«በኔ ያስተማሪነት ችሎታ ተጠራጥረሽ ነው? ወይስ ምኑ ነው ያስፈራሽ? ያ አልቃሻም ቢመጣ ኖሮ - እሱ ሊያስተምርሽ አልነበረም ወዲህ ለመምጣት የወሰን? »

«እኔ እንዲያው ከናንተ ጋር እዚህ እዬተጫወትሁ ጊዜ ለማሳለፍ ነው እንጂ - ፊቱንም ቢሆን ‹እዋኛለሁ› ብዬ አላሰብሁም ነበር።»

«ጥሩ ነው፤ አሁንም እንዳልሁሽ የዋና ልብስሽን በልብስሽ ውስት ለብሰሽ እንሂድና ቢያሰኝሽ አስተምርሻለሁ ካላሰኘሽም እኔ እዋኛለሁ፥ አንቺ ቁጭ ብለሽ ስታይ ቆይተሽ እንመለሳለን።»

«ለመሆኑ ይህን - በስንት ገዛኸው? » አለች የሚናገረውን ዝም ብላ ስትሰማ ቆይታ የዋና ልብሱን ይዛ ወደ ክፍልዋ ለመሄድ ስተነሳ።

«በስምንት ብር ነው እንዳትረሺው ጻፊው» አለ ፈገግ ብሎ ውብ ጥርሱን እያሳዬ።

«ገንዘብ ሲያንሰኝ እንድታበድሪኝ እጠይቅሻለሁ ብለኸኝ ነበረኮ መቸ ነው የምትጠይቀኝ? » አለች እንደ ቆመች ሽቅብ የሚያዩዋትን አይኖቹን ቁልቁል ገደም አድርጋ እያዬች።

«ሲያገለኝ ብዬሻለሁኮ! የመጣን ገና ትናንት ስለሆነ እስካሁን አላሰኘም።»

«ቢሆንስ - እስካሁን የማያልቅ ገንዘብ - ከየት እየመጣ ነው? »

«እዬተሰረቀ ወይም፥ እዬተቀማ ነዋ! ያ አልቃሻም አዝማሪ፥ ‹ሌባ ቀማኛ› የሚለኝ - እንዲያው ያለ ምክንያት መሰለሽ? ይህን ስለሚያውቅ ነውኮ! » ሲል እንደ ተቀመጠ ገደም አድርገው የሚያዩትን አይኖቻዋን ባሽሙር አስተያየት ሽቅብ እያዬ እዚያው ትታው እዬሳቀች ወደ ክፍልዋ ሄደች።

## ምእራፍ ሰላሳ አምስት

# አምባው ተሰበረ!

ደመቀችና በሻህ እመዋኛው ቦታ ሲደርሱ፥ ምንም እንኳዋ ቀኑ አዘቦት ቢሆን፥ እዚያ የሚዋኙበትና ዙሪያውን ከበው የሚዋኙትን የሚመለከቱት ተመልካቾች በመጠኑ በርከት ያሉ ነበሩ። ከሚዋኙት መካከል የሚበዙት፥ ሴቶችና ወንዶች ወጣቶች ነበሩ። ብቻ የወጣቶችን ያክል አይበዙ እንጂ ጸና ያሉ ሴቶችም ወንዶችም ነበሩባቸው።

«እዚያ እንቀመጥ» አለ በሻህ አንድ ከተመልካቾች፥ ትንሽ ገለል ያለ ከፍተኛ ቦታ በጁ አመልክቶ። ያ ገለል ያለ ከፍተኛ ቦታ እንደ፥ ዋናተኞችን ለማሳዬትም ሆነ ልብስን አውልቆ ጸሀይ ለመሞቅ የሚመች ነበር። ሄደው ከመቀመጣቸው አንድ ያዲስ አበባ መኮንን ከምሽታቸው ጋር የዋና ልብሳቸውን በፎጣ ጠቅልሎ የያዘ ልጅ አስከትለው ሲመጡ በሩቅ አየ።

«ኦ! እኒያ ሰዎች በጣም የማውቃቸው ናቸው፥ ሄጄ ሰላምታ ሰጥቻቸው ልምጣ» አለና በሻህ ተነስቶ ሄደ። መጀመሪያ እጅ ነስቶ፥ ለሴትዬዋ ጉንጬን ለወንድየው እጁን ከሰጠ በሁዋላ እዬተሳሳቁ ሞቅ ያለ ሰላምታ ተሰጣጥተው ትንሽም ሲነጋገሩ ቆይተው ባልና ምሽቱ ወደ ልብስ መለወጫው ቤት ገቡ።

«እነማን ናቸው? ዘመዶችህ ናቸው እንዲያ ተቃቅፋችሁ የተሳሳማችሁ? » አለች ደመቀች፥ በሻህ ተመልሶ አጠገብዋ ሲቀመጥ።

«ወንድዬው አቶ ታችበሌ ግዛው ሚስታቸው፥ ወይዘሮ ኩሪባቸው አምባዬ ይባላሉ። ከሁለቱም ጋር የስጋ ዝምድና የለኝም። ግን ካቶ ታችበሌ የት ልጅ ጋር በልጅነታችን ካቶሊክ ትምህርት ቤት አብረን ስንማር የማንለያይ ጉዋደኞች ነበርን።

ታዲያ ያንጊዜ እሱን ተከትዬ እቤታቸው እዬሄድሁ ተዋውቄያቸው በዚያ ሳቢያ፥ በፋሽስቶች ወረራ ጊዜ የኔን ብቻ ሳይሆን የጉዋደኖቼን ነፍስ ጭምር ከብዙ አደጋ ምናልባትም ከሞት ያዳኑ ናቸው። ቤታቸው ከሩፋኤል በላይ እሜካ ውስጥ ስለሆነ ጉዋደኞቼም እኔም አደጋ ጥለን ከምንሸሸግባቸው ቦታዎች፥ አንዱ የነሱ ቤት ነበር። መቸም ሴትዮዋ ግሩም የሆኑ ዘዴኛ ናቸው! አንድ ጊዜ ብቻ ‹ከሞት አዳንሁ› ብለው ሊገድሉን ነበር» አለ ወይዘሮ ኩሪባቸው እሱንና ሁለቱ ጉዋደኞቹን ለማዳን ያደረጉት ትዝ ብሎት ፈገግ አለና።

«እንዴት? » አለች ደመቀችም ወሬውን ከመስማትዋ በፊት የቅድሞሽ ፈገግ ብላ።

«አንድ ማታ፥ ሁለት ጉዋደኞቼና እኔ ከሩፋኤል በታች አንዱን ትልቅ የጣሊያን ጋራዥ ብዙ ከባድና ቀላል መኪናዎች በውስጡ እንደ ታጎሩ፥ በፈንጂ አጋይተነው፥ በሀርዛፍ ለበሀርዛፍ እዬተሹለከለክን ሄደን እነሱ ቤት ገባን። ያደረግነውን ስንነግራቸው ሶስታችንንም እያቀፉ ከሳሙን በሁዋላ የደስ ደስ አንድ ማንቆርቆሪያ ጠጅና አንድ ጠርሙስ ኮኛክ እንዲወርድልን አዘዙ።

«ፈንጠዝያው አሁን አደለም፥ ለሁዋላ ይሁን። አሁንስ ህይወታቸውን የምናድንበት ዘዴ ብንፈጥር ይሻላል። እንደሚያውቁት፥ እንዲህ ያለ አደጋ ሲጣል፥ ጣሊያኖች ሰፈሩን በሙሉ መፈተሽ ልማድ አድርገው የያዙት ዘየ ስለሆነ አሁን መምጣታቸው አይቀርምና፥ ቶሎ እንሸሽጋቸው» አሉ እሜቴ ኩሪባቸው።

«ወዴት? » አሉ ባልዬው ደስታቸው ያስረሳቸውን ምሽታቸውን ሲያስታውስዋቸው ደስ ብሎዋቸው።

«እቤት ውስጥ አይሆንም እውጭ ይሻላል» አሉና እሜቴ ይዘውን ወጡ። ከዚያ አጥሩ ጥግ አንድ ትልቅ የሳር ድርቆሽ ክምር ስለ ነበረ፥ ያን ክምር ከላይ ካናቱ ባልና ምሽታቸው ልጆቻቸውና እኛም ተጋግዘን ቶሎ ቶሎ እዬናድን ብዙ ሳር ካወረድን በሁዋላ፥ በዚያ ከክምሩ በናድነው ሳር ሶስታችነንም ከነልብሳችን ከግር እስከ ራሳችን ግጥም አድርገው እዬሸፈኑ ሶስት ሶስት ላይ አስረው እክምሩ ስር ጥለውን ሄዱ። ሶስታችን እንዲያ ታስረን እክምሩ ስር ወድቀን ለሚያየን ለዚያ አናቱ ላይ ለጎድለው ክምር መሙያ የቀረቡ ሶስት የሳር ሸክሞች እንመስል ነበር እንጂ፥ እንኩዋንስ ሰዎች ‹ሌላ ነገር ይሆናሉ› አሰኝቶ የሚያስጠረጥር ምንም አልነበረም።

«ወዲያው ባለቤቶቹ፥ እስከ ልጆቻቸው ትተውን እንደ ሄዱ ተሸፍነን የታሰርንበትን ድርቆሽ አልፎ የሚደርሰን አዬር አልበቃን ብሎ ታፈንና መድረሻ አጣን። ድርቆሹን ትንሽ ገለጥ አድርገን አየር እንድናስገባ እጃችን አብሮ ታስሮዋል። እንዳንጮህ የታሰርንበት ድርቆሽ ድምጻችንን አያሰማው ከመሆኑ ሌላ ‹ጣሊያኖች የመጡ እንደሆነ ይሰሙናል› ብለን ፈራን። እንዲያ በሁለት ሞቶች መሀከል ተወጥረን ስናነጣጥር ያጥሩ በር የቆርቆሮ መዝጊያ በሀይል ሲመታ ትንሽ ተሰማን። ወይዘሮ ኩሪባቸው እንደ ገመቱት ፈታሾች ነበሩ። ሶስት ጣሊያኖችና አምስት የኢትዮጵያውያን ወታደሮች ገብተው ዋናውን ቤትና ማድቤቱን የቤቶችንና፥ ያጥሩን ጣጋጥግ የድርቆሹን ክምር ዙርያ ሳይቀር እኩል ሰአት ያክል ምንጥር አድርገው በርብረው ሲያበቁ ሄዱ። ያ እኩል ሰአት ለኛ አመት መስሎ ታይቶን ነበር። ምናልባት ሌላ እኩል ሰአት እንዲያ እንደ ታፈን ብንቆይ ኖሮ እንኳ ሳንሞት አንቀርም ነበር!

«ፈታሾች ርቀው መሄድችውን ካረጋገጡ በሁዋላ ባልና ሚስቱ መጥተው ከታሰርንበት ሲፈቱን እንደ ልብ መተንፈስና መንቀሳቀስ እስክንችል በወደቅንበት እንዳለን ብዙ ቆዬን። ከዚያ በፊትና ከዚያ በሁዋላ እነሱም ሌሎች የውስጥ አርበኞችም እንዲሁ - ለምሳሌ በርሜል በላይችን እዬደፉና - ያንጊዜ ሁላችንም ቲም ያለበቀልን ወጣቶች ስለ ነበር - የሲት ቀሚስ እያለበሱ አስቀምጠውን ፈታሾች በእምጡን ቁጥር ‹ካሁን አሁን የተገኘን› እያልን ያልፈራንበት ጊዜ የለም! » እያለ ያቶ ታችበሌና የወይዘሮ ኩሪባቸውን ወሮታ ሲያወራ ባልና ምሽቱ የዋና ልብሳቸውን ለብሰው ፎጣቸውን በዬትከሻቸው ላይ ጣል አድርገው ከልብስ መለወጫው ቤት ብቅ አሉ። ሁለቱም ወፍራሞች ነበሩ። ከወንድየውም ሴትዬይቱ። በውቀት ይሁን ያለ ውቀት ወይዘሮ ኩሪባቸው የለበሱት የዋና ልብስ ለሳቸው የማይሆን ጠባብ ስለ ነበረ ውፍረታቸውን ይብስ አጉልቶ እያሳዬ ያሳጣቸው ነበር። ብቻ እሳቸው የዋና ልብስ መሆኑን እንጂ ልካቸው አለመሆኑን ከቁም ነገር የጻፉት አይመሉም ነበር። ዘና ብለው ከባላቸው ጋር እዬተጨዋወቱና እዬተሳሳቁ መጥተው እሳቸው እመዋኛው ጠርዝ ላይ ሲቀመጡ ባላቸው ውህ ውስጥ ገቡ።

ያቶ ታችበሌ የዋና ችሎታ በጣም መጠነኛ ነበር። ስለዚህ በግር የሚያስቆመው ወደሚያጠልቀው ክፍል ሲደርሱ እዬባቡ እጆቻቸውንና እግሮቻቸውን ባንድ ላይ በሀይል ሲያስሩ በዙሪያቸው ያለው ውሀ እዬታወከና እዬተንቦጫረቀ ሰው ባጠገባቸው ሊዋኝ አይችልም። እንዲያ ሰውን ካጠገባቸው እያሸሹ መዋኛውን በወርዱ እያቋዋረጡ ሶስት ጊዜ ያክል ወዲያና ወዲህ ከተመላለሱ በሁዋላ ስለ ደከማቸው ወጥተው ትንሽ አርፈው ቆዩና ምሽታቸውን ይዘው ገቡ። ወይዘሮ ኩሪባቸው የባላቸውን ያክልም

አያውቁ፤ ዋና መማር ከጀመሩ ያነሉት ሶስተኛ ቀናቸው ነበር። አስተማሪያቸው ባልዬው ነበሩ።

አቶ ታችበሌ ወደ ጥልቁ ክፍል እንዳይደርሱ እዬተጠነቀቁ ምሽታቸውን ከሆዳቸው ስር ባንድ እጃቸው ደግፈው በሚያስቆመው ክፍል ቀስ ብለው በጎናቸው እዬሄዱ።

«እይው እግርሽን ቀስ አድርገሽ መሬቱን አስለቅቂና፥ እጅሽንም እግርሽንም፥ ባንድ ላይ በሀይል ማነቃነቅ ነው» ይላሉ። ነገር ግን ወይዘሮ ኩሪባቸው እንደ ተነገሩት ለማድረግ በሞከሩ ቁጥር ሊገለበጡ ወናንድ ወገን ስለሚያጋድሉ ያን ጊዜ ባብተው ዋናውን ይረሱና ያስተማሪያችውን ወገብ ወይም አንገት አንቀው ሲይዙ ሁለቱም አብረው ወድቀው መሬቱ ቅርብ በመሆኑ እግራቸው እስኪነካውና እንደ ምንም ተፈራግጠው እስኪቆሙ፥ ‹እኔ እወጣ፥ እኔ እወጣ› ተያይዘው እዚያው ሲራኮቱ ይቆያሉ።

በሻህ የወዳጆቹን ችግር አይቶ ሊረዳቸው ስለ ፈለገ፥ በዋና ልብሱ ላይ የለበሰውን ልብሱን አውልቆ እዚያው ከደመቀች አጠገብ አስቀምጦ ሲነሳ፥

«አንቺም ልብስሽን አውልቂና ዋና መማር ባትፈልጊ እንኩዋ ጸሀይ ስትሞቂ ቆይ። እንደምታይው እዚህ የዋና ልብስ ለብሶ መዋኘት ወይም ጸሐይ መሞቅ ሳይሆን ደንበኛ ልብስ ለብሶ መቀምጥ ነው ነውሩ! » አለ ደመቀችን ከፈገግታ ጋር ገደም አድርጎ እያዬ። እውነትም ደንበኛ፥ ልብስ መልበስ ነውር ይመስል እዚያ የዋና ልብሳቸውን እዬለጠፉ ግማሽ እርቃናቸውን የሚሄዱ ወንዶችና ሴቶች ሁሉ እዬተጠቃቀሱም እዬተሳሳቁም፥ እንደ ጉድ አተኩረው የሚያዩዋቸው እነደመቀችንና እንደሱ ደንበኛ ልስብ ለብሰው ከመንጋው ገለል እያሉ የተቀመጡትን ጥቂት ሰዎች ነበር።

በሻህ ከደመቀች ትንሽ ራቅ እንዳለ ፊቱን ወደስዋ አዙሮ በግር ጣቶቹ ሽቅብ ተንጠራርቶ ቆመና፥ ሰውነቱን ለማፋታት ጎበስ ብሎ በጅ ጣቶቹ መሬት እዬነካ ቀና ብሎ ወደ ሁዋላው እዬታጠፈ እንዲህ ብዙ ጊዜ እንደ ጋለ ልምጭ ወደ ፊትና ወደ ሁዋላ ሲታጠፍ ሲዘረጋ ቆይቶ፥ በመዋኛው አናት፥ ዘልሎ ለመጥለቅ ወደ ተሰራው አረግራጊ ሳንቃ ሲሄድ የሰው ሁሉ አይን ተከትሎት ሄደ። በልጅነቱ በትምህርት ቤት ካገኘው ያካላት ማዳበሪያ ትምህርት ሌላ፥ ከችግር ጋር ሲታገል የኖረ ስለ ነበረ ባካላቱ መዳበርና በቅርጹ ያዩት ሰዎች ሁሉ የሚደነቁበት ነበር። ከጉልበቱ በላይ ያሉ አካላቱ፥ ታፋዎቹ ሰብሰብ ሆዱ፥ ክትት ደረቱና ትከሻዎቹ ሰፋ ሰፋ ግራና ቀኝ ክንዶቹ የበረት አለሎዎች እዬገቡ እንደ ተቋዋጠሩባቸው ሁሉ ጉጥር ጉጥር ራሱ በማደግ ላይ ከበረው

ዞማ ጠጉሩ ጋር ከበድ ብለው ሁሉንም ባንድ ላይ ሲያዩት፥ ‹የኮርማ አንበሳ ቅርጽ ያለው ነው!› የሚሉት አይነት ነበር! ደመቀች እስከዚያነለት ድረስ ልብሱን አውልቆ አይታው አታውቅም። ስለዚህ ለስዋ ያ ውብ፥ ያካላት ቅርጽ ያ የወንድ ውበት ከዚያ በፊት አይታው የማታውቅ አዲስ ክስተት ስለ ነበረ የስዋም አይኖች ዘልሎ እስኪጠልቅ ድረስ አልተለዩትም፤ አጅበውት ሄደው፥ ነበር። እግሮቹን ብቻ አለማየት ነው! እግሮቹ ከጉልበቶቹና ከቁርጭምጭምቶቹ ተቀራርበው ከመሀል፥ የግር ዛቢያዎቹ በሰፊ ተራርቀው ሲታዩ ከላይና ከታች ጫፎቻቸውን አገናኝተው ያቆሙዋቸው ጥምድ ደጋኖች ይመስሉ ነበር!

ባረግራጊው ሳንቃ ላይ ወጥቶ ቆሞ፥ ሽቅብ በሀይል እንዲያጉነው ለማድራት ሶስት ጊዜ እዚያው በቆመበት እዬዘለለ እዬተመለሰ፥ መዝለያውን አድርቶ ባራተኛው ሽቅብ ከሳንቃው በላይ ከሁለት ሜትር የሚበልጥ አዬር ውስጥ ከጉዋነ በሁዋላ እዚያ እንዳለ ግልብጥብጥ ብሎ ራሱን ወደ ታች እግሮቹን ወደ ላይ አደረገና ቁልቁል የተወረወረ ጣምራ ጦር የመሰሉ እጆቹን ወደ ላይ አስቀድሞ ወርዶ ውሀውን ቀድዶ እውስጡ ጥ - ልቅ ብሎ ጠፋ! ቀድዶ የገባበት ውሀም እንደ መታወከ ብሎ ቆይቶ ከዋጠው በሁዋላ አፉን እንደሚያጣጥም ሁሉ ክፍት ክድን አደረገና ግጥም አድርጎ ዝም አለ። ከዚያ በመዋኛው ጠርዝ ዙሪያውን የተቀመጠው ሰው ሁሉ አይኑን በጠለቀበት ቦታና ባካባቢው ላይ አተኩሮ ሲጠባበቅና ‹የት ጠፋ? ምን ሆነ?› እዬተባባለ ሲጠያዬቅ እሱ ሽኩቶ (ውስጥ ውስጡን ጠልቆ ሂደ) ወዲያ ታች አቶ ታችበሌ ምሽታቸውን በሚያስተምሩበት ደርሶ ብቅ ሲል ‹ያው እዚያ ወጣ! ያው እዚያ ሀች -!› እዬተባባለ ይንጫጫ ጀመር። የመዋኛው ቁመት ከጠለቀበት እስከ ወጣበት - ‹አምሳ ሜትር ነው› ይባላል።

በሻህ፥ ያን አምሳ ሜትር ርዝመት ያለው መዋኛ ሽኩቶ አቁዋርጦ ብቅ ከማለቱ ትንሽ እንኩዋ ሳያርፍ እንደገና እዬዋኘ ዘልሎ እጠለቀበት ቦታ ደርሶ ሲመለስ የጅ አጣጣሉ ጌጠኛ ስልት ተመልካቹን ሁሉ በጣም ነበር ደስ ያሰኘው። አምቦ፥ ሲያልፍ - ሲያገድም አንዳንድ ቀን ውሎ ከማደር ወይም ላዳር ብቻ ካልሆነ እዚያ ሰንብቶ ወይም ዋኝቶ ስለማያውቅ ከከተማው ነዋሪዎችም ሆነ ከተማውን ለረፍት ከሚያዘወትሩ ሰዎች መሀከል የሚያውቁት ቢኖሩ ጥቂት ይሆናሉ። ነገር ግን ያነለት መዋኛውን በሙሉ ርዝመቱ ሽኩቶ ሲያቁዋርጥና ሲዋኝ ያን መሰል የሌለው ውብ የጅ አጣጣሉን ቆመውም ተቀምጠውም ይመለከቱ የነበሩት ሁሉ ፈገግ ብለው ወደሱ እያዩ አድናቆታቸውንና

ፍቅራቸውን በልዩ ልዩ ምልክቶች ሲገልጹለት ከብዙ ጊዜ ጀምረው የሚያውቁትና የሚወዱት ይመስሉ ነበር።

«ወንዳንድ ወገን የ - ሚያዘነብኩሎ ባንድ እጅዎ ብቻ ስለ ደገፉዋቸው ነው አባባ! በሁለት እጆችዎ ቢደግፉዋቸው ወዳንድ ወገን አይገለበጡም። እሲ ይፍቀዱልኝና አንድ ጊዜ እኔ ላለማምዳቸው» አለ በሻህ አቶ ታችበሌ ምሽታቸውን ወደሚያስተምሩበት ቀረብ ብሎ ትንሽ ሲያይ ቆዬና። ከዚያ ባቶ ታችበሌ እግር ተተክቶ ወይዘሮ ኩሪባቸውን ባንድ እጁ ከታች ክፍል ሆዳቸወ ስር በሌላ እጁ ከታች ክፍል ደረታቸው ስር አስደግፎ በሁለት እጆቹ አመዛዝኖ ሲያንበለብላቸው (በሆዳቸው ሲያስተኛቸው) ግራና ቀኝ ወደፊትና ሁዋላ ማጋደላቸው ስለ ቀረ መባባታቸውም ቀረና ባልጋ ላይ እንደ ተኙ ሁሉ ዘና አሉ።

«እንግዲህ በሁለት እጆችዎ ውሀውን ውየቀዘፉ ከሱ ጋር አብረው ሁለት እግሮችዎንም ከውሀው ውስጥ ሳያወጡ ውሀው ውስጥ እንዳሉ እጥፍ ዘርጋ እያደረጉ፥ ውሀውን ወደ ሁዋላ ይግፉት» አለ እጆቹን ከስራችው እንዳነጠፈላቸው በጎናቸው ቀስ ብሎ እየሄደ። ነገር ግን ወይዘሮ ኩሪባቸው እንደ ነገራቸው እጆቻቸውንና እግሮቻቸውን እጥፍ ዘርጋ እያደረጉ ውሀውን ወደ ሁዋላ በሚገፉበት ጊዜ፥ እስበሳቸው ሁሉንም ትቶ እግሮቻቸው በሚሰሩት ላይ ስለሚያተኩር እጆቻቸውም የግሮቻቸውን ስራ መመልከት እንደሚፈልጉ ሁሉ መቅዘፋቸውን ረስተው ዝም ይላሉ። በጆቻቸውም መስራት እንዳለባቸው ያስታውሳቸውና በጆቻቸው መቅዘፍ ሲጀምሩ ደግሞ እግሮቻቸው እጆቻቸው የሚሰሩትን ማየት እንደሚፍልጉ ሁሉ ከውሀው ውስጥ ወጥተው ቀጥ ብለው ይቆማሉ። ስለዚህ፥ ቀስ እያለ መሄዱንም ትቶ ቆሞ አለና፥ በጆቹ ላይ እንድ ተንበለበሉ እዚያው ባሉበት እጆቻቸውንና እግሮቻቸውን ባንድነት አስተባብሮ ማሰራት ሲያለማምዳቸው ከቆዬ በሁዋላ ቀስ እያለ ሲሄድም በዚያው በለመዱት ቀጠሉ። ከዚያ እንዲያውም በጎናቸው እዬሄደ ቀስ አድርጎ እጆቹን ከስራቸው ገለል ሲያደርግም እጆቻቸውንና እግሮቻችወን አስተባብረው እያሰሩ ያለ ድጋፍ ላጫጭር ጊዜ ውሀው ላይ ለመቆየት ቻሉ። እንዲህ ያለ ድጋፍ ትንሽ ሄደው ሊጠልቁ ሲሉ ደገፍ ሲያደርጋቸው ቆይተው እዬተዝናኑ ሄደ ው ያለ ድጋፍ የሚዋኙበት ጊዜ ዘለግ ማለት ሲጀምር፥

«እንግዲህ ወጥተው ትንሽ ይረፉ እማማ፤ በጣም ጥሩ ነው፥ እንዲህ ያለም የለ! » ሲላቸው ወይዘሮ፥ ኩሪባቸው የዋና ሊቅ ሆነው እንደ ተመረቁ ሁሉ ደስታና ኩራት

ባንድነት ተሰምተዋቸው ፊታቸው በሙሉ በፈገግታ በራ። ከዚያ እሳቸውና ባላቸው ሊያርፉ ከመዋኛው ሲወጡ፥ እሱ ወደ ደመቀች ሄደ።

ደመቀች እንደ ነገራት ልብስዋን አውልቃ በዋና ልብስዋ ጸሀይ እዬሞቀች ካረገርጊው ሳንቃ ወደ ሰማይ ጉኖ ሲጠልቅና ሽኩቶ መዋኛውን በቁሙ ሲያቁዋርጥም ያን በተመልካቹ ሁሉ ዘንድ ያስወደደውን ጌጠኛ ዋና ሲዋኝ ቆይቶ፥ ወይዘሮ ኩሪባቸውን ዋና ሊያስተምር እዚያ ተቀምጣ እያዬች ቶሎ መጥቶ ዋና እንድትለማመድ እስኪጠይቃት በጣም ቸኩላ በጣም ናፍቃ ትጠብቀው ነበር።

«አሁንም እፍረትሽና ፍራትሽ - አብረውሽ አሉ? ትተውሽ አልሄዱም? » አለ በሻህ መጥቶ አጠገብዋ ሲቀመጥ።

«ገና አሁን ነውኮ የመጣን! እፍረትና ፍራት እንዲህ ባንድ ጊዜ ይተዋሉ! »

«ሰው የማያደርገውን ማድረግ ነው እንጂ የሚያሳፍርም የሚያስፈራም ሰው የሚያደርገውን ማድረግ ሊያሳፍርም ሊያስፈራም አይገባ ብዬ ነዋ! እዚህ እንደምታያቸው ወጣቶች ሴቶችም ትልልቅ ወይዘሮዎችም ልብሳቸውን አውልቀው ይዋኛሉ፤ ወይም - እንዲያ እዬተሮሩዋጡ ይጫወታሉ። ታዲያ - ይህን ሁሉ ሲያዩ እፍረቱም ፍራቱም አብረውሽ አይቆዩም፤ ባንድ ጊዜ ትተውሽ ይሄዳሉ መስሎኝ ነበር! » አለ ‹እንዲያ› ሲል እዬተሮሩዋጡ ወደሚጫወቱት ወጣቶች ሴቶ በጁ አመልክቶ።

«እነሱኮ የመጀመሪያቸው ቀን አደለም፤ ስለ ለመዱት ነው እፍረትም ፍራትን፣ የማይሰማቸው። እኔ ግን - ዛሬ መጀመሪያዬ ስለሆነ ነው መሰለኝ - እንጃ ፈራሁ! » አለች። ‹ከፈራሽ ተይው ይቅር› እንዳይላት ፈርታ እያመነታች። ታዲያ እንዲያባብላት ፈልጋ ነው እንጂ እፍረቱም ፍራቱም - ይልቁንም ወይዘሮ ኩሪባቸውን ካዬች በሁዋላ - ትተዋት ሄደዋል። ብቻ ልብዋ እዬወደደ ኩራትዋን ማሸነፍ አቃታት። በሻህ ስሜትዋ ከፊትዋ ከጠቅላላ ሁኔታዋ አነበበና፥

«የማለማምድሽኮ በጥልቁ ክፍል አደለም፤ በግር በሚያስቆመው ክፍል ነው። ስለዚህ - የምትጠልቂ መስሎ ስትፈሪ፥ እንኔ በጎንሽ ከመሆኔም ሌላ መሬቱ ለግርሽ ቅርብ ስለሆነ ቶሎ በግርሽ መቆም ትችያለና - እባክሽ እንሂድ» አለ አይን አይንዋን እያዬ።

«እሺ እንሂድ ልሞክረው» አለች፥ ስጋት ከልብዋ ሂዶ ደስታ ሲተካ በፊትዋ ወለል ብሎ እዬታዬ። እንደ ፈራችው ‹ከፈራሽ ተይው ይቅር› ቢላት ኖሮ እንዴት አንጀትዋ በተቆረጠ! ይቅርታ አታደርግለትም ነበር!

የደመቀች የዋና ልብስ በልከዋ ታይቶ የተገዛ ባለመሆኑ ያን ውብ ቅርጽዋን በሙሉ ውበቱ አያሳይም ነበር። ግን እንዲያም ሆኖ ካልተሸፈኑት አካላትዋ ጋር ባንድነት የተመልካችን አይን ትስብ ስለ ነበረ በሻህ አጅቦዋት ወደ መዋኛው ስትሄድ ፈገግ ብለው እስዋን እያዩና ያዩዋት ላላዩዋት እያሳዩ፥ ውበትዋን እያደነቁ የሚነጋገሩ ነበሩ።

እመዋኛው እንደ ደረሱ፥ እሱ ቀድሞ ገብቶ እስዋንም እጅዋን ይዞ እዬረዳ ካስገባት በሁዋላ ውሀው ከደረት በማያልፍበት ክፍል ቆመው፥ ልምምዱን በግብር ከመጀመራቸው በፊት፥ እሱም እስዋም የሚያደሩትን እዬመላለሰ በቃል ሲያስጠናት ቆዬ። ከዚያ ለወይዘሮ ኩሪባቸው እንዳደረገው በቆመበት እንዳለ እጆቹን ከስርዋ አንጥፎ በነሱ ላይ እንድንበለበልና ወደ ፊት ለመሄድ ሳትሞርክ እዚያው ባለችበት እጆችዋንም እግሮችዋንም ባንድ ላይ አስተባብረው ውሀውን እንድትቀዝፍ ይነግራት ጀመር። ነገር ግን እስዋ የምታዳምጥ ስለ ዋና የሚነግራትን ሳይሆን እንዲህ ደግፎዋት ከንብርትዋና ከደረትዋ ስር ያነጠፉቸው እጆቹ ከገላዋ ጋር ሲነካኩ አንድ እንግዳ ስሜት አንድ በሰራ አካላትዋ ተሰራጭቶ የሚያሞቅ ስሜት ተሰምቶዋት እሱን ታዳምጥ ስለ ነበረ፣ እመጀመሪያው ላይ ከተናገረው አንድ አልያዘችም። ብቻ እዬቆዬች የውስጥ ስሜትዋን መቆጣጠር ችላ የሚነግራትን ማዳመጥ ከጀመረች በሁዋላ እጆችዋንና እግሮችዋን አስተባብሮ ማሰራቱ የወይዘሮ ኩሪባቸውን ያክል አላስቸገራትም። ከስር በሁለት እጆቹ ደግፎዋት እንደ ቆመ እዚያው ባለችበት እጆችዋንና እግሮችዋን ባንድነት አስተባብራ ትቀፍ ጀመር። ከዚያ እዬሄዱ እጆቹን ከስርዋ ገለል ሲያደግ ትንሽ በትንሽ - መጀመሪያ ግማሽ ቀጥላ አንድ ሜትር ያክል ያለድጋፍ እስከ ሁለት ከዚያም እስከ ሶስት ሜትር ብቻዋን እዬዋኘች ደከም ብላ መጥለቅ ሲቃጣት ከስር በጆቹ ደገፍ እያደረጋት መዋኛውን በወርዱ ሁለት ጊዜ ካቋዋረጡ በሁዋላ፥

«እንግዲህ ላህንኑ ይበቃሻል እንውጣና እረፊ። ልካሰለቸሽ ሁዋላ እንደገና እንገባለን፤ አጀማመርሽ በጣም ጥሩ ነው። እዚህ አያያዝሽ የሁለት ቀን ልምምድ ብትጨምሪበት ያለ ረዳት ብቻሽን ይህን መዋኛ በቁሙ ማቋዋረጥ ትችያለሽ። ይህም - አምቦ በምትቆይባቸው ጥቂት ቀኖች ውስጥ ጥሩ ዋናተኛ ሆነሽ ትመለሻለሽ ማለት ነው» አለ ደግፎባቸው በነበሩት እጆቹ ቀስ አድርጎ በግርዋ ሲያቆማት አይኖችዋን ገደም አድርጎ እያዬ። አስተያየቱን ስታ ልብዋ ተሸበረባትና ቶሎ አንገትዋን ደፍታ ውሀውን

እያዬች ‹እሺ› አለች ከትንፋሽ የበለጠ በማይሰማ ዝቅተኛ ድምጽ። ከዚያ ወጥተው እመዋኛው ጠርዝ ላይ ጎን ለጎን ተቀምጠው ትንሽ እንደ ቆዩ፥

«እዚህ ወይም ልብሳችን ባለበት ሂደሽ ተኝተሽ ጸሀይ እይዬሞሽ እኪታርፊ እኔ ትንሽ ዋኝቼ ልምጣ» ብሎዋ ውሀው ውስጥ ገባ። እስዋም ተመልሶ መጥቶ ለልምምድ እስኪወስዳት ልብሳቸው ወዳለበት ከመሄድ እዚያው በተቀመጠችበት እንዳለች ሲዋኝ እዬተመለከተች ትጠብቅ ጀመር።

እዚያ ጥሩ ጥሩ ዋና አዋቂዎች ነበሩ። ነገር ግን በጅ አጣጣል እንኳዋንስ በሻህን የሚተካከል የሚቀርብ አንድ አልነበረም። እጅ አጣጣሉ ተመልካቹን ሁሉ ደስ አሰኝቶ ሳያስበው ያለ ውዱ ፈገግ እንዲል ያደርገዋል፤ የተመልካቹን ሁሉ ልብ ይማርካል። ውሀው ውስጥ እሱ ከመግባቱ በፊት እሱ ሲገባ አብረውት ገብተው የሚዋኙ ጥቂት ወንዶችም ሴቶችም ነበሩ። ብቻ የተመልካቹ አፍ ፈገግ ብሎ የሚነገር ስለሱ የተመልካቹ አይን አጅቦት በሄደበት የሚከተል እሱን ነበር።

እንዲያ በጅ አጣጣሉ ውበት የተማረከው ተመልካች ሁሉ በያፉ እያወደሰውና ባይኑ አጅቦ እዬተከተለው አንዳንድ ጊዜ በሆዱ ተንበልብሎ አንዳንድ ጊዜም በጀርባው ተንጋሎ፥ ደግሞ አንዳንድ ጊዜ በጎኑ ተጋድሞ እጅ እዬጣለ መዋኛውን በቁሞ ሶስት ጊዜ አቋዋረጠው። ከዚያ ወደ ደመቀች ከመመለሱ በፊት ትንሽ አርፎ ለመቀጠል ስላሰበ መጀመሪያ ዘልሎ ከሾኮተበት አጠገብ እመዋኛው ጠርዝ ላይ ወጥቶ ሲቀመጥ ሴቶችም ወንዶችም ወጣቶችም ቀርበው ለማነጋገር ምቹ አጋጣሚ ስላገኙ ከበውት ተቀምጠው የዋና ችሎታውን በተላይ እጅ አጣጣሉን እያደነቁ ሲያመሰግኑት ቆይተው፥

« ‹ጋሼ አንድ - ከባድ ሸክም ተሸክመህ እዬዋኘህ ከዚህ እዚያ ወዲያ ዳር ማሻገር ትችላለህ? » አለች ከበውት ከተቀመጡት ወጣቶ አንዱ፥ ‹ወዲያ ዳር› ሲል የመዋኛውን ዳር በቁሙ በጁ እያመለከተ።

« ‹ከባድ ሸክም› ማለት እንዴት ያለ ነው? » አለ በሻህ።

«ለምሳሌ - አንድ ሰው።»

«ጀርባዬ ለጭነቱ - ይበቃል ወይም አይመች እንደሆን እንጂ መቻልስ - ሁለት ሰዎችም ተሸክሜ ማሻገር በቻልሁ! » አለ በሻህ፥ ፍርጥም ብሎ።

«ግዴለም ይበቃል፥ ግዴለም ይመቻል» አሉ ወጣቶቹ፥ ባንድነት ተንጫጭተው። ደመቀች የተቀመጠችበት በሻህን የከበቡት ወጣቶች ከተቀመጡበት

ሩቅ ስለ ነበረ እጆቻቸውን ላይና ታች ወይም ጎንና ጎን እያነቃነቁ ሲንጫጩ ጫጫታቸውን ከመስማትና የጆቻቸውን ንቅናቄ ከማየት በቀር የሚናገሩት ምን እንደ ሆነ ለይታ መስማት አትችልም ነበር።

«በሉ እንግዲህ ሁለት ሆናችሁ ኑ» ብሎ በሻህ ቀድሞ ውሀው ውስጥ ሲገባ ከወጣቶቹ አንዱ ዘልሎ ገብቶ እበሻህ ጀርባ ላይ ከፍ ብሎ ተቀምጦ እንደሚታዘል ልጅ የበሻህን አንገት ከሁዋላው በሁለት እጆቹ ያዘ። ወዲያው ተከትላ አንድ ሴት ወጣት ዘልላ ገባችና እስዋም እንዲሁ እበሻህ ጀርባ ላይ ወጣች። ግን በሻህ እንዳለው ‹ጀርባው አልበቃ› ስላለ ተመቻችታ ለመቀመጥ የጉዋደኛዋን ወገብ ከሁዋላ ይዛ ወደ ላይ ስትስብ በሁለቱ ክብደት ላይ ደግሞ በላዩ እንዳሉ እስበሳቸው መጉዋተታቸው እጆቹንና እግሮቹን አስተባብሮ እንደ ልብ እንዳይሰራ ስላሰናከለው ይዞዋቸው ጠለቀ። ብቻ ጠልቆ አልቆዬም፤ ቶሎ በላዩ እንዳሉ ይዞዋቸው ወጥቶ ሁለት እግሮቹን በሀይል እያሰራ በሁለት እጆቹ እየቀዘፈ ሁለቱን ወጣቶች በላዩ ጭኖ እንደ ታንኩዋ ይንሳፈፍ ጀመር። ወዲያው እሱንና ባለዩ የተሳፈሩትን ወጣቶች እያዩ ይስቅ የነበረው ተመልካች ሁሉ ሳቁን ትቶ እጁን እያርገበገበ ይንጫጫ ጀመር። አንዳንድ ዋናተኞች እንዲያውም እዬዘለሉ ውሀው ውስጥ ገቡ።

መጀመሪያ በሻህ ሁዋላ ሁለቱ ወጣቶች ተከታትለው ውሀው ውስጥ ገብተው ወጣቶቹ ባንድነት እላዩ ወጥተው ሲያጠልቁት ራቅ ብላ እመዋኛው ጠርዝ ላይ ተቀምጣ ትመለከት የነበረች አንድ ሴት ዘልላ ውሀው ውስጥ ገባች። ዘልላ ስትገባ ልብ አድርጎ ያስተዋላት አልነበረም። የሁሉም አይን የሚመለከተው በሻህንና በላዩ የተሳፈሩትን ወጣቶች ነበር። ሁዋላ ብቻ እዬጠለቀች በወጣች ቁጥር ‹ድረሱልኝ› ለማለት እጆችዋን እያርገበገበች ቅብ ጥልቅ ብቅ ጥልቅ ስትል ከጣረሞት ጋር እዬተናነቀች ረዳት የምትጠራ መሆንዋን አንዳንድ ሰዎች አይተው ሲጮሁ የሁሉም አይን ወደስዋ ተመለሰና ጫጫታ ሽብር ሆነ። ያች ከጣእረ ሞት ጋር እዬተናነቀች ‹ድረሱልኝ› የምትል ሴት ደመቀች ነበረች!

በሻህ ተመልካቹ እዬተንጫጫ ወደሚመለከትበት አይኖቹን መለስ ከማድረጉ ደመቀችን ላንድ አፍታ ብቅ ብላ ስትጠልቅ አዬ። ወዲያው በቅጽበት ሁለቱን ወጣቶች ከጀርባው ወዲያ አራግፎ። እዬተምዘገዘገ ከጠለቀችበት ብቅ ስትል ከሌሎች ቀድሞ ደረሰላት። በትከሻው ተሸከሞዋት የቁም ዋና እዬዋኘ ጠሊቁን ክፍል አልፎ እግር በሚያስቆመው ክፍል ደረሰና እዬሮተ ይዞዋት ወጣ። ሰውነትዋ ሁሉ ተነፍቶ ትንፋሽ አጥታ አይኖችዋ ካፎታቸው ተጎልጉለው ወጥተው ፍጹም ሌላ ሆና ታስፈራ ነበር! ቶሎ

ከሆድዋ ከፍ ከራስዋ ዘቅዘቅ አድርጎ ይዞ ሲነቀንቃት ሊያጠልቃት ቁልቁል ከሚጎትታት ሰይጣናዊ እጅ ለማምለጥ ስትታገል ባዬር ፈንታ እዬሳበች አስገበው ውስጥዋን ሞልቶ ቆይቶ ባፍዋም ባፍንጫዋም እዬተቀዳ የወጣው ውሀ ከሩብ ባሊ አያንስም ነበር! ያ ትንፋሽ እስከታጣ ሞቶዋት የነበረው ውሀ እዬተቀዳ ወጥቶ ከፈሰሰ በሁዋላ ነፍስ ገዝታ እንደ ልብ መተንፈስ ስትችል አይኖችዋም የጥንት መጠናቸውን ይዘው ወደ ስፍራቸው ተመለሱ። ከመድከምዋ በቀር ተመልሳ ደመቀች ሆነች።

አቶ ታችበሌና ምሽታውም ሌሎች ከበው ይመለከቱ የነበሩትና በሻህን ለመርዳት በራስጌ - በግርጌ ይዋከቡ የነበሩት ወጣቶችም ያች ከሞት አፋፍ የተመለሰች ሴት አደጋው ከመድረሱ በፊት በሻህ ዋና ያስተምራት የነበረችቱ መሆንዋን አላስተዋሉም ነበር። እስዋ መሆንዋን ካስታወሱ በሁዋላ አንዳንዶቹ እንዲያ በመንገላታትዋ አዘናቸውን አንዳንዶቹ ከሞት በመትረፍዋ ደስታቸውን ሌሎች ዋና እንደማትችል እያወቀች እንዳዋቂ ዘልላ በሚያጠልቅ ውሀ ውስጥ በመግባትዋ ነቀፋቸውን እዬገለጹ እስበሳቸው ሲነገሩ ይሰሙ ነበር።

«አዩ -! ይችን የመስለች ልጅ ከፉኛ ተንገላታች! » አለ አንዱ ባጠገቡ ለቆመ ጉዋደኛው።

«ኧረ እንኩዋን እግዜር ከሞት አተረፋት እንጂ፥ መንገላታትዋስ ምንም አደል፤ ከቅድም አሁን እንኩዋ - እንዲያ ገርጥቶ የነበረው ፊትዋ ሲመለስ አታይም? » አለ ጉዋደኛው።

«እንደዚች ያለችዋን ምን ትያታለሽ? በሽተኛ አይሉዋት ጤነኛ! እስቲ - ዋና እንደማትችል እያወቀች ዘልላ በሚያጠልቅ ውሀ ውስጥ የምትገባ - ጤነኛ ትባላለች? ወይስ ምን? » ስትል አንድዋ ለጉዋደኛዋ ቀስ ብላ፥

«ምናልባት - ቂር -! » ኧልች ጉዋደኛ፤ ጠቁዋሚ ጣትዋን ከጆሮዋ ከፍ አድርጋ ራስዋ ላይ ተከላ፥ ቡሎን እንደምትፈታ ወደ ግራ እያዞረች። ‹አእምሮዋ ላልቶ ይሆናል› ማለትዋ ነው።

በሻህ ምንም እንኩዋ እሱም ሆነ ደመቀች የከበቡዋቸው ሰዎች ቀስ ብለው ይተቹት የነበረውን ባይሰሙ ደመቀች እንዲያ ተከባ እንደ ጉድ መታየትዋ ብቻ አሳፍሮዋት አይኖችዋን የምታሳርፍበት አጥታ ስትቸገር ተመልክቶ «እንግዲህ - እስቲ እንሂድ» አለ። እዚያ የነበሩት ሁሉ ያ አይነት አነገገር ‹እባካችሁ ወግዱልን› ማለት

መሆኑ ስለ ገባቸው መዋኘት የሚፈልጉት ለመዋኘት ጸሀይ መሞቅ የሚፈልጉት ጸሀይ ለመሞቅ ለዬብቻም በየጉዋዳቸውም እየሆኑ ሄዱ።

«አሁን ወደ ሆቴላችን ብንሄድ - ትችያለሽ? ወይስ ትንሽ አርፈሽ ትቆይ? » አለ የከበቡዋቸው ሰዎች ከሄዱ በሁዋላ አቶ ታችበሌ ጠርተው ወደ ማረፊያዋ እንዲወስዳት ነግረውት ተመልሶ ባጠገብዋ ሲቀመጥ።

«እሺ እንሂድ፤ እችላለሁ። አሁን ደህና ነኝ» አለች የፍረቱ ስሜት ገና ስላልለቀቃት፣ አይኖችዋ እሱን ፊት ለፊት ለማየት ድፍረት አንሰዋቸው እዬሸሹ። ከዚያ የዋና ልብስዋ ርጥብ ስለ ነበረ ኩታዋን ብቻ በላይ ደርባ ቀሚስዋን በፎጣ ጠቅልላ ይዛ በሻህም እንዲሁ ልብሱን ጠቅልሎ ይዞ በዋና ልብሱ ላይ ፎጣውን ለብሶ እዚያው አጠገብ ወደ ሆቴላቸው ሄዱ። እሱን የደረሰው አደጋ አፍዝዞት አደንዝዞት እስዋን አሳፍሮዋት ምንም ሳይነጋገሩ ዝም እንዳሉ ሆቴል ደረሱ።

«ይህ ርጥብ የዋና ልብስሽ በገላሽ ላይ ሳይቆይ ቶሎ ገብተሽ አውልቂና የደረቀ ልስብ ልበሽ፤ እኔም ልብስ ልለውጥና መጥቼ አይሻለሁ» ብሎዋት ወደዬክፍላቸው ገቡ።

እክፍሉ ገብቶ የዋና ልብሱን አውልቆ በቀዝቃዛ ውሀ ከተለቃለቀ በሁዋላ ሰአቱን ሲያይ አምስት ተኩል ሆኖዋል ከዚያ ወደ ደመቀች ክፍል ለመሄድ ቃጣና እንደገና እርምጃውን ገትቶ፥ ‹ምናልባት ተኝታ ማረፍ ትፈልግ ይሆን «እመጣለሁ» ብያት የል? አትተኛም› ብሎ ለጥያቄው መልሱን ራሱ ሰጥቶ ክፍሉን ቆፎ መንገዱን ቀጠለ። እስዋም እንዲሁ ገላዋን በንጹህ ውሀ ተለቃልቃ ልብስዋን ለውጣ፥ መከዳዋን ካልጋዋ ራስጌ አስጠግታ እሱን ተደግፋ ያነለት ጥዋት ሁለት ሰአት ባልሞላ አጭር ጊዜ ውስጥ የሆኑትን ብዙ ነገሮች አምጥታ ባይነ - ህሊናዋ ፊት በተራ አሰልፋ ስሜትዋ እዬተለዋወጠ፥ እንዲያ ከሚለዋወጠው ስሜትዋ ጋር አንዳንድ ጊዜ ፊትዋን ፈገግ አንዳንድ ጊዜም ፊትዋን ክርር ግንባርዋን ኩስትር እያደረገች፥ ትመለከት ጀመር።

በሻህ ልብሱን ውልቅልቅ አድርጎ ባጠገብዋ ጥሎ በዋና ልብሱ እፊትዋ ተንጠራርቶ ቆሞ፥ ያካላቱን ቅርጽ ያን እውነተኛ የወንድነት ውበት ሲያሳያት በሻህ ፊቱን ወደስዋ አዞሮ ‹ስገድላት› እንደ ተባለ ሁሉ በጁ መሬት እስኪነካ እያጎነበሰና ተመልሶ ወደ ሁዋላው እዬታጠፈ ብዙ ጊዜ በፊትዋ ደፋ ቀና ሲል በሻህ እንደ ኮርማ አንበሳ እዬተጎማለለ ከፊትዋ ወደ መዋኛው ሲሄድ በሻህ ከመዝለያው ሳንቃ ላይ እጆቹን አስቀድሞ እንደ ተወረወረ ጣምራ ጦር ውሀውን ከላይ ቀዶ ገብቶ ከታች ቀድዶ

ሲወጣ፥ ባሻህ ያን የሚያባብል ውብ እጅ አጣጣሉን መዋኛውን በሙሉ ርዝመቱ እዬተመላለሰ ሲዋኝ በሻህ ዋና ሊያስተምራት ከንብርት ዋና ከደረትዋ ስር በሁለት እጆቹ እቅፍ ድግፍ አድርጎ፥ እንደ ያዛት እሱ የሚያናገረውን እንዳትሰማ እስዋ የምታደርገውን እንድትረሳ አድርጎ ከተንበለበለችበት ግልብጥ ብላ አንገቱን እቅፍ አድርጋ እንድትስመው የሚገፋፋ ጽኑ አምሮት በውስጥዋ ተቀጣጥሎ ሲያሞቃት ሲያግላት፥ ያ ሁሉ በተራ ታያትና ያ ሁሉ ያን ጊዜ እዚያ አልጋዋ ላይ እንዳለች በትዝታ ሳይሆን በገሀድ እንደሚሆን ሁሉ አንድ ደስ የሚያሰኝ ሙቀት በሰራ አካላትዋ ስለ ተሰራጨ ደስ ብሎዋት መከዳዋን እድነ ተደገፈች አይኖችዋን ለበስ፥ ፊትዋን ፈገግ አድርጋ ዝም ብላ ትንሽ ቆዬች። ከዚያ ያ ውብ ትዝታ እንዲያ ልብዋን በደስታ ሲያዘምረው አልጋዋ ላይ ጋለል እንዳለች አይኖችዋን ለበስ አድርጋ ስታዳምጥ፥ የበሻህና ከበውት የተቀመጡት ወጣቶች ጠብ ስለ ታያት፥ አንድ ክፉ መንፈስ የሚጥም እልም ከምታይበት እንቅልፍዋ ውስጥ አስፈራርቶ እንደ ቀሰቀሳት ሁሉ ፈገግ ብሎ የነበረ ፊትዋን ክርር፥ ግንባርዋን ኩስትር አድርጋ ለበስ ብለው የነበሩ አይኖችዋን ገለጸች።

በሻህና ከበውት የተቀመጡት ወጣቶች የሚያጨቃጭቃቸው ምን እንደሆነ ባይሰማትም እጃቸውን እዬነቀነቁ ሲንጫጩ፥ ቆይተው፥ መጀመሪያ እሱ ቀጥለው ከወጣቶቹ ሁለቱ እዬዘለለ ውሀው ውስጥ ከገቡ በሁዋላ ሁለቱ ወጣቶች ተረዳድተው እሱን ብቻውን ይዘው ሲያጠልቁት ‹ገደሉት!› ብላ ልብዋ ተሸብሮ አእምሮዋ ተሰወረና የምታደርገውን ሳታውቅ አንድ ብርቱ ሀይል ከተቀመጠችበት አንስቶ ውሀው ውስጥ ወረወራት። ከዚያ በሁዋላ እንዴት ሆኖ ወጥቶ እስዋን ከሞት ሊያተርፋት እንደ ቻለ አልገባትም። ራስዋ ከጣረሞት ጋር ትንንቅ ገጥማ ስለ ነበረ፥ በሱና በጠላቶቹ መሀከል በተነሳው ጠብ ማን አሸናፊ ሆኖ እንደ ወጣ አላዬችም።

«እህ -! ወይ እናቴ የዳንግላይቱ! » አለች በዚያ አጭር ጊዜ ውስጥ ያ ሁሉ ብዙ ደስ የሚያሰኝና የሚያስፈራራ ነገር በተራ ተሰልፎ መጥጦ ባይነ - ህሊናዋ ፊት እያለፈ ሲሄድ ስትመለከት ቆዬችና። ከዚያ የበሩን መዝጊያ በለሰስታ ተመታ።

«ማነው? » አለች መከዳዋን ከተደገፈችበት ቀና ብላ። በሻህ መሆኑን አውቃለች።

«እባክሽ አትነሺ እዚያው ሁኚ። እይው ተቀመጥሁ» አለ ቶሎ ገብቶ ወንበሩን ወዳልጋው ቀረብ አድርጎ ሲቀመጥ።

«አሁን እንዴት ነሽ? ደህና ነሽ? » አለ ቀጠለና ነጠላ ጫማዋን አድርጋ በፊት ለፊቱ አልጋዋ ጠርዝ ላይ እንደ ተቀመጠች።

«አሁን በጣም ደህና ነኝ፥ አትስጋ ጋሼ። ያንጊዜ ነበር እንጂ ትንፋሽ ስላጣሁ የተጨነቅሁና - የደከመኝ - ያ ሁሉ እንስራ ሙሉ ውሀ ተቀድቶ ከወጣልኝ በሁዋላ ደህና ሆኛለሁ። አሁንማ ድካም እንኩዋ አይሰማኝም» አለች ፊት ለፊት እሱን ማየቱን አፍራ አይኖችዋን ማረፊያ ፍለጋ ወዲያ - ወዲህ እየሮጡ።

«ተመስገ - ን! እንኩዋን ደህና ሆንሽ! መቸም እስከ ዛሬ ድረስ አንዳንድ ያደረግሁት ነገር እንዳሰብሁት ሆኖ ሳይዋጣ ሲቀር ወይም ሲበላሽ ‹ምነው ባላደረግሁት› ብዬ - ሁልጊዜም እጸጸታለሁ። ነገር ግን - እንደ ዛሬ መጸጸት ብቻ ሳይሆን ራሴን ረግሜ አላውቅም! » አለ በሻህ ፍጹም ደህና መሆንዋን ስትነግረው አይኖቹን ወደ ሰማይ አንስቶ ምስጋናውን ካቀረበ በሁዋላ።

«ለምነው ራስህን የረገምኸው? »

« ‹መዋኘት አልፈልግም› ስትይኝ በግድ ለምኜ ወስጄ እንዲህ ያለ አደጋ ስለ ደረሰብሽ።»

«እኔ ደግሞ - ካስተማርኸኝ በሁዋላ ትንሽ ትንሽ ብቻየን መዋኘት ስለቻልሁ ‹ባንድ ቀን ዋና ላውቅ ነው› ብዬ፥ ‹እንኩዋን ስትጠይቀኝ እንቢ አላልሁ› ብዬ ደስ ብሎኝ ነበር።»

«ልክ ነው፤ አጀማመርሽ በጣም ጥሩ ነበረ፥ ዛሬ እስከ ምሳ ጊዜ ስትለማመጂ ብትቆይ ኖሮ ረዳት ጭረሽ ሳያስፈልግሽ ብቻሽን መዋኘት ትችዬ ነበር። ከዚያ ሁለት ሶስት ቀን ብትጨምሪበት ደግሞ ረዳት የማትፈልጊ ከመሆን አልፈሽ ‹ጥሩ ዋናተኞች› ከሚባሉት አንድዋ እንደምትሆኚ አይጠረጠርም። ብቻ - ለጊዜው ደህና አድርገሽ እስክትለምጅ ባጠገብሽ የሚጠብቅሽ ሰው ሳይኖር ብቻሽን መግባት ያው - እንዳየሽው አደገኛ ነው» አለ፥ ለምን ያለ ሰው ውሀው ውስጥ እንደ ገባች እንድትነግረው መንገዱ ለመክፈት። እስዋ ግን ምን ብላ እንደምትነግረው ጠፍቶዋት ዝም አለች።

«ለመሆኑ ቅድም - ያለ ጠባቂ እይገባሽ በሚያስቆመው ክፍል ሳልደግፍሽ ብቻሽን ትንሽ ውዲያና ወዲህ ስለ ተመላለስሽ ‹ከንግዲህ በቃ ረዳት አያስፈልገኝም አውቄያለሁ› ብለሽ ኖሮዋል? » አለ ቀጥሎ ከቅርታ ፈገግታ ጋር ከሱ የሚሸሹ አይኖችዋን ባይኖቹ ለመያዝ እዬተከተለ። ያለ ጠባቂ ውሀ ውስጥ የገባችበትን ምክናይት

እንድትነግረው የከፈተላትን መንገድ ተከትላ ስላልተናገረች በቀጥታ መጠየቅ የሚያስፈልግ መስሎ ታየው።

«አደለም» አለች አንገትዋን እንደ መድፋት አድርጋ የሚሸሹ አይኖችዋን መሬት ላይ አሳረፈችና።

«እንግዲያ እንዴት ነው? የገፉሽ ነበር? »

«አዎ» አለች ሁለቱ ወጣቶች ተጋግዘው ሲያጠልቁት ስታይ አንድ ልትቆቁዋመው ያልቻለች ብርቱ ሀይል ከውስጥዋ ተነስቶ፥ እንዴት ገፍቶ ውሀው ውስጥ እንደ ጣላት ስለ ታሰባት እሱን ባይነ - ህሊናዋ እያዬች ትንሽ ዝም ብላ ቆዬችና።

«ማነው እሱ? » አለ ሰው ገፉኝ ያለች መስሎት፥ በቅርታ ፈገግታ፥ ለስልሶ የነበረ ፊቱ ከመቅጽበት በቁጣ ክርር ብሎ። ደመቀች አንገትዋን ደፍታ አይኖችዋን እመሬቱ ላይ እንዳሳረፈች ስለ ነበረች የፊቱን መለዋወጥ አላዬችም።

«እንጃ፥ ስሙ - ምን እንደሚባል አላውቅም» ብላ ቀና፥ ስትል መቆጣቱን ከፊቱ አይታ ድንግጥ አለች።

«ስሙን ባታውቂው - መልኩን አታቂውም? ልታሳይኝ አትችይም? » አለ እንደ ትንታግ የቀሉ አይኖቹን በላይዋ ተከሎ።

« ‹ሰው ገፉኝ› ያልሁ መስሎህ ነው - የተቆጣህ? ሰው አልገፉኝምኮ ጋሼ። አንድ - ስሙ ይህ ነው ልለው የማልችል ስሜት ገፍቶ ውሀ ውስጥ ጣለኝ ማለቴ ነው እንጂ - ‹ሰው ገፉኝ› ማለቴ አደለም።»

«እ -! እንዴት ያለ ስሜት ነው ‹ወደ ሞት ሂጂ› ብሎ የገፉሽ? እስቲ - እንዴት እንደ ተሰማሽ ንገሪኝና፥ ስም አገኝለት እንደ ሆነ እኔ ልፈልግለት» አለ ቁጣው መለስ ብሎ እንደገና የቅርታ ፈገግታ በፊቱ እዬታዬ። ደመቀች አልመለሰችም እንደገና አንገትዋን ደፍታ መሬቱን እያዬች ዝም አለች።

«በይ ንገሪኝ እንጂ? »

«ስሙን የማላውቀው ነገር - ምን ብዬ ልንገርህ? »

«እንዴት ያለ ስሜት እንደ ተሰማሽ ንገሪኝና ‹ስም ልስጠው› አልሁሽኮ! »

«እንጃ፤ እንዴት አድርጌ እንደምነግርህ አላውቅም» አለችና የተሰማትን ስሜት እስከ ምክንያቱ ለመናገር የምትጀምርበት አጥታ መሬቱን እያዬች ስትፈልግ ቆይታ፥

«ዋኘተህ ወጥተህ እዳር እንደ ተቀመጥህ - በርከት ያሉ ወንዶችና ሴቶች ወጣቶች መጥተውው ከበውህ መቀመጣቸውንና ስትነጋገሩ ቆይታችሁ መጣላታችሁን ታስታውሳለህ? » አለች፥ መሬቱን ከምታይበት ወደሱ ቀና ብላ።

«ዋኘቼ ወጥቼ እዳር ስቀመጥ አሁን እንዳልሽው ወጥቶች መጥተው ከነሱ ጋር ስንነጋገር መቆዬታችነን አስታውሳለሁ። ነገር ግን - አልተጣላንምኮ! »

«እንዴት አልተጣላችሁም! ሁላችሁም እጃችሁን እዬነቀነቃችሁ ስትጨቃጨቁ ቆይታችሁ - በሁዋላ አንተና ከነሱ መሀከል ሁለቱ እዬዘለላችሁ ውሀው ውስጥ ገብታችሁ ተረዳድተው አላጠለቁህም? »

«እርግጥ እዳር ተቀምጠን ስንነጋገር ከቆዬን በሁዋላ ውሀው ውስጥ ገብተን - ሁለት ሆነው አጥልቀውኛል፤ ነገር ግን ተጣልተን አደለምኮ፥ የኔ እመቤት! »

«ታዲያ - ያ ሁሉ እጅ እዬነቀነቁ ሲጨቃጨቁ መቆዬትና ከዚያ በሁዋላ ውሀ ውስጥ ገብቶ መጥለቅ - ጥል ካልሆነ ምን ይባላል? አልገባኝም! » አለች፥ እውነትም ግራ እንደ መግባት ብሎዋት።

«እጃችነን እዬተነቀንቀን መጨቃጨቃችን እንኩዋ - ትዝ አይለኝም። ብቻ ወጣቶች በርከት ያሉ ስለ ነበሩና ሁሉም ባንድ ላይ ይናገሩ ስለ ነበሩ እንጃ ምናልባት ከሩቅ ለሚለይ የተጨቃጨቅን መስለን እንታይ ኖሮ ይሆናል። የሆነ ሆኖ ነገሩ እንዲህ ነው።

«ስለ ዋና ስንነጋገር ከመሀከላቸው አንዱ፥ ‹አንድ ሰው ተሸክመህ ሳትጠልቅ፣ መዋኛውን በቁሙ ማቁዋረጥ ትችላለህ ወይ?› ብሎ ስለ ጠዬቀኝ፥ ‹እንዲያው ሁለት ሰዎች ተሸክሜ ማቁዋረጥ እችላለሁ› አልሁት። ታዲያ፥ ያን ለማስከበር ነበር እኔና ሁለቱ ወጣቶች ተከታትለን የገባን። ሁዋላ ባንድ ላይ በጀርባዬ መቀመጥ አልመቻቸው ብሎ እስበሳቸው ሲታገሉ አንድ ጊዜ አጠለቁኝ ነገር ግን ቶሎ ይዣቸው ወጥቼ ጉዞየን ጀምሬ ነበር።

«እኔ መቸም ሩቅ ስለ ነበርሁ ምን፥ ትነጋገሩ እንደ ነበረ ለይቼ መስማት አልቻልሁም። ብቻ እንዲሁ - እጃችሁን እዬነቀነቃችሁ ስትጨቃጨቁ ቆይታችሁ

ውሀው ውስጥ እዬዘለላችሁ ስትገቡና ሁለቱ ባንድነት ሆነው ሲያጠልቁህ ሳይ፥ ተጣልታችሁ ለመጣለቅ ተፈካከራችሁ የገባችሁ - መሰለኝ» አለችና መልሳ አንገትዋን ደፋች።

«ታዲያ - የተጣላን ቢመስልሽስ - ዋና እንደማትችይ እያወቅሽ እጥልቅ ውሀ ውስጥ ዘለሽ የገባሽ ለምነው? » አለ ነገሩ እዬገባው ሲሄድ የስሜቱን መታወክ ከፊቱ እዬታዬ።

«እንጃ ምክንያቱን አላወቅሁትም» አለች አንገትዋን እንደ ደፋች።

«እባክሽ ንገሪኝ የኔ እመቤት» አለ በሻከረው ድምጹ ነገሩን ቢገባው እስከ መጨረሻው ከስዋ አፍ ለመስማት ስለ ፈለገ፥ ደመቀች ሳትመልስለት መሬቱን እያዬች ዘለግ ያለ ጊዜ ቆዬችና፥

«ሁለት ሆነው ሲያጠልቁህ ሳይ የማይለቁህ፥ የ - ሚገሉህ መሰለኝና - በጣም ፈራሁ። እንጃ፤ ዋና የማላውቅ መሆኔንም - ረስቸው ነበር» አለች ለራስዋ እንደምትናገር ሁሉ በጣም በዝቅተኛ ድምጽ።

የተናገረችውን ሲሰማ ያልተናገረችው ክፍል ለሱ ያላት ፍቅር እጅግ ሀያል መሆኑ ለሱ ያላት ፍቅር ዋና የማታውቅ መሆንዋን አስረስቶ ሞትን አስረስቶ እጥልቅ ውሀ ውስጥ ዘልላ እንድትገባ የሚያደርግ መሆኑ ያ ሁሉ የታየውና ልቡ በሀይል ስለ ተመታ ልቅሶ መጥቶበት መናገር፥ አቅቶት ምራቁን እዬመላለሰ እዬዋጠ ዝም ብሎ ቆዬ። አይኖቹ ትኩስ እንባ ሞልተው ነበር!

«እና - እኔን ለመርዳት ኖሮዋል፤ ዋና የማታውቂ መሆንሽን ረስተሽ - በሚያጠልቅ ውሀ ውስጥ ገብተሽ ልትሞች፥ ው - ውሀ በልቶሽ ልቅተሪ የነበር! » አለ ከሳግ ጋር በተደባለቀ ጎርናና ድምጽ። አልተመለሰችለትም፤ አንገትዋን ደፍታ እንደ ተቀመጠች ዝም አለች።

«ደመቁ» አለ ሁለቱም ላጭር ጊዜ ዝም ብለው ከቆዩ በሁዋላ። ‹አቤት› በማለት ፈንታ ዝም እንዳለች ቀና ስትል አይኖቹን እንባ ሞልተው አዬችና ወዲያው የስዋም አይኖች እንባ ሞልተው ከንፈሮችዋና ጉንጮችዋ እዬተንቀጠቀጡ ዝም ባል ትመለከተው ጀመር።

«እና - ይህን ያክል - ትወጅኛለሽ ማለት ነው? » አለ በዚያው በጎረነነ ድምጽ። መልስ ሳትሰጠው እንዲያ ከንፈሮችዋና ጉንጮችዋን እዬተንቀጠቀጡ እንባ የሞሉ አይኖቹን እንባ የሞሉ አይኖቹን እንባ በሞሉ አይኖችዋ ስታይ ቆይታ፥

«እወ - እወድሀለሁ ጋሼ» አለች በደካማ ድምጽ ያን አንድ ቃል መናገር የውሎ መንገድ ያክል ያደከም ይመስል እያረፈች። ከዚያ አመታት ሸሽጋ የኖረችው ምስጢርዋ አምልጦዋት ከወጣ በሁዋላ መመለስ ትችል ይመስል ደንግጣ ደመነፍስዋን አፍዋን ልታፍን ስልት ቶሎ እጆችዋን ያዘና ስቦ እቅፉ ላይ ጣላት። ወዲያው ለረዥም ጊዜ ሲነፋፈቁ የኖሩት ከንፈሮቻቸው ሮጠው ተገናኝተው ያኑ ያክል ተያይዘው የናፍቆት ሰላምታቸውን የፍቅር ሰላምታቸውን ሲለዋወጡ ቆይተው መቸ እንዴት ከወንበሩ ሰላምታቸውን ሲለዋወጡ ቆይተው መቸ እንዴት ከወንበሩ ተነስተው እንደ ሄዱ ሳይታወቃቸው ተቃቅፈው አልጋ ውስጥ መሆናቸው ያወቁ ሁዋላ በጣም ሁዋላ ፍቅራቸው ይዞዋቸው ከሄደበት ሌላ አለም ተመልሰው መጥተው ካረፉ በሁዋላ ነበር!

‹አምባው ተሰበረ አምባው ተሰበረ፥

‹እንድነእ ሙተራ እንደነ ጅበላ፥ ይፈር የነበረ፥

‹አምባው ተሰበረ አምባው ተሰበረ› በጎጃም ድንግልና ሲገሰስ ወይም ህግ ሲደርስ የሚዘፈን ዘፈን ነው።

ሙተራና ጅበላ የሚፈሩ፥ የማይበገሩ ብርቱ አምባዎች መሆናቸው የታወቀ ነው። ከኒህ አምባዎች አንዱ ጅበላ አጼ ዮሀንስ ሙሉ ሰራዊታቸውን ይዘው ሊሰብሩት ያልቻሉ ነው። ታሪክ ነጋሪዎች እንደሚተርኩት በአጼ ዮሐንስ ዘመነ መንግስት የሸዋው ንጉስ ምኒልክና የጎጃሙ ንጉስ ተክለ ሀይማኖት ንጉሰ ነገስቱን አጼ ዮሀንስን ለመቃወም ተመካክረው አሴ ዮሀንስ በሸዋ ላይ የዘመቱ እንደሆነ ንጉስ ተክለ ሃይማኖት ለርዳታ ሊደርሱ በጎጃም ላይ የዘመቱ እንደሆነ ንጉስ ምኒልክ ለርዳታ ሊደርሱ ይስማማሉ። ንጉሰ ነገስቱ አድማውን ሲሰሙ ምንም እንኩዋ ደርቡሽን ሊወጉ ወደ መተማ ለመዝመት ቢነሱ ካድመኞቹ አንዱን ንጉስ ተክለ ሀይማኖት ቀጥተው ለመሄድ ወደ ጎጃም ይገሰግሳሉ። ንጉሰ ተክለ ሀይማኖትም ንጉስ ምኒልክ እንደ ተስማሙት ለርዳታ ሊደርሱ ይስማማሉ። ንጉሰ ነገስቱ አድማውን ሲሰሙ ምንም እንኩዋ ደርቡሽን ሊወጉ ወደ መተማ ለመዝመት ቢነሱ ካድመኞቹ አንዱን ንጉስ ተክለ ሀይማኖትን ቀጥተው ለመሄድ ወደ ጎጃም ይገሰግሳሉ። ንጉስ ተክለ ሀይማኖትም ንጉስ ምኒልክ እንደ ተስማሙት ለርዳታ የማይደርሱላቸው መሆናቸውን ሲያውቁ ጅበላ አምባችወ ገብተው፥ ቁጭ! ከዚያ አጼ ዮሀንስ ጅበላን ከብበው ለመስበር ቢሞክሩ ዙሪያውን

እዬተጠመዱ የተቀመጡ ‹እነገብርኤል፥ እነሚካኤል፥ ወዘተ› እየተባሉ የቁዋጥኝ ናዳዎች ከላይ እዬተለቀቁ ብዙ ሰው ስለፈጁባቸውና ጅበላን መስበር የማይቻል መሆኑን ሲረዱ ከበባውን አንስተው በዚያ ቁጭት ጎጃምን አስዘርፈው ህዝቡን ከፉኛ በድለው ወደ መተማ ጉዞዋቸውን ይቀጥላሉ። ንጉስ ተክለ ሀይማኖትም ከበባው ዙሪያቸውን መሬት ሳይለቁ ከጅበላ ወርደው አጼ ዮሀንስ ገና የጎጃምን መሬት ሳይለቁ ቢደርሱባቸውና ምህረት እንዲያደርጉላቸው ለምነው ሁለት ተደራርቀው ንጉሰ ነገስቱ መተማ ይዘምታሉ። ነገር ግን የጎጃም ህዝብ ‹ይቅር› ሳይላቸው እንዳቄመባቸው ነበር የዘመቱ። አጼ ዮሀንስ መተማ በጦርነቱ፥ ውስጥ መሞታቸውን ሲሰማ፥ ንጉስ ተክለ ሃያኖት አጎበር ያስተክሉና እዚያ ውስጥ የንጉሰ ነገስቱን ምስል ያስቀምጡና የጎጃምን ህዝብ ‹ከተት› ብለው እንዲያለቅስ ያዝዙታል! ከዚያ መቸም ታዝዞ የሚያለቅስ አስለቃሽ ስለሚያስፈልገው አንድ አስለቃሽ ትመጣና፥

«ሲገዙ እንዳልኖሩ፥ እንዳልበሉ ሁላ፥

ለተባይ ሰጥተውን ዳርገውን ለተኲላ፥

ወጥተው ሲቀመጡ ንጉሱ ጀበላ

በጃችን ሳይጠጣ፥ በጃችን ሳይበላ

ደም መላሽ ሆነን መሀመድ አብደላ።

ዘሩን ይባረክለት የሚያምንበት አላ»

ስትል ንጉሱ ተቆጥተው እንድትያዝ ያደርጉና፥ ልቅሶው እንዲቀጥል ያዝዛሉ። ከዚያ ሁለተኛይቱ አስለቃሽ ትነሳና፥

«ደህና ተሰናድቶዋል ተጠርጎዋል መንገዱ፥

«አጼ በሄዱበት ንጉሱም ይሄዱ! » ስትል ለልቅሶ የከተተው ህዝብ፥ በማልቀስ ፈንታ በሳቅ ያወካል! ንጉሱ የሚያደጉትን አጥተው፥ «የተያዘችውን አስለቃሽ ልቀቁ» ብለው ልቅሶውን ፈትተው ተነሱ ይባላል።

እና - ድንግልናን መግሰስ የንጉስ ሰራዊት የማይበግራቸውን ሙተራንና ጅበላን እንደ መስበር ይቆጠራል ማለት ነው! ደመቀች ድንግል ባትሆንም በልጅነትዋ አግብታ በደረሰባት ክፉ አጋጣሚ ምክንያት ለግብረ ስጋ ግንኙነት ይሁን ለጋብቻ የከጀሉዋትን ወንዶች ሁሉ እንዳራስ ነብር አጠገብዋ ሳታስደርስ አርቃ እንደ ድንግሎች ተጠብቃ

ብዙ አመታት የኖረች ነበረች። ስለዚህ ያ ቀን በወንድ ጎን የሴት ቦታዋን ይዞ ደንበኛ የሴትነት ኑሮዋን ለመኖር የጀመረችበት ስለ ነበረ ድንግልናዋ የተገሰሰበት እለት እንደሆነ ተቆጥሮ ዘፋኝ አለእምኖሩ ነው እንጂ - ‹አምባው ተሰበረ› የሚዘፈንበት ነበር!

በሻህና ደመቀች ያነለት ምሳ አልበሉም፤ አልጋቸው ውስጥ እንደ ተኙ ዋሉ። ብዙ አመታት ተደብቆ ታምቆ የኖረ ፍቅር ብዙ አመታት ሲርብ የኖረ ፍቅር ባንድ ቀን ይጠገባል? የስበሳቸው ፍቅር በዬልባቸው ከተጸነሰ ጀምሮ እስከ ያነለት ድረስ በዬጊዜውና በዬምክንያቱ ሲለዋወጥባቸው የኖሩትን መልካምና ክፉ ስሜቶች ማለት ደስታውንና ቅርታውን ተስፋ ማድረጉንና ተስፋ መቁረጡን ቁጣውንና መልሶ ‹ይቅር› መልቱን ያን ሁሉ እስዋ ለሱ እሱ ለስዋ እዬተናዘዙ ፈጣሪ፥ በውነተኛ ፍቅር ለተጣመሩ ወንዶችና ሴቶች ብቻ ቆጥቦ በሚያድለው ደስታ ሲደሰቱ ውለው ቀኑ አልፎ የራት ጊዜ እምድረሱን ሲያዩ ለብሰው ለራታቸው ወጡ።

አምቦ ቅዳሜና እሁድን ብቻ ሳይሆን ሰኞን ጭምር አሳልፈው ማክሰኞ ወዳዲስ አበባ ተመለሱ። ተኮራርፈው ሳለ፥ ‹ለምን አምቦ መጣን?› እንዳላሉ ሁሉ አምቦን በመልቀቃቸው ቅር እያላቸው ነበር የተዉት። በተለይ ደመቀች ዋና ብቻ ሳይሆን የወንድ ግንኙነት ፈርቶ የሚሸሹትና ጠልቶ የሚርቁት አለመሆኑን በጣም የሚወደድ መሆኑን የወንድ ፍቅር ይልቁንም ‹የሚወዱት ወንድ ፍቅር› ማለት ትርጉሙ ምን መሆኑን ተምራ ያወቀችበት ስለሆነ ያነለት አምቦን ለቅቃ ስትሄድ በጣም ቅር ያላት ከመሆንዋ ብሌላ ከዚያ በሁዋላ ያምቦ ስም ሲጠራ ያን ሁሉ እያሳሰባት ትወደው ነበር። ወደ አዲስ አበባ እንደ ተመለሱ አዝማሪው ውቤን አቶ ማንደፍሮንና አቶ ታችበሌን ውል ሰሚዎች አድርገው የጋብቻ ውላቸውን ማዘጋጃ ቤት አስመዝግበው እንዲጋቡ ተስማሙ።

አዲስ አበባ እንደ ደረሱ፥ በሻህ ደስታውን ሊያበስረውና በቀጠሮው ያልተገኘበት ምክንያት ሊጠይቀው ወዳዝማሪው ውቤ ቤት ሄደው አጎት ሞተው በሀዘን ተቀምጦ አገኘው። ወዳምቦ ለመሄድ ተቃጥረው በተለያዩበት ማታ አዝማሪው ምሽቱ እቤታቸው ሲደርሱ ታመው የሰነበቱት ያዝማሪው ውቤ አጎት በጣር ውስጥ መሆናቸውን ስለ ሰሙ ወደ በሽተኛው ቤት ሄዱ። እዚያ ሲጠባበቁ አድረው በሽተኛው እንጋት ላይ በማረፋቸው በዚያ ተደናግጠው መላክተኛ ወደሱ ለመላክ እንኳዋ ሳይችሉ መቅረታቸውን ሲነግሩት በሻህ አዝኖ ለጥቂት ቀናት እዚያው ሲያስተዛዝንና ልቅሶ ደራሾችን ሲያስተናብር ሰነበተ። ከውልና ከሌላው የጋብቻ ሥነ ሥራት ሁሉ በፊት እሱና ደመቀች አምቦ ተጋብተው መሰንበቻውን ላዝማሪው ሲነግረው አዝማሪውን በጣም ደስ ብሎት ትልቅ ውለታ እንደ ዋለለት ሁሉ አንገቱን አቅፎ ሳመው።

# ምእራፍ ሰላሳ ስድስት

## ያመነው ለጠላው መድሀኒትም የለው

አዛዥ ተካልኝ እድሜያቸው ከሰባ አምስት አመት ካለፈ በሁዋላ መርሳት፥ ማብዛታቸውንና ጉልበታቸው እየደከመ መሄዱን ጌታቸው ደጃዝማች አሰፋ ተመልከተው አምሳ ብር የወር ደመወዛቸውንም እዳ ውስጥ በርስትነት የሰጡዋቸውን አንድ ጋሻ መሬትም እንደ ያዙ፥ እንዲያርፉ አድርገው ባዛዥነት ስራቸው ሌላ ወጣትነት ያለው ሰው ስለ ሾሙ፥ በጣም መሪር ሀዘን ተሰማቸው።

ደጃዝማች ብዙ ዘመን ሲያገለግሉዋቸው ኖረው ከሽመገሉ አሽከሮቻቸው እንደዬማእረጋቸው አንድ ጋሻም፣ እኩል ጋሻም ሩብ ጋሻም መሬት በርስትነት እዬሰጡ ያሰናበቱዋቸው ጥቂት ሰዎች ነበሩ። ነገር ግን አንድ ጋሻ መሬት ከሙሉ ደመወዝ ጋር ሰጥተው እንዲያርፍ ያደረጉት ካዛዥ ተካልኝ በቀር አንድ እንኩዋ አልነበረም። አዛዥ ተካልኝ ደጃዝማች አሰፋን ሰላሳ አምስት አመት ባዛዥነት ሲያገልግሉ እንኩዋንስ፥ ልግም እረፍት ያልነበራቸው ነፍስና ስጋቸውን በሙሉ ለጌታቸው አገልግሎት ሰጥተው የኖሩ ነበሩ። ለጌታቸው የነበራቸው ፍቅር ሆነ ታማኝነት መሰል አልነበረውም። አዛዥ ‹እርም ነው፤ የምወደውን ጌታዬን ያሰፋን ስጋ!› ካሉ የመጨረሻ አቡን የማይፈቱት መሀላ ነበር! ደጃዝማችም ይህን ሁሉ ደህና አድርገው ስለሚያውቁና በበኩላቸው አዛዥን አጥብቀው በመውደዳቸው ነበር ለማንም ለስጋ ዘመዶቻቸው እንኩዋ ያላደረጉትን ለሳቸው ማድረጋቸው። ነገር ግን አዛዥ ያን ለማንም ሳይደረግ ለሳቸው ብቻ የተደረገውን ከጥቅሙም ሌላ የፍቅርና ያክብሮት ምልክት የሆነ ልዩ ስጦታ ጭራሽ ከቁም ነገር አልጣፉትም። ላዛዥ ተካልኝ አዛዥነቱ እንኩዋንስ ላንድ ጋሻ መሬትና ላምሳ ብር የወር ገቢ፥ ከዚያ በላይ ለሆነ ነገርዎ የሚለውጥ አልነበረም! ያንጊዜ አዛዥነቱን ብቻውን ካንድ ወገን ጋሻ መሬቱን ካምሳ ብር የወር ገቢ ከሌላ ወገን ደልድለው፥ ‹ይምረጡ› ብልዋቸው ያለ ጥርጥር ‹እልል› እያሉ፥ አዛዥነቱን ያላንዳች ተጫማሪ ነገር በመረጡ ነበር።

ላዛዥ ተካልኝ አዛዥነት ለመኖር የሚያስችል ስራ ለመኖር የሚያገልግል መሳሪያ ሳይሆን በረዥም ጊዜ ልማድ ራሱ ኑሮ ራሱ ህይወት ኖኦር ይታያቸው ስለ ነበረ፥ ሲወሰድባቸው ‹ከንግዲህ አይኖሩም፥ ከንግዲህ የሉም› እንደ ተባሉ ሁሉ ከማዘንም

አልፈው፥ ግራ ገባቸው! እውነትም ‹አለሁ› ሲሉ እያሉ፥ የራሱን አለመኖር መርዶ መስማት ግራ የሚያጋባ አደለም?

አዛዥ በመሸምገላቸው ምክንያት በመዘንጋትም አቅም በማነስም የሚጎድለውን ስራና እሱም የሚያስከትለው ጉዳት እዬበዛ መሄዱን የሚያውቁት ደጃዝማች አሰፋና ባልተቤታቸው ወይዘሮ ጽጌ ቢሆኑም ላዛዥ ተካልኝ አንዳች የጎደለ ነገር ያለ መስሎ ታይቶዋቸው አያውቅም ነበር። በሳቸው አስተያየት ያንጊዜም እንደ ፊቱ ሁልጊዜው፥ ማልደው ተነስተው ጾም ካልሆነ እንጀራ ባዋዜያቸውንና ቡና በጨዋቸውን ቀምሰው እጌታቸው ግቢ እስኪደርሱ መቸኮላቸው ያልቀረ ከሆነ ያንጊዜም እንደ ሁልጊዜው ጌታቸው ሳይነሱ እግቢ ደርሰው ‹ስራየቤቱ› - ወንዱም ሴቱም - በለት ስራው መስማራቱን አይተው ያልተሰማራ ቢኖር አሰማርተው የተጋውን መርቀው የለገመውን ወቅሰው አጥፊውን ገስጠው በተግሳጥ የማይመለሰውን ቀጥተው የሚጣሉትን እንደ ሽማግሌ በምክር አስማምተው ባይስማሙ እንደ ዳኛ በፍርድ ለይተው ይህን ሁሉ ያን ጊዜም እንደ ሁልጊዜው ማድረጋቸው ያልቀረ ከሆነ ከዚህ ሁሉ የስራ ጉዳይም ሆነ ‹የስራ ቤቶች› ጭቅጭቅ እሳቸውን አልፎ ወይም እሳቸው ሳይፈጽሙት ቀርተው ከደጃዝማች ፊት ቀርቦ የሚያውቅ የሌለ ከሆነ ይህን ሁሉ ያን ጊዜም እንደ ፊቱ ማድረጋቸው ያልቀረ ከሆነ ይህ ሁሉ ያሉ መሆናቸውን እያረጋገጠ እንደሌሉ ተቆጥረው አዛዥነቱ ስሌላ ሰው መሰጠቱ ከማሳዘኑም አልፎ በጣም ነበር ግራ የገባቸው።

አዛዥ ተካልኝ በሙሉ ቤት አዛዥነታቸው እና ነገር እንዳይጎድል ባሳብም ሆነ በስራት እረፍት ሳያምራቸው ሲደከሙ ይኖሩ የነበረ ርስቱና የወር ደመወዙ እንዳይወሰድባቸው ወይም፥ ጌታቸው እንዲወዱዋቸው አልነበረም። የለም። ደመወዙንም ሆነ ርስቱን ላገልግሎታቸው ዋጋ ሳይሆን ጌታቸው እንዲያው በደግነታቸው እንደ ሰጡዋቸው ሲያመሰግኑ የሚኖሩበት የተለዬ ነገር ነበር። ሙሉ ቤት አዛዥነቱን ግን በደጃዝማች አሰፋ ሀብትና ብዙ ስራ የቤት ላይ ሙሉ ስልጣን ሰጥቶ፥ ዘመን እንዲያዝዙና እንዲገዙ አድርጎዋቸው ይኖሩ ስለ ነበረ፥ እንዲያ ያለውን የስልጣን ምንጭ እንዲሁ በስልጣን ምንጭነቱ ይወዱት ነበር እንጂ በዋጋ የሚገመት፥ በዋጋ ቤት ገብቶ የሚተመን አድርገው አይተውት አያውቁም ነበር።

አዛዥ ተካልኝ እውነተኛ ቅን ለስራውም ሆነ፥ ለሰራተኞች ጠንቃቃ መሪና አስተዳዳሪ በዚያ ላይ ጌታቸው ታማኝ በመሆናቸው ደጃዝማችም ይህን ሁሉ ተረድተው ሙሉ ስልጣን ስለ ሰጡዋቸው እቤት ውስጥ በሚገኘው ሀብት ሆነ በስራውና በስራተኞች ላይ ፈላጭ ቆራጭ እሳቸው ነበሩ። እሳቸው የወሰኑት ወደ ደጃዝማች ሄዶ አያውቅም፤ የመጨረሻ ነበር። ስለዚህ ‹ይህን ስሩ ያን አፍርሱ፥ ይህን

ጣሉ ያን አንሱ ይህን ውሰዱ ያን አምጡ፥ ይህን ብሉ ጠጡ ያን አስቀምጡ› ብለው እንደ መሰላቸው እንደ ልባቸው ሲያዝዙ ትእዛዛቸውን እንኳዋንስ የሚሸር ‹ለምን?› ብሎ የሚጠይቅ አልነበረባቸውም! ከሰራተኞች መሀከል ጥፋተኞችን የሚበዛውን ጊዜ እንደ ሁኔታው መክረውም ገስጠውም ያልፉዋቸዋል። ጥፋታቸው በምክርና በተግሳጥ የማይታለፍ ወይም የተደጋገመ ከሆነ ግን በስራትም ሆነ በሌላ ቅጣ ይቀጡዋቸዋል።

ብቻ፥ የተቀጡት ጥፋተኞች ጥፋታቸውን ተረድተው ይቅርታ እንዲያደርጉላቸው አማላጆች የላኩ እንደሆነ የተላኩትን አማላጆች ገፍተው አያውቁም። ስለዚህ የቤቱ ሰው ሁሉ - ወንዱም ሴቱም - ‹አይጠና ሆዱ› ብሎ ቅጽል ስም አውጥቶላቸው ነበር። ‹አይጠና ሆዱ› ጥፋተኞችን ሁሉ እንደ እግዜር ያልድልዎ የሚገስጡ የሚቀጡ ጥፋታቸውን ተረድተው ንስሀ ሲገቡ ራርተው ይቅርታ የሚያደርጉ ስለ ነበሩ ጥፋታቸውን ተረድተው ይቅርታ ባለመለመናቸው ቅጣቱ ከሚፈጸምባቸው በቀር፥ ከቤቱ ሰው በጣም የሚበዛው የሚወዳቸው እንደ አባት እንጂ እንደ አዛዥ የማያያቸው ነበሩ። እደጃዝማች አሰፋ ቤት ቅጣ ከተፈጸመባቸው በቀር ስለ አዛዥ ተካልኝ በበጎ ካልሆነ በክፋት በምስጋና ካልሆነ በሀሜት የሚናገር አልነበረም።

አዛዥም በዚያ ሁሉ ሰፊ ሀብትና በዚያ ሁሉ ‹ስራየቤት› ላይ የሚያዝዙ የሚገዙ ከመሆናቸው በላይ ደግሞ በቤቱ፥ ሰው ዘንድ የተወደዱና የተመሰገኑ መሆናቸውን ማወቃቸው የልብ ደስታና የጉልበት ብርታት ይሰጣቸው ስለ ነበረ፥ እንግዳ ካልያዛቸው በቀር ቀን እቤታቸው ተቀምጠው ትንሽ እንኳዋ ማረፍ አይወዱም፥ አይችሉም ነበር። የኮሶ መድሀኒት ጠጥተው እቤታቸው ከሚውሉበት ቀን በቀር በሌላው ቀን እሁድ እንኳዋ እቤታቸው አርፈው ውለው አያውቁም፤ እደጃዝማች ግቢ ደርሰው ከስራውና ከስራ የቤቱ ጋር እስኪገናኙ ይቸኩሉ ነበር።

አዛዥ ጽኑ ህመም ታመው አያውቁም። እንደ ጉንፋን ያለ ወይም ሌላ ቀላል ህመም መታመማቸውን አይተው ደጃዝማችም ሆኑ ባልተቤታቸው ወይዘሮ ጽጌ እቤታቸው አርፈው እንዲያሳልፉት የነገሩዋቸው እንደሆነ እንኳዋ ‹እሺ› አይሉም ነበር። ከስራውና ‹ከየስራ ቤቱ› ከጭቅጭቁ በጠቅላላው እዚያ ግቢ ካለው ነገር ሁሉ መለየቱ ሞት መስሎ ይታያቸው ነበር! እዚያ ግቢ ያለውን ሁሉ ንብረቱን ስራውንና ‹ስራየቤቱን› ‹የስራቤቱን› የስበስ መጨቃጨቅና መጣላቱን መክሮም ሆነ ገስጦ የተጣሉትን ማስማማቱን የማይስማሙትን ፈርዶ መለየቱን መቅጣቱን የቀጡትን ምሮ ከያፉ ሲመሰገኑ መስማቱን ይህን ሁሉ በረዥም ጊዜ ያዛዥነት ሕይወታቸው ለመዱትና ይህን ሁሉ በረዥም ጊዜ ያዛዥነት ሕይወታቸው ለመዱትና ይህን ሁሉ እያንዳንዱን

በረዥም ጊዜ እንደያንዳንዱ የሰውነት ክፍላቸው ለምደውት ወደዱትና በዚህ ሁሉ ፈንታ የሰውነት ክፍላቸው ለምደውት ወደዱትና በዚህ ሁሉ ፈንታ አንድ ጋሻ መሬት ሲሰሙ ‹ከንግዲህ አይኖሩም በዚህ ሁሉ ፈንታ አንድ ጋሻ መሬት ርስት ካምሳ ብር የወር ገቢ ጋር ይዘው እንዲያርፉ መወሰኑን ሲሰሙ ‹ከንግዲህ አይኖሩም! ከንግዲህ የሉም!› እንደ ተባሉ ሁሉ ማዘን ብቻ ሳይሆን ግራ ገባቸው! እውነትስ እንዲህ ያለው ከመወደድና ከመመስገን ጋር ረዥም ጊዜ ተይዞ የኖረ ስልጣን እንዲህ ያለው በረዥም ጊዜ መልመድ የሰውነት ክፍል የሆነ ራሱ ኑሮ ወይም ህይወት የሆነ ስልጣን ባንድ ጋሻ መሬት ርስትና በምሳ ብር የወር ገቢ ስልጣን በዋጋ ቤት ገብቶ የሚተመን አደለም! ብቻ ላዛዥ ያልታያቸው እድሜ ሲሄድ ብቻውን የማይሄድ የሚወዱትን ሁሉ ስልጣንንም ጭምር ህይወትንም ጭምር ይዞ የሚሄድ መሆኑ ነው! የሚወዱት ነገር ሁሉ ስልጣን ጭምር ከድሜ ተለይቶ የማይቀር እድሜን ተከትሎ የሚሄድ መሆኑ ያንጊዜ ላዛዥ አልታያቸውም። እድሜ ሲሄድ ስልጣን ብቻውን ቀርቶ እንኩዋንስ ብዙ ‹ስራ የቤት› እጅና እግርን አይንና ጆሮን እንደ ልብ አዝዞ ማሰራት እንደሚሳነው አልታያቸውም! እድሜ እሱን ካልደከመው የፈለገውን ያክል ሲሄድ ቢኖር ስልጣን ሳይለያቸው እንዳዘዙ እንደ ገዙ የሚኖሩ መስሎ ነበር የሚታያቸው!

‹ዝም በሉኝ! እኔ ተካልኝ እመክራለሁ እንጂ መካሪ እምፈልግ አደለሁም!› ይላሉ አዛዥ በደጃዝማች ውሳኔ ደስ ሊላቸው እንጂ ሊከፉቸው የማይገባ መሆኑን ወዳጆቻቸው ሲመክሩዋቸው። ‹ህ! እኔ ተካልኝ ለማኝ ነኝ?› ‹የምትትበላው ያውልህ እዚያ ተቀምጠህ ብላ› የምባል? ምጽዋተኛችውን ይፈልጉ! እኔ ተካልኝ ምጽዋተኛ አደለሁም! ደግሞ ‹የወር ደመወዝህ ከርስትህ ጋር መጦርያ ይሁን› ይሉኛል! ተጡዋሪ አባቴ ቄስ ታረቀኝ ፍቹን እንደ ነገሩኝ በነሱ አፍ በዚያ፥ በግዙ ‹የሚሸከሙት› ማለት ነው አሉ። ታዲያ እኔ ተካልኝ የህል ስልቻ ነኝ ወይስ፥ እጅ እግሬን ተጎምጃለሁ የሚሸከሙኝ? የለም እኔ ተካልኝ ምጽዋተኛ ጉምድምድ አደለሁም! ብራቸውንም መሬታቸውንም እዚያ - ምጽዋተኛቸውንና ጉምዳቸውን ፈልገው ይስጡት! »

አዛዥ እድሜ ሳይጫናቸው በሙሉ አቅማቸው ሳሉ፥ በቅንነት በትጋትና በታማኝነት ማገልገላቸውን ተመልክተው ደጃዝማች አሰፋ አንድ ጋሻ መሬት ርስትና አምሳ ብር የወር ገቢ ሰጥተው ከስራም ካሳብም እንዲያርፉ ሲያደርጉዋቸው በማመስገንና በመደሰት ፈንታ ማዘንና በጎ አድራጊያቸውን መውቀስ ለሰሚ ግራ መሆኑን እዬገለጹ ማዘናቸውንም መበሳጨታቸውንም እንዲተዉ ከሚመክሩዋቸው ዘመድ ወዳጆቻቸው መሀከል አዝማሪው ውቤና በሻህ ዘለሌ ነበሩ። ሁለቱ አዛዥ

ባዘኑበት ጊዜ ያልተለዩዋቸው ሀዘናቸውን ለማስረሳት አጥብቀው የሚጥሩ ነበሩ። አዝማሪው ውቤ ከምክሩ ሌላ በመሰንቆ ወይም በቃሉ ብቻ አዬዘፈነም እያንጎራጎረም ሲያጫውታቸው ያመሽ ነበር። አንዳንድ ጊዜም ተበሳጭተው ‹አታነጋግሩኝ› ሲሉ ይሰድባቸውና ‹ሂድ የታባትህ አንተ ከይሲ› ብለው ያባርሩታል። ብቻ ሁለቱም ሳይማረሩ አድረው ተገናኝተው ያው ምክሩ ጭዋታው ስድቡ መጣላቱ ይቀጥል ነበር!

«ይስሙ አባባ አዛዥ» አለ አዝማሪው ውቤ አንድ ምታ ራት በልተው ስለዚያው ስለ አዛዥ አዘነተኛነት ሲነጋገሩ። «እስቲ ይስሙኝ፥ አንድ ነገር ልጠይቅዎ? የዘሩበትን የእህል አይነት ሁሉ የሚያበቅል አንድ ጋሻ ለም መሬት ተሰጥቶዎ በዚያ፥ ላይ ለወር ወጪ እንዳይቸገሩ አምሳ ብር የወር ገቢ ተጭምሮልዎ፥ ‹አርፈው ለድሜዎና ለማእረግዎ የተስማማ የክብር ኑሮ ይኑሩ› ቢባሉ ባሪው ይመስል - ‹ከስራየ ጋር እንደ ተቆራኘሁ› ካልሞትሁ ብለው ነው እንዲሁ ራስዎንም ቤተሰቡንም የሚያስቸግሩ? ባሪያ እንኳዋ ተገድዶ ነው እንጂ፥ ወድዶ አይደለም ከስራው ጋር እንደ ተቆራኘ የሚሞት። በብር የተገዛ ባሪያ በሙሉ አቅሙ ሳለ የሚሰጠው አገልግሎት የተገዛበትን ዋጋ ለመመለስ እንደሚሰጠው ታስቦ ‹የገዥው ትርፍ ባሪያው ከሸመገለ በሁዋላ፥ እስከ እለተ ሞቱ የሚሰጠው አገልግሎት ነው› ይባላል። ታዲያ የባሪያው ጌታ የተቻለውን ያክል ትርፉን ለማብዛት ስለሚያስፈልግ ባሪያውን ካልሞተ ወይም ካልመነኮሰ አይለቀውም፤ ያስራዋል። ሰለዚህ ‹አራሽ ባሪያ ከርፉ ጋር እንጨት ፈላጭ ባሪያ ከምሳሩ ጋር ሳር አጫጅ ባሪያ ከማጭዱ ጋር እንደ ተቆራኘ ይሞታል› ይባላ። ታዲያ እርስዎ - ማለፊያው ጭዋ እንደ ባሪያ ‹ከስራየ ጋር ካልሞትሁ› ብለው ይህን ያክል ማዘንና መበሳጨት ምን ይባላል? ይህን የሰማ ሁሉ መሳቂያና መተረቻ አያርግዎም? »

«አይንህን ያብርረውና አንተ ከይሲ እኔ ተካልኝ ነኝ - በባሪያ የምመሰለው? ‹መስራት ስችል እጅና እግር እንደሌለው ለማኝ እንደሆነ አልቀበልም› የሚል ምናልባት - ‹ልበ ኩሩ› ይባል እንደሆነ እንጂ ‹ባሪያ? ባሪያ አይባልም፤ በባሪያ አይመስልም። ‹ምጽዋት አንቀበልም› የሚሉትን በባሪያ የሚመስል እንዳንተ ያለ ከይሲ ነው። እኔ የማዝንበትና የምበሳጭበት ላንተ አይገባህም፤ ዝም በል! » አሉ አዛዥ ለጊዜው ተቆጥተው።

«ይቅርታ ያድርጉልኝ አባባ! » አለ ባሻህ አዛዥ አዝማሪውን ገስጠው ዝም ካሰኙ በሁዋላ። «ይቅርታ ያድርጉልኝ። ይህ - ልቅ አፍ የሰጠውን የባለጌ ምሳሌ እዚያ ለሱ ትቼ በጠቅላላ አሳቡ በፍሬ ነገሩ እኔም እስማማለሁ። ደጃዝማች አሰፋ ለርስዎ

ያደረጉትን ሌሎች ትልልቅ መኩዋንንት ብዙ ዘመን ላገለገሉ ሰዎቻቸው ያደረጉ የሚገኙ አይመስለኝም። ቢኖሩ እንኩዋ ያለ ጥርጥር በጣም ጥቂት ይሆናሉ። ስለዚህ ደጃዝማች ሊመሰገኑ እንጂ ሊወቀሱ የሚገባ አይመስለኝም። ለርስዎም የተሰጠዎ ርስትና የወር ገቢ ለረዥም ጊዜ አገልግሎትዎ ጋር ነው እንጂ ምጽዋት አደለም። ስለዚህ - እንደኔ እንደኔ ከሁለታችሁም በኩል ‹ይህ ቀረ› ተብሎ ህሊና የሚቆረቁር ነገር ሳይሆን ‹ስራውና ድካሙ ብቻ ቀረብኝ ብለው አዝነዋል› ሲባል ላሽሙዋጣጮችና ለፌዘኞች እንዳይመቹ ደስ ያለዎ እንጂ ያዘኑ መስለው ባይታዩ የሚሻል ይመስለኛል። ነገር የለም። እርስዎ ራስዎ ሲናገሩ የሰማሁት ምሳሌ አሁን በርስዎ ላይ ቢጠቀስ በጣም ይስማማል። ያ ከርስዎ የሰማሁት ምሳሌ፥ ‹ሳትዋጋ ንገስ ቢሉት ካልተዋጋሁ አልነግስም ብሎ ሲዋጋ ንጉስነቱንም ህይወቱንም አጣ› የሚባለው ሰው ነው። ይህ አሁን እርስዎ የሚሉት ከዚያ ጋር ተመሳሳይ አደለም? »

«እንዴት ሆኖ? » አሉ አዛዝ በሻህን፥ ዝም ብሎ ሲሰሙ ቆይተው።

«መቸም ደጃዝማች ያዛዥነቱን ስራ ለሌላ፥ ሰው አለ ሰጡብዎ ማዘንዎንና እሳቸውን የሚወቅሱ መሆንዎን ሲሰሙ ‹ደስ ያሰኘሁት መስሎኝ ያደረግሁት ይህን ያክል አሳዝኖት የሚወቅሰኝ ከሆነ መወቀሱ ካልቀረ የሰጠሁትን ርስትና የወር ገቢ መልሼ ወስጃለሁ› ሲሉ ይችላሉ። ታዲያ እንዲህ ያሉ እንደሆነ - እርስዎ ሌላ ገቢ የለዎ። ወይም ከንግዲህ በሽምግልና ‹ሌላ ስራ ሰርቼ እኖራለሁ› አይሉ። እንዴት ሆነው ይኖራሉ? ከክፉ ችግር ላይ አይወድቁም? በውነት አባባ እኔ ከርስዎ አላውቅም እንጂ ደጃዝማች ያደረጉልዎ የሚያስደስት ነው እንጂ የሚያሳዝን አደለምና የረዥም ጊዜ አገልግሎት ዋጋዎን ይዘው ቤተ ክርስቲያንዎን እዬሳሙ ለራስዎም ለሳችወም ሙሉ ጤንነት እዬለመኑ በተረፈ ጊዜዎ ዘመድ ወዳጅ እዬጠዬቁ ሳያዝኑ ሳይበሳጩ የተረፈ እድሜዎን በሰላም እንዲያሳልፉ ነው - ከድፍረት አይቁጠሩብኝና ሽቅብ የምመክርዎ። ይህ ቤት የፍቅር፥ የደስታ የጭዋታ ቤት ስለሆነ ነው - ጋሼ ውቤና እኔ ያጠመደ ሊይዘን እስኪቸል የምናዘወትረው! እና - እዚህ እደስታ ቤት ሀዘን እንዲገባ እንወድም። አዘን በሌለበት ቤት ከሩቅ ፈልጎ ጠርቶ ካስገቡት፥ ክፉ ነው፥ ‹ውጣ› ቢሉት አይወጣም፥ እዬወለደ እዬተወላለደ ቤቱን የሀዘን ብቤት ያደርገዋል! ስለዚህ እባክዎ ሀዘንዎንና ብስጭትዎን ወዲያ ይትዉ» አለ በሻህ።

‹ደጃዝማች «ጋሻ መሬቱንም የወር ገቢውንም መልሼ ወስጃለሁ» ቢሉት እንዴት ሆነው ይኖራሉ?› ብሎ በሻህ የጠዬቃቸው ጥያቄ አዛዥ በብስጭት ውስጥ ሳሉ ያልታያቸውና መስል ሊሰጡበት የማይችሉ ስለ ነበረ ሲያወርዱ ሲያገላብጡ ቆዩና፥

«እውነትህ ነው ልጄ» አሉ ቀና ብለው። «ይህን ያክል ክፉ አደሉምና አይሉ እንደሆን እንጂ ካሉማ - ‹የሰተ ቢነሳ የለበት ወቀሳ› አደል? ምን ይከለክላቸዋል? እንኩዋንስ በወር የሚሰጡኝን አምሳ ብር መሬቱንም ቢሆን - እሳቸው ‹በርስትነት ሰጥቸዋለሁ› ብለው በቃል ነገሩ፤ የሰፈረ ወይም በውለሰሚ ፊት የተነገረ መቸም የለ! ስለዚህ ‹የሰጡሁትን መልሼ ወስጃለሁ› ሲሉ ከፈለጉ ምን የሚከለክላቸው ነገር ይኖራል? እኔስ የምኖርበት - እናንተ የማታውቁት ምን ሌላ ነገር አለኝ? ብቻ በጣም ተበሳጨሁ በጣም አዘንሁና ‹የሚያልፍ ብስጭት አውሮ ወደማያልፍ ጸጸት መርቶ ያዳርሳል› እንደሚሉት ይህ ሁሉ አልታዬኝም አልታሰበኝም ነበር።»

«ምንም የሚያበሳጭ ነገር የለኮ አባባ! »

«ህ! የሚያበሳጭ ነገርማ አለ እንጂ እንዴት የለም? »

«ምን የሚያበሳጭ ነገር አለ? »

«አዬህ! አያችሁ? ልጆቼ፣ እኔ ከዚያ ቤት ብቀር ሌላ ቤት አላውቅም። ጌቶች ሳይወለዱ እኔም ገና በልጅነት ነበር ላባታቸው የጌታ ያደርሁ። እሳቸው ተወልደው አባታችው ከሞቱ በሁዋላ ብዙዎች ያባታችወ አሽከሮች ለዬመኩዋንንቱ ሲያድሩ እኔና ጥቂት ብቻ ነእብርን ከልጅዬው ጋር የቀረን ከዚያ በድሜም በማእረግም እያደጉ ሄደው ቤታቸውን ከወላጆቻቸው ቤት ሲለዩ ከልጅነታቸው ጀምሬ ያልተለዩሁዋቸው በመሆኔ መጀመሪያ ሙሉ ቤት አዛዣቸው አድርገው የሾሙ እኔን ነው። ከዚያ ጊዜ ጀምረን ይህን - ያክል ጊዜ አብረን ስንኖር» ሲሉ አዛዥ ከጌታቸው ጋር አብረው የኖሩ ረዥምና ውብ ጊዜ በሙሉ ርዝመቱ በሙሉ ውበቱ በፊታቸው ተዘርግቶ ታያቸውና የሚናገሩትን አቋዋርጠው እሱን እየተመለከቱ ዝም አሉ። እንዲያ ዝም ብለው የማያዩ አይኖቻቸውን ሳያረግቡ አሻግረው እማዶው ግድግዳ ላይ ተክለው ትንሽ ሲመለከቱ ቆይተው «አዎ» ከንቅልፋቸው እንደ ተቀሰቀሱ ሳይረግቡ ፈዝዘው የቆዩ አይኖቻቸውን መላልሰው አርገበገበው። «ምን ስል ነበር? አዎ ይህን ያክል አብረን ስንኖር እኔ ያደረግሁትን እሳቸው እንዳደረጉት እኔ ያዘዝሁትን እሳቸው እንዳዘዙት አድርገው ከመቀበል በቀር

እግዚአብሄር ይስጣቸውና አንድ ቀን ‹ለምን እንዲህ አደረግህ?› ብለው ጠይቀውኝ አያውቁም።

«ስለዚህ እሳቸውን ራሴ ቤቴን ቤቱ ስራውን ስራዬ ብዬ በሙሉ አምኜ የኖርሁ ነኝ። ይህ የምኖርበት ቤት እንኩዋ የዚያ ቤት ክፍል ሆኖ ነው እንጂ እርም ነው የምወደውን ጌታዬን ያሰፋን ስጋ የተለዩ መስሎ ታይቶኝ አያውቅም! ታዲያ - ለካስ የልም ኑሮ ኑሮዋል የምኖር ‹የሰጠሁህን መሬትና ብር ይዘህ እዚያው እቤትህ አርፈህ ተቀመጥ› ሱሉኝ ድንገት ነቃሁና ደነገጥሁ! እድሜየን ሙሉ እሳቸው ራሴ ቤቱ ቤቴ መስሎኝ ስኖር እንዲህ አለመሆኑ ድንገት ሲገለጽልኝ አዘንሁ! ተበሳጨሁ፤ ብቻ ግዴለም! መልሼ ወስጃለሁ ቢሉሳ?› ላልኸው» አሉ አዛዥ ዋእደ በሻህ ባገጫቸው እያመለከቱ፥ «እንዲያ የሚሉ እንኩዋ አይመስለኝም፤ ይህን ያክል ክፉ አደሉም። ነገር ግን ‹አይመጣምን ትተሽ ይመጣልን ባሰብሽ› ነውና አንተን ያሰጋህን ያደረጉ እንደሆነ ይብሱን የማይካድ ነው። ስለዚህ ልጆቹ እግዚአብሄር ይስጣችሁና እንደ መከራችሁኝ» ሲሉ እንግዲህ አላዝንም አልበሳጭም ጌታየንም አልወቅስም» ሲሉ አዛዥ አዝማሪው ውቤም በሻህም ደስ ብሎዋቸው እዬተነሱ ጉልበታቸውን ሳሙ።

አዛዥ ‹ከንግዲህ አላዝንም አልበሳጭም ጌታየንም አልወቅስም› እያሉ በሻህና አዝማሪውን ውቤ ስለ ጨቀጨቁዋቸው እነሱም ዝም አሰኝተው ለማረፍ ብለው ሳይሆን ምክራቸው ትክክለኛ መሆኑን አእምሮዋቸው ስለ ተረዳ የመከሩዋቸው እውነት መሆኑን ስላመኑ ያን የሰጡዋቸውን ምክር ተከትለው ሳይዝኑ ሳይበሳጩ፥ በሰላም አዲሱን ኑሮ ለመኖር የሚችሉ መስሎዋቸው ነበር። ነገር ግን አልቻሉም!

አዛዥ ተካልኝ እድሜያቸው ሙሉ - ከዚያም ረዥም ጊዜ የሚበዛውን ባዛዥነት - ከብዙ ‹ስራ የቤት› መሀከል የኖሩ ስለ ነበሩ ከዚያ ሊለዩ እማበል ገፍቶ በደረቅ አሸዋ ላይ ጥሎት እንደ ሸሸ አሳ መኖር የማይችሉ መስሎ ተሰማቸው! ከዚያ ሁሉ ‹ስራየ ቤት› ግርግር ተለይተው ብቻቸውን እቤታቸው ሲቀመጡ ከሰው ተለይተው እንደ ክፉ ወንጀለኛ ባንድ ጠባብ ክፍል ታስረው የተቀመጡ መስሎ ተሰማቸው! ስለዚህ ምንም እንንኩዋ ወዳጆቻቸው የሰጡዋቸው ምክር ትክክለኛ መሆኑን አእምሮዋቸው ቢረዳ ልባቸው እንዳያዝንና እንዳይበሳጩ ለማድረግ አልቻሉም ልብ እንደ ሌሎች ያካል ክፍሎች ያእምሮን ትእዛዝ የማይቀበል ሽፍታ አደል? ስለዚህ ልባቸው ‹እንቢ› ብሎ ማዘናቸውን መበሳጨታቸውን ቀጠሉ።

አዝማሪው ውቤና በሻህ ወይም ሌሎች ዘመድ ወዳጆች እቤት ከሌሉ አዛዥ በዚያ ባዘኑበት ጊዜ ባልተቤታቸውንና ደመቀችን እወጥቤታቸው እንዲቀመጡ አድርገው እሳቸው ከበገናቸው ጋር ብቻ መጫወቱን ነበር የሚያዘወትሩ። ብዙ የበገና ድርድሮችን ባያውቁም የበገና ምት ማለፊያ አድርገው ያውቁ ነበር። ደጃዝማች አሰፋን እንኩዋ በሁዋላ ይብለጡዋቸው እንጂ፥ መጀመሪያ ያስተማሩ እሳቸው ነበሩ። ድርድር ግን እንኩዋንስ ራሳቸው ገጥመው ሊደርድሩ በበገና ተጭዋጮች ዘንድ ተለምደው ከኖሩት ብዙ ድርድሮችም የሚያውቁዋቸው በጣም የተወሰኑ ነበሩ።

እንግዶች ከሌሉ ራት፥ በልቶ እጃቸውን ከታጠቡ በሁዋላ እንደ ድሮው ተቀምጦ መጫወቱ ቀረ። አዛዥ ወደ በገናቸው ወይዘሮ ጌጤና ደመቀች ወደ ወጥ ቤታቸው ተሰማርተው አዛዥ ከበገናቸው ጋር ሲያንጐራጉሩ ሁለቱ ሴቶች ከወጥ ቤታቸው ውስጥ ተቀምጠው ያዛዥንና የበገናውን እንጉርጉሮ እዬሰሙ ምን ማድረግ እንደሚሻል ሲጨነቁ ሲቸገሩ እስከ ምኝታ ጊዜ ማምሸቱ የተለመደ ሆነና፥ ያን የጭንቅ ጊዘ አጥብቀው ይጠሉት አጥብቀው ይፈሩት ነበር!

«አይቀርም ሞቱ» ይላሉ አዛዥ በገናቸውን ይዘው የንጉሮ ድርድራቸውን ሲጀምሩ።

«አይቀርም ሞቱ፥ ከቶ አይቀርም ሞቱ፥

ምንም ቢታከቱ።

ከችግር ጋር ከስቃይ ጋር ምነው መዋንገቱ፥

ድል መሆኑ ላይቀር መረታቱ።

ድል መሆኑ ላይቀር ሞቱ

ሰውን ካፈር ለምንት ፈጠርኮ በከንቱ።

አፈር ሊሆን ላይቀር ሞቱ።

ወመዋእሊሁኒ ከመ ጽላሎት የሀልፍ።

ሰው ሆይ ያዳም ልጅ መሬት አንተ ወትገብእ ውስተ መሬት፥

ሀበ ሀለወት ብዝህት ሀጢያት፤

ከፉ ነህና የማይገባህ ያምላክ ስሬት።

ለምንት ፈጠርኮ በከንቱ፥

አፈር ሊሆን ላይቀር ሞቱ»

እያሉ እነኒህን ድርድሮች እዬመላለሱ ሲያንጎራጉሩ ቆይተው ሲደከማቸው ተነስተው ወደ ምኝታቸው ይሄዳሉ። አንዳንድ ጊዜ ግን እንጉርጉሮ ከሀዘን ወደ ብስጭት ይመራቸውና በገናውን ወርውረው ሲጥሉ ባልተቤታቸውና ደመቀች ሰምተው መጥተው ሲመክሩዋቸውም ሲለምኑዋቸውም ቆይተው ሲረጋጉ ወደ ምኝታቸው ይወስዱዋቸዋል። ያ በራትና በምኝታ መሀከል ያለው ጊዜ ሊደርስ ያዛዥን እንጉርጉሮ መስማቱና ብስጭታቸውን ማየቱ እያሰቀቁዋቸው ወይዘሮ ጌጤና ደመቀች ጊዜው መሸት ሲል ‹ምነ እንግዳ በመጣ!› እያሉ ይመኙ ነበር። አዝማሪው ውቤና በሻህ ሲመጡማ ደስታቸው ወሰን አልነበረውም! አዝማሪው ውቤ አንዳንድ ጊዜ ከመሰንቆ ጋር አንዳንድ ጊዜም በቃሉ ብቻ ሲዘፍን ወይም እሱና በሻህ ዱላ ቀረሽ ሲሰዳደቡ ቤቱ የሳቅና የጭዋታ ቤት ሆኖ ስለሚያመሽ የነሱን መምጣት ወይዘሮ ጌጤና ደመቀች አጥብቀው ይናፍቁ ነበር።

አንድ ማታ አዝማሪው ውቤና በሻህ መጥተው ራት ከተበላ በሁዋላ ጭዋታው፥ ከቀልድና ከተራ ጭዋታ አዝማሪው መሰንቆውን አንስቶ ወደ ዘፈን ተላለፈ። መሰንበቻውን እናዛዥ ቤት ጠላ ብቻ እንጂ ጠጅ አለመኖሩን ተመልከተው አዝማሪው ውቤ አንድ ማንቆርቆሪያ ጠጅ፥ በሻህ አንድ ጠርሙስ ኮኛክ፥ ይዘው መጥተው ነበር። ስለዚህ ራት እስኪበላ ጠላ ሲጠጣ ቆዬና፥ ወንዶች ሁሉም ጠጅ ወይዘሮ ጌጤና ደመቀች ኮኛክ ይዘው ጭዋታቸው እንደ ቀጠለ «አባባ አዛዥና እማማ ጌጤ ሳይቆጡኝ ቃላችሁን ስጡና ምስጢር ላውጣ። መቸም አንዳንድ ምስጢር የማይጎዳ ከሆነ እውጭ አይወጣም እንጂ በቤተሰብ ውስጥ እንዲነገር ይፈቀዳል» አለ አዝማሪው ውቤ የመሰንቆ ግርፉን አቁዋርጦ።

«ምን ምስጢር ነው ጌጤንና እኔን አስፈቅደህ የምታወጣው? » አሉ አዛዥ።

«ሁለታችሁ ያካፈላችሁኝ ምስጢር ነው።»

«ታዲያ አንተ የንስሀ አባታችን ነህ ኍልታችን ላንተ ምስጢራችነን ያካልፈንህ? »

«የንስሀ አባታችሁ ስለሆንሁ አደለም። ምስጢራችሁን መግለጽ ልባችሁ አሰገድዶዋቸው እናንተ መጻፍ ስለማትችሉና ከኔ የቀረበ መጻፍ የሚችል ወዳጅ ስለሌላችሁ ነው።»

«ምስጢር መያዝ የማትችል ወንፊት መሆንህን እያውቅን ላንተ የነገርንህ ነገር ካለ ምስጢር ባይሆን ነውና አንቆጣም ተናገር» አሉ አዛዥ ፈገግ ሲሉ አፋቸውን እንደ ልማዳቸው ግራ ቀኝ እስከ ጆሮ ግንዳቸው አላቀው።

«እማማ ጌጤም አይቆጡ? »

«አ - አልቆጣም» አሉ ወይዘሮ ጌጤም እያመነቱ። ምን እንደሚያመጣ ስለሚያውቁ መስጋታቸው በፊታቸው ላይ ይታይ ነበር።

«ገዳሜ ገዳሜ ገዳሜ ገዳሜ፥

ትመጣለህ ብዬ አንተን እዬጠበቅሁ አመሻለሁ ቆሜ።

ገደም ገደም አለ ሰው ሁሉ ሊተኛ፥

ተጎልቶ አድራለሁ ያንተ በሽተኛ» አለ አዝማሪው ሰው ሁሉ የሚያውቀውን ግጥም እንደ መግቢያ። ከዚያ - አንድ ቁራጭ ወረቀት ከኪሱ አወጥቶ እያዬ፥ «ወይዘሮ ጌጤ ላዛዥ ገጥመው አስጻፉኝ» ያለውን ከመሰንቆው ጋር አሰተባብሮ በዚያ በሚያምር ድምጹ መዝፈኑን አስከተለ።

«እንዳልተፈጠረ፥ ሌላ ወንድ ባገሩ፥

ወይዛዝሩ ሁሉ ያለው በሰፈሩ፥

ተካየ አንተን ብቻ ምነው ማባረሩ?

መቸም ልብህ አይችል ተካየ ሽጋ አይተህ፥

ትገባለህ የትም፥ በጥቅሻ ተጠርተህ

እዚያ እንዳትቀርብኝ እንደ ዋዛ ገብተህ፣

የት ይዤህ ብሰደድ ይሻለኛል ብለህ?

በጉንፎ አልከትህ! አልውጥህ በሆዴ!

ወዴት ልደብቅህ በሄድህበት ቀርተህ እንዳይፈላ ጉዴ? » ብሎ ሲጨርስ፥

«ውይ፣ ውይ ምን ውሸታሙ ነው እባካችሁ? ምን ወለ ወልዳው ነው? » አሉ ወይዘሮ ጌጤ አፍረው አይኖቻቸውን በሁለት እጆቻቸው ሸፈኑና። በሻህንና ደመቀችን የወይዘሮ ጌጤ ማፈርና መድረሻ አጥተው የሆኑትን የነበረው ሁሉ በጣም አሳቃቸው። አዛዥ ግን አዝማሪው ስለሳቸው የሚለውን ለመስማት አፋቸውን በሰፊው ከፍተው እሱን እያዩ ይጠብቁ ነበር። ከዚያ አዝማሪው «አዛዥ ለወይዘሮ ጌጤ ገጥመው አስጻፉኝ» ያለውን ቀጠለ።

«ሹመቴ ይወሰድ ይቅር ግዴለኝም፥

የልጅነት ጌጤ እኔ ካንቺ ሌላ ምንም አያምረኝም፥

ነገር ግን ያላንቺስ? ኧረ በስመ አብ ወወልድ! መኖር አልመኝም!

ንብረቴ ይወሰድ ሸቅዬ እበላለሁ፤

ባጣ እንኩዋ እምበላው ያንቺ ፍቅር እስካለኝ ጠግቤ እኖራለሁ፥

ግን ሳልሞት በቁሜ፥ በህይወት እያለሁ፥

አንቺን የሚቀማኝ ማንም እንደሌለ እምልልሻለሁ፥

የሰማዩን ሆነ የምድሩን ቀማኛ እፋለመዋለሁ።

ከወርቅ የበለጠ ያኖርሽኝ አድምቀሽ ያኖርሽን አሙቀሽ፥

ካልማዝ የበለጠ ያኖርሽኝ አስጊጠሽ፥

መተኪያ የሌለሽ ጌጤ ነሽ ጌጤ ነሽ።»

«ሆ፥ ሆ፥ ሆ! ትሰሙታላችሁ? እግዚአብሄርን ነውኮ ‹የሰማይ ቀማኛ› የሚለው! ደግሞ የሱ ጥጋቡ አነሰና - ይህ ፈረስና ገብስ የሚያጣላ ከይሲ እኔን ‹ከእግዚአብሄር ጋር እፋለማለሁ› ባይ አደረገኝ! እንዲያ ያለው የብሪት ቃል ከኔ እንደማይወጣ እሱ ያውቃል» አሉ አዛዥ ‹እሱ› ሲሉ ያንጊዜ እግዚአብሄር ተቆጥቶ መአት እንዳያወርድበት የፍራት መልክ እዬታየባቸው አይኖቻቸውን፥ በስማዩ አቅጣጫ ወደ ጣራው አንስተው። ያዛዥን ፍራት ሲያዩ ሁሉም በሳቅ አወኩ። ከዚያ አዝማሪው ቅኝቱን አስተካክሎ ዜማውንም የግጥሙን አይነትም ለወጠና ‹እሰይ ና ወዳጄ› ማለት ጀመረ።

«እሰይ ና ወዳጄ እሰይ ና እንጂ ምነው፥

ዛሬኮ ነው የኛ ነገ ለነገው ነው።

እንጫወት ዛሬ ደስ ይበለን ዛሬ እንባላ እንጠጣ፥

ነገ አናውቅምና ምን ይዞ እንዲመጣ።»

«ተቀበለኝ ሊቀመኲዋስ» አለ በሻህ ጥንታውያኑ ሲሉ የሰማው እንዳይቀርበት።

«ይዣለሁ» አለ አዝማሪውም።

«አናስብ ለነገ ዛሬ በልተን እንሙት

አዝማሪው አህያ ናቸው እንጂ እሚሉት

ሰዎች እንዳይመስሉህ ማሰብ የሚችሉት» ሲል ሳቅ ውካታ ሆነ። አዝማሪው በሻህ ለሰደበው «ልመስል» ሳይል የነገረውን ግጥም ተቀብሎ ከዘፈነ በሁዋላ ሌሎችን ግጥሞች አስከተለ።

«ተካልኝ ገስጤ እንኩዋን ደስ ያለዎ፥

የስሙ አዛዥነት እውን ሆነልዎ።

እስከ ዛሬ ድረስ ‹አዛዥ› የሚልዎ፥

የስም ነበር እንጂ የውን እንዳይመስልዎ

‹መቼ ገቡ? መች ወጡ?› የማይባሉበት፥

በጊዜዎ ሆነ በገዛ ራስዎ ሊያዙ እሚችሉበት፥

የስም ብቻ ሳይሆን እንዲሁ የዘበት

የተሾሙ አሁን ነው በውነት አዛዥነት።

እስቲ ደርዘን ውስኪ ያውርድ የደስ ደስ፥

እንስከር እንፈንጥዝ እስኪነጋ ድረስ» ሲል፥

«እባክዎ እንዲህ እንዲህ ያለውን ተውና ይልቅ ሌላ - የሚጥም ነገር አለህ እንዲሁ አምጣ። እንዲህ ከለውስ፥ ያ - ‹ሰው ካፈር የተሰራ ቢያጥቡት የማይጠራ

ነው? ወይስ ምን የምትለው ወይ ደግሞ ‹ሞሪኝ› የምትለው እሱ እንኳዋ ይሻላል» አሉ አዛዥ።

ምንም እንኳዋ በሻህና አዝማሪው ውቤም ሌሎች ዘመድ ወዳጆችም ከመከሩዋቸው በሁዋላ አዛዥ ሹመታቸውን በማጣታቸው የማያዝኑ መሆናቸውን እዬመላለሱ ቃል ቢሰጡ፥ ምንም ያክል ቢመከሩም ሀዘናቸውን ማሸነፍ አልሆነላቸውም። ያዛዥነት ስም እንኳዋ ያን ያለፈውን የሚያሳዝናቸውን ነገር ሁሉ አስከትሎ ስለሚመጣባቸው ስነሳ መስማት አይወዱም ነበር። እንኩዋንስ ተነስቶ ሳይነሳም እንዲሁ ቀን እረፍት ሌት እንቅልፍ የሚያሳጣ በሽታ ስለ ሆነባቸው እሱን የሚያስረሳ እንጂ እሱን የሚያስታውስ ምንም አይነት ነገር መስማት አይወዱም ነበር። ስለዚህ አዝማሪው ከሚያውቁዋቸው ረዣዥም ግጥሞቹ አንዱን የጀመረ እንደሆነ ለሀዘናቸው ምክንያት የሆነው ነገር ይረሳ ይሆናል ብለው ‹ሞሪኝን› ወይም ‹አየ ሰው ጎስቁዋላው ካፈር የተሰራ ቢያጥቡት ያልቃል እንጂ ምን፥ ቢሆን አይጠራ› የሚባለውን ግጥሙን እንዲጫወት ነገሩት። አዝማሪው ‹ሞሪኝ መሰንቆየ እከተልሻለሁ የሚለውን ግጥሙን ጨርሶ ሁለተኛውን ሊጀምር ሲል፥

«እሽ - ! አባባን እንቅልፍ ወስዶዋቸዋል! » አለች ደመቀች፥ ጠቁዋሚ ጣትዋን በከንፈሮችዋ ላይ አድርጋ። አዛዥ በወንበራቸው ላይ መከዳቸውን ተጠግተው ወደ ሁዋላ ጋለል ብለው በተቀመጡበት እንቅልፍ ሸለብ አድርጎዋቸው ስለ ነበረ አዝማሪው «ሞሪኝ» የሚባእልውን ግጥሙን ሲጫወቱ፥ ወደ መጨረሻ ያለውን ክፍል አልሰሙትም ነበር።

«የታባቱ ምቀኛ! ሌሊት ብቻየን ስሆን ትቶኝ ድራሹ ሊጠፉ አሁን ከሰው ጋር እንዳልጫወት - ተመቅኝቶኝ እንዲህ ያንገላጅጀኛል! » አሉ አዝማሪው እንቅልፍ ያስወሰዳቸውን እንጉርጉሮ ሲያቁዋርጥ አይኖቻቸውን ገለጥ አርገው፥ ጋለል ካሉበት ቀና ብለው ተቀመጡና። «እስቲ ልጄ ካመጣልን ኮኛክ ለሁላችንም ቅጅልን» አሉ ቀጥለው። ኮኛክ ተቀድቶ ሁሉም አንዳንድ መለኪያ ከጠጡ በሁዋላ ሌሊቱ ተገባድዶ ስለ ነበረ አዝማሪው ውቤና በሻህ - ተሰናብተው ሲወጡ፥ ጌጤና ደመቀች አዛዥን አስነስተው ወዳልጋቸው ወሰዱዋቸው።

በማግስቱ እንደ ተለመደው ወይዘሮ ጌጤና ደመቀች ጥዋት ቀደም ብለው ተነስተው አንዳቸው ቡና አንዳቸው እንጀራ ባዋዜ፥ አሰናድተው አቅርበው ሲጠብቁ አዛዥ ስለ ቀሩባቸው ባልተቤታቸው ወደ ምኝታ ቤታቸው ቢገቡ፥ እንደ ተኙ አገኙዋቸው።

አዛዥ ተካልኝ የደጃዝማች አሰፋ ‹አዛዥ› ሆነው በኖሩበት ጊዜ ሁሉ ጌታቸው ከመነሳታቸው በፊት እግቢ ደርሰው ስራየ ቤቱን በዬስራው ለማሰማራት ማልዶ መነሳት ለምዶባቸው ያዛዥነት ስራቸውን ከለቀቁ በሁዋላም ወደ ግቢ መሄዱ ቢቀር ማልዶ መነሳቱ አልቀረም ነበር። ስለዚህ ያለወትሮዋቸው ያነለት ተኝትወ መቆዬታቸው ባልተቤታቸውንና ደመቀችን አስትግቶውቸው፥

«ምነ ደህና አደሉም? ይነሱና ቁርስ እናርግ እንጂ ረፍዶዋልኮ! ደመቀች ወደ ስራዋ ለመሄድ ትቸኩላለች» አሉ ወይዘሮ ጌጤ፥ እምኝታ ቤታቸው ገብተው።

«ተነስቼ ነበርኮ! ብቻ - የማታው መጠጥ ነው መሰለኝ - ወገቤም ጉልበቴና እጄም እዬተንቀጠቀጠ ሱሪየን መታጠቅ ሲያቅተኝ ጊዜ ነው ተመልሸ የተኛሁ» አሉ አዛዥ። ከዚያ ባልተቤታቸው አስነስተው ሱሪያችውን አስታጥቀው ቁርስ ወደ ሚያደርጉበት ይዘዋቸው ሄዱ። አዛዥ ያነለትቡና ብቻ ጠጡ እንጂ እንጀራ አልበሉም። ‹ባፌ እዬዞረ አልዋጥልኝ አለ› ብለው በንጀራው ፈንታ ቡና ደጋገው ጠጡ።

ከቁርስ በሁዋላ ሁለቱ ሴቶች ወደ ዬስራቸው ሲሰማሩ አዛዥ እንደ ልማዳቸው ‹ወንበር አውጡልኝ› ብለው እደጅ መቀመጣጫውን ትተው፥ ወደ ምኝታ ቤታቸው ተመልሰው ተኙ። በልማዱ ወደ ደጃዝማች ግቢ መሄዳችወ ከቀረ በሁዋላ ወይዘሮ ጌጤና ደመቀች ትተዋቸው ወደ ስራቸው ሲሄዱ ጥዋት ቁርስ አድርገው ከተቀመጡ በሰባት ሰአት ለምሳ እስኪነሱ ድረስ እደጃቸው ከወንበራቸው ጋር እንደ ተጣበቁ ሁሉ ሳይነቃነቁ ነበር የሚውሉ። ከሁድ በቀር ወደ ቤተ ክርስቲያን አይሂዱ! አንዳንድ ዘመዶችና ወዳጆች ሊጠይቁዋቸው ካልመጡ እሳቸው ፈልገው ዘመዶችና ወዳጆች ሊጠይቁ አይሄዱ! እደጃቸው ይቀመጡና ያለፈ ይህወታቸውን ጠርተው አምጥተው አንዳንድ ጊዜም ድምጻቸውን እያሰሙ ከሱ ጋር ሲነጋገሩ ነበር የሚውሉ።

«እንዲህ ብቻዎን ቁጭ ብለው የቀኑን ደቂቃ ሲቆትሩ ከሚውሉ፥ አንዳንድ ጊዜ ወደ ቤተ ክርስቲያን ሄደው ቢሳለሙ አንዳንድ ጊዜም - ወደ ጉዋደኞችዎ ሄደው ቢጫወቱ ቀኑ ረዝሞ አያስለችዎም ነበርኮ! » ይላሉ ወይዝሮ ጌጤ ባለቤታቸው ብቻቸውን ሲናገሩ ባጋጣሚ የሰሙ እንደ ሆነ፥ የሚያደርጉት ይጨንቃቸውና ቀረብ ብለው።

«ዛሬኮ - ቅዳሴ አይኖርም ጌጤ፥» ይላሉ አዛዥ ያዘቦት ቀን የሆነ እንደ ሆነ።

«ቅዳሴ ባይኖርስ - ተሳልመው ቢመጡ ምናለ? እዚያ ደርሰው እስኪመጡ ጊዜ ያልፍልዎታል። ወዲያውም ወገብዎ ይፍታታል።»

«ቅዳሴ ቢኖርም ባይኖርም ሁልጊዜ እቤተክሲያን የሚገኙ ሬሳዎች ብቻ ናቸው። ስለዚህ - ከነሱ ጋር ሁልጊዜ እዚያ ለመገኘት ስሞት ያደርሰኛል። ‹ወደ ጉዋደኞችህ ሂድ› የምትይኝስ - ምን ጉዋደኛ አለኝ? ጉዋደኞች ላበጅ እችል የነበርሁበትን ጊዜስ የት እንዳሳለፍሁት አጣሽው? እድሜዬን ሙሉ ጉዋደኞቼ አድርጌያቸው የኖርሁ ወንዶችም ሴቶችም፥ እደጃዝማች አሰፋ ቤት ወይዘሮ ጌጤ ሳይስቡት እንደማይችልም ታውቂያለ» ሲሉ፥ ወይዘሮ ጌጤ፥ ሳይስቡት፥ ባለበቤታቸውን ለሀዘናቸው ጠንቅ ወደ ሆነው ነገር በመምራታቸው በውስጣቸው ራሳቸውን እዬወቀሱና እየተጸጸቱ ቶሎ ካጠገባቸው ይሸሻሉ።

አዛዥ ያነለት እቁርስ ላይ ቡና ብቻ ደጋግመው ጠጥተተው ከተኙ በሁዋላ አልተነሱም። በተለይ ካካላታቸው ‹ይህን አመመኝ› የሚሉት ሳይኖር እህል መብላቱን ስለ ተዉ መነሳት እስኪያቅታቸው ድረስ ይደከማቸው ጀመር። አንድ ጉርሻ እህል የጎረሱ እንደሆነ ባፋቸው ውስጢ ሲንከራተት ብዙ ቆይቶ፥ ‹ልዋጥህ› ሲሉት ሽቅብ ስለሚተናነቃቸው እንኩዋንስ እህል መብላት ሊያምራቸው መልኩን ማየትና ስሙን መስማትም አስጠላቸውና እያደር ሰውነታቸው እያለቀ እዬደከመ ይሄዱ ጀመር። ባዛዥነት ስራቸው ላይ በነበሩበት ጊዜ ሁሉ ለምሳቸው እቤታቸው ደርሰው ከሚመለሱበት አጭር ጊዜ በቀር ከጥዋት እስከ ማታ ቀኑን ሙሉ በስራ ተጠምደው ሲውሉ አንድ ቀን ‹ደከመኝ› ሲሉ ተሰምተው አያውቁም ነበር። ስራቸውን ለቅቀው እቤታቸው መዋል ጀከመሩ በሁዋላ፥ ሀዘንና ብስጭት ሲይዙዋቸው ድካምና እርጅና ተሸሽገው ከኖሩበት እዬወጡ ተጨምረው ትንሽ እንኩዋ ሳይታገሉ ቶሎ ጣሉዋቸው!

አዛዥ ተካልኝ ታምሞ የተኛ ሰው ለመጠየቅ ካልሆነ እድሜያቸውን ሙሉ ራሳቸውን ታምመው ሀኪም ቤት ተኝተው አያውቁም። ሀኪም ቤት በጣም ይጠሉ ነበር። ስለዚህ ደመቀችም ወይዘሮ ጌጤም ሐኪም ቤት ገብተው እንዲታከሙ ቢለምኑዋቸው ‹እንቢ› ብለው አንድ ሳምንት እቤታቸው ተኙ። ከዚያ በሁዋላ አዝማሪው ውቤና በሻህ የንስሀ አባታቸውን ጨምረው ይልቁንም ቄሱ በግዝት ስላስፈራሩዋቸው ፍልውሀ ህክምና ቤት ገቡ። እዚያ ‹የደመቀች አባት ናቸው› ሲባል አንደኛ ማእረግ፥ ባንድ ክፍል ውስጥ ለብቻቸው አስተኙዋቸው። አስራምስት ቀን በህክምና ቤት ቆዩና ሀኪሞች በጊዜው የታወቀውን ምርመራ ሁሉ ካደረጉላቸው በሁዋላ በሽታቸውን ሊያቁ ስላልቻሉ ያደረጉላቸው የክህምና ርዳታ፥ የምግብ

ፍላጎታቸው እንዲሻሻልና ብርታት እንዲያገኙ ለማድረግ በመሞከር የተወሰነ ነበር። ያም ቢሆን አልተሳካ። ያልታወቀ በሽታ መድሀኒት ይገኝለታል? በሽታቸው ሀኪሞች አይወቁት እንጂ ያዛዥነት ስራቸው ለሌላ ሰው መሰጠቱ ነበር! መድሀኒቱም ከደጃዝማች አሰፋ እንጂ ከሀኪሞች የሚገጥ አልነበረም! ምናልባት ደጃዝማች አሰፋ ሄደው ‹ያዛዥነት ስራንህ መልሽልሀለሁ› ቢሉዋቸው ሳይድኑ ባልቀሩ ነበር!

ደመቀች ጥዋት ጥዋት አዛዥ ወደ ተኙበት ክፍል ሄዳ ይሰሙ እንደሆነ እሳቸውን ያለዚያ ወይዘሮ ጌጤን እንዴት እንዳደሩ ሳትጠይቅ ወደ ምድብ ስራዋ ሄዳ ስለማታውቅ አንድ ጥዋት እንደ ልማድዋ በሩን ቀስ አድርጋ ከፍታ ስትገባ አዛዥ፥ ከወገባቸው በላይ ያለ አካላቸውን በተደራረቡ መከዳዎች ላይ አሳርፈው አይኖቻቸው ገርበበ ቢሉም ጋለል ብለው ተቀምጥወ የሚያዩ መስለው አዬችና «እግዚአብሄር ይማርዎ እንደ ምን አደሩ? » አለች ትንሽ ፈገግ ብላ ለራስዋ እንደምትናገር በሹክሹክታ። ነንዲያ ቀና ማለታቸው ስለ ተሻላቸው መስሉዋት ደስ ብሎዋት ነበር።

«ያው እንደ መሰንበቻው ነው፥ ምንም ለውጥ የለ» አሉ ወይዘሮ ጌጤ።

«ለምን እንዲህ አቃኑዋቸው? ይደከማቸዋልኮ! »

«ጭንቅ ቅንቅ አለኝ እንዲህ - ሆኘ ትንሽ ልቆይ አሉኝ» ሲሉ ወይዘሮ ጌጤ አዛዥ አይኖቻቸውን ገለጥ አድርገው ደመቀችን አዩና ሰፊ አፋቸውን እስከ ጆሮ ግንዳቸው አላቅቀው፥ ዝም ብለው ቆዩ። ከዚያ ሁለት የከሱ እጆቻቸውን ከብርድ ልብሱ ውስጥ እያዘገሙ አውጥተው፥ የባልተቤታቸውንና የደመቀችን እጆች ፍለጋ ሲሰዱ፥ ለምን እንደሆነ ባያውቁም ሁለቱም እጆቻቸውን እንደ ሚፈልጉ ስለ ተረዱ ቶሎ ሰጡዋቸው።

«ደመቁ» አሉ አዛዥ በጣም በደከመ ድምጻቸው የሁለቱን እጆች ባንድ ላይ አገናኝተው እንደ ያዙ፥ ዝም ብለው ቆይተው። «እናትሽም - ጌጤን - አደራ። እዚህ - የሰጠሁሽን - አደራ - በሰማይ - እጠይቅሻለሁ። እንደ - ምታውቂው - አንድ - ረዳት - የላትም። አንድ - ልጅ - ብቻ ፈጥረን - ነበር - እሱም - ከኔ - ቀድሞ - ሞተ» አሉ፥ እያንዳንዱን ቃል በግድ እዬታገሉ ካፋቸው ካስወጡ በሁዋላ፥ እያረፉ እዬቆዩ።

«እባክዎ እንዲህ አይበሉ አባባ! ሀኪሞች ‹ከድካም በቀር ሌላ በሽታ የለባቸውም› ብለውናል። ስለዚህ እንደ ምንም እዬታገሉ ትንሽ እህል ቢቀምሱ ደህና ይሆናሉኮ! »

«ጌጤን - አደራ - ብዬሻለሁ። ለ - ለኔ - ግን - እንዲህ - እንዲህ - ያለ - ሞት - ቢሹት - የማይገኝ - ማ - ማለፊያ - ሞት - ነው። ትልልቅ - ጌቶች - በ - በሚተኙበት ክፍልና - አልጋ - ተኝቶ - መሞት - ትልቅ - እድል - ነው እድለኛ - ነኝ። እድሜየን - ሙሉ - ስኖር - ጌታየ - ማለፊያ - አድርገው አኖሩ - እግዚአብሄር - ይስጣቸው። አሁን ደግሞ - አንቺ - ማለፊያ - አድርገሽ - በከበሬታ - ልትሸኚኝ - ነው። እግዚአብሄር ይባርክሽ - ልጄ። መከዳውን - ዝቅ አድርጉና - አስተኙኝ፤ ደከመኝ» አሉ ብዙ ስለ ተናገሩ ደከሞዋቸው ትንፋሻቸው ቁርጥ ቁርጥ እያለ። ደመቀች መከዳዎቹን ዝቅ አድርጋ ስታስተኛቸው አይኖቻቸውን እንደገና ገርበብ አረጉ። ትንሽ ቆይተው ያንኩዋርሩ ጀመር።

«አይዞዎ እማማ እንቅል ነው» ብላ ደመቀች ወይዘሮ ጌጤን ስታበረታታቸው ቆይታ ወደ ስራዋ ወጣች። በሶስተኛው ቀን ጥዋት ደመቀች ገና የህክምና ቤቱን በር ስትገባ ወይዘሮ ጌጤን ከክፍሉ ውጪ፥ ኩታቸውን አሸርጠው ሲያለቅሱ ከሩቅ አይታ አዬሮጠች ወደሳቸው ስትሄድ እሳቸውም ስላዩዋት

«ጉድ ሆን ደመቁ ጉድ ሆን» እያሉ ተቀበሉዋትና ሁለቱም ተቃቅፈው ይላቀሱ ጀመር።

ደጉ ሰው ቂም የለሹ አዛዥ ተካልኝ ገስጤ፥ ከብዙ ጊዜ ድካም በሁዋላ በሰባ ሰባት አመታቸው ለሁልጊዜ አረፉ። ቃል ሁሉ ከውስጣቸው ሲያልቅና እንደበታቸው መንቀሳቀሱን ሊተዉ ሲል እንኩዋ መጨረሻ፥ ካፋቸው የወጡት ቃላት፥ - እንደሳቸው እምነት - እስከ ሞት የሚያደርስ በደል የበደሉዋቸውን ጌታቸውን ደጃዝማች አሰፋን የሚመርቁ መሆናቸው ፍጹም ደግና ቂም የለሽ ለመሆናቸው ምስክር ሆኖ የሚኖር ነው!

## ምእራፍ ሰላሳ ሰባት

# የደመቀችና የታምራት ተገኘ መፋታት

በሻህና ደመቀች አምቦ እንዳሉ ወዳዲስ አበባ ሲመለሱ ጋብቻቸውን ማዘጋጃ ቤት አስመዝግበው ወዲያው ሊጋቡ ተስማምተው ወስነው ነበር። ግን መቸም፥ በማህበር ውስጥ የሚኖሩ ሁሉ ለኑሮዋቸው ያቀዱትን ልክ እንዳቀዱት ወደ ፍጻሜ ለማድረስ ሁልጊዜ ስለማይሙዋላላቸው እነሱም ሲመለሱ አዛዥ ተካልኝን ለሞት ያደረሳቸው ችግር ተፈጥሮ የቆያቸው በመሆንና ከዚያም ሞታቸው ስለ ተከተለ የሚጋቡበት ቀን ላንድ አመት እንዲዘገይ ሆነ።

አዛዥ ከሞቱ በሁዋላ በሻህ፥ አዝማሪው ውቤና ያዛዥ ባልተቤት ወይዘሮ ጌጤ፥ ጭምር ጋብቻቸው አርባቸው እንደ ወጣ ያለዚያም መንፈቃቸው ከወጣ በሁዋላ እንዲሆን ፈልገው ነበር። ነገር ግን ደመቀች ‹ያባቴን ሙታመት ሳላስቆርብ ከሬን ካንገቴ አልፈታም› ስላለች ሙታመታቸው እስኪወጣ መቆዬት ግዴታ ሆነ።

ደመቀች፥ ስትጠላ አጥብቃ የምትጠላውን ያክል ስትወድም አጥብቃ የምትወድ ስለ ነበረች፥ አዛዥ ተካልኝ እንዲያ አጥብቃ የምትወዳቸው ነበሩ።

«እና - አባባ ሞተው ተራ ዘመድ እንደ ሞተብኝ ሁሉ ‹አርባቸው ወይም መንፈቃቸው ከወጣ ክርሽን ካንገትሽ ፈትተሽ፥ አጊጠሽ ተሰረጊ› - ነው የሚሉኝ? ምነ፥ አጥንታቸው አይወቅሰኝም? ነፍሳቸው አትታዘበኝም? ወላጅ አባቴ ቢሞቱ ሙታመታቸውን ሳላስቆርብ አጊጨ እሰረግ ኖሮዋል? አባባ ደግሞ ከወላጅ አባቴ የበለጠ የሚያስቡልኝና እኔም ከወላጅ አባቴ የበለጠ የምወዳቸው እንደ ነበሩ፥ ከማንም የበለጠ እስዎ ያውቃሉኮ እማማ! » አለች ደመቀች ‹ያዛዥ ሙታመት እስኪወጣ አላገባም› ማለትዎን እንድትተው ወይዘሮ ጌጤ ሲለምኑዋት።

«እውይ ደመቁ፥ አባትሽን ጥሩ አድርገሽ አስታመሽ፥ ደስ አሰኝተሽ ሸኝተሻቸዋል። ማንም አባትዋን የምትወድድ ልጅ አንቺ ለሳቸው ካደረግሽው የበለጠ ልታደርጊ አትችልም። ደግሞ አሁን የሰጋሁ፥ ‹ሙታመታቸውን ሳላስቆርብ አላገባም› ማለትሽ ምናልባት ለበሻህ፥ እሱን ላለማግባት የፈጠርሽው ምክንያት መስሎ ታይቶት እንዳይቀዬምና - ጋብቻችሁ እንዳይሰናከል ነው» አሉ ወይዘሮ ጌጤ።

«እርስዎ ‹ከፈቃዴ ወጣሽ› ብለው አይቀየሙኝ እንጂ ለሱ አያስቡ ግዴለም እማማ። ከሱ ጋር ተስማምተናል።»

«እንዴት ነው የተስማምችሁ? ጋብቻችሁ ላንድ አመት እንዲቆይ? »

«አዎ! »

«እንጃ! አይመስለኝም።»

«እኔን ካላመኑኝ እሱን ይጠይቁት? »

«እንግዲህ ተቀይሞዋል ማለት ነው! »

«እንዴት? »

«እስቲ እይው በቀደም እሱና ውቤ አጎናፍር አብረው መጥተው፥ ‹እባክሽ አንቺ ተቆጫት፤ እኛ ብንነግራት እንኩዋንስ አሳባችነን ልትቀበል፥ እንዲያውም፣ ‹ዳግመኛ ይህን ነገር ያነሳችሁብኝ እንደሆነ እጣላችሁዋለሁ› ብላ አስፈራርታ አባረረችን ብለው እያዘኑ ነበር የነገሩኝ። ታዲያ - ያን ያክል እያዘነ ‹አሳብዋን እንድተለውጥ ተቆጡልኝ› ብሎ አማላጅ የላከ ሰው መልሶ ‹ያሰብሽው እንደ ፈቃድሽ ይፈጸምልሽ› ማለቱ ቢቀዬም አደለም? »

«መቸ ነው እሱና ጋሼ ውቤ መጥተው የነገሩዎ? »

«ከትናንት ወዲያ ነው፥ ወይስ ከዚያ በፊት? ከሶስት ቀን በፊት ነው መሰለኝ። ብቻ መሰንበቻውን ሰዎች አብረውት እያመሹ ስላልተለዩን ብቻችነን እስክንሆን ስጠብቅ ነው እስከ ዛሬ ያልነገርሁሽ።

«እንግዲያስ እሱና እኔ ተስማምተን የጨረስን ትናንት ነው። ተቀይሞ ሳይሆን አሳቤን ተረድቶልኝ ደስ ብሎት እንዲያውም፥ አመስግኖኝ ነው የጨረስን።»

«እንጃ! እውነትም እንደሚባለው - ያን ያገርሽን ‹ያፍዝ ያደንዝዝ› አዙረሽበት እንደሆን ነው እንጂ በጤናው ያን ያክል አዝኖ የነበረ ሰው ደስ ብሎት እንዲያውም አመስግኖ ባሳብሽ አይስማማም! ቅድም - ‹እንዳይቀዬምና ጋብቻችሁ እንዳይሰናከል› ያሰኘ አፉ ሲነካው የሰማሁት ነገር ነው።»

«ምንድነው እሱ? »

«ተሰነባብተን ሲወጡ ይህ ‹ሙታን ሳላስቆርብ አላገባም› የምትለው ‹ምናልባት እኔን ማግባት ስላልፈልገች የምትፈጥረው ምክንያት ልሆን ይችላል› ብሎ እዬተበሳጨ ለውቤ ሲነግረው ሰምቸ ነበር።»

«መጀመሪያ ለምክንያት የፈጠርሁት መስሎት ተቀይሞ ለኔም እንዲያ ብሎኝ ነበር። ነገር ግን መሰለው አለመሆኑን ሳስረዳው አመነ።»

«እኔ እንኩዋ የሚያስፈልግ አልመሰለኝም ነበር፤ ግን ሁለታችሁ ከተስማማችሁ ይሁን» አሉ ወይዘሮ ጌጤ።

ምንም እንኩዋ ለጋብቻ እንዲጠይቃት ላመታት ደጅ ስትጠናው የኖረች መሆንዋን አምቦ ኑዛዜያቸውን ሲለዋወጡ ብትነግረው፥ ጋብቻቸው ተፈጽሞ እጁ እስኪያደርጋ ድረስ አንዳንድ የምታደርገው ወይም የምትናገረው ነገር ልታገባው በሰጠችው ቃል ተጸጽታ ወደ ሁዋላ ለመመለስ የምታደርገውና የምታናገረው መስሎት እዬጠረጠረ በሻህ ያለወትሮው ጠባዩ ይከፋ ነበር።

መጀመሪያ ቃልውና ለማጠፍ ያሰበች መስሎት በሻህ እንደገና ጥርጣሬ ያደረበት ካምቦ እንደ ተመለሱ የጋብቻ ውላቸውን ማዘጋጃ ቤት ለማስመዝገብ በተቃጠሩበት ቀን እሱ ምስክሮች እንዲሆኑ የተሰማሙባቸውን አቶ ማንደፍሮን አቶ ታችበሌንና አዝማሪው ውቤን ይዞ ሂዶ ሲጠብቃት ሳትገኝ በመቅረትዋ ነበር።

እንዳጋጣሚ ሻሽመኔ፥ አካባቢ ባንድ ያሜሪካን ሚሲዮን ውስጥ የሚሰራ አስተማሪ ይሁኑ ሰራተኛ አሜሪካዊ በጽኑ ስለታመመ ቶሎ አዲስ አበባ መጥቶ እንዲታከም ተወስኖ የሚያመጣው ሀኪም ሲላክ ደመቀች ረዳቱ ሆና እንድትሄድ ታዘዘች። በማግስቱ የጋብቻዋን ውል ማዘጋጃ ቤት ለማስመዝገብ ከጮኛዋ ጋር ቀጠሮ ሌላ በሽተኛው ቶሎ ሀኪም ቤት ደርሶ እርዳታ ከስዋም ቀጠሮ ሌላ በሽተኛው ቶሎ ሀኪም ቤት ደርሶ እርዳታ እንዲያገኝ ሲባል ጭምር እለቱን የሚመለሱ የሚመለሱ እንጂ እዚያው የማያድሩ መሆናቸውን ስላረጋገጠላት ቅር ቢላትም ትእዛዙን ተቀብላ ሄደች።

ታዲያ ‹ምናልባት በጊዜ ያልደረስሁ እንደሆነ› ብላ፥ - ለጥንቃቄ ያክል - በትእዛዝ ሻሽመኔ መሄድዋን በዛኸ ተካልኝ ቤት በኩል በሻህ እንዲያውቀው ላንድ ጉዋደኛዋ መልእክት ትታ ሄዳ ነበር። ነገር ግን በሻህ ተቆጥቶ በለቱም ሆነ በማግስቱ ወዳዛኸ ቤት ስላሄደ መልእክቱ በለቱም ሆነ በማግስቱ ወዳዛኸ ቤት ስላልሄደ መልእክቱ አልደረሰውም ነበር። እውነትም ‹የፈሩት ይደርሳል፥ የጠሉት ይወርሳል!› እንደሚሉት

እንደ ሰጋችው በሽተኛውን ይዘው በለቱ ሊመለሱ አልቻሉም። በጣም ደክሞ ስለ ነበረ፣ ብርታት የሚሰጠው ህክምና እዚያው ተደርጎለት በመኪና መጉዋዝ እስኪችል ሁለት ቀናት በሄዱበት መቆዬት ግዴታ ሆነባቸው። ተመልሳ የሆነውን ስትገልጽለትና እሱም ስላጡት ባይነግሩት ነው እንጂ መልእክት ትታ መሄድዋን ወይዘሮ ጌጤ ሲነግሩት ለጊዜው፥ ሁለቱ ሴቶች፥ ተመሳጥረው የሚያታልሉት ቢመስለውም፥ ከዚያ በሁዋላ ብዙ ጊዜ ሳይቆይ ውላቸው ማዘጋጃ ቤት ስለ ተመዘገበ አሳቡ እንደ ማረፍ ብሎ ነበር።

ከዚያ አዛዥ፥ ተካልኝ ከሞቱ በሁዋላ ደግሞ፥ ‹ሙታመታቸውን ሳላስቆርብ አላገባም› ማለትን ስታመጣባት ትእግስቱን ሊያልቅ ምንም ያክል አልቀረው! ለረዥም ጊዜ ከስዋ ጋር በጋብቻ እንዳይተሳሰር ሲሸሽ እንዳልኖረ ሁሉ ሊያገባት ከወሰነ ጀምሮ ይልቁንም አምቦ ሰንብተው ከተመለሱ በሁዋላ ቀን ባለፈ ቀኡጥር የሚከተለው ቀን ጋብቻቸውን የሚያስቀር ችግር ይዞ የሚመጣ መስሎ እዬተሰማው ቶሎ ተጋብተው እንዲያ ካለው የቀን እረፍትና የሌሊት እንቅልፍ ከከለከለው የልብ ጭንቀት እስኪገላገል ቸኩሎ ነበር። ባመታት የሚቆጠር ጊዜ አብሮዋት ሲኖር ከጋብቻ ውጪ ነበር። ባመታት የሚቆጠር ጊዜ አብሮዋት ሲኖር ከጋብቻ ውጪ እንዳልኖረ ሁሉ፥ «እድሜውን ሙሉ ታውሮ የኖረ ሰው ነገ ትበራለህ» ቢባል «ዛሬ እንዴት አድኤ» አለ › እንደሚባለው ሊጋቡ ተዋውለው ውላቸው ህጋዊ ሆኖ ማዘጋጃ ቤት ከተመዘገበ በሁዋላ እንኩዋ የቀኑ መተላለፍ ጋብቻቸውን የሚያስቀር መስሎ ታይቶት ትእግስት አጥቶ ነበር።

«ደመቁ» አለ አዛዥ ተካልኝ ሙታመት እስኪወጣ ጋብቻውን እንዲቆይ ፈቃዱ ይሆን ዘንድ ስትለምነው። «ደመቁ፥ አባባ አዛዥ ‹ያንቺን ያክል ያወዱኝ ነበር› ብዬ ባልመካም እኔ በጣም የምወዳቸውና የማከብራቸው አባቴ ነበሩ። ስለዚህ የኛ ጋብቻ ሙታመታቸው እስኪወጣ አንድ አመት መቆየቱ ከሞቱበት የሚመልሳቸው ቢሆን ወይም በሞቱበት አጥንታቸው እንዲለመልምና ነፍሳቸው መንግስተ ሰማያትን እንድትወርስ የሚያደርግ መሆኑን በርግጥ ባውቅ ላንድ አመት ብቻ ሳይሆን ለብዙ አመታት ጋብቻዬን አቆይቼ ስጾምና ስጸልይ በኖርሁ! ብቻ ይህ ሁሉም ምንም እንደማያደግላቸው አውቃለሁ። ከዚህ ሁሉ ይልቅ ፈጣሪ የሚወደውና የሳችወን ነፍስ ደስ የሚያሰኝ ‹ሊሞቱ አቅራቢያ አደራ አሉኝ› ያልሽውን ማድረጉ ነው። ቶሎ ትዳራችነን አቆቁመን ‹አደራ› እንዳሉሽ እማማ፥ ጌጤን ችግር እንዳይደርስባቸው ማጽናናት እግዚአብሔርን፣ ደስ ያሰኘዋል፤ አንቺም አደራሽን ተወጣሽ ማለት ነው። በኔ አስተያየት ይህ ነው የሚጠቅመው ሌላው፥ እንዲያው - እንዲህ ‹ነገ ከነገወዲያ› እያልሽ

ነገሩ ወደ መጨረሻ ግቡ ሳይደርስ ግቡ ሳይደርስ እንዲቀር ምክንያት ፈልገሽ እንደሆነ እንጂ - ምንም ትርጉም ያለው አይመስለኝም።»

«የምን፥ ‹ምክንያት›? አሁንም - ከብዙ ጊዜ ጀምሬ ስላንተ በልቤ ይዤው የኖርሁትን ፍቅርና አድናቆት ስመኘው የኖርሁትን ጭምር እንዲያ ግልጥልጥ አድርጌ ከነገርሁህ በሁዋላ ትጠረጥረኛለህ? እንዴት ያለ ክፉ ልብ አለህ ጋሼ! » አለች፥ በቅርታ ያጌጠ ፊትዋን ወደሱ መልሳ ይሁን አይኑን እያዬች።

«ምናባቴ ልበል? ነገሩ ማለቂያ አጣኮ! አምቦ የተስማማንበትን አታስታውሺም? ከዚህ እንደ ተመለስን ውላችን ማዘጋጃ ቤት መዝገብ አስገብተን ወዲያው እንድንጋባ ነበርኮ የተስማማን! ከዚያ በሁዋላ - አንድ ጊዜ አንቺ ‹ካቅሜ በላይ የሆነ ነገር ገጠመኝ› ስትይ ሌላ ጊዜ ከውል - ሰሚዎች ላንዱ የሚስማማው ቀን ለሁለቱ ሳይስማማ ሲቀር ለሁለቱም የሚስማማው ቀን ላንዱ ሳይስማማ ሲቀር እንዲሁ በዬምክንያት ውሉ ሳይገባ ምን ያክል ጊዜ ከንቱ እንደ ባከነ ታውቂያለሽ። ያ ካለቀ በኋላ ደግሞ አሁን ይኸው ‹ሙታመት እስካቆርብ አንድ አመት እንቆይ› ትይኛለሽ ታዲያ - ይህ ትእግስት አያሳጣም? ሙታመት ማስቆረብ በትዳር በኑሮ ሊለወጥ አይገባም ማለትስ፥ ‹ክፉ ልብ አለህ› ያሰኛል› የሚወዳትን ቶሎ አግብቶ ትዳር ለመያዝ የሚቸኩል ባይሆን በሌላ ይነቀፍ እንደ ሆነ እንጂ ‹ክፉ ልብ አለህ› የሚል አይመስለኝም» አለ በሻህ ፊት የተናገረውን መራራ ነገር ትንሽ ለዘብ አድርጎ።

«እሱን እንኩዋ ተወው! አሁን እንዲህ እንቅፋቱ እዬበዛ አስቸገረ እንጂ፥ ለጋብቻችን ቸኩሎ የነበረስባለበት አለ! » አለች ካሽሙር ፈገግታ ጋር ላንድ አፍታ ፊቱን ባይኖችዋ ዳሰስ አድርጋው ስትመለስ። እሱም ‹ሳንጋባ እስከ ዛሬ ለመቆዬታችን አላፊው አንተ ነህ› ማለትዋ መሆኑ ገባውና ፊቱ በፍረት ቀለም ትንሽ እንደ መቅላት ብሎ አይኖቹን ከስዋ ዘወር አደረገ። ከዚያ አንገቱን እንደ ደፋ ዝም ብሎ ቆይቶ፥

«እኔ እንኩዋ - ተስማምተን ከወሰን በሁዋላ በተለይ አሁን ‹ሙታመት ለማስቆረብ አንድ አመት እንቆይ› ስላልሽ በጣም ረዝሞ ስለ ታዬኝ ‹ምንም ጥቅም ለሌለው ነገር ለምን ያን ያክል ጊዜ እናባክናለን› ማለቴ ነበር።»

«አዬህ ጋሼ፥ እኔ ፊት ከደጃች አሰፋ ቤት አሁን ከዚህ ሀኪም ቤት ወጥቼ ከዚህ አገር ሰው ጋር ደህና አድርጌ ስላልተዋወቅሁ ያገሩን ልማድ አላወቀውም እንጂ ተወልጄ ባደግሁትበት አገር በጎጃም እናት አባት፥ ልጅ ወይም ባል የሞተባት ሴት፥ ሙታመት

ሳታስቀርብ ክርዋን ካንገትዋ አትፈታም። ሙታመት ሳታስቀርብ ክርዋን ፈትታ ማተብ ድሪና መስቀል ወይም ሌላ ጌጥ ባንገትዋ አድርጋ ብትታይ ወይም ባል ብታገባ ከውሾች እንጂ ከሰዎች ተራ አግብቶ የሚቆጥራት የለም። ሁሉም ‹ውሻ ውሻ› እያለ መድረሻ ነው የሚያሳጣት! ታዲያ ይህ ምንም ያከል ቢፍቁት እንደማይጠፋ ሆኖ ባእምሮየ ተቀርጾ ያባባን ሙታመት ሳላስቀርብ ክር ፈትቶ ባል የማግባቱን ነገር ሳስብ ልክ ውሻ የሆንሁ እዬመሰለኝ እረፍት አላእኝም፤ የህሊና ወቀሳ እዬተሰማኝ እጨነቃለሁ! እስቲ እንዲያው - ያባባን የረዥም ጊዜ ውለታ ሁሉ ልተውና እመቤታችን መድረሻ እንደ ሌለኝ እያወቁ ‹ልጅሽን ይዘሽ በምትሄጂበት መድረሻ እንደ ሌለኝ እያወቁ ‹ልጅሽ ይዘሽ በምትሄጂበት ሂጂ› ብለው ከቤታቸው ሲያባርሩኝ እመቤታችን ቢጣሉዋችው እንደ ሚጎድዋቸው እያወቁ ‹የደረሰ ይድረስብኝ› ብለው ከነልጄ ተቀብለው ማስጠጋታቸው ከዚያ ፖሊስ ጣቢያ ብታሰር ራሳቸውን በኔ ፈንታ መስዋእት አድርገው አቅርበው ከዚያ እንድወጣ ማድረጋቸው፥ እነዚህ ብቻ እንኩዋንስ ያንድ አመት የብዙ አመታት ደስታየን መስዋእት የሚያስደርጉኝ አደሉም? አባባን ከወላጅ አባቴ አንድ ጊዜ ሳይሆን ብዙ ጊዜ አብልጨ የምወዳቸው የውነተኛ አባቴ ነበሩ! ለዚህ ነበር - ‹ከኖርነው አይበልጥምና፥ የህሊና እረፍት እንዳገኝ ሙታመታቸውን እስካስቀርብ አንድ አመት እንድቆይ ፍቀድልኝ› ብዬ የለመንሁህ። ነገር ግን - የሚያሳዝንህ ከሆነ ይቅር ግዴለም» አለች አይኖችዋን ከሱ እግሮችዋ ወደ ቆሙበት መሬት ስትመልስ፥ እንደ መተከዝ ብላ። በሻህ ለስዋ በነበረው ጽኑ ፍቅር ላይ ጥልቅ አድናቆት ስለ ተሰማው ለስዋ በነበረው ጽኑ ፍቅር ላይ ጥልቅ አድናቆት ስለ ተሰማው እንዲያ ያለውን ስሜት በሚገልጽ የቅርታ ፈገግታ አንገትዋን ደፍታ እንደ ተቀመጠች ዝም ብሎ ሲመለከታት ቆይቶ፥

«ይሁን፤ ይህ - የህሊና እረፍት የህሊና ሰላም የሚሰጥሽ ከሆነ አንድ አመት እንቆይ» አለ።

«ሳትቀዬም ከብልህ ነው? ወይስ - እንዲያው ለጊዜው - እኔን ደስ እንዲለኝ ብለህ ነው? » አለች አንገትዋን ደፍታ ከቆዬችበት ቀና አድርጋ እሱን እያዩች።

«የለም ሳልቀዬም ከልቤ ነው። እንዲያውም - እውነቱን ልንገርሽ? እንዲህ ያለው ሃይማኖተኛነትና የወዳጅ ፍቅር አጥባቂነት ከፍጥረት ብቻ የሚገኝ ባይሆን ኖሮ በትምርት የሚገኝ ቢሆን ኖሮ፥ እኔም ብማረው እንዴት በወደድሁ ነበር! ስለዚህ አንድ አመት ቅድም እንዳልሽው ከኖርነው ስለማይበልጥ ሳይከብደኝ እቆያለሁ» ሲል ደስ ብሎዋት ከተቀመጠችበት ተነስታ ሄዳ፥ አንገቱን እቅፍ አድርጋ ይዛ አፉን ሳመችና፥

«እግዜር ይስጥልኝ ጋሼ፥ ‹እንቢ› ትለኛለህ ብዬ፥ ፈርቸህ ነበር» አለች አንገቱን እንደ ያዘች በጭኖቹ ላይ ተቀምጣ አይኖቹን ቁልቁል ጠልቃ እያዬች።

«አስቀድሞ ‹ከፉውን አያሳይሽ› ማለት ነው እንጂ ካሳዬሽ አይጠዬቅ! ከፉ ብትጠይቂስ አንቺን ‹እንቢ› ማለት እንዴት ይቻላል» ሲል ምስጋናዋን ለመግለጽ አሁንም እቅፍ አድርጋ ሳመችው። ከዚያ እጭኖቹ ላይ እንደ ተቀመጠች ራስዋን በራሱ ላይ አንተርሳ ጆሮዎቹን ፊቱን ከንፈሮቹን በጆችዋ እዬዳሰሰች ‹ባንድ አመት ውስጥ ጋብቻችነን የሚያሰናክል ደግሞ ምን እንቅፋት ይገጥመን ይሆን?› እያለች ባሳብዋ ስታሰላስል፥

«ደመቁ» አለ። ወዲያው የሚለውን ለመስማት ራስዋን ከራሱ ላይ አንስታ በጭኖቹ ላይ እንደ ተቀመጠችም ዝም ብላ አፍ አፉን ታይ ጀመር።

«ለመሆኑ ተገብተን እኔ - ብሞት ሙታመቴን እስከታስቀርቢ ባል ሳታገቢ ከርሽን እንዳሰርሽ አንድ አመት ትቆያለሽ? » አለ እንድ እቀልድ ውብ ጥርሶቹን በከፊል ገለጥ አድርጎ።

«ምን አይነት ቀልድ ነው ይኸ? እንዲህ ያለ ቀልድ መልካም አደለም። በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ! ምን ጨካኝ ነህ እባክህ? » አለችና በፍቅር ስሜት ለስልሶ የነበረው ፊትዋ በቅጽበት ክርር ብሎ ከጭኖቹ ላይ ተነስታ እያማተበች ፊት ተቀምጣበት ወደ ነበረው ተመልሳ ሄዳ ተቀመጠች።

«እንዴ ለጭዋታ ነው እንጂ - እንድትቆጪ ብዬኮ አደለም። እና - ብትነግሪኝ ምናለበት? » አለ ምንም እንኩዋ መቆጣትዋን ከፊትዋ ቢያይ ጥርሱን በከፊል እንደ ገለጠ።

«ዝም በል አልሁህኮ ጋሼ! እኔ እንዲህ ያለ ጭዋታ መስማት አልፈልግም! ‹ባፍህ ውህ ይሙላና› አፍ የነካው ነገር ደህና አደለም» አለች ፊትዋን ክርር ግንባርዋን ኩስትር እንዳደረገች። በሻህ ሳቀና፥

«አፍ ነካው አልነካው መቸም ሰው ሲወለድ እንደሚሞት አስቀድሞ የታወቀ ነው። ደግሞ - አንዱ ቀድሞ ሌላው ተከትሎ ይሞታል እንጂ የተወለደው ሁሉ ባንድ ቀን ሞቶ አያውቅም። ስለዚህ ድንገት እኔ - ቀድሜ ብሞት ምን እንደምታደርጊ ነው የጠዬቅሁሽ» አለ ክርክሩን በማስረዘም፥ ቀስ በቀስ ቁጣዋን ለማስረሳት አሰቦ።

«እናቴ የደንግላይቱ እንዲህ ያለ ጉድ አትሰራኝም! ፈጣሪየ እንዲህ አያደርገኝም።»

«እኔም ባያደርገው እወዳለሁኮ! ብቻ - እንዲያው ቢያደርገው ማለቴ እንጂ! »

«እሱ ቸር ነው። በፍጡሩ እንዲህ አይጨክንም። እድኒህ አያደርግም እንጂ የሚያደርግ ከሆነ፥ የምለምነው ባይሆን እንኩዋ አንተን አንድ ደቂቃም ወደ ሁዋላ አቆይቶ ያንተን ሞት ሳያዬኝ ካንተ ጋር አብሮ እንዲወስደኝ ነው! » ስትል እውነት የሚሞት መስሎ ተስማምቶት እንባዋ ተንቻርፍፎ አሳዘነችውና የሱም አይኖች እንባ ሞሉ።

«ነገር ግን ፈጣሪየ ይህንም ከነፈገኝ» አለች ቀጥላ። «ፈጣሪየ ይህንም ነፍጎ ለጉድ ወደ ሁዋላ የሚያስቀረኝ ከሆነ አንድ አመት ብቻ አደለም፥ እድሜዬን ሙሉ ክሬን ካ - ካንገቴ ሳልፈታ፥ መንኩሼ፥ እመ - እመቃብርህ ላይ ጎጆዬን አሰርቼ እስኪ - እስኪ ጠራኝ ድረስ መቃብርህን እያሸተትሁ እኖ - እኖራለሁ! » ብላ አይኖቸዋን ሞልቶ ተንቻርፍፎ የነበረው እንባዋ እዬፈሰሰ የማያቆዋርጥ ስግ ጉሮሮዋን ሲተናነቃት የምትነግረው እያንዳንዱ ቃል እዬተቁዋረጠ ልክ ሞቶ እመቃብሩ የምትናገረው እያንዳንዱ ቃል እዬተቁዋረጠ ልክ ሞቶ እመቃብሩ ላይ እንደምታለቅስ ሁሉ ስቅ ስቅ ብላ ስታለቅስ ሲያያት ልቡ በውስጡ ሲሸበር አንጀቱ ሲላወስ ተሰማውና ወዲያው የሱም እንባ እዬወረደ ተነስቶ እቅፍ አድርጎ ይዞ ራሱን እዬወቀሰ ዝም እንድትል ዝም እንድልት ያባብላት ጀመር።

«እባክሽ ዝም በይ እባክሽ ማሪኝ ጥፋተኛ ነኝ፥ የኔ እመቤት! እውነትም ጨካኝ አውሬ ነኝ! ዳግም ይህን የመሰለ ነገር ላልናገር ማላ ይሁንብኝ! የዛሬን ብቻ ማሪኝ! » እያለ በደረቱ ጥብ -ቅ አድርጎ ይዞ በፊትዋ ላይ ያለውን ሁሉ እዬሳመ ሲለምናት ብዙ ጊዜ ቆይተው ሁለቱም ጸጥ እያሉ ሄዱ።

«እኔ ለቀልድ ለሳቅና ለጭዋታ ብዬ ነበር እንጂ የተናገርሁት እንኩዋንስ ይህን ያክል የሚያስለቅስሽ ትንሽም የሚያሳዝንሽ መሆኑን ብጠረጥር ኖሮ፥ ባልተናገርሁት ነበር! ደግሞ እንዲህ - ትንሽ የሚበቃው ስለ ልብ ያለሽ መሆንሽን ገና ዛሬ ማውቄ ነው፤ እስከ ዛሬ ድረስ የማውቅ በጣም ብርቱ በጣም ጎበዝ መሆንሽን ነበር! » አለ፤ ያ ከብርቱ ሳግ ጋር ተጣምሮ የሰራ አካላትዋን ከመሰረቱ ያናወጠው መሪር ልቅሶ አልፎ በደረቱ ላይ እንዳለች እዬሳመ እዬደባበሰ ሲማጠናት እዬተረጋጋች ሄዳ ሙሉ ሰላም ካገኘች በሁዋላ።

«እውነትህን ነው እንዲህ አልነበርሁም፤ አሁን ነው እንዲህ ደካማ እንዲህ ፈሪ የሆንሁ! » አለች ዝም ብላ ስታስብ ቆይታ።

«ከመቸ ወዲህ? ለምን? »

«አሁን» አለች በዝቅተኛ ድምጽ፥ ደረቱን እንደ ተንተራሰች አሁንም ዝም ብላ ቆይታ።

«እኮ ለምን? »

መልስ በመስጠት ፈንታ፥ እጭኑ ላይ እንደ ተቀመጠች ከደረቱ ብድግ ብላ በሁለት እጆችዋ ጉንጮቹን ይዞ ዝም ብላ ፊቱን እንደ መስታዋት ስታዬው ቆዬችና፥

«ጋሼ፥ እወድሀለሁ፤ በጣም ነው የምወድህ! ለዚህ ነው መሰለኝ ደካማ ፈሪ የሆንሁ አዎ ለዚህ ነው! » አለች በሹክሹክታ፤ ባፉ ይሰማ ይመስል አፍዋን ወዳፉ ጠጋ አድርጋ።

«እንዴት? » አለ እንዲያ እንደ ያዛት ፊቱ ሁሉ በለስላሳ የቅርታ ፈገግታ ተውቦ።

«ድሮ ከልጄ በቀር ሌላ የምወደው ነገር ሌላ ደስታ የሚሰጠኝ ነገር ስላልነበረኝና ዙሪያዬን የከበበኝ ሁሉ የሚያበሳጭ የሚያሳዝን የሚያስጠላ ብቻ ስለ ነበረ ለልጄ ብቻ የምኖር ልጄ ደህና ሁንልኝ ለራሴ የመጣ ቢመጣ ግድ የሌለኝ ምንም የማልፈራ ቁራጥ ነበርሁ! አሁን ግን - አንተ አንድያህን የኔ መሆንህን ካረጋገጥሁ በሁዋላ እንጃ ምን ልበልህ? ተለውጨ ሌላ መሆኔ ይሰማኛል! እንኩዋንስ እኔ በዙሪያየ ያለው ሁሉ አለሙ ሁሉ ተለውጦ ሌላ በጣም የሚወደድ በጣም የሚያባብል ሆኖ ታዬኝና ለራሴ መኖር የምወድ ሆንሁ! አሁን ካንተ ጋር ደስ ብሎኝ መኖር የምፈልግ ስለሆንሁ እንደ ዱሮው ‹የመጣው ይምጣ› ማለት የማልችል መቁረጥ የማይሆንልኝ ፈሪ ደካማ ሆኛለሁ ጋሼ! በህይወት ይሁን በሞት ካንተ መለየት አልፈልግም። ካንተ የሚለዬኝ ሁሉ ደመኛዬ ነው። ፈጣሪየን እንኩዋ ካንተ የሚለዬኝ ከሆነ እንደ ደመኛዬ ነው የምቆጥረው! እና - እንኩዋንስ አንተ ሞተህ እኔ ወደ ሁዋላ መቅረቱ እኔ ሞቼ አንተ ወደ ሁዋላ እንድትቀርም አልፈልግ! አብረን እንድንሞት ነው የምፈልግ! » አለች የሞቱን ነገር ስታነሳ አይኖችዋ እንደገና እንባ ሞልተው።

«እሺ የኔ እመቤት አብረን ኖረን አብረን ነው የምንሞት ማንማ አይለዩን! ብቻ - እንዲህ ስታለቅሺ ማየት አልፈልግም» አለ በደረቱ ላይ እንዳለች እቅ - ፍ - ጭን - ቅ አድርጎ ከሳማት በሁዋላ።

«አንተም እንዲህ የሚያስለቅሰኝ ነገር እንዳትናገር! እሺ? »

«ምነው ምዬልሽ? »

‹አመት እለት፥ ነው› ይባላል። ግን ሁልጊዜ አደለም። አመት እለትም ምእይትም ይሆናል። ‹ባንድ አመት መጨረሻ ክፉ ነገር ይደርስባቸዋል› ለሚባሉ አመቱ እለት ነው። ‹መልካም ነገር ታገኛላችሁ› ለሚባሉ ግን አመቱ ምእይት አመት ነው።

የጋብቻውን ቀን በብርቱ ናፍቆት ይጠባበቁ ለነበሩት ለበሻህና ለደመቀች ያዛዥ ተካልኝ ሙታመት እስኪወጣ አንድ አመት ሙሉ መጠበቁ ምንም እንኩዋ ወደው ያደረጉት ቢሆን፥ የምእይት አመት ያክል ረዝሞ ታይቶዋቸው ነበር። ነገር ግን ለጋብቻ ኑሮዋቸው ከሚያስፈልገው መሰናዶ ገና አንዱም ያልተያዘ ስለ ነበረ ባንድ ላይ ተቀምጠ እዬተመካከሩ የሚያስፈልጋቸውን ነገሮች በቅደም ተከተል ጽፈው በሚነጋገሩበት ጊዜ በቅድሚያ ከሚያስፈልጉት አይነተኛ ነገሮች አንዳንዶቹ ባመቱ ውስጥ ተሰናድተው ሊደርሱ የማይችሉ መስሎ ተስማቸውና፥ ያ ረዝሞ ታይቶዋቸው የነበረው አንድ አመት ያጥራቸው ጀመር።

ከሁሉም አስቀድሞ ተጋብተው የሚገቡበት ቤት አልነበራቸውም። የኪራይ ቤት በከተማው ስለ ጠፉ አልነበረም፤ እሱም ሞልቶ ነበር። ነገር ግን ያዛዥ ተካልኝን ባለተቤት ወይዘሮ ጌጤን ለመርዳትና ለማጽናናት ባጠገባቸው የሚከራይ ቤት አለመኖሩ ስላወቁ እዚያው አዛዥ ግቢ ውስጥ አንድ ቤት ሰርተው አብረዋቸው ከመኖር በቀር ብቸኛነት እንዳይስማማቸው ለማድረግ የሚችሉበት ሌላ መንገድ አልነበራቸው። በቤት እቃ በኩልም፣ ችግሩ ከቤቱ ችግር እምብዛ የቀለለ አልነበረ። በሻህ በትዳር፥ ላይ በነበረበት ጊዜ ገዝትቶ የነበረውን የቤት እቃ ሁሉ ምሽቱን ፈትቶ አቶ ማንደፍሮ ሆቴል ሲገባ ስለ ሸጠው ገና ሁሉም ‹አንድ› ተብሎ የሚገዛ ነበር። ስለዚህ ቤት አፋጥነው ለመስራትና ሊቆይ የሚችለው ቆይቶ እቤት ሲገቡ ግድ አስፈላጊ የሚሆነውን የቤት እቃ ለመግዛት ተስማምተው ወሰኑ። ግን ለዚያ ሁሉ የሚሆን ገንዘብ አልነበራቸውም። ከባንክ ለመበደርም ተያዥ የሚሆን ርስት ወይም እዳቸውን በየወሩ ለመክፈል የሚያስችል በቂ ደመወዝ ሊኖራቸው ያስፈልጋል። ስለዚህ ለሁሉም በሻህ ቶሎ ስራ

እንዲይዝና የሁለቱን ደመወዝ አጣምረው እዳቸውን በዬወሩ ከፍለው እንዲጨርሱ ተዋውለው ገንዘብ ከባንክ እንዲበደሩ ተስማሙ።

ስራ ፈልጎ የማግኘቱ ጉዳይ ለበሻህ ምንም ያክል ጊዜ አልፈጀበትም። ካንድ ወር ባልበለጠ ጊዜ ትምርት ሚኒስቴር በትምርት እቅድና ፕሮግራም መምሪያ ውስጥ በሁለት መቶ ብር የወር ደመወዝ ተቀጠረ። በዚያ ላይ አቶ ማንደፍሮ መጻህፍት ቤት ቀን የሚሰራውን ትቶ ማታ በከበባቸው ለሚደረገው ንግግርና ክርክር የቃለ - ጉባኤ ጸሀፊነቱን እዬቀጠለ፥ በመቶ አምሳ ብር ፈንታ በወር አድን መቶ ብር እንዲከፍሉት፥ ካቶ ማንደፍሮ ጋር ተስማሙ። ስለ ኢትዮጵያ ታሪክ ባህልና በጠቅላላው የማህበራዊ ኑሮ ስራት መማር ለሚፈልግ እዚያ በሊቃውንቱ ክበብ የሚደረገውን ንግግርና ክርክር የመሰለ ትምርት ቤት እንደሌለ የምን ስለ ስለነበረ እንኩዋንስ በወር መቶ ብር ደመወዝ እዬተከፈለው ለሊቃውንቱ ጉባኤ ተካፋይ መሆኑ እስካልቀረበት ድረስ ስራውን በነጻም ቢስራ ደስታውን አይችለውም ነበር!

ስለዚህ በሻህ ሶስት መቶ ብር ደመቀች አንድ መቶ አምሳ ብር የወር ደመወዛቸው፥ ሳይቸገሩ ብድራቸውን በየወሩ እዬከፈሉ ለመጨረስ እንደሚያስችለው ተማምነው ለቤት መስሪያና ለቃ መግዣ የሚበቃቸውን ገንዘብ ከባክድ ተበድረው ቤቱ ቶሎ ተጀመረ።

በሻህ በትርፍ ጊዜው፥ ለቤቱ ስራ የሚያስፈልገውን እቃ ራሱ እያቀረበ ለስራቸው ብቻ በሚያስከፍሉት ዋጋ ላይ ከልዩ ልዩ የቤት ስራ ተቋዋራጮች ጋር ተነጋግሮ ተዋዋለ። ስለዚህ መሰረቱ በስሚንቶ የተገነባ መጠነኛ የንጨት ቤት ጌጣጌጡ ሲቀር ግድግዳው ተገድግዶ ባጡ ቆርቆሮ ተከድኖ ልስኑ ተለስኖ፥ መዝጊያዎችና መስኮቶች ተገጣጥመው በስምንት ወር ውስጥ ሁሉም ተጠናቀቀ። የቀሩት የቀለም የባጥ ገበር (ጣራ) ስራዎችና እነሱን የመሳሰሉ ጌጣጌጦች ነበሩ። እነሱን ለማጠናቀቅ የሚያስፈልገው ጊዜ እከስ፥ ጋብቻው ቀን የሚቆይ አልነበረም። የቤት እቃውም እንዲሁ የሚሰራው ተሰርቶ የሚገዛው ተገዝቶ የቤቱ ስራ በመጨረሻ መልኩ እስኪጠናቀቅና ገብቶ እስኪመረቅ በዬቦታው ተቀምጦ ይጠባበቅ ነበር። ‹ቤት ለሁለት ከውጭ ግድግዳው ለወንድ ከውስጥ ጉዋዳው ለሴት› ሲባል እዬሰማ በሻህ የቤት ውስጥ እቃ ለመግዛት ብቻውን ገብያ ሄዶ አያውቅም። ደመቀች ወደ ስራዋ የማትሄድበት ቀን ቅዳሜ ጠብቆ፥ ሲመቻቸው ወይዘሮ ጌጤ ጭምር ያለዚያም እሱና ደመቀች አብረው እዬሄዱ ነበር የሚገዙ።

አንድ ቅዳሜ ወይዘሮ ጌጤን ስላልተመቻቸው ሁለቱ እጮኞች ብቻ ለመጋረጃ ላልጋና ለጠረጴዛ ልብሶች የሚሆኑ ጨርቆች ለመግዛት ወዳዲስ ከተማ ሄዱ። እዚያ በሻህ ከረዥም ጊዜ ጀምሮ የሚያውቀው አንድ መኪና ሰፊ ስለ ነበረ፥ መጀመሪያ ወደሱ ሱቅ ሄደው ደመቀችን ከሰፊው ጋር ካስተዋወቀ በሁዋላ የሄዱለትን ጉዳይ ገልጾ፣ ጨርቆችን ያነለት ገዝተው የሰጡት እንደሆነ በምን ያክል ዋጋና መቸ ሰፍቶ ጨርሶ እንደሚያስረክባቸው ተነጋግረው ተዋውለው እጮኞቹ ጨርቆችን ገዝተው ለማምጣት ሄዱ።

ከመኪና ሰፊው ሱቅ ቀኝና ግራ ፊትና ሁዋላ ያ ሰፈር በሙሉ የጨርቃ ጨርቅ ሱቅ ነው። ስለዚህ በሻህና ደመቀች ከሰፊው ሱቅ ወጥተው ከመንገዱ ባሻገር እዚያው ፊት ለፊት ‹አቶ በቀለ ዘሩ› በሚባሉ ሀብታም ጎጃሜ ሱቅ ገቡ። ሱቁ ከመስፋቱም ሌላ ዙሪያውን ከወለሉ እስከ ጣራው እዬተጨናነቀ የታጨቀው ልዩ ልዩ አይነት ጨርቅ ተሸጦ ያልቅ የማይመስል ግሩም ነበር! ያን ሰፊ አዳራሽ በቁሙ ከዳር እስከ ዳር በሁለት በከፈለው የመሸጫ ጠረጴዛ ጀርባ ነበሩ። ከሚያስተናግዱት ሰራተኞች ጀርባ ትንሽ ገባ ብለው ደግሞ አንድ ቀጭንና ወፍራም ሽማግሎች ተቀምጠው ቡና ቀርቦላቸው እዬጠጡ ይጫወቱ ነበር። ቀጭኑ የሱቅ ባለቤት አቶ በቀለ ዘሩ ወፍራም ባለቤቱን ለስራ ጉዳይ ሊያነጋግሩ የመጡ እንግዳ ነበሩ።

የዚያ ሁሉ ሀብት ባለቤት ሂሳብ ስለሚያውቁና የሂሳብ ሰራተኛም ቀጥረው ስለሚያውቁ ‹የውጭና የገቢ ሂሳብ መዝገብ ኖሮዋቸው አያውቅም› እዬተባለ ይነገርላቸው ነበር። ‹ጨርቅ ከውጭ መጣ› ሲባል፥ በገፍ ገዝተው በመጋዘናቸው አጭቀው እዚያ እያወጡ ሲ.ቃቸውን ከጣራው እስከ ወለሉ ሞልተው እዚያ ተደርድረው የሚሸጡት ሰራተኞች እዬሸጡ አምጥተው የሚሰጡዋቸው ገንዘብ እዬተቀበሉ አጠገባቸው ባለ የስድስት ቀን ገቢ ለዬብቻ የሚቀመጥበት ስድስት ኪሶች ያሉት የብረት ሳጥን ማኖር ነው። ታዲያ ማታ ሰራተኞች ከሄዱ በሁዋላ በለቱ የገባውን ገንዘብ - ብሩንም ሳንቲሙንም በየመልኩ አንድ ባንድ ቆጥረው በራሳቸው ይጽፉና ገንዘቡን መልሰው ለቀኑ በተመደበለት ቦታ አስቀምጠው የብረት ሳጥናቸውን ቆልፈው ደህና ሆኖ መቆለፉን ነቅነቅ አድርገው አረጋግጠው ይሄዳሉ። ራሳቸው ልክ እንደ መዝገብ የጻፉበትን ይዞ የሚኖር የታመነ ስለ ነበረ ‹በጣም ይተማመኑበት ነበር› ይባላል። በሳምንቱ መጨረሻ የስድስቱን ቀን ገቢ ከስድስቱ ኪሶች አውጥተው እንደገና ቆጥረው በራሳቸው ጽፈው ካስቀመጡት ጋር ካመሳከሩ በሁዋላ ሁሉንም አንድ ላይ ወስደው ባንድ ያገቡታል። ታዲያ ያን ሁሉ ጥንቃቄያቸውን አልፈው ከመጋዘናቸውም ሆነ ከሱቃቸው ሰራተኞች ብዙዎቹ ይሰርቁዋቸው ነእብር። ስርቆቱም አይን የሊለው

እውር ብዙዎቹ ይሰርቁዋቸው ነበር። ስርቆቱም አይን የሌለው እውር ስርቆት ስለ ነበረ እኒያ የሚሰርቁ ሰራተኞች ‹ከሶስት ቢበዛ ካራት አመት በሁዋላ አብረዋቸው አይቆዩም፤ ወጥተው የራሳቸውን የንግድ ቤት ይከፍታሉ› ይባል ነበር።

‹ከሰራተኞችዋ ብዙዎች ባዶ እጃቸውን መጥተው ባጭር ጊዜ ውስጥ ከርስዎ መወዳደር የሚያምራቸው ነጋዴዎች የሚሆኑ በርስዎ ገንዘብ መሆኑ እዬታወቀ ለምን ሁሉንም እዬተቆጣጠረ ገንዘብዎ እንዳባክን የሚጠብቅልዎ የታመነ የሂሳብ ሰራተኛ አይቀጥሩ?› ብለው ወዳጆቻቸው ሲመክሩዋችው፥

‹ወዬው ጉ - ድ! ሚካኤልን ነው ወይስ ገብርኤልን የሂሳብ ሰራተኛ አድርጌ የምቀጥር? ያው ሰው አደል የሚቀጠረው? ታዲያ ያ ሰው የታመነ መሆኑን ከሚሰርቁት ጋር ተሻርኮ የማይሰርቀኝ መሆኑን በምን አውቃለሁ? ስለዚህ ለተጨማሪ በላተኛና ለተጨማሪ ጭቅጭቅ ተጨማሪ ገንዘብ ከምከፍል ያሉት ይበቁኛል። ወዲያውም መስረቅ ነው እንጂ ክፉ፥ መሰረቅ ባገሬ ምርቃት ነው። ያገሬ ሽማግሎች ሲመርቁ «ተሰረቅ እንጂ አትስረቅ» ይላሉ። «አጥተህ የማትሰርቅ ተርፎህ የምትሰረቅ ሀብታም ሁን» ማለት ነው። ስለዚህ ፈጣሪየ ሀብቱን ሰጥቶኝ ጤናውን ካልነፈገኝ «ተስርቆም ተሰጥቶም የሚተርፈው ይበቃኛል» ይላሉ› ያብል ነበር። እውነትም ብዙ ሰራተኞቻቸው ባዶ እጃቸውን እዬመጡ ባጭር ጊዜ ውስጥ ጌቶች ሆነው የዬራሳቸውን የንግድ ቤት የሚከፍቱ በሳቸው ገንዘብ መሆኑን ቢያውቁም በተስረቀው ገንዘብ ከመበሳጨትና ከሰረቁት ሰዎች ጋር ከመጣላት ይልቅ፥ የተቻላቸውን ያክል ከተጠነቀቁ በሁዋላ፥ ከዚያ አልፎ ከሚሰረቀው የተረፈው በቆቶዋቸው በሰላም የሚኖሩ ነበሩ። አንዳንድ ጊዜም እንደ ተሰረቁ ማወቃቸውን፥ በቀልድ መልክ ለሰረቁት ሰራተኞች ለራሳቸው ይነግሩዋቸዋል። አንድ ቀን እሳቸው ሱቅ አጠገብ የነበረ ሱቅ መለቀቁን ሰምተው፥

«አንተ እገሌ» አሉ ከሶስት አመት በላይ የመጋዘናቸው ጠባቂ የነበረና እንደሚሰርቃቸው ይጠረጥሩት የነበረ ሰራተኛቸውን።

«አቤት ጌታዬ! »

«እዚህ ከኔ ጋር መስራት ከጀመርህ አራት አመት ሊሆንህ ነውኮ! እና እንግዲህ - ከዚህ ስትወጣ የምትከፍተው የጨርቃ ጨርቅ ሱቅ ሱቅ እንደሆነ እዚህ አጠገባችን ‹የእገሌ› ሱቅ ‹ተለቆዋል› ሲባል ሰምቻለሁና ቶሎ ሌላ ሰው ሳይቀድምህ ተከራየው» አሉ እዬተባለ ይነገርላቸው ነበር።

ስላቶ በቀለ ዘሩ፥ ሰው እያጋነነ የሚያወራው በሙሉ እውነት ላይሆን ቢችልም በገንዘብ ከመጨቃጨቅና ተካሰሰው ሙግት ከሜድ ተጎድተውም ቢሆን በሰላም ስራቸውን ብቻ መከታተል የሚወዱ መሆናቸው በሰፊው የታወቀላቸው ሰው ነበሩ። ስለዚህ ተሻርከውም ይሁን ተቀጥረው ከሳቸው ጋር መስራት የሚፈልጉ ሰዎች ብዙ ነበሩ። ያነለት አብረዋችወ ተቀምጠው ቡና እዬጠጡ ያነጋግሩዋቸው የነበሩት ሽማግሌም በሚያገቡት ወረት መጠን ሽሪካቸው ሆነው አዲስ አበባ አብረው ቢነግዱ ወይም ጎጃም ደብረ ማርቆስ ቅርንጫፍ የጨርቃ ጨርቅ ሱቅ ከፍተው እሳቸው ያን ቢያስተዳድሩ ይስማሙ እንደሆነ ሊጠይቁዋቸው የመጡ ነበሩ።

በሻህና ደመቀች እዚያ ሱቅ እንደ ገቡ ገብያተኛውን ከሚያስተናግዱት ሰራተኞች ወዳንዱ ቀርበው የፈለጉትን በሻህ ሲነገረው ባይነትም በቀለምም የተለያዩ ጨርቆች አምጥቶ እመሸጫው ጠረጴዛ ላይ አስቀመጠላቸው። ደመቀች እኒያን ጨርቆች እያገላበጠች ካዬች በሁዋላ የሁሉም ቀለሞቻቸው ደስ ስላላሰኙዋት እነሱን ትታ እማዶው መስቀያ ላይ እዬተደራረበ ወደ ተቀመጠው ጨርቅ ለማየት ቀና ስትል አይኖችዋ እስሩ ተቀምጠው በሚጫወቱት ሽማግሎች ላይ አረፉ። ስትገባ እኒያ ሽማግሎች እዚያ መቀመጣቸውን ልብ አላደረገችም ነበር። ካዬቻቸው በሁዋላ ግን አይኖችዋ ከነሱ ላይ አልተነቃነቁም! ከነሱ አንዱን ደህና አድርጋ የምታውቃቸው በሳቸው ላይ የተተከሉ አይኖችዋን መንቀል አልቻለችም! ከመወፈራቸውና ከማርጀታቸው በቀር በጠቅላላው ፊት - ውሀቸ በተለይ በግንባራቸው ላይ የሚታዬው እንጉዝ ሁሉም የኒያ ፊት የምታውቃቸው ሰው ናቸው! እንዲያ አይኖችዋን ሳታረግብ በላያቸው ተክላ ‹ነው? አደለም?› እያለች ባሳብዋ ስትቸገር ስለ ቀረቡላቸው ጨርቆች በሻህ መላልሶ ለጠዬቃት መልስ ስላልሰጠችው ቀና፥ ብሎ የመጣችለንት ጉዳይ ረስታ ወደ ሁለቱ ሽማግሎች አተኩራ የምትመለከት መሆንዋንና ፊትዋ መለወጡን ሲያይ፥

«ምነ፣ ምን ሆንሽ? » አላት። መልስ ሳትሰጠው እኒያ ሽማግሌ ከጉዋደኛቸው ጋር እዬተጫወቱ ሲስቁ፥ ከላይ ጥርሳችው ቀጥላ በግራ፥ በኩል ያለች አንድ ጥርሳቸው ‹ብልዝ› መሆንዋን ስታ የምታውቃቸው አረጋገጠችና፥

‹ልክ እሱ ነው!› አለች በሹክሹክታ ፊትዋ ክርር ግንባርዋ ኩስትር ብለው።

«ማን እሱ? » አለ በሻህ ያን የሚያውቀውን የቁጣ ምልክትዋን ሲያይ እንደ መደንገጥ ብሎ።

«እሱ ነው፤ እንሂድ ጋሼ ከዚህ ቶሎ እንውጣ» ብላ ዘወር ስትል፣ ‹ለምን?› ብሎ እንኳዋ ሳይጠይቅ፥ ዝም ብሎ ተከተላት። ከሱቅ ከወጡ በሁዋላ፥

«እንግዲህ ያስቆጣሽ ምን እንደሆነ አልገባኝምኮ ደመቁ። ‹እሱ ነው› ያልሽውስ ማነው ‹እሱ›? » አለ በሻ፥ ጠጋ ብሎ ክንድዋን ይዞ።

«ያብዬ አባት።»

«የልጅሽ አባት? »

«አዎ! »

«ታዲያ ቢሆኑ ምን ያደርጉሻል? »

ልብዋ ስለ ተሸበረና አሳብዋ እንደ ተበታተነ ስለ ነበረ ምን እንደምትመልስለት አታውቅም ነበር፤ ስለዚህ አለመለሰችለትም። እንዲያ ክንድዋ ይዞ እንደ ቆሙ፥ በዚያ ጠባብ መንገድ ተደራርቦ ይሄድ የነበረው የመኪና መንጋ ላንድ አፍታ ጋብ ሲል ተሻግረው እመኪና ሰፊው ሱቅ ገቡ። ከዚያ ወንበር አቅርቦ እስዋን አስቀመጠና፥

«እንካ እባክህ፥ ላንተ ጭምር ቶሎ ብና አስመጣ፥ ሞክሼ» አለ በሻህ፥ መኪና ሰፊውን አንድ ብር አውጥቶ። መኪና ሰፊውም እንደሱ፥ ስሙ ‹በሻህ› ነበር።

«እግዜር ይስጥልኝ! እኔ አሁን ነው የጠጣሁ። እንካ አንተ ሩጥና ሁለት ቡና አምጣ! » አለ ሰፊው ከበሻህ የተቀበለውን ብር ለልጁ ሰጥቶ።

ደመቀች፥ ከድንጋጤዋ ስትወጣ በጥልቅ አሳብ ውስጥ ጠልቃ አሳብ ሁለት ሞክሼዎች የተነጋገሩትን አትሰማም ነበር። ቡና ከመጣላቸው በሁዋላ በሻህ ሄዶ አጠገብዋ ሲቀመጥ ብቻ፥ ቡናው መጥቶ አጠገብዋ ተቀምጦ መኪና ሰፊው፥ አብሮዋቸው ከነበረበት ወደ ስራ ተመልሶ መኪና ሲሰፉ አዩችና ተንቀልፍታ እንደ ቆዩች ሁሉ አይኖችዋን፥ እያሻሸች ደጋግማ አርገብግባ፥ «እህ -» አለች ሳታስበው በረዥሙ ተንፍሳ።

«አይዞሽ! ለመሆኑ - ነጥቀው የሚወስዱሽ መስሎሽ ነው እንዲህ የደነገጥሽ? » አለ በሻህ ትንሽ የተረጋጋች ስለ መሰለው የቅርታ ፈገግታ በፊቱ እዬታዩ።

«ነጥቆ የመውሰዱ ነገር እንኩዋ - ለጊዜው አልታሰበኝም፤ እንዲያው ሳየው ብቻ ንደግጨ ራሴን አዞሮኝ ልውደቅ ነበር! ድንጋጤው ካለፈልኝ በሁዋላ ደግሞ ሌላ ነገር ታሰበኝና ፍራት ያዘኝ።»

«ምን ሌላ ነገር ነው ደግሞ ያስፈራሽ? »

«ሳንፋታ ጠፍቼ መምጣቴን በዬምክንያቱ ብዙ ጊዜ ስናገር ስለ ሰማህ መቸም ታውቃለህ፥ ጋሼ! ታዲያ - እዚህ አገር ነዋሪ ሆኖ እንደሆነ እዚህ አገር ባይኖርም ጋብቻችነን ካወቀ ችግር ሊፈጥር የሚችል አይመስልህም? » አለች ፍራትዋን በሚገልጽ አስተያየት ቀና ብላ አይን አይኑን እያዬች። ነገሩ እስዋም እሱም አስበውት የሚያውቁ አዲስ በመሆኑ፥ በሻህ ራሱን ደፋ አድርጎ ዝም ብሎ ሲያስብ ቆዬና፥

«እዚህ አገር ነዋሪ ካልሆነ እንኩዋ - የኛ ጋብቻ በራዲዮ አይነገር! ወይ በጋዜጣ አይጻፍ! እንዴት አድርገው ሊያውቁ ይችላሉ? ከጊዜ ብዛት ቢያውቁና የሚከስሱ ቢሆንስ - ምናልባት ‹ካሳና መቀጫ ክፈሉ› እንባል እንደሆን እንጂ፥ ሌላ ምን ይመጣብናል? ስለዚህ አትጨነቂበት፤ ምንም አደል። ብቻ ማናቸውም እስቲ - ልሂድና እዚህ አገር ተቀማጭ ሆነው እንደሆነ ልጠይቃቸው» አለ ራሱን ከደፋበት ቀና አድርጎ።

«እንዴት አድርገህ ትጠይቀዋለህ? »

«በልጅነቴ አገራቸው ለትምህርት ሄጄ እኖር የነበርሁና እዚያ የማውቃቸው መስዬ አነጋግራችዋለሁ። አገራቸው ‹ደብረ ኤልያስ ነው› ስትይ ሰምቻለሁ፤ ደብር ከሆነ ደግኖ - ያለ ጥርጥር ትምህርት ቤት ይኖራል! »

«ትምህርት ቤትስ - ከሩቅ አገር ሳይቀር እዬሄዱ የሚማሩበት የዜማ የቅኔና የሌላም ትምህርት ቤት አለ ብቻ ‹ሄጄ ላነጋግረው› ማለትህ አልወደድሁትም እንጂ» አለች ሄዶ የሚጠላ መስሎዋት ሰግታ።

«ግዴለሽም እንደማውቃቸው አሳምኜ እዚህ የሚኖሩ ወይስ ደርሰው ሊሄዱ የመጡ መሆናቸውን አረጋግጨ ነው የምመጣ» ብሎዋት ሄደ። ደመቀች ሰግታ ስለ ነበረ እስከ መኪና ሰፊው በር ድረስ ተከትላአው እዚያው ቆማ አቶ በቀለ ዘሩ ሱቅ እስኪገባ ትመለከተው ነእብር፡ እዚያ ገብቶ ሁለቱን ሽማግሎች ከነበሩበት ቦታ ስላጠቸው ‹አመለጡኝ› ብሎ አይኑ በያቅጣቻው ሲቃብዝ ከውስጥ ወጥተው ገበያተኛው በቆመበት ክፍል አንድ ጥግ ይዘው ቆመው ሲነጋገሩ አያቸውና ሄዶ፣

«ጤና ይስጥልኝ» አለ ትንሽ እጅ እንደ መንሳት ብሎ።

«ጤና ይስጥልኝ፥ ጤና ይስጥልኝ» አሉ ሁለቱም ንግግራቸውን አቋርጠው።

«ይቅርታ ያድርጉልኝና ጌታ፥ ቅድም እቃ ልገዛ ገብቼ እዚያ ውስጥ ተቀምጠው ዓይዎ የማውቅዎ መስሎኝ ላነጋግርዎ ካሰብሁ በሁዋላ ድንገት ‹መሰል› እንደ ሆኑ ብዬ ፈርቼ ዝም ብዬ ወጥቼ ነበር። ነገር ግን ከወጣሁ በሁዋላ - ስለ ጸጸተኝ ነው ተመልሼ የመጣሁ። እርስዎ - ጎጃም ደብረ ኤልያስ ልጅ ታምራት ተገኝ አደሉም? » አለ ባገጩ፥ ወደ ታምራት ተገኝ አመልክቶ። ታምራት አልመለሰም፤ ዝም ብሎ አይኖቹን በባሻህ ላይ ተክሎ ይመለከተው ጀመር።

«ግራዝማች ታምራት ተገኝ» አሉ የሱቁ ባለቤት አቶ በቀለ ዘሩ።

«ኦ - ! ይቅርታ ያድርጉል ግራዝማች እኔ የማውቅዎ በልጅነቴ የኤልያስ ቅኔ ቤት ስማር እርስዎም እንደ ዛሬው ሳይሸመግሉ ‹ልጅ ታምራት› እዬተባሉ የደብረ ኤልያስንና ያካባቢውን ወንበዴና ሽፍታ ሁሉ እያሳደዱ የሚማረከውን እዬማረኩ ‹አልማረክ› ያለውን እያቆሰሉ እዬያዙ ‹አመልማል ጐሜ› እያሰኙ በሚመለሱበት ጊዜ ያገሩ ህዝብ ደስ ብሎት በልልታ በሆታ ሲቀበልዎ ነው። ‹ግራዝማች› ሲባሉ አልነበርሁም። ለዚህ ነው የማእረግ ስምዎን ሳልጨምር በስምዎ ብቻ የጠራሁዎ። እና - ይቅርታ ያድርጉልኝ» አለ ሁለቱም ይቅርታ አሁንም ትንሽ እንደ መስገድ ብሎ። በሻህ ጀግናነቱን ሲያወራለት ታምራት ተገኝ ልቡ ተነክቶ የሽማግሌ ፊቱ ሁሉ የደስታ ፈገግታ ብቻ ሆኖ ዝም ብሎ ሲሰማ ቆዬና፥

«ኧረ ግዴለም ምንም አደል ግራዝማችነቱ ሁዋላ ተገድጄ በውድ ዋጋ የገዛሁት ነው ተወልጄ፣ እስከሞት የማይለዬኝ ዘምዴ እናቴ ያወጣችልኝ ስም ነው» አለ ታምራት እንደ መሳቅ ብሎ።

«እንዴት እባክህ? ደግሞ ተገድዶ በውድ ጋዋ የሚገዙት በውድ ጋዋ የሚገዙት ሹመት እንዴት ያለ ነው? » አሉ አቶ በቀለ ዘሩም እንደ መሳቅ ብለው።

«የማቻከል ገዥ የነበሩትን ደጃች ማስረሻን ታውቃቸው የለም? » አለ ታምራት ጉዋደኛውን እያዬ።

«በስም ብቻ ነው በቅርብ አላውቃቸውም።»

«መልካቸውን ባታውቅ መቸም ወሬያቸውን ደህና አድርገህ ሳታውቅ አትቀር፤ እዚያው ጎጃም ‹ከንጉሶች እወለዳለሁ› የሚሉ ናቸውኮ! ታዲያ እኒያ ሰው ከዘመዳቸው ከጎጃሙ ገዥ ጋር ተጣልተው አዲስ አበባ ሲመጡ ‹ፊታውራሪ› ነበሩ። እዚህ መንግስትን ደጅ እዬጠኑ፣ ለረዥም ጊዜ ሲጉላሉ ከቆዩ በሁዋላ መንግስት ከፊታውራሪነት የደጃዝማችነት ማእረግ ሰጥቶ ከጌታቸው ከጎጃሙ ገዥ ስለ መለሳቸው በኛው ክፍል በማቻከል ላይ ላይ ተሾመው መጡ። ከዚያው ወዲይማ - ምን ልበላቸው ‹እንደገና ወደሚ - ጉላሉበት አገር ሊሄዱ ነው› የተባሉ ይመስል ‹ገንዘብ ያለህ ና ወዲህ በለኝ› ይሉ ጀመር በሙሉ ማቻከል ‹ሀብት አለው የሚባለው ጉዛምን ነጋዴ ሁሉ በመብራት እዬተፈለገ ወደሳቸው እንዲሄድ አድርገው ከላይ ከፊታውራሪነት እስከ ታች እስከ ሻለቃነት ድረስ የያንዳንዱን የስም ማእረግ መሾሚያ ዋጋ ራሳቸው ቆርጠው እንደ ልቡ አርሶና ነግዶ እንዳይበላ በማእረግ ስም እያሰሩ ለቀቁት! እዩትላችሁ እኔም ያንጊዜ ነው ግራዝማችነቱን ሁለት ሸህ ጥሬ ብሬን ከፍዬ የተቀበልሁ! መቸም - የሙቀጫ ልጅ ይመስል እንዲያው ልጅ ስባል ከመኖር አንድ የማእረግ ስም ቢኖረኝ እወድ እንደ ነበረ አልክድም። ግን ስልፈገው ስመኘው የኖርሁት የማእረግ ስም እንደ ወጉ ካገር ግዛት ጋር ከክብር ጋር ነበር እንጂ - እንዲህ እንደ ሸቀጥ እቃ በብር የሚገዛ ስም አልነበረም! » አለ ታምራት ያገሩ ሰው ‹በዬክል ሌጦ የተገዛ የማእረግ ስም› እያለ የሚያሽሙዋጠው ትዝ ስላለው ፍርጥም አለና።

«መቸም ዋጋ ስለ ተከፈለበት የማእረግ ስም መሆኑ አይቀር! » አሉ አቶ በቀለም እንደሱ ፍርጥም ብለው።

«እንግዲህ ልሂድ፤ ኤልያስ አምስት አመት ያክል በትምርት ቤት ስኖር በዬ - ምክንያቱ ድግስ እያደረጉ ካህናቱን በጋበዙ ቁጥር እቤትዎ ብዙ ቀን የበላሁ ስለሆንሁ አይቸዎ ሰላምታ እንኩዋ ሳልሰጥዎ መሄዱ ከብዶኝ ነው፥ ከወጣበሁ በሁዋላ ተመልሼ እንኩዋ ሳልሰጥዎ መሄዱ ከብዶኝ ነው ከወጣሁ በሁዋላ ተመልሼ የመጣሁ። በተለይ - ‹እንዶዳሞ የደንግላይቱ› ከሚባል አገር ሚስት ሲያገቡ ያደረጉት ደግስ አይረሳኝም› ሲል በሻህ፥

«አ - እንዶዳሞ ኪዳነ ምህረት» አለ ታምራት እንደ መሳቅ ብሎ።

«አዎ እንዶዳሞ ኪዳነ ምህረት ማለቴ ነው። ያንጊዜ ያደረጉትን ድግስ ሳስታውሰው እኖራለሁ። እንዲያ ባለ ደስታ የጀመሩትን የጋብቻ ኑሮ አሁንም በደስታ

በሰላም እንደሚኖሩ ተስፋ አለኝ» አለ በሻህ ደመቀች ስትናገር የሰማውን እሱ ያዬውና የሚያውቀው አስመስሎ።

«እንዲያ ባለ ደስታ የተጀመረው ጋብቻስ - ሰላምና ደስታ ይዞልኝ በመምጣት ፈንታ አዘና አዘንና ብስጭት ጥሎብኝ ሄዶ - ከበሽታ ላይ ስለ ጣለኝ ይኸው ከድሜየ በፊት አረጀሁ።»

«እንዴት? » አለ በሻህ ያዘነ እንዲመስል ግንባሩን ቁጥር አድርጎ።

«አሁን እንደሚለው» አለ ታምራት ወዳቶ በቀለ ዘወር ብሎ «አሁን እንደሚለው ያች ከንዶዳሞ ያገባሁት ልጅ ስድስተኛ ምሽቱ ብትሆንም ከስዋ በፊት አምስቶቹን ምሽቶቼን በቀንጅነታቸው (በድንግልነታቸው) ሳገባ ላንዳቸውም ያን ያክል ድግስ ደግሼና እንደዚያ ጊዜ ደስ ብሎኝ አላውቅም! ቤትዋ የመሰረተ - ጌታ ቤት ስለሆነና ከዚያ ቤት ተጋብቶ መዋለድን ሰው ሁሉ የሚመኘው ስለ ነበረ በጣም ደስ ብሎኝ ነበር። ነገር ግን መጨረሻው የሚያሳዝን ሆነ።»

«እንዴት? ከፉ ነገር ደረሰ? » አለ በሻህ ግንባሩን ቁጥር እንዳደረገ።

«እንደ ተጋባን -ስትጸንስ ጊዜ ‹ምንም ቢሆን እኔ በት ከሚደረግላት የተሻለ ጥንቃቄ እናትዋ ሳያደርጉላት አይቀሩም› ብዬ እዚያ እንድትገላገል ሰድጀት ወንድ ልጅ ከወለደች በሁዋላ ልጄን ይዛ ጠፍታ እዚህ አገር መጣች። ታዲያ እየውልህ - ልጄን ከማጣቴም ሌላ እኔ ወደ ቤትዋ ልመልሳት እዬተመላለስሁ ደጅ ስጠና ገፍታኝ መሄድዋ በመፈልግና በማስፈለግ ጉልበቴንም ገንዘቤን ጨርሸ ተስፋ ቆርጬ ከተቀመጥሁ በሁዋላ አሁን በቅርቡ ‹ልጅህማ - ለትምርት በሀር ተሻግሮ ሄደልህ› ብለው መርዶውን ነግረውኝ እሱን ያገኘሁ መስሎኝ ፎቶውን ገዝቼ በመስታዋት አስገብቼ ራስጌዬ አስቀምጬዋለሁ» አለ ታምራት፥ እዬተከዘ።

«የልጁ ለትምርት ወደ ፈረንጅ አገር መሄድስ ደስ የሚያሰኝ ነው እንጂ የሚያሳዝን ‹መርዶ› አይባልም። እናቱስ አሁን እዚህ አዲስ አበባ ናቸው ማለት ነው? » አለ በሻህ።

«ፊት ወዲህ መምጣትዋን ነው እንጂ አሁንማ - ትኑር ትሙት ምኑን አወቅሁት? ‹ሞታለች› የሚሉም፥ ‹ፈረንጅ ቤት ገብታ ትሰራለች› የሚሉም አሉ። እስንቱ ፈረንጅ ቤት ሄዶ መፈልግ ይቻላል? አዲስ አበባ የሰው ዱር ነው፤ እንኩዋንስ እንዲህ ባለው

የሰው ዱር በንትሽ መንደርስ ቢሆን ‹አውቆ የተሸሸገ ቢጠሩት አይሰማም› እንደሚሉት አደል? አውቃ ይተሸሸገችውን ማን ሊያገኛት ይችላል! »

«ደህና ከሆኑስ - ጊዜ ይወስድ ይሆናል እንጂ ይገኛሉ። እስቲ ስማቸውን ይንገሩኝና እኔም ላስፈልግ።»

«ባገኛትስ - እንዲያው ‹ረግጣው ሄዳ አልፍታው ቀረች ከመባል ብዬ እልክ ይዞኝ ነው እንጂ ይህን ያክል ዘመን ከስንቱ ጎረምሳ ጋር ስትዘል ኖራ እኔም እንዲህ - ካረጀሁ በሁዋላ ‹ምሽት ትሆነኝ› ብዬ ነው? እንዲያው አሁን እንዳልሁህ ጥቃት ስለማልወድ አንድ ጊዜ በጄ አግብቻት ከዚያ በሁዋላ እንኩዋን እስዋ መሄድ ፈልጋ እኔም ከስዋ ጋር ባንድ ቤት ማደር አልፈግሁ! እና - እንዲያው ለማናቸው ስምዋ ‹ደመቀች ጸሀይ› ነው። »

«ድንገት ወሬያቸውን ያገኘሁ እንደሆነ የት አገኘዎታለሁ? አዲስ አበባ ነዋሪ ሆነው እንደሆነ አድራሻዎችን ቢነግሩኝ» አለ በሻህ።

«ለጊዜው እዚያው አገሬ ደብረ ኤልያስ ስለሆንሁ ባንድ ሳምንት ውስጥ፥ ሳልመለስ አልቀርም። ወደፊት ግን - ጭነት እያስጫኑ ከጎጃም እዚህ ከዚህ ጎጃም ለመመላለስ ያቅሙ ነገር የሚያወላዳ እዩሆነ ስለ ሄደና ወረትን አምኖ የሚሰጡት ባላደራም ዛሬ ማግኘት ስለማይቻል የሚሳካልኝ ከሆነ ራሴ ተቀም -ጨ የምከታተለው አንድ ሱቅ መሳይ እዚህ ያለዚያ ደብረ ማርቆስ ለመክፈት ነው የማስብ። የኔ ነገር ኤልያስ ለትናንሽ ሽቀጣ ሽቀጥ ነው እንጂ ከዚያ ከፍ ላለ ነገር አይሆንም፤ ገብያው ጠባብ ነው።»

«ደግ እንግዲህ - እርስዎ ከሄዱ በሁዋላ የሜቴን ወሬ ያገኘሁ እንደሆነ ላቶ በቀለ ጽፌ ብሰጣቸው ይደርስዎ የለም? » አለ በሻህ በፊቱ ወደ በቀለ አመልክቶ።

‹ይደርሰኛል ይደርስዋል› አሉ ሁለቱ ሽማግሎች እስበሳቸው ተያይተው እዩተቀባበሉ። አቶ በቀለን በማያውቁት ሰው በመታወቃቸው ካንድ ወገን ኩራት ሲሰማቸው ከሌላ ወገን ደግሞ በሻህን ‹ምናልባት ሰላይ ይሆን?› ብለው ጠረጠሩት።

«ስምህንኮ አልነገርኸንም» አሉ አቶ በቀለ በሻህ ለሁለቱም የጅ ሰላምታ እዩሰጠ ሲሰናበት።

«አ! ይቅርታ አድርጉልኝ በሻህ ዘለሌ እባላለሁ። እንዳትረሱት ጻፉት።»

«ግዴለም፥ ሁለታችንም የጥንት ነጋዴዎች ስለሆን እንረሳም። የጥንት ነጋዴ በራሱ እንጂ በወረቀት ጽፎ አያውቅም» አሉ አቶ በቀለ ዘሩ እዬሳቁ። በሻህ እንደ ተለያቸው፣

«በል እንዲህ እኔም ልሂድና ነገ ልመለስ አንተም እስቲ በነገሩ አስበህበት እደር» አለ ታምራት ሲነጋገሩበት ስለ ቆዩት፥ ስለ ሽርክናው ጉዳይ።

ደመቀች እበሻህ ከሄደበት ጊዜ ጀምራ ከልጅ አባትዋ ጋር ‹ይጣላ ይሆን?› ብላ ሰግታ የገብያተኛውን ጫጫታ ነፋስ ጎላ አድርጎት ባሰማት ቁጥር ተነስታ ወደ በር ሄዳ ወዳቶ በቀለ ሱቅ ስትመለከት አማን መሆኑን ካዬች በሁዋላ ተመልሳ ስትቀመጥ፥ እንዲሁ በያጭጫሩ ጊዜ እዬተነሳች ወደ በሩ ሄዳ አይታ ስትመለስ ቆይታ በመጨረሻ መንገዱን እዬሮጠ ተሻግሮ ሲመጣ ስታየው ነፍስዋ ገባች።

«አነጋገርኸው? » አለች ገና ሳይቀመጥ።

«አዎ ተነጋገርን። አገራቸው እንደሚኖሩና አሁን በስራ ጉዳይ ደርሰው ለመሄድ እንደ መጡ ነገሩኝ» አለ በሻህ ‹ወደ ፊት አዲስ አበባ ወይም ደብረ ማርቆስ ለመኖር አስባለሁ› ያለውን እንዳትሰጋ ሰውሮ። ከዚያ ታምራት ግራዝማች መባሉንና ያን ስም እንዴት እንዳገኘው ላቶ በቀለና ለሱ ያወራላቸውን ሊነግራት ሲጀምር አንድ ታክሲ ሰው ድጦ ብርቱ ጫጫታ ስለ ሰሙ፥ በሻህ ተነስቶ ወደ በሩ ሂዶ ቢያይ፥ ካቶ በቀለ ሱቅ ፊት ለፊት በቆመው ኦቶብስ ዙሪያ እጅግ ብዙ ህዝብ ተሰብስቦ እስበሱ እዬተገፋፋ ይተራመሳል።

ከመጀመሪያ እዚያ የነበረ ያይን ምስክር ሁዋላ ለበሻህ እንደ ነገረው ‹አንድ ሽማግሌ ከሱቅ ወጥተው መንገዱን ሊያቋርጡ ሲሞክሩ ኦቶብሱ ስለ ደረሰባቸው የሚያልፍ መስሎዋቸው ተመልሰው እመንገዱ ዳር ይቆማሉ። ኦቶብሱ እዚያ መቆሙን ካዩ በሁዋላ በስተፊቱ መንገዱን ቶሎ ለመሻገር ሮጥ ሮጥ እያሉ ሊሻገሩ ትንሽ ሲቀራቸው ከኦቶብሱ በስተግራ ፈጠን ብሎ ከሚሄድ ታክሲ ጋር ሳይተያዩ ይገናኙና በላያቸው ይሄድባቸዋል። ከዚያ ባለ ታክሲው ደንግጦ ቶሎ ያቆምና እስሩ የወደቁትን ሰው ለማዳን ወደ ሁዋላ ለማፈግፈግ ሲሞክር ከሰውዬው በመሸሽ ፈንታ ይብሱን ይደቁዋቁሳቸዋል! የኒያ ሰው እንኩዋንስ ነፍሳቸው ሬሳቸው በሲማው እንዳለ አልተገኘም። ራሳቸው ተፈጥፍጦ እጆቻቸውና እግሮቻቸው ተሰባረው ሁልመናቸው በደም ተለውሶ አገላብጦ ላላያቸው ማን መሆናቸውን ማወቅ አይቻልም ነበር!›

ግርግሩ ጸጥ ካላና ኦቶብሱም ከሄደ በሁዋላ የሆነውን ጠይቆ ለመመለስ በሻህ አደጋው ወደ ደረሰበት ስፍራ ሲሄድ አቶ በቀለንና አንዳንድ ሰራተኞቻቸውንው ከፖሊሶች ጋር ባንድ ላይ ቆመው ሲነጋገሩ ስላገኛቸው ቢጠይ፥ ያ አሰቃቂ አደጋ የደረሰበት ታምራት ተገኘ መሆኑን ነገሩትና በጣም ደነገጠ። አስከሬኑን የፖሊስ መኪና እስኪደርስላቸው ልብስ አልብሰው እሱቁ በረንዳ ላይ አስቀምጠውት ነበር። የሚረዳው ነገር እንዳለ አቶ በቀለን ጠይቆ ምንም የሚያደርገው ነገር አለመኖሩን ከነገሩት በሁዋላ ወደ ደመቀች ተመለሰ።

«የምታውቀው ሰው ነው የተዳጠ? » አለች ደመቀች የፊቱን መክበድና ያይኖቹን መደፍረስ ስታይ፤

«አዎ» አለ፥ ራሱን እንደ መድፋት አድርጎ።

«ማነው? እኔም - የማውቀው ይሆን? » አለች እዬፈራች።

«ግራዥማች ታምራት ተገኘ» አለ የደረሱ አይኖቹን ወደስዋ ቀና አድርጎ።

ደመእቅች አይኖችዋ በሱ ላይ እንደ ተከለች ደርቃ በድን ሆና ቀረች! ነፍስ ካወቀች ጀምራ እንደ ታምራት ተገኘ የምትጠላውና የምትፈራው ኖሮ አያውቅም! በጽኑ ጥላቻዋ የተነሳ እንኩዋንስ ሌላ ገድሎት አለመቻልዋ ነው እንጂ የምትችል ብትሆን ራስዋ ብትገድለው ደስ የሚላት ይመስላት ነብር! ከሱ ለመራቅ ካገርዋ ሸሽታ አዲስ አበባ ስትኖር እንኩዋ ለብዙ አመታት እሱን ባሰበች ቁጥር እሱ በሌልበትም እኩይ መንፈሱ ያልተለያት ባጠገብዋ ያለ እዬመሰላት ትፈራ ነእብር። አንድ ወንድ እንደ ባል አምርራ ትጠላው ስለ ነበረ ለብዙ ጊዜ ለግብረ ስጋ ወይም ለጋብቻ ጉዋደኝነት ሊቀርቡዋት የሞከሩትን ሌሎች ወንዶች ሁሉ ትጠላቸውና ትፈራቸው የነበረ በሱ ምክንያት በሱ አይን እያዬቻቸው ነበር። ነገር ግን ያነለት በዚያ አደጋ መገደሉን ስትሰማ የስዋ እንዲያ ከመጠን አሳልፎ መጥላት እንደ ገደለው ሁሉ ያን ያክል ስትጠውላው ኖራ በመገደሉ እስዋን የገዳዩ ተባባሪ እንደሚያደርጋት ሁሉ ልታውቀው ባልቻለች ምክንያት የበደለኛነት የወንጀለኛነት ስሜት ተሰማትና ልክ ተገድዶ ነፍስ እንደ ገደለ ሰው ምርር ብላ አለቀሰች! በሻህ ‹ለልጅ አባትሽ አታልቅሽ› ብሎ መገላገሉ በሌላ እንዳይተረጎም በገዛ እጅዋ ዝም እስክትል ዝም ብሎ ሲመለከታት ቆይቶ፥

«መጠሪያቸው ይህ እንዲሆን አስቀድሞ ከፈጣሪ የታዘዘ በመሆኑ ነው፥ ካገራቸው መጥተው ዛሬ እዚህ እንዲህ ባለ አደጋ የሞቱ። ስለዚህ - ትእዛዙን

በትእግስት ከመቀበል በቀር ምንም ማድረግ አይቻልምና ተነሽ እንሂድ» አለ ቀድሞ ተነስቶ።

«ቅርብ ዘመዳቸው ኖረዋል? » አለ መኪና ሰፊው ደመቀች ልትሂድ ስትነሳ። ቀደም ብላ ያለቀሰችውን መሪር ልቅሶ አይቶ ስለ ነበረ።

«አዎ፥ ዘመድ ነበሩ» አለ በሻህ።

## ምእራፍ ሰላሳ ስምንት

# ክፉ ቁራኛ ለቅቆ ሲሄድ አስለቅሶ ነው!

ደመቀችና በሻህ በታምራት ተገኘ ላይ የደረሰው አደጋ አደንዝዞዋቸው አድብኖዋቸው ከመኪና ሰፊው ሱቅ ወጥተው በታክሲ አዛዥ ተካልኝ ቤት እስኪደርሱ ሁለቱም አፍ አፋቸውን የተለጎሙ ይመስል ሳይናገሩ ዝም እንዳሉ ነበር የደረሱ። ታክሲ ነጂው ሲለፈልፍ እንኳዋ መልስ መስጠት ይቅርና አይሰሙትም ነበር። ያ ታክሲ እንጂ ሊያስቃቸው ፈልጎ ወሬ እዬለዋወጠ ‹የባጥ የቆጡን - የቆን› ለፍልፎ ከነሱ እንኳዋንስ ሳቅ የቃል መልስ ባለማግኘቱ ዘወር ቢል ሁለቱም እንዳዘንተኞች አንገታቸውን ደፍተው ስላያቸው ‹የተኩዋረፉ ባልና ምሽት ወይም ፍቅረኞች ሳይሆኑ አይቀሩም› ብሎ ‹ኤ! እንዲህ እርቀ - ሰላሙን ያውርድላችሁ እንጂ እኔ ምን ላድርጋችሁ!› እንደሚል ሁሉ አፉን ገጥሞ አገጩን ወደ ታች ሳብ ትከሻዎቹን ወደ ላይ ገፋ አደረገና እሱም ዝም አለ።

«ምነ የምትፈጉትን አጥታችሁ ነው ባዶ እጃችሁን የመጣችሁ? » አሉ ወይዘሮ ጌጤ ሁለቱ እጮኞች ከታክሲው ወርደው አጥሩን ሲገቡ፥ እሳቸው እውጭ ስለ ነበሩ።

«እሱስ ሞልቶ ነበር ብቻ - መምረጡ አቅቶት ‹እርስዎ ጭምር ባሉበት መርጠን ብንገዛ ይሻላል› ብለን ትተነው መጣን እንጂ» አለ በሻህ። ደመቀች ምንም ሳትናገር ገብታ በቀጥታ ወደ ምኝታ ቤትዋ ሄደች።

«ምነ ምን ሆነች? » አሉ ወይዘሮ ጌጤ ሁኔታዋን ሁሉ ሲያዩ እንደ መደንገጥ ብለው።

«የመኪና አደጋ ደርሶ ሰው ሲሞት አይታ፥ ደነገጠችና ‹ራሴን አመመኝ› አለች።
»

«ቡና ያሸላት ይሆን? »

«ቡና እንኩዋ - እዚያ እማውቀው መኪና ሰፊ ሱቅ ጠጥተን ነበር፤ ግን አልረዳትም። ምናልባት ስትተኛ ያልፍላት እንደ ሆነ፥ እስቲ እንተዋት» አለና በሻህ ገብቶ ጠላ እንዲጠጣ ወይዘሮ ጌጤ ቢለምኑት በቀጠሮ አመካኝቶ ይቅርታ ለምኖዋቸው ሄደ።

ደመቀች በልጅነትዋ ልጅ አዝላ አገርዋን ትታ ወደማታውቀው አገር ተሰደደች የልጅ አባትዋ አምርራ ከመጥላትዋና ከመፍራትዋ ብዛት የተነሳ መሆኑን ካዛዥ ተካልኝና ከወይዘሮ ጌጤ ብቻ ሳይሆን ከስዋ ጭምር በዬጊዜው በዬምክንያቱ ሲሰማ ኖሮ ያነለት ከራስዋ ጭምር ያን ያክል ያዘነችበትና ያለቀሰችበት ምክንያት ወደ ሲሄድ በመንገድም እቤቱ ከደረሰ በሁዋላም በሻህ ካሳቡ አውጥቶ አውርዶ ሊገባው አልቻለም፣ እንኩዋንስ እሱን እስዋንም ሊገባት አልቻለ!

እመኝታ ቤትዋ ገብታ ከነልብስዋ ትራስዋን ከፍ አድርጋ ተደግፋ አልጋዋ ላይ ጋለል እንዳለች አሳብዋን ከደነዘዘበት ማሰብና መስራት ሲጀምር አቶ በቀለ ዘሩ ሱቅ አይኖችዋ ጨርቅ ፍለጋ በሄዱበት ታምራት ተገኘን ማየትዋ ከዚያ ደንግጣ መውጣትዋ ከዚያ በሻህ ሊያነጋግረው ሄዶ ተመልሶ የተነጋገሩትን ሲያወራት የመኪና አደጋ ደርሶ ረብሻ መሆኑ ከዚያ ባደጋው ታምራት ተገኘ መሞቱን ስትሰማ ሳትስበው ያለውድዋ መራር ልቅሶ ማልቀስዋ ‹ለምን እንዲያ አለቀስሁ!› አለች ያሰበች መስሎዋት ድምጽዋን አሰምታ።

ከዚያ፥ መልሱን ጣራዉ ይነግራት ይመስል አይኖችዋን ሳታረግብ እሱ ላይ ተክላ ዘለግ ያለ ጊዜ ከቆዬች በሁዋላ አሳብዋ አይኖችዋን እዚያው በተተከሉበ ትቶ ታምራትን ካቶ በቀለ ጋር ተቀምጦ ሲስቅ ወዳዬችበት ቦታ ሄደ። ያነለት ካቶ በቀለ ጋር ተቀምጦ ሲስቅ ያየችው ታምራት ከፊት ውህውና ከብልዝ ጥርሱ በቀር ድሮ ኤልያስ ከምታውቀው ታምራት ፈጽሞ የተለዬ ነበር። ያንለት ያዬችው ታምራት ሆዱን ነፍቶ ለብቻ እፊቱ ያስቀመጡት ትልቅ ስልቻ የመስለ ኩልኩልቱ አገጩን እላይ ትቶ ወርዶ በደረቱ ላይ ሊነጠፍ ምንም ያክል ያልቀረው የፊቱ ቆዳ ሳይወጠር እንደ ደረቀ አንጋሬ የተጨመታተረ የራስ ጠጉሩ ከቀኝና ከግራ ጆሮዎቹ በላይ እንዲሁም ከሁዋላ እማጅራቱ አቅራቢያ ትንሽ ሲቀር ሙልጭ ብሎ የተመለጠ ከመሆኑ ሌላ ያሞጠሞጠ

በምንም በምኑ ድሮ ኤልያስ የምታውቀውን ታምራትን የማይመስል ነበር። ግን ያ ሁሉ ይሁን እንጂ ታምራት መሆኑ፥ በፊት ውህው ይታወቅ ነበር።

ታምራትን ኤልያስ ትታው ከሄደችበት ጊዜ ጅምራ እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ በህልምዋ ሳታየው የምታድርበት ሌሊት አልፎ አልፎ ነበር። የሚበዛውን ጊዜ በህልምዋ እዬመጣ ሲያስፈራራት ሲያስጨንቃት ነበር የሚያድር። ታዲያ ሁልግዚኤም በምታውቀው ወይም በውነተኛ መልኩ መጥቶባት አያውቅም። አንዳንድ ጊዜ ከግሩ እስካንገቱ ጠጉሩ ከመጠን አልፎ የጎፈረ ወይም ጨርሶ የተመለጠ ትልቅ ውሻ ካንገቱ በላይ ፊቱ ብቻ ታምራት ሆኖ ይመጣባታል! ለኢላ ጊዜ ከግሩ እስካንገቱ ችጋር ያከሳው ነብር ወይም አንበሳ ካንገቱ በላይ ፊቱ ብቻ ታምራት ሆኖ ይመጣባታል! ደግሞ ሌላ ጊዜ ፊቱ የታምራት የሆነ ያይጥ መንጋ ተሰብስቦ ሊቀራመታት ይከባታል። እንዲሁም ሌላ ጊዜ ከግሩ እስካንገቱ ስጋ ያልጎረሰና ቆዳ ያልለበሰ አጽም ብቻ ካንገቱ በላይ ፊቱ ታምራት ሆኖ ይመጣባታል! ያነለት እበቀለ ዘሩ ሱቅ ያዬችውም ያውሬ መልክ አይኑረው እንጂ ድሮ የምታውቀው ታምራት አልነበረም። ከፊት ውህውና ከጥርሱ በቀር በልዩ ልዩ ያውሬና ያስከሬን መልክ በህልምዋ እዬመጣ ሲያስፈራራት እንደ ኖረው ሁሉ የሚያስፈራ ነበር!

ያንለት እበቀለ ዘሩ ሱቅ ያዬችው ታምራት ከዚያ በፊት በልዩ ልዩ መልክ በህልምዋ እዬመጣ ሲያስፈራራት የኖረውን የሚመስል መሆኑን ስታስብ በቆዬች መጠን አእምሮዋ እንደ መታወክ አለና እሱንም ያንለት ያዬችው በህልምዋ ይሁን በውንዋ እርግጠኛ መሆን አቃታት! ‹በህልሜ ይሆን ያዬሁት?› አለች፤ ትራስዋን ተደግፋ አልጋዋ ላይ ጋለል እንዳለች አይኖችዋን ሳታረግብ እጣራው ላይ ተከላ፣ ያነለት ታምራትን ያዬችና ሞቱን ሰምታ ያለቀሰች በህልምዋ አለመሆኑን በውንዋ መሆኑን የሚያረጋግጥ ማስረጃ እንዲያመጣ አእምሮዋን አጥብቃ ባስጨነቀችው መጠን ራስዋ ይዞርባት ልብዋ ይሸበርባት ስለ ጀመረ ፍራት ያዛት። ወዲያው እኒያ በህልምዋ እዬመጡ ሲያስፈራርዋት የኖርሩት የታምራት ፊት ያላቸው ልዩ ልዩ አውሬዎች አስከሬኖችና እበቀለ ዘሩ ሱቅ ያዬችው ታምራት ጭምር ባንድ ላይ ሆነው እጭዋታ ሜዳ ተሰብስበው እያወኩ ‹ጅው - ጅው› ጭዋታ ወደ ታች ሚጫወቱ ህጻናት በራስዋ ውስጥ ወደ ላይ እዬጉዋኑ ወደ ታች እዬወረዱ ዙሪያ እዬዞሩ ራስዋ እኪዞር ጅሮዋ እስኪደነቁር መንጫጫት ስለ ጀመሩ ‹ምንድነው ይሄ? ላብድ ነው እንዴ!› አለች ጋለል ካለችበት ቀና ብላ ተቀምጣ አይኖችዋን እዬመላለሰች እያሻሸችና ገለጥ ከደን እያደረገች። ያ ያራዊትና ያስከሬን መንጋ እንዲያ ሽቅብ እዬጉዋነና ቁልቁል እዬወረደ ዙሪያ እዬዞረ የሚያውከ ባካላውያን አይኖችዋ ፊት እንደሆነ ሁሉ አይኖችዋን ገለጥ

ከደን፥ ባደረገች መጠን ባይነ - ህሊናዋ ፊት ውካታው ጫጫታው እዬጨመረ እዬባሰ ስለ ሄደ እውነት የታመመች መስሎዋት ካልጋዋ ዘልላ ሄዳ በሩን ከፍታ፥

«እማማ፥ እማማ፥ እማማ» ስትል፥

«ደመቄ» አሉ ወይዘሮ ጌጤ ‹አቤት› ለማለት።

«እማማ፥ ይምቱ ቶሎ» ብላ በሩን ዘግታ ወደ አልጋዋ ከመመለስዋ ወይዘሮ ጌጤ እንኩዋ ገና ሳይገቡ ያ በራስዋ ውስጥ እዬተተራመሰ ያወካ የነበረው ያራዊትና ያስከሬን መንጋ ወይዘሮ ጌጤ ማስፈራሪያ እንደ ሆኑ ሁሉ ስማቸው ሲጠራ ድራሹን ጠፍቶ ጸጥ አለች። ቢሆንም ገና የመጨነቅ መልክ ይታይባት ነበር።

«ምነ ምን ሆንሽ? አልተኛሽም? » አሉ ወይዘሮ ጌጤ ያን የመጨነቅ መልክ ስላዩባት ትራስዋን ተደግፋ አልጋዋ ላይ ጋለል እንዳለች ባጠገብዋ ተቀምጠው ፊትዋን እዬደባበሱ።

«ልተኛ ብሞክር ያሚያስፈራራው ነገር ሁሉ ተሰብስቦ እዬመጣብኝ መተኛት አልቻልሁም፤ ፈራሁ።»

«እኔማ - በሻህ ‹መኪና ሰው ድጦ ሲገድል አይታ ሰውነትዋ በድንጋጤ ስለ ታወከ ብቻዋን እንተዋትና ትረፍ› ብሎኝ ስለ ሄደ ተኝተሽ ድንጋጤው እስኪያልፍልሽ ነበርኮ - ሳልመጣ የቆየሁ» ሲሉ ወይዘሮ ጌጤ ያ ያነለት የሆነው ህልም የሚመስል ነገር ሁሉ እውን መሆኑ ተረጋገጠላትና ‹እ -› አለች የቆዬችበት ጭንቀት ለቀቅ ሲያደርጋት በፊትዋ እዬታዬ።

«ለመሆኑ ያን ያክል ያስደነገጠሽ ምንድነው? መኪና የዳጠውን ሰው ታውቂው ኖሮዋል? »

«ደመቀች መልስ ከመስጠትዋ በፊት መከዳዋን ከተደገፈችበት ቀና ብላ ተቀምጣ ትንሽ ስታስብ ቆዬችና ያነለት የተዳጠው ሰው ብዙ፥ ጊዜ እንደ ነገረቻቸው ያ አገርዋን አስለቅቆ ያባረራት፥ አጥብቃ የምትጠላውና የምትፈራው የልጅዋ አባት መሆኑና ሞቱን ስትሰማ ሳታስበው ያለውድዋ የምትወደው ሰው የሞተባት ይመስል ሰውነትዋን መቆጣጠር እስኪያቅታት እዬተንቀጠቀጠች ማልቀስዋን በዝርዝር ከነገረቻቸው በሁዋላ፥

«ምንድነው እንዲያ ያስለቀሰኝ እማማ? ፊትኮ - እንኩዋንስ ሌላ ሰው ሲገድልልኝ የምችል ብሆን እኔ ራሴ ብገድለው እወድ ነበር! » አለች።

«ህ! አንድያውን ለሁልጊዜ ትቶሽ ስለ ሄደ ነዋ! ድሮውንስ የሚጠሉት - ክፉ ቁራኛ ክፉ መንፈስ በጠሎትና በጠበል አንድያውን ለቅቆ ሲሄድ አንቀጥቅጦና አስለቅሶ አደል? » አሉ ወይዘሮ ጌጤ ደግ ፊታቸው በቅርታ ፈገግታ ተውቦ እዚያ እንደ ተቀመጠች አይን አይንዋን እያዩ። እንዲያ ፊታቸው በፈገግታ እንደተዋበ ትክ ብለው ሲያዩዋት በዚያ አስተያየታቸው የፈገግታ መልእክት እንዳስተላለፉላት ሁሉ የስዋም ውብ ፊት በፈገግታ ይበልጡን ተውቦ አንገታቸውን እቅፍ አድርጋ ይዛ ሳመቻቸው። እውነትም ሊገባት ባልቻለ ምክንያት ያ እስከዚያ ድረስ እንደ ብርቱ ቁራኛ በሄደችበት እዬተከተለ ሲያስጨንቃት የኖረው የታምራት ተገኘ ክፉ መንፈስ እያንቀጠቀጠ ካስለቀሳት በሁዋላ አንድያውን ለቅዋት እንደ ሄደ ሁሉ ዳግመኛ ሳይመለስባት ተፈጥሞ እንደ ሄደ ሁሉ እስከዚያነለት ድረስ ተሰምቶዋት የማያውቅ የነጻነትና የደስታ ስሜት ተሰማት! ሰውነትዋ መሬት ለቅቆ መብረር የሚችል መስሎ ተስማት!

በማግስቱ ከስራዋ እንደ ተመለሰች በሻህ ሲመጣ ትናንቱን ይታይባት የነበረው ከባድ ሀዘን ምልክቱ እንኩዋ ጠፍቶ በዚያ ፈንታ ፊትዋ ሁሉ በደስታና በፈገግታ በርቶ አገኛትና እሱንም ደስ አለው።

«ደህና እንቅልፍ አግኝተሽ የትናንቱ ድንጋጤ ሁሉ አለፈልሽ? » አለ ልብስዋን ለውውጣ፥ ሁልጊዜ እቤት ስትቆይ እንደምታደርገው ባገርዋ ልብስና በነጠላ ጫማ ከወይዘሮ ጌጤ ጋር ተቀምጠው ይጫወቱ ስለ ነበረ ለሁለቱም የጅ ሰላምታ ሰጥቶ ከተቀመጠ በሁዋላ።

«እንደ ትናንት የሰላም እንቅልፍ ተኝቼ አላውቅም ጋሼ። ራቴን በልቼ አልጋዬ ላይ እንደ ወደቅሁ ካንድ ጎኔ ሳልገላበጥ ነው ሌሊቱ የነጋ! እና - እንዲያ ያለ የሰላም እንቅልፍ ተኝቼ ስላደርሁ ነው መሰለኝ - ዛሬም ደስ ቀኑን ሙሉ ድካም ሳይሰማኝ እንደ ዱሮው ሳይቸከኝ ደስ ብሎኝ ስሰራ ነው የዋልኩ።»

«እሰይ እንኩዋን ሁሉም አልፎ ደህና ሆንሽ። እንግዲህ ሁል ጊዜም ዛሬው ሳይቸክሽ ደስ እያለሽ እንድትሰሪ እማማም እኔም ተስፋ አለን! » አለና ሳይነበብ የሚተረጎም መልእክት በሚያስተላልፍ አስተያየት ከፈገግታ ጋር እስዋንም ከወይዘሮ ጌጤንም እያለዋወጠ አይቶ አይኖቹን መልስ ሲያደርግ ሁለቱ ሴቶች፥ እስበሳቸው ተያይተው ትናንቱን የተነጋገሩት ትዝ አላቸውና ተሳሳቁ። በሻህ የደመቀች እጮኛ እንደ

መሆኑ ስለ ልጅዋ አባት አሞሙዋት ከዚያ አልፎ መናገር ተገቢ ስላልመሰልው ሰአቱን አዩና፥

«እንግዲህ ልሂድ። እንዴት አድረሽ እንደ ዋልሽ ለመጠዬቅና እማማ ጭምር ባንድ ሂደን እቃ የምንገዛበትን ቀን ለመቃጠር ነው እንጂ አሁን የመጣሁ የምቸኩልበት ስራ አለኝ» አለ።

«እየውልህ የኔን ነገር ዘመድ ሲመጣ የማቀርብላት መስተንግዶ ወሬ ነው! እባክህ ባይሆን ከወሬው በሁዋላ እንኩዋ አንድ ብርጭቆ ጠላ ጠጣና ሂድ» ብለው ወይዘሮ ጌጤ፥ ራሳቸውን እዬወቀሱ ብድግ ሲሉ፥

«የለም ዛሬ አልጠጣም እማማ ለሌላ ቀን ይሁንልኝ። ዛሬ እከበባችን ባንድ ሰአት ስብሰባ ስላለ፥ እዚያ ቀድሜ መገኘት አለብኝ» ብሎ አብሮዋቸው ስለ ተነሳ እቃ ለመግዛት ወይዘሮ ጌጤ ጭምር ገብያ የሚሄዱበትን ቀን ወስነው ሄዱ።

ተከስተ ተፈሪ መኮንን ትምህርት ቤት በነበረበት ጊዜ ሁሉ ደመቀች እሁድ እሁድ ስትወስድለት ሀኪም ቤት የምትሰራበት ቀን የሆነ እንደሆነ እረፍት ካላቸው ጉዋደኞችዋ አንድዋ በስዋ ፈንታ ተተክታ እንድትሰራላትና እስዋም በረፍትዋ ቀን በስራ ችላት ጉዋደኛዋ እግር ተተክላ እንድትሰራ ተደራጅታ እንደ ነበረው ሁሉ የጋብቻዋን መሰናዶ ስታሰናዳም ከጉዋደኞችዋ ጋር እንደዚያው ተደራጅታ ስለ ነበረ ለሀኪም ቤቱም ሆነ ለጋብቻዋ መሰናዶ ስራ የጊዜ ችግር አልገጠማትም።

ቤቱ ተሰርቶ አልቆ በዬቀኑ እያንዳንዱን ክፍል ከሌላው የተለዬ የራሱ በሚያደርገው ቀለማቀለም ከፈፍና ጌጣጌጥ ሲያጌጥ እያንዳንዱን ክፍል ከሌላው ልዩ የሚያደርገው እቃ በየክፍሉ እየገባ ሲያሳምረው ባዬች ቁትር የስዋም ደስታ እንዲሁ በዬቀኑ እየጨመረ እዬበዛ ይሄድ ነበር።

የሰርጉ ቀን እየቀረበ ሲሄድ ከቤቱም ሆነ ከቃው ወይም ከሌላው ለሰርግ ከሚያስፈልገው መሰናዶ የጎደለ ነገር ቢኖር ለማሙዋላት ከወይዘሮ ጌጤ ሌላ አዝማሪው ውቤና ምሽቱ ውባዬሁ ከደመቀችና ከበሻህ ጋር አብረው ነበር የሚያመሹ። የተደረገውን አመስግነው ወይም ነቅፈው ወደ ፊት ለሚደረገው ተመካክረው ወስነው ከጨረሱ በሁዋላ ራት አብረው በልተው - ጠላ መቸም ከወይዘሮ ጌጤ ቤት አይጠፋ - በሻህ ጠጅ ወይም ኮኛክ ገዝቶ አምጥቶ እዬተጠጣ ጭዋታው ውካታው ዘፈኑ ሁልጊዜ ሰርግ እንደ ሆነ ነበር የሚያመሸ! መቸም ውባዬሁ ከለመደቻቸው ሰዎች ጋር ከሆነች እስዋ ባለችበት ጥርስ መክደን አይቻል! የተለመደውን ተራ ነገር እንኩዋ

ባደራረግዋና ባነጋገርዋ ልዩ የሚያስቅ የማስረግ ስጦታ ነበራት! ስለዚህ በሻህና ደመቀች ከተጫጩ በሁዋላ ከወይዘሮ ጌጤም ከደመቀችም ጋር ተለማምደው የቅርብ ወዳጆች ሆነው ስለ ነበረ በቁጥብ ወይዘሮነት መሸፈኛዋን ከላይዋ አውልቃ ጥላ እንደ ልማድዋ እዬቀበጠች አንዳንድ ጊዜ ለራስዋ እያነበነበች አሮጊት ትሆናን ምርኩዝዋን ይዛ ችግርዋን ለራስዋ እያነበነእብች ጉብጥ ጉብጥ እያለች ስትሄድ አንዳንድ ጊዜ የጸሎት መጽሀፍ ይዛ የምትደግም ቀና ብላ ትእዛዝ ሰጥታ መለስ ብላ ስትደግም ቀና ብላ ተራግማ መለስ ብላ ስትደግም እንዲህ ከትእዛዝ ከስድብና ከርግማን ጋር እያሰባጠረች ጸሎት ስታደርግ ደግሞ አንዳንድ ጊዜ እመቤትዋ የቀጣቻት ወይም የተቆጣቻት ባሪያ ትሆንና ለብቻዋ ዘወር ብላ ብዙ ጊዜ አማርኛ አጥርተው የማያውቁ አገልጋዮች በሚናገሩበት የተሰባበረ አማርኛ እመቤትዋን ስትሰድብና ስትረግም አደራረግዋንና ሁኔታዋን እያዩ ሁሉም በሳቅ ሲያውኩ አምስት ሆነው ቤቱን ብዙ ሰው እንዳለበት አድምቀውት አሙቀውት ነበር የሚያመሹ። በተለይ ስለ እመቤቶች የምቀልደው ለደመቀች የድሮ እመቤትዋን ወይዘሮ ጽጌን አምጥቶ በፊትዋ ቁጭ አድርጎ ያሳያት ስለ ነበረ ካፍዋ አውጥታ አትናገረው እንጂ ሳቁ እንደ ሌሎች ቶሎ አያልፍላትም ነበር። ከዚያ ባልዋ መሰንቆውን ሲመታ እስዋ ተቀምጣ በቃልዋ ስትዘፍን ቆይታ ተነስታ ደመቀችንም ወይዘሮ ጌጤንም እዬጎተተች አስነስታ እዬዘፈነች ታዘፍናቸዋለች።

ወይዘሮ ጌጤ የባላቸው ሞት በልባቸው የተወውን የማይሽር ቁስል እዚያው እንዳለ ደብቀው የሀዘን ልብሳቸውን ጥለው ያዘቦት ልብስ ለብሰው እንዲያ ከውባዬሁና ከደመቀች ጋር የሚዘፍኑና የሚቦርቁ ደመቀችን ደስ ያሰኙ መስሎዋቸው ነበር እንጂ እሳቸውን ደስ ብሎዋቸው ወይም ዘፈን የሚያውቁ ሆነው አልነበረም። በቃላቸው ሆነ ባንገታቸው ዘፈን የሚሉትን ነገር ምሞከረውት አያውቁም። ታዲያ የማያውቁበትን ባንገታቸው ለመዝፈን ክርኖቻቸውንና ትከሻዎቻቸውን ወደ ሁዋላ ቶሎ ቶሎ ገፋ ገፋ አንገታቸውን፥ ለሰላምታ፥ እጅ እንደሚነሱ ሁሉ ወደ ፊት ደፋ ደፋ፥ እያደረጉ ከውባዬሁና ከደመቀች ጋር አብረው ሲጨፍሩ ሌሎችን በሳቅ ይገድሉዋቸው ነበር። ደመቀች ጎትታ እስከታስቀምጣቸው ድረስ ተቀጥተው እያለቀሱ እንደሚዘፍኑ ሁሉ ከንፈራቸውን ንክስ ፊታቸውን ጭምድድ አድርገው እንዲያ ሱክ ሱክ ሱክ ሲሉ አዝማሪው ውቤ መንሰንቆ መምታቱን ሌሎች መዝፈናቸውን ትተው እሳቸውን እያዩ በሳቅ፥ ያውኩባቸዋል!

ውባዬሁ በቃልዋም ባገትዋም ‹ግሩም› የምትባል ዘፋኝ ባትሆንም - በመጠኑ መዝፈን ታውቅ ነበር። ደመቀች በቃልዋ ከውባዬሁ የተሻለች አልነበረችም። ባንገትዋ ግን የሚያክላት አልነበረም። ወገብዋን በሁለት እጆችዋ ደገፍ አድርጋ አንዳንድ ጊዜ

አንገትዋን ወደ ቀኝና ወደ ግራ ትከሻዎችዋ እዬመታች በጎጃም ‹ዋንጫ ልቅለቃ› የሚሉትን ያንገት ዘፈን ስትዘፍን ትቆይና፥ እንዳይደክማት እሱን ‹በንጉንጉዶ› አቁዋርጣ ከዚያ ደረትዋ ወደ ፊት አንገትዋን ወደ ሁዋላ እዬመታች ‹ደንግላሳኛውን› ያንገት ዘፈን ትዘፍናለች። እንዲያ የተለያዩ ያንገት ስልቶች ‹በንጉድጉዶ› እያሰባጠረች ስትዘፍን ቆይታ ሲደክማት ሰዎችን እንዳታይ ታፍርና አይኖችዋን በሁለት እጆችዋ ጋርዳ ወደ ወንበርዋ ትሮጣለች።

ደመቀች አፋራም በመሆንዋ የውባዬሁ መቀለጃ ነበረች። መጀመሪያ ‹ሙሽሪት› ነበር የምትላት። ሙሽራ በስዋና በደመቀች አገር በጎጃም ‹የገላጭ› የሚባለው በአል ተደርጎ በድግስና በዘፈን እስከትገልጥ ድረስ ከሚዜዎችዋ ከደንገጡሮችዋና እጫጉላዋ ውስጥ ልዩ ልዩ የጫጉላ ጭዋታ ሲያጫውቱዋት ከሚሰነብቱት ልጆች በቀር ለሊላ ሰው አትታይም። የሙሽራው እናት አባት ወይም እቶችና ወንድሞች ደመቀች እንደ ሙሽራ አፋራም በመሆንዋ ነበር ውባዬሁ ‹ሙሽሪት› የምትላት ሁዋላ፥ ‹ሙሽሪት› ማለትዋን ትታ ‹ስእልዋ› ትላት ጀመር።

«ተነሽ ስእልዋ ቅብጠት ላስተርምሽ። ከታወቀበት ‹የሴት ልጅ መቅበጥ ከወርቅ ያስጌጥ› ይላሉ ሊቃውንት እናንቶቻችን! ስለዚህ ተነሽ በነጻ ላስተምርሽ» አለች ውባዬሁ አንድ ማታ እንደ ልማዳቸው ራት በልተው ሲጫወቱ ኩታዋን ጥላ በቀሚስዋ ብቻ ተነስታ የደመቀችን እጅ ይዛ እዬጎተተች።

«አ - ይ፥ እኔ ቅብጠት አልችልም፤ አላውቅበትም፤ ተይኝ እባክሽ! » አለች ደመቀች እጅዋን ለማስለቀቅ እዬሞከረች።

«ብታውቂበትማ ‹ላስተምርሽ› እልሽ ኖሮዋል? ስለማታውቂ ነውኮ አዝኘልሽ ‹በነጻ ላስተምርልሽ› ያልሁሽ፤ ተነሽ» አለች ውባዬሁ ጎትታ ስታስነሳት።

«ስሜ መብዛቱ እባካችሁ! ደግሞ አሁን ‹ስእልዋ› የሚባል ስም አወጣችልኝ! ለመሆኑ እንደ ስእል አምራለሁ ማለት ነው - ‹ስእልዋ› ብለሽ የሰዬምሽኝ? » አለች ደመቀች አፍራ እዬሳቀች መቅበጥ ልትማር በግድ ተጎትታ ተነስታ።

«ያውም የስአሊዎች አለቃ እግዜር ተጠንቅቆ አሳምሮ የሳለሽ ነሻ! ብቻ አሳምሮ የሳለሽን አሳምሮ የሰራሽን ደስ እንዲለው ይህን ውብ ስራውን ይህን በዚህ ዳሌና በዚህ ደረት መሀከል እዬታጠፈ የሚዘረጋ እዬቁዋጠረ የሚፈታ ወገብሽን እንዲህ እንዲህ እያደረግሽ ለሚያይሽ ሁሉ እያሳዩሽ ራስሽንም የሰራሽንም እንዳታስመሰግኝና

እንዳታስደንቂ ነፍስ እንደ ሌለው ስእል ባስቀመቱሽ ቦታ እንዳለሽ - ተቀምጠሽ ቀረሽ። ለዚህ ነው ‹ስእልዋ› ያልሁሽ! » አለች ውቤቱ ‹እንዲህ እንዲህ፥ እንዲህ› ስትል ወገብዋን እዬሸረበችና ፈገግ ብላ አንገትዋን ጎደድ ጎደድ፥ ጎደድ፥ እያደረገች ቄንጠኛ አካሄድ እዬሄደች።

ደመቀች እንደ ውባዬሁ ወገብዋን እዬሸረበችና አንገትዋን እያጉዋደደች ቄንጠኛ አካሄድ በመሄድ ፈንታ የውባዬሁን አካሄድ ማየት ብቻ አሳፍሮዋት በቆመችበት እንዳለች ‹ውይ -እናቴ የደንግላይቱ!› ብላ አይኖችዋን በሁለት እጆችዋ ጋርዳ ትስቅ ጀመር።

«በይ እንደኔ ወገብሽንና አንገትሽን ‹እንዲህ እንዲህ እንዲህ› እያደረግሽ ሂጂ እንጂ ምን ያስቅሻል? » አለች ውቢቱ ከሚያባብል ፈገግታ ጋር ወገብዋንና አንገትዋን አስማምታ እንደ ፊተኛው ቄንጠኛ አካሄድ እዬሄደች። ደመቀች በቆመችበት መቆዬት እንኳ አልቻለችም። እዬሳቀች ወደ ወንበርዋ ሄዳ ተቀምጣ እንባ እስኪወርዳት ስቃ አልወጣላት አለ።

«እንደዚች ያለችቱ ምን ትባላለች እባካችሁ? ‹ውበት ከንቱ ውበት መና› አትባልም? እጭ! እስቲ ይህ እግዚአብሄር - ወይ የኔን ድፍረት ለስዋ ቢሰጣት፥ ወይ የስዋን ውበት ለኔ ቢሰጠኝ ምን ችገረው ኖሮዋል? ‹እግዜር ሲንቆጠቆት ሁሉን አሞዋልቶ አይሰጥ› ትል ነበር እናቴ፤ እውነትዋን ነው! ምነው እቴ! ላንተ ይብላኝልህ እንጂ እኔስ ምን ቸገረኝ! ላንተ ግን - መጥኔውን ይስጥህ አንተ በሹ! እግዜርዋ ረስቶ ያስቀረባትን ነፍስ ልዘራባት ጥሬ ነበር አልሆነልኝም! እንግዲህ ይችን የማትንቀሳቀስ ውብ ስእልህን እሳሎንህ አስቀምጠህ እቤትህ ሰው በመጣ ቁጥር እንዳመጣብህ አንተ እያገላበጥህ ስታሳይ መኖር ነው! » ባል ወገብዋን በሁለት እጆችዋ ይዛ ቆማ እውነት በሚመስል የውሸት መመረርና መጸየፍ የሚያሳይ ፊት የታች ከንፈርዋን ረዘም ቅንድቦችዋን አንዱን ወደ ላይ አንዱን ወደ ታች ጠምም አድርጋ ደመቀችን ዘቅዝቃ ስታይ ቆዬችና እንዲያ ተጨፍግጎ እንዲያ ከፍቶ የነበረ ፊትዋ ከመቅጽበት የስዋ ብቻ በሆነ ለዛ ያስጌጠው ፈገግታ በርቶ እዬሳቀች ሮጣ በደመቀች እቅፍ ላይ ወድቃ ትስማት ጀመር። ያን የውባዬሁን በያጭሩ ጊዜ መለዋወጥና በተለዋወጠች ቁጥር የምታደርገውን እያዩ ሁሉም - መቀለጃ የሆነችቱ፥ ደመቀች ሳትቀር - ስቀው አልወጣላቸው አለ።

ያ ከሰርጉ ቀን በፊት አስራ አስምት ቀናት ያክል ማታ ማታ አዝማሪው ውቤና ውባዬሁ ከወይዘሮ ጌጤ ከደመቀችና ከበሻህ ጋር የነደመቀች ቤት መሰናዶ

እስኪጠናቀቅ ድረስ እወይዘሮ ጌጤ ቤት መሰናዶው ከተጠናቀቀ በሁዋላ እዚያ ራታቸውን በልተው ሲጫወቱ ሲደሰቱ ሲስቁ ያመሹ የነበሩት ጊዜ ለበሻህና ለደመቀች በዬለቱ ይሰጣቸው ከነበረው ደስታ አልፎ በጋብቻ ህይወታቸው ሁሉ ሊረሱት ያልቻሉ ባነሱት ቁጥር የህይወት ጉዋደኛቸው ሆኖ ሲያስቃቸው ሲያስደስታቸው የኖረ ነበር።

ውባዬው «እግዜር ሲንቆጠቆትር ሁሉን አሞዋልቶ አይሰጥ» ትል ነበር እናቴ› እንዳለችው ፈጣሪ ሁሉን አሞዋልቶ ያደላቸው ቢኖሩ እጅግ ጥቂት ይሆናሉ። ደመቀች የወደደችውን እንድትጠላ የጠላችውን እንድትወድ ወይም ያመነችበትን እንድትክድ የካደችው የማትመለስ ደፋር ነበረች። ነገር ግን በተወለደችበት ቤተሰብና ባካባቢው ‹ሀጢያተኛ ነው፤ ነውር ነው ሴት ልጅ ይህን ወይም ያን ማድረግ አይገባትም ወዘተ .....› ሲባል እዬሰማች ተምራ አምናበት ያደገችውን ሁሉ እንኩዋንስ እስዋ ልታደርገው ሌሎች ሲያደርጉት ማየቱ ከተረዳች በሁዋላ ፈሪ ነበረች። አምናበት የኖረች ስህተት መሆኑን ከተረዳች በሁዋላ እንኩዋ አስተሳሰብዋንና አሰራርዋን ቶሎ ለውጣ ባካባቢው የሚኖሩትን ለመምሰል ጊዜ የሚወስድባት ዳተኛ ነእብረች።

በሻህ በበኩሉ የሰው ክብር የማይነካ፥ የራሱን ክብር የማያስነካ ኩሩ፥ ጀግና፣ ደግ፥ ቸር፥ ነበር። በኒህ መስመሮች እንኩዋንስ የሚበልጡት የሚያክሉት ብዙ አይኖሩ ይሆናል። ነገር ግን ቁች ብለው ተረት እዬተረቱ ቀልድ እዬቀለዱ አዳዲስ ወሬ እዬፈጠሩ ወይም የተፈጠረውን እያሰማመሩ እንዲሁ፥ ወዘበሬታ ወይም አሉባልታ ‹ጭዋታዎች ናቸው› ከሚባሉት ሰዎች ጋር የሚቆጠር አልነበረም። ሌሎች እንዲያ ያለ ጭዋታ ሲጫወቱ መስማት ወይም መመልከት በጣም ቢወድም እሱ አያውቅበትም ነበር። አዝማሪው ውቤ እሱን የሚነካ ቀልድ ያመጣ እንደሆነ በስድብ ነበር አጠፋውን የሚመልስለት። ተማርረው አይለያዩም እንጂ በጭዋታ ላይ ‹ዱላ ቀረሽ› የሚጣሉ ለዚህ ነበር።

ለዚህም ከሰርጋቸው በፊት አስራምስት ቀናት ያክል ማታ ማታ አዝማሪው ውቤና ምሽቱ ውባዬሁ አብርዋቸው እያመሹ ውባዬሁ በቃልዋም ባንገትዋም እዬዘፈነች ከዚያ ብሶትዋን ለራስዋ እንደታዋይ አሮጊት ጸሎት ከትእዛዝና ከስድብ ጋር እያሰባጠረች እንደምትደግም ግብዝ እመቤት ተቀጥታ ወጥታ ብቻዋን እመቤዋን እንድምትሰድብ አገልጋይ እዬሆነች አዝማሪው ውቤ ከመሰንቆው ጋርም በቃሉም ብቻም እዬዘፈነ አንዳንድ ጊዜ እንደ ኮከብ ቆታሪ አንዳንድ ጊዜም እንደ ጠንቁዋይ እዬሆነ ባልና ምሽቱን ሲያጭውቱዋቸው ያን አይነት ጭዋታ በሻህና ደመቀች ቢወዱትም እነሱ ያልነበራቸው ከፈጣሪ ያልታደሉት ሆነና ለጊዜው ይሰጣቸው ከነበረው ደስታ አልፎ በጋብቻ

ህይወታቸው ሁሉ ባነሱት ቁጥር እያጫወተ ሲያስቃቸው ሲያስደስታቸው የድሜ ልክ ጉዋደኛቸው ሆኖ ቀረ።

ለደመቀችም ለበሻህም ሁለተኛ ጋብቻቸው ስለ ነበረ ለሰርጉ ብዙ ድግስ መደገስም ብዙ ሰው መጥራትና ለመጀመሪያ ጋብቻ የተለመደውን ስነ - ስራት ሁሉ ማድረግም እንደሚያስፈልግ ተስማምተው ነበር። ወይዘሮ ጌጤ ብቻ ‹ወልጄ ለመዳር ባልታደል በዚች በምወዳት በመንፈስ ቅዱስ ልጄ የናትነት ወግ ይድረሰኝ› ብለው ለመጀመሪያ ጋብቻ የሚደረገው ሙሉ ሰርግ እንዲደረግ ወጥረው ይዘው ነበር። የደመቀች ምኞት እንደ ወይዘሮ ጌጤ ነበር። ነገር ግን በሻህ ብቻ ሳይሆን አዝማሪው ውቤ ጭምር እንዲህ ያለ በነሱ ደረጃ ያሉ ተራ ሰዎች አድርገውት የማያውቁ ነገር ማድረግ ከውጪና ከድካሙ በላይ እንደ ቅብጠት ተቆጥሮ ላሜተኞችና ላሽሙዋጣጮች የሚያጋልጣቸው ከመሆኑ በቀር ጥቅምም ደስታም የማይሰጥ መሆኑን እዬገለጹ ባንድነት ስለ ተቃወሙዋቸው ወይዘሮ ጌጤ ተሸነፉ። ደመቀችም የነሱን ውሳኔ ተቀበለች።

«እሺ እስቲ ይሁን የኛን አሳብስ አይሆንም አላችሁ፤ ታዲያ የሰርጉ እለት ከቤተ ክርስቲያን ስትመለሱ አብረዋችሁ የሚመጡና - እዚህ ምሳ የሚበሉት እንግዶች ስንት እንደሚሆኑ አስባችሁዋል? መቸም - እድኒያው እንደ ቤተክሲያን ተመልሳችሁ ብቻችሁን ምሳችሁን አትበሉ» አሉ ወይዘሮ ጌጤ ያዝማሪውንና የበሻህን አሳብ ተገድደው ከተቀበሉ በሁዋላ።

«ስራት ቁርባኑ የሚያደርጉት ካህናት አምስት ኍልቱ የውል አባቶችና ሶስቱ ውለ ሰሚዎች ባንድነት አምስት ጎረቢቶችና የደመቀች ጉዋደኞች ባንድነት አስራ አራት በድምር ሀያ አራት ናቸው ያሰብናቸው» አለ አዝማሪው።

«ያልታሰበ ሊኖር ስለሚችል እስቲ ግዴለም ሰላሳ እናድርጋቸው» አሉ ወይዘሮ ጌጤ።

በስነ - ስራት በኩል በሻህንና ደመቀችን በጣም ቅር አሰኝቶዋቸው የነበረ - በሻህ እንኩዋ ግድ አልነበረውም፤ ደመቀች ስለፈለገች - ሁለቱንም ቆርበው ለመጋባት ሲጠይቁ ‹ፈቶች ሁለተኛ ሲያገቡ በጸሎት እንጂ በተክሊልና በቁርባን እንዲያገቡ የቤተ ክርስቲያን ህግ አይፈቅድም› ብለው የጊዮርጊስ ገበዝ ‹አንገቱን ለሰይፍ› ማለታቸው ነበር።

«ስንት መኩዋንንት ሲያገቡ፥ ሲፈቱ ኖረው በመጨረሻ ሲደክማቸው እዬቆረቡ ሲያገቡ ስናይ ኖረን የለም? ታዲያ እንዲህ ያለው የቤተ ክርሲያን ህግ ለድሆች የተሰራ ነው ማለት ነው? » አለ በሻህ እዬተበሳጩ ስለዚህ ጉዳይ ካዝማሪው ውቤ ጋር ሲነጋገሩ።

«ህጉ እንኩዋ በጌቶችና በድሆች መሀከል ልዩነት ሳያደርግ፥ ክርስቲያኖች ለሆኑ ሁሉ የተሰራ ነው። በስልጣንና በገንዘብ እዬተባበሉ እንዲህ ያለ ምእመናንን ከቤተ ክርስቲያን የሚያርቅ ልዩነት ለመፍጠር ታጥቀው የተነሱ ነው - ካህናቱ ናቸው። ታዲያ -እናንተ ደመቀች ‹ካልቆረብን› አላችሁ እንጂ፥ እንደኔስ ቢሆን ቁርባኑ ቀርቶ እቤት ክርስቲያን መጋባትም ከፈለጋችሁ ከጭቅጭቁ ገበዙ እንዳሉት ጸሎት ተደርጎላችሁ ብትጋቡ በቂ ይመስለኛ። ነገር ግን፥ ‹አነጋግራቸው› ካልኸኝ እስቲ ልሂድና ላነጋግራቸው» አለና አዝማሪው ውቤ የጊዮርጊስን ገበዝ ቄስ ገእብዝ ተግባሩን ፍለጋ ሄደ።

«እንኩዋንስ በቁርባን መጋባት ፈልገው ወደ ቤተ ክርስቲያን የሚመጡትን መከልከል የማይፈልጉትንስ ቢሆን መክሮ፥ አስተምሮ ወደ ቤተ ክርስቲያን ማቅረብና ጋብቻቸውን በስጋ ወደሙ የተባረከ የተቀደሰ እንዲሆን አድርጎ የክርስቲያን ቤተሰቦች እዬበዙ እንዲሄዱ ማድረግ የናንተ የቤተ ክርስቲያን መሪዎችና አስተማሪዎች ተግባር አልነበረም፥ ቄስ ገበዝ? » አለ አዝማሪው ውቤ ቄስ ገበዝ ተግባሩን ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን እቃ ቤት አግኝቶዋቸው ቁጭ ብለው ስለሄደበት ጉዳይ ሲነጋገሩ።

«ሌላ ሰው አንድ መሀይም እስዎ አሁን የተነጋገሩትን ቢነግረኝ ባልገረመኝ ቀኝ ጌታ! የሚያስገርመኝ እንኩዋንስ ማንም ሰሞነኛ የሚያቀውን የቤተ ክርስቲያን ህግ ከዚያ በላይ ብጹ መጽሐፍት ከነትርጉማቸው ጠንቅቀው ከሚያውቁት ከርስዎ እንዲህ ያለውን ነገር መስማቱ ነው! እኒህ የሚጋቡት እጮኞች ፈቶች መሆናቸውን ያውቃሉ፤ እኛም እነሱ ነግረውን አውቀናል። ስራተ - ተክሊል ተደርጉላቸው ስጋ - ወደሙን ተቀብለው የሚጋቡ ደግሞ ደናግልና ደናግልት እንጂ ፈቶች እንዳልሆኑ እርስዎ ደህና አድርገው ያውቃሉ። ታዲያ አሁን እያወቁ እንዴት - ‹ህግ ይፍረስ› ብለው ያስቸግሩኛል? » አሉ ቄስ ገበዝ ተግባሩ አዝማሪው ውቤን በመገረም መልክ እያዩ።

«ፈቶች ሁሉ፥ ‹የተፈጥሮ ግዳቸውን በዝሙት እዬተወጡ ይኑሩ› የሚል የቤተ ክርስቲያን ብቻ አደለም እንዲያውም የሚበዛው ከቤተ ክርስቲያን ውጭ ነው።

«ከቤተ ክርስቲያን ውጪ የሚደረገው ጋብቻማ - ‹እንደ ጋብቻ አይቆጠርም› ትሉ የለ? » አለ አዝማሪው አሁንም ባሽሙር መልክ ፍርጥም ብሎ።

«ማን እንዲያ አለ? » አሉ ቄስ ገበዝ የጊዮርጊስን ቤተ ክርሲያን ባለስልጣኖች ያላቸው መስሎዋቸው።

«ምነው የቤተ ክርሲያናችሁ ህግ ፍትሀነገስቱ ‹ወይመጥዉዎሙ ቁርባነ ቅዱስ በጊዜ ተክሊል ዘቦቱ ይወሀዱ ክልኤሆሙ፥ ወይከውኑ አሀደ ስጋ ወዘእንበለ ዝንቱሰ ኢይሆለቁ እሎሙ አውስቦ› ይል የለም? ረሱት እንዴ! እንዲህ እነዚህ እጮኞች ‹ስጋ - ወደሙን ተቀብሎ የማይደረግ ጋብቻ በክርስቲያን ህግ ከጋብቻ የማይቆጠር ከሆነ አቁርባችሁ አጋቡን› ነው የሚሉ። ታዲያ እዚህ ላይ ‹አቁርበን እናጋባችሁም› ሲሉዋቸው እርስዎ አደለሙ ‹የቤተ ክርስቲያን ህግ ይፍረስ› የሚሉት? » አለ አዝማሪው ውቤ ቀኢስ ገበዝን ፊት ለፊት ፍጥጥ አድርጎ እያዬ።

«አየ ጉ -ድ! እንዲህ ያለው ክፍሉን ከጠቅላላ አካሉ ነጥሎ ለማደናገር መሞከር ለኔ አይሆንምኮ ቀኝ ጌታ! ከጠቀሱ ክፍሉን ከሙሉ አካሉ ጋር እንዳለ መጥቀስ ነው! አሁን የጠቀሱት በጠቅላላ ስለ ጋብቻ ከተደነገገው አንድ ትንሽ ቅርንጫፍ ቀንጥበው ነው። የምንነጋገረው ግን በተለይ ስለ ፈቶች ጋብቻ ነው። አሁን ነገስቱ የሚለው ‹ወለእመ ኮኑ ዘይትዋሰቡ መአስባነ ኢይግበሩ ሎሙ ወለብእሲት ድንግል በጊዜ ተዋስቦ። ወለእመ ደገሙሰ ይደልዎሙ ጽሎተ ካህን ዘአስተርዮ› ነው። ታዲያ ይህን እንዴት ያልፋታል? » አሉ ገበዙ ፈገግ ብለው በፈንታቸው አዝማሪውን ፊት ለፊት ፍጥጥ አድርገው እያዩ።

«እኔን ለማደናገር ከሙሉው ህግ ቅርንጫፍ ቀንጥበህ አነበብህ» ብለው ሲነቅፉ እርስዎ ቅርንጫፍ እንኩዋ ሳይቀነጥቡ ‹ላም ባልዋለበት ኩበት ለቀማ› እንደሚሌው ጭራሽ ያልተጠዬቀውን ስለ ተክሊል የተደነገገውን አንቀጽ ነው ያነበቡ። እጮኞችም እኔም የጠዬቅነው ቆርበው እንዲጋቡ ነው እንጂ ስራተ ተክሊል እንዲደረግላቸው አልጠዬቅንም ተክሊል ለደናግል ለደናግልት መሆኑን እናውቃለን።»

«በህጉ ተክሊልና ቁርባን አይለያዩም፤ ሁለቱ አብረው የሚሄዱ ናቸው።»

«የቤተ ክርስቲያን ህግ ብቻ ሳይሆን ማናቸውም ህግ የሚያሻማ ነጥብ የማያጣ መሆኑ የታወቀ ነው። ህግ የሚሻማ ባይሆን ኖሮ ትርጉዋሚ ባላስፈለገ ነበር። ብቻ ህግ ምንም አይነት ትርጉዋሚ ቢኖረው ባፈጻጸም ረገድ ‹በሀብታሞችና በድሆች

በባለስልጣኖችና፥ በተራ ሰዎች መሀከል ልዩነት ሊኖር አይገባም› እያለች የምታስተምረዋ ቤተ ክርስቲያን ራስዋ ልዩነት ልታደርገው ይገባታል! መቸም ሲያገቡ ሲፈቱ ኖረው በመጨረሻ ቆርበው የሚጋቡ መኖራቸውን እናውቃለን! » አለ አዝማሪው የህጉ ክርክር የትም ሊያደርሰው እንዳልቻለ ሲያይ ነገሩን ወደ ህሊና ዳኝነት መለስ አደረገና።

«ህጉ ምንም ትርጉዋሜ አያስፈልገው ግልጽ ነው። ‹ባፈጻጸም ረገድ ቤተ ክርስቲያን በህብታሞችና በድሆች መሀከል ልዩነት ታደርጋለች› ላሉትም እኔ፥ ይህን ስራ ከያዝሁበት ጊዜ ጀምሮ፥ እንዲህ ያለ ነገር ሲደረግ አይቻለሁ ስምቻለሁ› ብሎ እንኩዋንስ ሰው ሰይጣን አይመሰክርም! ከዚያ በፊትም ቢሆን እኔ እስከማውቀው ድረስ የተደረገ አይመስለኝ። እንዲያ ያለ ስህተት ተደርጎ እንደሆነም እንዲታረምና ወደ ፊት እንዳይደገም ‹ብርቱ ጥንቃቄ ይደረግ› ይባላል እንጂ ‹አንድ ጊዜ ስህተት ምንም ቢሆን ለጠዬቁኝ ፈቃድ መስጠት አልችልምና ንግግራችነን በዚህ እናልበው። ‹ምክር ስጠኝ› ይሉኝ እንደሆነ ግን ወዳጆችዋ በጋብቻቸው ቀን ይምጡና ‹ጸሎተ - አስተስርዮ› ብቻ ተደርጎላቸው ስራተ - ጋብቻቸው ይፈጸም። እግዚአብሄር እድሜውን ካልነፈጋቸው አስራ አምስት አመታት ያክል በጋብቻ ተሳስረው ከቆዩ በሁዋላ ተዋውቀው የሚተማመኑ ባልና ሚስት መሆናቸውን ሲያረጋግጡ ስጋ - ወደሙን ባንድ ሊቀበሉ ይችላሉ። ደህና አድርገው ሳይተዋወቁ ዛሬ ስጋ ወደሙን ተቀብለው ተጋብተው ነገ ቢፋቱ ለነሱም ለቤተ ክርስቲያንም የሚበጅ አይሆንም። የምሰጥዎ ምክር ይህ ነው። አሁን ያለቃው የመላከ ገነት መምጫ ስለ ደረሰ ይፍቀዱልኝና ልሂድ» ብለው ቆስ ገበዝ ተነሱ።

«ላለፈው ስህተታችን ምህረት እንድናገኝ ጸሎት ተደርጎልን ከንግዲህ፤ እኛ ሁለታን በስጋ ወደሙ አንድ ስጋ ሆነን ለመኖር ተስማምተን ወስነናልና አቅሩባችሁ አጋቡን› ብለው ወደ ቤተ ክርሲያን የሚመጡትን ምእመናን መግፋት ከህጉም ከህሊናም ፍርድ ጋር የሚስማማ አይመስለኝም። ‹ህጉ እንዲከበር ብለው ሳይሆን ቅር ብሎት እሱም ለመሄድ ሲነሳ። ‹ህጉ እንዲከበር ብለው ሳይሆን ሌላ ነገር ፈልገው ነው› ማለቱ ተሰማቸውና ቄስ ገበዝ፥

« ‹ስራተ - ተክሊል ይደረግላቸው› ያሉ መስሎኝ ነበር እንጂ የተቃወምሁ ‹ቁርባን ብቻ ከሆነ› - ምን አለ እሱ ይቻላል» አሉ በመጨረሻ እስከዚያነለት ሲለመኑ የሰነበቱት ያልገባቸው ለመምሰል እዬሞከሩ!

# ምእራፍ ሰላሳ ዘጠኝ

# የበሻህና የደመቀች ጋብቻ

በጠቅላላ አነጋገር የሚስማሙትና የሚዋደእዱት ለመገናኘት የማይዋደዱትና የማይስማሙት ለመለያየት ሲጥሩ፥ ሲግሩ የሚኖሩ መሆናቸው የታወቀ ነው። ነገር ግን ባንጻሩ፥ ጣልቃ እዬገቡ የሚያሰናክሉና የሚከለክሉ ልዩ ልዩ ተቃራኒ ሀይሎች ስላሉባቸው ለመገናኘትም ሆነ ለመለያየት ከሚፈልጉት ሁሉ ወደዬሚፈልጉት ግብ መድረስ የሚችሉት ሰዎች የመንፈስ ነጻነት የፈቃድ ብርታትና ቆራጥነት ያላቸው ጥቂት ናቸው። የሚበዙት በስልጣን በባህል በልማድና እነሱን በመሳሰሉት ልዩ ልዩ አስገዳጅ ሀይሎች ተገድደው የማይፈልጉትን የሚጠሉትን ኑሮ ተሸክመው እንደ ተቸገሩ እንዳማረሩ የሚኖሩ ናቸው! የሚሰማሙት ለመገናኘት የሚስማሙት ለመለያየት ሲፈልጉ ፍላጎታቸው እንዳይፈጸም ጣልቃ እዬገቡ የሚከለከሉ አስገዳጅ ሀይሎች አይኖሩ ኖሮ በቤተሰብ (ባልና ምሽት) በማህበር ከዚያም አልፎ በአለም አለመግባባት ወይም ሁከት ባልኖረ ነበር!

ደመቀችና በሻህ የመንፈስ ነጻነት የፈቃድ ብርታትና ቆራጥነት ካላቸው ጥቂት ሰዎች መሀከል መሆናቸውን ታሪካቸው ያሳያል። እንዳገሩ እንደ ልማድ የልጆችን የጋብቻ ኑሮ ለመወሰን ሙሉ ስልጣን ያላቸው ወላጆች በመሆናቸው የደመቀች አባት እንኩዋንስ አብራው መኖር ፊቱን ላንድ አፍታ ማየቱ ለሚያስጠላት ባል ድረው አብራው እንድትኖር ስላስገደዱዋት ባባትዋ ስልጣን በባህሉ በልማዱ በሁሉ ሽፍታ ‹ባል› የሚባለው ሁሉ ያን የጠላችውን ባልዋን መስሎ ስለ ታያት ዳግመኛ ባል ላታገባ ምላ በልጅነትዋ ልጅ አዝላ ወደማታውቀው አገር የተሰደደች ነበረች። በተሰደደችበት አገርም ለነጻ ምርጫዋና ለፈቃድዋ ዋጋ ሳይሰጡ የራሳቸውን ፈቃድ ብቻ ለማስፈጸም የተፈታተኑዋትን ሁሉ ባጠገብዋ አላስደርስ ያለች በመሆንዋ ‹የነብር አራስ› የተባለ ስም የወጣላት ነበረች።

በሻህም ቢሆን ገና ለጋ ወጣት ሳለ ጀምሮ ለሁሉም ያካልና የመንፈስ ነጻነትና እንደዬችሎታው ሰርቶ የመኖር መብትን አጥብቆ የሚመኝ ባንጻሩ የግፍ የጭቆናና ያድልዎ ስራ በማንም ላይ ሲሰራ ባዬ ቁጥር እንደ እግር እሳት የሚያንገበግበውና የሚያመው ነበር። ሁዋላ እዬበሰለና እያስተዋለ ሲሄድ፥ የያንዳንዱ ነሳእንትም ሆነ

መብት መታፈንና የግፉ የጭቆናው ያድልዎው ቀንበር በህዝቡ ላይ መጫን ሁሉም የጠቅላላው ስራት ዘርፎችና ቅርንጫፎች ስለ ሆኑ ያ የሁሉም ስር የሁሉም መሰረት የሆነው፥ ጠቅላላው ስራት ካልተለወጠ ምንም ቢሆን የኢትዮጵያ ህዝብ ለነጻ ህዝብ የሚገባውን ነጻነት ሆነ መብት ሁሉ ማግኘትና ከጭቆና ሁሉ መውጣት እንደማይችል አመነ። ስለዚህ ያን ክፉ ስራት ጠልቶ በዚያ ክፉ ስራት ላይ መንፈሱ ሸፍቶ እሱ እስኪለወጥ ድረስ ሲታገል መኖር እንጂ ምንም ቢሆን አንገቱን በዚያ ስራት የጭቆና መንቆር ውስጥ ላያስገባ ወስኖ ስለ ነበረ ስራውን ትቶ፥ ምሽቱን ፈትቶ የሱን ለመሰለ አላማ የተሰለፉ ቡድኖች ቢኖሩ ከነሱ ጋር ተባብሮ ያለዚያም ባሳቡ የሚስማሙትንና ለምነቱ ተካፋዮች የሚሆኑትን እዬፈለገ አስተባብሮ ስራቱን ለማስለወጥ እንደ ታጠቀ ተጠነቀቀ የሚኖር ነበር።

ኢትዮጵያ ከጠላት የቅኝ ቀንበር ነጻ ወጥታ፥ እሱ ካርባኝነት እንደ ተመለሰ እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ - የሌሎችን ነጻነት እስካልነካ ድረስ - አሳቡን በቃል ይሁን በጽሁፍ ለሌሎች ለማካፈልና የሌሎችን ለመካፈል ነጻነቱ የማይወሰንበት በተፈጥሮም ይሁን በትምርት ባገኘው እውቀት እንደ ችሎታው ሰርቶ ለመኖር መብቱ የሚጠበቅበት ስራተ - ማህበር እንደሚመሰረት ሙሉ እምነት ነበረው። ስለዚህ ለነጻ ህዝብ የሚገባውን አገልግሎት እዬሰጠ ህዝቡን ደስ አሰኝቶ እሱንም ደስ ብሎት ለመኖር የመንግሥት ስራት ይዞ ምሽት አግብቶ ነበር። ነገር ግን ባጭር ጊዜ ውስጥ የተመሰረተው ስራተ ማህበርም ያገባት ምሽትም ተስፋ እንዳደረው ደስ በማሰኘት ፈንታ የሚያስጠሉ የሚያንገፈግፉ ሆነው ስላገኛቸው እንኩዋንስ እዚያ ስራት ውስጥ እሱን በሚመስል ሌላ ስራት ውጽጥ ስራ ላይገባ ያችን «ፋናየን» በመልክ እንኩዋ የምትመስል ምሽት ላያገባ የማለ ነበር!

መቸም መሸፈትን የሚወደው የሚወደውን አጥቶ የሚጠሉትን እንዲሸከሙ መገደድ ነው! የሚወዱት ከተገኘ እሱን ትቶ መሸፈት አይኖርም። የሚወዱት ከተገኘ ከራሱ መወደድም አልፎ የሚጠሉትን እንኩዋ ያስወድዳል። በበሻህና በደመቀች የደረውሰውም እንዲያ ያለ ነበር። ከማንም ከማንም የበለጠ፥ የሚወዱት ነገር ፍቅር ገጠማቸውና አስጠልቶ አስጸይፎ አንገፍግፎ ያስሸፈተውን ነገር ሁሉ እንዲወዱ አደረጋቸው!

የሚወዱትን ተነፍገው የሚጠሉትን ተጭኖባቸው እንዲኖሩ ስለ ተገደደ ባስገደዳቸው የወላጅ አባትና የመንግስት ስልጣን በጨቆኝዋ ስራተ - ማህበርና በጨቆዋኝ ባህል ላይ ሸፍተው የኖሩትን ደመቀችንና በሻህን በመሀከላቸው የተፈጠረው

ጽኑ ፍቅር አስመርሮ ያስሸፈታቸውን ክፉ ነገር ሁሉ አስረስቶ ተጋብቶ መኖርን ችባ አላማቸው አድርጎ አሳይቶ እሱን ወደ ጠላው ስራትና ወደ ጠላው ስራ እስዋን ወደ ጠላችው ጋብቻ መለሳቸው! ፍቅራቸውን ተገላልጸው እንዲጋቡ ከወሰኑበት ጊዜ ጀምሮ ለሁለቱም ቀን ባሳባቸው ሌት በልማዳቸው የሚታያቸው ተጋብተው የሚኖሩት የደስታ ህይወት ብቻ ሆነ! በምንም አይነት ስራተ - ማህበር ውስጥ - ከሚኖሩባት በሚከፋ እንኩዋ - ይኑሩ ምንም አይነት ስራ - የተሸካሚነት እንኩዋ - ይኑሩ ምንም አይነት ስራ - የተሸካሚነት እንኩዋ - ይሰሩ ምንም አይነት ተጋብተው ለመኖር የማይከፍሉት ውድ ዋጋ የማይቀበሉት ከባድ ፈተና አልነእብረም! ግፉ በደሉ ጭቆናው ሁሉ ከነበረበት ጠፍቶ አልነበረም፤ ሁሉም በነበረበት እንዳለ ነበር፤ ነገር ግን ለነሱ ተጋብቶ ከመኖርና ከፍቅራቸው በቀር ያ፥ ሁሉ ክፉ ነገር አይታያቸውም፥ አይሰማቸው ነበር! ፍቅር ባለበት ያ ሁሉ ክፉ ነገር አይኖርም። ቢኖርም አይታይም፤ አይሰማም!

እኒያ በስራቱ በባህሉ በወላጅ አባቱም በመንግስቱም ስልጣንና ሀይል ሁሉ ላይ ሸፍተው የኖሩ ሁለት ደመቀችና በሻህ በብርቱዎቹ ብርቱ በሀይለኞች ሀይለኛ፥ በፍቅር ድል ሆነው ተማርከው ገርመው እሱ እስካለ ድረስ የከፉው ስራት የከፉው ባህል የስልጣኑ ጭቆና ሁሉ ‹ከበደን› ላይሉ የማራኪያቸውን የፍቅርን ትእዛዝ ‹አሜን› ብለው ተቀብለው ከሽፍትነት ወደ ሰላማዊ ኑሮ ተመለሱ። የጋብቻ በአላቸውን ያከበሩ፥ ከፋሲካ በሁዋላ በሁለተኛው እሁድ ነበር።

የሰርጉ እለት ለምሳ የሚጋብዙት እድምተኞች ግፋ ቢል ከሰላሳ እንዳይበልጡ በሻህና አዝማሪው ውቤ ከወይዘሮ ጌጤና ከደመቀች ጋር ተነጋግረው ተስማምተው ነበር። ግን በተከተሉት ጥቂት ቀናት በሻህ ከመስሪያ ቤቱም ከመስሪያ ቤቱ ውጪም ከነበሩት ጉዋደኖቹና ወዳጆቹ ጋር ሲገናኙ የጋብቻው ነገር በተነሳ ቁጥር አፋቸውን አውጥተው ‹አትጋብዙንም ወይ?› ያሉትን አፍሮ ‹ጋብዣችሁዋለሁ› ሲል ‹እገሌን ቢቀሩ ምን ይሉኝ› እያለ ያልጠዬቅትንም ሲጋብዝ እንዲህ በፍረትና በይሉኝታ የጠዬቁትንም ያልጠዬትንም ‹ጋብዣችሁዋለሁ› ሲል መጨረሻ እሱና አዝማሪው ውቤ ከወይዘሮ ጌጤና ከደመቀች ጋር የተስማሙባቸው እድምተኞች ሰላሳ መሆናቸው ትዝ ስለው የማስታወሻ ደብተሩን አውጥቶ በዬቀኑ የጋበዛቸውን ሰዎች እዬለቀመ በተራ ጽፎ ቢደምራቸው ድምራቸው ሰማይ ወጥቶዋል! ከነወይዘሮ ጌጤ ጋር እንዲጠሩ የተስማሙባቸውና ሁዋላ እሱ የጨመራቸው እምድተኞች ቁጥር ባንድነት ዘጠና ስድስት ሆነዋል!! ጥሪውን ያደረገው በዬቀኑ እንጂ ባንድ ጊዜ ባለመሆኑ ያን ያክል ሰው የጠራ መስሎት ስላልነበረ ድምሩን ሲያይ ደነገጠ። ብቻ የሆነው ከሆነ በሁዋላ ምን

ይደረጋል? መቸስ - እዬተዞረ የተጠሩትን ሰዎች ‹እንዳልተጠራችሁ ቁጠሩት ርሱት› አይባል ነገር!

የበአሉ ዋዜማ እለት ቅዳሜ ጥዋት የተጠሩት ሰዎች ቁጥር ዘጠና ስድስት መድረሱን ላዝማሪው ውቤ ሲነግረው፥

«እንዲያ ከሆነማ - ቤቱ አይበቃንም ማለት ነዋ! እንግዲህ ድንኳዋንና ጠረጴዛዎችም ወንበሮችም መከራየት ሊኖርብን ነው፤ ያለዚያ - ለዚሁ ሁሉ ሰው እንደማይበቃ እርግጠኛ ነኝ» አለና አዝማሪው ተያይዘው ድንኳዋን ጠረጴዛና ወንበር ወደሚያከራዩ ሰዎች ሄደው አንድ ትልቅ ድንንኳዋን ሀያ ጠረጴዛዎችና መቶ ወንበሮች ተከራይተው ሁሉም ያነለት ከዘጠኝ ሰአት በሁዋላ ከተካዮች ጋር እቦታቸው ደርሶ እንዲተከልላቸው ተስማምተው ኪራዩን ከፍለው ተመለሱ።

በሻህ ያን ያክል ሰው ከመጥራቱ በፊት ወይም ወዲያው እንደ ጠራ ለወይዘሮ ጌጤና ለደመቀች ‹ሳይነግራቸው ይቀራል› ብሎ ስላልጠረጠረ አዝማሪው ውቤ ‹ነግረሀል ወይስ አልነገርሀም?› ብሎ አልጠዬቀውም። ነገር ግን በሻህ ጥዋቱን ሁሉ ያጠፋው ጥፋት በሙሉ ክብደት ተጭኖት አዝማሪው ውቤ ‹እናድርግ› ያለውን ዝም ብሎ አብሮት ከማድረግና ለጠዬቀው ከመመለስ በቀር እንደ መሰንበቻው አሳብ ሲያቀርብና ደስ ብሎት ሲናገር ስላላዬው ጤና ያጣ መስሎት፥

«ዛሬ ምን ሆነሀል? ፍዝዝ ብለሀል» አለው።

«ፈዝዣለሁ እንቅልፍ አልጠገሁም፤ ለዚህ ይሆናል።»

«እነሀ ሰዎች ድንኳዋን የሚተክሉ ምን ሊያደርጉበት ነው? » አለች ደመቀች በሻህንና አዝማሪውን ከቤቱ ራቅ አድርገ አጥሩ አጠገብ ድንኳዋን ሲያስተክሉ በመስኮት ብቅ ብላ አይታ።

«አዲሱ ቤትና እቃው ወረቱ ሳያልፍ እንዳይበላሽ ነገ ምሳው እዚያ እንዲበላ ብለው ይሆናል፤ መልካም አደረጉ። እኔም ካፌ አውጥቼ አልተናገርሁትም እንጂ በተለይ እቃው፥ ወጥም መጠጥም ሳይፈነጠቅበት ስለማይቀር ‹ምን ማድረግ ይሻል ይሆን?› እያልሁ ሳስብ ነበር» አሉ ወይዘሮ ጌጤም እንደስዋ በመስኮቱ ብቅ ብለው አይተው ሲመለሱ።

አዝማሪው ውቤና በሻህ ድንኩዋኑን አስተክለው ሙሽሮች የሚቀመጡበት ከፍ ብሎ እንዲደለደል አድርገው ጠረጴዛዎችንና ወንበሮችን ቦታ ቦታቸውን ካስያዙ በሁዋላ የንግዶችን ያቀማመጥ ተራ እዬተመካከሩ መደቡ። ካህናቱ አቶ ማንደፍሮ የከበባቸው አባሎች የውል አባቶችና ውለ - ሰሚዎች እንዲቀመጡ አደረገ። ከዚያ ቀጥለው ሌሎች እንግዶች እንደ እድሚያቸው ወይም እንግዶች ከፈለጉ ተዝናንተው ለመጨዋወት እንዲመቻቸው በዬጉዋድ በዬጉዋዳቸው እንዲቀመጡ ምርጫው ለነሱ እንዲሆን ተስማሙ። ከዚያ ደከሞዋቸው ስለ ነበረ ለማረፍ፥ እዚያው እድንኩዋኑ ውስጥ ተቀምጠው ትንሽ ዝም ብለው እንደ ቆዩ አዝማሪው በማግስቱ እዚያ ድንኩዋን ውስጥ ሙሽሮች አጊጠው ከፍተኛ ቦታቸውን ይዘው በደስታ ሲፍለቀለቁ እንግዶቻቸው በዬተመደበላቸው ቦታ ተቀምጠው እዬበሉ እዬጠጡ እዬተጫወቱ ሲሳሳቁ ሲደሰቱ፥ ያ ሁሉ ታዬውና ፊቱ ፈገግ ብሎ፥ ራሱን ወዝወዝ ወዝወዝ ሲያደርግ በሻህ ተመልክቶ፥

«ምን ታስቦህ ነው ራስህን የወዘወዝህ? » አለው።

«ነገ እዚህ ድንኩዋን ውስጥ የሚሆነው ሲታዬኝ አንድ የቀረ ነገር አስጸጽቶኝ ነው። ነገ አንተና ደመቁ ላንድ ቀን ነግሳችሁ ያን ቀን ‹ልብስ - መንግሥታችሁን› ለብሳችሁ እዚያ ላይ ትቀመጡና፥ ይህን ድንኩዋን የሞላ አጃቢ ሰራዊታችሁ ደስ ብሎት እዬተጭዋወተ እዬተሳሳቀ ሲበላ ሲጠጣ ከከፍተኛ ቦታችሁ ዘቅዝቃችሁ እያያችሁ የምትሆኑትን ሁሉ ስለ ታዬኝ ‹ይህ ሁሉ ሰው መጠራቱና ለዚህ ሁሉ ሰው የሚደረገው ወጪም ድካምም መደረጉ ካልቀረ ምነው ባንድ ፊቱ እማማ ጌጤና ደመቁ እንዳሉት ሙሉ ሰርግ ተደርጎ ዘፈኑም ሌላ ሌላው ለሙሉ ሰርግ የሚደረገው ስራትም ሁሉ ባልቀረ ኖሮ!› ብዬ ሳስብ ነበር።»

«እንዲያ ቢሆን ኖሮማ - ማእረግ ያለው ነገር ይሆን ነበር። ግን እሱ እንዳይሆን ያደረግንበት አይነተኛ ምክንያት እንደምታስታውሰው የሚጋበዙበትን ሰዎች በጥቂቱ አድርጎ ከብዙ ወጪና ከብዙ ዳካም ለመዳን ነበር። ታዲያ በመጨረሻ - ይኸው እንደምታየው የተጠራው እንግዳ ፊት ከታሰበው ከሶስት እጥፍ በላይ ሆኖ ተገኘ! » አለ እብሻህ ቅርተኛ ፊቱን ወደ ጉዋደኛው መልሶ፥ አይን አይኑን እያዬ።

« ‹ሆኖ ተገኘ› ማለት ምን ማለት ነው? ‹እናንተ ያልጠራችሁት እንግዳ ራሱን ጋብዞ ተገኘ› ማለት ነው? አልገባኝም»

«ጋባዡስ እኔ ነኝ፤ ብቻ - ይህን ያክል ሰው የሰው ያጋበዝሁ አልመሰለኝም ነበር። ይህን ያክል ሰው መጋበዜን ያወቅሁት ገና ትናንት ማታ ከማስታወሻየ ለቅሜ ድምሩን ሳይ ነው።»

«ታዲያ - እንዲህ መሆኑን እማማ ጌጤና ደመቁ አውቀዋል? »

«አንተ እስክትመጣና - ‹የምናደርገው ነገር እናገኝ እንደ ሆነ እንክንነጋገር ባቆየው ይሻላል› ብዬ አለንገርሁዋቸውም። እንዲያውም ፈራሁዋቸው! » አለ በሻህ፥ ከቅርታ ፈገግታ ጋር።

«ትዲያ - አብረን አልነበር የአልን? » አለና አዝማሪው ፈገግ ብሎ «አሁንም ቢሆን ግዴለም ‹ሊያውቁ ይገባል› ለማለት ያክል ነው እንጂ ለነሱም ለኛም ችግር አይኖርም። አዲስ አበባ ለዚህ ደህና ነው። እንጀራም ጠላና ጠጅም ምናልባት አሁን ስለ መሸ በግ ባናገኝ የበሬ ስጋ መግዛት ስለምንችል የሚጎድለውን ለማሰናዳት ጊዜ አለ» አለና አዝማሪው በሻህን አጽናንቶ የተፈጠረውን ችግር አስታውቆ የሚጎድለውን ለመጠዬቅ እነወይዘሮ ጌጤ ወደ ነበሩበት ሄደ።

«እማማ ድንኩዋናችነን አያችሁልን? » አለ አዝማሪው ውቤ ጌጤ ደመቀችና ወባዬሁ ባንድ ላይ ተቀምጠው ለወጥ የሚያስፈልጉትን ነገሮች ተከፋፍለው ሲያሰነዳዱ።

«በጣም ጥሩ ስራ ነው የሰራችሁ። አዲሱ ቤት በወጥና በመጠጥ ፍንጣቂ እንዳይበላሽ ምሳው በድንኩዋን እንዲበላ ማሰባችሁን አያመሰገንሁ ለደመቁና ለውቢቱ ስነግራቸው ነው የቆዬሁ» አሉ ወይዘሮ ጌጤ።

«ቤቱ ከመቆሸሹም ሌላ፥ ለሙቶ ሰው አይበቃም ነበር እንጂ! » አለ አዝማሪው።

«መቶ ሰው? ከምን የመጣ - ምን የሚያደርግ እምቶ ሰው ነው? » አሉ ወይዘሮ ጌጤ እንደ መገረም እንደ መደንገጥም ብለው አይኖቻቸውን በጥፍ አውጥተው ባዝማሪው ውቤ ላይ አፍጥጠው።

«ይቅርታ ያድርጉልን እማማ ስህተት አድርገናል። ‹እነገሌን ጠርታችሁ እኛን የተዋችሁን እንደ ዘመዶችና እንደ ወዳጆች ባትቆጥሩን ነው ‹እያሉ አፍ አውጥተው የሚወቅሱት የበሻህ የቅርብ ጉዋደኞችም ወዳጆችም በዙና በይሉኝታ ከጋበዛቸው በሁዋላ ቁጥራቸውን ብናይ ዘጠና ስድስት ሆኖ አገኘው። ያው መቶ ማለት ነው! »

አለ አዝማሪው። ወይዘሮ ጌጤ ነገሩ እውነት አጥተው የማይመስ ስራ ሆነባቸው የሚናገሩትን አጥተው አንድ ጊዜ አስማሪው ውቤን አንድ ጊዜ በሻህን በመገረም አይን አዩና፥

«ታዲያ - እንዲህ ያለ ጉድ - እንዲህ ያለ - አይሰሩት ስራ ስትሰሩ ባይሆን ቀደም አድርጋችሁ አትነግሩንም ኖሮዋል? አሁን እመጨረሻ ላይ ምን እንድናደርግ ነው የምትነግሩን? ወደው ጉ - ድ! እስቲ - ‹ሰላሳ ሰው ብቻ ነው የምንጋብዘው› ስለ ተባለ ለወጥ የተገዙት በጎች ሁለት ብቻ መሆናቸውን ታውቃላችሁ፤ ለመጠጥ የተሰናዳውም አንድ ጋን ጠላና - ከሁለት እንስራ የማይበልጥ ጠጅ ነው። እንጀራውም ቢሆን በመጠኑ ነው። ታዲያ ይሄ - ከሰላሳ ሰው አልፎ እንኩዋንስ ለመቶ ላርባ ሰው ይበቃል? ‹በማግስቱና በሳልስቱ ሊጠይቅ ለሚመጣ ዘመድ አይትረፍ ሁሉም ሙጥጥ ብሎ ነገ ይለቅ› የተባለ እንደሆነ ብቻ ነው ላብራ ሰው እንኩዋ ሊዳረስ የሚችለው! እና - እንዲህ ያለ ነገር ደርሶብኝ ስላማላውቅ ‹እንዲህ ይሁን እንዲያ ይሁን› የምለው ነገር የለኝም። እናንተ እንደ ፈለጋችሁ አድርጉት! » አሉ ወይዘሮ ጌጤ፥ ለሰርጉ እለትም ከሰርጉ በሁዋላ መሰንበቻውንም ‹እንኩዋን ደስ ያላችሁ ጋብቻውን ይበጅ ያድርገው!› እያለ ለሚመጣው ዘመድና ወዳጅ ጋብቻውን ይበጅ ያድርገው!› እያለ ለሚመጣው ዘመድና ወዳጅ መጋበዣ እንደሚበቃ ታስቦ የተሰናዳው መሰናዶ እንደ ታሰበው ለሁሉም የማይበቃ መስሎ ስለ ታያቸው ከመገረምም አልፈው ተቆጥተው።

«እባክዎ አይዘኑብን ይቅርታ ያድርጉልን እማማ! መቸም እናንተን ሳናማክር ተስማምተን ከወሰንነው በላይ ሰው መጥራታችን ብርቱ ጥፋት መሆኑ የታወቀ ነው። ብቻ - እንኩዋንስ የስራ ጉዋደኞችና ወዳጆች ማንም ቢሆን አፍ አውጥቶ ‹ጋበዙኝ› ሲል ‹እንቢ› የማይባል ስለሆነና ‹ጋብዙን› ያሉትን ጋብዞ ያላሉትን መተው ደግሞ ከቅርብ ጉዋደኞችም ከቅርብ ወዳጆችም ለያይቶ ስለሚችል እንዲህ ያለ አስቸጋሪ ሁኔታ አስገድዶ የተደረገ ጥፋት ነው።»

« ‹ብታዝኝ ምን ታደርጊያልሽ?› ትለኝ እንደሆነ እንጂ፥ ማዘንማ እንዴት አላዝን? ዛሬ ቡኮ አቡክቼ ጠላ ጠምቄ ለነገ የሰርግ ምሳ አላደርስ? ከንግዲህስ ያለውን ያው ነግሬያችሁዋለሁ የጠራችሁት መቶ ሰው ነገ የሰርግ ድግስ ሊበላና ሊጠጣ ሲሰበሰብ እንጀራውን እንደ ቤተ ክርስቲያን መክፈልት እዬተፈታችሁ በጅ በጁ ሰጥታችሁ ጠላውንና ጠጁን እንደ ጠበል ረጭታችሁ አሰናብቱትና ያገር መሳቂያ

መተረቻ እንሁን! መቸም የተደረገው ይህን ነው የሚያመጣው! ታዲያ ይህ አያሳዝንም? »

«ብቻ - ባጠፋነው ጥፋት አይዘኑብን ይቅርታ ያድርጉልን እንጂ እንጀራ እንደ መከፈልት እመፈተቱም ጠላና ጠጅ እንደ ጠበል እመርጨቱም እንደርስ። እቤት ባለው ላይ የሚያስጨምረው ከነገሩን አንጀራውንም ጠላውንና ጠጁንም ለወጥ የሚሆን በግ ባናገኝ የበሬ ስጋም አሁን ገዝተን እናመጣለን።»

«በማንም ጭዋ ቤት እንጀራና ጠላ፥ ጠጅ ተገዝቶ ሰርግ ሲሰረግ አይቼም ሰምቼም አላውቅና - እባክህ ዝም በለኝ አቶ ውቤ! »

በሻህና አዝማሪው ውቤ፥ ወይዘሮ ጌጤን እንደያነሉቱ ሲቆጡ አይተዋቸው ስለማያውቁ ሁለቱም አዝነው ፈጣሪያቸውን ምህረት እንደሚለምኑ ሀጢያተኖች አንገታቸውን ደፍተው መሬት መሬቱን እያዩ ዝም ብለው ዘለግ ያለ ጊዜ ቆዩ። ከዚያ፥

«ጥፋተኛው እኔ ብቻ ስለሆንሁ እኔን ብቻ ይውቀሱኝ፤ የሚያዝኑ ከሆነም፤ በኔ ብቻ ይዘኑ እማማ» አለ በሻህ እስከዚያ ድረስ ሳይናገር ቆይቶ። «ጥፋተኛው እኔ ብቻ ነኝ፤ ጋሼ ውቤ በነገሩ ጭራሽ የለበትም፤ እስከ መንገሩም ገና አሁን ነው የነገሁት። ታዲያ እሱ እንዳለው - የማገባ መሆኔን ማን እንደ ነገራቸው እግዜር ይወቅ - አፍ አውጥተው ‹ለሰርግህ ሳትጋብዝን እንዳትቅር› ያሉኝን ጉዋደኞቼንና ወዳጆቼን በመናገራቸው ጠርቼ፥ ሌሎችን ስላልተናገሩ መተዉ አስቸግሮኝ በይሉኝታ ብዛት ነው - እንዲህ ያለ ጥፋት ያጠፋሁ። ደግሞ፥ መሰንበቻውን አሳቤ ተበትኖ ስለ ነበረ ትናንት ማታ ከማስታወሻዬ ለቅሜ ድምራቸውን እስካይ ድረስ እንዲያ ብዙ ሰዎች የጠራሁ አልመሰለኝም ነበር» አለ አንገቱን ከደፋበት ቀና አድርጎ ያዘነ ፊቱን ለወይዘሮ ጌጤ እያሳዩ።

«ጥፋቱ ያንዳችሁ ሆነ የሁለታችሁ ለኔ ምን ያደርግልኛል? ጥፋተኛው አንተ ብቻ ስለሆንህ - የተደረገው እንዳልተደረገ አይሆን! »

«የተደረገው እንዳልተደረገስ አይሆንም፤ ያለፈው መቸም አልፎዋል። ብቻ ለወደፊቱ እንዲህ ያለ ጥፋት የሚያጠፋ ሰው ‹የማይረባ ዋጋ - ቢስ ነው ብለው የሚፈርዱ እንደሆነ ጋሼ፥ ውቤን እንዳይጨምሩ፤ ተነጋግረው የወሰንነውን ሳልጠብቅ የቀረሁ ልበ - ቢስ እኔ ብቻ ስለሆንሁ በኔ ብቻ፥ እንዲፈርዱ› ማለቴ ነው» አለ በሻህ ለሱ ጉዳይ ሌሎች እንዲቸገሩ ራስ ምክንያት በመሆኑ የተሰማው የሀዘን ስሜት ከፊቱ

እዬታዬ። ወይዘሮ ጌጤ እንዲያ ጥልቅ ሀዘን የተሰማው መሆኑን ከፊቱ ሲያዩ ተቆጥቶ የነበረ ልባቸው እንደ መለስለስ አለና «ተወው ግዴለም አትዘን ያለውን እንደ ምንም እናብቃቃዋለን» ብለው ሊናገሩ አፋቸው የደረሰውን መልሰው ውጠው ዝም አሉ። ከዚያ ሁሉም እዬተከዙ ዝም ብለው ትንሽ እንደ ቆዩ፥

«አንተ በሹ» አለች ውባዬሁ ያን ዝምታ አቋዋርጣ። «አንተ በሹ! ያሁኑስ - እማማ እንዳሉት እንደ መከፈልት ተፈትቶም እንደ ጠበል ተረጭቶም መቸም እንዳያልፍ የለ ያልፋል፤ ግን - ለወደፊቱ ይችን ስእሌን ካገባህ በሁዋላም - እኒያ ሙቶ ጉዋደኞችህና ወዳጆችን ‹ስንሞትልህ ጋብዘን› ባሉህ ቁጥር በይሉኝታ እነሱን እያንጋጋህ እዬገባህ - ‹እንጀራሽና ወጥሽ ይበቃል ወይ?› እያልህ ሳታሳፍራት ልትኖር ነው? እ እ! በኔ እት ኪሳራ አንተ ባለ ይሉኝታ አትሆንም! ምነው ውቢቱ! አንቺ ስእሌ ይህን አመሉን ካልተወ በዚሁ የሚቀጥል ከሆነ እዚያው ከሙቶ ጉዋደኞቹና ወዳጆቹ ጋር ትተሽው ው - ል - ቅ ነው! » ስትል ውባዬሁ ያንገትዋንና የጆችዋን ንቅናቄ ከንግግርዋ ጋር አስማምታ ሁሉም ወይዘሮ ጌጤ ሳይቀሩ ከንግግርዋም ሁኔታዋን እያዩ በንድነት ሲስቁ ተጭኖዋቸው የነበረው ከባድ ቅርታ ከዬትከሻቸው ላይ ገለል ሲል ተሰማቸው። የውባዬሁም አላማ ያው ነበር። ውባዬሁ ያን ቀልድ ያመጣች እቤት የተሰናዳው ከሰርጉ እለት በሁዋላ መሰንበቻውን ለሚመጡ እንግዶች መጋበዣ ያንሳል እንጂ፥ ለሰርጉ ከስጋ በቀር ጠጁና ጠላውም (ቡኮ ስለ ነበረ ሌሊቱን ተነጋግሮ ተጨምሮ) እንጀራውም እንደሚበቃ ታውቅ ስለ ነበረ፣ መቸም ለሰርጉ የተጠራው እንግዳ ተጋብዞ መሄዱ ሳይቀር፥ በወይዘሮ ጌጤና በበሻህ መሀከል ቅርታ እንደ ተፈጠረ እንዳይለያዩ ብላ ነበር።

«ዝ - ም በይ አንቺን፥ የጠራሽ የለም! » አለ አዝማሪው ውቤ፥ ከሌሎች ጋር ሲስቅ ቢቆይም እንዲያ ያለ አስቸግሪ ሁኔታ ተፈጥሮ ሳለ በእምቀለድዋ የተቆጣ ለመምሰል በውሸት ግንባሩን ቁዋጥሮ።

«ታዛዥህ ነኝ ጌታየ! ‹ዝ - ም›! ‹ዝ - ም›! » ስትል ውቢቱ እንደሱ ‹ዝም› ን አስረዝማ፤ እንደገና ሳቅ ሆነ።

ወይዘሮ ጌጤ በውባዬሁ ቀልድ ከሌሎች ጋር ሲስቁ ቆይተው በሻህንና አዝማሪው ውቤን እንደ ቆሙ ትተዋቸው በወጥ ቤታቸው በኩል ወጡና ዘበኛቸውን ጠርተው ለወጥ የሚሆን የበሬ ስጋ ቶሎ ገዝቶ እንዲያመጣ ገንዘብ ሰጥተውት አልተመለሱም፤ እወጥ ቤታቸው ገብተው ስራ ጀመሩ። አዝማሪውና በሻህ ቆመው ሲጠብቁ ቆይተው

አለመመለሳቸው እነሱን ማሰናበታቸው መሆኑ ስለ ተረዱ ገለል ብሎላቸው የነእብረው አዘን እንደ ገና ተሰማቸውና እዬተከዙ ወጡ።

«አትዘኑ ልጆቼ! በጋ ሊያዘንብ የሚችለው ጌታ የኛን ትንሽ ጉዋዳ ሞልቶ ማደር አያቅተውምና! » አለች ውቢቱ በሻህና ባልዋ እያዘኑ ሲወጡ።

አዛዥ ተካልኝ ሊሞቱ አቅራቢያ ፈርተው እንደ ነበረው ባልተቤታቸው ወይዘሮ ጌጤ ወዲያውኑ በድህነት ላይ አልወደቁም። ደጃዝማች አሰፋ ተጫኔ አዛዥ የሞቱበትን ምክንያት በዝርዝር ከተረዱ በሁዋላ፤ በጣም አዝነውና ተጸጽተው ‹የሞተን ወዳጅ በቀሪ ወገኑ ይክሱታል› እንዲሉ ካዛዥ አምሳ ብር የወር ደመወዝ ሀያውን ካንድ ጋሻ መሬታቸው ሩቡን ለወይዘሮ ጌጤ ትተውላቸው ስለ ነበረ፥ ጥሩ አስተዳደር አዋቂ በመሆናቸው ራሳቸውን ችለው ደህና የሚኖሩ ነበሩ።

በሻህና አዝማሪው ውቤ ወጥተው እደጅ እንደ ቆሙ አቶ ማንደፍሮን በማግስቱ ጥዋት ወደ ቤተ ክርስቲያን ስለሚሄዱበት ሰአትና ከቤተ ክርስቲያን በሁዋላ ወደ ቤታቸው ከመመለሳቸው በፊት ሄደው ስለሚቀዩበት ቦታ ያሰቡትን ከነበሻህ ጋር ለመነጋገር በኦቶመቢል - እንደ ልማዳቸው ከነጃቸው ጎን ተቀምጠው - ሲመጡ አዩቃቸውና ሊቀበሉዋቸው ወዳጥሩ በር ሄዱ።

«ትልቅ ግብዣ ልታደርጉ አስባችሁዋል መሰለኝ - ይህን ያክል ድንኩዋን የተከላችሁ! » አሉ አቶ ማንደፍሮ ከኦቶመቢላቸው ወርደው ለሁለቱም የጅ ሰላምታ ከሰጡ በሁዋላ።

«ድንኩዋኑስ - ትልቅ ነበር! » አለ በሻህ እንደ መሳቅ ብሎ።

«ታዲያ ምኑ ነው ትንሽ? »

በሻህ እንደ ማፈር ብሎ አንገቱን ደፍቶ ትንሽ ዝም ብሎ ቆይቶ፥ ያደረገውን ጥፋትና የወይዘሮ ጌጤን በጣም ማዘን በዝርዝር ሲነግራቸው፥

« ‹ልጅ ያቦካው ለራት አይበቃም› የተባለው ልጆች እንዲህ እንዲህ ያለ ጥፋት ማድረጋቸው የተለመደ ስለሆነ ነውኮ! ብቻ - ግዴለም አትዘኑ። ጥፋተኛ ባይኖር ኖሮ ‹መታረም› የሚባለው ነገርም ቃሉም አይኖሩም ነበር። የማይታረም ነገር የለምና ይህም ይታረማል» አሉ አቶ ማንደፍሮ በሻህ ጥፋቱን ሲነግራቸው ሲስቁ ቆይተው።

«ታዲያ እኔ - እንዲያው ከበላዩ ልበ - ቢስ ብሆን ነው እንጂ - ልጅ አደለሁ! የሆነ ሆኖ ያጠፋሁትን ለማረም የሚጎድለውን እንዴንግሩንና አሁን ገዝተን እንድናሙዋላ እማማ ጌጤን ጋሼ ውቤና እኔ ብንጠይቃቸው ‹በጭዋ ቤት እንጀራና ጠላ ተገዝቶ ሰርግ ተደርጎ አያውቅም› ብለው ተቆጥተው ተነስተው ስለሄዱ ምን ማድረግ እንደሚሻል ቆመን ስንነጋገር ነው እርስዎ የመጡ።»

«መቸም - » አሉ አቶ ማንደፍሮ አንገታቸውን ደፋ አድርገው ትንሽ ሲያስቡ ቆዩና፥ «መቸም የተሰናዳው ድግስ የማይበቃ ከሆነ የታደመውን እንግዳ ጋብዞ ለመሸኘት ወይ ገዝቶ ያለዚያም ታምር ሰርቶ መሆን አለበት የጎደለውን መሙላት የሚቻል! በነህ በቀር ሌላ መንገድ አለበት የጎደለውን መሙላት የሚቻል! ከነህ በቀር ሌላ መንገድ ያለ አይመስለኝም። ስለዚህ ገዝቶ መሙላቱን እሜቴ ነውር ከቆጠሩት ታምር መስራት ሊኖርብን ነዋ! » አሉ እንደ መሳቅ ብለው፥ በሻህንና አዝማሪውን እያለዋወጡ እያዩ።

«እንዴት ያለ ታምር ነው የምንሰራ? » አለ በሻህ ቅር ያለው ፊቱን ወደሳቸው አቅንቶ።

«ቀኝ ጌታ ከቀጨኔ መድህኔ አለም የሊቅነቱ ስደተኛ መሆኑን ነግረኸኛል፤ አንተም የሚሲዮን ተማሪ የነበርህ መሆንህን አውቃለሁ፤ ስለዚህ ሁለታችሁም በታምር ሁለት አሳና አስምት እንጀራ ከብዙ ሴቶችና ከብዙ ህጻናት ሌላ አምስት ሺህ ሰዎ ከተጋበዙለት በሁዋላ አስራ ሁለት መሶብ ሙሉ ፍርፋሪ ተፍሮ መመለሱን ታስታውሱ የለም? »

«አዎ እናስታውሳለን፤ ብቻ - እንዲያ ያለውን ታምር የሰራ ክርስቶስ ነው እንጂ ሰው አይደለምኮ ጌታየ! » አለ አዝማሪው ውቤ በሻህ የሚመልስ መስሎት ቢጠብቅ ዝም ስላለ ለመጀመሪያ ጊዜ በንግግሩ ጣልቃ ገባና።

«ልክ ነው ያን ታምር የስራ ክርስቶስ ነው። ግን እምነት ያላቸው የሱ ተከታዮች ሁሉ እንዲያ ያለ ታምር ሊሰሩ የሚችሉ መሆናቸውን ገልጾ ያን ምሳሌ እንዲሆን ሰርቶ ያሳቸው ነበር። ስለዚኢህ የሱ ሁለት አሳና አርስት እንጀራ ከሴቶችና ከህጻናት ሌላ አምስት ሺህ ህዝብ አጥግቦ አስራ ሁለት መሶብ ሙሉ ፍርፋሪ የተፈረፈ ከሆነ አምነት ብቻ ያስፈልጋል እንጂ የናንተ ሁለት በግና ለስላሳ ሰው የተሰናዳው እንጀራ ጠጅና ጠላ መቶ ሰው አጥግቦ ለብዙ ሊተርፍ ይችላል! » አሉ አቶ ማንደፍሮ አሁንም እንደ መሳቅ ብለው በሻህንና አዝማሪውን እያለዋወጠ እያዩ።

«አየ - እንዲያ ያለ እምነት ያለው ሰው ዱሮ እንደሆነ እንጂ ዛሬ የት ይገኛል? » አለ አዝማሪው አይኖቹን ካቶ ማንደፍሮ ወደ መሬት መለስ አድርጎ።

«ዛሬም ቢሆን አንዳንድ እምነት ያላቸው ሰዎች አይተፉ። ይግረምህና ዛሬም እኔ ቤት እንዲያ ያለ ታምር የሚሰራ በምነት ‹ተራሮችን ተነስታችሁ ሂዱ› ቢላቸው የሚታዘዙት ሰው አለ! አንተ ፍሰሀ ታሪኩ አሻግሬ እንዲያ ያለ ታምር ይሰራ የለም? » አሉ ወደ ሾፌራቸው ዘወር ብለው።

«አዎ ጌታየ» አለ ፍሰሀ ጌታውን ፊት ለፊት ማየት ስላፈረ አንገቱን ደፍቶ ማረፊያ ያጡ አይኖቹን ወደ ቀኝም ግራም እያዙዋዙዋረ እያዩ። ፍሰሀ ጌታዉን ላለማስተሀቀር ብቻ ጥያቄያቸውን ባዎታ መለስ እንጂ ነገሩ ገብቶት አልነበረም፤ ታሪኩ አሻግሬ ያቶ ማንደፍሮ ሆቴል ሹም ነበር።

«አቶ ታሪኩ አሻግሬ አማኝ ስለሆነ ታምር የመስራት ጸጋ የተሰጠው ሰው ነው። ስለዚህ ለሰላሳ ሰው የተሰናዳው ድግስ ለሙቶ በቅቶ ለሌላ ሙቶ እንዲተርፍ ለማድረግ እንደ ልማዱ ታምር እንዲሰራ እንድለምነዋለንና እነሜቴን አታስቸግሩዋቸው» አሉ አቶ ማንደፍሮ በቀልድ መልክ። በሻህ አሳባቸው ስለ ገባው ልቡ ተነክቶ ስሜቱ ከፊቱ እንዳይታይበት ቶሎ ዘወር አለ። ከዚያ በማግስቱ ስለሚከተሉት ስለ ጋብቻው የስነ - ስራት ተራ እድንኩዋኑ ውስጥ ቁጭ ብለው ተነጋግረው ከተሰማው በሁዋላ አቶ ማንደፍሮ ቶሎ ወደ ቤታቸው ሄዱ.......

ያነለት ማታ ራት ቀደም ብሎ በጊዜ፥ ተበልቶ፥ በሻህና አዝማሪው ውቤት ወደ ምኝታቸው ሲሄዱ ወይዘሮ ጌጤ ደመቀችና ውባዩሁ ከሌሎች ሴቶች ጋር ወደዩስራቸው ተሰማሩ። እራት ላይ ወይዘሮ ጌጤ ‹ከሰርጉ እለት በሁዋላ መሰንበቻውን ለሚመጣ እንግዳ መጋበዣ ይሆናል› ብለው በጎን ያስቀመጡት ተጨምሮ የተሰናዳው መሰናዶ ለለቱ የሚበቃ መሆኑን አይተው ስላረጋገጡ በሻህና አዝማሪው ውቤ ለሰላሳ ሰው የሚሰናዳው ድግስ ያቶ ማንደፍሮ ሆቴል አዛዥ ታሪኩ አሻግሬ በታምር ለሙቶ ሰው እንዲበቃ የሚያደርገው መሆኑን አቶ ማንደፍሮ ‹በዘይቤ› ስለ ነገሩዋቸው ሁለቱም ወገኖች ምክንያቱን አይገላለጹት እንጂ በማግስቱ የሚደርስባቸው መስሉዋቸው የነበረው ውርደት የማይደርስ መሆኑን አውቀው እንደ መሰንበቻው እዬተጨዋወቱ እዬተሳሳቁ በልተው ተነሱ.......

አዝማሪው ውቤና በሻህ አቶ ማንደፍሮ ሸኝተ እንድኩዋኑ ውስጥ እንደ ተቀመጡ አንድ ልጅ እየሮጠች መጥታ «ለራት ትጠበቃላችሁ ተብላችሁዋል» ብላቸው ስለ

ሄደች እነ ወይዘሮ ጌጤ ቀርበው የሚጠብቋቸው መስሉዋቸው ተእንስተው እዬተቻኮሉ ራት ሲበሉ ወደ ሰነበቱበት ወዳዲሱ ቤት ቢሄዱ እንኩዋንስ ራት ሊቀርብ እነወይዘሮ ጌጤም በቦታው አልነበሩ። ወይዘሮ ጌጤ ደመቀችና ውባዬውሁ ራቱን ይዘው እነሱ ከገቡ በሁዋላ መጡ። ወይዘሮ ጌጤ ፊት ለፊት ውባዬሁና ደመቀች ቀላል ራት ይዘው ተከታትለው ከነሱ በሁዋላ የጣት ውሀ የያዘች ልጅ ተከትላ ሲገቡ አዝማሪው በዘፈን ስለ ተቀበላቸው ዘፈኑ ቀደም ብለው ከነበሩበት ከባድ ቅርታ በቀጥታ ወደ ጭዋታና ወደ ሳቅ ለመተላለፍ፥ በር ከፋች ሆናቸው።

«እማማ ጌጤነሽ ዝንከትዋ ወይዘሮ፥ እንኩዋን ደህና መጡ፥

ተጨንቀን ነበረ ቅድም ተቆጥተው፥ ትተውን ሲወጡ፤

እሲ እንደ ድሮዎ በደስታ ፍንክንክ ብለው ይቀመጡ፣

ፈገግ ይበሉና፥ ሽሙንሙን እያሉ ጥርስዎን ይግለጡ፤

ይቅርታዎንና ፊትዎ መጥፎ ነው አያምሩም ሲቆጡ፤» ሲል

አዝማሪው እንደ እንዲር በሚዝገመገም ውብ ድምጽ፥

«ውይ! ኧረ ፊተ መጥፎ - እዚያው አንተ ነህ! ደሞ ‹ፊትሽ መጥፎ ነው› ብሎ ይሰድበኛልኮ! ሆ! ሆ! ሆ! » አሉ ወይዘሮ ጌጤ እዬሳቁ ሲቀመጡ። ደመቀችና ውባዬሁም ይስቁ ጀመር። የጣት ውሀ ይዛ የነበረች ልጅማ አይ ደስታዋ! ቀደም ብለው፥ ወይዘሮ ጌጤ እንዲያው በማያስቆጣ ነገር ተቆጥተዋት በሽቃ ስለ ነበረ አዝማሪው ሲሰድብላት ደስ ብሎዋት ስቃ አላበቃ አለች።

«ጥርስሽን ያርግፈውና ሳቁን ወዲያ ሀኢደሽ ታረጊዋለሽ፥ አሁን የመጣሽለትን አስታጥቢን አንቺ - » አሉ ወይዘሮ ጌጤ፥ እሳቸው ስለ ተሰደቡላት ደስ ብሎዋት መሳቅዋ ገብቶዋቸው በፈንታቸው በሽቀው። ከወይዘሮ ጌጤ በሁዋላ አዝማሪው እዬታጠበ በበሻህ የሚቀልድ አስመስሎ ተቆጥተው ሳለ ‹እንጀራውን እንደ መክፈልት ፈትታችሁ ጠላውንና ጠጁን እንደ ጠበል ረጭታችሁ የጠራችሁትን እንግዳ ሸኙ› ያሉትን በግጥም እዬዘፈነ ሲያስታውሳቸው እንደ ገና ብቅ ሆነ።

«መቸም የበሻህ ጉድ አያልቅ ተወርቶ፥

‹ሚስት ላግባ› አለና ሚስት ሲያገቡ አይቶ፥

የማያውቅበትን ‹ሰርግ ላርግ› ‹ሰርግ› ሲሉ ሰምቶ

‹ሰርግ ልጋብዛችሁ› ብሎ ህዝቡን ጠርቶ -

ህዝቡም እውነት መስሎት ጮማ ጠጅ፥ ሊጋበዝ ሲጠብቅ ጎምዥቶ -

በጅ በጁ አስያዘና እንጀራ እንደ መከፈልት ፈትቶ ፈትቶ

በጣላ እንደ ጠበል አይን እይኑን ረጭቶ

አባረረው ወዲያ ጋኔን እንደ ያዘው ‹እግዜኦ› አሰኝቶ» ሲል

«ና እባክህ ሳመኝ የኔ ውብ! እውነትም እንደ ስምህ ውብነህ! ‹ስምን መላክ ያወጣዋል› አደል? » አለችና ውቢቱ ከሌሎች ጋር ስትስቅ ቆይታ አንገቱን እቅፍ አድርጋ ሳመችው.......

ከራት በሁዋላ ወይዘሮ ጌጤ ደመቀችና፥ ውባዬሁ እቤት ከነበረችቱ ሰራተኛና ሊረዱ ከመጡት ጎረቤቶች ጋር ስራውን ተከፋፍለው እንጀራ የሚጋግሩት ቡኮ አቅጥነው ሲጋግሩ ወጥ የሚሰሩት ከበግ ስጋው ጋር ሁዋላ ተገዝቶ የመጣውን የበሬ ስጋ ጨምረው ሲሰሩጠጅ የሚያጣሩት እያጣሩ በጋንም ከጋን የተረፈውን በንስራዎች ሲያስቀምጡ ባለጠላዎችም ድፍድፍ በጥብጠው እንዲሁ በንስራዎች ሲያስቀምጡ ሌሊቱ ተገባደደ።

ምን ጊዜም ቢሆን ከነወይዘሮ ጌጤ ቤት ጠላ ተለይቶ ስለማያውቅና በዬጊዜው ጠላ የመጥመቁ ስራ አድካሚ በመሆኑ ደመቀች እዚያ ቤት መኖር ከጀመረችበት ግዚኤ አንስቶ እንደ ጎጃሞች ለብዙ ጊዜ የሚሆን ድፍድፍ ደፍድፎ ማስቀመጥ የቤቱ ልማድ ሆኖ ነበር። ስለዚህ ለዚያ ጊዜም የተሰናዳው ድፍድፍ ለሰርጉለት በቅቶ ለብዙ ጊዜ የሚተርፍ ስለ ነበረ፥ በጠላ በኩል ‹ችግር ይኖራል› ተብሎ ፈቱንም ስጋት አልነበረ። ከስራው የሚበዛው ተጠናቅቆ የተረፈውም ደህና መንገድ መያዙን ካረጋገጡ በሁዋላ ሌሎች ሴቶች እንዲጨርሱት አድርገው ወደ ስምንት ሰአት ግድም ወይዘሮ ጌጤ ደመቀችና፥ ውባዬሁ ለማረፍ ወደ ምኝታቸው ሄዱ። ውባዬሁ እደመቀች አልጋ ላይ አብራት ነበር የተኛች። ራስዋ መከዳውን ከመንካቱ ወዲያ እንቅልፍ ወሰዳት። ደመቀች ግን በበነጋው ከጥዋት ጀምሮ ቀኑን ሙሉ የሚሆነውም ከበሻህ ጋር ከተጋቡ በሁዋላ የሚሆነውም በተራ ተከታትሎ እዬመጣ ባይነ - ህሊናዋ ፊት ሲያልፍ እዬታያት እንቅልዋን ብታባብለው አልመጣላት ስላለ አይኖችዋን በጨለማው ውስጥ እንዳፈጠጠች ብዙ ቆዬች።

ጥዋት በሻህና እስዋ እቤተክርስቲያን ሄደው ላይከዳት፤ ላትከዳው በስጋ ወደሙ ምለው ሲቆርቡ ከዚያ ተመልሰው እድንኩዋኑ ውስጥ በተደላደለላቸው ከፍተኛ ቦታ ተቀምጠው ለሰርጋቸው የተጠራው ሰው ያን ድንኩዋን ሞልቶ እዬበላ እዬጠጣ እነሱን ሽቅብ እያዬ ስለነሱ እያወራ የሚስቀው ሲስቅ የማይስቀው ራሱን ባዎታ ወይም ባሉታ እዬወዘወዘ ሲነጋገር ታያትና «ምን ይሉን ይሆን? ‹እሱም እስዋም በሁለት በኩል ደመወዝ የሚያገኙ በመሆናቸው ብር ስለ ሞላቸው ነው ለሁለተኛ ጋብቻቸው ይህን ያክል ሰው ጠርተው የሚጋብዙ› እያሉ ያሽሙዋጥጡን ይሆን? አየ - እንጃ! የሚበዙት ‹ጋብዙን› ብለው ጠይቀው የተጋበዙ ስለ ሆኑ እንዲያ የሚሉ አይመስለኝም» አለች።

ከዚያ እስዋና በሻህ ተጋብተው የሚኖሩት የደስታ ኑሮ ይታያታል። እቤት እንደ አንዳንድ የምታውቃቸው ባልና ሚሽት በገንዘብ ወይም በቅናት ተጣልቶ መጨቃጨቅ አይኖር። ሁልጊዜ ሲጨዋወቱ፥ ሲሳሳቁ ሲቃበጡ፥ ያመሹና ራታቸውን በልተው እቅፍቅፍ ብለው ሲተኙ እቤት መቆየት ባልፈለጉ ጊዜ፥ ወደ ሲኒማ ሲሄዱ አምቦ ሄደው እንደሱ ጌጠኛ እጅ አጣጣል ያስተምራትና ጎን ለጎን እጅ እዬጣሉ ሲዋኙ ያያቸው ሰው ሁሉ ሲያደንቃቸው ይታያታል።

ከዚያ ደስ እንዳላቸው እዬኖሩ አንድ በሻህን የሚመስል ወንድና ሁለት እስዋን የሚመሳስሉ ሴቶች ልጆች ወልደው ራሳቸውን በልጆቻችው እያዩ ደስታቸው ፍጹም ሲሆን ይታያታል። ከዚያ አርጅተው በሶፋ ወንበሮቻቸው ላይ ጎን ለጎን ተቀምጠው ባለፈ ህይወታቸው ደስ ያሰኙዋቸውንም ያሳዘኑዋቸውንም ነገሮች እያስታወሱ ሲሳሳቁ ይታያታል። ከዚያ ‹አባ መርሻና› ‹እማሆይ ሻሽቱ› የተባሉ እጅግ ይዋደዱ የነበሩ ባልና ምሽት አርጅተው መኩሰው ሲኖሩ በተስቦ በሽታ ባንድ ቀን ሞተው ሬሳቸው አንድ ላይ በመውጣቱ ‹ታምር› ተብሎ ሲነገር አገርዋ ሳለች እድነ ሰማችው እስዋና በሻህም እንዲያ ተዋደው ኖረው ካረጁ በሁዋላ የኔን ሞት እስዋ የስዋን ሞት እሱ ሳያዩ ባንድ ቀን ሞተው ሬሳቸው አንድ ላይ ሲወጣ ያዬና ፍቅራቸውን ያውቅ የነበረ ሁሉ ‹ግሩም ነው ታምር ነው!› እያለ እስበሱ ሲተች ይታያትና እውነት ያንግዜውኑ ሁለቱም ሞተው ሬሳቸው ባንድ ላይ ሲወጣ እንዳዬች ሁሉ አዘን ተሰምቶዋት የቅርታ ፈገግታ ፈገግ አለች። እንዲያ እጨለማው ውስጥ ፈገግ እንዳለች ትንሽ ቆዬችና፥

‹ሳናረጅ፥ ወይ እኔ ወይ እሱ ቀድመን የሞትን እንደሆነሳ? እንጃ! ፈጣሪየ አያርብኝ እንጂ እሱ ቀድሞኝ ከሞተ መንኩሼ አንድ ገዳም ወይም አንድ ቤተክርስቲያን ተጠግቼ መቃብር ቤት ነው የምኖር!› አለች የሁለታቸው ሬሳዎች ባንድ ላይ ሲታዩዋት በቅርታ ለስልሶ የነበረ ስሜትዋ የበሻህን ብቻ መሞት ስታስብ ክርር ብሎ። ስለ መቃብር

ቤት ኑሮ ስታስብ እናታችንና እማሆይ ወለተዬሱስ ልክ መጀመሪያ እንዳዬቻቸው ደብረ ማርቆስ መቃብር ቤታቸው በራፍ ወይባ የተነከረ ልብሳቸውን ለብሰው ቆባቸውን አድርገው ተቀምጠው እዬተጨዋወቱ ሲሳሳቁ ታዩዋት። ከዚያ መንኩሳ አብራቸው እንድትኖር የለመነቻቸውና መቃወማቸው እዚያ በቆየችበት ጊዜ በማሆይ ወለተዬሱስ እግር ተተክታ የሳቸውን ስራ እዬሰራች ስትሰነብት ያዬችው የኑሮዋቸው ስራት የሚጾሙበት ጊዜና ሁኔታ ሁሉ ተያይዞ መጥቶ አንድ፥ ባንድ እሱን ስታይ ውባዬሁ በንቅልፍ ልብዋ ‹እ - › ብላ በረዥሙ አማለለችና እንደምትበላ ሁሉ ማላመጥ ስለ ጀመረች እሳብዋ እናታችነንና እማይሆ ወለተዬሱስን እመቃብር ቤታአቸው ትቶ ወደ ውባዬሁ ተመለሰ።

ውባዬሁ እንዲያ ስታላምጥ ትንሽ ቆይታ ምስጢር በጆሮ እንደምትናገር ሁሉ ቀስ፥ ብላ ተንሾካሹካ፥ ‹ሄ - ሄ - ሄ - ሄ - ሂ - ሂ - ሂ - ሂ -› ብላ ስቅስቅ እንዲሁ በሹክሹክታ ደመቀችም ሳቅዋን መግታት አቅትዋት ‹ከት ከት› ብላ ሳቀች። ውባዬሁ ደመቀች ስትስቅ በግማሽ ነቃታ ‹ምን ያስቅሻ -ል? በክሽ ተ- › አለችና መናገር ከፈለገችው ቃል የመጨረሻው ፊደል ‹ኘ› ካፍዋ ሳይወጣ እዚያው እንዳለ እንቅልፍ መልሶ ወሰዳት። ደመቀች ብቻዋን ስትስቅ ቆይታ እዬመጣ እዬሄደ እንቅልፍ ከልክሎዋት የነበረው ያሳብ መንጋ ሁሉ ካይነ ህሊናዋ ፊት ገለል ሲላላት ተኛች። ግን ተኝታ ብዙ አልቆዬችም። ውባዬሁ ነቅታ መብራት አጥፍተው ሲተኙ እቤት ውስጥ የነበረ ከባድ ጨለማ ቀለል ብሎ ስለ ታያት መብራቱን አብርታ ሰአትዋን ብታይ ከንጋቱ አስራ አንድ ሰአት ሆኖዋል። ሙሽሮቹ ካስራ ሁለት ሰአት ቀደም ብለው ለጸሎት እቤተ ክርስቲያን እንዲደርሱ ነበር የተቀጠሩት።

«ደመቁ ተነሺ» አለች ውባዬሁ ደመቀችን፥ ከተኛችበት እዬነቀነቀች።

«አየ - ተይኝ እባክሽ ልተኛበት! » አለች ደመቀች፥ ከሚጥም እንቅልፋዋ ስለ ተቀሰቀሰች እያማረረች።

«ተነሽ ታጠቢና ልበሺ ሰአቱ አልፎዋል።»

«ስንት ሰአት ሆነ? »

«ካስራ አንድ አልፎዋል።»

ደመቀች መታጠቢያ ቤት ሄዳ ራስዋንም ፊትዋንም ከታጠበች በሁዋላ ከኍልት፥ አመት በፊት ገዝታ እመኝታ ቤትዋ ባስገባችው ቁም መስታዋት ፊት ቆማ እያዬች

ስትታጠብ የተፍተለተለውን ጠጉርዋን ውባዬሁ በማበጠሪያ እያፍታታች ስታበጥርላት መድረቁን ተመልክታ «ጠጉርሽንም ፊትሽንም አሁን ስለ ታጠብሽ ፊትሽ ነጥቶዋል ጠጉርሽም በጣም ደርቆዋል ትንሽ ቅባት በጆቼ መሀል ልምታና ልሽልሽ» አለች።

«ይቅርብኝ ውቤቱ ይብለጨለጭብኛል።»

«ይህን እንደ ጭራሮ የደረቀ ጠጉርሽንና የነጣ ፊትሽን ለማለዘብ ያክል ነው እንጂ እስኪብለጨለጭ ድረስ ቅባት አላበዛሽምኮ! ጭራሽ አይታይም። እስቲ አድርጌልሽ እይውና የሚብለጨለጭ ከሆነ በፎጣ ፈግፍገን እናጠፋዋለን።»

እውነትም ውባዬሁ እንዳለችው ትንሽ ያምበሬጭቃ ቅባት ከሽቶ ጋር አደባልቆ በመሀል እጆችዋ መትታ ጠጉርዋንና ፊዋን እሽ - ት ካደረገችላት እብሁዋላ ሲያዩት ቅባቱ የደረቀ ጠጉርዋን ከማለዘብና የነጣ ፊትዋን ከማለስለስ በቀር እንኩዋንስ ሊብለጨለጭ ምልክቱም አይታይ ነበር። ጠጉርዋ ለዝቦ ተበጥሮ፥ ፊትዋ ለስልሶ አምሮ ያችው የሁልጊዜይቱ ውብ ደመቀች ሆነች። ከሁልጊዜ የተለዩ አዲስ ነገሮች የተጨመሩ ካባውና ተረከዘ ረዥሙ ጫማ ነበሩ። ከዚያ አዲስ ጥልፍ ቀሚስና አዲስ ጥበብ ኩታ ለብሳ በላይ ክሳዱ በደማስ ከፈይ የተከፈፈ አረንጉዋዴ ቀለም ካባ ደርባ ባለ ረዥም፥ ተረከዝ ጫማ፥ አድርጋ ከውባዬሁ ጋር ሲወጡ በሻህንና አዝማሪው ውቤን በመዘግየታቸው የተቃጠሩበት ጊዜ እንዳያልፍ ሰግተው በዬደቂቃው ሰአታቸውን እያዩ ሲንቆራጠጡ አገኙዋቸው።

በሻህ፥ ቦልቦሌ ነጭ ሱሪውን ታጥቆ ነጭ እጀ ጠባብ ነጭ ኮትና ጥበብ ኩታውን ለብሶ በላይ ክሳሱ ባረንጓዴ ከፈይ የተከፈፈ ዳማ ቀለም ካባውን ደርቦ ውብ ጠጉሩ ጥሩ ሆኖ ተካክሎ ተበጥሮ አምሮበት ነበር።

« ‹ሴትና ልግመኛ አህያ ከሁዋላቸው እዬተከተሉ ካልነዱዋቸው በቆሙበት ውለው ያድራሉ እንጂ፤ ‹አውቀው ይሄዳሉ ማለት ‹ዘበት ነው› የሚሉት ተረት እውነት መሆኑ ዛሬ በናንተ ተመሰከረ» አለ አዝማሪው ደመቀችና ውባዬሁ ከቤት ሲወጡ።

«ይቅርታህን እሱ የረኞች ተረት ነው፤ የጭዋዎች ተረት፣ ‹ሴትና ውቃቢ፥ ቀረብ ብሎ ካልተለማመኑዋቸው አይነሱም› ነው» አለች ውቢቱ ባልዋን ከውብ ፈገግታ ጋር ገደም አድርጋ እያዬች።

ከዚያ ውባዬሁ ለስራ ወደ ቤት ስትመለስ ኦቶመቢል ቀርቦ ይጠብቃቸው ስለ ነበረ፥ ደመቀችና በሻህ እሁዋላ አዝማሪው ውቤ ከነጁ ጋር ተቀምጠው እቤተ

ክርስቲያን ሲደርሱ አቶ ማንደፍሮን ከክበባቸው አባሎች ጋር የውል አባቶችን ውለ ሰሚዎችንና ብዙ የበሻህን ጉዋደኞችም ወዳጆችም ተሰብሰበው ሲጠብቁ አገኙዋቸው።

«ምነው? በደህንነት ነው የቆያችሁ? አሁን አንድ ዲያቆን መጥቶ ‹ዛሬ ቀርበው እንዲጋቡ ቀጠሮ የተደገላቸው ሙሽሮች ቀርተው ነው? ወይስ ለምን ዘገዩ?› ብሎ ጠይቆን ‹በመንገድ ናቸው› በለን መለስነው» አሉ አቶ ማንደፍሮ።

«የአቶመቢላችን ጎማ ተንፍሶብን ስናስሞላ ነው» አለ አዝማሪው ውቤ ውሽቱን።

ወዲያው ሙሽሮች ሲጠብቁዋቸው በቆዩት አጃቢዎቻቸው ታጅበው ወደ ቤተ ክርስቲያኑ ቅድስት ሲገቡ ‹ጸሎተ አስተስርዮ› የሚያደርጉላቸውና ሁዋልማ የሚቆርቡዋቸው አምስት ካህናት (አንድ ገባሬ ሰናይና አንድ ንፍቅ ቀሳውስት አድን ስረይና ሁለት ላእካን ዲያቆናት) ልብሰ ተክህኖዋቸውን ለብሰው ለጸሎቱ የሚያገለግሉዋቸውን ሌሎች ንዋየ ቅድሳት ይዘው ጸሎት የሚያደርጉበትን ቦታ ከብበው ቆመው ይጠብቁ ነበር።

«ኑ ወዲህ ቅረቡ» አሉ ንፍቁ ቄስ የከበቡትን ቦታ ለሙሽሮቹ በጃቸው ሲያመለክቱ ወዲያው ፈገግ ብለው እንደ መስገድ አሉና።

ሁልጊዜ ከቅዳሴ በፊት እቤተ ክርስቲያን እንደሚሰፍነው ጸጥታ ያነለትም ቅድስቱንና ቅኔ መአልቱን የሞላው ህዝብ ጸሎቱና ትንፋሽ ሳይሰማ በያፉ ውስጥ ይዞ ይደግም ስለ ነበረ ከጽናቸው ቻቻታ በቀር ምንም ድምጽ የማይሰማበት ጸጥ ሰጥ ያለ ነበር። ጢማቸው ካገጫቸው ወርዶ አንገታቸውን አልፎ በደረታቸው ላይ የተነጠፈው ገባሬ ሰናይ ቄስ የጅ መስቀላቸውን ይዘው ንፍቁ ቄስ ወደ ፊትና ወደ ሁዋላ ሲወዘውዙት የጣን መአዛውን በቤተ ክርስቲያኑ ውስጥ ሁሉ የሚነዛ ጽናጽናቸውን ይዘው ስረዩ ዲያቆን እርፈ መስቀሉን ሁለቱ ላእካን ዲያቆናት የተቀጣጠሉ ጡዋፎቻቸውን ይዘው ሁሉም መርዶ እንደ ያዙ ሁሉ አንገታቸውን እዬደፉ ዝም ብለው ቆመው ሲታዩ ያስፈሩ ነበር። በቤተ ክርስቲያኑ ውስጥ በሰፈነው ጸጥታ ላይ የካህናቱ ልብሰ ተክህኖዋቸውን ለብሰው ልዩ ልዩ ንዋየ ቅድሳታቸውን ይዘው እንዲያ አንገታቸውን እዬደፉ ዝም ብለው መቆም ዝምታውን ጸጥታውን የበለጠ የሚያስፈራ ግርማ ሰጥቶት ነበር። ደመቀችና በሻህ እዬፈሩ እዚያ ካናቱ ከብበው በቆሙበት ቦታ መሀል ገብተው እንደ ቆሙ፥

«ወዲህ ቀረብ ብላችሁ ተንበርከኩ» አሉ ገባሬ ሰናዩ ቄስ ጎርነን ባለ ዝቅተኛ ድምጽ እሳቸው ፊት ሙሽሮች የሚንበንበረከኩበትን በጅ በስቀላቸው እያመለከቱ።

በሻህና ደመቀች እንደ ታዘዙት ከገባሬ ሰናዩ ቄስ ፊት ሲንበረከኩ ዝምታውና ስነ - ስራቱ ሁሉ ባካባቢው ከፈጠረው የሚያስፈራ ግርማ የተነሳ ጉልበታቸው፥ ብቻ ሳይሆን ልባቸው፥ ጭምር በውስጣቸው የተንበረከከ መስሎ ተሰማቸው! የማስተስረያው ጸሎት ከተደረገ በሁዋላ ገባሬ ሰናዩ ቄስ የጅ መስቀላቸውን ለንፍቁ ቄስ ሰጥተው እርፈ መስቀሉን ከስረዩ ዲያቆን ተቀብለው ከሙሽሮቹ ራስ ትንሽ ከፍ አድርገው ይዘው፥

«የማቴዎስ ወንጌል ምእራፍ 19 ከቁጥር 3 እስከ 7

«ፈሪሳውያን ኢየሱን ሊፈትኑት ወደሱ ቀርበው እንዲህ ብለው ጠዬቁት። ‹ሰው በማናእው ምክንያት ምሽቱን መፍታት ይፈቀድለታል?› ኢየሱስም መልሶ እንዲህ አለ። «ፈጣሪ መጀመሪያ ወንድ ሴት አድርጎ ሲፈጥራቸው ወንድ እናትና አባቱን ትቶ ከምሽቱ ጋር ስለሚጣመር ሁለቱ አንድ ስጋ ይሆናሉ» የሚለውን አላነበባችሁም? ስለዚህ ሁለቱ አንድ ስጋ ናቸው እንጂ ሁለት አደሉም፤ እግዚአብሄር አንድ ያደረገውን ሰው ሊለዬው አይችልምና» ብለው ቄሱ የወንጌል ጥቅሳቸውን አንብበው ሲጨርሱ «አናንተም» አሉ መጽሀፉን ለስረይ ዲያቆኑ ሰጥተው ሙሽሮችን እያዩ «እናንተም በሻህ ዘለሌና ደመቀች ጸሀይ ከዛሬ ጀምራችሁ አንድ ናችሁ እንጂ ሁለት አደላችሁም፤ እግዚአብሄር አንድ ያደረጋችሁን ሰው መከራ ወይም ደስታ ሊለያያችሁ አይችልምና። ሰለዚህ አዳምንና ሄዋንን በደሙ የዋጀ መድሀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ባለፈ ህይወታችሁ አውቃችሁ በድፍረት ሳታውቁ በስህተት ለሰራችሁት ሀጢያት ስሬትን ወደ ፊት በምትኖሩት ህይወታችሁ ቅበትንና ላንድነታችሁ ጽናትን ሰጥቶ ያኖራችሁ ዘንድ ቅዱስ ፈቃዱ ይሁን፤ አሜን አቡነ ዘበሰማያት» ብለው ካሳረጉ በሁዋላ ከሙሽሮቹ ራስ እክፍ አድርገው ይዘውት የነበረውን መስቀል በዬራሳቸው ላይ ላንዳንድ አፍታ አሳረፉና ከተነበረከኩበት አስነስተው ሲባርኩዋቸው የማስተሰሪያው ጸሎትና ቡራኬው ተፈጽሞ ካህናቱ ቅዳሴ ገቡ።

ስራተ - ቅዳሴው ተፈጽሞ ሙሽሮቹ፥ ቆርበው ሲወጡ፥ ባራት ኦቶመቢሎች ታጅበው በቀጥታ ወደ ገፈርሳ ሄዱ። እዚያ ከባህሩ አጠገብ በነበረ የምግብ ቤት ትናንቱን አቶ ማንደፍሮ ጉዳዩን ገልጸው ለሀያ ሰዎች ቁርስ እንዲሰናዳላቸው ትእዛዝ ሰጥተው ነበር። ስለዚህ የምግብ በቱ ባልተቤት ጠረጴዛዎችን ባበባ አስጊጠው በተለዬ ቦታ አሰርተው በጠቅላላው የሚበላውና የሚጠጣውም ሆነ የሚበላበትና የሚጠጣበት እቃ ባዘቦት ከሚሰናዳው የተለዬ ሆኖ እንዲሰናዳ አድርገው ይጠብቁ ስለ ነበረ፥ ጋባዡን አቶ ማንደፍሮንም ተጋባዞቹንም በጣም ደስ ብሎዋቸው ቁርስ ካደረጉ በሁዋላ ከዚያ

ተነስተው በባህሩ ዳር ዳርና በጫካው ውስጥ ለውስጥ እዬተዘዋወሩ ፎቶ ግራፍ ሲነሱ ሲጫወቱ ሲዝናኑ እስከ ስድስት ሰአት ቆይተው ወደ ቤታቸው ተመለሱ።

እቤታቸው ሲደርሱ ያገኙት ባሳባቸው ውስጥ ያልነበረ ፍጹም አዲስ እንግዳ ነበር! ያዛዥ ተካልኝን አጥር ዙሪያና ባካባቢው እስከ ወዲያ ድረስ ባዶውን ቦታም የሰፈርተኛውን ደጅም ሁሉ ሰው በሰው ተጨናንቆ መልቶት መተላለፍ ያስቸግር ነበረ። እዚያ የሚደረገው ሰርግ ይሁን ተዝካር ወይም ዝክር መሆኑን ሳያውቅ ድንኩዋን ተተክሎ ከጥዋት ጀምሮ መብልና መጠጥ ጠረጴዛና ወንበር ወዳጥሩ ግቢ ሲገባ ያዬችው ችግረኛ ሁሉ በጠቅላላ አነጋገር ‹የኔ ቢጤ› የሚባለው ስራ ፍለጋ ከያገሩ መጥቶ ሲያጣ ወደ ልመና የገባው ለሙግት ወድዶ ለምስክርነት ተገድዶ ከያገሩ መጥቶ ጉዳዩ ጉዳዩ ከቀጠሮ ወደ ቀጠሮ ሲተላለፍ ስንቁን ጨርሶ ለማኝ የሚሆን ነው ሌላውም ሰርቆት ሳይቀናው ለምኖ መብላትን ሁለተኛ የኑሮ ዘዴ አድርጎ የያዘው ሁሉ ድንኩዋንና እዚያ ብዙ ህዝብ መሰብሰቡን ሲያይ እዬመጣ በላይ በላዩ እዬተጨመረ ያጥሩን ዙሪያና አካባቢውን የሜዳ ገበያ አስመስሎት ነበር!

«እዚህ ዛሬ ምን አለ? » ይላል አዲስ መጪው እዚያ ከቆዩት ወዳንዱ ቀረብ ብሎ።

«ኧረ እንጃ እኔም ጠይቄ የሚነግረኝ አላገኘሁ።»

«ግድሱ ለምን ይሆን? ለሰርግ ወይስ ለተዝካር? » ይላል ሌላው ለሌላው።

«እኛ ምንስ ቢሆን ምን ቸገረን? ምሳችነን አብልተው አንዳንድ ኩባያ ጠላ ካጠጡን ተዝካር እንደሆነ ‹የሙት ነፍስ ይማርልን› ሰርግ እንደ ሆነም ‹ለሙሽራዋ ያባቱን ጋሻ እይማያሰቅል ወንድ ልጅ ይስጥልን› ብለን መርቀን መሄድ ነው! »

«ይገርማል! የዚህን ድግስ ምክንያት ከጠዬቅሁት ሁሉ አንድ ‹አውቃለሁ› የሚል ጠፋኮ! » አለ አንድ በሽተኛ ወፍራም ምርኩዙን ይዞ እያነከሰ ወዳንድ ለምስክርነት መጥቶ ስንቁን ከጨረሰ በሁዋላ ለማኝ ከሆነ ሰው ቀረብ ብሎ።

«አንተ ቢሰጡህ በልተህ፥ ጠጥተህ መሄድ ነው እንጂ ምክንያቱን መመርመር ምን አስፈለገህ? ዳኛ ነህ? ወይስ ቦሊስ! ምክንያቱን ምርመራ የገባህ? » አለ ለምስክርነት መጥቶ ለማኝ የሆነው ሰው ያለዳው ተገድዶ መጥቶ ለማኝ በመሆኑ እየተገረመ በቆመበት ያ የማይረባ ሰው እንዲያ ያለ የማይረባ ጥያቄ ስለ ጠዬቀው በስጨት ብሎ።

«ደህናም አይደል ይሄ? ምን ትርፍ ነገር ያናግረዋል! » አለ በሽተኛዉ የተመረኮዘውን ወፍራም ምርኩዝ ነቅነቅ ነቅነቅ እያደረገ ድፍርስ አይኖቹን ‹ትርፍ› በተናገረው ሰው ላይ አፍጥጦ።

«እና እኔን ልትመታበት ነው እሱን ምርኩዝህን እንዲያ የምትነቀንቀው? »

«እንዲሁ ከመሬት ተነስተህ ትርፍ ነገር ስትናገር አላስጦዝህስ! » አለ በሽተኛው።

«በያ ሞክሪው! አንቺን መምታት እንኩዋ አያፈልገኝም እንዲያ ምርኩዝሽን ብነጥቅሽ ትወድቂያለሽ! » አለ ትርፍ ተናገሪው አንድ እርምጃ ወደ ፊት ራመድ ብሎ በሽተኛውን በንቀት አይን ዘቅዝቆ እያዩ።

«እስቲ በል አንተ ሞክረው! » አለ በሽተኛው፤ ነገሩ ወደማያዋጣው ደረጃ መቅረቡን ሲያይ፥ መሮጥ የማይችሉ እግሮቹን በቆመበት ትቶ መሸሽ ይችል ይመስል አይኖቹ መሸሻ ፍለጋ ቀኝና ግራ እዬተሮሩዋጡ።

«ኧረ ተው ነውር ነው! በማይረባ ነገር ልትጣሉ ነው? » ብሎ አንድ ባጠገባቸው ቆሞ ይመልከታቸው የነበረ ሰው ለመጋልገል በመሀላቸው ሲገባ ሙሽሮች ካጃቢዎቻቸው ጋር ስለ መጡ ትርምስ ሆነና ጥለኞችም ተጠፋፉ።

«ሙሽሮች! ሙሽሮች! ለካስ ሰርግ ነው፤ እኒያው ሙሽሮች መጡ! »

«አዎ ሰርግ መሆኑ ነው። ብቻ ለምነው የማይዘፈን? የከበሮ ድምጽ እንኩዋን አይሰማም።

«ዘፈኑንማ - እዚያ በተዋወቁበት መሽታ ቤት ሲዘፍኑ ኖረው ጨርሰውት ነዋ! አታያቸውም? ተውለደው ሊድሩ የሚችሉ ትላልቆች ናቸውኮ! »

«እውነትህ ነው፤ እዚያ እመሽታ ቤታቸው ተጋብተው ኖረው ዛሬ፥ ግብዣ አድርገው ጋብቻቸውን ይፋ ማድረጋቸው ነው። ህ፥ የድሀ አምላክ ደህና አስመስክሮዋቸዋል፤ ‹ሀብታምን ባያቀብጠው ድሀን ምን በዋጠው አደል? » እዬተባለ ለማኞች እያሽሙዋጠጡዋቸው ሙሽሮች ያጥሩን በር ሲገቡ ሌላ አዲስ ነገር ሌላ እንግዳ ነገር አገኙ።

ትናንቱን ተተክሎ ካደረው ድንኩዋን ተያይዞ ሌላ መቃረቢያ ድንኩዋን ተተክሎ በውስጡ ምግብ በያይነቱ እስኪከብደው የተሸከመ ረዥም ጠረጴዛ ተዘርግቶዋል። እንጀራውና ዳቦው እዬተቆረሰ በሰፋፊ እቃ አለፍ አለፍ ብሎ ተቀምጦ የበጉና የዶሮው

ቀይና አልጫ ወጥ ምንቸት አብሹ እንፍሌው ክትፎው ያታክልቱ ወጥ በያይነቱ በትልልቅ ጎድጉዋዳ ሰሀን ተንቸርፍፎ ጥብሱ በትላልቅ ዝርግ ሰሀን ጥሬው፥ ሙዳ ሆኖ እዬተቆረጠ በጥራር በጥራር ሞልቶ ያ ሁሉ በዚያ በረዥም ጠረጴዛ ላይ እንዲያ በድርብ ተራ ተሰልፎ ሲታይ ከብዛቱ የተነሳ ገና ሳይበሉት ማየቱ ያጠግብ ነበር! ትናንቱን እትልቁ ድንኩዋን ውስጥ የገቡት ጠረጴዛዎች ሁሉም ነጫጭ ልብስ ለብሰው ጠጅና ጠላ በሞሉ ጠርሙሶችና ባላበባ የወረቀት ፎታ በያፋቸው በጎረሱ ብርጭቆዎች ተዝጎርጉረው ሲታዩ ሙሽሮችን ‹እንኩዋን ደስ ያላችሁ› ለማለት አጊጠው በሰልፍ የቆሙ ይመስሉ ነበር! እመቃረቢያው ድንኩዋን ውስጥ ምግብ ከተሰራበት ጠረጴዛ ጀርባ ዳቦና እንጀራ በዬመሶቡና በዬቅርጫቱ ጠጅና ጠላ በዬንስራው ጥሬ ስጋ በዬጥራሩ ልዩ ልዩ ወጥ በዬምንቸቱና በዬድስቱ ሁሉም በብዛት ባለቀው ለመተካት በደጀንነት ተሰልፎ ይጠብቅ ነበር! ከመቃረቢያው ድንኩዋን ራቅ ብለው አጥሩ ጥግ አንድ ሰንጋና ሶስት የበግ ሙክቶች እግር እግራቸውን ከባህር ዛፍ ጋር ታስረው ቆመው ነበር።

ሙሽሮች ያን ሁሉ እንግዳ ነገር ያን ሁሉ ቦታ ጠብቦት ይተትረፈረፈ ሙብልና መጠጥ እያዩ እድንኩዋኑ ውስጥ ከፍ ከፍ ብሎ በተደላደለላቸው ቦታ ላይ ሲቀመጡ ማን መቸ፥ እንዳመጣው፥ እንኩዋንስ ማወቅ መገመት አቅቶዋቸው በፊታቸው ይታይ የነበረው ፈገግታ ከደስታ ጋር የመቸገርና ግራ የመግባት ስሜት የተቀላቀለበት መሆኑ ይታወቅ ነእብር።

ትናንቱን አቶ ማንደፍሮ እቤት የተሰናዳውን የማይበቃ ሙብልና መጠጥ የሳቸው ሹም በታምር ለሙቶ፥ ሰው እንዲበቃ የሚያደርገው መሆኑን ‹በዘይቤ› ሲነግራቸው ተጨማሪ፣ ሙብልና፥ መጠጥ ከሆቴል እንደሚመጣላቸው መቸም እርግጠኞች ነበሩ። ነገር ግን ከሆቴል እንደሚመጣላቸው መቸም እርግጠኞች ነበሩ። ነገር ግን ያቶ ማንደፍሮ ሹም ታሪኩ አሻግሬ፥ ምንም ያክል ታምር መስራት ቢችል፥ ‹ያን ያክል ይሰራል› ብለው ማመኑ አስቸገራቸው! ለፍጡር የሚሰጠው የታምር መስራት ጸጋ ‹ያን ያክል ሊሆን ይችላል› ብሎ ማመኑ አዳገታቸው!

ካቶ ማንደፍሮ ሆቴል ተጨማሪ ድግስ መምጥቱን ትናንቱን እሳቸው በተናገሩት ላይ ገና ድንኩዋኑን እንደ ገቡ፥ በሻህ የጠረጴዛ ልብሶችን ታሪኩ አሻግሬንና የሆቴሉን አሳላፊዎች እንዲሁም አንዳንድ የሚያውቃቸውን የሆቴል እቃዎች ሲያይ አረጋገጠ። ብቻ ቢሆንም ካቶ ማንደፍሮ ሆቴል የመጣውና እዚያው እቤት የተሰናዳው ያን ያክል ሊሆን የማይችል ከመሆኑም ሌላ የሰንጋውና የበጎች ጭምር እዚያ መገኘት ካቶ

ማንደፍሮ ሌላ እርዳታ ያደረጉ ሰዎች መኖራቸውን የሚያመለክት ስለ ነበረ፥ በሻህ አዝማሪው ውቤን በጥቅሻ ጠርቶ ያ ሁሉ ድግስ ከምን የመጣ መሆኑን እንዲጠይቅ ነገረው። አዝማሪው ውቤን በጥቅሻ ጠርቶ ያ ሁሉ ድግስ ከምን የመጣ መሆኑን እንዲጠይቅ ነገረው። አዝማሪው ውቤ ሊጠይቅ ወደ ወይዘሮ ጌጤ ቤት ቢሄድ እዚያም እመቃረቢያው ድንኩዋን ከነበረው ሌላ የቤቱን መቀመጫ ክፍል እንጀራና ወጥ ጠጅና ጠላ፥ የያዘ እቃ ሞልቶት አገኘ።

«ያውልህ ስጦታ ያመጡት ሰዎች ስምና ስጦታው የተጻፈበት ደብተር እይና እዚያ አድርገሽው ሂድ፤ እኔ ስራ አለብኝ፤ ካንተ ጋር ተቀምጬ ስጦታ ያመጣ ሰው ስቆጥር አልውልም» ብላ ውባዬሁ አንድ ደብተር አምጥታ ሰጥታው ወደ ስራዋ ቸኮለች - ካቶ ማንደፍሮ ሌላ ስጦታ ያመጡ ሰዎች እነማን እንደ ሆኑ ባልዋ ሲጠይቃት።

እዚያ ደብተር ውስጥ አራቱ ገጾች ስጦታ ባመጡ ሰዎች ስምና ባመጡት የስጦታ አይነት ሞልትዋል። ያቶ ማንደፍሮ ስምና ስጦታቸው ብቻ አይታዩም። በተረፈ ከተጠሩት ሰዎች ሁሉ ስጦታ ያለመጡ በጣም ጥቂት ነበሩ። ከበሻህ የመስሪያ ቤት ጉዋደኞች አምስቱ ገንዘብ አዋጥተው፥ አንድ ሰንጋ ሶስት አንዳንድ በግ ሰጥተዋል። ሌሎች የመስሪያ ቤት ጉዋደኖችና ከመስሪያ ቤቱ ውጪ የነበሩ ወዳጆች ይብዛም ይነስ እንጀራና ወጥ ጠጅና ጠላ አምጥተዋል።

አዝማሪው ውቤ ተመልሶ ምሽቱ በሰጠችው ደብተር ውስጥ ያዬውን ለበሻህ በጆሮው ሲነግረው ጉዋደኞቹና ወዳጆቹ ፍቅራቸውን እንዲያ ባለ ልግስና በመግለጻቸው ልቡ ተነክቶ አይኖቹ እንባ አቀረሩ። ታዲያ፥ በሻህ ልብ አድርጎ ሳይመለከተው ቀርቶ ወይም ረስቶ ይሆናል እንጂ እንኩዋንስ ‹ጋብዙን› በለው ጠይቀው የተጋበዙ ሰዎች ባይጠይቁም ለሰርግ ወይም ለተዝካር በተጋበዙ ስጦታ ሳይዙ ባዱ እጅን ወደ ተጋበዙበት ቤት መሄድ በኢትዮጵያ ልማድ የሚያስነውር ነበር። ‹ጋብዙን› ማለትማ ‹እንዳር› የማለት ምልክት መሆኑ የታወቀ ነበር። ብቻ ‹የተጠሩት እንግዶች ስጦታ ያመጣሉ› ተብሎ መቸም እቤት በቂ ድግስ መደገሱ አይቀር!

ሙሽሮች ከተቀመጡ በሁዋላ ትናንቱን አዝማሪው ውቤ ከበሻህ ጋር እንደ ተስማሙት የክብር እንግዶችን ከሙሽሮች አቅራቢያ ሌሎችን እንደ እድሚያቸውና የፈልጉትን በዬጉዋዳቸው እንደዬምርጫቸው አስቀመጠ። ነገር ግን ያነሉት የመጡት የተጠሩት እንግዶች ብቻ አልነበሩም። ለምሳሌ ሙሽሮችን ካቆረቡት አምስት ቀዳስያን ሌላ አስር ካህናት አብረው መጥተው ከተጠሩት ጋር ተዳብለው የመጡት ብዙ ነበሩ። ስለዚህ ድንኩዋኑ እስከ ቻለ ድረስ እድንኩዋኑ ውስጥ አሳላፊዎች እዬረዱት ካቶ

ማንደፍሮ፥ ሆቴል ለመጠባበቂያ የመጡትን ጠረጴዛዎችና ወንበሮች ከድንኳዋኑ ጥግ ለግጥ ሰርተው እዚያ አስቀመጡዋቸው።

እንግዳው ሁሉ ቦታ ቦታውን ይዞ እንደ ተቀመጠ፥ ያቶ ማንደፍሮ ሆቴል ስልጡን አሳላፊዎች ነጫጭ ሽርጣቸውን ወደ ሁዋላ ሽብ እያደረጉ ከሆቴሉ በገፍ የመጣውን ልዩ ልዩ የፈረንጅና የኢትዮጵያ አረቄ ከምግብ በፊት ማባያ እንዲሆን ተሸክመው ማሳለፍ ጀመሩ። ታምር ሰሪው ታሪኩ አሻግሬ ጥር ይዞ ቆሞ እንደ የሙዚቃ መሪ የሚያደርጉትን ባፉ ሳይሆን በጁ እዬነገራቸው ላልደረሳቸው ለማዳረስ መድገም ለሚፈልጉት ለመድገም የጠርሙስና የመለኪያ ኩዋኩዋታ፥ ወይ የቃል ጫጫታ ሳያሰሙ ጸጥ ብለው እዬተዘዋወሩ ሲጋብዙ እንኩዋንስ ተጋባዦችን ተመልካቾችን ደስ ያሰኙ ነበር።

ከማባያው አንዳንድ የበቃእው ባንዳንድ ቆመው መደጋገም የፈለጉት ደጋግመው ሲያበቁ ሁሉም መብላት የፈለጉ መሆናቸውን አዝማሪው ውቤ ከያይናቸው ገምቶ ወዲያውም የጊዜውን መገባደድ ተመልክቶ ይህን ወደ ሙሽሮቹ ቀረብ ብሎ ስለ ነገራቸው ተነስተው ወደ መቃረቢያው ድንኩዋን ሄደው ማእዱን ባርከው ተመለሱ። ከዚያ የክብር እንግዶች አዝማሪው ውቤ አስነሳቸው። ከነሱ በሁዋላ ሌሎች እዬተከታተሉ ከዚያ በሁዋላ ሌሎች ባንድነት እዬተግተለተሉ ምግቡ በያይነቱ ወደ ተደረረበት ጠረጴዛ ሄደው መምረጥ የፈለጉት የመረጡትን መጥገብ የፈለጉት የቻሉትን እየያዙ ተመልሰው መብላቱ ተጀመረ።

ያ ሁሉ ድንኩዋኑን የሞላው ሰው የሚበላውን ይዞ ጠረጴዛው እየከበበ ተቀምጠው መብላት እንደ ጀመረ ጸጥ ከማለቱ የተነሳ፥ ያን ያክል ብዙ ህዝብ ባንድ ላይ ተሰብስቦ እዚያ የተቀመጠ አይመስልም ነበር። የዚያ ሁሉ ህዝብ አፍ ከሚናገረው ይልቅ የሚያላምጠው ጎላ ብሎ ለጆሮ ይሰማ ነበር። ቀስ እያለ ብቻ ሁሉም የሙብል አምሮቱን በመጠኑ ካስታገሰና ወደ መጠጡ ከተመለሰ በሁዋላ በድንኩዋኑ ውስጥ ንግግሩ ጎላ ብሎ ይሰማ ጀመር።

ከዚያ አሳላፊዎች ምግብ በያይነቱ ይዘው በዬጠረጴዛው እዬዞሩ እዚያው ተቀምጠው መመገብ ለፈለጉት እዚያው እየሰጡ ራሳቸው ከመቃረቢያው አምጥተው መብላት የፈለጉት እያመጡ ሲበሉ ቆይተው ሲበቃቸው ጠላና ጠጅ በገፍ ስለ ነበረ እዬተጠጣ መደሰቱ፥ መዝናናቱ ቀጠለና ሞቅታ ሲመጣ፥ መዝናናቱና መደሰቱ ወደ መሳቁና ወደ መፈንደቁ ከዚያ ወደ ውካታውና ወደ ጫጫታው እየተሸጋገረ ሄዶ ሁሉም ለየራሱ በተናገረው የሚስቅ እንጂ ሌላው የተናገረውን ሰምቶ የሚስቅ ከማይመስልበት ደረጃ ደረሰ።

ሙሽሮች ያን ሁሉ ጭዋታና ደስታ ያን ሁሉ ውካታ ከከፍታኛ ቦታዎች ዘቅዝቀው እያዩ የዚያ ሁሉ ደስታ ምክንያት እነሱ መሆናቸው ሲታሰባቸው እዚያ እንደ ነበሩት ሁሉ በሳቅና በውካታ ሊገልጹት የሚይችሉ እንዲሁ በዝምታ ለውስጣዊ ልባቸው ሙቀትን ላፋዊ አካላታቸው ውበትን የሚሰጥ ልዩ ደስታ ተሰምቶዋቸው ስለ ነበረ የሁለቱም ፊቶች እንደ በጋ የንጋት ሰማይ ወገግ ብለው ሁለቱም በጣም አምሮባቸው ነበር።

ከዚያ የደመቀች በደስታ ወገግ ብሎ የነበረ ፊት ትንሽ በትንሽ የቅርታ ጥላ ሲያጠልለው እንደ ሰማያዊ ፈርጦች ይፍለቀለቁ የነበሩ ውብ አይኖችዋን እንባ ሲመላቸው በሻህ አዬና፥

«ምነ ምን ሆንሽ? » አለ እንደ መደንገጥ ብሎ።

«ደህና ነኝ እንዲያ - እንዲያው ነው» አለች መሀረምዋን ከጉንፍዋ አውጥታ አይኖችዋን የምታሻሽ መስላ እንባዋን እዬጠራረገች።

«ደህና እለመሆንሽማ - ማልቀስሽም የፊትሽ መለወጥም ያሳያሉ። የሆንሽውን ንገሪኝ ‹እባክሽ! አመመሽ? »

«የለም ደህና ነኝ አባ - አባባን አስቤ ነው። ዛሬ ቢኖሩ ደስታውን አልችለው በልው ያደርጉት ይሆኑት የነ - የበረውን ታስቦኝ ነው! » አለች፥ መሀረምዋን ካይኖችዋ ሳትለይ፣ ንግግርዋ ሳግ እያደናቀፈው። አይኖችዋን የሞላው እንባ ስትጠርግ አዲስ የሚተካው ካይኖችዋም ተርፎ በቀኝና በግራ ጉንጮችዋ ይወርድ ነበር።

«ኧረ እባክሽ ሰው ጉድ ያላል! » አለ በሻህ የሚያደርገው ቅጡ ጠፍቶት።

«ምናባቴን ላድርግ? አቃተኝ እንጂ ልረሳቸው ሞክሬ ነበርኮ! » አለች እንኩዋን ውስጥ ሞቆ ስለ ነበረ አዬር የምትራግብና ላብዋን የምትጠርግ አስመስላ በመሀረምዋ ካይኖችዋም ከፊትዋም እንባዋን እዬጠረገች። ደግነቱ ደስታዉም ሳቅና ውካታውም ደርቶ ስለ ነእበ ልብ አድርጎ የተመለከታት አልነበረም ሁዋላ አዛዥን ለመርሳት ራስዋ ታደርገው ከነበረ ጥረት ሌላ በሻህም ወሬ እያለዋወጠ ያወራት ስለ ጀመረ ጸጥ እያለች ሄዳ እንደ ፊቱ ከሱ ጋር ትጫወትና ትስቅ ጀመር።

ከዚያ ሙሽሮችን ካቆረቡት ቀዳሲያን ተደርበው ከመጡት ካህናት መሀከል አንድ ወጥት ደብተራ ተነስቶ፣ ‹ቶሎ ድረስ እንደ ተባለ ሁሉ ፈጠን ፈጠን እያለ ሄደና ሙሽሮች በተቀመጡበት ሊደርስ ትንሽ ሲቀረው ቆሞ ማንጎድጎድ ስለ ጀመረ

ጫጫታው ጋብ ብሎ የሰው ሁሉ አይን ወደሱ ተመለሰ። ደብተራው አልሰከረም እንጂ ሞቅ ብሎት ጥርሱ ብቻ ሳይሆን የመጋ ፊቱ ሁሉ ይስቅ ነበር።

«አውርድ ወይነ ቤተ ቃና ወይነ ቤተ ቃና፥

ስቴ ካህናት ዘያስተፌስህ ልቡና» ሲል ካህናት ‹ማህሌተ ገንቦ› የሚሉትን እንደሚቀዳ ጥኡም ወይን ልብ የሚመስጥ ጥኡም ድምጽ እያንጐዳጐደ ትርጉዋሚዉ የገባው ያልገባውም ጥኡም ባንድ ላይ ያወካ ጀመር! ከዚያ ቀኝ እጁን እንደሚያቅፍበት ሁሉ መዳፉን ወደ ታች አድርጎ ዘርግቶ፥ ግራ እጁን እንደሚያተርስበት ሁሉ መዳፉን ወደ ላይ አድርጎ ከስር ዘርግቶ እንደሚያንተርስበት ሁሉ መዳፉን ወደ ላይ አድርጎ ከስር ዘርግቶ

«የማኑ ትህቅፈኒ ወጸጋሙ ታህተ ርእስየ፣

ዘፍቁርየ ዘፍቁርየ

እስከ ትትፌሳህ ወትትህሰይ ነፍስየ

ትብሉ መራት መራት ለመራዊህ» አለ እንዲያ ጥርስ ብቻ ሳይሆን የጋመ ፊቱ ጨምሮ እዬሳቀ ‹ትብሎ መራት ቢል ወደ ሙሽራዋ ‹ለመራዊህ› ሲል ወደ ሙሽራው ከንጉድጉዶው ገር በሁለት እጆቹ እያመለከተ። ያንጊዜው ውካታው ከድንኩዋኑ አልፎ እውጪ ለልመና በመጣው ህዝብ መሀከል አስተጋባ። ትርጉዋሚው ከሞላ ጎደል፥ ‹ሙሽራይቱ ምሽራዋን ‹ግራ እጁን አንተርሶ በቀኝ እጁ ሲያቅፈኝ ነፍሴ በደስታ ትሰከራለች› ትላለች» ማለት መሆኑ ስለ ገባት ደመቀች አፍራ መድረሻ አጥታ ነበር። አዝማሪው ውቤ በግጥም መረቀ። አዝማሪው ከሙሽሮቹ ጎን ቆሞ፥ ያለ መሰንቆ በድምጽ ብቻ የሚከተሉትን ግጥሞች ዘፈነ።

«አየ ፍቅር ከፉው አይ ፍቅር መልካሙ፥

ባህሪው አይታወቅ ምን ያክል ቢደክሙ!

ፍቅር ሀቀኛ ነው እውነተኛ ዳኛ

‹በጉቦ› ተታልሎ ህሊናው ያልተኛ

መሆንን የናቀ የስልጣን ምንደኛ፥

ታዲያ ምን ያደርጋል! ጨካኝ ነው ያለ ቅጥ!

የሰው ልብ ሲሰቃይ እያዬ፥ እሚያገላግጥ!
ፍቅር ሀይለኛ ነው የታወቀው ባለም፥
እሱን ተቋዋቁሞ ያሸነፈው የለም!
ቀድሞ አይግጠም እንጂ ፍቅር ሲገጥምኮ፤
አይትውም በዋዛ ያሸነፈው የለም!
ቀድሞ አይግጠም እንጂ ፍቅር ሲገጥምኮ፥
አይተውም በዋዛ ባይገድል ያስራል ማርኮ!
ደመቀች ባገርዋ በሻህም ባገሩ፥
በግፍ ላይ ያመጹ ሽፍታዎች ነበሩ።
እነህ ሁለት ልጆች ግፍ ያስሸፈታቸው፥
አምጸው ሲኖሩ ሰው ሁሉ ፈርቶዋቸው
የሽፍትነት ኑሮን ‹በቃችሁ› ሲላቸው፥
የማይቀር ሆነና በሱ እጅ መውደቃቸው፥
ሲሸሹት የኖሩት እንዳያገኛቸው፥
የሀይለኞች ሀያል ፍቅር ገጠማቸው።
ከዚያም ድል አድርጎ እንደ ማረካቸው
‹ሞት ይፍታችሁ› ብሎ ባንድ አቆራኛቸው።
‹አቤት› አይሉበት እሱ የለው ጌታ!
ምህረት አይለምኑት አያውቁ ይቅርታ!
ጨካኝ ነው ክፉ ነው ካስረ እማይፈታ!
እንግዲህ ሁላችን እንጸልይላቸው፥
ተሳስረው ሲኖሩ እስከ እድሜ ልካቸው

ፈጣሪ ጤናውን ሰጥቶ እንዲያኖራቸው

ትእግስቱን በሰፊው እንዲለግሳቸው።»

አዝማሪው ውቤ በግጥም ከመረቁ በሁዋላ አቶ ማንደፍሮ ተነስተው «ልጆቼ ደመቀችና በሻህ እንኩዋን ደስ ያላችሁ ጋብቻችሁን እንደ አብርሃምና እንደ ሳራ ጋብቻ የተባረከ ያድላችሁ» አሉ። «በሻህ» አሉ ቀጥለው። « ‹አንድ በሬ ብቻ አያርስ አንካሳ ቢሮጥ ሩቅ ግቡ አይደርስ!› እንዲሉ አባቶች ‹አንድ ሰው ምንም ያክል ብርቱ ምንም ያክል ብልህ ቢሆን ወንድነቱ ስለማያልፍ ብዙዎች ተባብረው የሚያደርጉት ለማድረግ አይችልም› እያልሁ ብዙ ጊዜ ነግሬሀለሁ። አሁን ወዳባቶች ምሳሌ ልመለስና ባንድ በሬ አርሶ ለቤተሰብ የሚበቃ ፍሬ ለማምረት ሰላማይቻል ምርት ለማምረት በሬዎች ሁለት መሆን አለባቸው ሩቅ ግብ ለመድረስም ሁለት ጤናማን ብርቱ እግሮች ያስፈልጋል ከቤተሰብ አልፎ የተራበን ያገር ህዝብ አብልቶ ለማጥገብ ደግ እንዲያውም ለእርሻ የሚጠመዱትን በሬዎች ማብዛት ያስፈልጋል።

«ዛሬ እናንተ ሁለት ብርቱ ወጣት፥ አራሾች በጋብቻ ቀንበር ስትጠመዱ መቸም ለራሳቸው ለቤተሰባቸው የሚበቃ እንደምታመርቱት የታወቀ ነው። ነገር ግን ከዚያ አልፋችሁ በምክርም በግብርም እዬተረዳዳችሁ የናንተን አራያ ተከትለው ከናንተ ጋራ ተባብረው የተራበን ያገር ህዝብ አብልቶ ለማጥገብ ባንድ ላይ የማጣመዱ ብዙ አራሽ በሬዎች ስለሚያስፈልጉ አንዲያ ያሉት አራሽ በሬዎች ማግኘት እንድትችሉ እንመኝላችሁዋለን፤ እንጸለይላቸዋለንም» ብለው ሲጨርሱ ተጨበጨበና ቄሱ አሳረጉ ያቶ ማንደፍሮ ንግግር ዘይቤው የገባቸው በሻህና አዝማሪው ውቤ ብቻ ነበሩ።

ከዚያ አቶ ማንደፍሮና አዝማሪው ውቤ ባባቶች ቦታ ወይዘሮ ጌጤና ወይዘሮ ውባዬሁ በናቶች ቦታ ሄደው እንደ ተቀመጡ ደመቀችና በሻህ ተከታትለው የናቶችንም ያባቶችንም ጉልበት ስመው ጉንጫቸውን ተስመው ቡራኬ ከተቀበሉ በሁዋላ አዲሱን ኑሮዋቸውን ወደሚጀምሩበት ቤታቸው ታጅበው ሲሄዱ የቀረው እድምተኛ ተነስቶ በደማቅ በጭብጨባ ሸኛቸው።



## ስለደራሲው በጥቂቱ

ሐዲስ ዓለማየሁ በጎጃም ጠቅላይ ግዛት በደብረማርቆስ አውራጃ ከየኔታ ዓለማየሁ ሰለሞን እና ከወ/ሮ ደስታ ዓለሙ ጥቅምት 7 ቀን 1902 ዓ.ም. የተወለዱ ሲሆን፥ ለቤተሰባቸው ብቸኛ ልጅ ናቸው።

ሀዲስ እድሜያቸው ለትምህርት ከደረሰበት ጊዜ አንስቶ በቤተሰባቸው አጠገብ እና በአባታቸው ሀገር ደብረ ኤልያስ ሄደው ከባህላዊ የግዕዝ ት/ቤት ዜማ ተምረዋል፥ቅኔ ተቀኝተዋል።

በ1918 ዓ.ም. ወደ አዲስ አበባ የመጡት ሀዲስ፥በዚያው አመት በተፈሪ መኮንን ት/ቤት ዘመናዊ ትምህርታቸውን ተከታትለው በኢጣሊያ ወረራ ዋዜማ በአዲስ አበባ በመምህርነት በጎጃም በጉምሩክ ሥራ ባለሙያነት ሠርተዋለል።

በኢጣሊያ ወረራ ወቅት 1929-1933 ዓ.ም. ከልዑል ራስ አምኃ ኃ/ስላሴ ጦር ጋር በአርበኝነት ሲዋጉ ቆይተው በምእራብ ኢትዮጵያ በጣሊያን ተማርከው፥ ወደ ኢጣሊያ በግዞት ከቆዩ በኋላ በ1936 ዓ.ም. ወደ ሀገራቸው በነፃነት ተመልሰዋል።

ከነፃነት በኋላ ዘመናዊት ኢትዮጵያን ለማደራጀት በተደረገው ትግል በማስታወቂያ ሚኒስቴር 1936፥ በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር - በኢየሩሳሌም 1937-1939 እና በተ.መ.ድ 1939-1946፥ በእንግሊዝ 1948፥ እንደገና በተ.መ.ድ 1949-1953 ሀገራቸውን በአምባሳደርነት ያገለገሉ ሲሆን በዚሁ "ወርቃማ" የሥራ ዘመናቸው በመዲናችን አዲስ አበባ- የአፍሪካ ኢኮኖሚ ኮሚሽን ECA እንዲመሰረት ከፍተኛ አስተዋፅኦ ያደጉ ክቡር ኢትዮጵያዊ ናቸው።

ከ1953 ዓ.ም. የታኅሣሡ መፈንቅለ መንግስት ሙከራ በኋላ እስከ 1961 ዓ.ም. ድረስ በሚኒስትርነት ማእረግ በሚኒስትሮች ም/ቤት የመማከርት ጉባኤ አባል፥ ከ1961 - እስከ 1966 ድረስ በሀገሪቱ ፓርላማ የህግ መወሰኛ ም/ቤት አባል ከ1966 ጎጃም ሕዝብ በመረጣቸው መሰረት የብሄራዊ ሸንጎ አባል 1966-1968 ሆነው ያገለገሉ ሀዲስ ዓለማየሁ "ኢትዮጵያ ምን አይነት አስተዳደር ያስፈልጋታል?" 1966 በሚለው መጽሐፋቸው ስለ ሀገራቸው ያላቸውን የመልካም አስተዳደር ራእይ ተመልክቶ ደርግ የሀገሪቱ ጠ/ሚኒስትር ሆነው እንዲሰሩ ጠይቋቸው አለመቀበላቸው ተነግሯል።

ሀዲስ አለማየሁ በ1929 ዓ.ም ለመጀመሪያ ጊዜ ካዘጋጁዋት "ያበሻና የወደኋላ ጋብቻ" በኩር የተውኔት ድርሰታቸው ፋቡላ አንስቶ "ተረትተረት የመሰረት" 1948 "ፍቅር እስከመቃብር" 1958፥ ወንጀለኛው ዳኛ 1974፥ "የልምዣት" 1980 በተሰኙት የረዥም ልቦለድ ሥራዎቻቸው ያልታተሙ ድርሰቶችም አሏቸው የኢትዮጵያን ዘመናዊ ሥነጽሑፍ በአያሌው የታደጉ "የቀለም ሰው" ናቸው።

ሀዲስ ዓለማየሁ "ፍቅር እስከመቃብር" በተሰኘው የአማርኛ ረዥም ልቦለድ ሥራቸው "ለኢትዮጵያ ሥነጽሁፍ አዲስ ምእራፍ ከፋች!" የሚል ሞገስ ያገኙ ሲሆን፥ በዚሁ ኪናዊ ሥራቸውም ፋሽስት ኢጣሊያ ከወጣ በኋላ ብዙዎቹ ኢትዮጵያውያን ደራስያን ያላተኮሩበትን የፊውዳል ኢትዮጵያን ገፅታ በተለየ ትኩረት በስፋትና በጥልቀት በመዳሰስ ኪናዊ በሆነ የቋንቋ ኃይልና ውበት የገለጹ፥ በፊውዳሉ ሥርዓት ላይ ያመፁ እንደ ጉዱ ካሣ፥ በዛብህ፥ ሰብለወንጌል፥ አበጀን የመሳሰሉ ሕይዋን ገፀባሕርያት በመሳል - በለውጥ የትግል መንፈስ ላይ ለነበረው አዲስ ትውልድ ሀዲስ ራዕያቸውን በጥበብ አጋርተዋል።

በአጻጻፍ ብልሃቱ በአማርኛ ሥነ ጽሁፍ ታሪክ ውስጥ አዲስ ፈር በቀደደው የ"ፍቅር እስከ መቃብር" ድርሰታቸው በሁለት የውጭ ቋንቋዎች ተተርጉሟል "አዲስ ዓለም አሳየን!" የሚል ሞገስ ያገኙት ሀዲስ ዓለማየሁ በ1960 ዓ.ም የቀ.ኃ.ሥ. ሽልማት ክብር በሥነጽሁፍ ነሐሴ 27 ቀን 1991 ዓ.ም. ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በሥነ ጽሑፍ የክብር ዶክትሬት ዲግሪ አግኝተዋል።

"ትዝታ" 1985 በሚለው ግለ ታሪካቸው ሰብዕናቸውን የተረኩልን ታሪክ ፀሐፊ፥ አርበኛ መምህር፥ አምባሳደር፥ ሚኒስትርና የሥነ ጽሑፍ ጠቢብ ሃዲስ ዓለማየሁ "የኢትዮጵያ ሥነ ጽሑፍ አባት!" የሚል የሀያስያንና የሕዝብ ሞገስ አግኝተው ኀዳር 28 ቀን 1996 ዓ.ም. በ94 ዓመታቸው አረፉ።

## የደራሲው ሥራዎች

1. ፍቅር እስከመቃብር(ልብወለድ)
2. ትዝታ(ታሪክ)
3. ወንጀለኛው ዳኛ(ልብወለድ)
4. የሕልም እዣት(ልብወለድ)
5. ተረት ተረት የመሰረት(ወግ)

6. የትምህርትና የተማሪ ቤት ትርጉም(ትምህርት)
7. ያበሻና የወደኋላ ጋብቻ(ተውኔት)
8. ኢትዮጵያ ምን ዐይነት አስተዳደር ያስፈልጋታል? (ታሪክ)

NIGUSS
DIGITAL LIBRARY